ኢትዮጵያ ከአንድ ትውልድ በኋላ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር
ባዘጋጀው ርዕይ 2020 የውይይት መድረክ
የቀረቡ ጽሑፎችና አስተያየቶች
(ከ13ኛው - 24ኛው <<ርዕይ 2020>>
መድረክ የቀረቡ)

ኢትዮጵያ ከአንድ ትውልድ በኋላ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ባዘጋጀው ርዕይ 2020 የውይይት መድረክ የቀረቡ ጽሑፎችና አስተያየቶች

(ከ13ተኛ - 24ተኛው ‹‹ርዕይ 2020›› መድረክ የቀረቡ)

ጥር 1999

ዋና አዘጋጅ
ጌትነት አለሙ

አዘጋጅ
ደምረው ጌታቸው

ኤዲቶሪያል ቦርድ
ጌትነት አለሙ
አለማየሁ ስዩም
አለሙ መኮንን
እዮብ ተስፋዬ
ገዛኸኝ አየለ
ኣሳቅ ዲዎን

ዲዛይን
ራሄል ይልማ
እና
ትዕግስት ጁነይዲን

© መብቱ፡ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር በሕግ የተጠበቀ ነው።

ስለመዕረሉም ሆነ ስለማህበሩ ጥያቄ ወይም መረጃ የምትሹ አድራሻችን የሚከተለው ነው።

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር
ፖ.ሣ.ቁ. 34282
ስልክ፤ 251-1-4 16 21 21
ፋክስ፤ 251-1-4 16 09 67
ኢ-ሜይል፤ eea@telecom.net.et
ድህረ-ገጽ፤ www.eeaecon.org

ISBN 978-99944-54-00-6

ማውጫ

መግቢያ ገጽ

ኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ እና ልማት በኢትዮጵያ
ሊሻን አዳም 1

አስተያየት
- ❖ መላት ደመቀ
- ❖ አህመድ ሁሴን

ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር 20
የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለመቀነስ አንድ አማራጭ አካሄድ 27
አክሊሉ ኪዳነ 33

አስተያየት
- ❖ ጥላሁን ግደይ
- ❖ ገነት መንግሥቱ

57
ሰላም፣ ዲሞክራሲ እና ልማት፤ የልሂቃን ሚና ዛሬና ነገ በኢትዮጵያ 62
ታደሰ ብሩ ኪርስሞ 67

አስተያየት
- ❖ አማረ አረጋዊ
- ❖ ጃለሌ ኤሬጋ

86
90
ኤነርጂ እና ልማት በኢትዮጵያ
በቀለ ባይሣ 95

አስተያየት
- ❖ መሉጌታ አዳመ
- ❖ ንያለልዑል ጠበቁ

121
128
ወጣቱ እና ልማት፤ ትናንት፣ ዛሬና ነገ በኢትዮጵያ 139
ዘሪቱ ንዳ እና ጎጃም ቦጋለ

አስተያየት
- ❖ ክፍለማርያም ጌታቸው 156
- ❖ አንዳርጋቸው ተስፋዬ 160

ትምህርት እና ልማት በኢትዮጵያ
ሥዩም ተፈራ 165

አስተያየት
❖ ዳርጌ ወሌ 187
❖ አያሌው ሺበሽ 192

ፋይናንስ እና የኤኮኖሚ ዕድገት በኢትዮጵያ
ንዋይ ገብረአብ 197

ገንዘብ እና ልማት በኢትዮጵያ
ለይኩን ብርሃኑ 207

ኢንተርፕረነርሽፕ እና ልማት በኢትዮጵያ
ወሮታው በዛብህ 217

አስተያየት
❖ እስራኤል ካሣ 252

የግብርና ዘርፍ ምርምር ለእድገት
(አሁን ያለበት ሁኔታና የወደፊት ተስፋው)
ስሜ ደበላ 257

የኢንዱስትሪ ምርምር እና ልማት በኢትዮጵያ
አሥራት ቡልቡላ 285

ሥርዓታት፣ የፖለቲካ ነፃነት እና ልማት በኢትዮጵያ
የራስወርቅ አድማሴ 295

አስተያየት
❖ ያዕቆብ አርሳኖ 322

መንግሥት፣ ኢንፎርሜሽን እና ሕዝብ
ዓቢይ ፎርድ 327

ሚዲያ እና ልማት በኢትዮጵያ
ዘካርያስ ቀነዓ 335

ከተሞች ለሀገር ልማት በኢትዮጵያ
አበበ ዘልዐል 357

አስተያየት
❖ አበበ ከበደ 374
❖ ይመር መሐመድ 379

መግቢያ

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ኢትዮጵያ ካለችበት የድህነት አረንቋ ወጥታ በእድገት እንድትራመድ እና ዜጎች በረዥም ጊዜ ዕይታ ውስጥ ስለአገራቸው የጋራ ርዕይ ጨብጠው የበኩላቸውን እንዲወጡ ለማስቻል ከ1995 ዓ.ም ጀምሮ ‹‹ርዕይ 2020›› የሚል መድረክ በማዘጋጀት ተከታታይ ውይይት በማካሄድ ላይ ይገኛል::

የ‹‹ርዕይ 2020›› የውይይት መድረክን ለማዘጋጀት የተለያዩ መነሻ ምክንያቶች ቢኖሩትም አንደኛው መጪውን ዘመን ጥርት ባለ እይታ የማየት ችሎታን ለማዳበር ነው:: በተለይም በተመረጡ የውይይት ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ ‹‹ኢትዮጵያ ከ25 ዓመት በኋላ አሁን ባለው ሁኔታ ብትቀጥል የት ትደርሳለች? አገራችን ከ25 ዓመት በኋላ የት ደርሳ፤ ምን ሆና ልናያት እንፈልጋለን? ይህንን ምኞት እውን ለማድረግ ከዛሬ ጀምሮ ምን መደረግ አለበት? በሚሉ ጭብጦች ላይ የጋራ ግንዛቤ ለመፍጠር ያለመ ነው:: ከዚህም ሌላ በነዚህና ከነዚህ ጋር ተዛማጅ ለሆኑ ጭብጦች የመፍትሔ ሐሳቦችና የተግባር መርሐግብሮች መመንጨት ያለባቸው የችግሩ ሰለባ ከሆነው ህዝብ መሆን እንዳለበት ተስምሮበታል:: ለችግሮቻችን መፍቻ ተጠያቂው መንግስት ብቻ ሳይሆን እያንዳንዱ ግለሰብ ሕይወቱን የመለወጥ ኃላፊነት የራሱ መሆኑን ተገንዝቦ አስፈላጊውን የዜግነት ግዴታውን እንዲወጣ ማድረግ ለፍትሀዊ ልማትና እድገት አማራጭ የሌለው መሆኑን በመረዳት ሕዝቡንም ለዚህ ጊዜ ለማይሰጥ ጉዳይ ማንቀሳቀስና ማነቃቃት ተገቢ ሆኖ በመገኘቱ ነው የ‹‹ርዕይ 2020›› የውይይት መድረክ የተዘጋጀው::

እዚህ ላይ በአጽንኦት መገለጽ ያለበት የውይይቱ አላማ መስተዳድሩንና የመስተዳድሩን ባለልጣናትን መጠየቅ፣ መተቸትና በኃላፊነት የመያዝ ሳይሆን አገራትዋ የሚያጋጥሟትን ችግሮች ህዝቡ እርስበርሱ ተወያይቶ፣ የመፍትሔ ሐሳቦችን የመፍጠርና ለነዚህም ተግባራዊነት ተገቢውን ጥረት የማድረግ ባህል እንዲያዳብር መርዳት ነው:: ችግር በመላ ቁጥር እጅን አጣጥፎ ምናልባትም የችግሩ ምንጭና ባለቤት የሆነው መስተዳድር መለመንና ፈጣሪን መማለድ መፍትሄ ሊሆኑ አይችሉም:: ሕዝብ በውይይቱ የደረሰባቸውን ሩይዳዎችም መሪዎቻችን ተግባራዊ ማድረግ አለባቸው:: ሕዝብ የማኖረው፣ መኖር ያለበት የራሱን ርዕይ እንጂ የሌላ መሆን የለበትም:: የመስተዳደሩና የፈጣሪ እርዳታ የሕዝብን ጥረት የሚያግዝ እንጂ የሚተካ አለመሆኑን መረዳት የግድ ይላል::

አቀራረቡ ለውይይት መነሻ የሚሆን ጎሳብ በጽሑፍ ማቅረብና በቀረበው ሃሳብ ላይ አስተያየት የሚሰጡ ተሳታፊዎችን መጋበዝ አንዱ አካል ሲሆን በውይይቱ የተስተናገዱ ሃሳቦች በአዳራሹ ተወስነው እንዳይቀሩና መላው ሕዝብ እንዲወያይበት ማድረግ የሚችልበት ሁኔታ እንዲመቻች ለማድረግ ጥረት ተደርጓል።

ከላይ እንደተገለጠው ውይይቶቹ ከ1995 ዓ.ም. ጀምሮ 27 የ‹‹ርዕይ 2020›› የውይይት መድረኮች አቅራቢዎችና በተጋባዥ እንግዶች የጎላ ተሳትፎ እጅግ በተሳካ ሁኔታ ተዘጋጅቷል። ውይይቱ በአዳራሹ ተወስኖ እንዳይቀር ‹‹ልሳነ ኢኮኖሚክስ›› በተባለው የማህበራችን ወርኃዊ መጽሄት ላይ ታትሞ እንዲሰራጭ ተደርጓል። ከዚህ በተጨማሪ ‹‹ልሳነ ኢኮኖሚክስ›› ህትመቶችን በአንድ ላይ በማሰባሰብ በመጽሐፍ መልክ ማሳተሙ ለተጠቃሚዎች የተለየ ፋይዳ ይኖረዋል ተብሎ ስለታመነ በ1999 ዓ.ም. የመጀመሪያው መጽሐፍ 12 የ‹‹ርዕይ 2020›› የውይይት ሃሳቦችን ይዞ እንዲታተም ተደርጓል። ይህ መጽሐፍ 2ተኛውና ተከታይ መጽሐፍ ሲሆን ከ13ተኛው እስከ 24ተኛው በ‹‹ርዕይ 2020›› መድረክ ላይ የቀረቡትን የውይይት ሃሳቦች የያዘ ነው።

በመጨረሻ በዚህ መጽሐፍ ውስጥ በተካተቱት 12 የውይይት ርዕስ ገዳዮች ላይ በአቅራቢነት እና ሃሰብ በመስጠት የተሳተፉትን እንዲሁም በውይይቱ ወቅት አስተያየትና ጥያቄዎችን በማቅረብ የተሳተፉ የ‹‹ርዕይ 2020›› ታዳሚዎችን በማህበራችን ስም ለማመስገን እወዳለሁ። ይህ መጽሐፍ ይበልጥ ተነባቢ እንደሚሆንና የያዛቸው የተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ገዳዮች በሕብረተሰቡ መካከል በቂ ግንዛቤ እንዲፈጥሩ ያለኝን እምነት እገልጻለሁ።

መልካም ንባብ!

ወልዳይ አምሃ
የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ፕሬዝዳንት

ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ እና ልማት በኢትዮጵያ

ሊሻን አዳም*

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ላደረገልኝ ጥሪና ኢንፎርሜሽን እና ልማት (information and development) በሚል ርዕስ ያዘጋጀሁትን ጽሁፍ እንዳቀርብ ስላመቻቸልኝ በቅድሚያ አመሰግናለሁ::

የጥናት መስኬ ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) በልማት ላይ የሚያመጣውን ተፅዕኖ፣ አዳዲሶች ቴክኖሎጂዎች ፖሊሲዎችና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም አውጪዎችና ለዕርዳታ ሰጪዎች ግንዛቤ ለማስጨበጥ ነው::

ወደ ርዕሱ ከመግባቴ በፊት ግን እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ አገሮችና ባደጉት አገሮች መካከል ያለው ሰፊ ክፍተት መንስኤው ከሆኑት ነገሮች መሀከል አንዱን መጥቀስ እፈልጋለሁ:: ያደጉ አገሮች ሦስቱ ቴክኖሎጂዎች ደረጃ የደረሱት በዕውቀት ላይ የተመሰረተ ፕላን በማውጣትና በህብረት በመተግበር፣ አስተዋይነትና ቀጣይነት ያለው ምርምር በማድረግ፣ የምርምርና የፈጠራ ውጤቶችን ከአገሮቻቸው ዕድገት ጋር እያዛመዱ በተግባር በማዋላቸው ነው:: በአደጉ አገሮች ማንኛውም ማህበራዊና ቁሳዊ ጉዳይ ላይ ምርምር ይካሄዳል:: አዳዲስ ሀሳብ ይፈልቃል:: ግማሹ ሃሰብ በፖሊሲ ቀረፃ፣ ሌላው ወደ አዲስ ሃሳብ፣ የተቀረው ወደ ፈጠራና ልማት ይቀየራል:: እንደገናም ምርምር በየዘርፉ ይቀጥላል:: በእንደዚህ አይነት ቀጣይ "iterative" ትግልና በህብረት በመሥራታቸው ነው ዛሬ በፊልም የምናያቸው ወይንም የጎበኘናቸው ህንፃዎች፣ የምንጠቀምባቸው አውቶብሶችና አይሮፕላኖች የተሰሩት:: ይህ ቀጣይ ዕውቀት ለዩኒቨርሲቲዎችና ለምርምር ማዕከላት ብቻ የተተው ሳይሆን ለመንግስትም፣ ለህዝብም ይደርሳቸዋል:: የመገናኛ አውታሮች (ጋዜጦች፣ መፅሔቶች፣ የምርመር ጽሁፎች፣ ራዲዮኖችና ቴሌቪዥኖች፣ እንዲሁም ኢንተርኔት) ለዕውቀቱ መሰራጨትና መስፋፋት ትልቅ ሚና አላቸው::

በእንዲዚህ አይነቱ ቀጣይ ጥረትና ህብረት የተገነባው የአንድ ሀገር የእውቀት መዋቅር (knowledge ecosystem) የእደገቷን ጥራትና አቅጣጫ ይወስናል:: ይህን ያነሳሁት እግረ መንገዴን ያንድ ሀገር እድገት «የህዝቡ ጭንቅላት ድምር ነው» እንደሚባለው ስለ

---

* ዶ/ር ሊሻን አዳም፤ በአሁኑ ጊዜ የግል የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አማካሪና ተመራማሪ ሲሆኑ፤ በተለያዩ የትምህርት ማዕከላት መምህር ናቸው:: በደቡብ አፍሪካ በሚገኘው ስትሌንቦሽ ዩኒቨርሲቲ ተባባሪ ፕሮፌሰር፤ በዩኒቲ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ አጀንክት ፕሮፌሰር እንዲሁም በተለያዩ የምርምር ተቋማትና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በማገልገል ላይ ይገኛሉ:: በ1995 ዓ.ም በሚሪላንድ ዩኒቨርሲቲ Hewlett Fellow of Information Technology ሆነው ሰርተዋል:: ከ1982 - 1995 በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ከፕሮጀክት አስተባባሪነት እስከ አህጉሩ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አማካሪነት አገልግለዋል:: በአፍሪካ ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ጉዳዮች ብዙ ተሳትፎ ከማድረጋቸውም በላይ በተለያዩ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጆርናሎች ኤዲቶሪያል ቦርድ አባል ሆነው እየሠሩ ይገኛሉ::

ኢንፎርሜሽንና እድገት ሲነሳ የኢትዮጵያን ህዝብ ሕብረ-የዕውቀት መዋቅር (knowledge ecosystem) ደረጃ ማጤን አስፈላጊ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

የኛው አገር የዕውቀት መዋቅር (knowledge ecosystem) በአብዘኛው በስሜታዊነት ላይ የተመሰረተ፣ ሌሎች የሰሩትን የሚጠራጠር፣ የሚንቅና የተሰራው ምርምር ለሌሎች እንዳይደርስ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ፣ በኮሜዲኖ ውስጥ የሚደበቅ በመሆኑ ለድህነታችን አጋዥ ሆኗል የሚል ግምት አለ። ይህን ስሜታዊነት ወደ ጎን ትተን ስለአገራችን የእውቀት መዋቅር፣ ስለ ኢንፎርሜሽን ፍሰትና አጠቃቀም (information flow and use)፣ በዕድገት ላይ ስላመጣው ጥቅም ወይንም ተዕእኖ ያለን ገንዛቤ እምብዛም መሆኑ በጣም አሳዛኝ ነው። በተለይም በዚህ ዘርፍ ያለነው የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ባለሙያዎች ለሀገራችን ኢንፎርሜሽንና ዕድገት ያበረከት ነው ምርምርና አስተዋፅዖ እዚህ ግባ የማይባል፤ አሳፋሪና የታሪክ ተጠያቂ ሊያደርገን የሚችል መሆኑን መግለፅ እወዳለሁ።

የዛሬውም ጽሁፍ፣ ጥልቀት ባለው ምርምር ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በዚሁ ሙያ በአፍሪካ አህጉር ለደርዘን አመታት በመሥራቴ ያለኝን ግንዛቤ (insight) ለማጋራት ነው። በዚህ ጽሁፍ፣ ስለ ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂና ዕውቀት ጽንሰ ሀሳብና በመሀከላቸው ስላለው ገዘምድና ከራሴ ሙያ አንፃር አገልጻለሁ። ቀጥዬ በኢትዮጵያ ውስጥ የነበረውን የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዕድገት አትታለሁ። ከዚህ በማስከተል አሁን ያለንበትን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ከተለያዩ አገሮች ጋር በማነፃፀር አቀርባለሁ። ስለ ኢንፎርሜሽን ICT እና እውቀት ሁኔታ በኢትዮጵያ አንዳንድ መሰረታዊ ጉዳዮችን ካነሳሁ በኋላ በወደፊት ርዕዬ ጽሁፌን እደመድማለሁ።

1. የኢንፎርሜሽን ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ እና ዕውቀት ፅንሰ ሀሳብና ከልማት ጋር ያላቸው ዝምድና

የኢንፎርሜሽን ኢንፎርሜሻን ቴክኖሎጂና ዕውቀት በጣም ተደጋግፈው ከመምጣታቸውም በላይ ማህበረሰቦች የኢንፎርሜሽን ማህበረሰብ (info society)፣ ኢኮኖሚው የእውቀት ኢኮኖሚ (knowledge economy)፣ ዘመናችን የኢንፎርሜሽን ዘመን (information age)፣ ከሆኑ ሰንበትበት ብለዋል። ኢንፎርሜሽን ከኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ከዕውቀት ተነጥሎ የማይታይበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። ለመሆኑ ኢንፎርሜሽን ምንድነው? ዕውቀትስ ምንድነው? ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ስንል ምን ማለታችን ነው?

ኢንፎርሜሽን እያንዳንዱ ሰው ከራሱ ግንዛቤና ግምት አንፃር ከሚተረጉማቸው ፅንሰ ሀሳቦች አንዱ ነው። ለባዮሎጂ ባለሙያው ስለ ጂኔቲክስ ኮድ መተላለፍ፣ ለቤተ-መጻህፍት ባለሙያው ከመጻህፍት ና መገለበች ጥርቅም፤ ለኮምፒዩተር ባለሙያው በኮምፒዩተር የተጠናቀረ መረጃ፤ ኢንፎርሜሽን ተብሎ ሊወሰድ ይችላል። ኢንፎርሜሽን ለግለሰብ፣ ለማህበረሰባዊና ለድርጅት ህልውና ወሳኝ የሆነ፤ ኮሙዩኒኬሽንና መረጃ ለማስተላለፍና ለመቀበል የሚረዳን፣ ችግሮችን ለመፍታት የሚጠቅም መሣርያ ነው። ኢንፎርሜሽን ብዙ መሰረታዊ ባህርያት አሉት።

ኢንፎርሜሽን በአንድ በኩል ግልፅነት ሊጎድለው እና የበለጠ እንድንጠይቅ ሲረዳ፤ በሌላ በኩል ጥርጣሬን በማስወገድ የዕውቀታችንን ይዘት የሚለወጥ ኃይል አለው። በኢንፎርሜሽን

ንድፈ-ሀሳብ (ቲዮሪ) ኢንፎርሜሽን ማለት አዲስ መልእክት ማለት ነው። መልእክቱ ኢንፎርሜሽን የሚሆነው ከጫጫታው በልጦ ሲጎላ ነው (high signal to noise ratio)። መልእክቱ ከዚህ በፊት የማይታወቅ ከሆነ የኢንፎርሜሽን ይዘቱ የበዛ ነው፤ ደግመን ከሰማን ግን የኢንፎርሜሽን ይዘቱ ዝቅተኛ ይሆናል። የምናውቀውን የሚነግረን ሰው ጊዜያችንን ከማባከን በስተቀር መልዕክት እንደማያስተላልፍ ሁሉ እንደ ማለት ነው።

በኢንፎርሜሽን ቲዮሪ «እየተጠና ነው»፣ «እየተደረገ ነው»፣ «እየተሰበሰበ ነው»፣ የሚሉት ግልፅ ያልሆኑ መልዕክቶች፤ የሚያስተላልፉት ኢንፎርሜሽን ዝቅተኛ ነው። ግለሰቡ «እየ. . . ተደረገ ነው»፣ «እየተሰራ ነው»፣ ይላሉ ብለን ቀድመን ከገመትን የሚያስተላልፉልን ኢንፎርሜሽን ዜሮ ነው።

ሌላው የኢንፎርሜሽን ባህሪይ፣ አንዱን በመረጃ ማበልፀግና ሌላውን ማራቆት ነው። የኢንፎርሜሽን ማህበረሰብ ኢንፎርሜሽን የሌለውና ያለው (info rich info poor) ብለን የምንጠራውን መፍጠር ነው። የኢንፎርሜሽን ድህ የሆነው ወገን ጉልበትና ሀይል ዝቅተኛ ሲሆን የኢንፎርሜሽን ሀብታም በድህው ላይ ተፅዕኖ የማድረግ ችሎታ ይኖራዋል። አንድ ሰው፣ ድርጅት ወይንም ማህበረሰብ በአንድ በኩል የኢንፎርሜሽን ሀብት ቢኖረው፤ በሌላ በኩል የኢንፎርሜሽን ድህ ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ፤ በጣም የተማረ ሰው የቴፕ ክር እንዴት እንደሚያዘፍን ላያወቅ ይችላል። የዓለምን ሁኔታ ጠንቅቆ የሚያውቅ ሰው የቤቱ፣ የጎረቤቱና የሰፈሩ ህይወት ግንዛቤ ላይኖረው ይችላል። ዋናው የኢንፎርሜሽን ሀብትና ድህነት ፅንሰ ሀሳብ የሚያተኩረው ባለማወቅም ሆነ በማወቅ አንድ ሰው ወይንም ማህበረሰብ ኢንፎርሜሽን እንዳይደርሰው እገዳ ተደርጎበት ህልውናውና ዕድገቱ ሊዛባ መቻሉ ነው።

- አንድ ግለሰብ፣ ድርጅት ወይንም ማህበረሰብ መገናኛ ብዙሃን የማይደርሰው ከሆነ፤
- ግለሰቦች ቡድን ፈጥረው ከቡድናቸው ውጪ መረጃ እንዳይወጣ የሚያደርጉ ከሆነ (ይህ በሳይንቲስቶች ዘንድ የተለመደ ተግባር ነው)፤
- ያልተማረና የተላለፈውን መረጃ ማገናዘብ የማይችል ከሆነ፤
- ከልክ በላይ በመኮፈስ ሊደርሰው የሚችለውን መረጃ የማያጣጥምና የማይቀበል ከሆነ፤
- የሚደርሰው መረጃ ከዚያ ፈቅ የማይል፣ ዘላለም ተመሳሳይ ወሬና ፍሬ ፈርስኪ ከሆነ፤
- የሚፈልገውን መረጃ ዋጋ (በገንዘብ፣ በጊዜ፣ በልፋት) መክፈል ከሚችለው በላይ ከሆነ የኢንፎርሜሽን ፍሰቱ ስለሚዛባ ያለመመጣጠንና ክፍተት (information asymmetry) ሊፈጠር ይችላል።

የኢንፎርሜሽን ክፍተት (asymmetry) በሚፈጠርበት ጊዜ ሁሉ መረጃውን የያዘው ወገን ልምጃ ለመቀበል (rent extraction) መቋመጡ አይቀሬ ነው። በኛ ሀገር ያለው የሙስና፣ ሌሎችም ሥነ ምግባር የጎደላቸው ድርጊቶች አብዛኛውን ጊዜ የኢንፎርሜሽን ክፍተት (information asymmetry) በመስፋት ላይ መሆኑን ሳትገነዘቡ አልቀራችሁም። እፊቱ የሚፈረመው ጽሁፍ እያለ፤ አልደረሰም ነገ ተመለሱ ከተባላችሁ፤ በናንተና በፈራሚው መሀከል የኢንፎርሜሽን ክፍተት አለ ማለት ነው።

በኢንፎርሜሽንና በልማት መካከል ያለው አንዱ ትልቁ ግንኙነት ትክክለኛ ኢንፎርሜሽን በጊዜው፣ በቦታው፣ ማግኘት ልማትን ሲያፈጥን በተቃራኒው የኢንፎርሜሽን ክፍተት (asymmetry) ዕድገትን መግታቱ ነው። እውነተኛ መረጃ ያለው ለመብቱ መከራከር

አይቀርም። ለመብቱ የሚከራከር ለእድገት መሰረት የሆነውን መልካም አስተዳደር ማምጣት ይችላል። ትንሽ ቅንጣት መረጃ በግለሰቦች፣ በድርጅቶችና በማህበረሰብ ላይ የምትፈጥረው ጫና ከፍተኛ ሊሆን ስለሚችል አብዛኛውን ጊዜ የኢንፎርሜሽንን ዋጋ በገንዘብ መግለጽ አይቻልም።

ስለ ኢንፎርሜሽን ይህንን ካልን፤ ስለ ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ትንሽ ግንዛቤ መስጠት እፈልጋለሁ። ከአስር አመታት በፊት ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT) የምንለው በአሁኑ ጊዜ ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ተብሎ የሚጠራበት ዋናው ምክንያት ተለያይተው የነበሩት የኮምፒዩተርና የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች በመዋሃዳቸው ነው። ድሮ በአንድ የስልክ መስመር ሃሎ ማለት ብቻ የነበረው ቀርቶ አሁን በዚያው መስመር የኢንተርኔት መልዕክት ማስተላለፍ በመቻላችን ነው። ድሮ ለዜናና ለመዝናኛ የሚያገለግሉት የሬድዮና ቴሌቪዥን ቻናሎች በኮምፒዩተር አማካይነት መረጃ ልንቀበልባቸው መቻላችን ነው። ይህ ውህደት (convergence) የቴሌኮሙዩኒኬሽን አገልግሎትን እያሻራረፈው መሆኑን መግለፅ ብቻ ግንዛቤያችንን ሊያስፋፋው ይችላል።

ለምሳሌ፤ እንዲት ግለሰብ እቤቷ ተቀምጣ በአንድ የስልክ መስመር ብቻ የስፖርት ዜና በኢንተርኔት ድህረ ገፅ እያየች የኢሜል መልዕክት እየላከች አሜሪካ ካለው አጎቷ ጋር ቴሌፎን (Voip) በምንለው እየተነጋገረች ደሴ ካለችው ጓደኛዋ ጋር በኮምፒዩተር ማውራት (Chat) ማድረግ ትችላለች። ይህ ውህደት (convergence) ለተጠቃሚው ዓለም ሲሆን ለአገልግሎት ሰጪዎች ራስ ምታት ሊሆንባቸው ይችላል። ለዚህም ነው የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ነፃ አውጪ ነው (liberating) ተብሎ የሚወሰደው።

የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ የምንለው የኮምፒዩተርና የሶፍትዌር መረጃዎች የግንኙነት መረቦች (network) ብቻ ሳይሆን፤ በእነሱ የሚሰሩትን ሰዎች፣ ህጎች፣ አሮጌዎችና አዳዲሶች የመገናኛ ዘዴዎች፣ ወዘተ... ማለታችን ነው። የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዋናው መሰረታዊ ባህሪይ ኢንፎርሜሽን ማቀናበርና ማስተላላፍ (information processing)፣ ማስቻል ብቻ ሳይሆን ዕውቀትን ለማካፈል (knowledge sharing) ማስቻሉ ጭምር ነው። ኢንፎርሜሽንና እውቀት በየቦታው ተፈላጊ የመሆናቸውን ያህል ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂም የማይገባበት ቦታ እየጠፋ መጥቷል። መረጃውን በቀላሉና በርካሽ ለማቅረብና በቀጥታ ለተጠቃሚው በማድረስ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን የሚስተካከለው የለም። ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ሶስት መሰረታዊ ባህሪዎች አሉት።

1. በአንድ ማህበረሰብ ያለው የባህል፣ የኢኮኖሚ፣ የድርጅታዊና የሳይንሳዊ አቋም የICT አጠቃቀምና ሚና ይወስነዋል። ሲንጋፖር የእስያ መገናኛ መዕከል (hub) የሆነችውን ያህል፣ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ማዕከል (hub) ልሁን ብትል መረባረብ ያለበት በኢኮኖሚው፣ በድርጅታዊና ሳይንሳዊ አቋም ላይ እንጂ በቴክኖሎጂ ግዢ ላይ አለመሆኑን ይህ ያሳየናል።
2. ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አብይ ጉዳይ አንድ ማህበረሰብ በፈቀደው አቅጣጫ መግራትና የሚያመጣውን ጥቅምና ውድቀት መቆጣጠር መቻሉ ነው። ይህ ማለት ትክክለኛውን ፖሊሲ በመቅረፅ አገራችን ከዚህ ቴክኖሎጂ ብዙ መጠቀም ትችላለች ማለት ነው።

3. ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ለግለሰብ፣ ለድርጅትና ለማህበረሰብ የሚጠቅም በጎ ጎን (enabling) ብቻ ሳይሆን አፍራሽ (constraining) ጎኖችም አለ·ት:: ይኸኛው ባህሪይ በጭፍኑ "·ቴክኖሎጂ ወይንም ሞት" ከማለት ረጋ ብሎ የሚጠቅመውንና የሚያሳድገውን መምረጥ እንዳለብን የሚያስገነዝብ ነው::

ቀደም ብዬ እንዳልኩ·ት የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ አንደኛው ጥቅም ዕው·ቀትን ለማሰራጨት መርዳቱ ነው:: «ዕው·ቀት ኃይል ነው·» ("knowledge is power") የሚለው የጥንቱ አባባል «ዕው·ቀት ልማት ነው·» ወደሚለው በመሸጋገር፣ የዕው·ቀት መጎልበትና መሰራጨት ለልማት በር መክፈት ወሳኝ መሆኑ ስለታመነበት፤ ባለፉ·ት አስርተ አመታት ከኢንፎርሜሽን ማኔጅመንት ይልቅ ለዕው·ቀት መሰራጨት (knowledge management and sharing) ከፍ·ተኛ ትኩረት ተሰጥቷል:: የአለም ባንክ እንደ ኮሪያ፣ ሲንጋፖርና ሆንግኮንግ ያሉ· አገሮች በአጭር ጊዜ ያደገ·ት ዕው·ቀት-መር ፈለግ በመከተላቸው በመሆኑ ታዳጊ ሀገሮችም ይህንኑ መስመር ተከትለው ህዝባቸውን ካስተማሩና አዳዲስ ቴክኖሎጅ መጠቀም ላይ ቢበረቱ ጥሩ ው·ጤ·ት ያገኛሉ ብሎ ያምናል:: ያደገ· ሀገሮች ከተፈጥሮ ሃብታቸው ይልቅ ወደ እው·ቀት የመሸጋገራቸው ዋናው ሚስጥር እየቀነሰ ከሚሄደው የተፈጥሮ ሃብታቸው የበለጠ ው·ጤ·ት ማግኘት የሚችሉ·ት ዕው·ቀትና ብልሃት ሲኖራቸው መሆኑን በማመናቸው ነው::

የተፈጥሮ ሀብታቸው አየተመናመነ የሚሄደው እንደ ኢትዮጵያ ያሉ· አገሮች የማያስፈልጋቸው፤ በእው·ቀትና ብልሃት ላይ የተመሰረተ ቀጣይ ፕላኖች ማስፈጸም ሲችሉ ነው:: ለዚህም እንዲረዳ፤

1ኛ/ ዕው·ቀትን በመጨበጥና ለራሳቸው በሚሆን መልኩ ማደራጀትና ማሰራጨት፤
2ኛ/ ህብረተሰቡን በማሰልጠንና ዕው·ቀትን እንዲጠቀመ·በት ማድረግ፤
3ኛ/ የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን ለዕው·ቀት ስርጭት መጠቀም አለባቸው::

ዋናው ነገር ዕው·ቀት በሰዎች አእምሮ ው·ስጥ ያለና በአመቺ ጊዜ ብቻ የሚተላለፍ በመሆኑ፤ አንድ ሰው· በግድ ዕው·ቀት እንዲጠቀም ወይንም እንዲያሰራጭ ማድረግ ስለማይቻል ድርጅ·ቶችና መንግሥ·ት· እው·ቀትና ብልሃት የሚያስፋፉ·በትንና የሚያንሸራሽሩ·በትን መንገድ መቀየስ አለባቸው· የሚለው· ነው:: ያለኝ አነስተኛ ግንዛቤ የሚጠቁመው በሀገራችን የሚንሸራሸረው· ዕው·ቀት አነስተኛ ከመሆኑም በላይ አዳዲስ ሀሳቦችን ተቀብለን ወደ ሥራ ለመተርጎም ወይንም የመጀመርያው·ን እርምጃ ለመራመድ በጣም የሚያስቸግረን ቅን ባልሆነ ልቦና በንቀት ላይ የተመሰረተ· እዚያው· የሚረገጥ፤ አንዳንዱም ወደ ኋላ የሚራመድ፤ የዕው·ቀት መዋቅር (knowledge ecosystem) ው·ስጥ የምንገኝ በመሆናችን ነው:: ለመሆኑ ከዚህ እንዴ·ት· መው·ጣ·ት· ይቻላል?

ብዙ·ዎቹ፤ ሳይንቲስቶች የሚስማሙ·በት· መፍትሄ እው·ቀት እንዲንሸራሸር ከተፈለገ፤

1ኛ/ ዕው·ቀት· ለሰዎች በሚገባ መልኩ በአድራጊው· አንደበት· ተቀናብሮ በተግባር በትረካ መልክ መቀረብ አለበት:: ጋዜጠኞች ባለመ·ያዎች፣ ወይም ባለመ·ያዎች ጋዜጠኞች፣ መሆን ሲችሉ· ጥሩ አስተማሪዎች፣ የተግባር ልምድ ያላቸው· መሆን ይችላሉ::

2ኛ/ ዕው·ቀት· በትረካ (narrative) መልኩና በተግባር ካልቀረበ ትኩረት አይስብም:: ተቀባይ በሰማው·ም በኖ ይቀራል:: ይህም ማለት፤ በተለምዶ እንደሚደረገው· ዕው·ቀትን

በመጻህፍት፣ በመገናኛ ብዙሃን ወይንም በሰበካ መልክ ማሰራጨት ብቻ ሊያሰርፀው አይችልም። በዕውቀትና በተግባር መካከል ድልድይ እንዲሰራ ከተፈለገ መጀመርያ ዕውቀቱን ማስረጽ ያስፈልጋል፤ ቀጥሎ ግለሰቦች በተግባር (action) ህይወታቸውን እንደሚቀይሩ አምነው መንቀሳቀስ አለባቸው።

3ኛ/ መማር የሚቻለው፤ የለመድነውና የምንወደው ዕውቀት ማግኛ መንገድና ሥር የሰደደው አስተሳሰቦች መቃወስ (disrupt) ሲጀመሩ ነው። ልምዶቻችንና አስተሳሰቦቻችን ከተቃወሰ ለአዳዲስ አስተሳሰቦች በር በመክፈት መንገዶችን መቀየስ እንጀምራለን። ለድህነት ምሰሶ የሆኑትን የሥራ ባህላችንን፣ ጥገኝነት፣ ቅን ያልሆነ አስተሳሰብ፣ ስንፍናንና ስለ ግልና የአካባቢ ንፅህና ያለንን አስተሳሰብ ማቃወስ የሚቻለው፣ አሁን እንደተያያዝነው ፊት ለፊት በቀጥታ በስብሰባ ስንፍናንና ብዙ በአላትን በማወገዝ ሳይሆን፤ ብልሃት በተሞላበት የህብረተሰቡን ማህበራዊ ህይወት፣ የነዚህን ችግሮች ጉዳት ባገናዘበ መልኩ፣ በተዘዋዋሪ በሚቀርቡ የልምድ ቀዋሽ (disruptive metaphor) ዘዴዎች ስንነሳ ነው።

4ኛ/ ዕውቀትን ማጋበስ ወይንም ዕውቀት የሚደራጅበትን ተቋሞች መገንባቱ ብቻ ያንድን አገር አጠቃላይ የዕውቀት መዋቅር (knowledge ecosystem) ሊያዳብር አይችልም። በተንዳኛ ዕውቀቱ ካንዱ ወደ አንዱ የሚተላላፍበትን ቻናል (channel) መገንባቱና ለተግባር (action) መነሳሳቱ የበለጠ ውጤት ያመጣል። ሰዎች ስለተለያዩ ጉዳዮች የሚወያዩበትን ጠቃሚ ማህበራዊ መረቦች (network) መገንባት ለዕውቀት መስራጨት የበለጠ አስተዋዕኦ ያደርጋል የሚል ግምት አላቸው። ደግነቱ በሀገራችን ብዙ ማህበራዊ መረቦች (social network)፣ ለምሳሌ፤ እንደዛሬው ስብሰባ አይነት አንዱ ተናጋሪ ሌላው አድማጭ የሚሆንባቸው ወይንም እንደቡና ላይ ወሬ አይነቶቹ አሏት። እነዚህን በመንተራስና በማዳበር ለእውቀት መንሸራሸር በሚያመቹ መንገድ ማስተካከል ከዕውቀት ወደ ተግባር ለመሸጋገር የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይቻላል።

ዋናው ቁምነገር መንግሥት በምርምርና በሥርዐት፣ እንዲሁም በእውቀት ፍለት ካመነና ከተንቀሳቀሰ፣ ምሁራኖችና በየአህጉሩ የተበታተኑ ኢትዮጵያውያን ተባብረው የዕውቀት መተላለፍያ ማህበራዊ መረቦችን ካጠናከሩ፤ በዕውቀት መዋቅራችን (knowledge ecosystem) ላይ ሰፋ ያለ ጥናት ካካሄድንና ውጤቱንም ተግባራዊ ካደረግን፤ አገራችንን በዕውቀት-መር እድገት መስመር ላይ ልናሳትፍ እንችላለን።

ይህ ማለት የወጪ ዕውቀት አያስፈልገንም ማለት አይደለም። ብዙዎች ኢትዮጵያውያን ከወጪው ዓለም መረቦች ጋር ግንኙነት ስላላቸው ርብርብ ማድረግ ያለበን የሀገር ውስጥን ዕውቀት አቅም መገንባት ላይ መሆን አለበት። «የሰው ወርቅ አያደምቅ» እንደሚባለው ሁሉ በወጪ ኮንሰልታንት እውቀት ላይ ያደገ አገር የለምና የሀገራችንን የእውቀት መዋቅር (knowledge ecosystem) መገንባቱ የህዝባችን አንገት ከድህነት ቀና ስለሚያደርገው ትኩረቱ በሩቁ አቅም ላይ መሆን አለበት። ለመሆኑ በሀገራችን ያሉ የእውቀትና የመረጃ ሁኔታ ምን ይመስላል?

2. የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን እድገት በኢትዮጵያ

አገራችን ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን ለማስገባት ቀዳሚ ብትሆንም ላለፉት መቶ አመታት ያደረገችው እመርታ እምብዛም የሚያኮራት ሆኖ አልተገኘም:: ለምሳሌ፤ በቴሌኮሙዩኒኬሽን ዘርፍ ከአፍሪካ የመጀመሪያዎቹ ቀደምት አገራት ብትሆንም International Telecommunication Union አምና ባወጣው Digital Access Index ቀመር ከመጨረሻዎቹ ተርታ በአምስተኛ ላይ ትገኛለች:: ኮምፒዩተር ወደ አገር በማስገባትና በመጠቀም ኢትዮጵያ አንዷ ቀዳሚ አገር ነበረች:: ኮምፒውተሮች ወደ ኢትዮጵያ የገቡት አንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1960፣ ዝምባብዌና ዛምብያ 1961፣ ኮትዲቯር ናይጄርያና ጎረቤታችን ኬንያ 1962 ነው:: ነገር ግን በኮምፒውተር አጠቃቀምና (info use) የሰው ሀብት (info density) Orbicom የሚባለው የጥናት ድርጅት ባወጣው ሰንጠረዥ ሀገራችን የመጨረሻዋ አገር ነች:: የመረጃ መዋቅሮቻችንም ይኽን ያህል ዕድገት አሳይተዋል ማለት አይቻልም:: ለግንዛቤ እንዲረዳን የመረጃ መዋቅሮቻችንን በስድስት ተደጋጋፊ ክፍሎች ከፍለን ማየት እንችላለን፤

1. አብያተ መዛህፍትና ቤተ መዛግብቶቻችን
2. በመንግስትና በግል ድርጅት የሚጠናቀሩ መረጃዎች
3. ከምርምርና ስርፀት የሚወጡ መረጃዎችና የምርምር ውጤቶች
4. በመገናኛ ብዙሃን ለህዝብ የሚቀርቡ መረጃዎች
5. በኢንተርኔት ስለ ሀገራችን ያለው ኢንፎርሜሽን
6. የባህልና የተለምዶ ዕውቀታችን (indgenous knowledge)

ሀ. የአብያተ መዛህፍትና ቤተ መዛግብቶች ዕድገት

ቅኝ ገዢዎች በተለያዩ አፍሪካ ሀገራት ትተው ከሄዱት አንዱ ቁም ነገር አብያተ መዛህፍት እንዲስፋፉ መሰረት መጣላቸው ነው:: ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ ብዙዎቹ የደቡብ አፍሪካ አገሮች አብያተ መዛህፍታቸውን ቢያስፋፉም በኛ አገር ግን ከየትምህርት ቤቱና በየከተማው ብቅ ብቅ ካሉት አንዳንድ መዛህፍት ቤቶች በስተቀር ይህ ነው የሚባል የአብያተ መዛህፍት ዕድገት ማምጣት አልቻልንም:: በነፍስ ወከፍ አንባር ሲታይ የአገራችን የቤተ መዛህፍት ድርሻ ከዓለም በጣም ገቅተኛ ነው:: በአገራቱ ያሉት መዛህፍት ቤቶች አነስተኛ በመሆናቸው ለዩኒስኮም ዘገባ ያስቸገሩ ይመስለኛል::

በዓሜው ዘመን በየትምህርት ቤቱ ብቅ ብቅ ያሉት አብያተ መዛህፍት ቤቶች በደርገ ዘመን ማርክሲስዚም ሌኒንዚምን ለማስፋፋት በቀበሌ የጥናት ክለቦች አማካይነት መደራጀት ጀምረው ነበር:: ምንም እንኳን የያዙት መዛህፍት ዓይነት የአገዛዙ ነፀብራቅ የሆኑ የማኦ፣ የማርክስ፣ የኤንግልስ፣ የሊኒንና የሩስያ ሥነ-ዕሁፍ ቢሆንም ለቤተ መዛህፍት መደራጀት የተደረገ ተኩረት ከአሁኑ ጊዜ የተሻለ ነበር::

እንዲያውም የመሠረተ ትምህርት ዘመቻን አስታክኮ ወደ 7000 ሺህ የሚጠጉ የንባብ ቤቶች በየቀበሌው በመላ ሀገሩ ተቋቁመው ነበር:: በአሁኑ ጊዜ በኢሉባቦር ዞን ከሚገኙትና በአስገራሚ ሁኔታና አክስፋም ካናዳ በሚባለው ድርጅት ብርታት ተርፈው ህዝቡን አንባቢ ካደረገት 12 የማሆኑ መዛህፍት ቤቶች በስተቀር ሁሉም የንባብ ቤቶች ከመጥፋታቸውም

በላይ የተጠቀሱ ጎልማሶች እንደገና ተመልሰው መሀይም መሆናቸውን የምናውቀው ጉዳይ ነው። ስለ አሊባባሮቹ ቤተ መፃህፍት ሰሩ ባለ በታተመ ሌላ ጥናት ስለገለፅኩ እዚህ አልደግመውም።

ዋናው ቁምነገር የአብያተ መፃህፍት ያለመኖር ህዝቡ እውቀትን እንዳይጨብጥ ብቻ ሳይሆን በእነርሱ አማካይነት የሚያገኘውን የመገናኘትና ትግሩን የመወያየት፣ በተለይም በወላቱ ላይ እውቀትን የመገብየት ቅናት መቀነሱ፣ ስለእድገታችን መቀጨጭ አስተዋፅ ማድረጉ ነው። አሁን በየትምህርት ቤቱ፣ አልፎ አልፎም በየከተማው፣ ያሉት አብያተ መፃህፍት አልፎ አልፎ ብልጭ ከሚለው የውጭ የመፃህፍት ዕርዳታ በቀር፣ በገንዘብና በማቴሪያል እጥረት እየዘቀጠ ከመሄዳቸው በቀር ለእድገት ያደረጉት አስተዋጽኦ አይታይም። ብዙዎቹ የአካዳሚ (የትምህርት ቤት) ቤተ መፃህፍት ከጊዜና ከቴክኖሎጂ ጋር የሚለውጡ የእውቀት በሮች ሳይሆኑ፤ አስተማሪ አንብበው ያለውንና የጠቀሳቸውን መፅሀፍት ተቀምጠ ማንበቢያ ወይንም ለአጭር ጊዜ የመፃህፍት ዋሻ ህንፃዎች ሆነው ቀርተዋል። የፎቶ ኮፒ ቴክኖሎጂ መስፋፋትና መርከስ እስከናካቴውም የነዚህን ጠቀሜታ እያሳነሰ መጥቷል። ለአብያተ መጽሀፍቶች መደራጀት መደረግ ከሚገባቸው ነገሮች መሀከል፤

- የኢለባሪያን ተሞክሮ በመጠቀም ህዝቡ የሚሳትፍበትን የአካባቢ ማንበቢያ ቤቶች ማስፋፋት፤
- አዳዲስ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የአገልግሎታቸውን ስፋት ማዳበር፤
- በአብያተ መጻህፍቶች መካከል የወድድርና የመረዳዳት ስሜት መፍጠር፤
- የንባብ ሳምንቶችን በዓል በማዘጋጀት ወጣቱንና ህዝቡን ወደ ንባብ ቤቶች መሳብ።

ስለንባብ መስፋፋት ሲነሳ በቅርቡ የደረሰብኝን ነገር ልናገር። አንድ ሻይ ቤት ተቀምጬ ሻይ አዝዤ ወረቀቱን በማገላበጥ ላይ እንዳለሁ ልጁ መጥቶ እዚህ ማንበብ አይቻልም አለኝ። ሻይ እስክጠጣ እኮ ነው የማነበው ስለው ማንበብ አይፈቀድም አለኝ። ታዲያ እነዚህ የሚያወሩትን ለምን ፈተድክላቸው ስለው ወሬ ይቻላል አለኝ።

ለ. በመንግሥትና በተለያዩ ድርጅቶች የሚጠናቀሩ መረጃዎች

በአገራችን በመንግሥትና በተለያዩ ድርጅቶች (በእርሻ፣ በትምህርት፣ በጤና፣ በከተማ መሬት፣ በንግድ፣ በታክስ፣ በወንጀል፣ በኢንቨስትመንት፣ በበድር) እስታትስቲክስ ላይ የተደረገ ሰፊ ጥናት ባለመኖሩ ምን ያህል ዳታ ቤዞችና የቱን ያህል ተጠቃሚዎች እንዳሏቸው መገመት ያስቸግራል። የመረጃንና የመዛግብትን አያያዝ ጠቃሚነት ባለማወቅ በህዝቡ ላይ በየመስሪያ ቤቱ የሚደርሰው መጎላላት፣ ለምሳሌ፤ ኮምፒዩተር ተበላሽቷል፣ መብራት ጠፍቷል፣ ወደ ኮምፒዩተር እየቀየርን ስለሆነ ባለመያ የለም፣ ወዘተ... እየተባለ የሚባክነው ጊዜ ሲታይ እስካሁን የተደረገው ለውጥ የመረጃ ችግራችንን ከመፍታት ይልቅ ያባባሰው ይመስላል። በ1980ዎቹ፤ መጀመሪያ በኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን የተጀመረው የመረጃ ማጠናቀሩ ሥራ በ1990ዎቹ፤ መባቻ ላይ ጋብ ካለ በኋላ በአሁኑ ጊዜ እያንሰራራ ይገኛል። በተለይም በአሁኑ ጊዜ መንግሥት ቀልጣፋ አሰራርን ለማስፋፋት ባደረገው ጥረት በተለያዩ ድርጅቶች ኮምፒውተሮችን በመጠቀም የተጠቃሚዎቹን መገላላት ለማሳጠር አንዳንድ እርምጃዎች በመውሰድ ላይ ይገኛል።

ነገር ግን የሚሰበሰበው የመረጃ ጥራት፣ የኢንፎርሜሽን ባለሙያዎች እጥረትና ጥራት፣ የኮምፒዩተር ባለሙያዎች ፍልሰት፣ ስለኮምፒዩተር አጠቃቀም ያለውን ግንዛቤ፣ እንዲሁም የመሳሰሉት ችግሮች እስካሁን የተደረገውን ጥረት ያሰናክሉት ይመስላል። በአንዳንድ ግለሰቦች የሚነገረው ኮምፒዩተርን ተጠቅመን 30 ቀናት የሚፈጀውን ሥራ ወደ 30 ደቂቃ አውርደናል የሚለው አባባል በአገራችን ስለኮምፒዩተር ያለው ግንዛቤ ገቸተኛ መሆኑን ግልጽ አድርጎታል። ኮምፒዩተሮች ያለ ሰዎችና ሰራተኞች ወይም ካለማህበረሰቡ የባህል ለውጥ ብቻቸውን ሥራውን ከ30 ቀናት ወደ 30 ደቂቃ አያሸጋግሩም። ቁም ነገሩ ያለው ከሰዎች አስተሳሰብ መቀየርና የሥራ ቅልጥፍና እንጂ በቴክኖሎጂው መቀየር ላይ አይደለም። ሰዎች ከፈለጉ፣ የአሰራርና የአመራር ቅልጥፍና ከተቀየረ፣ ኮምፒዩተሮች ጥሩ መሳሪያ ሊሆኑ ይችላሉ። አለበለዚያ የተበላሸውን በፍጥነት እንዲበላሽ መንገድ ይከፍታሉ።

ሆኖም ኮምፒዩተሮችን መጠቀም የተሻለ የሥራ ቅልጥፍና አያመጣም ማለት አይደለም። በጥናት ላይ የተመሰረተና በመረጃ መረቦች ላይ የተደገፈ የኮምፒዩተር አጠቃቀም መረጃ ለማደራጀትና መገላላትን ለመቀነስ የሚያገለግል ብቻ ሳይሆን ያለንን ኢንፎርሜሽን በማቀነባበር፣ ትርጉም (meaning) እንዲኖረው ያደርጋል። በእርሻ፣ በትምህርት፣ በጤና፣ የሚሰበሰበው መረጃ ከእስታትስቲክስና በየቀበሌው ና በየወረዳው ከሚሰበሰበው ጋር ቢገናኝ ለፕላን፣ ለትምህርት፣ ለምርምርና ስርፀት መዳበር መሰረት ይሆናል።

በኢትዮጵያ እስከ አሁን ያለው የኮምፒዩተር መረጃ ስርዓት ለድርጅቶቹ፣ የውስጥ ፍላጎት ማማያ የተደራጀ እንጂ ከተለያዩ መሥሪያ ቤቶች ጋር ለመለዋወጥና ለመዳበር የተደራጀ ባለመሆኑ ጠቃሚነቱንና ልፋቱን ዋጋ አሳጥቶታል። በዚህ በኩል ያለንን እንቅስቃሴ ትርጉም ለመስጠት፤

1ኛ/ በኮምፒዩተር የሚጠናቀሩ ማናቸውም መረጃዎች ለልውውጥ በሚያመች መልኩ መዳበር አለባቸው፤

2ኛ/ በየመስሪያ ቤቱ ያሉ የኢንፎርሜሽን ባለሙያዎች ጥራት ያለው፣ መረጃ እንዲያጠናቀሩና እንዲለዋወጠ ማመቻቸት ያሰፈልጋል፤

3ኛ/ በኮምፒውተር የሚተላለፈውን መረጃ ህገዘቡ በቀላሉ የሚያገኝበት መንገድ መመቻቸት አለበት፤

4ኛ/ ለህዝብ የሚጠቅመ ማለትም ለትምህርታዊነት የሚረዱ መረጃዎች አፕሊኬሽን (የጤና፣ የትምህርት፣ የቢዝነስ) እንዲስፋፉ ያስፈልጋል።

ሐ. ከምርምርና ስርፀት የሚወጠ መረጃዎች

የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምርምር ወጤቶቻችን ልንነባባው ለምንፈልገው የኢንፎርሜሽን ማህበረሰብ መሰረት ቢሆኑም፤ አገራችን በአሁኑ ጊዜ በእርሻ፣ በጤና፣ በኢሚስትሪ፣ በታሪክ፣ በሶሲዎሎጂ፣ በኢኮኖሚክስ፣... ዘርፎች ከሚታየው እንቅስቃሴ ሌላ በተለያዩ የሙያ ዘርፎች የሚያመረቃ የምርምርና ስርፀት ወጤት ባለቤት ለመሆን አልቻለችም። አገራችን እየተረባረበችበት ያለችው የድህረ ምረቃ ፕሮግራሞች የማስፋፋት ሥራ የምርምርና ስርፀትን አቅም ይገነባል ብለው የሚያስቡ ቢኖሩም በሌሎች ዓለማት እንደታየው ዓይነት ተመራማሪዎችን የሚያበረታታ የሞራል፣ የማቴሪያል፣ ሁኔታዎች በሌለበት በድህረ ምረቃ ደረጃ ማስተማር ብቻውን ምርምርና ስርፀትን ሊያስፋፉ ያለመቻሉን ከቅርብ ጊዜ ልምዳችን አይተናል።

በዚህም በዙሪያ አገራችን የምርምር ውጤቶች የሚታተሙባት ሳትሆን ተደብቀው ከሚቀሩ
አንዷ ነች። ሰባ ሚሊዮን ህዝብ ከሚኖርባት አገር ከ10 በታች ጆርናሎች ይታተሙባ
የተመራማሪዎች የማሳተም ስንፍና፣ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችግሮችና የኢንተርኔት ግልጋ
ማነስ፣ ከእጅ ወደ አፍ የሆነው የተመራማሪዎች ኑሮ ተዳምሮ፣ ከጎረቤቶቻችንና ከአብዛ
የአፍሪካ አገሮች በታች በሆነ የምርምር ውጤቶች ህትመት (scientific publishing)
እንድንገኝ አድርጎናል። ጥቂት ኢትዮጵውያን ወደ ውጭ አገር ሄደው በሙያቸው አ
በሚባሉት፤ የሌሎችን ችግር በሚፈቱበት፤ አገራችን በአገር ውስጥ የምርምር ስር
ህትመት፤ ሃብታችን እንደዚህ መድረቁ በጣም አስገራሚም፣ አሳዛኝም ነው። ጠለቅ
የአገር ችግር የሚፈታ ቀጣይ ምርምር በየፊናው፣ በየዘርፉ፣ ለህዝቡና ለተመራማሪዎ
ካልተሰራጨ እንገነባለን የምንለው የእውቀት-መር ኢኮኖሚ ዘበት ሆኖ ይቀራል
መንግሥትና የምርምር ተቋማት ጠለቅ ያለ ምርምር እንዲሰሩ ብቻ ሳይሆን እንዲታተም
ማበረታታት አለባቸው። በአንዳንድ ደቡብ አፍሪካ አገሮች እንደሚደረገው ተመራማሪዎ
ምርምሮቻቸውን ባሳተመ ቁጥር የማበረታቻ የደመወዝ ጭማሪዎችና የመጻህፍት መግ
በመስጠት እየተደበቁ የቀሩትን ብቻ ሳይሆን አዳዲስ ተመራማሪዎችን ማበረታታት ይቻላ
የኢንተርኔት አግልግሎትን ያለምንም ችግር የሚያገኙበትን ሁኔታም ማመቻች
ያስፈልጋል።

መ. ከመገናኛ ብዙሃን የሚቀርበው አንፎርሜሽን

የኢንፎርሜሽን ጉዳይ ሲነሳ መገናኛ ብዙሃን መነሳታቸው ስለማይቀር በዚህ በኩል ያደረግሁ
ምርምር (የተደረገም መኖሩን አላውቅም) በጣም አነስተኛ በመሆኑ ጥቂት ነገሮች ብቻ ብዬ
ማለፍ እወዳለሁ።

የቴሌቪዥንና የሬዲዮ የአየር ጊዜ፤ እንዲሁም የግል ጋዜጦች መስፋፋት በአንጻራዊ ሁኔታ
ቢታይም ለሀገራችን ህዝቡን ለማስተማር፣ የስራና የእድገት በር ለመክፈት፣ እንዲሁም
የባህል ለውጥ ለማምጣት ለሚደረገው ጥረት አጋዥ ለመሆናቸው ብዙ ይቀራቸዋል።

1ኛ/ በአገራችን የፕሬስ፣ የሬዲዮና የቴሌቪዥን መገናኛ ብዙሃን በዝቅተኛ ደረጃ ያሉበት
በየቀኑ የግል ጋዜጦችን ጨምሮ ከ50 ሺህ ጋዜጦች በታች የሚነበቡበት፤ አንድ ጋዜጣ
ለ1400 ሰው የሚዳረስበት ነው። የኮምዩኒቲ ሬዲዮኖች ያለመኖር፤ ያሉትም የመገናኛ
ብዙሃን ብዙውን በከተሞች፤ በተለይም በአዲስ አበባ ላይ ማተኮር፣ የገጠሩን ህዝብና
ህይወት ያማከለ የኢንፎርሜሽን ፍልሰት ያለመፍጠራቸው ሌላው ችግር ነው።

2ኛ/ የአገራችን መገናኛ ብዙሀን በአብዛኛው በመንግሥት ድጋፍና ችሮታ የሚንቀሳቀሱ
ሆነው በመቆየታቸው፤ አብዛኛውን ጊዜ የመንግሥታቱን መመሪያ ከማስፈፀም ያለፈ
ማህበረሰቡን ያሳተፉ የፕሮግራም ቅንጅት (community programming) ያልታዩባቸው፤
ህገበ የሚባለውን የሚሰማ እንጂ የሚዲያ እውቀት (media literacy) ኖሮት ፍሬውን
ከገለባ የሚለይበት፤ የሚዲያ ተጠቃሚ (critical reader) ባለመሆኑ፤

3ኛ/ ለመገናኛ ብዙሃን እድገት፣ ለጋዜጠኝነት ሙያ መዳበር፣ ደመወዝ፣ ጥቅማጥቅሞች
እና ድጎማ ማበረታቻዎች በመንግሥትም ሆነ በግል የተወሰደው እርምጃ የሚያበረታታ
ባለመሆኑ፤

4ኛ/ መንግሥትና የዕርዳታ ሰጪዎች ክሊኒኮችን እና ትምህርት ቤቶችን የመሥራታቸውን
ያህል ለመገናኛ ብዙሃን እድገት ያደረጉት አስተዋጽዖ ዝቅተኛ በመሆኑ መገናኛ ብዙሀን

ገቢያቸውን የሚያገኙበትን የማስታወቂያ ሥራ እንዲያሳድዱ የመገፋፋቱ አገማሚያ በማመዛዘን፤

5ኛ/ የሚዲያ ትምህርት ቤቶችና ስልጠናዎች (media training) በጥራት፣ በመጠንና በዓይነት ተደራጅተው ባለመገኘታቸው፤ ያለትም ከቴክኒካዊ ስልጠናዎችና መሰረታዊ የጋዜጠኝነት ሙያ አልፈው ጠለቅ ያለ የህገመንን ችግር የሚፈታ የጋዜጠኝነት ሙያ ስለማያላብሱ በተለይ በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ በጋዜጠኝነት ሙያ ትምህርት ለመስጠት ገና በጅምር ላይ መሆናችን፤

6ኛ/ የሚንሸራሸረው ኢንፎርሜሽን በአብዛኛው ያደጉ አገሮችን ችግር የሚፈታ እንጂ የአገር ውስጥ ችግሮች ላይ ያተኮረ ባለመሆኑ፤

7ኛ/ ከልምድና እወቀት ማነስ ጋር ተዳምሮ የጋዜጠኝነት ስነምግባር (Code of Ethics) በአብዛኛው ባለመኖሩ፤ ካለፋት አስር አመታት ወዲህ ያለምንም ሙያና ሰርተፊኬት፣ ከምንም ተነስቶ የሚሰራበት የጋዜጠኝነት ሥራ በመስፋፋቱ በአብዛኛው ወሬ ተጽፎ፣ ወሬ ተነቦ፣ የወሬ መሰራጨት እየተባባሰ ከመምጣቱም በላይ፣ የማህበረሰባችንን የእወቀት መዋቅር (knowledge ecosystem) እየተፈታተነው መምጣቱ መሰራታዊ ችግሮቻችን ናቸው። ከኢንፎርሜሽን ሙያ አንባር ስናየው ህብረተሰቡ ያልተረጋገጠ፣ ያልተሟላ ሳይንሳዊ መሰረትና ከህይወቱ ጋር ያልተያያዘ ወሬ በማንበብ፣ በማኘክና በማሰራጨት ብዙም ሊንገዘ አይችልም የሚለው ግምት ያመዝናል።

የመገናኛ ብዙሃን የማህበረሰቡን ህልውና በማያዳብርና ዲሞክራሲያዊ ስርአት በመገንባት ብቻ የተወሰነ ሳይሆን፤ ሰዎች በቀን ተቀን የህይወት ተሳትፎአቸው የበለጠ እንዲተጉ፣ ሪስክ እንዲወስዱ (Risc taking)፣ ወደ ሁሞላ ያስቀሩን የስንፍና፣ ቅን ያለመሆን፣ በእወቀትና በምርምር ላይ ያልተመሰረተ ልማት፣ አገልል መኮፈስ፣ ተጠያቂነት፣ አብሮ ለመሥራት ያለመቻል፣... የመሳሰሉት መሰረታዊ ችግሮቻችንን የሚፈቱ፤ ህዝቡ ስሚ ብቻ ሳይሆን ተሳታፊና የሚተላለፈውን መልእክት ዳሬውን ከነለባ የሚለይ (critical thinking) ዜጋ ለመፍጠር ማገዝ አለባቸው። ለዚህም መንግሥት መንገዶችንና ትምህርት ቤቶችን የመገንባቱን ርብርብ፣ የሰሞችን የአስተሳሰብ ክህሎት መገንባቱ ላይም መረባረብ አለበት። አንድ ትምህርት ቤት ወይንም ዩኒቨርሲቲ ከመሥራት ሀገር አቀፍ መገናኛ ብዙሃንን የእወቀት ስርጭት ሲስተም (knowledge diffusion system) ማቃናቱ የበለጠ ዋጋ ይኖረዋል።

ሠ. በኢንተርኔት ያለው መረጃ

በኢንተርኔት ያለው መረጃ ባብዛኛው ባደጉ አገሮች ችግር ላይ መፍትሄና በቋንቋቸው ላይ ያተኮረ ሲሆን ካለፉት 10 ዓመታት ወዲህ በworld wide web እድገት ላይ ተመስርቶ የተደራጀው ኢንፎርሜሽን ታይቶና ተሰምቶ በማይታወቅ ፍጥነት እማደገም በላይ ስለተፈለገው ጉዳይ መረጃ ለማግኘት በተበታተነ መልኩም ቢሆን ኢንተርኔት የመጀመሪያውን ደረጃ ከያዘ ቆይቷል። ኢንተርኔት የዓለም መረጃ መስተዋት ነው። ሆኖም አገራችን በኢንተርኔት አማካኝነት ያዳበረችው ኢንፎርሜሽን መዋቅር፤ ጥቂት ግለሰቦችና ድርጅቶች ስለድርጅቶቻቸውና ራሳቸው ካደራጁት ድህረ ገፆች፤ በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት፣ ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማዕከልና የግል ጋዜጦች ያለት ከማያቀርቡት ዜና በቀር፣ በሀገራችን ችግሮች ላይ የተሳሉ ዕሁፎችና የስታትስቲክስ መረጃዎችን ከኢንተርኔት ማግኘት አስቸጋሪ ነው። ለምሳሌ፤ ዩኒቨርስቲዎቻችን ምን እንደማሰራና የት እንዳሉ እንኳን ለማወቅ በማያስችል፣ ድምጸቸው ከኢንተርኔት ላይ መጥፋቱ በጣም የማያሳዝር ነው። ይህ

የሚያሳየው ስለ ኢንተርኔት ኢንፎርሜሽን በአጠቃላይ ስለ ኢንፎርሜሽን ያለው ግንዛቤ (information literacy) በጣም ዝቅተኛ ከሆነባቸው የአፍሪካ አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ መሆኗን ነው። በኢንተርኔት ላይ የተመሰረተ ኢንፎርሜሽን ለማደራጀት፤

1. በድህረ ገፅና በዳታ ቤዝ የሰለጠነ ሰው ጎይል ማፍራት እና ለዘመናችን የሚሆን የኢንፎርሜሽን ግንዛቤ (information literacy) ማዳበር፤
2. በኢንተርኔት ያለውን ጥሩና መጥፎ ኢንፎርሜሽን መለየት ከተለያዩ መገናኛ ዘዴዎች መረጃን የማጠናቀርና ያገኘውን ኢንፎርሜሽን የማዳበር ችሎታ መፍጠር፤
3. በኢንተርኔት መረጃ አገልግሎት የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ተጠቅመን ኢንፎርሜሽን ለህዝቡ ለማሰራጨት የሚረዱ ቀጣይ ምርምሮችን ማድረግና ውጤቶቹን መጠቀም ያስፈልጋል።

ከዚህ ጋር ተያይዞ ሳይጠቀስ የማይታለፈው የህትመት ኢንዱስትሪያችን (publishing and content industry) መጎልበት አስፈላጊነት ነው። የስነጥበብ ፈጠራ ሥራዎች፣ ፊልም፣ መዝሙርና ሌሎችም በኢንተርኔትና አዲሱን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ለዓለም ህዝብ እንዲደርሱ ማመቻቸት አለብን።

ረ. አገር በቀል (የተለምዶ ባህል) እውቀት

ከባህል መድኃኒት ጀምሮ፤ ሽመና፣ ቅጥቀጣ፣ የሸክላ ሥራ፣ ባህላዊ ሥዕል፣ ፍግና አመድን ተጠቅሞ ምርትን ማሳደግ፤ የመሳሰሉት... የተለያዩ ችግሮችን ለመፍቻ ህዝቡ የገነባቸው ዕውቀቶች ሲሆኑ ሳይዳብሩና እዛው ሲረገጡ ቆይተዋል። በአንድ በኩል አዲሱ ዘመናዊ ዕውቀት የድህወን የተለምዶና የተካባተ ዕወቀት ወደጎን በመተውና በማጨለም፣ የአደጉ አገሮች ዕወቀት ለአገራችን መፍትሄ እንዲሆን ሲያበረታታ፤ በሌላ በኩል እርዳታ ሰጪዎችና የተማሩ ሰሦች በራሳችን እንዳንተማመንና ባለን ላይ ከመገንባት ይልቅ ጥገኝነትና የውጪ አድማቂነትን ስለሚያበረታቱ አገር በቀል ዕውቀትና ግኝታችን (indigenous knowledge and innovation) ብዙም ሳይሻሻልና ሳይዳብር፤ እንደማረሻችን ሁሉ ከብዙ ሺህ ዘመናት በላይ ሳይቀየር ቀርቷል። በአገር በቀል ዕውቀትና ስርፀት የኋላቀርነታችን መንስኤ አዳዲስነገሮችን ተቀብለን ከህይወታችንና ልምዳችን ጋር በማዛመድ አክሳሪ ሊሆኑ ወይም ጉዳት ሊያስከትሉ የማችሉትን ሁኔታዎች ገምግመን የመወሰን ችሎታችን (entrepreneurship) ዝቅተኛ መሆን ነው።

ካለንበት ሁኔታ ለመውጣት በአገር በቀል እውቀታችንና በስርጭቱ ላይ ሰፊ የማህበራዊ ጥናትና ምርምር ማካሄድና ጠቃሚ ዕውቀት እንዲንሸራሸር፣ ዕውቀት አመንጪዎች (ለምሳሌ የባህል መድኃኒት አዋቂዎች) እንዲበራቱ ማድረግ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂ ተጠቅሞ ዕውቀት ሳይባክንና ሳይጠፋ አጠራቅሞ፣ አደራጅቶ፣ ለተጠቀሚው ትውልድ ማስተላለፍ ያስፈልጋል። በዘመናዊ ትምህርትና በባህል ዕውቀት መካከል ያለውንም ድልድይ ማጠንከር፣ ምናልባትም የአገራችንን ኢኮኖሚ ለማዳበር የሚረዱ የተደበቁ ጠቃሚ ዕውቀቶችን እንድናገኝ ይረዳን ይሆናል። ባህላችን እውቀታችንና ካለን ሰፊ የጀኔቲክስ ሃብትና ባዮዳይቨርሲቲ አንፃር የገጠሩ ሀብታችን ከአዲስ ዕውቀት ጋር ቢዋሃዱ አገራችንን ሊያሳድጉ የሚችሉ የቱሪዝም ያልተበከሉ ምርቶችን (organic products) በማስፋፋት እንደ እስኮትላንድ ያሉ አገሮች «ፈሳሽ ወርቅ» የተባለውን «ውስኪ» ለኢኮኖሚያቸው መሰረት እንዲሆን እንዳደረጉት ሁሉ አዳዲስ ምርቶችን ማምረትና ለዓለም ገበያ ማቅረብ እንችላለን።

ከዚህም በላይ የጠቀስኩዋቸው የኢንፎርሜሽን ምንጮቻችን ማለትም አብያተ መፃህፍት ቤቶች፣ በመንግሥትና በድርጅቶች የሚጠናቀረው መረጃ፣ መገናኛ ብዙሃንና አገር በቀል ዕውቀቶችን ተደጋጋፊ ሆነው ሲያድጉ ብቻ ነው በአገራችን እድገቶችንን የሚያፋጥነን የዕውቀት መዋቅር (knowledge ecosystem) መገንባት የምንችለው። ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ በእነዚህ የኢንፎርሜሽን ምንጮች መሀከል ያለውን ግንኙነት የሚያጠናክር መሳሪያ መሆኑ እግረ መንገዳችንን ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂንም እንድናዳብር ያደርጋል። ለመሆኑ የአገራችን ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ እድገት ምን ደረጃ ላይ ነው?

3. የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሁኔታ በኢትዮጵያ

በሀገራችን ባለፉት ጥቂት አመታት ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የለውጥ ጭላንጭል ቢያሳይም ከጎረቤት አገሮቻችን አንፃር እንኳን ሲመዘን ኋላቀር ነው። የቴሌፎን እድገት ከ 0.33 ወደ 0.7 በመቶ አድጓል። የሞባይልም ቁጥር ዕድገት በመጠኑ ወደ 0.2 በመቶ ደርሷል። በአፍሪካ በአማካኝ የቴሌፎን እድገት 2.74 በመቶ ሲሆነ ሞባይልም ከ6 በመቶ በላይ ነው። ይሁንና በአገራችን ካለው አናሳ መስመር 60 በመቶ የሚሆነው የቴሌፎን አገልግሎትና ከ80 በመቶ በላይ የሚገመተው ሞባይል አገልግሎት በአዲስ አበባ ላይ ያተኮረ ነው። የቴሌኮሙዩኒኬሽን ድጋፍ ከአገሪቱ አጠቃላይ አመታዊ ገቢ 1.7 በመቶ ብቻ ነው።

በአገራችን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በኩል ያለው ፖሊሲና ርዕይ አጥጋቢ ባለመሆኑ ያገኘ ነውም ውጤት ዝቅተኛ ነው። እንደህንድ፣ ብራዚል፣ ስዊኒያ፣ ኮስታሪካ፣ ያሉ አገሮች የውጭ ኢንቨስትመንት በመሳብ ያገር ውስጥ አቅምን በመገንባት ላይ ያተኮረ ፖሊሲ በመከተላቸው ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ለኢኮኖሚያቸው እገዛ አድርጓል።

ሁሉን አቀፍ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፖሊሲ ባለመኖሩና በኮምፒዩተር ላይ የተጣለው ታክስ ከሌሎች አገሮች አንፃር ከፍተኛ በመሆኑ የኮምፒዩተሮች ብዛት ከህገዘቡ ብዛት አንፃር በጣም ዝቅተኛ ነው። ኮምፒዩተሮች በድርጅቶችና በመሥሪያ ቤቶች እንጂ በነፍስ ወከፍ መግዛት አሁንም እንደብርቅ የሚታይበት አገር ኢትዮጵያ ነች። እንደ ITU 1995 ዘገባ በኢትዮጵያ ያሉት ኮምፒዩተሮች ብዛት 150,000 ሲሆኑ በነፍስ ወከፍ 1 ኮምፒዩተር ለ 500 ሰው ቢዳረስ ነው። በአፍሪካ በአማካይ 1 ኮምፒዩተር ለ 70 ሰው የሚደርስ ነው።

በሌላ በኩል የኢትዮጵያ ቴሌኮሙዩኒኬሽን ኮርፖሬሽን «ለውጥ እያመጣሁ ነኝ» ይበል እንጂ በተለይ በኢንተርኔት በኩል ያለው ችግር በጣም ከፍተኛ ነው። በኢትዮጵያ የኢንተርኔት ተገልጋዩች ቁጥር በዓለም ዝቅተኛው ሲሆን ጥራቱም የዚያኑ ያህል አሳሳቢ ነው። በሀገራችን ከ12ሺ በላይ የኢንተርኔት ተገልጋዮች ወይም ወደ 70ሺ የሚሆኑ ተጠቃሚዎች አሉ። ይህ ደግሞ ከ 1000 ሰው አንዱ ብቻ ኢንተርኔት ይጠቀማል ማለት ነው። በአፍሪካ አገሮች በአማካይ ከ60 አንዱ ሰው የኢንተርኔት አገልግሎት ያገኛል። በኢትዮጵያ ከ350,000 በላይ ከሚሆኑ የመንግሥት ሰራተኞች 2200 ብቻ ናቸው የኢንተርኔት ተጠቃሚ የሆኑት።

ጥናቶች እንደማ,ያሳዩት አሳሳቢው ነገር ባለፉት ሁለት አመታት የኢንተርኔት ደንበኞች ቁጥር ይህን ያህል ለውጥ አለማሳየቱ ነው። ለዚህም መንስኤ ከሆኑት ነገሮች መሃከል፤

1. የአገልግሎት ደረጃ ዝቅተኝነትና የዋጋው ከሰው የመግዛት አቅም አንፃር ከፍተኛ መሆን፤
2. የኢትዮጵያ ቴሌኮመ·ዩኒኬሽን ኮርፖሬሽን የኢንተርኔት አገልግሎት በጅምላ አቅርቦ የግል ድርጅቶች እንዲቸረችሩትና መልካም አገልግሎት በመስጠት እንዲወዳደሩ ከማድረግ ይልቅ ራሱ አቅራቢ፣ ጅምላ አከፋፋይና ቸርቻሪ መሆኑ፤
3. በጅምላ የኮመ·ዩኒኬሽን መረብ (bandwidth) ገዝቶ ለድርጅቶችና ለትምህርት ቤቶች እንዲዳረስ አለመድረጉ፤
4. በቴሌ ሞኖፖሊ ላይ ያተኮረ የገበያ ስርአት (markert structure) መኖሩ፣ የመሳሰሉት ዋና ዋና ምክንያቶች ናቸው።

በመሆኑም ብዙ ኤክስፐርቶች የቴሌኮመ·ዩኒኬሽን በመንግሥት ቁጥጥር ስር መሆኑ ለዝቅተኛው የኢንተርኔት እድገት ዋናው ምክንያት ነው ብለው ሲከራከሩ፤ አብዛኛዎቹ ግን የቴሌኮመ·ዩኒኬሽን ችግር የባለቤትነት ሳይሆን በተቀላጠፈና በተፋጠነ መልኩ ህዝቡንና ሥራ ፈላጊ ኢትዮጵያውያንን እንዲሁም የግል ድርጅቶችን ባላሳተፈ መልኩ፣ ድህነታችንን ለመቅረፍ በማያስችል መንገድ፣ መደራጀቱ ነው ይላሉ። በመሆኑም ፖሊሲ አውጪዎች አዳዲስ ሀሳቦችን በመቀበል የተለያዩ መሻሻሎችን ካላደረገ· ቴሌኮመ·ዩኒኬሽን ኮርፖሬሽን አደርጋለሁ በሚለው ብቻ አገራችን በፍጥነት አትራመድም። መንግሥት የተለያዩ በጥናት የተደገፉ የኢንፎርሜሽን ኮመ·ዩኒኬሽን እቅዶችን ተግባራዊ ካላደረገ፣ ተጠቃሚዎችንና ርዕይ ያላቸውን ሌሎች ሰዎች ካላዳመጠ፣ የሌሎችን አገሮች ተሞክሮዎች ካልተከታተለና የግል ድርጅቶችን በስፋት ካላሳተፈ፤ በራሱ ጥረት ብቻ ህገበኩን በፈጣኑ ቴክኖሎጂ ወደፊት ሊያራምድ አይችልም። በመከራ ብቻ ውስብስብ የሆነውን ቴክኖሎጂ ለጥቅም ማዋል አስቸጋሪ ነው።

በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ትምህርትና ስልጠና፣ እንዲሁም በሶፍትዌር በኩል ያለው ሁኔታም ሲታይ ይህን ያህል የሚያመረቃ አልሆነም። በኢትዮጵያ ወደ 120 የሚጠጉ የኮምፒዩተር አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች ወደ 5,000 የሚጠጉ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለመ·ያዎች አሉዋቸው። ይህ ቁጥር በአጭር ጊዜ ወደ 20,000 ያድጋል ተብሎ ይገመታል። ወደ 20 የሚጠጉ ድርጅቶች ከዓለም አቀፍ ኩባንያዎች ግንኙነት ሲኖራቸው የተቀሩት ግን በማሰልጠን ላይ የተሰማሩ አገራዊ ተዋናይ ብቻ ናችው። ብዙዎቹ ኩባንያዎች የአስተዳደርና የገንዘብ አቅም የሌላቸው ሲሆኑ አብዛኛዎቹ ያለንን ዕምቅ የወጣት ኃይል በሥራ ለማሰማራት የማይችሉበት ደረጃ ላይ ይገኛሉ።

ከነዚህም አብዛኛዎቹ ምንም የጥራት፣ የዕውቀት (content) ለውጥ ሳያደርገ· ከማሰልጠኛ ወደ ኮሌጅ የተሸጋገሩ የወጣቶች መዋያ ቦታዎች (መዋለ ወጣቶች) ናቸው ማለት ይቻላል። የሀገራችን የኮምፒዩተር ትምህርት ጥራት ዝቅተኛ መሆን በዓለም ከሚታየው ጠለቅ ያለ ዕውቀት ያላቸው ሰዎች ፍላጎት አንፃር ሲታይ አሳሳቢ ብቻ ሳይሆን አሳዛኝም ነው። ጥቂት በጣት የማ,ቆጠሩ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ከሚያደርገ·ት መፍጨርጨር በስተቀር የሀገራችንን ችግር መፍታት አልፈው በአለም ገበያ ለመወዳደር የሚችሉ እና፤ ወጣቶችን ለማፍራት የሚደርገ·ት ጥረት እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው። መሰረታዊ የኮምፒዩተርና የኮምፒዩተር መረብ (computer networking) እውቀት ያለመኖሩን ለመገንዘብ ብዙ መሄድ

አያስፈልግም። በሀገራችን የኮምፒዩተርና የኮምፒዩተር መረብ ችግሮችን ለመፍታት የሚችሉ ድርጅቶች ባለመኖራቸውና ባለትም የመተማመናችን አትም ገቸተኛ በመሆኑ በአለፈው ወር የኤሌክትሪክ ሂሳባችንን በነጭ ወረቀት ተሰልፈን ለመክፍል ተገደናል።

በመንግሥት ድርጅት አወቃቀር አንባር ሲታይ የተበታተነ ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓትና ደምብ ያመለነ ነው። የኢንፎሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ አዲስ በተቋቋመው በኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሥልጣን፣ በኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙሃንና ቴሌኮሙዩኒኬሽን ኤጀንሲና እነሱን በሚያስተዳድሩ የሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች በተበታተነ መልኩ ተደራጅቷል። የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፕሮጀክት ለማስፈፀም የተቋቋመው ባለሥልጣን ገና በመደራጀት ላይ ቢሆንም እስካሁን ይህ ነው የሚባል የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ቅንጅት አላሳየም። የትኞቹ የኢንፎርሜሽን ቴክሎጂ ግንባታዎች ቅድሚያ እንደሚሰጣቸው በደንብ አጥንቶ በተግባር ማዋል አለበት።

አብዛኛው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥራ የግል ድርጅቶችን ያላተፈ እንዲያውም ለቴሌ የተተወ ይመስላል። እንደዚህ ለመሳሰለት ጉዳዮችና ኢትዮጵያ ውስጥ ስላለው ኢንፎርሜሽንና ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሁኔታ ብዙ ማለት ይቻላል። ጊዜ ለመቆጠብ ያህል አንዳንድ መሰረታዊ ጉዳዮችን ማንሳቱ ብቻ ይበቃል።

4. ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂና የልማት መሰረታዊ ጉዳዮች

ለመሆኑ ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ እንደኛ ላለ አገሮች ምን ጥቅም ይሰጣል? ለምን ጊዜያችንና ጉልበታችንን እናባክናለን? ኮምፒዩተሮች ከመግባት ለምን ተጨማሪ መምህራን ወደ ማሰልጠኑ አናተኩርም? ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በወባ፣ በሳንባ፣ በኤች አይ ቪ አድስ ለሚሰቃየው ወይንም የእህል ጉርሻ ለመቅመስ ለሚማሰነው ወገን ምኑ ነው? የሚለት ጥያቄዎች በአብዛኛው በእንደዚህ ዓይነቱ ስብሰባ ይነሳሉ።

በመጀመሪያ የባሬው ጽሁፍ በቴክኖሎጂ ላይ ያተኮረ ሳይሆን በኢንፎርሜሽን እና በእውቀት መዋቅራችን ላይ የተመሠረተ መሆኑን ሳታጠኑት አይቀርም። በቴክኖሎጂ የሚጅምር ማንኛ ውም ሥራ ፕላን ወይንም ፕሮግራም መጨረሻው ውድቀት ነው። ከችግራችን በፊት ቴክኖሎጂን ካስቀደምን ወይንም አንዳንድ አማካሪዎች እንደሚነግሩን፤ የትምህርት፣ የጤና፣ የድህነት ችግሮቻችንን በአዳዲስ ቴክኖሎጂ ድባቅ ለመምታት ካሰብን፤ እንደነ «ተፈጥሮን በቁጥጥራችን ሥር እናደርጋለን» የሚለውን የደርግ አይነቱ የየዋሆች የዋህ፣ የሞኞች ሞኝ፣ ውድቀት መጋበዝ ነው። ሆኖም ቴክኖሎጂን የማስቀድመው የዋህነት አሁንም አልፎ አልፎ መታየቱ አልቀረም።

ለምሳሌ፤ አሁን በየሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚታየው (Flat Panel Display) የማሰጠው አይነቱ የናሳዝማ ትምህርት የመምህራኖችን ሚናና የቴክኖሎጂን ጥቅምና ጉዳት (opportunites and limitations) ያላገናዘበ፤ በሌሎች ዓለማት ያለውን ተሞክሮ ያላየ ይመስላል። ምንም እንኳን ከበሰተኋላው ያለው አስተሳሰብ ማለትም ጥሩ አስተማሪ የማግኘት፣ አንድ አይነት ደረጃ ያለው ትምህርት በአገር አቀፍ ደረጃ መማር፣ ወዘተ... የሚደገፍ ቢሆንም ከአሁን ቀደም ያለ ተሞክሮዎች የማያሳዩት፤ ቴክኖሎጂ ላይ የተመሰረተ ተማሪዎችንና አስተማሪዎችን ፊት ለፊት የማያወያይ ትምህርት ወጤቱ አጥጋቢ ያለመሆኑን ነው።

ጥናቶች የሚያመለክቱት መምህራን፣ የጤና ሰራተኞች፣ የቤተ መፃህፍት ባለሙያዎች፣ ወዘተ... ለእውቀት መተላለፍ እንደ በር ክፋች (gate keepers) ካላገለገሉ፤ እንዲያውም ቀደም ብዬ እንዳመለከትኩት እውቀት በትረካና በሚያሳትፍ መልኩ ካልተላለፈ የመማር ውጤቱ (learning outcome) ዝቅተኛ ይሆናል። ቴክኖሎጂው በሚበላሽበት ጊዜ ወይም መብራት ሲጠፋ ተመልሶ ወደ ቀድሞው ሁኔታ ለመመለስ ስለሚያስቸግር የትምህርት ቀንዱና ጭራው ይጠፋል።

ምንም እንኳ ከፍተኛ ትምህርት ቤቶቻችንን በኢንተርኔት ማገናኘት፣ ወጣቶች ኮምፒዩተሮችን እንዲማሩ ማድረግ፣ ወሳኝ ቢሆኑም ቴክኖሎጂን በማስቀደም የሚደረገው ለውጥ በአብዛኛው ጊዜ ከጥቅሙ ጉዳቱ ማመዘኑ አይቀሬ ነው። በሀገራችን ባለው ቴክኖሎጂ አጠቃቀም ዙሪያ የተደረገ ማህበረሰባዊ ጥናት (Social Research on Technology Application) ያለመኖሩን ያህል በድፍኑ የኮምፒዩተሮች በትምህርት ቤቶችና በወረዳዎች መትከል በትምህርቱና በአመራሩ ላይ ለውጥ ያመጣለ ብሎ ማመን የዋህነት ነው።

ባለፉት አመታት የትምህርት ሽፋኑ ቢጨምርም፤ ያለን የመማር አቅም ወይንም በጥራት እውቀት ለወጣቶች ለማስተላለፍ የተደረገው ጥረት ዝቅተኛ መሆን፣ በአጠቃላይ የሚታዘዝ ወይንም «አይቻልም» «ክልክል ነው» «መመሪያ ነው» ብሎ የሚገድብ እንጂ መፍትሄ የሚሻ (innovative) አቅም ያለመገንባታችን፣ ለምርምርና ለሳይንስ የሰጠነው ትኩረት የዛለ መሆኑ እና የሳይንስ መዋቅሮቻችንንም ባለመስፋፋታቸው፤ ሌሎች አገሮች የተሰሩትን ቴክኖሎጂዎች ከማህበረሰባችን ፍላጎት አንፃር መጠቀም አልቻልንም። በነዚህ ችግሮች ላይ በጥናት ያልተደገፈ ቴክኖሎጂ ብንጨምር «በቁስል ላይ እሾክ» እንደመጨመር ይሆናል።

አዳዲሶቹ ቴክኖሎጂዎች የመማር አቅማችን (learning outcome) እንዲጨምሩ ሆነው መደራጀት አለባቸው። ይህ ግን ትምህርት ቤቶችን የኮምፒዩተር ባለቤት ከማድረግ የበለጠ ትእግስትን ይጠይቃል። እንደ ቺሊና ኮስታሪካ ያሉት የላቲን አሜሪካ አገሮች ቴክኖሎጂን በትምህርት ቤቶች ለማስፋፋት የፈጀባቸው ጊዜ ከ15 ዓመት በላይ ሲሆን ያገኙት ወጤትም ገና በማንሰራራት ላይ መገኘቱ፤ እንደኛዎቹ አገር ላሉት የፖሊሲ አውጪዎችና አማካሪዎቻቸው ጥሩ ትምህርት ይሆናል የሚል ግምት አለ።

ይህ ማለት ቴክኖሎጂ ለትምህርታችን አያስፈልግም ማለት አይደለም። በዩኒቨርሲቲዎቻችን ያሉ ተማሪዎችና የነገሎች ቴክኖሎጂ ሀሞሪያት በቂ የቴክኖሎጂ አቅርቦት ቢኖራቸውና በማንኛውም መልኩ የተመረቀ ተማሪ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መንጃ ፍቃድና በመልካም ኮምፒዩተሮችን የመጠቀምን ብቃት (ለምሳሌ፤ አካውንታንት ከሆነ ከአጠቃላይ የኮምፒዩተራይዝድ አካውንቲንግ እውቀት፣ የጂአግራፊ ባለመልካ ከሆነ GIS፣ የጤና ባለመልካ ከሆነ አጠቃላይ ቴሌሃልገ) እውቀት እንዲኖራቸው ብናደርግ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን ለእድገታችን እንዲጠቅመን መንገድ አበጃጅን ማለት ነው። እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ኋላቀር አገሮች ማፍራት ያለባቸው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በየልማት ዘርፉ ማለትም (በእርሻው፣ በጤናው፣ በትምህርቱ፣ ወዘተ...) የሚጠቀም (IT literate) ዜጋን ነው።

አሁን በአሜሪካ ሀገሮች እንደሚታየው ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ድህነትን ያጠፋል፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ያወጣውን የምእተ አመቱን ግቦች ለመምታት ሚና አለው፣ ብሎ ከማስተጋባት ይልቅ በየእድገት ዘርፉ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሰግስጎ የሚገባበትን መንገድ

(mainstreaming) መቀየሱ የበለጠ ያዋጣናል። በአንድ በኩል ወጣቶቻችን በጣም ጠለቅ ያለ እውቀት እንዲያገኙና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ላይ ዝንባሌ ያላቸው ውስብስብ ወደሆነና ተግባር-ነክ (ትግር-ፈት) የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ትምህርት እንዲያገኙ፣ በሌላ በኩል ከላይ እንደጠቀስኩት በማንኛውም ዘርፍ የሚሰለጥን ባለሙያ በሙያው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፍቃድ (sectoral IT licence) የሚያገኝበትን ሁኔታ ብናመቻች፤ ሁለት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ጥቅሞች ማግኘት እንችላለን።

1ኛ/ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዝንባሌ ኖሮት በሙያው በደንብ የሰለጠነ የሰው ኀይል በዓለም አቀፍ-ደረጃ ተቀባይነት ማግኘት ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚያችንና ለውጭ ምንዛሪያችን አጋዥ ይሆናል።

2ኛ/ ከየዘርፉ ተውጣጥተው ስለ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በዚያ ሴክተር ስላለው ጥቅም በቂ እውቀት የሚያገኙት አዳዲስ መንገዶችን በመቀየስና የቀረበላቸውን ቴክኖሎጂ በመጠቀም ሥራን በማቀላጠፍ በየሴክተሩ ለኢኮኖሚችን እድገት ጥሩ አጋዥ ይሆናሉ።

እነዚህን ማድረግ የሚቻለው፤

1ኛ/ መንግሥት ፖሊሲዎችን ለማውጣት ጊዜ መፍጀት ሳይሆን አንዳንድ መሻሻሎች ማድረግ ሲችል፤ (ለምሳሌ፤ በዩኒቨርሲቲ ያለው የኢንተርኔት አቅርቦት ያለገደብ የሚስፋፋበትን ሁኔታዎች ማመቻቸትና ዩኒቨርሲቲዎች ተማሪዎቻቸው በቂ የሆነ እውቀት እንዲያገኙ መንገድ ሲጠርግ ነው፤

2ኛ/ መንግሥትና የግል ድርጅቶች ጠለቅ ያለ እውቀት ያላቸውን ኢትዮጵያውያንን በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂና ሶፍትዌር አገልግሎት ስራዎች እንዲሳተፉ ማበረታቻዎች (ለምሳሌ፤ የባንክ ብድር፣ የሚሰሩበትን የተመቻቸ መሰረተ ልማት፣ ስልክ፣ ፈጣን የኢንተርኔት አገልግሎት፣ ቢሮዎች፣ ወዘተ...) በመስጠት በምርምር ተቋሞችና በቴክኖሎጂ ፓርኮች እንዲሳተፉ ቢያደርጉ፤

3ኛ አሁን በብዙዎቹ የግል ድርጅቶች የተያያዘው ላይ ላዩን የሚያሞኝ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ትምህርት ቢቀርና በተግባር የተደገፈ፣ የጊዜውንና የዓለም አቀፉን ገበያ ማዕከል ያደረገ ትምህርት መስጠት መጀመር ጊዜ የሚሰጠው አይደለም። እየተሰጠ ያለው ትምህርትም ይሁን ወጣቶች ሁኔታዎችን አመዛዝነው ስለ ሥራ አወሳሰን የሚያሳዩት ብስለት (enterprenuership)፣ በቡድንና በህብረት የመስራት ልምድ (team work)፣ ተአማኒነትን (integrity)፣ ሀላፊነትን የመወጣት (accountability)፣ ልምዶች እንዲያዳብሩ አስፈላጊ ነው። እንዲሁም የፈጠራ ሥራ ብቻ ሳይሆን የፕሮጀክት የማስፈጸም አቅም እንዲገነቡ ማድረግ፤

4ኛ/ እንደ ቤተ መፃህፍት፣ የመንግሥት መረጃ ድርጅቶች፣ የመገናኛ ብዙሃን፣ የሳይንስ ህትመቶች፣ ወዘተ... ያሉት የአውቀት መዋቅሮቻችን የሚጠናከሩበትና በአዳዲስ ቴክኖሎጂ የሚታገዙበት ሁኔታ ቢመቻች፤

5ኛ/ በሀገራችን አዳዲስ ቴክኖሎጂ እና የማህበረሰቡን ቴክኖሎጂ አጠቃቀም በሚመለከት መሰረታዊ ማህበረሰባዊ ጥናቶች ቢደረጉና ውጤታቸውም ለህዝቡና ለፖሊሲ ቀረፃ የሚያገለግሉበት ሁኔታ ቢመቻች። ይህም ቴክኖሎጂን ብቻ ሳይሆን የህዝቡ ቋንቋና ባህል ላይ ቴክኖሎጂው የሚያመጣውን ተጽዕኖ የሚያካትት ቢሆን፤

6ኛ/ ንግድ ነክ ያልሆነ (non-marketing) ስለ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ጥቅም ለህዝቡ በተለያዩ ባለሙያዎች በመገናኛ ብዙሃን ግንዛቤ የሚሰጥበት ሁኔታ ቢመቻች፤

7ኛ/ የኮሙዩኒኬሽን ልማት በመንግሥት፣ በህዝብና በትናንሽ የግል ድርጅቶች ቅንብር የሚያድግበት ሁኔታ ቢመቻች ጥሩ ውጤት ማምጣት ይቻላል።

5. የወደፊት ርዕይ

በፈጣኑ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘመን የሃያ አመት ቀርቶ የሃያ ወራት ርዕይ ማሰቀመጥ በጣም አስቸጋሪ ነው። የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዑደት (cycle) ከ5 ዓመታት መብለጥ ስለማይችል ርዕዩና ፖሊሲውም ከ5 ዓመት ካለፈ ዋጋ የለውም። ቀደም ብለው የነበሩት ተንባዮች ሁሉ ትክክለኛ ርዕይ ለማስቀመጥ አልቻሉም። በ1949 የIBM ፕሬዝዳንት የነበረው ቶማስ ዋትሰን ዓለም ከአምስት ኮምፒዩተሮች በላይ ገበያ አይኖራትም ብሎ ተንብዮ ነበር። እንዲያውም ከዚህ በፊት ያሉት ትንበያዎች፣ ርዕዮች፣ በአብዛኛው የህዝቡን የዕድገት ደረጃና የሀገሮችን አቅም ያላገናዘበ፡ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች የሚባሉ፡ ህልሞችና መፈክሮች ሆነው ቀርተዋል። ኢትዮጵያን ጨምሮ ብዙ ኋላ ቀር ሀገሮች እንዚህን ህልሞች በቴክኖሎጂ ፖሊሲዎቻቸው ቢያካትቱም በተግባር ለመተርጎም ግን አዳጋች ሆኖባቸዋል።

ስለዚህ የማያዋጣው አዲስ ቴክኖሎጂ በ20 ዓመት ይህን ያህል ያድጋል ብሎ መገመቱ ሳይሆን በ5 ዓመት ውስጥ በህገባችን የዕለት ተዕለት ሥራ ላይ ምን ለውጥ ያመጣል? ማለቱ ይሻላል። ትክክለኛው ርዕይ በተለያዩ የሥራ ዘርፎች የሚሰሩ ባለሙያዎች ኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን በቀን ተቀን ተግባሮቻቸው እንዴት ማዋሀድና መጠቀም እንዳለባቸው ተረድተው የሚያደርጉት እንቅስቃሴ ነው። ያም ቢሆን የሚከተሉትን የ5 ዓመት ርዕይ ማቅረብ ይቻላል።

- በመጀመሪያ በአገራችን ያሉት የዕውቀት መዋቅሮች ተጠናክረው ህዝቡ የሚያገኘውን መረጃ የሚያጣጥም ኢንፎርሜሽን Literate ይሆናል ብዬ አስባለሁ። ኢትዮጵያ ብዙ መቶ ሺ. የማቹጠሩ ወጣቶችና አዛውንቶች የሚሳተፉበት፣ ለአካባቢ ችግሮች መፍቻ ህዝቡ የሚሰባሰብባቸው የዕውቀት መቅሰሚያ የሆነ የህዝብ ቤተ መፃህፍትና የአዳዲስ ቴክኖሎጂ መጠቀሚያ ማዕከሎች ይኖሯታል ብዬ እገምታለሁ።
- ቴሌኮሙዩኒኬሽን አሁን ካለበት 0.7% ወደ 3% ያድጋል፤ የሞባይል ተጠቃሚዎች ባስፈለጋቸው ጊዜና ቦታ አገልግሎት ከሰቀ መግዛት ይችላሉ ብዬ እገምታለሁ።
- የኢንተርኔት አገልግሎት በየቀበሌው፡ በየጤና ጣቢያው፣ በየትምህርት ቤቱ ይስፋፋል። የአገራችን ገበሬዎችና ነጋዴዎች የሚያስፈልጋቸውን መረጃ ከኢንተርኔት ያገኛሉ ብዬም አስባለሁ።
- የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቶች ኢንፎርሜሽን በጥራት በማቅረባቸው ይመካሉ። ይወዳደራሉ። ኢትዮጵያ በተለያየ መልኩ ማለትም በእርሻ፣ በጤና፣ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂ፣ በጋዜጠኝነት አንቱ የተባሉ ጋዜጠኞችና ኤዲተሮች ይኖሯታል። ጋዜጠኞች የሚሰባሰቡባቸው የዕውቀት መቅሰሚያ የሆነ የህዝብ ቤተ መፃህፍትና የአዳዲስ ቴክኖሎጂ መጠቀሚያ ማዕከሎች ይኖሯታል ብዬ እገምታለሁ። በዚህም ዘና ከማቅረብ ይልቅ ወደ ትንተና (አናሊስስ)፣ በቻቸውን አንድን ፕሮግራም ከማቅረብ ይልቅ ባለሙያዎችንና ህዝቡን በሚያሳትፍ መልኩ ማቅረብን ይመርጣሉ ብዬም አስባለሁ።
- ኢትዮጵያ ለዓለም ኢንፎርሜሽን ሀብት በሳይንሳዊ ምርምሮችና በኢንተርኔት አማካይነት አስተዋጽዎ ታበረክታለች። የውጪ የምርምር ተቋሞች በኢትዮጵያውያን እንግዳ ተቀባይነትና የዕውቀት ሀብት መዋቅር በመደነቅ ከኢትዮጵያውያን ጋር ለመስራት ደፋ ቀና እንደሚሉ ይታየኛል።
- በኢንፎርሜሽንና በኮሙዩኒኬሽን ዕድገት ላይ የሚሰሩ ድርጅቶች፤ ማለትም የብሮድካስቲንግና የቴሌኮሙዩኒኬሽን ኤጀንሲ እንዲሁም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ባለስልጣን ተዋህደው የተለያዩ የመገናኛ ቴክኖሎጂዎች ድህነትን ለመፍታትና የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣት እንዲችሉ ሁኔታዎች ይመቻቻሉ ብዬ አስባለሁ።

- አገር በቀል እውቀታችን ከየስርቻው ወጥቶ ለአገራችን ዕድገትና ለህዝባችን ብልፅግና በሚሆን መልኩ ይደራጃል ብዬም እመኛለሁ::
- የህትመትና የሥነ ጥበብ ኢንዱስትሪዎች (content industry) ጎልብተው ለህዝባችንና ለዓለም ተጠቃሚዎች በመድረስ ኢኮኖሚያችንንና ባህላችንን ያሳድጋሉ ብዬ እገምታለሁ::
- ሁሉም ባለሙያ በቂ የኮምፒዩተር ዕውቀት ይኖረዋል:: ኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር ተቋሞች፤ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥራን የሚያግዙና አዳዲስ ንግድ የሚያስፋፉ የንግድ ማቆጥቆጫ ማዕከሎች (IT business incubation centers) እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ፓርክ ይኖሯታል:: በዚህ ፓርክ በውጪ የሚኖሩ አትዮጵያውያን፣ የውጪ ዜጎችና ወጣቶች የአገራቸውን፣ የአህጉራቸውንና የዓላማችንን ችግሮች በአዳዲስ ቴክኖሎጂ ምርምር፣ ስርዐትና አፕሊኬሽን ይፈታሉ:: ፓርኩ ዕውቀት ያለምንም ገደብና ፍርሃት የሚንሸራሸርበት ይሆናል::
- ሀገራችን ኢንፎርሜሽንን፣ ዕውቀትን፣ ኮሙዩኒኬሽንን፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን፣ በተመለከተ ማህበራዊ ጥናት የሚያካሂድ ማዕከል ይኖሯታል:: ከዚህ ማዕከል የሚወጡ ምርምሮች ለፖሊሲና ለልማት ዕገዛ ያደርጋሉ::
- በመሆኑም የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ለአገራችን ኢኮኖሚ እድገት የሚያደርገው አስተዋጽኦ አሁን ካለው የሀገር ሀብት ከ2% በታች ወደ 5% በላይ ያድጋል ብዬ አስባለሁ::

ስለዚህም ያገራችን የኢንፎርሜሽን ዓላማ ማተኮር ያለበት በ3 ዋና ጉዳዮች ላይ መሆን አለበት ብዬ አምናለሁ::

1. የኢንፎርሜሽን መዋቅሮቻችንን፤ ማለትም ቤተ-መጻህፍቶቻችንን በኮምፒውተርና በኢንተርኔት በማጠናከር መረጃዎችን ማቅረብ፤ አገር በቀል እውቀታችንን በምርምር ውጤቶች ሲደገፍ፣ የእውቀት ጥልቀትን (knowledge density) በማሻሻል፣ የእውቀት ተጠቃሚ ህበረተሰብ (knowledge consumer) መገንባት፤
2. የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ትምህርት በጥራትና በጥልቀት በመስጠት ዓለም ከደረሰበት ደረጃ አንጻር በማገናዘብ ችግር-ፈቺ የኮምፒውተር አፕልኬሽን የሚፈጥሩ ወጣቶችን በማፍራት፣ የእውቀት ኢንተርፕራነሮች (knowledge entrepreneurs) ቁጥር ማብዛት፤
3. የኢንፎርሜሽን ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ትምህርት በየዘርፉ (በእርሻ፣ በጤና፣ በሳይኮሎጂ፣ ወዘተ. . .) በመስጠት ሁሉም ባለሙያ የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ በመሆን የየሴክተሩ ችግር ፈቺና የኢንፎርሜሽን አመንጪ (information producers) የሆነ የእውቀት ሰራተኛ (knowledge workers) እንዲሆን ማገዝ ያስፈልጋል::

በግሎባላይዜሽን ዘመን እንደ ደሴት ሆኖ መቆየት ስለማይቻል አገራችን በእውቀት ኢኮኖሚ እንድትሳተፍ ከፈለግን፣ የእውቀት ሰራተኛ፣ የእውቀት ኢንተርፕራነር፣ የእውቀት ተጠቃሚ፣ መገንባቱ ምርጫ የሌለው እርምጃ ነው::

በዶ/ር ሲሻን አዳም ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

መላት ደመቀ*

አስተያየት እንድሰጥ ስጠየቅ ብዙም አላንገራገርኩም፤ ስለ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT) ብዙ የማውቀው አለ በማለት ሳይሆን የማላውቀውን ለመማር የተሻለ ዕድል አገኛለሁ በማለት ነበር አወያይ (discussant) ለመሆን የተስማማሁት፤ ጽሁፉንም ለማንበብ ተቻኩዬ ነበር። ያለ ምክንያት አልነበረም፤ እንደሰማችሁት ብዙ ዕውቀት እንደሚገኝበት አስቀድሜ አውቅ ነበርና።

ሀ. አጠቃላይ ሀሳቦች

አቅራቢዉ ዶ/ር ሊሻን ሀሣቡን ለመግለፅ ከተጠቀመበት የአማርኛ ቋንቋ ብዙ ተምሬአለሁ። በተላል አማርኛ ሣይንሳዊና ተክኖሎጂ ንድፈ ሀሣቦችን ለማሰረዳት ችሏል። አንዳንዱማ በእንግለዝኛውም ብዙ ያልተለመደ ቃል ነው፤ ለምሳሌ፤ (knowledge ecosystem) የአማርኛ ቃል መገኘቱ ብቻ ሣይሆን ዕንሰ ሐሳቡም በተለያየ መልክ በመገለፀ እውነትም እውቀትን በትረካ መልክና በተግባር ይዘቱ ለማቅረብ ይቻላል አሰኝቷል። ብዙ አከራካሪ በሆኑ ነጥቦችም ላይ ዶ/ር ኒሻን የሰጠው አስተያየት በጣም ሚዛናዊ በመሆኑ ሁለቱንም ገጽታዎች በሚገባ ለማየት ይቻላል። በጽሑፉ ወስጥ የተለያዩ ጠለቅ ያሉ ትችቶችም ቀርበዋል። ለምሳሌ፤ የአገራችን የእወቀት መዋቅር (knowledge ecosystem) በአብዛኛው በስሜታዊነት ላይ የተመሰረተ፤ ለሌች የሰሩትን የሚጠራጠር፣ የሚንቅና የሚያፈርስ፤ የተሰራውንም በኮሚኖ ወስጥ የሚደብቅ ባህል ነው ያለን ይላል ፅሑፉ። ፖሊሲውም በዘፈቀደ የሚቀረፅ ነው። ይህም ማለት ተወቃሽ ፖሊሲ ብቻ ሳይሆን ባህላችንና ባህሪያችን ጭምር መሆኑን መረዳት ይቻላል። የተመራማሪዎች የማሳተም ስንፍና ምቹ (enabling) ፖሊሲ በአለመኖሩ ምክንያት እየተባባሰ መምጣቱንም ማየት ይቻላል። መማርና የሥራ ባህላችንን መቀየር የሚቻለው ያለን አስተሳሰብና ልምድ ሲቃወስና ለአዲስ አስተሳሰቦች በር መክፈት ሳንጀምር ነው ይላል። ይኽ የችግሮቻችን ሁሉ ቁልፍ ይመስለኛል።

በአገራችን የአስተሳሰብ ቀውስ ባለመኖሩ ነው ዕወቀትን ለማግኘትና ለመመራመር ዝግጁነት ያላነው። ነሀሉ በፊት ያለንበት ደረጃ አስከፊና መለወጥ እንደሚገባው የተረዳን አይመስልም። ለምሳሌ፤ ድህነትን በዐጋ የመቀበል፣ የእግዜር ጉዳይ እንጂ ልንቀይረው የማንችለን የራሳችን ስህተት መሆኑ፣ ብዙ የገባን አይመስልም። አስተዳደሩ ሲበድለን ህጋዊና ግዴታችን እንጂ፣ ስህተት መሆኑን እና መለወጥ መቻላችንን አናስበውም። በአጭሩ ሁኔታዎች የማይመቹ መሆናቸውን ስናይ በአዲስ አሠራርና አስተሳሰብ የመቀየር አዝማሚያ

---

* ዶ/ር መላት ደመቀ፤ ከአለማያ እርሻ ኮሌጅ በእርሻ ኢኮኖሚክስ ሳይንስ ባችለር ዲግሪ በ1980፤ በኢኮኖሚክ ፖለሲና ፕላኒንግ የማስተርስ ዲግሪ ከአ.አ ዩኒቨርሲቲ በ1984፤ በኢኮኖሚክስ የዶክትሬት ዲግሪ ከእንግሊዝ አገር ስትራትክላይድ ዩኒቨርሲቲ በ1989፤ በአ.አ ዩኒቨርሲቲ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋክልቲ በመምህርነትና ዲን ሆነው አገልገለዋቸውም በላይ አሰሸዬት ፕሮፌሰር ሆነዋል። በተጨማሪም በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ፖስት ዶክቶራል ፌሎ ሆነው ለሰባት ዓመታት (ከ1992 - 1999) ያገለገሉ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በዚምባብዌ ሐራሬ የአለም ምግብ ድርጅት (FAO) ቢሮ አማካሪ ናቸው። (ዘመናቲ በመሉ እንደ አውሮፓውን አቆጣጠር ናቸው።)

ጭራሽ አይታየንም። አገር ጥሎ መሰደድን አለዚያም እዚሁ ባለንበት በለጋሽ አገሮች እርዳታ ለመኖር ነው የምንፈልገው። እርዳታ (food aidን ጨምሮ) ሊያሳፍረን ቀርቶ ጭራሽ የመረዳት ግዴታ እንዳለ አድርገን ነው የምናስበው።

ዶ/ር ሊሻን እንደሚለው ለመማር መጀመሪያ የአስተሳሰብ ቀውስ ያስፈልጋል። ይሁን እንጂ የልምድ ቀዋሽ (disruptive metaphor) ሁኔታዎችን ገና ማየት አልጀመርንም። ተማሪው የሚማረው (አስተማሪውም የሚያተኩረው) የግልና የጋራ ችግሮችን (አገር አቀፍ ችግሮችን ጨምሮ) ለመፍታት፣ ለመመራመርና የራሳችንን ዕውቀት ለማዳበር ሳይሆን የተባፈውን የሌላ አገር ዕውቀት እንደ ውዳሴ ማርያም ለማነብነብና በመጨረሻ ደመወዝ ለማግኘት ይመስላል። አብዛኛዎቹ ኮሌጆችና ዩኒቨርሲቲዎች ለምርምርና ለተመራማሪዎች የሚሰጡት ትኩረት ባለመኖሩ ለአገራችን የዕውቀት አቅም መዳበር የሚያደርገው አስተዋጾኦ በጣም አነስተኛ ነው።

በዶ/ር ሊሻን አባባል ኮሌጆች ምንም የዕውቀት ይዘት ለውጥ ሳያደርገ ወደ ኮሌጅ ደረጃ የተሸጋገሩ የወጣቶች መዋያ ቦታዎች (መዋለ ወጣቶች) ሆነዋል። እንኳንስ ለአገራችን ለሌላው አገር ሊተርፍ የሚችል እምቅ ዕውቀት (potential knowledge) ያላቸው ወጣቶች ጊዜአቸውን እንደዚህ ሲያባክኑ ጭራሽ ችግር መሆኑን እንኳን አንረዳም። ትምህርት ያለ ተማሪው ተሳትፎና ያለ ምርምር ድጋፍ የሚገኝ ይመስለናል። ጥራት በሌላቸው የውጭ መምህራን አገርን የሚገነባ ዕውቀት እንዲሁ የሚገኝ ይመስለናል። ችግሩ የት እንደሆነ ስላልገባን (ዶ/ር ሊሻን እንዳለው) በውጭ ኮንሰልታንቶች ዕውቀት የምናድግ እየመሰለን ብዙ ገንዘብ እናወጣለን።

ለዕውቀት መዋቅሮቻችን ዝቅተኛነት ለመረጃ መዋቅሮቻችን የሰጠነው አነስተኛ ቦታ መሆኑን ከቀረበው ከዶ/ር ሊሻን ጽሁፍ መረዳት ይቻላል። በተለይ የቤተ-መጻህፍት ገዳይ የሚያሳገኝ ነው። መዕሐፍት የሚነበቡት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ብቻ እየሆነ ነው። ለነገሩ በእነዚህም ቢሆን መጽሐፍት የማይነበቡበት አጋጣሚ ብዙ ነው። ትምህርታቸውን ከጨረሱ በኋላ የሚያወቱትን ትንሽ ዕውቀት እንኳ እንዳይረሱ የሚረዳ የህዝብ ቤተመጻህፍት በሌለበት ግዙፍ እየሆነ የመጣውን የአገራችንን ችግር ሊፈታ የሚችል የተማረ የህብረተሰብ ክፍል ይኖራል ብለን መጠበቁ የዋህነት ነው። ተማረ የምንለው በአጭር ጊዜ ውስጥ እውቀቱ እየመነመነ፣ (knowledge degradation) ባዶ የሚሆን ይመስለኛል። ውድ ጊዜአችንን በጫት፣ በአለባልታ እያባከነው እንዴት ለማደግ እንደምንችል አይገባኝም።

በመንግሥትና በተለያዩ ድርጅቶች የሚጠናቀሩ መረጃዎች በኃላፊነትና ለዕውቀት ተብለው ስለማይሰበሰቡ አጥቅማቸው ገዳታቸው ሳያመዝን አይቀርም። የሌለንን አለን፣ ያለንን የለንም፣ ዓይነት መረጃ ነው የሚሰበሰበው።

እንደ ቤተ-መጻህፍቱ ሁሉ የመገናኛ ብዙሃኑም ለአገር ዕውቀት ግንባታ የሚረዳ አይደለም። ትኩረቱ ሁሉ ሚዛናዊነት በሌለው በፖሮፖጋንዳ ሥራ ላይ ነው። በኢንተርኔት በኩል ሰላለው መረጃ እንኳንስ ህዝቡ ዩኒቨርሲቲዎችም በሚያሳፍር ደረጃ ላይ መሆናቸውን ከቀረበው ጽሁፍ መረዳት ችለናል። ተራ የe-mail መልዕክት መላክ ፈተና በሆነበት ሁኔታ ነው ያለነው።

በአጠቃላይ በዚህ ጽሑፍ የተረዳሁት ስለ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ (IT) ብቻ አይደለም። በመሠያዬም፣ ማለትም፤ በእርሻው ዘርፍ ጭምር ለምን የቴክኖሎጂ ዕድገት ማስመዝገብ እንዳልቻልን መረዳት ችያለሁ። በዕወቀትና በመረጃ መዋቅሮቻችን ላይ ሳይሆን በቴክኖሎጂ ብቻ በማተኮራችን አሁን ላለንበት ኃላቀርነት ተዳርገናል ማለት ይቻላል።

ለ. ከሌሎች አገሮች ምን መማር እንችላለን – Success Cases

የሶስት አገሮችን ልምድ በአጭሩ ለመቃኘት እሞክራለሁ።

1. ህንድ

ህንዶች የሶፍትዌር ኢንዱስትሪአቸውን የማስፋፋት ሥራ ከብዙ አገሮች ቀድመው ሲጀምሩ ዛሬ የደረሱበት ከፍተኛ ደረጃ ለመድረስ እንደሚችሉ የተረዱት ርዕይ የነበራቸው መሪዎቻቸውና በዕውቀት የበለፀጉት ጠበብቶቻቸው ብቻ ነበሩ።

- በ1988 (የዛሬ 17 አመት ገደማ) የተክኖሎጂ ፓርኮችን በዋና ዋና ከተሞች በማቋቋም ነው ሥራ የጀመሩት፤
- የውጭ ባለሀብቶች ያለምንም ችግር ዕውቀታቸውን እና ገንዘባቸውን በIT መስክ እንዲጠቀሙ ከቀረጥ ነፃ የሚያስፈልጋቸውን መሣሪያዎች እንዲያስገቡ አድርገዋል፤ በይበልጥም በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነውና እንግሊዝኛ ተናጋሪ የሆነው የሰው ኃይላቸው የውጭ ባለሀብቶችን በቀላሉ ለመሳብ አስችሏል፤
- የፈጠራ ሥራ ይበረታታ ዘንድም Intellectual Property Right በሥራ ላይ እንዲውል አድርገዋል፤
- የቴሌፎን መስመሮችንና አገልግሎትን ለግል ባለሀብቶች ከ1992 ጀምሮ ክፍት በማድረግ በሚፈጠረው ውድድር ሕገበ የተሻለ አገልግሎት በአነስተኛ ዋጋ እንዲያገኝ ተደርጓል፤
- በራሳቸው ቋንቋ በመጠቀም በየአካባቢው ያለው ህዝብ የIT ተጠቃሚ እንዲሆን ሲያደርጉ ከ418 ቋንቋዎች በላይ ተናጋሪ ለሆነው ህዝብ ወሳኝ ነበር። በዚህ ረገድ የክልል መንግሥታት ጥረት ቀላል አልነበረም። ለምሳሌ፤ ባለብዙ ቋንቋ ኮምፒዩተር (Multilingual Word Processor) ለሀሎም ኢንተርኔት (internet) ተጠቃሚ እንዲደርስ አድርገዋል።

በመሆኑም የህንድ ኮምፒዩተር አንቀሳቃሽ ሥርዓት (software) ኢንዱስትሪ ዕድገት በዓመት 50% ሲደርስ የተጠቃሚው ቁጥር በየዓመቱ 50% እያደገ ሄደ። ዛሬ ህንድ (IT) ጋር በተያያዘ ልማት ብቻ በዓመት ከ30 ቢሊዮን ዶላር በላይ ገቢ ታገኛለች። የሀገሪቱም የወደፊት ዕድገት አስተማማኝ መሠረት ላይ ነው ያለው። Rocket ወደ ህዋ እስከ መላክና ከ1 ቢሊዮን በላይ ህዝብ ራሳቸው በራሳቸው መመገብ ችለዋል።

2. ብራዚል

ብራዚል በ1980ዎቹ የአገሯ የIT አቅም ገንቢታ ጠንካራ አገር-በቀል ኩባንያዎች እንዲፈጠሩ ከአደረገች በኋላ በ1990ዎቹ የውጭ ባለሀብቶችን በስፋት በመጋበዝ የIT ዕድገቷን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማሸጋገር ችላለች።

- በ2000 ዓ.ም. ብቻ እስከ 30 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት የውጭ ኢንቨስትመንት በማስገባቷ በተለይ የቴሌኮሙኒኬሽን መስመሮቿን ወደ ከፍተኛ ደረጃ ለማድረስ አስችሏታል፤
- በመንግሥት ሞኖፖሊ ሥር የነበረውን የቴሌን አገልግሎት በ1995 ወደ ግል ዘርፉ እንዲዛወርም አድርጋለች፤
- የምርምር አቅሟን በየዓመቱ በዕጥፍ ለማሳደግ ችላለች፤

- የህዝብ ቤተ-መጻህፍት በሙሉ በinternet እንዲገናኙ ተደርገዋል፤
- የህዝብ የኢንተርኔ አገልግሎት community access centers በየቦታው ተቋቁመዋል፤
- በየዓመቱ በ25% እያደገ የሄደው የsoftware ኢንዱስትሪው ብቻ በ2002 ዓ.ም. 10,000 ኩባንያዎችንና ከ20,000 በላይ ሠራተኞችን ማቀፍ ችሏል፤
- የIT ማደግም የብራዚል ቡና በቀጥታ (online) በጨረታ እንዲሸጥና ገበሬዎቻቸውና አገራቷ ከቡና የተሻለ ገቢ እንዲያገኙ ረድቷል፤
- ለህዝቡ ኮምፒዩተር በርካሽ የሚቀርብበትን ለማመቻቸትም ሁሉም ኩባንያዎች ተባብረው እንዲሰሩ በማድረግ እስከ 200 የአሜሪካ ዶላር በሚደርስ ገንዘብ ብቻ ድሃው ህዝብ የኮምፒዩተር ባለቤት እንዲሆን አስችለዋል። በተጨማሪ መንግሥት ለኮምፒዩተር መግዣ የብድር አገልግሎትን አመቻችቷል።

ስለዚህ ብራዚል ዛሬ በላቲን አሜሪካ ግንባር ቀደም በIT ቴክኖሎጂ የዳበረ አገር ለመሆን በቅታለች።

3. ኮስታሪካ

በኮስታሪካ ደግሞ አገራቷ ከቡናና ሙዝ የምታገኘው የውጭ ምንዛሬ እያሽቆለቆለ በመሄዱ አማራጭ መፈለግ ግድ ሆነ።

- በተፈጥሮ ሀብትና በርካሽ የሰው ጉልበት ብቻ የተመሰረተ ኢኮኖሚ የትም እንደማያደርስ የተረዱት ገና በ1990ዎቹ መግቢያ ላይ ነበር፤
- ታዋቂ የIT ኩባንያዎችን (በዋነኛነት Intelን) በመሳብ ዛሬ ከአሜሪካ ቀጥሎ ከፍተኛው የComputer Microprocessor ምርት በአገራቸው እንዲመረት አድርገዋል፤
- ከፍተኛ የጥራት ደረጃ ያለው የሰው ኃይል በማሰልጠናቸው ነው ትላልቅ ኩባንያዎችን መሳብ የቻሉት፤ በ2000 ዓ.ም. ከኮምፒዩተር ጋር የተያያዙ ምርቶች ከጠቅላላው የኮስታሪካ የውጭ ንግድ ገቢ 37% ሲይዙ ቡና ወደ 5% እንዲሁም ሙዝ ወደ 10% ሊወርዱ ችለዋል።

ይህ የኢኮኖሚ ለውጥ (transformation) በአጭር ጊዜ ውስጥ ሊገኝ የቻለው ዕውቀትን መሠረት አድርገው የሚመለከታቸው በሙሉ ተባብረው በመሥራታቸው ነው። በመቀጠልም አብዛኛው ህዝብ ከአዲሱ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ይሆን ዘንድ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን ቀርፀው በመንቀሳቀስ ላይ ናቸው።

ሌሎች በርካታ አገሮችም በተመሣሣይ ከ IT ብዙ ጥቅም ማግኘት ችለዋል። IT ጥቅም ላይ የዋለው ለተለያዩ ዓላማዎች ነው።

1. የውጭ ገበያ (export) ክፍለ ኢኮኖሚን ለማገዝ፤
2. የአገር ውስጥ የማምረት አቅምን ለማጎልበት፤
3. በዓለም አቀፍ የገበያ ትስስር ውስጥ የተሻለ ቦታ ለመያዝ፤
4. የማህበራዊ ኢኮኖሚ የsocio-economic ልማትን ለማገዝ (ት/ቤት፣ ጤና ጣቢያ፣ ባንክና የህዝብ አስተዳደር)፤

5. የፖለ·ቲካ ለወ·ጥ፣ ዲሞክራ·ሲ·ያዊ ባህል ለማዳበር፣ በ·ተ·ለ·ይ·ም በinternet በሚሠራጭ ዜና ጽሁ·ፍ newsletter የወ·ይ·ይት መድረክ በመክፈት፣ ሁ·ሉ·ም ድ·ም·ጹን የማሰማት ዕድል እንዲ·ያ·ገ·ኝ ተ·ደ·ርጓ·ል።

ሆኖም በICT በሚገባ ለመጠቀም የልማት ዓላማን ማስቀደምና IT ም ይኽንኑ ዓላማ ለማሳካት እንደመሣሪ·ያ (enabler strategy) ማየ·ቱ አስፈ·ላ·ጊ ነው። በ·ተ·ጨ·ማ·ሪ ሰፊና ሁ·ሉን ባቀ·ፈ መልኩ መጠቀሙ ከ IT የሚገኘው·ን ጥቅም የበለጠ ከፍ ያደርገዋል።

ለአንድ ለ·ተ·ነጠለ ዓላማ ብቻ ለመጠቀም መሞከሩ ብዙ ፋ·ይ·ዳ የለው·ም። ለሁ·ለገ·ብ ጠቀሜታ የማዋለ· (mainstreaming) አስፈ·ላ·ጊ·ነ·ት·ን ዶ/ር ሊ·ሻ·ን ጠቁ·ሟ·ል። በመሰ·ኩ· የ·ተ·ሰ·ማ·ሩ ሁ·ሉ የሚሳ·ተ·ፉ·በ·ት·ና በ·ጋ·ራ· የሚሰ·ሩ·በ·ት·ን መንገድ መቀ·የ·ስ·ም ው·ጤ·ታ·ማ ለመሆን ወሳ·ኝ ነው። ይኽ·ንን·ም በቅ·ን·ጅ·ት ለመም·ራ·ት ር·ዕ·ይ ይጠ·ይ·ቃ·ል። ለዚ·ህ·ም ሲ·ባ·ል ብዙ· አ·ገ·ሮ·ች የረ·ጅ·ም ጊዜ ዕቅድ ያ·ወ·ጣ·ሉ። ለ·ም·ሳ·ሌ፤ ማ·ሌ·ዥ·ያ በ1996 Vision 2020 የሚ·ባ·ል የIT ዕቅድ በማ·ወ·ጣ·ት ነው የዕ·ወ·ቀ·ት·ና የመ·ረ·ጃ ኢኮ·ኖ·ሚ·ያ·ቸ·ው·ን ለመገ·ንባ·ት እን·ቅ·ስ·ቃ·ሴ የ·ጀ·መ·ሩ·ት። ው·ጤ·ት ለማ·ግ·ኘ·ትም ብዙ· ጊዜ አ·ል·ወ·ሰ·ደ·ባ·ቸ·ው·ም።

በ IT ው·ጤ·ታ·ማ የሆኑ· ሁ·ሉ· ለሚ·ከ·ተ·ሉ·ት· ት·ኩ·ረ·ት· እ·ን·ደ·ሰ·ጠ· ሊ·ጤ·ን ይገ·ባ·ል።

1. የሰለጠነ የሰው· ኃይል፤

ይኽ·ን በሚ·መ·ለ·ከ·ት· ዶ/ር ሊ·ሻ·ን በሚገባ አስቀ·መ·ጧ·ል። እኔ የም·ጨ·ም·ረ·ው· ቢ·ኖ·ር አስበ·ን፤ አቅ·ደ·ን ነ·ሰ·ራ·ን በቀ·ላ·ሉ·ና በአ·ጭ·ር ጊዜ ው·ስ·ጥ ነ·ፃ·ነ·ቱ· ባለ·ሙ·ያ·ዎ·ች·ን ማፍ·ራ·ት እን·ች·ላ·ለ·ን። ብዙ· ወጣ·ቶ·ች ዕድ·ሉ·ን ቢ·ያ·ገ·ኙ· ነ·ማ·ን·ም አገር ሰው· ያላ·ነ·ሰ መሥ·ራ·ት· ስለሚ·ች·ሉ· የው·ጭ ባለሀ·ብ·ቶ·ች·ን መሳ·ብ ይ·ች·ላ·ል።

2. ዘመናዊ የቴሌኮሚኒኬሽን ወይም የICT መስመሮችና መረቦች networks፤

ዘመ·ና·ዊ የ·ቴ·ሌ·ኮ·ሙ·ኒ·ኬ·ሽ·ን መስመሮች·ና መረቦች· network ሲ·ኖ·ሩ· ብቻ· ነው· በዛሬው· ዓለም የልማ·ት· እ·ን·ቅ·ስ·ቃ·ሴ፣ IT·ን ጨ·ም·ሮ የሚ·ፋ·ጠ·ነ·ው። በሀገራ·ች·ን ያለው· የ·ቴ·ሌ·ኮ·ሙ·ኒ·ኬ·ሽ·ን አገል·ግ·ሎ·ት· እ·ን·ኂ·ን·ስ የው·ጭ· ባለሀ·ብ·ቶ·ች·ን ሊ·ስ·ብ ቀ·ር·ቶ· የገ·በ·ተ·ን·ም ጥ·ለው· እ·ን·ዲ·ሁ·ም የሚ·ያ·ደ·ር·ግ ይ·መ·ስ·ለ·ኛ·ል። ይኽ·ን ት·ግ·ር ለማ·ቃ·ለ·ል ደ·ግ·ሞ ብዙ·ዎ·ች· የ·ተ·ጠ·ቀ·መ·ባ·ት·ን መንገድ ማለ·ት·ም privitization እና de-regulation የሚ·ሉ· ይ·ላ·ል። ያኔ ሕ·ዝ·ብ አገል·ግ·ሎ·ት· በል·መና·ሳ·ይ·ሆ·ን ኩ·ባ·ን·ያ·ዎ·ች· እ·የ·ለ·መ·ኑ· አገል·ግ·ሎ·ት· ያ·ገ·ኛ·ል።

3. ደጋፊ ፖሊሲ፤

ፖ·ሊ·ሲ· ለIT መስፋ·ፋ·ት· የሚ·ጫ·ወ·ተ·ው· ሚ·ና በ·ጣ·ም ከ·ፍ·ተ·ኛ መሆኑ· ግ·ል·ፅ ነው። ት·ክ·ክ·ለ·ኛ ፖ·ሊ·ሲ· ይ·ቀ·ረ·ፅ ብ·ዙ· አ·ገ·ሮ·ች· ዋ·ና·ው·ን ባለ·ጉ·ዳ·ይ (stakeholder) ማሳ·ተ·ፍ· ነ·በ·ረ·ባ·ቸ·ው። ለ·ም·ሳ·ሌ፤ አ·ን·ድ· የICT Agency ቢ·ቋ·ቋ·ም በቦ·ር·ድ· እ·ን·ዲ·ጉ·ዳ·ደ·ር·ና የቦ·ር·ዱ·ም አባ·ላ·ት· በአ·ብ·ዛ·ኛ·ው· የሚ·መ·ለ·ከ·ታ·ቸ·ው· ክ·ፍ·ሎ·ች· (stakeholders) ይ·መ·ላ·ለ·ሉ። በሀገራ·ች·ን ብዙ· ጊዜ የሚ·ያ·ጋ·ጥ·መ·ን ግን መንግሥ·ት· ብቻ·ው·ን ፖ·ሊ·ሲ· ያ·ወ·ጣ·ል፣ በሥ·ራ· ላ·ይ· ብቻ·ው·ን እ·ን·ዲ·ው·ል ያደ·ረ·ጋ·ል፣

በትክክለኛ ሥራ ላይ መዋሉንም ራሱ መንግሥት ብቻ ተቆጣጣሪ ነኝ ይላል። የዚህ ዓይነቱ አሠራር የትም ስለማያደርስ ሁሉን አቀፍ ተሳትፎን የሚያጎለብት አሠራር በ IT ብቻ ሳይሆን በሌሎችም መስኮች ብንጀምር በአጭር ጊዜ ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት ይቻላል።

4. የግል የIT ኩባንያዎች መዳበር፤

የግል IT ኩባንያዎች ባልተስፋፋበት የኤኮኖሚና ሶሻል ልማቱ በ IT ይታገዛል ማለት አይቻልም። ለዚህም መንግሥት አስፈላጊውን የፋይናንስ፣ የገበያ፣ የባለቤትነት ህግ፣ የአስተዳደርና የመሳሰሉትን ድጋፍ ይሰጣል። በአንዳንድ ባለሀብቶች በጋራና በፅቅድ በመንቀሳቀስ ተወዳዳሪ ሆነው ለመገኘት መዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል። በሀገራችን የመንግሥቱን ትኩረ በመስክ የተሰማሩ ባለሀብቶች ምን ያህል በጋራ ይሠራሉ? ብንል መልሱ ምንም ነው። ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ Private Limited Company ብዙም አይረዳም። በአክሲዮን መልክ በተደራጀ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ኩባንያ (Share Company) ሰፋ ባለ አቅም መንቀሳቀስ ያስፈልጋል። በማህበር በመደራጀት በፖሊሲ ቀረፃና መንግሥት ለሴክተሩ አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ ማድረግ ወይም መማፀን (lobby) ያስፈልጋል።

5. ይዘትና አጠቃቀም (Content and application)

ይህ እንግዲህ የህዝቡን ቀጥታ ፍላጎት ለማሟላት፣ በራስ ቋንቋ፣ በሀገር መረጃና ዕውቀት መጠቀምን ይመለከታል። በሚገባ የሰለጠነ የሰው ኃይል ካለ ይህም ብዙ አስቸጋሪ አይሆንም።

ሐ. ዕድገታችን እንዴት ሊፋጠን ይችላል?

ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለልማታችን ወሳኝ እንደሆነ በየጊዜው ሲገለፅ ቆይቷል። ነገር ግን እንዴት ፈጣን ዕድገት ማስመገዘብ እንደሚቻል በቂ ግንዛቤ ያለን አይመስልም። ከተለያዩ አገሮች ልምድ የምንማረው ፈጣን ዕድገት የገዛላይ ያህል እርምጃን ይጠይቃል። ለዚህ ደግሞ IT እንደዋነኛ መሣሪያ በማገልገል ላይ ነው። የዚህ ዓይነቱን የፈጣን ዕድገት አማራጭ ደግሞ ብዙዎች leap frogging ሲሉት አንዳንዶች tiger leap (ለምሳሌ በ Estonia) ሌሎች ደግሞ antelope-jumping (ለምሳሌ በታንዛንያ) ብለው ይጠሩታል።

የኢኮኖሚና የሶሻል ልማታችን ዶ/ር ሊሻን በሚጠቁመን በIT አቅም ግንባታ ቢታገዝ የአገራችን ዕድገት ቢያንስ በዓመት በአንድ እና ሁለት በመቶ ጭማሪ ሊያሳይ እንደሚችል ከሌሎች አገሮች ልምድ በመነሳት መገመት ይቻላል። በይበልጥ ደግሞ ውድድሩ በተጋጋለበት globalized ዓለም ውስጥ ጥሩ ተፎካካሪ ለመሆን ሌላ አማራጭ ሊኖረን አይችልም።

ለላው ዕድገታችንን ሊያፋጥን የሚችለው የአስተዳደርና የፖሊሲ አወቃቀራችንን በመቀየር ህዝቡ በጋራና በመተማመን ለመሥራት እንዲችል የዲሞክራሲ አሠራርን ማስረፅ ነው። መልካም አስተዳደርና በህዝብ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ (demand-driven) ፖሊሲ በየመስኩ በኖረን የኢኮኖሚ ዕድገታችን በዓመት ከሠላት እስከ ሦስት በመቶ ሊጨምር እንደሚችል

በእርግጠኝነት መናገር ይቻላል። የቻይናው ፈጣን የኢኮኖሚ ዕድገት ለዚህ በቂ ማስረጃ ነው። መልካም አስተዳደርንና የህዝብ ተሳትፎን ደግሞ IT በመጠቀም በቀላሉ ማጎልበት እንደሚቻል ከላይ ተመልክቷል።

በIT ብንታገዝ እና መልካም አስተዳደር ቢኖረን ሌላ ከፍተኛ ጥቅም እናገኛለን። በእንግሊዝኛው አጠራር synergy ወይም multiplier effect በምንለው መንገድ ማለት ነው። በተለይ ወጣቱና የተማረው ክፍል ሀገር ጥሎ መሄድ ሳይሆን እዚሁ ሠርቼ ያልፍልኛል የሚል ዕምነት ሊኖረው ይችላል። አገር ጥለው የሄዱትም ዕውቀትና ሀብታቸውን ይዘው ሊመጡ ይችላሉ። ያለንን የሰው ኃይል በሚገባ ጥቅም ላይ በማዋላችን ዕድገታችንን እንደገና ከአንድ እስከ ሁለት በመቶ በዓመት በተጨማሪ ልናሳድገው እንችላለን።

ሲጠቃለል እንግዲህ ያለምንም ብዙ ወጪ የሀገራችን ልማት በቀላሉ ከአራት እስከ ሰባት በመቶ በዓመት ተጨማሪ ዕድገት ሊያሳይ ይችላል። ይህም ማለት ኢኮኖሚው አሁን በአራት በመቶ እያደገ ነው ብንል ወደ ሰምንት በመቶ እና ከዚህ በበለጠ ፍጥነት ማሳደግ ይቻላል። ዋናው ፍላጎቱና በጋራ በአንድነት ዕውቀትን መሠረት አድርጎ መሥራት ነው። አሁን ከገባንበትም የRicardian ወይም Malthusian ወይም የድህነት ወጥመድ (trap) መውጣት እንችላለን ማለት ነው።

በመጨረሻም፤ ለመጠቆም የምፈልገው መንግሥት፣ የግል ባለሀብቶች እና የሲቪል ማህበራት በጋራ (በconsensus) ለመንቀሳቀስ ከሞከሩ ዶ/ር ሊሻን አንዳንድ በርዕይ መልክ ወደፊት ሊሠሩ ይችላሉ ያላቸው ዛሬ ወይም በቅርቡ የማይሠሩበት ምክንያት አይታየኝም። ለምሳሌ፡ ቤተመጻህፍትን በየአከባቢው መክፈት፣ የኢንተርኔት አገልግሎትን በየቀበሌውና ጤ ጣቢያው፣ በየት/ቤቱ፣ መክፈት ጊዜ የሚወስድ፣ ብዙ ገንዘብ የሚጠይቅ አይደለም የብሮድካስቲንግና የቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ መዋሀድ እንዲሁም የሚመለከታቸውን በቦር ውስጥ ማካተት ጊዜ የሚወስድ አይደለም። የቴክኖሎጂ ፓርክ ወይም IT business incubati centers ለማቋቋም ገና ረጅም ዓመት የምንጠብቅ ከሆነ ሌላው ዓለም ወደፊት፤ እኛ ወደ ኋ የመሄዳችን ነገር አሁንም ይቀጥላል ማለት ነው። ዋናው ቁምነገር በራስ ተነሳሽነ አስተውሎት ባለው ድፍረት (initiative) ተጠቅሞ ፓርኩን ለመጀመር ዛሬውኑ ጥረት ማድ ነው።

እዚህ በየጊዜው እየተገናኘን መነጋገሩ ብቻ በቂ አይደለም። ፈጥነን ወደ ሥራ ገ መልካም ነው እላለሁ።

አመሰግናለሁ!

ዶ/ር ሲሻን አዳም ባቀረቡት ጽሑፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት

አህመድ ሁሴን*

በመጀመሪያ የኤኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበርን ላመሰግን እፈልጋለሁ። በዚህ ኢንፎርሜሽን፣ ኮሙዩኒኬሽን፣ ቴክኖሎጂ እና ልማት በኢትዮጵያ በሚል ታላቅ ፎረም ላይ አወያይ ሆኜ በመጋበዜ ክልብ ደስ ብሎኛል። የዛሬ አራት-ና አምስት ዓመት አካባቢ የኢትዮጵያ ኢንፎርሜሽን፣ ቴክኖሎጂ ባለሙያዎች ማህበርን ስናቋቁም ትልቁን ዕርዳታ ያደረግለን የኢትዮጵያ ኤኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ነው። በተለይ በገዚው የማህበሩ ፕሬዝዳንት የነበሩት ዶ/ር ብርሃኑ ነጋ በፎአችን ድረስ በመገኘት አዲሱ የእኛ ማህበር ከማህበራቸው ሊማር የሚችለውን በሰፊው አንድ ክሰዓት በኋላ የፊደ ውይይት አካሂደን ከእርሳቸው ብዙ ተጠቅመናል። ዛሬ የማህበራችን ሊቀመንበር አቶ ቦጋለ ደምሴን ጨምሮ ሦስት የሥራ አስፈጻሚ አባሎቻችን በውይይቱ ላይ እዚህ ይገኛሉ። ለዚህም እንደገና የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበርን ላመሰግን እፈልጋለሁ። ሁለተኛ ሊሻንን በማመሰከት ነው።

ሊሻን የረጅም ጊዜ ጓደኛዬ ሲሆን በምርምር ሥራው ብዙ አውቀዋለሁ። ባቀረበልን ጽሑፍ ብዙ የገረመኝ የአማርኛ አጠቃቀሙ ነው። ICT ለአማርኛ ጽሑፍ አባድ በመሆኑ ጽሑፉን ከማንበቤ በፊት የቋንቋ ችግር ይደርስብታል ብዬ ሰግቼ ነበር። ሆኖም ጽሑፉን ካነበብሁ በኋላ በደንብ የተዋጣለት ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

እኔም ከእርሱ ጽሑፍ ብዙ ተምሬአለሁ። ለምሳሌ፤ ልምጃ የሚል ቃል ከየት እንዳመጣው ባላወቅም ልማር ችያለሁ። Knowledge ecosystem የሚለውን ቃል የአወቅት መዋቅር ብሎታል። በጣም ጥሩ ትርጉም ነው። ሊሻንን አመሰግናለሁ።

ሊሻን ባቀረበልን ንግግር ላይ እኔ አስተያየቴን መጀመር የምፈልገው ከርዕዩ ነው። ምክንያቱም ርዕይ ላይ ለመድረስ ምን አስቀመጠ? ብዬ ለማየት ስለፈለግሁ ነው።

ለእኔ ሊሻን በሰጠኝ ጽሑፍ ላይ የሃያ ዓመት ርዕይ ቢሆንም አሁን በአቀረበው ላይ ርዕዮን አምስት ዓመት አድርጎታል። የመጀመሪያው አስተያየቴ እንዴት በቴክኖሎጂ፣ በተለይ ደግሞ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሃያ ዓመት ርዕይ ለኛር ይችላል የሚል ነበር። እኔም ርዕዩ ወደ አምስት ዓመት መወረድ አለበት ባይ ነኝ። ምክንያቱም ሊሻን ሃያን እንዳስቀመጠው ከተቀበልን መሳቂያ እንዳንሆን ስለምስጋ ነው። ቴሌኮሙዩኒኬሽን ኩባንያም በዚህ ረገድ ቀድሞ የነበረውን ርዕይ አሁን በማስተካከሉ የሚያስመሰግነው ነው እላለሁ።

---

* ዶ/ር አህመድ ሁሴን፣ የሂልኮ ኮምፒዩተር ሳይንስ ኮሌጅ፣ ዳይሬክተር ጀነራል።
አቅራቢው በዚህ ጽሁፍ የመጨረሻ ረቂቅ ላይ አስተያየት ወይም ማስተካከያ አልሰጠበትም።

ሊሻን ተለፍንና የሞባይል መሳሪያዎችን በአምስት ዓመት ውስጥ ከሱቅ እንድንገዛ አመኖሉ
ያለውን እኔም እጋራለሁ:: ሆኖም በበኩሌ አምስት ዓመት ይፈጅል የሚል እምነት የለኝም
በአምስት ዓመት ካልናቸውማ ሌላ ሦስት ዓመት ጨምረውብን ስምንት ዓመት እንዳያረገ
እስጋለሁና! እንደ እኔ በሁለት ዓመት ሁለቱን መሣሪያዎች ከገበያ ላይ መግዛት የምንችልበት
ደረጃ ላይ እንደርሳለን ብዬ አስባለሁ::

ሌላ ርዕይ ሊጨምር:: ምናልባት መሳቂያ ሊሆን ይችላል:: ቢሆንም እርሱም፣ አንድ የበኖ
አምራች ገበሬ ቤቱ ሆኖ በተንቀሳቃሽ ቴሌፎኑ የኒውዮርክ በኖ ገበያን ሲከታተል ማየት
እመኛለሁ:: በእውነቱ ይኸ በአምስት ዓመት ሊደርስበት የማንችለው ሊሆን ይችላል::
የምንነጋገረው ርዕይ ስለሆነ ለራሴ ነጻነት ሰጥቼ ሲሆን በዚያውም አንድ ነገር ማየት
እንድንችል በማሰብ ነው:: እንዲህ

ዓይነት ገበሬ ለመፍጠር ምንድነው የሚያስፈልገን? የሚለውን ጥያቄ እንድናስብና መልስ
እንድንሰጠው ስለፈልግሁ ጭምር ነው::

ዶ/ር ሊሻን ትልቁና የመጀመሪያው ተግባራዊ እንዲሆንና አገራችንም እዚያ እንድትደርስ
ያሳሰበን ጠቃሚ ነገር ስለመረጃ ያለን ግንዛቤ እንድንመረምር ነው:: እርሱ ሲናገር
አልጠቀሰውም እንጂ በጽሑፉ ፍላጎት ቀስቃሽ የሆኑ ነገሮችን አስቀምጧል:: ለምሳሌ፣ መረጃ
ወይም መልዕክትና ጫጫታ (sound and noise) :: ይኸንን መለየት የሚችል ማህበረሰብ አለን
ወይ? መልዕክትንና ጫጫታን የማንለይ ከሆነ እንዴት አድርገን መፍጠር እንችላለን? የመረጃ
አሰባሰብና ስርጭት፣ መረጃ የትክክለኛ ውሳኔ ዋና ግብአት መሆኑን መገንዘብ፣ የሚሉትን
ሀሳቦች በደንብ አስቀምጠዋልናል::

ሁለተኛው የሊሻን ነጥብ እንዲሁ በደንብ ተቀምጧል፤ መረጃና ዕድገት ያላቸው ቁርኝት:: ብዙ
ጊዜ የሚያነሳኝመኝ መረጃ ወይም ኢንፎርሜሽን «ዳቦ አይሆንም» የሚል አባባል በተለያዩ
ጋዜጦች አነባለሁ:: መረጃ ከዕድገት ጋር ቁርኝት እንዳለው ለማስረዳት ሊሻን በደንብ
ሄዶበታል:: ቁርኝቱን ለማሳየት ሰፊ ሥራ የሚጠበቀን ይመስለኛል:: እንደሚታወቀው
ዕድገት ማቀድን ይፈልጋል፣ ዕቅዱን ማስፈጸም ይፈልጋል፣ አፈጻጸሙንም መከታተል
ይፈልጋል፣ ወዘተ... እነዚህ ሁሉ ያለመረጃ የሚሆኑ አይደሉም:: የመረጃ ጉድለት የዕድገት
መሰበርን ያመላክታል:: ለዚህ ነው መረጃ ከዕድገት ጋር ቀጥታ ግንኙነት አለው የሚል
እንደምታ የሚያሳየው:: እንግዲህ ይህ በሁሉም ዘርፍ ነው:: ICTን ልዩ የሚያደርገው ነገር
ግን ለኢኮኖሚ፣ ለማህበራዊና ለፖለቲካ ዘርፎች እንደ ኢንፍራስትራክቸር ሆኖ ስለሚያገለግል
ነው::

ከጤናው ጋር፣ ከኢኮኖሚው ጋር፣ ከግብርናው ጋር፣ ከትምህርቱ ጋር፣ ከመልካም
አስተዳደር ጋር፣ ከሁሉም ጋር የተቆራኘ ነው:: ከሊሻን ጽሑፍ እንደተረዳነው መረጃ ከቦታና
ከጊዜ (space & time) ጋር ግንኙነት እንዳለው ነው:: ከላይ ሊሻን ያነሳቸው ሁለት አብይት
ጉዳዮች መረጃና ግንዛቤና፣ መረጃና ልማት፣ ሲሆኑ ሦስተኛው ሊሻን ያነሳው ነጥብ የመረጃ
ቴክኖሎጂ ድርሻ ነው:: ስለሶስቱ ወሀደት አስገንዝበናል:: ኮሙዩኒኬሽንና መረጃ የቅልጥፍና
ጥያቄም ናቸው:: ይኸንን አስመልክቶ ሊሻን ሦስት ነገሮች አንስቷል:: አንደኛው፣ መረጃን
ከምንፈልገው ለልውውጥ በሚያመች መልኩ መጭመቅና የሚለው ሲሆን ይህ የቴክኖሎጂን ድርሻ
ያሳያል:: እሱ ደግሞ ያስተሳሰብ ለውጥ ይጠይቃል:: መልዕክቱን ከጫጫታ ለይቶ

ማውጣት። ሁለተኛው መረጃን በጥራት ማሰራጨት የሚለው ነጥብ ነው። ሦስተኛው መረጃ ተገልጋዩ መጠቀም በሚችልበት መልኩ መረጃን ማትረብ፤ ማለትም አጠቃቀሙን ማቅለል፤ ይህ ካልሆነ አንጠቀምበትም ማለት ነው። በተለይ ሊሻን አጽንኦት የሰጠው ቴክኖሎጂ ከመረጃ በፊት መሆን የለበትም የሚለውን ሀሳብ ሲሆን አንዳንዶቻችን ግን በታቃራኒው «ቴክኖሎጂ ወይንም ሞት» እያልን መሆኑን በሚገባ አስቀምጦታል።

ሊሻን ያነሳው አራተኛው ነጥብ ተዋናዮቹ እነማን ናቸው? ብሎ የጠየቀው ነው። በጽሑፉ በግልጽ ላይታይ ይችላል። ሆኖም ለዚህ ርዕይ መድረሻ የሚጠቅሙን፣ የሚያገለግሉን እነማን ናቸው? ብሎ በመጠየቅ፤ መንግሥትን ይጠቅሳል፣ አስተዳደርን፣ የግልና የመንግሥት ድርጅቶችን ይጠቅሳል፣ ተመራማሪዎችን ያነሳል፤ ተማሪዎችን፣ ባለሙያዎችን፣ ያመለክታል። በተለይ ሊሻን ያነሳውና አጽንኦት የሰጠው ጥሩ ነጥብ መገናኛ ብዙ኎ን ያላቸውን ድርሻ ማመልከቱ ነው። ይህ ብዙ ጊዜ አይነሳም። በጣም ብዙ የወደድኩለት ነጥብ ነው። መጨረሻ ላይ ሕገበ-ንም እንደ አንድ ተዋናይ ማንሳቱ አግባብ ነው እላለሁ።

ሊሻን አምስተኛ ነጥብ እነዚህ ያየናቸው ነገሮች በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ሲመዘኑ ምን ይመስላሉ? የሚለው ጥያቄ ነው። እዚህ ላይ እንደገና ያነሳቸውን መመልከት ያስፈልጋል። መጀመሪያ ለመረጃ ያለን ግንዛቤ የት ደረጃ ላይ ነው ያለው? የሚል ነጥብ አንስቷል። የአንድን መረጃ ዋጋና ሰንሰለት አለመገንዘብ ማለትም አንድ መረጃ ወጤቱ የት ድረስ ነው? ሰንሰለቱ እስከ ምን ድረስ እንደሆነ፣ አለመገንዘባችን ትልቁ ችግራችን ነው። ክፍ ብለን እንዳየነው የመረጃ ምንጮችን ለይተን አለማወቃችን ሌላው ትልቅ ችግራችን ነው። መልዕክትን ከጫጫታ መለየት አለመቻላችን እንዲሁ ሌላው ትግራችን ነው። ይህ የሚያሳየን ብዙ የግንዛቤ፣ ወይም የአስተሳሰብ ለወጥ በኢትዮጵያ እንደሚያስፈልገን ነው።

የመረጃና የልማት ትስስር በግልጽ አልታየም፤ ብዙ ጥረት አልተደረገም። እዚህ ላይ የመገናኛ ብዙኃንን ድርሻ በጣም ብዙ እንደሆነ ነው የምገምተው። መረጃ ወገንን ለመከላከል የማይጠቅመን ከሆነ፣ ወይም መረጃ ዳቦ የማይሆነን ከሆነ፣ ምን ጥቅም አለው የሚሉትንና የመሳሰሉትን ግንዛቤ ለማጥፋት ብዙ ሥራ እንደሚጠበቀን ነው። መረጃ ከዕድገት ጋር ያለውን ትስስር ነጥሮ ማውጣት ትልቁ ሥራችን ይሆናል ብዬ አምናለሁ። ይህንን ካላደረግን ለሥራችን ትልቅ እንቅፋት ይሆንብናል።

ሦስተኛው የሊሻን አብይ ርዕስ የቴክኖሎጂ ድርሻ ነው። ቴክኖሎጂ ስንል ደግሞ ከኮምፒዩተር ጋር የተገናኘ ነው። ከጥቂት ዓመት በፊት ኮምፒዩተር እንደ (ቅንጦት) ምኞት ዕቃ ነበር ሲነሳ የነበረው። በሌላ ጥግ ደግሞ «ቴክኖሎጂ ወይም ሞት» የሚለው ይታያል። አሁን እነዚህ ሁለት ጫፎች ላይ ያሉት አስተሳሰቦች መኖራቸውን ለማመልከት ነው እንጂ በመካከል ጥሩ፣ ጥሩ ምሳሌዎችም አሉ። እነሱንም ለመጥቀስ እፈልጋለሁ። ጊዜ ቢኖር ቢታዩ የምፈልጋቸውን ሁለት ነጥቦች ማንሳት እፈልጋለሁ።

አንዱ የዓለም አቀፍ ትስስር (globalization) ራዕይ ማስቀመጥ፤ ከሊሻን ጽሑፍ እንደተገነዘብኩት ርዕዩ በአብዛኛው የተቀመጠው ከአገር አንፃር ወይም በአገር ታጥሮ የተቀመጠ ይመስለኛል። ሆኖም globalization ከፍተኛ ግብአት እየሆነ መጥቷል። ግሎባላይዜሽን አንድን ርዕይ ለማስቀመጥ የሚኖረው ድርሻ ምን ይሆናል? የሚለው በእኔ አነባበብ ቁልጭ ብሎ በሊሻን ጽሑፍ አልወጣም። ሁለተኛው ከዚሁ ጋር የተያየዘው የIT ነገር ነው በአንድ በኩል። IT እንደ መዳኛችን (saviour) ሊታይ ይችላል። ግሎባላይዜሽን ሊወጠን

ደርሷልና። ከእሱ ለመትረፍ IT'ን እንደ ትልቅ መሣሪያችን ልናየው እንችላለን። ይሁን የግለ-ባላይዘሽን ትልቁ ሰርጎ የመግባት ኃይል IT መሆኑንም ማወቅ አለብን። ከዚህ በተረፈ ለወይይት ይሆናሉ ብዬ የማሰባቸውን አንዳንድ ነጥቦች አነሳለሁ።

ሊሻን ባነሳቸው ርዕዮች ዘንድ የዛሬ አምስት ወይም አሥር ዓመት ለመድረስ እምቅ ኃይሉ አለን ወይ? በእኔ ግምት መልሱ አዎን ነው። እስቲ አውሮፓ፣ አሜሪካን የነበሬትሁ አብሮአችሁ ሲማሩ የነበሩትን አውሮፓውያን፣ አሜሪካውያን፣ ጓደኞቻችሁን አስታውሷችሁ። እነሱ ምን አላቸው እኛ የሌለን? እኛስ ምን አለን እነሱ የሌላቸው? የሚሉትን ጥያቄዎች ብታነሱ በእኔ ግምትና በእኔ ልምድ መልሱ በጣም ቀላል ነው። ከእነሱ በምንም የምንናንስበት ነገር የለም ነው። አንዳንድ ነገሮች ሊጎድሉን ይችላሉ። እነሱን ማስተካከል ይቻላል። ቁምነገሩ እምቅ የሰው ሀብት አለን፣ በተለይ በግለሰብ ደረጃ ስናይ።

ኢትዮጵያ በICT ዕድገት ጎዳና እንድትራመድ ማድረግ ለሀለንተናዊ ዕድገቷ አስተዋጽኦ አለው ወይ? የሚለው ነጥብ ሌላው ሲሆን እሱም በደንብ በጋራ ይመስለኛል። ሦስተኛው እንዲጋራ የምፈልገው ICTን ራሱን ችሎ እንደ አንድ ክፍለ ኢኮኖሚ ለማየት በአሠነ ገዢ ባንችልም ሊሻን እንዳለው ICT ለሌሎች ዕድገት አስፈላጊ መሆኑን ካመንበት ከጎንዳ ቅድሚያ ሰጥተን ልናሳድገው የሚገባ ዘርፍ ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ጥያቄ በማያወላውል መልክ መመለስ አለብን።

ከዚህ በላይ መረጃ እወቀት ነው ብለናል። እወቀት ደግሞ ዕድገት ነው ስንል በግልጽ መቀመጥ ያለበት ይመስለኛል። ለግብርናው፣ ለንግዱ፣ ለቱሪዝም፣ ለአገልግሎቱ፣ ለፋብሪካው፣ መንገድ ጠቃሚ ነው ስንል፣ ICTም እንደዚያው ወይም የበለጠ ጠቃሚ ነው ወይስ ባነሰ ጠቃሚ ነው? ብለን መመለስ አለብን። ይህ ነጥር መወሳት ያለበት ነገር ይመስለኛል።

ሌላው ሊሻን በጽሑፉ በደንብ እንዳስቀመጠው የሰው ኃይላችን ምናልባት ብዙ ላያስከፋ ይችላል ባይ ነኝ። አስተማሪ ሰለሆንክ ይመለከተኛል፤ ከማየውና ካለኝ ልምድ የሰው ኃይላችን ብዙ የማያስከፋ አይደለም። ችግሩ ያለው ሥራ ላይ ነው። የሰው ኃይላችንን በሥራ ማሳተፉ ላይ፤ እነሱ ያላቸውን ዕምቅ ችሎታ መጠቀሙ ላይ። እነሱን በማሳተፉ ላይ ያለው ተነሳሽነት በጣም ደካም ነው። በዚህ ጉዳይ እንደ አንድ ነጥብ ሊነሳ የሚችለው ምናልባት እነዚህ መሳሪያች የሚሠሩበት አካባቢ ወይም መ/ቤት ኃይለኛ ተቃውሞ መኖሩ ሊሆን ይችላል። እነዚህ መሳሪያች ናቸው፤ ቴክኖሎጂ በተፈጥሮው መሳሪያችን የበለጠ ያቅሩል፤ ይሰባል፤ ማኔጅመንቱ ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች የቴክኖሎጂ ሳሪያ ለኖረው ይችላል። በዚህ መከበል የሚፈጠር ክፍተት አለ።

በተለያዩ ምክንያቶች በኢትዮጵያ ለICT ያለው የተጣባ አመለካከት (resistance) አሠንም ክፍተኛ ነው። ኮምፒዩተሮች ይገባለ፣ የኢንተርኔት ግንኙነት ማስተበለ የመጀመሪያ ነው፣ እሱም አሠን አሠን እየተለወጠ መኖዮ እንደሆን እንጂ ኮምፒዩተሩ ማኔጅሩ በር ይቀመጣል፣ ልብስ ይለብሳል፣ ጸሐፊዋ ታይን የምታደርገው ግን በአርጌ ታይን ራይተር ነው።

ኋላው ችግር ኮምፒዩተር ተጣ ማለት ችግራችን ሁሉ ተቃለለ ብለን የምናስበው ነው። ሰው ሳይሆን ኮምፒዩተር ሥራውን ይሠራል የሚባል ግምት ለሰው የሚንሰጠውን ግንባቤ በጣም

አናሳ አድርጎታል። ለዚህ ነው ስለሥልጠና የማነሳው። እንደ እኔ እንደ እኔ ኮምፒዩተር እስክሪፕቶ ነው። ከዚያ በተረፈ የሚያመጣው ነገር የለም። ሰዎች ኮምፒዩተር ከገዙ ከፍተኛ ውን ኢንቨስትመንት ያደረጉ ይመስላቸዋል። ሆኖም ኢንቬስትመንታቸው ገና ተጀመረ ማለት ይቻላል። የሶፍት ዌር፣ የሰው ኃይል ሥልጠና እና ከሱ ጋር በተጓደኝ የምናስባቸው ነገሮች አሉ። ይህን ግንዛቤ ማግኘት አለበት።

ሌላው ጉዳይ የ ICT የግል ድርጅቶችን እንደ ድርጅት፣ እንደ ተቋም፣ (በውስጡ ያሉትን ሠራተኞች ትተን ማለቴ ነው ሊሻንም አንስቶታል) ብዙ ችግሮች አለባቸው። ስለዚህ ነው፣ ለምሳሌ፤ ብዙ የ ICT ፕሮጀክቶች ጨረታዎች ብንመለከት አገር በቀል ኩባንያዎች እዚህ አገራችን እያሉ የውጭ ኩባንያዎች ይወስዷቸዋል። እነዚህ የውጭ ኩባንያዎች ደግሞ የሚጠቀሙት የእኛኑን ባለሙያዎች ነው። ይህ የሚያሳየን የት ጋ ነው የጎደለን? እንደ ድርጅት መሆን ነው? እንደ ድርጅት መቀጠል ነው ያቃተን? ብለን መጠየቅ እንገደዳለን። ባሙያዎቻችንን ብዙ እወቀትና ችሎታ አላቸው እላለሁ። በእርግጥ ኤክስፓገር ሊጎድላቸው ይችላል። ሆኖም ሁሉም ሲጀምር እንዲሁ ነው። ሁሉም እያጠፉ ነው የሚማረው፣ በዚህ ረገድ ብዙ ገንዘብ እየባከነ ነው በአገራችን። ኩባንያዎቻችን በጣም የማኔጅመንት ብቃት ይጎድላቸዋል፤ እንደ ኢንስቲትዩሽን የመቀጠል ብቃት ይጎድላቸዋል። እዚያ ላይ ችግሩን ለይተን ማወቅ ያለብን ይመስለኛል። ባጠቃላይ መሥራት ይቻላል ብዬ ነው የማምነው። ማሰራት የሚያስችል ሁኔታ ወይም ከባቢ ካለ ማለቴ ነው።

ሌላ ከዚህ ጋር የተገናኘው የማኔጅመንት ብቃት ነው እያስቸገረን ያለው። ለምሳሌ፤ ፕሮጀክቶች ተግባራዊ ወይም ውጤታማ ሳይሆኑ ይቀራሉ። የት ጋር ነው ችግሩ? ኩቴክኒሺያኑ ወይንስ ከፕሮጀክቱ ርዕይ? እኔ ከሁለቱም አይመስለኝም። ከማኔጅመንት ብቃት ማነስ ነው ብዬ እላለሁ። ሌላው ግን በባለሙያዎቻችንም ድክመት አለ ብዬ የምለው፣ ዶ/ር በፊታዱ በአንድ ወቅት በVision 2020 እንዳሉትና ከእርሳቸው ጋር የምስማማው ባለሙያዎቻችን የፕሮፌሽናሊዝም ብቃት ይጎድላቸዋል። የቴክኒክ ችሎታው አለን፣ ግን ትጋት የለንም፣ ተአማኒነት ያንሰናል፣ አንዳንዱም ትዕዛዝ ያለመቀበል ሁኔታ ይታያል። ሌላው ትልቁ ችግራችን ግን ለጊዜ ያለን ግንዛቤ ነው። ስለ IT ስንነጋገር ስለቅልጥፍና ነው። ቅልጥፍና ማለት ደግሞ ጊዜ ነው። ሠራተኛው፣ ፕሮግራመሩ፣ ወይም ቴክኒሺያኑ፣ ለጊዜ ያለው ግንዛቤ አናሳ ከሆነ አስቸጋሪ ነው። ኃላፊነትን የመወጣት አቅም በጣም በጣም አናሳ ነው።

ሌላው በIT ዙሪያ የሚነሳውና በአጽንኦት የማታየው የቡድን ሥራ ነው። Team work የማባለው! ብዙ ሥራዎች የቡድን ሥራ ናቸው። ብዙዎቻችን፣ እኔንም ጨምሮ፣ ለብቻችን መሥራት ነው የማሻለን፤ ከሰው ጋር መሥራት አንችልበትም። እነዚህን ጉዳዮችና ሌሎች ያነሳናቸውን ርዕዮች ሁሉ ለማሳካት አንድ ግንዛቤ ላይ መድረስ አለብን እላለሁ።

ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር
የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለመቀነስ አንድ አማራጭ አካሄድ

አክሊሉ ኪዳኑ*

1. መግቢያ

የዚህ ጽሁፌ ዋና ዓላማ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፈጣን እድገት እንዲያስመዘግብ ሲሆን ተያይዘው የሚመጡትን የማህበራዊ፤ የጤናና የኢኮኖሚያዊ ቀውሶች እስካሁን ስንሞክራቸው ከነበሩት አካሄዶች እስቲ ለየት ባለ መልኩ እንመልከታቸው የሚል ነው። እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመቀነስ እና ብሎም የሕዝቧን ችግሮች ለመቅረፍ በስነ ተዋልዶ፤ በተለይም በቤተሰብ መጣኔ ላይ ያተኮሩ ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች ላይ ስንረባረብ ቆይተናል፤ ሁላችንም የተቻለውን ያህል ብናደርግም በማንኛውም መለኪያ አጥጋቢ ውጤት አላገኘንም።

በኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር በየዓመቱ 2.8 በመቶ እያደገ ነው፤ አሁንም የሴቶች የመጀመሪያ ጋብቻ አማካኝ ዕድሜ 16 ነው፤ አንዲት ኢትዮጵያዊ ሴት በአማካኝ 6 ልጆች ትወልዳለች፤ እንዲሁም ከሚወለዱ 1000 ሕፃናት መቶው አንድ ዓመት ሳይሞላቸው፤ 172ቱ ደግሞ አምስት ዓመት ሳይሞላቸው፤ ይሞታሉ። በዚህ ሂደት የኢትዮጵያ ሕዝብ በየ23 ዓመት በእጥፍ እየጨመረ ይሄዳል። ለአብነት ለመጥቀስ አሁን ያለው ወደ 70 ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝብ ከ23 ዓመት በኋላ፤ ማለትም በ2028፤ ወደ 140 ሚሊዮን ሊጠጋ ይችላል ማለት ነው።

ይህ በእንዲህ እያለ ድህነትን ከሀገራትዋ ለመቅረፍ፤ የሚደረገው ጥረት በቂ ወጤት እያመጣ አይመስልም። አሁንም የሀገራትዋ ነፍስ ወከፍ ገቢ ወደ 100 የአሜሪካ ብር ብቻ ነው። አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብተው መማር ካለባቸው ህፃናት 24 በመቶ ብቻ ናቸው ት/ቤት ያሉት፤ ከአምስት አመት በታች ያሉ ህፃናት 50 በመቶ እጅ ተመጣጣኝ ምግብ አያገኙም፤ ከሚወለዱት ህፃናት ከመቶ ዘጠና እጅ በቂ ችሎታ ባላቸው የህክምና ባለሞያዎች ድጋፍ አያገኙም።

ከላይ የተጠቀሱትን ችግሮች ለመቅረፍ በመንግሥትም ሆነ ለሌች ጉዳዩ በሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች መከራ እየተደረገ አይደለም ብዬ ለመናገር ባልችልም፤ መከራው አጥጋቢ ውጤት እያገኘ ነው ብዬ ለመናገር አልደፍርም። ስለዚህ የጽሁፌ ዋና መልእክት የሕዝብን ቁጥር ለመቀነስ፤ ብሎም ጥሩ የኑሮ ደረጃ ላይ ለማድረስ፤ አሁን የያዝነውን አቅጣጫ ብንለውጥስ? የሚል ነው። ይህንን ለማድረግ እንዲረዳን ያክል ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር ስንት ነው? የሚለው ሃሳብ ላይ አተኩራለሁ። ብዙ ግዜ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ እድገትና ስለሚያስከትለው ችግሮች በየመድረኩ ስንናገር ዓይነተኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ስንት

---

*ዶ/ር አክሊሉ ኪዳኑ የሚገኙ-ሃሳብ የኖናትና ምርምር ማዕከል ዳይሬክተር ናቸው። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን እ.አ.አ. በ1977 በሥነ ጽሑፍ፤ የማስተርስ ዲግሪያቸውን በ1983 በዲቨሎፕመንት ኘላኒንግ እንዲሁም ደግሞ የዶክትሬት ዲግሪያቸውን በ1990 በዲሞግራፊ አሜሪካን ከሚገኝ አሊኖይ ዩኒቨርሲቲ ተቀብለዋል። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለአራት ዓመታት በመምህርነት አገልግለዋል።

ነው? እንዴትስ ሊደረስበት ይችላል? የሚለውን ብዙም አናነሳውም። ብናነሳው ግን የትግርኛችንን መፍትሄ ሊጠቁመን ይችላል ብዬ እገምታለሁ።

ስለዚህ በዚህ ጹሁፌ በመጀመሪያ ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር የሚለው ፅንሰ ሃሳብ ምን ማለት እንደሆነ ገልጬ፣ ፅንሰ ሃሳቡን የሚደግፉና የሚቃወሙ ሰዎች አመለካከትና የራሴን አስተያየት አቀርባለሁ። ከዚያም ምርትና ፍጆታን ለመጨመር በነፍስ ወከፍ የሚያስፈልገውን የተፈጥሮ ሃብቶች አጠቃቀም አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ገቢ ያላቸውን ሃብታምና ደሃ የሚባሉትን ሀገሮች ከኢትዮጵያ ጋር እያወዳደርኩ አቀርባለሁ። ቀጥሎም የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ከነሮ ደረጃ ጋር ያለውን ግንኙነት የተወሰኑ መስፈርት በመጠቀም ለማሳየት እሞክራለሁ። በመጨረሻም ሀገራችን ኢትዮጵያ ያሏትን የተፈጥሮ ሃብቶች በቅጡ ተጠቅማ፣ የህዝቧን የነሮ ደረጃ አሻሽላ የህዝቦቿን ቁጥር እድገት መግታት የምትችልበትን አቅጣጫ በ2020 ርዕይ አስቀምጣለሁ።

ይህንንም አጋጣሚ በመጠቀም ሃሳቤን ለመድረክ ወይይት እንዳቀርብ እድሉን ለሰጠኝ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እንዲሁም ለጹሁፌ አስፈላጊ የሆኑትን መረጃዎች፣ ኮምፒዩተር ውስጥ በማስገባትና ጽሁፉንም በመጻፍ ለረዱኝ ለወ/ት ሜሮን በቀለና ወ/ት ማርታ ከበደ ከፍተኛ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

2. ዓይነተኛው የሕዝብ ብዛት

በእንግሊዝኛ "Optimum" የሕዝብ ቁጥር የሚለውን ወደ አማርኛ ለመተርጎም ትንሽ አስቸግሮኛል። ከብዙ ወጣ ወረድ በኋላ «ዓይነተኛው» የሕዝብ ቁጥር የሚለውን ለጊዜውም ቢሆን ልጠቀምበት ወስኛለሁ። ሆኖም ወደፊት ከዚህ የተሻለ የአማርኛ ቃል ከተገኘ የማይቀየርበት ምክንያት አይኖርም።

2.1 ዓይነተኛው የሕዝብ ብዛት ምን ማለት ነው?

ዓይነተኛው የሕዝብ ብዛት የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ አንድ ትርጉም ለመስጠት የሚያስቸግሩ ብዙ የተለያዩ ሁኔታዎች ቢኖሩም፣ መሰረታዊ የሆኑ በአብዛኛው ሁኔታዎች ሊሰሩ የሚችሉ ትርጉሞችን ግን በአጭሩ ማስቀመጥ ይቻላል።

1ኛ. ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር የሚለው ፅንሰ ሃሳብ በአንድ ሀገር ውስጥ ሊታጨቅ የሚችል ከፍተኛው የሕዝብ ቁጥር ማለት አይደለም። ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር የሚወስነው የሚፈለገውን ጥሩ ነሮ ለማግኘትና በቀጣይነት ለመያዝ ምን ያህል ጥፋት ወይም ፍጆታ በሀገሪትዋ የተፈጥሮ ንብረት ላይ ሊደርስ ይችላል በሚለው ይመዘናል።

2ኛ. ሁሉም ዓይነተኛ የሚባሉ የሕዝብ ቁጥሮች ሊሆኑ ከሚችሉት አነስተኛው (viable) የሕዝብ ቁጥሮችና የሀገሪቷ የመሸከም አቅም (carrying capacity) ከሚፈቅደው የሕዝብ ብዛት መሃከል መሆን አለባቸው። ይህ ትርጉም ችግር የለውም ማለት አይደለም። ለምሳሌ አነስተኛው ሊሆን የሚችል የሕዝብ ቁጥር የሚለው ነገር የማህበራዊ ምርጫ ጉዳይ ሊሆን ስለሚችል ከቦታ ቦታ በእጅጉ ሊለያይ ይችላል። ሆኖም በአሁኑ አካሄድ የሕዝብ ቁጥር እየናረ የሚሄድ በመሆኑ ይህ አነስተኛው ሊሆን የሚችል የሕዝብ ቁጥር በሚለው ላይ ሀብረተሰቡ አንድ ዓይነት ስምምነት ማድረግ ይኖርበት ይሆናል።

3ኛ አሁን ዓለም ያለችበትን ሁኔታ ስንመለከት፤ የተፈጥሮ ሃብትም ሆነ ሰው ሰራሽ ሃብት፣ ለሁሉም ሰው እኩል ሊከፋፈል ስለማይችል የእያንዳንዱ ሰው ፍጆታ እኩል ሊሆን አይችልም:: ምንም እንኳን ይህንን ክፍተት ለማጥበብ ሁሉም ቢፈልግም እውነታው ግን ሙሉ ለሙሉ ሊሳካ የሚችል አይመስልም:: ስለዚህ ይህ ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር የሚለው ፅንሰ ሃሳብ ይህን ሃቅ ማቀፍ ይኖርበታል::

በአጠቃላይ የአንድ ሀገር ዓይነተኛው ሕዝብ ቁጥር ማለት አንድ ሀገር ያለውን የተፈጥሮ ሃብት በመንከባከብ እየተጠቀመ ለሕዝቡ ጥሩና ተከታታይ የኑሮ ደረጃ የሚያረጋግጥበት ሂደት ማለት ነው::

በዚህ ትርጉም ከሞላ ጎደል ከተስማማን፣ ይህንን ፅንሰ ሃሳብ በሚደግፉና በማይደግፉ ሰዎች ያለውን ልዩነት በሚቀጥለው ክፍል አሳያለሁ::

2.2 የዓይነተኛው ሕዝብ ቁጥር ፅንሰ ሃሳብ ደጋፊዎች

"እኛ ራሳችን ተነጋግረን የወደፊቱ ዓይነተኛ የሕዝብ ቁጥር ላይ ካልደረስን፣ ያ ቁጥር ለኛ ፍታዴ ውጭ በሁኔታዎች ይወሰናል:: ይህ ደግሞ እኛ በፍጹም የምንፈልገው ቁጥር ላይሆን ይችላል::"[1]

ይህ ጥቅስ ዓይነተኛውን የሕዝብ ቁጥር ፅንሰ ሃሳብ በጽኑ የሚደግፉ ወገኖችን አቋም የሚገልጽ ሲሆን ለዚህ የሚያቀርቧቸው ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው::

1ኛ ይህ የዓይነታዊ የህዝብ ቁጥር ፍለጋ የሚለው አካሄድ ገም ብሎ የአካዳሚክ ጥያቄ አይደለም:: የወደፊቱን አቅጣጫዎችንና አሁን ያለንበትን ቅድመ ሁኔታ የሚያመለክት በጣም ጠቃሚ የሆኑ ጥያቄዎችን የምንጠይቅበት ነው:: ለምሳሌ ያክል፤ አሁን ያሉት ብሔራዊ የውሃ፣ የአፈር፣ የደን፣ የኃይል፣ ክምችቶች ምን ያህል ናቸው? እያንዳንዳቸው የወደፊት አቅርቦቶች በማይጨመርሱ መልኩ ስንት ሰው መደገፍ ይችላሉ? የአንድ ሀገርንስ የኑሮ ሁኔታ በምን መልኩ ሊቀይሩት ይችላሉ? እነዚህንና የመሳሰሉትን የወደፊቱን አቅጣጫ የሚያመለክቱ ጥያቄዎች እንድንጠይቅ ያደርገናል::

2ኛ ወደኋላም መለስ ብለን እስካሁን ድረስ ኑሮአችንን ለማሸነፍ ስንል አወቀንም ሆነ ሳናውቅ ምን ያህል የተፈጥሮ ስርዓት (ecosystem) አዛበተናል? የትኞቹን መልሰን መተካት እንችላለን? የትኞቹንስ ለዘለዓለም አጥተናቸዋል? በዚህስ ምክንያት የደረሱትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ቀውሶች በምን መልኩ ልንቋቋማቸው እንችላለን? የወደፊት ህልውናችንን ለማረጋገጥ ከአሁኑ ቅድሚያ የምንሰጣቸው ነገሮች ምንድናቸው? የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እንድናነሳም ያስገድደናል::

3ኛ ይህ ዓይነታዊ የሕዝብ ቁጥር የሚለው ፅንሰ ሃሳብ የሕዝብ ቁጥርን ብቻ የተመለከተ አይደለም:: ከዚሁ ጋር ተያይዘ ዓይነታዊ እርሻ፣ ዓይነታዊ ውሀ አጠቃቀም፣ ዓይነታዊ ኢንዱስትሪ፣ ዓይነታዊ ዲሞክራሲ፣ ከመሳሰሉት ፅንሰ ሃሳቦች ጋር በጽኑ የተሳሰረ ነው:: በአጠቃላይ ዓይነታዊ የሕዝብ ቁጥር የሚለው ፅንሰ ሃሳብ ተከታታይነት ያለው ልማት

[1] Wilcox, Boyd. 1996. "Optimum Population and the Search for Sustainability" p. 5, National Optimum Population Commission, Oregon, USA.

ከሚለው ዕንሰ ሃሳብ ጋር የተቆራኘ ነው። ሁለቱን አጣምሮ በማየት አቅማችንን አውቀን የማ,ያሞላነን አቅላጫ መከተል እንችላለን።

በአጠቃላይ የዓይነታዊ ሕገብ ቁጥር ደጋፊዎች የሚሉት፣ ይህን ፅንሰ ሃሳብ ተቀብለን ለሀገራችን አንድ ተቀባይነት ያለው የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ተከትለን ካልሄድን፣ ነገሮች ከኛ ቁጥጥር ወጥተው ህልውናችን ከፍተኛ አደጋ ላይ ይወድቃል ነው።

2.3 የዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር ፅንሰ ሃሳብ ተቃዋሚዎች

ይሁንና ይህንን የዓይነተኛ የሕገብ ቁጥር ፅንሰ ሃሳብ በጽኑ የሚቃወሙ ወገኖችም አሉ። እነዚህም በአብዛኛው አመለካከታቸው ሊብራል (liberal) የሆነ፣ ለህብረተሰባዊ መብት፣ በተለይ ለሴት መብት፣ በእጅጉ የሚከራከሩ ሰዎች ናቸው። ዓይነተኛ የሕዝብ ቁጥር የሚለውን ዕንሰ ሃሳብ ከዚህ በታች በተመለከተው መልክ ክፉኛ ይቃወሙታል። የክርክራቸው አቅላጫ እንደሚከተለው ነው።

1ኛ እስቲ መለስ ብለን የዕንሰ ሃሳቡን <u>ታሪካዊ</u> አመጣጥ እንመልከት። በክፍለ ዘመኑ መጀመሪያ አካባቢ የነበሩ ታዋቂ ኢኮኖሚስቶች የሕዝብ ቁጥር "ኢኮኖሚያዊ" በሆነ መልኩ እንዴት ተቆጣጥሮ፣ ተገቢው የሕዝብ ቁጥር ላይ መድረስ እንደሚቻል ሲያስቡና ሲመራመሩ ነበር። ይህም ልክ "ትርፋዊ" በሆነ መንገድ የፋብሪካ ዕቃ እንደማምረት ማለት ነው።

2ኛ የህገብ ብዛት ክርክር አጀማመሩ "የቁጥር" ጉዳይ ነበር። ቀስ በቀስ ግን ወደ "ጥራት" ጉዳይ እየተለወጠ መጣ። የዘረኝነትም ነገር ተቀላቀለበት። ከዚያም በ1920ዎቹና በ1930ዎቹ አካባቢ ዲሞክራሲያዊ የሚባሉ ሀገሮች ውስጥ በአመለካከትና በሰውነት ቅርጹ "የጠራ" ሰው ለማፍራት በሚል ሰበብ ጥናቶች (eugenic) ተጀመሩ። በአንዳንድ የህብረተሰቡ አካላት (በተለይም በድሆችና በአላስንክሎች) ላይ የተለያዩ ዓይነት መከራዎች ከፈታቸው ወጭ ሲደረግባቸው ቆየ። እነዚህም ጥናትና መከራዎች እንደ "ትርና" የማ,ታዩ ሰዎችን መካን ለማድረግ የታቀዱ ናቸው።

3ኛ አሁን በነባቱኛ ደረጃ እየተካሄደ ያለው የአካባቢ መበከልና መራቆት በቀጥተኛ መንገድ ከሕገብ ቁጥር መብዛት ጋር የተያያዘ አይደለም። ሁሉም ሰው እኩል ፍጆታ ስለሌለው እኩል አካባቢውን አይበክልም። እንደምሳሌ ቢጠቀስ፣ በኢንዱስትሪ የበለፀጉ ሀገሮች የዓለምን አንድ አምስተኛ (1/5) ሰው ይዘው የዓለምን ሶስት አራተኛ (3/4) ሃብት ፍጆታ አላቸው። ስለዚህም ለአካባቢያው መበከል ከድርሻቸው በላይ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ማለት ነው። ይህ የማ,ያሳየው ችግሩ የሕገብ ቁጥር ብዛት ሳይሆን የሃብት እኩል አለመከፋፈል ነው። በበለፀጉ ሀገሮች ውስጥም ቢሆን ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚያዊ መበላለጥ በመኖሩ የሀገሬው ሰው እኩል ፍጆታም ሆነ አካባቢውን የመበከል ድርሻ የለውም።

4ኛ ስለዚህ ይህ ዓይነታዊ የሕገብ ቁጥር የሚለው ዕንሰ ሃሳብ ትኩረታችንን አካባቢውን ከሚ,ያራቁት፣ ከሚበክሉ ዓቢይ ምክንያቶች ላይ እንዳናደርግ አድርጎናል። ማተኮር ያለብን ዓይነታዊ የሕገብ ቁጥር የሚለው ላይ ሳይሆን <u>አንደኛ</u>፣ መበከል የሚያስከትሉ ቴክኖሎጂዎች ላይ፣ <u>ሁለተኛ</u>፣ ፍጆታዎች ላይ፣ <u>ሶስተኛ</u>፣ ለአጭር ጊዜ ጥቅም ሲባል አላስፈላጊ የተፈጥሮ ሃብት በሚያባክኑ ብሎም በሚያጠፉ፣ የሰውን መብት በሚነፍጉ፣ በልማት ስም የማኅዲ ሆኖም ድሃ ገበሬዎችን በስደት ላይ በሚጥሉ (የእንጨት ቆረጣ፣ የማዕድን ቁፋሮ፣ የመሳሰሉት) አጥፊ ተግባሮች በማቆም ላይ ነው። መረዳት ያለብን፣

እነዘህ ሁሉ ድርጊቶች የመንግሥታትና የዓለም አቀፍ የገንዘብ ተቋማት ድጋፍ ያለውቸው አጥፊ ሂደቶች መሆናቸውን ነው::

5ኛ ይህ ዓይነተኛ የሕዝብ ቁጥር የሚለው ዕንሰ ሃሳብ የሕዝብ ብዛት ወይንም ስብጥር (composition) ይህን መምሰል አለበት ብሎ የሚጠቁመው ቁጥር ወይንም ዓይነት የለውም:: ስለዘህም ወረደም ወጣም የሀገርን ሕዝብ ቁጥርና ዓይነት ከሚወስነው የመንግሥት ወይንም የወጣው አካል አመለካከት ውጣው ለሆን አይችልም:: ስለዘህም ዞር ዞር የአንድ ህብረተሰብ ክፍል ከሌላው ያነሰ ተፈላጊነት አለው ብሎ መከራከሩ አይቀርም:: ለዓመታት ሲወጠ የነበሩ የስነ ሕዝብ ፖሊሲዎች የትኞቹን የህብረተሰብ ክፍሎች እንደ "ትርፍ" ያዩ አንደነበር እናውቃለን:: እነዘህ "ትርፍ" የሕዝብ ክፍሎች ደግሞ ወይ ድሆች ወይ አካለ ስንኩሎች አለበለዘያም ደግሞ አንዳንድ ተቀባይነት ባህርይ የሌላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ሆነው ይገኛሉ:: ስለዘህም ይህ የሕዝብ ቁጥር የሚለው ፈሊጥ ሃብት ያላቸውንና ፍጆታቸው በገዙት አካባቢውን በማበክሉ ህብረተሰብ ላይ ያነጣጠረ አይደለም::

6ኛ በተለይ ደግሞ፣ ዓይነታዊ የሕዝብ ቁጥር የሚያራምዱ፣ እስካሁን ድረስ ያወጡት የስነሕዝብ ፖሊሲዎች ከሁሉም በላይ ለጥቃት ያጋለጠት ምስኪን ሴቶችን ነው:: ብዙ ጊዜ አደገኛ የተባሉ የወሊድ መቆጣጠሪያዎች (እንደ Norplant) መፈተኛዎችና መሞከሪያዎች፣ ከስምምነታቸው ውጣው ወይንም ሳይነግሯቸው፣ የሚደረጉት በሴቶች ላይ ነው:: እነዘህ መከራዎች አንዳንድ ጊዜ መካን እንደሚያደርጉ ወይንም ደግሞ ሌሎች የጤና ጠንቅእንደሚያስከትሉ በቢታወቅም፣ መከራዎቹን ተከታትሎ ያስከተሉትን ጉዳት ለማከም የሚደረግ ጥረት የለም:: ይህ ዓይነታዊ የሕዝብ ቁጥር የሚለው ዕንሰ ሃሳብ የሴቶችን ሰብዓዊ መብት ከመግፈፍና ህልውናቸውን ለፖሊሲ አውጭዎች፣ ለአጭር ጊዜ ትርፍ ፈላጊዎች አንዳንዱም ለህክምና ባለሞያዎች አሳልፎ ከመስጠት ያለፈ አይደለም::

በመጨረሻም የዓይነተኛ ሕዝብ ቁጥር ጽንሰ-ሃሳብ ተቃዋሚዎች ከታች የተጻፈውን አንድ የዓይነተኛ ዕንሰ ሃሳብ ደጋፊ የተናገረውን እንደሚከተለው ይጠቅሳሉ::

> *"አንድ ድሃ ረሃብተኛን ማዳን ሌሎች ብዙ ድሃ ረሃብተኞችን እንዲያፈራ እድሉን መስጠት ነው"*[2]

2.4 ዓይነተኛ የሕዝብ ብዛት በሚለው ዕንሰ ሃሳብ ላይ ያለኝ አስተያየት

የእኔን አስተያየት፣ የዕንሰ ሃሳቡ ተቃዋሚዎች ካነሱዋቸው ሃሳቦች ከመጨረሻውበመጀመርና የኢትዮጵያንም ወቅታዊ ሁኔታ በምሳሌነት እያነሳሁ ከዚህ በታች ለማቅረብ እሞክራለሁ::

1ኛ ዓይነተኛ የሕዝብ ቁጥር የሚደግፉ ፖሊሲዎች የሴቶችን ሰብአዊ መብቶች ይጋፋሉ፣ ብሎም አደገኛ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ሴቶች ሳያውቁ እንዲወስዱ እያደረገ መካን አድርጓቸዋል የሚለው ክርክር በአንዳንድ ሀገሮች ላይ ይሰራ ይሆናል:: ይህም እጅግ በጣም መወገዝ የሚያስፈልገው ነው:: ሆኖም ይህ ጉዳይ በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙም ተቀባይነት ያለው አይመስለኝም:: ለዚህም ሁለት ዋና ምክንቶች አሉኝ::

[2] Bhapia, Rajani and Reisz, Tom. (ND) Enivironmentalism and Population Control in Population Control Quoted from Gareth Hardin - Major Figure in Population and Environment Movement.

ሀ) በ1993 ዓ.ም የወጣው· የኢትዮጵያ የስነ-ሕዝብ ፖሊሲ የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴ የሚጠቀሙ ያገቡ· ሴቶች በጊዜው ከነበረው· 4 በመቶ ወደ 44 በመቶ ማደግ ይገባዋል ይላል እንጂ ይህንን ዓይነት መከላከያ ዘዴ ይጠቀሙ· የሚለው· ነገር የለውም። ስለዚህም የኢትዮጵያን ሴቶች ሆነ ተብሎ አደገኛ የወሊድ መከላከያ ዘዴ እንዲወሰዱ የተደረገ ግፊት ያለ አይመስለኝም።

ለ) የወሊድ መቆጣጠሪያ ዘዴዎችን ከሚጠቀሙ· በጣም ጥቂት ሴቶች በአብዛኛው የሚጠቀሙት ክኒን (38 በመቶ) ወይንም መርፌ (46 በመቶ) ነው። አደገኛ የተባለውን Norplant የሚጠቀሙ· በአንፃሩ ጥቂት (5 በመቶ) ናቸው። የክኒንና የመርፌ ጉዳት ግልፅ ባይሆንም ጠቀሜታው· ሳይበልጥ አይቀርም ብዬ እገምታለሁ። ስለዚህ ዓይነታዊ የሕዝብ ቁጥር ለማምጣት በሚል ሰበብ በሴቶች ላይ ጉዳት ሊያደርሱ· የሚችሉ· እርምጃዎችን በፅኑ· ብቃወምም የሕዝብን ዕድገት ለመቀነስ የሚወስዱትን አግባባዊ የወሊድ ቁጥጥር ዘዴዎች በጎጂነት አልፈርጃቸውም።

2ኛ የዓይነተኛው· የሕዝብ ቁጥር ፅንሰ ሃሳብ እንደ «ትርፍ» የሚቆጠሩ ሰዎችን፣ በተለይ ድሆችንና አካለስንኩሎችን ለማስወገድ የሚደረግ ሴራ ነው· የሚለው· በመጠኑም ቢሆን እውነታ ያለው· አባባል ነው· ብዬ እገምታለሁ። የሚወገዝም ነው። ሆኖም ኢትዮጵያን በተመለከተ በተቀናጀ መንገድ ድሃዎችንና አካለ ስንኩሎችን የሚያስወግድ ሂደት የታየ አይመስለኝም። እንዲያውም አሁን ያለው 8 በመቶ የሚሆነው· የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚወስደው· የህብረተሰብ ክፍል በገቢም ሆነ በትምህርት ደረጃው· ድሃ ተብለው ከሚገመቱት የተሻሉ· ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ በሀገሪቷ የወሊድ ቁጥጥር ማነስ የተነሳ የሚጎዱት ወይንም በሞት የሚለዩት ድሃውና አቅመ ደካማው· መሆኑ· አይካድም። ይሁን እንጂ የጉዳታቸው· መነሻ የመንግሥት ፖሊሲዎች ሳይሆኑ· ማልቱስ (Malthus) እንደሚለው· ጦርነት፣ በሽታ፣ ድርቅ፣ የመሳሰሉት ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ናቸው። እንግዲህ በወሊድ መቆጣጠሪያ መንገድ መቀነስ ያልቻለ ሕዝብ፣ ከሀገሪቱ አቅም በላይ ከሆነ፤ ማልቱስ የሚለው· ነገር ሊመጣ ነው። ኢትዮጵያ ከዚህ ክፍል የተፈረጀች ይመስላል።

3ኛ ሀገር ሁሉ· ወይንም ሰው ሁሉ· እኩል ፍጆታ የለውም፣ ስለዚህም የተፈጥሮ ሃብት በእኩል እያባከነ ወይም እየበከለ አይደለም፤ ያበለፀገ· ሀገሮች ሕዝቦች ከድርሻቸው· በላይ የተፈጥሮ ሃብትን እየተጠቀሙና እያጠፉ· ናቸው። ችግሩ ይህ ነው· እንጂ በእርግጥ የሕዝብ ቁጥር በዝቶ መፍትሔው· ዓይነታዊ ቁጥር መፈለግ ሆኖ አይደለም፣ የሚለው· አባባል እውነትነት አለው። የኢትዮጵያም ሁኔታ ይህንን አባባል በመጠኑ· የሚደግፍበት መንገድ አለ፤ ለምሳሌ፤ በኢኮኖሚ ደረጃው· የላይኛው· 10 በመቶ የሆነው· የኢትዮጵያ ሕዝብ የገቢ ድርሻው· 34 በመቶ ሲሆን፣ የታችኛው· 10 በመቶ ድርሻው· 3 በመቶ ብቻ ነው።[3] ቢሆንም የሕዝብ እኩልነትን መ·ሉ· ለመ·ሉ· ማምጣት ስለማይቻል ዓይነተኛው· የሕዝብ ቁጥር የሚለው· አስተሳሰብ የኋላ የኋላ በሃብትና በፍጆታ የተለያዩትን የአንድ ሀገር ሕዝብ በመጠኑም ቢሆን የሚያቀራርብ ይመስለኛል።

4ኛ ዓይነተኛው· የሕዝብ ቁጥር ፅንሰ ሃሳብ «ከቁጥር» ወደ «ዓይነት» የመለወጡ· ጉዳይና በሰበቡም በአእምሮና በቅርጽ የተለዩ የህብረተሰብ አካልን ለመፍጠር የተደረገው· መከራ ከተቋረጠ ወደ 70 ዓመት ገደማ ቢሆነውም እንደገና ሊመጣ ይችላል ብሎ መጠርጠሩ አይከፋም። በኢትዮጵያ እንዲህ ዓይነት ሂደት የመምጣቱ ዕድል በጣም አነስተኛ ቢሆንም በሌላ ሀገር የመከሰቱ አጋጣሚ ትንሽም ቢሆን በእጅጉ· የሚያሳሰብ ነገር ነው። በማንኛውም መልኩ· በጽኑ· መቃወም የሚገባን ነገር ነው።

---

[3] World Development Report, 2001.

ስለዘህ በእኔ ግምት ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር የሚለው ፅንሰ ሃሳብ መጥፎ መስሎ አይታየኝም። ይህ የሕዝብ ቁጥር አንድ ማጂክ ቁጥር ሳይሆን አሁን ያለንበትን ሁኔታ አይቶ የወደፊቱ አቅጣጫ ምን መሆን እንዳለበት የሚጠቁም ነገር መሆን አለበት። በተለይ ደግሞ የሕዝብን ቁጥር በመቀነስ ላይ ያተኮረ ብቻ ሳይሆን አንድ ሀገር ያለውን የተፈጥሮም ሆነ ሰው ሰራሽ ሃብት በማያሟጥጥ መልኩ ዘለቄታዊና «ጥሩ» የኑሮ ደረጃ የሚያመጣ አካሄድንም ያጠቃለለ መሆን አለበት። ይህንን ሃሳብ ከተቀበልን፣ በኔ ግምት አግባባዊ የሕዝብ ቁጥር የሚለው ፅንሰ ሃሳብ የሚከተሉት ዋና ዋና ጥቅሞች ይኖሩታል እላለሁ።

ሀ. አሁን ያለንበትን ሁኔታ ተረድተን የወደፊቱን አቅጣጫ እንድንገምት ይረዳናል፣

ለ. አሁን በእጃችን ያሉት የተፈጥሮ ሃብቶች (ውሃ፣ አፈር፣ ደን፣ እምቅ ኃይል...) ምን ያህል እንደሆኑ እንድንመረምር ያደርገናል። ምንስ ያህሉን እየተጠቀምን እንዳለን ለማወቅ ይረዳናል፣

ሐ. ያሉን ሃብቶች እየተሟጠጡ በማይሄዱበት መንገድ እንዴት ሊጠቅሙን እንደሚችሉ ሊጠቁመን ይችላል፣

መ. እስካሁን ድረስ ስናባክናቸው የነበሩና መተካት ያለባቸው ነገሮች ምን እንደሆኑ እንድናውቅ ያደርገናል፣

ሠ. በሕዝብ ብዛትና ባሉን የተፈጥሮ ሃብቶች መካከል ያሉትን የቅራኔዎች ዓይነትና መጠን ለማወቅ ይረዳናል፣

ረ. ከተፈጥሮ ሃብት ውጭ የዲሞክራሲያዊና የመልካም አስተዳደር ሂደታችንንም ሊያመለክተን ይችላል፣

ስለዘህ በዘህ ጽሁፌ ላሳይ የምሞክረው ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር የሚለው ፅንሰ ሃሳብ ወደ ተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም እንደሚያመራን ነው። የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም በበኩሉ ወደ ኑሮ ደረጃ አመልካቾች ይወስደናል። በመጨረሻም የጥሩ ኑሮ ደረጃ አመልካቾች ደግሞ ወደ ሕዝብ ቁጥር ብለውም ወደ ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር ሊጠቁመን እንደሚችል ነው። ይህንንም ለማድረግ መረጃዎቼን ከ Living Planet Report (2004) እወስዳለሁ። በጽሁፉ ውስጥ የሚገኘው መረጃ በአብዛኛው በአውሮፓ አቆጣጠር የ2001 ዓመተ ምህረት ነው።

በጽሁፉ የዓለም ሀገሮች በሶስት ቦታ ተከፍለዋል፤ 1) ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው የሚባሉት በቁጥር 61 የሚሆኑ፣ 2) መካከለኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ በቁጥር 93 የሚሆኑና፣ 3) ከፍተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ በቁጥር 54 የሚሆኑ ይገኙበታል። የእነዚህ መረጃ በአማካኝ ነፍስ ወከፍ ይለካል። በተጨማሪም የኢትዮጵያን ሁኔታ ለብቻ የሚያሳይ ለማነፃፀር እንዲረዳ ሆኖ ቀርቧል።

3. የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት አይነተኛው የሕዝብ ቁጥር የሚለው አካሄድ፣ በየአካባቢያችን ያሉት የተፈጥሮ ሃብቶች ምን ያህል እንደሆኑና ምን ያህሉን ደግሞ እየተጠቀምንባቸው እንዳለን እንድናውቅ ይረዳናል። በዘህ ጽሁፍ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም የሚለካው የአንድ ሀገር ሕዝብ ያለውን ዕውቀትና ቴክኖሎጂ በመጠቀም፣ ምርት አምርቶ፣ ለፍጆታ ለማዋል በያለበት እየተጠቀመበት ባለው በመሬት፣ በውሀ ወይም በእምቅ ኃይል ስፋት ነው።

በዘህም መሰረት ከዘህ ቀጥሎ ኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን የተፈጥሮ ሃብቶች (ማለትም የመሬት፣ የውሀ፣ የደንና የእምቅ ኃይል) ምን ያህሉን እየተጠቀምንባቸው መሆኑን፤ ከሌሎች አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ገቢ አላቸው ከተባሉት ጋር እያወዳደርኩ በአጭሩ አሳያለሁ። ይህም ሲሆን ያሉትን የተፈጥሮ ሃብት አወጣጥ ለመጠቀም የሚያስፈልገንትን የትምህርትና የቴክኖሎጂ ደረጃ ወይንም ደግሞ የመንግሥት መልካም አስተዳደርና የሕገበኑን ቀና አመለካከት ሳይሬሕምር ነው። እነዚህ እያንዳንዳቸው ራሳቸውን የቻሉ ርዕሶች ስለሆኑ በዘህ ጽሁፌ ውስጥ አልተጠቃለሉም።

3.1 የመሬት ሃብት

ስዕል አንድ የአጠቃላይ መሬት (ማለትም የእርሻ፣ የግጦሽና የአሣ ቦታን) አጠቃቀም
ያሳያል። በዝቅተኛ የገቢ ደረጃ ውስጥ በተመደቡ ሀገሮች ምርታቸውን ለማምረት በነ
ወስጥ 0.8 ሄክታር ቦታ ሲጠቀሙ መካከለኛ ገቢ ያላቸው 1.9 ሄክታር፣ ከፍተኛ ገቢ ያላቸ
ሀገሮች 6.4 ሄክታር፣ ይጠቀማሉ። በኢትዮጵያ 0.7 ሄክታር ይጠቀማሉ።

ይህ የሚያሳየው ምርት አምርቶ ለመጠቀም ሃብታም ሀገሮች በአማካኝ ነፍስ ወከፍ በ
የኢትዮጵያን 9 ጊዜ እየተጠቀሙ እንዳለ ነው። ዝቅተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ ሀገራትን
እንኳን በአማካኝ የነፍስ ወከፍ ቦታ ስፋት ከኢትዮጵያ በትንሹም ቢሆን የበለጠ አጠቃላይ
የመሬት ቦታ እየተጠቀሙ እንደሆነ እንረዳለን።



ስዕል 2 የሚያሳየው የእርሻን መሬት አጠቃቀም ነው። በዚህ መሰረት ምርትን አምርቶ
ለመጠቀም ነፍስ ወከፍ ገቢ ያላቸው ሀገሮች የኢትዮጵያን ወደ ሶስት እጅ ግድም የእርሻ ቦታ
እየተጠቀሙ እንዳለ ይታያል። ዝቅተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉትም እንደዚሁ ከኢትዮጵያ
ከፍ ብ ቦታ በላይ እየተጠቀሙ እንደሆነ ስዕሉ ያሳየናል።

ስዕል 3 የሚያሳየው የግጦሽ ቦታ አጠቃቀም ሲሆን ሃብታም የሚባሉት ሀገሮች በአማካኝ ነፍስ ወከፍ 0.26 ሄክታር መሬት እንደሚጠቀሙ ነው። ይህም ኢትዮጵያዊያን በነፍስ ወከፍ ለግጦሽ ከሚጠቀሙበት 0.08 ሄክታር ቦታ በሦስት ጊዜ እንደሚበልጥ ያሳያል። ሆኖም ኢትዮጵያውያን የሚጠቀሙበት ቦታ መሃከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገሮች በእጥፍ ያህል ቢያንስም አንስተኛ ገቢ ካላቸው ግን ከእጥፍ በላይ ይበልጣል።



ስዕል 4 የሚያሳየው የደን ቦታን አጠቃቀም ነው። ይህን በተመለከተ መካከለኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ ሀገሮች በአማካኝ በነፍስ ወከፍ የሚጠቀሙት ቦታ ከሁሉም በላይ ነው። ይህም ከኢትዮጵያ ነፍስ ወከፍ አጠቃቀም ጋር ሲወዳደር በአራት እጥፍ እንደሚበልጥ ይታያል።



ስዕል 5 የሚያሳየው የእሣ ምርትን ለማካሄድ አሁን የሚያስፈልገውን የነፍስ ወከፍ ቦታ ነው። ከፍተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ ሀገሮች ከሌሎች ሀገሮች በተለይ ከኢትዮጵያ ጋር ሲወዳደር በጣም በከፍተኛ ደረጃ እንደሚበልጡ ይታያል። የእሣ ምርት በሀገራችን ይህ ነው የሚባል ቦታ የለውም ለማለት ያስደፍራል።



በአጠቃላይ የመሬትን ሃብት አጠቃቀም በተመለከተ ከፍተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ ሀገሮች ከሌሎች አገሮች አ.ትዮጵያን ጨምሮ በእጅ እንደሚበልጠ ነው። ይህም በስተመጨረሻ ለማሳየት እንደሞከርኩት በኮሮ ደረጃ ላይ ብሎም በሕዝብ ዕድገት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ እንዳለው ነው።

3.2 የእምቅ ኃይል ሃብት

ስዕል 6 የሚያሳየው አጠቃላይ የእምቅ ኃይል (ማለትም የካርቦን ዳይ አክሳይድ፣ የማገዶ እንጨት፣ የኑክሌርና የሃይድሮ-ኤሌክትሪክ) አጠቃቀምን ነው። በዚህ መሰረት የአጠቃላይ እምቅ ኃይልን ለመጠቀም ሀብታም የተባሉት ሀገሮች አማካኝ ነፍስ ወከፍ 4 ሄክታር ቦታ ሲጠቀሙ እንደ አ.ትዮጵያ ያሉ ከድሃ የሚመደቡ ሀገሮች ግን 0.3 ሄክታር ቦታ ብቻ እንደሚጠቀሙ ይታያል። ይህም ማለት ከአንድ ሽህ ሰላሣ ሦስት በሙቱ ጊዜ በላይ ማለት ነው። በዚህ ረገድ መሃከለኛ ገቢ አላቸው የሚባሉትም ሀገሮች ከፍተኛ ገቢ ካላቸው በእጅ እንደሚያንሱ ይታያል።



ስዕል 7 የአጠቃላይ ካርቦንዳይኦክሳይድ አወጣጥ emission ያሳያል። በስዕሉ መሰረት ሃብታም የተባሉት ሀገሮች ይህንን በተመለከተ ከሌሎች ጋር ሲወዳደሩ ከፍተኛ የሆነ ቦታ እየተጠቀሙ እንደሆነ በግልጽ ይታያል። በአንጻሩ ድሃ የተባሉት ሀገሮች ኢትዮጵያን ጨምሮ የካርቦንዳይኦክሳይድ አወጣጣቸው እጅግ በጣም አነስተኛ ነው።



ስዕል 8 ከደን እንጨት የሚገኝ ኃይልን ለማውጣት በሥራ ላይ እየዋለ ያለውን የነፍስ ወከፍ የቦታ ስፋት ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ እያንዳንዱ ሰው በአማካኝ 0.27 ሄክታር ቦታ ይጠቀማል። ይህም ሃብታም የሚባሉ ሀገሮች በነፍስ ወከፍ ከሚጠቀሙበት አንድ ሺህ ሦስት መቶ ሀምሳ በመቶ ሲሆን የዚህ እንደምታ የሆነ የዛፍ ጭፍጨፋ በአገራችን እየተካሄደ መሆኑን ነው።



ስዕል 9 የሚያሳየው የኑክሌር ኃይል ለማመንጨት እየተፈለገ ያለውን የቦታ ስፋት መጠን ነው። በዚህ መሰረት የበለጸገ ሀገሮች በአማካኝ በነፍስ ወከፍ 0.49 ሄክታር ሲጠቀሙ ዝቅተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ ሀገሮች ኑክሌር ኃይልን ለማውጣት የሚጠቀሙበት ምንም ቦታ አለመሆኑን ያሳያል።



በአጠቃላይ አነጋገር ዕምቅ ኃይልን አውጥቶ በሥራ ላይ ለማዋል የበለፀጉ ሀገሮች በነፍስ ወከፍ እየተጠቀሙበት ያለው ቦታ ከድሃ ሀገሮች ጋር ሲወዳደር እጅግ ከፍተኛ ነው። ይህም ወደተሻለ ኑሮ ደረጃ እየወሰዳቸው መሆኑን ከታች እንመለከታለን።

3.3 የውሀ ሃብት

ስዕል 10 እንደሚያሳየው የውሀ ኃይልን ለማመንጨት ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ሀገሮች በአማካኝ ነፍስ ወከፍ 0.01 ሄክታር ቦታ አገልግሎት ላይ ሲያውሉ ሌሎቹ (ኢትዮጵያን ጨምሮ) ከቁጥር የሚገባ ቦታ አይጠቀሙም።



ስዕል 11 የውሀ ሃብት ፍጆታን ያሳያል። ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ሀገሮች በአማካኝ ነፍስ ወከፍ 1.03 ኪዩቢክ ሜትር ውሀ በየዓመቱ ይጠቀማሉ። ይህም ማለት ኢትዮጵያ ከምትጠቀመው 0.04 ኪዩቢክ ሜትር 25 ጊዜ በላይ መሆኑ ነው። ዝቅተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ ሀገሮች እንኳን ከኢትዮጵያ 14 ጊዜ ግድም እየተጠቀሙ እንደሆነ ይታያል።



ስዕል 12 የሚያሳየው ተከማችቶ የሚገኘውን የውሀ ሃብት መጠን ነው። በኢትዮጵያ የተከማችው የውሀ ሃብት በነፍስ ወከፍ 29 ሺህ ኪዩቢክ ሜትር ውሀ ሊደርስ ይችላል። ይህም ማለት በበለጸገ ሀገሮች ካለው ወደ 3 ገዜ ሲሆን በዝቅተኛ ገቢ ላይ ካሉ ሀገሮች ካለው ወደ 5 እጅ ነው። ይህ የሚያሳየው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የውሀ ክምችት ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሲወዳደር በጣም ከፍተኛ ቢሆንም ውሀውን አውጥቶ መጠቀሙ ላይ ግን ከሁሉም ዝቅተኛ መሆኑን ነው።



ስዕል 13 የሚያሳየው በመንገድ፤ በሩብራካ፣ በአጠቃላይ ከአርሻ ውጭ ላሉ ግንባታዎች በሥራ ላይ እየዋለ ያለውን የቦታ ስፋት ነው። በዚሁ መሰረት የበለጸገ ሀገሮች በአማካኝ ነፍስ ወከፍ 0.23 ሄክታር ቦታ ሲጠቀሙ ኢትዮጵያ በአንጻሩ 0.04 ሄክታር ቦታ ብቻ እየተጠቀመች መሆኑ ነው። ይህም የበለጸገ አገሮች በአማካኝ ነፍስ ወከፍ የሚጠቀሙበት አንድ ስድስተኛ መሆኑ ነው።



በአጠቃላይ ከላይ እንዳሳየሁት አምርቶ ለፍጆታ ለማቅረብ ሲባል በበለፀጉ ሀገሮች በጥቅም ላይ እየዋለ ያለት ቦታዎች ድሃ ከሚባሉ ሀገሮች ሲወዳደር እጅግ ከፍተኛ ነው:: በመሆኑም የኑሮ ደረጃ መጠን በሚመለከት በበለፀጉ ሀገሮችና ድሃ በሚባሉ ሀገሮች መሃከል ሌላ ልዩነት እንዳለ በሚቀጥለው ምዕራፍ አሳያለሁ::

4. የኑሮ ደረጃ አመልካቾች

ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት የጽሁፌ ሃሳብ የተፈጥሮ ንብትን በቅጡ መጠቀም ወደ ተሻለ የኑሮ ደረጃ ያመራል ሲሆን ይህም ደግሞ በተራው ወደ ዓይነተኛው ሕገብብ ቱሪዝም ይወስደናል የማል ነው:: ከዚህ በታች ባለው ዕሁፍ በሚለኒዬም የልማት እቅድ (Millennium Development Goals) ውስጥ ያሉትን የኑሮ ደረጃ መስፈርቶች በመጠቀም ዝቅተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ ገቢ ያላቸውንና ኢትዮጵያን ጨምሮ በሌሎች መካከል ያለውን ልዩነት ለማሳየት እሞክራለሁ::



4.1 የገቢ ስርጭት

ስዕል 14 የሚያሳየው ሀገራዊ የገቢ ስርጭት ነው። በተለይም በኢኮኖሚው እርከን በእያንዳንዱ ሀገር የታችኛው 25 በመቶ ያላቸውን ሀገራዊ የገቢ ድርሻ ነው። በዚሁ መሰረት ከፍተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ ሀገሮች በኢኮኖሚ እርከን የታችኛው 25 በመቶ የሆኑት በአማካኝ የጠቅላላ ገቢውን 7.4 በመቶ ድርሻ አላቸው። በሌላ መንገድ በኢትዮጵያ ይኸው የህብረተሰብ ክፍል ያላቸው የገቢ ድርሻ 2.4 በመቶ ሲሆን ዝቅተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ ደግሞ በአማካኝ 5.8 በመቶ ድርሻ አላቸው። ይህ የሚያሳየን ምንም እንኳን ሃብታም የሚባሉ ሀገሮች ውስጥም የገቢ አለመመጣጠን ቢኖርም በኢትዮጵያ እየታየ ያለው የገቢ ስርጭት በእጅጉ የተዛባ መሆኑን ነው።

4.2 ሕፃናት የተመጣጠነ ምግብ አለማግኘት

ስዕል 15 የሚያሳየው ከአምስት ዓመት በታች ከሆኑ ህፃናት ስንቱ ያህል የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት እንደማይችሉ ነው። በዚህ መሰረት በኢትዮጵያ ውስጥ 47 በመቶ የሚሆኑት ህፃናት የተመጣጠነ ምግብ እንደማያገኙ ሲታይ ሃብታም በሚባሉ ሀገሮች ውስጥ በአማካኝ 4 በመቶ አያገኙም። ይህ ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሁኔታ ሃብታም ከሚባሉት ሀገሮች ጋር ሲወዳደር በ12 እጅ ግድም ያንሳል ማለት ነው። ድሃ የሚባሉት ሀገሮች እንኳን ከኢትዮጵያ በግማሽ ያህል የተሻለ ሁኔታ ላይ ይገኛሉ።



4.3 የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት የሚከታተሉ

ስዕል 16 የሚያሳየው ዕድሜአቸው የሚፈቅድላቸው የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ገብተው የሚማሩትን ወጣቶች ብዛት ነው። መካከለኛና ከፍተኛ ገቢ አላቸው በሚባሉ ሀገሮች ውስጥ በአማካኝ 86 እና 84 በመቶ የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርትን የሚከታተሉ ሲሆን በኢትዮጵያ 24 በመቶ ብቻ ናቸው። በሌላ አነጋገር ተጨማሪ 76 በመቶ በዕድሜአቸው መሰረት ትምህርት መከታተል ሲገባቸው በተለያዩ ምክንያቶች ይህ እየሆነ አይደለም። ዝቅተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉት ሀገሮች እንኳ እድሜአቸው ፈቅዶ የትምህርት ዕድል የሚያገኙት ወጣቶች ብዛት በአማካኝ ከኢትዮጵያ ከእጥፍ በላይ ይበልጣሉ።



4.4 ሴቶችና ወንዶች ትምህርት ስለ መከታተል

ስዕል 17 የሚያሳየው አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በመከታተል ሁኔታ በሴቶችና በወንዶች መሃከል ያለውን ልዩነት ነው። በበለፀጉ ሀገሮች መሃከል በአማካኝ ለእያንዳንዱ 102 ሴት ተማሪ 100 ወንድ ተማሪ ሲኖር፣ በኢትዮጵያ ሁኔታ ግን ለእያንዳንዱ 88 ሴት ተማሪ 100 ወንድ ተማሪ እንደሚኖር ነው። ይህም ማለት በኢትዮጵያ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን በተመለከተ የሴቶች ተማሪዎች ቁጥር ከወንዶቹ ያነሰ መሆኑን ነው። ሆኖም የኢትዮጵያ ሁኔታ ከሌሎቹ ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው አማካኝ ሁኔታ በመጠኑ የተሻለ መሆኑ ይታያል።



4.5 የህፃናት ህልፈት

ስዕል 18 የሚያሳየው ከተወለዱ አምስት ዓመት ሳይሞላቸው በተለያዩ ምክንያቶች ለህልፈት የሚዳረጉትን ህፃናት ብዛት ነው። በእኔ ግምት ይህ መስፈርት ከሌሎች የኑሮ ደረጃ መስፈርት በሙሉ የበለጠ ጠቃሚነት አለው። ምክንያቱም መስፈርቱ የሚያመለክተው በአንድ ሀገር ውስጥ ያለውን የጤና ሁኔታ ብቻ ሳይሆን የኢኮኖሚንና የእውቀት ደረጃ ጭምርም ስለሆነ ነው። በኢትዮጵያ ከሚወለዱ 1000 ህፃናት መሃከል 172ቱ አምስት አመት

ሳይሞላቸው ህይወታቸው ያልፋል፤ ከፍተኛ ገቢ ባላቸው ሀገሮች ይህ ቁጥር 6፤ መካከለኛ ገቢ ባላቸው ሀገሮች 34 ነው።



4.6 በወሊድ ላይ ስለሚሞቱ እናቶች

በወሊድ ምክንያት የሚሞቱ እናቶች መጠን ያንድን ሀገር የኑሮ ደረጃ በእጅጉ ይጠቁማል። ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ሀገሮች ችግሩን ሙሉ በሙሉ ማስወገድ ደረጃ ላይ የደረሱ ይመስላል። በኢትዮጵያ ሁኔታ ግን አሁንም ከፍተኛ ችግር ነው። ስዕል 19 እንደሚያሳየው ከአያንዳንዱ 100000 ወላድ ሴቶች 1800 በወሊድ ላይ እንዳሉ ይሞታሉ። በሌላ አነጋገር 2% የሚሆኑ ማለት ነው። ከፍተኛ ገቢ ባላቸው ሀገሮች ይህ ችግር ሙሉ ለሙሉ ተወግዷል ባያስኝም እጅግ በጣም ትንሽ ነው ለማለት ያስደፍራል።



4.7 በጤና ባለሙያዎች እርዳታ የሚወለዱ

ስዕል 20 እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ ውስጥ በጤና ባለሙያዎች እርዳታ እየተወለዱ ያሉ የህጻናት ብዛት 10 በመቶ ብቻ ናቸው። ማለትም 90 በመቶ በየቤቱ በቂ የጤና ባለሙያዎች

እርዳታ ሳያገኙ የሚወለዱ ናቸው። ይህም በልጆቹ እድገትና የወደፊት ኑሮ ላይ አስጊ ሁኔታ መፍጠሩ አይቀርም። በአንፃሩ ከፍተኛ ገቢ ባላቸው ሀገሮች ውስጥ የሚወለዱ ህጻናት ሙሉ በሙሉ የጤና ባለሙያዎች እርዳታ እንደሚያገኙ ይታያል።

ዝቅተኛ ገቢ አላቸው በሚባሉ ሀገሮችም እንኳ በባለሙያዎች እርዳታ የሚወለዱት ህጻናት ብዛት ከኢትዮጵያ ከ4 እጅ በላይ እንደሚበልጥ ይታያል።



4.8 የሕዝብ ቁጥር እድገት መጣኔ

ስዕል 21 የሚያሳየው በየዓመቱ የህዝብ ቁጥር በምን ያህል እጅ እየጨመረ እንዳለ ነው። በዚሁ መሰረት የኢትዮጵያ ሕዝብ በየአመቱ በ2.8ጎ እያደገ መሆኑ ይታያል። በሌላ በኩል ደግሞ በበለፀጉ ሀገሮች በአማካኝ 0.6ጎ እድገት ይታያል። ይህም ማለት የኢትዮጵያ ሕዝብ ከበለፀጉ ሀገሮች ሕዝቦች ጋር ሲወዳደር በአምስት እጥፍ ፍጥነት እያደገ ነው ማለት ነው። በሌላ አነጋገር ኢትዮጵያም ሆነች ሌሎች ድሃ የሚባሉ ሀገሮች በያዙት የሕዝብ ዕድገት ፍጥነት ከሄዱ የሕዝባቸውን ቁጥር በእጥፍ ለመጨመር ከ20 እስከ 25 ዓመት ብቻ ይወስድባቸዋል።



4.9 የወሊድ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም

በዚህ ጽሁፍ የወሊድ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም የሚያመለክተው በመውለድ እድሜ በጋብቻ ላይ ያሉትን ሴቶች ብዛት ብቻ ነው። በዚሁም መሰረት ስዕል 22 እንደሚያሳየው በኢትዮጵያ የወሊድ መቆጣጠሪያ እየተጠቀሙ ያሉ ሴቶች በአማካኝ 8ን ብቻ ናቸው። ይህም ከበለፀጉ ሀገሮች አማካኝ 70.5ን ጋር ሲወዳደር በ9 እጅ እንደሚያንስ ነው። ዝቅተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉ ሀገሮች እንኳ የተጠቃሚ ሴቶች ቁጥር ከኢትዮጵያ ከ3 እጅ በላይ እንደሚበልጥ ይታያል።



5. በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም፣ በኑሮ ደረጃና በሕዝብ ቁጥር እድገት መሃከል ያሉ ግንኙነቶች

ከዚህ በፊት እንደገለጽነው የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ወደ ጥሩ የኑሮ ደረጃ ያደርሳል። ይህ ደግሞ ቀስ በቀስ ወደ ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር ሊያመራ ይችላል። ከዚህ በታች የተዛፈው ይህንኑ ለማሳየት የተደረገ መከራ ነው።

5.1 በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና በኑሮ ደረጃ መካከል ያለ ግንኙነት

በዚህ ክፍል በአጠቃላይ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና በኑሮ ደረጃ መስፈርቶች መካከል ያለውን ግንኙነት አሳያለሁ። በዚሁ መሰረት ከሠንጠረዥ 1 የሚከተሉትን ዋና ዋና ግንኙነቶች መረዳት ይቻላል።

- በአጠቃላይ የመሬት ቦታ አጠቃቀምና በገቢ ድርሻ መሃከል ጠንካራ የሆነ አሎንታዊ ግንኙነት አለ። ይኸውም ማለት በአንድ ሀገር የቦታ አጠቃቀም በጨመረ ቁጥር በገቢ ክፍፍል ያለው መሻሻል በመጠኑም ቢሆን ይስተካከላል ማለት ነው።
- እንዲሁም በአጠቃላይ የቦታ አጠቃቀምና በሴቶችና በወንዶች ትምህርት መከታተል መሃከል ተመሳሳይ የሆነ ግንኙነት አለ። በሌላ አነጋገር የቦታ አጠቃቀም በጨመረ ቁጥር የሴቶችና የወንዶች በአዕምሮአዊ ትምህርት የመማር ዕድል እየጨመረ ይሄዳል ማለት ነው።

- በአንዛሩ በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና በህዛናትና በወላድ እናት አልፈት መካከል እጅግ በጣም ጠንካራ የሆነ አሉታዊ ግንኙነት አለ። ይህም ማለት የተፈጥሮ ሃብትን በበለጠ እየተጠቀምን ስንሄድ የህዛናትንና በወሊድ ላይ ያሉ የእናቶች አልፈትን በከፍተኛ ደረጃ መቀነስ ይቻላል ማለት ነው። እንግዲህ ይህ በአጠቃላይ የሚያሳየን የተፈጥሮ ሃብትን በትክክል መጠቀም የአንድን ሃገር የኢኮኖሚያዊም ሆነ የጤና ዕድገትን እያሻሻለ እንደሚሄድ ነው።

5.2 በኑሮ ደረጃና በሕዝብ ዕድገት መሃከል ያለ ግንኙነት

የተፈጥሮ ሃብትን መጠቀም የኑሮ ደረጃን በእጅጉ እንደሚያሳድገው ሁሉ የኑሮ ደረጃ ከፍ ማለት በዘለቀለ የሕዝብ ዕድገት ፍጥነት በጣም እንደሚቀንስ ይታያል። ሠንጠረዥ 2 የሚያሳየው ይህንኑ ግንኙነት ሲሆን ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተሉት ናቸው።

- በኢኮኖሚ ዕርከን የበታቾቹ 25 በመቶ ያለት የገቢ ድርሻቸው እየጨመረ በመጣ ቁጥር የአንድ ሀገር ሕዝብ ዕድገት ፍጥነት እየቀነሰ ይሄዳል።
- በአንድ ሀገር ሕዝብ ከአምስት ዓመት በታች ያሉ ህዛናት የተመጣጠነ ምግብ ማግኘት የወሊድ ቁጥጥር ከሚወስዱ ሴቶች ብዛት ጋር አዎንታዊ ግንኙነት አለው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ የሕዝብ ቁጥር የመቀነስ አዝማሚያም ያሳያል።
- ሴቶችና ወንዶች በእኩልነት ትምህርት እየተከታተሉ በሄዱ ቁጥር የሕዝብ ዕድገት ፍጥነት በጣም እየቀነሰ ይሄዳል። ብሎም የሕዝብ ብዛት ሊቀንስም ይችላል
- አንደኛ ክፍል የሚገቡ ህዛናት ቁጥር እየጨመረ ሲመጣ የወሊዱ መቆጣጠሪያ አጠቃቀም እየጨመረ ይመጣል። ከዚያም የሕዝብ ቁጥር ቅነሳ አዝማሚያ ይታያል።
- በጤና ባለሙያዎች ዕርዳታ የሚወለዱ ህዛናት መጠን እየጨመረ ሲመጣ ዓመታዊ የሕዝብ ዕድገት መጠን በትንሹም ቢሆን እየቀነሰ የመሄድ አዝማሚያ ያሳያል።

ከላይ ለማስረዳት እንደሞከርኩት ሁሉ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም የኑሮን ደረጃ እንደሚያሻሽለው ሁሉ፣ የኑሮ ደረጃ እየተሻሻለ በመጣ ቁጥር የሕዝብ ዕድገትን እየገታው ይመጣል ማለት ነው።

ሠንጠረዥ 1፡ በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና በኑሮ ደረጃ አመልካቾች መሃከል ያለው ግንኙነት

የተፈጥሮ ሃብት ዓይነት	የድሃ አገሮች ገቢ ድርሻ	የሕፃናት ተመጣጣኝ ምግብ አለመብላት	የሴቶችና ወንዶች በእኩልነት የመማር ሁኔታ	የሕፃናት እልፈት	በወሊድ ላይ እልፈት
ጠቅላላ ቦታ	.286**	-.558**	.265**	-.602**	-.532**
ጠቅላላ ሃይል	.213*	-.517**	.202*	-.557**	-.501**
የከርሰምድር አነሳደድ አመጣጥ	.186*	-.517**	.180*	-.558**	-.516**
ጠቅላላ ውሃ	.273**	-.174*	NS	-.201*	-.377**

** በጣም ጠንከራ ደረጃ .01

* ጠንከራ ደረጃ .05

ሠንጠረዥ 2፡ በኑሮ ደረጃና በሕዝብ ቁጥር እድገት መሃከል ያለ ግንኙነት

	የሕዝብ ቁጥር ዕድገት	የወሊድ መቆጣጠሪያ መጠቀም	የሕዝብ ብዛት
የኢኮኖሚ ድርሻ	-.445**	.067	.101
የተመጣጠነ ምግብ የማያገኙ ህፃናት	.539**	.635	-.018
ሴት/ወንድ 1ኛና 2ኛ ደረጃ ት/ቤት የሚማሩ	-.308**	-.008	-.033
1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ	.008	.211**	-.075
በጤና ባለሙያ የሚወለዱ	-.032	.060	.028

** በጣም ጠንካራ ደረጃ .01

* ጠንካራ ደረጃ .05

6. ማጠቃለያ

የዚህ ዕሁፍ ዋና ዓላማ ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር የሚለው ዕንስ ሃሳብ ፈጣን የሕዝብ እድገትን ለመቀነስ እንደ አንድ አማራጭ አቅጣጫ ለማሳየት ነው፡፡ በዚህ መሰረት የተፈጥሮ ሃብትን በብቃት መጠቀም የኑሮን ደረጃ አሻሽሎ እንዴት ወደ ሕዝብ እድገት ቅነሳ ሊያመራ እንደሚችል አይተናል፡፡

6.1 ርዕይ 2020

በትልቁ አስቡ!
በትንሹ ጀምሩ!
አሁኑኑ ተንቀሳቀሱ!

ለኢትዮጵያ በ2020 ያለኝ ርዕይ አሁን የበለፀጉ ሀገሮች ያሉበት አጋማሽ የኑሮ ደረጃ ለማድረስ ነው፡፡

ሰንጠረዥ 3 የሚያሳየው የሚሊኒየም ልማት ግቦች መስፈርቶች አስመልክቶ ኢትዮጵያ በ2020 የበለፀጉ ሀገሮች አሁን የደረሱበት አጋማሽ ላይ ለመድረስ ምን ማድረግ እንዳለባት ነው፡፡

- በኢኮኖሚ እርከን የመጨረሻ 25% የሆኑት የሚያገኙት የገቢ ድርሻ ከ2.4% በ1.5 እጅ ተባዝቶ ወደ 3 7% ማደግ ይኖርበታል፡፡
- የተመጣጠነ ምግብ የማያገኙት ህፃናት ብዛት ከ47% በ6 እጅ ቀንሶ ወደ 8% መውረድ ይኖርባታል፡፡
- የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ገበተው የሚማሩ ልጆች ብዛት ከ24% በአጥፍ ያህል ጨምሮ ወደ 43% ማደግ ይኖርበታል፡፡

- በአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ያሉ ሴቶች ተማሪዎች ብዛት ከወንዶቹ ጋር እኩል መሆን ይኖርበታል።
- አሁን ያለው ከፍተኛ የህፃናት ሀልፈት ከ172 ቀንሶ ወደ 86 መውረድ ይኖርበታል። እንዲሁም በወሊድ ጊዜ ሞት ከ1800 ወደ 900 መውረድ ይኖርበታል።
- በጤና ባለሞያዎች እርዳታ የሚወለዱ ህፃናት ብዛት አሁን ካለው 10% ወደ 50% ማደግ ይኖርበታል።

ሠንጠረዥ 3: የምዕተ-ዓመት ልማት አመልካቾች፣ ርዕይ 2020

የምዕተ-ዓመት ልማት አመልካቾች	ኢትዮጵያ 2001	የሃብታሞቹን ሀገሮች ግማሽ ለመድረስ ማጣጥ	ኢትዮጵያ በ2020
በኢኮኖሚ እርከን የበታቾቹ 25% የገቢ ድርሻ፤ መቶኛ	2.4	1.5	3.7
ያልተመጣጠነ ምግብ የማያገኙ ከ5 ዓመት በታች ያሉ ህፃናት፤ መቶኛ	47.0	ከ6.0 (ያነሰ)	8.0
አንደኛ ደረጃ የሚገቡ፤ መቶኛ	24	2	43
ሴቶችና ወንዶች ትምህርት ቤት አገባብ፤ መቶኛ	88	-	100
አምስት ዓመት ሳይሞላቸው የሚሞቱ ከ1000	172	-	86
በወሊድ ላይ የሚሞቱ እናቶች ከ100,000	1800	-	900
በጤና ባለመ.ያዎች ዕርዳታ የሚወለዱ ህፃናት፤ መቶኛ	10	5	50

ከላይ የተጠቀሱት ከሞላ ጎደል በሥራ ላይ ከዋሉ የኢትዮጵያን የሕዝብ ቁጥር እድገት በከፍተኛ ደረጃ ይገድበዋል ብዬ አምናለሁ። ሰንጠረዥ 4 እንደሚያሳየው በ2020:-

- የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚወስዱ ሴቶች ቁጥር አሁን ካለው 8% በአራት እጅ ጨምሮ ወደ 35% ይደርሳል።
- የሕዝብ ቁጥር እድገት አሁን ካለው 2.8% በዓመት ሃምሳ በመቶ ቀንሶ ወደ 1.14% በዓመት ገቢ ይላል።
- የሃገሪቷ የሕዝብ ቁጥር በ2020 82 ሚሊዮን ይሆናል። ይህ 82 ሚሊዮን የሕዝብ ቁጥር ለ2020 ዓይነተኛው ቁጥር ተብሎ ቢገመትም ቋሚ ነው ማለት አይደለም። በጊዜው ላለው የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና ለሚያስከትለው የኑሮ ደረጃ እድገት ተመጣጣኝ የሆነ የሕዝብ ብዛት ነው ማለት ይቻላል።

ይህ እንግዲህ በ2020 የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀምና ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለሚመጣ የኑሮ ደረጃ እድገትና የሕዝብ ቁጥር ትነሳ ለኢትዮጵያ ያለኝ ርዕይ ነው።[4] በእርግጥ የተፈጥሮ ሃብትን ከላይ በጠቀስኩት መልኩ ለመጠቀም የትምህርት፣ የቴክኖሎጂ ብቃት፣ የመንግሥት መልካም አስተዳደርና የሕዝብ ቅን አስተሳሰብ በእጅጉ ይጠይቃል።

[4] ሕዝብ አምራችም ተጠቃሚም እንደመሆኑ ጽሁፉ የሕዝብን አምራችነት አልተመለከተም።

ዕሁፉ እነዚህን ሁሉ እንዲያካትት አልታቀደም። ሌሎች ሰዎች በእያንዳንዱ ላይ ዕሁፍ ማቅረብ ይችላሉ። የኔ ዕሁፍ ከፍ ብዬ እንደጠቀስኩት የተፈጥሮ ሃብትን በቅጡ መጠቀም እንዴት ወደ ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር እንደሚያመራ መጠቆም ብቻ ነው። ይህንንም ዕሁፌ ያደረገ ይመስለኛል።

ሠንጠረዥ 4፡ የሕዝብ ቁጥር ዕድገትና ብዛት፤ ርዕይ 2020

የሕዝብ ቁጥርና ዕድገት አመልካቾች	ኢትዮጵያ 2001	የሀብታሞቹን ሀገሮች ግማሽ ማባዣ	ኢትዮጵያ በ2020
የወሊድ መቆጣጠሪያ የሚወስዱ ሴቶች፤ መቶኛ	8	4	35
የየአመቱ የሕዝብ ቁጥር መጠን፤ መቶኛ	2.8	በ2 (ሲቀነስ)	1.14
የሕዝብ ቁጥር በሚሊዮን	70	-	82

6.2 የአስተሳሰብ ጉዳይ

«ኢትዮጵያውያን አብሮ መብላት እንጂ አብሮ መሥራት አይችሉም»

ከላይ በርዕይ መልክ ያስቀመጥኩት ደረጃ ለመድረስ ከፍተኛ የዕውቀትና የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ይጠይቃል። እንዲሁም የኢትዮጵያን ሕዝብ በቅንነትና በብቃት መምራት የሚችል መሪና አመራር ያስፈልጋል። ከሁሉም በላይ ግን ለብዙ ዘመናት በሀገራትዋ ስር ሰደው የቆዩትን ክልማት ጋር አብረው የማይሄዱትን አመለካከቶች መቀየር ያስፈልጋል።
በመጨረሻ ከዚህ ጋር በተያያዘ የገጠመኝን ሁለት በእጅጉ የተለያዩ ገጠመኞች በማውሳት ጽሁፌን አጠቃልላለሁ።

የላፊ 3 ወር ገደማ ለስብሰባ ከአንድ ሀገር ወደ ሌላ ስዜድ ሎስ አንጀለስ የሚባል የአሜሪካ ከተማ ስድስት ሰዓት ማሳለፍ ነበረብኝ። አውሮፕላን ማረፊያ ተቀምጬ ከሚሰለቸኝ ብዬ ታክሲ ኮንትራት ይገፍ ከተማዋን ለማየት ወጣሁ። ታክሲውን የሚነዳው ነጭ ወንድ ጎልማሳ ከመቅጽበት ቤቨርሊ ሂልስ የሚባል የሃብታሞች መኖሪያ መንደር ወሰደኝ። ከዚያም በጣቱ በጣም የሚያማምሩ ቤቶች እየጠቆመ «ይህ እከሌ የሚባል ፊልም ተዋናይ ቤት ነው፤ ይህ ደግሞ እከሌ የሚባል ባስኬት ቦል ተጫዋች ቤት ነው፤ እዚያ ጋ ደግሞ እከሌ የሚባል ሚሊየነር ይኖራል» እያለ በከፍተኛ ስሜትና አድናቆት ይነግረኛል። እኔም ለብዙ ጊዜ በትዕግሥት ካዳመጥኩት በኋላ ትንሽ ስለሰለቸኝ እስቲ አንድ ጥያቄ ልጠይቅህ አልኩት። እሱም በፈቃደኝነት ፈገግ አለ። እኔም ቀጥዬ ለመሆኑ እናንተ አሜሪካኖች ለምንድነው በሰው የምታመልኩት? አሁን ስለነዚህ ሰዎች ስትነግረኝ ልክ እንደ መልአክ እያየሃቸው ነው! በእኛ ሀገር በዘፋኝም ሆነ ስፖርተኛ ወይንም ሃብታም ሰው እንደናንተ አናመልክም! እንዲያውም ከቱም ነገር አንቆጥራቸውም! አልኩት። እሱም ሲመልስ «ይኸውልህ የኔም ሆነ የሌሎች አሜሪካኖች ለነዚህ ሰዎች ያለን አመለካከት የማምለክ ነገር አይደለም። እነዚህ ሰዎች አብዛኛ ዎቹ ከእድግ ዝቅተኛ ደረጃ በትጋታቸውና በታታሪነታቸው እንደዚህ ያለ ከፍተኛ ደረጃ

የደረስ· ናቸው። ስለዚህ አሁን በከፍተኛ ስሜት የምነግርህ እነዚህ ሰዎች እዚህ ደረጃ በመድረሳቸው ያለኝን አድናቆትና ከፍተኛ ግምት ለማንፀባረቅ ብቻ ነው እንጂ የማምለክ ነገር አይደለም አለኝ»። እኔም በጥያቄዬ አፍሬ፣ ስለሰጠኸኝ ማብራሪያ አመሰግናለሁ ብዬ ንግግራችንን በሌላ ተየርን።

የነኑ ቀን መሂጃዬ ሰዓት ደርሶ አውሮፕላን ማረፊያ አድርሶኝ ብቻዬን ቁጭ ብዬ ሳስብ አንድ ነገር ትዝ አለኝ። የዛሬ 10 ዓመት ገደማ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ መምህር እያለሁ ተማሪዎቹን ይዤ ሰሜን ሸዋ ደብረሲና ከተማ አካባቢ ሄጀ ነበር። አንድ ቀን ጠዋት መረጃ ለመሰብሰብ ወደ ገጠር ከመሄዳችን በፊት የቡና ሱሰኛ ስለሆንኩ ቡና ፍለጋ ከቡና ቤት፣ ቡና ቤት፣ መሂድ ጀመርኩ። በየሄድኩበት የማሽን ሳይሆን በጀበና ተፈልቶ በፔርሙስ የተቀመጠ ቡና ብቻ ነው ያለው ይሉኛል። እኔ ደግሞ ተፈልቶ በፔርሙስ የቆየን ቡና ስለማልወድ ፍለጋዬን ተጠልኩ። መጨረሻ ላይ ተስፋ ስለቆረጥኩ አንድ ቡና ቤት ገብቼ ያንኑ ያገኘሁትን የፔርሙሱን ቡና ስጠኝ አልኩና መጠጣት ተያያገዘኩ። አዲስ የተፈላ ቡና ባለማግኘቴ ቅር ብሎኝ ስለነበር አጠገቤ ቁሞ የነበረውን የቡና ቤቱን አሳላፊ ቁጣ ባዘለ አነጋገር አዲስ አበባ ቅርባችሁ ነው! ኩስማችሁም ትንሽ የምትባል አይደለችም! ለምንድነው የቡና ማሽን የማታስመጡት? ብዬ ዘለፋ ያለበት ጥያቄ አቀረብኩለት። እሱም ረጋ ባለ መንፈስ «ይኸውልህ ጋሽ! እዚህ አካባቢ ማሽን ማስመጣት ትግር አለበት አለኝ»። እኔም የምን ትግር? ብዬ ወየሪ ያገዘኩት። «ትግሩ ምን መሰለህ! አሁን አንዳችን የቡና ማሽን ብናስመጣ በለጠን፣ ቀደመን፣ ብለው ሌሎች ባለቡና ቤቶች በመርዝ ይገድሉታል። ስለዚህ ይህን ፈርቶ ቀድሞ ማሽን የማያመጣ ሰው ጠፍቶ፣ ከተማዋ እስካሁን ያለማሽን ቀርታለች» ብሎ አጫወተኝ።

በኔ ግምት በዘአበርሊ ሂልስና በደብረሲና መሃከል ያለውን ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ ልዩነት ሊገልጹ ከሚችሉት ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ በሁለቱ ቦታ ነዋሪዎች መሃከል ያለው የአስተሳሰብ ልዩነት ይመስለኛል።

<u>የመረጃ ምንጫዎች</u>

በዚህ ጽሁፍ ላይ ለመረጃዎቹ እንደዋነኛ ምንጭ የተጠቀምኩባቸው ከታች የተመለከቱት ናቸው።

1. Living Planet Report, 1999 – 2004. WWF International, Switzerland
2. World Development Report, 2000 – 2004. Oxford, England
3. Millenium Development Goals indicator

በዶ/ር አክሊሉ ጹሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

ጥላሁን ግደይ*

በመጀመሪያ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር ይሸንን የ2020 ርዕይ በተለያዩ ሁኔታዎችና አርዕስቶች ሕዝቡን በማወያየታቸው በጣም አመሰግናለሁ።

በአገራችን ውስጥ ያለውን የኢኮኖሚ እና የሰብአዊ ኑሮ ዕድገት የውይይት ደረጃ ከፍ አድርጎታል። ለዚህም ማህበሩን በጣም አመሰግናለሁ።

የተማርነው ስዎች ተደብቀን እንቆር ነበር። አሁን ግን ማህበሩ ያገራችንን ችሎታ እያወጣው ነው። ስለዚህም በብዙ መንገድ ዕድገት ይታየኛል። ስለዚህም ደግሚ ማህበሩንና አባላቱን አመሰግናችኋለሁ።

ይ/ር አነሊስ በጣም ሰፋ ያለ ጊዜ ወስደው ጥሩ ነጥብ አቅርበውልናል። እርሳቸውንም በጣም አመሰግናለሁ።

ወ/ሮ ገነት ብዙውን ጠቅሳዋለች፤ እኔ አጠር አጠር አድርጌ ነው የማቀርበው፤ ብዙ ጊዜ አልፈጅም።

በመጀመሪያ ነገር እኔ ዲሞግራፈር አይደለሁም፣ የጤናም ሰው አይደለሁም። አቶ ሳህሉ ሲያስተዋውቀን እንደሰማችሁት እኔ በልምዴ የልማት ሰው ነኝ። ቀደም ሲል ብዙውን ዓመት የሠራሁት በልማት መስክ በመሆኑ ወደ ቤተሰብ ዕቅድ ሥራ ስገባ ወደ አገሬ መመለሱ ስቦኝ ከመሆኑ በቀር እንዴት ሕዝቡ ሲያድግ ባየሁበት ሁኔታ፤ ሰውን አሰልጠኜ ሥራ ሲይዝ ተደስቼ የኖርኩበትን ሁኔታ ትቼ፤ ስዎች በእርሻም ሆነ በሚሠሩት ሥራ የተሻለ ኑሮ ሲያገኙ በማየት ስደሰትበት የኖርኩበትን ትቼ፤ እንዴት ወደ ቤተሰብ ዕቅድ ሥራ እገባለሁ? ብዬ በጭንቀት ላይ ነበርኩ። ሆኖም ወደ አገሬ ልገባ ስለፈለግሁኝ ሥራው አንገኝ። የቤተሰብ ዕቅድ ድሮ ከነበረኝና ከነልሆቴ ጋር የሚያያዘው ምኑ ይሆን? ብዬ ራሴን ጠየቅሁ። በአንድ በኩል ልማት እየሠራን እያለን በሌላ በኩል ሳናውቀው ከሥሩ የሚሸረሸርብን ሁኔታ መኖሩን ተገነዘብሁ። አሁም ከኢኮኖሚ ጋር ያልተመጣጠነ የሕዝብ ዕድገት መሆኑን ተረዳሁ። እንግዲያውስ ይሸንን ሥራ ከያገሀው ልማትን ከኋላ ጀምሬ እየሰራሁ ነው የሚል እምነት አደረብኝ እና ከልብ አስቤበት እና ሥራውን ተቀብዬው እየሰራሁ እገኛለሁ።

ይኸ የሕዝብ ቁጥር መቀነስ የሚለው ተደጋግሞ ቢነሳም ትክክል ባለመሆኑ የሕዝብን ዕድገት ከኢኮኖሚውና ከአገሩ ዕድገት ጋር ማጣጣም በሚለው መለወጥና፤ የሕዝብ ዕድገት መቆጣጠሪያ የሚለውም አሁንም ያልሆነ ትርጉም ስለሚያስተላልፍ የቤተሰብ ዕቅድ (Family

---

* አቶ ጥላሁን ግደይ በሚነሶታ ምህንድስና የባችለር ዲግሪ በ1970 ከቀድሞ ቀ.ኃ.ሥ የኒቨርሲቲ፤ ከአሁኑ አ.አ. ዩኒቨርሲቲ፤ ማስተርስ ዲግሪያቸውን ደግሞ በግብርና ምህንድስና ከአሜሪካን አገር ኮርኔል ዩኒቨርሲቲ በ1975 አግኝተዋል። አቶ ጥላሁን ለ24 ዓመታት በአገር ውስጥና በውጭ አገር በተለይም በምዕራብ አፍሪካና በአሜሪካን አገሮች በተለያዩ የሥራ መስኮችና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ውስጥ በከፍተኛ ኃላፊነት አገልግለዋል። ከ2002 ጀምሮ የPathfinder International የኢትዮጵያ ተወካይ እና የ OIC Ethiopia የቦርድ ሰብሳቢ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

Planning) ቢባል ይመረጣል። ለወደፊቱም በውይይታችን ይኸንን እያረምን እንደምንሄድ ተሰፋ አደርጋለሁ።

በዶ/ር አክሊለ ጽሑፍ ላይ እስካሁን ድረስ በቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት እንሰጣለን ብለን የወሰድነው አቅጣጫ መመርመር አለበት፤ ትክክልም አይመስለኝም ብለዋል። በስተመጨረሻ፤ በመደምደሚያ ላይ ደግሞ የቤተሰብ ዕድገት መቆጣጠሪያ ዘዴ ተጠቃሚ ሴቶች ብዛት ከ8% አላለፈም፤ ይህም ሂደቱ ጥሩ ባላመሆኑ ሌላ አቅጣጫ እንፈልግ ብለው ዶ/ር አክሊሉ በፍጆታ እና በመሳሰሉት ንድፈ ሀሳቦች አቅርበዋል።

እርሳቸው ሰፊ ሥራ በመሥራታቸው ላመሰግን፤ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ከንድፈ ሀሳብ ይልቅ ከእውነታ ጋር አያይዘው ቢያስተምሩን ኖሮ የተሻለ ነበር የሚል የግል አስተያየት አለኝ፤ ሆኖም ትክክል ላልሆን እችላለሁ።

ቢሆንም በእኔ አስተያየት፤ ጥናትም በቅርቡ ያደረግነው አለ፤ ዶ/ር አክሊሉ በ2000 የተካሄደውን DHS ጥናት በመጥቀስ ሥነ-ተዋልዶ የሚጠቀሙ ሴቶች ብዛት 8% ናቸው አሉን እንጂ አሁን በቅርቡ ባደረግነው ጥናት፤ እንዲያውም DHS በዚህ ዓመት ይደገማል፤ ሥነ-ተዋልዶ የሚጠቀሙ ሴቶች ብዛት 21% ደርሰዋል። በተለይም ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ባላቸው የአገራቱ ክልሎች በወሊድ ዕድሜ ያሉትና ተጠቃሚ ለመሆን ፈልገው ዕድሉን ያላገኙት የሴቶች ብዛት እስከ 35% ደርሳለ። ይህ ምን ማለት ነው? አቅርቦቱ ኖሮን የእነሱን ፍላጎት ብናሟላ ኖሮ ወደ 56% የሚደርሱ ሴቶች የሥነ-ተዋልዶ መቆጣጠሪያ ዘዴ ይወስዱ ነበር ማለት ነው። ይህ ያልሆነበት ምክንያት ሕዝብ ሳያውቀው፤ ወይም ሕዝብ ሳይፈልግ ቀርቶ ሳይሆን፤ በመድኃኒት አቅርቦት፤ በኮንትራሴፕቲቭ አቅርቦት፤ አገልግሎቱን ለሰፊው ሕዝብ በማትረብ ረገድ ሁላችንም፤ በዚህ የተሰማራን ሰዎች ሁሉ ሰለደከምን ነው።

ሆኖም ባለፉት አሥርና አሥራ ሁለት ዓመታት በተደረገት ከፍተኛ ጥረት፤ እንደነገርኳችሁ አሁንም እንደገና ጥናት ይደረጋል፤ በቅርቡ በተደረገው ጥናት መሠረት 21% የአገራችን ሴቶች ተጠቃሚ ናቸው። 35% ደግሞ እባካችሁ ኑልን እያሉ ነው።

ዶ/ር አክሊሉ ስለ ሊበራሎች አስተሳሰብ ሲያቀርቡልን ሥነ-ተዋልዶን የሚቃወሙ እንዳሉ ነግረውናል። እነዚህ ሊበራሎች የሴቶችን መብት የሚደግፉ ናቸው ብለው የጠቀሱት በእኔ አስተያየት ትክክል መሰለ አልታየኝም። የሴትን መብት የሚደግፍ ሊበራል ሰውማ የሥነ-ተዋልዶን መብት ከሴቶች አጠቃላይ መብት ጋር አያይዞ ያያል። በዲሞክራቲክ አገሮች ሴቶች ከፈለጉ፤ የእነሱን ጤና የማጎዳ ሆኖ ከተገኘ፤ ውርጃም የማካሄድ መብት አላቸው፤ በእነሱ ሰውነት የሚወስን ማነው? የሚለም አለ። ለጊዜው መደዚያ አልሄድም። ሆኖም ሴቶች በሚፈልጉት ርቀት የመውለድ መብት ሊኖራቸው ይገባል እላለሁ። ከሁሉ በላይ ግን የሴቶችን መብት የሚደግፉ ወይም ለሴቶች መብት የሚከራከሩ ሰዎች የሥነ-ተዋልዶን አገልግሎት አቅርቦት መደገፍ ያለባቸው ይመስለኛል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ባለው ሁኔታ ለምሳሌ፤ የNorplant አንድ የምንጠቀምበት የሥነ-ተዋልዶ መከላከያ ዘዴ ነው። እሱን በሚመለከት አደገኛ ነው የሚሉና፤ ሴቶች በዚህ መድኃኒት የመከራ ሰለባም ሆነዋል የሚሉ ሰዎች አሉ ተብሏል። ይህ ሁኔታ በኢትዮጵያ እንደሌለ ዶ/ር አክሊሉም ተናግረዋል። በእውነቱ ለመናገር፤ በተለይ ደግሞ በፋርማሲ ሥራ ውስጥ ያላችሁ

ሰዎች እንደምታውቁት፣ መድኃኒቶች አገር ውስጥ ሲገቡ ያለው ቁጥጥር የትየለሌ ነው። በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተፈቀደ መድኃኒት ብቻ ነው የሚገባው፤ የዓለም ጤና ጥበቃ የመሰከረላቸው መድኃኒቶች ብቻ ናቸው የሚገቡት። እንደዚሁም ደግሞ ላኪ አገሮች ኃላፊነት ስላለባቸው እነሱ አረጋግጠው ነው የሚልኩት እንጂ እንደዚሁ ከመንገድ ወይም ከነጋዴ ተገዝተው የሚገቡ የሥነ-ተዋልዶ መከላከያ መድኃኒቶች እንደሌሉ ማረጋገጥ አፈልጋለሁ። በተጨማሪ የአሜሪካ የሕዝብ ተወካች ምክር ቤት አንድ ያሳለፈው ህገ-ደንብ አለ። Tolbert Amendment ይባላል። እሱም በዶ/ር አክሊሉ ጽሑፍ ውስጥ ተጠቅሷል። እሱ ምን ይላል? እያንዳንዱ የሥነ-ተዋልዶ ተጠቃሚ ሴት፣ ያሉት የመከላከያ ዘዴዎች ተነግሯት፤ እያንዳንዳቸው የሚያስከትሉት ተጽዕኖ ወይም ክፉ ጎን ተነግሯት፤ አውቃ፣ ወድዳ፣ የምትገባበት መሆን አለበት እንጂ በግዴታ፣ ኮታ ለመሙላት ብቻ ሴቶችን መገፋፋት የለብንም የሚል ውሳኔ ስላለ፤ በአሜሪካ አገር ድርጅቶች እየተረዳን በኢትዮጵያ የምንሠራ ድርጅቶች በሙሉ ለዚህ ህገ-ደንብ ተገዢዎች ነን። ከዚያም በላይ ኢትዮጵያውያን በመሆናችን ኃላፊነትም ለሕዝባችን አለብን። ስለዚህ የአሠራራችን ዘይቤ በዕውቀት ላይ የተመሠረተ ምርጫ (Informed choice) ነው።

ዶ/ር አክሊሉ ሌሎች የተናገሩትን አንድ የጠቀሱት፣ በጣም የሚያሳዝን፣ ነገር አለ። 'ድሃ ረሃብተኞችን ማዳን ሌሎች ብዙ ድሆች እንዲያብቡ ዕድሉን ማስፋት ነው' ያሉት። ከእኔ ጋር ትስማማለችሁ፤ በጣም የሚያሳዝን፣ ትክክለኛ ያልሆነ አነጋገር ነው። የሰውን ሕይወት ማዳን ሰብአዊ ነው፤ ሞራላዊም ነው፤ ሆኖም ስለሥነ-ሕዝብ ስንናገር ያገራችንን ሕዝብ ተጨባጭ ሁኔታ ማየት ይገባናል። በመሆኑም፣ ቅድም እንዳልኩት፣ ስለሥነ ሕዝብ ስንናገር ከአገር ዕድገትና ከቤተሰብ ችሎታ ጋር የተመጣጠነ የልጆች ብዛት ወይንም የሕዝብ ዕድገት መጣኔ ማለታችን ነው። ሁለቱ ይመጣጠኑ ማለታችን እንጂ የሕዝብ ብዛት ይቀነስ፣ ወይም ይቁም፣ ማለታችን አይደለም። አሁን ኢትዮጵያውያን 70 ሚሊዮን ደርሰናል። ሁላችሁም እንደምታውቁት 14 ሚሊዮን የሚሆኑ ሕዝባችን ሥር የሰደደ የምግብ እጥረት አለባቸው፣ ይራባሉም። ካሁን በፊት በአፄ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት 25 ሚሊዮን ሕዝብ በነበርንበት ጊዜ፣ ረሀብ መጣ ተብሎ እርሳቸውንና መንግስታቸውን የጣለውን ሁኔታ እናስታውሳለን። ያን ጊዜ 1-2 ሚሊዮን ተራበ ብለን አ! አ! ያልን ሰዎች፣ አሁን 14 ሚሊዮን፣ ይኸም ደግሞ ሥር እየሰደደ፣ እያደገ እንደሚሄድ ይነገራል። በ2020 የUNFP ትንበያ የሕዝባችን ቁጥር 170 ሚሊዮን እንደሚደርስ ያመለክታል። አሁን 70 ሚሊዮን ሆነን ራሳችንን መመገብ ያልቻልን ሕዝብ 170 ሚሊዮን ሰንሆን እንዴት ነው የምንሆነው?

በነገራችን ላይ እኔ ት/ቤት በነበርኩበት ጊዜ መንግሥት በሚያድለን ደብተር በስተጀርባው ላይ አንድ ጥቅስ ነበር። አፄ ኃይለስላሴ ተናገሩ ተብሎ ነው የተጠቀሰው።

«ልጅ ወልዶ ካላስተማረ ያነቀ ፀደቀ»።

እርግጠኛ ነኝ፣ ከእኔ ጋር ትስማማላችሁ፣ ልጅ ወልደን እንነቅ የሚለውን ድርጊት መደገፋቸው እንዳልሆነ። ሆኖም ወልደን ካላሳደግን፣ ዕድሜአቸውን በሙሉ እንደምንኮንናቸው በመረዳት፣ ማስተማር፣ በደንብ ማሳደግ፣ የእያንዳንዱ ቤተሰብ ኃላፊነት በመሆኑ፣ ይኸንን ያላደረገ ቤተሰብ ልጁን ኮነነ፣ ለዘለዓለም በድህነት እንዲኖር ፈረደበት፣ ማለትን የሚያጠናክር ምክር አዘል አባባል ይመስለኛል።

ዶ/ር አክሊሉ በጻፉት ጽሑፍ ውስጥ አሁንም የሥነ ተዋልዶ ዘዴዎች በማመለክት፣ ለምሳሌ፤ ይኸ Norplant አደገኛ ነው የሚለው፤ እርሳቸውም ከአቀራረባቸው፤ የሚያምኑበት መስለውኛል፤ ሆኖም በወሊድ ዕድሜ ደረጃ ካሉት የእኛ ሴቶች 5% ብቻ ናቸው የሚጠቀሙት ብለዋል። እኔ እንደ ኢትዮጵያዊነቱ 5% ለምን ይጠቀመበታል አደገኛ ከሆነ? እላለሁ። ሆኖም ቅድም እንዳልኩት፤ በብዙ ጥንቃቄ ላይ ተመሥርቶ ወደ አገራችን የሚገባ መድኃኒት እንጂ፣ አደገኛ መድኃኒት እንደማይገባ ከማረጋገጡም በላይ፤ በእውነቱ እንደዚህ ያሉ ነገሮች፣ እንደዚህ ያሉ ውሸቶችን፣ ሕዝባችንን በዘለቄታው የሚጎዱ መሆናቸውን ማስገንዘብ እወዳለሁ። የሥነ ሕዝብ አገልግሎት የሚሰጠ ድርጅቶች ኃላፊነት አለባቸው፤ ተጠያቂዎችም ናቸው፤ ይኸ እንዲረጋገጥልኝ እፈልጋለሁ።

በተጨማሪ ግን በቅርበ ትግራይ ሄደን ከሃይማኖት መሪዎች ጋር ሥነ-ሕዝብና ዕድገት በማል ርዕሰ የሁለት ቀን ውይይት አካሄደን ነበር። በዚያ ላይ እንደምትገምቱት ብዙ ተቃውሞ ተነስቶ ነበር፤ በስተመጨረሻ መደምደሚያው ላይ ግን የተስማማነው፣ የአርቶዶክስ፣ የእስልምና ኃይማኖት፣ የፕሮቴስታንት፣ የካቶሊክና የሰባት ቀን አድቬንቲስት መሪዎች፣ ከሕዝብና ከቤተሰብ አቅም ጋር ያልተመጣጠነ ብዙ ልጆች መውለድ እንደማይጠቅመው፣ ሴቶች ካለዕድሜ ቀድመው ጋብቻ መፈጸማቸውን እንደማይጠቅመው፣ የሴቶችን ግርዛት ከልብ እንደማይጠቅመው፣ ሲናገሩ አንዱ የካቶሊክ መሪ የማከብለውን ጥያቄ አቀረበልን። «ለምንድንነው እናንተ ዘመናዊ የመከላከያ ዘዴ ብቻ የምታስተምሩት? እሱን ብቻ የምትገፉት? ለምን የተፈጥሮ ዘዴንም አታስተምሩም?»። ይኸም በጊዜ መቆጣጠር ማለት ነው፤ ቀጥለውም የሐይማኖት መሪው ሲናገሩ «ዘመናዊ መድኃኒት እዘ ጉጂ ተጽዕኖ አለው በሴቶች ጤና ላይ» ብለዋል። እኛም የተፈጥሮ ዘዴን በምርጫ እናቀርባለን፣ እናስተምራለን፣ የሚፈልገ ይመሰዱበታል። እኛማ እሱ ቢሆንልን ኖሮ ፍላጎታችን ነበር፤ ብለን መልሰናቸዋል። በተጨማሪም አስገራንም ጉጂ ጉን አለው፤ ፖራሲትሞልም እንዲሁ ከፋ ጉን አለው፤ እስቲ እናንተ ንገሩን፣ ከዘመናዊ መድኃኒት ክፉ ጉን የለለው አለ? ስለዚህ ዕድገት የሚያመጣውን ነገር መቀበል ለአገርም ዕድገት በመሆኑ እንመርምረው፤ እናጣራ፣ በትክክል መሆኑን እናረጋግጥ እንጂ፣ ዘመናዊ መድኃኒት በመሆኑ ብቻ አንቀበልም የሚለው አስተያየት ትክክል እንዳልሆነ ይኸንን አጋላጭ ተጠቅሜ መናገር እፈልጋለሁ።

ዶ/ር አክሊሉ ስለናጅታ ሲናገሩ፤ ውሃ ሀብታችን ብዙ ነው ስላልተጠቀምንበት ነው እንጂ ብለዋል። ይህ ሀሳብ ትንሽ ያስፈራኛል። እውነት ሊሆን ይችላል፤ ትክክልም ሊሆን ይችላል፤ የነርሰ ምድር ውሃችንና ወንዞቻች ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ።

ያስፈራኝ ግን ምናልባት ይኸ የሕዝብ ብዛት ሳይሆን ችግራችን፤ የተፈጥሮ ሀብታችንን ማለትም መሬታችን፤ ውሃን፤ ወዘተ...፤ በደንብ ስላልተጠቀምን ነው፤ ወደማለው ትርጉም እንዳይወስደን ሰግቼ ነው።

አንደተባለው ሴቶችን ማስተማር ራሱ የሕዝብን ዕድገት ከአኮኖሚ ዕድገታችን ጋር ያመጣጥነናል፤ ሰውን ማስተማር፣ ልማትን ማካሄድ፤ እነዚህ ቅድሚያ ቢሰጣቸው፤ የሕዝብን ዕድገት ይቆጣጠራል። እውነት ነው፤ ለምሳሌ፤ አዲስ አበባ ውስጥ የወሊድ መጣኔ ከገጠር ይልቅ አነስተኛ ነው። በዚህ ሁሉ እናምናለን፤ ሴቶችን ማስተማር፣ ሕዝብን ማስተማር፣ የህዝብ ዕድገት እንደሚቆጣጠር እናውቃለን። ሆኖም የእኛ አስተሳሰብ ኢትዮጵያ እኮ አደገኛ ሁኔታ ላይ ነች ያለችው፣ ስለዚህ የተፈለገው ዕድገት ላይ እስክንደርስ ድረስ፣ ምንም እንኳ ዶ/ር አክሊሉ ቅድም እንዳሳየው ክፍተት/ልዩነት ቢኖርም፤ አስቸኳይ ጣልቃ ገብ የሥነ-

ተዋልዶ አገልግሎት (intervention) ያስፈልጋል። ስለዚህም ነው የሥነተዋልዶ አገልግሎት ከዕድገትና ከትምህርት ጋር አብሮ መሄድ አለበት የምንለው።

በአጠቃላይ፣ ቅድም እንዳልኩት በሥነ-ተዋልዶ አጠቃቀም ዕድገት እየታየ ነው፤ በመውለድ ዕድሜ ላይ ከሚገኙ ሴቶች 21% ይጠቀማሉ። አገልግሎት የሚፈልጉት ቅድም እዳልኩት ተጨማሪ 35% አለ። እነሱን ብናሟላ ሌሎች አገሮች የደረሱበት መድረስ እንችላለን።

ሕዝቡን በየቦታው ሄደን ስናነጋግር የሚሉት አላቸው። ሦስት ክልሎች ሄደናል፤ አማራ፣ ትግራይና ደቡብ። በአማራ ክልል «መሬት አህል ፈራ፣ መደብ ልጅ አፈራ» ብለውናል፤ በየቀኑ ሁኔታውን ስለማያዩት፤ የሃይማኖት አባቶቻችንም የሚሉት አላቸው። «ብዙ ተባዙ የተባለውን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ አይተናል፣ ልጆቻችን አሁንማ በዝተው፣ ተባዝተን አገራችንን ሞልተውታል፤ ያገራችን ሕዝብ በሬ ግንባር በምታክል መሬት እያረስ ነው። ለድህነት ተዳርገናል፣ አስከመቼ ነው የምትጠብቁት፣ ለምን አትመጡም እኛ ዘንድ?» ይሉናል።

ስለዚህ መሬት አለን ገና ያልታረሰ የምንለው ነገር እውነትም ቢሆን ፣ እርሱ ደግሞ አብሮት የማሄዱ ነገሮች ስላሉ ችግር አለ። ውሃ አለን የምንለው ነገር ትክክልም ቢሆን፣ ከእርሱ ጋር አብረውት የማሄዱ ነገሮች ስላሉ፣ ይኸም ችግር አለው። ቅድም በመደምደሚያው ላይ ዶ/ር አክሊሉ እንዳለው መልካም አስተዳደር፣ መልካም ትምህርት፣ ሊኖረን ያስፈልጋል በእኔ አስተሳሰብ። እነዚህ ሁሉ የሚመጡት ግን ጥሩ ትምህርት ሲኖረን፣ ጥሩ ዲሞክራሲ ሲኖረን፣ ዲሞክራሲ ደግሞ ከትምህርት ጋር አብሮ የሚሄድ ነው፤ መብታችንን ስንጠይቅ ማለት ነው፤ ለመብታችን ስንቆም፣ ስንመርጥ፣ ማለት ነው፤ ሁሮ ሁሮ እኔ ሕዝባችንን ማስተማር አለብን እላለሁ።

እኔ ስማር ክፍል ውስጥ ከ20 ያነሰን ልጆች ነበርን። አሁን ተመልሼ ከተማርኩበት ት/ቤት ሄጄ ሳይ በአንድ ክፍል ውስጥ ከ80-130 ተማሪዎች አሉ። የት/ቤት ኃላፊዎችን ሳነጋግር እንዲያውም ያንተ ት/ቤትማ ጥሩ ነው፣ ሌላ ቦታ ከዚያ ይበልጣል አሉኝ። ከዚህ በተጨማሪ በፈረቃ ነው የሚማሩት።

የነገ አገር ተረካቢዎች ሆነው፣ ዓለም በቴክኖሎጂ መጥቆ በሄደበት ጊዜ 47% በምግብ እጥረት የተጎዱ ህፃናት ባለበት፣ ከእሱም ውስጥ 58% ለዕድሜያቸው የቀጨጩ ሆነው ሳለ፣ የወደፊት ሕዝባችንን ሊመሩ ወይስ ኢትዮጵያን ለጥፋት ሊደርጉት ነው?

በአጠቃላይ ይኸ ዕድል ስለተሰጠኝ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር እያመሰገንሁ፣ የጀመረውን ሄደት በዚህች ክፍልና በዚህች ቁጥር ሳይወሰን በመላ አገራቱ ውስጥ ይኸንን ውይይት እንዲቀጥል እየተማፀንኩ አስተያየቴን በዚህ እቋጫለሁ።

አመሰግናለሁ።

የዶ/ር አክሊሉ ኪዳኑን ጽሑፍ አስመልክቶ የተሰጠ አስተያየት

ገነት መንግሥቱ*

ከሠላሳ አስተዳደማ «ዓይነተኛ የሕዝብ ቁጥር» (Optimum Population Size) በማለ ርዕስ ዶ/ር አክሊሉ ኪዳኑ ባቀረቡት ጽሑፍ ላይ በመመርኮዝ ለመወያያ የማሠኑ መነሻ ሃሣቦችን እንዳቀርብ ዕድል ስለተሰጠኝ አመሰግናለሁ::

ዶ/ር አክሊሉ በዚህ ርዕስ ላይ ስላቀረቡት ጽሑፍ እያመሰገንኩ፣ በጽሑፉ ዙሪያ አንዳንድ መሠረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ያለኝን አስተያየት አቀርባለሁ::

ዶ/ር አክሊሉ ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር የማለው ጽንሰ ሃሣብ ምን ማለት እንደሆነና በዚህ ዙሪያ የተለያዩ ሀሳቦችን ያቀረቡትን አስተያየቶች፣ እንዲሁም የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ከሕዝብ ብዛት ጋር ያለውን ተዛምዶ አቅርበዋል:: በኢትዮጵያ የኅመታዊ የሕዝብ ዕድገትን ለመቀነስ አቅላጫዎችን መቀየር እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል::

ዶ/ር አክሊሉ በእንግሊዘኛው Optimum Population Size የማለውን 'ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር' በማለ ስለተረጐመት እኔም ይህንኑ አባባል በዚህ ጽሑፍ ውስጥ እጠቀማለሁኝ::

ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር

በተለያዩ ሀሳቦች እንደተገለፀው ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር የማለው ጽንሠ ሃሣብ የቆየ ነው:: በአጭሩ ለመግለጽ በአንድ በተወሰነ መትት ና ጂኦግራፊያዊ አካባቢ ያለን ሀብት ግምት ውስጥ በማስገባት የሕዝብን ጥሩ የነሮ ደረጃ ለማረጋገጥ በሚያስችል ሁኔታ ሊኖር የሚገባው የሕዝብ ብዛት ማለት ነው:: ይህም ሲባል የነፍስ ወከፍ ገቢ ከፍተኛ ደረጃ ላይ የደረሰበት፣ ያለውን ሀብት ለመጠቀም የሚያስችል በቂ የሰው ኃይል ያለበት፣ ምርታማነት ከፍተኛ የሆነበት፣ ሥራ አጥነት በጣም አነስተኛ የሆነበት እና የተለያዩ የማሕበራዊ አገልግሎቶች በበቂ መቅረብ የሚችልበት፣ በአጠቃላይ የእያንዳንዱ ዜጋ ደህንነት (welfare) የተረጋገጠበት ሕብረተሰብ መፍጠር የሚያስችል ሁኔታ ማለት ነው::

አብዛኞቹ ኢኮኖሚስቶች ይህንን ጽንሰ-ሃሣብ ብዙም አይደግፉትም:: ምክንያታቸውም አንድ አገር በደረሰበት ወይም ሊደርስበት ከሚችልበት የኢኮኖሚና የማሕበራዊ ዕድገት ደረጃና ካለው የተፈጥሮ ሀብት አኳያ ሊኖረው የሚገባው ትክክለኛ የሕዝብ ብዛት ይኼ ነው ብሎ ለመገመት ስለማይቻልና ማድረግ ቢቻል እንኳን የተለያዩ ሁኔታዎች ተከስተው፣ ለምሣሌ፣

---

* ወ/ሮ ገነት መንግሥቱ በብሔራዊ ሥነ ህዝብ ጉዳይ ጽ/ቤት የሥነ ተዋልዶ ጤና የሴቶችና የወጣቶች ጉዳይ ማስተባበሪያ መምሪያ ኃላፊ፤ በመ/ቤቱ የሥነ ህዝብ ፖሊሲን በመቅረጽ የተሳተፉ ሲሆን ከዚህ በፊት በማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን የሥነ ህዝብ ጥናትና ምርምር ማዕከል የሠሩ ናቸው:: የትምህርት ደረጃቸው ከኢ.አ የኒቨርሲቲ በእስታትስቲክስ የጣችለር ዲግሪ እና ከአውስትራሊያ ናሽናል ዩኒቨርሲቲ በዲሞግራፊ የማስተርስ ዲግሪ አግኝተዋል::

የአዲስ ቴክኖሎጂ መፈጠር፣ የሀብት ግኝት፣ ያልታሰበ የተፈጥሮ ሆነ ለው ሠራሽ አደጋ፣ የመሳሰለት የተገመተውን ቁጥር ተቀባይነት እንዳይኖረው ስለሚያደርጉት ነው። በተጨማሪም ይህን ዓይነተኛ የሕዝብ ቁጥር ለማስላት ብዙ ጉዳዮችን መመልከት የሚጠይቅና መረጃዎችንም ማግኘቱ አዳጋች መሆኑን ይጠቅሳሉ።

ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር በአብዛኛው ንድፈ ሃሣባዊ (theoretical) ነው። ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥርን ለማስላት ከተፈጥሮ ሀብት በተጨማሪ ሌሎች ጉዳዮች እንደ ቴክኖሎጂ፣ የሠለጠነ የለው ኃይል፣ የኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ የመሳሰሉትን ሰፋ ባለ መልኩ መመልከት የሚጠይቅ ነው። በመስኩ ያሉ ባለሙያዎች በኢትዮጵያ ያለው ፈጣን የሕዝብ ዕድገት ስለሚያስከትለው ችግር ስጋታቸውን የሚገልፁ ቢሆንም የኢትዮጵያ ዓይነተኛው የሕዝብ ቁጥር ይህን ያህል ነው ብለው ያላስቀመጡትም ይህንኑ በመረዳት ይመስለኛል።

የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም

የበለፀጉ አገሮች የተፈጥሮ ሀብታቸውን በብቃት በመጠቀም ሕዝቦቻቸውን ጥሩ የኑሮ ደረጃ ላይ እንዲደረሱ በጽሑፉ ውስጥ ተወስቷል። በአጠቃላይ አገላለጽ የተሻለ የልማት ደረጃ ላይ ያለብን አንድ መሠረታዊ ጉዳይ አለ።

የበለፀጉና ደሀ አገሮች በተለያዩ የሥነ ሕዝብ ለወጥ ሂደት (Demographic transition) ውስጥ ያለፉ ወይም በማለፍ ላይ ያሉ በመሆናቸው የሥነ ሕዝብ ችግራቸው አፈታትና መፍትሔም እንደዚያው የተለያየ ነው።

የበለፀጉ አገሮች አሁን ያሉበት ደረጃ ላይ የደረሱት በረጅም የጉዞ ሂደት መሆኑንና ከኢኮኖሚያቸውና ከቴክኖሎጂያቸው ዕድገት ጋርም የሕዝባቸው ባሕልና አስተሳሰብ፣ በተለይም ትምህርት፣ ቴክኖሎጂ እና የኢኮኖሚው ዕድገት በፈጠረው ሁኔታ አብሮ አድጓል። በዚህም ምክንያት የሕዝቡ ቁጥር በየዓመቱ የሚያድግበትን ፍጥነት ወሳኝ የሆኑ ዲሞግራፊያዊ (የሥነሕዝብ) ጉዳዮች ሞትና ወሊድ ጊዜያቸውን ጠብቀው ተከታትለው መቀነስ ችለዋል። ስለዚህም በእነዚህ አገሮች የሕዝብ ቁጥር የሚያድግበት ፍጥነት በታዳጊ አገሮች የሚታየውን ያህል አልነበረም።

በአንፃሩ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ አገሮችን ሁኔታ ስናይ አብዛኛው የልማታቸው ዕድገትና የተለያዩ ማህበራዊ አገልግሎቶች፣ የጤናን ጨምሮ መሻሻል፣ ከበለፀጉ አገሮች በመጡ ቴክኖሎጂዎች በመታገዝ ነው። በዚህም ምክንያት በእነዚህ አገሮች የሞት መጣኔ ቀደም ሲል ከነበረው በከፍተኛ ሁኔታ ቀንሷል። ነገር ግን የወሊድ መጣኔ በጥቂቱ እንኳን ለመቀነስ ረጅም ጊዜ ወስዷል። ቀደም ሲል በበለፀጉት አገሮች እንደታየው የሞትን መጣኔ መቀነስ ተከትሎ ባላደጉ አገሮች የወሊድ መጣኔ አልቀነሰም። አሁንም ቢሆን የወሊድ መጣኔ ባላደጉ አገሮች ከፍተኛ ነው። በሞትና በወሊድ መጣኔ መካከል ባለው ሠፊ ልዩነት ምክንያት ዓመታዊ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጣኔ ከፍተኛ ሊሆን ችሏል። ይህም ሁኔታ ባላደጉ አገሮች ለድህነታቸው መባባስ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። ስለዚህ ባላደጉ አገሮች ያለው ፈጣን ዓመታዊ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት የልማት ጥረታቸውን ስለሚፈታተን የቤተሰብ ዕቅድ ፕሮግራም ሳይኖራቸው ልማት ላይ ብቻ በማተኮር የሕዝብን የኑሮ ደረጃ ማሻሻል አዳጋች ይሆናል።

ይህ ሁኔታ ያጋጠማቸው በርካታ በኤሲያና አንዳንድ በአፍሪካ የሚገኙ አገሮች በየዓመቱ የሕዝባቸው ቁጥር የሚጨምርበት ፍጥነት ልማታቸውን በመፈታተኑና ወደፊትም በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚኖረውን ጫና በማሰብ ከልማት መርሀ ግብራቸው ጐን ለጐን የሥነሕዝብ ፖሊሲ በማውጣትና በመተግበር ለመቆጣጠር ችለዋል።

ስለዚህ በደሀ አገሮች ላይ የሚታየውን የሕዝብ ቁጥር ፈጣን ዕድገት መፍትሔ ለመሻት እነዚህ አገሮች ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብት መጠንና አጠቃቀማቸውን ከበለፀጉ አገሮች ጋር በማወዳደር ብቻ ላይ የሚወሰን አይደለም። በኔ ግምት እነዚህ ደሃ አገሮች ያላቸውን የተፈጥሮ ሀብት በብቃት ለመጠቀም የሠለጠነ የሰው ኃይል፣ ገንዘብ፣ ቴክኖሎጂ እና ምቹ ፖሊሲዎችና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎች ያስፈልጋሉ ብዬ አምናለሁ። ድሃ አገሮች የተፈጥሮ ሀብት ቢኖራቸውም ይህንኑ ሀብት ተጠቅመው የሕዝባቸውን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል እንዲችሉ ቢያንስ እውቀትና ቴክኖሎጂ እንደሚያስፈልጋቸው ዶ/ር አክሊሉም ገልፀዋል።

የሕዝብ ቁጥር በራሱ የአንድ አገር የልማት ደረጃ ጠቋሚ አይደለም። ነገር ግን የአንድ አገር ሕዝብ የኑሮ ደረጃ ለመወሰን የሕዝብ ብዛት አንድ ገዳይ ነው። ሁለት አገሮች እኩል የሕዝብ ብዛት ኖሯቸው የተፈጥሮ ሀብታቸው መጠን፣ የሕዝብ ሥርጭት በዕድሜ /የተረጂው ሕዝብ ብዛት/፣ የሠለጠነ የሰው ኃይላቸው፣ የሕብረተሰቡ የባሕልና የአስተሳሰብ ሁኔታ ወዘተ.. በመሳሰሉት ሊለያዩ ይችላሉ። ስለዚህ ሁለቱን አገሮች የሕዝብ ብዛታቸውን ብቻ በማየት ማወዳደር አይቻልም። በሌላ በኩል የሥነ ሕዝብ ፖሊሲዎች ወይም ፕሮግራሞች የሚወጡት ፈጣን የሆነውን ዓመታዊ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ለመቀነስ እንጂ የሕዝብ ብዛትን ለመቀነስ አይደለም። የሕዝብ ብዛትን በተለይም ባላደጉ አገሮች ለመቀነስ ቢፈለግም በቀላሉ የሚቻል ጉዳይ አይደለም። በእነዚህ አገሮች የሕዝብ ቁጥር የሚጨምረው በሁለት ምክንያቶች፣ ማለትም በአሁኑ ወቅት የወሊድ መጠን ከፍተኛ በመሆኑና አብዛኛው ሕዝብ በአነሰተኛ ዕድሜ ክልል (population momentum) ውስጥ ስለሚገኝ ነው።

የትኩረት አቅጣጫችን ምን ይሁን?

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ እንደሚታወቀው ዓመታዊ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከፍተኛ ነው። በዚሁ የሚቀጥል ከሆነ በየ25 ዓመቱ የአገሪቷ ሕዝብ እጥፍ እንደሚሆን መረጃዎች ይጠቁማሉ። የአገሪቷን የኢኮኖሚ ዕድገት ደረጃና የሥነሕዝብ ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት በ1985 ዓ.ም. መንግሥት የሥነሕዝብ ፖሊሲን አውጥቷል። የሥነሕዝብ ፖሊሲው ዓቢይ ዓላማ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጣኔንና የአገሪቷን የተፈጥሮ ሀብቶች ልማትና አጠቃቀም በማጣጣም ከረጅም ጊዜ አኳያ የሕዝቡን የኑሮ ደረጃና አጠቃላይ ደህንነት እንዲሻሻል ማድረግ ነው። ፖሊሲው በግልጽ እንዳስቀመጠው ትኩረቱ በሁለት አቅጣጫ ነው። ይኸውም በአንድ በኩል ልማትን ማፋጠን፣ የተለያዩ ማሕበራዊ አገልግሎቶችን ማስፋፋት፣ ጐጂ ልማዶችንና አስተሳሰቦችን ማስወገድ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሥነተዋልዶ ጤናን በተለይም የቤተሰብ ዕቅድ ትምህርትና አገልግሎትን በማስፋፋት ሕብረተሰቡ የአገልግሎቱ ተጠቃሚ በመሆን ቤተሰቡን በራሱ ኃላፊነትና ውሣኔ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም ትውልድ በማሰብ መመጠን እንዲችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት ነው።

በሌላ በኩል የቤተሰብ ዕቅድን በተመለከተ ዶ/ር አክሊሉ እንደ አንድ አማራጭ በመውሰድ ብዙ እንደታገልን ገልፀው ይህም ስላልተሳካ የተፈጥሮ ሀብትን ወደ መጠቀሙ ትኩረት አድርገን የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ ለማሻሻል እንሞክር ብለዋል። በአገሪቷ ውስጥ የተካሄዱ የተለያዩ ጥናቶች እንደሚያሣዩት የቤተሰብ ዕቅድ ትምህርቱም ሆነ አገልግሎቱ ከተጀመረ ብዙ አሥርት ዓመታትን ያስቆጠረ ቢሆንም በስፋት መስጠት የተጀመረው ግን ከጥቂት አመታት ወዲህ ነው። በማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን እ.ኤ.አ በ2000 የተጠና አገር

አቀና፡ የሥነ ሕዝብና ጤና ጥናት ውጤት እንዳሳየው በወሊድ ዕድሜ /15-49 ዓመት/ ካሉት ሴቶች መካከል 8 በመቶኛው ብቻ የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች ይጠቀሙ እንደነበረ ነው። የጤና ጥበቃ ስታቲስቲክስና በፓዝፋይንደር ኢንተርናሽናል በኩል በቅርቡ በአራት ክልሎች (በትግራይ፣ በኦሮሚያ፣ በአማራና በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦች ሕዝቦች) በተካሄደ ጥናት የቤተሰብ ዕቅድ ተጠቃሚዎች ብዛት ከ20 በመቶ መብለጡን አሳይቷል። ይህም ሆኖ ብዙ ሴቶች የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎች መጠቀም እየፈለጉ፣ ነገር ግን በተለያዩ ምክንያቶች የማይጠቀሙት ሴቶች ቁጥር ከፍተኛ ነው። ይኸው በ2000 የተካሄደው ጥናት ጨምሮ እንዳመለከተው በወሊድ ዕድሜ ካሉ ሴቶች መካከል 36 በመቶው ለመጠቀም ፈላጐቱ እያላቸው ሳይጠቀሙ የቀሩ ናቸው። በቅርብም የተካሄዱ ጥናቶች ተመሣሣይ ውጤት አስመዝግበዋል።

በሕብረተሰብ ውስጥ የቤተሰብ መመጠን ፍላጐት ባለሙያዎች በአራት ደረጃ ከፍለው ያያሉ። የተለያዩ ጥናቶች እንደሚጠቀሙት በአገራችን ያለው ሁኔታ በሁለተኛው ደረጃ ላይ የሚገኝ ነው። ቀደም ብሎ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት እምብዛም ያልተስፋፋበት፣ የሕብረተሰቡ እውቀት አነስተኛ በመሆኑ ሲሆን፣ ቤተሰቡን ለመመጠን ብዙም ፍላጐት አልነበረውም። በአሁኑ ወቅት ከዚያ ደረጃ አልፎ የሕብረተሰቡ አመለካከት የተለወጠበትና ቤተሰቦች ልጅ፣ቸውን መጎነው መውለድ ፍላጐት ያሳዩበት ሁኔታ የተፈጠበረት እና የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎችን ለመጠቀም ከፍተኛ ፍላጐት ያሳዩበት፤ ነገር ግን የተጠቃሚዎች ቁጥር አነስተኛ የሆነበት ደረጃ ላይ ነን። ይህም የሆነበት የመጠቀም ፍላጐት ከአገልግሎት አቅርቦት በላይ በፍጥነት ስለጨመረ ነው።

ስለዚህ በአሁኑ ወቅት በአገራችን የቤሰተብ ዕቅድ መጠቀም ፍላጐት ያላቸው ሴቶች ቁጥር ከፍተኛ ሲሆን፣ ተጠቃሚዎች ግን ጥቂቶች ናቸው። መደረግ ያለበት እና በመደረግም ላይ ያለው ለሕብረተሰቡ ተመጣጣኝ በሆነ ዋጋ ጥራት ያለው የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት በቀላሉ መዳረስ የሚቻልበትን መንገድ ማስፋፋት ነው። በዚህም ወደ ሶስተኛው ደረጃ ማለትም የቤተሰብ ዕቅድ አጠቃቀም በጣም ወደሚጨምርበትና ፍላጐት እያላቸው ላይጠቀሙ የቀሩ ቁጥር አነስተኛ ወደሚሆንበት ደረጃ ለመሸጋገር ይረዳል። በቅርቡ በጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የተጀመረው የጤና ኤክስቴሽን ኘሮግራም በማሕበረሰብ አቀፍ ደረጃ በመሰጠት ላይ ያለውን የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት በማጠናከር በስፋት ለሕብረተሰቡ ለማዳረስ እንደሚያስችል ይታመናል።

የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት መስፋፋት የእናቶችን ሞት ለመቀነስ ይረዳል። ከዚህ በላይ ሴቶች የማሕበራዊና የኢኮኖሚ ሁኔታቸውን ለማሻሻል በእጅጉ ይረዳቸዋል። ከሌሎች አገሮች ልምድ መረዳት እንደሚቻለው ሴቶች ብሎም ሕብረተሰቡ የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ተጠቃሚዎች እንጂ ተገዢዎች አይደሉም። የቤተሰብ ዕቅድ አገልግሎት ማግኘት ከሥነተዋልዶ ጤና መብትም አኳያ የሚታይ ነው። የቤተሰብ ዕቅድ ዘዴዎችን በተመለከተ ዝርዝር መረጃ ከሌሎች ጽሑፎች መመልከቱ ጠቃሚ ነው።

በመጨረሻም የአገራችን የኢኮኖሚና ማሕበራዊ እድገት ደረጃና የሥነ ሕዝብ ሁኔታን ከግምት ውስጥ በማስገባት እንዲሁም ከሌሎች አገሮች ልምድ በመማር ሁለቱንም ማለትም ልማትን በማፋጠንና ጥራት ያለው የሥነተዋልዶ ጤና/የቤተሰብ ምጠና ኘሮግራም በስፋት ለሕብረተሰቡ ማዳረሱ ሕዝቡን ጥሩ የኑሮ ደረጃ ላይ ለማድረስ የሚያስችል አማራጭ ነው እላለሁ።

ሰላም፣ ዲሞክራሲ እና ልማት፤ የልሂቃን ሚና ዛሬና ነገ በኢትዮጵያ

ታደሰ ብሩ ኬርሰሞ*

1. መግቢያ

እበራችና እበራን!

በዛሬዉ ምሽት በዚህ መድረክ «ሰላም፣ ዲሞክራሲ እና ልማት፡ የልሂቃን ሚና ዛሬና ነገ በኢትዮጵያ» በሚል ለአገራችን ኢትዮጵያ የወደፊት ዕጣ ፈንታ ያለኝን ምኞት፣ ተስፋና ስጋት ለእናንተ እበራችና እበራን እንዳቀርብ የጋበዛችሁን የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር ከልብ አመሰግናለሁ::

ይህ ርዕስ ለዉይይት በቀረበበት ወቅት ብሔራዊ ምርጫ የተቃረበበትና በእኔም ሆነ በብዙ ኢዮጵያውያን ወገኖቼ ይህ ምርጫ ከዚህ በፊት ከነበሩት ይበልጥ የአገራችንን የወደፊት ዕጣ ፈንታ በመወሰን ረገድ ወሳኝ ሚና ይኖረዋል የሚል ግምት መኖሩ ለዛሬዉ ዉይይት ጥሩም፣ መጥፎም፣ አጋላሚ ነው:: ጥሩነቱ ርዕሱ ከወቅቱ አንገብጋቢ ጉዳይ ጋር መያያዙ ሲሆን ክፋቱ ደግሞ የምርጫው መቅረብ ሁላችንንም የበለጠ ወገንተኛ /partisan/ ያደርገናል፣ እናም ገለልተኛ የሆነ ውይይት ማድረግ ይከብደን ይሆናል ብዬ ሰግቻለሁ::

የተከበራችሁ ታዳሚዎች በዛሬዉ ዕለት «ሰላም፣ ዲሞክራሲ እና ልማት፡ የልሂቃን ሚና ዛሬና ነገ በኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ የራሴን እጅግ ዉስን የሆነዉን ግንዛቤ ለዉይይት ሳቀርብ ስለርዕሱ ከኔ የበለጠ እዉቀት ያላቸዉ ሰዎች እዚህ አዳራሽ ውስጥ መኖራቸውን እያወቅሁ ነው:: በመሆኑም የማቀርበዉ አስተያየት ለዉይይት መነሻነት ታገለግል እንደሆን እንጂ ርዕሱን በብቃትና በጥልቀት ትዳስሳለች ብዬ በማመን አይደለም::

ንግግሬን ፈር ለማስያዝ በሚከተለዉ አኳኋን ሸንሽኘዋለሁ:: በቅድሚያ «ሰላም»፣ «ዲሞክራሲ»፣ «ልማት» እና «ልሂቃን» ስል ምን ማለቴ እንደሆነ በአጭሩ ከገለፅኩ በኋላ እነዚህ አራት መልካም ነገሮች በአንድ አገር በአንድነት እንዲገኙ መሟላት አለባቸዉ ብዬ የማምንባቸዉን ሁኔታዎች ለመዳሰስ እሞክራለሁ:: ቀጥሎ እነኚህ አራት መልካም ነገሮች እኔ በተረዳሁት መጠን ዛሬ በኢትዮጵያችን ዉስጥ በምን ሁኔታ ላይ እንዳሉ ከገለፅኩ በኋላ ዛሬ ማድረግ ያለብንን ጉዳዮች ከከወንን የ2020ዋ ኢትዮጵያ አገራችን ልትደርስበት ትችላለች ብዬ የማምነዉንና እንድትደርስም አጥብቄ የምመኝዉንና ደረጃ ለማየት እሞክራለሁ::

---

* ዶ/ር ታደሰ ብሩ ኬርሰሞ በኢኮኖሚክ ንድፈ ሀሳቦች የማስተርስ ዲግሪ ከዩክሬይን፤ Inter Disciplinary Doctoral Degree ከፖላንድ የፖሊሽ ሳይንስ አካዳሚ፤ እንዲሁም በሥራ ዓለም አንድ ዓመት ያህል በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፍተኛ ኢኮኖሚስት፤ 6 ዓመት ያህል በዩኒቲ ዩኒቨርስቲ ኮሌጅ የኢኮኖሚክስ ትምህርት ክፍል ኃላፊና መምህር፤ አሁን ደግሞ በኢንሸዩቲቭ አፍሪካ አገር በቀል መያድ የፕሮግራም ማኔጀር ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ::

2. ትርጓሜ

አንዳንድ ደጋግመን የምንጠቀምባቸዉ ቃላት በጣም አሻሚ የሆነ ትርጉም ያላቸው መሆኑ የሚገርም ነው። ከእነዚህ ቃላት አንዱ «ሰላም» ነዉ። ሰላምን ለማደፍረስ የሰላም አጀንዳ ማንገብ እየተደጋገመ መምጣቱ የሰላም ትርጉም ምንኛ የተዛባ መሆኑን ያመለክታል ብዬ አስባለሁ። አደልና ሂትለርም በርካታ የሰላም ጥሪዎችን አድርጓል። በአንድ ወቅት የሶማሊያው መሐመድ ዚያድ ባሬ የሰላም ሰልፍ መርተዋል። የዩጋንዳው ማርሻል ኢዲአሚን ዳዳም ራሳቸዉን የሰላም መከታ አድርገው ሲቆጥሩ ኖረዋል፤ ኒሻንም ተሸልመዋል። እኛም አገር የነበሩና ያሉ መንግሥታት ሁሉ ራሳቸውን የሰላም ጋሻ ጃግሬ አድርገው ሲቆጥሩ ኑረዋል። እነዚህ ሁሉ አገራት ግን ሰላም የተናፈቀባቸው ነበሩ። ለአንዳንዱ «ሰላም» ተቀናቃኞችን ደምስሶ ከጨረሱ በኋላ የሚጣሉት የሌለበት ሁኔታ ማለት ነው፤ ለአንዳንዱ ደግሞ በፍርሃትና ዝምታ መገዛት ማለት ነው። ለሌሎች ደግሞ «ሰላም» ማለት መቻቻልና መደራደር ማለት ነው። በሁሉም ትርጓሜዎች «ሰላም» ቀጣይ የሆነ የአመፃና ሽብር አለመኖር ነው። ለዛሬዉ ዉይይት እኔም ይህንን ቀላል ትርጓሜ ማለትም የአመፃና ሽብር አለመኖርን እጠቀማለሁ፡ ሆኖም የማተኩረዉ በአገር ውስጥ ሰላም /domestic peace/ ላይ ብቻ መሆኑን መግለጽ እወዳለሁ። ዓለም-አቀፍ ሰላም በአገር ውስጥ ሁኔታዎች ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ ቢኖረውም በዋነኛነት የሚወሰነው በአገር ውስጥ ሁኔታዎች ነው ብዬ አምናለሁ።

ለሌላው አወዛጋቢ ቃል «ዲሞክራሲ» ነው። በአሁኑ ጊዜ አብዛኞቹ የዓለም መንግሥታት ራሳቸውን «ዲሞክራሲያዊ» ብለው ያወጁ ናቸው። ምርጫ ፈጽሞ የማይካሄድባቸው ሀገራት ቁጥር በጣም አነስተኛ ነው። በዲሞክራሲ ስም አምባገነን ሥርዓት መዘርጋት ፋሽን ከሆነ ሰንብቷል። የነባሮቹን ዲሞክራሲያዊ አገሮች ተግባርም ከአምባገነኖቹ መለየት አስቸግሯል። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ይሆን ይሆናል «ዲሞክራሲ የሚባል ነገር በዓለም ላይ የለም» ዓይነት አስተያየቶች ከተሰማሩ ሰዎች አንደበት ሲነገር የምንሰማው። አንዳንዶቹማ «እውን አሁን ከምር አሜሪካ ውስጥ ዲሞክራሲ አለ?» «እዉን እንግሊዝ ውስጥ ዲሞክራሲ አለ?» ወዘተ... እያለ «ያሳጥጠናል»። ሰዎች እንዲህ ዓይነቱ ምዕታዊ ድምዳሜ ላይ የሚደርሱት ዲሞክራሲን በውጤቱ መመዘን ስለሚፈልጉ ይመስለኛል። እነዚህ ሰዎች ያልተረዱት ወይም ለረዱት ያልፈለጉት ዲሞክራሲ የአስተዳደር ሥርዓት መሆኑን ነው። በዚያ አልፎ የሚመጣው ውጤት ሳይሆን ሥርዓቱ ነው ዲሞክራሲያዊ ነው ወይም አይደለም የሚባለው። ዲሞክራሲ ከሌሎች የአስተዳደር ሥርዓቶች ሲወዳደር መልካም ውጤቶችን ለማስገኘት የተሻለ አማራጭ ነዉ ተብሎ ይታመናል። ይህ ዕምነት ግን ሁሌ ዕውነት ላይሆን ይችላል። ውጤቱ ጥሩም ይሁን መጥፎ ሥርዓቱ ዲሞክራሲያዊ ከሆነ ውጤቱም ዲሞክራሲያዊ ነው።

ዲሞክራሲ ሥልጣንና ኃላፊነት የዜጎች የሆኑበት፣ እያንዳንዱ ዜጋ ደግሞ ይህንን ሥልጣንና ኃላፊነት በተጥታ አሊያም በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮቹ አማካይነት በተግባር ላይ የሚያውልበት ሥርዓት ነው። ዲሞክራሲ የነፃነት መዋቅር ነው።

ለዲሞክራሲ መስፈን በርካታ መዋቅራዊ ሁኔታዎች መሟላት ያለባቸው ሲሆን የሰብዓዊ መብቶች መከበር፡ የአብላጫዎች መሪነትና የውሳኔን ብዙሃን የመሆን መብት መረጋገጥ፡ የመር ሠራዊቱ በሕዝብ በተመረጠ ሲቪል አስተዳደር ሥር መሆን፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች

በነፃነት መደራጀትና መንቀሳቀስ፤ የነፃና ፍትሃዊ የፖለቲካ ፍክክርና ምርጫ መኖር፤ የዳበረ ነፃ ፕሬስና ሚዲያ መኖር፤ በሕግ የተገደበ ሥልጣን ያለው መንግሥት መኖር፤ በሕግ የተገደበ ሥልጣን ያለው የሕግ አውጭ አካል መኖር፤ ከፖለቲካ ነፃ የሆነ የፍርድና ፍትህ ሥርዓት መሰፈን ዋና ዋናዎቹ ናቸው።።

የእነዚህና መሰል መዋቅሮች መዘርጋትና ተግባር ላይ መዋል ነው አንድን የአስተዳደር ሥርዓት ዲሞክራሲያዊ የሚያደርገው እንጂ ይህንን ሥርዓት አልፎ የመጣውን ውጤት ጥሩነት ብቻ አይደለም። ለዚህም ነው ዲሞክራሲያዊ ሥርዓቶች አንዳንዴ ኢ-ፍትሃዊ ተግባር ሲፈጽሙ እንኳን ዲሞክራሲያዊነታቸውን ጥያቄ ውስጥ ማስገባት ተገቢ የማይሆነው።

እንደ «ሰላም» እና «ዲሞክራሲ» ባይሆንም «ልማት» የሚለውም ቃል አሻሚ ነው። እዚህ ላይ አንድ ቀልድ እንድናገር ይፈቀድልኝ። በሽርሽር ላይ የነበሩ የመንግሥት የኢኮኖሚ አማካሪዎች መንገድ ጠፍቶአቸው ከባዘኑ በኋላ ዋናዉ ኢኮኖሚስት «እስቲ ካርታውን ወዲህ በለው» ብሎ ካርታውን ተቀብሎ ዘርግቶ በጥንቃቄ ከለካ በኋላ በታላቅ የድል አድራጊነት ስሜት «የት እንዳለን በትክክል ደርሼበታለሁ! ይታየኛል እዚያ ማዶ ያለው ተራራ! አናቱ ላይ ነው ያለነው» አለ ይባላል። ይህንን ቀልድ የአፍሪካ መንግሥታት በተደጋጋሚ ይቀልዱታል። ማደጋችንን እና መሻሻላችንን ይነግሩናል፤ እኛ ደግሞ አልታይ፣ አልገባ እያለን እንቸገራለን። በእንዲህ ዓይነቱ ጊዜ የ«ልማት» ትርጉም ቢጠፋብን አይፈረድብንም። ልማት መለካት የሚቻልና መለካትም ያለበት ነው። የማይጨበጥ፣ የማይዳሰስ፣ የማይሸተት፣ የማይቀመስ «ልማት» ልማት ነው ብዬ አልገምትም። በቁጥሮች አጠቃቀምና ትርጓሜ ላይ ጥንቃቄ ሳናደርግ «ቁጥሮች እንደሚያመለክቱት በፍጥነት እያደግን ነው፤ ይህ ደግሞ በእርግጥም መልማታችንን ይመሰክራል» ማለት ከራሱ በላይ ካርታውን በማመን እዚያ ማዶ ያለዉ ተራራ ጫፍ ላይ ነው ያለነው እንዳለዉ የቀልዱ ኢኮኖሚስት መሆን ነው።

በእኔ እምነት ልማት የሕዝቡን የዛሬ ኑሮ እና/ወይም የነገ ተስፋውን በተጨባጭ መለወጥ አለበት። ይህም በአመጋገባችን፣ በጤናችን፣ በአለባበሳችን፣ በትምህርታችን፣ በአኗኗራችን፣ በአስተዳደራችን፣ እየተሻሻለ መምጣት መገለፅ አለበት። ልማት ደግሞ ከራስ ጋር ብቻ ሳይሆን ከጎረቤት ጋርም መነፃፀር አለበት። ሶቭየት ኅብረትና አልባንያ በከፍተኛ ፍጥነት እየለማን ነው እያሉ ራሳቸውን ሲሸነግሉ ቆይተው ዓይኖቻቸውን ገልጠው ጎረቤቶቻቸውን ሲመለከቱ የደረሰባቸውን የስነልቦና ውድቀት ልብ ይሏል።

«ልሂቃን» የሚለዉም ቃል አሻሚ ነዉ። ልሂቃን መንፈሳዊ እና/ ወይም ዓለማዊ ኃይል ባላቸው ቡድኖች፣ ማኅበራትና ተቋማት ውስጥ ባላቸው ከፍተኛ ተሰሚነት ምክንያት የግል ውሳኔያቸው በሀገሪቱ አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታ ያላቸው ሰዎችን ያጠቃልላል። ይህም ማለት በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በሳይንስ፣ በምርምር፣ በመንፈሳዊ ጉዳዮች፣ በሃይማኖቶች፣ በሙያ ማኅበራት፣ ወዘተ... መስክ ተደማጭነት ያገኙ - አብዛኛውን ጊዜ አመራሩንም የያዙትን - ሰዎች ያመለክታል። የፖለቲካ ልሂቃን፣ የኢኮኖሚ ልሂቃን፣ መንፈሳዊ ልሂቃን፣ የምሁራን ልሂቃን፣ የሃይማኖት ልሂቃን፣ የትምህርት ልሂቃን፣ የባህል ልሂቃን፣ ወዘተ... እያልን ብሔራዊ ልሂቃንን ከፋፍለን እያንዳንዱን በተናጠል ልናጠናው ብንችልም ሁሉንም የሚያስባስባቸው አንድ የጋራ ባሕሪይ

ግን ከላይ እንደተገለፀው የግል ሃሳባቸውና ውሳኔያቸው ፈጣን የሕዝብ ድጋፍን በማስገኘት በአገራቱ አጠቃላይ ፖለቲካ ላይ ጉልህ ተፅዕኖ ማሳደር የሚችል መሆኑ ነው። እነዚህ ግለሰቦች በእንግሊዝኛ ቋንቋ «ኤሊት» የሚባሉት ሲሆኑ ትክክለኛ የአማርኛ አቻ ስለመሆኑ እርግጠኛ ባልሆንም ከአቶ አንዳርጋቸው ጽጌ[1] በመዋስ «ልሂቃን» የሚለዉን ቃል እንድጠቀም ፍቀዱልኝ። ልሂቃን ከጠቅላላው ሕዝብ አንባር ሲታዩ ቁጥራቸው እጅግ አነስተኛ ነው።

«ፖለቲካ የተቀነባበረ የቡድን ፍላጎት መግለጫ ነው። አንድ የተወሰነ የኅብረተሰብ ክፍል የተለየ ፍላጎት ካለው ያንን የሚያስፈፅም የፖለቲካ ድርጅት ይነሳል። ግለሰብ ታጋይ ይነሳል፣ ይወድቃል፣ ይለወጣል፣ ይሞታል፣ ያ የሕዝብ ፋላጎት እስካልረካ ድረስ ግን ትግሉ ይቀጥላል። በመሆኑም የአንድ አገር ፖለቲካ የሚወሰነዉ ባሉት የተለያዩ ማኅበራዊ ፍላጎቶችና ቅራኔዎች እንጂ በግለሰቦች አይደለም» የሚል ክርክር እንደሚነሳ አውቃለሁ። ሆኖም «የሕዝቡን ፍላጎቶች» በቅድሚያ የሚገነዘቡት፣ ሕዝቡንም ስለ «ፋላጎቶቹ» የሚያስረዱትና ለትግል የሚያንቀሳቅሱት ግለሰብ ልሂቃን ናቸው፤ በኋላም ትግሉን የሚመሩት እነሱው በመሆናቸው የክርክሩ ጭብጥ «አልሸሹም ዞር አሉ» ነው።

ልሂቃን የሚናገሩት፣ የሚደራደሩት፣ የሚፈራረሙት፣ እንወክለዋለን በሚሉት የኅብረተሰብ ክፍልና በድርጅቶቻቸው ስም ይሁን እንጂ እንወክለዋለን በሚሉት ሕዝብ፣ በድርጅቶቻቸውና በእነርሱ በራሳቸው ውስጣዊ የግል ፋላጎቶች እንዲሁም በፍላጎቶችና በሚፈጽሙት ተግባር መካከል መጣመር እንዲኖር የግድ አይደለም። የሚመሩት ኃይል ፍላጎት በልሂቃኑ ስታራቴጂያዊ ግብ ላይ ተጽዕኖ ቢኖረውም ልሂቃን የዕለት ተዕለት ተግባራቸዉን በሚመስላቸዉ መንገድ ለመምራት አንባራዊ ነፃነት ከሌላቸዉ ልሂቃን መሆናቸዉ ይቀራል፣ ትግሉም በመሪ እጦት ተዳክሞ ይከስማል።

ስለ ልሂቃን ሚና ማሳየት የሕዝብን ሚና ማሳነስ የሚመስላቸው ሞልተዋል። እኔ ይህ አስተሳሰብ ትክክል አይመስለኝም። ልሂቃን ራሳቸው የሚወጡት ከሕዝብ ነውና የሕዝቡን ስነ-ልቦና፣ ሕልምና ርዕይ ይዘዉ መነሳታቸዉ የግድ ነዉ። በሌላ በኩል ደግሞ «ሕዝብ መሪዎችን ይመርጣል» ሲባል ምን ማለት እንደሆነ አንዳንዴ የምንዘነጋው ይመስለኛል። አብዛኛውን ጊዜ ሕዝብ መሪዎቹን አይመርጥም፣ መሪዎች ራሳቸውን ነው የሚመርጡት። በዲሞክራሲ ብቻ ነው ሕዝብ መሪዎቹን የመምረጥ መብት ያለው። ሆኖም በዴሞክራሲም ቢሆን ሕዝብ የሚመርጠው «ልምራችሁ» ብለው ከተነሱ ልሂቃን መካከል መሆኑ ግልጽ ሊሆን ይገባል። በዴሞክራሲም ቢሆን «ልምራችሁ» ያላለን ሰው «ምራን» ተብሎ አይመረጥም።

እርግጥ ነው ልሂቃን ከደጋፊዎቻቸው ተዕፅኖ ሙሉ በሙሉ ነፃ አይደሉም። ተከታዬች መሪዎቻቸው የሚታገሉት ለሚወክሉት ሕዝብ ጥቅም እንደሆነና ለሕዝቡም ፍላጎቶች ተገዥ እንደሆኑ ማመን ይኖርባቸዋል። ልሂቃንም ይህንን የሕዝብ አመኔታና እምነት ለመጠበቅ ሲሉ ተግባራቸው ገሃድ በሆነ መንገድ ከተከታዮቻቸው አጠቃላይ ስሜት እንዳይርቅ ይጥራሉ። አለበዚያ ተከታዮቻቸው በከሃዲነት ሊያወግዟቸውና ለአንጃ መፈጠር አመቺ

[1] አንዳርጋቸው ጽጌ፣ ጥር 1977፣ ነጻነትን የሚያዉቅ «ነጻ አዉጭ» ስልጣኔ፣ ዲሞክራሲ እና ብልጽግና፣ የፖለቲካ ልሂቃኑ ሚና በዘመናዊት ኢትዮጵያ።

ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል። ለልሂቃን አስጊ ነገር ተቃዋሚ ልሂቅ (አንጃ) ከተከታዮቻቸው ውስጥ ሲወጣ ነው። እንዲህ አይነቱ ከጉያ የወጣ ተቃዋሚ ልሂቅ የደጋፊዎችን ልብ በቀላሉ ማሸፈት ይችላል። ስለዚህም ነው በአንጃዎች መካከል ያለው ቅራኔ እጅግ የከረረ የሚሆነው «... ወደው የጠሉት ሰዉ ምነው ሰው አይመስል?» እንዳለችው ዘፋኝ ማለት ነው።

እንግዲህ የዛሬ ንግግሬ አሻሚ፣ ሆኖም ግን መልካም ስለሆኑ አራት ቁም ነገሮች ነው - ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ ልማት እና የልሂቃን ጎብረት።

3. መንደርደርያ

የ2020 ኢትዮጵያ ካለ ዲሞክራሲ እና ልማት ሰላምን፤ ካለ ሰላም እና ልማት ዲሞክራሲን፤ ካለ ሰላም እና ዲሞክራሲ ልማትን፣ ባጠቃላይ ደግሞ ካለልሂቃን ጎብረት ሰላም፣ ዲሞክራሲና ልማት ማምጣት በእጅጉ ይቸግራታል ብዬ ስለማምን ፈተናዉ ቢበዛም አራቱንም በጥምረት የምናገኝበትን መንገድ መፈልግ አለብን ብዬ አምናለሁ። ለዚህም ነው ዛሬ አራቱንም በጥምረት ላነሳቸው የደፈርኩት።

በበኩሌ ከመጀመርያው ዙር ርዕይ 2020 ውይይቶች ያገኘሁት ትልቅ ቁምነገር «ለችግሮቻችን መፍትሔ ማግኘት የምንችለው ልዩነቶቻችንን በማጥበብ አገራዊ ርዕይ ኑሮን ለጋራ ግብ በጎብረት ስንቀሳቀስ ነዉ» የሚለው ከድሮም ጀምሮ የነበረኝ ሃሳብ መጠናከሩ ነው።

ከዚህ በፊት በተደረገ ውይይቶች በስፋት እንደተወሳው የኢትዮጵያ ልሂቃን ልዩነቶቻቸዉን ከማጥበብ ይልቅ ማስፋት ላይ ጊዜና ንብረት ያጠፋሉ።

መንግስታችንም ልዩነቶችን በማስፋት ላይ ተጠምዶ ቆይቶል። የተማሩ ሰዎችም «የልዩነቶች መኖር ለእድገት አስፈላጊ ነው» ሲባል «ልዩነቶች እስከምን?» ሳይሉ በደፈናው የተቀበሉት ይመስላል። እኔ በሰራሁበት አንድ መ/ቤት በነበርኩት ክፍል በአንድ ወቅት የነበርን ሰዎች በሃሳብ የምንግባባና ልዩነቶቻችንን በውይይት የምንፈታ ስለነበርን ለዓመታት ሰው ሳይከሰስና ሳይቀጣ በመቆየቱ ያልተደሰቱ አለቃችን «ይህ ክፍል ልዩነት ያንሰዋል» በማለት ልዩነትን «በጥበብ» በማስገባታቸዉ ዛሬ ያ ክፍል በንትርክና በብጥብጥ ተዳክሞ፣ መዳከሙንም መቀበል አቅቶት፣ «ከቀድሞዉ ዛሬ እሻላለሁ» እያለ ሲከራከር ክፍሉ ራሱ ትንሽ ኢትዮጵያን ሆኖ ይታየኛል።

ስለገበያ ኢኮኖሚም ያለን ግንዛቤ ልዩነቶችን ከማስፋት ጋር የተቀናጀ ይመስለኛል። ኢትዮጵያ ዉስጥ «ፉክክር /competition/ የገበያ ኢኮኖሚ ሞተር ነው» ማለት ጎብረት /cooperation/ የገበያ ኢኮኖሚ እንቅፋት ነው እንደማለት ተደርጎ የሚወሰድ ይመስላል። ስለዚህም ይሆናል ስለውድድርና ፉክክር ማነስ ስናነሳ ስለጎብረት ማነስም አብረን ብዙ ጊዜ የማናነሳው። ኢትዮጵያ ውስጥ ስለጎብረት መናገር የሶሻሊስት አስተሳሰብ ተደርጎ ይቆጠራል። ውድድርና ጎብረት ተደጋጋፊ መሆናቸውን ማወቅ የተሳነን ይመስላል።

ስለአገር ስላምና ልማት ስናስብ ልዩነቶቻችን ላይ ሳይሆን አንድነታችን ላይ፣ የእርስ በርስ ፉክክር ላይ ሳይሆን ጎብረት ላይ፣ ማትኮር ይኖርብናል ብዬ አምናለሁ። ለዚህ የሚያበቃን ደግሞ «ስፊው ሕዝብ» የሚባል የማይጨበጥ አካል ሳይሆን በተጨባጭ እየኖርን ያለነው ዜጎች እናንተና እኔ ነን። ሕዝብ ባጠቃላይ ሳይሆን ግለሰብ የጥናታችን መነሻ ሊሆን ይገባዋል።

በእኔ እምነት የሀገርን ዕጣ ፋንታ በመወሰን ረገድ ግለሰቦች ወሳኝ ሚና አላቸው። በተለይም ደግሞ በዕውቀታቸው፣ በችሎታቸው፣ በመነያቸው፣ በማዕረጋቸው፣ በክብራቸው፣ በሃብታቸው፣ ወዘተ... ምክንያት የላቀ ተሰሚነት ያገኙ ግለሰቦች፡ ማለትም የልሂቃን ሚና ወሳኝ ነው ብዬ አምናለሁ።

4. የልሂቃን አደረጃጀት

በኔ ግምት የአንድን አገር አጠቃላይ የፖለቲካ ሁኔታ ከሚወስኑ ነገሮች አንዱ ምናልባትም ዋነኛዉ - በልሂቃን መካከል ያሉት ግንኙነቶች መጥበቅ ወይም መላላት ነው። በአንዲት አገር ያለው የልሂቃን አደረጃጀት ለዚያች አገር ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማት ወሳኝ ነው የሚል እምነት አለኝ። አንዲት አገር የተበታተኑና እርስ በእርሳቸው የሚባረሩ ወይም በርዕዮተ ዓለም የተሳሰሩ፣ አሊያም በድርድር የተቀራረቡ ልሂቃን ያላት ልትሆን ትችላለች።

4.1. የተበታተኑና እርስ በእርሳቸው የሚባረሩ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ (Disunified National Elite)

በአንዲህ ዓይነቱ ማኅበረተሰብ ውስጥ ያሉ ተባራሪ ልሂቃን መካከል ከፍተኛ የሆነ አለመተማመን በመኖሩ በግለሰብ ደረጃ የመገናኘትና በልዩነቶች ላይ የመነጋገር ፈቃደኝነት የለም። በእንዲህ ዓይነቱ ማኅበረሰብ ፖለቲካ ማለት ሸር፣ ብልጠት፣ ጠልፎ መጣልና ገፍትሮ መወርወር፣ ነው። የአንዱ ድል የሌላው ውድቀት /zero – sum game/ ከመሆንም ባለፈ ተያይዞ መውደቅም /negative-sum game/ ይኖራል። «ፖለቲካ ቆሻሻ ጨዋታ ነው» «ፖለቲካና ኮረንቲን በሩቁ ነው» የመሳሰሉ አባባሎች እንዲህ ዓይነት ልሂቃን ያለባቸውን ሥርዓቶች ከመታዘብ የመነሬዉ አባባሎች ይመስለኛል። እያንዳንዱ ልሂቅ «ሰላም የሚገኘው ጠላትን ደምስሶ በመጨረስ ነው» ብሎ ሰለሚያምን ለሰላም የሚያደርገው ትግል ሌሎች ልሂቃትን በማጥፋት ማረጋገጥ ይፈልጋል። ስለዚህ እንዲህ ዓይነቱ ማኅበረሰብ አለመረጋጋት የሰፈነበት፡ በመሳሪያ ኃይል የታገዙ አመፆችና የመንግስት ግልበጣዎች የበዙበት ይሆናል። በእንዲህ ዓይነት ማኅበረሰብ ውስጥ ዴሞክራሲን እንኳን መተርጎም ማለምም ያስቸግራል፡ ሰላም አይኖርም፡ ልማትም እጅግ የተንተባተበ ይሆናል። ሌላው ክፋቱ ደግሞ በእንዲህ ዓይነት አገር ውስጥ ያሉ ልባም ሰዎች ራሳቸውን ከፖለቲካ የሚያገለሉ ከመሆኑም በላይ ፖለቲካን በአጠቃላይ የሚጠሉ፡ ትችቶታቸውም በምፀት የተሞሉ ይሆናሉ። ይህ ደግሞ የተማረው ክፍል ለማኅበረሰቡ ሊያበረክት ይገባው የነበረውን ያህል እንዳያበረክት ያደርገዋል። ልባም ሰዎች ከፖለቲካ ጨዋታው ራሳቸውን በማግለላቸውም የመጠላለቱን ጨዋታ በአሸናፊነት የሚወጡት ጨካኞችና ምህረት የለሾች፡ መሰሪዎችና ቂመኞች ናቸው። እናም ፖለቲከኛ ማለት ተንኮለኛ፣ መሰሪ፣ ቀጣፊ፣ ማለት ነው በሚል ቅንና ደግ አላሚዎች የማይመኙት

ሙያ ይሆናል። ብዙዎቹ ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገሮች በተለይም ደግሞ የአፍሪካ ቀንድ አገሮች በእንዲህ ዓይነቱ ልሂቃን የተገነቡ በመሆናቸው ሰላምም፣ ዴሞክራሲም፣ ልማትም፣ ርቀዋቸው በአራቱም የዓለም ጫራ ሆነዋል።

4.2. በርዕዮተ-ዓለም የተሳሰሩ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ (Ideologically Unified National Elite)

በአንድ ማኅበረሰብ ያሉ ልሂቃን ለአንድ ርዕዮተ ዓለም የተገዙ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ገዥ ርዕዮተ-ዓለም ለሁሉም ጥያቄዎች የማያሻማ መልስ ያለው ተደርጎ ስለሚወሰድ ልሂቅነት የሚወሰነው ርዕዮተ-ዓለሙን በመረዳትና ተግባራዊ በማድረግ ብቃት ይሆናል። ሃይማኖቶች ለዘመናት ይህን ሚና ሲጫወቱ ቆይተዋል። ቆይቶ ደግሞ ሊኒኒዝም፣ ስታሊኒዝም፣ ማኦኢዝም፣ ...፣ ወዘተ፣ በተመሳሳይ መንገድ አገልግለዋል። አሁን ደግሞ በአገራችን «አብዮታዊ ዲሞክራሲ» ተመሳሳይ ሚና ለመጫወት የሚሞክር ይመስላል። የዚህ ርዕዮተ-ዓለም /ሃይማኖት/ ዋናው ሚና ሁሉንም ዜጋ በአንድ አይነት ቅርጽ ሞርዶ ማውጣት ነው። በርዕዮተ-ዓለም የተሳሰሩ /ideologically unified/ ልሂቃን ባሉበት ማኅበረሰብ የርዕዮተ-ዓለሙ አራማጅ መሪ ድርጅት መኖር የግድ ነው። ከዚህ ድርጅት የተለየ ሌላ ድርጅት እንዲኖር አያስፈልግም፣ አይፈቀድምም። የድርጅቱ መሪዎች ርዕዮተ-ዓለሙ በደንብ የገባቸውና የመተርጎም ብቃት ያላቸው ሰዎች ናቸው። ሌሎች አውራዉ ልሁቅ ያለውን የሚያሙ፣ ያሰበውን የሚያስቡ፣ ናቸው። በእንዲህ ዓይነት ማኅበረሰብ ፖለቲካ ማለት መሪውን ርዕዮተ-ዓለም ማጥናት፣ ማንጠር፣ መተንተን፣ መፈትፈት፣ ... «ወጉር መሰንጠቅ»፣ ማለት ነው። የእዚህ ፖለቲከኛ ሽምዳድ፣ ባህታዊ፣ ጥራዘ ነጠቅ እና ራሱን በማርቀቅ የሚመሳያት ነው። እንዲህ አይነቱ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ የሃሳብ ልዩነቶችን ፈጽሞ የማያስተናግድ በመሆኑ ዲሞክራሲ አይታሰብም። እንዲህ ዓይነቱ ማኅበረሰብ ሰላም የሰፈነበት ሊሆን ይችላል። በተወሰነ መጠንም ልማት ሊኖር ይችላል። ልማቱ ግን በነባነት ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ ጠንካራ መሠረት አይኖረውም። ቫቲካን እንደ አገር ለማየት ካልቸገርን ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ናት። የቀድሞዋ አልባኒያና ሶቭየት ኅብረትም ተቀራራቢ ምሳሌዎች ናቸው። ዛሬ ደግሞ ሰሜን ኮሪያ፣ ኩባ፣ ሳዑዲ አረቢያ፣ ሊቢያ፣ ወዘተ... እያልን መዘርዘር እንችላለን።

4.3. በድርድር የተቀራረቡ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ (Consensually Unified National Elite)

በአንዳንድ አገሮች ያሉ ልሂቃን ከእርስ በርሳቸው መጠፋፋት ይልቅ ልዩነቶቻቸውን በማጥበብ መደራደርን፣ ሊደራደሩ ባልቻሉባቸው ጉዳዮች ደግሞ የሕዝብ ዳኝነትን ይመርጣሉ።

በአንጃዎች መካከል ተመጣጣኝ ኃይል ሲኖርና አንዱ አንጃ ሌሎቹን ለማጥፋት የሞራል እና/ወይም የኃይል ብልጫ በሚያጣበት ጊዜ ልሂቃን ልዩነቶቻቸው ወደ ግጭት እንዳያመሩ መደራደርን ይመርጣሉ። አብዛኛውን ጊዜ እንዲህ ዓይነቶቹ ድርድሮች በግለሰብ ደረጃ ተጀምረው በድርጅቶች ይቋጫሉ። ቀስ በቀስም ድርድር የሚደረግበት አጠቃላይ ደንብና

ሥርዓት ወጥተው በሁለም ወይም በአብዛኛዎቹ ልሂቃን ይከበራሉ። ለድርድር የማያመቹ ጉዳዮች (ለምሳሌ፣ መንበረ-ሥልጣን) የሚወሰኑበትን ሥርዓት ያበጃሉ (ለምሳሌ፣ ተራ መግባት ወይም ምርጫ)። ልሂቃኑ በድርድር መግባባት ያልቻሉበት ጉዳይ በሕዝብ ድምጽ እንዲወሰን ሲስማሙ ፖለቲካ ድርድርም፣ ፉክክርም፣ ስለሚሆን የጠለቀ እውቀት የሚጠይቅ የሙያ መስክ ይሆናል። በዚህ ዓይነት ማኅበረሰብ ፖለቲካ አሸናፊና ተሸናፊ ያለበት ቢሆንም እንኳን፣ ካለመወዳደር ተወዳድሮ መሸነፍ የሚመረጥበት ጨዋታ ተደርጎ ስለሚወሰድ፣ ማሸነፍ በጣም የሚፈለግ ቢሆንም፣ መሸነፍ ግን የዚያን ያህል የሚመር አይሆንም። በሌላ አነጋገር ፖለቲካ ትርፍ ያለዉ ጨዋታ /positive sum game/ ነው። በዚህ ዓይነት ሁኔታ ፖለቲከኛ ከእያንዳንዱ ድርድርና ክርክር የራሱን ወገን ጥቅም ለማብዛት ወይም የራሱን ወገን ጉዳት ለመቀነስ የሚጥር፣ ሃሳቡን በቀላል ቋንቋ ለአብዛኛው ሰው በሚገባው አሳማኝ ምክንያት ማቅረብ የሚችል፣ አንደበተ ርቱዕ ጠበቃ መሆን ይኖርበታል። በዚህም ምክንያት ፖለቲካ ታጋሽነትና ብልህነትን የሚጠይቅ ሕዳናት ሲያድጉ መሆን የሚመኙት የተከበረ ሙያ ነው። ከእንዲህ ዓይነቱ ውድድርም በአሸናፊነት የሚወጡት አርቆ-አሳቢዎች፣ አስተዋዮች፣ ታጋሾቹና አንደበተ-ርቱአቹ ልሂቃን ይሆናሉ። ለእንደዚህ ዓይነቱ ማኅበረሰብ ሰላም የድርደርና የመቻቻል ውጤት ነው። እንዲህ ዓይነቱ ማኅበረሰብ ሰላምና ዲሞክራሲን ለማስፈን የተመቻቹ ሁኔታዎች ላይ ነዉ ማለት ይቻላል። የተለያዩ ሃሳቦች በነፃነት የመንሸራሸራቸው ዕድልም የሰፋ በመሆኑ ለእድገት አመቺ ነው።

በድርድር የተቀራረቡ ልሂቃን ያለው ማኅበረሰብ በሁለት ጽንፎች ማለትም በአንድ ጽንፍ እርስ-በርሳቸው የሚባረሩ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ፣ በሌላኛው ጽንፍ ደግሞ በርዕዮተ-ዓለም የተሳሰሩ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ፣ መካከል ላይ የሚገኝ በመሆኑ የሁለቱንም ባህርያት በተለያየ መጠን የያዘ «ማክያቶ» ነዉ። ነጭ ማክያቶ፣ መካከለኛ ማክያቶ እና ጥቁር ማክያቶ እንዳለ ሁሉ አንዳንድ ጊዜ ተፎካካሪዎች ጠላቶች መስለው የሚታዩና ድርድሮችም አስቸጋሪ ሲሆኑ (ለምሳሌ፤ ኢጣሊያ፣ ስፔን፣ እስራኤል፣ ወዘተ...) ሌላ ቦታ ደግሞ በተፎካካሪዎቹ ልሂቃን መካከል ያለው ልዩነት ለይቶ ማውጣት እስከሚያቅት ደረስ ሊመሳሰሉብን ይችላሉ (ለምሳሌ፤ ዩ.ኤስ. አሜሪካና እንግሊዝ)።

ለልማት ሰላም፣ ዲሞክራሲ እና ልሂቃን በአንድነት መገኘት አስፈላጊ ግን በቂ ያልሆነ ሁኔታ ነው። «በቂ ያልሆነ» የተባለው ዲሞክራሲ ቀደም ሲል የዘረዘርኳቸውና ሌሎችም ያልጠቀስኳቸው መዋቅራዊ ሁኔታዎችን ስለሚፈልግ ነው። እዚህ ላይ አጽንኦት ልሰጠበት የምፈልገው ጉዳይ ግን ጥሩ ሕገመንግስት፣ ጥሩ የምርጫ ህግ እና ግልፅና ፍትሃዊ ምርጫ፣ ወዘተ... ቢኖሩም እንኳን ልሂቃኑ ለድርድር የተዘጋጁ ካልሆኑ ዲሞክራሲ መኖር የማይችል መሆኑ ነው።

5. በድርድር የተቀራረቡ ልሂቃን ያሉበት ማኅበረሰብ እንዴት መገንባት ይቻላል?

ለመደራደርና በሰላማዊ መንገድ ለመወዳደር ዝግጁ የሆኑ ልሂቃን ያሉበት ማህበረሰብን ሆን ብሎ /deliberately/ መገንባት ይቻላልን? በራሱ የሚመጣስ ከሆነ እንዴት ነው የሚመጣው? ከየት ነው እንዲህ ዓይነቶቹ ልሂቃን የሚገኙት? ከሁለም በላይ ደግሞ እርስ-በርሳቸው

የሚባረሩ ልሂቃን ካለበት ማህበረሰብ ተደራጻሪ ልሂቃን ወደአለበት ማኅበረሰብ እንዴት ነው መሸጋገር የሚቻለው? የሚሉት ጥያቄዎች መሠረታዊ ናቸው::

ማንኛውንም ማኅበረሰብ በእውቅ /deliberately/ መገንባት ስለመቻሉ በጣም አከራካሪ ቢሆንም አወቀውም ይሁን ሳያወቁ ልሂቃን የሚያደርጉት ግን ይህንኑ ነው:: አንዳንድ ተመራማሪዎች (ለምሳሌ: ሂግሌይ፣ ገንትኸር፣ በርተን፣ ሼሴሎቪች[4]፣ ወዘተ...) እንደሚሉት ተጣባሪ ልሂቃን ያለበት ማኅበረሰብ በድርድርና ውድድር ወደሚለገበቡበት ማህበረሰብ ከሚከተሉት በአንደኛው መንገድ ሊሸጋገር ይችላል::

5.1. የውጭ ኃይል ተጽዕኖ

አንዲት አገር ጉልህ የውጭ ተዕዕና ካለባት የአገሪቱ ልሂቃን ቢያንስ በቁጥር የበዙቱ የውጪን ጠላት በጋራ ለመዋጋት ልዩነታቸውን ወደጎን በመተው የመቻቻል ዝንባሌ ያሳያሉ:: ይህ በተለይ በቅኝ ግዛት ዘመን በጉልህ የታየ ክስተት ነበር:: እንዲህ ዓይነቱ መቻቻል አብዛኛውን ጊዜ ከጋራ ድል በኋላ የሚፈርስ ቢሆንም አንዳንዴ ከድል በኋላም ቀጥሎ ለዘላቂ ድርድር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል:: የአሜሪካ፣ የካናዳ፣ የኒውዘርላንድ፣ የአውስትራሊያ፣ የአየርላንድ፣ የሕንድ፣ ወዘተ... ብሔራዊ ልሂቃንና እነሱን ተከትለው የመጡት ዲሞክራሲያዊ ሥርዓቶች በዚህ መንገድ የተገኙ ናቸው:: በኢትዮጵያ ግን በቅርብ ጊዜ እንኳን ከኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት በአሸናፊነት ብንወጣም ይህ ሊሆን አልቻለም::

5.2. ቀስ-በቀስ መሃል ላይ የመሰባሰብ ዝንባሌ

ያለውን ሥርዓት አፍርሶ በሌላ የመለወጥ ዓላማ ያላቸው የግራም ሆነ የቀኝ አክራሪዎች ፈጣን ድል ካልተቀዳጁ በስተቀር ጽንፈኛ አቋማቸው እያደር የመሟሸሽ አዝማሚያ አለው:: አክራሪነት ለአጭር ጊዜ በተለይም ለወጣቱ ትውልድ ማራኪ ሊሆን ቢችልም አንዱ አክራሪ ከሌላኛው ጽንፍ አክራሪ የማይሻል መሆኑን ደጋፊዎች መገንዘባቸዉ ስለማይቀር እና ተደጋጋሚ ሽንፈት የሚያስከትለውም ኪሳራ ከፍተኛ በመሆኑ መሃል መንገድ ላይ ተገናኝተው ግራ-ቀመስ ወይም ቀኝ-ቀመስ መንግሥት በመመሥረት ጥያቄ ላይ መሚገትን ይመርጣሉ:: በአንድ ወቅት አክራሪ የነበሩ የዴንማርክ፣ የኖርዌይ፣ የኢጣሊያን፣ የፈረንሳይና

---

[4] Higley, J & Gunther, R. Elite and Democratic consolidation in Latin America and Southern Europe Cambridge university press, 1991
- "Elite Settlements" American Sociological Review, 1987 Vol. 52, June, pp.295-307
Burton M.G. & J. Higley "The Elite Variable in Democratic Transitions and Breakdowns" American Sociological Review, 1989 Vol.54, February, pp.17-32.
Wesolowski, W ."Some Problems of Political Representation in Contemporary Poland." Center for Mediterranean Studies. University of Bristol, Sep. 1993
- "The Role of Political Elites in Transition from Communism to Democracy: The Case of Poland." SISYPHUS, Social Studies 2 (VIII), 1992
- "Transition from Authoritarianism to Democracy" Social Research Vol.57, No.2, 1990

የጃፓን ኮሚኒስቶችና ሩሺስቶች አቋሞቻቸውን አለዝበው በሃገራቸው ፓርላማና መንግሥታት ቁልፍ ቦታዎች በመያዝ አስተዳደሩን ወደእነሱ ለመሳብ መጣር ከጀመሩ ውሎ አድሯል። በዚህም አንዳንዶቹ ጥሩ ውጤት አስገኝተዋል።

5.3. ሰጥቶ መቀበል

ተደጋግሞ ሲፈፀም ባይታይም ከበለጠ ኪሳራ ለመዳን ሲሉ አንዳንዴ በሥልጣን ላይ ያሉ ልሂቃን ሥልጣናቸውን በድርድር ለተፋላሚዎቻቸው ሊለቁ ወይም ልዩነቶቻቸው እንዳሉ ሆነው በጋራ ለመስራት ሊስማሙ ይችላሉ። በእንግሊዝ በ1688-1689[5]፣ በስዊድን በ1809 በቡርዣዎችና በመሳፍንቱ መካከል ድርድር በመደረጉ በፈረንሳይ የፈነዳውን አይነት ሥር-ነቀል የቡርዣ አብዮት ሳያስፈልግ የሥርዓተ-ማኅበር ለውጥ ተደርጓል።

በድርደሩ መሳፍንቱ ሥልጣናቸውን ለቀው ክብራቸውን አስጠብቀዋል። በአዲሱ ሥርዓትም አንዳንድ የቀድሞ ማኅበራዊና ባህላዊ እሴቶችን የመጠበቅ ልዩ ስልጣን መሳፍንቱ በድርድሩ አግኝተዋል። በኮሎምቢያ 1957-1958 ሥልጣን ላይ የነበሩ ልሂቃን ቁልፍ ከሆኑ የመንግስት ሥልጣናት ግማሹን ለተቃዋሚዎች በመልቀቅ የፕሬዜዳንትነት ሥልጣንን በፈረቃ ለለዋወጡ ተስማምተዋል።

በቬንዙዌላ 1958 ሥልጣን ላይ የነበረው ልሁቅ ከተቃዋሚው ጋር ተደራድሮ ከፊል ሥልጣኑን በመልቀቁ ሊከሰል ይችል የነበረውን ከፍተኛ የደም መፍሰስ በመቀነስ ለዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረት ጥሏል። በፖላንድ 1989 ሥልጣን ላይ የነበረው ኮሚኒስት ልሁቅ ከተቃዋሚው «ሶሊዳሪቲ» ልሂቃን ጋር በክብ ጠረጴዛ ዙሪያ ተደራደሮ ፈርሞ ስልጣኑን ለቋል።

በተለይ የፖላንድ የክብ ጠረጴዛ ዙርያ ድርድር አስደናቂ ክስተት ነበር። በ1989 የፖላንድ ኮሚኒስት ሥልጣኑን ላለመልቀቅ መግደርደር የሚያስችለው በቂ ኃይል ነበረው። ወታደራዊ ኃይል በፓርቲ አመራር ሥር ነበር። ሶሊዳሪቲ ግን የታጠቀ ሠራዊት አልነበረውም። ኮሚኒስቱ ወገን ወታደራዊ ኃይልን መጠቀም ባይፈልግ ወይም ባይችል እንኳን እንደ ሶቭየት ኅብረቱ ኮሚንስት ፓርቲ «ሽግግሩን የምመራው እኔ ነኝ»፣ በሂደት ራሴም እየተለወጥኩ ነኝ፣ ማለትና ዕድሜን ጥቂት ማርዘም ይችል ነበር። በዚህ ፈንታ በስምምነት ሥልጣኑን በመልቀቁ አገሩን ከአደጋ አድኗል፤ ክብሩንም አስጠብቋል። ዛሬ ይኸውም ልሂቅ አቋሙን ከልሶና አለዝቦ ሶሻል ዴሞክራት ሆኖ በመቅረብ በዲሞክራሲያዊ ሠድድር በማሸነፍ በርካታ የስልጣን ወንበሮችን መልሶ ይዟል።

በ1994 የደቡብ አፍሪካ ዘረኛ መንግሥት መሪ ዲ. ክለርክና የነጻነት ተሟጋቹ ኔልሰን ማንዴላ እጅ ለእጅ ተጨባብጠው ወንበረ ሥልጣንን በመለዋወጥ የሰላምን የናቬል ሽልማት በጋራ አግኝተዋል። ዉዝግቡ በዚህ መንገድ በማለቁ የደቡብ አፍሪቃ ነጮች ከጥቁሮች ሊደርስባቸው ይችል የነበረውን የበቀል እርምጃ እንዳይኖር አድርገዋል። የደቡብ አፍሪቃ

[5] ዓመቶች በሙሉ በአዉሮፓዉያን አቆጣጠር ናቸው።

ጥቂሮች ደግሞ ነጮችን ቢያባርሩ ኖሮ አገራቸው ሊደርስባት ይችል የነበረውን ኪሳራ አንዳይደርስ አድርገዋል፡ «ሰጥቶ መቀበል» ይሏል ይህ ነው!

ከላይ እንደተብራራው «ግዥ መደብ በምንም ዓይነት ቢሆን ሥልጣኑን በፍቃዱ አይለቅም» የሚለው አባባል አብዛኛውን ጊዜ ትክክል ቢሆንም ሙሉ በሙሉና ሁሌ እውነት አለመሆኑን ያሳያል:: በሥልጣን ላይ ያሉ ልሂቃን ተቃዋሚዎቻቸውን በጦር ኃይል ከማጥፋት፣ ይህ ባይቻል ደግሞ በሚያሳዝን መልኩ በሶማሊያና ሩዋንዳ እንደታየዉ ከእርበርስ መጠፋፋት፣ ይልቅ የይስሙላ የ«ሰላም ጥሪ» ሳይሆን ሥልጣናቸውን ከፍለው ወይም ሙሉ በሙሉ ለቀው ለተቃዋሚዎቻቸው የሚያስረክቡበት ሁኔታ መኖሩን ከላይ በተዘረዘሩት ምሳሌዎች ለመግለጽ ሞክሬያለሁ:: እንዲህ ዓይነቱ ክስተቶች በጣም አልፎ አልፎ ብቻ የሚያጋጥሙና ብርቅዬዎች ከመሆናቸዉም በላይ እያንዳንዱ ድርድር ከብዙ ዓለም-አቀፍና አገር-አቀፍ ሁኔታዎች እንዲሁም ከእያንዳንዱ አገር ታሪክና ባህል ጋር የተወሳሰበ ናቸዉ:: ሆኖም ከሚከተሉት አንዱ ወይም ጥቂቱ መሟላት ለእንዲህ ዓይነቱ ድርድር ይጋብዛሉ ተብሎ ይታመናል::

1. ግጭት ቢነሳ ከአጠቃላይ ውድመት በስተቀር የአንድ ወገን ድል እንደማይገኝ በሁሉም ወገኖች ዘንድ ሲታመን ማለትም ተፋላሚዎች በኃይል ሲመጣጠኑ፡ ወይም አንዱ ሌላውን ማጥፋት ሳይችል ሲቀር፡
2. እያንዳንዱ ተደራዳሪ በድርደሩ የራሱን ሕልዉና ማስጠበቅ ሲችል ከሥልጣንም ድርሻ እንደሚኖረው ሲያረጋግጥ፡
3. በተራዘመ የርስ በርስ ጦርነት ምክንያት የታጋዮች ወይም የሕዝቡ ወይም የሁለቱም «አብዮታዊ» ስሜት ሲላሽቅና የአርበኝነት ወኔው እያደር ሲከዳው፡
4. ልሂቃኑ በረዥም ጊዜ የትግል ልምዳቸው፣ በበሰለ አመራራቸው ወይም እንደ ተረት በሚወራላቸው ጀግንነታቸው ምክንያት በተከታዮቻቸው ዘንድ ከፍ ያለ እምነትና ክብር ሲጎናጸፉና በዚህም ምክንያት ከጠላት ጋር ቢደራደሩ በብልሀት እንጂ በከሃዲነት እንደማይቆጠርባቸው ሲሰማቸው፡
5. አንዱ ወገን ለጊዜው ኃይል መሆኑ ቢሰማውም እንኳን ጦርነቱ ቀጥሎ ምናልባት ቢሸነፍ እጅግ ዋጋ የሚሰጠውን ሌላ ጉዳይ የሚያጣ መሆኑን፡ ዛሬ ጉልበቱ ሳይደክም ቢደራደር ግን ያ ከፍተኛ ዋጋ የሰጠውን ጉዳይ ማስጠበቅ እንደሚችል ሲያምን፡ ለምሳሌ፡ በደቡብ አፍሪቃ ነጮች የተጠበቀላቸው የባለመሉ ዜግነት መብት፣ የእንግሊዝ የዘውድ ክብር፣ የፓላንድ ኮሚኒስቶች እስከዛሬም ያላቸዉ ተሰሚነትና ቦታ፡ የኢትዮጵያ ለዓላዊነት (በአድዋ ጦርነት ማግስት በአፄ ሚኒሊክና በጣልያን መካከል የተደረገዉ ስምምነት)፣ ወዘተ... በዚህ መሰለ ድርድር የተጠበቁ እሴቶች ናቸው::

በሌላ በኩል ግን ዓለም-አቀፍ ተዕዕኖ ለእንደዚህ ዓይነቶቹ ድርድሮች መፈጠር ያለዉ ሚና ደካማ ነዉ:: የተራዘመ ዓለም-አቀፍ ፍጫና ቢደረግባቸዉም ሩይዳ ያለዉ ስምምነት ላይ መድረስ ያልቻሉ ልሂቃን ብዙዎች ናቸዉ:: ከዚህ የምንረዳዉ አንድ ተጨማሪ ሃቅ አንጂት የሚያራሩ የሰላም ንግግሮች የሚደመጥባቸው ዓለም-አቀፍና አገር-አቀፍ ጉባኤዎች፣ የሰላም ጉዞዎች፣ ሰላማዊ ሰልፎች፣ መዝሙሮች፣ ፖስተሮች፣ ወዘተ... ወዘተ...፣ ተራላሚ ልሂቃንን ተከታይ በማሳጣት ረገድ ሊኖራቸው ከሚችል የረዥም ጊዜና የዙሪያ ጥምጥም ደካማ ተጽዕኖ በስተቀር ወይም በሰላም ስም ለሚነሳ ሦስተኛ ወገን አመቺ ሁኔታን ከመፍጠር ሌላ ተራላሚዎችን ወደ ድርድር ጠረጴዛ በማቅረብ ረገድ እጅግም ተግባራዊ ሩይዳ የሌላቸው

መሆኑን ነዉ:: ለእንዲህ ዓይነቱ የሕዝብ ጥሪ እያንዳንዱ የልሂቃን ቡድን እሱ ሰላም ወዳድና ድርድር ፈላጊ ሲሆን ተቃዋሚው ወገን ለድርደር ያልተስማማ በመሆኑ ሳይወድ በግድ አማራጭ በማጣቱ የሚዋጋ መሆኑን በቁጭትና በሀዘን በመግለጽ ይመልሳል:: ተፈላሚዎች ራሳቸው ሰላምን ከሚማፀነዉ ሕዝብ ጋር ለሰላም የዘመሩበት አጋጣሚ ለቁጥር እስኪያታክት ብዙ ነው:: ይህ ብቻም አይደለም:: ልሂቃን በመሠረቱ ከሚወክሉት የሕብረተሰብ ክፍል የላቁ አባላት በመሆናቸው ሁሉን አውቅነት የሚያጠቃቸው በመሆኑ ከገለልተኛ ሊቃውንትና ከአገር ሽማግሌዎች የሚቀርብላቸውን ምሁራዊና አባታዊ ምክር ከልብ አያዳምጡም::

ከላይ የጠቀስኳቸው አይነት ብርቅዬ ድርድሮች ሁለት አስደናቂ ባሕርያትን ይዘዋል:: አንደኛ፣ የመጀመሪያዎቹ ዙር ውይይቶች ቁጥራቸው በጣም ጥቂት በሆኑ ልሂቃን (እንዳያዉም ብዙ ጊዜ በሁለቱ አዉራ ተፋላሚ ልሁቃን ብቻ) ተሳታፊነት በሚስጥር ወይም በአፊል ምሥጢር መከናወናቸው ነዉ::ከመጀመሪያዎቹ ምስጠራዊ፣ «የልብ-ከልብ» ዉይይት በኋላ ነዉ ሽምጋዮች ያለበት እሰጥ አገባ የበዛበት ድርድር የሚካሄደዉ:: የመጀመሪያዎቹ ዙሮች ፈላን፡ የኋለኞቹ ደግሞ ሳታታ፣ ናቸዉ::

ሊላው አስደናቂ ጉዳይ ደግሞ እጅግ የተለያዩ ርዕዩተ-ዓለሞችን የሚያራምዱ ተፋላሚ ልሂቃን አንድ አይነት ርዕዩተ-ዓለም ካላቸው ልሂቃን የበለጠ ተገናኝቶ የመደራደር ዝንባሌ ያላቸው መሆኑ ነው:: ይህ ብዙዎች ማመን ቢያስቸግራቸዉም ዕዉነት ነው:: ትናንሽ ልዩነቶች ከትላልቅ ልዩነቶች ይበልጥ በቀላሉ ይከራለና!

6. ለምንድነው ዘላቂ ሰላምና ልማትን ለማምጣት ዲሞክራሲ የተሻለ አማራጭ ነው የሚባለው?

ሰላም የሰፈነበት ሥርዓትና ሌሎችም ማህበራዊ ምርቶች /public goods/ ከሌሉ አንድ ማኅበረሰብ በአጥጋቢ ሁኔታ ሥራዉን መከወን አይችልም:: የሸብርና ዘረፋ ስልባቶች የሚያጠቁት፣ ለፍተው ያፈሩትን ሃብት ብቻ ሳይሆን ለወደፊቱም ሃብት የማፍራት ፍላጎትንም ጭምር ነው:: በመሆኑም ሥርዓተ-አልበኝነት ለልማት ተመራጭ መሆን አይችልም:: ሁሉንም የማኅበረሰብ አባላት የሚጠቅም በመሆኑ ብቻ ሰላማዊ ሥርዓት በሕዝቦች የጋራ ስምምነት ይሰፍናል ማለት ግን የዋህነት ነው:: ሰላም ከፍተኛ ወጪና መስዋትነትን ይጠይቃል፣ ውጤቱ ግን የጋራ ነው:: የሰላም ተጠቃሚ ሁሉም ነው፡ ወጪው ግን የግል ነው:: ስለዚህም እያንዳንዱ «ብልጥ» ሌላው ሰው ታግሎለት ሰላምን እንዲያመጣለት በመጠበቅ የግሉን ኪሳራ ሲቀንስ በሁሉም ሰው የሚወደደው ሰላም እንደተናፈቀ ይቀራል:: የሰዎች ኪሳራ የመቀነስ /cost minimizing/ ባህሪይ ለምርጫ ጥቂት ሰዓታት ለማጥፋት ምን ያህል እንደምንሰስት በማየት ብቻ እንኳን መታዘብ ይቻላል::

ዘላቂ ሰላምና ልማት በሕዝብ የጋራ ውሳኔና ፍላጎት የሚወሰን ቢሆን ኖሮ በዓለማችን ላይ ሰላምም ልማትም በኖሩ ነበር:: በሚፈለገዉ መጠን ባይሆንም ሁለቱም በዓለማችን ላይ አሉ:: ከሰላም የሚገኘው ጥቅም በግል ከሚያስወጣው ወጪ እጅግ የላቀ የሆነለት አካል በመኖሩ ግን የሕዝብ የጋራ ውሳኔ ጠባብ ያደርገዋል::

እዉቁ ኢኮኖሚስት ማንኸዩር ኦልሰን ተረት በመሰለ ጣፋጭ ትረካ ነው ይህንን ያብራራው[6]። ዘላን ወንበዴዎች /roving bandits/ ነጥቀው ይሮጣሉ፡ መቼ እንደሚመለሱ አይታወቅም። እነዚህ ወንበዴዎች ነጥቀው በሮጡ ቁጥር የማንበረሰበዉ ሃብት የማፍራት ፍላጎት ስለሚጸነም በሚቀጥለው ዙር የሚዘርፉት ነገር እያነሰባቸው ይመጣል። ቀን ባለፉ መጠን ነጥቆ መሮጥ ራሳቸውን እንደሚጎዳቸዉ ይገነዘቡና ከተዘዋዋሪ ወንበዴነት ወደ ቋሚ ወንበዴነት /stationary bandit/ ይቀየራሉ። ለንጥቂያቸዉ ሥርዓትና ልክ ያበጁለታል፡ ስሙን «ግብር» ይለዋል። ማንበረሰበዉንም፡ ራሳቸውንም፡ ከሌሎች ተዘዋዋሪ ወንበዴዎች ይከላከላሉ። ይህ ሥርዓት ከሥርዓት አልበኝነት በጣም የተሻለ፡ የቅሚያዉ መጠንም አስቀድሞ የሚታወቅ ከመሆኑ ጋር ማንበረሰበዉ ለሚከፍለው ተመጣጣኝም ባይሆን የሚያገኘው ጥቅም (ሰላምና ሌሎችም public goods) ስላለ ምርት ይጨምራል፡ ዕድገትም ይኖራል።

ይሁን እንጂ አምባገነን ሰፋሪዎች በተደላደሉ መጠን ፍጆታቸው እየናረ መሄዱ ፊጽሞ የማይቀር ነው። ለጦር ሠራዊቱ፡ ለቤተ-መንግሥቱ፡ ለቤተ-መቅደሱ፡ ለማሰልጠኛው፡ ለመታሰቢያ ኃውልቶች ግንባታ፡ ለመሰብሰቢያ አዳራሾች ግንባታ፡ ለክብረ-በዓላት ማስጌጫ፡ በዉጭ አገር ባንኮች ለሚከማቸዉ «መጠባበቂያ» ሂሳብ (ሞቡቱ 8 ቢሊዮን ዶላር የሚገመት ክምችት ነበረዉ ይባላል) ለአንባገነኖቹና ለቤተሰቦቻቸዉ የክብር ልብሶችና ጌጦች መግዣ (ኢሜልዳ ማርኮስ 3000 ጥንድ ጫማዎች ነበሯት)፡ ወዘተ...፡ የሚጠየቀው ወጪ በጨመረ ቁጥር ሕዝቡ በታክስ አለቧም በሌላ መንገድ እንዲከፍል የሚያስገደድ ሥርዓት በመስፈኑ ምክንያት አንስራርቶ የነበረው የሥራ ፍላጎት እንደገና ያሽቆለቁላል። የሰፋሪ ወንበዴዎችን የሃብት ማጋበስ፡ ምኞትና እዩልኝ ፉላጎቶች፡ ማርካት አይቻልም።

ሰፋሪ ወንበዴዎች /stationary bandits/ የፍጆታቸው ከአቅም በላይ መናር በተጨማሪ ሌሎችም ችግሮች አለባቸው። አንዱ የሥልጣን ሽግግር /succession/ ችግር ነው። ልሁቁ ወንበዴ በደከመ ወይም ባረጀ ጊዜ በማን እንደሚተካ ግልጽ መመሪያ ስለማይኖር ከአንድ አምባገነን ወደሌላኛው አምባገነን መሸጋገሪያ ላይ ብጥብጥና አለመረጋጋት ይኖራል። ስለሆነም በዚህ መንገድ የሚመጣው ሰላም ከአንድ ሰው የስልጣን እድሜ በላይ የመቆየቱ ነገር እጅግ በጣም አጠራጣሪ ነው። ይህ ጥርጣሬ ራሱ የረዥም ጊዜ ኢንቬስትመንትን የሚገታ የዕድገት ማነቆ ነው።

ንጉሣዊ ሥርዓትም ቢሆን ከሥልጣን ውርስ ችግር ሙሉ በሙሉ የነፃ አይደለም። የነገሥታቱ ፍጆታ ደግሞ እንደአምባገነኖቹ ሁሉ አቅምን ያገናዘበ አይደለም። የአለም ታላቅ ቤተመንግሥቶችና ቤተ-መቅደሶች የተገነቡት በነገሥታት መሆኑን ማስታወስ ይበቃል።

ንብረት በግል የመያዝ መብት ያለመንግሥት ሊከበር አይችልም። ወገናዊ ያልሆነ የፍትህ ሥርዓት ከሌለ ደግሞ ሁሌች አይረጉም፡ ቃልኪዳኖች አይከበሩም፡ በሰዎችና ተቋማት መካከል መተማመን ይጠፋል። ይህ ሁሉ ዕድገትን ያቀጭጫል።

---

[6]. Olson Mancure "Dictatorship, Democracy and Development" American Political Science Review Vol. 87 No. 3 PP. 567-576

አምባገነኖች የሰብዓዊ መብቶችን ማክበር፣ ለግል ንብረቶች ሙሉ ዋስትና መስጠትና ወገናዊ ያልሆነ የፍትህ ሥርዓት ማስፈን አይቻላቸውም። እነዚህ ደግሞ ከሌሉ ነፃ የሆነ ንግድና የካፒታል ዝውውር አይኖርም። ሰዎች ንብረቶቻቸውና ውሎቻቸው እንዲጠበቁላቸው የሚፈልጉት ገና ሥልጣን ላይ ካልወጡት ጉልበተኞች ብቻ ሳይሆን ሥልጣን ላይ ካለው ጉልበተኛ ማለትም ከመንግሥትም ጭምር ነው። እንዲያውም በጣም የሚያስፈራው ኃይል መንግሥት ነው።

ለፈጣን ዕድገትና ለዲሞክራሲ መስፈን የሚያስፈልግ ሁኔታ በመሠረቱ አንድ ነው። ነፃነትን፣ ሰላምንና ውሎችን ማስጠበቅ የሚችል እና ራሱን የሚቆጣጠር መንግሥት! ለተሳጠነ ልማት ምቹ ሁኔታን ለመፍጠር እንዲቻል መንግሥትን መቆጣጠር የሚያስችል የአስተዳደር ሥርዓት ያስፈልጋል። ይህ ደግሞ ዲሞክራሲ ነው። ዲሞክራሲ ሕግ አውጪው፣ ሕግ አስፈጻሚው፣ ሕግ ተርጓሚው እና ነፃው ፕሬስ እርስ በርስ እየተደጋገፉ፣ እየተጠባበቁና እየተራረሙ እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል።

ለዚህም ነው ካፒታል (ማለትም ገንዘብ፣ የሰለጠነ የሰው ኃይል፣ ወዘተ...) በአምባገነኖች ከሚገዙ አገሮች፣ ዲሞክራሲ ወደ ሰፈነባቸው አገሮች፣ የሚፈልሰው። አምባገነኖች ራሳቸው ከገዛ ራሳቸው አገር ወይም እነሱን የመሰለ ሌላ አምባገነን ከሚገዛው አገር ይልቅ ለሃብታቸው ማስተመጫነት የሚመርጡት ዲሞክራሲያዊ አገሮችን ነው። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት የካፒታል ፍልሰትን ከድሃ ወደ ሃብታም አገሮች እንዲሆን አድርጎታል።

7. የኢትዮጵያ ልሂቃን የት ናቸው? ወዴትስ እያመሩ ነው?

ክቡራትና ክቡራን! በእስካሁኑ ንግግሬ አፅንኦት ለመስጠት የሞከርኩት ፍሬ ሃሳብ ጥሩ ሕገ-መንግሥት፣ ሕጎች፣ መንግሥታዊ መዋቅሮች መኖራቸው እጅግ ጠቃሚ ቢሆንም እነዚህ ስላሉ ብቻ ሰላም፣ ዲሞክራሲና ልማት የማይመጡ መሆኑን ነው። ሕገ-መንግስትን፣ ፌደራላዊ አደረጃጀትን፣ ፕሬዚዳንታዊ ወይም ፓርላሜንታዊ አስተዳደርን፣ ከሌሎች መማርና መዋስ እንችላለን፡ ዜጎችን ከዚያ ማምጣት ግን ፈጽሞ አይቻለንም።

በ1980ቹ፣ መጨረሻ እና በ1990ቹ፣ መጀመሪያ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮች ልሂቃን «ሕገ-መንግስት ነርጅናል፡ መንግሥታችንንም በታወቁ የዲሞክራሲ መሥፈርቶች አሳያ አዋቅረናል። እናስ! ለነረጅነው ሕገ-መንግሥት ምቹ ሆነናል ወይ?» እያሉ ደጋግመው ራሳቸውን ሲጠይቁና ሲወቅሱ አስተውለናል።

ኢትዮጵያና ምሥራቅ አውሮፓ ውስጥ የለዉጥ ማዕበል የነፈሰው በተመሳሳይ ጊዜ ነው። ዛሬ ግን የትናየት ተራርቀናል! የኢትዮጵያ ልሂቃን ራሳቸውን መዉቀስ ግና መጀመራቸው ነው። ብዙዎቹ፣ አሁንም እንደ ድሮው ሁሉ ራሳቸውን «የቀለም ቀንድ»፣ «ምጡቅ»፣ ወዘተ... እያሉ ማሞካሸቱን የቀጠለበት ይመስላል። እርግጥ ነው! አንዳንድ አበረታች ጅምሮች እየታዩ ነው።

ከአመታት በፊት ክፍለ ታዲስ «የ ትዉልድ» በተሰኘ ተከታታይ መዕከፋ የኢትዮጵያዉያንን «ቦልሸቪክ» ልሂቆች ሕልምና ዕጣ ፈንታ አስነብቦናል።

ሳያስቡትና ሳይዘጋጁበት መንገድ ላይ የወደቀን ሥልጣን አንስተዉ በራሳቸዉም፣ በአገራችንም፣ ላይ አስከፊ ጉዳት ያደረሱት ወታደራዊ ልሂቃንን ታሪክ ደግሞ ዳዊት ወ/ጊዮርጊስ በ«የደም እንባ»፤ ዘነበ ፈለቀ ደግሞ በ«ነበር» ተርከዉልናል::

ፕሮፌሰር መስፍን ወልደማርያም ለ1997 እንቁጣጣሽ ስጦታ «የክህደት ቁልቁለት»ን አበርክተውልን የአንድ ልሂቃን ቡድን የብዙ ዓመታት የተቀነባበረ ሴራን እንድናይ ረድተውናል::

የዚህን ጽሑፍ ረቂቅ ወደማገባደድ በደረስኩበት ወቅት የአቶ አንዳርጋቸው ጽጌን «ነጻነትን የማያውቅ 'ነፃ አዉጭ': ስልጣኔ፣ ዲሞክራሲ እና ብልጽግና፤: የፖለቲካ ልሂቃን ሚና በዘመናዊት ኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ ያሳተሙት መጽሐፍ በድንገት እጄ ውስጥ ገባ:: ይህንን መጽሐፍ ጨርሼ ለማንበብ ጊዜ አላገኘሁም፤ ሆኖም በነበረኝ የተጣበበ ጊዜ ገረፍ ገረፍ አድርጌ «ኤሊት» ለሚለው የእንግሊዘኛ ቃል «ልሁቅ» እና «ልሂቃን» መጠቀምን ጨምሮ ረድቶኛል:: ጊዜ አግኝቼ መጽሐፉን በርጋታ ማንበብ ብችል ኖሮ ጹሑፌን በእጅጉ ያዳብርልኝ እንደነበር አልጠራጠርም::

እነዚህና ሌሎችም ያልጠቅሰኳቸዉ ሥራዎች መልካም ጅምሮች ቢሆኑም በቂ ሊባሉ ግን ፈጽሞ አይችሉም:: ስለኢትዮጵያ ልሂቃን ያለን እውቀት እጅግ በጣም ውስን ነው:: የምርምር ሥራዎችም በዚህ መንገድ የሄዱ አይመስለኝም::

የኢትዮጵያ ልሂቃንን ለማጥናት የሚከተሉት ነጥቦች ጠቃሚ ይመስሉኛል::

1. የኢትዮጵያ ልሂቃን በጣም መበታተናቸው ሳያንስ እርስ በርሳቸው በእጅጉ የሚፃረሩ፣ አንዱ ሌላኛውን ከምድር ገጽ ለማጥፋት ከመረረ ጥላቻ ጋር የተነሱ መሆናቸው፣ አገራችን ዛሬ ለምትገኝበት አሳዛኝ ሁኔታ የዳረገን ይመስለኛል:: የመጠፋፋቱ ትግል በደርግ ጊዜ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደርሶ የነበረ ሲሆን አሁንም መልኩን እየቀያየረ ቀጥሏል:: ኢትዮጵያዉያን ልሂቃን በአገራዊ ጉዳዮች የጋራ መግባባት ላይ ካልደረሱ በስተቀር ይህ የጥላቻና የመጠፋፋት ፖለቲካ በቀላሉ የሚቆም አይመስለኝም::
2. የአገራችን ልሂቃን በየራሳቸው ቡድን ውስጥ በርዕዮተ-ዓለም የተሳሰሩ መሆናቸው ሌላው ባህሪያቸው ይመስለኛል:: እያንዳንዱ ቡድን የሚመራበት የራሴ የሚለው ርዕዮተ-ዓለም አለው:: ልሂቃኖቻችን ርዕዮተ - ዓለማቸዉን ምሉዕ አድርገዉ ስለሚወስዱ ከዚያ ወዲያ ዕዉቀት ላሳር እስኪሉ ድረስ ችኮ ደብተራ ከመምሰላቸዉም በተጨማሪ በቡድን ዉስጥ የሚነሱ ለዕድገት አስተዋዕያ ሊኖራቸዉ ይችሉ የነበሩ ልዩነቶች በአግባቡ እንዳይስተናገዱ አድርጓል:: ትንንሽ ልዩነቶች በጠላትነት የሚያስፈርጁ በመሆናቸው ተቃዉሞን በግልዕ ከመናገር ይልቅ ዙርያ ጥምጥም፣ አግቦ፣ ተረቦችና ድብቅነትን አስፋፍቷል:: ዛሬ በሥልጣን ላይ የሚገኙ ልሂቃኖቻችን ንግግሮች በተረብ የተሞሉ መሆናቸዉ፤ ሥልጣን ላይ እንኳን ሆነዉ ሕቡዕ የገቡ የሚመስለዉ በዚህ ምክንያት ይመስለኛል:: ለማስረጃ ያህል እስከ ሕወሓት መስንጠቅ ድረስ ግማሹ ያህል የፖለቲካ ቢሮ አባላቱ በሕዝብና በሚዲያው የሚታወቁ አልነበሩም፤ በየጊዜዉ ታትመዉ የሚወጡ ፓሊሲ መሰል ሰነዶች ደራሲያቸዉ አይታወቅም:: የኢትዮጵያ ልሂቃን የተበታተኑ ሁነው በየራሳቸው ጎጆ ውስጥ ደግሞ በርዕዮተ-ዓለም መታጠራቸው ራሳቸውንም

አገራችንንም በእጅጉ ጎድቷል። አንዱ የሌላውን ሃሳብ ለመረዳት ጥረት እንዳያደርግ ዓይኖቻቸውንና ጆሮዎቻቸውን ሸፍኖታል። ይህ ደግሞ በመካከላቸው ያለው አለመተማመን እና የጥላቻ ፖለቲካ ሥር እንዲሰድ አድርጓል።

3. የኢትዮጵያ ልሂቃን (ሁሉም ማለት ይቻላል) ለእኩልነትና ፍትህ እንታገላለን ባይ አጋለጥታሪያን መሆናቸው ሌላው አቢይ ባህርይ ነው። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ለብራዝለዝም ርዕሱ ሃሳብ ተደርጎ ሲብጠለጠል ነበር። እንታገልለታለን፣ እንወክለዋለን፣ የሚሉት በታችኛው የሃብት ወለል ላይ ያለው የጎበረተሰብ ክፍል፣ ልሂቃን የሚያነበንቡትን «ድጋም» ለመረዳት በእጅጉ የሚቸገር በመሆኑ ወደፊት የምትመሰረተውን ማርና ወተት ለሕዝቧ በእኩል የሚፈስባት የተስፋይቱን ምድር እውን ለማድረግ፣ የታዘዘውን የሚፈጽም ትጉህ ምዕመን እንዲሆን ተደርጓል። ምናልባት ከኢ.ድ.ሕ. ልሂቃን በስተቀር ሁሉም የኢትዮጵያ የፖለቲካ ድርጅቶች የግራ ፖለቲካ አራማጆችና የኮሚኒዝም ጥቅር በልባቸው ያደረ ነው። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በተመሳሳይ እምነቶች መካከል ያለው ቅራኔ በተለያዩ እምነቶች መካከል ካለው ቅራኔ የባሰ ይከራል። ከ1960ቹ ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ እያወዛገበ ያለው ከጎሳ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ብሄረሰብ፣ ብሔር፣ ሕዝብ፣ ሕዝቦች፣ ወዘተ... አኖ አንዳርጋቸው ጽጌ «ዘመንኛነት» ያሉት አስተሳሰብ ከኢትዮጵያዊነት፣ አህጉራዊነትና ዓለም-ዓቀፋዊነት ጋር እየተጋፈጠ ልሂቃኑን እርስ በርስ ክፉኛ አላትሟል፤ እያላተመም ነው። የሚገርመው እነዚህ ዘውገኛ ልሂቃን በአገራቸው ጉዳይ የዘረኝነት ስሜት ቢያጠቃቸውም ራሳቸውን ግን «ዓለም-አቀፋዊ» ታጋይ ማድረጋቸው ነው።

4. «የኤርትራ ጥያቄ» ሌላዉ የኢትዮጵያ ልሂቃን መወዛገቢያ ሆኖ ቆይቷል። የኢትዮጵያ አካል ሁናም እያለ፣ አገርነቷ ከታወቀላት በኋላም የኤርትራ ጉዳይ ከኢትዮጵያ ልሂቃን ፖለቲካ መውረድ አልቻለም።

የኢትዮጵያ ልሂቃን እጅግ የተበታተኑና እርስ በርሳቸው የሚባሩ፣ በየራሳቸው ጎጆ ውስጥ ደግሞ በርዕዮተ-ዓለም የተሰነጠቁ መሆናቸውን ገልጫለሁ። በሌሎች አገሮች እንደታየው አንድም የጋራ የውጭ ጠላት ሲኖር ወይም የአክራሪዎች ተደጋጋሚ ሽንፈት ልሂቃኑን መሃል ላይ ሲያሰባስባቸው ወይም ደግሞ በሰጥቶ መቀበል ድርድሮች ነው።

የኢትዮጵያ ልሂቃን ወራሪ ጠላት በመጣ ጊዜ ልዩነቶቻቸውን ወደጎን በመተው በአንድነት መነሳታቸው የተለመደ ነው። በቅርቡም በኤርትራ ወረራ ወቅት ታይቶል። የሚያሳዝነው ግን ሁሉም ይህ ስምምነት ከደል በኋላ በኖ የሚጠፋ መሆኑ ነው። የዚህን ምክንያት በጥልቀት መመርመር ይኖርብናል። ድህነትና ረሃብም እንደ ጋራ ጠላት ሊያስተባብሩን ይገባ ነበር፤ ግን አልሆነም። ለምን? እኔ አላውቅም። ምርምር የሚሻ ጉዳይ ነው።

መሃል ላይ መሰባሰብ የተባለው ኢትዮጵያ ውስጥ የቱ ዳር፣ የቱ መሃል፣ እንደሆነ መለየት አስቸጋሪ ነው። በመጀመሪያ ደረጃ አብዛኞቹ ልሂቃኖቻችን ምንጫቸው የግራ ፖለቲካ በመሆኑ ፖለቲካችን እስከዛሬም ወደግራ ያዘመመ ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የግራ ፖለቲካ ከደረሰበት ስብራት ማገገም አልቻለም። በዓለም ላይ ሊብራሊዝም ሁሉን አቀፍ ድል

ፉኩያማ:: ፍራንሲስ ፉኩያማ «ታሪክ ባበቃበት ዘመን ነው ያለነው» ያለዉ ለዚህ ነው[7]:: እርግጥ ነው ፉኩያማም እንዳስተዋለው የግራ ፖለቲካ በቀላሉ አይሞትም፡ መፍጨርጨሩ፣ መንፈራፈሩና መንፈራገጡ አይቀርም:: ሩሲያ ውስጥ ሚካኤል ጎርባቾቭ «ፔሬስትሮይካ» (እንደገና መገንባት) የሚባል የተሃድሶ መድሃኒት ቀምሞለት ነበር፡ አልሆነም! እኛ አገር ደግሞ «አብዮታዊ ዲሞክራሲ» የሚባል ሌላ መድሃኒት ተቀምሞለታል! እሱም እጅግ ውስን ለሆነ ቦታ ማደንዘዣነት /local anesthesia/ ከማገልገል አልፎ የግራ ፖለቲካን መታደግ አልቻለም፡ አይችልምም! ከወትሮ፡ የአለም ፖለቲካ አንባር ከታየ የግራ ፖለቲካ አጠቃላይ ውድቀት ላይ ነው:: ኢትዮጵያ ከዓለም ዉጭ መሆን አይቻላትም፡ እናም የኢትዮጵያ ልሂቃን ሳያወዱም በሆን ሊብራሊዝምን ማጥናት ግድ ይሆንባቸዋል:: እርግጥ ነዉ! እድሜ ልክ ያጠኑትንና ያመኑበትን መተው በጣም ፈታኝ ነገር ነው:: የእድሜ ልክ ሌኒኒስቶችና ማኦኢስቶች በድንገት ሊብራል እንሁን ሲሉ የሚፈጥሩት አስቂኝ ትርኢት ሳስተውል "unlearning is more difficult than learning" «የተማሩትን አለመማር (መልቀቅ) በጣም ይከብዳል ከመማር» የሚለው ማን እንደተናገረው የማላውቀውን አባባል ትክክለኛነት አደንቃለሁ::

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች እንደታየዉ ኢትዮጵያም ዉስጥ የርዕዮተ ዓለም ፖለቲካ አላዋጣ ሲል ዘረኝነትና አክራሪ አማኝነት በከፍተኛ ፍጥነት እየተስፋፉ ነው:: ይህ ደግሞ ከርዕዮተ-ዓለሙ ትግል የባሰ አውዳሚ ነው:: ሣሙኤል ሃንቲግተን የስልጣኔ ግጭቶች /civilizational clashes/ የሚላቸውን ዓይነት ዘርና ሃይማኖትን መሠረት ያደረጉ ግጭቶች አገራችንን ያሰጓቷል[8]:: በዘርና በሃይማኖት[9] ስንሳደን የሚደርሰው ውድመት ምነው እንደ ድሮአችን በ«ላብአደር» እና «ወዛደር» ተጣልተን በተሳቀስን የሚያስብል ሊሆን ይችላል::

በአንድ በኩል ለእርስ በርስ መፋጀታችን ምክንያት ሆኖ በቆየው የግራ ፖለቲካ ላይ ኪሳራ መድረሱና ወደ ሊብራዝም ማምራታችን የማይቀር መሆኑ በግሌ ቢያስደስተኝም፣ በአንባሩ ደግሞ የርዕዮተ-ዓለሙን ክፍተት የዘር ፖለቲካና አክራሪ ሃይማኖቶች እንዳይተኩት እሰጋለሁ::

ይህም ሆኖ ግን ተስፋ ሰጭ ጅምሮች አሉ:: አንዱ ከላይ የጠቀስኩት የግራ ፖለቲካ ላይ የደረሰዉ አጠቃላይ ኪሳራ አገራችንም ዉስጥ ሊብራል አስተሳሰቦች እንዲያብቡ መንገድ ከፍቷል:: አሁን ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲዎች ወደ ፖለቲካዉ መድረክ እየመጡ ነዉ:: ከጥቂት ጊዜ በኋላ ደግሞ የቀኝ ፖለቲካ አራማጆች ይመጡና የኢትዮጵያ ፖለቲካን ወደ

---

[7] . «የሰዉ ልጆች ታሪክ የመደብ ትግል ታሪክ ነዉ» የሚለዉ የሂግል/ማርክስ (በኋላም ሌኒን፣ ማኦና የእኛዎቹም ልሂቃን ያራገቡት) ፍልስፍና ትክክል ከሆነ አሁን የመደብ ትግሉን ሊብራሊዝም በአሸናፊነት ተወጥኖልና ታሪክ አብቅቷል በማለት ፍራንሲስ ፉኩያማ የዛፈዉን The End of Historyን ያስታዉሷል:: «ታሪክ አላበቃም፣ አያበቃምም» ብሉ መከራከር የሂግል/ማርክስ ፍልስፍናን መሳርር እንደሆነ ልብ ይሏል::

[8] . ሣሙኤል ሃንቲግተን ለፍራንሲስ ፉኩያማ ምላሽ በመስለ ሁኔታ የርዕዮተ-ዓለሙ ትግል ማብቃት ወደ ባሰ civilizational clashes ማለትም የዘር፣ የሃይማኖትና የባህል ግጭቶች እያስገባን ነዉ ያለዉን ያስታዉሷል:: የቀዝቃዉ ጦርነት ማብቃትን ዉጤቶች በተመለከተ ከሃንቲግተንና ከፉኩያማ ማን ትክክል እንደሆነ ለመናገር እምንችልበት ደረጃ የደረስን አይምስልም::

[9] . የዘር ፖለቲካ ማብራሪያ የሚሻ አይመስለኝም፡ የሃይማኖቶች አክራሪነት እየተባባሱ መምጣታቸዉን የሚጠራጠር ካለ ፕሮቴስታንቶች ስለአርቶዶክስ አማኞች፡ አርቶዶክሶች ደግሞ ስለፕሮቴስታንቶችና ካቶሊኮች የሚሉትን እንዲሰሙ፡ የሚፅፉትን እንዲያነቡ እጋብዛለሁ:: እግረመንገዴንም አክራሪነት ከእስልምና ጋር ብቻ መያያዝ እንደሌለበት ማስገንዘብ እሻለሁ::

ቀኝ ስበዉ መሃል ላይ ያለዉን ፕሮግራም (centerist) አሸናፊ ያደርጉታል የሚል ተስፋ አለኝ:: ሌላዉ ተስፋ ሰጭ ሁኔታ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ ልሂቃን ወደ ሶስት ቡድኖች የመሰባሰብ ዝንባሌ ማሳየታቸዉ ነዉ:: ይህ ዝንባሌ በፓርቲዎች መቀናጀት ብቻ ሳይሆን በፕሮግራሞቻቸዉም ግልጽ እየሆነ መምጣት ጀምሯል:: የግንቦቱ ምርጫ ዉድድር ለምሳሌ፣ በአብዛኛዉ በሶስት ቡድኖች መካከል ነዉ የሚሆነዉ:: በምርጫ ወቅት መቀናጀቶች ወደ ሁለት ቢወርዱ ኖሮ በጣም የተሻለ ይሆን ነበር፣ ሶስትም ግን ትልቅ መሻሻል ነዉ::

ለኢትዮጵያዊያን ልሂቃን መግባባት፣ ያላቸው ሌላ አማራጭ፣ «ሰጥቶ መቀበል» ብዬ የጠራሁት ድርድር ነው:: አሁን በሥልጣን ላይ ያለዉ ልሁቅ በድርድር ሥልጣኑን መልቀቅ ወይም ማጋራት ይፈልጋል? ከድርድሩ ምን ሊያገኝ? አሁን ምንድነው ያጣው? እነዚህ ጥያቄዎች ለእኔ በጣም ከባዶች ናቸው፣ ግምቶቼን ግን ላስፍር::

አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ልሁቅ የህጋዊ ተቀባይነት /ligitimacy/ ችግር አለበት:: ገንባሁ የሚለው ዲሞክራሲ ወደ መቶ በመቶ የተጠጋ የምርጫ ድጋፍ ውጤት «እያመጣበት» የተቸገረ ይመስለኛል:: ከበርሊን ግንብ መፍረስ ወዲህ መቶ በመቶ የሕዝብ ድጋፍ የሚያኮራ ሳይሆን የሚሳፍር ሆኗል፣ ዘጠናም፣ ሰማንያም፣ ሰባአምስትም፣ ጥሩ አይደለም:: አሁን በሥልጣን ላይ ያለው ልሁቅ በምርጫ ወቅት የሚያገኘዉ ድጋፍ ወደ ሰባ በመቶ አካባቢ ወርዶለት በነፃና ፍትሃዊ ምርጫ የተመረጠ መንግሥት ነዉ መባል የሚፈልግ ይመስለኛል፣ ለዚህ ደግሞ ጥቂት ወንበሮችን በየአካባቢው ማጣት ይፈቅዳል የሚል እምነት አለኝ:: አስቸጋሪዉ ጥያቄ ለዚህ ምን ያህል ወንበሮችን ማጣት ይፈቅዳል? የሚለዉ ይመስለኛል::

«ይኸንንማ መራጩ ሕዝብ ነዉ የሚወስነዉ» እንደማትሉኝ ተስፋ አለኝ፣ ምክንያቱም ሥልጣን ላይ ያለዉ ልሂቅ የምርጫዉን ዉጤት መቆጣጠሪያ ስልቶችን ማበጀቱ ግልፅ ነዉና! በመሆኑም «ሕዝቡ ማንን ይመርጣል?» ሳይሆን «አሁን በሥልጣን ላይ ያለዉ ልሂቅ ለተቃዋሚዎቹ፣ ልሂቃን በየት አካባቢ ምን ያህል መቀመጫ መልቀቅ ይፈልጋል?» የሚለዉ ጥያቄ የበለጠ ነባራዊ ሁኔታዎችን ያገናዘበ ይመስለኛል:: ሕዝቡ በምርጫ የመወሰን መብቱን ገና ሙሉ በሙሉ እጁ ዉስጥ አላስገባም:: መራጩም፣ ተመራጩም፣ አስመራጩም ለምርጫ ስነ-ምግባር ተገዥ አይደሉም:: ለዚህም ነዉ የሚቀጥለዉ ምርጫ ዉጤት በአብዛኛዉ በገዢዉ ልሂቅ ፍላጎትና ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነዉ የሚል ግምት ያለኝ::

ይሁን እንጂ በታሪክ ዉስጥ ተደጋግሞ እንደታየዉ አፈና ረገብ ሲል ያልታሰቡ ፍንዳታዎች ይመጣሉ:: እናም የሚቀጥለዉ ምርጫ በሰላም ከተጠናቀቀ አሁን በሥልጣን ላይ ያለዉን የልሂቃን ቡድን ሲሶዉ ያህል የፓርላማ መቀመጫዎችና የአዲስ አበባን አብላጫ ወንበር ያሳጣዉ ይሆናል የሚል ግምት አለኝ::

ይህ ግምቴ ምኞትም ጭምር ነዉ:: ይህ ከተሳካ «ጠንክረን ተንቀሳቅሰን ቢሆን ኖሮ ለካንስ መንግሥትን በምርጫ መለወጥ እንችል ነበር» በሚል ቁጭት ልሂቃኖቻችን ለ2002ቱ ምርጫ ሰፊ ዝግጅት ማድረግ ከወዲሁ ይጀምራሉ:: ሕዝቡም በምርጫ ላይ ያለዉ ዕምነት ከፍ ይላል፣ በፓለቲካ ላይ ያለዉ ጥላቻ ይቀንሳል::

ይህ መልካም ምኞት እንዲሰምር ከአሁኑ ቢያንስ የሚከተሉት ተግባራዊ መሆን ይኖርባቸዋል፤

1. ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ማክበር፤
2. መነጋገርን፣ መደማመጥን መግባባትን፣ መቻቻልንና መደራደርን መልመድ፤
3. መራጩም፣ ተመራጩም፣ አስመራጩም፣ ለምርጫ ሥነ-ምግባር ተገዥ መሆን፤
4. በተለይ በሥልጣን ላይ ያለዉ የልሂቃን ቡድን የአገርን ጥቅም ማስቀደም፤
5. ልሂቃኖቻችን ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብ ጽንፈኝነት፣ አክራሪነት፣ ጥራዝ-ነጠቅነት፣ ሳስኝነት፣ አለመሆኑን በመረዳት ልዮነቶችን በማጥበብ ለጋራ ጥቅም በጋራ መሥራትን ሲለምዱና የመሃለኛዉን የፓለቲካ መስመር አሸናፊ ማድረግ ሲችሉ ነዉ::

እነዚህ ነገሮች ካሁኑ በተግባር ላይ ከዋሉ የ2002፣ 2007፣ 2012 እና 2017 ምርጫዎችን እያንዳንዱን ከቀደመዉ የበለጠ ዲሞክራሲያዊና የበለጠ አሳታፊ እንዲሆን ያደርጉታል::

ይህ በተግባር ተረጋገጠ ከቀጠለ በ2017 የምርጫ ክርክሮች የድህነት፣ የረሃብ፣ የብሔረሰብ፣ የድንበር፣ የወደብ፣ ጉዳዮች በጭራሽ አይነሱም:: ይልቁንስ ያኔ የሚያጨቃጭቁ አጀንዳዎች የአፍሪካ ቀንድ ፌዴራል መንግሥት እና የአፍሪካ ኅብረት ሥልጣን እስከምን ድረስ ይሂድ የሚሉትና ከግሎባላይዜሽንና ኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ይሆናሉ:: እናም! የ2020 ኢትዮጵያ ሰላምና ዲሞክራሲ የሰፈነባት፤ ልማት የተፋጠነባት፤ ልሂቃኖቿ ልዩነቶቻቸዉን በዉይይትና ድርድር የሚፈቱባት፤ ኅብረትና ፉክክር የተመጣጠነባት፣ አገር ትሆናለች::

ግሙቴ ፋርሽ ሁኖ የግንቦቱ ምርጫ ከተጨናገፈ ግን ኢትዮጵያ የሚገጥማትን መከራ ማሰብ እንኳን ይሰቀጥጣልና ስለዚህ ምንም ማለት አልፈልግም::

ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ::

በዶ/ር ታደሰ ብሩ ኬርስሞ ጽሑፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት

አማረ አረጋዊ*

በጣም አመሰግናለሁ። እኔ የዶ/ር ታደሰን ጽሑፍ ሳነብ እንደ ልብ- ወለድ ጽሑፍ (novel) ነው ያነበብኩት። ምክንያቱም አብዛኛውን ጊዜ የአንድ አገር ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች የሚተነትኑ ጽሑፎች ከተለያዩ አቅጣጫ ነው የሚያዩት፤ የኢኮኖሚ ጉዳይ ወሳኝ ወይም መሠረታዊ ጉዳይ እንደሆነ ያነሳሉ፤ ከዚያ ስለኢንፍራስትራክቸር ይናገራሉ፤ በተለይ ደግሞ እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ለረጅም ጊዜ በፊውዳል ሥርዓት ለማቀቁ አገሮች ወሳኝ ነገር ምንድን ነው ብለን ስንጠይቅ ሰፊው ሕዝብ ነው፣ ወዘተ... እያልን ስለምንሄድ ዶ/ር ታደሰ ያቀረቡት ግን ከዚህ በተለየ አቅጣጫ፤ ከልሂቃን አቅጣጫ፣ አይተው የአንድን አገር ሁኔታ መተንተን ሲጀምሩ ልዩ እንደሆነ ነገር ነው ያየሁት።

ሃሳባቸውን አንዳንዱን ለመቀበል ቢያስቸግረኝም በእርግጥ ለመቃወም ግን አስቸግሮኛል። ምክንያቱም ያቀረቡት ክርክር ጠንካራ (sound) ነው። የተደረገው ምርምርም ሰፊ ከመሆኑ ባሻገር ሕብረተሰብንም በአዲስ አቅጣጫ ለማየት ሞክረዋል። በመሆኑም ዶ/ር ታደሰን ከልብ አመሰግናለሁ።

የዶ/ር ታደሰ ጽሑፍ ለብዙዎች አነጋጋሪ ከሆነው ከትርጓሜ ነው የተነሳው። እርሳቸውም እንዳስቀመጡት ሰላም፣ ዲሞክራሲና ልማት በዓለም ላይ የተለያየ ትርጉም እየተሰጣቸው ነው። በተለይ ሥልጣን ላይ ያሉት ሰላምን የሚተረጉሙት፣ ተገዢው ሕዝብ የሚተረጉመው፣ በተለያየ መልክ ነው። እንዲሁም ሕዝብና መንግሥት ለዲሞክራሲ የተለያየ ትርጉም ይሰጡታል።

አሁን ግን የተፈለገውን ዓላማ ለማየት ቀላል ትርጉም ነው ዶ/ር ታደሰ ያስቀመጡልን።

ሰላም ማለት አሉ ዶ/ር ታደሰ፤ «በእኔ አመለካከት አመጽና ሽብር አለመኖር ብቻ ሰላም አድርጌ እወስደዋለሁ» ይኸ ነው መነሻዬ በማለት ቀላል የሆነ ትርጉም ወስደዋል።

«ዲሞክራሲ ስል ደግሞ በመሠረቱ የነፃነት መዋቅር ሆኖ፣ ሥልጣንና ኃላፊነት የዜጎች የሆነበት፣ እያንዳንዱ ዜጋ ይሄንን ሥልጣንና ኃላፊነት በቀጥታ አሊያም በነፃነት በመረጣቸው ግለሰቦች አማካኝነት ተግባር ላይ የሚውልበት ሥርዓት ነው» ብለውናል ዶ/ር ታደሰ።

---

* አቶ አማረ አረጋዊ አንደኛ ደረጃን በመቀሌ፣ ሁለተኛ ደረጃን በአዲስ አበባ ጀኔራል ዊንጌት ት/ቤት ካጠናቀቁ በኋላ ህክምና ለመማር በነበራቸው ፍላጎት እንግሊዝ አገር ለሦስት ዓመት የጠቅላላ ሳይንስ እንደተከታተሉ በ1966 ዓ.ም. የኢትዮጵያ አብዮት በመፈንዳቱ ወደ አገራቸው ኢትዮጵያ ተመለሱ። ከዚያም ሕወሓትን በከተማ ከተቀላቀሉ በኋላ በቀይ ሽብር ወቅት ለአንድ ዓመት ታሰረው እንደተፈቱ በ1969 ዓ.ም. በረሃ ገብተው ከሕወሓት ጋር ሲታገሉ ቆይተው በ1983 ዓ.ም. ኢሕአዴግ በአሸናፊነት የኢትዮጵያን መንግሥት ሥልጣን ስይዝ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ከዚያም የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ሆነው አገልግለዋል። በ1987 ዓ.ም. በገዛ ፈቃዳቸው ሥራቸውን በመልቀቅ አሁን ታዋቂ የሆነውን ሚዲያና ኮሚዩኒኬሽን ድርጅት በማቋቋም ሥራ አስኪያጅና ዋና አዘጋጅ ሆነው በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

ዶ/ር ታደሰ ስለልማት ሲነግሩን ደግሞ «ለእኔ የፈለገው ሰንጠረዥ፣ ቻርት፣ ይምጣ፣ ለእኔ ልማት ማለት የሚታይ፣ የሚጨበጥ፣ በምግቤ፣ በመኖሪያዬ፣ የሚዳሰስ፣ ለውጥ መሆን አለበት። ይኸ ነው ለእኔ ልማት» በማለት ጥርት ያለ ነገር አስቀምጠዋል። መሆንም ያለበት ነገር ይኸው ይመስለኛል።

እንግዲህ ወደ ዋናው ጉዳይ ስንገባ ይኸንን ሁሉ ዶ/ር ታደሰ ያስረዱን ቀደም ብዬ እንደገለጽኩት ከተለየ አቅጣጫ ነው።

እንደ ዶ/ር ታደሰ አባባል ሕብረተሰብም፣ አገርም፣ ዲሞክራሲም፣ ልማትም፣ ሊረጋገጥ የሚችለው በልሂቃን ዙሪያ በመሽከርከር በሚደረገው ትንተና ነው። ለምን እዚያ ላይ አተኮሩ ዶ/ር ታደሰ? ብለን ብንጠይቅ ግልፅ የሆነ መልስ አስቀምጠውልናል። ለእኔ በአንድ ሕብረተሰብ ወሳኝ የሆነው አካል ልሂቅ ነው ብለዋል። እሱ ነው ወሳኝ ነገር! ብለውናል።

እዚህ ላይ የሚነሳው ጥያቄና በውይይቱ እንዲብራራ የምፈልገው በአንድ ሕብረሰብ ውስጥ ወሳኝ የሚባለው ልሂቃን ናቸው ወይ? በአንድ አገር ሰላምም ሊመጣ፣ ዲሞክራሲም ሊመጣ፣ ልማትም ሊመጣ፣ ወሳኝ ብለን የምናስቀምጣቸው ልሂቃን ናቸው ወይ? የሚሉ ናቸው።

ምናልባት ሁላችንም የምንስማማው ልሂቃን በእርግጥ ትልቅ ሚና አላቸው፤ የማይናቅ ሚና አላቸው፤ መተኪያ የላቸውም፤ ልንል እንችላለን። ልሂቃን ወሳኝ ናቸው የሚለውን ግን ዶ/ር ታደሰ በበለጠ ቢያብራሩልን ጥሩ ይመስለኛል። በእውነቱ ሁሉም ነገሮች ተሸክርክሮ ያለው ልሂቃን ወሳኝ ናቸው በሚለው ዙሪያ ስለመጣ ማለቴ ነው።

ዶ/ር ታደሰ ልሂቃን ወሳኝ ናቸው ሲሉ ግን ገዘም ብለው አላስቀመጡም።

ልሂቃን ወሳኝ ናቸው የሚባልበትንም ምክንያት አስቀምጠዋል። «የህገ-ብን ፍላጎት አስቀድመው ያውቃሉ፣ የሕገ-ብን ፍላጎት አስቀድመው ይረዳሉ፣ ይኸንን ፍላጎት ለማሟላት የሚደረገውን ትግል የሚመሩትና የሚያደራጁት እነሱ ናቸው። እነዚህን ሚና የሚጫወቱ ከሆነ ለዚህ ነው ወሳኝ ያልኳቸው የሚል አባባል አላቸው። ስለዚህ አንዱ ይኸ ነው።

ዶ/ር ታደሰ ልሂቃን ወሳኝ ናቸው በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ብለው ካስቀመጡ በኋላ አደረጃጀት ላይ ያተኩራሉ። እሱ ብቻ ሳይሆን፤ አደረጃጀት ላይ ለምን አተኮሩ ሲባል ደግሞ፣ ምክንያቱን ሲገልጹ ልሂቃንን ወሳኝ የሚያደርጋቸው ደግሞ የልሂቃን አደረጃጀት ነው የሚልም ሃሳብ አላቸው። የአደረጃጀታቸው ሁኔታ በጣም ወሳኝ ነው ይሉና አደረጃጀታቸውን በሦስት ይከፍላሉ። እነሱም፤ የተበታተኑና እርስ በርሳቸው የሚዛረፉ፣ በርዕዮተዓለም የተሳሰሩ፣ እና በድርድር ሊቀራረቡ የሚችሉ ይሏቸዋል።

የመጀመሪያዎቹ የተበታተኑ እና እርስ በእርሳቸው የሚዛረፉ ልሂቃን በአንድ አገር ሰላምና ዲሞክራሲ ለማምጣት፣ ልማትን በማምጣት ረገድ፣ መፍትሔ ማምጣት እንደማይችሉ ጠቁመዋል።

በርዕዮተዓለም የተሳሰሩት ደግሞ ከእኛ ውጭ አመለካከት መኖር የለበትም፣ ሕብረተሰቡ አንድ ዓይነት አመለካከት ሊኖረው ይገባል፤ በአንድ ዓይነት አስተሳሰብ እንቀርጸዋለን፤ ይላሉ። በእኛም አገር ሕብረተሰቡን በሞላ አብዮታዊ ዲሞክራሲያዊ አድርገን እንቀርጸዋለን

የማ.ባል በይፋ የወጣ አመለካከት አለ፤ እንደዚያ ስለሚሉ መጨረሻቸው ምናልባት ሰላም ሊያገኙ ቢችሉም፣ ዲሞክራሲ አይኖርም፣ ሰላሙ ለልማት መሠረት አይሆንም። ብቸኛው መፍትሔ፤ በልሂቃን ዙሪያ እንደአደረጃጀት መፍትሔ ሊያመጣ የሚችል በድርድር ሊቀራረቡ የሚችሉ ልሂቃን ሲኖሩ ብቻ ነው።

የብ.ሄ.ተ.ኖ.ት አይጠቅሙንም፣ በርዕዮተዓለም የተሳሰሩትም አይጠቅሙንም፤ የተለያየ አመለካከት ያላቸው በድርድር መቀራረብ የሚችሉ ካሉ ግን መፍትሔው እነሱ ዘንድ ነው የሚል ሀሳብ ነው ዶ/ር ታደሰ ያስቀመጡት።

ይህ በጣም ደስ የሚል ነው። ታሪካዊ የሆኑ ምሳሌዎችንም አስቀምጠውልናል። ስለዚህ ልሂቃን ወሳኝ ከሆኑ፣ አደረጃጀታቸው ወሳኝ ከሆነ፣ ከአደረጃጀትም ደግሞ በድርድር የማቀራረብ የልሂቃን አደረጃጀት መፍትሔ ከሆነ፣ እንዴት እርሱ ሊመጣ ይችላል የሚል ጥያቄ ሲነሳ ደግሞ ሦስት ዓይነት አማራጭ አስቀምጠዋል ዶ/ር ታደሰ። እነዚህም፤ በድርድር ሊቀራረብ የማ.ች.ል የልሂቃን አደረጃጀት እውን ሊሆን የሚችለው ወይ በውጭ ተጽዕኖ፣ ወይ ቀስ በቀስ መሀከል ላይ የመሰባሰብ ዝንባሌ ባላቸው፤ ወይም ሰጥቶ መቀበል በሚለው መርህ ነው ብለዋል ዶ/ር ታደሰ።

በግልጽ በውጭ ኃይል የሚመጣ መቀራረብ ውጤት እንደሌለው፣ ዘለቄታም እንደሌለው ያስቀምጠና ለዚህ መፍትሔ የሆነውና ተመራጭም የሚሆነው፣ ሰጥቶ የመቀበል መርህ ነው ይላሉ ዶ/ር ታደሰ። እዚህችም ጋ አንድ የምትነሳ ጥያቄ አለች። ለረጅም ጊዜ ተቀብለን የኖርነው እውነታ አለች፣ ዶ/ር ታደሰ የተፈታተኑት።

ሥልጣን ያለው አካል ቢደራደርም ወዶ እንዳልሆነ፣ በአጠቃላይ ሲታይ ተደራድረው ሥልጣን ቢለቁም፣ የደቡብ አፍሪካው እነ ዲ. ክለርክም ቢሆኑ ሳይወዱ እንጂ ወድደው ነው ሥልጣን የለቀቁት ማለት እንደማይቻል ዶ/ር ታደሰ በሚገባ አስቀምጠዋል።

ስለዚህ ወድደው ሥልጣን ይለቃሉ የሚባለው ብዙ ጊዜ ስህተት ነው። በእኛም ሁኔታ ይህ ሊታሰብበት ይገባል። አስገድዶ ከሥልጣን ማውረድ የግድ በመሣሪያ መሆን አለበት ወይ? የፖለቲካ ተጽዕኖ ተደርጎ ከዚህ የባሰ ሊመጣ እንደሚችል በመገንዘብ፣ ኪሳራውን ለመቀነስ ሲባል የተደራደረን አካል ወድዶ ነው ስልጣን የለቀቀው የሚለው ሃሳብ በቀጣዩ ውይይት የሚመለስ ሊሆን ይገባል። በነገራችን ላይ ከዚህ ጋር ተያይዞ ዶ/ር ታደሰ ፖላንድን እንደ ምሳሌ እንስተው ነበር።

አንዳንድ ጊዜ (elite) የሚባለው አተረጓጎም ከምሁራን ጋር ተያይዞ የሚመጣ ነው። የፖላንድን ምሳሌ ስላነሱ አንድ ነገር ትዝ ብሎኝ ነው። በአንድ ሕብረተሰብ ሊመጣ የሚችል ለውጥ በልሂቃን ነው ካልን (elites intellectuals ናቸው ብዬ ብተረጉመው) የፖላንዱ ጊዳንስክ ንቅናቄ የልሂቃን እንቅስቃሴ ነበር ወይ? እንደሚታወቀው ይህ ንቅናቄ የአንድ ወደብ ሠራተኞች ንቅናቄ ነው። ኋላ ኋላ ሌሎች ተደባልቀው ሊሆን ይችላል። የእንደዚህ ዓይነት የሠራተኛ እንቅስቃሴ በፖላንድ ለውጥ አስከትሏል። እንዲህ ዓይነቱን የሠራተኛ እንቅስቃሴንስ እንደ ልሂቃን እንቅስቃሴ መቁጠር ይቻላል? ወይስ የፖላንዱ እንቅስቃሴ ጠቅሶ አጋላሚ ነው ሊባል ይችላል?

ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ፣ ዶ/ር ታደሰ ያስቀመጡት ነገር አለ። እንደ ሌላው አገር የኢትዮጵያን ልሂቃን መተንተንም ሆነ ማጥናት አስቸጋሪ እንደሆነ ይታያል። ምክንያቱም ሦስት ባሕሪያት እንዳሉት ዶ/ር ታደሰ ተናግረዋል። እነዚህንም ሲዘረዝሩ፤ የተበታተኑና የሚባረሩ ኢትዮጵያውያን ልሂቃን አሉ። በየራሳቸው ቡድን ውስጥ ከሌላው ጋር ሳይሆን በርዕዮተዓለም መተሳሰር ያደረጉ፣ ግን ከሌላው ጋር መተሳሰር ያቃታቸው፣ ልሂቃን አሉ። ሦስተኛውና ሌላው የጋራ ባሕሪ ግን ሁሉም ለፍትሕና ለእኩልነት እንታገላለን የሚሉ መሆናቸው ነው። ተጨማሪ ጥናት ቢያስፈልግም በአጠቃላይ እነዚህ ባሕሪያት አሏቸው የሚል ነገር ነው ዶ/ር ታደሰ ያላቸው ሀሳብ። የኢትዮጵያ ሁኔታ ከኢትዮጵያ ጥቅም አንፃር ታይቶ በልሂቃን ድርድር መፈታት እንዳለበት ነው ዶ/ር ታደሰ ያስቀመጡት። ይሁንና እኔም በትክክል የምቀበለው አንድ ያስቀመጡት ነገር አለ። ሁለት አማራጭ መንገድ አለ። አንዱ የሚፈለግ፣ ሌላኛው የማይፈለግ፣ አማራጭ!

የማይፈለግ አማራጭ በልሂቃን አካባቢ የነበረው ችግር የርዕዮተዓለም ችግር ነበር። አሁን፣ አሁን፣ ግን የርዕዮተዓለም ችግር አላዋጣ እያለ ሲሄድ በሌላ ችግር እየተተካ ነው። ያም ችግር የዘረኝነት ችግር ነው። በርዕዮተዓለም ያጋጥመን ከነበረው ችግርና ከደረሰብን ውድመት በላይ ብዙ ሊደርስብን ስለሚችል በጣም አስፈሪና ቀይ ካርድ ደረጃ እንዳለን፣ አደገኛ ሁኔታ ላይ እንዳለን፣ መሆኑ ሁላችንንም የሚያሳስበን ጉዳይ ነው።

መደራደሩ በአሸናፊነት ከተወጣ ግን ትክክለኛ መፍትሔ ሊመጣ ይችላል። ስለዚህ የአደጋ አማራጭ እንዳይመጣ፤ አሁን ሁለቱም ክፍት ናቸው! የእኛ ልሂቃን መቀራረብ እና መደራደር እንዳለባቸው ነው የሚታየኝ። ይህ ሊመጣ የሚችለው ግን ዶ/ር ታደሰ እንደ መፍትሔ ያስቀመጧቸው ነጥቦች አሉ። ሰብአዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶችን ማክበር፤ መግባባት፣ መቻቻልና መደራደር መልመድ፤ መራጩም፣ ተመራጩም፣ አስመራጩም ለምርጫ ደንብና ሥርዓት ተገዥ መሆን፤ በተለይ በሥልጣን ላይ ያለው የልሂቃን ቡድን የአገርን ጥቅም ማስቀደም፣ ዲሞክራሲያዊ አስተሳሰብን ማንገስ፣ ጽንፈኝነት፣ አካባቢነትንና የመሳሰሉትን ማስወገድ፤ ይኸ ነው መፍትሔው። እነዚህን ተግባራዊ ካደረግን ከዚያኛው አደጋ እንወጣለን (እናመልጣለን)። ይኸኛውን አካሄድ ካልሄድን፣ ያኛው አደጋ እንዳለ ዶ/ር ታደሰ አስቀምጠዋል። ትክክል ናቸው ዶ/ር ታደሰ።

በአጠቃላይ ስናይ የተለያዩ ጥያቄዎች ማንሳት እንችላለን። በልሂቃን ዙሪያ የተቀመጠው ሀሳብ ግን እኔ በበኩሌ በጣም ትክክልና ልናየው የሚገባ ነው እላለሁ። አዲስ አቀራረብ ነው። ዓለም ውስጥ ያለው ችግር ብቻ ሳይሆን በአገራችንም ያለ ችግር ነው። ምናልባት በአገራችን ሥረ-መሰረቱ ይተንተን ቢባል በተማሪው ንቅናቄ ውስጥ የጀመረ ችግር ሊሆን ይችላል። በተማሪ እንቅስቃሴ ውስጥ የነበረው የርዕዮተዓለም ብቻ ሳይሆን በተራ አመጋገብና አንዱ ክፍል ተቃውሞ (boycott) እናድርግ ሲል ሌላው አናደርግም የሚል፣ በትንሽ ነጥብ እንኳ እንዴት መካረር እንደነበረ፣ ከዚያ በኋላ ይኸ ኃይል ነው የተለያየ የፖለቲካ ድርጅቶች ፈጥሮ እስካሁን ድረስ ያለው። የዛሬው ችግራችን መሠረቱ እርሱ ሊሆን ይችላል። አንገብጋቢ ጉዳይ ነው። ዶ/ር ታደሰን እንደገና እያመሰግንሁ ይኸንን ዋና ጉዳይ በውይይት አዳብረን ዶ/ር ታደሰ ያቀረቡልንን ጽንሰ ሀሳብ በሌሎች ሀሳብ ሰጪዎች ብናዳብር ያገራችንን ችግር ለመረዳትና ለመፍታት ጠቃሚ ይመስለኛል።

አመሰግናለሁ!

በዶ/ር ታደሰ ብሩ ጽሑፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት

ጃለሌ ኤፊጋ*

ዶ/ር ታደሰ ያነሱት ሃሳብ፣ የአቀራረብ ክህሎቱና አትኩሮት የሳበበት አቅጣጫ ማለትም በኢትዮጵያ የኃላና የወደፊት ሁኔታ ላይ የልሂቃን ሚና ለተኮር የሚገባው እንደሆነ ማሳየታቸው እጅግ ጠቃሚ ሃሳብ ነው። በዕሁፉ ዙሪያ ያለኝን ሃሳብ ነጥብ በነጥብ ለማስቀመጥ እሞክራለሁ።

ዶ/ር ታደሰ ያነሱትን ሃሳብ እያደነቅሁ፣ ዕሁፉ ከተሰጠው ርዕስ ይልቅ የበለጠ ተስማሚ ነው በዬ የማስበው ርዕስ «ሰላም፣ ዲሞክራሲና ልማት፤ የልሂቃን ሚና ዛሬና ነገ በኢትዮጵያ» ነው።

በዕሁፉ የተቀመጠት ሶስት ዋና ዋና ሃሳቦች በነኖሩ መንገድ ትርጓሜ የተሰጣቸው ቢሆንም በሶስቱ መካከል ማለትም በሰላም፣ ዲሞክራሲና ልማት የተንፀባረቀው ቀጥተኛና ተሳሳቢ ግንኙነት በታሪክ ሂደት ሁልጊዜ የማይታይ (historically "unprovable") ሆኖ እናገኛዋለን።

በዶ/ር ታደሰ ዕሁፍ እንደቀረበው ዲሞክራሲ በአብዛኛው በወጤቱ ሳይሆን በመዋቅሩ መሰየም እንዳለበት ያመለክታል። ይሁን እንጂ ቅርፅን ያለ ወጤት ነኖሎ መወሰድ ምን ያህል (በዲሞክራሲና በሊሎች፣ ሁለት ዋና ሃሳቦች ማለትም በሰላምና ልማት) ያስኬደናል ብሎ መመርመር ጠቃሚ ይመስለኛል። ማለትም፡ ቅርፅ ያለ ይዘት (form without substance) ለይቶ መመልከት ዘላቂ አይሆንም የሚል አስተያየት አለኝ። ለዚህም (3ኛው ዲሞክራሲያዊ ማዕበል) በ3rd Wave of Democratization ውስጥ ያሉ ሃገራትን መመልከት በቂ ነው።[1] እነዚህን ሀገራት ስንከናወላቸው በአጠቃላይ በሽግግር ላይ ያሉ ዲሞክራሲዊ አገሮች (transition democracies) ሲባሉ ሊሎች፣ ደግሞ ክፊል ዲሞክራሲዊ አገሮች (semi-democracies) ይባላሉ። በሽግግር ላይ ያሉ የሚለው ሃሳብ የሚያመለክተው የተጠናከሩ ዲሞክራቲክ አገሮች (consolidated democracies) ለመሆን በሂደት ላይ ያሉ ለማለት ነው። እነዚህ ሀገራት አስርተ አመታትን ያስቆጠሩና አንዳንዶቹም ዲሞክራሲንና በተለይም ጊዜውን ጠብቆ የሚደረግ ምርጫን ማለትም ሰላማዊ የስልጣን ሽግግርን (peaceful transition of power) እና የአምባገነናዊ (authoritarian) ባህሪያትን አቀላቅለው ከሂደት ይልቅ እንደ ቋሚ አገዛዝ የአስተዳደር ባህሪ በመያዛቸው ክፊል ዲሚክራሲያዊ (semi-democracy) ሊባሉ ችለዋል።

ሌላው በዶ/ር ታደሰ በቀረበው ዕሁፍ ውስጥ ህዝብ በልማት ውስጥ ያለው ሚና አናሳ ሆኖ ታይቷል ብዬ አምናለሁ። ሕዝብ በሰላምና ዲሞክራሲ ግንባታ እንዲሁም በልማት ጉዳዮች

---

* ወ/ሮ ጃለሌ ኤፊጋ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ የማስተርስ ዲግሪያቸውን በDevelopment Studies from the Institute of Social Studies, the Hague, Netherlands; ከ1991 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት ክፍል በመምህርነትና ተመራማሪነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

[1] ለዚህ ማብራሪያ Samuel Huntington (1991) The Third Wave: Democratization in the last Twentieth Century. Oklahoma Press ይመልከቱ

ላይ ገለልተኛ (passive) አይሆንም:: ስለዚህም «ሰፊው ሕዝብ» የማይጨበጥ አካል ብቻ ተደርጎ የተወሰደው አቀራረብ ብዙም የሚያስኬድ አይመስለኝም::

የሀገር ሰላምንም ጉዳይ ስንቃኝ «ግለሰብ» የሚለውን ብቻ መነሻ ሃሳብ ማድረግ ሊቸግረን ይችላል:: ምክንያቱም የወል መብቶች ማለትም፤ እንደ ሴቶች፣ ሀገናት፣ አናሳ ህዝቦች፣ ወዘተ... መብቶች ጉልህ እየሆኑ መጥተዋልና!

የጽሁፉ አትኩሮት ልሂቃን ላይ በመሆኑ አሁን የአስተያየቴን አቅጣጫ ዶ/ር ታደሰ በከፋፈሉት የልሂቃን አደረጃጀት ላይ አደርጋለሁ:: በሦስት የተከፈሉትን አደረጃጀቶች አንድ በአንድ ለመመልከት እሞክራለሁ::

የተበታተኑና እርስ በእርሳቸው የሚፃረሩ ልሂቃን ያሉበት ማህበረሰብ (Disunited National Elite)

ይህ አይነቱ ህብረተሰብ ተፈጥሮአዊ ወይም በተለምዶ (natural) የምናገኘው አይነት ሕብረተሰብ ነው ብዬ አምናለሁ:: ልዩነት (diversity) በሕብረተሰብ (የልሂቃንን ሚና ጨምሮም ይሁን ሳይጨምር) የተለመደ የሕብረተሰብ ሁኔታ ነው::

ይሁን እንጂ በተለይም የልሂቃን ሚና የሚያተኩረው ጥንታዊ (primodial) በሆኑ ጉዳዮች ላይ ነው:: ለምሳሌ፤ ጎሳ፣ ዘር፣ ሃይማኖት ላይ፤ ይህም ግጭትን በሕብረተሰቡ ውስጥ የማስነሳቱ ብሎም ለሰላም እንቅፋት የመሆኑ አጋጣሚን ይጨምራል::

በፅሁፉ ውስጥም የተዘረዘሩት አብዛኛው አሉታዊ ገፅታዎች የሚከሰቱት በዚህ አይነት አጋጣሚዎች ነው::

በርዕዮተ-ዓለም የተሳሰሩ ልሂቃን ያሉበት ማህበረሰብ (Ideologically United National Elite)

ይህ አይነቱ ሕብረተሰብ በተፈጥሮ (natural) የሚገኝ ሕብረተሰብ አይደለም::

በእንዲህ አይነቱም ሕብረተሰብ ዲሞክራሲ፣ ሰላምና ልማት ዝግምተኛ መሆናቸው የማይቀር ነው::

በድርድር የተቀራረቡ ልሂቃን ያሉበት ማህበረሰብ (Consensually Unified National Elite)

ይህ ሕብረተሰብ ደግሞ የተለያዩ (diverse) ልሂቃን ያሉበት ግን ተስማሚ ዲሞክራሲ consenssional democracy ለመገንባት የሚወስኑበት አይነት ነው::

በዶ/ር ታደሰ ከቀረበ·ት ምክንያቶች በተጨማሪ እንዲህ አይነቱ የልሂቃን ሁኔታ የሚፈጠረው አንዱ ቡድን በሌላው ላይ የበላይ መሆን (dominate) በሚያቅተው ጊዜ ነው:: ለምሳሌ፣ በኔዘርላንድ፣ ቤልጂየም፣ ወዘተ... ሀገራት የሚታይ እውነታ ነው::

የውይይቱ ዋነኛ መነሻና ትኩረት ወደ ሆነችው ኢትዮጵያ ስንመለስ ደግሞ በስፋት ከተዘረዘሩት ጽንሰ ሃሳቦች (concepts)፣ እንዲሁም የልሂቃን ሚና በሕብረተሰቡ ውስጥ ምን ሊሆን እንደሚችል ከሚተነትነው ሃሳብ በመነሳት «በኢትዮጵያ በፅሁፉ መልካም ነው የተባለውን ውስጣዊ አንድነት ያላቸውን ልሂቃን (internally unified elite) ማምጣት ይቻላል ወይ? የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ ተገቢ ነው::

ይህንን ጥያቄ ለመመለስ ቀላል ባይሆንም ረጅም ትግልን የሚጠይቅ ሂደት ነው ብዬ አስባለሁ:: ይህንንም ስል ዋነኛው ምክንያቴ ብዙ ብዜረሰቦችን እንወክላለን የሚሉ ልሂቃን ይቅርና ለአንድ ብዜረሰብ ቆመናል በሚሉት መካከል እንኳ ያለውን የሃሳብና የርዕዮተ ዓለም (ideology) ልዮነት ለማስታረቅ ቀላል ስለማይሆን ነው:: አንዱ አብዮታዊ ዲሞክራሲ፣ ሌላው ሊብራሊዝም፣ ሌላኛው ደግሞ ፊዴራሊስት፣ ወዘተ... ብለው ያነሱአቸውን ሃሳቦች ማስታረቅና በእነርሱ መካከል እንኳ ተስማሚ ሃሳብ consensus ማምጣት ቀላል አይመስልም::

የልሂቃን ሚና በአብዛኛው በጽሁፉ የታየው ልሂቃን ለበቻቸው ሊጫወቱ በሚቻላቸው ሚና ላይ ሲሆን በተጨማሪ አትኩሮት የሚጠይቅ እነዚህ ሊሂቃን አንድ በተዋቀረ ስርዓት (structure) ውስጥ የሚሰሩ በመሆኑ መዋቅሩ በእነርሱ ላይ ሊያሳድር የሚችለውን ተፅዕኖ መገምገም ይመስለኛል::

ሌላው ሊተኮርበት የሚገባው ነጥብ ዲሞክራሲ ሁልጊዜ ከሰላም ጋር ተያይዞ እንደማይመጣ ነው:: ዲሞክራሲ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን የራስ አገዛዝ ነፃነት ሃሳብ (autonomy) ይዞ ይመጣል:: ይህም ህገሰች ራሳቸውንና ያላቸውን ሚና ዳግም እንዲመለከቱና እንዲከልሱ (redefine) የሚነሳበት አጋጣሚ ጥቂት ነው አይባልም:: ይህም ለግጭቶች መነሻ አንዱ ምክንያት መሆኑ ከታወቀ ስንብቷል::

በአንዳሩ ዲሞክራሲና ልማት ሁልጊዜ አብረው የሚሄዱ እንዳልሆኑ መገንዘብ እንችላለን:: ደቡብ ኮሪያን ብንመለከት ከዲሞክራሲ ቀድሞ የመጣው የኢኮኖሚ ልማት /እድገት/ ነው:: ኢንዶኔሻያንም ብንመለከት በአምባገነኑ ሱሃርቶ ዘመን የነበረው ልማትና የኢኮኖሚ እድገት የተሻለ እንደነበር መመልከት ይቻላል::

ኢትዮጵያን በተመለከተ ዶ/ር ታደሰንም ሆነ ተሳታፊዎችን ልጠይቅ የምፈልገው ዋና ነገር አለ:: እስከ አሁን ልሂቃን እያልን ብዙ ተነጋግረናል:: ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ «ልሂቃን እነማን ናቸው?» ብለን ልንጠይቅ ይገባናል:: በዶ/ር ታደሰ ትርጓሜ ልሂቃን የፖለቲካ ብቻ ሳይሆኑ የሃይማኖት፣ የትምህርት፣ ወዘተ... ተሰሚነት ያላቸው የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች ወይም ሰዎች በሚል ተተርጉሟል:: እውን የሃገር ሽማግሌዎችን፣ የሃይማኖት መሪዎችን፣ ወዘተ... ጨምረን እያሰብን ይሆን? በኢትዮጵያስ የፖለቲካ ሂደት ምን አይነት ተፅዕኖ አሳድሯል? መልሱን ለሁላችን እተዋለሁ::

በተለያዩ መድረኮች የምናያቸው ተመሳሳይ ገፅታዎች የልሂቃንን ማንነት ከተወሰነ ትውልድ፣ ብሎም ከተለመዱ ጥቂት ሰዎች፣ ከተማሪ ንቅናቄ ትውልድ (students movement generation) ያለፉ አያደርገውም። በአብዛኛው ልሂቅ (elite) የሚለው ቃል ወጣቱን፣ ሴቱን፣ የማያጠቃልል እስከማይመስል ደርሷልና ነው ይህንን የትኩረት ሃሳብ ማንሳቴ።

ከዚህም ባሻገር ይህ ከአንድ ትውልድ (ከአንድ ምንጭ) የተቀዳው ትውልድ በአብዛኛው የሃገሪቱን ፓለቲካ ወደ አንድ አቅጣጫ ዘመም እንዲል አድርጎታል።

በተጨማሪም በተለያዩ ትልቅ መድረኮች ላይ በልሂቃኑ መካከል የሚደረጉት ድርድሮች ከሕብረተሰቡ ጉልህ ችግር ይልቅ በልሂቃኑ የስልጣን ወንበር ላይ ያተኮረ አካሄድ የማያንፀባርቁ ሆነዋል።

ከላይም አንደጠቀስኩት ውስጣዊ ክፍፍል በኢትዮጵያ ልሂቃን መካከል የሚታይ አብይ ገፅታ ነው።

በመጨረሻም ጠቃሚ ሃሳብ ነው ብዬ የማምነው ለተወሰኑ ጊዜያት ከተተኮረባቸው የፖለቲካ ልሂቃንና የጎሳ ክፍፍል (categorization) ባሻገር የሕብረተሰብን አብሮነት የሚያጎሉ የሃይማኖት መሪዎችና የሀገር ሽማግሌዎችን ሚና ማዳበር ተገቢ ነው እላለሁ።

ኤነርጂ እና ልማት በኢትዮጵያ

በቀለ ባይሣ*

1. መግቢያ

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ወደ ቀረቡት ዋና ዋና ሃሳቦች ከመሄዳችን በፊት ስለ ኤነርጂ ምንነትና ተያያዥ ጉዳዮች መግለጹ ስለመስከ መጠነኛ ግንዛቤ ለማሰጨበጥና የጋራ መግባባትን ለመፍጠር ይጠቅማል የሚል ዕምነት አለኝ። ስለዚህም የአንዳንድ ጽንሰ-ሐሳቦች (ቃላት) ማብራሪያ ቀነስ ተሰጥቷል።

ኤነርጂ (energy) መነሻው ከግሪክ (*ergon* ማለትም work ወይንም ሥራ)ና ከላቲን (energia) የሆነ ከአንግሊዘኛ ተወስዶ በአማርኛ ውስጥም በማገልገል ላይ የሚገኝ ቃል ነው [1], [2]። በአጭሩ ኤነርጂ ሥራን ለመከወን የሚያስችል አቅም ወይም ጉልበት ተብሎ ሊገለጽ ይችላል። ኤነርጂ ብዙ ዓይነት ገጽታዎች አሉት። አንድ አካል በመንቀሳቀሱ ምክንያት ተንቀሳቃሽ (kinetic) ኤነርጂ ሲኖረው አካሉ ካለው አካላዊ (physical) ወይም ኬሚካላዊ ሁኔታ የሚኖረው ኤነርጂ ግን እምቅ (potential) ኤነርጂ ይባላል። ለምሳሌ ያህል ንፋስና የሚፈስ ውሃ ተንቀሳቃሽ ኤነርጂ ሲኖራቸው በከፍታ ቦታ ላይ የተከተረ (የተከማቸ) ውሃና ነዳጅ ዘይት እምቅ ኤነርጂ አላቸው።

ኤነርጂ ከብዙ ዓይነት ምንጮች ይገኛል። የማገዶ እንጨት፣ የድንጋይ ከሰል (coal)፣ ነዳጅ ዘይት፣ ውሃና ዩራንየም (ጨረር አመንጪ አቶሞች) ዋናዎቹ የኤነርጂ ምንጮች ናቸው። የኤነርጂ ምንጮች ብዙ ጊዜ ከኤነርጂ ጋር በቅጥያነት ይጠራሉ። ይህም የኤነርጂውን ምንጭ ለመጠቀም ያገለግላል። ለምሳሌ የእንጨት ኤነርጂ ሲባል ከእንጨት የሚገኝ ኤነርጂ ማለት ነው። በዚሁ መሠረት እንደምንጩ ዓይነት የድንጋይ ከሰል ኤነርጂ፣ የአቶም ኤነርጂ፣ የውሃ ኤነርጂ ወዘተ...፤ ተብሎ ይጠራል። ከዚህም በቀር ኤነርጂ እንደምንጩ ባሕሪይ ታዳሽ (renewable)ና ታዳሽ-ያልሆነ (non-renewable) ተብሎ ሊከፈል ይችላል። ታዳሽ ኤነርጂ ታዳሽ ከሆነ ምንጮች የሚገኝ ሲሆን እንደ እንጨት፣ ፀሐይ፣ ውሃ፣ ንፋስ፣ ጂኦተርማልና (የከርሰምድር መቀት/ እንፋሎት) የባሕር ሞገድ ያሉት ታዳሽ የኤነርጂ

---

* አቶ በቀለ ባይሣ ከሁለት ዓመት በፊት በተቋቋመውና በኤነርጂ ጉዳዮች ላይ የሚሠራ ኢንስድ (Ethiopian Network for Sustainable Energy Development) በመባል የሚታወቅ ማኅበር የቦርድ ሊቀመንበር ናቸው። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመጀመሪያ ድግሪያቸውን እ.አ.አ. በ1981 በመካኒካል ምሕንድስና፣ እንግሊዝ አገር ከሚገኘው ሊድስ ዩኒቨርሲቲ እ.አ.አ. በ1993 በኬሚካል ምሕንድስና የድሕረ-ምረቃ ዲፕሎማ አግኝተዋል። በመተሐራ ስኳር ፋብሪካ፣ በቀድሞው የኢንዱስትሪ ሚ/ርና በኢስት አፍሪካ ኢንቨስትመንት ለኩራቲስ የግል ኩባንያ ውስጥ ለ23 ዓመታት ሠርተዋል። በአሁኑ ወቅት በንጋት የመካኒካል ምሕንድስና አ.ማ. ውስጥ በሥራ አስኪያጂነት እየሠሩ ናቸው።

ምንጮች ናቸው። ከዚህ አንፃር እንደ ድንጋይ ከሰል፣ ነዳጅ ዘይትና የተፈጥሮ ጋዝ ያሉት ታዳሽ ያልሆኑ የኤነርጂ ምንጮች ናቸው።

በሳይንስ ወይም በተፈጥሮ ሕግ መሠረት ኤነርጂ ከአንዱ ዓይነት ወደ ሌላው ዓይነት ይቀየራል እንጂ ፈጽሞ ሊደመሰስ ወይም ሊፈጠር አይችልም። ለምሳሌ የውሃ ዕምቅ ኤነርጂ ወደ ኤሌክትሪክ ኤነርጂ ሊቀየር ይችላል። ይህም በየኩተሞቻችን ውስጥ የምንጠቀምበትን ኮረንቲ (electricity) ይሰጠናል። የነዳጅ ኤነርጂም እንዲሁ በመጀመሪያ ወደ መቀት ኤነርጂ፣ ቀጥሎ ወደ መካኒካዊ (mechanical) ኤነርጂ፣ በኋላም ወደ ኤሌክትሪክ ኤነርጂ ተቀያሮ ሰፊ አገልግሎት ሊሰጥ ይችላል።

ከላይ የኤነርጂ ዕንሰ-ሐሳቦችን ለመግለጽ ዘወትር ከምናያቸውና ከምናከናውናቸው ተግባራት ጋር ለማዛመድ ተሞክሯል። ይሁን እንጂ ሰፋ ተደርጐ ሲታይ ኤነርጂ የሕይወትም መሠረት ነው። እያንዳንዱ ሕይወት ያለው ነገር (የተክልም ሆነ የእንስሳ) ሕዋስ (cell) በሕይወት ለመቆየት ምግብ ያስፈልገዋል። ምግብ ደግሞ በዋናነት ኤነርጂን ለማመንጨት ይውላል። ስለዚህም በሕይወት ለመቆየት ኤነርጂ ስለሚያስፈልግ ሕይወትና ኤነርጂ እጅግ በጣም የተቆራኙ መሆናቸውን እንገነዘባለን።

ከዚህ መለስ ብለን ቀድሞ ወደአነሳነው የዘወትር ተግባራችን ስንመለከት ኤነርጂ ለብዙ ተግባራት አስፈላጊ መሆኑን እናጤናለን። በቤታችን ምግባችንን ከማብሰልና ብርሃንና መቀት ከማግኘት ጀምሮ፣ ወደ ሥራ ቦታችን ወይም ሩቅ መንገድ ለመሄድ ለሚያስፈልገን የማጓጓዣ መሣሪያና በመስክም ሆነ በቢሮ የሥራ ቦታ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ለምንጠቀምባቸው መሣሪያዎች፣ አገልግሎቶችና ሌሎች ግብአቶች ሁሉ ኤነርጂ አስፈላጊ ነው። አንዳንድ ምሳሌዎችን ለመጥቀስ ያህል በየብስ (በመኪናም ሆነ በባቡር)፣ በአየርና በባሕር ለሚያረጉ ጉዞዎች ነዳጅ ያስፈልጋል። በመስክ ለግብርናና ለኮንስትራክሽን ሥራ የሚያገለግሉ መሣሪያዎች የሚንቀሳቀሱት በነዳጅና በኤሌክትሪክ ኤነርጂ ነው። እዚህ ላይ እንደ እኛ አገር ያለው ኋላቀር ግብርና የዘመናዊ ኤነርጂ ቀጥተኛ ተጠቃሚ አይደለም ሊባል ይችል ይሆናል። ይህ እውነት ነው። ይሁን እንጂ ኋላቀሩ ግብርናም ቢሆን በእንስሳትና በሰው ጉልበት ተጠቃሚ በመሆኑ ኤነርጂ እንደሚያስፈልገው ሊጤን ይገባል። በሌላም በኩል የአገራችን ግብርና ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍተኛ የኬሚካል ማደበሪያ ተጠቃሚ ሆኗል። ማዳበሪያ ደግሞ በፋብሪካ ውስጥ በጣም ከፍተኛ ኤነርጂ በመጠቀም የሚመረት በመሆኑ ዞሮ ዞሮ ግብርናችንም ቢሆን ከፍተኛ የኤነርጂ ተጠቃሚ ነው። ማዳበሪያ በራሱ ለግብርናው እንደ ኤነርጂ ግብአትም የሚቆጠር ነው።

ኢንዱስትሪ ከፍተኛ የኤነርጂ ተጠቃሚ መሆኑ ግልጽ ነው። ልዩ ልዩ የማምረቻና የመገልገያ መሣሪያዎች፣ በነዳጅ መልክ ይሁን በሌላ፣ ያለ ኤነርጂ ሊንቀሳቀሱ አይችሉም። በተጨማሪም ለልማት ሥራዎች በጣም አስፈላጊ የሆኑት የኮንስትራክሽን (ግንባታ) ዕቃዎች፣ ብረትና ሲሚንቶ፣ በጣም ከፍተኛ ኤነርጂ የሚፈጁ የኢንዱስትሪ ምርቶች ናቸው። ወደ

መ·ገር ሲ·ሚ·ን·ቶ· ፋ·ብሪካ በ·ሚ·ወስ·ደ·ው የሆ·ለ·ታ መ·ንገ·ድ ላ·ይ በየ·ቀ·ኑ· የ·ሚ·መ·ላ·ለ·ሱ·ት·ን በር·ካ·ታ የ·ነ·ዳ·ድ· ቦ·ቴ·ዎ·ች የ·ተ·መ·ለ·ከ·ተ· ለ·ው ይህ·ን ጉ·ዳ·ይ በ·ቀ·ላ·ሉ· ሊ·ያ·ስ·ተ·ው·ል ይ·ች·ላ·ል።

ዘ·መ·ና·ዊ·ው የ·መ·ረ·ጃ·ና የ·መ·ገ·ና·ኛ· ዘ·ዴ (information and communication technology) ያ·ቀ·ፋ·ች·ው· ል·ዩ· ል·ዩ· መ·ሣ·ሪ·ያ·ዎ·ች (ሬ·ድ·ዮ፣ ·ቴ·ሌ·ቪ·ዥ·ን፣ ኮ·ም·ፒ·ው·ተ·ር፣ ስ·ል·ክ፣ ወ·ዘ·ተ...፤) ያ·ለ ኤ·ነ·ር·ጂ ሊ·ን·ቀ·ሳ·ቀ·ሱ· አ·ይ·ች·ሉ·ም። ሌ·ሎ·ች የ·አ·ገ·ል·ግ·ሎ·ት· ኢ·ን·ዱ·ስ·ት·ሪ (ሆ·ቴ·ሎ·ች፣ የ·ገ·በ·ያ ማ·ዕ·ከ·ሎ·ች፣ ሱ·ቆ·ች ወ·ዘ·ተ...፤) ም·ሳ·ሌ·ዎ·ች ማ·ቅ·ረ·ብ ይ·ቻ·ላ·ል። ይ·ሁ·ን እ·ን·ጂ ከ·ላ·ይ· የ·ተ·ገ·ለ·ጸ·ው ለ·አ·ብ·ነ·ት· በ·ቂ· ስ·ለ·ሚ·ሆ·ን የ·ኤ·ነ·ር·ጂ·ን· ሁ·ለ·ገ·ብ·ነ·ት·ና ለ·ሁ·ሉ·ም· ኤ·ኮ·ኖ·ሚ·ያ·ዊ·ና· ማ·ኅ·በ·ራ·ዊ· ዘ·ር·ፎ·ች· አ·ስ·ፈ·ላ·ጊ· መ·ሆ·ን ከ·ም·ሳ·ሌ·ዎ·ቹ· መ·ገ·ን·ዘ·ብ· ይ·ቻ·ላ·ል።

2 የኤነርጂና የልማት ቁርኝት

ኤ·ነ·ር·ጂ·ና· ል·ማ·ት· በ·ጣ·ም· የ·ተ·ቆ·ራ·ኙ· ና·ቸ·ው። ብ·ዙ· ኤ·ነ·ር·ጂ· የ·ሚ·ጠ·ቀ·ሙ· ሀ·ገ·ሮ·ች· ብ·ዙ· የ·ለ·ሙ· አ·ገ·ሮ·ች· ና·ቸ·ው። ም·ክ·ን·ያ·ቱ·ም· ቀ·ደ·ም· ሲ·ል· እ·ን·ደ·ተ·ገ·ለ·ጸ·ው· ሁ·ሉ·ም· ኤ·ኮ·ኖ·ሚ·ያ·ዊ·ና· ማ·ኅ·በ·ራ·ዊ· የ·ል·ማ·ት· ሥ·ራ·ዎ·ች· ኤ·ነ·ር·ጂ·ን ይ·ፈ·ል·ጋ·ሉ፤ ይ·ጠ·ቀ·ማ·ሉ። ቀ·ጥ·ሎ· የ·ቀ·ረ·በ·ት· ሥ·ዕ·ል 1 እ·ና 2 ይ·ህ·ን ሁ·ኔ·ታ በ·ተ·ጨ·ባ·ጭ· መ·ረ·ጃ ያ·ሳ·ያ·ሉ።

ሥ·ዕ·ል 1 የ·ዓ·ለ·ም· የ·ኤ·ነ·ር·ጂ· ፍ·ጆ·ታ· ካ·ር·ታ - የ·ኤ·ነ·ር·ጂ· ፍ·ጆ·ታ· ከ·ሕ·ዝ·ብ· ብ·ዛ·ት· ድ·ር·ሻ· ጋ·ር· ተ·ነ·ፃ·ጽ·ሮ· ሲ·ታ·ይ·ይ· [3]



በሥዕል 1 ላይ እንደታየው በ1999 (እ.ኤ.አ.) እንደ ካናዳ፤ ዩ.ኤስ.አሜሪካ፣ ጃፓንና ምዕራባ አውሮፓ ያሉ የለሙ አገራት ከዓለም የኤነርጂ ፍጆታ ከፍተኛውን ድርሻ (53%) የያዙ ሲሆን በሕዝብ ብዛት ሲታይ ግን የእነኚህ አገራት ድርሻ በጣም አነስተኛ (15%) ነው:: በሌላ በኩል በልማት ወደኋላ የቀሩ የአፍሪካና የምሥራቅ ኤስያ (አውስትራልያና አሽንያን ጨምሮ) አገራት ከዓለም ሕዝብ ሁለት ሦስተኛውን ድርሻ (67%) የያዙ ቢሆንም የኤነርጂ ፍጆታ ድርሻቸው ግን ከሩብ በታች (23%) ነው::

ሥዕል 2 የ108 አገራትን የ1999 (እ.አ.አ.) ዓመታዊ የነፍስወከፍ የአገር ውስጥ ገቢና የነኚህኑ አገሮች ዓመታዊ የነፍስወከፍ የኤነርጂ ፍጆታ ቻርት ያሳያል:: በቻርቱ ላይ እንደታየው ምንም እንኳን በአንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች የተነሳ መደበኛውን አካሄድ የማይከተሉ (ለምሳሌ አንዳራዊ ፍጆታቸው ከፍተኛ ከሆነው ውስጥ የምሥራቅ አውሮፓ አገሮችና ዝቅተኛ ከሆነው ውስጥ የደቡብ አሜሪካ አገሮች) ቢኖሩም ጠቅለል ባለ መልኩ ሲታይ ዝቅተኛ ዓመታዊ ገቢ ያላቸው አገሮች ዝቅተኛ የኤነርጂ ፍጆታ ሲኖራቸው ከፍተኛ ዓመታዊ ገቢ ያላቸው አገሮች ደግሞ ከፍተኛ የኤነርጂ ፍጆታ አላቸው:: ከዚህም መገንዘብ እንደሚቻለው የአንድ አገር ዓመታዊ የነፍስወከፍ የአገር ውስጥ ገቢ ከታወቀ የዚያን አገር ዓመታዊ የነፍስወከፍ የኤነርጂ ፍጆታ መገመት ይቻላል:: ከነኚህ ሥዕላዊና ስታቲስቲክዊ (statistical) መግለጫዎች መረዳት እንደሚቻለው የኤኮኖሚ ዕድገትና የኤነርጂ ፍጆታ ከፍተኛ ዝምድና (correlation) አላቸው::

በሥዕል 2 ላይ እንደታየው ሁለ የእህል (cereal) ምርት (yield) እና የኤነርጂ ፍጆታም ከፍተኛ ዝምድና አላቸው:: ከላይ በተጠቀሱት 108 አገሮች የኤነርጂ ፍጆታና የእህል ምርት ላይ ኩተደረገ አንድ ጥናት [4] ማየት እንደሚቻለው የኤነርጂ ፍጆታ እያደገ በሄደ ቁጥር በሄክታር የሚገኘው የምርት መጠንም እየጨመረ ይሄዳል:: እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ኋላ ቀር አገሮች በእርሻ ላይ የሚያውሉት ኤነርጂ በጣም ዝቅተኛ ሲሆን የእርሻ ምርታማነታቸውም (crop yield) እንዲሁ በጣም ዝቅተኛ ነው:: ለምሳሌ ያህል አነስተኛ፣ መካከለኛና ከፍተኛ የኤነርጂ ፍጆታ ካላቸው ውስጥ እነደ ቅደምተከተላቸው ኬንያን፣ ማሌዥያንና ፈረንሳይን ብንወስድና የእርሻ ምርታማናታቸውን ከኢትዮጵያ ጋር ብናነጻጽር በሰንጠረዥ 1 ላይ የታየውን ይመስላል::

ሰንጠረዥ 1: የኤነርጂ ፍጆታና የእርሻ ምርታማነት

ተ. ቁ.	አገር	የኤነርጂ ፍጆታ (ኪ.. ግ. ዘይት ተመጣጣኝ)	የእርሻ ምርታማነት (ኪ.. ግ. በሄክታር)
1	ኢትዮጵያ	32	1,141
2	ኬንያ	98	1,434
3	ማሌዥያ	2005	2,860
4	ፈረንሳይ	4,030	7,271

ሥዕል 2፤ የ108 አገራት ዓመታዊ የነፍስወከፍ ገቢና የነፍስወከፍ የኤነርጂ ፍጆታ ያላቸው ዝምድና



3 የኤነርጂ (በተለይ የነዳጅ ዘይት) ፖለቲካ

ኤነርጂ በኤኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ልማት ውስጥ ከሚጫወተው ወሳኝ ሚና የተነሳ በተለይ በለሙት አገሮች የፖለቲካ መስክ ሰፊ ትኩረት አግኝቷል። በተለይም የነዳጅ ዘይት (ፔትሮሊየም) ዘመን ከተጀመረበት ከ1859 (እ.ኤ.አ.) እና ፔትሮሊየም የለመ አገሮችን የኤነርጂ ፍጆታ ከፍተኛውን ድርሻ ከያዘበት ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የፔትሮሊየም ኤነርጂ የንግድ ገዳይ ከመሆን አልፎ ጦር የሚያማዝዝና በቅርቡ በኢራቅ፣ ቀደም ሲል በኩዌት ከደረሰው ሁኔታ እንዳየነው በዴሞክራሲ ወይም በሌላ ገዳይ ሽፋን አንድን ለዓላዊ አገር በወረራ እስከ መያዝ የሚያደርስ ሆኗል።

የዓለምን የነዳጅ ዘይት ፖለቲካ ሁኔታ ለመረዳት በመስኩ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ኃይሎችን መለየትና አሰላለፋቸውን ማጤን ይጠይቃል። አሁን ባለው ሁኔታ ዋና ዋናዎቹ ኃይሎች በ6 ሊከፈሉ ይችላሉ። እነርሱም ዓለምአቀፍ የዘይት ኩባንያዎች፣ የኩባንያዎቹ አገር መንግሥታት፣ ቀሪዎቹ የለመ አገሮች፤ የቀድሞ ኮሚኒስት አገሮችና ቻይና፤ ነዳጅ ዘይት ወደ ውጭ የሚሸጡ (oil exporting) በመልማት ላይ ያሉ አገሮችና ዘይት ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡ (oil-importing) ያልለሙ አገሮች ናቸው።

የዓለምን የነዳጅ ዘይት ምርትና ገበያ በከፍተኛ ደረጃ የሚቆጣጠሩት "*7ቱ ታላላቆች*" (*"The Big-Seven"*) በመባል የሚታወቁ ዓለም አቀፍ የነዳጅ ኩባንያዎች ናቸው [5]። ከነኚህ

ኩባንያዎች 5 ፡ የአሜሪካን ሲሆኑ 2ቱ የኢንግሊዝና የሆላንድ ናቸው። እነኚህ ኩባንያዎች በመካከለኛው ምሥራቅ (የዓለምን 50% ክምችት አለው) እና በሌሎች አካባቢዎች ካሉአቸው የነዳጅ ዘይት ጉድጓዶች ጀምሮ ያሉትን የነዳጅ ዘይት ምርትና ገበያ በዋነኛነት የያዙ በመሆናቸው እ.ኤ.አ. ከ1970 መጀመሪያ በፊት በዋነኛነት፤ ከዚያ ወዲህ ደግሞ ከኦፔክ (OPEC - Organization of Petroleum Exporting Countries) አገሮች ቀጥሎ ዋነኛዎቹ የነዳጅ ዘይት ትርፍ አጋባሾች ናቸው። የእነኝህ ኩባንያዎች ትርፍ ደግሞ ወደ እናት አገሮቻቸው (በተለይም ወደ አሜሪካ) የሚገባ በመሆኑ የኩባንያዎቹ አገር መንግሥታት ዋነኛዎቹ ተጠቃሚና ነዳጅን የፍላጎቶቻቸው ማስፈጸሚያ መሣሪያ አድርገውታል።

አብዛኛዎቹ የምዕራብ አውሮፓ አገሮችና ጃፓን በዓለም ላይ የሚቆጣጠሩት የነዳጅ ዘይት ምንጭ እጅግ አነስተኛ ወይንም ጭራሽ የሌለ በመሆኑ በዚህ ትግል ውስጥ ያላቸው ሚና የተሸናፊነት ነው። የዘይት ዋጋ መናር ሁሌ ኤኮኖሚያቸውን እንዳዳሸቀና ተጎጂ እንደአደረጋቸው ነው። የቀድሞ ኮሚኒስት አገሮችና ቻይና ይከተሉት በነበረው ራስን የመቻል የኤኮኖሚ መርሕ የተነሳ በተለይ ሩሲያና ቻይና የኤነርጂ ምንጫቸውን በሀገር ውስጥ በሚገኝ ሀብት (ለምሳሌ፤ በድንጋይ ከሰል፣ በአገር ውስጥ የከርሰምድር ነዳጆችና በውሃ) ላይ እንዲመሠረት ስለአደረጉና የነዳጅ ዘይት ፍለጋ ላይ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት አውጥተው ራሳቸውን በመቻላቸው ዘይት ወደ ውጭ ሻጭ አገሮች ሆነው ቆይተዋል። ይሁን እንጂ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተፈጠረው ሁኔታ ሩሲያና አንዳንዶቹ የቀድሞ ሶቪየት አገሮች ሲቀሩ ሌሎቹ አገሮች ቻይናን ጨምሮ የነዳጅ ዘይት አስመጪ ሆነዋል። ይህም ሆኖ ግን ከእነኚህ አገሮች ብዙዎቹ ከፍተኛ የኤነርጂ ምንጫቸው መሠረቱ ሀገር ውስጥ ሆኖ የተዋቀረ በመሆኑ በዓለም ላይ ባለው የነዳጅ ዘይት ገበያ መዋገርቅ ተጎጂነታቸው አነስተኛ ነው።

ዘይት ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡ ያልለሙ አገሮችም በዓለምአቀፍ የዘይት ኩባንያዎች የተለያየ ቀጥተኛና ስውር ዘዴዎች የተነሳ ዋነኛውን የኤነርጂ ምንጫቸውን በዘይት ላይ ስለአደረጉና ያላቸውን የነዳጅ ዘይት ሀብት እንዳያለሙ፡ ዕውቀትና አቅም ስለሚያንሳቸው ወይም እንዳያለሙ፡ ደባ ወይም ጫና ስለአለባቸው በትግሉ ውስጥ ያላቸው ሚና በመከራ ካፊሩት የውጭ ምንዛሪ ትልቁን ድርሻ ለነዳጅ ዘይት መግዣ ማዋል ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ በየዓመቱ ለነዳጅ መግዣ የምታወጣው የውጭ ምንዛሪ እንደወቅቱ የዋጋ ሁኔታ የሚቀያየር ቢሆንም በአጠቃላይ ግን አገሪቱ ከወጪ ንግድ ከምታገኘው ገቢ ውስጥ ከ36% እስከ 55% ይደርስ ነበር [6]። ከነዳጅ ዋጋ መናር የተነሳ ይህ የመግዣ ዋጋ መጠን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ 70% አሻቅቧል።

ሌላው በቅርቡ ከተከሰተው የኤነርጂና የአካባቢ (environment) ጉዳይ ፓለቲካ አንፃር የሚታየው የአሜሪካ መንግሥት የኪዮቶ ፕሮቶኮል (Kyōto Protocol) በመባል የሚታወቀውን ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቁ የዓለምን ሙቀት የሚጨምሩ ጋሶች (gases) መጠን ለመቀነስ የሚያስችለውን ዓለም- አቀፍ ስምምነት ለመፈረም አሻፈረኝ ማለት ነው። ምንም እንኳን ለእምቢተኝነቱ ሌላ ሽፋን ቢሰጠውም ከበስተጀርባው ያለው አንዱ ዓላማ

ሥዕል 2፤ የ108 አገራት ዓመታዊ የነፍስወከፍ ገቢና የነፍስወከፍ የኤነርጂ ፍጆታ ያላቸው ዝምድና



3 የኤነርጂ (በተለይ የነዳጅ ዘይት) ፖለቲካ

ኤነርጂ በኤኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ልማት ውስጥ ከሚጫወተው ወሳኝ ሚና የተነሳ በተለይ በለሙት አገሮች የፖለቲካ መስክ ሰፊ ትኩረት አግኝቷል። በተለይም የነዳጅ ዘይት (ፔትሮሊየም) ዘመን ከተጀመረበት ከ1859 (እ.ኤ.አ.) እና ፔትሮሊየም የለሙ አገሮችን የኤነርጂ ፍጆታ ከፍተኛውን ድርሻ ከያዘበት ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የፔትሮሊየም ኤነርጂ የንግድ ገዳይ ከመሆን አልፎ ጦር የሚያማዝዘና በቅርበ በኢራቅ፣ ቀደም ሲል በኩዌት ከደረሰው ሁኔታ እንዳየነው በዲሞክራሲ ወይም በሌላ ገዳይ ሽፋን አንድን ሉዓላዊ አገር በወረራ እስከ መያዝ የሚያደርስ ሆኗል።

የዓለምን የነዳጅ ዘይት ፖለቲካ ሁኔታ ለመረዳት በመስኩ ውስጥ ያሉትን ዋና ዋና ኃይሎችን መለየትና አሰላለፋቸውን ማጤን ይጠይቃል። አሁን ባለው ሁኔታ ዋና ዋናዎቹ ኃይሎች በ6 ሊከፈሉ ይችላሉ። እነርሱም ዓለምአቀፍ የዘይት ኩባንያዎች፣ የኩባንያዎቹ አገር መንግሥታት፣ ቀሪዎቹ የለሙ አገሮች፤ የቀድሞ ኮሚኒስት አገሮችና ቻይና፤ ነዳጅ ዘይት ወደ ውጭ የሚሸጡ (oil exporting) በመልማት ላይ ያሉ አገሮችና ዘይት ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡ (oil-importing) ያልለሙ አገሮች ናቸው።

የዓለምን የነዳጅ ዘይት ምርትና ገበያ በከፍተኛ ደረጃ የሚቆጣጠሩት "*7ቱ ታላላቆች*" (*"The Big-Seven"*) በመባል የሚታወቁ ዓለም አቀፍ የነዳጅ ኩባንያዎች ናቸው [5]። ከነኚህ

ኩባንያዎች 5ቱ የአሜሪካን ሲሆኑ 2ቱ የኢንግሊዝና የሆላንድ ናቸው። እነኚህ ኩባንያዎች በመካከለኛው ምሥራቅ (የዓለምን 50% ክምችት አለው) እና በሌሎች አካባቢዎች ካሉአቸው የነዳጅ ዘይት ጉድጓዶች ጀምሮ ያሉትን የነዳጅ ዘይት ምርትና ገበያ በዋነኛነት የያዙ በመሆናቸው እ.ኤ.አ. ከ1970 መጀመሪያ በፊት በዋነኛነት፤ ከዚያ ወዲህ ደግሞ ከአፔክ (OPEC - Organization of Petroleum Exporting Countries) አገሮች ቀጥሎ ዋነኛዎቹ የነዳጅ ዘይት ትርፍ አጋባሾች ናቸው። የእነኝህ ኩባንያዎች ትርፍ ደግሞ ወደ እናት አገሮቻቸው (በተለይም ወደ አሜሪካ) የሚገባ በመሆኑ የኩባንያዎቹ አገር መንግሥታት ዋነኛዎቹ ተጠቃሚና ነዳጅን የፍላጎቶቻቸው ማስፈጸሚያ መሣሪያ አድርገውታል።

አብዛኛዎቹ የምዕራብ አውሮፓ አገሮችና ጃፓን በዓለም ላይ የሚቆጣጠሩት የነዳጅ ዘይት ምንጭ እጅግ አነስተኛ ወይንም ጭራሽ የሌለ በመሆኑ በዚህ ትግል ውስጥ ያላቸው ሚና የተሸናፊነት ነው። የዘይት ዋጋ መናር ሁሌ ኤኮኖሚያቸውን እንዳዳሸቀና ተጎጂ እንደአደረጋቸው ነው። የቀድሞ ኮሚኒስት አገሮችና ቻይና ይከተሉት በነበረው ራስን የመቻል የኤኮኖሚ መርሕ የተነሳ በተለይ ሩሲያና ቻይና የኤነርጂ ምንጫቸውን በሀገር ውስጥ በሚገኝ ሀብት (ለምሳሌ፤ በድንጋይ ከሰል፣ በአገር ውስጥ የከርሰምድር ነዳጆችና በውሃ) ላይ እንዲመሠረት ስለአደረገና የነዳጅ ዘይት ፍለጋ ላይ ከፍተኛ ኢንቨስትመንት አውጥተው ራሳቸውን በመቻላቸው ዘይት ወደ ውጭ ሻጭ አገሮች ሆነው ቆይተዋል። ይሁን እንጂ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በተፈጠረው ሁኔታ ሩሲያና አንዳንዶቹ የቀድሞ ሶቪየት አገሮች ሲቀሩ ሌሎቹ አገሮች ቻይናን ጨምሮ የነዳጅ ዘይት አስመጪ ሆነዋል። ይህም ሆኖ ግን ከእነኚህ አገሮች ብዙዎቹ ከፍተኛ የኤነርጂ ምንጫቸው መሠረቱ ሀገር ውስጥ ሆኖ የተዋቀረ በመሆኑ በዓለም ላይ ባለው የነዳጅ ዘይት ገበያ መዋገርቅ ተገዥነታቸው አነስተኛ ነው።

ዘይት ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቡ ያልለሙ አገሮችም በዓለምአቀፍ የዘይት ኩባንያዎች የተለያየ ቀጥተኛና ስውር ዘዴዎች የተነሳ ዋነኛውን የኤነርጂ ምንጫቸውን በዘይት ላይ ስለአደረገና ያላቸውን የነዳጅ ዘይት ሀብት እንዳያለሙ ዕውቀትና አቅም ስለሚያንሳቸው ወይም እንዳያለሙ ደባ ወይም ጫና ስለአለባቸው በትግሉ ውስጥ ያላቸው ሚና በመከራ ካፊሩት የውጭ ምንዛሪ ትልቁን ድርሻ ለነዳጅ ዘይት መግዣ ማዋል ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ በየዓመቱ ለነዳጅ መግዣ የምታወጣው የውጭ ምንዛሪ እንደወቅቱ የዋጋ ሁኔታ የሚቀያየር ቢሆንም በአጠቃላይ ግን አገሪቱ ከወጪ ንግድ ከምታገኘው ገቢ ውስጥ ከ36% እስከ 55% ይደርስ ነበር [6]። ከነዳጅ ዋጋ መናር የተነሳ ይህ የመግዣ ዋጋ መጠን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ወደ 70% አሻቅቧል።

ሌላው በቅርቡ ከተከሰተው የኤነርጂና የአካባቢ (environment) ጉዳይ ፓለቲካ አንፃር የሚታየው የአሜሪካ መንግሥት የኪዮቶ ፕሮቶኮል (Kyōto Protocol) በመባል የሚታወቀውን ወደ ከባቢ አየር የሚለቀቁ የዓለምን መቀት የሚጨምሩ ጋሶች (gases) መጠን ለመቀነስ የሚያስችለውን ዓለም- አቀፍ ስምምነት ለመፈረም አሻፈረኝ ማለት ነው። ምንም እንኳን ለእምቢተኝነቱ ሌላ ሽፋን ቢሰጠውም ከበስተጀርባው ያለው አንዱ ዓላማ

ዓለምአቀፍ የዘይት ኩባንያዎቻቸውን ጥቅም ላለመንዳት የሚደረግ ትግል መሆኑ ይታወቃል::

ከላይ ከተነሰት ነጥቦች መረዳት የሚቻለው ትልቅ ቁምነገር ኃይል (ኤነርጂ) ትልቅ የፓለቲካ መሳሪያ ጭምር መሆኑና ብርቱ ጥረት አድርጎ የአገር ውስጥን የኤነርጂ ምንጭ ማልማት ከኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጠቀሜታው ባሻገር ትልቅ ፓለቲካዊ ጠቀሜታ እንደአለው መገንዘብ ይቻላል::

4 የኤነርጂ ልማትና የተጠቃሚነት ዕድል (Access) በኢትዮጵያ - አሁን ያለው ሁኔታ

የኢትዮጵያን የኤነርጂ ዘርፍ በሁለት ታላላቅ ክፍለ-ች (ዓይነቶች) - ባሕላዊ (traditional)ና ዘመናዊ - ወይም በአራት ዋና ዋና ክፍለ-ች ከፍሎ ማየት ይቻላል:: እነሰም፤ ሀ) ባሕላዊ (traditional) ማገዶና የእንስሳት (animate) ኤነርጂ[10] ለ) ኃይል ዘይትና ሌሎች የከርሰ ምድር ኃይሎች (fossil fuels) ሐ) የኤሌክትሪክ ኃይል (power) እና መ) ዘመናዊ ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች ናቸው:: የመጀመርያው አከፋፈል መደበኛና ድርርቦሽ የሌለው ነው:: ይሁን እንጂ ይህ አከፋፈል አንዳንድ ዋና ዋና ክፍለ-ችን የመሸፈን ችግር አለው:: ሁለተኛው አከፋፈል የድርርቦሽ ችግር (ለምሳሌ የኤሌክትሪክ ኃይልና ዘመናዊ ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች) ያለው ቢሆንም በአገራችን ካለው ሁኔታ ጋር በግልጽ የሚሄድና የዘርፉን ክፍለ-ች ለያይቶ ለመመልከት የሚያስችል በመሆኑ ተመራጭነት አለው:: ቀጥሎ የቀረበው የዘርፉ ቅኝት ይህንን አከፋፈል የተከተለ ነው::

4.1 የኤነርጂ ምንጮቻችን የልማት ደረጃ

ሀ) ባሕላዊ ማገዶና የእንስሳት ኤነርጂ

በኢትዮጵያ ዋነኛው ባሕላዊ ማገዶ እንጨት፣ የሰብል ቅሪቶች (crop residues)፣ ኩበት[11] እና የእንጨት ከሰል ናቸው:: እነኚህ የኤነርጂ ምንጮች አብዛኛውን የአገራችንን የኤነርጂ ፍላጐት የሚሸፍኑ ከመሆናቸውም በላይ በአገር ውስጥ የሚገኙና በባሕላዊ መንገድ የሚመረቱ ናቸው:: ይሁን እንጂ አነስተኛ ድርሻ ካላቸው ከሰብል ቅሪቶችና ከኩበት በቀር ዋነኛው ምንጭ ማለትም እንጨትና ከርሰ የሚመረተው ከሰል በአብዛኛው የሚገኙት ከደን ሀብት በመሆኑና የደን ሀብቱ እየተመናመነ በመሄዱ (ከ40% ወደ 2.8% ወርዷል) [7] ባሕላዊ ማገዶ የሚገኝበት ሁኔታ የልማት ሳይሆን የጥፋት ነው ለማለት ይቻላል:: የደን ሀብታችን መመናመን የተፈጥሮ አካባቢ ውድመትን እያስከተለ ያለ ገዳይ መሆኑ በስፋት

[10] የእንስሳት (animate) ኤነርጂ የሰውንም ይጨምራል::
[11] ኩበት:- ፋንዲያና የመሳሰሉትን ሁሉ ይጨምራል::

የማ፡ታ፡ወቅና ሣኣ፡ በስፋት፡ የማልማት፡ ፕሮግራም የሌለ ወይም ካለም ደካማ በመሆኑ፡ በዚህ ጉዳይ፡ ላይ፡ ሰፊ ማብራሪያ መስጠት፡ ከዚህ ዝግጅት፡ ውጪ መሄድ ይሆናል።

በኤነርጂ ምንጭነት፡ ብዙ ትኩረት፡ የማይሰጠውና በአገራችን የግብርና ዘርፍ ውስጥ ትልቁን ድርሻ የያዘው የእንስሳት፡ ኤነርጂ ነው። የአገራችን እርሻና የገጠሩ መጓጓጥ የተመሠረተው በእንስሳት፡ ጉልበት፡ ላይ መሆኑ እንደ ባሕላዊ ማገዶ ሁሉ የኋላቀርነት መገለጫ ነው። የአገሪቱ የሰውና የእንስሳት፡ ቁጥር እየበዛ ከመሄዱ አንፃር የእንስሳት፡ ኤነርጂ አቅርቦት፡ ጨምሮ፡ል ሊባል ይች፡ል ይሆናል። ይሁን እንጂ በድርቅና በምግብ ራስን ያለመቻል የተነሳ በእርሻ ላይ የተሰማራው የሰውና የእንስሳት፡ ቁጥር ቢጨምርም ሰውና እንስሳቱ በቂ ምግብ እስከአላገኙ፡ ድረስ ኤነርጂው ጨምሮ፡ል ለማለት፡ አይቻልም።

ለ) ነዳጅ ዘይት፡ና ሌሎች የከርሰ ምድር ነዳጆች (fossil fuels)

ለሀገራችን የሚያስፈልገው የነዳጅ ዘይት፡ ሙሉ በሙሉ የሚመጣው ከውጭ ነው። መጠኑም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ ሄዷል። እ.ኤ.አ በ1992/93 ወደ ሀገር ውስጥ ይገቡ የነበሩት፡ ልዩ ልዩ የነዳጅ ውጤቶች መጠን ወደ 555 ሺህ ቶን ነበር። ይህ በ2002 ወደ 1.1 ሚሊዮን ቶን በመድረስ በአሥር ዓመታት፡ ውስጥ የእጥፍ፡ ዕድገት፡ አሳይቷል ማለት፡ ነው [8]።

በሌላ በኩል እስከአሁን በተካሄደው የማዕድን ፍለጋ የነዳጅ ዘይት፡ ባይገኝም አገሪቷ ሌሎች የከርሰ ምድር ነዳጆች በበቂ ደረጃ እንዳላት፡ ታውቋል። አሁን ባለው መረጃ መሠረት፡ ኢትዮጵያ ወደ 100 ቢሊዮን ሜትር ኩብ የተፈጥሮ ጋዝና ከ200 ሚሊዮን ቶን በላይ የድንጋይ ከሰል ክምችት፡ እንዳላት፡ ተረጋግጧል [4]። ይሁን እንጂ ባለፉት፡ ዓመታትና አሁንም ቢሆን እነኚህን የኤነርጂ ምንጮች፡ ለማልማት፡ ጥረት፡ የቀጠለ ቢሆንም እስከአሁን ተጨባጭ ውጤት፡ አልተገኘም። በመንግሥት፡ በኩል ያለው አያያዝም በዕቅድ፡ ላይ ያልተመሠረተ፡፣ በሰው ኃይል ልማት፡ ላይ ያላተኮረና ያዝ ለቀቅ ዓይነት፡ ይመስላል። አስተማማኝነቱ፡ ተረጋግጦ የክምችቱ፡ ጉድጓዶች ለምርት፡ ከተዘጋጁ ዓመታት፡ን ያስቆጠሩት፡ የነለበት፡ ጋዝ እስከአሁን ወደ ምርት፡ ያለመሸጋገሩ፡፣ እንዲያውም የውጭ ኩባንያዎች፡ ይባ ያለበት፡ መምሰሉና ለኮል-ፎስፌት፡ ፕሮጀክት፡ የሚሰጠው ድጋፍና ትኩረት፡ እያነሰ መሄዱ ይህንኑ አመላካች፡ ነው።

ሐ) የኤሌክት፡ሪክ ኃይል

ኢትዮጵያ ለኤሌክት፡ሪክ ኃይል ማመንጫነት፡ ሊውሉ የሚች፡ሉ ብዙ የመጀመሪያ ደረጃ (primary) የኤነርጂ ምንጮች፡ አሏት። እዚህ ላይ መታወቅ ያለበት፡ የኤሌክት፡ሪክ ኃይል ከውሃ ብቻ ሳይሆን ከነዳጅ ዘይት፡፣ ከድንጋይ ከሰል፣ ከፀሐይ፣ ከነፋስ ወዘተ፤ ሊመነጭ የሚች፡ል መሆኑ፡ ነው። አገሪቱ በአሁኑ ወቅት፡ በአንዳንዳዊ ሁኔታ፡ በስፋት፡ እየተጠቀመች፡በት፡

ባለው የውሃ ኤሌክትሪክ ኃይል[12] ላይ እንኳን ብናተኩር ባለው መረጃ መሠረት የኢትዮጵያ የውሃ ኤሌክትሪክ ኃይል እምቅ አቅም (potential) ከ15 ሺ እስከ 30 ሺ ሜጋዋት ይደርሳል [9]። ይሁን እንጂ እስከአሁን የለማው 663 ሜጋዋት [10] ወይንም የጠቅላላው እምቅ አቅም ከ2% እስከ 4% ያህል ብቻ ነው። ከዚህ ከለማው ውስጥ ደግሞ የአነስተኛ የውሃ ኃይል ድርሻ 6.5 ሜጋዋት ወይም 1% ያህል ብቻ ነው። በመሠረቱ አነስተኛ የውሃ ማመንጫዎች ያለውጭ ብድር በአገራችን አቅምና የመሣሪያ አስተዋጽኦ ሊሠሩ የሚችሉ በመሆናቸው ይበልጥ ሊበረታቱና ሊታገዙ በተገባ ነበር።

መ) ዘመናዊ ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች

ዘመናዊ ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች ከባሕላዊ ማገዶ ውጭ ያሉትን ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች ሁሉ የሚያጠቃልል ነው። በዚህም መሠረት ከእፀዋት የሚገኝ የነዳጅ አልኮል፣ ባዮጋዝ፣ የውሃ ኃይል፣ የፀሐይ ጨረር፣ የንፋስ ኃይል፣ ጂኦተርማልና ከታዳሽ ምንጮች የሚገኝ ሃይድሮጅን ዘመናዊ ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች ናቸው።

ኢትዮጵያ በተለይ በውሃ ኤሌክትሪክ፣ በፀሐይና በጆኦተርማል ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች እጅግ በጣም የታደለች ነች። ከላይ እንደተጠቀሰው ከፍተኛ የውሃ ኤሌክትሪክ ኃይል ሀብት አላት። ከዚህም በተጨማሪ ኢትዮጵያ በመሬት አቀማመጧ በሐሩር ክልል ውስጥ ስለምትገኝ በየዓመቱ ከፍተኛ የፀሐይ ብርሃንና ረጅም የብርሃን ጊዜ ታገኛለች። ስለዚህም በፀሐይ ኃይል የታደለች ነች። በጆኦተርማል ኃይልም ቢሆን ኢትዮጵያ እንዳውም በዓለም ደረጃ ከፍተኛውን የሀብት ድርሻ ካላቸው ውስጥ እንዷ ነች የሚሉ ጥናቶች አሉ። በጆኦተርማል ብቻ 700 ሜጋዋት ኃይል ማመንጨት እንደሚቻል የጃክ ቫሬትና [11] ሌሎች ሳይንሳዊ ጥናቶች ያሳያሉ።

ይሁን እንጂ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ከከፍተኛ የውሃ ኃይል በቀር በኢትዮጵያ ውስጥ የለማ ወይም እየለማ የሚገኝ ታዳሽ የኤነርጂ ምንጭ የለም ማለት ይቻላል። ከጆኦተርማል ሀብት ውስጥ እስከአሁን የለማው 7.3 ሜጋዋት ብቻ ነው [10]። ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች እንደ ነዳጅ ዘይትና ድንጋይ ከሰል ከባቢ አየርን ስለማይበክሉና የአየር ለውጥ ስለማያመጡ በዓለም ላይ የ21ኛው ክፍለ ዘመን የኤነርጂ ምንጮች እነርሱ እንደሚሆኑ የታመናል። ከዚህም የተነሳ የለመሙም ሆነ በመልማት ላይ የሚገኙ አገሮች ትኩረታቸው ወደነርሱ ሆኗል። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አብዛኛው ሕዝባቸው በገጠር በሚኖርባቸው አገሮች ገጠሩን በኤሌክትሪክ ለማዳረስ የሚቻለው በየቤቱ ወይም በየመንደሩ ሊተከሉ የሚችሉ አነስተኛ የኃይል ማመንጫዎችን መጠቀም ሲቻል ነው። ለዚህ ደግሞ ታዳሽ የኤነርጂ ማመንጫዎች

---

[12] በ1996 ኢትዮጵያ ካነበራት 706 ሜጋ ዋት ጠቅላላ ኤሌክትሪክ የማመንጨት አቅም ውስጥ 94% ወይም 663 ሜጋ ዋት ከውሃ የሚመነጭ ነበር። የተቀረው 43 ሜጋ ዋት የሚመነጨው በአብዛኛው ከናፍጣና በትንሹ ከጂኦተርማል ነው።

በጣም ተስማሚ ናቸው። ለምሳሌ የፀሐይ ማሾዎች (solar lantern) በየገጠሩ ቤት በማስገባት ገጠሩን የኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል (ሥዕል 3 ይመልከቱ)።

ሥዕል 3፤ ከኤሌክትሪክ ማከፋፈያ መስመር ርቀው ላሉ የገጠር አካባቢዎች የሚያገለግሉ የፀሐይ ማሾዎች



በተመሳሳይ ሁኔታ ከመብራትም ሌላ ለሰዎችና ለከብቶች እንዲሁም ለእርሻ የመስኖ ሥራ የሚያገለግሉ በፀሐይ ኃይል የሚሠሩ የውሃ ፓምፖች፣ ለምግብ ማብሰያ የሚያገለግሉ የፀሐይ ምድጃዎችና በቤት ጣሪያ ላይ የሚገጠሙ የፀሐይ ውሃ ማሞቂያዎችን መጠቀም ይቻላል (ሥዕል 4፣ 5፣ 6 እና 7 ይመልከቱ)።

❹



ሥዕል 4፣ 5፣ 6 እና 7፤ ለሰዎችና ለከብቶች እንዲሁም ለእርሻ የመስኖ ሥራ የሚያገለግሉ በፀሐይ ኃይል የሚሠሩ የውሃ ፓምፖች፤ ባለሣጥን የፀሐይ ምድጃና በቤት ጣሪያ ላይ የሚገጠሙ የፀሐይ ውሃ ማሞቂያዎች፤







ይሁን እንጂ በጅምር ደረጃ በኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል ከሚካሄድ አንድ ፕሮግራም ውጭ በኢትዮጵያ ይህን በስፋት በማካሄድ ላይ የሚገኝ ፕሮጀክት የለም። የፌዴራሉም ሆነ ክልላዊ መንግሥታት ለዚህ ጉዳይ ገና ትኩረት አልሰጡትም። የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን (ኤፕኮ) መብራት ለገጠር ከተሞች ሲያስገባ የነበረውና እያስገባ የሚገኘው በናፍጣ ጄኔራተሮች ነው [10]። በተመሳሳይ መልክ አነስተኛ ኃይል የሚፈልገውና ለት/ቤቶች የፕላዝማ ቴሌቪዝን የሚያስገባው አዲሱ ፕሮጀክትም ቢሆን የናፍጣ ጄኔራተሮችን ነው የሚጠቀመው። ኤፕኮም ሆነ መንግሥት እስከአሁን ያላቸው ትኩረት በከፍተኛ የውሃ ኃይል ማመንጫዎችና በናፍጣ ጄኔራተሮች ላይ ብቻ ነው። ተገቢ *የኤነርጂ ድብልቅ (energy mix)* እና አካባቢን መንከባከብ የሚባሉት ጉዳዮች እስከአሁን ትኩረት ያገኙ አይመስልም።

ተገቢ *የኤነርጂ ድብልቅ* የተባለው ጉዳይ በተደጋጋሚ ከሚከሰተው ድርቅና ባለፉት ሁለትና ሦስት ዓመታት ካጋጠመን የኃይል እጥረት አንፃር ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው። ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከአገሪቱ ጠቅላላ ኤሌክትሪክ የማመንጨት አቅም ውስጥ 94% ከውሃ የሚገኝ መሆኑ የረጅም ጊዜ ድርቅ ቢከሰት ሊኖር የሚችለው አደጋ በጣም ከፍተኛ መሆኑን አመላካች ነው። ስለዚህም ከኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያዎቻችን ከፊሉ ከውሃ ውጭ በሌላ የኤነርጂ ምንጭ የሚጠቀሙ ሊሆኑ ይገባል። የተፈጥሮ ጋዝ፣ ጂኦተርማል፣ የድንጋይ ከሰልና የንፋስ ኃይልን የመሳሰሉ የኤነርጂ ምንጭ ሀብቶቻችንን ለዚህ

ጥሩ ተነሳሽነት ሊሆኑ ይችላሉ። ከነዚህ ውስጥ እስከአሁን በትንሹ የተሞከረው የኤነርጂ ምንጭ ጂኦተርማል ብቻ መሆኑ በመስኩ የተሠራው የልማት ሥራ በጣም አነስተኛ መሆኑን ያሳያል።

የኢትዮጵያን የኤነርጂ ምንጮች የልማት ሁኔታ ከተመለከትን በኋላ ንጽጽራዊ የኤነርጂ ፍጆታችንና ተጠቃሚነታችንን መመልከቱ አስፈላጊ ይሆናል።

4.2 የኤነርጂ ፍጆታና የተጠቃሚነት ዕድል

በሌሎች ኃላቀር ኤኮኖሚ ባላቸው አገሮች እንደሚታየው ሁሉ በኢትዮጵያ ከፍተኛውን የኤነርጂ ምንጭ ድርሻ የያዘው ባሕላዊ ማገዶ ነው። ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከኢትዮጵያ የኤነርጂ ፍጆታ 94.5%ቱ የሚመነጨው ከባሕላዊ ማገዶ ነው [12]። ይህ ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነጻጸር እጅጉን የበዛ ድርሻ ሲሆን የኋላ ቀርነት መገለጫም ነው።

ነዳጅ ዘይትና የኤሌክትሪክ ኃይል በለሙት አገሮች የኤነርጂ ምንጭ ውስጥ ያላቸው ድርሻ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። ይህም በመሆኑ የኤኮኖሚ ልማትና የዘመናዊነት ምልክቶች ሆነው ይታያሉ። ነዳጅ ዘይትና የኤሌክትሪክ ኃይል በኢትዮጵያ የኤነርጂ ፍጆታ ውስጥ ያላቸው ድርሻ ግን 5.5% ብቻ ነው። ከዚህ ውስጥ የኤሌክትሪክ ኃይል ድርሻ 1% አይሞላም። ምንም እንኳን በአገሪቱ ውስጥ የዘመናዊ ኤነርጂ ምንጮች ድርሻ አነስተኛ ቢሆንም የዘመናዊው ኤኮኖሚ ማለትም የአምራች ኢንዱስትሪ፣ ትራንስፖርት፣ ኮንስትራክሽን፣ ማዕድንና የአገልግሎት ዘርፎች ዋናኞቹ አንቀሳቃሾች በመሆናቸው በኤኮኖሚው ውስጥ የሚጫወቱት ሚና በጣም ከፍተኛ ነው።

ዘመናዊ ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች በኢትዮጵያ የኤነርጂ ፍጆታ ውስጥ ያላቸው ድርሻ በጣም አነስተኛ ከመሆኑ የተነሳ ከቁጥር የሚገባ አይደለም። ለአነኚህ የኤነርጂ ምንጮች የተሰጠውም ትኩረት በጣም አነስተኛ ነው። እዚህ ላይ አንድ በጣም የሚያሳዝን ሁኔታ ማንሳት አስፈላጊ ይሆናል። በፊንጫአ ስኳር ፋብሪካ ውስጥ ያለው የኤታኖል ማምረቻ በዓመት ከ8 እስከ 12 ሚሊዮን ሊትር ለመኪና ነዳጅ የሚሆን ኤታኖል የማምረት አቅም አለው [13], [6]። ኤታኖል እንደ ብራዚልና አሜሪካ ባሉት አገሮች በስፋት በጥቅም ላይ እየዋለ የሚገኝ ታዳሽ ነዳጅ ነው። ይሁን እንጂ ነዳጅ አከፋፋዮቹ የዘይት ኩባንያዎች ለብሔራዊ ጥቅም ከሚሰጡት ገቅተኛ ትኩረትና በመንግሥትና በኩባንያዎቹ መካከል በተነሳው ውዝግብ ይህ ታዳሽ ነዳጅ እስከዛሬ ድረስ ከመኪና ባለፈ ለመኪና ነዳጅነት ጥቅም ወሎ አያውቅም። የስኳር ፋብሪካ ተረፈ-ምርት የሆነውና ለኤታኖል ማምረቻ ጥሬ ዕቃ የሆነው ሞላሳ (molasses) የስኳር ፋብሪካውን ምርት እያወከና ከተጣራ (treatment) በኋላ ወደ ወንዝ እየተደፋ ይገኛል።

በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ዘመናዊ የኤነርጂ ፍጆታ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው። ገጠሩ ላሬም ቢሆን ጥንት እንደነበረው በጭለማ ውስጥ የሚገኝ መሆኑ ለዚህ ትልቅና በቂ ማስረጃ ነው። እ.ኤ.አ. በ1994 የነበረው የኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ የኤነርጂ ፍጆታ ከ21 ኪ..ግ. የነዳጅ ዘይት ጋር ብቻ የሚመጣጠን ነበር [14]። ይህ ከሰሐራ በታች ከሚገኙት የአፍሪካ አገሮች የነፍስ ወከፍ የኤነርጂ ፍጆታና ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው ከሌሎች ካልለሙት አገሮች ጋር ሲነፃፀር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። በተለይም እንደ ኬንያ ካሉ ጎረቤት አገሮች ጋር ሲነፃፀር ከ20% ያነሰ ነው። ከሰሐራ በታች ካሉት አገሮች አማካይ ጋር ሲነፃፀር ደግሞ ከ8% እስከ 6% ያህል ብቻ ነው (ሥዕል 8 ይመልከቱ) [14]። ንዕዕሩ ከለሙ አገሮች ፍጆታ ጋር ሲሆን ደግሞ የኢትዮጵያ ዘመናዊ የኤነርጂ ፍጆታ የእነርሱን ከ0.4% እስከ 0.5% ያህል ብቻ ነው (ሥዕል 2 ይመልከቱ)።

ሥዕል 8-የዘመናዊ ኤነርጂ የነፍስ ወከፍ ፍጆታ በተመረጡ አገሮች



በኤሌክትሪክ ፍጆታ አንፃር ብቻ ሲታይ የኢትዮጵያ የነፍስ ወከፍ ፍጆታ በ1998 (እ.ኤ.አ.) 24 ኪሎዋት ሰዓት ብቻ ነበር። በአንፃሩ በሥዕል 9 ላይ እንደታየው የሱዳንና የታንዛንያ ፍጆታ የኢትዮጵያን 2 እጥፍ፣ የኬንያው 5 እጥፍ፣ የመፈለረሻዎች ያልለሙ አገሮች በአማካይ 3 እጥፍ፣ ከሳሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገሮች በአማካይ 20 እጥፍ፣ በመልማት ላይ ያሉ አገሮች በአማካይ 32 እጥፍ ነው። ይህ ኃላቀርነትን የሚያንፀባርቅ ብቻ ሳይሆን እጅግ የሚያሳፍርም ጭምር ነው።

ከተጠቃሚነት ዕድል አንፃር ስንመለከት በኢትዮጵያ የዘመናዊ ኤነርጂ ተጠቃሚነት ዕድል ያለው የሰው ቁጥር እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። አብዛኛው የገጠሩ ነዋሪ (73% በ1996 እ.ኤ.አ.) ከዘመናዊ የኤነርጂ ምንጮች ነጭ ጋዝን ብቻ ነው የሚጠቀመው ማለት ይቻላል፤

ለዚያውም ለመብራት ብቻ። የነጭ ጋዝ ፍጆታው ደግሞ ከጠቅላላ የኤነርጂ ፍጆታ ጋር ሲነፃፀር 1% እንኳን አይሞላም [14]።

በኤሌክትሪክ ኃይል ተጠቃሚነት ዕድል በኩልም ብንሄድ ቁጥሩ እንዲሁ በጣም ዝቅተኛ ነው። በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽን የ5 ዓመት ዕቅድ መሠረት በዚህ ዓመት (1997) ይደርስበታል ተብሎ የታሰበው የኤሌክትሪክ ተጠቃሚነት ዕድል ደረጃ ከመቶ 17 አጅ ነው [10]። እንደ ሕንድ ባሉ በመልማት ላይ በሚገኙ አገሮች ብዙዎቹ ክልላዊ መንግሥታት (states) መቶ በመቶ ኤሌክትሪክ አግኝተዋል፤ ዝቅተኛ የተጠቃሚነት ዕድል ደረጃ ላይ ናቸው የሚባሉት ደግሞ 75% ደርሰዋል።

የኤነርጂ ተጠቃሚነት ዕድል ማደግ ሰፊ የኤኮኖሚ ዕድል ይፈጥራል። ለእንጨትና ኩበት ለቀማ እንዲሁም እህል ለመፍጨትና ውሃ ለመቅዳት ለመሳሰሉት የሚባክነውን የሰው ጊዜ ያድናል። የኤሌክትሪክ ኃይል መብራት የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ በገጠሩ የመጠጥና የመስኖ ፓምፖችን፣ የጎጆ ኢንዱስትሪዎችን፣ የጤናና የትምሕርት ተቋማት መገልገያ መሣሪያዎችን ለያንቀሳቅስ ሰለሚችል ልማትን ያስፋፋል። ከዚህና ከሌሎች አገሮች ተመክሮ እንደምንረዳው በአገራችን የኤሌክትሪክ ተጠቃሚነት ዕድል ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ መሆን በሰፊው ተንሰራፍቶ ላለው ድህነታችን መቀጠል ከፍተኛ አስተዋጽዖ አበርክቷል። ስለዚህም ድህነትን ለመቀነስ መወሰድ ካለባቸው ቁልፍ እርምጃዎች አንዱ ገጠሩን ጨምሮ በመላ አገሪቱ የኤሌክትሪክ ተጠቃሚነት ዕድልን ማሳደግ ሊሆን ይገባል።

ሥዕል 9፡ የተመረጡ በመልማት ላይ የሚገኙ አገሮች የነፍስ ወከፍ የኤሌክትሪክ ፍጆታ - እኢአ በ1998



መግለጫ፡ *ዝቅተኛ ልማት ላይ ያሉ አገሮች አማካይ፤ **በመልማት ላይ ያሉ አገሮች አማካይ፤ †አፍሪካ ከሰ.በታች = ከሰሃራ በታች ያሉ የአፍሪካ አገሮች

አሁን ያለውን የኤነርጂ ልማትና የተጠቃሚነት ዕድል ሁኔታ ዳስሰን ከማብቃታችን በፊት የኤነርጂን ተቋማዊና የመሪ ዕቅድ ሁኔታ በአጭሩ መመልከቱ አጠቃላይ መንግሥታዊ አደረጃጀቱንና አቅጣጫውን ለማጤን ይረዳል።

4.3 የኤነርጂ አደረጃጀት፣ የፖሊሲና የመሪ ዕቅድ (ማስተር ፕላን) ሁኔታ

ሀ) አደረጃጀት

ካለፉት አራት ዓመታት ወዲህ በኤነርጂ ዘርፍ ውስጥ ያሉ የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች አደረጃጀት የተበታተነ ሆኗል [15]። አሁን ባለው ሁኔታ የገጠር ኤነርጂ ጉዳዮችን የሚመለከተው የገጠርና የግብርና ሚኒስቴር ነው። በሚኒስቴሩ ሥር ኤነርጂን የሚከታተለው አካል ቀድሞ በማዕድንና ኤነርጂ ሚ/ር ሥር የነበረው የኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል ነው። የዘመናዊ ኤነርጂ ጉዳዮችን በዋናነት የሚከታተለው የመሠረተ ልማት ሚኒስቴር ሲሆን በሥሩም የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኤጀንሲ፣ ኤፕኮና የነዳጅ ዲፖዎች አስተዳደር ይገኛሉ። የከርሰምድር ነዳጆች ልማት ጉዳይ ኃላፊነት የተሰጠው ለማዕድን ሚ/ር ሲሆን የኤነርጂ የነዳጅ ንግድና አምራች ኩባንያዎችን የሚቆጣጠረው ደግሞ የንግድና የኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ነው። ከዚህ አደረጃጀት መረዳት እንደሚቻለው የአገሪቱን የኤነርጂ ሁኔታ በሀላፊነና መልኩ የሚመለከት፣ የሚያቅድ፣ የሚያስተባብርና የሚመራ መንግሥታዊ አካል የለም። በተለይም አሁን ባለው ሁኔታ በአገሪቱ የነዳጅ ኤነርጂ የወደፊት የዕድገት አቅጣጫን የሚመራ መንግሥታዊ መ/ቤት የለም። በአጭሩ የኢትዮጵያ ኤነርጂ ዘርፍ አንድ ባለቤት የለውም ማለት ይቻላል። ይህ አካሄድ ከሌሎች የለመም ሆነ ያልለመ አገሮች ፊጽሞ የተለየ ነው። ሁሉም ማለት ይቻላል፤ ወይ "የኤነርጂ ሚኒስቴር" ወይንም "የኤነርጂና የማዕድናት ሚኒስቴር" በመባል የሚታወቅ የመንግሥት መ/ቤት አላቸው (ይህን መረጃ በቀላሉ ከኢንተርኔት ማግኘት ይቻላል)።

በሌላ በኩል እስከ አሁን ባለው ሁኔታ በኢትዮጵያ የዘመናዊ ኤነርጂ አምራች ድርጅት አንድ ኤፕኮ ብቻ ነው ማለት ይቻላል። ፍንጫላ ስካር ፋብሪካ ኤታኖል የሚያመርት ቢሆንም ገበያ ውስጥ ስለሌለ ከቁጥር ሊገባ አይችልም። እንደ መካነየሱስ ቤተክርስትያን ባሉ መንግሥታዊ ባልሆነ ድርጅቶች የተገነቡ አነስተኛ የውሃ ኤሌክትሪክ ማመንጫዎች ቢኖሩም አቅማቸው በጣም ትንሽና ከአንድ ሠፈር የማያልፍ በመሆኑ የነርሱም ከቁጥር የሚገባ አይደለም። ይህ ሁኔታ የዘርፉን ዕድገት በእጅጉ ጎድቶታል። በነዳጅ ስርጭት በኩል መንግሥት በወሰደው ሞኖፖሊ (monopoly)ን የማጥፋት እርምጃ በቅርቡ ከአንድም ሁለት የነዳጅ አከፋፋይ ድርጅቶች ገበያ ውስጥ ገብተዋል። ይህ ጥሩ ጅምር ነው። በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦትም በኩል ከኤነርጂ ውጭ ሌሎች ኤነርጂ አምራች ድርጅቶች ቢኖሩ የዘርፉ ዕድገት ሊፋጠን ይችላል።

ለ) ፖሊሲና መሪ-ዕቅድ

ፖሊሲን በሚመለከት እ.አ.አ. ከ1994 ወዲህ ኢትዮጵያ የኤነርጂ ፖሊሲ አላት [16]። ይህ ፖሊሲን በሚመለከት እ.አ.አ. ከ1994 ወዲህ ኢትዮጵያ የኤነርጂ ፖሊሲ አላት [16]። ይህ ጥሩ ጅምር ነው። ይሁን እንጂ በፖሊሲው ላይ የተቀመጡ ብዙ ጉዳዮች ተግባራዊ ሲሆኑ ስለማይታይ ፖሊሲው ትኩረት ያገኘ አይመስልም። በአጠቃላይም ፖሊሲው አስፈጻሚ ያጣ ይመስላል። በሌላ በኩል ደግሞ ከላይ በተጠቀሰው ተቋማዊ ትግር ምክንያት ለጉዳዩ ጠቅላላ ባለቤትነትን የሚወስድ አካል ስለሌለ በንድፍ ደረጃም ሆነ ከዛ ከፍ ባለ ደረጃ የተዘጋጀ መሪ ዕቅድ የለም። ያለው አንድ ብቸኛ መሪ ዕቅድ የኤሌክትሪክ ኃይል ልማትን ብቻ የሚመለከት የ25 ዓመታት ዕቅድ ነው። ይህ ዕቅድ ኤፕኮን ብቻ የሚመለከት ከመሆኑም በላይ ከኤሌክትሪክ ኃይል ውጪ ያለውን የኤነርጂ ዘርፍ የሚመለከት ባለመሆኑ ስለአጠቃላዩ ኤነርጂ ዛሬ ላይ ሆነን ነገን ለመመልከት የሚያስችለን አይደለም።

4.4 የኤነርጂ ብክነትን የማስወገድ (Efficiency) እና የአገልግሎት አሰጣጥ ሁኔታ

በኢትዮጵያ የኤነርጂ አቅርቦት ላይ ትግር እንደአለ ሁሉ በአጠቃቀምም ላይ ከፍተኛ ብክነትን የማስወገድ ትግር አለ። ከባሕላዊው ማገዶ በንጅምር ባሕላዊው ባለሦስት ጉልቻ ምድጃ ማገዶን በጣም ያባክናል። ኢፊሸንሲ (Efficiency)ው ከ10% የማይበልጥ ነው። ባለፉት ዓመታት በኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከልና በጅርመን የእርዳታ ድርጅት በጂ.ቲ.ዜድ. በተደረገው ጥረት የተሻሻለ የእንጨትና የከሰል ምድጃዎችን ለመሥራትና ለማሰራጨት ተችሏል። ይህ መልካም ሲሆን ስርጭቱ ላይ ግን ገና ብዙ ይቀራል። ጥረቱ በስፋት ከቀጠለ ከፍተኛ የደን ጥፋትን የሚያስቀር ከመሆኑም በላይ በጭስ ምክንያት የሚመጣውን ሰፊ የመተንፈሻ አካል የጤና ትግር ያስወግዳል።

በዘመናዊ ኤነርጂ በኩል ከላይ እንደተገለጸው ዋናው አምራች ኤኘኮ ነው። በቅርቡ የተጀመሩ ጥረቶች መልካም ቢሆኑም ኤኘኮ እንደሚታወቀው ሁሉ በተለይ በኃይል ማከፋፈል ላይ ከፍተኛ ብክነትና በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ከፍተኛ ድክመት አለበት። በተለይ ደግሞ ኤነርጂን በሚቆጥቡ መሳሪያዎች ላይ ኮርፖሬሽኑ እስከአሁን ትኩረት የሰጠ አይመስልም። ለምሳሌ ከሁለት ዓመት በፊት በተቋቋመው በኤነርጂ ጉዳዮች ላይ የሚሠራ ማኅበር - በኢንስደ (Ethiopian Network for Sustainable Energy Development) - በቀረበ አንድ ጥናት መሠረት አሁን ያሉትን አምፖሎች በኤነርጂ ቆጣቢ አምፖሎች (ሥዕል 10 ይመልከቱ) በመቀየር ብቻ ከ100 ሜጋዋት ያላነሰ የኤሌክትሪክ ኃይል ከብክነት ማዳን ይቻላል [17]። ይህ ጉዳይ ግን እስከአሁን ትኩረት አላገኘም። በፋብሪካዎችና በሌሎች ድርጅቶችም ውስጥ ኤነርጂ ቆጣቢ መሳሪያዎችን በመጠቀምና የአሠራር ሁኔታዎችን በማሻሻል ከፍተኛ የኤነርጂ ቁጠባ ማድረግ ይቻላል። ይሁን እንጂ ጉዳዩ ገና ትኩረት ስለአላገኘ በአሁኑ ወቅት ከፍተኛ የኤነርጂ ብክነት በየቦታው ይታያል።

ሥዕል 10: ኤነርጂን በ80% ያህል የሚቆጥብ ኮምፓክት ፍሉረሰንት (compact fluorescent) አምፖል



4.5 የኤነርጂ ቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት

በኢትዮጵያ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት በአጠቃላይ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ደካማ ነው። ይበልጥ ደግሞ የሚያሳዝነው በመስኩ ያለው የአቅም ግንባታና በአገር ውስጥ ቴክኖሎጂን የማልማት ጥረት በጣም አናሳ መሆኑ ነው። በተለይ በኤነርጂ ዘርፍ የአቅም ግንባታና በአገር ውስጥ ቴክኖሎጂን የማልማት ጥረት በጣም ደካማ ነው። ለምሳሌ ኤፕኮ ባለፉት 50 ዓመታት ውስጥ በኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጫ ጥናት፣ ዲዛይንና ግንባታ እንዲሁም እንደትራንስፎርመር ባሉ መሳሪያዎች ፍብረካ ውስጥ በመግባት ሰፊ አቅም መፍጠር ይችል ነበር። ይሁን እንጂ ይህ ገዳይ ትኩረት ባለማግኘቱ ኮርፖሬሽኑ ዛሬም ቢሆን እነኝህን አገልግሎቶችና መሣሪያዎች ከውጭ እያስመጣ ነው። ቀደም ሲል ኤፕኮ የራሱ ማሰልጠኛ የነበረው ሲሆን አሁን ግን እሱም ተዘግቷል።

በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትም በኩል ብንሄድ በአ.አ. ዩኒቨርሲቲ በኤሌክትሪካልና መካኒካል ምሕንድስና መስክ የተጀመሩ የድኅረምረቃ ትምህርቶች አሉ። ይህ ጥሩ ዕድገት ነው። ይሁን እንጂ በምርምርና ዲዛይን ልማት ላይ የሚሠሩ ሰፊ ፕሮጀክቶች የሉም። ለዚህም የተመደበ በጀት የለም። በአጠቃላይ የአንድ አገር ሳይንስና ቴክኖሎጂ ሊያድግ የሚችለው በግዢ ያለመሆኑ ሊጤንና ለገዳዩ በቂ ትኩረት በመስጠት የምርምር ተቋሞችን መገንባት፣ የቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ሥራዎችን ማስፋፋትና ማበረታታት በተገባ ነበር።

5. አሁን ያለው ሁኔታ ቢቀጥል ኢትዮጵያ በ2020 የት ትደርሳለች?

ቀደም ባለው ክፍል አንዳንድ ጠቋሚ መለኪያዎችን በማስቀመጥና ከሌሎች አገሮች ጋር በማነፃፀር አሁን ያለውን የኢትዮጵያ ኤነርጂ ሁኔታ ለማሳየት ተሞክሯል። ቀጥሎ የአሁን ጊዜውን ቁጥሮች (figures) በመውሰድ፣ ያለፋትን ዓመታት የዕድገት ፍጥነትና ሊመጡ የሚችሉትን አንዳንድ ለውጦች ከግምት ውስጥ በማስገባት በኢትዮጵያ በ2020 ሊኖር የሚችለውን የኤነርጂ አጠቃላይ ሁኔታ ለመተንበይ ተሞክሯል። እነኚህንም ቀደም ሲል በተገለጹት 4ቱ የኤነርጂ ዘርፎች መግለጹ የተሻለ ይሆናል።

5.1 ባሕላዊ ማገዶና የእንስሳት ኤነርጂ

በመጨመሪ፡ ዓመታት ዋነኛው ባሕላዊ ነዳጅ የሆነው የእንጨት ፍላጐት በአብዛው ከሕዝብ ብዛት የተነሳ እየጨመረ ይሄዳል። ይህም ከእርሻ መሬት መስፋፋትና ከኮንስትራክሽን ፍላጐት ጋር ተዳምሮ በቂ ጥበቃ የማይደረግለት የተፈጥሮ ደን ወድሞ በእርሻ እንዲተካ እያደረገ ይሄዳል። በዚህም የተነሳ በገጠሩ እንጨት አዱር መስበር ወይም መልቀም የማባለው ነገር ፊጽሞ እንዲቀር ሊያደርግ ይችላል። በአቶ አልአዛር ጥላሁን ጥናት ትንበያ መሠረት አሁን ያለው ሁኔታ ከቀጠለ የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ደን ያለበት የደቡቡና የምዕራቡ በሙሉ ያልቃል [18]። ይህ ማለት ግን አሁን የተፈጥሮ ደን ያለበት የደቡቡና የምዕራቡ የአገሪቱ አከባቢዎች ደን እነዳሌለባቸው እነደተቀሩት የአገሪቱ አከባቢዎች ይሆናሉ ማለት እንጂ ከዚያ በኃላ እንጨትና የእንጨት ዘር የማባል ከአገሪቷ ምድር ይጠፋሉ ማለት እንዳልሆነ ግልጽ መሆን አለበት። በየቤቱ ጓሮና ጥበቃ ባላቸው አከባቢ የማተከሉ ዛፎችና ወኅ፡ ዘራሽ ቁጥቋጦዎች ይኖራሉ። ዋነኞቹም የባሕላዊ ነዳጅ ምንጮች እነርሱ ይሆናሉ ማለት ነው። ይህም ሆኖ ባሕላዊ ነዳጅ በጠቅላላው የአገራችን የኤነርጂ ፍጆታ ውስጥ ያለው ድርሻ ከኅብረተሰቡን ሥፍራ ይዞ ይቆያል። ይሁን እንጂ በሌሎች የኤነርጂ ምንጮች የኤነርጂ ምንጮች ዕድገት የባሕላዊ ማገዶ ፍጆታ ዕድገት እየቀነሰ ይሄዳል።

በለላ በአብዛኛው የኤነርጂ ምንጮች መካከል የእርሻ ተረፈ ምርትና የከብቶች ፍግ ለመሬት ማዳበሪያነት ሊውሉ ይችላሉ። አሁን ባለው ሁኔታ ግን በአብዛኛው ለማገዶነት በመዋል ላይ ይገኛሉ። በዚህም ምክንያት ለእርሻ የሚውለው መሬት ከእነኚህ ውጤቶች የሚያገኘውን ተፈጥሯዊ ማዳበሪያ በማጣቱ ለምነቱ እየጠፋ ሄዷል። ከዚህም በበለጠ ሁኔታ በደኖች መመናመን ምክንያት የአፈር መከላት/መሸርሸር በመከተሉ የእነኚህ ሁሉ ድምር ውጤት በእርሻው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። አሁን ያለው ሁኔታ ከቀጠለ ምናልባትም በነዚህ የኤነርጂ ምንጮች ላይ በሚካሄደው የተዛባ አጠቃቀም ምክንያት ለወደፊቱ ከፍተኛ የሆነ የእርሻ ምርት መቀነስ ሊያጋጥም እንደሚችል ይገመታል።

5.2 ነዳጅ ዘይትና የከርሰ ምድር ነዳጆች (የተፈጥሮ ጋዝና የድንጋይ ከሰል)

የኢትዮጵያ የነዳጅ ዘይት ውጤቶች ፍላጐት ባለፉት ዓመታት በነበረው ፍጥነት እያደገ ከሄደ ዛሬ ነለበት ከ1.2 ሚሊዮን ቶን በ2020 ወደ 10 ሚሊዮን ቶን በዓመት ሊደርስ ይችላል። ይሁን እንጂ ዋጋው እየናረና የዓለም መቀት ወይም የአየር ንብረት ለውጥ ችግር እየጨመረ መሄድ አንፃር ወደፊት ነዳጅ ዘይትን መጠቀመ ከባድ እየሆነ መሄዱ አይቀርም። በተለይ የዋጋው መናር ከግማሽ በላይ የሚሆነውን የውጭ ምንዛሪ ገቢዋን በነዳጅ ዘይት ውጤቶች ግዥ ላይ ለምታውለው ኢትዮጵያ ከባድ የኤኮኖሚ ጫና ይፈጥራል።

በለላ በአብዛኛው ለሚታሰበው ፈጣን የኤኮኖሚ ዕድገት ነዳጅ የግድ ስለሚያስፈልግ አማራጭ የአቅርቦት ሁኔታ መፈለግ ይኖርበታል። ከዚህ አኳያ አገሪቷ ያላትን የተፈጥሮ ጋዝና

የድንጋይ ከሰል እንዲሁም ኤታኖልና ሌሎች ታዳሽ ነዳጆች መጠቀም ያስፈልጋል። በተጨማሪም ከዚህ ቀደም በሌላ ጥናታዊ ጽሑፍ እንደአቀረብኩት [6] በየብስ ማጓጓዣ አይነትና የኤነርጂ አጠቃቀም ላይ ለውጥ ማድረግ ያስፈልጋል። አሁን ባለው ሁኔታ አብዛኛው (92%) የገቢና የወጭ ንግድ ዕቃዎች የሚጓዙት በቶን-ኪሎሜትር እጅግ ዝቅተኛ የኤነርጂ ፍጆታ ባለው የባቡር ማጓጓዣ ሳይሆን በጣም ከፍተኛ ፍጆታ ባለው የጭነት መኪና ማጓጓዣ ነው። በዓለምአቀፍ ደረጃ በቶን-ኪሎሜትር ሲታሰብ የባቡር ማጓጓዣ የሚመጣጠነው ከ30 የጭነት መኪና ማጓጓዣ ጋር ነው። ይህ የሚያሳየው ከፍተኛ ጥቅም ሊሰጥ ይችል የነበረው የባቡር ማጓጓዣ ለዘመናት ቸል መባሉና እነዲዳከም መደረጉ አገሪቱን በጣም መገዳቱን ብቻ ሳይሆን ፈጣን ለውጥ ካልተደረገ ጎጂነቱ በይበልጥ የሚቀጥል መሆኑን ጭምር ነው።

የነዳጅ ዘይት ፍላጎትን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ ሌላው መወሰድ ያለበት እርምጃ ባቡርና በኤሌክትሪክ የሚሠሩ ባቡሮችና አውቶቡሶችን (trolley-buses) ማስፋፋትና መጠቀም የነዳጅ ዘይት ፍጆታን መቀነስ ከማስቻሉም በተጨማሪ የመለዋወጫ ፍጆታንና ሌሎች ወጪዎችን ይቀንሳል። ይሁን እንጂ አሁን ያለው ሁኔታ ነዳጅ ዘይትን መግዛት ከመቀጠል ያለፈ አይመስልም። አካሄዱ ቶሎ ካልተቀየረ አሁን ያለው የዕድገት ፍጥነት በነዳጅ ችግር ምክንያት ብቻ እንኳ ሊቀንስ ይችላል።



ሥዕል 11 በኤሌክትሪክ የሚሠራ ባቡር



ሥዕል 12 በኤሌክትሪክ የሚሠራ የከተማ አውቶቡስ (ትሮሊ አውቶቡስ)

5.3 የኤሌክትሪክ ኃይል

አሁን ያለው የነፋስመከፋ የኤሌክትሪክ ኃይል ማመንጨት አቅም ወደ 10 ዋት ሲሆን በኢነኮ ስሌት መሠረት የነፋስመከፋ የኤሌክትሪክ ኤነርጂም 28 ኪሎዋት ሰዓት በዓመት ነው [10]። እዚህ ላይ ይህ የነፋስመከፋ የኤሌክትሪክ ኤነርጂ ምን ማለት እንደሆነ በምሳሌ ለማየት እንሞክር፦

በዚህ አዳራሽ የተሰበሰብን ሰዎች እያንዳንዳችን በቤታችን ውስጥ ባለ 60 ዋት (ሻማ) የሆኑ አሥር አሥር አምፖሎች አሉን እንበል። አምፖሎቹን በየቀኑ ከምሽቱ 12 ሰዓት እስከ አምስት ሰዓት እናበራቸዋለን ብንል የየወሩ የኤሌክትሪክ ኤነርጂ ፍጆታችን 90,000 (=60x10x5x30) ዋት ሰዓት ማለትም 90 ኪሎዋት ሰዓት ይሆናል ማለት ነው። ይህ የምጣድ፣ የፍሪጅ፣ የካውያና የመሳለሉትን ፍጆታ ሳይጨምር መሆኑን ልብ እንበል። በአገራቱ የሚመረተው የኤሌክትሪክ ኤነርጂ እኩል ለኢትዮጵያ ሕዝብ በሙሉ ያለአድልዎ ተከፋፍሎ ቢሰጥ ኖሮ እያንዳንዳችን እዚህ የታደምን ተሰብሳቢዎች የመጪዎቹን 3 ዓመት ከሁለት ወራት (=90÷28=3.2 ዓመት) የኤሌክትሪክ ኮታችንን በአንድ ወር ውስጥ ብቻ ተጠቅመን የምንጨርስ ስለሆነ፣ ከእያንዳንዱ ወር ተጠቃሚነት በኋላ ለቀጣዮቹ 3 ዓመት ከሁለት ወራት አንዳችም የኤሌክትሪክ ኃይል እንዳንጠቀምና በጨለማ እንድንኖር በተፈረደብን ነበር። እዚህ ላይ ለምሳሌ በቀረበው የኮታ ሕግ መሠረት ከዛሬ ጀምሮ ለሚቀጥሉት 3 ዓመት ከሁለት ወራት ኤሌክትሪክ መጠቀም ብንከለከል ምን ይሰማናል? ይህን ለጥቂት ሰኮንዶች በምናባችን እንድንኖረው በጥያቄ መልክ ያቀረብኩትን ኑሮ ለ3 ዓመት ከሁለት ወራት ብቻ ሳይሆን ለዕድሜ ልክ በቋሚ ጨለማ ውስጥ የሚኖሩ ዜጐቻችን ከጠቅላላው ሕዝብ 85% ናቸው። ይህ ሁኔታ እንዲቀጥል መፍቀድ ምን ያህል ኢፍትሐዊ መሆኑን ከዚህ ምሳሌ መገንዘብ እንችላለን።

በአሜ ኃይለሥላሴ ዘመን መጨረሻ የነበረው የአገራችን የኤሌክትሪክ ኃይል የማመንጨት አቅም 260 ሜጋዋት ብቻ ነበር። ይህ አቅም በደርግ 17 የሥልጣን ዘመናት ያደገው በ153 ሜጋዋት ብቻ ነው። በአለፉት 14 ዓመታት በ293 ሜጋዋት ጨምሮ በአጠቃላይ የኤሌክትሪክ የማመንጨት አቅማችን ወደ 706 ሜጋዋት አድጓል። ያለፉትን 31 ዓመታት ያምረን ስናይ የተደረገው ጭማሪ 446 ሜጋዋት ነው። ይህ በዓመታዊ ዕድገት ስሌት ሲታይ 3.3% ብቻ ሆኖ እናገኘዋለን። ዕድገቱ በዚህ ሁኔታ ቢቀጥል በ 2020 ሊደርስ የሚችለው ወደ 1,482 ሜጋዋት ወይም የዛሬውን እጥፍ ያህል ብቻ በመሆኑ አሁን ካለንበት የኃላቀርነት ሁኔታ የሚያወጣን አይደለም።

የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን ከሶስት አመታት በፊት ባሠራው የመሪ-ዕቅድ ጥናት መሠረት የሀገሪቱ የኤሌክትሪ ኃይል ፍላጐት እ.ኤ.አ በ2025 ወደ 2,335 ሜጋዋት ወይም 9.9 ሚሊዮን ሜጋ ዋት ሰዓት ይደርሳል [19]። በዚያ ዓመት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት 117.6 ሚሊዮን እንደሚደርስ ይገመታል። ስለዚህም በዚያን ወቅት የሚኖረው የነፍስወከፍ የኤሌክትሪክ ፍጆታ 84.2 ኪሎዋት ሰዓት ይሆናል ማለት ነው። ይህ አሁን ካለንበት ደረጃ ጋር ሲነፃፀር የ3 እጥፍ ዕድገት ያህል ነው። ይሁን እንጂ እንደ ኬንያ ያሉ ጐረቤቶቻችን ዛሬ ካሉበት ጋር እንኳ ሲነፃፀር ከ2/3ኛው ያነሰ ነው። ይህ የሚያሳየው አሁን የታያዘው ጉዞ ከኃላቀርነትም ሆነ ከድህነት ሊያላቅቀን የማይችል መሆኑን ነው።

5.4 ዘመናዊ ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች

እስከአሁን የነበረው የዘመናዊ ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች ልማት ከከፍተኛ የውሃ የኤሌክትሪክ ኃይል ልማት ውጭ ያለው ከቁጥር ውስጥ የማይገባ መሆኑ ቀደም ሲል ተገልጿል። ከዓመት እስከ ዓመት ያለማቋረጥ የሚፈሱ በቀላሉ ተገድበው አነስተኛ የኤሌክትሪክ ኃይል ሊሰጡ የሚችሉ ወንዞች እያሉ፣ የ"13 ወራት" የፀሐይ ብርሃን ፀጋ እያለ፣ በቀንድ ከብቶች ብዛት ከአፍሪካ 1ኛ ሆነን ማለትም ባዮጋስ ሊሰጥ የሚችል በጣም ብዙ አዛባ እያለ ወዘተ፤ በዘመናዊ ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች ልማት ላይ የተሠራው ሥራ እጅግ በጣም አነስተኛ በመሆኑ ገጠሩ ዛሬም እንደ ጥናቱ በጨለማ ውስጥ ይገኛል። በከተማም ቢሆን ከየቤቱ የሚወጣው ቆሻሻ በአግባቡ ጥቅም ላይ ቢውል አንደአሁኑ አካባቢን በመበከል ፋንታ ኤነርጂን ሊያመነጭ ይችላል።

ይሁን እንጂ ከሁለት ዓመታት ወዲህ በዋነኛነት በዓለም ባንክና በኢትዮጵያ የገጠር ኤነርጂ ልማትና ማስፋፊያ ማዕከል በኩል የተጀመረ ሰፊና ተስፋ ሰጭ ዕቅድ አለ። በዚህ ዕቅድ መሠረት የገጠር ኤሌክትሪክ ልማት ፈንድ የሚባል ተቋም ተቋቁሟል። የተቋሙ ተግባር ለገጠር የኤሌክትሪክ አልማ ባለሀብቶችና የሕብረት ሥራ ማኅበራት ብድር መስጠትና መያዊ እገዛ ማድረግ ነው። ዕቅዱን በሰፊው ተግባራዊ ማድረግ ከተቻለ በመጪዎቹ 20 ዓመታት በርካታ አነስተኛ የውሃ ኤሌክትሪክ ጣቢያዎች፣ የፀሐይ ኤሌክትሪክ መብራቶች፣ የንፋስ ኃይል ኤሌክትሪክ ማመንጫዎችና የመሳሰሉት በየገጠሩ ሊተከሉ ይችላሉ። የነኚህ ጣቢያዎች ጠቅላላ ኤሌክትሪክ ማመንጫት አቅም በ20 ዓመታት ጊዜ ውስጥ ወደ 300 ሜጋዋት ያድጋል የሚል ግምት አለ። ይህ ካልሆነ ግን ገዳዩ ከ"ባለሀበት ሄድ" ብዙ የማይሻል ሆኖ ሊዘልቅ ይችላል።

5.5 ጠቅላላ የኤነርጂ ፍጆታ ዕድገት

ከላይ በተለያዩ የኤነርጂ ምንጮች ሊኖር የሚችለውን ዕድገት ለማመልከት ተሞክሯል። የእነኚህ ድምር ውጤት የነፍስወከፍ ዘመናዊ የኤነርጂ ፍጆታውን ወደ 93 ኪሎግራም ዘይት ተመጣጣኝ በዓመት ሊያደርሰው እንደሚችሉ ይገመታል። ይህ ደግሞ ከሌሎች ጋር ሲነፃፀር እንኳን ከ23 ዓመታት በኋላ ይቅርና በዛሬም ደረጃ ቢሆን በጣም ዝቅተኛ ነው።

6 በ2020 የኢትዮጵያ የኤነርጂ ገጽታ ርዕይ (vision)

ዛሬ ላይ ሆነን 23 ዓመታትን ወደፊት ማየት በጊዜው ርዝመት ምክንያት አስቸጋሪ ነው። ስለዚህም በ2020 የኢትዮጵያ የኤነርጂ ዘርፍ ምን ሊመስል ይችላል? ምንስ መምሰል ይገባዋል? ለሚለው ጥያቄ መልስ መሻት ከባድ ነበር። ሆኖም ከሌሎች አገሮች ልምድና ከአሁኑ በጣም ፈጣን በሆነ የአገራችን የኤኮኖሚ ልማት ርዕይ ላይ በመመሥረት መከራዎን ቀናሎ አቅርቤአለሁ። ይህንንም በኤነርጂ ዓይነቶች እንመልከት፡-

6.1 ባሕላዊ ማገዶና የእንስሳት ኤነርጂ

በደኖች መመናመን ምክንያት የተፈጠረው ችግር በሕገ-ወጥና በመንግሥት በኩል ከፍተኛ ግንዛቤ እያገኘ ይሄዳል። ከዚህም በመነሳት ልዩ ልዩ የፖሊሲ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፤ ለውጥም ያመጣሉ። ለምሣሌ የገፍ ባለቤትነት መብትና የማልማት ፖሊሲ ይወጣል፤ ይህም ገፍ እንዲተከል ያበረታታል፤ በደንና በእርሻ ምርታማነት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ የሚያሳድረውን የአሁኑን የቤት ውስጥ ማገዶ አጠቃቀም ያሻሽላል። በተጨማሪም የባዮ ጋዝ አጠቃቀምን በማስፋፋት፣ የተሻሻሉ ምድጃዎችን በማሠራጨት፣ የድንጋይ ከሰልንና አዳዲስ የኤነርጂ ምንጮችን ለቤት ውስጥ ማገዶነት በመጠቀም የባሕላዊ ማገዶ አጠቃቀም ይሻሻላል፤ ድርሻውም እየቀነሰ ይሄዳል።

የእርሻ ምርታማነት ከአሁኑ በብዙ እጥፍ ያደገ ስለሚሆን ከእርሻ የሚገኘው ተረፈ ምርት ከፍተኛ ይሆናል። የመሬትን ለምነት ለመጠበቅ ሲባር የሚገባው ቀርቶ ለማገዶነት የሚተርፍ ከፍተኛ ተረፈ ምርት ይገኛል። በምርታማነት መጨመር የተነሣ የገበሬውና የጎጆ ኢንዱስትሪው ባለሀብት ገቢ መጠን ስለሚጨምር ብዙ የገጠር አካባቢዎች ዘመናዊ የኤነርጂ ምንጮችን ማለትም እንደ ኤሌክትሪክና ባዮ ጋዝ ያሉትን መጠቀም ይጀምራሉ። በደን ላይ ብዙ ጉዳት ሳይደርስ ማገዶን በዘዴና በብልሃት የመሰበሰብ አሠራር ትምህርት ስለሚሰጥና አሠራሩ ስለሚለመድ ደን ሳይጨፈጨፍ ተጨማሪ የማገዶ አቅርቦት ይኖራል። በእነዚህ ሁሉ ምክንያቶች በ2020 ባሕላዊ የኤነርጂ አቅርቦት አስተማማኝና በአካባቢው ላይ ተጽዕኖ ሳያሳድር የሚከሄድ ይሆናል። በዚህም ምክንያት በ2020 የደን ይዞታ ለመጀመሪያ ጊዜ የመቀነስ ሂደቱን ለውጦ የመጨመር ሁኔታ የሚታይበት ይሆናል። ከላይ በጠቀስናቸው ምክንያቶች ደን ስለሚያገግም በ2020 የደን ሽፋን አሁን ካለበት 2.8% ወደ 6.0% እና ከዚያ በላይ ያድጋል።

6.2 የኤሌክትሪክ ኤነርጂ

በዶ/ር ብርሃኑ ነጋ ስሌት [20] መሠረት አብዛኞች በስፋፋ (40% በደርስ)፣ የኤኮኖሚው ምርታማነት (የአብዛው ምርታማነትና የገበሬው ምርታማነት) በሻሻልና የሕዝብ ዕድገት ፍጥነት አሁን ካለበት በ 0.4% በቀንስ፣ የኢትዮጵያ የነፍስወከፍ ዓመታዊ ገቢ በ2020 ወደ ብር 1,623 ለያድግ ይችላል። ይህ ቁጥር በ1973 ቋሚ ዋጋ በመሆኑ ወደ አሜሪካን ዶላር ሲቀየር 784 ዶላር ይሆናል። በዚህ ጽሑፍ የመጀመሪያ ክፍል አካባቢ የታየውን የአገሮች የነፍስወከፍ ገቢና የኤነርጂ ፍጆታ ዝምድና ያስታውሱ። ይህ ገቢ ከ260 ኪሎግራም በላይ የሆነ የዘመናዊ ኤነርጂ ፍጆታ ጋር የሚዛመድ ነው። በወቅቱ ከሚኖረው የሕዝብ ብዛት ጋር ሲሰላ ጠቅላላ የኤነርጂ ፍላጐቱ ከ30.6 ሚሊዮን ቶን በላይ

ባለፉት ዓመታት የነበረው የኢትዮጵያ የኤሌክትሪክ ኤነርጂ ፍጆታ ከጠቅላላው የዘመናዊ ኤነርጂ (ነዳጅ ዘይትና ኤሌክትሪክ) ፍጆታ ከ10% እስከ 15% ነው። የወደፊቱ አማካይ 10% በሆነና ከላይ የቀረበውን ስሌት ብንጠቀም በ2020 የ3.1 ሚሊዮን ቶን ዘይት ተመጣጣኝ ወይም የ36.18 ሚሊዮን ሜጋዋት ሰዓት የኤነርጂ ፍጆታ ወይም የ8,615 ሜጋዋት የማመንጨት አቅም ያስፈልጋል ማለት ነው። 8,615 ሜጋዋት የዛሬን 12 እጥፍ በመሆኑ በጣም ከፍተኛ ዕድገት ነው። እስከ ዛሬ ድረስ የተጠናቀቁትን የኤሌክትሪክ ማመንጫዎችንና አንዳንድ ታሳቢዎችን እንኳን ብንጨምር ሊደርስ የሚቻለው 2,500 ሜጋዋት ላይ ብቻ ነው። ይህም በመሆኑ በዶ/ር ብርሃኑ የተሰላው የኤኮኖሚ ዕድገት የማመጣ ከሆነ (ይመጣል የሚል ርዕይ አለኝ።) ኤሌክትሪክ የማመንጨት አቅማችን እንደእስከ አሁኑ በ3.3% ሳይሆን በ 11.5% በዓመት ማደግ አለበት።

በኔ ርዕይ በ2020 ከኤሌክትሪክ ማመንጫ ጣቢያዎቻችን የሚመነጨው ኃይል 40%ው ወይም ወደ 3,450 ሜጋዋት የሚሆነው ከውሃ ውጭ ካሉ የኤነርጂ ምንጮች የሚገኝ ይሆናል።

6.3 የነዳጅ ዘይት

ከላይ የተጠቀሰውን የዶ/ር ብርሃኑ ነጋን የኤኮኖሚ ዕድገት ስሌት ተከትለን ብንሄድና በዚህም ዘርፍ የሚኖረው ዕድገት የሌሎች አገሮችን ፈለግ ይከተላል ብንል እንዲሁም ነዳጅ ዘይት ከጠቅላላው የዘመናዊ ኤነርጂ ፍጆታ ባለፉት ዓመታት የነበረውን አማካይ ድርሻ 90% ቢይዝ ኢትዮጵያ በ2020 27.5 ሚሊዮን ቶን ነዳጅ ዘይት ያስፈልጋታል። ይህ ከዛሬ ፍጆታ ጋር ሲነፃፀር 23 እጥፍ በመሆኑ እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው። እያሻቀበ ከሚሄደው ዋጋና ከዓለም መቀት መጨመር ችግር የተነሳ በሌሎች ምንጮች ለመተካት ከሚደረገው ዓለም አቀፍ ጥረት አኳያ በወቅቱ የሚኖረውን ፍላጐት ማሟላት አስቸጋሪ ይሆናል። ስለዚህም ከፍተኛ የፖሊሲ ለውጥ ያስፈልጋል። ዋናው የፖሊሲ ለውጥ መደረግ ያለበት አሁን የተገኙትን የከርሰምድር ነዳጆችን በፍጥነት በማልማት ላይና በየብስ ማጓጓዣ አይነትና የኤነርጂ አጠቃቀም ላይ ነው። በተለይም የተፈጥሮ ጋዝ ልማቱ በጣም ቢፋጠን በመስኩ ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል። ቀደም ሲል እንደተገለጸው ባቡርና የከተማ አውቶቡስን በማስፋፋትና በኤሌክትሪክ ወደሚሠሩ በመለወጥም የነዳጅ ዘይት ፍላጎትን በከፍተኛ ደረጃ ለመቀነስ ይቻላል። በዚህም መሠረት በ2020 የተፈጥሮ ጋዝ አጠቃቀም ለማዳበሪያነት፣ ለቤት ውስጥ አገልግሎትና ለመሳሰሉት ከመዋል በተጨማሪ ለኤሌክትሪክ ማመንጫነት በመዋል የዘመናዊ ኤነርጂ ፍጆታውን 15% ይሸፍናል፤ የባቡርና የከተማ አውቶቡስ አገልግሎት በጣም በመስፋፋት በኤሌክትሪክ የሚሠራው ባቡር የገቢና የወጭ ንግድ ዕቃዎች በማጓጓዙ ሥራ ቢያንስ የ30% ድርሻ ይኖረዋል፤ 30% የከተማ አውቶቡስ በኤሌክትሪክ የሚሠራ ይሆናል፤ የሚል ርዕይ አለኝ።

ከዚህ ጋር ደግሞ ኤታኖልና ባዮዲዝል (biodiesel)ን የማምረቱ ሥራ ይበልጥ ቢስፋፋና ዓለም እየሄደበት ወደአለው የሃይድሮጂን ኤኮኖሚ[13] ለመግባትም አንዳንድ ጅምር ሥራዎች ቢሠሩ በወቅቱ የሚኖረው ፍላጐት ይሟላል የሚል ርዕይ አለኝ::

6.4 ዘመናዊ ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች

እነኚህ የኤነርጂ ምንጮች ለገጠሩም ሆነ ለከተማው ለያገለግሉ የሚችሉ ቢሆንም በይበልጥ ለገጠሩ ተስማሚ ናቸው:: በቀላሉም ሊስፋፉ ይችላሉ:: ይህን ታሳቢ በማድረግ አንድ ትልም ማስቀመጥ ይቻላል:: በ2020 ከኢትዮጵያ ገጠር አካባቢዎች 30% የፀሐይ፣ የውሃ፣ የንፋስ ወዘተ፤ ኤሌክትሪክ ተጠቃሚነት ዕድል ይኖራቸዋል:: ይህ ርዕይ ሊሟላ የሚችለው አሁን በተያዘው ጉዞ እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: ልዩ ልዩ የሥልጠና፣ የምርምር፣ የመሣሪያ ፍብረካና የመሳሰሉ የኤነርጂ ልማት ማስፋፊያ ፕሮግራሞችን ማካሄድና በየገጠሩ ሰፊ የብድር አሰጣጥ ሥርዓትን መዘርጋት ይጠይቃል:: የሌሎች አገሮችን ልምድ መቅሰምና ለግብርናው እንደሚደረገው ሁሉ የኤነርጂ ጎብረት ሥራ ማጎበራትን ማቋቋም ጠቃሚ ይሆናል::

6.5 አጠቃላይ ጉዳዮች

ቀደም ባሉት ዓመታት ተቋቁሞ በ2020 ኢትዮጵያ ራሱን የቻለና ዘርፉን ከላይ ለተጠቀሱት ግቦች የሚያበቃ የኤነርጂ ሚኒስቴር ይኖሩታል:: መ/ቤቱም በሥሩ በርካታ ልዩ ተቋማት ይኖሩታል፤ የኤነርጂ ጉዳዮችን ሁሉ ያስተባብራል፤ መሪ-ዕቅድ ያወጣል፣ አፈጻጸሙን ይከታተላል፤ ለቴክኖሎጂ ሽግግርና ልማት ልዩ በጀት በመመደብ የኤነርጂ ቴክኖሎጂን ያለማል፣ ያስፋፋል፣ በዘርፉም የሰው ኃይል ይገነባል፤ ከዩኒቨርሲቲዎች ጋር በመተባበር ምርምር እንዲካሄድ ያደርጋል::

በ2020 በኢትዮጵያ የሚገኙ የመኖሪያና የመሥሪያ ቤቶች ሁሉ ኤነርጂ ቆጣቢ አምፖሎችንና ሌሎች መሣሪያዎችን ይጠቀማሉ:: ብክነትን ማስወገድ የሕዝቡ ባሕል ይሆናል፤ በአገልግሎት ሰጭና ተቀባዩ ወገን መካከል ጤናማና ቀልጣፋ ግንኙነቶች ይፈጠራሉ፤ እነኚህም የሕዝቡን የኑሮ ደረጃ በእጅጉ እንዲሻሻል ያደርጋሉ የሚል ርዕይ አለኝ::

እንደዛሬው ኤፕኮ ብቻ ሳይሆን በርካታ የኃይል አምራች ኩባንያዎች በዘርፉ ውስጥ ይኖራሉ:: የአገልግሎት ጥራታቸውም ደረጃውን የጠበቀና ተገልጋዩን ሕዝብ ደስ የሚያሰኝ ይሆናል:: ኢትዮጵያ በኃይል አቅርቦት ጥሩ ደረጃ ላይ ይገኛሉ ከሚባሉት አገሮች አንዷ ትሆናለች::

---

[13] የሃይድሮጂን ኤኮኖሚ የሚባለው ነዳጅ ዘይትንና ሌሎች የከርሰምድር ነዳጆችን በሃይድሮጂን በመተካት የሚፈጠር ኤኮኖሚ ነው:: የከርሰምድር ነደጆች ታዳሽ ባለመሆናቸው፣ ለዓለም መሞቅ እየጨመረ መሄድ ምክንያት በመሆናቸውና እየአለቁም ስለሄዱ የ21ኛው ክ/ዘመን ነዳጅ ሃይድሮጂን ይሆናል የሚል እምነት አለ:: ለተግባራዊነቱም የለመ አገሮች ሰፋፊ ፕሮግራሞች ይዘዋል::

ምሥጋና

ይህን የውይይት መድረክ ላዘጋጁውና በዚህ መድረክ ላይ ጽሑፍ እንዲቀርብ ለጋበዘኝ ለኢትዮጵያ የኤኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር፣ ይህንንም ላመቻቹት ለአቶ ኃይለ ልዑል ጠብቂና ለዶ/ር አሰፋ አደማሴ እንዲሁም በጽሑፉ የመጨረሻ ክፍል ዝግጅት ላይ ተሳትፎ በማድረግና አጠቃላይ አስተያየት በመስጠት ለረዱኝ ለአቶ ሙሉጌታ አዳሙና መረጃ በመስጠት ለተባበሩኝ ሁሉ ከፍተኛ ምሥጋናዬን አቀርባለሁ።

ዋቢ መጻሕፍት/ሰነዶች (References)

[1] Oxford University Press, 1994: *Pocket Oxford Dictionary*, Oxford University Press, March 1994.

[2] Meriam-Webster, 1986: *Webster's Ninth Collegiate Dictionary*, Meriam-Webster Inc. Publishers, Springfield, Massachusetts, U.S.A.

[3] Daniel Yergin, Robert Stobaugh, Jennifer Weeks and Henry Lee (Reviewer), 2004: "Energy Supply, World" in *Encarta Encyclopedia Standard 2004*, multimedia encyclopaedia, Microsoft Corporation.

[4] Bekele Bayissa, 2003: "The Energy Dimension in Food Security" in Tesfahun Fenta and Osman Ali (Editors): *Proceedings of the Food Security Conference 2003*, UNCC, Addis Ababa, 13-15 August 2003, organised by Professional Associations Joint Secretariat.

[5] Tanzer, Michael, 1974: *The Energy Crisis: World Struggle for Power and Wealth*, Monthly Review Press, New York and London, U. S. A.

[6] Bekele Bayissa, 2002: "The Prevailing Fuel Crisis and Mitigating Measures" in Desta Mebratu and Mulugeta Tamire (Editors), *Proceedings of Energy Conference 2002*, Addis Ababa, 21-22 March 2002, organised by Professional Associations Joint Secretariat.

[7] Ethiopian Forestry Action Programme (EFAP): *Ethiopian Forestry Action Programme, Final Report Vol. II - The Challenge of Development*, Ministry of Natural Resources Development and Environment Protection, Addis Ababa, 1994.

[8] National Bank of Ethiopia: *National Bank of Ethiopia -Annual Report*, issues of 1992/93 and 2001/2002, National Bank of Ethiopia, Addis Ababa.

[9] Ministry of Economic Development and Cooperation (MEDaC), 1999, *Survey of the Ethiopian Economy (1992/93- 1998/99)*, (unpublished), Addis Ababa.

[10] Ethiopian Electric and Power Corporation (EEPCo), 2002: "Power Sector Development Program" in EEPCo's website, *htpp//www.eepco.gov.et*

[11] Varet, Jack: "Prospects of Geothermal Energy Utilization in Ethiopia", *Sinet: An Ethiopian Journal of Science* Vol. 1, No.1, 1978.

[12] Mekonen Kassa: *Notes on National Energy Supply and Consumption, 1995/96*, Ethiopian Rural Energy Development and Promotion Centre.

[13] Araya Asfaw (Editor), *ENSED Newsletter*, Volume 1, Number 3, December 2003.

[14] Mekonen Kassa, 2002: "Managing the Rural Energy Transition in Ethiopia" in Desta Mebratu and Mulugeta Tamire (Editors), *Proceedings of Energy Conference 2002*, Addis Ababa, 21-22 March 2002, organised by Professional Associations Joint Secretariat.

[15] የተወካዮች ምክር ቤት፣ 1994፡ "የኢትዮጵያ ፌዴራል ዲሞክራሲያዊ ሪፐብልክ አስፈጻሚ አካላትን አደረጃጀት ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 256/1994"፣ *የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ*፣ 8ኛ ዓመት ቁጥር 2፣ አዲስ አበባ።

[16] Transitional Government of Ethiopia, March 1994: *Energy Policy of the Transitional Government of Ethiopia*, Addis Ababa.

[17] Araya Asfaw (Editor), *ENSED Newsletter*, Volume 1, Number 1, October 2003.

[18] Aleazar Tilahun, 2002 "Is Fuelwood Energy the Future Prospect for the Ethiopian Poor?" in Desta Mebratu and Mulugeta Tamire (Editors), *Proceedings of Energy Conference 2002*, Addis Ababa, 21-22 March 2002, organised by Professional Associations Joint Secretariat.

[19] Zelalem G/Hiywot and Mekbib Lemma, 2002 "Past Experiences and a 25 Year Electric Power Development Plan of Ethiopia" in Desta Mebratu and Mulugeta Tamire (Editors), *Proceedings of Energy Conference 2002*, Addis Ababa, 21-22 March 2002, organised by Professional Associations Joint Secretariat.

[20] ብርሃኑ ነጋ፣ 1995: "የኢትዮጵያ ዕጣ ፋንታ ከአንድ ትውልድ በኋላ"፣ *ልሳነ ኤኮኖሚክስ የኢትዮጵያ ኤኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር መጽሔት (Economic Focus, Bulletin of the Ethiopian Economic Association (EEA)*, Vol. 5, No. 4, July 2003.

ኤነርጂ እና ልማት በኢትዮጵያ ጽሑፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት

መ·ሉ·ጌታ አዳመ·*

በአቶ በቀለ ባይሣ "ርዕይ 2020 በኢትዮጵያ-ኤነርጂና ልማት በኢትዮጵያ" በሚል የቀረበውን ጽሑፍ ስመለከት አቶ በቀለ ይህን ጽሑፍ ሲያዘጋጅ ከፍተኛ ጥረትና ድካም እንዳደረገ ለመገንዘብ ችያለሁ። ላደረገው ከፍተኛ ጥረት ያለኝን አድናቆት ልገልጽ እወዳለሁ።

እኔ አስተያየቴን ለመስጠት የምሞክረው ጠቅለል ባለ መልኩ ነው። በመጀመሪያ በአቶ በቀለ ጽሑፍ ውስጥ ብዙ አልተብራራም ብዬ የማስበውን የባሕላዊ ኤነርጂ አጠቃቀምና ከእርሱ ጋር የተዛመዱ ችግሮች ላይ ያለኝን ሀሳብ አርባለሁ። ከዚያ ቀጥዬ በዘመናዊ የኤነርጂ ምንጮች ላይ በጽሑፍ ከተነሱት ሃሳቦች ተጨማሪ በማከል አስተያየቴን አበቃለሁ።

የባሕላዊ ኤነርጂ አጠቃቀምና ተዛማጅ ችግሮች

በኢትዮጵያ በ1991 ዓ.ም በአጠቃላይ 10.83 ሚሊየን ቶን ተመጣጣኝ ነዳጅ ዘይት ያህል በጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፤ ከዚህ ኤነርጂ ውስጥ 84% ከባዮማስ፣ 10.4% ከእንስሳት፣ ቀሪው 5.5% ከዘመናዊ ኤነርጂ ማለትም ከኤሌክትሪክ ኤነርጂና ከነዳጅ ዘይት የተገኘ ነው። በዚህ መሠረት የኢትዮጵያ የኤነርጂ አጠቃቀምን ስናይ 95% ባህላዊ የኤነርጂ ምንጮች ከሚባለው በመሆኑ ምን ያህል ለልማት አመች እንዳልሆነ እንገነዘባለን። በሌላ በኩል ከአጠቃላይ የኤነርጂ ፍጆታችን 81.1% ለቤት ውስጥ አገልግሎት ሲውል፣ ለግብርና 6.5%፣ ለትራንስፖርት 6.2%፣ ለኢንዱስትሪ 3.0 % እንዲሁም ለአገለግሎት 3.0% ነው። በዚህ መሠረት ከአጠቃላይ የኤነርጂ ፍጆታችን ለአምራች የኢኮኖሚ ዘርፎች የዋለው ከ20% የማይበልጥ መሆኑን እንገነዘባለን። እንዲሁም ሙሉ ለሙሉ ለዘመናዊ ኤነርጂ ማለትም ለኤሌክትሪክ ማመንጫዎች ግንባታ እንዲሁም ለነዳጅ ዘይት መግዣ የሚሆነውን የውጭ ምንዛሬ የሚያመነጨው ዮግብርናው ክፍለ ኤኮኖሚ ከዚህ ከዘመናዊ ኤነርጂ የሚጠቀመው ፊጽሞ፣ ከቁጥር የማይገባ 0.03% መሆኑን እንገነዘባለን። በእኔ አመለካከት የኢትዮጵያ የኤነርጂ ችግሮች እንግዲህ ከዚህ የተዛባ አጠቃቀም የሚመነጭ ነው ሊባል ይችላል። ይህም ማለት በአንድ በኩል አብዛኛው የኤነርጂ ፍጆታችን በባሕላዊ የኤነርጂ ምንጮች ላይ የተመሠረተ በመሆኑና ይህ የኤነርጂ አጠቃቀም በግብርናው ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ ከፍተኛ መሆን፤ እንዲሁም ለዘመናዊ ኤነርጂ የሚያስፈልገው የውጭ ምንዛሪ ከግብርናው ክፍለ

---

* አቶ መ·ሉ·ጌታ አዳመ· ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሜካኒካል ምህንድስና የመጀመሪያ ዲግሪ፤ ከእንግሊዝ አገር ሬዲንግ ዩኒቨርሲቲ በሪኒወብል ኤነርጂ እና በኤንቫይሮንመንት ሁለተኛ ዲግሪ፣ በማዕድንና ኤነርጂ ሚኒስቴር በተለያዩ የኤነርጂ ፕሮጀክቶች በኃላፊነት፤ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በግል አማካሪነት እያገለገሉ ይገኛሉ።

ኤኮኖሚ የሚገኝ በመሆኑ፤ ይህም በተዘዋዋሪ መንገድ አሁንም ከግብርናው የሚገኝ በመሆኑ፤ በግብርናው ላይ ያለው ጫና በግልጽ ይታያል። በሌላ በኩል ከአጠቃላይ የኤነርጂ አቅርቦታችንና ፍጆታችን ለአምራች ክፍላተ ኤኮኖሚዎች ማለትም ለግብርና፣ ለኢንድስትሪ፣ ለትራንስፖርት እና ለአገልግሎቶች የሚቀርበው የዘመናዊ ኤነርጂ አናሳነት በተለይም ለግብርናው ኢኮኖሚ ጥቅም ላይ የሚውለው የዘመናዊ ኤነርጂ ኢምንትነት የኤነርጂ አጠቃቀማችን የግብርናውን ኤኮኖሚ በሁለት በኩል የሚገዳ መሆኑን እንገነዘባለን። ማለትም ለእድገቱ አስተዋጽዖ ሳያደርግ በክፍለ ኤኮኖሚው ላይ በከፍተኛ ደረጃ ጫና የሚያሳድርና የሚያቀጭጨው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል።ይህን መሠረታዊ ጉዳይ ሰፋ አድርገን እንየው።

ተደጋግሞ እንደተነገረው ከፍተኛው የሀገሪቱ የኤነርጂ ፍጆታ በደን ውጤት፣ የማገዶ ዛፍ፣ የእርሻ ቃርሚያ፣ የከብቶች ፍግ፣ በመሳሰሉት በአጠቃላይ ባዮማስ ኤነርጂ በመባል በሚታወቀው የኤነርጂ ውጤት ላይ የተመሠረተ ነው። ይህ የኤነርጂ ዓይነት ከአጠቃላይ የሀገሪቱ የኤነርጂ ፍላጐት ከ84 በመቶ በላይ የሚሸፍን ነው። ይህ ቢያንስ ሁለት አሉታዊ ተፅኖዎች አሉት። እነዚህም፤

1ኛ/ በየጊዜው ቁጥሩ እየጨመረ የሚሄደውን የሀገሪቱን ህዝብ የቤት መሥሪያ፣ የማገዶ እንጨት እና ሌሎችም ፍላጐት ለሚሟላት ሲባል ያለተመጣጣኝ የዛፍ ተክል የሚነሄደው የደን መጨፍጨፍና መመናመን እንደዚሁም በተጓዳኝ የሚፈጠሩት ጐጂ ተጽዕኖዎች ናቸው። እነዚህም ተጽዕኖዎች እንደሚታወቀው ሁሉ የለም አፈር መታጠብ፣ የመሬት መራቆት፣ የአካባቢ የአየር ጠባይ መለወጥ፣ የበረሃማነት መከሰት መንስኤዎች ለሆነ ይችላሉ። እዚህ ላይ የሌሎችና የማገዶ አጠቃቀም ብቻውን ለደን መመናመን ዋነኛ መንስኤ ነው፤ ማለት አይደለም። በአብዛኛው ለእርሻ ሲባል የሚመነጠር መሬት ለደን መመናመን ዋነኛው ምክንያት ነው። የእርሻ መሬት መስፋፋት ደግሞ የእርሻ ቅሪቶችን ለማገዶነት ወይንም ለቤት ውስጥ ኤነርጂ ለማዋል አመች ሁኔታን ይፈጥራል።

2ኛ/ የእርሻ ቃርሚያን እና የከብቶችን ፍግ በማገዶነት መጠቀም በትግር ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ተመራጭ አይደለም። የእርሻ ቀርሚያና የከብቶች ፍግ ሁላችንም እንደምናውቀው የመሬትን ለምነት በመጨመር ምርታማነትንም ያሳድጋሉ። ይህም ከላይ እንደተነሣው ለእርሻ ሲባል የሚመነጠረውን መሬት ለመቀነስ ያስችላል። አንድ ቆየት ያለ የዓለም ባንክ ጥናት እንዳመለከተው /እ.ኤ.አ. በ1982 ዓ.ም የተደረገ ነው። የእርሻ ቃርሚያንና የከብቶችን ፍግ ለማገዶነት በመጠቀም የተነሣ በ1984 ብር ወደ ግማሽ ቢሊዮን ብር የሚያወጣ የሰብል ምርት እንደታጣ ይጠቅሳል። በቅርቡ "Woody Biomass Project" በሚባለው መሥሪያ ቤት በተጠናው ጥናት በዓመት የእርሻ ቃርሚያንና የከብቶችን ፍግ ለማዳበሪያነት በመጠቀም ፍንታ ለማገዶነት በመጠቀማችን ምክንያት 271,000 ሜትሪክ ቶን ያህል የምርት መቀነስ ያጋጥማል።

3ኛ/ ከላይ እንደተጠቀሰው የባዮማስ ኤነርጂ ከአጠቃላይ የሀገሪቱ ኤነርጂ 84% የሚሸፈን ነው። ይህ ኤነርጂ ሁሉም ማለት ይቻላል ለቤት ውስጥ ማገዶነት የሚያገለግል በመሆኑ

ለግብርና፣ ለኢንዱስትሪ፣ ለትራንስፖርትና ለሌሎች አምራች የኤኮኖሚ ዘርፎች ጥቅም ላይ ሊውል የማይችል ነው። በሌላ በኩል ይህን የባዮማስ ኤነርጂ ሙሉ በሙሉ በነዳጅ ዘይት ለመተካት ቢታሰብ አሁን የምናስገባውን የነዳጅ ዘይት 17 እጥፍ ማለትም 20 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን ነዳጅ ያስፈልጋል። ይህ አሁን ባለው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ፊጽሞ የማይቻል ነው። በተጨማሪም ይህ የሚያመለክተው እንግዲህ በቀላሉ የምናየው የባዮማስ ኤነርጂ፣ የሀገር ምርት ከመሆኑም ሌላ፣ ለተጠቃሚው በአብዛኛው በነጻ ወይንም በቀላል ዋጋ የሚገኝ በመሆኑ አብዛኛውን የኤነርጂ ፍላጐታችንን የሚሸፍን መሆኑን እንገነዘባለን። በተጨማሪም ምንም እንኳን ከባዮማስ ኤነርጂ ወደ ሌሎች ዘመናዊ ኤነርጂ ዓይነቶች ለመሸጋገር ተፈላጊ ሂደት ቢሆንም ከሚጠይቀው ከፍተኛ መዋዕለ-ነዋይ አንጻር ይህ ሽግግር በአጭር ጊዜ ተፈጻሚ ሊሆን እንደማይችል መረዳት ይቻላል።

ያለው አማራጭ ምንድነው? በእኔ ግምት የሚከተሉት አማራጮች ያሉን ይመስለኛል።

1ኛ/ ዘመናዊና አገር በቀል የኤነርጂ ምንጮች፣ ማለትም፤ እንደ ተፈጥሮ ጋዝና የድንጋይ ከሰል ለቤት ውስጥ ማገዶነት ለመጠቀም ከፍተኛ ጥረት መደረግ አለበት። ጥረቱ የተጀመረ መሆኑን እገነዘባለሁ። ይህ ምናልባት በአጭር ጊዜ እስከ 10% የሚሆነውን የባዮማስ ኤነርጂ ፍጆታ በመተካት በረጅም ጊዜም ደግሞ ከ40% - 50% የሚደርሰውን ፍጆታ በመተካት ሊከናወን ይችላል የሚል ግምት አለኝ።

2ኛ/ ከእርሻ ቃርሚያ የሚገኝን ተረፈ ምርት በቀጥታ ለማገዶነት መጠቀም ጨርሶ መቆም ያለበት ጉዳይ ነው። ይህ ታዲያ ሊሆን የሚችለው ለገጠሩ የቤት ውስጥ የኤነርጂ ፍላጐት የሚሆን አማራጭ ማቅረብ ሲቻል ነው። ይህን ፍላጐት ለሚሟላት በእርሻ ማሣ ዙሪያና በጓሮ፣ ሊተከሉ የሚችሉና ለከብት መኖነት ጭምር የሚያገለግሉ በአጭር ጊዜ የሚያርሱና መሬት ውስጥ "Nitrogen" የተባለውን ንጥረ ነገር ሊጨምሩ የሚችሉ የዛፍ ተክሎችን መትከል ዋና አማራጭ ሆኖ፣ ከዚህ በተጨማሪ፣ ለማገዶ ዛፍ ተብሎ ተከልሎ በሚመደብ ቦታ ዛፎችን መትከል ለገጠርና ለገጠር ከተሞች የቤት ውስጥ የኤነርጂ ፍላጐት ሚሟላት ይቻላል።

3ኛ/ ሌላው አማራጭ የባዮጋስ ኤነርጂን ማስፋፋት ነው። የባዮጋስ ኤነርጂ በአብዛኛው የከብቶችን ፍግ በመጠንሰስ የሚገኝ ጋስ ሲሆን ይህ ኤነርጂ ንጹሕና፣ አጠቃቀሙ ምቹ፣ ማለትም በየቤታችን ውስጥ እንደምንጠቀምበት LPG /*Liquefied Petroleum Gas*/ ወይንም በተለምዶ ቡታ ጋዝ ተብሎ እንደሚጠራው አይነት ጋስ ነው /በይዘት ትንሽ ለየት ይላል/። ባዮጋስ ለቤት ውስጥ ማብሰያና ለመብራት አገልግሎት ይውላል። ባዮጋስ ሌላውና ዋናው ጥቅሙ የከብቶች ፍግ ተጠንስሶ የሚገኘው ጋስ ማገዶ ሲሆን ቅሪቱ ደግሞ ተመራጭነት ያለው አካባቢን የማይበክልና ሽታ የሌለው ለመሬት ማዳበሪያነት የሚያገለግል መሆኑ ነው። ስለዚህ የከብቶችን ፍግ በቀጥታ ለማገዶነት ከመጠቀም ይልቅ ወደ ባዮጋስ ለውጦ መጠቀም ሁለት ጠቀሜታዎች አሉት፤ እንደ ማዳበሪያ ሆኖ በማገልገል የመሬትን ለምነት ያሻሽላል። ለማገዶነት በመዋል ለቤት ውስጥ ምግብ

ማብሰያና መብራት ሊውል የሚችል ኤነርጂ ይሰጣል። ይህ ማለት ጥቅሙ በጣም ከፍተኛ ነው፤ ማለት ነው። ሌላው የዚህ ማገዶ ጥምቅ የከብቶችን ፍግ ወደ ባዮጋስ ለመለወጥ የሚያስችለውን መጠንሰሻውን በሀገር ውስጥ ቁሳቁስ፣ በሀገር ልጅ ዕውቀትና ጉልበት መሥራት የሚቻል መሆኑ ነው። ታዲያ ምን ያደርጋል ለአንድ አማካይ ቤተሰብ የሚያስፈልገው የባዮጋስ መጠንሰሻ ከ 7,000 ብር እስከ 10,000 ብር የሚገመት ወጭ የሚያስከትል በመሆኑ ምንም እንኳን አጠቃላይ ኤኮኖሚያዊ ጥቅሙ ሲታይ አዋጭ ቢሆንም የአሥርና የአሥራ አምስት ዓመት የቤት ውስጥ የማገዶ ፍጆታውን ሂሣብ በአንዴና በቅድሚያ እንዲከፍል የሚያስገድድ አማራጭ በመሆኑ፣ ለብዙሃኑ ድሃ የገጠር ኗሪ ኢትዮጵያዊ ቀርቶ ከመካከለኛ ገቢ በታች ላለው ከተማ እንኳን የማይሞከር አማራጭ ሆኗል። በዚህ ምክንያት፤ ከዚህ ግሩም ከሆነ የቤት ውስጥ ማገዶ ልናገኝ የምንችለውን ሁለገብ ጥቅም ሳናገኝ ቀርተናል። ይህን የኤነርጂ ምንጭ ለገጠሩ የቤት ውስጥ ማገዶነት መጠቀም፤

1ኛ/ የእንስሳት ፍግ ለማዳበሪያነት መጠቀም ስለሚያስችል ጥራቱ የጠበቀ፣ መጠኑ የጨመረ፣ ምርት ማምረት ያስችላል። በዚህም ምክንያት ምናልባት ያለብንን የምግብ እህል እጥረት ለሚሚላት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል።

2ኛ/ ንጹሕ አካባቢን የማይበክል፣ የእናቶችንና ሕፃናትን ጤና የማይጐዳ፣ የቤት ውስጥ ማገዶ፣ ማግኘት ስለሚቻል ከጤና ጋር የተያያዙ የቤት ውስጥ ብክላ /Indoor pollutions/ ችግሮችን ያስወግዳል።

በእነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የባዮጋስ ማስፋፊያ ፕሮግራም ነድፎ በሥራ ላይ ማዋል ጠቀሜታው የበዛ ነው ባይ ነኝ። እዚህ ላይ አንድ ትዝብት ላንሳ። ሥራ ላይ በቆየሁባቸው ጊዜያት በሙሉ ለብዙ የተለያዩ ፕሮጀክቶች እጃቸውን ለመዘርጋት የማይቦዝኑት ዕርዳታ ሰጭዎችና አበዳሪዎች አንዳቸው፣ ከሌሎቻቸው ሳይለዩ፣ ባዮጋዝን ለማስፋፋት ሥራ ለመስገስ ወይንም ለማበደር ብዙም ፍላጐት ሲያሳዩ አላየሁም፤ አልሰማሁምም። ይህ ለምን ሆነ? እኔ በበኩሌ እስካለሁበት ምክንያቱ ግልጽ አልሆነልኝም። እዚህ ላይ አንድ ተጨማሪ ነገር ልጥቀስ የማዳበሪያ ኤጀንሲ በሚባለው መሥሪያ ቤት በኩል፣ ከዛሬ 5 ዓመት በፊት ይመስለኛል፣ እስከ 4,000,000 የሚደርሱ የባዮጋስ መጠንሰሻዎች ለማሠራት የሚያስችል ፕሮጀክት ከማዳበሪያ ግኝር ፕሮጀክት ጋር በተጓዳኝ በዓለም ባንክ የገንዘብ ድጋፍ ሊካሄድ ነው፤ የሚል ና ከላይ ካለኩት ጋር የሚቃረን ዜና መሰል ወሬ ስምቼ ነበር። ጉዳዩ አሁን ምን እንደደረስ የሚነግረኝ አላገኘሁም። በበኩሌ የተባሉት መጠንሰሻዎች ስለመገንባታቸው የማውቀው የለም።

ይህን ባሕላዊ የኤነርጂ ምንጭ ላይ የምሰጠውን አስተያየት አቶ በቀለ ባቀረበው ርዕይ ላይ ትንሽ ልሬሬምር እና ላጠቃል። የአቶ በቀለ ርዕይ ባሕላዊ ኤነርጂን በተመለከተ የሚከተለውን በሬሬምር በበኩሌ እመርጣለሁ። አስፈላጊውን የፖሊሲ አቅጣጫ ከተከተልንና የገጠሩ

- የእርሻ ቃርሚያ ለማገዶነት ጥቅም ላይ መዋሉ ቀርቶ ሙሉ ለሙሉ ለመሬት ማዳበሪያነት ይውላል። በዚህም ከኬሚካላዊ ማዳበሪያ ነፃ የሆነ ተጨማሪ የምግብ የእህል ምርት ማምረት ይቻላል።
- የእንስሳትን ፍግ እስከ 6,000,000 በሚደርሱ የባዮጋስ መጠንለሻዎች ወደ ባዮጋዝነት በመለወጥ ንፁሕ፣ ዘመናዊ የባዮጋስ ኤነርጂ በመቀጠም የቤት ውስጥ ማብሰያ ኤነርጂና የመብራት ኤነርጂ ፍላጐቱን የሚያሟላው የሕዝብ ቁጥር ወደ 30,000,000 ወይንም በጊዜው በገጠራቱ ኢትዮጵያ ይኖራል ተብሎ ከሚገመተው ከ40% በላይ ይሆናል።
- ቀሪው 60% የገጠሩ ኗሪ ለማገዶና ለእንስሳት መኖ ብሎ በማሳው ዙሪያ ወይንም በጓሮው ከሚተክለው ፈጣን ውጤት ከሚሰጠው የዛፍ ተክል እና ለማገዶ ተክል በተከለለ ቦታ ከተተከለ ማገዶ ሙሉ በሙሉ የቤት ውስጥ ኤነርጂ ፍላጐቱን የሚያሟላ ይሆናል።
- በከተሞች አካባቢ የሚኖሩ ከመካከለኛ ገቢ በታች ኑሮ ያላቸው ቤተሰቦች ከማገዶ ተክልና ከደን ውጤቶች እንዲሁም ከድንጋይ ከሰል የሚዘጋጅ የቤት ውስጥ ኤነርጂ ፍላጐታቸውን ሙሉ ለሙሉ ያሟላሉ።

ዘመናዊ የኤነርጂ ምንጮች ልማት

በኢትዮጵያ ሁኔታ ዘመናዊ ኤነርጂ ስንል የነዳጅ ዘይትንና የኤሌክትሪክ ኤነርጂን ማለታችን መሆኑ ግልጽ ነው። በጹሑፍ ውስጥ እንደተገለጸው በ2020 የኢትዮጵያ ኤኮኖሚ ዕድገት ተፋጥኖ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ ከ1600 ብር በላይ ሊደርስ ይችላል በሚል ስሌት አሁን ካለው 653 ሜጋዋት የኃይል ማመንጫ በ2020 ወደ 8615 ሜጋዋት ሊደርስ ይገባል የሚል ሃሳብ ቀርቧል። ይህም ማለት 8000 ሜጋዋት አቅም ያላቸው ተጨማሪ የኃይል ማመንጫዎች በሚቀጥሉት 23 ዓመታት መገንባት ያስፈልጋል ማለት ነው። በአለፉት 40 ዓመታት የገነባናቸው የኃይል ማመንጫዎች አቅም 800 ሜጋዋት አልሞላም። ከዚህ ስንነሳ 8000 ሜጋዋት የማመንጨት አቅም ያላቸው ተጨማሪ የኃይል ማመንጫዎችን ለመገንባት አሳን ሞልቶ አይቻልም ባይባልም፣ ይቻላል የሚለው ሁኔታ ግን በጣም አጠራጣሪ ነው። በተመሰነ ደረጃ ይህን ርዕይ ተግባራዊ እናድርግ ብንል እጅግ ከፍተኛ መዋዕለ-ነዋይና ከፍተኛ የተቀናጀ ጥረት ያስፈልጋል።

8000 ሜጋዋት ለማመንጨት የሚጠይቀው መዋለ ንዋይ ወደ 180 ቢሊዮን ብር የሚጠጋ ነው። ይህ በብዙው የኃይል አመንጭና አከፋፋይ ኩባንያ በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኮርፖሬሽን ብቻ የሚቻል ስላልሆነ ይህን ጥረት እንዲያግዙ የውጭ ኢንቬስተሮች መሳብ አለባቸው። እነዚህን ኢንቬስተሮች ለመሳብ ደግሞ ብዙ መሥራት ያስፈልጋል። ለምሳሌ፤

- የኤሌክትሪክ ታሪፍ ማሻሻል፣
- የብሔራዊ የኤሌክትሪክ ማስተላለፊያ ግሪድ አጠቃቀምና ክፍያ መወሰን
- የፍላጐት መፈጠር አይቀሬነት መረጋገጥ አለበት።
- የፍላጐት አስተማማኝነትና ዘላቂነትም ወሳኝነት አለው።

ከዚህ በተጨማሪ አሁን ያሉት የኃይል ማመንጫዎች በጽሑፉ እንደተገለጸው ከ94% በላይ በውሃ ኃይል የሚሠሩ ናቸው። ያለን ምቹ የኃይል ማመንጫ ሃብት የውሃ ኃይል በመሆኑ ወደፊት ይገነባሉ ተብለው የሚታሰቡት የኃይል ማመንጫዎች በአመዛኙ ከውሃ ኃይል መሆኑ አይቀሬ ነው። ስለዚህ 80% እንኳን ከውሃ ኃይል ይመነጫል ብለን ብናስብ ወደ 6400 ሜጋዋት የሚያመነጩ የኃይል ማመንጫዎች በውሃ ላይ መመሥረት ይኖርባቸዋል። እንደሚታወቀው የአንድ በውሃ ኃይል ላይ የተመሠረት የኃይል ማመንጫ ከዕቅድ እስከ ግንባታ ከአሥር ዓመታት ያላነስ ጊዜ ይፈጃል። በጽሑፉ እንደተገለፀው በዕቅድ ደረጃ ሊያዙ የሚችሉ የኃይል ማመንጫዎች በአጠቃላይ ከ2500 ሜጋዋት አይበልጥም። ቀሪውን 4000 ሜጋዋት የኃይል ማመንጫ ለማቀድና ሁሉንም የኃይል ማመንጫዎች ከዲዛይን እስከ ግንባታ ለማከናወን ከፍተኛ የዕቅድ፣ የማስተባበር፣ የማቀናጀት፣ ለኢንቬስተሮች ምቹ ሁኔታ የመፍጠር፣ የስልጠና ፕሮግራሞችን ማካሄድ እና የመሳሰሉ በርካታ ሥራዎችን መሥራት እንደሚያስፈልግ እንገነዘባለን። ማነው ይህን ሥራ የሚሠራው? የሚለው ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም።

ይህ የሚታሰበው ርዕይ 2020 በኢትዮጵያ ዕውን እንዲሆን ካስፈለገ ኤነርጂ በተለይም ዘመናዊ ኤነርጂ ለሌሎች ክፍላተ-ኤኮኖሚዎች የሚያበረክተውን ወሳኝ አስተዋጽዖ እንዲያበረክትና የኤነርጂ እጥረት ለሌሎች የኤኮኖሚ ዘርፎች እንቅፋት እንዳይሆን ከፍላጐት ትንቢያ ተነስቶ አጠቃላይ የኤነርጂ ልማት ዕቅድ የሚነድፍ ተቋም አስፈላጊነቱ ግልጽ ነው። በመጨረሻም፣

አቶ በቀለ ኤነርጂና ፖለቲካ በሚለው ክፍል ውስጥ ካነሳቸው ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትንሽ ልጨምር፤ ኢትዮጵያ የዚህን ፖለቲካ ተዕጽኖ ለመቋቋም ያላት እድል ፊጽሞ ዝግ አይመስለኝም። ለምሳሌ፤

- ❖ የድንጋይ ከሰል ልማት ማካሄድ /200 ሚሊዮን ሜትር ኩብ/
- ❖ የተፈጥሮ ጋዝ ልማት ማካሄድ /100 ቢሊዮን ሜትር ኩብ/
- ❖ በኦጋዴን፣ በጋምቤላ፣ በአባይ ሸለቆ፣ አካባቢ ሊኖር ይችላል ተብሎ የሚገመተውን የነዳጅ ዘይት መፈለግና ማልማት
- ❖ እንዲሁም በቅርቡ እንደ ተገለፀው በባሌ አካባቢ ይኖራል ተብሎ የተገመተውን የዩራኒየም ፍለጋና ልማት የማካሄድ ዕድል እንዳለን የታወቀ ነውና፣ በዚህ ልማት ላይ ለማተኮርና ለመረባረብ መሞከር፤ ምናልባት በ2020 ሲቻል ሙሉ ለሙሉ፣ አለበለዚያም በከፊል በነዳጅ ዘይት ምክንያት ሊመጣ የሚችልን እየከረረ የሚሄድ ተፅዕኖ ለመቋቋም ያስችለናል የሚል ግምት አለኝ።

ከዚህ በተጨማሪ አሁን ዓለም የያዘው አቅጣጫ፣ የነዳጅ ዘይትን መሟጠጥ አይቀሬነትን በመገንዘብ፣ ነዳጅ ዘይትን የሚተኩ አማራጭ የኤነርጂ ምንጮችን ማፈላለግ ላይ ነው።

- ከእነዚህ አንዱ የነዳጅ ዘይትን አማራጭ ለመተካት ለምሳሌ፤ ፊውል ሴልስ - ሃይድሮጅን እንዲሁም የኤሌክትሪክ ኤነርጂን ለመኪኖች ማንቀሳቀሻነት ማዋል ነው።
- በተጨማሪም፤ እንደ ነፋስ ኃይል፣ የፀሐይ ኃይል፣ የመሳሰሉትን በስፋት በጥቅም ላይ በማዋል ተንቀሳቃሽ ላልሆኑት የኤነርጂ አቅርቦቶች ማለትም - ለከተማም ሆነ ለገጠር የኤሌክትሪክ መብራት ለመስጠት፣ ለወፍጮ፣ ለውሃ መሣቢያ ሞተሮች፣ ለመሳሰሉት ለማዋል ይቻላል። በተለይ ይህን የነፋስ ኃይልን በተመለከተ የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ኃይል ኮርፖሬሽን እስከ 6 ሚጋዋት የኃይል ማመንጫ ለመገንባት በጥናት ላይ እንዳለ ለመገንዘብ ችያለሁ።

ኤነርጂ እና ልማት በኢትዮጵያ

ኃይለልዑል ጠብቂ*

መግቢያ

ይህን አድማሰ - ሰፊና ጥልቅ የኤነርጂ ጥናት በማለፊያ አማርኛ ያቀረበውን አቶ በቀለንም በአድናቆት ጭምር አመሰግናለሁ። በአማርኛ ስለኤነርጂ እንዲህ ያለ ጥናት ማቅረብ መቻሉን በጣም እጠራጠር ነበር። እድሜ ለአቶ በቀለ እንደሚቻል ዛሬ አምኛለሁ። እሱ በተለመው ፈር ሌሎች የኤነርጂ ልማት አጥኚዎችና ተመራማሪዎች ወደፊት በተመጣጣኝ ጥራትና ጥልቀት የሚያብራሩልንን፣ የሚያስረዱንን የኤነርጂና ልማት ትስስር ቁም ነገሮች ለማንበብና ለመስማት ፅኑ ተስፋ አለኝ።

አስተያየቴን የማቀርበው በአራት አርእስት ነው። ዓላማዬም የቀረበልንን ፅሁፍ ለመተቸት ሳይሆን በኤነርጂና ልማት ትስስር የጐን ብርሃን (side light) በመፈንጠቅ ያለንን ግንዛቤ ለማበልፀግ የሚል ተስፋ ነው።

በመጀመሪያ ስለ አገራችን ደን ሀብት መራቆት ዋና ምክንያት፣ ቀጥሎ ለልማትና ኤነርጂ ትስስር የሰውና የለማዳ እንሰሳቱ ኤነርጂ በአገራችን ያላቸውን ቀዳሚና መሠረታዊ ሚና፣ በሶስተኛ ተራ ከቅሪት አካል (fossil fuels) ነዳጅ ማዕድናት የሚገኘውን ጥቅምና መዘዝ፣ በአራተኛ ተራ ደግሞ በኤነርጂ አቅርቦትና ፍጆታ ብክነትን ማመንመን ለልማት የሚኖረውን መሠረታዊ ሚና መዳሰስ ነው።

ለደን ሀብት መራቆት ዋና ምክንያት

በድሮ ዘመናት የሀገራቱን የቆዳ ስፋት 40% አልብሶ የነበረው የደን ሀብት እየተመናመነ ወደ 2.8% ወርዷል። «ለዚህም መራቆት ግንባር ቀደም ዋና ምክንያት የደኑ ዛፍ እየተቆረጠ በእንጨት ማገዶና በከሰል ማገዶነት በየቤቱ መንደዱ ነው» የሚለው ለአስርተ ዓመታት ከየአቅጣጫው ምሁራን ሲያስተጋበት የኖረው ይህ ድምዳሜ በዛሬ የወይይታችን ዕሁፍ ተደግሟል። በጉዳዩ የጠራ ምርምር ተካሄዶ ይህ ድምዳሜ ነጥሮ ወጥቶ እንደሆነ ግን አላወቅም።

ነገር ግን ድሮ የደን ሀብት 40% የሃገራችንን ቆዳ ስፋት አልብሶ በነበረ ጊዜ እንኳ ዛፍ ከደን ለማገዶ ብቻ ይቆረጥ ነበር ወይ? ለማገዶ የሚቆርጠውስ የትኛው የህብረተሰብና የቤተሰብ ክፍል ነው? በባህላችን ከጥንት ጀምሮ የቤተሰቡን የዕለት ምግብ ማብሰል ከዋና ዕለታዊ ተግባራቸው አንዱ በመሆኑ «እንጨት ሰበራ» «ጭራሮ ለቀማ» (ያውም ደረቁ በአቅራቢያቸው ከተገኘ) ወዘተ... የሚንከራተቱት ሴቶች ናቸው። እርጥብም ሆነ ደረቅ ዛፍ ቆርጦ ለመጣል፣ ለመፍለጥና እንዲሸከሙት ለመቆራረጥ ግን መሣሪያ፣ አቅምና ጊዜ ሴቶች ያንሳቸዋል። እርጥብ እንጨት ከሆነም ለሽክም ከባድ ነው። ቤት ሲደርስም ተማግዶ በዋዛ አይነድም። ስለዚህ የቤተሰቡን ምሳና እራት ምግብ ቶሎ አያበስልም!

በእነዚህና ሌሎች ምክንያቶች የማገዶ እንጨትና ከሰል የደን ሀብት ግንባር ቀደምና ዋና ጠር መሆኑን ለማመን ያስቸግራል። ከጠቅላላ ቁጥራችን 80% የሆነው የገጠሬ ህዝብ መኖሪያ ቤቶች አሁንም አንደድሮው የሚሠሩት በአመዛኙ ከዛፍ ተዋፅኦ ነው። ለምሶሶና ግድግዳቸው፣ ለጣሪያቸው፣ ለበር፣ ለመስኮት፣ ሁነኛ ዛፍ ከደንም ሆነ ከሌላ ተቆርጦ ነው። የትናንሽ ከተሞች መኖሪያ ቤቶችና በትልልቅ ከተሞች መለስተኛ ገቢ ያላቸው ቤተሰቦች መኖሪያ፣ ከቆርቆሮ ጣሪያና ከአራት ማዕዘን ቅርፃቸው በቀር አሠራራቸው ከገጠር ቤቶች የተለየ አይደለም። ባህላዊ የቤት ዕቃዎች እንደ አልጋ፣ መቀጫ፣ በርጩማ፣ ገበቴ፣ የመሳሳሉት ከዛፍ እንጨት ነው የሚሠሩት። ለግብርና መሣሪያዎች እንደማረሻ፣ ድግር፣ ሞፈርና ቀንበር፣ መጥረቢያ፣ ወዘተ...፣ ተስማሚ የዛፍ እንጨት ያሻል። ለነዚህ ጉዳዮች የዛፍ እንጨት ቆራጮቹ ወንዶች ናቸው። ከተቆረጠው ዛፍ የተረፈ ቀጫጭን ቁርጥራጭና ቅጠላ ቅጠል ለማገዶ ይጋዝ ይሆናል።

በየሚኖሩበት ቀዬ የህዝብ ቁጥር እያደገና የእርሻ ማሳ ምርት ከዓመት ዓመት ሲመነምን ባጠገባቸው ሆነ ከሌላ ሩቅም ቢሆን ወደ ደን ለበስ ለም መሬቶች መፍለስ ጥንትም እንደ ዛሬ ገበሬው ህዝብ ዘንድ የተለመደ ነው። በበጋ ወራት ሲፈልሱ ገበሬዎች ደኑን ዛፍ ለመጣልና ቆራርጦ ከማሳ አውጥቶ ክረምት እስኪገባ አርሶ ለማዘጋጀት አቅም ስለሚያንሳቸው ጊዜውም ስለማይበቃ፣ ደኑን ለመመንጠር ዛፎችን በእሳት ማቃጠል የተለመደ ነው። ያልነደደ ጉቶውም ይነቀላል። በደኑ ዛፍ አመድ ጭምር ከዳበረው ሰፋፊ ማሳ በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የተትረፈረፈ ምርት ያገባሉ። በተመሳሳይ ለምሳሌ ብራዚል አማዞን ጫካ በሰደድ እሳት የሚመነጥሩት መሬቱን ለርሻና ለከብት ግጦሽ የሚፈልጉት ሰዎች እንደሆኑ ከዜና አውታሮች እንረዳለን። ባጠቃላይ እያደገ ለሚሄድ ህዝብ ቁጥር በቂ ምግብ ለማምረት ደኖች እየተመነጠሩ መመናመናቸው በየአህጉራቱ የተከሰተ መሆኑ በታሪክ የተመዘገበና በምርምር የተጠና ኩነት ነው።

ለቤት መሥሪያና ለቤት ዕቃ፣ ለግብርና መሣሪያዎች፣ ወዘተ... ወይንም ለማገዶ እንጨትና ከሰል እንኳ ዛፍ ወይም ቅርንጫፍ ሲቆረጥ መልሶ ያቆጠቁጥና ያድጋል። ነገር ግን ለእርሻ መሬት ዛፍ በእሳት ሲመነጠርና ጉቶው ተነቅሎ መሬቱ ሲታረስ በስፍራው ከተዘራው እህል በቀር ዛፍ፣ ወዘተ... አይበቅልም። ቢበቅል እንኳ ሳያድግ ይነቀላል።

የህዝብ ቁጥር 3% በዓመት በሚያድግበት አገር የህዝቡ ቁጥር በ የ23 ዓመቱ እጥፍ ይደርሳል። በባህላዊ የግብርና መሣሪያና ሥርዓት እስከታረሰ ድረስ ግን ለተጨማሪው ህዝብ ምግብ ለማምረት ደን እየተመነጠረ የእርሻ መሬቶች ቆዳ ስፋት እጥፍ መሆን ይኖርበታል።

በድርቅ ዓመታት የደን ዛፍ ቅጠሎች ይደርቁና የፀሐይ ጨረርና የአየሩ ግለት የሚለኩሱት ሰደድ እሳት ለደኑ መመናመን የበኩሉን አስተዋፅኦ ያደርጋል። በተለይም በአቅራቢያው ማሳው የመከነበት የተራበ ገበሬ ይህ ቢያጋጥመው ሰደድ እሳት የጀመረለትን ምንጠራ ይጨርስና ደን የነበረውን ስፍራ አርሶ ይዘራዋል።

በነዚህና ሌሎች ምክንያቶች ለሃገራችን ደን መራቆት ግንባር ቀደሙ ዋናው ምክንያት በየቤቱ ለባህላዊ ምድጃ የሚቆረጠው ዛፍ ብቻ አለመሆኑን ልንገነዘብ እንገደዳለን። ከተቻለ እያንዳንዱ ከላይ የተጠቀሱና ሌሎች ምክንያቶች ለደን መራቆት በየበኩላቸው የሚያደርጉት ድርሻ በምርምርና በጥናት ነጥሮ ሊጣራ ይገባል። ይህ ካልሆነ የቤት ማገዶ ነው ደንን ያራቆተ

በሚል መሠረት ይህን ጥሩት ለመግታትና ለመቀልበስ የማይፈይዱ እርምጃዎች ውሎ አድሮ የደንን መራቆት ለመግታት እምብዛም ያልጠቀሙ መሆናቸውን ብዙ ጊዜና ልፋት ካፈሰስን በኋላ በዐዕት ለመገንዘብ እንገደዳለን።

በየቤቱ ምግብ ለማብሰልና ለሌላም ከባህላዊ ምድጃ የማገዶ ኤኔርጂ ይዘት 90% በላይ የሚባክነውን ለመቆጠብ በአገራችን በተካሄደ ምርምርና ስርፀት ተገኝተው የተሠሩ የተሻሻሉ ምድጃዎች ሥርጭት ውሱን መሆኑ በቀረበልን ጥናት ተጠቅሷል። የነዚህ የተሻሻሉ የማገዶ ምድጃዎች ሥርጭት ግን ከከተሜ ቤተሰቦች (ያውም ከፊሉ) ወደ 80% ህዝብ ወደማያንርባቸው ገጠር አካባቢዎች ገና አልዘለቀም።

የተሻሻሉት የማገዶ ብክነት ቆጣቢ ምድጃዎች በአገር አቀፍ ደረጃ ቢሰራጩ ግን በተለይ ለገጠሬ የቤት እመቤቶች ሁለት ጥቅሞች ያስገኙ ነበር።

1. ለአባካኙ ባለሶስት ጉልቻ ምድጃ ማገዶ ፍለጋ ወትሮ የሚያውሉት ጊዜና የሚደርስባቸው አካይድ ድካም በተቆጠበው ማገዶ መጠን ይቀንሳል።
2. በአባካኙ ምድጃ ሲቀቅሉ እናቶችና ካጠገባቸው የማይለዩት ህፃናት በማገዶ ጢስ የሚደርስባቸው ከፍተኛ የጤና ጠንቅና ጉዳት ይቀርላቸዋል።

እነዚህ የማገዶ ብክነት ቆጣቢ ምድጃዎች የሚያስገኙት ሁለት ጥቅሞች ለደን መራቆት መቀነስ ከሚያስገኙት አናሳ ጥቅም ተዳምሮ ምድጃዎቹ በአገራችን ገጠር በሙሉ እንዲዳርሱ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ፕሮግራም ነው።

በአገራችን የሰውና የእንሰሳት ጡንቻዎች ኤኔርጂ ግብአት ለልማት ያለው ግንባር ቀደምና መሠረታዊ ሚና

ከሰውና ከዜት እንሰሳቱ ጡንቻ ለሥራ ስለሚገኘው (animate) ኤኔርጂ ግብአት ዛሬ ከቀረበልን ጥናት እንደምንረዳው በሰውና በእንሰሳት ጉልበት ብቻ ለሚከናወነው «የአገራችን እርሻና የገጠሩ መንገባ የሰውና የእንሰሳቱ ቁጥር እየበዛ ቢሆንም በድርቅና በምግብ ራስን አለመቻል የተነሳ ሰውና እንሰሳቱ በቂ ምግብ እስካላገኙ የኤኔርጂ ግብአቱ ጨምሯል ማለት አይቻልም»።

ጡንቻዎች ለሥራ ኤኔርጂ የሚያበረክቱት፣ ሰውና እንሰሳቱ ከሚመገቡት ምግብና መኖ አካላቸው በሚያነጥረው ኤነርጂ በመሆኑ የግብአቱ መጠን ምን ያህል ይገመታል? አንድ አካለ መሉ ሰው ይዘቱ 2400 ኪሎ ካሎሪ ኤኔርጂ ያለው የተመጣጠነ ምግብ በየዕለቱ እንደሚያስፈልገው በኢንተርናሽናል ደረጃ ተመድቧል። ከዚህ ምግብ ኤኔርጂ 80% ውን የሚጠቀመበት/የሚፈጭት የሰውየው ሳምባ፣ ልብ፣ ጨንራና አንጀት፣ ኩላሊት፣ አንጐል፣ ወዘተ...፣ ያሉ ክፍለ አካላቱ ናቸው። ኤነርጂውን የሚጠቀመበትም የሰውየው ገላ በጤናማ ህይወት ሁኔታ እንዲጠበቅ ሰርክ 24 ሰዓት ያለማቋረጥ ለሚያከናውኑት ተግባሮቻቸው ነው። ስለዚህ ከጠቅላላው 2400 ኪሎ ካሎሪ ጡንቻዎች ከገላ ውጭ ለሚያደርገት እንቅስቃሴ ሁሉ የሚተርፈው 20% ወይም 480 ኪሎ ካሎሪ በቀን ነው። ይህን ኤኔርጂ ድርሻቸውን ጡንቻዎች የሚጠቀመበት ለሥራ ብቻ ሳይሆን ለማንኛውም አካላዊ እንቅስቃሴ

(ለመገናኛም ጭምር) እንደሆነ ልብ እንበል:: ይህ የ480 ኪሎ ካሎሪ ለምሳሌ የ138 ግራም ደረቅ እንጨት ወይም የ74 ግራም ከሰል ወይም የ46 ግራም (50 ሲ.ሲ) ነጭ ጋዝ ላምባ ወይም የ45 ሲ.ሲ ቤንዚን ተመጣጣኝ ኤኔርጂ ይዘት ነው::

ስለዚህም ለሰውየው ጠንቻምች ጉልበት ሥራ በቀን የሚተርፈው የኤኔርጂ ድርሻ ለሌላ እንቅስቃሴ በዋለው መጠን ይቀንሳል:: ነገር ግን 480 ኪሎ ካሎሪ ሙሉ ለሙሉ ለምርት ሥራ ይዋል ቢባል እንኳ: አንድ ገበገ ገበሬ 300 ቀን በዓመት ጠንክሮ ቢሠራ ለሥራው የሚያውለው የ13.5 ኪሎ ግራም ማለትም 15 ሊትር ቤንዚን ተመጣጣኝ ኤኔርጂ ብቻ ነው::

የእርሻ በሬዎችና የጋማ ከብቶች የሰውን ጉልበት ሥራ ለማገዝ የሚያበረክቱት ኤኔርጂ ግብአት መጠን ከሰው ጠንቻ ከ 5 እስከ 8 እጥፍ አይበልጥም::

ነገር ግን ከሰውና ከእንስሳቱ ጠንቻ ለስራ ከሚቀርበው የኤኔርጂ ግብአት አናሳ መጠን አንባር ለአገራችን ኤኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ከሰዎች ጉልበት በጠቅላላው በየዓመቱ የሚደረገውን አስተዋፅኦ መናቅ ስተት ይሆናል:: በ1986 (እ.ኤ.አ) የኢትዮጵያን ኤነርጂ ዘርፍ በ41 ጥራዝ በስፋትና በጥልቀት በዳሰሰው ብሔራዊ የኤኔርጂ ኮሚቴ ያወጣው ጥናት[14] ስለዚህ ጉዳይ የሚከተለው ተገልጧል:: ለኤኮኖሚና ማህበራዊ ተግባሮች ሁሉ በ1984 ዓመት አገሪቱ ከተጠቀመችበት ጠቅላላ ኤኔርጂ አቅርቦት 9.1% የሰውና የእንስሳት ጉልበት ነው:: ይህ በዚህ ዓመት ከነዳጅ ዘይት የቀረበውን ድርሻ ሁለት እጥፍ፣ ከኤሌክትሪክ የቀረበውን 15 እጥፍ ነው:: በዓመቱ ባህላዊ ግብርና ተግባሮችን ለማከናወን ገበሬዎችና ቤተሰቦቻቸው ያቀረቡት ኤኔርጂ ግብአት ከአካል ውጭ (non-animate) ማለትም ከነዳጅና ከኤሌትሪክ ምንጮች ጠቅላላ የቀረበውን ሶስት እጥፍ የበልጣል:: ለባህላዊ ግብርና ከሰዎች ጉልበት ብቻ የቀረበው የ700.000 ቶን እህል ኤኔርጂ ይዘት ተመጣጣኝ እንደሆነ የኮሚቴው ሪፖርት ገልጧል:: የዚህ ሰባት ሚሊዮን ኩንታል እህል ኤኔርጂ ይዘት 2.3422 ቢሊዮን ኪሎ ካሎሪ ወይንም 234200 ቶን ነዳጅ ዘይት ኤኔርጂ ይዘት ነው::

አንድ ተጨማሪ ንፅፅር ከጥናቱ እንመልከት:: በኢትዮጵያ በ 1984 ዓመት በጠቅላላ በመንገድና በባቡር ከተጋዘው ጭነት ቶን ኪሎ ሜትር 10 እጥፍ የሚበልጥ በኢትዮጵያ ገጠር በሰዎች ሽክምና በጋማ ከብት ተግዞ ነበር:: ዛሬ ከ 20 ዓመት በኋላ በዚህ ረገድ የተደረገ መሻሻል እንዳለ ቢጠና ውጤቱ አዎንታዊ የሰው ድካም ተቃልሏል የሚል ይሆን? እንጃ !

ያገራችን ኢኮኖሚ መሠረትና ምሰሶ የሆነው ግብርናው ዘርፍ የሚላወሰው በገበሬዎችና የሥራ ከብቶቻቸው ጠንቻ ኤነርጂ ግብአት በመሆኑ ይህ ግብአት ለልማት ግንባር ቀደም ሚና እንዳለው ግልጥ ነው:: ባለፉት የ25 ዓመታት የአገራችን ልማት ፖሊሲ የግብርና መር ኢንዲስትሪ ልማት ነው ሲባል ቆይቷል:: ይህም ከግብርና ዘርፍ ትርፍ ምርት በሚጠራቀም ጥሪት አያሌ ኢንዱስትሪዎች እየተገነቡ በሂደት የኤኮኖሚውን መሪነት የኢንዱስትሪው ዘርፍ ይረከባል ማለት ነው:: በቀረበልን ጥናትና ከላይ እንደተመለከትነው ግን ግብርና እንዲሁም ለገበሬው ለምርትና ለኑሮ ተግባሮቹ ማከናወኛ ያሉት ኤኔርጂ ግብአት ከአካሉና ከእንስሳት ጠንቻዎች ብቻ ነው:: ይህ ጥናት በአፅንኦት ያስረዳው በተደጋጋሚ ድርቅና በምግብ (እና

[14] Ministry of Mines and Energy, ETHIOPIAN NATIONAL ENERGY COMMITTEE and CESEN-ANSALDO/FINECANICA, 1986 "Energy in Ethiopia: A Comprehensive Study" Addis Ababa

መኖ) እራስን አለመቻል የተነሳ በያመቱ ለገጠሩ የኤኔርጂ ግብአት ሊጨምር አልቻለም። በእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ ለግብርና መር ኢንዱስትሪ ልማት የምናውለው አስተማማኝ ጥሪት ከግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ መቼ ይተርፈን ይሆን?

ከነዳጅ ማዕድናት ኤኔርጂ ግብአት የሚገኘው ጥቅምና አጃቢው መዘዝ

በዘመናችን የተትረፈረፈ ምርትና ልማት ባለቤት የሆኑት የበለፀጉ አገሮች በገፍ የተጠቀሙበት ኤኔርጂ ግብአት ለሚሊዮኖች ዓመታት በየአህጉሩ በአንዳንድ ሥፍራዎች ከርስ ምድር ውስጥ ተቋጥረው ከቆዩን ተፈጥሮ - ሰጥ ነዳጅ ማዕድናት ቅርሶች ነው። እነዚህ ክምችቶች እንደ ድንጋይ ከሰል፣ እንደ ነዳጅና ዘይት፣ እንዲሁም እንደተፈጥሮ ጋዝ፣ ያሉ ናቸው። ማንኛውም ኤኔርጂ ማዕድን ከተከማቸበት አውጥቶ፣ ውስጡ የተቋጠረውን ኤኔርጂ ማላቀቅ፣ ማዕድኑ በተገቢው ቴክኖሎጂ/ዘዴ አማካይነት በአየር ኦክሲጂን መንደድ አለበት። ከማዕድኑ የተለቀቀው ኤኔርጂ በሌላ ተስማሚ ቴክኖሎጂ አማካይነት ለምርት (ግብርና ወይም ኢንዲስትሪ፣ ወዘተ...) ወይም ለአገልግሎት (ትራንስፖርት፣ መብራት፣ ወዘተ...)፣ ለመሳሰሉት ይውላል። ይህ ከነዳጅ ማዕድኑ ኤኔርጂ የምናገኘው ጥቅም ነው።

ግን ይህን ጥቅም አጅበውና ተጣምረው ከባድ መዘዞች የሚያስከትሉ የማዕድኑ ቅሪቶችም ይከሰታሉ። ከነዚህም ቅሪቶች ዋናዎቹ አመድና በዓይን የማይታዩ ጋዞች እንደካርቦን ዳይአክሳይድ፡ የማይታይ የውሃ እንፋሎትና ጥቂት ሌሎች ናቸው። አመዱ በተመደበለት ስፍራ ይደፋል። ሌሎቹ ግን ማዕድኑ ከተማገደበት ቴክኖሎጂ ጢስ መውጫ (chimney or exhaust pipe) ወደ አከባቢው አየር ይለቀቃሉ።

ከአካባቢው አየር ውስጥ እየተደባለቁ በጣም ካልተበረዙ እነዚህ ቅሪት ጋዞች በአቅራቢያው ላሉ ሰዎች፣ እንሰሳትና እፅዋት ጤና እጅግ አደገኛ ናቸው (እንደ ትምባሆ ጢስ ማለት ነው)። ተበርዘውም ቢሆን ለረጅም ጊዜ የአየርና እነዚህን ቅይጥ የሚተነፍሱ ሰዎች፣ እንሰሳቱና እፀዋቱ ለአስጊ በሽታዎች (እንደ ካንሰርና ሌሎችም) ይዳረጋሉ። ከጋዞቹ አንዳንዱ በአየር እርጥበት ከሚሙ አሲድ ስለሚሆኑ - የጣሪያ ቆርቆሮ ያዝጋሉ። የድንጋይ ሃውልት ገፅ ያበልዛሉ፣ ያሟሟሉ። ለምሳሌ፤ የአክሱም ሀውልት ሮም አደባባይ ተተክሎ በቆየበት አሥርተ ዓመታት፣ እና የአቴንስ አክሮፖሊስ ጥርብ ድንጋዮች ላይ፣ የደረሰውን ጉዳት ልብ ይሏል! እነዚህ ጉዳቶችና ጠንቆች ነዳጅ ማዕድኑ በሚማገድበት ሥፍራ አቅራቢያ የማዕድኑ ቅሪቶች የሚያስከትሉዋቸው ጉልህ የጤና ጠንቆችና በንብረት ላይ የሚያደርሱት ጉዳቶች ናቸው።

ቀጥሎ እነዚሁ ቅሪቶች በምድር አቀፍ (world wide/global) ደረጃ የሚያስከትሉትን ጉዳት እንመልከት። የነዳጅ ማዕድኑን ኤኔርጂ መልቀቅ አጅቦ ወደ አየር ከሚወጡት የጋዝ ቅሪቶች ካርቦን ዳይአክሳይድ ዋናው ነው። ከአካባቢው አየር የተደባለቀው ካርቦን-ዳይአክሳይድ በምድር ዙሪያ አትሞስፌር (global atmosphere) ውስጥ በተፈጥሮ ያለው መጠኑ አናሳ ካርቦን-ዳይአክሳይድ ክምችት (%) በትንሹ ያሳድጋል። የአትሞስፌር ካርቦን-ዳይአክሳይድ ክምችት አንዱ ባህርይ ምድራችን በፀሐይ ጨረር ከሚደርሳት መቀት አነስተኛ ድርሻ ወደ ህዋው ተመልሶ እንዳይወጣ አፍኖ ማስቀረት ነው። ይህ ባህሪ ያላቸው ካርቦን-ዳይአክሳይድ እና መጠናቸው ግን እጅግ አናሳ የሆኑ እንደ ሚቴን (methane) ያሉ ከነዳጅ ማዕድናት ጋር

የተከማቹና አንዳንድ ሌሎች ለአ-ሠራሽ ጋዞች ግሪን-ሐውስ ጋስስ (greenhouse gases) በመባል ይታወቃሉ::

በኢንዱስትሪ የበለጸገ አገሮች ባለፉት 150 ዓመታት የነዳጅ ማዕድናት ኤነርጂ ተጠቅመው በለሙና በበለጸገበት ሂደት ወደ አትሞስፌር የተለቀቁት የካርቦን-ዳይኦክሳይድና ሌሎች ግሪን ሀውስ ጋዞች እየናሩ ቀስ በቀስ የምድር መጋል (global warming) ተከስቷል፣ እየተባባሰም ነው:: የምድር መጋል የአየርን ነባር ባህሪ (climate) በየቦታው እያናጋ የተለያዩ ጉዳቶች ተከስተዋል:: በአንድ ሥፍራ ድርቅ የሚከሰትባቸው ዓመታት ተደጋጋሚነት እየተቀራረበ ይመጣል:: ለምሳሌ፤ ይህ በአገራችን እየታየ ነው:: ሌላ ሥፍራ ጐርፍና የመሬት መጥለቅለቅ ቶሎ ቶሎ ይከሰታሉ:: ይህም በአውሮፓ፣ በአሜሪካና፣ በእስያ እንዲሁም በሞዛቢክ ባለፉት ጥቂት አመታት ተከስቷል::

በአጭሩ የምድር መጋል አያሌ የኤኮኖሚና ማህበራዊ ጉዳትና ጥፋት በየክፍለ ዓለማቱ እያደረሰ ነው:: የነዳጅ ማዕድናት ኤኔርጂ ግብአት ለልማት የሚያበረክተውን ጥቅም የሚያጅበ ግሪን ሐውስ ጋሶች የሚያስከትሉት የምድር መጋል መዘዝ መባባስ የለመትንና ያልለሙትን አገሮች ትኩረት አግኝቷል:: በ2000 ዓ.ም. ኪዮቶ ጃፓን የተደረገው የተባበሩት መንግሥታት የሥነ ምህዳር (environment) ጉባዔ ውሳኔ ወይም ኪዮቶ ኘሮትካል ትኩረት የምድርን መጋል መግታትና በፍጥነት መቀልበስ ነው:: ኘሮቶኮሉን ፈርመው ካፀደቁት አገሮች አንዷ ኢትዮጵያ ናት::

ኘሮቶኮሉን ያፀደቁት ሁሉም አገሮች በተለይ ግን የበለፀጉት ኢንዱስትሪያዊ አገሮች በገፍ የሚጠቀሙበትን የነዳጅ ማዕድናት ኤኔርጂ ግብአት በፍጥነት ለመቀነስ ፍቱን እርምጃዎችን መተግበር ይበጅናል፣ ይጠቅመናል፣ ብለው ወድደው ለአሃዛዊ ቅነሳ መጠን ግዴታ ገብተዋል:: እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ያልለሙት አገሮች ግን ለልማት የሚያውሉዋቸውን የማዕድናት ኤኔርጂ መጠን ውሱን ለማድረግ የሚቻላቸውን ጥረት ሊያደርጉ ተስማምተዋል::

የነዳጅ ማዕድናት ኤኔርጂን ጠንቅ እስከተወሰነ ደረጃ ለመቀነስ ምንጫቸው ጢስ አልባና ታዳሽ የሆኑ እንደ ውሀ ኃይል (hydropower)፣ የፈጣን ንፋስ ኃይል (wind power)፣ የፀሐይ ጨረር ኃይል (solar power)፣ የከርሰ ምድር ግለት ኃይል (geothermal power)፣ አጥምዶ መተካት ይቻላል:: እከከ ተወሰነ ደረጃ ባንድ ሥፍራ ሊመረት የሚቻለው ኢኮኖሚያዊ የእነዚህ ታዳሽ ኤኔርጂ ምንጮች መጠን ከውሃ ኃይል በቀር ውሱን ነው:: እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ የነዳጅ ማዕድናት ገበያ ዋጋ ዝቅተኛ ሆኖ ስለኖረ ከውሀ ኃይል በቀር ለሌሎች ምንጮች ኤኔርጂ ማጥመድ ቴክኔሎጂ፣ ምርምርና ሥርፀትና ልማት ትኩረት አልተሰጠም ነበር:: አፔክ (OPEC) በ 1974 (እ.ኤ.አ) የነዳጅ ዘይት ገበያ ዋጋ ሶስት እጥፍ ያናረውን ተከትሎ በቀጣይ ዓመታት ዋጋው ሽቅብ መዝገሙ የታዳሽ ኤኔርጂ ምንጮች ቴክኖሎጂ ልማት ቆስቁሷል::

በአንድ ሥፍራ ያለ ነዳጅ ማዕድን ክምችት በተዛቀና በተመረተ መጠን በዚያው ልክ ቀሪ ክምችቱ ይመነምናል፣ በመጨረሻም ተሟጥጦ ያልቃል:: ለምሳሌ፤ በዩኤስኤ፣ ብሪታንያ፣ ጀርመኒ፣ በኮትዲቯርና በሌሎች አገሮችም በአንዳንድ ሥፍራ የነበሩ የከሰል ወይም የነዳጅ ዘይት ወይም የተፈጥሮ ጋዝ ማዕድናት ክምችቶች ተሟጥጠው አልቀዋል:: ስለዚህ በነዳጅ

ማዕድናት ኤኔርጂ ለዘላለም መተማመን አይቻልም። በአንዳሩ ታዳሽ ኤኔርጂ ምንጮች አያልቁም፣ ሠርክ ይታደሳሉ።

በአፍሪካ አህጉር ከፍ ያለ እምቅ ሃይድሮ ኤኔርጂ (potential) ከታደሉት አገራችን አንዷ ናት። በመሆኑም አስፈላጊውን ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ ተበድሮም ቢሆን ይህን እምቅ ሀይል በየወንዙ ተፋሰስ እያለሙ ጥቅም ላይ ማዋል ተገቢ ነው። ሀይድሮ ኤኔርጂ ግን እንደግብርና ለተደጋጋሚ ድርቅ ጥቃት የተጋለጠ ነው። ይህንንም ሀይድሮ ኤኔርጂ ባህሪ እንደ ግብርና ምርታችን ገዘናብ ጠባቂ (rain-fed) ብለው አንድ ኢኮኖሚስት አስምረውበታል። ከአምና በፊት ባለፉት ቅርብ ዓመታት በሳምንት አንዴ፣ በመጨረሻም ሁለቴ በፈረቃ ቀኑን ሙሉ፣ ኤሌክትሪክ የተቋረጠብን የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። የኤሌክትሪክ አቅርቦት እንደዚህ ሲቋረጥ በኤኮኖሚ፣ ማህበራዊና በቤተሰብ አገልግሎት ላይ ከባድ ጉዳት አድርሷል።

ከጂኦተርማል ኤኔርጂ በቀር የሌሎቹ ከላይ የተጠቀሱ ታዳሽ ኤኔርጂ ምንጮች ባህሪይ እንደፀሐይ ጨረር ቀንና ሌሊት እኩል ስለማይገኝ፣ እንደንፋስ ሀይል ፍጥነቱ እንደወቅቱ (season) ከፍ ዝቅ ስለሚል፣ ከነሱ የሚመነጨው ኤኔርጂ አቅርቦት ከፍ፣ ዝቅ፣ ማለት አይቀሬ ነው። በታዳሽ ኤኔርጂ በስፊው ሲጠቀሙ የታዳሽ ኤነርጂ ፊሰስ በሚያንስበት አጋጣሚ ከተጠባቂ የነዳጅ ኤነርጂና ከሌሎች ምንጮች ሚሚላት አስፈላጊና የተለመደ ነው።

ምንጊዜም ቢሆን የትም ቦታ የምድር መጋልን ለመግታት የሚበጅ አንድ አስተማማኝ ዘዴ አለ። ይህም የሚፈለገው ጥቅም ሳይጓደል፣ እንደ ተጠበቀ ሆኖ ለማንኛውም ጉዳይ የሚወለወን ኤኔርጂ ግብአት መጠኑን መቀነስ/ማመንመን ነው። ይህም በኤኔርጂው አጠቃቀም ላይ በፊት የነበረውን ብክነት (energy waste) በመቀነስ በትንሽ ኤነርጂ ብዙ ጥቅም እንዲገኝ በሚያደርገ ኤነርጂ ቆጣቢ (energy saving) ዘዴዎችና ቴክኖሎጂዎች መጠቀም ነው። ለኤነርጂ ቆጣቢ ዘዴዎቹና ቴክኖሎጂዎቹ የሚያሻቸውን ያነሰ ኤነርጂ ግብአት ለመመገብ የሚነደው ኤነርጂ ማዕድን መጠን ያነሰ በመሆኑ፣ ሲቃጠልም የምድርን መጋል የሚያባብሰው ካርቦን-ዳይኦክሳይድ ወደ አትሞስፈር የሚለቀቀው ጋዝ መጠንም ያነሰ ይሆናል።

በሁለም ኤኔርጂ ግብአትና አቅርቦት ብክነትን የማመንመን ጥቅም ለልማት

ማናቸውንም ምርትና አገልግሎት ተግባር ለማከናወን ስለኤነርጂ ቆጣቢ ማለትም በአነስ መጠን ኤነርጂ በሚያባክኑ ዘዴዎችና ቴክኖሎጂዎች መሥራትና መገልገል ከፍ ያለ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ስነ ምህዳራዊ ጥቅም አለው።

በየቤተሰቡ በባህላዊ ምድጃ ማገዶ አጠቃቀም ይባክን የነበረውን ኤኔርጂ ለመቀነስ በአገራችን በተደረገው ምርምርና ስርፀት መሠረት የተዘጋጁ የተሻሻሉ ምድጃዎች ቆጣቢነት የማገዶ ወጪያችውን ለመቀነሱ ምድጃውን ገዝተው የሚሠሩበት ቤተሰቦች አያሌ ቁጥር ይመሰክራል።

ነገር ግን እኛ ኩሞዎች በምንጠቀምባቸው ዘመናዊ ኤኔርጂ ግብአቶች እንደናፍጣ፣ ቤንዚን፣ ኤሌትሪክ ኤነርጂ ያለውን ተመሳሳይ ብክነት ለመቀነስ ምርምርና ሥርፀት በአገራችን ተደርጎል ወይ? ካልተሳሳትኩ እስካሁን የተደረገ የለም! አጠቃቀማችን በቂ መሆኑ ተረጋግጦ

የግለሰብንና የሃገርን ኢኮኖሚ የሚጐዳ ብክነት ካልሆነ በቀር፣ ብክነቶቹን መቀነስ ለምን ትኩረት አልተሰጠውምን?

ለምሳሌ፣ ለትራንስፖርት በናፍጣ አጠቃቀማችን ላይ የሚታየው ብክነት ቀላል አይመስለኝም:: ቀደም ባሉ ዓመታት ዲገል ሞተር ከባድና መካከለኛ ጭነት መኪኖችና አውቶቡሶች ማንቀሳቀሻ የነበረው ናፍጣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ለትንሽ አቶሞቢሎች ጭምር ነዳጅ ከሆነ ዓመታት ተቆጥረዋል:: ታዲያ ሁሉም ባይባል አብዛኛዎቹ ናፍጣ አንዳጅ ከባድና ቀላል ተሽከርካሪዎች ሲንቀሳቀሱ ከጢስ መውጫቸው የሚቡለቀለቀው ከባድ ጥቁር ጥቀርሻ ለጤንነት እጅግ ክፋ ጠነቅ ከመሆኑም አልፎ ናፍጣው ከውጭ ሲገዛ የተከፈለበትን የውጭ ምንዛሬ እያባከነ እንደሆነ የታወቀ ነው:: ለዚህም ሳይሆን አይቀርም በ1989 ዓ.ም. በወጣው የትራፊክ ደንብ ጥቁር ጥቀርሻ የሚወጣው ማንኛውም ተሽከርካሪ 80 ብር እንዲቀጣ የተደነገገው::: ነገር ግን ይህ ደንብ አስከባሪ ያጣ መሆኑ ሁሉቀን በግልጽ ይታያል!

ናፍጣ የሀይድሮጅንና የካርቦን ውሁድ ሃይድሮካርቦን ነው:: ዲገል ሞተር ውስጥ ናፍጣው ሙሉ ለሙሉ ተቃጥሎ ኤኔርጂውን ካቀበለ፣ ተሽከርካሪው በሙሉ ፈረስ ጉልበት ሀይልና በፍጥነት ይንቀሳቀሳል:: ሞተሩ ውስጥ ናፍጣ በከፊል ብቻ ከተቃጠለ ግን ከናፍጣው ሳይቃጠል የቀረው ካርቦን ጥቁር ጥቀርሻ ሆኖ ከጢስ መውጫ ሲቡለቀለቅ ይወጣል:: ተሽከርካሪው በያለፈበት ጥቀርሻው አካባቢ ይበክላል:: ተሽከርካሪው ጉልበት ያንሰዋል፣ ለናፍጣው የተከፈለው ብርቅ የውጭ ምንዛሬ በከፊል ይባክናል::

ጥቀርሻው የተደባለቀበት አየር ወትሮ የሚተነፍሱ ሰዎች በተለይ ህፃናትና አረጋውያን ለከባድ ንንፋን፣ ብሮንካይትስ፣ ኒሞኒያና አስም፣ እንዲሁም ለሳምባ ነቀርሳ (ካንሰር) ይዳረጋሉ:: ናፍጣው ጥቀርሻው ያስያዛቸውን በሽታ ለመታከሚያ መድሀኒት የሚከፈለው ብርቅ የውጭ ምንዛሪ ከግብርና ምርቶች ኤክስፖርት እንደሚገኝ ልብ ይሏል! ታዲያ ይህ የናፍጣ ብክነትና ጠንቅ በነተሞችና በአውራጐዳናዎች እየተበራከተ ሳለ ለምን ብክነቱን ለማስቀረት ምርምርና ስርዐት አናካሂድም? ለምንስ ብክነቱን ማስቀሪያ የሆኑ በሌሎች አገሮች በተመጣጣኝ ዋጋ በስፊው ገበያ ላይ ውለው የሚያገለግሉ ቴክኖሎጂዎች እኛም አገራችን ሥራ ላይ አናውልም? አገራችን በየአመቱ ከምትገዛው የነዳጅ ዘይት ውጤቶች መጠን ከፍተኛ ድርሻ የያዘው ናፍጣ ነው:: ለነዳጅ ዘይት ውጤቶች ዘንድሮ የምንከፍለው የውጭ ምንዛሪ ከጠቅላላ ኤክስፖርታችን ገቢ 70% እንደሚወስድ ተገምቷል:: ከዚህ ወጪ ከፍተኛውን ድርሻ በሚወስደው ናፍጣ አጠቃቀማችን የሚታየው ጉልህ ብክነት እስከ መቼ ችላ ይባላል?

የኤኔርጂ ብክነትን የሚቀንሱ ቴክኖሎጂዎች በለመ አገሮች በልዩ ልዩ ኢኮኖሚና ማህበራዊ ዘርፎች ሥራ ላይ እየዋሉ፣ ሰፊ ጥቅም እያስገኙ መሆኑ በቀረበልን ጥናት ተገልጧል:: ከእነዚህም አንዱ ኤኔርጂ ቆጣቢ አምፑል ለምሳሌ በ10 ዋት ኤሌትሪክ ኤኔርጂ ግብአት ብቻ የቀድሞው 40 ዋት ኤኔርጂ ከሚያስፈልገው አምፑል እኩል ደማቅ ብርሀን ይሰጣል:: በዚህም ቆጣቢ አምፑል 30 ዋት ኤኔርጂ ግብአት ይባክን የነበረው ይድናል:: የኤሌክትሪክ ደንበኛው ለኤሌትሪክ መብራት ይከፍል ከነበረው ወርሃዊ ኤሌትሪክ ፍጆታ 75% ቀንሷል ማለት ነው:: በሩብ ወጭ የቀድሞውን ያህል ደማቅ ብርሀን እያገኘ ይጠቀማል:: ይህ በአንድ አራተኛ ኤኔርጂ ግብአት ብቻ የቀድሞውን ያህል ጠቃሚ መስራትና አገልግሎት ማግኘት ዘዴ factor four efficiency የሚል ስያሜ ተሰጥቶታል:: በትራንስፖርት- ህንፃ ግንባታ- በመስኖና- በግብርና- በኢንዱስትሪ ሂደቶች (processes)፣ ወዘተ... ተመሳሳይ ጥልቅ የኤኔርጂ

ብክነት ትነሳዎች፣ የሚያስገኙ ቴክኖሎጂዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ገበያ ላይ በቅርብ ዓመታት ወጥተው በሌሎች አገሮች እያገለገሉ ነው።

በዚህ ረገድ ታዋቂው የኤነርጂ ቁጠባ ተመራማሪና ደራሲ ኤሞሪ ሎቪንስ[15] ከ 15 ዓመት በፊት የሚከተለውን ጽፎ ነበር።

የኤነርጂ ቁጠባ ልማትን ከማጓተት ይልቅ ለሚለሙ አገሮች የልማታቸው ማፋጠኛ ወደር የሌለው ሳይሆን አይቀርም። ኢንዱስትሪያዊ አገሮች በህሊና - ቢስነት በያገራቸው ገበያ ያጡትን ያረጁና ያፈጁ ቴክኖሎጂዎች ወደ ሚለሙ አገሮች በገፍ ማራገፍ ትተው፣ ከሁሉም በላይ አነርጂ ቆጣቢ የሆኑትን ብቻ ሊያቀርቡላቸው ይገባል። የሚለሙት አገሮችም ብልህና ብልጥ የቴክኖሎጂ ሽማቾች በመሆን የተፈጥሮ ሀብት ብክነትን መቆጠብ የልማታቸው ስራቴጂዎችና ኘሮግራሞች እምብርት ማዕከል ማድረግ አለባቸው። ዓለም አቀፍና የሁለትዮሽ እርዳታ ሰጭዎችም ኤነርጂ ቁጠባን የርዳታቸው ግንባር ቀደም ዓላማ ማድረግ ይገባቸዋል። የሎቪንስን ምክር ባልለሙትም ሆነ በለሙት አገሮች ሰሚ ያገኘ አይመስልም! ከሎቪንስ ምክር ገን ለሚ አገሮች በየበኩላቸው ተስማሚ የሆኑ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎችን መፈብረክና ሥራ ላይ ማዋል ቀዳሚ ተግባራቸው ሊያደርጉ እንደሚገባቸው አንዘንጋ!

በዚህ ረገድ በ1988 (እ.ኤ.አ) ከወጣ «ኤነርጂ ለዘላቂ ዓለም»[16] መፅሀፍ የሚከተለውን እንመልከት። የክረምትን ከባድ ቅዝቃዜ ለመከላከል የቤት ውስጥ አየር ማሞቅ በማያስፈልግበት ለሚ አገር፡ በነፍስ ወከፍ ባመት ከ753 ኪግ ነዳጅ ዘይት ኤነርጂ በሚመጣጠን ጠቅላላ ፍጆታ ብቻ የሚለሙ አገር ዜጐች፣ በምዕራብ አውሮፓ በ1970 ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ፣ ከነበረው የሚመጣጠን ከፍተኛ የኑሮ ደረጃ መድረስ ይችላሉ። ይህን የኑሮ ደረጃ ለመቀዳጀት 753 ኪ.ግ ነዳጅ ኤነርጂውን፤

1. 80% እንደአግባብነታቸው በተመረጡት ልዩ ልዩ ነዳጅ ዓይነቶች ሆኖ ለፍጆታ መቅረብ ይኖርበታል። ቀሪው 20% ደግሞ በኤሌትሪክ መልክ ነው ለፍጆታ የሚቀርበው።
2. በሁሉም የኤኮኖሚና የማህበራዊ ዘርፍ የሚጠቀሙባቸው ቴክኖሎጂዎች በ 1970 ዎቹ ገበያ ላይ ውለው በነበሩ ከፍተኛ ኤነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች (best available) መሆን አለበት።

ይህ 20% በኤሌክትሪክ መልክ የሚቀርበው ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ኤነርጂ ፍጆታ ከ151 ኪ.ግ ነዳጅ ዘይት ኤነርጂ የሚመጣጠን የ1752 ኪሎ ዋት ሰዓት ኤሌክትሪክ በዓመት ብቻ ነው። ዛሬ በቀረበልን ጥናት ከተጠቀሰው በ 1998ዓ.ም. በኢትዮጵያ ከነበረው የነፍስ ወከፍ ኤሌክትሪክ 24 ኪሎዋት ሰዓት ዓመታዊ ድርሻ ይህ 1752 ኪሎዋት-ሰዓት 73 እጥፍ ነው።

በ1970 ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ ገበያ ላይ በነበሩ ኤነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂዎች ብቻ ብንጠቀምበት ይህ 753 ኪ.ግ ተመጣጣኝ ነዳጅ ዘይት የነፍስ ወከፍ አመታዊ ፍጆታ፣ የገጠር ኤነርጂ ልማት ማዕከል ለ1999 ባወጣው አጠቃላይ የኤነርጂ ሰንጠረዥ በድምሩ 17.43 ሚ ቶን ተመጣጣኝ ነዳጅ ዘይት መሠረት፡ የ65 ሚ ሕዝብ የነፍስ ወከፍ አመታዊ ፍጆታ የነበረው 268 ኪ.ግ ነዳጅ ዘይት 2.8 እጥፍ ነው።

---

[15] Lovins. A, 1989 "Abating Global Warmming – at a profit" Rocky Mountain Institute USA

[16] Goldemberg J., Johansson T., Reddy A. & Williams R., 1988 "Energy for a Sustainable World", Wiley Eastern New Delhi, India

የመጀሀፉ ደራሲ ምች ስመግር በዓለም አቀፍ ደረጃ የታወቁ የኤነርጂ ተመራማሪ ሊቃውንት ናቸው። ይህ የ753 ኪ.ግ ነዳጅ ዘይት ተመጣጣኝ ኤነርጂ ዓመታዊ የነፍስ ወከፍ ፍጆታ በቂነት ለማስረገጥ የሚያስገነውን ጥቅም በምግብ ማብሰል፣ በመቅ ወሃ፣ በማቀዝቀዝ ፍሪጅ፣ በመብራትና ቲቪ፣ በልብስ ማጠቢያ፣ በማንገር፣ በአምራች ኢንዱስትሪ ምርቶች፣ በጥሬ ብረት፣ በሲሚንቶ፣ በአልመኒየም፣ በወረቀትና ካርቶን፣ በናይትሮጂን ማዳበሪያ፣ በግብርና፣ በማዕድንና በግንባታ የነፍስ ወከፍ ድርሻና ጥቅም ገርገር አሃዞች አስቀምጠዋል።

የቴክኖሎጂዎች ኤኔርጂ ቆጣቢነት መዕሀፉ ከታተመበት 1988 ወዲህ ባለፉት 17 ዓመታት በሁሉም አቅጣጫ ተሻሽሏል። በለመት አገሮች አሁን የወደፊት ኤኔርጂ ቁጠባ ዓላማ ግብ መሆን ይገባዋል የሚባለው «factor ten» ኤኔርጂ ቁጠባ ነው። በፊት ያስፈልግ ከነበረው ኤኔርጂ ግብአት አንድ አሥረኛ ኤኔርጂ ብቻ የቀድሞውን ያህል ጥቅም የሚያስገኙ ቴክኖሎጂዎች በተመጣጣኝ ዋጋ ገበያ ላይ ካሁኑ እየወጡ ነው።

በዚህ ረገድ የአለም አቀፍ ዘላቂ ኤነርጂ መረብ ከስድስት መር በፊት ያወጣው 2050 ኤነርጂ ርዕይ፣ በአውሮፓ በትክለርና የነዳጅ ማዕድናት መጠቀም እንደሚቀር ይተነብያል[17]። ይህን የሚያስችለው በታዳሽ ኤነርጂ ምንጮችና ከሁለም ይበልጥ ደግሞ በስፋትና በጥልቀት ውጤታማ ኤነርጂ ቁጠባ (energy efficiency) ባላቸው ቴክኖሎጂዎች በመጠቀም ነው። አሁን ሥራ ላይ ያለ ቴክኖሎጂዎች ከሚፈጁት 10 - 25% ኤነርጂ ብቻ አብዛኛውን ምርትና አገልግሎት የሚያከናውኑ ቴክኖሎጂዎች በዛሬው ገዘ እንኳ እንዳለ ተረጋግጧል። እዚህ ላይ እንግዲያው ወደዚህ ቁጠባማ ሥርዓት ለመሸጋገር አውሮፓ ለምን 45 ዓመት ያስፈልጋል? ምክንያቱ አሁን ለሚያገለግሉት አያሌ ቴክኖሎጂዎች የፈሰሰውን እጅግ ከፍተኛ መዋዕለ ንዋይ መተካት የሚቻለው ቀስ በቀስ ስለሆነ ይመስለኛል። ገና በመልማት ላይ ባሉ አገሮች ግን በሥራ ላይ ያሉ ኤነርጂ ቴክኖሎጂዎች እጅግ ጥቂት ስለሆኑ ግን እነዚህ አገሮች ይህ መስናክል አይጋረጥባቸውም! በሌላ ቃላት በመልማት ላይ ያሉ ንቁ አገሮች ብክነታቸው የመነመነ ኤነርጂ ቆጣቢ ቴክኖሎጂ ለሁለም ማህበራዊና ኤኮኖሚያዊ ዘርፎች ከወዲሁ እየተጠቀመ፣ ለኤነርጂ ልማት የሚያፈሰትን መዋዕለ-ንዋይ መመጠንና የኤነርጂን ሥርጭት የማፋጠን ዕድል ከፊታቸው ተደቅኖላቸዋል።

በ2020 ኢትዮጵውያን ለዘላቂ ልማት በነዳጆችና በኤሌክትሪክ በነፍስ ወከፍ የሚያስፈልጋቸው ዘላቂ ኤነርጂ ግብአት መጠን፣ በአሁኑ ጊዜ በጐረቤቶቻችንና በሌሎች ለሚ አገሮች ካለው ብክነት ከለፈነበት ፍጆታ ንፅፅር አተያይ መተንበይ ይህን ዕድል እንዳያሳጣን እሰጋለሁ።

የኤኔርጂ የነፍስ ወከፍ የወደፊት ፍጆታችን እድገት አሁን በዓለም ዙሪያ እየተፋፋመ ከመጣው የኤኔርጂ ብክነት ቅነሳ ተጣምሮና ተቀናጅቶ ሊተመን ይገባል። ባጭሩ ለወደፊቱ የሚያስፈልገንን የኤኔርጂ ግብአት መጠን ስንተምን ከአቅርቦት ማሳደግ ጐን ለጐን የኤኔርጂ ብክነት መቀነስ ለሚያስገኘው ጥቅም ትኩረት ሰጥተን የኤነርጂ ልማታችንን ፖሊሲና ስትራተጂ በመቀየስ እንዲሆን የግድ ያስፈልጋል።

[17] INFORSE "NEW VISION FOR A TRANSITION TO SUSTAINABLE ENERGY IN EUROPE BY 2050" see www.inforse.org/Europe/enpolicy.htm.

መደምደሚያ

በነዚህና በመሰሉ ምክንያቶች ከአንድ ትውልድ በኋላ ለዘላቂ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት ከሠላም አንፃር ተስማሚ የሆኑ አራሳቸው ዘላቂ የሆኑ ልዩ ልዩ የኤነርጂ ግብአቶችን ኢትዮጵያውያን ባለቤት እንደማሆኑ ተስፋ አደርጋለሁ። የዘህን ዓይነት ዘላቂ የኤነርጂ አቅርቦቶችና ግብአቶች መወጠን አላማው የሆነ የኤነርጂ ፖ.ሊ.ሲ በአጭር ጊዜ ውስጥ (2-3 ዓመት) ብቁ ባለሞያዎች በማደራጀትና ምርምሮች ተመሥርቶ ለህዝቡ አስተያየት እየቀረበ መረቀቅ አለበት። ለዚህ ስብሰባ ባሬ የቀረበው ጥናት እንደፊር ቀዳጅ ሆኖ ለምንመጣው ኤነርጂ ፖ.ሊ.ሲና ስትራተጂ ምርምሮች በሰፊውና በጥልቀት መክናወን የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበርና የኢትዮጵያ ዘላቂ ኤነርጂ ልማት መረብ ትብብራቸውን እንዲያጠናክሩ፣ እንዲያስፋፉ፣ ዕኑ ምኞት አለኝ።

ዘላቂ ኤነርጂ ልማት ለአገራችን ዘላቂ ሁለገብ ልማት መሳኝ ነው! ይቻላል! ያሞጣል!

ይቅናን!

ወጣቱ እና ልማት፤ ትናንት፣ ዛሬና ነገ በኢትዮጵያ

ዘሪቱ ንዳ* እና ሳጃም ቦጋለ**

1. መግቢያ

ለአንዲት ሀገር እድገት አስፈላጊ ነገሮች ከሆኑት አንዱ አምራች የሰው ኃይል ነው። አምራች የሆነው የሰው ኃይል ደግሞ ወጣቱ ነው። ወጣት ማለት የአንድ ሀገር የዕድገት ደም ስር ነው። ስለዚህ ወጣቱ ያለውን እምቅ ችሎታ ተጠቅሞ ለሀገሩ፣ ለወገኑ፣ እንዲሁም ለማህበረሰቡ አኩሪ የሆኑ ነገሮችን ሠርቶ እንዲያልፍ የተለያየ ድጋፍ ያስፈልገዋል። ወጣቱ አንዱ የማህበረሰብ አካል በመሆኑ ማህበረሰቡ ደግሞ ለወጣቱ በአለው አቅም ለሀገሩ እድገት እንዲበረታታ የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ከዚህ በተጨማሪም ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤት፣ መንግሥት እና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት የራሳቸውን ድርሻ መወጣት መቻል አለባቸው። ወጣቶች ባላቸው አቅም መጠን በተለያዩ ቀናት የተለያዩ ስራዎችን ሰርተው አልፈዋል፤ እየሰሩም ይገኛሉ፣ ወደፊትም ይሠራሉ። ይሁንና ብዙ ጥያቄዎች ሊነሱ ይገባል፤ ወጣቱ ባለው ችሎታ መጠንና ዓይነት ሠርቷል ወይ? ለወደፊቱስ የመሥራት የሞራል ብቃት አለው ወይ? ለሥራ ተነሳሽነቱስ ምን ያኽል ነው? በአጠቃላይ እራሱን ለሚመጡት ለውጦች አዘጋጅቷል ወይ? እና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች መመለስ ያስፈልጋል።

አንዲት አገር አደገች ልንል የምንችለው ባላት ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ስትራቴጂዎች እንዲሁም ባህላዊ እሴቶች በፊት ከነበራት አቅም አንፃር ተሻሽላ እና ይበልጥ ጐልብታ እንዲሁም ከሌሎች አገሮች ጋር ሲነፃፀር ከፍተኛ ሆና ስትገኝ ነው። አንዲት አገር ከሌሎች አገሮች ጋር ብቁ እና ተወዳዳሪ ልትሆን የምትችለው ደግሞ ባላት የሰው ኃይል ብዛት ብቻ ሳይሆን በሚሰሩ ሥራዎች መጠን ነው። እነዚህን ሥራዎች ሊያከናውን የሚችለው አካል ደግሞ ወጣቱ ነው። በመሆኑም ወጣትነት ሲነሳ የአገር ልማት፣ የአገር ልማት ሲነሳ ወጣትነት፣ ሁለቱ የአንድ ሣንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው።

ከዚህ አስተሳሰብ አንፃር ወጣቱ የአንዲት ሀገር የጀርባ አጥንት የሆነ የህብረተሰብ ክፍል ተደርጐ ሊቆጠር ይችላል።

ከሁሉም በላይ በገጠር አካባቢዎች የሚኖሩትን ወጣቶች ከግምት ውስጥ ማስገባት አስፈላጊ ነው። እነዚህ ወጣቶች በቁጥር እጅግ ከፍተኛ በመሆናቸው አካባቢን ለመንከባከብና ለማልማት፣ የተሻለ የምርት ስርዓቶችን ለመፍጠር እና ለውጦችን ለማምጣት ይችላሉ። ወጣቱ ትውልድ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ፣ ማህበራዊ ልማዶችን እና እምነቶችን በግልጽ በመጠየቅ እና በመወያየት ለሥልጣኔ መሳሪያ ሆኖ ያገለግላል።

---

* ወጣት ዘሪቱ ንዳ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስ ትምህርት ክፍል የአራተኛ ዓመት ተማሪ ከመሆኗም በላይ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ህብረት አባል ነች።

** ወጣት ሳጃም ቦጋለ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የውጭ ቋንቋዎች እና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል አራተኛ ዓመት ተማሪ ነች።

ይህ ከሆነ ወጣቱ ለአንድ አገር ልማት ያለውን ሚና አውቆ ምን ያክል እየተንቀሳቀስ ነው? ወጣቱ ያጋጠመው ችግሮች ወይም ለሥራ እንቅፋት የሆኑት መሰናክሎች አሉበት ወይ? ምንስ መደረግ አለበት? እነዚህንና ሌሎች ተጓዳኝ ሀሳቦች በዚህ አጭር ጽሁፍ ለመዳሰስ እንሞክራለን::

ጽሑፋችን ሰባት ክፍሎች አሉት:: ክፍል አንድ መግቢያው ሲሆን፤ በሁለተኛው ክፍል የወጣትነት ትርጉም ቀርቧል፤ ክፍል ሁለት ውስጥ ወጣትና ልማት ከተለያዩ ገጽታዎች ተዳስሷል:: ሌሎች አካላት በወጣቱ ሕይወት ውስጥ የሚጫወቱት ሚና በክፍል ሶስት ታይታል:: ክፍል አራት ወጣቱንና መሰናክሎቹን ይተነትናል:: በክፍል አምስት ንግግራችንን እናጠቃልል እና በመጨረሻው ክፍል ርዕያችንን፣ ምኞታችንን፣ አቅርበናል::

2. ወጣትነት ምንድን ነው?

የወጣትነት ብያኔና በወጣትነት የዕድሜ ክልል ወስጥ የሚታቀፉት ሰዎች ቁርጥ ያለ ገደብ የለውም:: ወጣትነት የሚታወቀው እድሜን መሠረት ባደረገ ክልል ውስጥ ነው:: በዚህ መሠረት «ወጣት» የሚለው ፅንሰ ሃሳብ በተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ይዘቶች አንባር ስናየው በርካታ ትርጉም የተሰጠው ቃል ነው:: ወጣት ማለት በሰው ልጅ ሥነ-ህያዊ ምዕራፍ አንድን የእድሜ ክልል የሚወክል እና የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ-ልቦናዊ፣ ማህበራዊ አቋምና ደረጃ ያለው ነው::

ለወጣትነት ከተሰጠት ትርጉሞች መካከል የሥነ-ህዝብ (Demographic) ገለጻዎች ወይም ትንታኔዎች የተለየ የዕድሜ ገደብ በመወሰን «ወጣትነት» የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ለማስረዳት ይሞክራሉ:: በዚህም የተነሳ ልዩ ልዩ ሀገሮች በራሳቸው ማህበራዊ፣ ልማዳዊና ባህላዊ እሴቶች ላይ በመመርኮዝ የተለያየ የዕድሜ ክልል አስቀምጠውለታል:: ለምሳሌ:-

በተባበሩት መንግስታት	15-24 ዓመት
በህንድ	15-35 ዓመት
በናይጄሪያ	18-35 ዓመት
በደቡብ አፍሪካ	14-35 ዓመት

ባለው የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙትን የህብረተሰብ ክፍል በወጣትነት የዕድሜ ክልል እንደሚመደቡ እንረዳለን::[18]

አገራችንን ኢትዮጵያን ብንወስድ ከ15-29 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ ያሉት በወጣትነት ይካተታሉ:: በዚህ መሠረት ከሀገሪቷ የህዝብ ብዛት 1/3ኛው ግድም ወይም 29% ወጣት ነው ተብሎ ይገመታል:: ወጣት ስንል እንግዲህ ከላይ በተጠቀሱት የእድሜ ክልል በህፃንነት እና በአዋቂነት መሃል የሚገኝ የመሸጋገሪያ ዘመን እንደሆነ እንረዳለን:: ይኸም ለፈጠራና ለለውጥ አገራችን ከፍተኛ እምቅ ሐይል እንዳላት በግልጽ ያሳየናል::

በወጣትነት ዘመን ውስጥ ያለ ሰው ሊኖሩት የሚችሉ አጠቃላይ ባህሪያት አሉ:: እነርሱም ትኩስነት፣ አፍላነት፣ ደፋርነት፣ ቅንነት፣ ታዛዥነት፣ አምራችነት እና የመሳሰሉት

[18] ምንጭ፤ ከኢንተርኔት

መገለጫዎች ናቸው። እነዚህ ባሕሪያት ናቸው እንግዲህ ወጣቱን ለበጎም፣ ለክፉም፣ ነገሮች ምቹ የሚያደርጉት።

ወጣትና ልማት

3.

«ልማት ለሚለው ፅንሰ ሃሣብ እንደ የሙያ ዘርፉ የተለያየ ፍች ይሰጠዋል። ጠቅለል ባለ መልኩ ስናየው ግን «ልማት» ማለት ውስብስብ፣ ጥልቅ እና ፈርጀ-ብዙ ሂደት ሲሆን ከኢኮኖሚ ዕድገት ብቸኛ አተያይ ልቆ ሁሉንም የኑሮ አውታሮች እና የማህበረሰቡን መላ አቅም አጣምሮ በመያዝ በማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሽግግር ወይም ለውጥ ውስጥ ሁሉም አባላት አስተዋጽኦ እንዲያደርጉና ውጤትን በጋራ ለመቀየስ የሚያስችል ሂደት ነው። በመሆኑም የልማት መርህ በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ፍላጐት ላይ እንዲመሰረት እና የማህበረሰቡን ጥልቅ መለያ ወይም ማንነት የሚያንፀባርቅ ሊሆን ይገባዋል» (The Cultural Approach to Development)

በዚህ ብያኔ መሠረት ልማት በዋነኛነት ህዝብን መሠረት ማድረግ አለበት። የህዝቡን የኑሮ ፍላጐትና ምኞት ለሚሟላት ደግሞ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ መመዘኛ ዎችን ማካተት የግድ ይላል። በመሆኑም ልማት በሁሉም የኑሮ ፈርጆች ህብረተሰቡን ከአንድ የኑሮ ደረጃ ወደ ሚቀጥለው የተሻለ የኑሮ ደረጃ ማሸጋገር አለበት። በጥቅሉ ልማት የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በስፋት ሲታይ የኢኮኖሚ ዕድገት መመዘኛ ከሆኑ ከIndustrialization እና Modernization መጥበብና መራራቅ በተጨማሪ በልማት ሒደት ውጤት ላይ ማህበረሰቡ የባለቤትነት ስሜት ኖሮት ንቁ ተሳትፎ ማድረግ እንዳለበት ይሰማናል። ይህን ለማድረግ ደግሞ ወጣቱ ከፍተኛ ኃላፊነት አለበት። ምክንያቱም ወጣቱ ከፍተኛ የሥራ ፍላጐት፣ ተነሳሽነት፣ ፈጣሚነት፣ አስፈጣሚነት/ ሠርቶ ማሰራት/ የሚችል የአንድ ሀገር የህብረተሰብ ትልቁ ብቸኛ ክፍል በመሆኑ ነው። ወጣቱ ለአንድ አገር ዕድገት ከፍተኛ ሚና መጫወት ይችላል። ከነዚህም ጥቂቶቹ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ባህላዊ እሴቶችን ያጠቃልላል።

3.1 ፖለቲካዊ

ስለ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ቀደምት ወጣት ገዳይ በምንዳስስበት ጊዜ የተለያዩ ምሁራን እና ደራሲያን ስለ ከተማና ስለ ገጠሩ ወጣት ብዙ ብለዋል። ከዚህም ተነስተን የኢትዮጵያ ወጣት በሶስቱ ወቅቶች የነበራቸውን አጠቃላይ እንቅስቃሴ ጠቅለል ባለመልኩ ለማየት እንሞክራለን።

የኢትዮጵያ ወጣቶች በተለያዩ የፖለቲካ ሥርዓቶች እንዲሁም ታሪካዊ ወቅቶች ዘርፈ-ብዙ ተግባራትን እንዳከናወኑ መገንዘብ ይቻላል። ሀገርን የሚመለከቱ የጋራ ጉዳዮች በሚያጋጥመበት ጊዜ በአንድነት መንቀሳቀሳቸው የነበረና ዛሬም ያለ ሕያው ታሪካችን ነው። ዘመናዊ ትምህርት የማግኘት ዕድል ባልነበረበት ዘመን በግብርና እና በዕደ ጥበብ በመሠማራት አገራቸውን ከመገንባት ጐን ለጐን የውጭ ወረራን ይከላከሉ ነበር። ዘመናዊ ትምህርት ከተጀመረ ወዲህ ደግሞ ሁለንተናዊ ጭቆናን በመቃወም ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ልማት፣ ለፍትህ፣ ለዲሞክራሲና ለተሻለ አስተዳደር በጽናት ታግለዋል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ታሪክ እንደሚያስረዳው በተለይ ከ1953 ዓ.ም. ወዲህ ባሉት ዓመታት ውስጥ ኅብረተሰቡን በንቃትና በሰፋት በማንቀሳቀስ የትግል ፋና ወጊ ሆነዋል። ኢ-ፍትሃዊና ጨቋኝ የአገዛዝ ሥርዓቶችን ለማስወገድ ተቃውሞ በማንሳት፣ እንዲሁም ህብረተሰቡን ለኢኮኖሚያዊና ለማህበራዊ ልማት፣ ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲና ለተሻለ ሥርዓት በስፋት በማንቀሳቀስ፣ በግንባር ቀደምትነት በጽናት የፈፀሙት አኩሪ ትግልና በመስዋዕትነታቸው ያስገኟቸው ድሎች ለአሁኑ ወጣት መሠረት ሆነው አልፈዋል። በዚህ አንባር «መሬት ላራሹ» ዲሞክራሲያዊ መብትን አንግበው በመነሳት የፊውዳሉን ሥርዓት በመገርሰስና አርሶ አደሩን ከግባርነት ለማላቀቅ ያደረጉት አኩሪ ታሪክና የከፈሉት መስዋዕትነት ለወጣቱ ታላቅ አርአያ ሆኖ ለዘለዓለም ይኖራል።

ከዚህ ተነስተን ከ1966 ዓ.ም. ወዲህ የወጣቱ ህይወት ምን ይመስላል? የሚለውን በአጭሩ እንቃኝ። በጊዜው በተቋቋሙ ልዩ ልዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ውስጥ ወጣቱ ገብቶ ብዙ መስዋዕትነትን መክፈሉ ይታወሳል። በተለያዩ የትምህርት፣ የሥነ ምግባር እና የኃላፊነት አውዶች ውስጥ ያደገ የአገሪቱ ብርቅ ዜጐች፣ በብሔረሰብና ሐይማኖት ሳይለያዩ በተለያዩ ድርጅቶች ውስጥ ገብተው ለዲሞክራሲና ለሰብአዊ መብት ሲያደርገ በነበረው ከፍተኛ ትግል በብዛት መሰዋታቸው የትናንት የታሪክ አሻራችን ነው። የአንድ ትውልድ አባላት በዚህ ዘመን ተሰደዋል፣ ተሰውተዋል። ይኸም የሚያመለክተው ወጣቱ በአገር ፍቅር ተነሳስቶ ሕይወቱን ለዲሞክራሲና ለሰብአዊ መብት መስዋቱን ነው።

ይሁንና በዚህ ዘመን ወጣቱ ከቤተሰብ ቁጥጥር ወጥቶ እንደነበር አንዳንድ መረጃዎች ያመለክታሉ። ቤተሰብ በጊዜው በተቋቋሙ የወጣት ድርጅቶች ላይ ጫና የማሳደር ምቹ ሁኔታና አቅም አልነበረውም። በነዚህና በመሳሰሉት ችግሮች ምክንያት የወጣቱ ትግል ተነሳሽቶ ወጣቱ ለከፍተኛ ስደትና ህልፈት ተዳርጓል።

በአሁኑ ወቅት ደግሞ በአጠቃላይ መልኩ ስናየው፣ ምንም እንኳ የአሁኑ ወጣት ከቀድሞዎቹ ጋር ሲነፃፀር ብዙ የፖለቲካና የማህበራዊ ጫና የሌለበት ቢመስልም፣ በዘር በመከፋፈሉና በነፃነት ለመደራጀት ባለመቻሉ፣ የአሁኑ ትውልድ የቀድሞዎቹ ወጣቶች ከሰሩት ስራዎች ጋር ሲነፃፀር እምብዛም እንዳልሰራ ይሰማናል። ያም ሆኖ ወጣቱ እጁን አጣምሮ የተቀመጠ ኃይል ሳይሆን አቅሙ በፈቀደለት መጠን እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። የበለጠ መሥራት እንዲችል ችግሮቹን በማጤን መፍትሔ ማፈላለግ የእያንዳንዱ ህብረተሰብ ኃላፊነት እና ግዴታ ነው ብለን እናምናለን። በተለይ ወጣቱ ወደፊት እንዴት በነጻ ተደራጅቶ መሠማራት ይችላል? ድክመቱንስ እንዴት ያስወግዳል? ወጣቱ ለአንዲት ሀገር ልማት ያለው ሚና ምን ይመስላል? እነዚህና የመሳሰሉት መልስ ማግኘት ያለባቸው ይመስለናል።

3.2 ማህበራዊ

ወጣቶች በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ ለአንድ ሀገር ዕድገት የድርሻቸውን መወጣት መቻል አለባቸው። ወጣቱ ትውልድን የመቅረጽ ሀላፊነት ያለበት መሆኑን አወቆ በህብረተሰቡ ውስጥ በሚገኙ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ ለተተኪው ትውልድ የሚተላለፍ ቅርስ መትከል መቻል አለበት። ይኸም ሲባል ጥሩ ስነ-ምግባር ያለው፣ ለሥራ ተነሳሽነት ስሜት ያለው፣ የባለቤትነት ስሜት አስርጾ፣ ለሀገሩ ዕድገት ተሟጋች እና ስም አስጠሪ ትውልድ እስካልሆነ ድረስ፣ አንዲት ሀገር ከነበረችበት አረንቋ ውስጥ ወጥታ ለምንመኘው እና ለምንናፍቀው ዕድገት እንደርሳለን ማለት ተረት-ተረት ይሆናል። የማህበራዊ ህይወት ቀውስ

ለአንዲት ሀገር ዕድገት ውድቀት ዋነኛ ተጠቃሽ ምክንያት ነው። ለአንዲት ሀገር ማህበራዊ ህይወት ቀውስ ደግሞ ተጠያቂ ወጣት ነው። ወጣቱ በማህበራዊ ህይወት በኩል ከፍተኛ ሚና መጫወት ያለበት መሆኑን አውቆ ለዕድገት የሚሆኑ መሠረታዊ ነገሮችን በመገንዘብ ለዕርሱ እና ለወገኑ፤ ብሎም ለሀገሩ፣ ጠቃሚ የሆነ ነገር ሰርቶ ማለፍ አለበት እንላለን።

3.3 ኢኮኖሚያዊ

ወጣቱ ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ ዕድገት እንደ ሐብት (resource) የሚያገለግል አካል ነው። በመሆኑም አንዲት ሀገር ያላትን ሀብት በሚገባ ለመጠቀም እንድትችል የወጣቱ በኢኮኖሚያዊ ዕንቅስቃሴዎች ላይ በቂ ተሳትፎ ማድረግ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ. ወጣቱ የተረጅነትን ስሜት አስወግዶ እራሱ ሥራን ፈጣሪ መሆን አለበት። ስራ ፈጣሪ ስንል ወጣቱ ማንኛውንም ስራ ላይንት ኑሮውን የሚያሻሽልበትን መነገድ እራሱ ማመቻቸት መቻል አለበት ማለት ነው። በተጨማሪም ባለበት የሥራ ሁኔታ ላይ ብቃቱን ከማሰየት አልፎ ለአንድ ሀገር የኢኮኖሚ ድቀት የሚያመጡ ችግሮችን፣ ለምሳሌ፣ እንደ መስና ያሉ ነገሮችን መዋጋት መቻል አለበት። ሌላው ደግሞ ወጣቱ ከማውራት ይልቅ ወደ ሥራ የሚሰማራበትን ጊዜውን በአግባቡ ተጠቅሞ እርሱ ከፈለገበት ግብ እንዲሁም ሀገሩ እና ወገኑ የሚጠብቁበትን ከሚመለከተው ክፍል ጋር በመሆን ተዋረዱን ጠብቆ በአግባቡ መስራት ያለባቸውን ስራዎች ማከናወን መቻል አለበት። ይህም ሲባል፣ በቴክኖሎጂ ምጥቀት፣ ኢንዲስትሪ፣ ትምህርት እና አጠቃላይ ልማት ላይ መሳተፍ ብቻ ሳይሆን እንደ ሞተር አንቀሳቃሽ ሆኖ ማገልገል መቻል ነው። በተለይ ሥራ አጥነትን ከማጥፋትና በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙትን ሀብቶች በአግባቡ መጠቀም መቻል አለበት። የሀገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ስንመለከተ ወጣቱ ብዙ የኢኮኖሚ ችግሮች እንዳለብት ግልጽ ነው። ዋናው በሽታ ግን የስራ ፍላጐት አለመኖር እና የአስተሳሰብ ድህነት ናቸው። ማንም ሰው ከስራ እና ገቢውን በአግባቡ መጠቀም ከቻለ ከሚፈልግበት ቦታ ለመድረስ የሚያግደው ምንም ነገር የለም። በመሆኑም ወጣቱ የአንዲት ሀገር የኢኮኖሚ ዕድገት ከሰው ሀይል እስከ ሌሎች ከፍተኛ ቴክኖሎጂ ዕድገት ከማመንጨት አልፎ የአገሪቷ የጀርባ አጥንት መሆኑን ተገንዝቦ ድርሻውን መወጣት አለበት እንላለን።

4. የሌሎች አካላት ሚና በወጣቱ ሕይወት

ወጣቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ እንዲኖረው ጉልህ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ አካላት አሉ። ከነዚህም ውስጥ በዋነኝነት ተጠቃሾቹ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ት/ቤትና መንግስት ናቸው።

4.1 ቤተሰብ

በአንድ ቤተሰብ የሚወለዱ ልጆች በብዙ አቅጣጫ የቤተሰቦቻቸውን መደያ፣ ስነ-ምግባር፣ የአኗኗር ሥርዓት፣ ሀይማኖት፣ እንደሚቀስሙ ይገመታል። ብዙዎቹ የሥነ አዕምሮ ምሁራን እንደሚስማሙበት «ቤተሰብ ለህፃናት ማደግ፣ ለአስተሳሰባቸው መበልፀግ እና ለመሳሰሉት ነገሮች እንደ ሞዴል ሆነው ያገለግላሉ።» ታዳጊ ህፃናት ብዙ ጊዜ በመሰል ኩረጃ (Psychological Imitation) ብዙ ትምህርቶችን ይማራሉ፤ አስተሳሰባቸውንና የፈጠራ ችሎታቸውን ከፍ ያደርጋሉ። ቤተሰብ ለህፃናት ሞዴል እስከ ሆነ ድረስ የሚያደርገው ማንኛውም እንቅስቃሴ በህፃናት የወደፊት ዕጣ ፈንታ ላይ ተጽኖ አለው።

አያሌ የሥነ-ልቦና ምሁራን የመንፈስ ጭንቀት (disturbance) የደረሰባቸውን ሰዎች ለመርዳት ብዙ ጊዜ የሚያተኩሩት ሰውዬው በእንዴት አይነት ሁኔታ እንደ አደገ እና የቤተሰቡ ሁኔታ ምን እንደሚመስል በመመርመር እና በማጥናት ነው። እንዲህ አይነቱ የምርምር ዘዴ በልጅነት ጊዜ ተገተው ያልተሟሉ የሰው ልጅ ፍላጐቶች (needs) በሰውዬው ህይወት ላይ ምን አይነት ጉዳት ጥለው እንዳለፉ ለማውቅና መፍትሔዎቻቸውንም ለመፈለግ አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር ያስችላል።

ህፃናት ትምህርት ለመቅሰምና ለመማር አዕምሮአቸው ዝግጁ በመሆኑ ያዩትን፣ የሰሙትን እና የተነገራቸውን በቀላሉ ይይዛሉ። ህፃናት ከጨቅላ እድሜያቸው ጀምሮ ተኮትኩተው ካደጉ የወደፊት ትውልድ ታላቅ ሊቅ፣ ፈላስፋ፣ ታዋቂ ባለቅኔዎችና መሃንዲሶች ሊሆኑ ይችላሉ። ወጣቶችን ለዚህ አይነት ሙያ ሊመራቸውና ሊያበቃቸው ከሚችሉት አካላት ቤተሰቦቻቸው ተጠቃሽ ናቸው። ወላጆች ልጆቻቸው በፍቅር፣ በትዕግስትና በግልጽ ውይይት አካባቢያቸውን እንዲያውቁና እንዲጠይቁ፣ እንዲመረምሩ፣ በማድረግ ረገድ የራሳቸው ድርሻ አላቸው። ከእንዲህ ዓይነት ቤተሰብ የወጣ ወጣት አስተዋይ፣ ደፋር፣ አመዛዛኝ እና ተመራማሪ እንዲሁም ሰውን እና አገሩን አፍቃሪ፣ ይሆናል። በተጨማሪም፣ ወደፊት በኑሮው ደስተኛ ሆኖ ለመኖር ይችላል። በአጠቃላይ፣ የወላጆች እንክብካቤ በአካላዊ ጥቅም ብቻ ሳይወሰን ለነ-ልቦናዊ እና ማህበራዊ ዕድገቶችን ስለሚጨምር ጥሩ ዜጋን ለማፍራት ያስችላል።

4.2 ማህበረሰብ

ወጣቱ የህብረተሰቡ አንድ አካል እንደመሆኑ መጠን በአካባቢው ከሚገኘው ህብረተሰብ የሰማውን፣ ያየውን፣ ነገር ይቀስማል። ህብረተሰቡም ለወጣቱ ጥሩ-ሥነ ምግባር የማስተማር፣ የሥራ-ፍላጐት ተነሳሽነት የማበረታት እና የሀገር ፍቅር እንዲኖረው የማድረግ፣ ሃላፊነት አለበት። ወጣቱ የተለያዩ የሥነ-ምግባር ጉድለቶችን የሚማረውም ከማህበረሰቡ ነው። ከዚህ አንፃር ህብረተሰቡ ለወጣቱ ያለው ሚና ከፍተኛ ሆኖ እናገኘዋለን።

የሰው ልጅ በተፈጥሮ ብቻውን የሚኖር ፍጡር አይደለም። በመሆኑም የሰው ልጅ በአንድነት፣ በባህል፣ በሀይማኖት፣ በስርአት፣ በአመለካከት አንድ የሚያደርጋቸው ከልምድ አንፃር የተለየዩ ነገሮች አሉ። አንድ ሰው ከሌላው ሰው የሚፈልገው ነገር ስላለ፣ ብቻውን ከሚኖር ይልቅ ከማህበረሰቡ ጋር መኖር ይገደዳል። ይህም ማለት አንድ ማህበረሰብ የራሱ የሆነ ቋንቋ፣ ባህል፣ የአኗኗር ስርአት፣ የአመጋገብና የአለባበስ ስርአት፣ አሉት። ማህበረሰቡም እነዚህን ስርአቶች በወግና በስርአት ጠብቆ የመኖር ግዴታ አለበት። አንፃር ወጣቱ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ የማህበረተሰቡን ባህል፣ ልምድና ወግ ጠብቆ የመኖር ግዴታ አለበት። ምክንያቱም የአንዲት ሀገር ባህል፣ ልምድ፣ ሀይማኖት፣ ቋንቋ፣ የማንነቱ መገለጫ በመሆናቸው ለተተኪው ትወልድ የማስተላለፍ እርሱም ግዴታ አለበትና!

ኢትዮጵያ ሰፊ ታሪክና የባህል ቅርስ ያላት ሀገር ናት። በኢትዮጵያ ብልጽግናንና እድገትን ለማፋጠን፣ የሕዝቡን ወግ፣ ልማድ፣ ስርአት፣ በአጠቃላይ፣ ባህልና ቅርሶች፣ መገምገምና መልካሙን ይዞ መራመድ አይነተኛ ዘዴ ነው። በአሁኑ ወቅት ወጣቱ በዚህ ረገድ ምንም ሥራ እንደማይሰራ፣ አቅም እንደሌለው እና ጊዜውን በከንቱ እንደሚያባክን አድርገው የሚቆጥሩ ብዙ የማህበረሰብ ክፍሎች አሉ። ለዚህም ይመስላል «ከራስ በላይ ንፋስ» እንዲሉ እያንዳንዱ ወላጅ ከራሱ ልጆች በስተቀር ሌሎችን ልጆች እንደራሱ ልጆች ቆጥሮ ጥሩ ሥነ-ምግባር እንዲይዙ ጥረት ሲያደርግ የማይታየው።

በአንፃሩ ግን በቀደመው ጊዜያት የነበረውን ማህበረሰብ ስንዳስስ የአንድ ቤተሰብ ችግር የአጠቃላይ የማህበረሰቡ ትግር መሆኑን እንገነዘባለን። የእኔ፣ የአንተ፣ ልጅ፣ የሚል ነገር አልነበረም። በዚያን ወቅት የነበሩ ወጣቶች ለሀገራቸውና ለወገናቸው አኩሪ ታሪክ እና ድል እንዲሰሩ ማህበረሰቡ ያበረታታቸው እንደነበር ታሪክ ያስረዳናል። ስለዚህ ማንኛውም ወጣት የሚፈልቅበት ማህበረሰብ ለወጣቱ ትውልድ በብሔራዊ ስሜትና የዜግነት ክብር ላይ የተመሰረተ ሁለንተናዊ ተሳትፎ ማለትም፤ አደጋን በቁርጠኝነት የመጋፈጥና በሥራ ክቡርነት የማመን ባህሪያት ተላብሶ በአቅም መኖርን በማዳበር ጥሩ ዜጋ ሆኖ እንዲያድግ ያደርግ ነበር።

በአጠቃላይ ህብረተሰቡ «አንተህን ቆርጠ ጤናህን ይስጥህ» አይነት አስተሳሰብ ቀርፎ የእኔ ልጅነትን ስሜት በመፍጠር እያንዳንዱ ወጣት የራሱ ልጅ መሆኑን አውቆ ወይም ተረድቶ የሚጠበቅበትን የአባትነት እና የእናትነት ኃላፊነት መወጣት እንዳለበት እናምናለን።

4.3 ትምህርት ቤት

ትምህርት ቤት ከቤተሰብና ከማህበረሰብ ቀጥሎ ለወጣቶች ስነ-ልቦናዊ እና መልካም አስተዳደግ መደበኛ እና ኢ-መደበኛ የማስተማር ዘዴ በመጠቀም ለወጣቱ ሁለንተናዊ ለውጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው። ወጣቶች ከመደበኛ ትምህርት ጋር በተጓዳኝ የስነ-ምግባር፣ ከሰው ጋር አብሮ የመኖር፣ የመስራት፣ የመረዳዳት፣ የመፍጠር፣ ችግርን የመፈታትና የመሳሰሉትን የህይወት መሰረታዊ ነገሮች የሚያገኙት ከትምህርት ቤት እንደሆነ ይታወቃል። እነዚህን ነገሮች በተገቢው መንገድ ለማግኘት ደግሞ የመምህሩ እና የተማሪው እንዲሁም የሁለቱ ግንኙነት አስተዋጽኦ ከባድ ነው። መምህሩ በትምህርት ትውልድን የመቅረጽ ሃላፊነት አለበት። ተማሪውም የት/ቤት ህግና ደንብ በማክበር፣ ታላላቆቹን በማክበር፣ ታዛዥነትን በመላበስ፣ ትምህርቱን በስነ-ስርአት መከታተል እና በአጠቃላይ ለወደፊቱ የአገሪቱ የዕድገት ሁኔታ ላይ በመረባረብ የግሉን ድርሻ ማበርከት ይኖርበታል። እነዚህ ሁለቱ ከተሳኩ ለወጣቱ ሁለንተናዊ ዕድገት ት/ቤት ዋነኛው የዕውቀት መሠረት ከመሆኑም በላይ የተማሪውና የመምህሩ መስተጋብር የአባትና የልጅ ግንኙነት ይሆናል። አለበለዚያ ግን ወጣቱን ከተፈለገው ግብ ለማድረስ አዳጋች ይሆናል ብለን እናምናለን።

ወጣቱ የሚፈልገውን ትምህርት (መደበኛ እና ኢ-መደበኛ) ቀስሞ እንዲወጣ ሁል ጊዜ ማጤንና መቡቱን በደንብ ማወቅ መቻል አለበት። በትምህርት ቤት ውስጥ ጥሩ የመማር ማስተማር ሂደት እንዲኖር ከሚያደርገው አበይት ነገሮች ውስጥ የትምህርት ቤት አጠቃላይ ሁኔታ፣ የመምህሩና የተማሪው ግንኙነት፣ ለትምህርት የሚያስፈልገው ቁሳቁሶች መኖር፣ ዋናዎቹ ተጠቃሾች ናቸው። ለአብነት የመምህራንና የተማሪውን ግንኙነት እንዳስስ።

ጥሩ የመማር-ማስተማር ሂደት እንዲኖር ከተፈለገ የአባትና የልጅ ግንኙነት ሁለቱ መካከል መኖር እንደሚገባ ግልጽ ይመስለናል። መምህሩ የተማሪዎቹን ደካማና ጠንካራ ጐኖች የመለየት፣ የመርዳት፣ የማገዝ እና ብሩህ ተስፋ እንዳላቸው የማሳየት ኃላፊነት አለበት። ተማሪው ደግሞ መምህሩ የሚለውን ነገር በአግባቡ የመተግበርና የማክበር ግዴታ አለበት።

ወደ አውነታው ስንመጣ ግን በተለይ በአሁኑ ሰዓት ይህ ሆኖ አናገኘውም። መምህሩ ተማሪውን፣ ተማሪው መምህሩን፣ ሲኮንኑ ይስተዋላል። ይህ ደግሞ ለመማር ለማስተማር ሂደት ትልቅ እንቅፋት ነው። በተለይ ዛሬ ዛሬ በግልጽ እንደሚታየው በመጀመሪያ እና

በሁለተኛ ዙር (cycle) ትምህርት ቤቶች የተማሪው ሥነ-ምግባር የከፋ ሆኖ ይታያል። በተቃራኒው ደግሞ የቀደሞው ተማሪዎችን የትምህርት ቤት ሕይወት ሲናገሩ እንደምንሰማውና ታሪክ እንደሚያስረዳንም የመምህሩና የተማሪው ግንኙነት ከቤት ውስጥ ካለው የወላጅ ግንኙነት የማያንስ ነበር። እዚህ ላይ የተማሪውን ሥነ-ምግባር ማነስ በስፋት አነሳን እንጂ ምግባረ-ብልሹ የሆኑ መምህራንም በየት/ቤቱ መኖራቸው ይታወቃል። እነዚህ መምህራን ደግሞ የተረከቡትን ኃላፊነት ያልተወጡ በመሆናቸው ተወቃሽ መሆናቸው አይቀርም። ስለዚህ ተማሪውም ወደ ት/ቤት የሚሄደበትን ዓላማ አውቆ ጊዜውን በአግባቡ መጠቀም አለበት እንላለን። መምህሩም ያለበትን ሃላፊነትና ግዴታ ለመወጣት እና ጥሩ ትውልድ ለመቅረጽ ደፋ-ቀና ማለት ይኖርበታል። እንዲህ አይነት የመምህርና የተማሪ ግንኙነት ሲኖረን ነው አገራችንን ከምንፈልገውና ከምንመኘው የዕድገት ደረጃ ልናደርሳት የምንችለው።

4.4 መንግስት

መንግስት የህዝብ አገልጋይ እንደመሆኑ መጠን የህገቡን ፍላጐት፣ ምኞት እና አደራ በመጠበቅ፣ ለአንዲት ሀገር ያስፈልጋል ተብሎ የሚገመት ፖሊሲ፣ ህግ እና ደንብ ያወጣል የሀገርን ልማት ለማፋጠንና ደህንነቱን ለማስከበር።

መንግስት የሚያወጣቸው ህጐች እና ደንቦች የሀገሪቱን እና የህብረተሰቡን የኑሮ ሁኔታ ያማከለ መሆን መቻል አለበት። ወጣቱ አንዱ የህብረተሰብ አካል ከመሆኑም በላይ የወደፊት ሀገር ተረካቢም ስለሆነ መንግስት ለወጣቱ ከፍተኛ ግምት በመስጠት የወጣቱን ደህንነት የሚጠብቅ፣ ወደ ሥራ የሚመራ፣ ለወደፊት ብሩህ ተስፋ የሚሰጥ እና በነፃነት ተዘዋውሮ የሚሰራበትን ሁኔታ የሚያመቻች ፖሊሲ መቅረጽ አለበት።

ለመንደርደሪያ እንዲሆነን በቀድሞው መንግስት የነበረውን የወጣቱን ሁኔታ እንዳስስ። በዚያን ጊዜ ወጣቱ በግዴታ በማህበር ተደራጅቶ ይንቀሰቀስ ነበር። የአሁኑ ወጣት በራሱ ተነሳሽነት በተለያዩ ማህበራት በመደራጀት ብዙ ለሀገር እድገት እየሰራ ይገኛል። ነገር ግን ወጣቱ ትኩስ ሀይልና እምቅ ችሎታውን በሚጠበቅበት ደረጃ ተጠቅሟል ማለት ግን አይቻልም። ከዚህ አንፃር መንግስት ወጣቱን ከማደራጀት አልፎ ራሱን እንዲችል ብሎም ለሀገሩ እድገት ተቆርቋሪ ወይም ሀገር ወዳድ እንዲሆን አስተዋፅኦ እንዳለው እናምናለን። ወደ ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ፣ አንድ ማህበር ለማደራጀት የወጣቶች ስብስብ ብቻ ጠቀሜታ የለውም። በፋይናንስ፣ በሞራል፣ በማኔጅመንት፣ በፖሊሲ አቀራረጽ መንግስት የሚፈለግበትን ሁሉ ማሟላት አለበት።

ነገር ግን ይህ ሲሆን አናይም። ባለን ተጨባጭ ማስረጃ መሰረት ወጣቱ ከመንግስት እምብዛም ድጋፍ አልተደረገለትም። ይህ ደግሞ መንግስት ለወጣቱ ያለውን ዝቅተኛ አመለካከት ይገልጻል። በርግጥ ለሀገር ዕድገት እንቅፋት ይሆናሉ ብሎ ሲያስብ ፖሊሲዎችን ያወጣል። ነገር ግን እነዚህ ህጐችና ደንቦች ከማህበረሰቡ ሞራል ጋር አብረው አይሄዱም። ማህበራዊ ችግሮችን ለመቆጣጠርና ለማስወገድ የፖሊሲ(ህግ) መኖር ብቻ ለችግሩ መፍትሔ ሊሆን አይችልም። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን በአንድ ወቅት የፊሪንሳይ መንግስት አውጥቶ የነበረውን ፖሊሲ እንይ።

በአንድ ወቅት በፈረንሳይ ሃገር ሴተኛ አዳረነትን ለማጥፋት ህግ አውጥተው ነበር። እ.ኤ.አ. በ1938 ዓ.ም. የፈረንሳይ መንግስት ባስተላለፈው ትዕዛዝ መሰረት በአገሪቱ ውስጥ ያሉ ዝሙት የሚፈፀምባቸው ቤቶች ተዘጉ። ይህ ትዕዛዝ የሴተኛ አዳሪ ቤቶችን አስዘጋ እንጂ ከቀድሞ ኑሮአቸው የተሻለ ኑሮ እንዲኖሩ ምንም መንገድ አልቀየሰም። ለአንድም ሴተኛ አዳሪ ሥራ አልሰጠም፤ በመሆኑም እነዚህ ሴተኛ አዳሪዎች ኑሮአቸውን ለመግፋት ሲሉ የሴተኛ አዳሪነት ሥራቸውን ከቀድሞው በስፋ ሁኔታ ማካሄድ ጀመሩ። ይህም የሚያመለክተው የዝሙት ቤቶችን መዝጋትና የሴተኛ አዳሪዎችን ማውገዝ አዲስ አይነት ሴተኛ አዳሪዎች እንዲፈጠሩ ምክንያት ሆነ እንጅ ምንም አይነት ለውጥ አለማምጣቱን ነው።

ወደ ሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ስንመጣ ለወጣቱ የተለያዩ ፖሊሲዎች መቀረጻቸው ይታወቃል። ነገር ግን አንዳንዶቹ የሀገራችንን ወጣቶች የኑሮ፣ የሥራ ባህል እና የትምህርት አቅም ያገናዘበ እና የሚያመዛዝኑ አይመስለም። ስለዚህ አንድ ፖሊሲ በሚቀረጽበት ጊዜ የአፈፃፀሙን ሁኔታ ትኩረት የሚሰጥ፣ ወጣቱን ከሥራ-አጥነት የሚያላቅቅ እና የተለያዩ የወጣቱን ችግሮች መቀረፍ የሚችል መሆን አለበት እንላለን።

5. ወጣቱና መሰናክሎቹ

ወጣቶች ከጠቅላላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ከፍተኛውን ክፍል እንደሚይዙ በተለያዩ ዓመታት የተካሄዱ የህዝብ ቆጠራዎችና ትንበያዎች ያሳያሉ። ለአብነትም በ1997 ዓ.ም. በተደረገው ትንበያ መሠረት የኢትዮጵያ ሕዝብ ብዛት ወደ 73 ሚሊዮን እንደሚያሻቅብ፣ የወጣቶች ደግሞ 28.4% (14.4% ወንድ እና 14% ሴት) እንደሚሆን እና ከነዚህም መካከል 5.3% በከተማ፣ ቀሪው ደግሞ 23% የገጠር ወጣቶች እንደሚሆኑ ተገምቷል። ይህን ያህል ግምት ያለው የወጣት ኃይል ግን የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ስነልቦናዊ እና ፖለቲካዊ ችግሮች ሰለባ ሆኖ ይገኛል። ይህም በአገራቱ የልማት እንቅስቃሴ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ አለው።

የወጣቱን ችግር በተለያዩ ጥናቶች እንደተመለከትነው ዘርፈ - ብዙ እና የተለያየ መልክ እና ባህሪይ ያላቸው ናቸው። ይህም ባህርይ የሚመነጨው የችግሮቹ መንስኤ የሆኑት ምክንያቶች የተለያዩ መሆናቸው ነው። እነኝህን የተለያዩ ችግሮች በአራት ዋና ዋና ክፍሎች መለየት ይቻላል። እነኝህም:- ኢኮኖሚያዊ ችግሮች፣ ማህበራዊ ችግሮች፣ ስነልቦናዊ ችግሮች እና የጤና ችግሮች፣ ናቸው።

5.1 ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች

በአብዛኞቹ ምሁራን እንደተጠቀሰው ዋነኛው የወጣቶች ኢኮኖሚያዊ ችግር ሥራ አጥነት ነው። ወጣት ሴቶችና ወንዶቹ ከትምህርት ዓለም ወደ ሥራ ዓለም ለመግባት የሚያደርጉት ሽግግር ያለወላጆቻቸው ረዳትነት፣ የራሳቸውን ሕይወት በራሳቸው መምራትና ማስተዳደር የሚጀምሩበት ጊዜ በመሆኑ የመሸጋገሪያ እርከን ነው። ወጣትነት በራስ የመተማመን እሴት የሚገነቡበትና ኃላፊነት እምብዛም የሌለበት ወቅት በመሆኑ ወሳኝ የለውጥ ደረጃ ተደርጐ ይቆጠራል። በዚህ የሽግግር ወቅት ወሳኙ ነጥብ (factor) ወጣት ልጆች ሥራ ማግኘት ወይም አለማግኘታቸው ነው። ወጣቶች ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁ ሥራ የማግኘት ዋስትና

ከሌላቸው የሚያስከትለው ተዕዕኖ ኢኮኖሚያዊ ብቻ ሳይሆን ማህበራዊና ስነ-ልቦናዊ ጭምር ይሆናል::

በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የወጣቶችን ስራ አጥነት መጠን በተመለከተው

ከ 15-19 = 11.1%
ከ 20-24 = 12.7%
ከ 25-29 = 9%

በአጠቃላይ 33 በመቶ ግድም እንደነበር በ1999 የተካሄደው የስራ ቅኝት ጥናት ያመለክታል::

የአገራቱ የሥራ አጥ ቁጥር በጾታ ስብጥር ሲታይ ደግሞ የሴት ወጣቶች ስራ አጥነት ችግር ከወንድ ወጣቶች ጉልቶ ይገኛል:: በ1999 የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው የሴቶች የስራ አጥ መጠን በመቶኛ ሲሰላ እንደሚከተለው ነው::

ዕድሜ	የሴቶች	የወንዶች
15-19	16.8%	6.4%
20-24	17.8%	7.4%
በጠቅላላው	**34.60%**	**13.80%**

ይህም የሆነበት ምክንያት በግምት እንደተመለከትነው ሴቶች በአብዛኛው ምርታማ ባልሆኑ በተለያዩ የቤት ውስጥ ስራዎች ስለሚሰማሩና ወደ ትምህርት ዓለም ገብተው እንደ ወንዱ ወጣት እኩል ለመሳተፍ በአብዛኛው የተነፈገ በመሆናቸው ነው:: በአጠቃላይ መልኩ ስናየው የወጣቶች የስራ አጥነት መንስኤ የሚከሰትበት ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው::

5.1.1 ኢኮኖሚያዊ ኋላቀርነት

የኢትዮጵያ ወጣቶች ችግር በዋነኝነት የሚመነጨው ከኤኮኖሚ ኋላቀርነት እንደሆነ ለማንም እንግዳ ነገር አይደለም:: ይህ ደግሞ ለድህነት ዳርጎናል:: ድህነት ተስፋ የመቁረጥን ስሜት ሊፈጥር ይችላል:: በተዘዋዋሪም ሆነ በቀጥታ የኢኮኖሚአችን አለመዳበር ወጣቱን በከፍተኛ ሁኔታ ተዕዕኖ አሳድሮበታል::

5.1.2 የመዋዕለ-ንዋይ (የኢንቨስትመንት) አለመስፋፋት

ኢንቨስትመንት ለእድገት ያለው ሚና ይሄነው ብሎ ለመግለጽ ያዳግታል:: በአገራችን የኢንቨስትመንት አለመስፋፋት፣ ወጣቱ ጊዜውን በማይረባ ነገር እንዲያሳልፍ፣ ሥራ ላይ እንዳያውል፣ ወደ መጥፎ ተግባራት እንዲሰማራ፣ በማድረግ የራሱ አስተዋጽኦ አለው ብለን እናምናለን::

5.1.3 ወጣቶች አግባብ ያለው ትምህርት እና ስልጠና ያለማግኘት

ትምህርት ለአንድ አገር የእድገት መሠረት እንደሆነ ሁል ጊዜ በጆሮአችን የምንሰማው፣ በዓይናችንም የምናየው፣ እውነታ ነው::

ይህንን ትምህርት በተግባር ላይ ሊያውል የሚችል ክፍል ወጣት ነው። ወጣቶች በሀገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ንቁ ተሳታፊ እና በልማት እንቅስቃሴዎች ውስጥ የተሻለ ተሳትፎና ተጠቃሚ እንዲሆኑ የሚሰጠው ትምህርት መሠረታዊ ዕውቀት በማስጨበጥ እና የማሰብ አድማሳቸውን በማዳበር ጉልህ ሚና አለው።

የሚሰጠው ትምህርት ንድፈሀሳብ ማለትም፣ በመማህፍት እና በመጽሔቶች ላይ የሰፈረውን ማወቅ ብቻ ከሆነ ልማት በሚጠይቀው መንገድ መሥራት የማይቻል ሆኖ እናገኘዋለን። ከዚህም በመነሳት ትምህርት ለልማት ወይም ለእድገት መሠረት ሊሆን የሚችለው በንድፈሀሳብ የተሰምነውን በተቻለ መጠን በተግባር ደጋግመን ስንፈትሽ ነው። በመሆኑም ወጣቱ ትውልድ በአካባቢው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ባህላዊ ግንባታዎች ላይ ለመሳተፍ እንዲችል በቂ ሁኔታዎች የተመቻቹለት አይመስለም። በዚህ ሁኔታ አመራች እና ብቁ ዜጋ ማፍራት ያዳግታል።

የአንዲት ሀገር የትምህርት ፖሊሲ በሚቀረጽበት ጊዜ የሀገሩን አቅም፣ የእውቀት ደረጃ፣ የህብረተሰብ ተሞክሮ እና የሥራ እድል የሚያመቻች እና በአጠቃላይ ሀገሪቷ ከነበረባት ከርፈ-ብዙ ችግሮች የሚያላቅቅ መሆን አለበት። ወደ አገራችን ስንመጣ ይህ ሁኔታ ብዙም አይታይም። ወጣቱን አግባብ ያለው እውቀትና ክህሎት የማያስጨብጥ እና የህብረተሰቡን ተሞክሮ ያላገናዘበ የትምህርት ፖሊሲ መኖሩ የሀገሩን ኢኮኖሚ ወደታች ከመገሥተቱም በላይ በትውልድ ዘንድ አደጋ ጥሎ ያልፋል። ሀገራችን ደግሞ የዚህ ሰለባ ሆናለች የሚል ግንዛቤ አለን።

5.1.4 የሥራ ባህል በወጣቱ ባህላዊና ስነ-ልቦናዊ ይዘት አለማዳበር

ወጣቶች የተረጅነትን ስሜት አስወግደው ራሳቸውን የሚችሉበት መንገድ መመቻቸት አለበት። ይህ ደግሞ የሚመጣው ሥራን ባህል አድርጎ፣ ጊዜን በአግባቡ ተጠቅሞ፣ ማንኛውንም የሥራ አይነት በመስራት ነው። ሥራን የመናቅ መንፈስን አስወግዶ፣ ሁል ጊዜ ይህንን መስራት አለብኝ እያለ ሥራን የደም ስር አድርጎ ከተንቀሳቀደሰ፣ ወጣቱ ሥራ ፈጣሪ፣ የግዜን ምንነት አዋቂ፣ እና፣ ሁል ጊዜ ደስተኛ፣ ሆኖ መኖር ይችላል። የአገራችንን ካባራዊ ሁኔታ ስንዳስስ ግን ይህ የሥራ ባህል አለመኖር ለኢኮኖሚያዊ ችግሮች ዋነኛ ተጠቃሽ መንስኤ ነው ብለን እንገምታለን።

5.1.5 የአንፎርሜሽን እና ህዝብ መገናኛ ዘዴዎች አለመስፋፋት

እንደሚታወቀው የኢንፎርሜሽን እና የህዝብ መገናኛ ዘዴዎች ምን ጊዜም ለኢኮኖሚ እድገት ብቻ ሳይሆን ለማህበራዊና ለፖለቲካ እንዲሁም ለቴክኖሎጂ እድገት ማስተላለፊያ እና ማስፋፊያ መንገዶች ናቸው። የህዝብ መገናኛ ዘዴዎች የማስተማርያ፣ የማሳወቂያና የመዝናኛ መሳሪያ ከመሆናቸው ባሻገር ህዝብን እርስ በርሱ በሃሳብ በማገናኘት እና በማቀራረብ፣ በመንግስትና በህዝብ መካከል የማያቋርጥ የኢንፎርሜሽን፣ የሃሳብና የአስተያየት ችሎታ ላይ የተመሰኑ በመሆኑ ህዝቡ አእምሮውና ችሎታው በሚገባ ካልዳበረ የማቴሪያል፣ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የማህበራዊ እና የባህል፣ ዕድገት ይገኛል ማለት አስቸጋሪ

ወደ አገራችን ስንመጣ የኢንፎርሜሽን እና የህዝብ መገናኛ ዘዴዎች አለመስፋፋት ለወጣቱ መንፈላዊና ስነልቦናዊ እወቀት አለመዳበር አንዱ ምክንያት መሆኑን እንገምታለን::

ከላይ በተገለጹት እና በሌሎችም በርካታ ምክንያቶች የኢትዮጵያ ወጣቶች በስፋትና በጥልቀት ለተባባሰ የሥራ አጥነት ችግር ተጋልጠው ይገኛሉ:: በዚህም ምክንያት አገራቱ ከወጣቱ የምትጠብቀውን ምርታማነት እና የዳበረ ጥቅም ለማግኘት ሳትታደል ቆይታለች::

5.2 ሌሎች ማህበራዊ ችግሮች

የወጣቶች ሌሎች ማህበራዊ ችግሮች ዘርፈ ብዙ የሆነ ንዑስ ክፍል ነው:: እነዚህም በማህበራዊ ሕይወታቸው ወጣቶች ሀገር ገንቢና አምራች ዜጐች እንዳይሆኑ የሚያግዷቸው አደንዛዥና እጽ፣ አልኮል መጠጥ፣ የጐዳና ተዳዳሪነት፣ የወጣት አጥፊነት፣ ወንጀልና ወንጀለኝነት እንዲሁም የሴተኛ አዳሪነት ናቸው::

5.2.1 አደንዛዥና ዕጽ

አደንዛዥና እጾች የሚባሉት በጥጥር፣ በፋሳሽ፣ በጭስ ወይም በትነት በቀጥታ ወደ ሰውነት ተዋህደው የወጣቱን አእምሮ በማደንዘዝ መደበኛውን የተፈጥሮ ዑደት የሚያቃውሱ ነገሮች ናቸው:: ሲጋራ እና ጫት ዋነኛዋቹ የወጣቱን ምርታማነት የሚያውኩ ጥጥር ነገሮች፣ አደንዛዥና ዕጾች፣ ናቸው:: የሲጋራ ተጠቃሚ ወጣቶች ከዕለት ወደ ዕለት እየጨመረ እንደመጣ የሚያሳይ መረጃዎች አሉ:: ከሲጋራ ጎን ለጎን ደግሞ የጫት ተጠቃሚ ወጣቶች ቁጥር በየጊዜው በፍጥነት የመጨመር አዝማሚያ አሳይቷል:: ከአንዳንድ ጥናቶች እንደሚታየው በአዲስ አበባ ከተማ ካሉ ወጣቶች 20% ገደማ የማጨስ ልምድ ያላቸው እንደሆኑ ያመለክታል::

የማደንዘዝ ኃይላቸው ከፍተኛ የሆኑት እንደ ሃሺሽ፣ ኦፒየም፣ ማሪዋና፣ ኮኬይን እና ሄሮይን ሲሆኑ በየከተማው ማዕከል የወጣቶችን ህይወት ሲበክሉ ይታያል:: በተለይ በጐዳና ተዳዳሪዎች ላይ የሚታየው ችግር ቤንዚን መሳብ ሆኖ እናገኘዋለን:: በባህላዊ መልክ በስፋት የማጠቀሙት የእፀፋሪስ ተክልም ቢሆን ከዘመናዊ ዕጾች ባላነሰ በወጣቱ ዘንድ ተስፋፍቶ ይገኛል::

5.2.2 አልኮል መጠጥ

የአልኮል ተገዥነት ለላው ዋነኛ የወጣቶች ችግር ሆኖ ይገኛል:: ከባህላዊ መጠጦች፣ ጠላ፣ ጠጅና አረቂ፣ ጅምሮ እስከ ዘመናዊ መጠጦች ድረስ በወጣቱ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ ተጽዕኖ እንዳላቸው እናያለን:: ወጣቱ ለአልኮል ተጠቂ የሆነበት አንዱ ምክንያት በሀገሪቱ ወጣቶች ለአልኮል መጠጥ ብቱ የሚሆኑበት የዕድሜ ክልል የሚደነገግ ህግ ባለመኖሩ ነው::

በመሆኑም አልኮል መጠጥ በወጣቱ ላይ እያስከተለ ያለው ችግር ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተስፋፋና ለሀገሪቱ ሊያበረክቱ በሚችሉት አስተዋጽኦ ላይ ተዕዕኖ እያደረገ ይገኛል::

5.2.3 የጐዳና ተዳዳሪነት

የጐዳና ተዳዳሪነት ትግር ወጣቱን ከሚያጠቁት ዋና ዋና የማህበራዊ ጠንቆች አንዱ ነው። በአብዛኛው ወጣቶችን ወደ ጐዳና ተዳዳሪነት የሚያመሩ ከቤተሰብ (ከአሳዳጊ) ኢኮኖሚያዊ፣ ሥነልቦናዊ እና ማህበራዊ ሁኔታ የሚመነጩ ትግሮች ሆነው ይገኛሉ።

ከነዚህም ከቤተሰብ ወይም ከአሳዳጊ ጋር የተያያዙ ትግሮች መካከል፦

- የወላጆች ከሥራ መፈናቀል
- ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ፍልሰት
- የቤተሰብ ድህነት ሁኔታ
- የቤተሰብ መለያየት (ፍቺ) እና
- የባልና ሚስት ጥቃት (violence) ዋናዎቹ ናቸው።

በባልና ሚስት መካከል ያለው ትግር በመዲናችን በአዲስ አበባ ከተማ ከሌሎች የሀገራቱ ክፍሎች የከፋ እንደሆነ ጥናት ያመለክታል። በአዲስ አበባ ለናሙና ከተወሰዱት 4500 ተጠኚዎች 55 በመቶው እድሜያቸው 3-17 ዓመት የሚደርስ ሕፃናትና ወጣቶች ሲሆኑ እነርሱም በባልና ሚስት ጥል ምክንያት የተፈናቀሉ መሆኑ ታውቋል።

የወጣቱ ሥነ-ልቦናዊ ትግሮች የጎዳና ተዳዳሪነትን በማስፋፋት ረገድ ሌላኛው ከፍተኛ ትግር ነው። በዚህ ረገድ የእኩያ ተፅዕኖ (peer influences) ወይም ሥነ-ልቦናዊ አለመረጋጋት ዋነኞቹ መንስኤዎች ናቸው።

የጐዳና ተዳዳሪ ወጣቶች ለፀረ-ማህበረሰብ ድርጊቶች ተጋልጠው ይገኛሉ። ሲጋራ፣ ጫት እና ሌሎች አደንዛዥ እጾች እንዲሁም አልኮል ከሚጠቀሙ ወጣቶች መሀከል ዋነኞቹ የጐዳና ተዳዳሪ ወጣቶች ናቸው። ለወጣት አጥፊነት ተጋልጠውም የሚገኙት እነዚሁ የጐዳና ተዳዳሪዎች ናቸው።

5.2.4 ወጣት አጥፊነት

ይህ የወጣት አጥፊነት ትግር በተወሰነ የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ላይ የሚታይ የፀረ-ማህበረሰባዊ ድርጊትና የወንጀል ተግባሮች ናቸው። ህብረተሰቡ በማይቀበለው መንገድ ህይወታቸውን ከሚመሩት ውስጥ የወጣት አጥፊዎች በመጀመሪያ ረድፍ የሚቀመጡ ናቸው። ዕድሜያቸው ከ18 ዓመት ያልዘለለ ወጣቶች ወንጀል ፈጽመው ሲገኙ በወጣት አጥፊነት ይመደባሉ። የሚወሰደውም የህግ እርምጃ ከአዋቂ አጥፊዎች ወይም ወንጀለኞች የተለየ ነው። የዚህን መሰል ድርጊት የሚፈጽሙ ወጣቶች ከስብዕና (personality) አለመስተካከል እና ከአስተዳደግ (socialization) ግብዓቶች ጉድለት የመነጨ ነው።

በግምት በርካታ ቁጥር ያላቸው ወጣት አጥፊዎች ዝቅተኛ ገቢ ካላቸው የህብረተሰቡ ክፍል የወጡ ናቸው። ድህነትና ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት ለወጣት አጥፊነት እንደዋነኛ መንስኤ ቢቆጠርም ከወላጅና ከህብረተሰብ አያያዝ ጉድለት የተነሳ ችግሩ ሊፈጠር ይችላል። ይህ የወጣት አጥፊዎች ቁጥር ከቀን ወደ ቀን እያደገ እንደሄደ መመልከት ይቻላል።

5.2.5 ወንጀልና ወንጀለኝነት

ወንጀልና ወንጀለኝነት የሚያመለክተው በህግ በተደነገገ የወጣትነት የዕድሜ ክልል የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚፈጽሙት ህገ-ወጥ ተግባሮች እና ወንጀሎች ናቸው። ወንጀለኝነት በወጣቱ ዘንድ ተስፋፋቱ ከሚገኘው የቡድን ፀብ ተለይቶ የሚታይ ችግር አይደለም። ወንጀለኝነት ከወጣት አጥፊነት የሚለየው የሁለቱ የዕድሜ እርከን የተለያየ መሆኑ ነው። ወጣት አጥፊነት የሚታየው ከ9-17 ዕድሜ ባሉ ታዳጊዎች ላይ ሲሆን ወንጀለኝነት ግን ለመምረጥ እና ህጋዊ መብት ለመውሰድ ለአቅም የደረሱ ከ18 ዓመት በላይ ባሉ ወጣቶች ላይ ነው።

5.2.6 ሴተኛ አዳሪነት

የጾታ ንግድ በአብዛኛው የወጣቱን የተፈጥሮ ባህርይ ወደ አጥፊነት ከሚያሸጋግሩ ተግባሮች አንዱ ነው። በመዲናችን ብቻ ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ወጣት ሴቶች በጾታ ንግድ ተግባር ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። ይህ የወጣቱን ምርታማነትና የወደፊት የሀገሪቱን አደራ ለመቀበል ያለውን ብቃት የሚያዳክም ተግባር ነው።

ለጾታ ንግድ ዋነኛው መንስኤ ከሌሎች ማህበራዊ ጠንቆች ጋር በጉልህ ተቆራኝቶ መገኘት ነው። እነዚህም ያለ ዕድሜ ጋብቻ፣ ከገጠር ወደ ከተማ ፍልሰት፣ የወጣት ሴቶች ሥራ አጥነትና ተገቢውን የትምህርት አገልግሎት አለማግኘት፣ ሆነው እናገኛቸዋለን። ይህም የጾታ ንግድ ችግር በከተሞች አካባቢ በስፋት የሚታይ ጉልህ ችግር ሆኖ ይገኛል። በሀገራችን ነበራዊ ሁኔታ HIV/AIDS ና ሌሎች የአባለዘር በሽታዎች መስፋፋት ዋነኛውን ሚና እየተጫወተ የሚገኘው ቁጥራቸው በርካታ የሆኑ ወጣቶች በጾታ ንግድ ላይ ተሰማርተው ስለሚገኙ ነው።

5.3 የጤና ችግር

የጤና ችግሮች የሚያመለክቱት በወጣቱ ላይ የሚከሰቱ አካላዊ (physiological) እክሎችንና ተዛማጅ የጤና ቀውሶችን ነው። በተጨባጭ የኢትዮጵያን ሁኔታ ስናይ ወጣቱ ለተለያዩ የጤና ችግሮች ተጋልጦ ይገኛል። ከነኝህ የጤና ችግሮች ዋነኛው HIV/AIDS ሲሆን ሌሎች በግብረ ሥጋ ግንኙነት የሚተላለፉ የአባለዘር በሽታዎች፣ ጽንሰ ማቋረጥ፣ ያልተፈለገ እርግዝና እና ሌሎች ተመሳሳይ ችግሮች ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በወጣቶች መሃል በስፋት የሚገኘው የጤና ችግር ዋነኛ ምንጩ መሠረታዊ የሥነ-ተዋልዶ አገልግሎት እና የጾታ ትምህርት ከማጣት የመነጩ ናቸው።

HIV/AIDS ከዕለት ወደ ዕለት ከፍተኛ የጤና ችግር ከመሆን አልፎ የሀገሪቷን የልማት እንቅስቃሴ ችግር ላይ በመጣል ላይ ይገኛል። HIV/AIDS ወረርሽኝ በተለይ በወጣቱ ላይ በስፋት ይታያል። በሀገሪቱ ውስጥ HIV ወረርሽኝ 85 በመቶ የሚደርሰው ዕድሜያቸው ከ14-29 በሆኑ ወጣቶች ላይ ነው። ይህ ቁጥር እየጨመረ እንደሆነ የሚያሳይ መረጃም አለ።

ሌሎችም የአባላዘር በሽታዎች በአብዛኛው ወጣቶች ላይ በከፍተኛ ሁኔታ ተፅዕኖ እንዳላቸው በጉልህ ይታያል። ከዚህ በተጨማሪ ወጣት ሴቶች ላይ የሚታየው ጉልህ ያልተፈለገ ዕርግዝና፣ የጽንስ ማቋረጥ፣ እና የለጋ ህፃናት በየመንገዱ መጣል የመጡት በዚሁ መሠረታዊት የሥነ-ተዋልዶ ትምህርቶችና የጤና አገልግሎቶች ለወጣቱ በተገቢው በለመድረሳቸው ነው።

5.4 ስነ-ልቦናዊ ችግር

የወጣትነት የዕድሜ ክልል በህፃንነት እና በአዋቂነት የዕድሜ ዕርከን መካከል የሚገኝ የሽግግር ዘመን ሲሆን በዚህ የዕድሜ ክልል ወጣቶች የተለያዩ የአስተሳሰብና የሥነ-ልቦና ለውጦች ይታዩባቸዋል። የሁሉም ፍላጐቶች ተጣጥሞ ባለመገኘት ምክንያት ወጣቶች ለተለያዩ የሥነ-ልቦና ችግሮች ተጋልጠው ይገኛሉ። እነዚህ የሥነ-ልቦና ችግሮች አለመረጋጋት ለማጎበረሰቡ ደንብ፣ ባህል፣ እንዲሁም ለተለያዩ ወገኖች ተገዢ ያለመሆንን ያስከትላል። በተጨማሪም ማህበረሰቡ ከሚከተለው የሥርዓት ጐዳና ማፈንገጥ እና ከማህበረሰቡ እስከ መገለል የሚያደርስ የጐላ ተፅኖ አለው። በዚህም የተነሳ ወጣቱ ለተለያዩ የባዕድ ባህል ተጋልጦ የባህል ቅኝ ተገዢነት ዋነኛ ተጠቂ ይሆናል።

ከዚህ ጋር ተያያዥነት ያለውን ነገር ለመጥቀስ በሀገራችን ወጣቶች በተለይም ከተሞች መሐከል ጐልተው ከሚታዩ የሥነ-ልቦና ችግሮች ዋነኛው በምዕራባዊያን ባህል ተገዥ (Identity crises) መሆንና የራሳቸውን ባህል የመናቅ ችግር ነው። ሌላው ደግሞ ሀገራችንን በድህነት አረንቋ እንድትዘፈቅ ያደረጋት ሥነ-ልቦናዊ እንከን ተገቢ የሆነ የሥራ ባህል በወጣቱ መካከል መጥፋት ነው። የስንፍናና የተስፋ መቁረጥ ችግሮች ወጣቱ ለምንም ዓይነት የልማት እንቅስቃሴዎች እንዳይነሳሳ አድርገውታል።

6. ማጠቃለያ

ወጣቱ ለአንድ ሀገር የመሠረት ድንጋይ ጥሎ የሚያልፍ የጎበረተሰብ ክፍል ነው። በዚህ እርከን የሚገኙ ወጣቶች ከማንኛውም ጎበረተሰብ የበለጠ የመሥራት ችሎታ ያላቸው፣ እምቅ ውሳጣዊ ሐይል የተላበሱ፣ ለለውጥ ዝግጁ የሆኑ፣ እንዲሁም ለአጠቃላይ ለሀገር ልማት በተጠሩ ጊዜ ደራሾች ናቸው። ታዲያ እነዚህ ወጣቶች አስፈላጊ የሆነ የሀገር ዕድገት እንዲያመጡ ቤተሰብ፣ መንግስት፣ ማህበረሰብ እና ትምህርት ቤቶች የራሳቸውን ድርሻ በተቀናጀ መልኩ ሊወጡ ይገባል እንላለን።

«ድር ቢያብር አንባሳ ያስር» እንዲሉ ከላይ የተጠቀሱት አካላት ወጣቶች አላስፈላጊ ነገሮች በሚያከናውኑበት ጊዜ እኔን አይመለከተኝም ማለትን ማቆም አለባቸው፤ የአንዲት አገር እድገት የሁሉም ሰው የቅንጅት ተግባር ነውና! በዓለማችን በኢኮኖሚ የበለፀጉ አገሮች ዛሬ፡ አንቱ የተባሉት በአንድ እጅ በማጨብጨብ አይደለም። የነበረባቸውን ችግር በማየትና በመገምገም፣ አምራቹንና ትኩሱን ሐይል በሚፈለግበት ጊዜና ቦታ በመጠቀም ነው። የአገራችን ወጣቶች ግን በአሁኑ ጊዜ ለአገራቸው ዕድገት ሊያበረክቱ የሚችሉትን ያክል አላበረከቱም። ለዚህም ዋና ዋና ተጠቃሽ ምክንያቶች ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ጤና እና ስነ-ልቦናዊ ችግሮች ናቸው።

ወጣቱ የነገው የሀገር ተረካቢ በመሆኑ፣ ምንም እንኳ የተለያዩ ችግሮች ቢኖሩበትም፣ እነዚህን ችግሮች ተቋቁሞ አትም በፈተደ መጠን አንድ እርምጃ ወደፊት መራመድ አለበት። አራሱን ለታላቅ ግዳጅ ማዘጋጀት ጠቃሚ ቦታ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነውና።

በአጠቃላይ፣ ወጣቱ ለልማት እራሱን አዘጋጅቶ የሚጠበቅበትን በመሥራት ለመጪው ትውልድ መሠረት የሚሆን የመንፈስ ጥንካሬን ትቶ ማለፍ አንዱ የስኬት ቁልፍ ነው እንላለን።

7. ርዕይ

7.1. እኛ ወጣቶች ያሉን መሠረታዊ ፍላጐቶች ተሟልተው፣ ችግሮቻችንን ለዘለቄታው መፍታት የምንችልበት መንገድ ተቀይሶልን፣ ገዝባሌዎቻችንን እና ተሰጠአችንን የምናጐለብትበት፣ ህያው ከሆነ ሁኔታዎች ጋር እራሳችንን ማጣጣም የምንችልበት ርግራሞች እና አካሄዶች፣ ወጣቱን ከማራራቅ ፈንታ ሊያቀራርብ የሚችል ሥርዓት በሀገራችን ተገንብቶ፣ ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ሲተገበር፣ ማየት እንሻለን።

7.2. እነዚህን ከላይ የጠቀስናቸውን ነገሮች በተሟላ መልኩ ለመተግበር ወላጆች፣ ትምህርት ቤት፣ ማህበረሰብ እና መንግስት እንዲሁም መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋማት ወሳኝ ሚና እንዳላቸው እንገምታለን። ይህንን ሰንል በተለይ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብና መንግስት ወጣቱን በመገንባት አንባር ትልቁን ድርሻ ይዘው እንደሚገኙ እናስባለን። እነዚህ አካላት ለወጣቱ ትልቅ ትኩረት ሰጥተው፣ ወጣቱ ይበልጥ ፍሬያማ ሊሆን የሚችልበትን መንገድ ቀይሰው፣ ከወጣቱ ጋር ቅንጅት በመፍጠር፣ አገራችንን ለማልማት በአንድነት ሲንቀሳቀሱ ማየት እንመኛለን።

7.3. በተለይም በአሁኑ ሰዓት ወጣቱን በይበልጥ ለማንቃት አቅመና ስልጣኑ ያለው በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋማት እጅ ነው። እነዚህ ክፍሎች በፋይናንስ፣ በቴሳቴስ እና በትምህርት ወጣቱን የማነጽ ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው ብለን እናስባለን። ይህንን ስንል መንግስት የአገራችንን የሥራ አጥ ቁጥር በመቀነስ፣ የወጣቱን የሥራ ፈጠራ ክህሎት ማዳበር የሚችልበትን መንገድ በተለይም ተስማሚ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች ፈጥሮ ማየት እንሻለን።

7.4. የዛሬ 2020 በኢትዮጵያ ወጣቱ በነባ የመደራጅት መብቱ ሙሉ በሙሉ በተግባር ተረጋግጦለት፣ እርሱም መብትና ግዴታውን በወል ተገንዝቦ፣ በዘር፣ በሐይማኖትና በለለች ምክንያቶች የማይታመስበት፣ እርሱም በአካባቢው ካሉት ክፍሎች ጋር ጥሩ ሥነ-ምግባር የተሞላበት ግንኙነት ፈጥሮ ለራሱ፣ ለቤተሰቡ፣ ለማህበረሰቡ እና ለሀገሩ ከፍተኛ ሥራ ያበረክታል የሚል ጽኑ ዕምነት አለን።

7.5 ወጣቶች ከላይ ከተጠቀሱት አካላት ጋር በመሆን የሚጠበቅባቸውን ሠርተው (ፍሬ አፍርተው) ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ት/ቤት እና መንግስት የሚተማመኑባቸው በቂ ዜጋ መሆናቸውን አስመስክረው፣ በተለይ ደግሞ ወጣቶች የቤተሰብ፣ የማህበረሰብ እና የትምህርት ቤት ውጤት እንደሆኑ የሚነገርበት ዘመን መጥቱ ማየት እንሻለን።

ወጣቶች ከራሳችን የማጠበቅብንን ሁሉ ለማድረግ ሀገራችን ከኛ ብዙ ነገሮችን እንደምትሻ በመገንዘብ ያለብንን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ለመፍታት ለሚከሰቱት ማናቸውም ድርጊቶች የፍርሃትን በር በመዘጋት፣ የምንቸገረኝነትን ስሜት አስወግደን፣ እኛው እራሳችን ለችግሮቻችን መፍትሄዎች ፈላጊ፣ ቀያሽ እና ተሰሚ ሆነን፣ በ2020 አገራችን ዛሬ ካለባት የድህነት አረንቋ ውጭ ማየት እንመኛለን።

ዋቢ መፃህፍት/ BIBILIOGRAPY

- Bahru Zewdie (1991) Modern Ethiopian History 2nd ed. AAU Press. Addis Ababa.
- Encyclopedia Americana (1987). vol. 13
- Encyclopedia Britannica (1985). vol 23
- Internet
- Population Census (1994). Addis Abeba
- Estimated Population Census (1999). Addis Abeba
- Slavin. R. (1986) Educational Psychology. Engle Wood Cliffs. New Jersey
- Sprental H. (1975) Personality. New York
- በአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር የተዘጋጀ ጥራዝ (1994)

ወጣቱ እና ልማት፤ ትናንት፣ ዛሬና ነገ በኢትዮጵያ ጽሑፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት

ክፍለማርያም ጌታቸው*

በዛሬው ዕለት ወጣት/ተማሪ ዘሪቱ ንዳ እና ጐጃም ቦጋለ «ወጣትና ልማት፤ ትናንት፣ ዛሬ እና ነገ በኢትዮጵያ» በሚለው ጽሁፋቸው ላይ አስተያየት እንድሰጥና ቤቱን ለወይይት የሚጋበዙ ሀሳቦችን እንድጠቁም ዕድሉን በማግኘቱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ማህበር ስም የተሰማኝን ደስታና አክብሮት ለመግለጽ እወዳለሁ::

የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለመያዎች ማህበር ይህንን መድረክ አዘጋጅቱ የችግሩን ባለቤት በመጋበዝ በመያወም ውስጥ ያሉ ባለመያዎችን በችግሩ ላይ ጥናት እንዲያቀርቡ እና በጥናቱ ላይ ማንኛውም አቅመና ችሎታው ያለው የሀገሪቱ ዜጋ በእኔነትና ይመለከተኛል በሚል አስተሳሰብ ሰፊ እና ግልጽ ውይይት በማድረግ ከዚህም መፍትሔዎች እንዲጠቁም ማህበሩ የያዘው ሰፊና ሀገራዊ ርዕይ እንዲቀጥልበት ድጋፍ ያስፈልጋል እላለሁ::

«ከመቀደም ይልቅ መቅደም» የሚለውን የአበው አነጋገር ብዙውን ጊዜ እመርጣለሁ:: ምክንያቱም በአሁኑ ሰዓት በተለይ ኢትዮጵያ አገራችን ችግር ቀድሟት እሷ ደግሞ ችግርን በመከተል ከችግር እና ከረሀብ ያልወጣች አገር መሆኗ የሚያሳስበኝ ነውና! ምንም እንኳን «ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል» እንደሚባለው አገራችንም ከፊቷ የተጋረጠውን የልማት፣ የፖለቲካ እና ማህበራዊ ችግር በዘገምተኛ ጉዞ የምትፈታው ቢሆንም በእጅጉ ሊተኮርበትና ሊበረታታ ይገባዋል ባይ ነኝ:: ይህን ካልኩ ዘንዳ ወደ ተሰጠኝ ተግባር ልመለስ::

ሁለቱ ጓደኞቼ «ወጣቱና ልማት፤ ትናንት፣ ዛሬ እና ነገ በኢትዮጵያ» በሚለው ጽሁፋቸው ላይ ያለኝን አስተያየት ለመስጠት ያመቸኝ ዘንድ አቀራረቤን በሦስት ክፍሎች ለማቅረብ እወዳለሁ:: በመጀመሪያው ክፍል የምናየው ሦስት ነገሮችን ይሆናል:: እነሱም ዐሀፊዎቹ ወጣትነት ምንድን ነው? ወጣቱና ልማት እንዲሁም የሌሎች አካላት ሚና በወጣቱ ህይወት ዙሪያ የሚለው ይሆናለ::

በክፍል ሁለት ዐሀፊዎቹ ባቀረቧቸው ቀሪ ጽሁፎች ላይ ማለትም ወጣቱና መስናክሎቹ፣ ማጠቃለያ ሀሳብ እና ርዕይ በተሰኙት ርዕሶች ዙሪያና በአጠቃላይ የጽሁፉ ይዘትና በአድማጭና በአንባቢ ላይ ያለውን አሳማኝነት እመለከታለሁ::

በክፍል ሦስት በጽሁፉ ላይ የሚጨመርና ይበልጥ ለወይይት ያመቻሉ የምላቸውን ሀሳቦች አቀርባለሁ::

---

* ወጣት ክፍለማርያም ጌታቸው በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ትምህርት ክፍል የአራተኛ ዓመት ተማሪ ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ህብረት አባል ነው::

በመጀመሪያው ክፍል ሀሀፊዎቹ በመግቢያቸው ወጣትነት ምንድን ነው? በሚለው ርዕስ ሥር፤ ወጣት የሚለውን ቃልና ዕንሰ-ሀሳቡን ያብራሩት እንደሚከተለው ነበር።

ወጣትነት የህይወት መሠረት፤ የአንድ ሀገር የዕድገት መሠረት እና እምቅ ኃይል ያለው ነው ብለዋል። ይህም የሚያመላክተውን ወጣትነት የጎጎት ስሜት የሚፈጠርበት፣ ለተግባር መነሣሣትና በተለያዩ የሙያ መስኮች ለመሠማራት የራስን አቅጣጫ የሚቀይስበት ጊዜ ሲሆን፤ ከዚህም በተጨማሪ የፈጠራ ክህሎት የሚያቀጠጥበት የእድሜ ዘመን ነው። ከዚህ ጋር በማያያዝ የወጣትነትን የዕድሜ ክልል በሀገራችንና በተለያዩ ሀገሮች አመልክተዋል። የወጣትነት የዕድሜ ክልል እንደየአገሩ ሁኔታ ይለያያል። ይህም የሆነበት ምክንያት አገሮች ካላቸው የተለያዩ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ ሁኔታዎች ምክንያት መሆኑን እንደሆነ ጠቁመዋል። በተያያዘ መልኩ ልማት የሚለውንም ቃል ለማስረዳት ሞክረዋል። ይህንንም የገለፁት ወጣቱ በፖለቲካ፣ በማህበራዊ እና በኢኮኖሚው የነበረውንና ያለውን ሚና በሦስት መንግስታት ዘመን በመከፋፈል ነው።

ፖ፤ የወጣቱን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴ ከአፄው አገዛዝ ጀምሮ እስከ አሁኑ መንግስት ድረስ ያለውን ሚና ጠቅለል ባለ መልኩ ለማሳየት ሞክረዋል። ይህንን በተመለከተ ከ 1953 ዓ.ም. ወዲህ ያለው ወጣት የነበረበትን ማህበረሰብ በማነቃቃት ከግለሰብ መብት አልፎ አገራዊ መብት እንዲነበር ለማድረግ የበቃ ትወልድ መሆኑን፣ ከነዚህም ውስጥ የመሬት ላራሹን ጥያቄና የብሔረሰቦችን እኩልነት ጥያቄ ማንሳቱ የሚጠቀሱ ናቸው። ከዚያም በ 1966 ዓ.ም. ወዲህ በነበረው ጊዜ ወጣቱ እርስ በእርሱ የተናቆረበት እና የትወልድ እልቂት የደረሰበት መቅት እንደነበር በግልፅ አስቀምጠዋል። ከ1983 ወዲህ ያለውን ወጣት በአጠቃላይ ስንመለከት፡ ከተድሞም፤ ጋር ሲነፃፀር በወረቀት ላይ በሰፈረው ዴሞክራሲያዊ ሀሳብ አማካኝነት በትንሹም ቢሆን ስለመብቱ ለመናገርና መብቱን ለማስከበር እየተንደፋደፈ ይገኛ ል። ይህንን ያልኩበት አንድ ምክንያት ልናገር።

ደሞክራሲያዊ ስርዓት ያራምዳሉ ከሚባሉ ሀገሮች አንዷ አገራችን ኢትዮጵያ ናት። እነዚህ ሀገራት በሀገ መንግስታቸው ካካተቷቸው መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች መካከል ስለመምረጥ እና መመረጥ መብት ድንጋጌዎች ናቸው። በዚህ መሠረት የኢ.ፌ.ድ.ሪ ህገ መንግስት በምዕራፍ 3 ከሚገልጻቸው መሠረታዊ ደሞክራሲያዊ መብቶችና ነፃነቶች መካከል በአንቀጽ 38 የተቀመጠ ስለ ዜጎች የመምረጥና የመመረጥ መብት ህግ አለ። በዚህ ህግ መሠረት ዕድሜው ለመምረጥ የደረሰ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ መምረጥ እንደሚችል ነው። የከፍተኛ ተቋማት ተማሪዎች የዚህ እድል ተጠቃሚ ለመሆን ሳይታደሉ ቆይተዋል። በአሁኑ የምርጫ ዘመን ግን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፡ ተማሪዎች ባደረጉት ተከታታይነት ያለው የመምረጥ ጥያቄ በምርጫ ቦርድ በኩል ተቀባይነት ሊያገኝ ችሏል። ይህም እጅግ ፈታኝ ከሆነ ጥረት በኋላ መሆኑ ሊጠቆን ይገባል።

በዚህ መልኩ የወጣቱን ፖለቲካዊ እንቅስቃሴዎች ለመዳሰስ ከቻልን በሚቀጥለው ርዕስ የወጣቱን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ እንመለከታለን። ሀሀፊዎቹ እነዚህን ሲያብራሩ ወጣቱ ሀገር ተረካቢ እና የማመጣውን ትውልድ የመቅረጽ ኃላፊነት ያለበት መሆኑን ተገንዝቦ በህብረተሰቡ ውስጥ በሚደረጉ ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ በመሳተፍ ለተተኪው ትውልድ የሚተላለፍ ቅርስ መከተል መቻል ይኖርበታል ይላሉ። ይህንን ሳያደርግ ቢቀር ለሚመጣው ማህበራዊ ተወስ እና ለአንዲት ሀገር ዕድገት ወድቀት እንደ ዋነኛ ተጠቃሽ ምክንያት ተደርጎ እንደሚቆጠር በዕውቀታቸው ላይ አስፍረዋል። ነገር ግን ለአንዲት አገር

ማህበራዊና የፅድንቷ ውድቀት ተጠቃሽ ሆኖ በዋነኛነት መቀመጡ አግባብ ነውን? ወጣቱ በአገራቱ ውስጥ ከሚኖሩት ማህበረሰቦች አንዱ አካል መሆኑ ግልፅ በሆንም የአንድ ሀገር ፅድንት እና ውድቀት ከተለያዩ ምክንያቶች ጋር ሊያያዝ ይችላል።

ከዚህ በተያያዘ መልኩ ወጣቱ የተረጅነትን ስሜት አስወግዶ አራሱን ሥራ ፈጣሪ መሆን እንዳለበት፣ ጊዜውን በአግባቡ የሚጠቀም የሥራ ፍላጐቱን አዳብሮ እና የአስተሳሰብ ድህነቱን መዋጋት መቻል እንዳለበት በጽሁፋቸው ላይ አስፍረዋል። ከዚህ በተጨማሪ የሌሎች አካላት ሚና በወጣቱ ህይወት በሚለው ጽሁፋቸው ውስጥ ወጣቱ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴው ገልፀ ሚና እንዲኖረው ከሚያደርጉት አካላት ውስጥ ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ት/ቤትና መንግስት ዋነኞቹ ናቸው። እነዚህ አካላት ወጣቱን በማንቃትና የወደፊት ህልውናውንና ስብዕናውን በመገንባት ደረጃ ቅልት አስተዋጽኦ አላቸው። ይህም የሚሆነው ግን ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ትምህርት ቤትና መንግስት በጋራ ግልጽ በሆነ መንገድ መነጋገርና ችግሮች ካሉ በጋራ ለመፍታት ጥረት ሲያደርጉ ብቻ ነው። በተለይ ችግሮቹን በመፍታት ረገድ ወጣቱ እራሱ፣ የራሱን ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ተነጋግሮ መፍትሄ የመሻት ልምድ ማዳበር አለበት። የዚህን አይነት አካሄድ መንግስት እና ማህበረሰብ እንዲያመቻቹ፣ ጸሀፊም፣ አግባብ ያለው ጥያቄ ጠይቀዋል።

ከፍል ሁለት ውስጥ ወጣቱና መሰናክሎች፣ በሚል የወጣቱን መሰናክሎች ከኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች፣ ከጤና ችግሮች፣ ከስነ-ልቦናዊ ችግሮች፣ አንባር ሰፊና በርከር ባለ መልኩ ተመልሟል። ከነዚህ ውስጥ በኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ችግሮች ከፍል የመዋዕለ ንዋይ (ኢንቨስትመንት) አለመስፋፋት፣ ወጣቱን አግባብ ያለው ትምህርትና ስልጠና እንዲያገኝ እንዳላስቻለው፣ የሥራ ባህል በወጣቱ ዘንድ አለመዳበር፣ የኢንፎርሜሽን እና ህዝብ መገናኛ ዘዴዎች አለመስፋፋት፣ በወጣቱ ሕይወት አሉታዊ ተጽእኖ አሳድረዋል ብለዋል። በተጨማሪም ወጣቱ ለአደንዛዥ ዕጽ ተጠቃሚነት፣ የአልኮል ሱሰኝነት፣ ሱሰኛ አዳሪነትና እና ወደ ወንጀለኝነት ለማዘንበል መነሻዱን አመላክተውናል። በመጨረሻም ዐሀፊም፣ በማጠቃለያቸው እና በርዕያቸው እንደሚከተለው ብለዋል። ወጣት አስፈላጊ የሆነውን አከናማያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ለውጥ እንዲያመጣ መንግስት፣ ማህበረሰብ፣ ት/ቤትና በተሰብ የራሳቸውን ድጋፍና ድርሻ በተቀናጀ መልኩ ለያበረክቱ ይገባል ብለዋል። «ድር ያበጠር አንበሳ ያስር» ነው፣ በወጣቱ ህይወት ዙሪያ ገልህ ሚና ያላቸው አካላት በአንድነት ከወጣቱ ጋር በመተባበር ችግሮቹንና ችግራቸውን በጋራ መፍታት እንዳለባቸው ይህም ሊሆን የሚችለው የወጣቱ መሠረታዊ ፍላጎቶች ተሟልተው፣ ችግሮቻችንን ለዘለቂታው መፍታት የምንችልበት መንገድ ተቀይሶልን፣ በሀገራችን ፍትሀዊና ነፃ መንግስት ተመሥርቶ፣ ወጣቱ ከመራራት ይልቅ መቀራረብ ሲችል ነው። እነዚህ ሁኔታዎች በልጽጋ ማየት እንደሚሻ፣ በርዕያቸው ላይ አስቀምጠዋል። ማንኛችንም በነሆን አገራችን ያለባትን ችግሮች ለመፍታት ችላ፣ ወጣቱም በነሳት ለመደራጅት በቅዶ፣ ማየት ደስ ይለናል ብዬ አምናለሁ። ጸሀፊ በአንባቢው እይታና አሳማኝነት ዙሪያ ስመለከት ሀሀፊም፣ ጸሀፊቸውን ያቀረበት በአጠቃላይ በወጣቱ ህይወት ዙሪያ ችግሮች ብቻ ነው ለማለት አያስደፍርም፣ ምክንያቱም ከመጀመሪያ እስከ ማጠቃለያና ርዕያቸው ድረስ ወጣቱ ለሚያጋጥመው ችግሮች መወሰድ የሚገቡትን እርምጃዎችና መፍትሄዎች በምሉዕ

ሌላው ደግሞ ሀሀፊዎቹ በዕሁፋቸው ላይ ከተጨባጭ መረጃ ይልቅ የሚሰማቸውንና ሀሳባዊ የሆነ ጽሁፍ ያቀረቡ ይመስለኛል። ከጽሁፉ እንደረዳሁት ያቀረቡት የሀሳቦች ጥርቅም ነው። ይህንን ስል ግን ጽሁፉ አጥጋቢ ሳይሆን ቀርቷል ለማለት አይደለም። እንደ ተማሪነታቸው ያላቸውን ጊዜና ጉልበት በተጨናነቀ መልኩ ተጠቅመው ይህን ጽሁፍ ማዘጋጀት መቻላቸው የሚመሰግናቸዉል አላለሁ።

ከዚህ ቀጥዬ በጽሁፍ ላይ ቢጨመሩ ለወይይት መልካም ይሆናሉ የምላቸውን ሀሳቦች ልሰንዝር።-

* ልምድን በተመለከተ፤ የአሁኑ ዘመን ወጣት በያደርግ ይመረጣል የምለው የበፊቶቹ ወጣት ትውልዶች ጥንካሬአቸውንና ድክመታቸውን በያጠን፤ ከዚህም በተጨማሪ በዘመኑ የገጠማቸውን ችግር በምን አይነት መልኩ ለመፍታት እንደሞከሩ፤ ከማህበረሰቡ፣ ከት/ቤትና ከመንግስት ጋር የነበራቸው ግንኙነትስ ምን ይመስል እንደነበረ የሚሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ጠቃሚ ሆኖ አግኝቻለሁ።
* ለላው ደግሞ በወጣቱ ዘንድ ትልቅ ሚና ይኖራቸዋል ብዬ የማምነው የሀይማኖት ተቁማት ናቸው። እነዚህ ተቁማት ከማንኛውም ነገር በነፃ መልኩ፣ ወጣቱ ለሀይማኖቱ ቀናኢ እንዲሆን፣ ለሀገሩና ለወገኑ ተቆርቋሪ እና ኃላፊነት የሚሰማው፣ በእኩልነት እና በመከባበር የሚያምን ሆኖ እንዲያድግ ያስተምራሉ ብዬ አምናለሁና።
* ከዚህም በተጨማሪ ወጣቱ በዘር፣ በጐሳ፣ በሀይማኖት፣ ልዩነት ሳያምን፣ ምንም እንኳን የሀሳብ ልዩነት ቢኖርም፤ ልዩነቱን በጠረጴዛ ዙሪያ ሰላማዊ በሆነ መንገድ መፍታት እንዲችል ማህበረሰቡ እና መንግስት ሁኔታውችን ሊያመቻቹለት የግድ ይላል።

በመጨረሻ እኔም እንደ አንድ ወጣት ለወጣቱ የምመኘው ሁሉም ወጣት የአስተሳሰብ ልዩነት እንደሚኖር አምኖ፤ ልዩነቶቻችንን ግን በመቻቻል፣ ለአንዲት ሀገራዊ ልማትና እንድነት እንሰ እላለሁ። ከዚህም በተጨማሪ ማንም ሰው ትልቅ ሆኖ አልተፈጠረም፣ ወደ ትልቅነት ያመራል እንጂ! ይህንንም ለማጠናከር አንዲት አባባል ልናገርና ጽሁፌን ልቋጭ።

«ማንም ትልቅ ሆኖ አልተወለደም
ወደ ትልቅነት ያድጋል እንጂ»

አሜ ንይለሥላሴ

ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

ወጣቱ እና ልማት፤ ትናንት፣ ዛሬና ነገ በኢትዮጵያ ጽሁፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት

አንዳርጋቸው ተስፋዬ*

የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር «ወጣትና ልማት፣ ትናንት፣ ዛሬ እና ነገ በኢትዮጵያ» በሚል ርዕስ በዘሬቱ ንዳና ኅጃም በጋለ በጋራ በቀረበ ጽሑፍ ላይ አስተያየት እንድሰጥ ስለጋበዘኝ አመሰግናለሁ።

የጽሑፉ አቅራቢዎች የጽሑፋቸውን ይዘት በመግቢያው «ወጣትና ልማት፣ ትናንት፣ ዛሬ እና ነገ» በማለት በአጭሩ ከአሰፈሩ በኋላ ወጣቱ ብዙ አኩሪ ሥራዎችን ፈጽሞ እንዳለፈና ለወደፊቱም ብዙ ድጋፎች እንደሚያስፈልጉት በአጽንኦት ጠቁመዋል። ወጣቱ የማሕበረሰቡ አካል እንደመሆኑ መጠን ሕብረተሰቡም እሱን የማበረታታት ኃላፊነት እንዳለበት አስምረውበታል። ሕብረተሰብ ሲሉ ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤት፣ መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ያጠቃልላል።

መግቢአቸውን የደመደሙት በጣም አንገብጋቢ ጥያቄዎች ናቸው ያሉአቸውን በማንሳት ነው። እነዚህም

1. ወጣቱ ባለው ችሎታ መጠንና ዓይነት ሰርቶአል ወይ?
2. ለወደፊትስ የመሥራትና የሞራል አቅም አለው?
3. ለሥራ ተነሳሽነቱስ ምን ያህል ነው?
4. እራሱን ለሚመጡ ለውጦች አዘጋጅቶአል?

በተጨማሪም የጽሑፉ አቅራቢዎች ወጣቱ የአንዲት አገር የጀርባ አጥንት እንደመሆኑ መጠን ብዛት ያለውን የባላገር ወጣት ማጠቃለል አለበት ብለዋል። ወጣቶች አካባቢን ለመንከባከብ፣ በልማት የተሻለ የምርት ስርዓቶችን ለመፍጠርና ለውጦችን ማምጣት ይችላሉ። እንደ አቅራቢዎቹ አስተሳሰብ ወጣቱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለማስተዋወቅ፣ ማሕበራዊ ልምዶችንና እምነቶችን በግልጽ በመረዳትና በማወያየት በስልጣኔ መሣሪያነት ሊያገለግል ይችላል ብለዋል።

የጽሁፉ አዘጋጆች ዘርዘር ባለው መግቢያቸው ወጣቱ በተለያዩ ጊዜያት በልማት ሲሳተፍ መቆየቱን ከገለጹ በኋላ ነው ወጣት ምን ማለት እንደሆነ መተርጎም የሞከሩት። በገለጻውም ወጣት ማለት በሰው ልጅ ስነሕይወታዊ ምዕራፍ አንድን የዕድሜ ክልል

---

* ፕሮፌሰር አንዳርጋቸው ተስፋዬ በሶሲዮሎጂ በአሜሪካን አገር ከሚቺጋን ዩኒቨርሲቲ (አን-አርበር) ፒ.ኤች.ዲ እ.አ.አ. በ1973 ዓ.ም ያገኙ ሲሆን፤ በማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር የማህበራዊ ጉዳይ ዳይሬክተር ሆነው ካገለገሉ በኋላ ወደ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተላውረው መጀመሪያ የማህበራዊ ጉዳይ ትምህርት ክፍል ዳይሬክተር፤ ከዚያም በሀገር ልማት መስክ ሃያት ዳይሬክተር በመሆን በጠቅላላው ለ40 ዓመታት አገራቸውን ያገለገሉ አላውንት ናቸው።

የሚመለከተና የተለየዉ ኢኮኖሚያዊ፣ ስነ ልቦናዊ፣ ማህበራዊ አቋምና ደረጃ ያለው ነው ሲሉ ይፈተታል። በኢትዮጵያ ወጣት ማለት ከ15 እስከ 29 ዓመት ክልል ውስጥ ያለ መሆኑን ይገለጻሉ። ሆኖም ለወጣት ትርጉምም ሆነ ስለዕድሜ ገደብ የጠቀሱት ዋቢ ጽሑፍ የለም። እርግጥ ባይጠቅስም የዕድሜው ገደብ በ1996 ዓ.ም. ከወጣው የኢትዮጵያ መንግስት ብሔራዊ የወጣቶች ፖሊሲ ጋር አንድ አይነት ነው።

በተባበሩት መንግስታት ፖሊሲ መሠረት ወጣት ማለት በ15-24 ዓመት ዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኝ ሰው ነው። ስለዚህ ኢትዮጵያ ከተባበሩት መንግስታት እና ከሎሎችም አዛኞች ተለይታ ለምን ለከፍተኛው የወጣት ዕድሜ ጣሪያ ገደብ 29 ዓመት እንዲሆን የመረጠችበት ምክንያት አልተጠቀሰም።

የመንግስት ፖሊሲው ግን 20 ዓመት የመረጠበት ምክንያት ወጣቶችን አንቀሳቅሶ እምቅ አቅማቸውንና ችሎታቸውን ለልማት ለመጠቀም መሆኑን ይጠቅሳል። ሆኖም ጽሑፉ አተራረቡም ሆነ ፖሊሲው በኢትዮጵያ ወጣቶች ዙሪያ ሎሎች አደናጋሪ ሕጎች መኖራቸው ባለመጠቀሱ የሕጉን ትንታኔ ያልተሟላ የሚያደርግ መሆኑን አላመለከተም።

በ1949 ዓ.ም. የወጣው ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በአንቀጽ 52 ከ16 ዓመት በታች ያሉትን ወጣቶች ለአነስ መጠን ያልደረሱ ብሎ፣ የሚቀጡበትንም የተለያዩ አንቀጾች አስቀምጧል። ከ16 እስከ 18 ዓመት ያሉትን ግን ከሞት ፍርድ ሲያድናቸው እንደማንኛውም አነስ መጠን እንደደረሱ ሰዎች በመደበኛ ወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እንዲዳኙ ያደርጋል። ስለዚህ የወጣቶችም ፖሊሲ ሆነ የዛሬው የውይይት ጽሑፍ ካለው ከአገራቱ ሕግ ጋር መጣጣም ይኖርባቸዋል።

ለዛሬው ውይይት የቀረበው ጽሑፍ የወጣቱ ልዩ ባሕሪያት ያላቸውን እንደሚከተለው አቅርበአቸዋል።

- ንቁነት
- አፍላነት
- ደፋርነት
- ቅንነት
- ታጣቂነት
- አምራችነት

እነዚህ ባሕሪያት ወጣቱን ለደጉም ለክፉም ነገሮች አመቺ እንደሚያደርጉትም ጠቁመዋል።

በሌላ በኩል የመወያያ ጽሑፉን አተራረቡም ሌላ ዋና የወጣቱ ተግባር ያደረጉትን የልማት ምንነት ከጠቀሱ በኋላ በልማት ሂደት ውጤት ላይ ማሕበረሰቡ ባለቤትነት እንዲኖረውና ንቁ ተሳትፎም እንዲያደርግ በአጽንኦት ጠቁመዋል። ወጣቱም በዚህ ረገድ ከፍተኛ ኃላፊነት እንዳለበትም እንደሚያምኑ ገልጸዋል። ለዚህም እምነት መነሻ

ያደረጉት መጣቱ ከፍተኛ የሥራ ፍላጎት፣ ተነሳሽነት፣ ፈጻሚነት፣ አስፈጻሚነት (ሠርቶ ማሠራት) የሚችል የአንድ አገር ትልቁና ብቸኛ ከፍል ነው ብለው ስለሚያምኑ ነው። ስለዚህ መጣቱ ለሀገሪቱ እድገት ታላቅ ሚና መጫወት ይችላል ይላሉ።

ምንም እንኳን የአንድ አገር ወጣት ታላቅ ሚና እንደሚኖረው ባይካድና ወጣት የሚለውም ቃል ሰፋ ብሎ ቢተረጎምም እንደእኔ አስተያየት ገደብ ሊኖረው ይገባል። ወጣቱ በሙሉ በተለይም ትምህርት ቀመሱ የከተማው ወጣት፣ በአብዛኛው "ከፍተኛ የሥራ ፍላጎትና ለሥራ ተነሳሽነትና ሥራ ፈጻሚ" ነው ማለት በከተሞች፣ በየቀበሌው በዋልጌነት የሚታዩት በርካታ ሥራ አጥም ይሁኑ ሥራ ፈት ወጣቶች ሁኔታ መዘንጋት የለበትም። በየሁለተኛ ደረጃዎችና በኮሌጆች ያሉ ወጣቶችስ ተነሳሽነት የሚያመረቃ ነው ወይ?

የጽሑፉ አዘጋጆች በልማት በኩል ወጣቱ በተለይ በፖለቲካ፣ በማሕበራዊ ጉዳይና በኢኮኖሚ ረገድ በሦስት ፖለቲካ ወቅቶች ያደረገውን አስተዋጽኦ ዘርዝረዋል።

1ኛ ዘመናዊ ትምህርት የማግኘት ዕድል ባልነበረበት ዘመን በግብርናና በዕደ ጥበባት በመሠማራት አገራቸውን ከመገንባት ጎን ለጎን የውጭውን ወረራ ተከላክለዋል። ዘመናዊ ትምህርት ከተጀመረም በኋላ ሁለንተናዊ ጭቆናን በመቃወም ለኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ልማት፣ ለፍትህ፣ ለዴሞክራሲና ለተሻለ አስተዳደር በብርቱ ታግለዋል።

2ኛ ለዚሁም በተለይ ከ1953 ዓ.ም ወዲህ ሕብረተሰቡን በማንቀሳቀስ ኢ-ፍትሐዊ አገዛዞችን በመቃወም እንዲሁም ለኢኮኖሚያዊና ለማሕበራዊ ልማት፣ ለፍትህና ለዴሞክራሲ በመሰለፍ አኩሪ ድል በመስዋዕትነት አስገኝተዋል። ለአሁኑም ወጣት መሠረት ሆነው አልፈዋል። መሬት ላራሹ የሚለውን አንግበው በመነሳት የፊውዳሉን ሥርዓት አፍርሰው አርሶ አደሩን ከባርነት አላቀዋል። ይህም ለዘላለም በታላቅ አርአያነት ይኖራል።

3ኛ ከዚህም ተያይዞ ከ1966 ዓ.ም. በኋላ በልዩ ልዩ የፖለቲካ ድርጅቶች ወስጥ በመግባት ብዙ መስዋዕትነት ከፍለዋል። በዚህም ምክንያት የአንድ ትውልድ አባላት ለዴሞክራሲና ለሰብአዊ መብት ተሰደዋል፣ ተሰውተዋል።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ከላይ የተዘረዘሩትን መስዋዕትነት መክፈላቸው አሌ የሚባል አይደለም። በተደረጉት መስዋዕቶች የተከፈለው የሰው ሕይወትና ንብረት ሁሉ አስፈላጊ ነበር ወይ? የጽሑፉ አዘጋጆች ይህን በመጠኑም ቢሆን አለመጥቀሳቸው ጽሑፉን ያልተሟላ አያደርገውም? የወጣቱንስ ስሜታዊነትና ግንፍልነት የሚተኩትን የወጣቱን አሉታዊ ድርጊቶች መሸፋፈን አይሆንም? ጸሐፊዎቹ በወጣቶች ላይ የደረሰውን አደጋ በቤተሰብ ቁጥጥር ማነስ ወይም መላላት እንደሆነ አስመስለውታል። በአላስፈላጊ መስዋዕትነት ውስጥ የወደቁት ወጣቶች ከየትኛው ሕዝብ ክፍል የተገኙ ነበሩ? የነዚህ ወጣቶች ወላጆች ስንቶቹ ነበሩ ከልጆቻቸው በላይ ትምህርት የነበራቸው? ተምሬአለሁ የሚለው ወጣት ወላጆቹን በድንቁርና ነው፣ ስትጨቁን፣ ስትገዛ የነበረው በማለት፣ ፊት ከመንሳት ሌላ፣ በዕውነት የወላጆቹን ድምጽ ይሰማ ነበር? በዚህስ የተነሳ ወላጆች ምን ያህል ውጣ ውረድ ነበር የደረሰባቸው? የተሰውስ አልነበሩም?

ጽሑፉ ሞጥሎ በወጣቱ ሚና ላይ አስተዋጽኦ አላቸው የሚላቸውን የሕብረተሰብ አካላትን ተግባር ይጠቅሳል። እነዚህም ቤተሰብ፣ ማህበረሰብ፣ ትምህርት ቤትና መንግስት ናቸው። ይህ ክፍል በአጠቃላይ የሚጠቁመው ወጣቱ መልካም ስነምግባር እንዲኖረው ከታች ጀምሮ በየደረጃው ኮትኩተው ማሳደግ ያለባቸው እነዚህ አካላት መሆናቸውን በአጽንኦት ይጠቁማል። ይህ ሊፈታ የሚገባው ችግር መሆኑ ለብዙ ጊዜ የተነገረ ነው፣ ሆኖም አሁንም ያልተፈታ ችግር ነው። ስለዚህ ጽሑፉ ዘይዎቹን በጠቁም ጠቃሚ ነበር። ቤተሰብ፣ ማሕበረሰብና ትምህርት ቤት ጥሩ ምግባርን በምሳሌነት ቢያስተምር ማለት ቀላል ነው። ነገር ግን የሚደረገውን ጥረት ሌሎች አፍራሽ ልማዶችንና ጎጂ የስልጣኔ የውጭ ባህሎች ይሸረሽሩታል፣ ይህ ደግሞ ከብዙ ወላጆች አቅም በላይ ነው። ወጣቱ ደግሞ ተማርኩ፣ ሰልጥኛለሁ፣ ባይ ስለሆነ ለብዙ ወላጆች በተለይ ላልተማሩትና በትምህርት ላልገፉ በዝቅተኛ ኢኮኖሚ ደረጃ ላሉት የሕብረተሰቡ አካላት በጣም ከባድ ነው። የወጣቱ ፍላጎት የሚለካው በወላጆች አቅም ሳይሆን በአደባባይ፣ በስውርም ሆነ በግልጽ ገበያ፣ በሚቀርቡ የሽቀጣሽቀጥ፣ የመገናኛና፣ በሰላ ማርኪያዎች ነው። ይህ ሁኔታ በቁጥጥር ሊውል የሚችለው የጽሑፉም አቅራቢዎች እንደጠቆሙት የትምህርት ቤቶች አቅም ጠንክሮ ስነሥርዕትና ስነምግባርን በተማሪዎች ላይ ሊያሰርጽ ሲችል ነው። ትምህርት ቤቶች ግን ይህን ማድረግ ከተሳናቸው አመታት ተቆጥረዋል። መምሕራንና የትምሕርት ቤት አስተዳዳሪዎች ለትግሩ እጅ የሰጡ ይመስላል። ስለዚህ በት/ቤት የሚገኙ ወጣቶች በየመንገዱና በየአደባባዩ ከሚገኙ አቻ ወጣቶች የተሻለ ጠባይና ሥነምግባር ያላቸው አይመስሉም።

የጽሑፉ አቅራቢዎች መንግስት የወጣቱን አስተዳደግና ስነምግባር የመቅረጽ ሀላፊነት አለበት ብለዋል። ነገር ግን መንግስት አንዳንድ የስነምግባር ሁኔታዎችን የሚያበላሹ፣ የሚሸረሽሩ፣ ከፍ ብለው የተጠቀሱ ልማዶችንና ሱሶችን እንኳን ለመቆጣጠር አልቻለም ወይም ጠንካራ ፍላጎት አላሳየም። በየትምህርት ተቋማቱ የሚገኙ ወጣቶች ከታች እስከ ላይ የብዙ ሱሶች ተጠቃሚነታቸው ይታወቃል። ሆኖም የሚወሰዱ እርምጃዎች አይታዩም። እንዲያውም እንደ ፌት ያለው በመንግሥት አንደገቢ ማስገኛ ተቆጥሮ ሲበረታታ ይታያል። በዚህም ምክንያት ፌት በምሥራቅ ከሐረርጌ፣ በደቡብ ከጅማ፣ ዘምዩ በሰሜን እስከ ጎንደር እርማጨሆ ዘልቆአል። ሌሎችም ዕጾች እንደሚዘዋወሩ በፖሊስ ከመጠቆሙም ሌላ ወጣቶችም እንደሚጠቀሙባቸው ይታወቃል። ስለዚህ በጽሁፉ የተሰጠው ጥቆማ ሙልነም ሆኖ ሳለ እንደማንኛውም በየጊዜው እንደሚሰጡ ሀሳቦች በማይሰሙ ጆሮዎች ላይ ወድቀው እንደሚቀሩ እሰጋለሁ።

ጽሑፍ አቅራቢዎቹ በመጨረሻ ሰፊ አስተያየታቸው የወጣቱን ችግሮች በኢኮኖሚያዊና በማህበራዊ መስኮች በ4 ዋና ዋና ክፍሎች፣ ማለትም፣ የኢኮኖሚ ችግሮች፣ ማሕበራዊ ችግሮች፣ ሥነ ልቦናዊ ችግሮች፣ የጤና ችግሮች መድበዋቸዋል።

ዋናው የወጣቱ ኢኮኖሚያዊ ችግር እንደ ጽሑፍ አቅራቢዎቹ ሥራ አጥነት ነው። ይህንኑም በአሐዝ ሲገልጹ እ.ኤ.አ በ1999 ዓ.ም ወጣቱ 33 በመቶ ሥራ አጥ ነበር። ሥራ አጥነቱ ደግሞ በሴቶቹ እንደሚብስ ገልጸዋል። ሥራ አጥነት ደግሞ ብዙ ችግሮች እያስከተለ እንዳለ እዚህ አዳራሽ ያለነው በሙሉ የምንመሰክረው ይመስለኛል።

በአሁኑ ሰዓት ዝሙት አዳሪነት (ሴተኛ አዳሪነት የሚለው ቃል ትክክል አይመስለኝም) ሊታመን ከሚቻል በላይ አገሪቱን እያጥለቀለቀ ነው። በዚህ ላይ የጎዳና ተዳዳሪ ወጣቶች ሲደመሩ እውነት ምን እየጠበቅን ነው ያሰኛል። በወጣት ወንዶችም በኩል ከሥራ አጥነት የሚመነጩ ብዙ አሳሳቢ ተግባሮች አሉ። ቦዘኔነት፣ ወጣት ጥፋተኝነትና ወንጀለኝነት አልተረዳነው እንዳይሆን እንጂ ትልቅ በጉያችን ይዘነው የምንኖር ፈንጂ ነው። የወንጀልና የወጣት ጥፋተኝነት እስታትስቲክስ በአገራችን የወጣቱ ተግባር ሆኖአል። ለምሳሌ የ1991 ዓ.ም. እስታቲስቲክስ ብንመለከት በአመቱ የተፈጸሙት ጥፋቶችና ወንጀሎች እንደሚከተሉት ተተንትነዋል።

ከ9-15 ያሉ ወጣቶች የዓመቱን 1.8%ኙውን
ከ16-18 ያሉ ወጣቶች የዓመቱን 10.6%
ከ19-30 ያሉ ጎልማሶች የዓመቱን 49.1%

በጠቅላላ 61.5% በወጣቱ የተፈጸሙ ናቸው። ስለዚህ ወንጀል የወጣቱ ተግባር ሆኖአል።

በጽሑፍ አቅራቢዎች አስተያየት የነዚህ ሁሉ ችግሮች ምንጭ የትምህርት ሥርዓቱ ድክመት መሆኑን ጠቁመዋል። የሥርዓተ ትምህርቱ አወቃቀርና የትምህርቱ አሰጣጥ ወጣቱን በተግባራዊ ትምህርት እንደማያዘጋጅ ጠቁመዋል። ይህ አስተያየት ብዙዎቻችን ከሞላ ጎደል የምንጋራው ይመስለኛል። ሆኖም የወጣት ጥፋተኝነትና የወንጀል መነሻዎች በዚህ ብቻ አይወሰኑም።

የጽሑፉ አቅራቢዎች መደ ጽሑፋቸው መደምደሚያ አቅራቢያ የወጣቱ ማሕበራዊ ችግሮች በማለት እንደ አደንዛዥ ዕጽች፣ አልኮል መጠጦች፣ ጎዳና ተዳዳሪነት፣ ወጣት አጥፊነት፣ ወንጀለኛነትና፣ ዝሙት አዳሪነት (ሴተኛ አዳሪነት) የጤናና ስነልቦናዊ ችግሮች ብለው ዘርዝረዋል።

አቅራቢዎቹ፣ እነዚህ ሁኔታዎች የሚያስከትሉትን ችግሮች ጠቅም ጠቅም በማድረግ ቤተሰብ፣ ሕብረተሰብና መንግስት አስፈላጊ እርምጃዎችን እንዲወስዱ አሳስበዋል። ግን ቤተሰብም ሆነ ሕብረተሰቡ ምን ያህል ግንዛቤ አለው? የተወሰነ ግንዛቤ ቢኖርስ ግን አስተባብሮ ነው ሰፋ ያለና ጠለቅ ያለ እርምጃ ሊወሰድ የሚቻለው? መንግስት ከላይ ለተዘረዘሩት ተግባሮች ሰፋ ያለ ግንዛቤ እንደሚኖረው ሳንጠረጥር አንቀርም። ሆኖም ዓይነት አርነኒ እርምጃዎች እንዲልተወሰዱ ይታወቃል።

በመጨረሻም የጽሑፉ አቅራቢዎች በወጣቱ ዙሪያ ብዙ አሳሳቢ ጉዳዮችንና እውነታዎችን ጉዳዮችና አስተያየቶች፣ ተቀባይነት ቢኖራቸውም ባይኖራቸውም፣ ለማሳሰብ እድል በማግኘቴ፣ የውይይቱም አዘጋጆች ለዚህ ዕድል ስላበቁኝ፣ ሁሉንም ከልብ አመሰግናለሁ። እንዲሁም መላው ተሰብሳቢ በትዕግስት ስላዳመጣችሁኝ ከልብ አመሰግናለሁ።

ትምህርት እና ልማት በኢትዮጵያ

ሥዩም ተፈራ*

1. መግቢያ

ለመነሻ ያህል ልማት ሲባል ሰፊና ጠለቅ ያለ ገለፃና ትንታኔ ውስጥ ሳይገባ በአጠቃላይ አንድ እንደ ኢትዮጵያ ያለ ጎብረተሰብ ካለበት ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ማለትም በኢኮኖሚውም ሆነ በማኅበራዊው እንዲሁም በፖለቲካው የሆነ የመሻሻል ሁኔታ ካሳየ ወደ ልማት ጎዳና እየሔደ ነው የሚለውን እንውሰድ። ትምህርት ሲባልም አንዱ የልማት ግብአት እንደመሆኑ የተማረና የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ልማት እንዲመጣ በመሳሪያነት የሚያገለግል መሆኑን ልማትንና ትምህርትን በዚህ መልክ ካየናቸው ለመነሻ ግንዛቤ እናድርግ። ባጭሩ ልማትንና ትምህርትን በዚህ መልክ ካየናቸው ለመነሻ በቂ ሳይሆን አይቀርም ብዬ እገምታለሁ።

ሆኖም ትምህርት ለልማት ቁልፍ ሚና ሊጫወት የሚችለው አንዳንድ ሁኔታዎች ሲሟሉ እንጂ እንዲሁ እንደነገሩ በየዘመኑ ትምህርት በመሰጠቱ አይደለም። እነዚህም ሁኔታዎች ከሞላ ጎደል የሚከተሉት ናቸው ተብሎ ይገመታል።

ሀ. ትምህርቱ ዓላማዎች ያሉትና እነዚህም ዓላማዎች በአገሪቱ ልማት ላይ ያተኮሩና የጎብረተሰቡን ችግሮች የሚፈቱና እንዲሁም የጎብረተሰቡንፍላጎት የሚያንፀባርቁ ሲሆኑ፤

ለ. እነዚህም የትምህርት ዓላማዎች በፖሊሲ መልክ ሲቀረፁ የሚመለከታቸው የጎብረተሰቡ ክፍሎች በተለይም መምህራን፤ ወላጆች፤ የትምህርት ባለሙያዎች፤ እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ የትምህርቱ ውጤት ተጠቃሚዎችና የትምህርቱን ዕድገት የሚረዱ ወዘተ... ለይስሙላ ሳይሆን በሚገባ ሲሳተፉ፤

ሐ. ትምህርቱም በአገር ልማት ዕቅድ ላይ ተመስርቶ አሰተማማኝ የልማት ውጤት እንዲያመጣ በጥራትና የትምህርቱም ተሳትፎ ፍትሀዊ እንዲሆን ከአገሪቱ ኢኮኖሚ አንፃር በተመጣጠነ ሁኔታ የሚሰጥ ከሆነ፤

ይህንን ካልሁ በኋላ የዛሬው ውይይታችን ርዕስ ቀደም ብሎ እንደተገፀለው «ትምህርት እና ልማት በኢትዮጵያ» የሚል ነው። ጽሑፉም በስምንት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን የአገሪቱ ትምህርት በየዘመኑ የተጓዘውን ሒደት በመቃኘትና ለአገር ልማት ያደረገውን አስተዋጽኦ መከራ እና ማድረግ የሚጠበቅበትን ለመተግበር ያልቻለበትን ምክንያቶች ለመተንተን ተሞክሯል። በመጨረሻም በ2020 (በኢትዮጵያ አቆጣጠር) ትምህርትን በሚመለከት አንዳንድ ርዕይዎች ለመሰንዘር ጥረት ተደርጓል። ከዚህ ሌላ ማሰታወስ የሚያሰፍልገው በጽሑፉ የተጠቀሱት ዓመታት በሌላ ካልተገለጸ በስተቀር በኤውሮፓውያን አቆጣጠር መሆናቸውን ነው።

---

* ፕሮፌሰር ሥዩም ተፈራ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የመጀመሪያ የባችለር ዲግሪ አግኝተዋል፣ ከዚያም በትምህርት፣ በፖላንና አስተዳደር ከአሜሪካን አገር ፒ.ኤች.ዲ. ዲግሪ ተቀብለዋል። ትምህርታቸውን እንዳጠናቀቁም ወደ አገራቸው ተመልሰው በተማሩት መስክ ከ20 ዓመት በላይ በመምህርነትና በተመራማሪነት ብዙ ያበረከቱ ሰው ናቸው። ብዙ ጽፈዋል፤ በታወቁ ጥናታዊ መጽሔቶችም (Journals) ላይ አሳትመዋል። በተለያዩ ኃላፊነት አገልግለዋል። በተለይም በ Institute of Educational Research ዳይሬክተር እና በ Education Faculty Dean በመሆን በትምህርትና ልማት ብዙ የሠሩ ናቸው።

2. በአገራቱ የዘመናዊ ትምህርት አጀማመር

በመሠረቱ የጥንታዊ ሥልጣኔ ባለቤት ለሆነች አገር ትምህርት አዲስ ነገር አይደለም። የኦርቶዶክስ ሃይማኖት በአገራቱ ከተሰበከበት ከአራተኛው ክፍለዘመን አንሰቶ በቤተ ክርስቲያኗ አማካይነት የሃይማኖት ትምህርት ለብዙሃኑም ባይሆን ለጥቂቱ በጽሑፍ ጭምር ሲሰጥ ቆይቷል ። በዚህም የተነሳ አገራቱ ከሰሐራ በታች ካሉት የአፍሪቃ አገሮች ብቸኛዋ የጽሑፍ ቋንቋ ያላት ለመሆን በቅታለች። እንዲሁም በእስልምና ሃይማኖትም የቁራአን ትምህርት በተለይም በአገራቱ ምሥራቅና ምዕራብ ክፍሎች ይሰጥ ነበር።

ሆኖም ሁለቱም ሃይማኖቶች ተልዕኮአቸው ያተኮረው በዚህኛው ዓለም ላይ ሳይሆን በወዲያኛው በመሆኑ በልማት በኩል በተለይም በኢኮኖሚው ዘርፍ ያደረጉት አሰተዋፅኦ እምብዛም አልነበረም። በተጨማሪም በጣም የሚገርመው አገራቱ የጽሑፍ ቋንቋ ባለቤት ብትሆንም አስከትርብ ጊዜ ድረስ አብዛኛው ሕዝብ ይፈርም የነበረው በአውራ ጣቱ ስለነበር ለሶስተኛው ዓለም ስም ማውጣት የማይሳናቸው ምዕራባውያን «በአውራ ጣት የሚፈርምባት አገር» /the Land of the Thumb Print/[1] በሚል ስያሜ እንድትታወቅ አድርገዋት ነበር።

ለልማት መሠረት ተብለው ከሚታመንባቸው ግባአቶች አንዱ የሆነው ዘመናዊ ትምህርት አገራቱ ሊገባ የቻለው በጣም ዘግይቶ በሀያኛው ምዕተ ዓመት መግቢያ ላይ ነው። ከዚያ ተደም ብሎ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት ሚሲዮናዊያን በተለይም በሰሜኑ የአገራቱ ክፍል እምነታቸውን ለማሰራጨት ሲሉ በመጠኑም ቢሆን ዘመናዊ ትምህርት ቀላቅለው ይሰጡ ነበር።

በአስራዘጠነኛው ምዕተ ዓመት መገባደጃ ላይ ግን በአገራቱ መዕከላዊ አገዛዝ ሥርዓት እየሰፈነ በመምጣቱና እንዲሁም የአገራቱም ኢኮኖሚ በመጠኑም ቢሆን ዘመናዊ መልክ መያዝ በመጀመሩና ከአድዋ ድል በኋላ የዲፕሎማቲክ ግንኙነት እየሰፋ በመምጣቱ የዘመናዊ ትምህርት መጀመር እየጎላ መጣ።[2] ይህንኑ ፍላጎት ለማንፀባረቅ ይመስላል ምኒልክም በ1906 ምኒልባትም በአገራቱ መጀመሪያ የሆነውን የትምህርት አዋጅ አወጡ። አዋጁም በአጠቃላይ ስለትምህርት አሰፈላጊነት ብቻ ሳይሆን በተለይም ስለ መደ ትምህርት አንባር ሲታይ አዋጁ ከዘመኑ አስተሳሰብ መልካምነት የማጠቅስም ነበር። ከመደ ትምህርት የመጠቀ ይመስላል። ምክንያቱም እንኳን በዚያ ዘመን ይቅርና አሁንም ቢሆን ሕብረተሰቡ ስለ መደ ትምህርት ያለው አስተሳሰብ አስከዚህ ጤናማ አይደለም። አዋጁን በሚመለከት ለግንዛቤ ያህል ከሞላ ጎደል ለመጥቀስ፤

«አስካሁን ማንም የእጅ ሥራ ዐዋቂ የነበረ ሰው በወርደት ስም ይጠራ ነበር፤ ስለዚህም ማንም ሰው ለመማርና፤ ለመሰልጠን የሚደክም አልነበረም በዚህ ጎዟ በሆነ ሁኔታ ብንኖር በተክርስቲያኖች ይዘጋለ፤ ይልቁንም ክርስቲያንነት አይገኝም። በሌሎች አገሮች እየንዳንዱን ነገር መማር ሳይሆን አዲስ ነገሮችም ይሠራሉ። ስለዚህ ከዛሬ ዠምሮ ለወደፊት ወንድ ልጅችና ሴት ልጅች ሁለ ክስድስት ዓመታቸው በኋላ ወደ ትምህርት ቤት እንዲገቡ ይሁን። ልጅታቸውን ለማስተማር ለማይተጉ በተሰበት ወላጅታቸው ሲሞቱ ንብረታቸው ለልጅታቸው መሆኑ ቀርቶ ለመንግስት ይተላለፋል፡ ተማሪ ቤቶችንና አስተማሪዎችን የሚየዘጋጀው መንግሥቴ ነው።[1]»

ከአዋጅም በአሻገር ዳግማዊ ምኒልክ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ለመክፈት ወሰኑ። ሆኖም ቃለወስቱና መኳንንቱ ለውጥ የማይፈልጉና የዘመናዊ ትምህርት መግባት በተለይም ለኦርቶዶክስ ሃይማኖት አስጊ ሆኖ ስለተሰማቸው ከፍተኛ ተቃውሞ ገጠማቸው። ነገር ግን ለውጥ ፈላጊው ዳግማዊ ምኒልክ ተቃውሞውን በዘዴ በማርገብ የኦርቶዶክስ ሃይማኖት ተከታይ የሆኑ መምህራን ከግብፅ ለማስመጣት የሚከተለውን ደብዳቤ ለአቡነ ቄርሎስ ለአስከንድርያው ፓትሪያርክ ላኩ።

«ይድረስ ለአቡነ ቄርሎስ

በአዲስ አበባ ከተማችን ትልቅ የተማሪ ቤት ማድረግ አስበናል። ይህንን አሳባችንን አቡነ ማቴዎስ ሰምተው በሀገራችን በግብፅ ብዙ የተማሩ ለማስተማር የበቁ ሰዎች አሉ ቢሉን አርሶም ወደ አቡነ ቄርሎስ ልከው እንዲሰዱልን ያድርጉ ብለን ነገርናቸው። ይኸው ጽፈንልዎታልና የአቡነ ማቴዎስን ማጉተም አይተው የሚገኝልሞ እንደሆን ያለ ትዕግስት በስልክ በቶሎ ቢያስታውቁን እንወዳለን። ወደርሶም መላካችን ከሌላ አገር ከማስመጣት ለትምህርትም ለሁለም ነገር የሃይማኖት ወንድምታችን ቢመጡ ይሻላል ብለን ነው።[4]

ሰኔ ፭፫ ቀን ፲፰፻፺፫ ዓ.ም
አዲስ አበባ ተጻፈ።»

ከዚያም ብዙም ሳይቆይ አምነታዊ መልስ ለደብዳቤው በመግኘቱ በ1908 የመጀመሪያው ዘመናዊ የመንግሥት ትምህርት ቤት በዳግማዊ ምኒልክ ስም ተከፈተ። የተጀመረውም ለሌላው ምሳሌ እንዲሆን መጡ በማሆኑ የመኳንንት ልጆች ነበር። አብዛኛው መኳንንት ግን ልጁን ወደ ዘመናዊ ትምህርት ቤት ለመላክ ፈቃደኛ ባይሆንም የምኒልክን ትዕዛዝ ለማክበር ያህል አሽከሮቻቸውን በተለይም የማጠሏቸውን ይልኩ እንደነበርና እነዚህም ከትምህርት ቤት እየጠፉ ስለአስቸገሩ ምኒልክ ለመኳንንቱ ወደ ትምህርት ቤት መልሰው እንዲልኳቸው ደብዳቤ ይጽፉ እንደነበርና ከእነዚህ ደብዳቤዎች አንዱ እንደዚህ ይነበባል።

«ይድረስ ከነጋድራስ ኃይለጊዮርጊስ፤ አዲስ አበባ

ከፈረንጆች አስተማሪዎች ዘንድ ባንተ ስም የገቡት ተማሪዎች አበበ ወልደሚካኤል፤ አበበ ይርጉ፤ አባተ አይተንዓሰ፤ በቀለ ዘገየ፤ በሻህ ተክለሃይማኖት፤ ገብረየሱስ ጎረድ፤ ዘውዴ ዘመድአገኘሁ፤ ከፍሌ ወልደሐዋን፤ ዘውዴ ግዛው፤ ቅላው ዘለለው፤ ወርቁ አሰጨናቂ፤ ሸዋረጋ ወልደሐዋን፤ ስምረት ወልደ ሚካኤል እነዚህ እየወሰዱ ትምህርት ትተውሞል ብለውናልና፤ እነዚህን የተቀበሩ ልጆች እተማረ ቤት ገብተው አንዲማሩ ይሁን። እንግዲህ ግን እነዚህ ልጆች ትምህርታቸውን ሳይማሩ የቀሩ እንደሆነ ግን ያስተማሪዎችን ደሞዝ እናንተ ትከፍላላችሁ።[5]

*ታህሣሥ ፴ ቀን ፲፰፻፺፩ ዓ.ም
ደብረ ሊባኖስ ተጻፈ።»*

እንግዲህ እንደዚህ የመሰለውን ደብዳቤ በመጻፍ ጭምር ነበር ዳግማዊ ምኒልክ ዘመናዊ ትምህርት እንዲለመድ ይሞክሩ የነበሩት። የትምህርት ቤቱም ትኩረት በዘመኑ አስተረጓሚነት ወይም ትርጁማንነት ተፈላጊ ስለነበር የፈረንሳይኛ፤ የእንግሊዝኛና የዐረብኛ

ቋንቋዎችን በማስተማር ላይ ነበር። በተጨማሪም ከምኒልክ ትምህርት ቤት ሌላ አንዳንድ አገረ ገዥዎች የምኒልክን ፈለግ በመከተል በራሳቸው ወጪ ጥቂት ትምህርት ቤቶች ከፍተው እንደነበር ይነገራል። ምኒልክም ከአዲስ አበባ ወጭ ሶስት ትምህርት ቤቶች ከፍተው እንደነበረም ይጠቀሳል።

ምንም እንኳን የዘመናዊ ትምህርት መሠረቱ ቢጣልም በአገሪቱ ሁለተኛ የሆነው የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት በ1925 እስከተከፈተበት ድረስ ጉዞው አዝጋሚ ነበር። የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት መከፈቱን ተከትሎም በደሴ፤ በሳሬ፤ በድሬዳዋ፤ በነቀምቴ፤ በይርጋ ዓለም፤ በጅጅጋ፤ በአሰበ ተፈሪ፤ በአምቦ፤ በጅማ፤ በደብረ ማርቆስ ት/ቤቶች ተከፍተዋል። ከእነዚህም ሌላ እዚህ ላይ መጠቀስ የሚገባው በአገሪቱ የመጀመሪያ የሆነው የሴቶች ት/ቤት እቴጌ መነን በ1931 መከፈት ነው። በአጠቃላይ ሲታይ በአገሪቱ እስከ ኢጣሊያን ወረራ ድረስ ወደ ሃያ የሚጠጉ የመንግሥት ት/ቤቶች እንደነበሩና የተማሪዎችም ቁጥር ከአራት ሺህ በላይ እንደደረሰ፣ እንደሁም በተለያዩ የአውሮፖ አገሮችና በአሜሪካ በድምር ወደ ሁለት መቶ የሚደርሱ ተማሪዎች እንደነበሩና ከእነዚህም ውስጥ አሥር የሚሆኑት ሴቶች እንደነበሩ ተመልክቷል[6]።

3. ትምህርት በኢጣሊያን ወረራ

የኢጣሊያን ወረራ ገና በማቆጥቆጥ ላይ ለነበረው ዘመናዊ ትምህርት እንደ መቅሰፍት ነበር የመጣበት። የኢጣሊያን ፋሺስት የነበሩትን ጥቂት የተማሩ ወጣቶችን ሆነ ብሎ ከመጨረስ አልፎ ገና እንደ ገባ ነበር በቅኝ አገዛዝ ላይ የተመሠረተ የትምህርት ፖሊሲ ያወጀው። በፖሊሲውም መሠረት ለኢትዮጵያዊ የሚሰጠው ትምህርት እስከ አራተኛ ክፍል ድረስ ሆኖ የሚማረውም ትምህርት ለኢጣሊያን ጌታው ብቁ አገልጋይ እንዲሆንና የኢጣሊያንንም ፋሺስት መንግሥት ታላቅነት እንዲያውቅ የሚያደርገው ነበር። ከዚህም በላይ «ከፋፍለህ ግዛ» በሚለው የቅኝ አገዛዝ መርህ መሠረት የተማሪው መማሪያ ቋንቋ እንደተደነገገው በአዲስ አበባ በአማርኛ፤ በኦሮሞ በኦርምኛ፤ በሲዳሞ በሲዳምኛ፤ በከፋ በከፊኞ፤ በሱማሌ በሱማልኛ እንዲሆን ነበር[7]። ፋሺስት ኢጣሊያን ይህን ዓይነት የቋንቋ ፖሊሲ ያመጣው ሕዝቡን በቋንቋ ለያይቶ አንድነቱን አሳጥቶ ለመግዛት እንዲያመቸው ያደረገው ዘዴ ነበር። ደግነቱ አገሪቱን የጠቀመው የፋሽሊት ኢጣልያን አገዛዝ ባጭሩ መቀጨቱ ነው።

4. ትምህርት ከኢጣሊያን ወረራ በኋላ

የኢጣልያን ወረራ እንዳበቃና ወዲያውም የአገሪቱ የዕድገት ግንባታ እንደተጀመረ ቅድሚያ ከተሰጣቸው ጉዳዩች አንዱ ትምህርት ነበር። ምናልባትም ትምህርት ለየት ያለ ትኩረት የተሰጠው አገሪቱ በፋሽሊት ኢጣሊያን በቀላሉ ሽንፈት ሊገጥማት የቻለው በኋላ ቀርነቷ ነው የሚል የመንግሥት አስተሳሰብ በይፋም ባይነገር በመኖሩ ይመስላል። እንዲያውም ይህንኑ አስተሳሰብ አርበኞች በተሻለ መልኩ እንዲህ ሲሉ በግጥም ገልጠውታል።

በማይጨውስ በአጋዶስ መቺ ይገባ ነበር፤
በሰማይ ላይ ገባ በማናውቀው አገር።

የኢጣልያን ወረራ ባበቃ ማግሥት ትምህርት ቤቶችን እንደገና ከሥር ጀምሮ ለማቋቋም በገንዘብም ሆነ በሰው ኃይል እንዲሁም በቁሳቁስ በጣም ፈታኝ ነበር። ከሁሉም በላይ ፋሺስት

አብለዮን ጥቂት የተማሩትንም በማጥፋቱ ምክንያት በተለይም የመምህራን እጥረት እጅግ የጎላ ነበር። ስለሆነም በመምህርነት ለማሠማራት የተቻለው በአብዛኛው የቤተክህነትና የማሲዮን ትምህርት ያላቸውን እንጂ በመምህርነት መያ የሰለጠኑ አልነበሩም። በአጠቃላይ በ1942 የትምህርት ሚኒስቴር ሠራተኞች መምህራንን ጨምሮ ሰባ ብቻ እንደነበሩ አንድ የዘመኑ ደሞዝ መክፈያ ዝርዝር ያስረዳል። ለትምህርትም የተመደበው በጀት በ1942 ከስድስት መቶ ሺህ ብር[8] የዘለለ አልነበረም። ጠቅላላ የተማሪውም ቁጥር በ1943 19,000 ደርሶ ነበር። ሆኖም ቀስ በቀስ በስድስት ዓመታት ውስጥ የተማሪው ቁጥር ወደ 53,000 እንደደረሰ ተመልክቷል[9]።

ለላው በዚህ ወቅት መታወሰ የሚገባው እንግሊዝ የፋሽስት ኢጣልያን ወራሪ ጦር ከአገር ለማስወጣት ባደረገችው አስተዋጽኦ ምክንያት ለተወሰነ ጊዜም ቢሆን በአገሪቱ ተሰሚነት አግኝታ ነበር። በዚህም የተነሳ በትምህርቱም በኩል ተፅእኖ ማድረጓ አልቀርም። እንደማታወሰው ከኢጣልያን ወረራ በፊት የትምህርት ይዘት ወደ ፈረንሳይኛ ያዘነበለ ሲሆን በዚህ ጊዜ ደግሞ ወደ እንግሊዝኛ ፊቱን አዞረ። ስለሆነም እንግሊዝኛ የማስተማሪያ ቋንቋ እንዲሆን ተደረገ። ሥርዓተ ትምህርቱም በተቻለ መጠን እንግሊዝ በዘመኑ ለአፍሪቃ ቅኝ ግዛቱቿ የቀረፀችውን ዓይነት እንዲመስል ተሞክሯል።

ከዚህም ለላ አስራሀለተኛ ክፍል የደረሱ ተማሪዎች የእንግሊዝን «ማትሪኩሌሽን» የሚባለውን ፈተና እንዲወስዱም ተደረገ። ይህ ሁሉ የሚያመለክተው ዘመናዊ ትምህርት ከገባ በአጭር ጊዜ ውስጥ ለሀለት የውጭ ተፅኖ መጋለጡን ነው። ምንም እንኳን በአጠቃላይ የተማሪው ቁጥር 95,000 የደረሰው ገና በ1954/55 ቢሆንም ለአገሪቱ የመጀመሪያ የሆነው የከፍተኛ ትምህርት ተቋም አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ግን የተቋቋመው ቀደም ብሎ በ1951 ነበር። እንደሚገመተውም ኮሌጁ ሲቋቋም መምህራኑ በሙሉ ለማለት ይቻላል የውጭ ዜጐች ነበሩ። የተማሪዎቹ ቁጥር ከመቶ በታች ሲሆን እነሱን ውጭ ልኮ ማስተማሩ ሳይቀል አይቀርም ለማለት ያስችላል።

ብዙም ሳይቆይ ገና ሥርዓተ ትምህርቱ የእንግሊዝን ቅኝት በሚገባ ሳይለማመደው በአምሣሎቹ መጀመሪያ ላይ ወደ አሜሪካን ተቀየረ። አሜሪካንም በተቻለ መጠን በሥርዓተ ትምህርቱ ላይና እንዲሁም በመማሪያ ማስተማሪያ መጻሕፍቱና በተለይም «የሰላም ጓድ» በተሰኙ የአሜሪካን መምህራን አማካይነት ተፅእኖውን ማንፀባረቁ አልቀረም። ከዚህም በተጨማሪም የትምህርቱ እርከን በእንግሊዝ 4+4+4 የነበረው የአሜሪካንን እንዲከተል ለማድረግ በ1963/64 ወደ 6+2+4 ማለትም የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ስድስት ዓመት ሲሆን የመለስተኛ 2ኛ ደረጃ ሀለት ዓመትና የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ደግሞ አራት ዓመት እንዲሆን ተደረገ። እንግዲህ የአሜሪካኑ ደግሞ በአገሪቱ ትምህርት ላይ ሶስተኛው የውጭ ጫና መሆኑን ያጠናክራል።

እዚህ ላይ አንድ መታወስ የሚገባው ጉዳይ የአገሪቱ ግምባታ እስካሁን የሚካሔድ የነበረው በየዓመቱ በሚወጣ ዕቅድ እንጂ ረዘም ላለ ዓመታት በወጣ ዕቅድ አልነበረም። ነገር ግን ከ1957 አንስቶ የአምስት ዓመት ዕቅድ ተጀመረ። በዚህ ዕቅድ መሠረት ትምህርት የለጠነ የለው ኃይል በማምረትና የትምህርት ጥራትን በማሻሻል ላይ እንዲያተኩር ታቅዶ ነበር። ሆኖም የዕቅዱ ውጤት በተጨባጭ ሳይታወቅ ሁለተኛው የአምስት ዓመት ዕቅድ በ1962 ተጀምሮ ነበር። ይህም እንደ መጀመሪያው ውጤቱ በይፋ ሳይነገር ሶስተኛው የአምስት ዓመት ዕቅድ በ1972 እንደተጀመረ በ1974 አብዮት ተከሰተ።

ምንም እንኳ የትምህርቱ ሂደት በመጀመሪያ የአምስት ዓመት ዕቅድ ያስመዘገበው ውጤት በሚገባ ባይታወቅም ሂደቱ ግን እንደቀጠለ ነበር። በአጠቃላይ የተማሪዎቹ ቁጥር በ1959/60 ወደ ሩብ ሚሊዩን እንደደረሰ ተመዝግቧል። ይሁን እንጂ ከውጭም ከውስጥም በትምህርቱ ሥርዓት ላይ የተለያዩ ትችቶች[10] ይሰነዘሩ ነበር። ከብዙው በጥቂቱ ለመጥቀስ ያህል፤

ሀ/ የትምህርቱ ዕድል የሚደርሰው ለጥቂቶች ብቻ እንደነበረ፤

ለ/ የትምህርቱ ስርጭት ፍትኃዊ እንዳልነበረ፤ ለምሳሌ፤ በያታ፤ በወንዶችና በሴቶች ተማሪዎች መካከል በ1ኛ ደረጃ ትምህርት የሴቶች ተሳትፎ 32 በመቶ በ2ኛ ደረጃ 29 በመቶ እንደነበረና እንዲሁም በጠቅላይ ግዛቶች መካከል ለምሳሌ በ1974 ከነበሩት 124 የ2ኛ ደረጃ ት/ቤቶች ሰባዎቹ በአዲስ አበባ፤ በሸዋና በኤርትራ ብቻ እንደነበሩ።

ሐ/ ሥርዓተ ትምህርቱ ዕውቀት ተኮር እንጂ ሙያ ተኮር አለመሆኑ፤

መ/ በየትምህርት ደረጃው የሚወድቀው ተማሪ ቁጥር ከፍተኛ መሆኑ ለምሳሌ፤ አንደኛ ክፍል ከሚገቡት መካከል በመጨረሻ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የሚደርሱት 6 በመቶ ብቻ እንደሚሆኑ፤

ሠ/ ሥርዓተ ትምህርቱ እምብዛም የአገራቱን ፍላጐትና ችግር አለማንፀባረቁ፤

ረ/ የትምህርቱ አመራርና አስተዳደር በጣም የተማከለ በመሆኑ በቢሮክራሲ የተተበተበ መሆኑ የሚሉ ነበሩ።

እነዚህ ከላይ የተዘረዘሩት ትችቶች እምብዛም አጠያያቂ ባይሆኑም ምናልባት እዚህ ላይ አንድ ግልጽ መሆን የሚገባው ነገር የትምህርት ዕድል የሚያገኙት ጥቂቶች ነበሩ በሚልም እነዚህ ጥቂቶች የተባሉት ግን ዕድሉን አግኝተው በተጨባጭ የተጠቀመበት በአብዛኛው ከድሃው ቤተሰብ የመጡት እንጂ ከመኳንንቱና ከሀብታሙ የመጡት አልነበሩም። እነሱማ ዕድሉም ቢኖራቸው ብዙዎች አልተጠቀመበትም፣ ምክንያቱም በዚያ ዘመን እንደሚባለው *ሁሉ በእጃቸው ሁሉ በደጃቸው* ነበርና። ስለዚህ በማወቅም ባለማወቅ የትምህርት ዕድል በዚያን ዘመን ያገኘ የነበረው የመኳንንቱና የሀብታሙ ልጅ አልነበረም የሚለው ግንባቤ ቢመሰረት ምክንያቱም ፈረንጆች እንደሚሉት *ለሰይጣንም ቢሆን የሚገባውን መሥጠት* ያስፈልጋል።

ቀደም ብለውም በትምህርቱ ላይ ከተነሱት ትችቶች በተጨማሪ ሌላ የትምህርቱን ሁኔታ የሚያባብስ ገዳይ ተከሰተ። ይኸውም በ1961 የአዲስ አበባ የአፍሪቃ የትምህርት ኮንፈረንስ በሚባል የሚታወቀው መካሔዱ ነው። በዚህ ኮንፈረንስ ላይ የኢትዮጵያ የትምህርት ተሳትፎ ከሌሎች ከሰሐራ በታች ካሉና በቅርብ ጊዜም ከቅኝ አገዛዝ ቀንበር ከወጡ አገሮች ጋር ሲነፃፀር የአንደኛ ደረጃው 3.3 በመቶ ሲሆን የ2ኛ ደረጃው ደግሞ በባሰ ሁኔታ 0.5 በመቶ[11] ሆኖ ተገኘ። ኢትዮጵያ ተሸላ የተገኘችው ከአንድ አገር ብቻ ነበር። ይህም በስልጣን ላይ ለነበረው መንግሥት አሳፋሪ ነበር።

የኮንፈረንሱም ዋና ዓላማ አፍሪቃ እስካሁን ድረስ በትምህርት ያደረገችውን እርምጃ ለመቃኘት ና የወደፊትም ርዕይ ለማስቀመጥ በመሆኑ ኮንፈረንሱ በመጨረሻ ካስተላለፋቸው ዋነኛው ውሳኔ በሃያ ዓመት ውስጥ ማለትም በ1981 ለሁሉም ሕፃናት የ1ኛ ደረጃን ትምህርት ለማድረስ የሚል ነበር። በዚህም መሠረት መንግሥትም የአንደኛ ደረጃን ተሳትፎ ለመጨመር በዓለም ባንክ በተገኘ ብድር መነሪ አድርጐ ነበር። ይሁን እንጂ በ1974/75 የአንደኛ ደረጃ ተሳትፎ ከአሥራ ሁለት በመቶ አልዘለለም[12]። በአጠቃላይ ግን የ1961 ውሳኔን

በሚመለከት በሌሎችም አገሮች ቢሆን፣ ከሃያ ዓመት በኋላ የታየ ነገር ቢኖር 1981 መጥቶ መሔዱ ብቻ ነው።

4.1 የመጀመሪያው በአገሪቱ ትምህርት ላይ የተደረገ ጥናት

ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በትምህርቱ ይዘት ላይ የተነሱት ትችቶችና በተጨማሪም የአዲስ አበባ የአፍሪቃ የትምህርት ኮንፈረንስ ላይ የተጋለጠው የአገሪቱ የትምህርት ሁኔታ ተደማምረው ይመስላል መንግሥት አንድ "Education Sector Review"[13] የተሰኘ አገር አቀፍ የሆነ ጥናት በትምህርቱ ላይ እንዲካሔድ በ1972 ወሰነ። የጥናቱም ዋና ዓላማ የትምህርቱን ሁኔታ በአጠቃላይ የሚቃኝና ትምህርቱም ለአገሪቱ ዕድገትና አንድነት እንዴት እንደሚጠቅም ለሳብ እንዲያቀርብ ነበር። አጥኝዎቹም በአጠቃላይ 80 ሲሆኑ ከግማሽ በላይ ግን ኢትዮጵያውያን ነበሩ። ይሁንና የትምህርቱ ጉዳይ በቀጥታ የሚመለከታቸው መምህራንና ወላጆች በጥናቱ ላይ ተሳትፏቸው እምብዛም አልነበረም። በመጨረሻም ጥናቱ እንደ አማራጭ ካቀረባቸው መፍትሔዎች መካከል መንግሥት የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በሚመለከት የመረጠው አብዛኛውን ተማሪ እስከ አራተኛ ክፍል ለማስጨረስ የሚያስችለውንና ከዚያ የተረፉትን ደግሞ ሃያ በመቶ ብቻ ወደ ሁለተኛ መለስተኛ ደረጃ የሚያደርሰውን ነበር። ይህም በተለይ በመምህራንና በወላጆች ተቀባይነት አላገኘም። በተጨማሪም ተግባራዊ እንዲሆን የተወሰነውም አብዮት የፈነዳበት ወቅት በመሆኑ ቅራኔዎች ስለበዙበት በዛው ተዳፍኖ ቀረ።

4.2 የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ አገልግሎት

የዚህን ዘመን የትምህርት ሒደት ይህ ነገር ሳይጠቀስ ቢጠቃለል በርግጥም አንድ የጐደለ ነገር እንደቀረ ሳይሰማ አይቀርም። ምናልባትም ከዛሬ አርባ ዓመት በፊት ሳይሆን አይቀርም እንደርዕይ የሚቆጠር በአገሪቱ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ ተከስቶ ነበር። ይኸውም በዘመኑ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቨርሲቲ ይባል በነበረው ማለትም በዛሬው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ተጀመሮ የነበረው የኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ አገልግሎት[14] የተሰኘው ኘሮግራም ነው። የዚህም ኘሮግራም ዋና ዓላማ የዩኒቨርሲው ተማሪዎች ከመመረቃቸው በፊት ሶስተኛ ዓመት እንደጨረሱ ለአንድ ዓመት ለኅብረተሰቡ አገልግሎት እንዲሰጡ ነበር። በዚሁ መሠረት ከ1965 ጀምሮ ተማሪዎቹ በአብዛኛው የአገሪቱ ክፍሎች እየተላኩ ብዙሃኑ በ2ኛ ደረጃ ት/ቤት መምህርነት የቀሩት ደግሞ በሚሰለጥኑበት ሙያዎች አገልግሎት እንዲሰጡ አድርጓቸዋል። ይህም ዕድል ለኅብረተሰቡ አገልግሎት ከመስጠት ባሻገር በአጠቃላይ በቅርብ ሕገበኑን ለማወቅና በተለይም የነበረበትን ችግር ለመገንዘብ እንዳስቻላቸው ይገመታል።

እንደዚህም ዓይነቱ ፕሮግራም ምን ያህል ትምህርት ለሃገሪቱ ልማት አስተዋፅኦ ሊኖረው እንደሚችልና ከዚያም አልፎ ሕገበኑንና የተማረውን ክፍል በመተሳሰብ ሊያስተሳስር እንደሚረዳ ለመገንዘብ ይቻላል። ስለሆነም ይህን መሰል የአገልግሎት ኘሮግራም እንደገና በሚገባ ተጠንቶና ነፍስ እንዲዘራ ተደርጐ ወደፊት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ላይ ተግባራዊ ቢሆን የአገሪቱ ልማት ትርጉም ሊኖረውና ሊሳካ ስለሚችል ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ምናልባትም ተማሪዎች የከፍተኛ ትምህርትን ወጭ እንዲጋሩ ለሚለው የተሻለና ጠቃሚ አማራጭ ሊሆን ይችላል።

ማጠቃለያ

በዚህ ዘመን ዘመናዊ ትምህርት ወደ አገራቱ የገባበት ሲሆን አገባቡ ግን አንዲህ በቀላል አልነበረም። ምኒልክ ቀሳውስቱንና መኳንንቱን በዘዴ በማግባባት፣ ኃይለሥላሴ ደግሞ ተማሪውን አዳራ ት/ቤት በማስገባትና በማባበል ዘመናዊ ትምህርት ተቀባይነት እንዲያገኝ በማድረግ ነበር። ዘመናዊ ትምህርትም ቢያንስ ቢያንስ፣ የአገራቱን ቢሮክራሲ የሚያንቀሳቅስ ምሁራን እንዳፈራ ብዙም የሚያጠያይቅ አይደለም።

ምናልባትም የሚያጠያይቀው ጉዳይ ዘመናዊ ትምህርት ለአገራቱ ልማት ምን ፈይዷል የሚለው ነው። ለዚህም መልስ ጠቅሟል ወይም አልጠቀመም ብሎ ከመመለስ በፊት ግን አንድ ሌላ ጥያቄ መነሳት ያለበት ይመስላል። ይኸውም ትምህርት ምን ዓይነት የልማት ዓላማዎች ሲኖሩትና በምን ዓይነት ሁኔታ ሲሰጥ ነው ትምህርት ለልማት የሚጠበቅበትን አስተዋፅኦ የሚያደርገው የሚለው በቅድሚያ መታየት ይገባው ይሆናል። በመሆኑም ያለፈው ትምህርት ብቻ ሳይሆን አሁንም ወደፊት የሚሰጠው ትምህርት ከዚህ አንፃር መታየት ሊኖርበት ይገባል። በሌላ በኩል ግን እዚህ ላይ ሳይነሳ መታለፍ የሌለበት ጉዳይ በዚህ ዘመን በ60ዎቹና በ70ዎቹ ዓመታት የነበሩት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በመማራቸውና በማወቃቸው የተነሳ ይመስላል የሕገባቸው ሕሊና /conscience of their people/ በመሆን አብዮት አንዲመጣ የታገሉት። ሰለዚህም የእነርሱ ርዕይ በመጀመሪያ ደረጃ አብዮት በአገራቱ በማምጣት፣ ከዚያም ሕገባቸውን ከነበረበት ስቃይ የሚያወጣ ልማት ለማካሄድ ሳይሆን እንዳልቀረ ግንዛቤ ከተወሰደ በዘመኑ የተሰጠው ትምህርት መና አልቀረም በማለት ለማጠቃለል ያስችል ይሆናል።

5 ትምህርት በዘመነ አብዮት

ከመነሻው አንሰቶ የዚህ ዘመን የትምህርት ሒደት መለያው ዘመቻ ነበር ቢባል ማጋነን አያሆንም። ለምሳሌም ያህል የዕድገት በጎበረት ዘመቻ፤ መሐይምነትን የማጥፋት ዘመቻ፤ የመተከልና የጋምቤላ ዘመቻ። በአገራቱ በ1974 አብዮት እንደተከሰተ ትምህርቱም አብዮቱን እንዲያንፀባርቅ በ1976 ለአገራቱ በወጣው የብሔራዊ ዲሞክራሲያዊ አብዮት ፕሮግራም[15] መሠረት የትምህረቱ መሠረታዊ ዓላማ ማሐይምነትን ማጥፋት፤ ሳይንስና ቴክኖሎጂ እንዲሁም ሥነጽሑፍንና አርት እንዲዳብሩ ማድረግ እንደሆነ ተደነገገ። ከጊዜ በኋላም ይኸው ዓላማ ትምህርት ለምርት፤ ትምህርት ለሳይንሳዊ ምርምርና ትምህርት ለሶሻሊስታዊ ንቃት በሚል መፈክር ተጠቃለለ።

አብዮቱ እንደተከሰተ ብዙም ሳይቆይ የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች ዕድገት በሕብረት በተሰኘ ዘመቻ በመላ አገራቱ ለልማት ሥራ እንዲዘምቱ በ1975 በመደረገ የተነሳ በጠቅላላ በአገራቱ ትምህርት ለሁለት ዓመት ተቋረጠ። እዚህ ላይ ግን መነሳት የማገባው ለዚህን ያህል ጊዜ የተካሄደው ዘመቻ ውጤቱ ምን እንደነበረ በጥናት ላይ የተመሠረተ መረጃ ያለ አይመስልም።

ከዕድገት በሕብረት ዘመቻ ባሻገር ግን የትምህርቱ ሒደት የአንደኛ ደረጃን ትምህርት ተሳትፎ ለመጨመር ጥረት በመደረገ በ1973/74 የአንደኛ ደረጃን ት/ቤቶች ቁጥር ወደ 3000 አካባቢ የነበረው በ1986/87 ወደ 8000 እንደደረሰና የተማሪዎቹም ተሳትፎ ወደ 34 በመቶ እንደአደገ ተመልክቷል[16]። ይህም ከአብዮት በፊት ከነበረው 12 በመቶ ሲነፃፀር ከፍተኛ ነው። ሆኖም

ለትምህርት የተመደበው ባጀት በ1974 ከነበረው 17 በመቶ በሰማንያዎቹ ዓመታት ውስጥ ወደ 9 በመቶ በማሽቆልቆሉ የተነሳ የትምህርቱ ጥራት ገዳይ አጠያያቂ ደረጃ ላይ ደረሰ። የጥራቱም ጉዳይ በተማሪዎች የመማሪያ መጻሕፍት እና በመምህራን እጥረት ላይ ተንፀባረቋል። በዚህም የተነሳ 5500 የሚሆኑ አሥራ ሁለተኛ ክፍል የጨረሱ፣ ነገር ግን ምንም የመምህርነት ሙያ ሥልጠና የሌላቸው በወር በጣም አነስተኛ ደሞዝ የሚከፍላቸው የድጎማ መምህራን የሚባሉ ተቀጥረው ነበር። የድጎማ መምህራንም የተባሉት በተለይ በገጠሩ ኅብረተሰቡ፣ መምህራኑን እህል በመስጥርና በመሳሰሉት ይደጉሟቸው ስለነበር ነው። የትምህርቱ ጥራት በዚያን ወቅት አስጊ ሁኔታ ላይ እንደነበር ለመጥቀስ በዚያን ጊዜ የምኒልክ ት/ቤት ርዕሰ መምህር የነበሩት ስለ ት/ቤቱ የትምህርት ሁኔታ ለአንድ ቃለ መጠይቅ መልስ ሲሰጡ እንዲህ ገለፀውታል።

"በምኒልክ ት/ቤት በመደበኛውና በማታው 11,600 ተማሪዎች አሉ። ከብዛታቸው የተነሳ መምህራን እያንዳንዱን ተማሪ በትምህርቱ ሊረዱት አይችሉም። ስለሆነም ተማሪዎችና መምህራን የርቀት ትምህርት የሚያካሒዱ ይመስላሉ። ለምሳሌ አንድ መምህር ለተማሪው የክፍል ሥራ ሊሰጠው አይችልም። ተማሪዎች በአንድ ክፍል ሰባና ሰማንያ ሲሆኑና ለላላ ብቻ ሲያልፉ አብዛኞቹ ለምን እንደወደቁ መምህሩ ሊያውቅ እይችልም[17]።"

ከላይ እንደተጠቀሰው የትምህርቱ ሁኔታ አሳሰቢ በመሆኑ መንግሥትም «የኢትዮጵያ አጠቃላይ ትምህርት ጥናታዊ ግምገማ»[18] በሚል ርዕስ አንድ አጥኚ ኮሚቴ በ1983 አቋቋመ። የጥናቱም ዋና ዓላማ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርትን መገመገምና ችግሮችን ለይቶ አውቆ መፍትሔዎች እንዲጠቁመ ነበር። በዚሁ መሠረት የተለያዩ አጥኚ ቡድኖች ተቋቁመው ሰፋ ያለ ጥናት አካሒደው በ1986 በመጨረሻ ትምህርቱ የሚሻሻልበትን የተለያዩ መፍትሔዎች አቀረቡ። ይሁን እንጂ የጥናቱ ውጤት ለመንግሥት ቢቀርብም ለጥናቱ ብዙም ትኩረት ሳይሰጥ መንግሥት የራሱን የአሥር ዓመት ጠቋሚ ዕቅድ በማውጣት ተግባራዊ ለማድረግ በገፃቸት ላይ እንዳለ የመንግሥት ለወጥ መሣሪያ ጥናቱም፣ የአሥር ዓመቱም እቅድ፣ የEducation Sector Review ዓይነት ዕጣ ስለደረሰው በዛው ተዳፍኖ ቀረ።

ከትምህርቱ ጥራት በተጨማሪ ስለዚህ ዘመን ትምህርት መታወስ የሚገባው አማሪካ አብዮቱ እንደተከሰተ በአገሪቱ የነበራት ተሰሚነት በሶሺየት ዩኒየን ተተካ። በዚህም የተነሳ የአገሪቱ ትምህርት ለአሪነቱ ጊዜ ለውጭ ተዕንኦ ተጋለጠ። ስለሆነም በተለይ ሥርዓተ ትምህርቱ ከመደበኛ ትምህርት አማሲሰጠ ትምህርቶች በተጨማሪ በየትምህርት ደረጃው የሶሺሊስት ርዕዮተ ዓለምን የሚያንፀባርቁ ኮርሶች እንዲሰጠ ተደረገ። ይህ የሚያመለክተው የሚሰጠው ትምህርት ለአገሪቱ ልማት መጭመም አለመጭመሙ ታይቶ ሳይሆን መንግሥት የሚከተለውን የፖለቲካ ሥርዓት ማንፀባረቁ ብቻ ነው።

5.1. መሐይመነትን ለማጥፋት ዘመቻ

ምናልባት በዚህ ዘመን በትምህርት በኩል ከተደረገት ጥረቶች መካከል ሳይጠሳ መታለፍ የሌለበት ገዳይ ቢኖር ለብዙ ዘመናት በማወቅም ሆነ ባለማወቅ በመንግሥት ተበንግዶ የቆየው የመሐይምነትን የማጥፋቱ ነገር ነው። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው መሐይምነት በአገሪቱ ለብዙ ዘመን ተንሠራፍቶ የመቆየቱ ገዳይ አስገራሚ የሚያደረገው አገሪቱ ከጥንት ጀምሮ የራስዋ የሆነ የጽሑፍ ቋንቋ ባለቤት ሆና መቆየቷ ነው። ምንም እንኳን በመንግሥት በኩል መሐይምነትን ለማጥፋት ይህን ያህል ትኩረት ባይደረግም አንዳንድ ቡድኖች ግን

«የፊደል ሠራዊት» በሚል ስም በአምሳዎቹ ዓመታት መከራ አድርገው እንደነበር ይታወሳል።

የዚህን ዘመን ትምህርት ምናልባት ለየት የሚያደርገው መሐይምነትን ለማጥፋት ከ1979 ጀምሮ የተወሰደው እርምጃ ነው። ምናልባትም ይህ እርምጃ የተወሰደው መንግሥት ከሚያራምደው ርዕዮተዓለም አንጻር ሲታይ መሐይም ሕዝብ ይዞ ሶሻሊስት ርዕዮተዓለም ማካሄድ እንደማይቻል በመገንዘቡ ይሆናል። በዘመቻውም ወቅት *የተማረ ሁሉ ያስተምር* በሚል መፈክር ዘመቻው በተጧጧፈ ሁኔታ ተካሒዷል። ዘመቻውም አሥራ አንደኛው ዙር በ1990 ላይ ሲደረስ የመሐይማን ቁጥር በ1974 ከነበረት ከ93 በመቶ ወደ 24 በመቶ መውረዱ ተበሰረ። የዩኔስኮም ድርጅት አገሪቱ መሐይምነትን ለማጥፋት ላደረገችው ጥረትና ላስመዘገበችውም ውጤት ሽልማት አበረከተ። እዚህ ላይ አንድ መገንዘብ የሚያስፍልገው ጉዳይ ግን በመሐይምነት ላይ የሚደረገው ዘመቻ በአንድ ጊዜ የሚያከትም አለመሆኑ ነው። ምክንያቱም መሐይምነት እንደ አንዳንድ በሽታ የማገርሸት ባሕርይ አለው። ስለዚህም እንዳያገረሽ ተከታታይ የሆነ ክትትል ያስፈልገዋል። ምናልባትም በአሁን ጊዜ በዚያን ዘመን ከመሐይምነት ተላቀዋል ተብለው ሠርተፊኬት የተሰጣቸው ሠርተፊኬቱን ይዘው ይገኙ እንደሆን እንጂ ብዙዎቹ መሐይመነት አገርሽቶባቸው ሊሆን ይችላል። ለማንኛውም በመረጃ የተደገፈ ጥናት ያለ ስለማይመስል ለማወቅ ያስችግራል።

5.2. ከፍተኛ ትምህርት

ከፍተኛ ትምህርትን በተመለከተ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው የመንግሥት ትኩረት በአብዛኛው መሃይምነትን ለማጥፍትና የአንደኛ ደረጀ ትምህርትን ተሳትፎ በመጨመር ላይ በመሆኑ ያሳየው ዕድገት እስከዚህም አልነበረም። በአጠቃላይም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የተማሪዎች ቁጥር ከ 15,000 አልዘለለም[20]። ምናልባት ከፍተኛ ትምህርት ለየት ያለ ለውጥ በዚህ ዘመን ያሳየው በ1978 የድህረ ምረቃ ፕሮግራም ለመጀመሪያ ጊዜ መጀመሩ ነው። ይህም ያለምክንያት አልነበረም። በአብዮቱ ምክንያት በተፈጠሩ የፖለቲካና እንዲሁም የተለያዩ ምክንያቶች የአገሪቱ ምሁራን ከዚህ በፊት ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ ከአገር መውጣት ጀመሩ። በተጨማሪም የውጭ አገር መምህራን በተለይ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ አገር ጥለው በመሔዳቸው ዩኒቨርሲቲው በመምህራን ተራቆተ። ከዚህ አልፎ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ የተላኩትም አብዛኞቹ ሳይመለሱ ቀሩ። ለምሳሌ በ1992 የተደረገ አንድ ጥናት እንደጠቆመው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በሰባዎቹ ዓመታት ያስተምሩ ከነበሩት 135 ኢትዮጵያውያን መምህራን በሰማንያዎቹ ግማሽ የሚሆኑት ጥለው ወደ ውጭ እንደሔዱ ያመለክታል[21]። ከዚህ ሌላ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የ1983/84 የአካዳሚክ ምክትል ፕሬዚዳንት ዓመታዊ ሪፖርት እንዳመለከተው 300 የሚሆኑ ለከፍተኛ ትምህርት ተልከው 22 ወይም ሰባት በመቶ ብቻ እንደተመለሱ ጠቅሷል[22]። በዚህም የተነሳ የተፈጠረውን ከፍተኛ የመምህራን እጥረት በመጠኑም ቢሆን ለመቋቋም እዚህ አገር ውስጥ የድህረ ምረቃ ፕሮግራም እንዲጀመር የተደረገ ይመስላል ።

5.3. የ1985 የመምህራንና የተማሪዎች ዘመቻ

ከከፍተኛ ትምህርት ጋር በተያያዘ ሌላ መነሳት የሚገባው የዘመቻው ባሕል እንደገና አገርሽቶ በ1984 በተከሰተው ድርቅና ርሀብ የተነሳ ችግረኛውን ሕዝብ ወደ መተከልና ጋምቤላ ሳጀ ሠርቶ ለማስፈር የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች ያለምንም ውይይትና

ቅድመ ዝግጅት በድንገት በ1985 የዓመቱን ትምህርት አቋርጠው እንዲዘምቱ ተገደዱ። እንዲህ ዓይነቱ እርምጃ ጥያቄና ቅሬታ ማስነሳቱ አልቀረም። መሰረታዊ የነበረውም ጥያቄ ለምን ችግረኛውን ሕዝብ እንድንረዳው ተጠይቅን ሳይሆን፣ እውን የዘመቻው ዓላማ ለሠራሪው ጎጅ እንድንሠራ ነው ወይስ ከበስተጀርባው መንግሥት ሌላ ዓላማ ቢኖረው ነው የሚል ነበር። መልሱ እስካሁንም ድረስ በተጨባጭ የታወቀ አይመስልም። ለማንኛውም በመቤሬሻ ዘመቻውም ይህ ነው የሚባል በተጨባጭ ለሰሩሪው ያስገኘው ሩይዳ አልነበረም።

ሦስተኛ ለመነመት የሚቻል ነገር ቢኖር መንግሥት ስለ ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መምህራንና ተማሪዎች ያለው አስተሳሰብ ጤናማ ያልነበረና በጥርጣሬ ላይ የተመሠረተ እንደነበር ነው። ይህ ዘመቻ ያረጋገጠው ነገር ቢኖር መንግሥትና የተማረው ክፍል በጋራ ነልተው ሕዝቡን ነትግሩ ለማውጣት የሚደረግ ጥረትና ከዚያም አልፎ የአገር ልማት ለስምር እንደማይችል የሚያስትምር ስለሆነ ለወደፊት ጠቃሚነት ሊኖረው ይችላል። ትምህርት ለልማት የማጠቅመውም ሁለቱ ለአገር ልማት ሲወያዩና የጋራ ርዕይ ሲኖራቸው ይመስላል።

5.4. በዘመኑ የወጡ የትምህርት አዋጆች

በዚህ ዘመን አራት ያህል ትምህርትን የሚመለከቱ አዋጆች ተደንግገዋል። የመጀመሪያው የግል ት/ቤቶች ተወርሰው በሕዝብ ቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ያደረገው በቁ54/1983 የወጣው ነው። ይህ አዋጅ የግል ት/ቤቶች እንዳይኖሩ በመከልከሉ በመንግሥት ት/ቤቶች ላይ ጫና ፈጥሮ ነበር። በለላ በነሁል ግን ምንም እንኳን ዘመነ የሶሽያሊዝም ሥርዓት የሰፈነበት ነበር በባልም፣ የዘመነ ባለሥልጣናትና ሀብታሞች ልጆቻቸውን አዋጅ ሳይመለከታቸው ለውጭ ነሚኒ፡ ዜሮች ልጆች በተቋቋመ ት/ቤቶችና እንዲሁም በሚሲዮን ት/ቤቶች ያስተምሩ ነበር።

ከዚህም ለላ የኢትዮጵያ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን የሚያቋቁም አዋጅ በቁ. 62 1982 ለወጣ እንዲሁም አዋጅ ቁ.103 1983 የት/ቤቶች አስተዳደርና ቁጥጥር በገጠር ወይም በከተማ ኗሪዎች በተቋቋመ የት/ቤት ኮሚቴ እንዲሆን አድርጓል[23]። ይህ አዋጅ በመሠረቱ የሚደገፍና መጠናከርም መለመድም ያለበት ነበር። ምክንያቱም በተለይ ት/ቤት ጎብረተሰቡን በቅርብ የሚያገለግል ተቋም እንደመሆኑ ከጎብረተሰቡ መቆራኘትና ሕብረተሰቡ በተቻለው መጠን መነከባከብ ማስተዳደርና መቆጣጠር ይገባዋል። ምናልባትም ይህ ጎብረተሰቡ በት/ቤቶች ላይ የሚኖረው ኃላፊነት የመንግሥት በትምህርት ቤቶች ላይ የሚያደርገውን አለአስፈላጊ ጣልቃገብነት ሊያስቀረው ይችላል። ሆኖም ግን በዘመኑ አዋጁ ተግባራዊ ይሁን እንጂ በት/ቤቶች የመንግሥት ጣልቃገብነትን አስቀርቶ ነበር ለማለት ማስረጃ ማቅረብ የሚቻል አይመስልም። ለላም ተጨማሪ አዋጅ በቁ.107 1985 የከፍተኛ ትምህርትን አስተዳደር የሚመለከት እንደወጣ ይታወሳል።

5.5. ማጠቃለያ

በዚህ ዘመን እንደታየው በትምህርት አማካይነት «አዲሱን ሰው» በሶሻሊስታዊው ርዕዮት ለመቅረጽ ተሞክሮ ነበር። ነገር ግን እንኳን አዲሱን ሰው ለመፍጠር ይቅርና ሌላ አስተሳሰብ የነበረውን ምሁር እንኳን በአገሩ ውስጥ አገሬ ብሎ እንዳይቀመጥ ለአገር ልማት የበኩልን አስተዋጽኦ እንዳያደርግ መንግሥት በፈጠረው የፖለቲካና የተለያዩ ችግሮች የምሁራን ፍልሰት በመከተሉ አገራቱ በተማረ የሰው ኃይል እጥረት እስከዛሬ ድረስ ልታንሰራራ

አልቻለችም። በዚህም የተነሳ *የድህይቱ አገር ዕጣ ፈንታ* እንደሚባለው አስተምሮ ለሰው ሆኗል። ምናልባትም በዚህ ዘመን በትምህርት ከተደረጉት ጥረት ሁሉ ተወደደም ተጠላም ሊመሰገን የሚገባው ሕዝብን ከመሐይምነት ነፃ ለማወጣት የተደረገው መከራ ነው፤ ምንም እንኳን በአሁን ጊዜ ከመሐይምነት ተላቀው ነበር የተባሉት ሁኔታቸው ባይታወቅም።

በሌላ በኩል በዘመኑ የነበረው የመንግሥትና የምሁራን ግንኙነት በእምነት ላይ የተመሠረተ ባለመሆኑ፣ የአገሪቱ ምሁራን ለአገር ልማት የሚጠበቅባቸውን ተሳትፎ ለማድረግ ባለመቻላቸው ትምህርት በዚያን ዘመን ለልማት በተጨባጭ ይህን አድርጓል ለማለት ያስቸግራል።

6. ትምህርት ከ1994 ወዲህ

6.1. የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ

በሥልጣን ላይ የነበረው መንግሥት በ1991 ሲወርድ የሽግግር መንግሥት ከተቋቋመ በኋላ የነበረውን የትምህርት ሥርዓት ለመቀየር አንድ የትምህርት ፖሊሲ አውጭ ኮሚቴ ተቋቋመ። በዚሁ መሠረት ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲና ከሌሎች ሃያ ሁለት ከሚሆኑ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የተውጣጣ፣ በአጠቃላይ አርባ ሁለት አባላት ጥናት ካካሔዱ በኋላ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ[24] ተበለ። ከ1994 ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን ተደረገ። ምናልባት እዚህ ላይ ስለትምህርት ፖሊሲ ቀረፃ አንዳንድ ግንባቤ ማንሳት ያስፈልግ ይሆናል። በመጀመሪያ ደረጃ አንድ የትምህርት ፖሊሲ ሲቀረፅ የሕዝብን ፍላጐትና ችግር አውቆ ይህንኑ ለሚሟላትና ለመፍታት ብሎም የአገር ልማት የሚጠበቅባቸውን ተሳትፎ ለማድረግ ድረስ ፖሊሲው በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ የሚጠቅማቸውና የሚመለከታቸውን ወገኖች በፖሊሲው ቀረፃ ወቅት ለይስሙላ ብቻ ሳይሆን ተገቢ በሆነ ሁኔታ ማሳተፍና ይጠበቅበታል።

በዚህም መሠረት የትምህርት ፖሊሲን ቀረፃ በተመለከተ የመምህራን ተሳትፎ የሚያጠያይቅ አይደለም። ምክንያቱም ፖሊሲው ተግባራዊ ሲሆን ቀጥተኛና ወሳኝ ሚና በተለይ በመማር ማስተማሩ ሒደት የሚጫወቱት መምህራኑ ናቸው። ይህም ተሳትፏቸው ከመጀ ግደታቸው ብቻ ሳይሆን ከነጓደኞች ጭምር ፖሊሲውን በበቃት እንዲተገብሩት ያነቃቃቸዋል። በትምህርት ፖሊሲ ቀረፃ ወቅት የወላጆችም ተሳትፎ አማራጭ የለውም። ምክንያቱም ከወላጆች የበለጠ ለልጁ ትምህርት በቀጥታ የሚመለከተውና የሚቆረቆር የለምና። ስለሆነም ሌላ አካል ለአንተም፣ ለልጅህም፣ ቢሆን የሚበጃትህን የማወቀው እኔ ነኝና የአንተ ተሳትፎ አያስፈልግም ሊል አይገባውም። ከዚህም በላይ ደግሞ የትምህርት ፖሊሲ ዋና ዋና መሠረታዊ ዓላማ የአገር ልማት እስከሆነ ድረስ የትምህርትን ወጤት በተመለከተ ለምሳሌ እንደ ቀጣሪዎች ያሉ፣ በፖሊሲው ቀረፃ ጊዜ በተለይም የትምህርቱ ዓላማ በአገር ልማት ላይ ያተኮረ ለመሆኑ ለማረጋገጥ እንዲቻል ተሳትፏቸው ወሳኝ ነው። ከዚህ አንፃር የመምህራን ተሳትፎ በትምህርት ሥልጠና ፖሊሲ ቀረፃ ላይ ሲታይ፣ ምንም እንኳ መምህራን በአዲስ አበባና በአንዳንድ ክልሎች በፖሊሲው ረቂቅ ላይ በትምህርት ቤት ደረጃ እንዲወያዩ በደረጓም፣ የተሰበሰበው የውይይቱ ሪፖርት[25] እንዳመለከተው ከሆነ የተሰጡት አስተያየቶች ረቂቁን እንዳለ የመቀበል እንጂ ፖሊሲውን የማያዳብሩ እንኳን ሳልቦች አልተሰነዘሩም። ስለሆነም የወይይቱን ሁኔታ አጠያያቂ ያደርገዋል። ከዚህም በተጨማሪ በዚያን ወቅት የመምህራን ማህበር ሁለት ላይ ተከፍሎ የነበረበት በመሆኑ በረቂቅ ፖሊሲው ላይ የተደረገውን ውይይት ጥያቄ ውስጥ ያስገባዋል። እንዲሁም የወላጆችና የሌሎች

የትምህርቱ ፖሊሲ ተጠቃሚዎች ተሳትፎ ለመኖሩ በተጨባጭ ያለ ማስረጃ አልተገኘም። እንግዲህ በእንደዚህ ያለ ሁኔታ ነው ፖሊሲው ተግባራዊ እንዲሆን የተደረገው።

6.2. የትምህርት ተሳትፎና ጥራት

ለማንኛውም አዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት ከ1994 እስኪ እስከ 2004 ድረስ ማለትም ላለፉት አሥር ዓመታት የተደረገውን መቃኘት፣ አሁን ያለውን፣ ወደፊትም ሊሆን የሚችለውን፣ ሁኔታ ለመገመት ያስችል ይሆናል። ስለዚህ በ2004 በነበረ መንግሥት መረጃ[26] በተገኘው መሠረት የትምህርት ተሳትፎ በየትምህርት ደረጃ የሚከተለውን ይመስላል።

ሀ. የአንደኛ ደረጃ የተማሪዎች ተሳትፎ ወደ 9.5 ሚሊዮን የደረሰ ሲሆን ይህም 68.4 በመቶ መሆኑ ነው። ከዚህም ውስጥ አራት ሚሊዮን ወይም 59 በመቶ የሚሆኑት ሴቶች ናቸው።

ለ. የሁለተኛ ደረጃ /9-12/ የተማሪዎች ተሳትፎ ወደ 700,000 የደረሱ ሲሆን ከዚህም 16 በመቶ ሴቶች ናቸው። ከዚህ ጋር ተያይዞ ልዩ ትኩረት የተሰጠው የሙያና የቴክኒክ ትምህርት ወደ 87,000 እንደደረሰና የሴቶችም ድርሻ 47.5 በመቶ ሆኗል።

ሐ. በከፍተኛ ትምህርት በመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የተማሪዎች ቁጥር ወደ 130,000 እንደደረሰና የሴቶችም ተሳትፎ 23 በመቶ ደርሷል።

መምህራንንም በሚመለከት በአንደኛ ደረጃ ብዛታቸው ከ140,000 በላይ እንደደረሰና ከዚህም 33 በመቶ ሴቶች እንደሆኑ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ቁጥራቸው ወደ 15,000 እንደተጠጋና የሴቶችም ደረጃ ስምንት በመቶ ሲሆን በአጠቃላይ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መምህራን ወደ 165,000 አካባቢ ደርሶ ነበር። ከላይ እንደሚታየው የትምህርት ተሳትፎ በየትምህርት ደረጃው በአንፃራዊ መልኩ ፊት ከነበረው ዕድገት ማሳየቱ የሚደገፍ ነው። እዚህ ላይ ግን አንድ መታወስ ያለበት ቁም ነገር አለ። ይኸውም ትምህርቱን በሚመለከት የትምህርት ተሳትፎና የትምህርት ጥራት ሁለቱም አማራጭ የሌላቸው ተፈላጊዎች ናቸው። በአንድ በኩል የትምህርት ተሳትፎ ፍትሃዊ እንዲሆን በፆታ፣ በሃይማኖት፣ በገጠር፣ በነተማ፣ በሀብታም፣ በደሃ፣ ወዘተ... መካከል ልዩነት ሳያደርግ መስጠት አለበት። በሌላ በኩል የትምህርት አሰጣጡ ጥራት ያለው ሆኖ የሚማረው ግለሰብ ብቁ ዕውቀትና መያ ኖሮት ለራሱም ሆነ ለአገር ልማትም ተገቢውን አስተዋፅኦ እንዲያደርግ የሚያስችለው ጥራት ያለው ትምህርት እንዲሆን ይጠበቃል። አለበለዚያ ግን ትምህርቱ ትርጉም አይኖረውም፤ ለትምህርቱ የሚወጣውም ወጪ መና እንደቀረ ይቆጠራል። እንግዲህ ኋላ የቀሩ አገሮች ትምህርት ችግሩ እዚህ ላይ ነው። የትምህርቱን ተሳትፎ ለመጨመር ትኩረታቸውን ተሳትፎ ላይ ሲያደርጉ የትምህርቱ ጥራት ይጐዳል። በሌላ በኩል ደግሞ ትኩረታቸውን የትምህርት ጥራት ላይ ሲያደርጉ የትምህርቱ ተሳትፎው ይቀንሳል። ይህ የሚሆነው የትምህርት ተሳትፎው እና የትምህርት ጥራቱ በእኩል ደረጃ በአንድ ጊዜ እንዲያካሂዱ ገንዘቡና የተማረ የሰው ኃይል፣ እንዲሁም አስፈላጊው ቁሳቁስ በደህንታቸው የተነሳ እንደማይፈለገው ስለሌላቸው ነው።

ስለሆነም አንዳንድ አገሮች በትምህርት ጥራቱ ላይ ከማተኮር ይልቅ በትምህርት ተሳትፎ ላይ ማተኮሩን ይመርጣሉ። ምናልባትም ከፖለቲካውም ሆነ ከይስመላ አንፃር ሲታይ የትምህርቱን ተሳትፎ መጨመር ለጊዜው የሚያዋጣ ይመስላል። ምክንያቱም የትምህርት

ተሳትፎ መጨመር በቁጥር ስለሆነ የሚገለፀው፣ በተለይ ብዛቱ ከጨመረ፣ ሰሚውን ሊያግባባና ሊያስደስት ይችላል። ትምህርት ጥራት ግን በተለይ የሚገለጠውም ሆነ የሚያጋልጠውም ገና ወደፊት በሥራ ዓለም ተማሪው ሲሰማራ በመሆኑ ለጊዜውም ቢሆን ሳይታወቅ ተሸፋፍኖ ሊቆይ ስለሚችል ሳይሆን አይቀርም።

ቀደም ብሎ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው ተግባራዊነት ከትምህርት ተሳትፎ አንፃር እንደታየው ሁሉ ከትምህርት ጥራት አንፃር ሲታይ ደግሞ ምን ይመስላል የሚለውን ማየት ተገቢ ይሆናል። የትምህርት ጥራት ከሚመዘንባቸው መስፈርቶች በመጀመሪያ ደረጃ አንዱ በየትምህርት ደረጃው ያሉ መምህራን ያላቸው የዕውቀትና የሙያ ብቃት ነው። በዚህ መሠረት ትምህርት ሚኒስቴር በአንደኛ ደረጃ በመጀመሪያው ሳይክል /1-4/ የሚያስተምሩ መምህራን ቢያንስ በሰርቲፊኬት ደረጃ የሰለጠኑ እንዲሆኑ የሚጠበቅ ሲሆን በ2003 በወጣው የመንግሥት መረጃ[27] 97 በመቶ ይህን እንዳሟሉ ይገልጻል። በሁለተኛው ሳይክል /5-8/ የሚያስተምሩ ደግሞ ቢያንስ በዲኘሎማ የሰለጠኑ መሆን ሲጠበቅባቸው እንደ 2003 ዘገባ 31 በመቶ ብቻ እንደሚያሟሉ አመልክቷል። እንዲሁም ሁለተኛ ደረጃ /9-12/ የሚያስተምሩት ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ሲጠበቅባቸው 39 በመቶ ብቻ የተባለውን እንደሚያሟሉ ጠቁሟል። ሌላው የትምህርት ጥራት መስፈርት የመምህር እና የተማሪ ጥምረት የሚባለው ሲሆን በዚህም በኩል እንደ ትምህርት ሚኒስቴር መመሪያ በአንደኛ ደረጃ ከሃምሳ ተማሪዎች መብለጥ የለበትም ሲል እንደ 2003 መረጃ ግን የመምህር ተማሪ ጥምረት በአማካይ 64 ደርሶ ነበር። ይኸው ጥምረት በሁለተኛ ደረጃ እንደ ትምህርት ሚኒስቴር መመሪያ አርባ መሆን ሲገባው በአማካይ 45 እንደደረሰ ተመልክቷል።

በተጨማሪ የትምህርት ጥራት መስፈርትን የሚመለከት የመማሪያ መጽሐፍ ጉዳይ አንዱ ነው። በዚህም በኩል እንደ ትምህርት ሚኒስቴር መመሪያ በአንደኛ ደረጃ አንድ የመማሪያ መጽሐፍ ለአንድ ተማሪ ይላል። ነገር ግን እንደ 2003 ዘገባ አንድ መጽሐፍ ለ2.5 ተማሪዎች ነበር የሚደርሰው። በሁለተኛ ደረጃ እንደ አንደኛ ደረጃው አንድ መጽሐፍ ለአንድ ተማሪ የሚል ቢሆንም እንደ 2003 ሪፖርት አንድ መጽሐፍ ለ1.5 ተማሪ ነበር የሚደርሰው።

6.3. ከፍተኛ ትምህርት

ከትምህርት ጥራት ጋር በተያያዘ የከፍተኛ ትምህርትንም ሁኔታ መቃኘት ተገቢ ሳይሆን አይቀርም። በአሁን ጊዜ የተማሪዎች የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ ቀደም ብሎ ከነበረው እያደገ እየመጣ ነው። በ2003 ከመንግሥት የተገኘ መረጃ እንደሚያመለክተው በ1992 የከፍተኛ ተማሪዎች ጠቅላላ ቁጥር 15,000 ብቻ የነበረው በአሁን ወቅት ከ130,000 በላይ እንደሆነና ከዚህም ውስጥ ሀያ በመቶ ሴቶች እንደሆኑ ነው። ይህም ሆኖ ግን ከሰሐራ በታች ካሉ አፍሪቃውያን አገሮች የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ ጋር ሲነፃፀር የእነሱ በአማካይ ሶስት በመቶ ሲሆን የኢትዮጵያ ግን 1.5 በመቶ[28] ነበር። በርግጥም የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ እንደዚህ በጣም ማነሱ አሳሳቢ ነው። ስለሆነም የከፍተኛ ትምህርትን ተሳትፎ በመጠኑም ቢሆን ከፍ ለማድረግ ስድስት ዩኒቨርሲቲዎች መጨመራቸውና በቅርብ ጊዜም ሌሎች አሥራ ሶስት ዩኒቨርሲቲዎችእንደሚከፍቱ መታቀዱ ተስፋ ሰጪ ነው። ይህ ሁሉ እርምጃ ይበል የሚያሰኝ ነው።

ይሁን እንጂ የአገር ልማት ውጤታማ እንዲሆን የተማሩውና የሰለጠነው የሰው ኃይል በብዛት ብቻ ሳይሆን በዕውቀቱና በሙያው ብቃት ያለው እንዲሆን ያስፈልጋል። ብቃቱ

እንዲኖረው ትምህርቱ በጥራት መሰጠት አለበት። ለዚህም ከሁሉ በፊት ቢያንስ ለትምህርት ጥራት አስፈላጊ የሆኑ መሠረታዊ ግብአቶች መሟላት ያስፈልጋቸዋል። አለበለዚያ የከፍተኛ ትምህርት ተመራቂው በሥራው ዓለም በዕውቀቱም ሆነ በሙያው ብቃት እንደሌለው ሲታወቅ ምን ይደረጋል? በምዕራቡ ዓለም አንድ መኪና ከተሸጠ በኋላ እንከን ሲገኝበት ወደ ፋብሪካው ይመለስ እንደሚባለው ምሩቁም ወደ ዩኒቨርሲቲ ይመለስ ሊባል ነው?

ቀደም ብሎ ስለአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ የትምህርት ጥራት ሲነሳ መሠረታዊ የሆኑ የትምህርት ጥራት መስፈርቶች በዋነኝነት ከተጠቀሱት አንዱ የመምህራን በሚፈለገው መጠንና ጥራት የመኖራቸው ጥያቄ ነው። በዚሁ ረገድ ምንም እንኳ ተጨባጭ መረጃ ለማቅረብ ባይቻልም፣ በአሁኑ ወቅት ከሚታየው የከፍተኛ ትምህርት የተማሪ ብዛት አንፃር ሲታይ የመምህራን እጥረት እንዳለ ለመገመት ይቻላል። እንደ አንድ መንግሥት መረጃ[29] መሠረት በ2003 የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ኢትዮጵያውን መምህራን 3097 ሲሆኑ ከእነዚህም 176 ማለት 5.7 በመቶ ሴቶች ነበሩ። የውጭ አገር መምህራን ደግሞ 397 ሲሆኑ በጠቅላላው የከፍተኛ ትምህርት መምህራን 3944 እንደነበሩ ያመለክታል። በአሁኑ ጊዜ የከፍተኛ ትምህርት መምህራን እጥረት የተከሰተው ኢትዮጵያውያን የሆኑ መምህራን በመጠንም ሆነ በጥራት እንደሚፈለገው ለማግኘት አለመቻሉ ነው። እንደሚታወቀው ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ለማስተማር ቢያንስ ሁለተኛ ዲግሪ ያስፈልጋል። ሌላውና ትልቁ ችግር በአጠቃላይ አነጋገር የመምህርነት መያ ከሌሎች መያዎች ጋር ሲነፃፀር የሚያስገኘው ጥቅም፣ በተለይ በደሞዝ፣ ግለሰቦችን እንደሚፈለገው ወደ መያው አይስብም። በዚህም የተነሳ ይመስላል፤ በመያው ተሰማርተው የነበሩት በብዛትም ባይሆን በመጠኑ የተሻለ ደሞዝና ጥቅማጥቅም ፍለጋ ወደ ሌሎች ድርጅቶች ሲለዩ ይስተዋላል። ለምሳሌ፤ ይህን በሚመለከት አንድ ጥናት[30] በ2000 ዓመት የተደረገ እንዳመለከተው በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከ1993 እስከ 2000 ባለው የስድስት ዓመት ጊዜ ከመቶ በላይ የሚሆኑ የዩኒቨርሲቲው አንጋፋ መምህራን እንደለቀቁ ይገልጻል። ከእነዚህም መካከል ብዙዎቹ የለቀቁት ከሕክምና፤ ከሳይንስ፤ ከቴክኖሎጂ፤ ከቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ፋኩልቲዎች መሆናቸውም ተመልክቷል።

ከዚህም በላይ ለከፍተኛ ትምህርት መምህራን እጥረት ዋና መሠረታዊ ችግር የሆነው፣ ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው፣ በአብዮት ዘመን መከሰት የጀመረው የምሁራን ፍልሰት ነው። እስካሁንም እየቀጠለ ያለ በመሆኑ ለከፍተኛ ትምህርት ወደ ውጭ ከሚላኩት መምህራን መካከል ትምህርታቸውን አጠናቀው የሚመለሱት እስከዚህም አይደለም። በተጨማሪም በ1993 ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተባበሩት አርባ መምህራን በዩኒቨርሲቲው ላይ የመምህራን እጥረት እንደፈጠረ የሚታወስ ነው። ዛሬ ለመምህራን እጥረት እንደ መፍትሔ ተብሎ የተያዘው የውጭ አገር መምህራንን ከፍተኛ ደሞዝ እየከፈለ ማምጣት ነው። ይህም ሆኖ በተፈለገው ብዛትና ጥራት ለማግኘት የተቻለ አይመስልም። ከዚህም አልፎ እስከመቼ ድረስ ነው የውጭ አገር መምህራን ላይ መተማመን የሚቻለው? በአነሱም በሊማም የአገሩ ሰው እንዳይሸሽ የሚቻለውን ያህል ማድረግ ከላቲያ ያለው መፍትሔ ሳይሆን አይቀርም። አለበለዚያ ስንት ነገር ከውጭ ይመጣል? ደላሩ፤ የዕርዳታው አህል ወዘተ...?።

ምርምርና ጥናትን በተመለከተ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም አንዱና ዋነኛው ተልኮ ከመማር ማስተማሩ ሒደት ገን ለገን ጥናትና ምርምር ማካሔዱ ነው። ምክንያቱም ሁለቱም በጣም ትስስር ስላላቸው በተለይም የመማር ማስተማሩ ሒደት የሚበለጽገውና ውጤታማም የሚሆነው በጥናትና ምርምር ሲታገዝ ነው። አለበለዚያ ግን የመማር ማስተማር ሒደት ይመክናል። ከዚህም በላይ ጥናትና ምርምር በአገር ልማት ላይ ለከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን

በመፍታትና እንዲሁም አዳዲስ ግኝቶች ለልማቱ በማበርከት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ይጠበቅበታል። ስለሆነም የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ጥናትና ምርምር እንዲጎለብት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል። ሆኖም ጥናትና ምርምር እንዲሁ በምኞት የሚካሔድ ስላልሆነ ቢያንስ፣ ቢያንስ፣ ጥናትና ምርምር ለማካሔድ የሚያስፈልጉ መሠረታዊ የሆኑ ግብአቶች፣ እንደ ተማራማሪዎች፤ ገንዘብ፤ የተለያዩ ቁሳቁሶችና ከሁሉም በላይ ደግሞ የተቋሟቱ አካባቢ የሃሳብና የመጻፍ እንዲሁም የጥናትና ምርምር ግኝቶችን የማሰራጨት ነፃነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል። በአሁኑ ሰዓት እነዚህ የተጠቀሱት ግብአቶች በመጠንም ቢሆን በየተቋማቱ ለመኖራቸው ማስረጃ ለማቅረብ ያስቸግራል። ምናልባት ለማለት የሚቻለው በአንዳንድ ተቋማት ምርምርና ጥናት ለማድረግ ጥረት ቢኖርም የተደረገ ጥቂት ጥናቶች ለአገር ልማት ያደረጉት አስተዋፅኦ በተጨባጭ ይህ ነው ለማለት የሚያስችል አይመስልም። ሌላው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚካሔዱ አንዳንድ ምርምርና ጥናቶች የሚደረጉት በአገሪቱ አንገብጋቢ በሆኑ ችግሮች ላይ ሳይሆን፣ ገንዘብ ይዘው ለሚመጡ የውጭ ድርጅቶች፣ ባላቸው አጀንዳ ስለሚመስል ለወደፊቱ ሊታሰብበት የሚገባ ጉዳይ ሳይሆን አይቀርም። በአጠቃላይ ጥናትና ምርምር በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በአገሪቱ ልማት ቁልፍ ሚና እንዲጫወት መደረግ ይኖርበታል።

6.4. የሙያና ቴክኒክ ትምህርት

የሙያና ቴክኒክ ትምህርት ቀደም ብሎ በነበረው የትምህርት ሥርዓት ብዙም ትኩረት ሳይሰጠው እንደቆየ ይታወሳል። ምናልባትም ሕብተረሰቡ ስለሙያና ቴክኒክ ትምህርት የነበረው አስተሳሰብ ዝቅተኛ ስለነበርና በተጨማሪም በመንግሥት በኩል የቀለም ትምህርት ከሚያስወጣው ወጪ ጋር ሲነፃፀር በጣም ከፍተኛ በመሆኑም ይሆናል። ለማንኛውም እስከ 1995 ድረስ የሙያና ቴክኒክ ተቋማት ቁጥር በአገሪቱ በአጠቃላይ ሃያ እንኳን አልደረሱም ነበር።

ነገር ግን ከአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ወዲህ የሙያና ቴክኒክ ትምህርት ለየት ያለ ትኩረት በማግኘቱ የተቋማቱ ቁጥር በ2004 ወደ 159 ሲደርስ የተማሪውም አጠቃላይ ቁጥር ወደ 87,000 ከማደጉም በላይ ከዚህ ውስጥ 47 በመቶ ሴቶች እንደሆኑ ተመልክቷል[31]። ይህ ከቁጥር መጨመር አንፃር ሲታይ በተማሪዎች ዘንድ ስለሙያና ቴክኒክ ትምህርት ጤና አመለካከት እየተፈጠረ ያለ ይመስላል። በሌላ በኩል ግን ሌላ የተሻለ አማራጭ በማጣታቸው ይሁን አይሁን በጥናት የተደገፈ መረጃ ለጊዜው ባለመኖሩ በቁጥር የመበዛታቸው ጉዳይ በውል ማወቅ አስቸጋሪ ነው።

ከዚህ ጋር ተያይዞ መነሳት ያለበት ከላይ እንደተጠቀሰው የሙያና ቴክኒክ ትምህርት ሥልጠና ከፍ ያለ ወጪ ስለሚያስከትል በተለይም የተማረው ቁጥር እየጨመረ ሲሔድ ወጪውም ስለሚንር የሚሰጠው የሥልጠና ጥራት ሊቀንስ ስለሚችል ሥልጠናው የለብ ለብ እንዳይሆን ያሰጋል። ከሁሉም በላይ ግን የሙያና ቴክኒክ ትምህርት ሥልጠናውን በተመለከተ የሚነሳው ወሳኝ ጥያቄ ተማሪዎቹ ሰልጥነው ሲወጡ በሙያቸው ሥራ ተቀጥረው ወይም በራሳቸው ሥራ ፈጥረው ራሳቸውን ችለው ከዚያም አልፈው ለአገር ልማት አስተዋፅኦ ሊያደርጉ ይችላሉ ወይ የሚለው ነው? ለዚህ መልስ ወሳኙ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ስለሚሆንና ይህም በቅርበ አስተማማኝ ዕድገት ያመጣል ለማለት ሰለማይቻል ዞሮ ዞሮ የተማረ ሥራፈት ወይም ስሙን ለማሻሻል ያህል የተማረ ባለሙያ ሥራፈት እንዳይፈጠር ያስፈራል።

6.5. የትምህርት አመራርና አስተዳደር

ቀደም ብሎ በነበረው መንግሥት በትምህርት ላይ ከተሰነዘሩት ትችቶች አንዱ የትምህርት አመራርና አስተዳደር በጣም የተማከለ ከመሆኑ የተነሳ ማንኛውም ጥቃቅን ወሳኔ ሁሉ የሚመሰነው በዋናው መሥሪያ ቤት ባለሥልጣናት ስለነበር አመራሩና አስተዳደሩ በቢሮክራሲ የተተበተበና ብቃትና ቅልጥፍና የጐደለው የሚል ነበር። ከዚህም በተጨማሪ የአካባቢውን ሁኔታ ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባ ነበር የሚባለው።

ስለሆነም በአዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ለእነዚህና ለመሳሰሉት መፍትሔ ያመጣል በማለት የትምህርት አመራርና አስተዳደር ያልተማከለ እንዲሆን ተደረገ። ሆኖም ይህ ዓይነቱ አመራርና አስተዳደር የታቀደውን ውጤት እንዲያመጣ ከሁሉ አስቀድሞ በተለይ በትምህርትና አስተዳደር በቂና የሰለጠነ የሰው ኃይል ያስፈልጋል። በወቅቱ በዚህ በኩል ያለው የማፈለገውን ያህል እንደማይኖር እየታወቀ ነበር ፖሊሲው ተግባራዊ እንዲሆን የተደረገው። በሌላ በኩል የሁለተኛ ደረጃ ርዕሰ መምህራን ቀደም ብሎ በአብዛኛው የማመደቡት በዩንስ በትምህርት አመራርና አስተዳደር ሙያ የመጀመሪያ ዲግሪ የነበራቸው ነበሩ። ነገር ግን አዲሱ ፖሊሲ ተግባራዊ ከሆነ በኋላ በመምህራን መመረጥ አለባቸው በሚል አስተሳሰብ የትምህርት አመራርና አስተዳደር ሙያቸው ያልሆኑ በቦታው እንዲቀመጡ ተደረገ። እዚህ ላይ የማገርመው ግን ለብዙ ዓመታት በተለይ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በዚህ ሙያ በመጀመሪያና በሁለተኛ ዲግሪ የሰለጠኑና የሚሰለጥኑም መኖራቸው ነው። ይሁን እንጂ በለሙያዎች እያለ ለሌሎች አለሙያቸው ገብተው ለምን በምርጫ ሰበብ እንዲመደቡ እንደተደረገና የትምህርቱም አመራርና አስተዳደር በብቃትና ቅልጥፍና እንዴት እንደሚካሔድ አበይያቲ ነው።

6.6. የማስተማሪያ ቋንቋ

አማርኛ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የማስተማሪያ ቋንቋ ሆኖ ከ1963 ጀምሮ አዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ተግባራዊ እስከሆነበት ድረስ እንደቆየ ይታወሳል። ከዚያ ወዲህ ግን የአንደኛ ደረጃ ትምህርት በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንዲሰጥ ተደረገ። በመሠረቱ የአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማሪያና የመማሪያ ቋንቋ መሆኑ ከሬዳጎጂ አንፃር ሲታይ እምብዛም የማያጠያይቅ አይሆንም። ነገር ግን ቀደም ብሎ እንደተገለፀው አዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ሲቀረፅ ጎበረተሰበ በማገባ ስላልተሳተፈበት ችግር ነበረው። ስለሆነም የአፍ መፍቻ ቋንቋ የማስተማሪያ ቋንቋ ሲሆን ችግሮች መከሰታቸው አልቀረም።

መጀመሪያው የጎበረተሰበን በጎ ፈቃድ ቢያገኝ ኖሮ ለማከሰቱት ችግሮች ከሕገ-በ ትብብርና እንዲሁም ለአንዳንዶችም ችግሮች የመፍትሔ ሃሳቦች ለማግኘት ይቻል ነበር። ከዚህም በተጨማሪ የአፍመፍቻ ቋንቋ የማስተማሪያ ቋንቋ ሲሆን አዲስ እንደመሆኑ መጠን ተገቢው ፍተሻ ሳይከናወንበትና አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶች ሳይደረጉ በጥድፊያ ተግባራዊ በመደረጉ ችግሮች ተከስተዋል። ከችግሮቹም መካከል ለመጥቀስ ያህል፤

ሀ. በየአፍ መፍቻ ቋንቋ ችሎታ ያላቸው በቅድሚያ በማፈለገው መጠንና ጥራት የሰለጠኑ መምህራን አለመዘጋጀታቸው

ለ. እንዲሁም በየአፍ መፍቻ ቋንቋ በማፈለገው መጠንና ጥራት የመማሪያና ማስተማሪያ መጻሕፍት አለመዘጋጀታቸው፤

ሐ. አንድ የአንደኛ ደረጃ ተማሪ በሚኖርበት አከባቢ የእርሱ/ የእርሷ አፍ መፍቻ ቋንቋ ባልሆነ እንዲማር ወይም እንድትማር ጫና እንዳይደረግ በቅድሚያ ታወቆ ዝግጅት አለመኖሩ፤

መ. በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪዎች በአንደኛ ደረጃ በአፍ መፍቻ ቋንቋ እንጂ በተጨማሪ አማርኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎች እንዲማሩ ይደረግ ሁለተኛ ደረጃ ሲገቡ የማስተማሪያ ቋንቋው እንግሊዝኛ ይሆናል[32]። እንደገና መቀያየር በተማሪዎች ላይ የሚፈጥረው ስነልቦናዊ ችግር የተጠና አይመስልም። ምናልባትም ተማሪዎቹ ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በስተቀር አንዱንም በሚገባ ሳይዙት ተወናብደው እንዳይቀሩ የሚያሰጋ ሁኔታ የተፈጠረ ይመስላልና ሊጠናና ሊታሰብበት የሚገባ ነው።

6.7. ማጠቃለያ

አዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ የትምህርት ሥርዓቱ በአዲስ መልክ ያከናወናቸውንና በቀጣይነት የሚያከናውናቸውን ለመዳሰስ ጥረት ተደርጓል። አሁን ደግሞ እነዚያን እንደሚከተለው ለማጠቃለል ተሞክሯል።

1. የአንደኛ ደረጃና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ተሳትፎ ቀደም ብሎ ከነበረው በከፍተኛ ደረጃ ያደገ ቢሆንም የትምህርቱ ጥራት ግን አጠያያቂ መሆኑ ተመልክቷል።
2. የመዋያና የቴክኒክ ትምህርትም ፊት ከነበረው በጣም አነስተኛ ቁጥር ከፍ ማለቱ የሚደገፍ ሲሆን ነገር ግን ሰልጥነው ሲወጡ ተቀጥረው ወይም የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው ራሳቸውንም ረድተው ለልማት የሚጠበቅባቸውን አሰተዋፅኦ ለማድረግ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ ያስችላቸው ይሆ? የሚል ጥያቄ አስነስቷል ::
3. የከፍተኛ ትምህርት ተሳትፎ ከፍ ማለቱ መልካም ገፅታ ሲሆን በተለይ የመምህራን እጥረት በጥራትም ሆነ በመጠን የተፈለገውን ያህል አለመገኙቱ የትምህርቱን ጥራት
4. የትምህርቱአመራርና አሰተዳደርም የሰለጠኑ ባለሙያዎች በትምህርት አመራርና አሰተዳደር በሚፈለገው ጥራትና መጠን አለመኖራቸውና ጥቂትም ቢኖሩ በሙያቸው አለመመደባቸው የትምህርቱን አመራርና አሰተዳደር ብቁነትና ቀልጠፋነት አጠራጣሪ አደርጎታል።

በዚህ አጋጣሚ እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጉዳይ በ2015 «ትምህርት ለሁሉም» የተባለውን ግብ ለመምታት የአንደኛ ደረጃን የትምህርት ተሳትፎ ለመጨመር በአሁኑ ወቅት እየተደረገ ያለው ርብርቦሽ ነው። በመሠረቱ የሚደረገው ጥድፊያና ርብርቦሽ የሚደገፍ ቢሆንም የትምህርቱ ትኩረት ሁሉ ቁጥሩን የመጨመር ላይ እንጂ ትምህርቱ በጥራት እመስጠቱ ላይ አይመስልም። ስለዚህም ለወደፊቱ የሚያስጋው ዋና ጉዳይ በ2015 የታቀደው ግብ መድረሱ አለመድረሱ ሳይሆን ትምህርቱ በጥራት ባለመስጠቱ ለወደፊቱ በተማሪዎች የትምህርት ችሎታ ላይ ጥሎት የሚያልፈው የትምህርት የችሎታ መነስ ችግር ነው። ስለሆነም ችግሩን በቀላሉ ወደፊት ለመፍታት ሰለማይቻል ከአሁኑ ትኩረት ተሰጥቶት መታሰብ ያለበት ጉዳይ ነው።

አሁንስ ያለው ሁኔታ ቢቀጥል?

7. የአገሪቱ የትምህርት ሥርዓት እስካሁን እንደነበረው ቢቀጥል የሚለው ጥያቄ ከተነሳ ማለትም በሌላ አነጋገር በትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲው ላይ የሕዝብ ተሳትፎ ሳይታከልበትና የሕዝብን ትግርና ፍላጐት ሳያንፀባርቅ መቀጠሉ ስለሚሆን ትምህርትና ልማት ሳይጣጣሙ ቀደም ብሎ እንደነበረው ይካሔዳሉ ማለት ነው። በዚህ ሁኔታ የትምህርቱ ሂደት ወደፊት መን ሊመስል እንደሚችል የአሁኑን ሂደት ግምት ውስጥ በማስገባት አንዳንድ ተጨባጭ ሁኔታዎችን ለማንሳት ይቻላል። ለምሳሌ፤ የአንደኛ ደረጃን ትምህርት ተሳትፎ በተመለከተ በተለይ በ2015 «ትምህርት ለሁሉም» የተባለውን ግብ ለመምታት በአሁኑ ጊዜ የተጀመረው የአንደኛ ደረጃ ትምህርት የማስፋፋት ሂደት ቢያንስ ቢያንስ እስከ 2015 በቀጣይነት እንደሚካሔድ ይጠበቃል። በዚህም የተነሳ የትምህርቱ ትኩረት የተሳትፎውን ቁጥር መጨመሩ ላይ ስለሚሆን የትምህርቱ ጥራት ግን እንደሚያሽቆለቁል ለመገመት አያዳግትም። ስለዚህ ይህ የትምህርት ጥራት መውደቅ ለወደፊቱ በተማሪዎች የትምህርት ችሎታ ላይ ሊያስከትል የሚችለው አደጋ በቀላሉ መፍትሔ የማይገኝለት ቸግር በትምህርቱ ሥርዓት ላይ ጥሎ ያልፋል።

እንዲሁም የሙያና ቴክኒክ ትምህርት ተሳትፎ እየጨመረ ይሔዳል። ነገር ግን የሙያና የቴክኒክ ትምህርት ከቀለም ትምህርት የበለጠ የገንዘብና የቁሳቁስ ወጪ ስለሚጠይቅ የትምህርቱ ጥራት አጠያያቂ ሊሆን ይችላል። ከዚህም በላይ ግን ስልጠናውን የሚወጡት ተቀጥረውም ሆነ የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው ራሳቸውንም ችለው ለልማትም ተገቢውን አስተዋፅኦ እንዳያበረክቱ የአገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታ ዕድል ሊፈጥርላቸው ይችላል ወይ? የሚለው ጥያቄ ወሳኝ ነው። ስለዚህ የሚያስጋው የተማረ ሙያተኛ ሥራፈት ችግር እንዳይባባስ ነው።

ቢተጨማሪ የከፍተኛ ትምህርትን በተመለከተ ተሳትፎውን የመጨመር ጥረቱ እየቀጠለ እንደሚሔድ ነው። በዚያው መጠን ግን አሁን የሚታየው የከፍተኛ ደረጃ መምህራን እጥረት እየተባባሰ እንደሚሔድና የትምህርቱም ጥራት አስጊ መሆን ብቻ ሳይሆን በተለይ በሥራው ዓለም ተመራቂዎቹ በሚሰማሩበት ወቅት ችሎታቸው አሰተማማኝ ሆኖ ባይገኝ ለልማትም የሚያደረጉት አስተዋፅኦ የሚያጠያይቅ ሊሆን ይችላል። በአጠቃላይ የትምህርቱ ሒደት ከቁጥር አንፃር ሊጋሽብ ይችላል። ሆኖም የፍሬው ጉዳይ አጠራጣሪ ይሆናል። እንደሚታወቀው የትምህርት ወሳኝነት ቁጥሩ ብቻ ሳይሆን በተለይ ትርጉም ያለው የአገር ልማት ለማምጣት ወሳኙ ጥራት እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል።

8. ርዕይ

ስለ አገር እድገት ርዕይ ሲነሳ አንድ የሰማሁት ቀልድ ትዝ ይለኛል። በሰማንያዎቹ ዓመታት አካባቢ ነው ይባላል። የሁለቱ ሀያላን መንግሥታት መሪዎች ኢየሱስ ዘንድ ቀርበው ኢየሱስ ሆይ ምን ይህል ጊዜ ይቀራቸዋል አገሮቻችን የዕድገት ጫፍ ላይ ለመድረስ ይሉታል? ኢየሱስም አሜሪካ ሀያ አምስት ዓመት ሩሲያ ደግሞ ሃምሳ ዓመት ይላቸዋል። የእኛም አገር መሪ ከማን አንሼ ነውና የእኔስ አገር ይለዋል? ኢየሱስም በመገረም ስለአንተ አገር እንኳን እኔ የሰማይ አባቴም የሚያውቅ አይመስለኝም አለው ይባላል። እንግዲህ ይታያችሁ እኔ ምን ልበል? ይህን ያነሳሁት ምን ያህል ትንበያ አዳጋች እንደሆነ ለማሳየት ነው። በአጠቃላይ ግን እኔ እንደሚመስለኝ እንኳን ስለአገር ይቅርና በግለሰብ ደረጃ እንኳን ብዙዎቻችን ስለራሳችን

የወደፊት ሁኔታ ከመጠየቅ ይልቅ ስለአለፈው ሕይወታችን ብንጠየቅ የሚቀለንና የምንደሰት ይመስለኛል። ምናልባት የጥንታዊት አገር ሰዎች በመሆናችን ይሆን? ለማንኛውም ቅገርት ተፈርቶ ሳይተኛ እይታደርምና ሕልምም ሆነ ቅገርት የምለውን ልበልና ለእናንተ ልተወው።

በመጀመሪያ ደረጃ ታሳቢ አድርጌ የተነሳሁት ወደፊት የአገራቱ የትምህርት መሠረታዊ ዓላማ እንዳለፉት ዘመናት የመጣውን መንግሥት ሥልጣን ላይ ማቆያ መሣሪያ ሆኖ የሚያገለግል ሳይሆን ትኩረቱ በአገር ልማት ላይ የሚሆንና የትምህርቱም ፖሊሲ ሲቀረፅ እንዳለፈው ጊዜ እኔ ነኝ ለአንተ የሚበጀውን የማውቅልህ በሚል አሰተሳሰብ ሳይሆን በሕዝብ ተሳትፎ እንደሚሆን ነው። በዚህም የተነሳ መንግሥት በተለዋወጠ ቁጥር ሲቀያየር የነበረው የትምህርት ፖሊሲ ከእንግዲህ ወዲህ አስፈላጊ ሆኖም ሲገኝ የሚቀየረው በሕዝብ ጥያቄ ብቻ እንደሚሆን በመገንዘብ ነው። በዚህ መሠረት አሰከ ሀያ ሀያ የሚከተሉት ሊሆኑ ይችላሉ ብዬ አገምታለሁ።

1. በየደረጃው የሚኖረው የትምህርት ተሳትፎ አገራቱ በምታወጣው የልማት ዕቅድ እንጂ ለይስሙላ ተበለው ተሳትፎው በቁጥር ብቻ እንዲያድግ አይደረግም። በመሆኑም የትምህርት ተሳትፎና የትምህርት ጥራት በተመጣጣኝ ሁኔታ ሰለሚሰጠው የአገር ልማት እንዲመጣ ያደርጋሉ።
2. የትምህርት ተሳትፎና ጥራት ተመጣጥነው ሰለሚካሔዱ የአገር ልማትም ሰለሚከተል የተማረ ሥራፈትም እየጨመረ በመሔድ ፈንታ ቀስ በቀስ ይቀንሳል።
3. ዘመናዊ ትምህርት አገራቱ ከገባበት ጊዜ ጀምሮ እሰከዛሬ ድረስ ለአምሰት የውጭ ተዕኖዎች ተጋልጧል። ለመጥቀስም ያህል መጀመሪያ ለፈረንሳይ፣ ከዚያም በመቀጠል ለእንግሊዝ፣ ለሶስተኛ ጊዜ ለአሜሪካን፣ ከዚያም ለሩሲያ፣ በአሁኑ ወቅት ደግሞ በተጥያም ባይሆን ለአሜሪካ፣ በዓለም ባንክ አማካይነት። ሰለሆነም የኢትዮጵያ ትምህርት ኢትዮጵያዊ መሆን ነው እንጂ የተሳነው በተረፈ ግን ሊሆን ያልሞከረው የለም። ስለዘህም ይህ የውጭ ተዕዕኖ አብቅቶለት ትምህርት የሕዝቡን ባሕልና ፍላጎት ያንፀባርቃል።
4. የሀለተኛና የክፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች በገዛ ፈቃዳቸው ተነሳስተውና ተደራጅተው በሚማሩበትና በሚሰለጥነበት የተለያዩ መደያዎች ለአገር ልማት ቀጣይነት ያለው አገልግለት ለማበርከት ይሠማራሉ።
5. የኢትዮጵያ መምህራን የጋራ ዓላማ ኖሯቸው ለአገራቱ ልማት ከፍተኛ አሰተዋፅኦ ለማድረግና የመምህርነትም መደያ እንዲዳበርና እንዲከበር በአንድነት አንድ ብሔራዊ የመምህራን ማኅበር በነፃ አቋቁመው ይንቀሳቀሳሉ።
6. እሰከዛሬ ድረስ እንደባላንጣ ይተያዩ የነበሩት የአገራቱ ምሁራንና መንግሥት እስካሁን የነበራቸውን አለመተማመን ለአገር ልማት ሲሉ አቻችለው አገራቱን ካለችበት የድህነት አዘቅት ለማውጣት ይጣጣራሉ።
7. ከአገር ተሰደው የነበሩት የአገራቱ ምሁራን ወደ አገራቸው እንኳን ባይመለሱ ባለበት ሆነው አገራቸውን የሚረዱበት ድርጅት በማቋቋም ለአገር ልማት የሚችሉትን አሰተዋፅኦ ያደርጋሉ። እንዲሁም ወደፊት በአገር ልማት ለመሳተፍ ፈቃደኝነት ሰለሚኖር የምሁራን ፍልሰት ጋብ ይላል።
8. በዘመነ ግሎባላይዜሽን ዕውቀት ከምንጊዜውም የበለጠ ከፍተኛ ዋጋ የሚያወጣ ሀብት እየሆነ እየመጣ ሰለሆነ የአገራችን አንዳንድ ባለሀብቶች ትርፍ ከማግኘት ባሻገር ትምህርት በጥራት የሚሰጥባቸው ጥቂት የግል ኮሌጆች፤ ወይም ዩኒቨርስቲዎች እንደሚከፍቱና

እነዚህም ተቋማት በሀያ ሀያ ስመ ጥር ተቋማት በመሆን ለአገር ልማት አስተዋፅኦና ለባለቤቶቻውም ቋሚ መጠሪያ ይሆናሉ::

እንግዲህ ሁሉንም እንኳን ባይሆን ጥቂቶችን እንደ አፍህ ያድርግልህ በሉኝና ጽሑፍን ወደ ማብቃቱ ልሂድ:: ከዚያ በፊት ግን አንድ ስመን በማላውቀው ገጣሚ የተቋጠረች ስንኝ አጠቅሳለሁ:: እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ ተማሪ በተለይ ቀደም ባለው ዘመን በመማሩ የተነሳ ይመስላል ሕሊናው እያስጨነቀው ለውጥ ያስፈልጋል እያለ ይጮህ እንደነበር ይታወሳል:: ሆኖም ጩኸቱ የምድረበዳ ጩኸት ሆኖበት ጆሮ ዳባ ልበስ ተብሎ ነበር:: ይህች ስንኝ ያንን ሁኔታ የምታስታውስ ስለመሰለችኝ የዚህ ጽሑፍ መዝጊያ አድርጌያታለሁ::

ስንኟ እንዲህ ትነበባለች::

አለማችን ጩኸት ነው
አለማችን ጩኸት ነው
አራታችን ጩኸት ነው
የዩታችን ጩኸት ነው
ይህ ሁሉ ሲጮህ ዝም በል ይሉታል
ዝምታ ሲጮህ ግን እንዴት ያደርጉታል::

References

1972. "Education in Ethiopia during the Italian Fascist Occupation" **The Interantional Journal of African Studies**, Vol. 3, 367

ንጉሤ ሥዩም 1974 «የትምህርት ሁኔታ በኢትዮጵያ» የካቲት መጽሔት: ቁ.8

ኢህአዴግ ም/ቤት 1997 የኢህአዴግ ትምህርት ፖሊሲ አፈጻጸም ከ1987-1996 ዓ.ም ያልታተመ: አዲስ አበባ

ኢህአዴግ ም/ቤት 1997= የኢህአዴግ የትምህርት ፖሊሲ አፈጻጸም ከ1987-1996 ዓ.ም ያልታተመ አዲስ አበባ

ኢህአዴግ ም/ቤት 1997. የኢህአዴግ የትምህርት ፖሊሲ አፈጻጸም ከ1987-1996 ዓ.ም. ያልታተመ አዲስ አበባ

ጳውሎስ ኞኞ 1984. አጤ ምኒልክ: አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ቤት

Addis Ababa University 1984. Annual Report of the Academic Vice President, Unpublished, Addis Ababa

Ayalew Shibeshi 1989, "Some Trends in Regional Disparities in Primary School Participation in Ethiopia, " **The Ethiopian Journal of Education**, Vol. XI, No.1

Bahiru Zewde 1991. **A History of Modern Ethiopia** 1855-1974, London: James Currey Ltd. 103-104

Bjerkan.Ole-Christian 1972, Plans, Targets, and Trends in Ethiopian Education, Unpublished PhD Dissertation, University of Maryland

ትምህርት ሚኒስቴር 1986. በአጠቃላይ የትምህርት ሥልጠና ፖሊሲ ረቂቅ ላይ ከክልሎች የተሰበሰበ፤ ያልታተመ አዲስ አበባ

Korten, D. and F.Korten 1966. "Ethiopia's use of National Service", **Comparative Education Review**, 10:3

Ministry of Education 1952. Ministry of Education Yearbook for 1949-50, Unpublished, Addis Ababa

Ministry of Education 1972. Education: A Challenge to the Nation: A Report of the Education sector Review, Unpublished, Addis Ababa

Ministry of Education 1977, Basic Information on Education in Ethiopia, Unpublished, Addis Ababa

Ministry of Education 1986 Evaluative Research of General Education System in Ethiopia • Unpublished Addis Ababa

Ministry of Education 1994. **Education and Training Policy,** Addis Ababa: EMPDA

Ministry of Education 1994. **Education and Training Policy,** Addis Ababa, EMPDA.

Ministry of Education 2003 **Education and Statistics: Annual Abstract** 1995 EC.(2002-03) Addis Ababa

Ministry of Education 2003. **Education Statistics: Annual Abstract 1995 E.C. (2002-03)** Addis Ababa

Mulugeta Wodajo, 1959, "Postwar ReforminEthiopianEducation, **Comparative Education Review** 2:3, 24-30

National Literacy Campaign Coordinating Committee 1984. **Every Ethiopian will be Litrate and will Remain Literate,** Unpublished Addis Ababa

Pankhurst, Richard 1962. "The Foundation of Education, Printing, Newspapers, Book Production and Libraries and Literacy in Ethiopia," **Ethiopia Observer,** 6:3

Provisional Militaery Administrative Council 1977. Basic Information on Education in Ethiopia, Unpublished, Addis Ababa

መረሰኤ ኀዘን ወ.ቂርቆስ 1994. የዘመን ታሪክትዝታዬ በዳግማዊ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት አዲስ አበባ ዛመራ አሳታሚ ገጽ 29-30.

Seyoum Teferra 1992. "Brain Drain Among Academicians in Two Higher Education Institutions in Ethiopia", **The Ethiopian Journal of Education,** Vol. XIII, No.2

Seyoum Teferra 2000. "The causes and Magnitude of Brain Drain in Higher Education Institutions With a Particular Reference to AAU: "Go West Young Man, (Go)," **Bulletin of the Institute of Development Research,** Vol.1,No.3.

ማኅተመሥላሴ ወ.መስቀል 1950 ዝክረ ነገር አዲስ አበባ: ገጽ 600-601

Tekeste Negash 1990. **The Crisis of Ethiopian Education: Some Implications for Nation-Building,** Uppsala University, 3

Tekeste Negash 1990. **The Crisis of Ethiopian Education: Some Implications for Nation-Building,** Uppsala University

Teshome Yizengaw 2004. "The Status and Challenges of Ethiopian Higher Education System and Its contribution to Development", **The Ethiopian Journal of Higher Education,** Vol.1, No.1

Tilahun Sineshaw 1994 "A Critical Examination of the 1979-1991 Ethiopian National Literacy Campaign" in Harold Marcus (ed.) **The 12th International Confernance of Ethiopian Studies.**

ትምህርት እና ልማት በኢትዮጵያ ጽሁፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት

ዳርጌ ወሌ *

ከክፍሉ ሊሞገስ
ከክፍሉታ፣ ከዘሪሁን

አስቀድማ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር በዚህ ውይይት ላይ በአስተያየት ስለጋበዘኝ አመሰግናለሁ።

እንደምታውቁት አስተያየት እንድሰጥበት የተጠየቅሁት ፕሮፌሰር ሥዩም ተፈራ "ትምህርት እና ልማት በኢትዮጵያ" በተሰኘ ርዕስ ባዘጋጁት ጽሁፍ ላይ ነው። አስተያየቴንም እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

የጽሁፉ ርዕስና አቀራረብ

1.

የጽሁፉ ርዕስ ማለትም "ትምህርት እና ልማት በኢትዮጵያ" በጣም ሰፊ ከመሆኑ የተነሳ ለማንኛውም ባለሙያ ቢሆን በገዘርገዘርና በተሟላ መልክ ለማቅረብ እንደሚያስቸግር ሁላችንም የምንስማማበት ይመስለኛል። ዘመናዊ ትምህርትን ብቻ በሚመለከት እንኳን፣ የተለያዩ የትምህርት ደረጃዎች ለምሳሌ፣ የመሠረተ ትምህርት እና የከፍተኛ ደረጃ ትምህርት ለልማት ያላቸውን አስተዋጽኦ በየፊርጁ ማየት ይቻላል። በዚህ ላይ፣ ለብዙ ዘመናት ወደኋላ ተመልሶ በጉዳዩ ላይ ቅኝት፣ ትንተና እና ርዕይ ማስቀመጥ ፈታኝ ነገር ነው።

ይህ ጉዳይ ለአንዳንድ አንባቢያን ግልጽ ሊሆን ቢችልም፣ ፀሐፊው በመግቢያው አካባቢ አሳቸው ያተኩሩባቸውን የትምህርት ጉዳዮችና እነሱንም ለመምረጥ የገፋፏቸውን ምክንያቶች በጽሁፋቸው ውስጥ በአጭሩ ቢያስቀምጡ ሃሳባቸውን ለመከታተል ይጠቅም ነበር። በዚሁ ሳይነት፣ በአሳቸው አመለካከት 'ልማት' ሲባል የትኞቹ ነገሮች ትኩረት እንደሚያሻቸው በጽሁፉ ውስጥ ማስመልከቱ ይረዳል።

የጽሁፉ ዓላማና አቀራረብ በመግቢያው ላይ በግልጽ ተቀምጠዋል። በዚህ አንፃር ፀሐፊው "የአገሪቱ ትምህርት በየዘመኑ የተጓዘውን ሂደት በመቃኘትና ለአገር ልማት ያደረገውን መዘራና ማድረግ የነበረበትን ለማድረግ ያልቻለበትን ምክንያቶች ለመተንተን ተሞክሯል" ብለዋል። ቀጥለውም አንዳንድ ርዕዮች የመሰንዘር መዘራ እንደሚያደርጉ ገልጸዋል።

---

*ፕሮፌሰር ዳርጌ ወሌ የመጀመሪያ ድግሪያቸውን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ካገኙ በኋላ ፒኤችዲ በ Educational Psychology ከአሜሪካ አገር ተቀብለዋል። ከ20 ዓመት በላይ በመምህርነት እና በምርምር የሰሩ ምሁር ናቸው። በ Education Faculty Assistant Dean ሆነው ሠርተዋል። በመስካቸው ብዙ የታወቁ የጥናት መጽሔቶች ላይ የምርምር ጥናቶችን አሳትመዋል።

በእኔ አስተያየት፤ የአሁኑንና የወደፊቱን የአገሪቱን የትምህርት ሁኔታ ለመገንዘብ ወይም ለማሻሻል ወደኋላ ሄዶ ያሳለፍናቸውን ሂደቶች ማጤን አስፈላጊና ጠቃሚ ነው። በዚህም ረገድ ዐሐፊው ዘመናዊ ትምህርት ተጀመረበት ከሚሉበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ ያሉትን ሂደቶች አጠር ባለ መንገድ ዳሰዋል። በተለያዩ ንዑስ አርእስት ሥር ትምህርት ለልማት ተገቢውን አስተዋጽኦ እንዳያደርግ አድርገዋል የሚሏቸውንም ነገሮች ጠቅሰዋል። ሆኖም በእንደዚህ ዓይነት ጽሁፍ ውስጥ ረጅም ታሪክን አጢኖ እልባት ለማውጣት ሲሞክር አንዳንድ ሂደቶች እንዳይዘነጉ ጥንቃቄ ያስፈልጋል። ለአብነት ያህልም ከመደበኛ የመንግሥት ትምህርት ቤቶች ሌላ የማሰልጠኛ ተቋሞች እየተባሉ ይካሄዱ የነበሩ (ለምሳሌ፤ የቴሌ፣ የባንክና የኢትዮጵያ አየር መንገድ ማሰልጠኛዎች) ነበሩ። የግል ትምህርት ቤቶች ጎላ ባለ አኳኋን የሚካሄዱባቸው ቦታዎችና ጊዜዎችም ነበሩ። ከፖሊሲ ባሻገር እንደነዚህ ዓይነት ተቋሞች ለልማት የነበራቸውና ያላቸው አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ ቢገባ ውይይቱን ያዳብራል።

2. የጽሁፉ ዐቢይ መልእክትና ይዘት

በእኔ አመለካከት፣ ጽሁፉ የሚያስተላልፈው አንድ ዋና መልእክት ቢኖር የአገሪቱ ትምህርት ለልማት አመርቂ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችለው የትምህርት ፖሊሲ በመቅረጽ ረገድ አግባብ ያላቸውን የጎበረተሰብ ክፍሎች ያሳተፈና ተደማጭነት የሚያገኝ በቂ ውይይት ሲደረግ ነው። ይህን ነጥብ ፀሐፊው ስለ "Education Sector Review" እና በ1994 (እ.ኤ.አ.) ስለወጣው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ እንዲሁም "ርዕይ" በሚል ንዑስ ርዕስ ሥርና በሌሎችም ቦታዎች አስፍረዋል።

በይዘት ረገድ ዐሐፊው ያሉትን መድገም የሚያስፈልግ አይመስልኝም። ቢሆንም አላቸው እንዳቀረበው አልፎ አልፎ አንዳንድ ተራማጅ ሊባሉ የሚችሉ አመለካከቶች ታይተዋል። ለምሳሌ በሃያኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ የሴቶች ትምህርት አጽንኦት አግኝቷል። ሆኖም የወይይት ድክመት፣ እንዲሁም የዘመቻ፣ የውጭ ተጽእኖ እና አንስቶ-የመጣል አካሄዶች በትምህርት ላይ በተለያዩ ጊዜያት በማየላቸው ፍትሃዊነትን፣ ጥራትንና የመሳሰሉትን ለማሟላት እንዳስቸገረ ተገልፃል።

በመጨረሻም ዐሐፊው በርዕይ አንፃር ያቀረበው አሳብ ባጭሩ ሲቀመጥ በቂ የሕዝብ ተሳትፎ ያገኘ የትምህርት ፖሊሲ የሚኖር ከሆነ ትምህርት ለልማት ብዙ አስተዋጽኦ ያደርጋል የሚል ነው።

3. በጽሁፉ ውስጥ የተነሱና ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባ ጉዳዮች

ይህን ንኡስ ርዕስ በሚመለከት የሚከተሉትን ነጥቦች ላሰምርባቸው እፈልጋለሁ።

ሀ. በመንግሥትና በትምህርት ፖሊሲ መሃከል ያለው ቁርኝት

ይህን ጉዳይ ዐሐፊው በተለያየ መልኩ አልፎ አልፎ አንስተውታል። ለምሳሌ፤ ፀሐፊው ደርግ መመሪያ ያደረገው የሶሻሊስት ርዕዮተዓለም በትምህርት ላይ የነበረውን ጫና አንስተዋል። በዚህ አኳያ ለሌች ምሳሌዎችንም መስጠት ይቻላል። ለምሳሌ፤ ምንም እንኳን ፀሐፊው

ስለኢትዮጵያ ዩኒቨርሲቲ፡ አገልግሎት ሲያወሱ ፕሮግራሙ የተቋረጠበትን ምክንያት በዝርዝር አስቀምጠዋል፤ እንዲቋረጥ ካደረጉት ዋና ዋና ምክንያቶች አንዱ የለውጥ አቀንቃኝ ወጣቶች የመንግሥትን ፍላጎት የሚጻረር ነገር ይሰራሉ የሚል አስተሳሰብ እንደነበረ ግንዛቤ አለ። ሦስተኛ የትምህርት ፖሊሲ በወቅቱ ባለው መንግሥት አጠቃላይ የአስተዳደርና የልማት ሂደት ይወሰናል።

ሰ. የተከታታይ እድገት ጥያቄ

የትምህርት እቅዶች የዘመን መልከና የያዝ-ጣል እንዲሁም የመዋገርቅ አሰራሮች እንደነበራቸው ዐሐፊው በአንዳንድ ቦታ ጠቅሰዋል። እነዚህ አሰራሮች በትምህርት ላይ አለ-ታዊ ተጽእኖ ሊኖራቸውም እንደሚችል ከጽሁፉ መረዳት ይቻላል። ለምሳሌ በደርግ ዘመን የትምህርት የ-መደበው ባጀት ቀድሞ ከነበረው (በመቶኛ ሲሰላ) መቀነሱ የመደበኛ ት/ቤቶች ውስ-ማኑን ጎድቷል። በትምህርት ሁኔታ ላይ የሚደረገ ጥናቶችም ፋይዳቸው በሚገባ ሊይመዘን ወደጎን የሚተዉ ከሆነ ጉዳት አለው። በብዙ ድካም የተገኘ ውጤት የሚቀለበስ ከሆነም ከሸረት ነው። ስለዚህም እቅዶችና አፈጻጸሞች ተከታታይ እድገት እንዲያስገኙ መጣር አንድ ወሳኝ ነገር ነው።

ሐ. የውጭ ተጽእኖ

ፈረንሳይ፣ እንግሊዝ፣ አሜሪካ፣ የቀድሞው ሶቪየት ሕብረት እና ሌሎች አገሮች በአገራችን በመንግ ትምህርት ላይ ተጽእኖ እንደነበራቸው ግልጽ ነው። አሁንም አንዳንዶቹ አላቸው። ይህንን ጉዳይ በሚመለከት የአገር ፍላጎት፣ ጥቅምና ልማት የትምህርት ዋና ግብ በመሆኑ ላይ ላይደራደሩ፣ እንዲሁም አገራቱ ያለቻቸውን ባለሙያዎች ተሳትፎ እያስተናገዱ ራስን ለመቻል የማረዳ ማሚያ ግብአት ከውጪ መቀበል የሚያስኬድ ይመስለኛል። በዚህ ረገድ ዐሐፊው ስለውጪ ተጽእኖ ካነሱት ጋር አያይዞ ስለውጪ አስተዋጽኦ መነጋገር ይረዳል። በእኔ እምነት ጥያቄውና አጣብቂኙ የውጭ አስተዋጽኦን ማስቀረት ሳይሆን "የውጭ ተጽእኖ ወይም ጫና አስቀርቶ አሊያም በተቻለ መጠን አሳንሶ የውጭ አስተዋጽኦ እንዴት ማግኘት ይቻላል?" የሚለው ነው።

መ. የመምህራን ጉዳይ

መምህራንን በሚመለከት ፀሐፊው በተለያዩ ቦታዎች ችግሮችን ጠቅሰዋል። ለምሳሌ በመምህራን እጥረት ምክንያት የ "ድጎማ" መምህራን የሚባሉ ተሰማርተው እንደነበር ገልጸዋል። በአሁኑ ጊዜም ችግሩ በከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች አካባቢም ጎልቶ መታየቱን ጠቁመዋል። ይህ ጉዳይ በጣም አሳሳቢ ከሚባሉት ነገሮች ውስጥ ነው። በተለይም ለሥልጠና የሚመረጡት ተማሪዎች ችሎታ፣ የሥልጠናው ሁኔታና ከሥልጠናው በኋላ መምህራን በደሞዝ፣ ማበረታቻና የእድገት መሰላል ብቻ ሳይሆን በአስተዳደራዊ ሁኔታዎች ረክተው እንዲሰሩ ማድረግ ወሳኝ ነው። በእኔ ግንዛቤ፣ ለመምህራን አስተዳደራዊ አሰራሮችና የት/ቤቶች ሁኔታ ከገንዘብ ማነቃቂያ ያላነሰ ዋጋ አላቸው። ከዚህ ጋር በተያያዘ "ለወደፊቱ በዚህ አንባር ምን ዓይነት ማሻሻያዎች ለማየት ዕድል አለ?" የሚል ጥያቄ ማንሳት ተገቢ ነው።

ሠ. የትምህርት ጥራት ጥያቄ

ዐሐፊው እንደጠቆሙት የትምህርት ተሳትፎና ጥራት አብረው መሔዳቸው አስፈላጊ ነው። በጥራት በኩል ደግሞ ብዙ ችግሮች እንዳሉ በተለያየ ሁኔታ ይገለጻል። ጥራት ከተንጸባረቀባቸው የሚባሉት ገንዘብና ቁሳቁስ ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ ግምት የሚሰጠው የሰው ኃይል፣ ገዚ አና የተማሪዎች ሞራል፣ እንዲሁም ተነሳሽነት ጭምር ነው። እዚህ ላይ መነሳት ያለበት ጥያቄ "ለትምህርት ጥራት ዋና ዋና መሳኞች ምንድናቸው?" ብቻ ሳይሆን "እነዚህስ ነገሮች እንዴት ሊሚለ ይችላለ? የሚለውም ጭምር ነው።

4. ሊነሱ ወይም ሊብራሩ የሚገባቸው ሌሎች ነገሮች

ርዕሱን በሚመለከት ዐሐፊው ብዙ ነገሮችን ዳሰዋል። "በፖሊሲ ዝግጅት ላይ እውነተኛ የሕዝብ ተሳትፎ ይኖራል" የሚል ነጥብ ለርዕያቸው መሠረታዊ ታሳቢ በማድረግ ይህ ታሳቢ ነገር የማይሳካ ከሆነ ትምህርት ለልማት አመርቂ አስተዋጽኦ ሊያደርግ እንደሚችልም በርዕይ መልክ አስቀምጠዋል። "እሳቸው ያዩት ርዕይ ምን ያህል ይሳካ ይሆን?" ብዬ ሳስብ የመጠልኝን አንዳንድ አሳቦች ወይንም ተጓዳኝ ታሳቢዎች ማካፈል እወዳለሁ።

እነዘህም፤

ሀ. የሕዝብ ቁጥር መጨመር

በዚህ አንባር በ2.8% የሕዝብ እድገት መጠን በ2015 (እ.ኤ.አ.) የአገራቱ ሕዝብ ብዛት 94 ሚለዮን አካባቢ ይሆናል የሚል ግምት አለ። ከዚሁ ውስጥ ለትምህርት የሚደርሱ ሕዛናትንና ለለጮችን ግምት ውስጥ በማስገባት የሕዝብ ብዛት በትምህርት ተሳትፎ መጠንና ጥራት ላይ ተጽእኖ ሊኖረው እንደሚችል መገንዘብ ያሻል።

ለ. የኢኮኖሚ ሁኔታ

የአገራቱን የኢኮኖሚ ሁኔታ (ለምሳሌ የምርት መጠን እና የነፍስ ወከፍ ገቢ) አገራቱ ለትምህርት ልትመድብ የምትችለውን ባጀትና ሕዝቡ ለትምህርት የሚያደርገውን አስተዋጽኦ ይወስነዋል። በተለይም የድህነት አንድ መገመቻ የሆነው "National poverty line" ከአገራቱ ሕዝብ ውስጥ 44% የሚሆነው በአስከፊ ድህነት የተጠቃ መሆኑን ስለሚጠቁምና ችግሩ በገጠር ብቻ ሳይሆን በከተማም ስለሚታይ ይህ ሁኔታ ሕዝቡ ለትምህርት የሚያደርገውን አስተዋጽኦ በጣም ይገታዋል። ተገቢው ትምህርት ካልተሰጠ ደግሞ ልማቱና የኢኮኖሚ እድገቱ ይቀጭጫል። ነገሩ የተሳሰረ ነው። በርዕዩ የተሻለ ተስፋ እንዲኖረን የተቀነባበረ እቅድና አፈጻጸም ያሻል።

ሐ. የሠለጠነ የሰው ኃይል ፍላጎት

ከሕዝብ ቁጥር መጨመር ጋር በተያያዘ ወደፊት ለአገራቱ በተለያዩ መስኮች የሚያስፈልጋትን የሠለጠነ የሰው ኃይል ብዛት ከግምት ውስጥ ማስገባት ከትምህርት የሚጠበቀውን አስተዋጽኦና ሊከሰት የሚችለውንም ችግር ሊጠቁም ይችላል። ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ ለ100,000 ሰው አንድ ሐኪም እንዳለን አንዳንድ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ይህን ቁርኝት አሻሽሎ ልማትን ለማፋጠን የትምህርቱ መስክ በ2020 (እ.ኤ.አ.) ምን ያህል ብቃት ይኖረዋል?

ሙ. ያልተማከለ አስተዳደር ጥንካሬ

በዚህ ረገድ ለገጠሩ የአስተዳደር አካባቢዎች በተገቢው ሁኔታና ደረጃ ሥልጣን ለማካፈል የሚወሰደው እርምጃና በአጠቃላይ መልካም አስተዳደር ወደፊት ትምህርት ለልማት በሚኖረው አስተዋጽኦ ላይ ተጽእኖ ይኖረዋል። ያልተማከለ አስተዳደር እንዲጠናከር ደግሞ ለሲቪሉ ማህበራት (በተለይ የባለሙያዎች መሚላት) ያሻሉ። ስለዚህም አንዱ ጥያቄ "አሁን ያለው የትምህርት ሁኔታና ውጤት ለወደፊት የሚፈለገውን ግብአቶች ያሟላል ወይ? " የሚል ሲሆን ሁለተኛው "ይህስ ካልሆነ በወደፊቱ የትምህርት ተሳትፎ፣ ጥራትና፣ አግባብነት (relevance) ላይ ምን ያህል ተስፋ ማድረግ ይቻላል? " የሚል ነው።

ሠ. የኢንፎርሜሽንና ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ (ICT) ሁኔታ

የኢንፎርሜሽንና ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ሁኔታ በአገሪቱ የትምህርት እንቅስቃሴ ላይ የሚኖረውን ሚና ገና በትጠ ባንነነዘበውም ወደፊት እየጨመረ ይሔዳል የሚል ግምት አለ። ይህ ሁኔታ በአግባቡ ካልተያዘ ከፍተኛ ሀብት እንዲባክን ከማድረጉም በላይ በትምህርት ጥራት ላይ ገንቢ ያልሆነ ተጽእኖ ሊኖረው ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ ነገር ደግሞ ትምህርት ለልማት የሚኖረውን አስተዋጽኦ ይገታዋል። በአንፃሩ ግን የትምህርት አደረጃጀት እና ሥርዓተ ትምህርት እንዲሁም ተማሪዎችና አስተማሪዎች ስለ ICT ያላቸው አመለካከት በሚገባ ከተጠነሰሰ በተለመደው አኳኋን በክፍል ውስጥ ከሚሰጠው ትምህርት ባሻገር በቴክኖሎጂ ድጋፍ በክፍል ውስጥ የሚሰጥ ትምህርት፣ እንዲሁም በርቀትና በተከታታይ ትምህርት ረገድ ጥሩ አስተዋጽኦ ሊገኝ ይችላል። ያኔ ትምህርት ለልማት ያለው አስተዋጽኦ ይጨምራል። ይህን በማመለከት "በአሁኑ ጊዜ ICTን ለትምህርት ጥዳያ, የምንጠቀምበት መንገድ እስከምን ድረስ አጥጋቢ ነው?" የሚለው ጥያቄ መመለስ አለበት።

ረ. የተከታታይ ማምጣትና ማሻሻያ ጥያቄ

የትምህርትን ሂደት በተሻለ ሁኔታ ፊር ለማስያዝ አግባብ ባለው መንገድ የተዘጋጀ ፖሊሲ አውጥቶ ወደመተግበሩ መግባት በቂ አያደለም። አስፈላጊውን የመከራ ጊዜ በመስጠት አተግባበሩን መደያዊ በሆነ አኳኋንና በሐቀኝነት በተገበረው ወቅት እየገመገመ አስፈላጊ ናቸው የሚባሉ ማስተካከያዎችን የማድረግ መደያዊ አመለካከትና ቁርጠኝነት ያሻል። በዚሁ ጉዳይ ላይ የሚደረጉ ጥናቶች እንዳጠናከሩና ውጤታቸውም ከአገር ልማት አንፃር እየታየ ጊዜ ላይፈጅ የሚፈለገው ማሻሻያ ካልተደረገ ትምህርት ለልማት የተሻለ አስተዋጽኦ ያደርጋል ብሎ ተስፋ ለማድረግ ያስቸግራል።

5. ማጠቃለያ

ጽሁፉ በየዘመናቱ የትምህርትና ልማት ትስስር እንዴት እንደነበረና በዚህም አኳያ የተከሰቱ እንቅፋቶችን ጠቁሟል። በእኔ አስተያየት ርዕሱ ውስብስብ ነው። ትንተናውም ሊስፋፋ ይችላል። ሆኖም ተጨማሪዎቹ ጉዳዮች የየራሳቸውን ጽሁፎችና መድረኮች ይፈልጋሉ። ይህ እንዳለ ሆኖ፣ ፕሮፌሰር ሥዩም፣ ለመመጠን፣ ለማተኮጅትና ርዕይ ለማሳለቅ አስቸጋሪ በሆነ በዚያ ጉዳይ ላይ ብዙ ሳሪ ነገሮች አነተው በተለይም የታሪክ ክስተቶች ጠቅሰው ውይይት በሚገባ ሊቀስቅስ የሚችል ጽሁፍ በማቅረባቸው ሊመሰገኑ ይገባል።

ትምህርት እና ልማት በኢትዮጵያ ጽሁፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት

አያለው ሸበሸ*

የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር በዚህ ጽሁፍ ላይ አስተያየት እንድሰጥ ስለጋበዘኝና «ትምህርትን» የመወያያ ርዕስ አድርጎ በማቅረቡ ከልብ ላመሰግን እወዳለሁ። የጽሁፉን አቅራቢ ፕሮፌሰር ሥዩም ተፈራን በትምህርት ሥርዓት የረኸርም ጊዜ ቆይታችው ካካበቱት ልምድና ዕውቀት በመነሣት ድንቅ ጽሁፍ በማቅረባቸው «ይበል›› እላቸዋለሁ።

ይኸን ካልኩ በኋላ አስተያየቴን እንደሚከተለው አቀርባለሁ።

ጽሑፉ በስምንት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን የአገራቱ የትምህርት ሥርዓት በየዘመኑ የተጓዘውን ሂደት በመቃኘት የገጠመውን ውጣ ውረዶች ያሳያል። በመጨረሻ በሀያ ሀያ ጸሀፊው ለትምህርት ዘርፎች ያላቸውን ርዕይ አቅርቧል።

ጽሁፉ ከቤተክርስቲያን ትምህርት ጀምሮ፣ ዘመናዊ ትምህርት እንዴት መጀመር እንደተቻለ፣ ያገጠመውን ችግሮችና በውስጡም የነበሩትን ቅራኔዎች ከማመልከቱም በላይ በተከታታይ የተደረገውን አዋጆችና የለውጥ ድንጋጌዎችን እያጣቀሰ የሚያቀርብ በመሆኑ የአገሪቱን የትምህርት ዕድገት ታሪክ ለሚያጠኑ ደህና መሠረት እንደሚሰጥ ይታመናል።

ብዙም የማይታወቅ አንዳንድ ብርቅ መረጃዎችንም አካቷል። ለምሳሌ፤ ከአጼ ምኒልክ ለነጋድራስ ኃይለጊዮርጊስ የተጻፈውን ደብዳቤ ያጠኗል። በአንድ በኩል ንጉሠ ነገሥቱ ለዘመናዊ ትምህርት መሰፋፋት የነበራቸውን ትጋት ሲያሳይ፣ በሌላ በኩል ዛሬ እንዲህ ዓይነቱን ትምህርት ያቋረጠ ተማሪዎችን የመከታተሉ ሥራ፣ ከትምህርት ቤት ዲሬክተር የሥራ ደረጃ እንኳን በታች ሆኖ ስንመለከተው ዘመናዊ ትምህርትን በዚህች አገር በእግሩ ለማቆም ምን ያህል ፈታኝ እንደነበር የሚያሳይ ነው።

በአጠቃላይ ጽሁፉ የአገራችንን የትምህርት ዕድገት ገጽታ እጥር ምጥን ባለ መልክ የሚያሳይ በመሆኑ ሊመሰገን የሚገባው አስተዋጽኦ ነው።

ይሁን እንጂ ጥያቄ ሊነሣባቸውና ውይይት ሊካሄድባቸው የሚገባቸው ብዙ ጉዳዮች አሉ።

1. ጽሁፉ ከመነሻው ላይ አገሪቱ የጽሁፍ ቋንቋ ባለቤት ብትሆንም እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ አብዛኛው ሕዝብ ይፈርም የነበረው በአውራ ጣቱ ስለነበር ለሶስተኛው ዓለም ስም

---

* አቶ አያሌው ሺበሺ የመጀመሪያ ዲግሪ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ማስተርስን ከ Bristol University እንግሊዝ አገር ተቀብለዋል። አቶ አያሌው ሺበሺ ተባባሪ ፕሮፌሰር ናቸው። በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ· ከ25 ዓመት በላይ በመምህርነትና በምርምር ላይ ብዙ ጊዜ የሠሩ ናቸው። ከዚህ ቡተጨማሪ በተለያዩ ኃላፊነት ሠርተዋል። በመምሪያ ኃላፊነት እና በምክትል ዲንነት በEducation Faculty እንዲሁም የContinuing Education አስተባባሪ በመሆን ለረጅም ጊዜ ሰርተዋል።

ማውጣት የማይሳናቸው ምዕራባዊያን «በአውራ ጣት የሚፈርምበት አገር» በሚል ስያሜ ትታወቅ ነበር ይላል።

አሁንስ ይኸ እውነታ ተቀይሯል? በቅርብ ያለው ስታትስቲካዊ መረጃ እንደሚያሳየው ከአልማሳው የህብረተሰብ ክፍል ከ60% በመቶ በላይ አሁንም በአውራ ጣቱ የሚፈርም ነው። ይኸ እውነት ሆኖ እያለ ለምን ያለፈ ታሪክ መስሎ ቀረበ?

አፄ ምኒልክ ያወጁት የትምህርት አዋጅ የመጀመሪያው የትምህርት አዋጅ በመሆኑና በረዘመም ጽንሰ ሀሳብ ሊደነቅ ይገባል። ሆኖም አንድ ትምህርት ቤት አቋቁሞ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ህፃናት ባሉበት አገር ሁሉንም ልጆች ለትምህርት መጋበዝ ምን ያህል በተጨባጭ ሁኔታው ላይ የተመሠረተ ነው? ጽሁፉ ሊተችበት የሚገባ ጉዳይ ነው።

በጽሁፉ ውስጥ ጎልቶ የሚወጣው አንድ መሠረታዊ ሀሳብ የትምህርት ሥርዓታችን በውጭ አገር ተጽዕኖ ሥር መውደቁ ነው። እንደተባለውም የትምህርት ሥርዓቱ በተለያዩ ጊዜያት፣ በተለያዩ አገሮች «የጡት አባትነት» መካሄዱ ግልጽ ነው። በተለይ ከነፃነት በኋላ በመጀመሪያ በእንግሊዝ ቀጥሎም በአሜሪካ ተጽዕኖ ሥር መውደቁ ገሀድ ነው። ይህም፤

- በትምህርት ሚኒስቴር ዋና ዋና ሹማምንቶች የውጭ ሰዎች መሆናቸው፤ መምህራኑ ከእነዚህ ሀገራት ወይም ፕሮቴክተሮች የመጡ በመሆናቸው፤
- መፃህፍት በቀጥታ ከእነዚያ አገሮች የመጡ ወይም በእነርሱ የተደረሱ በመሆናቸው፤
- የትምህርት መዋቅሩን እንደፈለጉ መቀያየር በመቻላቸው በእነዚህና በመሳሰሉት ይገለፃል።

ይህ እውነት ሆኖ ሳለ ጽሁፉ በድህረ አብዮት የትምህርቱ ሥርዓት በሶቭየት ህብረት ተጽእኖ ሥር ወድቆ ነበር ይለናል። ይህ ጉዳይ ሁለት ጥቂዎችን የሚያስነሳ ይመስለኛል።

መጀመሪያ አገሪቱ በአጠቃላይ በሶቪየት ተጽእኖ ሥር ብትወድቅም ትምህርትን በሚመለከት በአስከ ቅርርብ የነበረው ከቀድሞው የጀርመን ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ (GDR) እንጂ ከሶቭዬት ህዛብ ጋር የነበረ አይመስለኝም። እንዲያውም የትምህርት ሚኒስቴር ሠራተኞች ወዲህኛ አገር መመላለሱን የውሀ መንገድ አድርገውት ስለነበር «ከሞትና ከGDR የሚቀር የለም? የሚል አባባል ተፈጥሮ እንደነበር አስታውሳለሁ።

ሁለተኛ ርዕዮቱን በመከተል የማርክሲዝም ትምህርት ከአንደኛ ደረጃ እስከ ዩኒቨርስቲ ድረስ እንዲሰጥ መደረጉ እንዳለ ሆኖ በትምህርት ሥርዓቱ ላይ ብዙ ለውጥ የተደረገበት አይመስልም።

ጽሁፉ በንጉሠ ነገሥቱ መንግሥት ጊዜ የነበረውን የትምህርት ሥርዓት ፋይዳ ሲያጠቃልል የአገሪቱን ቢሮክራሲ የሚያንቀሳቅስ ምሁራን እንዳፈራና ለሕዝባቸው ሕሊና /Conscience of their people/ የሆኑ ወጣቶችን እንዳበቀለ ይገልፃል። የመጀመሪያው አከራካሪ አይደለም። ለሕዝባቸው ሕሊና የሆኑ ወጣቶችን ማፍራቱን ግን በጥሞና ልናየው የሚገባ ጉዳይ ነው።

በዚያን ዘመን መጨረሻ ለሕዝብ መብት የተከራከሩ፣ ለውጥ የናፈቁና ላመኑበት ነገር ያለማወላወል ቆመው የታገሉና የወደቁ ወጣቶች መፈጠራቸው ገሀድ ሀቅ ነው።

ግን የእነዚህ ወጣቶች መፈጠር የትምህርት ሥርዓቱ ውጤት ነው? የትምህርት ዓላማውስ ምን ነበሩ? ሥርዓተ ትምህርቱስ? ትልቁ ተልዕኮ በመያው የተካኑ ግን ሥርዓቱን አሚን ብለው የሚቀበሉ ታማኝ አገልጋዮች ለመፍጠር እንደነበር በግልጽ ይታወቃል። ስለሆነም በዚህ በዙል እንዲያውም ግቡን የሳተ የትምህርት ሥርዓት ነበር ብንል የሚያሰኪያ ይመስለኛል።

እንዲያውም ከ60ዎቹ መጨረሻ ጀምሮ ለደረሰብን እርስ በርስ የመጨራረስ ችግርና ከዚያም ወዲህ ላለው የመደማመጥ ችግሮች ሁሉ ያን የትምህርት ሥርዓት ተጠያቂ የሚያደርጉ ጽሁፎችም ብቅ እያሉ ነው። ያ የትምህርት ሥርዓት መምህሩ የሚያንቆረቁረውን እውቀት ቀድቶ የሚሄድበት እና በፈተና ወቅት ተማሪው መልሶ ለመምህሩ የሚያስረክብበት አንጂ ጠያቂነት፣ መቻቻል፣ ዲሞክራሲ የመሳሰሉት የማይታወቁበት በመሆኑ የሚያጋጥሙ ችግሮች ከኃይል ውጭ መፍታት የማይችል ትውልድ ፈጥሯል የሚሉም አሉ። ማጠቃለያው ከእነዚህ ሐሳቦች አኳያ ሊታይ ይገባው ነበር እላለሁ።

5. በዘመነ አብዮት ስለተካሄደው ትምህርት የዕድገት በህብረት ዘመቻ፣ የመሠረተ ትምህርት ዘመቻ፣ የጋምቤላና መተከል ዘመቻ፣ የከፍተኛ ትምህርትና በዘመኑ የወጡ አዋጆችን ከተመለከተ በኋላ ትምህርት በዚያን ዘመን ለልማት በተጨባጭ ይህን አድርጓል ለማለት ያስቸግራል ሲል ይደመድማል። ይህ አባባል ምን ያህል ሚዛናዊ እንደሆነ ለመገመት የሚያስቸግር ይመስላል።

- የዕድገት በህብረት የዕውቀትና የሥራ ዘመቻ በሚገባ ያልታቀደ፣ ያልተጠና ምናልባትም ወታደራዊው መንግሥት ተቃዋሚዎችን ሆን ብሎ ለማራቅ የተጠቀመበት ነው ማለት ይቻላል። ግን የተካሄደው ዘመቻ ውጤት ምን እንደነበር የሚያሳይ መረጃ የለም ብሎ ማለት፣ የተከፈለውን መስዋዕትነት ማኮስመን እንዳይሆን እሰጋለሁ። እጅግ ቢያንስ የመሬቱ አዋጅ ያለዚያ ዘመቻ ተግባራዊ ይሆን ነበር ብሎ ማሰብ የሚያስቸግር ይመስለኛል። በገጠሩ ህብረተሰብ ዘንድ የተፈጠረውን የአስተሳሰብ ለውጥና ህሊና ከፍ ማለትም ሌላው የሚጠቀስ ጉዳይ ነው።
- መሐይምነትን ለማጥፋት የተደረገውም መከራ የሚናቅ እንዳልነበርና የዩኔስኮን ሽልማት ያስገኘ እንደነበር በጽሁፉ ተጠቅሷል።
- ከፍተኛ ትምህርትን በሚመለከትም የድህረ ፕሮግራም መጀመር ብቻ ሳይሆን አሁን ወደ ዩኒቨርሲቲነት ያደጉት፣ የአርባምንጭ፣ የአዋሳ፣ የጅማ፣ የናዝሬት ወዘተ... በኮሌጅነት ሥራቸውን የጀመሩት በዚያን ጊዜ እንደነበር የሚታወቅ ነው። ይህም የማስፋፋት ሥራ መደረጉን የሚያሳይ ነው። በአጠቃላይ በዘመነ ደርግ ስለነበረው የትምህርት ሥርዓት የቀረበው ትንተናና የተደረሰበት ማጠቃለያ የሚጣጣም አይመስለኝም።

6. ጽሁፉ አዲሱ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ተግባራዊ መሆን ከጀመረበት ጊዜ ወዲህ የትምህርት ሥርዓቱ ያከናወናቸውን ጉዳዮች ይዳስሳል። በቁጥሩ በኩል የተደረገው ዕድገት አበረታች እንደሆነ ገልጾ የትምህረቱ ጥራት ግን አጠያያቂ መሆኑን ያመለክታል።

የትምህርት ጥራቱን አጠያያቂነት ብዙ ሰው የሚስማማበት ይመስለኛል። ጽሁፉ የጠቀሳቸው መሰረታዊ መሆኖ፣ የተማሪ መምህር ጥምርታ፣ የተማሪ መጽሐፉ ጥምርታ የመሳሰሉት የጥራት አመልካቾች ቢሆንም ሌሎችንም ማከል ይቻላል። ከሁሉም አንባር የሚያመለክተው ወደ ታች ስለሆነ በዚህ ረገድ የተደረሰበት መደምደሚያ አግባብ ይመስለኛል።

የቋሃር አድጎትን በተመለከተ የተሰጠው ማጠቃለያ ግን ለሁሉም የሚያስማማ አይመስልም። በአፈጣጠሙ በትርበቡ የወጣው የ1996 ዓ.ም ዓመታዊ ስታትስቲክስ መረጃ እንደሚያሳየው ጥቅል የትምህርት ተሳትፎ 68.4% በመቶ ደርሷል ይላል። በ1997 ከዚያ ከፍ እንደሚል ይገመታል። ቢ ብለው ሲያዩት ግን ቢያንስ ሁለት ችግር አለው።

ትምህርት ለሁሉም'' ዓለም አቀፍ የትምህርት አዋጅ አኳያ ዋናው መለኪያ ንጥር የተሳትፎ መጠን (NER) ነው። በዚህ ስንለካው ትምህርት ቤት የገቡት 57.4% ብቻ ናቸው። ከ7ኛ በላይ አሁንም የትምህርት ዕድሉን አላገኙም። ከዚህም በተጨማሪ ሥርጭቱ የተመጣጠነ ስላልሆነ በአንዳንድ ክልሎች በተለይም በአርሶ አደር አካባቢ ያለው የተሳትፎ መጠን የማስደነግጥ ነው። ቅድም የጠቀስኩት የመረጃ ምንጭ እንደሚያመለክተው የተሳትፎ መጠን በአራር 14.8%፣ በሱማሌ 15.1% ብቻ ነበር። በ1997 ከፍ ሊል ይችላል። ቢሆንም በቀረሙት 10 ዓመታት የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን ለሁሉም ማዳረስ ይቻላል እንኳ ቢባል አለ የተባለው ''ርብርቦሽ'' መቀጠል የሚኖርበት ይመስለኛል።

ሌላው ጉዳይ ''የትምህርት ለሁሉም'' ዓላማ በመደበኛው ትምህርት ላይ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የጎልማሶችን፣ የህፃናት፣ ልዩ ትምህርትን፣ ወዘተ... ያካተተ ሲሆን በዚህ ረገድ ምን እንደተሠራ በጽሁፉ የተገለጸ ነገር የለም። ስለሆነም የትምህርቱ ጥራት ብቻ ሳይሆን 2015 ሊሳካይ ግብ መድረስ፣ አለመድረሱ አሁንም ዋና ጉዳይ ይመስለኛል። ዋናው ጉዳይ ጥራት ነው የሚለው የሚያነናጋ መርህ እንዳይሆን እፈራለሁ።

1. በመሐረሻ ዐሐፊው ለሀያ ሀያ ያሏቸውን ርዕይ ነግረውናል። ብዙዎቹ ዐሐፊው እንዳሉት እንዳናነሀ ያርግልን የሚያሰኙ ናቸው። አንዳንዶቹን ግን ሳያስፈልግ ያራቁብን ያመስለኛል። ሀያ ሀያ ለመድረስ 15 ዓመት[1] ይቀረናል። ለስራበት 15 ዓመት ረዥም ጊዜ ነው።

አመሰግናለሁ

ፋይናንስ እና የኤኮኖሚ ዕድገት በኢትዮጵያ

ንዋይ ገብረአብ*

በዚህ ዘርፍ ልምድ ያላችሁ፣ ጥናት ያደረጋችሁ፣ ልትኖሩ ስለምትችሉ ለማደርገው ግድፈት በቅድሚያ ይቅርታ ለመጠየቅ እፈልጋለሁ። ርዕይ 2020 ኢትዮጵያ ምን ሊሆን ይችላል? ምሚለውን በመጨረሻ ላይ ትንሽ ለመጠቆም እሞክራለሁ። በተረፈ ፋይናንስ እና የኤኮኖሚ ዕድገት በኢትዮጵያ በሚለው ላይ ለማተኮር ነው የምሞክረው። ርዕሱ በጣም ሰፊ ነው። ሰፊ ስለሆነም እንዴት አድርጎ ወደ ጭብጡ መሄድ ይቻላል? የሚለው የራሱ የሆነ ጥያቄ ያስነሳል። ምናልባት፣ እኔ የሞከርኩት ቀስ ብሎ ርዕሶቹን ማስተዋወቅ ይበጃል የሚል በመሆኑ መጀመሪያ ላይ የፋይናንስ ዘርፍ ምን ያካትታል የሚለውን ትንሽ ጠቀስ ማድረግ አፈልጋለሁ። እንደሚታወቀው የፋይናንስን ዘርፍ በሁለት መክፈል እንችላለን፤ ፎርማል የሆነ ገበያ እና ኢንፎርማል የሆነ ገበያ። ፎርማል የፋይናንስ ገበያ የሚያካትታቸው እንስቲቲዩሽንስ ባንኮችና ኢንሹራንስ ኩባንያዎች ሲሆኑ ሥራቸው ለየት ያለ ቢሆንም አሁን አሁን ማይክሮፋይናንስ (microfinance) እየተባሉ የሚታወቁ የፋይናንስ አገልግሎት ድርጅቶች፤ ምናልባትም ጠርቀም ብለው ቢዳብሩ ወደ ገጠር ባንኮች ሊቀየሩ የሚችሉ፣ እንደዚሁም ማህበራት (coops) ሊጠቀሱ ይችላሉ። መጨረሻ ላይ ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄድ የሰነድ (securities) ገበያዎችንም አነሳለሁ፤ ስለእነሱም ምንነት ትንሽ ዘርዘር አድርጌ አጠቃላለሁ።

የፋይናንስ ገበያ ፎርማል ነው ስንል ምን ማለታችን ነው? በህገ-ደንብ የሚመራ ወጥ ሆኖ የሚታይ የወለድ ተመን ወይም የትርፍ ግራፍ ያለው ገበያ ሲሆን የሰነድ ገበያ ከሆነ አቅርቦትና ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ወጥ የሆነ ግራፍ የሚኖረው ገበያ ነው። ኢንፎርማል የምንለው በዘልማድ በየአገሩ የሚገኝ የፋይናንስ ገበያ ነው፤ ብዙውን ጊዜ የግል አበዳሪዎች ናቸው። በተለይ በባላገሩ፣ ባንኮች በደንብ ባልተሠራጩበት አገር፣ እንደዋነኛ የብድር ምንጭ ሆኖ የሚያገለግለው ይኸው የኢንፎርማል ገበያ ነው። ለምሳሌ ያህል ብጠቅስ፤ ኢትዮጵያ ውስጥ በቀድሞው ዘመን በንጉሡ ጊዜ በተለይም ቡና በሚያመርቱበት አካባቢዎች የግል አበዳሪዎች በብዛት ይንቀሳቀሱ ነበር፤ በጣምም የተስፋፉ ነበሩ። ብድሩ የሚካሄደው የተወሰነ ገንዘብ በቅድሚያ ሰጥተው፣ ለምሳሌ ብር 100 እንበል፣ እስከእነወለዱ በዓመቱ መጨረሻ ላይ ብር 200 የሚከፈልበት ሁኔታ ነው። አንዳንድ ጊዜም አበዳሪው ራሱ የሰብል ገዢ ይሆንና በሰብል ግዢ አማካኝነት ብድሩን ይቀበላል። ይኸም ብድሩ እንደሚከፈል ለማረጋገጥ ያመቸዋል። ስለዚህ የምንነጋገረው በኢንስቲቲዩሽን መልክ እነዚህ ሁሉቱ እንደሚሆኑ ታሳቢ ብናደርግም እኔ ዛሬ መነጋገር የምፈልገው መደበኛ የፋይናንስ ገበያ ላይ በማተኮር ነው።

---

* አቶ ንዋይ ገብረአብ በሚኒስትር ማዕረግ የጠቅላይ ሚኒስትር ኤኮኖሚ አማካሪ እና የኢትዮጵያ ልማት ምርምር ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር ናቸው።

ፎርማል ገበያ ምን ይመስላል? እነዚህ ባንኮች እና ሌሎች ኢንስቲቲዩሽንስ ምን ይሰራሉ? የሚለውን መጀመሪያ ላይ አንስተን ብንመለከት፤

የባንክ ዋና ሥራው የቁጠባ ገንዘብ ከተለያዩ ሰዎች መሰብሰብ ነው። በግለሰብ፣ በቤተሰብ እና በኩባንያዎች ያረጃ የቁጠባ ገንዘብ ይሰበሰባል። ይህን የሰበሰበውን የቁጠባ ገንዘብ ብድር ለሚፈልጉ ሰዎች ይሰጣል። ቆጣቢንና ተበዳሪን ያገናኛል ማለት ነው። ባንድ በኩል ሊታሰብ በጣም ትልቅ ተግባር ወይም ሥራ ነው። ምክንያቱም ባንክ ባይኖር ኖሮ እያንዳንዱ ተበዳሪ እየሠረ ገንዘብ ከሚቆጥበው ላይ ሊበደር ነው ማለት ነው። በባንክ አማካኝነት ከብዙ ሺህ ሰዎች የተሰበሰበን ገንዘብ በቀጥታ ተበድሮ ለመዋዕለንዋይ ኢንቬስት ማድረግ ይቻላል ማለት ነው። ስለዚህ የፋይናንስ ኢንስቲቲዩሽንስ የማገናኘት ኃላፊነት (intermediary role) እንዳላቸው በብዙ መልክ ልናይ እንችላለን። ይኸም ቆጣቢንና ተበዳሪን ማገናኘት ማለት ነው። ዋነኛው የባንክ ተግባር ይኸ መሆኑን ለመጠቆም ነው።

ኢንሹራንስ በመሠረቱ የሚሠራው አደጋን (risk) መሸፈን ነው። ብዙ ዓይነት አደጋዎች አሉ። የመኪና አደጋ አለ፤ የሕይወት አደጋ አለ፤ በያይነቱ የአደጋ ዋስትና አለ። በምርትም ላይ በሆን፣ አገራችን ውስጥ አልተለመደም እንጂ፣ የአየር ለውጥ (መዛባት) ስለሚኖር የገበሬው ሰብል ከጠፋ ዋስትና ሰጥቶ መሸፈን ይቻላል። መድህን ትግርን አሸትቶ የሚከላከል ተግባር አድርጎ መቁጠር እንችላል።

በሌላ ጎኑ ደግሞ ይህ በኢንሹራንስ የተጠራቀመው ገንዘብ በቋሚነት አንድ የመድህን ድርጅት እንዲንቀሳቀስ፣ በተለይ እንዲያድግ ከተፈለገ፣ እንቬስት ሊያደርግ የሚችልበት ሁኔታ እንዲኖረው ማድረግ ተገቢ ነው። ባንክ ያበድራል፤ ኢንሹራንስስ የሰበሰበውን ገንዘብ እንዴት አድርጎ ነው ሥራ ላይ የሚያውለው? ብለን ብንጠይቅ ባደጉ አገሮች የተለመደው በስነድ (securities) ገበያ ውስጥ መሳተፍ ነው። ቀደም ብዬም ስነድ የሚለውን ቃል ስለተጠቀምኩ ይህ ምን ማለት እንደሆነ ትንሽ ላስረዳ።

በመሠረቱ ስነድ አንድ ዓይነት ወረቀት ነው፤ «እኔ ያንተ ብድር አለብኝ» (I owe you) የሚል መተማመኛ ጽሑፍ። መንግሥት እዚህ እኛ አገር የተለመደ የግምጃ ቤት ስነድ በየጊዜው ይሸጣል። እንደአጋጣሚ ግለሰቦች አይገዙም፣ ድርጅቶች ናቸው የሚገዙት፣ በተወሰነ የገንዘብ መጠንም የተገደበ ነው፤ በስነዱ ላይ ደግሞ ከወለድ ጋር ተመሳሳይ የሆነ ገቢ/ትርፍ አበዳሪዎች ያገኙበታል። ስነድ የብድር መሳሪያ (instrument) ሲሆን ጠንከር ያለ ኢኮኖሚ ቢሆን ኖሮ ግን መንግስት ትሬዠሪ ቢልስ መሸጥ ብቻ ሳይሆን የረጅም ጊዜ ቦንድ ይሸጣል። ያ የተሸጠው ቦንድ እንደገና ሁለተኛ ገበያ (secondary market) ይኖረዋል። ይህ በጣም ጠቃሚ ነው። በግል አንድ ቦንድ የገዛ ሰው ወይም ድርጅት ለሌላ አሳልፎ ይሸጣል ማለት ነው። ሲሸጥ ዋጋውን ቀንሶ ነው። እና፣ ሰፋ ያለ ሁለተኛ ገበያ ወይም የገበያ ሥርዓት ሊኖረው የሚችል መሣሪያ (instrument) ቦንድ ነው።

ሌላኛው የሰነድ ገበያ የአክሲዮን ገበያ ነው። አንድ ኢንቬስተር ከባንክ ብቻ መበደር የለበትም። ከፊለገና ታዋቂነት ካለው ለሕብረተሰቡ አክሲዮን ሽጦ ገንዘብ ማሰባሰብ ይችላል። ስለዚህ የሰነድ ገበያ ስንል እነዚህን ሁለቱን ማለታችን ነው። በመጨረሻ፣ በተለይ ዶ/ር መለዳሮ ገና ስላለ ላልፈው አልችልም፤ ስለ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽንስ (MFI) ማንት አፈልጋለሁ።

የማይክሮፋይናንስ ኢንስቲትዩሽንስ እንደ ባንክ የሚንቀሳቀሱ ናቸው። ባንክ ግን አይደሉም። ባንክ የማይሆንበት ምክንያት፣ 1ኛ/ ባንክ የሚያበድረው ከሕዝብ በቁጠባ (በተቀማጭ) መልክ የሰበሰበውን ገንዘብ ነው። እነዚህ ማይክሮ ፋይናንስ ኢንስቲትዩሽንስ ግን የሚያበድሩት በያንስ አስከያድገ ድረስ የራሳቸውን ተቀማጭ ገንዘብ ወይም ሀብት (equity) ነው። ተቀማጭ ገንዘብ መቀበል ከቀጠሉ በቁጠባ መልክ እነርሱ ዘንድ ተቀማጭ የተደረገው ገንዘብ እያደገ ይሄዳና፣ የሚያበድሩት ገንዘብ ከራሳቸው ገንዘብ ሳይሆን፣ በአብዛኛው በቁጠባ መልክ ከሚሰበሰብ ገንዘብ ሲሆን፤ በይበልጥ እንደ ባንክ አገልግሎት የሚሰጡበት ሁኔታ ይኖራል። ስለዚህ ማይክሮፋይናንሶች ምን ዓይነት ሚና አላቸው? ብለን ስንጠይቅ እንደዋነኛነት ልናነሳ የምንችለው፤ በተለይ በታዳጊ አገሮች፣ ለኢንቬስትመንት የሚውል የመዋዕለ ንዋይ አቅርቦት ምን ያህል ከእነሱ ይመነጫል? ማለታችን ነው።

አንድ ኢንቨስተር፣ በተለይ ትልቅ ኢንቬስተር ከሆነ፣ በመሠረቱ ሁለት ምንጭ ነው ያለው። ከሰነድ ገበያ ላይ ሊያገኝ የሚችለው የጥሬ ገንዘብ መጠን አንደኛው ሲሆን ሁለተኛው የባንኮች ሚና ነው።

በኢትዮጵያ የሰነድ ገበያ እምብዛም ባለመሆኑ ባንኮች በኢንቬስትመንት ያላቸው ሚና ምንድን ነው? ብለን ብንጠይቅ ይሻላል። በዚህ ረገድ የተጠና ጽሑፍ እስካሁን አላየሁም፤ ግምት ውስጥ የምትለኝ ከሆነ ምናልባት ከ15 በመቶ አያንስም ባይ ነኝ። ይህ ምን ማለት ነው? በአጠቃላይ በየዓመቱ የግል ክፍለ ኤኮኖሚው ኢትዮጵያ ውስጥ ከ7 እስከ 8 በመቶ የአገር ውስጥ ሀብት (GDP) ኢንቨስት ያደርጋል ብንል፣ ከዚህ ውስጥ እስከ ሁለት በመቶ የአገር ውስጥ ሀብት ከባንክ ብድር የሚገኘው ነው ማለት ከቻልን፣ ይህ ለእኔ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ነው። ልክ ነኝ፣ ልክ አይደለሁም፣ ወደፊት በጥናት መታየት ያለበት ጥያቄ ይመስለኛል። እንደ እኔ ግን የባንኮች ሚና በኢትዮጵያ ውስጥ ከኢንቬስትመንት አኳያ ከፍተኛ (significant) ነው።

ባንኮች በቅጡ የማይሳተፉበት መድረክ ካለ አነስተኛ ተበዳሪዎች የሚባለው ክፍል (category) ስንመጣ ነው። አነስተኛ ተበዳሪዎች ለዋስትና የሚያሲዙት ንብረት የላቸውም። እኛ አገር ያሉት ባንኮች ዋስትና ጠያቂው ነው የሚያበድሩት። እነዚህ አነስተኛ ኢንቬስተርስ ከአገራቸው አጠቃላይ ኢንቨስትመት ምን ያህል ነው ድርሻቸው? ብለን ብንጠይቅ፣ ምናልባት ‹የእውር ግምት› ሊሆን ይችላል፤ በእኔ ግምት እስከ ግማሽ ሊደርስ ይችል ይሆናል እላለሁ። በየዓመቱ ለለያይ ይችላል። ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ በየዓመቱ የሚያረገው

ኢንቬስትመንት ቢያንስ አንድ ሦስተኛው እንኳ በአነስተኛ ኢንቬስተርስ ነው የሚካሄደው የምንል ከሆነ፣ በዚህ አካባቢ ላለው ኢንቬስትመንት ባንኮቻችን ምንም ሚና የላቸውም ወደ ማለት ደረሻ ነው የምንደርሰው። ከዚህ ተለቅ ላሉ፣ መካከለኛ ለሆኑ፣ ኢንቬስተሮች ብዙውን ጊዜ ገንዘብ የሚያገኙት ከባንክ ነው። ስለዚህ በእነዚህ ላይ ባንክ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው ።

በተረፈ አንድ ኢንቬስተር በራሱ የገንዘብ ምንጭ የቱን ያህል ይንቀሳቀሳል? የሚለው ለሁላችንም ቢሆን ግምት ነው ሊሆን የሚችለው። የተደራጁ ኢንቬስተርስ በየጊዜው ከዲፖሪሺዬሽን ፈንድ የሚያጠራቅሙት ገንዘብ ስለሚኖር፣ እንዲሁም ከትርፍ የሚያገኙት ገንዘብ ስለሚኖር፣ የባንክን ድጋፍ በሰፊው ላይጠይቁ ይችላሉ። ለተቀረው ግን፣ በተለይ አዲስ ጅማሪ ለሆነውና በንግድ እንቅስቃሴ ውስጥ ጥቂት ዓመታት ብቻ ለሠራ ኢንቬስተር፣ እናንተም ልትገምቱት እንደምትችሉት፣ አብዛኛው የገንዘብ ምንጭ ከባንክ ብድር እንደሚሆን ነው።

የባንኮችን ጠቀሜታ ባጭሩ እንደዚህ ከገለጽሁ ማንሳት የምፈልገው፣ ባንኮች ምን ዓይነት ችግር አለባቸው? የሚለውን ነው።

ባንክም ሆነ ኢንሹራንስ አንዱ ትልቁ ለሥራው አመርቂነት የሚያስፈልገው መረጃ ወይም፣ ኢንፎርሜሽን ማለት ነው። መረጃው ደካማ በሆነ መጠን ኢንቅስቃሴው ላንካላ ሊሆን ይችላል። መረጃው ጥሩ በሆነ ልክ ደግሞ የተሻለ እንቅስቃሴ ሊያደርግ ይችላል። ኤኮኖሚስቶች የመረጃ ክፍተት (information asymmetry) የሚሉት ይሄንን ነው።

ተበዳሪው ስላበዳሪው መረጃ አለው፤ አበዳሪው ግን ስለተበዳሪው የሚፈለገውን ያህል መረጃ የለውም። ይህ ክፍተት በግንኙነታቸው መሃከል ችግር እንዲፈጠር ይጋብዛል። የችግሩ ዓይነት ይለያያል። አንዱ ጫፍ ተበድሮ ያለመክፈል ነው፤ ሌላው ጫፍ ከዚያ በመለስ በወቅቱ ያለመክፈል፣ በየጊዜው ጊዜ አራዝመልኝ ብሎ መጠየቅ፣ ይህንን የመሳሰሉት ናቸው። ይህ ዋነኛው ችግር ሲሆን ቅድም እንደጠቀስኩት ሌላው ችግር ባንኮች ዋስትና ሳይጠይቁ የማበደር ችሎታቸው ነው። ይህ በሕግ የተወሰነ ገደብ አይደለም። ስለተበዳሪው ምን ያህል መረጃ ቢኖራቸው ነው፣ ስለሚፈለገው ፕሮጀክት ምን ያህል መረጃ ቢኖራቸው ነው፣ በአዋጭነት ግምገማ (feasibility analysis) ላይ ብቻ ተመርኩዘው፣ ዋስትና ሳይጠይቁ ወይንም ደግሞ አነስተኛ ዋስትና ብቻ ተቀብለው ብድር መስጠት የሚችሉት? የሚሉት ጥያቄዎች ስንመለከት ችግሩ በእኛ ሁኔታ ከፍተኛ መሆኑን መገንዘብ እንችላለን።

በመሠረቱ አንድ ባንክ ባገሩ ላይ ስላለው የኢንዱስትሪ ሁኔታ በዝርዝር ሙሉ መረጃ ይነረው ማለት አይቻልም። የዚያ ዓይነት መረጃ ከተለያዩ ምንጮች ባንኩ ማግኘት መቻል ነበረበት። ከምርምር ደርጅቶች፣ መንግሥት ከሚያወጣቸው ጽሑፎች፣ የግሉ ዘርፍ በየሙያው ከሚያደርገው የማማከር አገልግሎት መረጃዎች፤ እነዚህ ሁሉ ሰፋ ያለ የመረጃ ምንጮች ቢኖር ኖሮ፣ አንድ ባንክ፣ ለምሳሌ፣ የጫማ ፋብሪካ፣ ማቋቋም እፈልጋለሁ ብሎ

ብር፡ የሚለይ አንበሴተር በመጣ፣ የገበያውን ሁኔታ በዝርዝር ባያውቀውም ከእነዚህ ምንጮች በቂ መረጃ ከያዘ የምትቀረው የፕሮጀክት ግምገማ ሥራ አነስተኛ ሁና በተገኘች ነው። ነገር ግን መረጃ የማግኘት ችግር ስላለበት፣ ስለገበያው ሁኔታ፣ ስለፕሮጀክት ገርዝዝር ሁኔታ፣ ስለሚፈለገው የቴክኖሎጂ ዓይነት፣ ይሸንን ሁሉ ባንኩ በገዛ እራሱ እንዲሠራ ስለሚገደድ፣ ለስህተት የሚዳርገት ሁኔታዎች ሰፊ ሆኖ ስለሚገኝ፣ ይመስለኛል ራሱን ከአደጋ ለመከላከል ሲባል አንድ ባንክ የዋስትናን ቅድመ ሁኔታ የሚያመጣው። እና ከእንደዚህ ዓይነት ሁኔታ በቀላሉ ለመውጣት እንችላለን ለማለት አደጋች ይመስለኛል። ይህ አስከሆነ ደረስም ባንኮች የሚፈለገውን ያህል በልማት ተሳትፎ ሊያደርጉ አይችሉም ማለት ነው።

ከዚህ ሁኔታ ጊዜ ለመቆጠብ፣ ጊዜዬ እየሄደብኝ ነው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ የባንኮች እንቅስቃሴ ምን ይመስላል? የሚለውን አጠር አድርጌ አያለሁ። አንዱ መመዘኛ ምን ያህል ወለድ ያበደራሉ ባንኮች በብለይ ከብበዳሪው? የሚለው ነው። ምክንያቱም የቁጠባ ገንዘብ ከመሰብሰብ ብሃሉ ዋነኛው የባንክ ብግባር እንቨስትመንት ማበረታታት ነውና። አንድ እንቨስተር ብድር ብበድሮ 30 በመቶ የወለድ ብመን ብሸክሞ ያብርፋል ለማለት አስቸጋሪ መሆኑን ከወዲሁ ይሸንን መናገር እንችላለን። የወለዱ ብመን ዝቅተኛ በሆነ መጠን ከባንክ ብበድር አትራፊ በሆነ መልክ ንግድ business ውስጥ መግባት ይቻላል ማለት ስለሆነ፣ የወለድ ብመናችን አትዮጵያ ውስጥ ምን ይመስላል? የሚለው ጠቃሚ (important) ጥያቄ ይመስለኛል። አሁን ያለው የማበደሪያ ምጣኔ ዝቅተኛው 7.5 በመቶ፣ ከፍተኛው እስከ 14 በመቶ ይደርሳል። ከፍተኛው ወለድ አልፎ አልፎ ይመስለኛል፤ በብለይ አቶ ለይኩን እዚህ ስለሚገኙ ሊነግሩን ይችላሉ፤ በግል ባንኮች አካባቢ ይመስለኛል የዚህ ዓይነት የወለድ ብመን ያለው። አማካኝ የወለድ ምጣኔ ብሎ ብሔራዊ ባንክ የሚያወጣው ጽሑፍ ወደ 10.5 በመቶ ነው። ከሌሎች አገሮች ጋር ሲብያይ ይሄ ምን ይመስላል? እንግዲህ አትዮጵያ ውስጥ ደህና እየሠራን ነው ወይስ አይደለም? የሚለውን ለመገንዘብ ራሳችንን ከሌሎች ጋር ማስብያየት ነው። ከአጎራባች አገሮች ጋር የእኛን ሁኔታ ብናስብያይ፣ ምናልባት አንድ አምሳ አገሮች አሉ አፍሪካ ውስጥ፤ ናሚቢያ፣ ደቡብ አፍሪካ፣ ግብጽ፣ ሌሎች ከሰሜን አፍሪካ ቱኒዚያ ሊጠቀሱ ይችሉ ይሆናል። ስድስት፣ ሰባት አገሮች ሊሆኑ ይችላሉ ወደ 10 በመቶ አካባቢ የብድር ወለድ ብመን ያሳዩው። ገረቤት አገሮች እንደ ኬኒያ አይነት 20 በመቶና ከዚያ በላይ የሚሆን ይመስለኛል፤ አንዳንድ ጊዜም 30 እና 40 በመቶም ይያርሳል። ስለዚህ ከወለድ ብመን አካያ ስናየው የኢትዮጵያ ፋይናንስ ዘርፍ ጤነኛ ዘርፍ ነው ማለት እንችላለን። ጥሩ ሁኔታ ላይ አለን ማለት ነው።

ሁለተኛ መመዘኛ በቁጠባ ብቀማጭ ሂሳብ ወለድና በማበደሪያ ወለድ መካከል ያለው ልዩነት (spread) ነው። እዚህም ላይ ኢትዮጵያ ውስጥ አሁን ያለው በአብዛኛው እስከ 6 በመቶ ብቻ የሚሆን ይመስለኛል። የማስቀመጫ ወለድ አነስተኛው ሦስት በመቶ ነው። አብዛኛው የማበደሪያ ወለድ አማካኝ 10.5 በመቶ እንካ ወስደን በሁለቱ መካከል ያለውን ልዩነት ብናሰላ 7.5 መቶ ነው። ይህ እጅግ ከፍተኛ ነው (exorbitant) የሚባል አይደለም። ለማነፃፀር

ያህል፤ በዳበሩ አገሮች የሁለቱ ልዩነት (spread) 3 እና 4 በመቶ ሊሆን ይችላል። የማበደሪያ ወለድ (lending rate) እንደ ዋጋ ንረቱ (inflation) ይለያያል፣ ግን 5፣ 6፣ 7 በመቶ ነው። የእኛው አገር ከእነዚህ ጋር ሊነጻጸር ይኸን ያህል ያልተለመደ የወለድ ተመን ነው። አልወሰድም። ስለዚህ በአጠቃላይ ከወለድ ተመን አንጻር ስናየው ደህና ይመስለኛል።

ሌላው መመዘኛ አድርገን መውሰድ የምንችለው የተበላሸ ብድሮች Non Performing Loans (NPLS) ናቸው። በአማርኛ ሲተረጎሙ ምልባት በአግባቡ የብድር ገንዘብ የማይመለሱባቸው ወይም በሽተኛ ብድሮች ማለት ይቻላል። በባዝል (Basil) ስምምነት ተቀባይነት አለው ተብሎ የሚወሰደው የማይመለስ ብድር ምጣኔ ከ10 በመቶ በታች መሆን አለበት ይላል። ምናልባት ላላደጉ አገሮች እስከ 15 በመቶ ይፈቀዳል ካልን፣ ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው እጅግ በጣም ከፍተኛ ነው፤ መጥፎ ሁኔታ ነው ማለት ይቻላል። ዛሬ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ አካባቢ፣ ምናልባት የግል ባንኮች አንዳንዶቹ ሻል ያለ ውጤት አላቸው፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ግን፣ ትልቁ ባንክ፣ ወደ 33 በመቶ ነው፤ ይህ ጥሩ አይደለም። ከጠቅላላው ያልተመለሱ ብድሮች (outstanding loans) 33 በመቶው በሽተኛ ናቸው ማለት ነው። ይህ ዝቅ ማለት አለበት፤ አሁንም እየቀነሱ መጥተዋል፤ ወደፊት በስፋት ይቀንሳሉ ብለን ተስፋ እናደርጋለን። አንዳንዶች የግል ባንኮች ሻል ያለ ውጤት ያላቸው አሉ። ምናልባት በውይይት ወቅት ሊነሳና ገለጻ ሊደረግባቸው ይችላል።

ሌላው ስለዘርፉ ስንነጋገር ማየት የምንችለው ምን ያህል ውድድር (competition) አለ? የሚለውን ነው። ይኸ ብዙ ጊዜ የሚነሳ ጥያቄ ነው። በእርግጥ የግል ባንኮች በገበያው መሳተፍ ከጀመሩ በጣም አጭር ጊዜ ነው። አዋሽ ባንክ ነው የመጀመሪያው፤ እሱም የ10 ጊዜ ትልቅ ተወዳዳሪ ይሆናሉ ብሎ ማለት አስቸጋሪ ነው። ግን የ1996 የሰኔ ወር የሥራ ውጤት ልጠቅስላችሁ እፈልጋለሁ። የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ባንድ በኩል፣ የግል ባንኮች በሌላ በኩል፣ ሆነው ከተቀማጭ ገንዘብ/ሂሳብ አንፃር ሲታይ የግል ባንኮች 22.1 በመቶ ሲይዙ የንግድ ባንክ 73.6 በመቶ ነበር የያዘው። ቀሪው 5.3 በመቶ የሌሎች የልማት ባንክ እና የሲቪክ ማህበረሰብ ተቀማጭ ነው። ስለዚህ ከተቀማጭ ገንዘብ አንፃር ሲታይ የግል ባንኮች ዝቅተኛ ቦታ ነው ያላቸው።

ይሁንና ከብድር አኳያ ስናይ ሁኔታው ለየት ያለ ነው። ጠቅላላ ብድርና ያልተሰበሰበ ብድር (outstanding loans) ነው አሁን የምንናገረው። አሁንም የሰኔ 1996 ዓ.ም. ሪፖርት ስንመለከት ያርሻቸው ምን ነበር? 23.8 በመቶ የግል ባንክ፣ 76.8 የንግድ ባንክ። ይህ አጠቃላይ ብድር ነው። ከዚህ ውስጥ የመንግስትን ብድር ብናወጣ፣ ምክንያቱም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ለመንግስት ብዙ ያበድራልና፤ ማለትም ለመንግስት የተሰጠውን አግልለን ብናይ፣ የግል ባንኮች ድርሻ ወደ 40.1 በመቶ ከፍ ይላል፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ድርሻ ወደ 59.9 በመቶ ዝቅ ይላል። እንደገና ደግሞ ቀጥታ ከመንግስትም ብድር ውጭ የመንግስት ድርጅቶችን ብድር ወደ ጎን ብንተው፣ ማህበራትንም እንዲሁ ወደ ጎን ብናድርግ (እነርሱ

ሂሳብ ላይ በመሆናቸው ነው እንጂ በጣም አነስተኞች ናቸው)፣ የግሉን ከፍለ ኢኮኖሚ እ.ኤ.አ. ብድር ብቻ ብንወስድ ድርሻቸው ምን ይሆናል? የግል ባንኮች 50.2 በመቶ ሲሆን የመንግስት ባንክ 49.8 በመቶ ነው። በእኔ ግምት 10 ዓመት ለተካሄደ ጉዞ ይኸ በሚበቃ ሁኔታ ውድድር ያለበት ገበያ ነው ብሎ መናገር ያስደፍራል።

ከዚህ በዘለለ ጉዳይ ላይ የውጭ ሰዎች ይተቹናል። የአንድ ባንክ ሥርዓት (Mono- bank system) ነው ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው፤ አንድ ባንክ ሌሎችን በበላይነት የሚመራበት ሁኔታ ነው፤ ይሉናል። አንድ ባንክ ከሌሎች በጣም ልቆ በሚገኝበት ሁኔታ ጤናማ የሆነ የፋይናንስ ዘርፍ ለኖር አይችልም ይላሉ። ወደ ገርገር ስንገባ ግን ሁኔታው ለየት ያለ ነው። እዚህ አልጠቀስኩም እጂ ጠቅላላ ያልተሰበሰበ ብድር ስንል በተወሰነ ጊዜ ላይ የተከማቸ ብድር (stock) ማለታችን ነው፤ የዛሬ ሦስት ዓመት ወይም አራት ዓመት የተሰጠም ቢሆን። በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ (flow) ምን ያህል ብድር ይሰጣል? የሚለውን ብናይ በማያጠራጥር ሁኔታ ከ50 በመቶ በላይ የሚበልጠውን ድርሻ የያዙት የግል ባንኮች ናቸው። ስለዚህ መንገዱን ወይም በውጤት (performance) አነጋገር ዘርፉ ምን ዓይነት አቋም አለው ብለን ስናይ ከላይ ብልሽ የሆኑ ብድሮች ባይኖሩ ኖሮ ጤናማ ዘርፍ ብለን በወለድነው ነበር።

የመሸጉ ብድሮች መኖር፣ ያውም ደግሞ በዚህ ከፍተኛ ደረጃ መኖር፣ ግን ሙሉ በሙሉ ጤናማ ዘርፍ ነው ለማለት አያስችለንም። ቅድም እንደጠቀስኩት ደግሞ ይህ ምንን ነው የሚያመለክተው? በተበዳሪና በአበዳሪ መካከል ያለው ግንኙነት ጥሩ ያለመሆን ነው። ወደ ኋላ፣ ኋላ፣ ብንሄድ እንደ አፈ ታሪክ ተወስዶ የሚነገርለት "ተበዳሪ ይሞታል፣ ወይም አበዳሪ ይሞታል" ይባላል። ከዚያም በመለስ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ "ተበድሮ አለመክፈል ምን ያመጣል? ግፋ ቢል ፍርድ ቤት ነው፤ ፍርድ ቤት ተኬዶ 10 ዓመት፤ 15 ዓመት ይወስዳል፤" እየተባለ ይነገር ነበር። አሁን አበዳሪው ባንክ በዋስትና የያዘውን ንብረት መሸጥ በመቻሉ ችግሩ እየቀለለ መጥቶአል። ይህ የባንክ ጉዳይ ብቻ አይደለም። በአንድ ህብረተሰብ ውስጥ ያለ የመተማመን ግንኙነት ምን ያህል ዳብሯል? የሚለውን የሚያመለክት ነው። በሂደት እየተስተካከለ እንደሚሄድ እመን ይመስለኛል።

በመጨረሻ ላይ ሁላችሁም ምናልባት እንዲነሳ የምትፈልጉት ርዕስ ይኖራል እና እርሱን አንስቼ ልጨርስ። የገንዘብ ገበያው ነፃ ነው ወይስ ቁጥጥር ያለበት? ይህንን ጥያቄ ቅድም ወልዳይ ሲያነሳው ነበር፤ ሊበራላይዜሽን ማለቴ ነው። ይኸንን ገበያ ለፋ አድርገን ብናየው! ሁለት ገበያ ነው። በአንድ በኩል የፋይናንስ ገበያ (financial market) የሚባለው አለ፤ በሌላ በኩል የውጭ ምንዛሪ ገበያ የሚባል አለ።

የፋይናንስ ገበያ የሚወለነው በወለድ ተመን ነው። ይህ ገበያ ሁለት ፊት (ገጽታ) አለው። አንደኛው የብድር ገበያ (credit market) የሚሉት ነው። ባንኮች ማበደር የሚችሉት የገንዘብ አቅርቦት አላቸው። መበደር የሚፈልጉ ሰዎች ደግሞ አሉ። በእነዚህ መሀከል

እንደማንኛውም ገበያ በፍላጉትና በአቅርቦት መካከል ያለው ግንኙነት የወለዱን ተመን ይወስነዋል። አንዱ ገጽታው ይኸ ነው።

ከዚህ ጋር አብሮ የሚሄድ ሌላው ገበያ የገንዘብ ገበያ ነው፤ አጠቃላይ የገንዘብ አቅርቦት አለ፣ አጠቃላይ የገንዘብ ፍላጎት አለ። ይህ የሚመራው በማዕከላዊ ባንክ (central bank) ነው። በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምን ያህል ይመራል/አይመራም፣ ጎላ ልንነጋገር እንችላለን። ስለዚህ በፋይናንስ ገበያ ላያ ያለው የወለድ ተመን የሁለቱ ገበያዎች ጣምራ ውጤት ነው። የብድር ገበያ ብቻ አይደለም፤ የማዕከላዊው ባንክ ገንዘብ የመርጨት እና ገንዘብ ከሕገወጥ የመሰብሰብ (የመሳብ) ኃይል አለው። እንደ የሁኔታው ደግሞ ይኸን ያስተካክላል። በዚህ ላይ የሚያደርገው ቅኝት በገንዘብ አቅርቦት ላይ የወለድን መጠን ይወስናል። እነዚህን ሁለት ገበያዎች ይዘን ነው እንግዲህ ነፃ ገበያ ብለን መነጋገር የምንችለው።

በሌላ በኩል የውጭ ምንዛሬ ገበያ አለ። የውጭ ምንዛሪ ገበያ እንደዚሁ ሁለት ገጽታ አለው። መለስ ልበልና የውጭ ምንዛሪ ለምን ያስፈልጋል? የሚለውን ላንሳ። የውጭ ምንዛሪ የምንፈልገው ከውጭ ዕቃ ለመግዛት ነው፤ ከውጭ አገልግሎት ለመግዛት ነው። አገልግሎት ማለት ውጭ አገር ልጅን ልኬ ለማስተማር ብፈልግ ለትምህርት የምከፍለው ነው፤ ውጭ አገር ሄጄ መታከም ብፈልግ ለህክምና የምፈልገው የውጭ ገንዘብ ነው፤ ገንዘብ ያለው ሰው ከሆንኩ ደግሞ ውጭ አገር ሄጄ መዝናናት ከፈለግሁኝ ለቱሪዝም የሚከፈለው የውጭ ገንዘብ ነው፤ ይኸንን የመሳለት ናቸው አገልግሎቶች። ስለዚህ የውጭ ምንዛሪ ገበያ ከዕቃ ወይም ከአገልግሎት ግዢ እና ከሽያጭ ጋር የተያያዘ ገበያ ማለት ነው።

አንድ ሰው ብር ይዞ ወደ ባንክ ይኼዳል እንበል። ይኸን፣ ይኸን፣ ማድረግ እፈልጋለሁ ይላል። የውጭ ምንዛሪ፣ ለምሳሌ፤ ዶላር ወይም ዩሮ ወይም ሌላ ሰጠኝ ይላል። ባንኩ ያለውን ይሰጠዋል። በአቅርቦትና በፍላጎት መሃል፣ አሁንም እንደማንኛውም ገበያ፣ ያለመጣጣም ካለ የውጭ ምንዛሬ ተመኑ ይለዋወጣል። ዛሬ የአንድ ዶላር ዋጋ 8.60 ወይም 8.70 መሆኑ ቀርቶ ዘጠኝ ብር ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነቱ አንዱ ገበያ ነው።

ሌላው የውጭ ምንዛሪ የሚፈለግበት ምክንያት አለ ወይ? ቢባል መልሱ አሁንም ቢሆን አዎን ነው። ምንድን ነው ሁለተኛው የውጭ ምንዛሪ የሚፈለግበት ምክንያት? በውጭ ምንዛሬ ገንዘብ መያዝ እና በውጭ አገር ቋሚ ንብረት ለመግዛት ከተፈለገ የውጭ ምንዛሪ ይፈለጋል። ብር መያዝ ትቼ ዶላር መያዝ እፈልጋለሁ። ስለዚህ ዶላር መግዛት እንድችል ገበያው ይነር፣ ይፈቀድልኝ፣ ማለት ነው። ልዩነት የለውም፤ ዶላሩን እዚህ አገር ወይም አሜሪካን አገር ባስቀምጥ፣ እዚህና ውጭ አገር ተቀመጠ ያው ነው! ገንዘብ ከአገር ውጭ ሲቀመጥ ካፒታል ከዚህ ወደ ሌላ ሸሸ ማለት ነው። የካፒታል መሸሽና አለመሸሽ ጥያቄ ነው እንጂ የውጭ ምንዛሬ ገበያ ጥያቄ አይደለም። በመሠረቱ በምን መልክ ነው ሀብቱን መያዝ የሚፈልገው ይኸ ሰው? በአገር ገንዘብ ወይስ በውጭ ገንዘብ? በምን መልኩ ነው ይኸንን ሀብት መያዝ የሚፈልገው? በንብረት ወይስ በጥሬ ገንዘብ? አገር ውስጥ ባለ ንብረት ወይስ

ውጭ አገር ባለ? አገር ውስጥ ባለ ገንዘብ ወይስ በውጭ ገንዘብ? እነዚህን አይተን ነው የመጨረሻ ዝቅተኛ ነጥ ያሁን ወይስ አይሁን ብለን መዳኘት የሚኖርብን። ጊዜው እየጠበበ ሄዶ ጠንካራ ማጠቃለያ አሄዳለሁ።

ስለዚህ፣ የኢትዮጵያ የውጭ ምንዛሬ ገበያ ምን ይመስላል? ስንል፣ በፋይናንስና በውጭ ምንዛሬ አነባበቡ እንደጠቀስኩት በከፊል የተከፈተ፣ በከፊል ግን ቁጥጥር ያለበት ሥርዓት ነው ማለት ይቻላል።

የቀረችውን ጊዜ የርዕይ 2020 ኢትዮጵያ ምኞቴን በመግለጽ እንድጠቀምበት፣ ፍቀዱልኝ።

የሚኒስትሩን ጥያቄዎች ብዙውን ላልመልስ እችላለሁ። 2020 ኢትዮጵያ ምን ዓለም ውስጥ ትኖራለች? የሚለውን ማለቴ ነው። 2020 ኢትዮጵያ የምትኖርበት ዓለም ግሎባላይዝድ ነው። ይኸ ነው፣ ትልቅ መሳኝ ጉዳይ። ይህ ማለት ዛሬ ያላት አንዳንድ ገደብ ይነሳል። ዓለም ነው። ያንን ለማድረግ አንስት የምታደግ ኤኮኖሚ ሆና መንቀሳቀስ ትችላለች ወይ(ነው ጥያቄው የሚሆነው። ገደቡን ለማንሳት እኔ እንደሚመስለኝ ሁለት መሠረታዊ (fundamental) ጉዳዮች ማሟላት ያናርባታል ይህች አገር። የምሥራቅ ኤሲያም ልምድ ይኸንን ነው የሚያሳየው። አንደኛ፤ በወጪ ንግድ የሚመራ ዕድገት መኖር አለበት። ይህ ማለት ምን ማለት ነው? ይኸ ኤኮኖሚ ከሌሎች ኤኮኖሚዎች ጋር ተፎካክሮ አሸንፎ ዕቃ ወደ ውጭ ገበያ ልኮ መሸጥ መቻል አለበት። ይኸንን ለማድረግ ብዙ ቅድመ ሁኔታዎች (pre-requisites) አሉት። መድረሻው ግን ይኸ መሆን አለበት። ይኸ ሲሆን የፋይናንስ ነፃ ገበያ ያቻላል። አንደኛ፤ ይኸ ነው።

ሁለተኛው፣ እዚያ ደረጃ ለመድረስ መልካም አስተዳደር፣ ግልጽ የሆነ ተጠያቂነት ያለበት አስተዳደር፣ የማስፈጸምና የመፈጸም ብቃት (enforcement and compliance) ያለበት ሀገር መፍጠር አለብን። አለበለዚያ የወጪ-ንግድ-መር ዕድገትም ቢኖር፣ የውጭ ምንዛሪም ኖሮን፣ የፋይናንስ ገቢያውንም ለቀቅ አድርገን መንቀሳቀስ ብንችልም፣ በመሰናክል፣ በገቦ፣ በተጭበረበረ አሰራር፣ ኤኮኖሚው ይገዘገዛል። መሉ በመሉ ላላደገ አገር ደግሞ አይሆንም ይኸ። ስለዚህ የተከለ ሥርዓት የተመቻ ሆኖ፣ ቅድም አቶ ሌይኩን እንዳነሱት፣ የታክስ ምጣኔ ሌላ ጉዳይ

ነው፣ ኢትዮጵያ ውስጥ እኮ የታክስ ምጣኔው 10 በመቶ ቢባል እንኳE ላጭበርብር የሚል ሞልቷል። ስለዚህ የታክስ ምጣኔው ብቻ አይደለም ጥያቄው፤ ደንብን ያለማክበር፣ ያለመከተል (non-compliance) ችግር አለ በታክስ ላይ፣ በባንክ ላይ፣ በአስተዳደር ላይ፣ ካርታ ተሰጥቶን ቤት የምንሠራ ከሆነ ትንሽ ሴንቲሜትር ሰረቅ በማድረግ ላይ፣ በሁሉም ላይ አለ፣ በንግድ ልውውጥ (transaction) ጭምር። ገበያ ውስጥ የሚሠሩ ነጋዴዎች አንዱ ሌላው ላይ ምን እንደሚያደርግ ያውቁታል። ከእንደዚህ ዓይነት ሥርዓት ወጥተን፣ ከውጭ አገር ጋር ደግሞ ተፎካካሪ ሆነን፣ በዚያን ዘመን መኖር የምንችል ኤኮኖሚ መፈጠር አለበት በ2020 ኢትዮጵያ። ለእኔ ይኸ ነው ትልቁ ፈተና (challenge)።

ገንዘብ እና ልማት በኢትዮጵያ

ለይኩን ብርሃኑ*

መግቢያ

ለልማት አስፈላጊ የሆኑ በርካታ ጉዳዮች ወይም ግብአቶች ስለመኖራቸው ለዚህ ጉባኤ ማብራራት አስፈላጊ አይደለም:: ልማት የብዙ ግብአቶች የተባበረና የተቀነባበረ እንቅስቃሴ ውጤት መሆኑ የታወቀ ነው::

አሁን ባለንበት ዓለም አለገንዘብ ትርጉም ያለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ማሰብ አይቻልም::

ገንዘብ የኢኮኖሚ ደም ነው ማለት የሚቻል ይመስለኛል:: አለደም እና ጤናማ ሥርጭቱ ስለጤናማ የሰው አካላትና ስለጤናማ ሰው ማሰብ እንደሚያስቸግር ሁሉ አለገንዘብና ጤናማ ሥርጭቱ ስለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሕይወት፣ ስለድህነት ቅነሳና ስለብልጽግና ማሰብ እጅግ አስቸጋሪ ነው:: ከዚህ አንጻር ገንዘብ ቁልፍ የልማት መሳሪያ ነው ማለት ይቻላል::

ይህ ሲባል ግን ገንዘብ ልማትን የማምጣት መለኮታዊ ኃይል እንደሌለው መገንዘብ አስፈላጊ ነው:: ከሀይማኖት አንጻር ሲታይ የሰው ደም ፈጣሪና የተግባር አዛዥ መለኮታዊ ኃይል ያለው ፈጣሪ ራሱ ነው:: በመሆኑም የሰው ደም በመላው የሰው አካል አንዱንም ሳያስቀር የሚያስስ፣ ጉዞውን ለአንድ አፍታም ሳያቋርጥ ቀንና ሌሊት ለዓመታት የሚጓዝ የፈጣሪ ትዕዛዝ አክባሪ ነው፣ ሰው ራሱ በራሱ ድርጊት በጉዞው ላይ መሰናክል ካልፈጠረበት በስተቀር::

ገንዘብ የሚፈጠረውና የሚሰራጨው በመለኮታዊ ኃይል ሳይሆን በሰው ስለሆነ፣ በአፈጣጠሩና፣ በሥርጭቱ እንከን ስለማያጣ በልማት ላይ የሚጫወተው ሚና ከክቡር የሰው ደም ሚና ጋር ይመሳሰል ለማለት እንጂ አንድ ዓይነት እንዳልሆነ ግልጽ ነው:: የሰው ሥራ እንከን አልባ ባይሆንም፣ ሰው እንከኖችን የማስወገድ ችሎታ ያለው ነው:: በዚህም በርካታ አገሮች የልማት ደም የሆነውን ገንዘብ ከሞላ ጎደል ለልማትና ዕድገት ቁልፍ መሣሪያነት በብቃት እየተገለገሉበት፣ ከድህነት ማጥ ወደ ብልጽግና መሸጋገራቸውን ስናይ ሁኔታው ገንዘብን ለልማት መሣሪያነት በብቃት ለመጠቀም የሚፈልጉ ደሀ አገሮችን ሁሉ የሚያበረታታ ነው::

---

*አቶ ለይኩን ብርሃኑ በሚከተሉት የተለያዩ ከፍተኛ ኃላፊነት አገልግለዋል:: እ.ኤ.አ. ከ1996 ዓ.ም እስከ ዛሬ ድረስ የአዋሽ ኢንተርናሽናል ባንክ ፕሬዚዳንት፣ ከ1991 እስከ 1995 ዓ.ም የብሔራዊ ባንክ ገ/ር፣ ከ1989 እስከ 1991 ዓ.ም እና ከ1983 እስከ 1986 ዓ.ም የኢትዮጵያ ሥራ አመራር ኢንስቲትዩት ዳይሬክተር፣ ከ1986 እስከ 1989 ዓ.ም በጠቅላይ ሚኒስትር ቢሮ የትራንስፖርትና ኮሚዩኒኬሽን ሴክተር ኃላፊ፣ ከ1980 እስከ 1983 ዓ.ም የእርሻ ሰብል ገበያ ድርጅት ም/ዋና ሥራ አስኪያጅ እና ከ1978 እስከ 1980 የንግድ ባንክ ዋና ሥራ አስኪያጅ ሆነው ያገለገሉ ሲሆን ከዚህ ጊዜ ውስጥ ለአንድ ዓመት ያህል የብሔራዊ ባንክ ተቆጣጣሪ ሆነው ሰርተዋል:: አቶ ለይኩን ብርሃኑ እ.አ.አ ከ2001 ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የኢትዮጵያ ባንኮች ማህበር ሊቀመንበርም ናቸው::

በአገራችንም ይህ ቁልፍ መሣሪያ ለአገራችን ልማት የሚያደርገው አስተዋጽኦ ይበልጥ እየጐለበተ የሚሄድበትን ሁኔታዎች ማጠናከሩ አስፈላጊ ነው።

ገንዘብና ልማት የተቆራኙ ናቸው። ገንዘብ ልማትን ለማምጣት ቁልፍ ሚና ይጫወታል። ገንዘብ በኢኮኖሚው ውስጥ ላሉ የተለያዩ ኃይሎች ማለትም ለባለንብረቶች፣ ለኅብረተሰቦች፣ ለአምራቾችና ለሸማቾች የመገናኛ ድልድይ ሆኖ በማገልገል የማምጣት ኃይል አለው። ልማት ደግሞ ለሌላ ልማት የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን ይጨምራል። በዚህም የገንዘብና ልማት ቁርኝት በማያቋርጥ የመደጋገፍ ሂደት እንደ ለለላው ምንጭ እና ደጋፊ ነው ማለት ይቻላል። ይህ የሚሆነው ግን የልማት እንቅስቃሴ ተሳታፊዎች ሁሉ የሚጠበቅባቸውን ሚና በብቃት ሲወጡ ብቻ ነው።

ማናቸውም ቁልፍ መሣሪያ በአጠቃቀም ችሎታና ብቃት ካልታገዘ የመሣሪያው መኖር ብቻ ፋይዳ የለውም። በአጠቃቀም ብቃት ማነስ መሣሪያው ከሚያስገኘው ጥቅም ይልቅ ጉዳት ሊያመጣን ይችላል። ስለዚህም ገንዘብ ለልማት ቁልፍ መሣሪያ ነው ሲባል የአጠቃቀሙን ብቃትና ብቁነትና ታሳቢ በማድረግ ነው።

ለምሳሌ ያህል ከኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር ባልተገናዘበ መልኩ ገንዘብ እየታተመ ቢበተን፣ ገንዘብ ልማትን የሚያመጣ ቁልፍ መሣሪያ መሆኑ ይቀርና ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የዋጋ ንረትን በማስከተል ገንዘብ ዋጋ ያጣል። በዚህም ገንዘብ የቆጠቡ ዜጐች ሁሉ ለከፋ ድህነት የሚዳረጉበት ሁኔታም ይከሰታል። ገንዘብ የዚህ ዓይነቱን አስከፊ ጥፋት እንዳያደርስ ግን መንግሥታት ሁሉ ተገቢ ጥንቃቄ ያደርጋሉ፣ ማድረግም አለባቸው።

ከዚህ በላይ ለግንባቤ እንዲረዳን ለመግለጽ የተሞከረው በአጠቃላይ ገንዘብ ለልማት ያለውን አስተዋጽኦ እና በአጠቃቀሙ ላይ መወሰድ ስላለበት ጥንቃቄ ሲሆን፤ በሚቀጥለው ክፍል አገራችንን ካለችበት ኋላቀር የኤኮኖሚና ማህበራዊ ሁኔታ ለማውጣት በገንዘብ አሰባሰብና አጠቃቀም ዙሪያ ትኩረት በሚሹ ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ ለመስጠት እሞክራለሁ።

2. የአገራችን የገንዘብ አሰባሰብ፣ አጠቃቀምና ስርጭትን ለማሻሻል መከናወን ያለባቸው ሁኔታዎች

አገራችንን ለማልማት ለዘመናት ልዩ ልዩ ጥረቶች የተደረጉ መሆኑ የማይካድ ቢሆንም፣ አገራችን ዛሬም ከመጨረሻዎቹ ኋላ ቀር ታዳጊ አገሮች ጐራ ሆና ከድህነት ማጥ ለመውጣት የምትጥር አገር ነች። ስለሆነም፣ ገንዘብም ሆነ ሌሎች የልማት መሣሪያዎች ሁሉ እስከ ዛሬ ተባብረው ከድህነት እንድትወጣና የለማችና የበለፀገች አገር እንድትሆን ሊያደርጓት አልቻሉም። ሁለ ይህ ነው። ይህ ገሀድ ሀቅ ከመሆኑም በላይ ብዙ ማብራሪያና የኋላ ቀርነት መግለጫ የሆኑትን የድህነት መለኪያ ስታትስቲካዊ መረጃዎችን ማቅረብ የሚቻል ቢሆንም፤ ለግንባቤ እንዲረዳ የሚከተሉትን መጥቀሱ አግባብ ይመስለኛል።

አገራችን ኢትዮጵያ መሠረታዊ የሰፈነባት፣ ንፁህ የመጠጥ ውሀ በስፋት ለሕዝቦችዋ ያልተዳረሰባት፣ ዘመናዊ የጤና አገልግሎት ያልተስፋፋባት፣ እጅግ በጣም ብዙው ሕዝቧ መንገድ አርቆ የሚኖሩባት፣ ከቂያቸው ወጥተው የሌላውን ሕዝብ አኗኗር ያላዩ፣ ዘመናዊ የትራንስፖርት አውታር ያላገናዘበ እና በዓለም እጅግ ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ እርከን ላይ የምንገኝ ሕዝብ የምንኖርባት አገር ነች:: እነዚህን አስከፊ ሁኔታዎች ለመግለፅ የተገደድኩት ምንኛ ሰፊ ሥራ እንደሚጠብቀንና ሁኔታዎቹን ለመለወጥ ገንዘብ አንዱ ዋነኛ መሣሪያ መሆኑን ለማመልከት ነው::

ለዚህ አላባኛ ሁኔታ መፈጠር በርካታ ምክንያቶችን መደርደር ይቻላል፡ ለደህንነት ተጠያቂ ማነው ብሎ መጠየቅም ይቻላል:: የኢኮኖሚያችንን ያለፉ ታሪኮች የሚተነትኑ በርካታ ጥናቶች አሉ:: ታሪክ፣ በአጠቃላይ የኢኮኖሚ ታሪክ ጭምር፣ ያለፈ ጉዳይ ነው:: በጉ ትምህርት የሚሰጥ ከሆነ ያን ትምህርት መስደ ወደፊት መጓዝ ነው ዋናው ቁም ነገር:: ስለሆነም፣ የትናንትናችን አቅጣጫ አሁን ካለንበት ኋላ ቀር የልማት ደረጃ አገራችን መጥቃ እንድትወጣ ዛሬና ወደፊት ምን ማድረግ አለብን፡ በሚለው ጥያቄ ላይ ቢሆን የሚሻል ይመስለኛል:: ይህን አቅጣጫ በመከተል ገንዘብ ለአገራችን ልማት መጫወት የሚገባውን ቁልፍ ሚና እንዲጫወት፣ የአገራችን የገንዘብ ምንጮች፣ የገንዘብ ሥርጭት እና የአጠቃቀም ብቃት እንዲጎለብቱ፡ ምን ቢደረግ ይሻላል? በሚለው ጥያቄ ላይ በማተኮር አንዳንድ ነጥቦችን ማንሳት እፈልጋለሁ::

2.1 የገንዘብን ክምችት መፍጠርና ማዳበር

ገንዘብ ቁልፍ የልማት ኃይል ሰጭ መሣሪያ ሊሆን የሚችለው ሲሰባሰብ ወይም ሲከማች ነው:: ገንዘብን ማሰባሰብ ማለት ለልማት የሚሆን ስንቅ መሰነቅ ማለት ነው::

ትንንሽ የውሀ ምንጮች በተፈጥሮአዊ ቅንብር ወይም በሰው ሠራሽ ዘዴዎች ሲጠራቀሙ የኤሌክትሪክ ኃይል ምንጭ ይሆናሉ፣ በረሃን በመሰኖ ያለማሉ:: ምንጮች በተናጠል ከሚሰጡት ጥቅም ይልቅ ሲጠራቀሙ የሚሰጡት ጥቅም እጅግ የጐላ ነው:: ገንዘብም ሲከማች ልማትን የማምጣት ግርማ ሞገስ ይላበሳል::

ለዚህም የባህላዊ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ተቋማትን እና ዘመናዊ የገንዘብ ማሰባሰቢያ ተቋማትን ይበልጥ ማስፋፋትና ማጠናከር ያስፈልጋል:: የገንዘብ ማሰባሰቢያ ተቋማት በሚገባ በስፋት የሚደራጁበትን ሁኔታ ማመቻቸት ማለት ለእህል ምርት አስቀድሞ እንደምርቱ መጠን የሚያስፈልገውን ማዳበሪያ መጋዘን እንደማዘጋጀት፣ ወይም የኤሌክትሪክ ኃይል ለማመንጨት ወይም ውሀን ለመስኖ እርሻ ለማዋል ግድብ እንደመሥራት የሚቆጠር ነው:: ስለዚህ የሚከተሉትን አቅጣጫዎች ተከትሎ መንዝ አስፈላጊ ይመስለኛል::

በአገራችን እ.ኤ.አ. ማርች 31 2005 ያለ መረጃ እንደሚያሳየው ያሉት የባንክ ቅርንጫፎች ብዛት 379 ነው:: ከዚህ አህዝ ውስጥ 147 ቅርንጫፎች ባለፉት 10 ዓመታት ውስጥ በተቋቋሙ የግል ባንኮች የተጨመሩ ናቸው:: እነዚህ ታዳጊ ባንኮች ከጠቅላላ የባንክ ቅርንጫፎች ብዛት 39% ያህል ድርሻ በመያዝ ለኢኮኖሚያችን አስተዋጽኦ አድርገዋል::

ገንዘብን እንማስባስብ አንጻር አነስተኛ ብድር የሚሰጡ የገንዘብ ተቋማት እና የብድርና ቁጠባ ማህበራትም የበኩላቸውን አስተዋጽኦ በማድረግ ላይ ናቸው። ይሁን እንጅ ከአገራችን የሕዝቧ ብዛትና የቆዳ ስፋት አኳያ ያሉት የባንክ ቅርንጫፎች ብዛት በጣም አነስተኛ ነው። ስለዚህ ያሉት ባንኮችና ልዩ ልዩ የገንዘብ ተቋማት ይበልጥ የሚስፋፉበትንና የሚጠናከሩበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ያስፈልጋል። ለምሳሌ፤ ያህል እ.ኤ.አ. በ31/12/2004 ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ሩብ ዓመታዊ ሪፖርት በተገኘው መረጃ መሠረት በኢትዮጵያ ውስጥ ባሉት ባንኮች እጅ ተሰባስቦ የሚገኝ ጠቅላላ ተቀማጭ ገንዘብ 34.6 ቢሊዮን ብር ነበር። የግል ባንኮች ያሰባሰቡት ብር 8.3 ቢሊዮን ወይም 24 በመቶ ያህሉን ነው። በአገራችን ከባንክ ውጭ በርካታ ገንዘብ ይዘዋወራል። ይህ ከባንኮች ውጭ የሚዘዋወረው ገንዘብ በባንክ ተቋማት እጅ ከሚገኘው ገንዘብ ጋር እየተዳበለ ቢሄድ በባንኮች አማካኝነት ለልማት ሊውል የሚችለው ገንዘብ ይዳብራል። ይህን ለማድረግ ደግሞ የገንዘብ ተቋማትን ማስፋፋት ይጠ ይቃል።

ሌላ ዋና የገንዘብ ማሰባሰቢያ አካላት የመድን ተቋማት ናቸው። እነርሱም የሚጠናከሩበትንና የሚስፋፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል።

ለአገራችን ልማት አስፈላጊ የሆኑ፣ ነገር ግን አሁን የሌሉ የገንዘብ ተቋማት፣ ወደፊት ስለሚፈጠሩበትና ስለሚስፋፉበት ሁኔታ አጥንቶ ተግባራዊ ማድረግና ወደ ሥራ መስኩ የሚገቡትን ባለሀብቶች ማበረታታትና ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው ማድረግ ያስፈልጋል። ለምሳሌ፤ የቬንቸር ካፒታል ተቋማት፣ የኢንቨስትመንት ባንኮች፣ የሞርትጌጅ ኩባንያዎች፣ የአክሲዮን ገበያ፣ ወ.ዘ.ተ.፣ ለልማት የገንዘብ ኃይል በመፍጠር ረገድ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ፣ ግን በአገራችን የሌሉ፣ የገንዘብ ተቋማት ናቸው።

«አንድ ዓመት ጐመን መብላት ጠልቶ ዕድሜ ልኩን ጐመን ሲበላ ይኖራል» የሚል አባባል አለ። አባባሉ የቁጠባን አስፈላጊነት የሚያመለክት ነው። የማይቆጥብ ሰው እኩ ከድህነት ሊወጣ አይችልም፡ አነስተኛ ገቢ ያላቸው ድሆች ሁሉ መቆጠብ እንደሚችሉ ደግሞ በብዙ ጥናቶች በማያሻማ መልኩ የተረጋገጠ ነው። በመሆኑም፣ ደሀ ስለሆንን መቆጠብ አንችልም ማለት አይቻልም።

ስለዚህ የቁጠባ ባህል በባሕላዊ ተቋማትም ሆነ በዘመናዊ ተቋማት ይበልጥ እየተስፋፋ እንዲሄድ የማያቋርጥ ትምህርት መስጠት የግድ አስፈላጊ ነው። ቁጠባን የሚያበረታቱ ልዩ ልዩ ሥልቶችንም መጠቀም ያስፈልጋል። በነገራችን ላይ ያለችውን አነስተኛ ገንዘብ በገንዘብ ተቋማት የማይስቀምጥ ዜጋ ሁሉ ለአገሩ ልማት የሚያስፈልገውን የገንዘብ ክምችት የማኰልበት ሚና ስለሚጫወት የአገሩ ልማት ቀጥተኛ ተሳታፊ የመሆን ዕድል ያገኛል። በአገር ልማት ባለው አቅም መሳተፍ ደግሞ የሚያኮራ ተግባር ነው።

መንግሥት በተለይም በማህበራዊና መሠረተ ልማት ዘርፎች ከፍተኛ የልማት ተግባራትን ለማከናወን እየጸበረ የሚሄድ ገቢ ስለሚያስፈልገው የመንግሥትን የአገር ውስጥ ገቢ ማጐልበት አስፈላጊ ነው። ይህን ለማድረግ፤

- የታክስ መሠረት ማስፋፋትና የአሰባሰብ ሥርዓት ማጠናከር፣
- መንግሥት ለልማት የሚያስፈልገውን ወጭ መሸፈን እንዲችል ታክስ መክፈል ከድህነት ለመውጣት የሚያረገውን ትግል ማገዝ መሆኑን ሳያሰለሱ ማስተማር፣
- የታክስ አጣጣልን ፍትሐዊነት፣ ከከፋዩ አቅም ጋር የተገናዘበ መሆኑንና በአብዛኛው የታክስ ከፋይ ተባባይነት ያለው መሆኑን እንዲሁም የኢንቨስትመንት ፍላጐትን የሚያሳድጉና ታክስ ከመክፈል የመሸሽን ዝንባሌ የማያጐለብት መሆኑን ማረጋገጥ፣
- የመንግሥትን ገቢና ወጪ ሕብረተሰቡ እንዲያውቀው በማድረግ፣ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ማጎልበትና ተአማኒነትን ማጠናከር፣

ለተከናወኑ ከሚገቡ ጉዳዮች መካከል ጥቂቶቹ ናቸው::

በሌላ በኩል በማናቸውም አገር በተለይ ገና በማደግ ላይ ባለ አገር ለፈጣን ልማት የሚያስፈልገውን የገንዘብ ኃይል ሁሉ በአገር ውስጥ ብቻ ማመንጨት አዳጋች መሆኑ ይታወቃል:: ስለዚህ ከውጭ ምንጮች ለልማት ሊውል የሚችል ገንዘብ የሚገኝበትን ሥልቶች ማጥናትና ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል:: ይህም ማለት የውጭ እርዳታ፣ የብድርና የኢንቨስትመንት ምንጮችን ማስፋፋት ነው::

የውጭ እርዳታ፣ የብድርና የኢንቨስትመንት ምንጮችን ማስፋፋት በሶስት አቅጣጫ ይገለጣል:: እነሱም፤

- ታዳጊ አገሮች ለዕዳ ስረዛ ያላቸውን ዕድል መጠቀም የሚያስችል ሁኔታዎችን በሚሟላት ዕዳን ማሠረዝ፣
- ብድር የሚከፈል ዕዳ መሆኑን በመገንዘብ ከመክፈል አቅም ጋር በተገናዘበ መልኩ ለልማት ተግባራት የሚውል ገንዘብ በተቻለ መጠን በአነስተኛ ወለድና በረጅም ጊዜ ክፍያ መበደር፣ እና
- ያገር ውስጥ ኢንቨስተሮችና የውጭ ኢንቨስተሮች ሙዋዕለ ንዋያቸውን ለአገር ኢኮኖሚ ልማት እንዲያውሉ የሚያበረታቱ ምቹ ሁኔታዎችን ማጐልበት ናቸው::

ያገር ውስጥ እና የውጭ ባለሀብቶች ሀብታቸውን ለአገራችን ግንባታ እንዲያውሉ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ያስፈልጋል::

በአገሪቷ ለኢንቨስትመንት ያሉትን ዕድሎችና ማበረታቻዎች በስፋት እና ቀጣይነት ባለው መልኩ ማስተዋወቅ፣

- በመንግሥትና በኢንቨስተሮች መካከል የጋራ ውይይት ማጐልበት፣
- ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን የማያቋርጥ ጥረት ማድረግ፣
- የሕግ የበላይነትን ለማስፈን መደረግ የሚገባውን ጥረት ሁሉ አጠናክሮ መቀጠል፣

- የኢኮኖሚ ዕድገት አብይ መሠረት የሆኑትን የአገር ውስጥ ኢንቨስተሮች አትኮኖ ችሎታ ለማጎልበት የውጭ ባለሀብቶች ከአገር ውስጥ ባለሀብቶች ጋር በጋራ እንዲሰሩ ማበረታታት፣
- በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ባለሀብቶች ወደ አገራቸው ገብተው በልዩ ልዩ ኢንቨስትመንት መስክ እንዲሳተፉ ማበረታት::

2.2. የገንዘብ አጠቀቃም ብቃትን ማጎልበት

ለልማት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ማፍራት አንድ ዋና ተግባር ነው:: ገንዘብ ለልማት ቁልፍ መሳሪያ መሆኑን የሚወሰነው ግን የገንዘቡ አጠቃቀም ብቃት ነው:: ስለዚህ የገንዘብን አጠቃቀም ብቃት ማጎልበት እጅግ ወሳኝ ነው:: ከዚህ አንጻር የሚከተሉትን አቅጣጫዎች መከተል ያስፈልጋል፡

የዋጋ ንረት ከቁጥጥር ውጭ ከሆነ ለልማት ሊውል የሚችል የተጠራቀመ ገንዘብ በቀላሉ ዋጋ ቢስ ሊሆን ስለሚችል የዋጋ ንረትን ከቁጥጥር ውጭ ከሚያደርጉ ፖሊሲዎች እና ድርጊቶች መቆጠብ ያስፈልጋል:: በአገራችን የተረጋጋ ዋጋ ማስፈን ሲተኮርበት የነበረ ቢሆንም፣ ይህንኑን አጠናክሮ መቀጠል ያስፈልጋል:: አስተማማኝ የዋጋ መረጋጋት ከሌለ ኢንቨስትመንት በእጅጉ ይጐዳል::

የመንግሥትም ሆነ የግል የልማት ፕሮጀክቶችና ልማትን ያመጣል ተብሎ የሚታሰብ ማናቸውም የኢንቨስትመንት ተግባር አስቀድሞ የሚያዋጣ፣ በእርግጥም ልማትን ሊያመጣ የሚችል መሆኑን በጥናት ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ይህንንም ለማድረግ የሚያስችል አቅም መገንባት ያስፈልጋል:: ይህ ካልሆነ በብዙ ድካም የተገኘ ገንዘብ በቀላሉ ሊባክን ይችላል::

ለልማት የተመደበ ገንዘብ ለታሰበው የልማት ሥራ መዋሉን ማረጋገጥ ያስፈልጋል:: ለልማት የታቀደ ገንዘብ በቀላሉ አስቸኳይ ነው ለሚባል ፍጆታ ሊውል ስለሚችል ለልማት ተግባር የታቀደውን ገንዘብ ለልማት የማዋል ዲሲፒሊን የማዳበር ጉዳይ ቸል ሊባል የሚችል አይደለም::

ከልማት የሚገኝ ገንዘብ ወይም ሀብት እዚያው ተመልሶ ልማትን ለማስፋፋት ወይንም ለሌሎች የልማት ተግባራት እንዲውል የሚያበረታቱ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን መከተል ያስፈልጋል:: ለምሳሌ፤ በቅርቡ የአክሲዮን ትርፍ ድርሻቸውን መልሰው ለኢንቨስትመንት የሚያውሉ ባለአክሲዮኖች ከአክሲዮን ትርፍ ድርሻ ግብር ነጻ እንዲሆኑ መደረጉ ኢንቨስትመንትን ያበረታታል:: ሌሎች ሥልቶችንም አጥንቶ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል::

በመንግሥት ደረጃም ሆነ በግል የልማት ሥራዎችን የሚያከናውኑ አካላት ሁሉ ብቃት ያላቸው መሆኑን ለማረጋገጥ አቅማቸውን መገንባት ያስፈልጋል:: ይህ ካልሆነ የልማት ፕሮጀክቶች በተወሰነላቸው ገንዘብና ጊዜ ስለማይጠናቀቁ አላስፈላጊ ተጨማሪ ወጭዎችን

በማስከተል፣ ለገንዘብ ብክነት በር ይከፍታሉ። ስለዚህ በፕሮጀክት ቀረጻ፣ አፈጻጸምና ኦዲት አገራችን ያላትን አቅም በየጊዜው ማጐልበት ያስፈልጋል።

ሆን ተብሎ የልማት ገንዘብ እንዳይባክን የታማኝነትን ባሕል ማጐልበት እና ሙስናን አጠፊ መሣሪያ ያስፈልጋል።

ማንኛውም የልማትም ሆነ ሌላ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አስተማማኝ በሆነ የሂሳብ አያያዝ ሥርዓትና ወቅቱ ተጠብቆ በአዲተሮች በተመረመረ ሂሳብ ካልተደገፈ የገንዘብን አጠቃቀም ትክክለኛነት ማረጋገጥ አይቻልም። የኢኮኖሚ ተግባራቱንም የሚያከናውኑ ተቋማት በመስተዋት ፊቱን አይቶ እንደማያውቅ ሰው ይቆጠራሉ። አስተማማኝና ወቅታዊ የሂሳብ መለኪያዎች የማናቸውንም ሥራ የፋይናንስ ሁኔታ ቁልጭ አድርገው ስለሚያሳዩ ወሳኝ መረጃዎች ናቸው። የገንዘብ ብክነትም ካለ በቶሎ እንዲታወቅና የእርምት እርምጃ እንዲወሰድ ያግዛሉ።

በአገራችን አስተማማኝ የሂሳብ ሥርዓት ዘርግተው የሚሠሩ፣ በአዲተሮች የተመረመረ ሂሳብ ያላቸው የኢኮኖሚ ተቋማት በጣም ውስን ናቸው። ሀገም በአዲተሮች የተመረመረ ሂሳብ እንዲያቀርቡ የሚያስገድደው የአክሲዮን ኩባንያዎችን ብቻ ነው። ነገር ግን የአክሲዮን ኩባንያዎች ያልሆኑ ነአክሲዮን ማህበራት በላቀ ደረጃ የሚንቀሳቀሱ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ ተቋማት መኖራቸው የታወቀ ነው። በመሆኑም በአዲተሮች የተመረመረ አስተማማኝ የሂሳብ መለኪያዎች በሌለበት ሁኔታ ብዙ ድርጅቶች መክሰራቸውን ሳይገነዘቡ በድንገት ቢሸመኗመዱ አይገርምም። ፊቱን በመስተዋት የማያይ ሰው ያለበትን ጉድፍ እንዴት ሊያይ ይችላል። ስለዚህ ነተወሰነ ደረጃ በላይ ያሉ የኢኮኖሚ ተቋማት በአዲተሮች የተመረመረ የሂሳብ እንዲያዘጋጁ በሕግ መደንገግ አስፈላጊ ይመስለኛል። ይህ እርምጃ የመንግሥትን ግብር ለሚሰበስቡ አካላት ይጠቅማል፣ ብድር ለሚሰጡ ተቋማት ይጠቅማል፣ የፋይናንስ አቋም ግልጽነትን ያጐለብታል፣ ለድርጅቶች ባለሀብቶችም ያለበትን ትክክለኛ የፋይናንስ አቋም በየጊዜው እንዲያውቁ ያደርጋል፣ ለሂሳብ ሠራተኞችና ለአዲተሮች የሥራ ዕድል ይፈጥራል። በመሆኑም ሊተኮርበት የሚገባ ፖሊሲ ይመስለኛል።

የራስን ገንዘብ በጥንቃቄ መጠቀም በጣም አስፈላጊ ነው። በብድር የተገኘ ገንዘብን መጠቀም ደግሞ የበለጠ ጥንቃቄ ያስፈልግዋል። ምክንያቱም የብድር ገንዘብ ቢባክን ባለዕዳ መሆን ስለማይቀር የባከነን የብድር ዕዳ ለመክፈል ሲባል ለልማት ሊውል የሚችለውን ገንዘብ ወይም ሌላ ሀብት ለባከነው ገንዘብ ዕዳ ክፍያ ማዋልን ስለሚያስከትል ልማት በእጅጉ ይጐዳል። በመሠረቱ የብድር ገንዘብ ዕዳውን ለመክፈል በሚያስችል የልማት ተግባር ላይ ሊውል ይገባል። ተበድሮ ለፍጆታ ማዋል አደገኛ ነው። ብድር ካልተከፈለ ደግሞ የገንዘብን ዝውውር ከመጉዳቱም በላይ ውሎ አድሮ አበዳሪም ስለሚያሳጣ በቀላሉ ልማት በገንዘብ እጥረት ሊጐዳ ይችላል። ስለሆነም የብድር ገንዘብ አጠቃቀምን ለማጐልበት በግልም ሆነ በመንግሥት ደረጃ የሚደረገውን ጥንቃቄ ማጠናከር ያስፈልጋል።

2.3 የግንዘብ ሥርጭትን ማጐልበት

ግንዘብ ማግኘት የማይችል የኢኮኖሚ አካል የደም ስርጭት እንደማይደርሰው የሰው አካል በድን ይሆናል:: የሰው ልዩ ልዩ አካላት የተያያዙና የሚደጋገፉ እንደመሆናቸው የኢኮኖሚ ልዩ ልዩ አካላትም የተያያዙና የሚደጋገፉ ናቸው:: አንዱ የሰው አካል በድን ከሆነ የመላው አካል ጤናማ እንቅስቃሴ እንደሚጐዳ ሁሉ፣ አንዱ የኢኮኖሚ አካል በግንዘብ ዕጥረት ከተጠቃ አጠቃላይ ኢኮኖሚው ይጐዳል:: ስለዚህ ልዩ ልዩ ከፈላቱ ኢኮኖሚያቸው የማይስፈልጋቸውን የግንዘብ ሥርጭት በወቅቱ እንዲያገኙ ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ ተገቢና አስፈላጊ መሆኑ ግልጽ ነው::

በአገራችን ያሉ ባንኮች እ.ኤ.አ. በ31/12/94 በብድር መልክ ለልዩ ልዩ ክፍላተ ኢኮኖሚዎችና ለመንግሥት የሰጡት ብድር መጠን 26.4 ቢሊዮን ብር ያህል ነው:: ከዚህ አሀዝ ውስጥ ባለፉት 10 ዓመታት የተቋቋሙት የግል ባንኮች ድርሻ ብር 7.2 ቢሊዮን ወይም 27 በመቶ ያህል ሲሆን፣ ቀሪው 73 በመቶ የመንግሥት ባንኮች የሰ ጡት ብድር ነው:: አሀዞቹ ባንኮች ገንዘብን በማሰባሰብ ለልማትና ለኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የሚያደርጉትን ጉልህ አስተዋጽኦ ያመለክታሉ:: ይሁን እንጂ ዘላቂነት ያለው ፈጣን ልማትና ዕድገት ለማምጣትና ነዳህነት ለመውጣት የሚያስፈልገው የገንዘብ ኃይል ከተጠቀሰው አሀዝ በጣም ከፍተኛ እንደሆነ መገመት አያዳግትም:: በተለይ የንግድ ባንኮች ከሚያበድሩት ብድር ውስጥ ከፍተኛውን ድርሻ የሚይዘው ለሥራ ማስኬጃ የሚውል የአጭር ጊዜ ብድር ነው:: ይህም የሚሆንበት ዋና ምክንያት የንግድ ባንኮች የሚያሰባስቡት ገንዘብ በአጭር ጊዜ ወይም እንደተጠየቀ የሚከፈል የአስቀማጮች ገንዘብ በመሆኑ በረጅም ጊዜ ለሚከፈል ብድር እንደልብ መስጠት ስለማያስችላቸው ነው::

ይህም ሆኖ ባንኮቹ በተወሰነ ደረጃ ለልማት ማካሄጃ የረጅም ጊዜ ብድር እየሰጡ ነው:: ንግድ ባንኮች የዚህ ዕይነቱን ብር በስፋት ለመስጠት በረጅም ጊዜ የሚከፈል የገንዘብ ምንጭ ማግኘት አለባቸው:: የረጅም ጊዜ ብድር ሊሰጡ የሚችሉ የገንዘብ ተቋማትም ይበልጥ መስፋፋት አለባቸው:: በአንጻሩ ግን ንግድ ባንኮች የሚሰጡት የአጭር ጊዜ ሥራ ማስኬጃ ብድር ለልማት ተቋማት ሥራ እንቅስቃሴ ወሳኝ መሆኑን ማጤን ያስፈልጋል:: ኢኮኖሚያቸን በአጠቃላይ ለልማት የሚፈልገው ገንዘብ ኃይል አሁን ማቅረብ ከሚቻለው በላይ መሆኑ ግልጽ ስለሆነ ገንዘብን የማሰባሰብ ተግባር ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል::

መንግሥት ከራሱ ገቢ፣ ከውጭ በእርዳታና ብድር በሚገኝ ገንዘብ የማህበራዊ አገልግሎቶችንና ለልማት የሚያስፈልጉትን ልዩ ልዩ መሠረተ ልማቶችን ለማስፋፋት ጥረት ያደርጋል:: ይሁን እንጂ እነዚህ የልማት መስኮች ያለበት ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ሲታይ፣ ዕድገታቸውን ለማፋጠን ከፍተኛ የገንዘብ ኃይል እንደሚያስፈልግ እሙን ነው:: ስለዚህ ከውጭ የሚገኘውን ዕርዳታና ብድር ባግባቡ በመጠቀምና ምንጮቹን በማስፋፋት ለልማት የሚያስፈልገውን የገንዘብ ስርጭት ይበልጥ ማዳበር ያስፈልጋል::

ሁለቱ በገጠርና በከተማ ያሉ በርካታ አነስተኛ የኢኮኖሚ ተቋማት ብድር የሚያገኙት በዋናነት ከባንኮች ሳይሆን፣ አነስተኛ ብድር ከሚሰጡ የገንዘብ ተቋማት ነው። እነዚህ ተቋማት ያላቸው የገንዘብ ኃይል ከተቋም ተቋም የሚለያይ ቢሆንም አቅማቸው በአጠቃላይ ውስን ነው። በመሆኑም፣ ከአባሎቻቸው ከሚያሰባስቡት ቁጠባ ዕድገት አንጻር የአነስተኛ ኢኮኖሚ ተቋማትን የብድር ፍላጐት በሚፈለገው ደረጃ ሊያሟሉ አይችሉም። የጂአግራፊ ሥርጭታቸውም ውስን በመሆኑ አገልግሎታቸው ገና የተስፋፋ አይደለም። ስለዘህ የአገልግሎታቸውን አድማስ ከማስፋፋት ጐን ለጐን፣ የእርስ በርስ ግንኙነታቸው የሚጠናከርበትን ሥልት በመቀየስ የሚደጋገፉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል። የዘህ ግኑኝነት መጠናከር በአንጻራዊ እይታ የገንዘብ አቅሙን ያጐለበተ አነስተኛ ብድር ሰጭ ተቋም ገና ያልደረጀውን ተቋም ለአጭር ጊዜም ቢሆን እንዲያግዝ ስለሚረዳ ነው።

በአጠቃላይ በአገራችን አሁን ያሉና ወደፊትም የሚቋቋሙ ባንኮችና ልዩ ልዩ የገንዘብ ተቋማት ተባብረውና ተደጋግፈው ልማትን ይበልጥ እንዲያግዙ በመካከላቸው ያለውን የሥራ ግኑኝነት ይበልጥ ማጠናከር ያስፈልጋል። ጠንካራ ግኑኝነት ካለ በአንድ የገንዘብ ተቋም ያለ የገንዘብ ክምችት እጥረት ወዳለበት የገንዘብ ተቋም እንዳስፈላጊነቱና እንደተገቢነቱ እንዲፈስ ምቹ ሁኔታዎችን ይፈጥራል። በተቻለ መጠን ገንዘብ ፈላጊ እያለው ሥራ ፈትቶ እንዳይቀመጥ ሊደረግ የሚገባውን ሁሉ ማድረግ ያስፈልጋል።

በገንዘብ ድርጅቶች መካከል ያለውን የሥራ ግኑኝነት ስለማጠናከር ያነሳሁዋቸው እነዚህ ነጥቦች ወደ አንድ ቁም ነገር ያመራሉ። ይኸውም፣ ያለው የገንዘብ ኃይል ውስን ስለሆነ የገንዘብ ምንጮችን ከማጐልበት ጐን ለጐን የገንዘብ ድርጅቶች እርስ በርስ የሚወዳደሩ ቢሆንም፣ ተባብረው በጋራ እንደ አንድ ውህድ አካል በመንቀሳቀስ የገንዘብ ሥርጭትን ማጐልበት የሚችሉና የሚገባቸው መሆኑን ነው። በዚህ ረገድ ገና ብዙ መሥራት ይጠበቅብናል።

ገንዘብ ለልማት የሚያደርገውን አስተዋጽኦ ይበልጥ ለማጐልበት የሚያግዙ ልዩ ልዩ ነጥቦችን እንስቻለሁ። ነጥቦቹ አቅጣጫ አመልካች እንጂ የተግባር መመሪያ እንዳልሆኑ ግልጽ ነው። በአቅጣጫ አመልካችነት የተነሱትን ነጥቦች በተግባር ለመተርጐም በርካታ ሥራዎችን መሥራት፣ ጥናቶችን እና ቀጣይ ውይይቶችንም በተደራጀ መልኩ ማካሄድ ያስፈልጋል።

በመጨረሻም፣ ገንዘብ ለልማት ቁልፍ መሣሪያ መሆኑን አጉልተን ለማንሳት ሞከርን እንጂ የልማት ኃይሎች በርካታ ናቸው። ከሁሉም በላይ ግን የልማት አንቀሳቃሽ ሞተር የሆነው ውጫዊ ኃይል ሰው ነው። ሌሎች የልማት ኃይሎች ሁሉ ለሰው ተገዢ የሆኑ ግዑዛን ናቸው። ልማት የሰዎች ቅን አእምሮ ሀብረት ውጤት ነው ማለት ይቻላል። ስለሆነም፣ ልማትን ለማምጣት በተቻለ መጠን የሰው አእምሮ በቅንነት ስለ ልማት እንዲያስብ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለልማት ማሰብ የሚችል ጤናማ አእምሮ ከባቢ ሁኔታ ደግሞ ሠላም ነው። ስለዚህ፣ አገራችን በአገር ውስጥና ከአጐራባች አገሮች ጋር ዘላቂ ሠላምን ለማጐልበት የምታደርገው እንቅስቃሴ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል። ለዚህ ከቡር ዓላማ መንግሥትና ዜጐች ሁሉ በህብረት መሠለፍ አለባቸው። በእኔ ግምት ዘላቂ ሰላምን ለማስፈን የሚከፈል

ዋጋ በምንም መልኩ ሰላምን ለማጣት ከሚከፈል ዋጋ ሊበልጥ አይችልም። ነገም ሆነ በ «2020 ኢትዮጵያ» የበለፀገች ኢትዮጵያን ማየት የምንችለው የተረጋጋ ሰላም መሰፈኑን እያረጋገጥን ለልማት በጎብረት ስንንቀሳቀስ ብቻ ነው።

ኢንተርፕረነርሺፕ እና ልማት በኢትዮጵያ

ወሮታው በዛብህ*

ብልፅግና የለምኞ ፅኑ ፍላጎት፣ ጥረትና የተሻለ ሥራዎች ፍሬ ሊሆን፣
ኂላ ቀርነት ደግሞ የለምኞ ያልተሻለ ፍላጎቱች፣ ጥረቶችና ሥራዎች ክምችት ነው።

በሌላ በኩል

ብልፅግና የበለፀገ፣ ኂላ ቀርነት ደግሞ ኂላቀር የሆኑ አስተሳሰቦች ውጤቶች ናቸው።
ኂላ ቀርነት የአስተሳሰብ በሽታ ነው። በሽታው የብዙ አሰቃቂ ነገሮች ምንጭ ነው።
የኂላ ቀርነት መድኃኒቱ የተሻለ ሥራ ነው።
የተሻለ ሥራዎች የሚሰሩት የተሻለ አስተሳሰብ ባላቸው ሰዎች ነው።
የተሻለ አስተሳሰብ ካላቸው የዓለም ሰዎች ውስጥ ግምባር ቀደም የሆኑት ኢንተርኘረነሮች ናቸው።

2020 የኢንተርኘረነሮች ዘመን ነው።

I. ኢንተርኘረነርሺኘና ኢንተርኘሪነሮች ፅንሰ ሀሳቦች

I.I ኢንተርኘረነርሺኘ - ጽንሰ ሀሳብና ትርጉሞች

"100% is such an important percentage in commitment. The whole world would work if you were committed to 100% excellence in everything you do."
Jack Canfield

የሰው ልጅ የሥራ፣ የሀብትና የዕድገት ዋና ዋና ምንጮች የሚባሉት አራት የምርት ግብዓቶች ወይም ጥሬ ሀብቶች መሬት፣ የሰው ኃይል፣ ካፒታልና ኢንተርኘረነርሺኘ ናቸው። የመጀመሪያዎቹ ሶስቱ ጥሬ ሀብቶች በቀላሉ ይታያሉ፣ ይለካሉ፣ ይታወቃሉ። ኢንተርኘ ረነርሺኘ ግን በቀላሉ የሚታይ፣ የሚቆጠርና የሚታወቅ አይደለም። በመሆኑም ኢንተርኘ ረነርሺኘ ለረጅም ጊዜ እንደ ምርት ግብዓት /ጥሬ ሀብት/ የተወሰደ አልነበረም። ኢንተርኘ ረነርሺኘ በተለያዩ ዘመኖች የራሱ የሆነ አተረጓጎም፣ የራሱ የሆነ ድርጊትና የራሱ የሆኑ ተዋንያን ያሉት ሆኖ ይቀርባል። ኢንተርፕረነርሺፕ ሁሉም የሚስማሙበት አንድ ወጥ የሆነ ትርጉም የለውም። በተለያዩ ጥናቶችና በተለያዩ ምሁራን ኢንተርኘረነርሺኘ ማለት ምን ማለት ነው ለሚለው የተለያየ መልሶች ሰጥተዋል።

ቃሉ በ17ኛው ክፍለ ዘመን ከፈረንሳዮች ኢንተርኘራንደርሺኘ ከሚለው የተወሰደ ሲሆን ይህም ኃላፊነት (risk) መውሰድ፣ አንድን ነገር ከሌላው በተለየ መንገድ ማድረግ ብለው ይተረጉሙታል። ሌሎች የማያደርጉትን ሥራ (ኃላፊነት) ወስዶ ማድረግ ማለት ነው። ከ17ኛ

---

* ደራሲ ወሮታው በዛብህ: አምፐርቴክ ኢትዮጵያ ቢዝነስ ሶሳይቲ - የኢትዮጵያ ኢንተርኘራነሮች ማህበር ኘሬዝዳንት፤ ጂአየስ የኢንተርኘራነርሺኘ ስልጠናና የምክር አገልግሎት እንዲሁም ሐብረ-ብርሃን ኃ.የ.የግል ማህበር ዋና ስራ አስኪያጅ። ስ.ቁ.: 011-551 78 71 /011-552 21 78/ 091-140 77 53
e-mail: werotawb@yahoo.com Website: www.bds-ethipia.netleebs

ው ክፍለ ዘመን ወዲህ ኢንተርፕረነርሽፕ ኃላፊነትን መስዶ ሌሎች የማያደርጓቸውን አዳዲስ ነገሮች መፍጠር ወይም ለሌሎች ሥራዎችን በተለየ መንገድ ከማከናወን ጋር ይያያዛል::

ከብዙዎቹ ትርጉሞች መካከል ለኢትዮጵያ ይበልጥ ጠቃሚ የሆኑትን አንዳንዶቹን እናቀርባለን:: አንድ ምሁር ኢንተርፕረነርሽፕ የማያቋርጥ አዳዲስ ሃብት የመፍጠር ሂደት ነው ይላሉ:: "It is the daynamic process of creating incremental wealth" በዚህ ሰው አገላለጽ አንደኛ ሀብት የመፍጠሩ ሂደት ቋሚና ቀጣይነት ያለው ነው:: ሁለተኛ ይህ ሀብት የመፍጠር እንቅስቃሴ ለሌሎች ከሚያደርጉት ለየት ባለ መንገድ የሚካሄድ ነው:: ብዙ ጊዜ አብዛኞቹ ሰዎች የሚያዩት በቀላሉ የማይታይ ሰፊ ሰዎች ደግሞ የሚያዩት ለሌሎች የማይታዩትና አነሱ የሚያደርጉት ሌሎች የማያደርጉት የተለየ ነገርን የሚጠይቅ ሀብት የመፍጠሪያ ኃላፊነትን የመወሰድ መንገድ ነው::

ሁለተኛ ትርጉማችን ከላይ ያልናቸውን ያጠናክርልናል:: በተለይ ጆሴፍ ሽምፕተር የሚባሉ አስተሪያዊ- አሜሪካዊ ኢኮኖሚስት ኢንተርፕረነርሽፕን ሲገልፀው አሮጌን ነገር በአዲስና በተሻለ ነገር የመተካት ሂደት ነው ብለው ያስቀምጠታል:: (Enterpreneurship is a process of creative destruction) ይህም ማለት የነበረውን ግብርና በዘመናዊ ግብርና የፈጠሩትን የትራንስፖርት፣ የሕክምና፣ የባንክ፣ የትምህርት፣ የጤና፣ የመኖሪያ ቤት እንቅስቃሴዎች በተሻሉ ነገሮች የመተካት ሂደት ነው:: ኢንተርፕረነርሽፕ ማለት ይህ የተሻለ አሰራር ነው ብለው ነበር ጆሴፍ ሽምፕተር በወቅቱ ያስተማሩት:: ይህንን በመንተራስ የተፈጠረው ግንዛቤ ሁሉም ሥራዎች የተሻለ ለሌሎች መንገዶች ያሏቸው መሆኑን ነው:: ጆሴፍ ሽምፕተር አንድን ነባር ሥራ የተሻለ ማድረግን፣ መፍጠር፣ አዲስ ነገር የመስራትንና የተሻለ ሂደትን ኢንተርፕረነርሽፕ ነው ይለዋል::

ለሌችም ምንጮች እንደማያሳዩት ኢንተርፕረነርሽፕ አንድን ኃላፊነት በግል የመወሰን፣ ኃላፊነቱን (risk) በግል የመወጣትና በግል ስኬታማ የመሆን ሂደት ነው ይላሉ:: በተለይ ለኢትዮጵያውያን አንባቢዎች ይህንን Enterpreneurship is the process of taking individual risk independently and individually የሚለውን ትርጉም አጠናክሮ ማቅረብ ያስፈልጋል:: ምክንያቱም አንድን ነገር ለመለወጥ፣ የተሻለ ለመኖር፣ ሀብት ለማፍራት፣ የተሻለ ዕድገት ያለው ህይወት ለመኖር ኃላፊነትን በሙሉ ራስ መውሰድ ያስፈልጋል:: ጆሴፍ ሽምፕተር እንዳስተመጠት የሚመጠትን ጫናዎች በራስ መወጣት፣ በራስ ጥረት፣ በራስ ስራና ችግሮችን ተወጥቶ የተሻለ ደረጃ ላይ መድረስ ያስፈልጋል::

ኢንተርፕረነርሽፕ አዲስ ነገር የመፍጠር ችሎታ ነው:: ከአራቱም በጣም ውድ የሆነው ጥሬ ሀብት (resource) ኢንተርፕረነርሽፕ ነው:: በጆሴፍ ሽምፕተር ትርጉም ብንሄድ ኢንተርፕረነርሽፕ አራቱን የምርት ግብዓቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ አዋህዶ አዲስ ነገር የመፍጠር ወይም የነበረውን የማሻሻል ሂደት ነው:: ኢንተርፕረነርሽፕ አጋጣሚዎችን የማፈላለግና ወደ ቢዝነስ የመለወጥ ሂደት ነው::

አድገትቸው ኋላ ቀር በሆኑ ሀገሮች የኢንተርፕረነርሽፕ ግብዓት በደንብ የታወቀ አይደለም:: በእነዚህ ሀገሮች ለዚህ የምርት ግብዓት በቂ ግንዛቤ ያልተፈጠረበት ሁኔታ ነው ያለው:: ኢንተርፕረነርሽፕ ያለትን ጥሬ ሀብቶች ለተሻለ ዕድገት፣ ለአዳዲስ ምርቶችና አገልግሎቶች ፈጠራ የማዋል ጥረት ነው:: ኢንተርፕረነርሽፕ ወደ ኋላ የቀሩ አሰራሮችን በአዲስ አሰራሮች

መሥሪትና አዳዲስ ሥራዎችን የመፍጠር ሂደት ነው። ኢትዮጵያዊው ምሁር ነጋድራስ ሀብተ ጊዮርጊስ ዐቢይ «ሀብት ማለት የተከማቸ ሥራ ማለት ነው።» ብለው ነበር። ብዙ ሥራዎች መፍጠር ማለታቸው ነው። ብዙ ስራዎች በግብርና፣ በኢንዱስትሪ፣ በንግድ፣ በትምህርት፣ በመንገድ ሥራው፣ በባንክ፣ በኢንሹራንስና በሌሎች ዘርፎች መፍጠር ማለት ነው። ብዙ ሠራተኞችን በሥራ ማሰማራት ማስቻል ማለት ነው።

ብዙ ሠራተኞች ባለማቋረጥ ሲሰሩ ሀብት ለሀገራቸው ይፈጥራሉ። ብዙ ሠራተኞች ቤት ሲሠሉ በላተኞች ይሆናሉ። ሀብት የሚያፈሩት ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በአዲስ መንገድ ሲሰሩ ነው። ከነባሩ አሰራር ሲወጡ ነው። ግብርናውንና ኢንዱስትሪው አዲስ ነገር ሊፈጥር የሚችል መልከ ዙንቀሳቅሰው ሚሊዮን ሰራተኞችን የሚያሰራ ሥራዎች ሲፈጥሩ ሀገር የሚኮራና ሀብት ያገኛል። ይህ ከምናየው በላይ የተሻለ ለመኖር መመኘትና መነሳሳት ወደ ከፍተኛ ማማ ፈጠራ ይገፋፋል። ከዚህ ከሚኮርፍ ሀብት ገቢ ግብር በመሰብሰብ ሀገር ለሌሎች የልማት እንቅስቃሴዎቹ የሚሆን ገንዘብ ያገኛል።

ሠራተኞች ሥራው ላይ የተሰማራ የገቢ ባለቤትም ራሱን ለበለጠና ለተሻለ የኑሮ ደረጃ ያስተምራል። ይህ ለተሻለ የገቢ ምንጭ የተመቻቸለት ሀበረተሰብ ደግሞ ብዙ ነገር የመግዛት አቅሙ ያድጋል። «ያደገ» የፍጆታ ጥያቄን ለማሟላት በሁሉም ዘርፍ ላይ ያሉ አምራቾች የሚሸጧቸውን ነገሮች በብዛት ያቀርባሉ። የተመረተው ምርት ደግሞ በብዛት የሚሸጥ ከሆነ በቀላዙ ብዙ ምርቶች ይመረታል። ይህ ቀጣይነት ያለው ሂደት በአገር ደረጃ ትልቅ ሀብት ያፈራል። ስለዚህ ስለ ኢንተርፕረነርሽፕ የሚጽፉ ሰዎች አትኩረው የሚናገሩት ኢንተርፕረነርሽፕ ማለት የማያቋርጥ ሀብት የመፍጠር ሂደት ወይም እንቅስቃሴ መሆኑን ነው። ይህ አዳዲስ የሥራና የሀብት ፈጠራ ጥበብ ከአዳዲስ ቴክኖሎጂ፣ ከአዳዲስ አስተሳሰብ እና ከአዳዲስ የኑሮ ደረጃ ጋር ሲገናኝ የበለጠ መስራትን ያበረታታል።

ኢንተርፕረነርሽፕ ቀጣይነት ያለው የአዳዲስ ሥራ፣ ሀብትና ቴክኖሎጂ ፈጠራ ዋስትና ነው። በተለይ የህበረተሰቡ ለሥራ የመነሳሳት ባህል ባደገ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ለመኖር የመነሳሳት ሁኔታ ያንን ነገር ለማግኘት የሚያደርገው ጥረት ኢንተርፕረነርሽፕን ያሳድገዋል።

ከሚያድጉት ጥረቶች የሚያድግ የህበረተሰብ ሀብት ማፍራት ይቻላል። ኢንተርፕረነርሽፕ ኋላ ቀርነትን፣ ድህነትን፣ በሽታን፣ የትምህርትና ህክምና ተቋማት እጥረትን ያቃልላል። ምክንያቱም በእነዚህ ዙሪያ ላይ ያሉ በርካታ የኢኮኖሚ ተዋንያን ኢንተርፕረነሮችን የሚፈጥር ሂደት ነው። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው ጆሴፍ ሺምፕተር "Entrepreneurhip is the process of creative destruction" ብለው ባወጡት ፅንሰ ሀሳብ መሠረት ብዙ አሰራሮች ዘመናዊ ሲሆኑ ብዙ ችግሮችን ይፈታሉ።

ለምሳሌ ግብርናው ባደጉት ሀገሮች የበለጠ ዘመናዊ ሆኗል። ከማምረቻ ቦታዎች ጀምሮ ለተጠቃሚው ፍጆታ እስከሚደርስ ድረስ የሚኖሩት የምርት እንቅስቃሴዎች በመሀል የሚፈጥሩት ብዙ አዳዲስ የሥራ ግንኙነቶች አሉ። የግብርናው ውጤት ወደ ዘመናዊ ፋብሪካዎች (ዱቄት ማካሮኒና ፓስታ ሆኖ) ወደ አከፋፋዮች ሱቅ ይበተናል። ከአከፋፋዮች ሱቅ ግማሽ በቀጥታ ለሚጠቀሙት ግማሾቹ እዚያም አዘጋጅተው ለህበረተሰቡ ለሚያቀርቡ ሬስቶራንቶች፣ ምግብ ቤቶች ይከፋፈላል። በዚህ ሁሉ ሂደት የተፈጠሩት አዳዲስ አሰራሮች የአዳዲስ የሥራ እድሎችና የሀብት ምንጭ ይሆናሉ።

አዘህ ላይ ሀብትን ስናነሳ የሚበልጠው መሬት ያፈራት አይደለም። ትልቅ ሀብት የተፈጠረው በሂደቱ በተፈጠሩ ተጨማሪ ሥራዎች ነው። ትልቅ የሀብት ምንጭ የሆነው አሀሉን ከማያመርተው ገበሬ የበለጠ ምግብ አዘጋጅቱ ለበላተኛው ያቀረበው ሰው ነው። ምክንያቱም ምግብ አዘጋጅቱ የሚያቀርበው አዲስ ዕውቀት፣ አዲስ ቴክኖሎጂ፣ አዲስ ሂደት (value added) ስለተጨመረበት ነው። በተጨማሪም አዲስ አገልግሎት አዲስ የአቀራረብ ጥበብ ጨምሮበታል።

የኮምፒዩተር ቴክኖሎጂም ዛሬ ዓለምን የአንድ ቤተሰብ አገር አድርጓታል። ኢንተርኔት፣ ፋክስ፣ አ.-ሜይል፣ ሞባይል፣ ቴሌፎን...። ሥራን የሚያፋጥን፣ ጊዜን የሚቆጥብ፣ የገበያ ጥያቄን በቀጥታ በስልክ፣ በኢ-ሜል፣ በፋክስ የመፈፀም፣ ለአምራችና ገዥ በርካታ ግብአት ፈጥሯል። በተለይ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ውጤት አለም የበለጠ የአዳዲስ ምርቶች ተጠቃሚ የሆነበት ወቅት ላይ ደርሰናል። ዛሬ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ከግብርናው የበለጠ ትልቅ የዓለም ሀብት ምንጭ ሆኗል።

ሂደቱ ብዙ ሚሊዮን ሰዎችን አሳትፏል። ከማይክሮ ሶፍት ፈጠራ ጀምሮ ይህንን ቴክኖሎጂ አስከመሸጥና በዚህ እስከመጠቀም፣ ከማይክሮ ሶፍቱ በተጨማሪ የተፈጠሩት አላቂ እቃዎችና መለዋወጫዎች፣ ተጨማሪ ግብአቶች ሚሊዮን ኢንዱስትሪዎችን በየዕለቱ እንዲንቀሳቀሱ አድርገዋል።

ምናልባት ዛሬ በየትኛውም ዓለም አንቱ ከሚባል የግብርና ሥራ ይልቅ አንቱ የሚባለው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኢንተርፕረነር ትልቅ ዕውቀት፣ ገንዘብና ሀብት የፈጠረ ሆኗል። ውጤታማነቱ ቀጥታ ከሥራው ስፋት፣ ብዛት፣ ፍጥነት፣ ጥራትና ዘመናዊነት ጋር የተያያዘ ነው። በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥራዎች ላይ የተሰማሩ ሰዎች በግብርናው ዘርፍ ከተሰማሩት የበለጠ ፈጥነው አደገዋል።

በከፍተኛ ውድድር በመንቀሳቀስ ላይ ያሉት በግብርና ውስጥ ካሉት ይልቅ በቴክኖሎጂ ዘርፍ ውስጥ ያሉ ኢንተርፕረነሮች ናቸው። ምክንያቱም ዘመናዊ ቴክኖሎጂ፣ ሚሊዮን ዘመናዊ ፈጠራዎችን አምርቶአል፤ ይህ የፈጠራ ዘርፍ ለተወሰኑ ሰዎች የተተወ አይደለም። የዚህ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አድገት ብዙ ሚሊዮን ሰዎችን በቀጥታ አሳትፏል።

ስለዚህ ነው ኢንተርፕረነርሽፕ አዳዲስ ስራዎችንና ሀብትና ትርፍ የመፍጠር ሂደት ነው የሚባለው። ኢንተርፕረነርሽፕ ያሉትን ግብአቶች ለተሻለ ደረጃ የሚያደርስ ሥራ ነው። አንዷን ሄክታር መሬት በኢንተርፕረነርሽፕ ከብዙ ሄክታር መሬት የበለጠ ምርታማ ማድረግ ይቻላል። በዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎች ማረስ እና መሬትን የተሻለ ማምረቻ ማድረግ የሚቻለው በኢንተርፕረነርሽፕ ነው።

ሰውን የተሻለ አምራች ማድረግ የሚቻለው በኢንተርፕረነርሽፕ ነው። ሰውን ለተሻለ ስብእና ለተሻለ አምራችና ትርፋማ ዜጋነት የሚያበቃው የኢንተርፕረነርሽፕ ሂደት (process) መኖር ነው። ምክንያቱም በዚህ ዙሪያ ያሉ ሰዎች እየበዙ ሲሄዱ የኑሮ ደረጃ ይቀየራል። ኑሮን በተላለ አለመኖር አሞንታዊ ተዕእኖ አለው። በበረዶ የሚሸፈኑ ብዙ የአውሮፓ አገሮች በረዶውን ተቋቁመው ለመኖር ከበረዶው የሚበልጥ መቀት መፍጠርና ማሞቂያ ኤሌክትሪክ

ያለው ቤት ውስጥ መኖር አለባቸው። ይህ ማሞቂያ ያለበት ቤት ውስጥ መኖር ቀላል አይደለም፤ የኤሌክትሪክ ወጭ አለው። ይህንን ወጭ ተቋቁሞ ለመኖር ጥሩ ገቢ መፍጠር ያስፈልጋል። ጥሩ ገቢ ፈጥሮ ለመኖር ጥሩ ሥራ ያስፈልጋል። ጥሩ ሥራ ላይ ለመቀጠርም ሆነ የራስን ሥራ ለመፍጠር፣ መማርና መሰልጠን፣ ጊዜን መቆጠብ፣ ጉልበትንና ገንዘብን በአግባቡ መጠቀም፣ ጤናንና አራስን በሚገባ መያዝ ግዴታዎች ይሆናሉ።

በተለይ ሁለንም የኢኮኖሚ ጥሬ ሀብቶች ለተሻለ ውጤታማነት የሚያበቃቸው ኢንተርፕረነርሽፕ ነው። ስው የተሻለ፣ የተማረ፤ የሰለጠነ! በየጊዜው መሆን የሚችለው በኢንተርፕረነርሽኘ ሂደት ነው። መንግስትም ሆነ ግለሰቦች በያዙት ዙሪያ ተጨማሪ ገንዘብ የሚፈጥረው ፈጠራ ሲጨመርበት፣ አዲስ ገንዘብ የሚፈጥር ሥራ ላይ ሲውል ነው። አዲስ ዋጋ (value) የሚፈጥር እንቅስቃሴ ውስጥ ሲገባ ነው። ገንዘብንም የተሻለና ትልቅ ገንዘብ የሚያደርገው የኢንተርኘረነርሽኘ እንቅስቃሴና ሂደት ነው። ስለዚህም ኢንተርኘረነርሽኘ የብልጽግናና የእድገት የበለጠ ምንጭ የሆነ ጥሬ ሀብት ነው።

1.2 ኢንተርፕረነርሽፕ - የዕድገት ሁኔታዎች

"Change is the law of life. And those who look only to the past or present are certain to miss the future."

John F. Kennedy

ኢንተርኘረነርሽኘ በጆንስ ሃሳብ ደረጃ፣ እንደ አንድ ግብዓት መወሰድ ከተጀመረ ሁለት መቶ ዓመታት ሆኖታል የሚሉ ነፍሶች አሉ። ይህ ከነአዳም ስሚዝ 1734 እ.ኤ.አ እና ከዚያም በኋላ ከተፈጠሩ እውቅ ኢኮኖሚስቶች ሃሳብ ጋር የሚያያዝ ነው። ኢንተርኘረነርሽኘ በተፈጥሮ ወይስ በትምህርትና ስልጠና ነው የሚገኘው? የሚለውና ተደጋግሞ የሚነሳው ጥያቄም ገና ያልተመለሰ ለሀለት መቶ አመታት የቆየ ነው። አንዳንዶቹ በተፈጥሮ አብሮ ይወለዳል ሲሉ፣ ሌሎቹ ደግሞ በትምህርትና በስልጠና የሚገኝ ነው ይሉታል።

ኢንተርኘረነርሽኘ ከተጀመረ ሁለት መቶ ዓመት ሆኖታል የሚለው በአመዛኙ ተቀባይነት አያገኝ በሂደም ከዚያ በፊት ያሉት የኢንተርኘረነርሽኘ እንቅስቃሴዎች አልነበሩም ወይ? ዓለም ለዚህ ደረጃ እንዴት ደረሰች? ብሎ በመጠየቅ ወደ ኋላ (ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ) የነበሩ እንቅስቃሴዎችን ሲመረምሩ ያገኟዋቸው ጭብጦች አሉ።

ከ14ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአለም ላይ የግብርናው እንቅስቃሴ በአመዛኙ ይካሄድ በነበረበት ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ውስጥ በተለይም በፈረንሳይ መንግሥትና መገናኛ ባልዳበረበት፣ መንግሥት ዳር እስከዳር ሄዶ ግብር ለመሰብሰብ በማይችልበት ሁኔታ ከገበሬዎች መሃል ግብር በመሰብሰብ ላይ ይሳተፉ የነበሩ የኢንተርኘረነርሽኘ ሥራ የሚሰሩ ነበሩ። በዚያን ጊዜ የነበረውን ኢንተርኘረነርሽኘ የገበሬውና የግብር ሰብሳባ የኢንተርኘረነርሽኘ እንቅስቃሴ ብለውታል።

በዚህ ዘርፍ ምንም እንኳን ሁሉም አርሶ አደሮች በግብርናው ዘርፍ የሚሰማሩ ቢሆኑም ከአርሶ አደሮች መካከል ጥቂት ትርፍ መፍጠር የቻሉ ገበሬዎች ለመንግሥት ቀድመው

የራሳቸውን ገንዘብ ከፍለው፣ ፈቃድ አውጥተው ከገበሬው ላይ ለመንግስት ሊሰበሰቡ የሚችሉትን ግብር ይሰበስቡ ነበር። ከገበሬው የሰበሰቡት ለመንግሥት ከከፈሉት ያነሰ ከሆነ ከዛራ ላይ ይወድቃሉ። የሰበሰቡት ሲበልጥ ደግሞ ትርፋማ ይሆኑ ነበር። ትርፍ ለማምጣትም ሆነ ከዛራውን ለመቀበል ፈቃደኛ የነበሩ ኃላፊነት የወሰዱ ገበሬዎች ትርፍ (risk takers) በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ገብተው የታዩበት ሁኔታ ነበር።

ከዚህ በኋላ ያለው የ15ኛውና የ16ኛው ክፍለ ዘመን የኢንተርፕረነሪያል እንቅስቃሴ ደግሞ ከነዚህ ትርፍ መፍጠር ከሚችሉ ገበሬዎች መካከል መሬት ያልበቃቸው፣ አዳዲስ አካባቢን የማልማት ፍላጎታቸው የሰፋ፣ ባገኙት ገንዘብ ተጨማሪ የሰው ኃይል ቀጥሮ ተጨማሪ ማሠራት ህልም ውስጥ የገቡ ሰዎች ደግሞ አዳዲስ አካባቢዎችን ማስፋፋት ጀመሩ። ወደ አዳዲስ አካባቢዎች ሲሄዱ መንገዳቸው አልጋ በአልጋ አልነበረም። አዲስ አካባቢ ሲያቀኑ ጠርነት አለ «ግጭት አለ»፤ ከተፈጥሮና ከሰው ጋር መጋጨት ነበር። ያንን ሁሉ ተቋቁመው ወደ አዳዲስ አካባቢ እየሄዱ እያለመ የእርሻና የማዕድን ስራዎች እንቅስቃሴ የጀመሩ ኢንተርፕረነሮች የታዩበት ጊዜ ነው።

እነዝህን የ15ኛና 16ኛ ክፍለ ዘመኖች የኢንተርፕረነርሽፕ እንቅስቃሴ ያካሂዱ የነበሩ ሰዎችን አንዳንድ መጽሐፎች የአዳዲስ አካባቢ ማስፋፊያ military expedition entrepreneurs የሚል ስያሜ ይሰጧቸዋል። ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላው በመሄድ በአንድ አካባቢ በርከት ብሎ መስፈር የመንደርተኝነትን፣ በአንድ አካባቢ የመኖርን ክስተት በመፍጠሩ ከዚሁ ጋር ተያይዘው የሚመጡ ሌሎች እንቅስቃሴዎች ተጀመሩ።

የ17ኛው ክፍለ ዘመን ትልቅ ትኩረት የሰጠው ለግንባታ ሥራዎች ነው። ተፈጥረው የነበሩት አንዳንድ የኢንተርፕረነርሽፕ እንቅስቃሴዎች ግንባታ ላይ ያተኩሩ ነበሩ፤ መንገድ፣ ትምህርት ቤቶች፣ መኖሪያ ቤቶች፣ ቢሮዎች፣ ድልድዮች ሥራዎች ተጀመሩ። ቀደም ብሎ እንደተጠቀሰው በአንድ አካባቢ የመኖር ሁኔታ ተከሰተ። ያንን የማስተዳደር፣ እዚያው አካባቢ ያለውን ማነበረሰብ በትምህርትና በተለያዩ የጤና አገልግሎቶች በድልድይ ግንባታዎች በተለያዩ ማነበራዊ መሰረተ ልማቶች አካባቢውን የማሳደግ እንቅስቃሴ ሲጀመር ተፈላጊ ሆኖ የተገኘው እንቅስቃሴ ከግንባታ ሂደት ጋር ትስስር ያለው ነበር።

በሽክላ፣ በሽመና፣ በቆዳ ስራ፣ ፈጠራዎች ተጀመሩ። እንግዲህ የ17ኛው ክፍለ ዘመን የኢንተርፕረነርሽፕ እንቅስቃሴ የምንለው ሲቪል አንጂነሪንግ (የግንባታ ኢንተርፕረነርሽፕ ወይንም ኮንትራክተር ኢንተርፕረነርሽፕ) የታየበትን ጊዜ ነበር።

18ኛው ክፍለ ዘመን የኢንዱስትሪ ኢንተርፕረነርሽፕ ሂደት ነው። ከእነዚህ በግንባታ ላይ ከነበሩና ከዚህ ተሳማጅ በሆኑ ሌሎች እንቅስቃሴዎች ወደተሻለ አዳዲስ ኢንዱስትሪን የመፍጠር ሥራ የገቡበት የ18ኛው ክፍለ ጊዜ ነው። በተለይም በታላቋ ብሪታንያ የተከሰተው የኢንዱስትሪ አብዮት፣ ከኢንዱስትሪ ግንባታ ጋር የተያያዙ አዳዲስ ግኝቶች የተገኙበት የሥራ እንቅስቃሴ ነው።

የ18ኛው ክፍለ ጊዜ የኢንዱስትሪያል ኢንተርፕረነርሽፕ ሂደት ከሌሎች የሚለየው ያተኮረው በኢንዱስትሪ ምርቶችና በኢንዱስትሪው ፈጠራ ላይ መሆኑ ነው። ይህ ደግሞ የኢንዱስትሪ ፈጣሪ የሆኑ ኢንተርፕረነሮች የፈለቁበት ክፍለ ዘመን እንደነበር ያሳየናል። የዚህ የኢንዱስትሪ

አመት መምጣት ዓለምን እጅግ እንደቀየራት አሁን የደረስንበት የሕይወት ደረጃችን ትልቅ ምስክር ነው። አሁን ለደረስንበት የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘመን ትልቁን መሰረት የጣለው የአስራ ሰባተኛው ዘመን የኢንዱስትሪው አብዮት ነው።

የአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን ኢንተርፕረነርሽፕ አሁን ላለንበት የእንቅስቃሴ ሂደት አድርሶናል። ከ18ኛ የአስራ ሰባተኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ያለው 19ኛውና 20ኛው ክፍለ ዘመን በተለይ በአገልግሎት ዘርፍ ላይ ው ከፍለ ዘመን ምርቶች ስርጭት ንግድን በሀገር ውስጥና በዓለም አቀፍ ገበያዎች ላይ የሚመረቱ በጤና፣ በዋስትና፣ በትምህርት አገልግሎት ዘርፎች ላይ ትላልቅ እንቅስቃሴዎች ማስፋፋትን የተጀመረበት ጊዜ ነው። የአገልግሎቱ ዘርፍ የዓለም የሀብት ምንጭ የሆነበት ዘመን ነበር። አሁን አድገዋል የምንላቸው ሀገሮች ከኢንዱስትሪውም አልፈው የ20ኛው ክፍለ ዘመን የአገልግሎቶች ኢኮኖሚ በይበልጥ ተጠቃሚዎች ሆነዋል።

ያለፈው ክፍለ ዘመን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የበለጠ ያደገበት ጊዜ ነው። ትልቅ ሀብት ለማፍራትና የሕዝብን ሕይወት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ለማድረስ ኃይል ያለው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ውጤት ነው። የሶፍትዌር ምርቶችና የሌሎች ፕላኔቶች ጥናትና ምርምር የበዛበት ክፍለ ዘመን ሆኗል።

የኢንተርፕረነርሽፕ ጽንሰ ሃሳብ ከ1970ዎቹ ወዲህ በሁለት ዋና ዋና ምክንያቶች በአለም ላይ ከፍተኛ ተቀባይነት አግኝቷል። 1ኛ/ እስከዚህ ጊዜ ድረስ ኮርፖሬሽኖችና ታላላቅ ኢንዱስትሪዎች ብቸኛ የሀብትና የሥራ ምንጭ ናቸው ተብለው ነበር። አነስተኛና መካከለኛ የግል እንቅስቃሴዎች ዛሬ በዓለም ላይ እየፈጠሩ ያሉት ትልቅ የሥራ እድልና የምርት አቅርቦት ጋር ሲነፃፀር እና ኢንተርፕረነርሽፕ ደግሞ በአብዛኛው በአነስተኛና በመካከለኛ ደረጃ ውስጥ ያሉ ግለሰቦችና ቡድኖች የሚፈጥሩት ገደብ የሌለው እንቅስቃሴ በመሆኑ ከ1970ዎቹ ወዲህ ኢንተርፕረነርሽፕ አለምን የቀየረ ትልቅ የሀብት ምንጭ ነው የሚል የበለጠ ንቁህ የሆነ ግንዛቤ ፈጥሯል። 2ኛ/ ሰዎች የግል ሥራ ፈጠራ ላይ ይበልጥ ያዘነበሉበት ጊዜ ነው።

በ1980ዎቹ አካባቢ ለየት ያሉ ጥናቶች ተካሂደዋል። ጥናቶቹ ኢንተርፕረነሮች በየትኛውም ሥርዓትና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የተለየ ችሎታ ያላቸው መሆናቸውን አረጋግጠዋል። እነኝህ አለም አቀፍ ችሎታዎች ያሏቸው በርካታ ሰዎች ያሉባቸው አገሮች የኢንተርፕረነርሽፕ ግብአታቸው ሰፊ ነው። እነኚህ የኢንተርፕረነሪያል ችሎታዎች ያሏቸው ሰዎች ቁጥራቸው አነስተኛ የሆነባቸው ሀገሮች በእድገት ወደኋላ ቀርተዋል። የኢንተርፕረነርሽፕ ሂደት ዝቅተኛ መሠረት ባለባቸው ባላደጉ ሀገሮች ውስጥ በግብርናው፣ በግንባታው፣ በኢንዱስትሪው፣ በአገልግሎት ዘርፉና አሁን ደግሞ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂው ግስጋሴ ያላቸው ሚና ውስን ነው። በዚህ ውስጥ የገባው የሥራ ፈጣሪ የቢዝነስ ጎብረተሰብ ድርሻ በጣም አነስተኛ ነው።

ከዚህ እውነታዎች ጋር ተያይዞ ኋላቀርነትና እድገት ከኢንተርፕረነርሽፕ ጥሬ ሀብት መኖር አለመኖር ጋር ቀጥታ ግንኙነት አለው ተብሎ በፖለቲካ መሪዎች ደረጃም ከፍተኛ ግንዛቤ የተደረሰበት ዘመን ላይ ነን። ያደጉ ሀገሮች በተለይ ከ1980ዎቹ ወዲህ ደረጃቸውን የጠበቁ ተብለው የተቀመጡ የጋራ ዓለም አቀፍ ችሎታዎችን ያካተቱ ሥልጠናዎች ለየሀገሮቻቸው ህዝቦች በተለይም ለወጣቶችና ሴቶች ይሰጣሉ።

1.3 ለምች ወደ ቢዝነስ (ወደ ራሳቸው ሥራ ፈጠራ) ለምን ይገባሉ?

"There is a difference between interest and commitment. When you're interested in doing something, you do it only when it's convenient. When you are committed to something, you accept no excuses, only results."

Ken Blanchard

ብዙ ለምች ወደራሳቸው ሥራ ፈጠራ የሚገበሳቸውን ዋና ዋና ምክንያቶች በሚከተሉት ሁለት ክፍሎች ለይተን ማየት እንችላለን!

1.3.1 ዓላማዎች፡

1. የኢኮኖሚ ዓላማዎች፣
2. የግል ዓላማዎች
3. የጠረታ ጊዜ ዓላማዎች

1.3.2 በሌላ አመዳደብ

1. የግል ምቾትን ለመጠበቅ
2. የግል ዝናና ክብር ለማግኘት
3. የቤተሰብ ደህንነትን የበለጠ ለማስከበር
4. የግል ነፃነትን ለመቀዳጀት
5. ደስታን ለማግኘት

1.4 የዓለም ኢንተርፕረነሮች መርሆዎች

"If we did all the things we are capable of doing, we would really astound ourselves."

Thomas A. Edison

ዛሬ ዓለም የምትፈልገው የሚከተሉትን መርሆዎች የሚያሟሉ አንተርኘረነሮችን ነው፤

- ለራሳቸውና ለተፈጥሮ ታማኞች የሆኑ
- አዳዲስ ነገሮች የሚፈጥሩ፣
- ለመብት የሚቆሙ፣
- ለህብረተሰቡ ደህንነትየሚጠነቀቁ፣
- ለተነሱባቸውዓላማዎችየሚቆሙ፣
- በሚሰሩት ሥራ ትክክለኛነት የማይጠራጠሩ፣
- ባገኙት የማይኩራሩና የማይደናገጡ፣
- ቦታቸውን አውቀው ክፍተቱን የሚሞሉ፣
- ቢዝነሳቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁና የሚለሩ፣
- ጤነኞች የሆኑ፣
- ለመሥራት የማይሰንፉ፣
- ከህብረተሰቡ ጋር የሚበለፅጉ፣

የሚመሩና የሚያነሳሱ፣
ለውጦችን የሚያልሙ፣ እና
ለመርሆዎቻቸው ተገዢዎች የሆኑ

የአሜሪካ ኢንተርፕረነሮች ማህበር መርሆች

"Life is like a combination lock; your job is to find the right numbers, in the right order, so you can have anything you want."

Brain Tracy

የአሜሪካውያን ኢንተርፕረነሮች ማህበር የፀደቁ የኢንተርፕረነሮች መርሆዎች የሚከተሉት ናቸው፤

- ተራ ሰው ለመሆን አልመርጥም::
- ተራ ሰው አለመሆን መብቴ ነው:: ከቻልኩ አጋጣሚዎችን አፈላልጋለሁ እንጂ ቋሚ ቀስትና አልሻም:: የምጠብቅ፣ ቀላል ሆኜ የምገመት፣ መንግሥት አለልኝ ብየ የምመካ ዜጋ መሆን አልመኝም::
- አዋጪ ኃላፊነቶችን ለመውሰድ፣ ለማለም፣ ትልቅ ነገር ለማቋቋም ለመውደቅም ለመነሳትም እፈልጋለሁ::
- የራስን ተነሳሽነት ለትንሽ ጥቅም አልሸጠውም:: ዋስትና ካለው የማይለወጥ ህይወት ይልቅ ለወጦችን እመርጣለሁ::
- ነፃነቴን በምንም ዓይነት ጥቅም አልሸጠውም፤ ክብሬን ለምስክር ወረቀት አልለወጠውም::
- ለማንም አለቃ አልሰግድም፤ ለማንም ደግ አድራጊ ልቦና አንገቴን አልሰብርም::
- ቀጥ ብዬ መቆም ክብሬ ነው:: ሳልፈራ ኮራ ብዬ እሄዳለሁ:: አስቤ ለራሴ የተሻለውን አደርጋለሁ:: በፈጠርኳቸው ሥራዎች እደሰታለሁ፤ ዓለምን በድፍረት እቀበላታለሁ፤ ከእግዚአብሔር ጋር ይህን ሰርቻለሁ እላለሁ::

ኢንተርፕረነር መሆን ማለት የእነዚህ ሁሉ መርሆዎች ባለቤት መሆን ነው:: ኢንተርፕረነርሽፕ በአሜሪካ ኢኮኖሚ ዕድገት ቁልፍ የሀብት ዕድገት ምንጭ ነው:: ለዚህም በአሜሪካን ውስጥ ያሉት የትናንሽ ድርጅቶች (ቢዝነስ) ቁጥር ከጠቅላላው ሃገዝብ ጋር ያላቸው ጥምረት (Ratio) በየጊዜው እያደገ መምጣቱ ታይቷል:: እነዚህ 5% የሚያህሉ አንተርፕ ረነሮች /ሥራ ፈጣሪዎች/ በየዓመቱ 90% የሚሆነውን አዳዲስ የሥራ ዕድል ለአሜሪካውያን ይፈጥራሉ::

የኢትዮጵያ ኢንተርፕረነሮች ማህበር መርሆዎች (Non-Official Credo of Ethiopian Enterpreneurs Association)

"You must take personal responsibility. You cannot change the circumstances, the seasons, or the wind, but you can change yourself."

Jim Rohn

አትዮጵያ በ2020 ልትደርስበት ለማታለመው ርዕይ የሚከተሉትን መርሆዎች የሚያማሉ አንተርፕረነሮች ያስፈለንታል።

- በአእምሮ ሙሉ ነፃነት ያላቸው፣
- በማንኛውም ሥራ አርአያ ሆነው ሌሎችን ለሥራ የሚያነሳሱ፣
- ለብልጽግና ተጨማሪ ሥራዎችን ያለማቋረጥ የሚፈጥሩ፣
- በዘመናዊ የቢዝነስ ሥራ ውስጥ በይበልጥ የሚገቡ፣
- የድርጅት አሰራራቸውን እጅግ ዘመናዊ የሚያደርጉና በእቅድ የሚመሩ፣
- የበለጸገች ሀገርን ለመገንባት ግምባር ቀደም የሚሆኑ፣
- ተጨማሪ ወጣት አንተርፕረነሮች ለማፍራት ብዙ ወጪ የሚያደርጉ፣
- ራስን ከብክነት በመከላከል የሀገርን ሀብት የሚያሳድጉ፣
- በጋራ የመሥራት የሥራ ባህልንና ኃላፊነትን የሚያዳብሩ፣ እና
- ለተሻለ የሀገር ራዕይ የሚነሱና የኢትዮጵያን የኢኮኖሚ ተወዳዳሪነት የሚያሳድጉ።

ከ 1.4-1.6 በቀረቡ የአንተርፕረነሮች መርሆዎች የሚመሩ የቢዝነስ ሰዎች በብዛት የሚኖሩበት ዓለም ዕድገት ፈጣን ነው። በነዚህ መርሆዎች የታነጹ ብዙ ሥራ ፈጣሪዎች ያሏቸው ሀገሮች የብልፅግና ጉዞአቸው ፈጣን ነው። በእነዚህ መርሆዎች የሚመሩ የግሉ ኢኮኖሚ ተዋንያን ጥቂቶች የሆኑባቸው ሀገሮችም በስልጠና መሠረቱን ማሻሻል ይችላሉ።

1.7 የስኬታማ ኢንተርፕረነሮች ዓለምአቀፍ ችሎታዎች

"Ninety – nine percent of all failures come from people who have a habit of making execuses."

George Washington

ከ1960ዎቹ ወዲህ በኢንተርፕረነሮች ችሎታዎች ላይ ጥናቶች ተካሂደዋል። ከነዚህም ውስጥ በተባበሩት መንግሥታት በኩል ማኔጅመንት ሲስተም ኢንተርናሽናል ለአምስት ዓመታት በብዙ ሀገሮች ባደረገው ጥናት አስር የጋራ የሆኑ የስኬታማነት ችሎታዎች ወጥተዋል። ብዙዎቹ ሥራ ፈጣሪዎች ሲወድቁ፤ ጥቂቶች ስኬታማ የሆኑት በነዚህ ችሎታዎች ምክንያት እንደሆነ ጥናቱ ገልጿል። እነዚህም ችሎታዎች በሦስት ዋና ዋና ቡድኖች ተመድበዋል፤

1. የተነሳሽነት ችሎታዎች (achievement cluster)፣ **የተጠና ኃላፊነት እርምጃ መውሰድ** (risk taking)፣ **ምቹ አጋጣሚዎችን መጠቀም** (opportinity seeking)፣ **ፅናት** (persistence)፣ **ቃልን/ውልን ማክበር** (commitment to the work of contracts)፣ **ዘላቂ ውጤታማነት እና ጥራትን መፈለግ** (demand for efficiency and quality)
2. **የማቀድ ችሎታዎች** (planning cluster)፣ **ግልጽ ዓላማ ማስቀመጥ** (goal setting)፣ **መረጃ ማፈላለግ** (information seeking)፣ **ስልታዊ እቅድና ክትትል መኖር** (systematic planning and monitoring)፣

ኔ የመፈፀም ችሎታዎች ናቸው (power cluster) ሌሎችን ማላመንና ሰፊ ግንኙት መኖር (persuationn and networking) እንዲሁም ራስን መቻል፣ የግል ነፃነትና በራስ መተማመን (indepndnce and self-confidence) ናቸው::

እነዚህ ችሎታዎች ቀደም ሲል እንዳየነው ከ1960ዎቹ ጀምሮ የተገኙ፣ በ1970ዎቹ በሌሎች ጥናቶች የተረጋገጠ ሆነው ከ1980ዎቹ ወዲህ ደግሞ የሁሉም ችሎታዎች መገለጫዎች የሆኑ ሦስት ባህሪያት በድምሩ ሰላሳ ባህሪያት ተጨምረውባቸዋል::

ለኩባማ ኢንተርንረነሮች ከነዚህ ችሎታዎችና ባህሪያት ብዙዎቹን የያዙ የቢዝነስ ሰዎች ናቸው::

በመሆኑም ኢንተርንረነሮች፣

- በራሳቸው የሚጀምሩ፣ ውሳኔን መወሰን የሚችሉ፣ ኃላፊነትን የሚወስዱ፣ ተነሳሽነት ያላቸው፣ ውድቀት ሲያጋጥማቸው በፅናት የሚወጡ ነገር ግን ከስህተታቸውየሚማሩና ለኩባቸውንየሚያሳድጉ መሆኑ፣
- ሀይወታቸውንና አካባቢያቸውን መቆጣጠር የሚችሉ፣
- ጠንክረው በብርታት የሚሰሩ፣
- ችግርን መፍታት የሚችሉ፣ ችግሮችን ቀድመው የሚያውቁና አጋጣሚዎችን የሚጠቀሙ፣
- አላማና ስኬት ተኮር የሆኑ፣ ገንዘብን ሳይሆን ነፃነትን አላማቸውና ህልማቸው አድርገው የሚሰሩ፣
- አዳዲስ ነገሮችን የሚፈጥሩ፣ አዳዲስ ነገሮችን ሲሞክሩ አዳዲስ መፍትሄዎችንለመተግበር የቆዩ ችግሮችን ለመቅረፍ ፈቃደኞች የሚሆኑ፣
- በሥራ የሚያድጉና የት እንደሚደርሱ የሚያውቁ ናቸው::

"You will never become successful as long as you continue to blame someone or something else for your lack of success."

Jack Canfield

ለሁለት መቶ ዓመታት ከቆየው ከኢንተርኘረነርሽኘ ፅንሰ ሃሳብ ፅድገት የተወለደውና ዛሬ ትልቅ እውቅና የተሰጠው ሌላው ፅንሰ ሀሳብ ኢንትራኘረነርሽኘ ነው:: ኢንትራኘረነርሽኘ በሌሎች በተቋቋሙ የራሳቸው ባልሆኑ የግል/የመንግስት ተቋማትና ኮርፖሬሽኖች ውስጥ የተሻለ ፈጠራ የመሥራትና ለውጥ/ፅድገት የማስመገገብ ሂደት ነው:: አዳዲስ አጋጣሚዎችን በማየትና ያሉትን የምርት ግብዐቶች በተሻለ መንገድ በማቀናጀት የተጀመረ ድርጅትን የማስፋፋት/ የማሳደግ ሂደት ነው::

ኢንትራኘረነሮች የሚባሉት የሰለጠኑ ባለሙያ የሆኑ የኢንተርኘረነሮች ክህሎቶችና ባህሪዎች ያሏቸው ተቀጣሪ የሆኑባቸውን ድርጅቶችን የሚያሳድጉ ሌሎች የበላይ አለቆችና ባለቤቶች ያሉባቸው ሥራ መሪዎች ናቸው::

ይህ ፅንሰ ሃሳብ በአሁኑ ጊዜ ሌሎች በየክፍሉ ያሉ ታታሪ፣ ታማኝና የተለየ ውጤት በየተቀጠሩባቸው የመንግስትም ሆነ የግል ተቋማት የሚያስመዘግቡ ሠራተኞችም በማካተት ላይ ይገኛል። የኢንትራፕረነሮች ቁጥር ማላደግ ለመንግሥትም ሆነ መንግሥታዊ ላልሆኑና በተለይ ለግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ መሻሻል ዓይነተኛ ሚና ይጫወታል።

1.9. ኢንተራፕረነርሽፕና ልማት

"Decide upon your major definite purpose in life and then organize all your activities around it."

Brain Tracy

የሀገራት ዕድገትና ልማት ከዕውቀት፣ ከሙያ፣ ከሀብት ፈጠራ፣ ከቴክኖሎጂ ግስጋሴ፣ ጉልህ ከሆነ የኑሮ ደረጃ ለውጥና መሻሻል ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት አለው።

ልማት ከምንም በላይ በዕውቀትና በሥራ የበለፀገ የሕዝብ አዕምሮና አስተሳሰብ ባለቤትነት ነው። ልማት የበለፀገ የፈጠራ ተነሳሽነት ያለው የሕዝብ አዕምሮ ነው። ይህ የበለፀገ የሕዝብ አዕምሮ አዳዲስ የፈጠራ ወጤቶችን፣ የማያቋርጥ ሥራ ሀብትና መሻሻል ይፈጥራል። ከብዙ የፈጠራ ሥራዎች ገቢ በየዓመቱ በደመወዝና በግብር መልክ ለሀገር የሚከፈለው ገንዘብ እየጨመረ ይሄዳል።

ከሀገር የገቢ ምንጮች ማደግ ጋር ተያይዘው የኢኮኖሚና የማህበራዊ ልማት አውታሮች (መገናኛ፣ ትምህርት፣ ጤና፣ መብራት፣ ስልክ፣ ውኃ፣ ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ሌሎችም) ግንባታዎች ስርጭት ይፋጠናሉ።

የተፋጠነ የልማት እንቅስቃሴ ያላቸው ሀገሮች የህዝባቸው በራስ የመተማመን የአስተሳሰብ ደረጃ ያድጋል። የተፋጠነ የልማት እንቅስቃሴ የአስተሳሰብ፣ የገንዘብ፣ የማቴሪያልና የፈጠራ ምንጮች በአብዛኛው ኢንተርፕረነሮች ናቸው። በዓለማችንና በአህጉራችን ብዙ ኢንተርፕረነሮች ያሉባቸውና ያልለሙ (ያላደጉ)፣ ጥቂት ኢንተርፕረነሮች ኖረውባቸው ደግሞ ያደጉ (የበለፀጉ) የሚባሉ ሀገሮች የሉም።

ስለዚህ ሀገሮችን ለማልማት የለማ አዕምሮ ያለው ህብረተሰብ ያስፈልጋል። ለልማት ኢንተርፕረነሮችና ኢንትራፕረነሮች ግምባር ቀደም ድርሻ ያላቸው ናቸው።

2. የኢንተርፕረነርሽፕ አበረታች ወይም ገቺ ሁኔታዎች

"All blame is a waste of time. No matter how many faults you find with another, and regardless of how much you blame him, it will not change you."

Wayne Oyer

አራቱም የምርት ግብዐቶች መሬት፣ የሰው ኃይል፣ ካፒታልና ኢንተርፕረነርሽፕ ከማንኛውም ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ክስተቶች ቁጥጥር ወጪ አይደሉም። የትኞቹም የሰው ልጅ እንቅስቃሴዎች ለግብዐቶቹ ዕድገትና መሻሻል አሉታዊ ወይም አዎንታዊ ተፅዕኖዎች አሏቸው።

ከዝህም ውስጥ በተለይ በለፈው በዓለም ሕገብ የተለያዩ ክፍል ህብረተሰብ የዘወትር አመለካከት፣ አሠራርና አኗኗር መሰረት የሚከተሉትን 10 አበረታች/ገቺ ሁኔታዎች እናያለን፤

2.1 የሥራ ባህል እምነትና ልምድ ሁኔታዎች

"If you keep on doing what you've always done, you'll keep on getting what you've always got."

Jack Canfield

ሥራን የሚያበረታቱ - ሥራን የሚያንኪስሱ/የሚንቁ፣ ሠራተኛውን ክፍል የማያበረታቱ ሁኔታዎች መኖር/አለመኖር፣

- የሥራን ፍሬ በአግባቡ የመጠቀም/ያለመጠቀም ልምዶችና ግፊቶች፣
- ጠንክር የመስራት/አለመስራት ተነሳሽነት መኖር/አለመኖር፣
- ትግርትን ተቋቁሞ ለወጤት መብቃት/አለመብቃትና በእድል ማሳበብ/ አለማሳበብ፣
- ራስን ለከፍተኛ ቦታ ብቁ ማድረግ/ያለማድረግ እምነትና ልምድ፣
- ከዓመት አመት አሠራርን፣ አኗኗርን፣ በራስ መተማመንን እያሳደጉ፣ ራስን መቻልን እያዳበሩ መሄድ/አለመሄድ፣
- ነባር የአሰራር ባህሎችን በዘመናዊ አሰራሮች የመተካት ተነሳሽነትና ጥረቶች መኖር/ አለመኖር ፣
- የሥራ ክፍፍል፣ ኃላፊነቶችና ግዴታዎች ሰፊ መሠረት መያዝ/አለመያዝ፣
- ቀናና ፍትሃዊ የሥራ ውድድሮች ባሕል መኖር/ አለመኖር፣
- ሥራ የማያሰሩ ባህላዊና የእምነት እንቅፋቶች መኖር/ አለመኖርና ሌሎችም ይገኙበታል።

ከእነዚህ የሥራ ባህሎች፣ እምነቶችና ልምዶች ውስጥ በጎ የሆኑት ጎኖች በሚጐለብት ህብረተሰብ ውስጥ የኢንተርፕረነርሽፕ ግብዓት እንዲሻሻል ሲያበረታቱ በጎ ያልሆኑት ተዕዕኖዎች የሚበዛባቸው ደግሞ ግብዐቱ እንዳይጠናከር እንቅፋት ይሆናሉ።

2.2 ትምህርት፣ ስልጠናና ሙያ

"Create your future from your future, not your past."

Werner Erhard

የህብረተሰቡ ዕውቀትና አስተሳሰብ ባደገባቸው ሀገሮች የኢንተርፕረነርሽፕ ዕድገት መሰረቱ ይጠናከራል። ከዕውቀትና ሙያ መስፋፋት ጋር የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎችና የገቢ መፍጠሪያ ውድድሮች ይኖራሉ። የሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት መስፋፋት ዘመናዊ አሰራሮችን፣ ያልነበሩ እንቅስቃሴዎችን ለመጀመር ያስችላለ። በየጊዜው በሚፈጠሩትን የተሻሉ ምርቶችና አገልግሎቶች ለመጠቀም ዝንባሌ አቅምና ጣዕም ያለው የህብረተሰብ ክፍል እየጨመረ ሲመጣ በዚያው መጠን የኢንተርፕረነርሽፕ ዕድገትም ይፋጠናል። በተቃራኒው በትምህርት፣ በሙያ ስልጠናዎች፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ዕድገት ዝቅተኛ ደረጃ ባላቸው ሀገሮች ደግሞ የዚያኑ ያህል ዝቅተኛ የሆነ የኢንተርፕረነርሽፕ ግብዓት ይኖራል።

የተማረና ዕውቀት ያለው ህብረተሰብ ፍላጎቱ የበዛ፣ ተጨማሪ ፍላጎትን የሚወልድ የተሻለ የሚያረኩትን ምርቶችና አገልግሎቶች በመፍጠር ለተሻለ ኑሮ የሚያነሳሳ ስለሆነ በነዚህ

ሀገሮች አዳዲስ ነገሮች የመፍጠር ጥረት በየጊዜው እየጨመረ ስለሚሄድ የማያቋርጡ ውድድሮች ይኖራሉ። የማያቋርጡ ውድድሮችና ሥራ ፈጠራዎችም የተሻለ ሀብትና ብልጽግና ምንጮች በመሆናቸው እነዚህ ዓይነት ሰዎች የበዙባቸው ሀገሮች ዕድገታቸው ከዓመት ዓመት ከፍ ይላል።

2.3 የኢኮኖሚና ማህበራዊ መሠረተ ልማቶች ዕድገት

"You weren't an ancient. You weren't mass produce, you aren't an assembly – line product. You were deliberately planned, specifically gifted, and lovingly positioned on the earth by the Master Crafts man."
Max Luncado

የኢኮኖሚ መሠረታዊ ልማቶች (ጤና፣ ትምህርት፣ ባንኮች፣ ኢንሹራንሶች፣ የመገናኛ አውታሮች እና የማህበራዊ መሠረተ ልማቶች ስልክ፣ መብራት፣ ውሀ፣ ብዙሀን መገናኛዎች) ያላደገና ኋላ ቀር መሆን በኢንተርፕረነርሽፕ ዕድገት፣ ውጤታማ መሆንና አለመሆን ላይ ብርቱ ተፅዕኖዎች አሉዋቸው።

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት በተስፋፋባቸው ሀገሮች በርካታ የግል ስራዎች በየዓመቱ ይፈጠራሉ። በየዓመቱ በሚፈጠሩት አዳዲስ ሥራዎች ለሥራ የደረሱ የራሳቸውን ሥራ ያልፈጠሩ ሰዎች ተቀጥረው የገቢ ምንጭ ያገኙባቸዋል። ኋላቀር የኢኮኖሚ ዘርፎች በአዳዲስ እንቅስቃሴዎች ይተካሉ። አዳዲስ የሥራና የፈጠራ አጋጣሚዎችና ውድድሮች ይፈጠራሉ። ልዩ የሆኑት ምርቶችና አገልግሎቶች ገበያውን እያሸነፉ ስለሚሄዱ የማያቋርጡ የፈጠራ ሥራዎችና ለውጦች ይመዘገባሉ። ብዙ ገበያ ያላቸው የሥራና የፈጠራ ውጤቶችም ሰፊ የብልፅግና መሠረቶች ይዘረጋሉ። ኢንተርፕረነሮች በሚያድግ ኢኮኖሚ ውስጥ አብረውና ቀድመው ያድጋሉ።

እነዚህ ከላይ የተገለፁትን በማያስመዘግቡ ሀገሮች የኢንተርፕረነሮች ዕድገት ኮስማና ይሆናል።

2.4 የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና የአስፈፃሚዎች ብቃት

የኢኮኖሚ ፖሊሲዎች ግልጽነት፣ ነፃና ፍትሐዊ የሆነ የግል የገበያ ውድድርን መፍጠር/ መቻል/ አለመቻል፣ ለሰሩት ለፈጠሩት ውጤት ህጋዊ ከለላ ማግኘት አለማግኘት፣ ለበለጠ የካፒታል ፈጠራ አቅም ግንባታ ማበረታቻ ያለው/የሌለው መሆን፣ የብድር፣ የዋስትና መጠንና ለፈጠራ ስራዎች - ለዘመናዊ የኢኮኖሚ ዘርፎች ማበረታቻ መኖር/አለመኖር፣ የኢንቨስትመንትና የካፒታል እንዲሁም የትርፍና የግብር አከፋፈል አበረታች መሆን አለመሆን፣ የሚወጡ ፖሊሲዎችን የሚያስፈፅሙ አካላት በለው ኃይል፣ በግንዛቤና በቁላቁል የተደራጁ መሆን/አለመሆን፣ ዘመኑ የስራ ፈጣሪዎች - (an era of entrepreneurs) የሆነበት ደረጃ ላይ የተደረሰበት መሆኑን የተገነዘበ ፖሊሲ መኖር/አለመኖር በኢንተርፕረነሮች ዕድገት ላይ ቁልፍ ተፅዕኖዎች ያደርጋሉ።

ሕዝብን የተሻለ የሚያሰራ ሥራ ፈጣሪዎችን የበለጠ የሚያበረታታ የኢኮኖሚ ፖሊሲዎችና ብቁ አስፈፃሚዎች ያሉባቸው ሀገራት ለነባርና አዳዲስ ኢንተርፕረነሮች መጠናከር በጎ አስተዋጽዖ ሲኖራቸው ከዚህ በተቃራኒው ያሉት ደግሞ አሉታዊ ጎናቸው ይበዛል።

የፖለቲካ ሥርዓትና መልካም አስተዳደር ሁኔታ

"...the same level of thinking that created them cannot solve the significant problems we face."

Albert Einstein

የሠራተኛን የፈጠራ ውጤት ተጠቃሚነትና የግል ባለቤትነት የሚያበረታታ የፖለቲካ ሥርዓት በርካታ ሥራ ፈጣሪዎችንና ተወዳዳሪዎችን ያፈራል። ሕዝብን ለተሻለ ሀብት ማፍራት ያነሳሳል።

በነፃ የቢዝነስ ሀሳብን ወደ ተግባር ለመለወጥ ገደብ የማይጥል፣ የሠሩትን የማይወርስ፣ የሥራ ተነሳሽነትን የማያዳክም ፍትሀዊ ስርዓት ለኢንኮርኘረነርሽኘ ግብዐት ዕድገት ምቹ የሆነ። የመንግሥትና የህዝብ ሥራና ይዞታ ተለይተው በውል በሥርዓት ባልተመጠባቸውና በማይተገበሩባቸው ሀገሮች ደግሞ ለግል ሥራ ፈጣሪዎች የሚመቹ ሁኔታዎች አይኖሩም። ዋናው የፖለቲካ ሥርዓቱ ለብዓዊ መብቶች ሲያስከብር፣ ለው ሊሰራ የሚችለው ሙያና ገንባሌው ገብቶ የመስራትና የውጤቱም ተጠቃሚ መሆኑ ሲያረጋግጥ ከፍተኛ ሀብት የሚፈጥር ውስጣዊ ተነሳሽነት ይኖራል።

መልካም አስተዳደር - ፍትህ፣ እኩልነት፣ ነፃ ውድድር፣ በጥረት መኖርና ማደግ፣ በዘር፣ በቀለም፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ፓርቲ ሳያሳብቡ - ሀገርን የተሻለ የማስተዳደር ችሎታ ነው።

መልካም አስተዳደር በአብዛኛው ህዝብ አስተሳሰብ አዕምሮ ውስጥ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ታማኝነት ያለው አራቱን የምርት ግብዐቶች በጥንቃቄ የሚያስተዳድርና ለዕድገት፣ ለብልፅግና መሻሻል የሚያበቃ የአመራር ብቃት ነው።

መልካም አስተዳደር ያለውን የሀገራቱን ጥሬት በመቆጠብ የተሻለ ዕድገት በሚያመጡ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ዘርፍ እንቅስቃሴዎች ላይ ትልቁን ትኩረት የማድረግ ችሎታ ነው።

መልካም አስተዳደር የሰላም ምንጭ ስለሆነ የህዝብን አዕምሮ ሰላማዊ ያደርጋል። ለሥራ ያነሳሳል። የሀገርንና የህዝብን ሀብት ከብክነት ይጠብቃል።

መልካም አስተዳደር በራሱ የሚተማመን፣ በራሱ የሚመራ ትግር ፈች የሆነ ህብረተሰብ ይፈጥራል።

መልካም አስተዳደር ከሙስናና ከበቀል የፀዳ ሆኖ የበለጠ ጊዜውን ለመጪው ጊዜ ዕድገትና መሻሻል ላይ ያደርጋል።

መልካም አስተዳደር የሀገርን ጥቅምና ክብር ያስጠብቃል። የዜጎቹን መብት ያስከብራል።

መልካም አስተዳደር ትድሚያ ተግባሩ ብሔራዊ ትግር መቅረፍና የህብረተሰብንና የሀገር አቅምን ማሳደግ ነው።

መልካም አስተዳደር - ቀና፣ ታታሪ፣ ሀገር ወዳድ፣ ህዝብ አክባሪ፣ ሀቀኛ፣ የአመራር ችሎታና ራዕይ ያላቸው የፖለቲካና የአስተዳደር መሪዎች ያሉት ሥርዓት ነው።

መልካም አስተዳደር በእውነተኛ የጥረትና የላብ ዋጋቸው የሚኖሩ ዜጎችን ቁጥር የሚያሳድግ አርአያነቱ ምንጊዜም ከህዝብ አዕምሮ የማይወጣ - ለተተኪው ትውልድ የተሻለ የኢኮኖሚና የማህበራዊ መሠረቶችን አስፍኖ መጪውን ጊዜ ተናፋቂ የሚያደርግ ታላቅ ራዕይ ያለው አመራር ነው።

መልካም አስተዳደር የፍትሕና የዳኝነት ሥራ ተስተካክሎ የሚሰራበት፣ ፈጣን ውሳኔዎች የሚሰጥበትና የማስፈፀም ብቃት ያለበት አመራር ነው።

እነዚህ ከላይ የተገለፀትና ሌሎቹም የመልካም አስተዳደር መገለጫዎች በዝተው በሚገኝ ባቸው ሀገሮች የኢንተርፕረነርሽፕ ዕድገት ይፋጠናል። የበሐራዊ ሥራ ፈጣሪዎች ቁጥር ይጨምራል። የሌላ ሀገር ኢንቨስተሮችን ይጋብዛል። ጥሩ ብሄራዊና አለምዓቀፋዊ ወድድሮች ውስጥ የሚያስገቡ የቢዝነስ ልምዶች ስለሚፈጥር ኢንተርፕረነርሽፕ ዕድገቱ ይሰፋል።

ከዚህ ተቃራኒ በሆኑ የፖለቲካ ሥርዓት የሚኖሩና በመልካም አስተዳደር ዕጦት በሚለቃቹ ሀገሮች ደግሞ የኢንተርፕረነርሽፕ ዕድገት ይቀጭጫል።

2.6 የሕዝብ ብዛት

"If you want to be happy set a goal that commands your thoughts, liberates your energy, and inspires your hopes."

Andrew Carnegie – The richest man in America in the early 1900s

የተማሩ፣ ዕውቀትና ሙያ ያላቸው የራሳቸው አስተማማኝ ገቢ ያላቸው፣ በኢኮኖሚ ነፃ የሆኑ ብዙ ሠራተኞች፣ ሻጮችና ሸማቾች የሚበዙባቸው ሀገራት ለኢንተርፕረነርሽፕ ማደግ ከፍተኛ አስተዋጽዖ ያደርጋለ።

ብዙ ያልተማሩ፣ ዕውቀትና ሙያ የሌላቸው፣ የራሳቸው የሆነ አስተማማኝ የገቢ ምንጭ/ሥራ የሌላቸው፣ በላተኞች በበዙባቸው ሀገሮች ደግሞ የኢንተርፕረነርሽፕ እንቅስቃሴ ጎልቶ አይታይም። የሕዝብ ብዛት ሀብት የሚሆነው በዚህ አንቀጽ መግቢያ ላይ ያሉትን መመዘኛዎች ሲያሟሉ ማለትም ትክክለኛ ሥራ የሚሰራውና ራሱን የሚያሻሽለው የህብረተሰብ ቁጥር ለተከታይ ሕዝብ የተሻለ የኢኮኖሚ መሠረትና አቅም በየጊዜው የሚገነባ ሲሆን ነው።

ከዚህ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት የየትኛውም ሀገር ትልቅ ሀብት የላቀ አስተሳሰብ የሥራ ተነሳሽነት ያለው ህዝብ መሆኑን ነው። የፈጠራ ውጤት የሀብት ባለቤት የሆነ ህዝብ ታላቅ የሀገር ሪሶርስ ነው። ትልቁ ሀብት የተሻለ ለመኖር የተሻለ መሥራቱ ነው። የነገውን ህይወቱን ከትላንት የተሻለች ለማድረግ የሚያደርገው ጥረቱ ነው። ባለው መሠረት ላይ አዲስ የዕድገት ደረጃ የሚያስመዘግብ ሕዝብ የተሻለች ሀገር ትኖረዋለች - የተሻሉ የሥራ ፈጣሪዎችም ይኖሩታል። በደንብ ሠርቶ የተሻለ ኑሮ፣ የሚኖር ትውልድ ተክቶ የሚያልፍ ሕዝብ የኢንተርፕረነርሽፕ እውነተኛ ምንጭ ነው።

ከዚህ ላይ ሳይጠቀስ መታለፍ የሌለበት የየትኛውም ሀገር ትልቅ ሀብት የላቀ አስተሳሰብ የሥራ ተነሳሽነት ያለው ህዝብ መሆኑን ነው። የፈጠራ ውጤት የሀብት ባለቤት የሆነ ህዝብ ታላቅ የሀገር ሪሶርስ ነው። ትልቁ ሀብት የተሻለ ለመኖር የተሻለ መሥራቱ ነው። የነገውን ህይወቱን ከትላንት የተሻለች ለማድረግ የሚያደርገው ጥረቱ ነው። ባለው መሠረት ላይ አዲስ የዕድገት ደረጃ የሚያስመዘግብ ሕዝብ የተሻለች ሀገር ትኖረዋለች - የተሻሉ የሥራ ፈጣሪዎችም ይኖሩታል። በደንብ ሠርቶ የተሻለ ኑሮ፣ የሚኖር ትውልድ ተክቶ የሚያልፍ ሕዝብ የኢንተርፕረነርሽፕ እውነተኛ ምንጭ ነው።

አሜሪካውያን ወላጆች እንዲህ ይላሉ፤ «ልጆቻችን ከኛ የተሻሉ የሆኑት ከኛ የተለየ ተአምር ፈጥረው አይደለም:: በእኛና በእኛም ወላጆች ጥሩ መነሻ ስለተፈጠረላቸው ነው» ይላሉ::

የብዙሀን ማስተማሪያዎችና መገናኛ ብዙሀን ትኩረትና ሽፋን

"Talent is cheaper than table salt. What separates the talented individual from the successful one is a lot of hard work."

Stephen King

የብዙሃን ማስተማሪያዎች፤ ቴሌቪዥን፣ ሬዲዮ፣ ጋዜጦች፣ መፃህፍትና፣ መጽሔቶች ለህይወት የሚጠቅሙ መረጃዎችን፣ ልምዶችን፣ ዕውቀትንና ሌሎችንም ሙከራዎች እያዝናኑ ለህዝብ የሚያስተዋውቁ መድረኮች ናቸው::

በየሀገሮቹ ብዙ የግል የቴሌቭዥን፣ የሬዲዮና የሌሎቹም መገናኛዎች ብዛትና ትኩረት በሥራ ፈጠራ፣ በመረጃ ስርጭት፣ ዕውቀትና ሙያን በማስተላለፍ፣ ልምድን በማካፈል ከፍተኛ አስተዋጽዖ አላቸው::

የዓለም ሀገራት እነዚህን ቁምነገሮች በቢዝነስ መልክ ሆነ በሌላ መልክ ለህዝብ የሚቀርቡ መልዕክቶችን ለማስተላለፍ 24 ሰዓት የሚሰሩ ብዙ የግል ቴሌቪዥንና ሬዲዮ ጣቢያዎች እንዲሁም የህትመት ሥራዎች ያስፈልጓቸዋል::

ዓለም በኪነጥበብ፣ በሥነ ጽሁፍ፣ በቴክኖሎጂና በሌሎቹም ኢንዱስትሪዎችና የህይወት ዘርፍ ፈጠራዎች፤ ያፈሯቸውን አዳዲስ ምርቶችና አገልግሎቶች ለማሰራጨትና ለማስተዋወቅ ብዙ የመገናኛ አውታሮች ያስፈልጓታል:: በነዚህ እንቅስቃሴዎች ሂደት ውስጥም የሥራ ፈጠራ ውጤቶችና ሀብት በብዙ ቁጥር የበለጠ ይፈጠራል::

ይህ አውታር ራሱ አንዱ ሰፊ የሥራ፣ የፈጠራ የዕድገትና የገቢ ምንጭ ከመሆን አልፎ በሚያስራጫቸው መረጃዎችና ትምህርቶች ሌሎቹን ለተሻለ ህይወት ያነሳሳል:: የዘርፉ መስፋፋት ኢንተርፕረነርሽፕ እንዲያድግ፣ አዳዲስ ሥራ ፈጣሪዎች እንዲፈልቁ ያግዛል::

የህዝብ የተለያዩ መገናኛ ብዙሀን ተጠቃሚ መሆን አንዱ የኢኮኖሚ አቅም እድገት መገለጫ ነው:: የዳበረ መገናኛ ብዙኃን የስልጣኔና የብስለት ደረጃ መሻሻል መኖርን ያሳያል::

መገናኛ ብዙኃን ከብዙ ኘሮግራሞቻቸው መካከል የየዘርፉን የሥራ ፈጣሪ አሸናፊ ጀግኖች ውጣ ውረዶች፣ ልምዶችና ስኬቶች ለህዝብ ያስተዋውቃሉ፣ ያስተምራሉ:: ብዙ ሰዎች አርአያ የሚሆኗቸውን ሞዴሎቻቸውን እንዲያገኙ ይረዳል::

በመሆኑም ሰፋፊ የግል መገናኛ ብዙኃንና የህትመት ሥራዎች ያሏቸው ሀገሮች የተሻለ የኢንተርኘረነርሽኘ መሠረት አላቸው:: ይህን አጋጣሚ ያልፈጠሩ ሀገሮች ደግሞ የብዙ የገቢና የሥራ ዕድሎች ከማጣታቸውም በላይ ህዝብ የመረጃ ማግኘት መብቱን እንኳን የማያስከብሩ ይሆናሉ:: በነዚህ ሀገሮች ውስጥ የኢንተርኘረነርሽኘ ዕድገት ሚና ጎልቶ አይታይም:: በዘርፉ ሊያድግ የሚገባው ሂደት ብዙ ውድድር ስለማይታይበት ይቀጭጫል::

2.8 የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ

"It is not the will to win that matters – every one has that. It's the will to prepare to win that matter."
Paul "Bear" Bryant

ብዙ የሥራና የገቢ መፍጠሪያ እንቅስቃሴዎች ላይ የተሰማሩ፣ ብዙ የሚያተርፉ፣ ከትርፋቸውና ዘለቄታዊ ሥራቸው የሚከፍሉት የትርፍ ግብር መጠን እያደገ የሀገርን ሀብትና ካፒታል በጉልህ የሚያሳድጉ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተዋንያን ቁጥር ከህብረተሰባቸው ውስጥ በየጊዜው እየጨመረ በሚሄድባቸው አገሮች፤ ወድድሩና ልምዱ እንዲሁም ዕድገቱ የኢንተርፕረነርሽፕን መሠረት ያሰፋል።

በተለይም ከቢዝነሱ ህብረተሰብ መካከል ኢንተርፕረነሮች (አለምዓቀፍ ችሎታዎችን በይበልጥ የሚያሟሉ) ጥሩ ቁጥር ያላቸው ሆነው ሲገኙ - ብዙ የኢኮኖሚ ዘርፎች ቀጣይነት ይኖራቸዋል።

ራሳቸውን ችለው የሚሰሩ፣ ፍትሀዊ በሆነ ውድድር የሚያሸንፉ የቢዝነስ ሰዎች ሲበዙ ሀገርን ሊያሳድግ የሚችል የቢዝነስ የሥራ ባሕል ይፈጠራል። ጥሩ የቢዝነስ ባሕል ብዙ አብረው የሚሰሩ የቢዝነስ ሰዎችን፣ አብረው የሚያድጉ ሥራ ፈጣሪዎችን ይፈጥራል።

የቢዝነስ ሥራ ጥበብ ነው። ብዙ ክህሎቶች አንድ ሰው ላይ ተሟልተው እንዲገኙ የሚያስገድድ ሙያ ነው። ቢዝነስ እንደማንኛውም ሙያ አሸናፊ ተወዳዳሪ ለመሆን ቀጣይ ትምህርት፣ የማያቋርጥ ስልጠና፣ ንባብ፣ የልምድ ልውውጥና መረጃ ያስፈልጉታል። በዚህም መሻሻል የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ተዋንያን የማያቋርጥ ሥራ ፈጣሪዎችና አሸናፊዎች ይሆናሉ።

የንግድ ምክር ቤቶቻቸው የጥናትና የምርምር ማዕከላት የብድርና የመረጃ ስርጭት ምንጮቻቸው፣ የምክር አገልግሎት መድረኮች ይሆኗቸዋል።

በዘመናዊ የኢኮኖሚ ዘርፎች - በኢንዱስትሪው፤ በሳይንስና ቴክኖሎጂው፤ በመጠቀ የአገልግሎት ዘርፎች ላይ ማተኮራቸው ሌላው የዕድገት መሠረት ነው። የቢዝነስ ሰዎች በጠንካራ ዲሲፕሊን ራሳቸውን፣ ሥራቸውን፣ ትርፋቸውን ሲጠብቁና ከብክነት ሲድኑ፤ የማደግ ተስፋቸው ከፍ ይላል። ከዚህ ውጭ ሲሆን ተስፋቸው ያንሳል። ብዙ ተስፋ ያላቸው ቢዝነስ ሰዎች ጥሩ የኢንተርፕረነሮች ምንጭ ሲሆኑ፤ ከዚህ ውጭ ከሆኑት የሚገኙት አነስተኛ ቁጥር ይኖራቸዋል።

3. ኢንተርፕረነርሽፕና ልማት በኢትዮጵያ ርዕይ 2020

"The greater danger for most of us is not that our aim is too high and we miss it, but that it is too low and we reach it."

Michael Angelo

በ2020 ኢትዮጵያ በኢንተርፕረነርሽፕ ጥሬ ሀብት ዕድገት፣ በህዝቧ የሥራ ትጋትና ሀብት ፈጠራ ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ካላቸው ሀገሮች ምድብ ትወጣለች።

ኢትዮጵያ በ2020 ከሠራተኛ ሀገሀቡ መካከል 2% የሰለጠኑ ኢንተርፕረነሮች ይኖሯታል። በነዚህ ሥራ ፈጣሪዎች አዳዲስ ሥራዎችና ሀብት ፈጣሪ እንቅስቃሴ ዋናነትና በሌሎች አርአያነት ተከትመው በሚሰሩ የቢዝነስ ሰዎችና ሠራተኞች ውጤት የተሻለ የኢኮኖሚ ዕድገት ያላት ሀገር ትሆናለች። ያለ ዕርዳታ ህዝቧን የምትመግብ፣ የምታስተምር፣ የምታክም፣ በራሱ ኢኮኖሚ ዕድገት የምትተማመን ሀገር ትሆናለች። ኢትዮጵያውያን ዋጋውና መስዋዕትነቱ ቀላል የሆነው ማለትም ራስን ለውጦ ሠርቶ ለማደግ ለራስ የሚተርፍ ለትውልድ የሚተላለፍ አዲስ የሥራ ባህልና ሀብት እንፈጥራለን።

የዚህ ርዕይ ዝርዝር ፈላሚዎችና አፈፃፀሙ በክፍል 5 ቀርቧል።

4. ኢንተርፕረነርሽፕ በኢትዮጵያ

"If you are bored with life, if you don't get up every morning with a burning desire to do things – you don't have enough goals."

Loo HoHz

በኢትዮጵያ የኢንተርፕረነርሽፕ ጥሬ ሀብት እጅግ ገቅተኛ በሆነ ደረጃ ላይ ይገኛል። ኢትዮጵያ ቀደም ሲል በ1.7 በተዘረዘሩት ኢንተርፕረነሮች አመዳደብ በተቀመጡት ክፍሎች ሁሉ በጣም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ኢንተርፕረነሮች አሏት። የሀገሪቱ ኋላቀርነት ከግብርና ኢኮኖሚ ባህላዊ አሰራር ጋር ከፍተኛ ተያያዥነት አለው። ይህ ጥንታዊ የኢኮኖሚ ክፍል በኋላቀር ዘይዎች በአብዛኛው በልማድ የሚሰራ ነው። በኢንዱስትሪው፣ በንግዱና በአገልገሎት ዘርፍ ያለው እንቅስቃሴ ጉልህ የሥራ ዕድሎች የተፈጠረባቸው አይደሉም።

በ1960ዎቹ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ በዘመናዊ የእርሻ ሥራ፣ በባንክና በማኑፋክቸሪንግ ተጀምረው የነበሩ ሥራዎች በሥርዓት ለውጥ ከባለሀብቶቹ እጅ በመንግሥት በመነጠቃቸው የሥራ ተነሳሽነትን ከመግደሉም በላይ የግል ሥራ ፈጠራ ህጋዊ ከለላ አጥቶ ነበር።

አሁን ባለው ሥርዓትም የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ለማሳደግ ሊሠራ የሚገባውን ያህል ባለመሰራቱና ፍትሀዊ የገበያ ውድድር ባለመኖሩ ዘርፉ ለውጥ የሚያመጣ አቅም አልገነባም። አሁንም መንግሥት በሞኖፖል የያዛቸው የግሉን ዘርፍ በፍትሀዊ ውድድር እንዲሰራ አላስቻሉትም።

4.1. ሥራ ላይ የተፈጠረው የህብረተሰብ አስተሳሰብ

ሥራ የእድገት ዋና ምንጭ ነው። የብዙ ኢትዮጵያውያን የሥራ መስክ ግብርና ነው። ግብርና በውርስ የሚገኝ ሥራ ነው፤ በልማድ የሚሰራ ሥራ ነው። ከሁሉም በላይ ለአብዛኛዎቹ የዘርፉ ሰዎች «ለትርፍ መፍጠር የሚሰራ ሥራ ሳይሆን፤ ለግል ህይወት ፍጆታና ለልውውጥ የሚያገለግል ነው። 85% የሚሆነው የህብረተሰብ ክፍል በአመዛኙ በዚህ ሥራ ላይ ነው። ለዚህ ህብረተሰብ ክፍል የግብርና ሥራ የህይወት ምንጭ ነው። ዘርፉ ትርፍ ፈጣሪ ባለመሆኑ ሊያድግ አይታይም። ዘመናዊ ባለመሆኑም ከተፈጥሮ ደግነት ጋር እጅጉን

የተሳሰረ ነው። የራሱን ተዋንያን እንኳ ያጠገበ አይደለም። በመሆኑም የገጠሩ ነዋሪ ህይወት ለማመን ከሚቻለው በላይ ዝቅተኛ ነው።

ሥራ ፈጣሪዎች በከተሞች ከሚኖረው ህዝብ መካከል እጅግ በጣም ጥቂት ናቸው። ከነዚህም ውስጥ ለራሳቸው ለብዙዎቹ ከእጅ ወደ አፍ በሆነ አነስተኛ ችርቻሮና የጉሊት ንግድ የተሰማሩ ይበልጣሉ። ሌሎች ሥራ የፈጠሩ ትርፋማ የሆኑ ድርጅቶች ጥቂቶች አሉ። ከገጠር በሚብስ መልኩ በከተሞች ሥራ አጥነት ዋናው ችግር ነው። አሁን ያሉት ብዙዎቹ ከተሞች ትርፍ የሚፈጥሩ ሥራ ፈጣሪዎች ወይም ትርፋማ በሆኑ በግል ድርጅቶች ተቀጥረው የሚሰሩ ነዋሪዎች የሚበዙባቸው አይደለም።

በገቢዎች ሚ/ር መግለጫ መሰረት 72,000,000 ህዝብ ባላት ኢትዮጵያ 330,000 የተመዘገቡ የንግድ ድርጅቶች ይገኛሉ። ይህም የንግድ ድርጅቶች የህዝብ ቁጥር ጥምርታ 1:22 መሆኑን ያሳያል። (በአሜሪካ 1:13 ደርሷል። ትልልቆችን ኮርፖሬሽኖች አይጨምርም።)

ኢትዮጵያ ውስጥ ያለው ሌላው የሥራ ዕድል የመንግሥት ዘርፍ ነው። ትልቁ የአሁኑ ሥራ ፈላጊ ተስፋ በመንግሥት የሲቪል ሥራዎችና ድርጅቶች መቀጠር ነው። በተለይ ብዙ የተማረው ክፍል እስካሁን የሚዘጋጀው በመንግስት ለመቀጠር ነው። በገጠርም ሆነ በከተማ ያሉ ወላጆች ልጆቻቸውን የሚያስተምሩት ለማስቀጠር ነው። ስለዚህ የህብረተሰቡ አዕምሮ ውስጥ ጉልህ ቦታ የያዘው ተቀጣሪነት እንጂ ትርፍማነት ያለው የራስ ሥራ መፍጠር አይደለም ። መንግስታዊ ያልሆኑ አገር በቀል የውጭ ድርጅቶች የሚፈጥሩአቸው የሥራ ዕድሎች ከህዝቡ ቁጥር አንፃር ውስኖች ናቸው።

4.2. የኢትዮጵያ ቢዝነስ መሰረቶች

"Every thing you want is just outside your comfort zone."

Robert Allen

የኢትዮጵያ የንግድ እንቅስቃሴ መሠረቶች የግብርና ውጤቶች ናቸው። ለሀገር ውስጥም ለውጪም ንግዳችን መሠረት የሆኑት በአብዛኛው የግብርና ውጤቶች ናቸው። የሌሎች ዘርፎች አለማደግ የቢዝነስና ኢንዱስትሪዎች ኋላቀር በሆነ ልማዳዊ የሥራ እንቅስቃሴ ላይ እንዲያተኩር አድርጐታል። የወጪና የገቢ ንግዳችን ሚዛኑን ሳይጠብቅ ከምንሸጠው በላይ ገዥዎች ነን። በመሆኑም በየዓመቱ ለልማት የሚተርፈን ገንዘብ አነስተኛ ነው። ከግብርና ውጭ ያሉት እንቅስቃሴዎች ለሀገሪቱ የሚፈጥሯቸው ሥራዎች ከህዝቡ ብዛት ጋር ሲወዳደር ጥቂቶች ናቸው። ከዚህ ጋር የሚጨመሩት ጥቂት ድርጅቶችም አዳዲስ ሳይሆኑ በነባርና ተመሳሳይ ዘርፎች ላይ ስለሚሰማሩ ቶሎ ይደክማሉ፣ ብዙዎቹም ይዘጋሉ።

የኢትዮጵያ የቢዝነስ ዘርፉ መደበኛ የትምህርት፣ የሙያ ማሻሻያ ስልጠናዎች ውስንነት ስለሚያጠቃው በአብዛኛው ዘመናዊና ተወዳዳሪ አይደለም። በተለይ ዓለም በፈጠራ ውድድር ላይ የበለጠ እየገባችና እየተቀራረበች ባለችበት የግሎባላይዜሽን ሂደት የተሻለ ተወዳዳሪነትን ማሳደግ ይጠበቃል። ጥራትና፣ ውጤታማ የሆኑ አሰራሮች ማዘውተር የግድ ሲሆን ይህን የሚያሟሉት ጥቂቶች ናቸው።

4.3 የኢትዮጵያ ኢንተርፕረነሮች እንቅስቃሴ

"Most people give up just when they're about to achieve success. They quit on the one – yard line. They give up at the last minute of the game, one foot from a winning touchdown."

H. Ross Perot

ኢትዮጵያ ከላይ በተገለፁት በግብርናው፣ በኢንዱስትሪው፣ በንግዱና በአገልገሎት ክፍለ-ኢኮኖሚዎች ከሚንቀሳቀሱት የቢዝነስ ሰዎች ውስጥ በጣት የሚቆጠሩ ኢንተርፕረነሮች (ከ10 አለምዓቀፍ የስኬታማ ሰዎች ችሎታዎች ብዙውን ያሚሉ) አሏት። በዓለም ላይ በተለይ ከ1960ዎቹና 1980ዎቹ የበለጠ ትኩረት የተሰጠው የኢንተርፕረነርሽፕ ዴቨሎፕመንት ስልጠና በሀገራችን ተገቢ ትኩረት (በህገቡ፣ በፖለቲከኞች፣ በፖሊሲ አውጪዎችና አስፈፃሚዎች እንዲሁም በቢዝነስ ህብረተሰቡ ዘንድ) አልተሰጠውም። በኢንተርፕረነርሽፕ ዴቨሎፕመንት ላይ ያሉ የማሰልጠኛ ማቴሪያሎችና መፃህፍት በሀገራችን ጥቂቶች ነበሩ።

በ1985 ዓ.ም በኢትዮጵያ ንግድ ምክር ቤት የተጀመረው የኢንተርፕረነርሽፕ ስልጠና 122 ሰዎችን አሰልጥኗል። ለተወሰነ ጊዜ ተቋርጦ ከጥቂት አመታት በፊት በኢንተርፕራይዝ ኢትዮጵያ እየተሰጠ ያለው ስልጠና አለ ይባል እንጂ በስፋት በመላ ሀገሪቱ አልተስፋፋም። በኢትዮጵያ ንግድ ም/ቤትና በኢንተርፕራይዝ ኢትዮጵያ ከሰለጠኑት ስልጣኞች ውስጥ በጣም ጥቂቶቹ በግላቸው የስልጠናና የምክር አገልግሎት ሥራ ውስጥ ቢገቡም ለውጥ ማምጣት የሚገባው ሥራ ውስጥ ገና መግባት አልተጀመረም ማለት ይቻላል። ኢምፐርቴክ ኢትዮጵያ - የኢትዮጵያ ኢንተርፕረነሮች ማህበርም በጽንሰ ሀሳብ ዙሪያ በህገቡ ዘንድ ግንዛቤ ከመፍጠር የዘለለ ውጤት የሚያስመዘግብ ሥራ ውስጥ ገና አልገባም። ማህበሩ የተቋቋመው ለኢንተርኘረነሮች የስልጠና፣ የምክርና የብድር አገልግሎት ማዕከል ለመሆን ነው። በዚህ ዓላማው ላይ የሚጠበቅበትን ያህል አልሠራም።

4.4 የኢትዮጵያ ኢንትራፕረነሮች ሁኔታዎች

"He who stops being better stops being good."

Oliver Cromwell

ኢንትራፐረነሮች በግልም ሆነ በመንግስት ሥራዎች ተቀጥረው የሚሰሩ ኢንተርፕረነሪያል ክህሎቶች ያሏቸው ተቀጣሪዎች ናቸው። የሚሰሩበት ቦታ ላይ ውጤታማ ሥራ የሚያስመዘግቡ የተለየ ቀና አስተሳሰብ ያላቸው ሠራተኞች ናቸው። ትልልቅ ሀሳቦችን የሚያመነጩ፣ የምርት ግብአቶችን በደንብ ተጠንቅቀው የሚይዙ፣ ከሙስናና ከዘረኝነት የፀዱ፣ ሠርተው የሚያሰሩበት መርህ ያላቸው አስተባባሪዎች ናቸው። እነዚህ ከፍተኛ አመኔታና ከበሬታ ያላቸው ሰዎች ሲበዙ በህብረተሰቡና በመንግስት፣ በሠራተኞችና አሰሪዎች መካከል መተማመን ይፈጠራል። ሲፈጠር፣ የሥራ ተነሳሽነትና ህብረት ያድጋል።

የእነዚህ ሰዎች ቁጥር በሀገራችን ዛሬ በጣም አነስተኛ ነው። በተቃራኒው ብክነት፣ ወንጀኝነት፣ ጊዜ ማጥፋት፣ በደንበኞች ማፌዝ፣ እኔ ያልኩህን ብቻ አድርግ፣ እኔ አውቅልሀለሁ የሚሉ ይበዛሉ። ሠራተኛን በማሰራትና በማስተባበር ፋንታ የያዙትን ቦታ

ለግል ጥቅማቸው ሲያውሉት ይታያሉ:: ተቀጣሪነታቸው፣ በደንበኞቻቸው ገቢ በህዝብ ክፍያ መሆኑን ይዘነጋሉ::

በኢትዮጵያ ታላቅ ራዕይና ህልም የሌላቸው ኢንተራፕረነሪያል ያልሆኑ ተቀጣሪ አስተባባሪዎችና ሥራ መሪዎች ብዙ ናቸው:: የሥራ ቦታ ደርሰው በመመለስ ደመወዝ ሲከፈላቸው ለምን ብለው ራሳቸውን የማይጠይቁ ቅር የማይላቸው ብዙ ተቀጣሪዎች አሉ::

በመሆኑም የኢትዮጵያ ኢንትራፕረነር መሠረቱ ጠባብ ነው::

4.5 የፖለቲከኞች ሁኔታ

"If you are willing to do more than you are paid to do, eventually you'll be paid to do more than you do."
Source Unknown

ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ፖለቲከኞች እንሰራላችኋለን ባዮች ናቸው:: እናደርግላችኋለን የሚሉ ይበዛሉ:: ሀብት ፈጣሪ ህዝብ፣ ሥራ ፈጣሪ ህዝብ ሲሆን ሀገር ከኢኮኖሚ ጥገኝነት እንደምትላቀቅ የማይረዱ ፖለቲከኞች ጥቂቶች አይደሉም:: የፈጠሩት/ሊፈጥሩት የሚፈልጉት ሥርዓት የነሱን እንጂ የህዝቡን ጥረት አጉልቶ እንዲያወጣ አይፈልጉም:: ከጎላ ቀርነት፣ ከሥራ አጥነት፣ ከበሽታ የሚወጣው ግን በህዝብ ተጋድሎ ነው:: የግሉ ክፍለ ኢኮኖሚ ሥራውን እንዲሰራ በአስተሳሰባቸውና በአፈፃፀማቸው ምቹ አጋሮች አልሆኑለትም::

ኢንተርፕረነሪያልና ኢንትራፕሪነሪያል አስተሳሰብ ያላቸው ፓለቲከኞች በሀገራችን በጣም ጥቂቶች ናቸው::

4.6 በኢትዮጵያ ኢንተርፕረነርሽፕን አበረታች ነገሮች

"History has demonstrated that the most notable winners usually encountered heart breaking obstacles before they triumphed. They won because they refused to become discouraged by their defeats."

B.C Forbes

በአሁኑ ጊዜ የግልን ክፍለ ኢኮኖሚ የሚያበረታቱ በተለይም ድህነትና ኋላቀርነትን ለመቀነስ ብሔራዊና አለምዓቀፍ ግዴታዎች መሠረት ፖሊሲ አውጪዎች ሥራ ፈጣሪዎችን መፍጠር ዋናው አማራጭ እንደሆነ የተገነዘቡበት ጊዜ ነው::

በገጠርም ሆነ በከተማ አዳዲስ የሥራ ዘርፎች ካልተፈጠሩ ግልጽና ድብቅ ሥራ አጥነት እንደሚባባስ በህዝቡም አዕምሮ ግንዛቤ ተፈጥሯል::

አሁን በመስራት ላይ ያሉ የንግድ ምክር ቤቶች ለሌሎች ሥራ ፈጣሪዎች የመረጃ ማዕከል ሆነው ሊያገለግሉ ይችላሉ::

በተለይ በግል ከፍተኛ ተቋማትና በመንግስት ቮኬሽናል ማሰልጠኛዎች ኢንተርፕረነርሽፕ በተጨማሪ ኮርስነት መስጠት ተጀምሯል:: ለየት ያሉ ሥራ ፈጣሪዎች እና የመፍጠር ዕድሎች እየመጡ ነው::

ኢኮኖሚና ትንንሽ ድርጅቶች ማቋቋምና የስልጠና እንቅስቃሴዎች ማካሄድ ለኢንተርፕረነሮች ድጋፍ ማግኘ ማፍያ ጣቢያዎችን ማዘጋጀት ነው።

ኢንተርፕረነር ዙርያ እየገቡ ያሉና እየተተረጐሙ ያሉ መፃህፍት ቁጥር በመጨመር ላይ ነው።

ኢንተርፕረነርሽፕን ለማስፋፋት የተቋቋሙ የግል ማህበራትና አማካሪዎች መኖር እገዛ ፈጥሯል።

በኢትዮጵያ የኢንተርፕረነርሽፕ ዕድገት ገቺ ሁኔታዎች

"A man is literally what he thinks you are today where your thoughts have brought you; you will be tomorrow where your thoughts take you."

James Allen

በአገራችን የኢንተርፕረነርሽፕን ጥሬ ሀብት ዕድገት የሚገቱ ብዙ ሁኔታዎች አሉ። ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፤

1. ሥራ ፈጠራ ላይ ያለው የህብረተሰብ ግንዛቤ ትክክለኛ አለመሆን፣
2. ከኃላቀርነት ጋር ለመኖር የብዙ ሰዎች ፈቃደኛ መሆንና በቂ እልህ አለመኖር፣
3. የራስንም፣ የሌሎችም ጥሬ ሀብቶች ማባከን ፣
4. ለራስና ለሌሎች የገቡትን ቃል አለማክበር፣ ተጠያቂነት መጥፋት፣
5. በቂ የትምህርት፣ የሙያና የክህሎት ስልጠና ኘሮግራሞች አለመስፋፋት፣
6. ፍትሀዊና አበረታች የሆነ የሥራ ውድድር በብዙዎች አዕምሮ ውስጥ አለመኖር፣
7. በህብረት ሰርቶ ለማደግ የሚረዳ ባህልና መተማመን አለመኖር፣
8. የግል የኢኮኖሚ ነፃነትና በራስ መተማመን አለመኖር፣
9. የረጅሙን ጊዜ እድገት ሳይሆን ዛሬን ባለው ሁኔታ መኖር፣ የሚመርጡ ሰዎች መብዛታቸው፤
10. የኢኮኖሚና የማህበራዊ አውታሮች አለመስፋፋት፣
11. ኢንትራፕረነርያል ክህሎቶች ያላቸው የፖለቲካ መሪዎች፣ ፖሊሲ አውጭዎችና፣ አስፈፃሚዎች ጥቂት መሆን፣
12. የአጋር ሀገሮችና የውጭ ድርጅቶች ለሀገሪቱ የሥራ ፈጣሪዎች የሚያደርጉት ድጋፍ አነስተኛ መሆንና ቀጣይነት ማጣት፣ናቸው።

ሀገሪቱ ልትጠቀምባቸው የምትችላቸው ጥሬ ሀብቶች

"Learn more to earn more."

Jack Canfield

ኢትዮጵያ ያልተጠቀመችባቸው የበለጠ መልማት ያለባቸው ጥሬ ሀብቶች አላት። ከነዚህም ውስጥ፤

- መሬትና የሰው ኃይል አላት። የሰው ኃይሏ በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጭም ያለ ነው።
- ለውጥ ማምጣት የሚችል የተሻለ የኢንተርፕረነሮች ምንጭ የሚሆን የወጣት ሀብረተሰብ አላት።
- የዓለም ህዝብ በደንብ የማያውቃቸው የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ የቱሪስት መስህቦች አሏት።
- ያልተሟላ ህይወት ያለው እልህ ውስጡ ቢቀጣጠልና ቢነድ ሀገርን መቀየር የሚችል ህዝብ አላት።

5. ኢንተርፕረነርሽፕና ልማት በኢትዮጵያ ርዕይ 2020 ዝርዝር ሀሳቦች፣ ኃላፊነቶችና ግዴታዎች

"Commit to life long self – improvement and learning improving your mind, increasing your skills, and boosting your ability to assimilate and apply what you learn."

Jack Canfield

ከ4.1-4.7 የተጠቀሱት ችግሮች ለኢንተርፕረነሮች እልህ የሚያጋቡ መልካም አጋጣሚዎች ናቸው። እነዚህን ተጋፍጦ ለውጥ የሚያመጣ የኢንተርፕረነሮች ሠራዊት ኢትዮጵያ ሊኖራት ይችላል። በመጪው 2020 የእነዚህ ሰዎች ቁጥር 2% ያድጋል። የኢትዮጵያ ልጆች ለውጥ የሚያመጣ ሀገርን ከኋላቀርነት የሚያወጣ ሥራ ፈጣሪ እንሆናለን። ለውጥ የምናመጣ ተቀጣሪ እንሆናለን። ለውጥን የምናበረታታ እንሆናለን። ምክንያቱም የተተወልን ምርጫ የተሻለ አዕምሮ፣ መልካም አስተሳሰብ፣ ጥረትና ሀብት ባለቤቶች መሆን ነው። የተሸከመችን ሀገር ባለዕዳዎች ባለውለታዎች ነን። የሀገራችንን ውለታ ለመመለስና ስሟን ለመቀየር እንችላለን።

ከዚህ በታች የሚከተሉት ክፍሎች በ2020 ኢትዮጵያን በገዘቀተኛ የዕድገት ደረጃ ካሉት ሀገሮች ምድብ እንድትወጣ ያደርጓታል። ለዚህም ሥራቸው ዋናው ግብዐታቸው እነዚህ ሁሉ የሀገራቱ ዜጎች የአሰተሳሰብ ብልፅግና፣ ከራስ የሚተርፈ ለትውልድ የሚሆን የሥራ ፈጠራ ተነሳሽነት እልህና ቁጣ ተቀጣጣይ ሰደድ ማንበልበል ይሆናል።

የአጋሮቻችን ትኩረትም በልማት፣ በግብርና በንግድ፣ በቴክኖሎጂ ሽግግር በኢንዱስትሪና በኢንቨስትመንት እንዲሆም በቱሪዝም ክፍለ ኢኮኖሚዎቻችን ላይ ለጋራ ጥቅም አብሮ መስራት ይሆናል። ኢትዮጵያ የለማች ሀገር ሆና ራሷን ችላ ስታድግ ማየት ይፈልጋሉ።

አሜሪካዊው ዊሊሰን ሀረል በዓፉት «ለኢንተርፕርነሮች ብቻ» በተሰኘው መጽሀፍ ውስጥ እንደገለፀት አሜሪካ እስከ 2004 እ.አ.አ ከነበራት 20 ሚሊዮን የቢዝነስ ባለቤቶች ውስጥ ኢንተርፕረነሮቹ አንድ ሚሊየን ወይም 5% ብቻ ናቸው።

ሕንዳዊቷ ዶ/ር አሩና የዘወትር ኢንተርፕረነሮች በተሰኘው መፅሀፍ እንዳሳዩት ህንድ አንደ ፐርሰንት ዜጐቿን አሰልጥና ኢንተርፕረነር ብታደርግ ከኋላ ቀርነት ሊያወጣት እንደሚችል በማመኗ ብሔራዊ የኢንተርፕረነርሽፕ የስልጠና ማዕከል/ፋውንዴሽን አቋቁማ በመስራት ላይ ነች።

ላይ 2020 ዕውን እንዲሆን የሚከተሉት የህብረተሰብ ክፍሎችና ተቋሞች የተለዩ ሚናዎችና ግዴታዎች አሉባቸው፡፡ እነዚህም፤

1. ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች (በሀገር ውስጥም ከሀገር ውጪም ያሉ)
2. ሁሉም የገጠር ነዋሪዎች (ሴቶች፣ ወንዶች፣ ወጣቶች)
3. ሁሉም የከተማ ነዋሪዎች (ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ወንዶች)
4. ሁሉም የንግድ ማህበረሰብ አባላትና ኢንተርፕረነሮች
5. ሁሉም ምሁራን
6. የመ/ያ ማህበራት
7. ሀገረሰባዊ ማህበራት
8. ሁሉም በቀልና ሀገር በቀል ያልሆኑ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት
9. ሁሉም የሐይማኖት ተቋማት
10. ሁሉም ባንኮችና የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት
11. ሁሉም የመንግስት አካላት (ፓለቲከኞች፣ ፓሊሲ አውጪዎች፣ ፓሊሲ አስፈፃሚዎች፣ መገናኛ ብዙኃን፣ የመንግሥት የማምረቻና የንግድ ተቋማት)
12. ትምህርት ቤቶችና ከፍተኛ ተቋማት
13. የጤና ተቋማት
14. የመሰረተ ልማት ተቋማት
15. አጋር የውጪ አገሮችና ድርጅቶች (የተባበሩት መንግስታት፣ የልማትና የንግድ ኤጀንሲዎች፣ ለጋሽ ሀገራት፣ አበዳሪ አለምዓቀፍ ተቋማትና ሌሎችም የኢትዮጵያ ህይወትና እድገት የሚያገባቸው ሁሉ) ለከፍተኛ ሥራና አጋርነት በሙሉ ልብ እንዲነሱላት ያስፈልጋል፡፡

ከያንዳንዳቸው የሚጠበቁ ኃላፊነቶችና ግዴታዎች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፤

5.1 ሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች

"Nothing great was ever achieved with out enthusiasm."

Ralph Waldo Emerson

- ራሳቸውን ለበለጠ ውጤታማ ሥራ ማዘጋጀትና ማነሳሳት፣
- በጥረታቸው ለራሳቸው አለኝታ መሆን፣ ለሌሎች የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች የበለጠ ቀና አስተያየት ያላቸው ብርቱ ተወዳዳሪዎች መሆን፣
- በመማር፣ በመሰልጠን፣ በማንበብ የራሳቸውን ዋጋ በማሳደግ የማያቋርጥ ብልፅግና ማስመዝገብ፣
- ከራሳቸው የሚተርፍ ሀብት መፍጠር፣
- በዘወትር ሥራቸው ታማኝነትን፣ እውነትን፣ ሀገር ወዳድነትን፣ ሥራ ወዳድነትን፣ ታታሪነትን፣ ራስን መቻልን፣ የግል ነፃነትን፣ ቁጠባና ኢንቨስትመንትን መርህ አድርገው መንቀሳቀስ፣
- የሀገራቸውን ምርቶች ለመጠቀም ቅድሚያ መስጠት፣
- የ2020 የኢትዮጵያ ርዕይ አርነት ሆኖ አንገታቸውን ቀና አድርገው ለመሄድ ቆርጠው የመነሳት ግዴታና ኃላፊነት አለባቸው፡፡

እነዚህ ሥራዎች በሀገሪቱ ፓሊሲ የተለያዩ ክፍሎች በግልፅ ወጥተው ህዝቡ እንዲያውቃቸው መደረግ አለበት ::

ከሀገር ውጪ ያሉ ዜጎች

ውጪ ያሉ ብዙዎቹ ያገሪቱ ዜጎች፣

- ዕውቀታቸውን፣ ልምዳቸውንና ገንዘባቸውን በሀገራቸው ኢኮኖሚ ላይ ኢንቨስት ማድረግ፣
- ከመቸውም ጊዜ የበለጠ ቶሎ ቶሎ ወደ ሀገራቸው መመላለስ፣ ያልመጡት እንዲመጡ ማድረግ፣
- ይህን የሚያመቻች ክፍል በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር በኩልና በኢትዮጵያ የውጪ ኤንባሲዎች መቋቋም አለበት::

5.2 የገጠር ነዋሪዎች

ሀ. ሁሉም

- የተሻለ፣ የበለጠ ራስን የቻለ ኑሮ መኖር አለባቸው:: ንጹህ ውሀ፣ የተሻለ መጠለያ፣ ት/ቤት፣ መንገድ፣ ክሊኒክ፣ ገበያ ቦታ መሟላት አለባቸው::
- የተራቆተ መሬቷን በደን ሽፍነው የሚሸረሸር አፈርዋን በዕርከን አድነው ተፈጥሮን የበለጠ መጠበቅ አለባቸው፣ ራሳቸውን የበለጠ ተጠቃሚ ያደርጋሉ::
- ከግል ፍጎታቸው በላይ አምርተው ለገበያ በማቅረብ ትርፍ መፍጠር አለባቸው ::
- ከመደበኛ ሥራቸው ውጪ ይማራሉ፤ የማይፅፍ፣ የማያነብ ገበሬ አይኖርም::
- ጤንነታቸውን በመንከባከብ የተሻለ የዕድሜ ዘመን ለመኖር ይዘጋጃሉ::
- ለሚጨምሩአቸው የቤተሰብ አባላት ተጨማሪ ገቢ ቀድመው መፍጠር ይጠበቅባቸዋል፤ አለዚያም የቤተሰባቸውን መጠን ይቆጣጠራሉ::

ለ. ያልተማሩ ወጣት ገበሬዎች

- በተለያዩ የዕደ ጥበባትና የእርሻ መሳሪያዎች ማምረቻ ማህበራት በመደራጀት አርሶ አደርነትን የሚተካ ሥራ ላይ ይሰማራሉ ፣
- በተለያዩ የንግድ ሥራዎች ላይ በመሰማራት የገቢ ምንጭ ይፈጥራሉ::
- የተሻለ የገጠር መንደሮች ይመሰርታሉ::

ሐ. ሴቶች የገጠር ነዋሪዎች

- የፈጠራ ችሎታቸውን ተጠቅመው ከፍጆታ የሚተርፍ ገቢ ይፈጥራሉ::
- የትምህርትና ስልጠና ተሳትፎአቸውን በመጨመር ኑሮአቸውን ያሻሽላሉ::
- እነዚህ ግዴታዎች በገጠር ፓሊሲ ውስጥ ተካተው ህዝብ ተወያይቶባቸው በተግባር ይውላሉ::

- የተሻለ ወጣት የቢዝነስ ሰዎችንና ኢንተርፕረነሮችን ለመተካት የተለያዩ የስልጠና፣ የምክር አገልግሎት የቡድን ልማትና ማበረታቻ ፕሮግራሞች ይኖሯቸዋል::
- አምነርቱክ ኢትዮጵያ ቢዝነስ ሶሳይቲ የኢትዮጵያ ኢንተርፕረነሮች ማህበር ወደ ትልቅ ሀገር አቀፍ፡ የኢንተርፕረነርሽፕ ፋውንዴሽን በማደግ በምክር፣ በስልጠናና በብድር አገልግሎት.ኢንተርፕረነሮች የማበረታታት ቁልፍ ድርሻ ይኖረዋል::
- በንግድ ሀብረተሰብ፣ በቻምበሮች፣ በንግድና ኢንዱስትሪ እንዲሁም በሀገር ውስጥ ገቢ ባለሥልጣን ፓሊሲዎች ዝርዝር ሀሳቦቹ ይካተታሉ::

5.5 ምሁራን

"The biggest mistake people make in life is not trying to make a living at doing what they must enjoy."

Malcolm S. Forbes

- የተማረ ማለት ለህይወት የሚያስፈልገውን ነገር የማንንም መብት ሳይደፍር አሟልቶ መኖር የሚችል ሰው ነው::
- ብዙዎች የራሳቸው ሥራ በመፍጠር ቀጣሪዎች በመሆን የተሻለ ነፃነትና ንብረት ይፈጥራሉ፣ መደቸውን ያሻሽላሉ::
- በተለያዩ የምርምር፣ ጥናት፣ ምክር አገልግሎትና የትምህርት ሥልጠናዎች ሕብረተሰቡን የበለጠ ያገለግላሉ ::
- ተደናቂ ኢንተርፕረነሮች እንዲወጣቸው የኢንተርፕረነርሽፕ ስልጠና ይከታተላሉ::
- ለሀገር የኢኮኖሚ ነፃነት፣ ሀብትና ንብረት ፈጠራ ፈር ቀዳጆች ሆነው ይሰራሉ::
- ራሳቸውን የበለጠ እያስተማሩና እያሰለጠኑ የራሳቸውን ዋጋ በየጊዜው በማሳደግ ገቢያቸውን ያሻሽላሉ::
- ለስልጠና፣ ለትምህርትና ለሥራ ወደ ውጪ ሄደው አይቀሩም፤
- ጊዜአቸውን፣ እውቀታቸውን፣ ልምዳቸውንና ተሰጥዖዋቸውን ለተሻሉ ሥራዎች ይጠቀማሉ::
- የተሻለ ስለሚሰሩ የተሻለ የሚኖሩ ይሆናሉ:: ለመኖርና ለሌሎችም አርአያ ለመሆን ይነሳሳሉ::

5.6 የመደያ ማህበራት

"Success is a sum of small efforts, repeated day in and day hour."

Robert Collier

- ራሳቸውን ችለው በሚፈጥሩአቸው ሥራዎችና በሚያገኙአቸው ገቢዎች የተሻለ ሥራዎች ላይ (ጥናቶች፣ ምርምሮች፣ የምክር አገልግሎቶችና ስልጠናዎች) ላይ ይሰማራሉ::
- ከመደያቸው ጋር ግንኙነት ካላቸው የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ጋር በህብረት ይሰራሉ::
- ለሌሎች የሥራ ዕድል ይፈጥራሉ::
- ትርፍ ፈላጊዎች ይሆናሉ ::
- መደዎች ሁሉ የተሻለ ዕድገት እንዲያመጡ ተገልጋዮችን ያግዛሉ::

- መጣት ኢንተርፕሬነሮችን በየሙያቸው ያፈራሉ፣ያበረታታሉ::
- የሥራ ፈጣሪዎችን ትግሮች በሙያቸው ያጠናሉ፤ መፍትሔም ይፈልጋሉ::
- በ5.5 እና 5.6 የተዘረዱት ኃላፊነቶች በሙያ ማህበራት ዓላማዎችና ውስጠ ደንብ ውስጥ ተካተው ይተገበራሉ::

5.7 ህዝባዊ ማህበራት

"There is no such thing as bad weathers only the wrong clothes."

Billy cemnolly

- የበለጠ በልማት ሥራዎች ላይ ይሰማራሉ::
- በአካባቢ ጤንነት፣ ደህንነት፣ ንፅህናና ውበት ላይ ጉልህ አስተዋጽዖ ያደርጋሉ::
- ኃላቀርነትን ለማስወገድ ህዝብን ያስተምራሉ፣ ያስተባብራሉ::
- ሥራዎችን ይፈጥራሉ::
- ወጣት ሥራ ፈጣሪዎችን ያበረታታሉ ይሸልማሉ::

5.8 መንግሥታዊ ያልሆኑ ተቋማት (NGOs)

"You have to believe in yourself when no one else does. That's what makes you a winner."

Venus Williams

- ሀገር በቀል የሆኑና ያልሆኑ ድርጅቶች የሚያግዙአቸውን ሰዎች ራስን መቻልን፣ ሥራ ፈጠራን ያበረታታሉ::
- ዕዝ የሚያደርጉት ራሳቸውን ለመቻል ለማፍሐረሐሩ ሰዎች ይሆናል::
- የሥራ ፍቅሩን በሚያሳድጉ የሀገር እንቅስቃሴዎች ይሳተፋሉ::
- በራስ አለመተማመን ይወገዳል::
- ሥራ ይፈጥራሉ፣ ያስፈጥራሉ::
- የሰዎችን የጥገኝነት፣ የጠባቂነት፣ የተረጂነት መንፈስ ያስወግዳሉ::
- የሥራ ውድድሮችና ማበረታቻዎች ያደርጋሉ::
- ኢንትራፕሬነሪያል ሥራ መሪዎችና አስተባባሪዎች ይሆናሉ::

5.9 የሐይማኖት ተቋማት

"None of us can change our yesterdays, but all of us can change our tomorrows."

Collin Powell)

- የሥራ ፍቅር፣ ተነሳሽነት፣ ታታሪነት፣ የሥራ ፈጣሪነት-ስነልቦናዎች መማሪያ ቦታዎች ይሆናሉ::
- ህዝቡን ለሥራና ለኤኮኖሚ ነፃነት ያነሳሳሉ::
- ለምዕመኖቻቸው ሥራ ይፈጥራሉ::

- ተረጂነትን፣ ተመፅዋችነትን፣ የበታችነትን፣ ተስፋ-መቁረጥን፣ የሥራ ጀላቁርነትን ያወግዛሉ፤ እነዚህን በማስወገድ ህዝብን ለብልፅግና ለማነሳሳት ያስተምራሉ።
- ለሥራ ፈጣሪዎች የምክር፣ ስልጠናና ብድር አገልግሎቶች ይሰጣሉ።
- የሥራ ቀናትን ያበዛሉ፤ የሥራ ጊዜን ይቆጥባሉ።

5.10 ባንኮችና የማይክሮ ፋይናንስ ተቋማት

- ለሥራ ፈጣሪዎች በዝቅተኛ ወለድና በረዥም የመመለሻ ጊዜ ብድር ይሰጣሉ።
- የባንክ ተገልጋዮቻቸውን ቢዝነሶች በጥናት፣ በምክር አገልግሎት፣ በስልጠና ያግዛሉ።
- አዋጭ የቢዝነስ ሀሳብና ተሰጥዖ ላላቸው ሥራ ፈጣሪዎች እያወዳደሩ ያለ መያዣ ብድር ይሰጣሉ።
- የቁጠባና ብድር አገልግሎት ማህበራትን ያደራጃሉ፣ ያጠናክራሉ።

5.11 የመንግሥት አካላት

"Grow or die."

Jack Canfield

1. ፖለቲከኞች፣

- የሀገርና የህዝብ ኢኮኖሚያዊ ነፃነትና ፍትሐዊ ውድድር ያሰፍናሉ።
- ሥራን ያበረታታሉ፣ ለሀብትና ለንብረት ህጋዊ ከለላ ይሰጣሉ፤ እድገትን ያመጣሉ።
- የልማት አውታሮችን በህዝብ ተሳትፎ ማሰራት ነው።
- የህዝብን የልብ ትርታ ማዳመጥና በለውጥ ጎዳና መጓዝ ነው።
- የተሻለ የህዝብን ምኞት፣ ሰላም፣ ተድላ፣ ህብረት፣ ብልፅግናና አንድነት ማስፈን ነው።
- የህዝብን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ማክበርና ማስከበር ይሆናል።
- ኢንትራፕረነሪያል የሆነ አመራርን ማስፈን ነው።
- መተማመንን፣ መከባበርን፣ መደማመጥን፣ መደጋገፍን የሚያስተናግድ ይሆናል።
- በቁጥር 2.5 ያሉትን የፖለቲካ መሪዎች ብቻ ኢትዮጵያን ይመራሉ፤ ለዕድገትም ያበቁታል።

2. ፖሊሲ አውጭዎች

"The voice inside your head is not the voice of God, it just sounds like it things it is."

Chen Huber

- የግሉን ክፍለ ኢኮኖሚ ሚና የሚያሳድጉ ለሥራ የሚያመቹ ግልፅ ፖሊሲዎችን ከህዝብ ጋር ተመካክረው ያወጣሉ።
- የማያሰሩ ጊዜ ያለፈባቸውን ፖሊሲዎች ያሻሽላሉ፣ ይቀይራሉ።
- ግልፅ የማስፈፀሚያ ህጎችንና መመሪያዎችን ያወጣሉ።
- በፖሊሲዎች አፈፃፀም ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በጊዜው ያጠናሉ።
- ኢንትራፕረነሪያል የሆኑ የአፈፃፀም መርሆዎችን ያወጣሉ፣ ይተገብራሉ።

ፓሊሲ አስፈፃሚዎች

"We don't see things as they are, but rather as we are."

Anis Nin

- የስራተኛው ህዝብ ጊዜ፣ ገንዘብ፣ ዕውቀትና ንብረት ከብክነት የሚያድን የአፈፃፀም ዘዴዎች ይጠቀማሉ ፣
- ከወንጀኝነት፣ ዘረኝነት፣ ከሙስናና በቀል የራቁ ይሆናሉ፣
- የመናዊ አሰራርን ይከተላሉ፣
- ሥራ ፈጠራን ያበረታታሉ፣

መገናኛ ብዙሀን

"Facts do not cease to exist because they are ignored."

Aldous Huxley

- የሥራ እድልን፣ ገቢን ለመፍጠር -የመረጃ ሥርጭትን የበለጠ ፍትሀዊ ለማድረግና ቢዝነስን ለማስፋፋት እንዲረዳ የ24 ሰዓት ስርጭት ያላቸው በርካታ የግል ቴሌቪዥን ጣቢያዎች ይኖሩታል፣ የመጀመሪያዎቹ የግል ቴሌቪዥን ጣቢያዎች በሚቀጥሉት አምስት አመታት እውን ይሆናሉ ::
- በርካታ የግል ጋዜጦች/ መፅሔቶች ይኖራሉ::

የመንግስት ይዞታ ማምረቻ ተቋማት

"It's never crowded along the extra mile."

Wayne Dyer

- ፍትሀዊ በሆነ የገበያ ቢዝነስ ሥነ ምግባር እንደሰሩ ይደረጋሉ ::
- ፍትሀዊና ውጤታማ ያልሆኑትን ወደ ግሉ የኢኮኖሚ ዘርፍ በማዛወር የተሻለ የሥራ ዕድልንና ገቢን ለሀገር እንዲፈጥሩ ይደረጋል::

5.12 ትምህርት ቤቶችና ከፍተኛ ተቋማት

"Success is a sum of small efforts, repeated day in and day hour."

Robert Collier

- ሥራ ፈጣሪዎችን ለማፍራት በሁሉም ደረጃ ኢንተርፐረነርሽፕን በትምህርትና ስልጠና ካሪኩለም ውስጥ ያካትታሉ::
- የአስልጣኞች ስልጠና ለመምህራንና ለሰልጣኞች ይሰጣል::
- ብሔራዊና ክልላዊ የኢንተርፐረነርሽፕ ፋውዴሽን በማቋቋም የስልጠና፣ የምክርና የብድር አገልግሎቶች ለኢንተርፐረነሮች ይሰጣል::

- በሀገር አቀፍና በየክልሎች ለሚቋቋሙ የኢንተርፕረነርሽፕ ፋውንዴሽን ማዕከሎች በሀገር ውስጥና ውጪ ያሉ የኢትዮጵያ ዜጎች በሙያቸው፣ በእውቀታቸው፣ በልምዳቸውና በገንዘባቸው ይተባበራሉ።
- የግል ዘርፍ የትምህርትና ስልጠና ተሳትፎ ያደርጋሉ።

5.13 የጤና ተቋማት

"You become like the people you spend the most time with. Pay any price to stay in the presence of extraordinary people."

Mike Murdock

- ህብረተሰብ የጤንነቱ ጉዳይ ከምንም ነገር በላይ የሚያሳስበውና የሚጠነቀቅበት ይሆናል።
- በርካታ የግልና የመንግሥት ጤና ተቋማትና መድኃኒት ፋብሪካዎች፣ ክሊኒኮና ሆስፒታሎች ይሰራሉ።

5.14 የመሠረተ ልማት ተቋማት

"Listen hundred times. Ponder a thousand times. Speak once."

Unknown Source

መገናኛ አውታሮችና የመሠረተ ልማት እንቅስቃሴዎችን ይፋጠናሉ። የትልቅ ሥራ ዕድል ምንጭም ይሆናል።

ከዚህ ከ5.1-5.14 ከቀረቡት የማህበራዊ፣ ፓለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተዋንያን ጠንካራ ጥረቶች እስከ 2020 ድረስ 2% የሚሆነው የኢትዮጵያ ሠራተኛ ክፍል ኢንተርፕረነር ይሆናል። ይህ ቁጥር ከቀረበው የኢትዮጵያ ህዝብ ትንሀ ሥራ ጋር ተዳምሮ ኢትዮጵያን በ2020 ዝቅተኛ የእድገት ደረጃ ካላቸው አገሮች ቡድን ያወጣታል። እነዚህ 10 አለምዓቀፍ ችሎታዎችን በብዛት ያሟሉ ሰዎችን በመጀመሪያዎቹ 10 ዓመታት በማሰልጠን፣ የምክርና የብድር አገልግሎት ፓኬጆችን በማቅረብ ማፍራት ይቻላል።

5.15 አጋር የሆኑ የውጭ ሀገራትና የልማት ድርጅቶች

"Doing more of what doesn't work won't make it work any better."

Charles J. Givens

- ለሥራ ፈጠራ እንቅስቃሴዎች ለስልጠና/ምክር አገልግሎትና ብድር/ ፋውንዴሽኖችን ለማጠናከር/ ይተባበራሉ።
- ከእርዳታ ይልቅ የሥራ/የንግድ ልውውጥ፣ የልማት ዕድገት ላይ ትኩረት ይሰጣሉ።

ማጠቃለያ

6

"You have to believe in yourself when no one else does. That's what makes you a winner."

Venus Williams

"Our lives improve only when we take chances – and the first and most difficult risk we can take is to be honest with ourselves."

Walter Andreson

"It's always too soon to quit!"

Norman Vincent Peale

የሁሉም የሀገራቱ ልጆች ግዴታዎችና ኃላፊነቶች የሚጀምሩት የራስን የግል አስተሳሰብ በመለወጥ ነው። የግል አስተሳሰብ ለወጥ ማለት የተሻለ ለመሥራትና ለሀገር ለማበርከት ራስን በከፍተኛ እልህ መነሳሳት ላይ ያተኩራል። ምክንያቱም ተፈጠርን እንጂ እየኖርን አይደለም። በኛ ኃላቀር ኑሮ የሀገራችንን ክብር አዋርደናል። ስንለወጥ ለራስም ለሌሎችም የተሻለ ለሚሰሩ የሀገራቱ ልጆች የበለጠ ምቹ መሆን እንችላለን።

ኢትዮጵያ ከዚህ ወደባሰ ዝቅተኛ ደረጃ እንዳትወርድ ዜጎቿ አይፈቅዱም፤ ተባባሪዎቿና አጋሮቿ አያስበትም። ከመጨረሻው ጠርዝ ላይ ደርሳለች። ይህ ደረጃዋ የማያናድደው ዜጋ ሊኖር አይገባም። ከዚህ በኋላ ያላት ዕድል ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገዶች ለዚህ ዝቅተኛ የዕድገት ደረጃ ባበቃናት ሁሉም ልጆቿ እልህና ታታሪነት ማበልፀግ ነው። የሚጠበቃት አማራጭ ማደግ ብቻ ነው ብለን በታላቅ ቁጭት እንነሳ፤ ይህም ይቻላል። ምክንያቱም ዘመኑ የኢንተርፕረነሮች ነው። የዕድገት የብልፅግና የጀብዱ መሥሪያ ጊዜ ላይ እንገኛለን።

ኢትዮጵያ በ2020 ከራሷ አልፋ ለሌሎች ሀገሮችም የምትተርፍ ሀገር ትሆናለች። ለዓለም በጎ-አድራጊዎች መልካም ውለታቸውን ትከፍላለች። በማደጓም ሊዝናኑባት የሚመጡባት ሀገር ትሆናለች። ሊሰሩባት፣ ሊኖሩባት የሚመጡባት ማራኪ ሀገር ትሆናለች። የበለጠ የሰላም፣ የፍቅር፣ የትብብር፣ የዲሞክራሲ፣ የፍትሕ፣ የእኩልነትና፣ የብልፅግና ሀገር ትሆናለች።

በ2020 ኢትዮጵያ ከ5.1-5.15 ያሉት ዋና ዋና የኤኮኖሚ፣ የፓለቲካና የማህበራዊ ህይወት ተዋንያን ኢትዮጵያን ለማሳደግ ከመቸውም ጊዜ የበለጠ የኢንትራፕረነሪያል የሥራ ፈጠራ ተነሳሽነት ይኖራቸዋል።

በነዚህና በሌሎችም ዘርፎች ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን የሚያስጀምሩ፣ የሚከታተሉና የሚያበረታቱ ፓሊሲዎች ይወጣሉ። የሚያሰሩ ፖሊሲዎችን የማያወጣና፤ የማያስፈፅም የፖለቲካ ስርዓትና-አስተዳደር ኢትዮጵያ ውስጥ ቦታ አይኖረውም። ምክንያቱም የኢትዮጵያ ህዝብ ብቸኛ ምርጫ ሠርቶ ራሱንና ሀገሩን የሚያሳድግ ስርዓት አቋቁሞ ብዙ ሥራዎች መፍጠር ነው።

በተጨማሪም በ2020 ኢትዮጵያ ካለበቸው ዕድገቷ እንድትደርስ የፓለቲካና የአስተዳደር መሪዎቿ ከዜጎቿ መካከል የበለጠ ዕውቀት፣ ሞያ፣ ልምድና በሳል አስተሳሰብ እንዲሁም ለኢትዮጵያ ብልፅግና የሚያመጣ ሀገር አቀፍ ራዕይ ያላቸው እንዲሆኑ ሀገሪቱ ታስገድዳለች።

ከ5.1-5.15 ባሉት ሁሉ ጉልህ ለውጥ የሚያመጣ የፖሊሲ ድጋፍ፣ መልካም ፖለቲካና አስተዳደር መፈጠር አለበት።

በሚፈጠረው አዲስ ስርዓትና የተለወጠ የህብረተሰብ አስተሳሰብ የኢትዮጵያን ብልፅግና እውን የሚያደርግ የኢንተርፕረነሮች ታላቅ መሠረት ይጣላል። በ2020 ኢትዮጵያ 2% የሚሆነው ሠራተኛ ህዝቧ ስልጠና የወሰደ ኢንተርኘረነር ወይም ሥራ ፈጣሪ ይሆናል።

እነዚህ ሥራ ፈጣሪዎች ከ1.4 - 1.6 ያሉትን የኢንተርኘረነሮች መርሆዎች መመሪያቸው አድርገው እንዲንቀሳቀሱ ይሰለጥናሉ። በተጨማሪም በ Annex 1 የቀረበውን የህብት ፈጠራ ቀመር ይጠቀማሉ። የሰው ኃይልን፣ ዕውቀትና፣ ካፒታልን፣ የሲቪክ ተሳታፊዎችን ለተሻለ ሥራ ፈጠራ ይጠቀማሉ።

እስከ 2020 ኢትዮጵያ ከ5.1-5.15 ካሉት ተዋንያን /በአዲስ አስተሳሰብ የታነፁ የፓለቲካ መሪዎችን ጨምሮ/ የምትሸልማቸው ብዙ የሥራ ፈጠራና የብልፅግና አርበኞች ይኖሯታል። በላቁ የፈጠራ ውጤቶቻቸው፣ በተቀባይነታቸው፣ በአመራርና በማስተባበር ብስለታቸው፣ በቀልጣፋ ውሳኔ አሰጣጣቸው፣ በፍትሀዊ ተወዳዳሪነታቸውና ለኢትዮጵያ በሚያስመዘግቡአቸው ከፍተኛ አስተዋፅዖዎች ሀገሪቱ የምትሸልማቸው በርካታ የሥራ ፈጠራ ጀግኖች ይኖራሉ። ኢትዮጵያ የነዚህን ሰዎች ሥራዎች፣ ባህሪዎችና ውጤቶች ለትውልድ መማሪያና መመኪያ በክብር መዝግባ ትይዛለች። በነዚህ ሞዴሎቻችንና በነሱ አርአያ ዙሪያ በመሰለፍ በሚሰሩ የኢኮኖሚ የማኅበራዊ ህይወትና የፖለቲካ አርበኞች ኢትዮጵያ ከኋላ ቀርነት ትወጣለች። የዜጐቿ ሁሉ መመኪያ ሀገርም ትሆናለች።

REFERENCE MATERIALS

AASBEA, Washington, DC. 20037. 2004

ANTHONY ROBBINS, Awaken the Gaint within, a Division of Simon F. Schuster, Inc., 2003

ANTHONY ROBBINS, Unlimited Power, Great Britain, by Simon of Schuster Ltd. 2000

ARUNA BHARGANVA, Every day Entrepreneurs, PK Mad havan. 2003

JACK CANFIELD, The Success Principles, USA 2005

NAPOLEON HILL, Think and Grows Rich, Untied States of America.

NORMAN VINCENT, The Power of Positive Thinking, London 1990

PAUL MCKENNA, Change Your Life in 7 days, London 2004

PEGGY LAMBING, CHARLES P. KUEHL, Entrepreneurship, second edition Prentice Hall, Inc, 2004.

PETER HAGOS GEBRE, Making it in America (Conversation) with successful Ethiopian American Entrepreneurs,

SPENCER JOHNSON M.D. Who Moved my Cheese? New York, 1998

THOMAS L. FRIEDMAN "The World Is Flat" USA, 2005 A brief History of the Globalize World in the Twenty – first Century, 2005

WEROTAW BEZABIH, The Dynamics of Entrepreneurship and the Ethiopian Perspective, A.A. August 2003.

WILSON HARRELL, Only For Entrepreneurs USA, 2004

ኒጋሮራስ ገ/ህይወት ባይከዳኝ - መንግስትና የሕዝብ አስተዳደር አ.አ 1916

ANNEX 1

OPTIMIZE ALL YOUR ASSETS

Human Assets

* Family
* Health
* Sprituality
* Happiness
* Well-Being
* Ethics
* Morals
* Character
* Values
* Unique Ability
* Relationships
* Habits
* Future
* Heritage

Intellectual Assets

* Wisdom
* Relationships
* Formal Education
* Life Experience (both good and bad)
* Reputation
* Systems
* Ideas
* Traditions
* Aliances
* Skills
* Talents



Financial Assets
Capitalize/Earn

- Cash
- Stocks & Bonds
- Retirement Plan
- Businesses
- Real Estate
- Things – Your Financial and Material Possessions

Civic Assets
Contribute/Give

* Taxes
* PrivateFoundations
* Charitable Contributions of Financial Assets, as well as Human and intellectual Assets

* Copyright 2002 Empowered Wealth, LLC

ኢንተርፕሪነርሽፕ እና ልማት በኢትዮጵያ ላይ የተሰጠ አስተያየት

እሥራኤል ካሣ*

በመጀመሪያ የኢትዮጵያ ኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር አገራዊ ራዕይ እንዲኖር፣ አርቆ ማሰብ እንዲቻል በፖለቲካ ሰዎች፣ በንግዱ ህብረተሰብና፣ የተለያዩ ባለሙያዎች መካከል የመወያየት ባህል እንዲዳብር ይህን መድረክ በተከታታይነት በማዘጋጀቱ ያለኝን አክብሮት መግለፅ እወዳለሁ።

በዚህም ምሳሌነት የመንግስትና የግል ኮሌጆች እንዲሁም ሌሎች ተመሳሳይ ማህበራት በተጠናከረ መንገድ የጥናት፣ የምርምርና የውይይት መድረክ ቢፈጥሩ ጠቃሚነት ያኖረዋል።

ይህ አይነት መድረክ በሀገራችን ብልፅግናና ልማት ለማምጣት መፍትሔ ሰጪ እንዲሆን፣ ኢንተርፕረነራዊ አመለካከት የሚያንፀባርቅበት ቢሆን ይበልጥ ስኬታማና ውጤታማ ያደርገዋል።

የዛሬው ውይይታችን ኢንተርፕረነራዊ አመለካከት ምን እንደሆነ ይገልፃል ብዬ አምናለሁ። በተሰጠኝ አጭር ጊዜ ዶ/ር ወሮታው ያላካተቱትን ሀሳቦችና ይበልጥ መዳበር ይገባቸዋል ብዬ ባሰብኩባቸው ላይ ትኩረት በማድረግ አስተያየት ለመስጠት እሞክራለሁ።

ዶ/ር ወሮታው ፅሁፋቸውን በአምስት ክፍሎች ከፍለው ሀሣባቸውን ለውይይት አቅርበዋል። የመጀመሪያው ሰፊ ማብራሪያ የሰጡበት የኢንተርፕረነርሽፕ እና ኢንተርፕረነር ፅንሰ ሀሳብ ሲሆን ሁለተኛው ክፍል የኢንተርፕረነሮች አበረታች ሁኔታዎች፣ ሦስተኛ ክፍል ኢትዮጵያና ልማት፡ በአንተርፕነርሽፕ ርዕይ 2020 እንዲሁም አራተኛው ክፍል ኢንተርፕረነርሽፕ በኢትዮጵያ ሲሆን በመጨረሻም፤

በተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎች (በምሁሩ፣ በንግዱ ህብረተሰብ፣ በሙያ ማህበራት በፖለቲካ ሰዎች፣ ባንኮች፣ በከተማና በገጠሩ ነዋሪዎች) መወሰድ የሚገባቸውን እርምጃዎች በፅሁፉ ተብራርተዋል።

ዶ/ር ወሮታው በዚህ በተሰጣቸው የውይይት ጊዜ ኢንተርፕረነሮች በሀገራችን ልማት ሊያመጡ የሚችሉበትን ጉልህ አስተዋፅዖ ለመግለፅ አስቸጋሪ ስለሚሆን ይህን ፅሁፍ በጥልቀት ሰርተውት በመፅሐፍ መልክ ቢያወጡት ከፍተኛ ጠቃሚነት ሊኖረው እንደሚችል ሳልጠቅስ አላልፍም። እንደ ዶ/ር ወሮታው በሀገራችን በአንተርፕረነር ላይ

ሰዓት ያላቸው ጥናታዊ ፅሁፎች ቢወጡ ምሁሩን፣ የንግድ ሀብረተሰቡን፣ ወጣቱን፣ በተለይ የፖለቲካ ሰዎችን አመለካከት በመለወጥ አብሮ የመሥራትን፣ አዲስ ነገር የማግኘትን፣ የመቻቻልን፣ ተስፋ ያለመቁረጥን እና በራስ የመተማመንን ባህል በማስተማር የበለፀገች ኢትዮጵያን በጋራ ጥረት ለመፍጠር ያስችላል ብዬ አምናለሁ።

ስለዚህ በኢንተርፕረነርሽፕ ላይ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር በይበልጥ ትኩረት ማድረግ ይገባዋል የሚል እምነት አለኝ። ምክንያቱም የኢንተርፕረነሮች ጥናትና ምርምር በተግባር ሊውል የሚችል ስለሆነ ነው።

ኢንተርፕረነርሽፕ የሰው ልጅ የሀብትና የእድገት ዋና ዋና ምንጮች የሚባሉት፣ ከምርት ግብዓቶች ከሆኑት ከመሬት፣ ከሰው ኃይል፣ ከካፒታልና ቀጥሎ አራተኛ ግብአት መሆኑን ማብራሪያ በፅሑፍ ተሰጥቶበታል።

በአጠቃላይ የተሰጠው ትርጉም ኢንተርፕረነር አንድን ነገር ከሌላው በተለየ መንገድ በራስ ተነሳሽነት ኃላፊነት ወስዶ የሚፈፅምና፣ አዳዲስ ሀብት የሚፈጥር ሲሆን አንተርፕረነርሽፕ ደግሞ አሮጌ አሰራር በአዲስ ነገር የሚተካ ሂደት መሆኑን ተገልጿል።

ስለኢንተርፕረነርሽፕ በምንወያይበት ጊዜ የኢንተርፕረነር ትርጉም፣ ቲዎሪዎች፣ የኢንተርፕረነር አይነቶች፣ ባህርያቶች፣ መገለጫዎች፣ ችሎታዎች፣ ጠቀሜታቸው እና አስፈላጊነታቸው እንዲሁም ከሰዎች፣ ከቴክኖሎጂና አካባቢያቸው (External Enviroment) ጋር ስለሚኖራቸው ግንኙነት በሰፊው መታወቅ ይገባዋል። የተለያዩ ሀገሮችን ልምድ መሠረት በማድረግ በሀገራችን የአንተርፕረነርሽፕ ባህል አብዮት እንዲኖር በሰፊው ለህብረተሰባችን ማስተማር ቅድሚያ ተሰጥቶት መስራት የሚገባው ስራ መሆኑ በፅሑፍ ተገልጿል።

ለኢንተርፕረነሮች መፈጠር ምቹ የማህበረ-ኢኮኖሚ፣ የቤተሰብ፣ የትምህርት፣ የፋይናንስ፣ የፖለቲካ መረጋጋት፣ የሀይማኖት፣ የእምነትና የግል ክህሎቶች አስፈላጊ መሆናቸውን በጥልቀት መታየት ይገባዋል። በሀገራችን በፖለቲካው፣ በሀይማኖቱ፣ በማህበራዊ ኢኮኖሚውና በባህሉ ዘርፍ ያሉትን ጎታች አመለካከቶች ለውጦ አዲስ የበለፀገ ማህበረሰብ ለመፍጠር የኢንተርፕረነርሽፕ ፅንሰ ሀሳብ ከ2020 ርዕይ ተነስቶ በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ወደ ህብረተሰባችን ማስረፅ የሚቻልበት ስልት መቀየስ ይገባዋል።

ኢንተርፕረነሮች በኢትዮጵያ በሚለው ርዕስ ጥናት ተደርጎ ጠለቅ ባለ መልኩ በፅሑፍ ቢቀርብ 2020 የዶ/ር ወሮታው ርዕይ ምን ያህል መተግበር እንደሚቻል አሳማኝ ነጥቦች ማመልከት ይቻል ነበር።

በሀገራችን በቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሥልጣን ዘመን ማክተሚያ አካባቢ ከ1950ዎቹና 1960ዎቹ ምቹ ሁኔታ በመፈጠሩ በኢትዮጵያውያን ኢንተርፕረነሮች ባንኮች፣ የኢንሹራንስ ኩባንያዎች፣ የተለያዩ ፋብሪካዎች፣ ዘመናዊ ሆቴሎች፣ ዘመናዊ እርሻዎች፣ ሕንፃዎችና

ልዩ ልዩ የአገልግሎት የሥራ ዘርፎች የተስፋፉበት የሥራ ስሜት የተንሳሳበት ወቅት እንደነበር በዛሬው ውይይት መጥቀስ አስፈላጊ ነው ።

እነዚህ እንደ አዲስ አበባ ንግድ ባንክ፣ መተሐራ ስኳር፣ አዲስ ጎማ፣ አንበሳ መድህን፣ ወንጂ ስኳር፣ ዋቢሸበሌና ሀራምቤ ሆቴሎች፣ ናሽናል ኢንጂነር፣ የመሳሰሉት ፋብሪካዎችና የአገልግሎት ዘርፎች በግልና ለህዝብ አክሲዮን በመሸጥ የተቋቋሙና በኋላም በመንግሥት የተወረሱ እስካሁን ያልተመለሱ በአሁኑ ወቅት የሀገሪቷን ከፍተኛ ታክስ በመክፈል የሚገኙ ተቋማት በወቅቱ በነበሩ በአንተርፕረነሮች የተቋቋሙ ናቸው።

ይህን የፈጠሩት አንተርፕረነሮች በደርግ ዘመን እንቅስቃሴያቸው ታግዶ ሥራቸውን ከማስፋፋት ይልቅ ንብረታቸው ተወርሶ በስደት አንዳንዱም በእሥር ዘመናቸውን አሳልፈዋል።

በአለፉት 10 አመታት በተፈጠረው የገበያ ሥርዓት መርህ ብዛት ያላቸው ድርጅቶች በአንተርፕረነሮች ተቋቁመው በርካታ የሰው ኃይል በመቅጠር፣ ታክስ በመክፈል ለሀገራችን ኢኮኖሚ ጉልህ አስተዋፅዖ በማድረግ ላይ ይገኛሉ።

እነዚህ የተቋቋሙት ባንኮችና ኢንሹራንስ ተቋማት የከፍተኛ፣ የአንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች፣ ሆስፒታሎችና ክሊኒኮች፣ ሆቴሎች፣ አስመጪና ላኪ ድርጅቶች፣ የእርሻና የኢንዱስትሪ ተቋማት፣ በአብዛኛው ኢንተርፕረነሮች በራሳቸው የግል ጥረትና ትግል የተቋቋሙ ቢሆኑም መንግሥት የበለጠ ድጋፍ ቢያደርግላቸው ኖሮ በአጭር ጊዜ፣ በአያሌ እጥፍ የማደግ እድል ይኖራቸው ነበር።

ወደፊትም የተጠቀሰው 2020 ርዕይ ተግባራዊ ለማድረግ የአንተርፕረነሮች በብዛት መፈጠር አስፈላጊ መሆኑ መታመን ይገባዋል። በዚህም ዶ/ር ወሮታው ሰፊ ገለፃ አድርገዋል።

ከድህነታችን ለመውጣት በየአመቱ ቢያንስ 200,000 አዳዲስ የአነስተኛና የመካከለኛ ደረጃ የንግድ ተቋማት መቋቋም ይኖርባቸዋል የሚል የግል ግምት አለኝ።

ለዚህም የመንግሥት አመለካከት ይበልጥ አንተርፕረነራዊ ቢሆንና ነፃ ውድድር ላይ የተመሰረተ የንግድ ሥርዓት ቢመሰርት የሀገሪቷ ገቢ በከፍተኛ ደረጃ ማደግ ይችላል የሚል እምነት አለኝ እንደ ዶ/ር ወሮታው።

በሀገራችን ኢኮኖሚ ከፍተኛ ቦታውን የያዙት የመንግሥት ልማት ድርጅቶች በአሁኑ ጊዜ እየተመሩበት ያለው አካሄድ መለወጥ ይገባዋል። የቦርድ አባላትም ሆኑ ሠራተኞችና ህዝቡ ከመንግሥት ጋር በአክሲዮን ባለቤት ሆነው ድርጅቶቹ ይበልጥ አትራፊ የሚሆኑበት መንገድ ቢቀየስ ለአንተርፕረነር እድገት ትልቅ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

የነፃ ገበያውን ሥርዓት የሚያስተጓጉሉ የፓርቲ ንግድ ድርጅቶች ጠቃሚነታቸው ለህገብና ለመንግሥት የጎላ ስለማይሆን በአክሲዮን ለህገብ ተሸጠው በንግድ ህግ መሠረት መተዳደር ይገባቸዋል። ይህም ነፃ ውድድር የሚሰፍንበት ሥርዓት በዶ/ር ወሮታው ጽሑፍ መከተት ነበረበት።

ዶ/ር ወሮታው በ2020 ኢትዮጵያ በአንተርፕረነሮቿ ዝቅተኛ ደረጃ ካሉት ሀገሮች ምድብ ወጥታ ያለእርዳታ ህገቧን የምትመግብ፣ የምታስተምር፣ የምታክም፣ በራስ የምትተማመን ሀገር ትሆናለች የሚል ርዕይ እንዳላቸው በጽሑፋቸው ገልፀዋል።

በግሌም በዶ/ር ወሮታው ርዕይ እስማማለሁ። ሆኖም ይህን ለማድረግ ምን አይነት ስትራቴጂዎች ይቀየሱ የሚለው መልስ ይበልጥ በዝርዝር ቢያቀርቡት ጥሩ ነበር።

እኔም የበለፀገች ኢትዮጵያን በ20 ዓመት ወስጥ ለማየት የሚከተሉት ስትራቴጂዎችና እርምጃዎች በሥራ ላይ መዋል ይገባቸዋል ብዬ አስተያየት መስጠት እፈልጋለሁ።

1) አንተርፕረነራዊ አመለካከት ያለው ለኢንተርፕረነሮች ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር የማህበራዊ፣ የኢኮኖሚያዊና የፖለቲካ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መፍጠር ምርምርና ሥርዐት የሚያምን፣ ሥራ የሚያሠራ ችግር የሚፈታ፣ ሥራ ፈጣሪውን፣ የሚነሳሳ፣ ፍትሐዊ የሆነ ቀልጣፋ ጥራትና አስተዳደር ያለው አመራር ያለው፣ ውጪ ያሉትን ኢትዮጵያዊ የሚያሳትፍና፣ ከተሞች ራሳቸውን ማስተዳደር እንዲችሉ የሚያደርግ ስርዓት፣
2) አንተርፕረነራዊ ካሪኩለም በመንደፍ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ከፍተኛ ደረጃ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ተማሪዎች እንዲሁም ለገበሬዎች፣ ለሠራተኞች፣ ለሀይማኖትና ለእድር መሪዎች የአንተርፕረነርና የኢንተራፕረነር ሥልጠናዎችን በመስጠት የሥራ ባህሪ እንዲለወጥ አሮጌው አስተሳሰብ በአዲስ እንዲተካ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ፣
3) ሁለቱ የሀብት ምንጭ የሆኑት መሬትና ካፒታል፣ በቀላሉ ለአንተርፕረነሮች ምቹ እንዲሆኑ ማድረግ (ከሌሎች ሀገሮች ልምድ የመሬት ፖሊሲውንና የፋይናንስ ፖሊሲያችን ጥናት አድርጎ መፍትሔ መስጠት፣ ስቶክ ማርኬት፣ የፋይናንስ ጋራንቲ ተቋማት መጀመር እንዲሁም መሬት እንደ ሀብት ተቆጥሮ በነፃ ገበያ ሥርዓት መሸጥ መለወጥ ማስቻል)፣
4) የንግዱን ህብረተሰብ ማጠናከር፣ የአክሲዮን ማህበራትና የኮፕሬቲቭ አንተርፕረነርሺፕ አስተሳሰብ ማስፋፋትና የህብረት ስራ ማህበራት ሊግ በአገር አቀፍ ደረጃ ማቋቋም እንዲሁም መሠረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራዊና የንግድ ህብረተሰቡን ትስስር በመፍጠር አቅም መገንባት፣
5) የExport ገበያችንን ለማሳደግ፣ ቴክኖሎጂን ለማስተላለፍ ጥሬ እቃ ለማግኘትና ሰላም ለመፍጠር በተለይ የአፍሪካን ህብረትን በማጠናከር ብሎም ዩናይትድ ስቴት አፍ አፍሪካን ወይም ፌደራል አፍሪካን ለመፍጠር ግንባር ቀደም ሚና በመጫወት የኢትዮጵያን ኢኮኖሚ ማሳደግ።

ከላይ የተገለፁትን 5 ነጥቦች በዶ/ር ወሮታው የተገለጹት መፍትሔዎች በመንግሥት ሀገ አውጪና አስፈፃሚው እንዲሁም በተለያዩ ሀብረተሰብ ክፍሎች በተግባር የሚውልበት መንገድ ቢኖር የበለፀገች ኢትዮጵያ በአንተርፕረነሮቿ እንደምትፈጠር በእርግጠኝነት መግለፅ ይቻላል።

በመጨረሻም ማርቲን ሉተር ኪንግ ስለኢንተሪፕረነር በገለፀው ጥቅስ ሀሳቤን ሳጠቃልል ይህን እንዳለ በእንግሊዝኛው አነበዋለሁ።

"I have a dream and thousands followed in spite of over whelming obstacles. In order to establish a successful new business the entrepreneurial leader must have a dream and work against all obstacles to achieve it"

የግብርና ዘርፍ ምርምር ለእድገት
(አሁን ያለበት ሁኔታና የወደፊት ተስፋው)

ስሜ ደበላ*

ትረንሞ፤ ዮናስ አድማሱ

መግቢያ

ይህ የውይይት ጽሑፍ የተዘጋጀው የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማኅበር «ርዕይ 2020 በኢትዮጵያ» በሚል መሪ ጭብጥ ሲያዘጋጃቸው በቆዩት ተከታታይ የውይይት ኮንፈረንሶች (ሴሚናሮች) በአንደኛው ተራ ገብቼ፣ ያለኝን ሐሳብና አስተያየት አንዳቀርብ በቀረበልኝ ጥያቄ መሠረት ነው። ይህንን፣ በአብዛኛው በራሴ ገጠመኝና ተመክሮ ላይ የተመሠረተ፣ ወዲያውም ግን ለርእሰ ጉዳዩ ተገቢነት አሏቸው ከሚባሉ ምንጮች የተለቀሙ መረጃዎችን ያካተተ የውይይት መንደርደሪያ ጽሑፍ በዚህ መድረክ ላይ እንዳቀርብ ስጠየቅ፣ ጥያቄውን የተቀበልኩት ደስ እያለኝ መሆኑን ልገልጽ እወዳለሁ።

በተፈጥሮ ሀብት የጥናት መስክ የተሰማሩ ባለሙያዎች (ኤክስፐርቶች)፣ ኢትዮጵያ ለግብርና ልማት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያበረክትና ሞልቶ የተረፈ ሊባል በሚችል የተፈጥሮ ሀብት (ለምሳሌ፣ መሬት፣ ውሃ፣ ቁጥራቸው የሚያመረቃ ለግብርና የሚመቹ ዐበይትና ንኡሳን የአካባቢ/የአየር ጠባያት፣ እንዲሁም በብዝኀ-ሕይወት ዝርያዎች ከፍተኛ ሃብት /ክምችት/) የታደለች ሀገር መሆኗን ይነግሩናል። ለምሳሌ፣ ከሀገሪቱ ጠቅላላ የመሬት ስፋት ማለትም ከ1.12 ሚሊዮን ካሬ ኪሎ ሜትር (ወይም 112 ሚሊዮን ሄክታር) ውስጥ 60 በመቶ የሚሆነው መሬት ለተለያዩ የግብርና ተግባራት የተመቸ መሆኑ ተጠቁሟል። እንዲሁም 30 ሚሊዮን ሄክታር ያህል ስፋት ያለው መሬት በግብርና ሥራ ሊለማ የሚችል መሆኑ፣ ነገር ግን ከዚህ ውስጥ በአንድ በተወሰነ የሰብል ዓመት በተጨባጭ እህል ለማምረት በጥቅም ላይ የሚውለው መሬት ስፋት ከ10 እስከ 12 ሚሊዮን ሄክታር የሚሆነው ብቻ መሆኑም ተጠቁሟል። የኢትዮጵያ የእንስሳት ሀብትም የተለያዩ ዝርያዎችን ያካተተ ሲሆን፣ በዋነኝነት የሚጠቀሱት፤ ከብቶች፣ በግና ፍየል፣ ዶሮ፣ ፈረስ እና ግመሎች ናቸው። የኢትዮጵያ የእንስሳት ሀብት ብዛት በአፍሪካ ውስጥ ከፍተኛ የሆነውንደረጃ የያዘ ነው። በተጨማሪም የመስኖና የዓሣ ሀብት ልማትን የመሳሰሉትን የተለያዩ የግብርና ተግባሮችን ለማዳበር እጅግ ከፍተኛ ዓቅምና ብዛት ያላቸውን ሐይቆችና ወንዞች አገሪቱ እንዳሏት ማንሣትም አስፈላጊ ነው። ስለተፈጥሮ ሀብት ሲነሳም በደን ልማት እና በዕፅዋት መትከል ተግባር ረገድ ሀገሪቱ ያላትን ዕምቅ ዐቅም መጥቀሱም ተገቢ ነው። እንደ እንግዳ ነገር ሊጠቀስ የሚገባው ባይሆንም፣ የማዕከለዊ የስታቲስቲክስ ባለስልጣን በ1998 ባወጣው መረጃ መሠረት፣ እ.ኤ.አ.

---

* ዶ/ር ስሜ ደበላ ከ1978 — 1989 በመንግሥት እርሻ ሚኒስቴር ውስጥ በዴፓርትመንት ኃላፊነት፣ ቀጥሎም በሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ም/ኮሚሽነር፣ በእርሻ ምርምር ተቋም በዳይሬክተርነት ያገለገሉ ሲሆን በForum Africa Country Director ሆነው አገልግለዋል። በአሁኑ ወቅት በአማካሪነት በመስራት ላይ ይገኛሉ።

በ2005፣ 73.044 ሚሊዮን ይሆናል ተብሎ ከሚገመተው የሀገሪቱ ሕዝብ 84 በመቶ የሚሆነው በገጠር የሚኖርና በግብርና ሙያ የተሰማራ በመሆኑ ምክንያት፣ ሀገሪቱ የዚሁ የተፈጥሮ ሀብት ክምችት ባለፀጋ መሆኗ ነው። ይህ ሁኔታ፣ መንግሥት አሁን የሚሠራበትን ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ ቀርጾ በሥራ ላይ ለማዋል እንደዋና መገለጫ አድርጎ ከመለዳቸው ምክንያቶች አንዱ ነው።

ይህም ሁሉ የተፈጥሮና የሰው ኃይል ዕምቅ ሀብት ያላት ሀገር ሆኖም፣ ኢትዮጵያ አሁንም ድረስ በዓለም ላይ በመጨረሻው የድህነት ደረጃ ላይ ይገኛሉ ከሚባሉት ሀገሮች አንዷ፣ የነፍስ ወከፍ ገቢዋ ከ100 የአሜሪካ ዶላር በታች የሆነባት ናት (ምንጭ፤ Human Development Report' 2005)። አገሪቱ፣ ድህነት በጣም የተንሰራፋባት ሀገር ስትሆን ከጠቅላላው ሕዝብ ወደ 44 በመቶ የሚጠጋው በድህነት የሚኖር ነው፣ በዚያው ልክ የምግብ ዋስትና ችግር እጅጉን የጠናባት ናት (ከጠቅላላው ሕዝብ ወደ 42 በመቶ የሚጠጋው በምግብ እጠት ሥጋት ውስጥ የሚኖር ነው)። ሁለቱም ችግሮች፣ ሳያሰልሱ ወይም ፋታ ሳይሰጡ የሚፈራረቁባት ናቸው። ይህም አልበቃ ያለ ይመስል፣ የሀገሪቱ የተፈጥሮ ሀብት ክምችት በሚያሳጋና ሊቆጣጠሩት በማይቻልበት አኳኋን እየተመናመነ ነው፤ ሐይቆችና ወንዞች እየደረቁ፣ የደንና የመሬት ንብረት እየተመናመነ ነው። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ትንሽ መሻሻል የታየበት ቢሆንም፣ በግብርናው ዘርፍ የሚታየው የምርት ውጤትና የዘርፉ ምርታማነት የሀገሪቱን የምግብ፣ የመኖ እና የኢንዱስትሪውን ዘርፍ የጥሬ ዕቃ ፍላጎት ለማሟላት ፈጽሞ የማይበቃ ነው። ይልቁንም ደግሞ፣ የምግብ ዋስትና ችግር በእጅጉ ሥር የሰደደ በመሆኑ፣ ከአምስት (5) አስከ ስድስት (6) ሚሊዮን የሚሆነው ሕዝቧ፣ በአማካይ ስሌት፣ ሁነኛ በሚባለው የምርት ዓመት እንኳን ያለምግብ እርዳታ ሊኖር የማይችልበት ደረጃ ላይ ደርሷል። አንዳንድ ጊዜም፣ እንዲህ ባለው እጠት የሚሰቃየው ሕዝብ ቁጥር፣ ለማስላት በሚያስቸግር ሁኔታ ከፍ ይላል፤ ለምሳሌ፣ እ.ኤ.አ. በ2003 ዓ. ም. ከ13 እስከ 14 ሚሊዮን የሚሆኑ ሰዎች የምግብ እርዳታ የሚጠብቁ ነበሩ።

አሁንም ያለው ይሁን ቀድሞ የነበሩት መንግሥታዊ ሥርዓቶች በተለሚቸው የሀገሪቱ የልማት ዕቅዶቻቸው የተለየና ተቀዳሚ ትኩረት የሰጡት ለግብርናው ዘርፍ ነው። ይህን የመሰለውን አቋም ለመያዝ ወይም እንዲህ ያለውን ትኩረት ለመስጠታቸውም በቂ ማጠየቂያዎች (ምክንያቶች) አሉ። ቀደም ሲል ከላይ እንደተጠቆመው፣ የግብርናው ዘርፍ ዋነኛው የሥራ መፍጠሪያ ዘርፍ ከመሆኑ በላይ፣ አብዛኛው የሀገሪቱ ሕዝብ ለመኖር የሚያስፈልገውን ምግብ የሚያገኝበትም ነው። በአስደናቂ ፍጥነት ቁጥሩ እያደገ ለሚሄደው ሕዝብና የእንስሳት ሃብት የሚያስፈልገው ምግብና መኖ የሚገኘው ከዚሁ ዘርፍ ነው። ሀገሪቱ የሚያስፈልጋትን የውጭ ምንዛሪ ክምችት በማዳበርም ረገድ ይኼው ዘርፍ የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ ነው። ሀገሪቱ ላሏት፣ እንደ ምግብ፣ ጨርቃጨርቅ፣ ያሉትንና ሌሎችንም ሸቀጦች ለሚያመርቱ የኢንዱስትሪው ዘርፎች አስፈላጊውን ጥሬ ዕቃ በማቀበል ሀገሪቱ ያላትን የውጭ ምንዛሪ ሀብት በዚሁ ተጠብቆ እንዲቆይ (እንዳይባክን) ለማድረግም አስተዋጽኦ የሚያደርገው አንዱ ይኼው ዘርፍ ነው። ስለሆነም፣ የኢትዮጵያን የግብርና ዘርፍ ይዞታና የአሠራር ሥልት አሁን ካለበት ወደተሻለ ሁኔታ መለወጡ ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው ነው።

ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸውን ዓይነት ዕምቅ ሀብት ስናይ፣ ታዲያ ይህችን ሀገርና ይህን ሕዝብ ምን ነካው? ብለን መጠየቃችን አይቀርም። ይህን ሁሉ ሀብት ይዘን መራባችን ጨርሶ መቀበል የሚያስችግርና የማይገባ ነገር ነው። የጠቅላላውን ዓለም ሁኔታ ስንመለከትም፣ በኢኮኖሚና የልማት ዘርፎች ምርትን እና ምርታማነትን ለማሻሻልና ለማሳደግ በተለያዩ የሚያስችለን፤ የተፈጥሮና የሰው ኃይል ሀብታችንን በወጉ ለመጠቀም የምንችልበት የተራቀቀ ዕውቀት በተፈለገ ጊዜ የሚገኝበት መሆኑ ይታወቃል። ኢትዮጵያም የዓለም አቀፉ ማኅበረሰብ አባል እንደመሆኗ፣ አሁኑ ወቅት ሜዳ ሙሉ በሆነው በዚህ ዕውቀትና ተመክሮ ተጠቃሚ ለትሆን የምትችል ሀገር ናት። አሁን በዓለም ላይ ከተንሰራፋው ዕውቀትና ተመክሮ በአንድ ነገ ያለው ምንጭ፣ በግብርናው ዘርፍ የተሠራው ጥናትና ምርምር ውጤት ነው። ምርምሩ ያተኮረውም፣ በግብርናው ዘርፍ ምርትንና ምርታማነትን በማሳደግ ረገድ ምትክ የሌለው አስተዋጽኦ የሚያደርገና የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ሐሳቦችን በማፍለቅና ተግባራዊ በማድረግ ላይ ነው።

ከዚህ በላይ የተባለውን ተገን በማድረግ፣ ይህ የውይይት መንደርደሪያ ጽሑፍ ያተኮረው፣ በሀገራችን ውስጥ የግብርና ምርምር ለልማት በሚል ላይ ነው። ጽሑፉ የግብርና ምርምር በኢትዮጵያ ሁኔታ ያሉትን የተለያዩ ገጽታዎች በሚዳስሱ የተለያዩ ክፍሎች ተዋቅሮ የቀረበ ነው። የጽሑፉ የመጀመሪያ ክፍል፣ የግብርና ምርምር በኢትዮጵያ ሁኔታ ያለመባቸውን ግቦች መነሻ አድርጎ፣ በአሁኑ ወቅት ይህ የግብርና ምርምር በኢትዮጵያ ውስጥ የጀመረበትን ሁኔታና አሁን ያለበትን ደረጃ የሚቃኝ ነው። በሚከተሉት ሁለት ክፍሎች ደግሞ፣ የግብርና ምርምር ውጤቶችና እነዚህ ውጤቶች በሀገሪቱ የልማት ተግባር ላይ ያስከተሉት ለውጥ ይተነተናል። በመጨረሻው ክፍል ውስጥ፣ አሁን ያለንበትን ሁኔታ በማሻሻልና የግብርና ምርምር ለሀገሪቱ ብሔራዊ ልማት ሁነኛ አስተዋጽኦ ሊያደርግ በሚችልበት ረገድ ለወደፊቷ ኢትዮጵያ ያለኝን ርእይ እፈነጥቃለሁ።

2. በምርምርና በልማት መካከል ስላለው ቁርኝት አጠቃላይ አስተያየት

ወደ ዝርዝር ጉዳዩ ከመዝለቃችን በፊት፣ በዚህ ጽሑፍ ርእስ ውስጥ በቅድሚያ ሊጤኑ የሚገባቸው ሁለት ዐበይት ቁም ነገሮች መኖራቸውን መገንዘብ ይኖርብናል። የመጀመሪያው ቁም ነገር «ምርምር» የሚለውን ቃል የሚመለከት ነው። *ዌብስተርስ ኒው ወርልድ ዲክሽነሪ* ባሰፈረው ፍች ወይም ብያኔ መሠረት፣ «ምርምር» ሲባል፣ «በአንድ በተወሰነ የዕውቀት መስክ፣ ሥርዓትን በተከተለ፣ ጥንቃቄና ትዕግሥትን በተላበሰ መንገድ፣ ተጨባጭ ግብሮችን ወይም መርሆችን ፈትኖ ለማውጣት[1] የሚደረግ ጥናትና ምርመራን ማኪያሄድ» ማለት ነው። ሁለተኛው ቁም ነገር «ልማት» የሚለውን ጽንሰሐሳብ የሚመለከት ነው። ከላይ የጠቀስነው መዝገበቃላት እንደሚለው፣ ቃሉ «ዕድገት/ማደግ፣ የሁኔታ ወይም የደረጃ ለውጥ ማድረግ፣ መዘጋጀት» ተብሎ ሊፈታ ይችላል። በዚህ መሠረት፣ እንድነጋገርበት የተሰጠኝ ርእስ፣ ቢያንስ የሚከተለው ትርጓሜ ወይም አንድምታ ወይም ማፍታቻ ሊወጣለት የሚችል ነው፤ በግብርናው ዘርፍ የሚኪያሄድ ምርምር፣ በአጠቃላይ የሀገሪቱን ልማት፣ በተለየ ደግሞ

[1] እዚህ ላይ «ግብር» የሚለው ቃል የገባው የግዕዙን «ተገብረ» (ተሠራ፣ ተደረገ፣ ተበጀ፣) የሚለውን መሠረት አድርጎ ሲሆን «ግብር» በተጨባጭ «የተሠራ፣ የተደረገ ወይም የሆነ» (fact) የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ እንዲያመለክት ሆኖ ነው። «መርህ/መርሆች» የሚለውም ቃል የእንግሊዝኛውን "principle/principles" ለመተካት፣ እንዲሁም፣ «ፈትኖ ማውጣት» «ማረጋገጥ» (prove/establish) የሚለውን ሐሳብ ለማመልከት የገባ ነው።

የግብርናውን ዘርፍ ልማት በማሳደግ ረገድ የሚጫወተው ሚና ምንድን ነው?» ላንድም፣ ግብርና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ወይም ከንውን ከሚታይባቸው ዘርፎች አንዱ ስለሆነ፣ «ልማት» የሚለውን ቃል ስናነሣ፣ «የኢኮኖሚ ልማት» ማለታችን እንደሆነ ይታወቃል የሚል መላ ይዘን መሆኑን ማጤን አለብን የሚለውንም መጠቆም አፈልጋለሁ።

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ፣ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ሊነሣ የሚችለው ሌላው ጉዳይ፣ በምርምርና በልማት መካከል ያለውን ቁርኝት የሚመለከት ነው። በዚህ ረገድ፣ በግብርናው ዘርፍ የሚደረግ ምርምር መድረሻ ወይም የመጨረሻ ዓላማ፣ ለዘርፉ የሚያስፈልጉ የሀብት ምንጮችን ምርትና ምርታማነት ከፍ ለማድረግ በሥራ ላይ ሊውሉ በሚችሉ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችና ተግባሮች/ልማዶች ዕውቀትንና ልዩ ልዩ ክህሎቶችን ማፍራት ነው። የግብርናውን ዘርፍ በሚመለከት፣ እነዚህ የተባሉት የሀብት ምንጮች፣ የሰው፣ የእንስሳ ወይም የመሣሪያ ጉልበትን፤ እንደ ዘር፣ እንደ ማዳበሪያና ሌሎችም ያሉትን በግዢ ሊገኙ የሚችሉ የካፒታል ግብአቶችን፤ በግዢ ሳይሆን በተፈጥሮ የሚገኙ፣ እንደ መሬት እና እንደ መስኖ ውሃ ያሉ ግብአቶችን፤ የሥራ አመራር ዕውቀትና ክህሎቶች አስፈላጊ ሆነው በሚገኝበት ሁኔታ የሚውለውን የጊዜ ግብአትና የመሳሰሉትንም ያካትታሉ። ይህን ሁሉ ዘርዝረን ስናበቃ ግን፣ ዋናው ቁም ነገር ወይም ጥያቄ የሚከተለው መሆኑን መርሳት የለብንም፤ ጥያቄው፣ «ከሀገር ውስጥም የመነጩ ይሁኑ ወይም ደግሞ ከውጭው ዓለም ለውስጥ ሁኔታችን እንዲስማሙ ሆነው የተቀዱ ቴክኖሎጂዎችና ልማዶች/ልምዶች መኖራቸው ወይም መገኘታቸው ብቻ፣ ለኢትዮጵያም ይሁን ለሌላ ማንኛውም ሀገር አመርቂ የኢኮኖሚ ልማት መሳካት በቂ ነው ወይ?» የሚል ነው።

ይህ ርዕሰ ነገር በተለያዩ አካባቢዎችና መድረኮች የውይይት ጉዳይ ሆኖ የቀረበ ስለመሆኑ እርግጠኛ ነኝ፤ ሆኖም ግልጽ የሆነ መግባባት ላይ መድረስ የመቻል ያለመቻሉ ጉዳይ ላይ ጥርጣሬ አለኝ። ነገር ግን በኢትዮጵያ ውስጥ የግብርና ምርምር ሥራ ከተወጠነበት ጊዜ አንሥቶ፣ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ያህል የነበረውን የኢትዮጵያን ተመክሮ መሠረት አድርገን ስንነሣ፣ በአጠቃላይ የቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ በተለይ ደግሞ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ ሀገራቱ በኢኮኖሚ ኋላ-ቀር በሆነ ደረጃ የምትገኝባቸውን ችግሮች ወይም ምክንያቶች ለመፍታት ያልቻሉ መሆናቸውን እንገነዘባለን። ለዚህ ምላሽ ሊሆን በሚችል መልክ ደግሞ፣ በግብርና፣ በነበት እርባታ እና በግብርና ውጤቶች ማምረት ላይ ለተሰማሩ የሀገሪቱ ማኅበረሰቦች ሊደርሱና በበቂ ሊዳረሱ የሚችሉ የቴክኖሎጂ የፈጠራ ውጤቶች አልነበሩም ብለው የሚከራከሩ ወገኖች ይኖራሉ። ይህ ክርክር በአንድ ረገድ እውነትነት ያለው ቢሆንም፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለዚህ ማፍረሻ የሚሆኑ ሌሎች ክርክሮችም ሊነሱ ይችላሉ። ለምሳሌ፣ ለአምራቹ ወገን ሊቀርቡና ለሀገሪቱም ሁኔታ እንዲስማሙ ሆነው እንደገና ሊታረቁ፣ ሊበጁ፣ በሀገሪቱም ኢኮኖሚ ዕድገት ላይ ለውጥ ሊያመጡ የሚችሉ፣ ቢያንስ፣ አመርቂነታቸው የተፈተነ አንዳንድ የቴክኖሎጂ ውጤቶች የነበሩ መሆናቸውን፣ በመጠኑም ቢሆን ልብና አንደበትን ሞላ አድርጎ በአስተማማኝነት መናገርም ይቻላል። ይህን ሐሳብ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ወደኋላ በማንሣት መሠረት ያለው መሆኑን ለማሳየት ይሞክራል። ለአሁኑ ግን፣ መጀመሪያ፣ ትኩረቴን በኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚኪያሄደው የግብርና ምርምር ተግባር፣ በአስገኛቸው ውጤቶች፣ በሀገሪቱ ልማት ላይ ባመጣቸው ለውጦች እና በእንከኖቹ ላይ ለማድረግ እፈልጋለሁ።

የግብርና ምርምር ዓላማዎች

በግብርናው ዘርፍ የሚኪያሄድ ምርምር፣ በማንኛውም ሌላ ማኅበራዊ-ምጣኔያዊ የልማት ዘርፍ ረገድ እንደሚደረገው ሁሉ፣ አጠቃላይ አላማ አድርጎ ሕብረተሰቡት ጉዳይ፣ የተፈጥሮና የሰው ኃይል ንብረቶችን ምርትና ምርታማነትን በማላደግ ረገድ የታለመ የዕውቀት ዓይነቶችን፣ መሣሪያዎችን እና ክሂሎችን ፈልጎ መገልገያ ማድረግ ነው። ይህ ዋንኛው ዓላማ ሆኖ ዝርዝር ዓላማዎቹን እንደሚኪያሄደው ምርምር ደረጃ ወይም ዓይነት የተለያዩ ሆነው እናገኛቸዋለን። የግብርና ምርምር በሚከተሉት የምርምር ዓይነቶች ሥር ሊደረጁም ተከፍሎ ሊታይ ይችላል፤

<u>መሠረታዊ ምርምር</u>፤ የዚህ ዓይነቱ ምርምር ዋና ዓላማ፣ ለዘርፉ ተገቢነት ያለውን ዕውቀትና መረጃ ማስባሰብ ነው። በምርምሩ የተገኘው ዕውቀት ተጨባጭ ጠቀሜታ አለው የለውም፣ ወይም በኢንዱስትሪው ዘርፍ ተግባራዊ ይሆናል አይሆንም የሚለው ጥያቄ ከትኩረቱ ውጭ ነው። በልማዱ፣ እንዲህ ያለው ምርምር የሚኪያሄደው በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ወይም በከፍተኛ ደረጃ በተዋቀሩ የምርምር ማዕከላት ነው። በዚህ ሥራ ለሚኪያሄደው ምርምር የተሰጠው ይህ ብያኔ በእርግጥ ትክክለኛው ነው ለማለት ያስቸግራል፤ ምክንያቱም፣ እንዲህ ያለው ምርምር፣ አስቀድመው ለታወቁና ለተለዩ ሸማቾች ወይም ተጠቃሚዎች የሚፈልጓቸውን ዕቃዎች ወይም የማምረቻ ሥልቶች ለማምረት በከፍተኛ ደረጃ ቴክኖሎጂ የተዋቀሩ ኢንዱስትሪዎችም የሚያኪያሂዱት በመሆኑ ነው። ባለንበት በኢትዮጵያ ሁኔታ እንዲህ ያለው ምርምር፣ በተለይ ለግብርናው ዘርፍ ያገለግላል በሚል መርህ የሚሠራውን ስንመለከት፣ በጣም ውሱን ነው።

<u>ስትራቴጂክ ምርምር</u>፤ በዚህ ደረጃ የሚኪያሄደው ምርምር ዋና ዓላማ፣ ለተለየ ሁኔታ ይበጃል ተብሎ ሳይሆን፣ በአጠቃላይ ግን ይጠቅማሉ የሚባሉ ምርቶችን ወይም የማምረቻ ሥልቶችን በማፍለቅ ወይም በማቀድ ላይ ያተኮረ ነው። በዚህ ዓይነት ምርምር የሚገኙ ውጤቶች የተገቢነታቸውና የተስማሚነታቸው ሁኔታ በሌሎች አካለት ታይቶ ለየሁኔታው እንዲበጁ ሆነው መታረቅ አለባቸው። ይህ ዓይነቱ ምርምር የሚኪያሄደው፣ አሁንም፣ በከፍተኛ ተቋማት የምርምር ተቋማት፣ ወይም ልዩ ሙያቸው ምርምር ተለይቶ በተመደበ ተቋማት ሲሆን፣ የሚሠሩት ምርምር የተወሰኑ የልማት ዓላማዎችን በኃላፊነት ለማስፈጸም ለተመደቡ ድርጅቶች መጠቀሚያ ነው።

<u>ተግባራዊ ምርምር</u>፤ ስሙ እንደሚያመለክተው፣ ይህ የምርምር ዓይነት የሚያተኩረው በጥናት የተደረሰባቸውን ውጤቶች በተለይ ለታወቁ ሁኔታዎች ተግባራዊ አገልግሎት የሚሰጡበትን መንገድ በመፍጠር ነው። ቀደም ብለው በተጠቀሱት ሁለት የምርምር ዓይነቶች የተገኙ የዕውቀት ዓይነቶች፣ ክሂሎቶች እና መሣሪያዎች ለልማት ድርጅቶች እና/ወይም ሠራተኞች ሊሰራጩ ወደሚችሉ አገልግሎት ሰጪ ምርትነት ወይም ማምረቻነት ይለወጣሉ። ባለንበት በኢትዮጵያ ሁኔታ፣ የዚህ ዓይነቱ ምርምር በአያሌ የግብርና ምርምር ተቋማት፣ በተለይም ደግሞ በፌዴራሉ መንግሥት እና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ደረጃ ይኪያሄዳል።

<u>የማጣጣም (የማዋደድ) ምርምር</u>፤ በተግባራዊ ምርምር ዘርፉ፣ አንዳንዴም በስትራቴጂክ የምርምር ዘርፉ የተገኙ ውጤቶች፣ ለተለዩ የአካባቢ እና የምርት ሥራ ሁኔታዎች እንዲስማሙ/ እንዲጣጣሙ ተጨማሪ የማሻሻልና የማረቅ ሥራ ከተኪያሄደባቸው በኃላ

በተግባር እንዲውሉ የሚደረግበት የምርምር ዘርፍ ነው። እነዚህ ውጤቶች ለታለሙላቸው አካባቢዎችና ሁኔታዎች የሚበጁ መሆናቸው አስቀድሞ መፈተን አለበት። ይህም በመሆኑ፣ የማጣጣም ምርምር በተለይ በልማት ደርጅቶች፣ በገበሬዎች/በነብት አርቢዎች ወይም በኤክስቴንሽን ፕሮገራም ወኪሎች አማካይነት ተነሳሥቶ፣ የምርምር ውጤቶቹ በሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት ከታሰቡት አካባቢዎችና ተግባሮች ጋር የሚጣጣሙ መሆናቸው ታይቶ የተጠቃሚዎቹን ይሁንታ (ወይም የ«ይለፍ» ማረጋገጫ) ማግኘት አለባቸው።

- <u>ቀጣይነትን የማረጋገጥ ምርምር</u>፤ ይህ ዓይነቱ ምርምር፣ እንደእህል ወይም እንደ እንስሳት ዝርያዎች ላሉት ሕያው ንብረቶች የሚያገለግል ሲሆን፣ ዋናው ዓላማው፣ በምርምሩ ተሻሽለው ለመጠቀሚያ የተሰራጩት የቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ ከሞላ ጎደልም ቢሆን ነባር ባሕርያቸውን እንደያዙ የሚቆዩ መሆናቸውን ማረጋገጥ ነው። የተሻሻሉ የእህል ወይም የእንስሳት ዝርያዎች፣ ዘራቸው ከሌሎች ዝርያዎች ዘር ጋር በመዳቀሉ ወይም በመጋባቱ ምክንያት የቀድሞውን ወይም ነባሩን ባሕርያቸውን ሊያጡ ይችላሉ። እነዚህ አዲስ ዘሮች የሚፈጠሩት በብዙ ወጪ በመሆኑ፣ ነባር ባሕርያቸውን በተቻለ መጠን ለረዥም ጊዜ እንደያዙ እንዲቆዩ ተደጋጋሚ የጥገና ሥራ ሊኪያሄድባቸው ይገባል።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ነጥቦች፣ አስፈላጊ ሆነው በታዩኝ ልዩ ልዩ ምክንያቶች የተነሣበ ተጨማሪ ማብራሪያን ተገቢ ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

- አንደኛ፤ ምንም እንኳን የምርምር ውጤቶች፣ ለአጭር፣ ለመካከለኛ እና ለረዥም ጊዜ አገልግሎት ሊሆኑ የሚችሉ ምርቶች ወይም የአመራረት ሥልቶች መሆናቸው በጊዜወቅም፣ በማንኛውም ዘርፍ ወይም ሳራ የሚኪያሄድ ምርምር የተለያዩ ደረጃዎች ያሉትና ለተለያዩ ዓላማዎች ወይም ግቦች የሚኪያሄድ ነው። አንድም፣ በምርምር የተገኙ ውጤቶች ሁሉ እንዳሉ፣ ወዲያውና በቀጥታ አገልግሎት ላይ የሚውሉ አይደሉም፤ ለአገልግሎት ይወሳሉ የሚለውን ይሁንታ ከማግኘታቸው በፊት ለአገልግሎት ሊወሉ የሚችሉበትን መልክና ቅርጽ መያዝ አለባቸው። በአንዳንድ ሁኔታዎች በምርምር የተገኙ ውጤቶች ወዲያውኑ በቀጥታ ተግባራዊ ሊሆኑ ቢችሉም እንኳን፣ ውጤቶቹ በተግባር በሚወሉባቸው ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ሁኔታዎች በተቻለ መጠን፣ ከፈለሰባቸው ዋጋ ባልተናነሰ የሚያተርፉ ወይም የሚያዋጡ መሆናቸው መረጋገጥ አለበት።

- ሁለተኛው ምክንያት፣ የምርምር ባለሙያዎች (ሳይንቲስቶች) የሕዝብን ገንዘብና ጊዜ የራሳቸውን ፍላጎትና ጥቅም ብቻ ለማሟላት ያወሉታል በማለት ብዙ ጊዜ ሲሰነዘር ከሚሰማው ስሞታ ጋር የተያያዘ ነው። እንዲህ ላለው ትችት መነሾው፣ የአንድ ኅብረተሰብ ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ልማት፣ ለምሳሌ በምግብ በኩል ራስን እንደመቻል ያለው የልማት ፕሮግራም፣ በአጭር ጊዜ ውስጥ ውጤት የሚገኝበት አይደለም የሚል እምነት ነው። ነገር ግን፣ የአንድ የምርምር ዘርፍን ውጤቶች በማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊው ልማት ዘርፍ፡ ውጤት እንዲያስገኙ የማድረጉ ሂደት ባጠቃላይ የረዥም ጊዜ ተግባር መሆኑን ማጤን አስፈላጊ ነው።

ሦስተኛ፣ የሚፈለገውን ወይም የታለመውን ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ግብ (ግቦች) በሚፈለገው የጊዜ ገደብ የመምታቱ ኃላፊነት ለምርምር አገልግሎት ተቋማት የሚሰጡ አይደለም። ተፈላጊውን ውጤት በታለመው የጊዜ ገደብ የማምጣቱ ኃላፊነት የሚወሰነው የምርምር ውጤቶችን በፍጥነት አባዝቶ ለማሰራጨት ሲባል መንግሥት ወይም የንግድ ተቋማት በሚያወጡት (በሚመድቡት) ሃብት እና በሚያጡት የማነቃቂያ ስልቶች ነው። የምርምር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት መሠረታዊ ኃላፊነት፣ የማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ልማት ግቦችን በአፋጣኝ ለመምታት የሚያግዙ መሣሪያዎችንና ሥልቶችን ማዋቀርና ለተጠቃሚዎቹ ማቅረብ ነው። ይህ ስለተባለ ግን፣ የምርምር አገልግሎት የሚሰጡ ተቋማት፣ የሚያመርቷቸውን ቁሳዊም ይሁን አእምሮአዊ ምርቶች፣ ሞክሮ እንደማላየት፣ እንደጎትመት፣ እንደሴሚናር እና እንደመገናኛ ብዙኃን ባሉ የስርጭት መንገዶችና ዘዴዎች እንዲታወቁና በሰፊው እንዲናኙ ከማድረግ ኃላፊነት ወይም ግዴታ ነፃ ናቸው ማለት አይደለም።

የግብርና ምርምር በኢትዮጵያ

4. ጥንተ ነገር (መነሻ)

4.1

ከሁሉ አስቀድሞ፣ የኢትዮጵያ ገበሬዎችና ከብት አርቢዎች፣ እንደየሁኔታው የሚበጁዋቸውን የተለያዩ የግብርና መሣሪያዎችንና ሥልቶችን (የግብርና ቴክኖሎጂዎችን) በብዙ ትውልዶች ዕድሜ ለሚተመኑ ዘመናት ሲገለገሉባቸው እንደነበሩ መታወቅ አለበት። እነዚህ፣ ወይ ከዚያው ከተጠቃሚዎቹ ከራሳቸው የፈለቁ፣ ወይም ደግሞ ከውጭ ጎብረተሰቦች በውሰት ተወስደው ለአካባቢው እንዲስማሙ ሆነው የታረቁ ቴክኖሎጂዎች የተመረቱት፣ በምርምር የለለጠኑ ባለሙያዎች (ሳይንቲስቶች) እንደሚያደርጉት፣ በሥርዓት በተቀናጀ መደበኛ ሳይንሳዊ ምርመራ ሳይሆን፣ በግብርናውና በከብት እርባታው በቀጥታ የተሰማሩት ገበሬዎችና ከብት አርቢዎች፣ በልምድና በተደጋጋሚ መከራ (በማንሳት በመጣል) አስተውለው፣ መርጠው እና ለሁኔታቸው እንዲስማሙ አድርገው በማበጀት ነው። እነሆም፣ ዘመንና ቦታ ያፈሯቸው የእህል ዘሮች፣ የተለያዩ የእንስሳ ዓይነቶች፣ የግብርና መሣሪያዎችና ቆላቁሶች፣ እንዲሁም፣ ዛሬም አብዛኛዎቹ ገበሬዎችና ከብት አርቢዎች የሚገለገሉባቸው፣ ከእህል ምርትና ከእንስሳት እርባታ ጋር የተያያዙ የንብረት አጠቃቀም ሥልቶች፣ እነዚህ ሁሉ የብዙ ትውልዶች ጥረት ከምችት-ውጤቶች ናቸው። እነዚህ ቴክኖሎጂዎችና ተግባሮች ባለፉት ዘመናት የታለመላቸውን የሥራ ግብ በወጉ ያሙዋሉና የተወጡ በመሆናቸው፣ ጠቀሜታቸውን አሌ ማለት አይቻልም። ከዚህም ይልቅ ደግሞ፣ ዛሬ ያሉን የምርምር ባለሙያዎች (ሳይንቲስቶች) የተሻሻሉ የማምረቻ መሣሪያዎችንና ሥልቶችን ወይም የእህልና የከብት ዝርያዎችን ለማምረትና ለማዳበር፣ ሀገሬዎቹ ባፈሩዋቸውና በየጊዜው እየለዋወጡ ባዳበሩዋቸው ዕውቀቶች ላይ የሚመሠረቱ ናቸው።

ይሁንና፣ ጊዜ ይሄዳል ይለወጣልና፣ አሁን ያሉት ተጨባጭ ሁኔታዎችም ሆኑ እየተለወጠ የሚሄደው ሁኔታ የሚፈጥራቸው ፍላጎቶችና ግዴታዎች፣ በነዚህ ነባር በሆኑት ባህላዊ ቴክኖሎጂዎችና የአሠራር ሥልቶች ላይ በተራዛሚ መመካትን የሚፈቅዱ አይደሉም። እንዲህ ያሉት ቴክኖሎጂዎች አብዛኛዎቹ በአሁኑ ጊዜ ያላቸው የክንውን ዓቅም ዝቅተኛ ከመሆኑ ሌላ፣ ወትሮም ሲታለሙ የታሰበላቸው ዓላማ «ለዕለት ተዕለት ኑሮ መገፊያ» የሚበቃ የግብርና ምርት ማፍራት ነው። ዛሬ ያለውም ይሁን የወደፊቱ የግብርና ዘርፍ፣

የዕለት ተዕለት ኑሮን ለመግፋት የሚውለው የግብርና ተግባር ሊያመዋላ ከሚችለው በላይ ያሉና የሚፈጠሩ ችግሮችንና ፍላጎቶችን ለማሙዋላት የተጠመደ ሆኖ መልማት አለበት። ከሁሉ በፊትና በተቀዳሚ፣ የግብርናው ሥልት፣ በአፋጣኝ እያደገ የሚሄደውን የሰውና የእንስሳት የምግብና የመኖ ፍላጎት ማሙዋላት መቻል አለበት። የኢንዱስትሪው ዘርፍ የሚያስፈልጉትንም ጥሬ ዕቃዎች ማቅረብ መቻል አለበት፤ በዚህም፣ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማንቀሳቀስ የሚያስፈልጉትን የማምረቻ ዕቃዎችና ሌሎችም ቆሳቁሶች ከውጭ ለማስመጣት የሚያስፈልገውን የውጭ ምንዛሪ ለማግኘት ወይም ያለውን ክምችት ለማዳን የሚያስችል መሆን አለበት፤ ይህ ሁሉ እውን ይሆን ዘንድ ደግሞ፣ የግብርናው ዘርፍ እያደገና እየሰፋ በሚሄደው ዓለም አቀፍ ገበያ ላይ መወዳደር የሚችል ሆኖ መገኘት አለበት። በመጨረሻም፣ ነባር የሆኑት ባህላዊ የግብርና ዘዴዎች አሁን ላለንበት ሁኔታ ያላቸው ዓቅም በቂ ስላልሆነ፣ በነሱ መጠቀሙ እንደመሬት፣ እንደ አፈር፣ ውሀ እና ደን ያሉትን የተፈጥሮ ንብረቶች ወደማመናመን የሚያመራ ነው። ነባሮቹን መለወጥ ወይም መተው ያለብን፣ የማምረቻ መሠረታችን የሆነውን የተፈጥሮ ንብረታችን መጠበቁንና በወጉ እጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ ሲባል ነው። እስከዛሬ ድረስ ሲሠራበት የቆየው፣ ከእጅ ወደ አፍ ያህል ለማምረት ብቻ ብቃት ያለው ነባር የግብርና ዘዴና ሥልት ለአለንበት ሁኔታ ብቁ አለመሆኑን መገንዘቡ ነው የኢትዮጵያን የግብርና ዘርፍ ለመለወጥና ለማሻሻል ምክንያት የሆነው። ይህ ለውጥና መሻሻል ተግባራዊ ሆኖ ተጨባጭ ውጤትን ሊያመጣ የሚችለው ደግሞ፣ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቅና በተግባር ላይ በማዋል ሲሆን፣ እነዚህ ቴኪኖሎጂዎች ደግሞ አሁን ባለንበት ሁኔታ ሊፈጠሩ የሚችሉት በመደበኛነት ተቀርጾ በተዘረጋ የግብርና ምርምርና ልማት ፕሮግራም አማካይነት ነው።

ሳይንሳዊ ምርመራን መሠረት ያደረገ መደበኛ የግብርና ምርምር ባህል፣ በአፍሪካ ደረጃ ብቻ እንኳን ሲታይ ወደኢትዮጵያ የዘለቀው በጣም ዘግይቶ መሆኑ የማይታወቅ አይደለም። ምንም እንኳን በጣም ቀደም ሲል በአምቦ እና በጂማ የእርሻ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ቀለል ያሉ የምርምር መከራዎች ሲከናወኑ የነበሩ ቢሆንም፣ የግብርና ምርምር በመደበኛነትና በሳይንሳዊ ገጽታው ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የተጀመረው እ.ኤ.አ. በ1954 ዓ.ም. የዓለማያ የእርሻ ኮሌጅ ከተቋቋመ በኋላ ነው። ይህም ሆኖ ግን፣ በነዚህ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ሲከያሄዱ የነበሩት መከራዎች ይከናወኑ የነበሩት በመምህራን፣ በአብዛኛውም በጊዜው በዘርፉ ይሰጡ ለነበሩት የቀለም ትምህርቶች ድጋፍ ለመስጠት ብቻ ሲባል ነበር። ይህ ስለተባለ ግን፣ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በምርምር ረገድ ያደረጓቸውን ጥረቶች ዋጋ ማሳነስ ማለት አለመሆኑ ግልጽ ነው።

በኢትዮጵያ መደበኛ የግብርና ምርምር አገልግሎት በመስጠት ረገድ በእርግጥም «እመርታ» ታየ የሚባልበት፣ እ.ኤ.አ. በፌብሩዋሪ 1966 ዓ.ም.፣ በፊት የግብርና ምርምር ተቋም (Institute of Agricultural Research (IAR)) በመባል ይታወቅ የነበረው ክፍል በተቋቋመበት ጊዜ ነው። ይህ ተቋም፣ ሲጸነስ የነበረውን የሥራ ኃላፊነትና ድርጅታዊ መዋቅር እንደያዘ አገልግሎት በመስጠት ቆይቶ፣ እ.አ.አ. በ1997 ዓ.ም. የድርጅት መዋቅር ለውጥ ተደርጎለት፣ ስሙም የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት (Ethiopian Agricultural Research Organization (EARO) በሚል ስያሜ ተለውጦ እስካሁንም አለ። ከዚያ ጊዜ ጀምሮ፣ የግብርና ምርምርን በብቸኛ ተግባርና ኃላፊነት ይዞ ሲንቀሳቀስ የቆየና አሁንም በዚያው የቀጠለ ብሔራዊ ተቋም እሱው ብቻ ነው።

፲፩ የግብርና ምርምር አሁን ያለበት ይዞታ/ደረጃ

፲፩.፩ የምርምር ተቋማት

በለቅጥ ወርቁ ዓመታት በሀገሪቱ ያሉት የምርምር ተቋማት ቁጥር በእጅጉ ከፍ ብሏል። በዚህ ረገድ ምንም እንኳን አንዳንድ ዓለምአቀፍ ድርጅቶች የተወሰነ አስተዋጽኦ ያደረጉ መሆኑንም ቢታወቅም፣ ዋነኛውን ሚና ሲጫወት የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት ነው። ምንም እንኳን አንዳንድ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና በግብርና ነክ ንግድ የተሰማሩ ተቋማት፣ የምርት ተግባራቸውን ዓቅም ከፍ ለማድረግ ቀለል ያሉ መሣሪያና ዘዴ የማሻሻል ምርምሮችን በማከያሄድ ተግባር የተሰማሩ ቢሆንም፣ ሥራዬ ብለው የግብርና ምርምር ተግባሮችን በተለየ ትኩረት የሚያከናውኑ የግል የምርምር ተቋማት የሉም። በመሆኑም ዘርፉ፣ በአንድ ሀገር በግብርና ምርምር ተግባር የተሰማሩ ተቋማት ስብስብ «ብሔራዊ የግብርና ምርምር ተግባር ሥርዓት» National Agricultural Research System (NARS) በሚል ይታወቃል። «ሥርዓት» የሚለው ቃል፣ በተቀናጀ ሥልት የሚንቀሳቀሱ ተቋማዊ አሠራሮችን (ዩኒትስ) ስለሚያመለክት፣ በዚህ ሁኔታ ይህንኑ አውቀን በጥንቃቄ ልንጠቀምበት ይገባል። በኢትዮጵያ ውስጥ፣ በዚሁ ስያሜ የሚንቀሳቀሱትን ተቋማት በቅርብ ለምናውቃቸው ወገኖች፣ እንዲህ ያለውን ስያሜ የሚመጥን አካልና ነፍስ ሙሉ ለሙሉ ተላብሰው እውን የሚሆኑበት ጊዜ የሩቅ መንገድ የሚያስኬድ መሆኑን ለመገንዘባችን አርግጠኛ ነኝ። አሁን ባለንበት ሁኔታ ግን፣ ምርምርን በማኪያሄዱም ሆነ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የግብርና ምርምር ተግባር ሥርዓት በሚለው ስያሜ ጥላ ሥር የሚንቀሳቀሱት የተለያዩ ተቋማት የሚያካሂዱዋቸውን የምርምር ሥራዎች በማቀናጀቱም ረገድ ያለውን ሚና የሚጫወተው ቁንጮ አካል የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት (EARO) በመባል የሚታወቀው ተቋም ነው።

አሁን ባለንበት ደረጃ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓት የሚያካትታቸው የምርምር ተቋማት የሚከተሉት ናቸው፤

- **ፌዴራላዊ የምርምር ማዕከላት**፤ ሙሉ በሙሉ በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት የበላይ አመራር ሥር የሚንቀሳቀሱት የምርምር ማዕከላት ወይም ቤተ ሙከራዎች 13 (በሥራ ሃስት) ሲሆኑ፣ በክልላዊ የግብርና ምርምር ተቋማት ኃላፊነትና ሥልጣን ሥር የሚንቀሳቀሱ፣ ነገር ግን የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት በሚመራቸው ፕሮግራሞች መሠረት ሥራቸውን የሚያከናውኑ ሌሎች ሁለት የምርምር ማዕከላት አሉ። እነዚህ ማዕከላት/ ቤተ መከራዎች የሚገኙት በተለያዩ ክልሎች ነው።
- **ክልላዊ የምርምር ማዕከላት**፤ በክልላዊ የግብርና ምርምር ተቋማት የበላይ አስተዳዳሪነት የሚመሩና የሚንቀሳቀሱ፣ ቀደም ሲል የተቋቋመ 10 (አሥር) የምርምር ማዕከላት በኦሮሚያ፣ በአማራ፣ በትግራይ፣ በደቡብ ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ እና በጋምቤላ ክልሎች ይገኛሉ። ከዚህ በተጨማሪ፣ ከጋምቤላ በስተቀር፣ በተጠቀሱት ክልሎች በሙሉ ስድስት የምርምር ማዕከሎች በመገንባት ላይ ናቸው።
- **ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት**፤ የግብርና ሳይንስ ትምህርቶች በሚሰጡባቸው የሀገሪቱ ዩኒቨርሲቲዎችና ኮሌጆች በመሉ የተወሰኑ የምርምር ሥራዎች ይኪያሄዳሉ።
- **ዓለምአቀፍ የግብርና ምርምር ማዕከላት**፤ በአሁኑ ወቅት፣ ዓለምአቀፍ የግብርና ምርምር አማካሪ ቡድን በመባል በሚታወቀው ተቋም ሥር የሚንቀሳቀሱ ስድስት ዓለምአቀፍ የግብርና ምርምር ማዕከላት በኢትዮጵያ ቅርንጫፎቻቸውን ከፍተዋል። በተጠቀሰው

የምርምር አማካሪ በዑድን ሥር ሳይሆን፣ ከሱ ውጭ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ሌላ ዓለምአቀፍ የግብርና ምርምር ማዕከልም አለ።[2]

እነዚህ የምርምር ተቋማት በሀገሪቱ ውስጥ ያላቸውን ስብጥር በሚመለከት፣ ተቋማቱ የሚገኙት የሀገሪቱ ዋና ዋና የግብርና ዞኖች በሚባሉት በአብዛኛዎቹ ሥፍራዎች ነው። ቀደም ሲል፣ የግብርና ምርምሩ ትኩረት የነበረው፣ በቂ ትኩረት ሳይሰጣቸው በቆዩትና በተለይ በከብት ርቢና እርሻን ከከብት ርቢ ቀላቅለው የሚንቀሳቀሱ ጎበረተሰቦች ባሉባቸው የውኃ-አጥ መሬት ክልሎች ላይ ነበር። በነዚህ አካባቢዎች ያሉትን ችግሮች ለመፍታት የተደረጉ ጥረቶች ቢኖሩም፣ አሁንም ብዙ የልማት ሥራ በተሻለ ሁኔታ መሥራት የሚያስፈልግበት ሁኔታ ነው ያለው።

4.2.2 ፕሮግራሞች

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት የግብርና ምርምር ፕሮግራሞቹን የሚመራው በአምስት መምሪያዎች ሥር አዋቅሮ ነው (እነዚህም፣ የእህል፣ የእንስሳት፣ የዐፈርና የውሃ፣ የደን እና የውኃ-አጥ ሥፍራዎች የግብርና ልማት ተብለው የተከፈሉ ናቸው)። ተቋሙ ሁለት የሥራ ክፍሎች (ዲፓርትመንቶች) አሉት (እነሱም፣ ሶሲዮ-ኢኮኖሚክስ እና የምርምር ኤክስቴንሽን ተቋም እና ልዩ የብሔራዊ ምርምር ፕሮግራሞች ክፍል የሚባሉት ናቸው)። በኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት መረጃ መሠረት ከላይ የተጠቀሱት የሥራ ክፍሎች የሚያኪያሂዷቸው የምርምር ፕሮግራሞች 56 ያህል ናቸው። የስያሜና የአወቃቀር ልዩነት የሚታይባቸው ከመሆናቸው በስተቀር፣ በሌሎች የግብርና ምርምር ተቋሞች በሙሉ የሚኪያሄዱት ፕሮግራሞች ሁሉ ተመሳሳይነት ያላቸው ናቸው።

- **የእህል ሰብል ምርምር ዘርፍ** ዋና ትኩረቱ አስፈላጊነታቸው ከፍ ባለ የእህል ዘሮች ላይ ምርምር ማኪያሄድ ነው፤ ከነዚህ ውስጥ፣ ጥራጥሬ፣ የአበባ እህሎች፣ የዘይት ሰብሎች፣ ፍራፍሬና አትክልት፣ እንደ ድንች ያሉ የሥራሥር ምግቦች፣ ወዘተ. ጥቂቶቹ ናቸው። ይህ ዘርፍ በዘረጋቸው ፕሮግራሞች ረገድ ካሉት ሁሉ እጅግ ትልቁ ሲሆን፣ የእህል ዘሮችን በማሻሻል፣ በመንከባከብና አጠቃቀማቸውን በመከታተል በኩል ተገቢውን ምርምር ያኪያሂዳል።
- **የእንስሳት ሳይንስ ምርምር** የሚባለው ዘርፍ፣ የእንስሳት ዝርያዎችን ማሻሻልንና መንከባከብን፣ የወተትና የጋማ ከብቶችን፣ የቀንድ (የሥጋ) ከብቶችን፣ የበጎችንና የፍየሎችን፣ የዶሮዎችን፣ የዓሣዎችን እና የንቦችን እርባታ መምራትና መቆጣጠርን የሚመለከት ዘርፍ ነው።

---

[2] አማርኛውን ከእንግሊዝኛው ጋር እያመሳከሩ ለማንበብ እንዲቻል የተባሉትን የምርምር ተቋማትና ማዕከላት በነሱም ሥር የሚንቀሳቀሱትን ድርጅቶች የእንግሊዝኛ ስያሜ እንደቅደም ተከተላቸው እናቀርባለን። የአራቱ የምርምር ማዕከላት የእንግሊዝኛ ስያሜ፣ እንደቅደም ተከተላቸው፤ **Federal research centers; Regional research centers; Higher learning institutions; International agricultural research centers** ሲሆን፣ በአራተኛው ጎራ ሥር የሚንቀሳቀሱት ማዕከላት የእንግሊዝኛ ስያሜ ምሕጻር ደግሞ፣ **CIAT, CIMMYT, CFOR, ICRAF, ILRI, IWMI** ሲሆን፣ እነዚህን በበላይነት የሚመራው የምርም ቡድን **Consultative Group on International Agricultural Research (CGIAR)** ይባላል።

የዐፈርና የውኃ ምርምር ዘርፍ፣ የዐፈር ንብረትን ባሕርይ እየለዩ መፈረጅን፣ የዐፈርን ለምነትና የዕፀዋትን ማዳበሪያ አቀራረብን፣ የውኃ አጠቃቀምንና ቁጠባን መቆጣጠርን፣ የመስኖና የውኃ ፍሳሽ አያያዝን የሚያጠና ዘርፍ ነው።

የደን ሀብት ምርምር ዘርፍ የደን ዛፍ ዘር ሳይንስና ቴክኖሎጂን፣ የእርሻ ማሳ ደን (agro-forestry) ልማትን፣ የተፈጥሮና ሰው-ተከል ደኖችን እና የደን ውጤቶችንና አጠቃቀምን የሚያጠና ዘርፍ ነው።

የውኃ-አጥ መሬት የግብርና ምርምር ዘርፍ የግጠሻ መሬትን፣ የቀንድ ከብቶችን፣ ግመሎችን፣ ዝናም አጠር (ቆላማ) ሰብሎችን፣ የደረቅ መሬት (የቆላ) የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ጥበቃ "የደረቀ መሬት (ቆላ) ደን ልማት የሚመለከት ዘርፍ ነው።

የሶሲዮ-ኢኮኖሚክስና የምርምር ኤክስቴንሽን ዘርፍ የአመራረት ኢኮኖሚክስና የእርሻ ጥበብ ዘዴዎችን፣ የግብርና ኤክስቴንሽን ምርምርንና የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ማስተላለፍን፣ የግብርና ውጤች ሽያጭንና ፖሊሲን የሚመለከት ዘርፍ ነው።

የልዩ ብሔራዊ ፕሮግራሞች ምርምር ዘርፍ፣ የግብርና ባዮቴክኖሎጂ ልማትን፣ የዕፀዋት እንክብካቤ ምርምርን፣ የምግብ ሳይንስና ድኅረ-ምርት፣ ዕፀ መዐዛዎችን፣ የእርሻ መሣሪያዎችንና ኃይል ማመንጫዎችን እና የእርሻ አካባቢ የአየር ጠባዮችን የሚመለከት ዘርፍ ነው።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት የምርምር ዘርፎች ዝርዝር እንደሚያመለክተው፣ የግብርና ምርምር ዘርፉ የሚያካትታቸው ፈርጆች በጣም ሰፊ ናቸው። የምርምሩ ተግባር ነባርና ልማዳዊ የሆኑትንም፣ እንደባዮ-ቴክኖሎጂ ያሉትን አዲስ የፈለቁ መስኮችንም ያካትታል።

4.2.3 ምርምር ተቋማት የሃብት ይዞታ

በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በምንጠቀምበት አገባቡ፣ «የግብርና ንብረቶች» የሚለው ጽንሰ ሐሳብ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓት ለሚያካሂደው የምርምር ተግባር አስፈላጊ (ወይም የምርምሩ ትኩረት) የሆኑትን የቁሳቁስ፣ የሰውና የገንዘብ ንብረቶችን (ሀብቶችን) የሚያመለክት ነው። በኢትዮጵያ ብሔራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓት ሥር ያሉት የምርምር ተቋማት በሙሉ ለሚያካሂዷቸው የምርምር ፕሮግራሞች ያላቸውን ሃብት ይዞታና ስብጥር ምን እንደሚመስል በግልጽ ማመላከቱ አስቸጋሪ ነው። በተለምዶ፣ ካሉት የምርምር ሃብት በርከት ያለውን ድርሻ ሲያገኝ የነበረው የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት (ኢግምድ) ሲሆን፣ አሁንም ድረስ ሁኔታው ከዚህ የተለየ አይደለም የሚል ግምት አለኝ። ስለዚህም፣ አሁን በእጃችን ያለውና እዚህ የቀረበው መረጃ ይኸው ድርጅት የሚጠቀምባቸውን ብቻ የሚመለከት ነው። ከዚህ ሌላ መታወቅ ያለበት ነገር፣ በየክልሎቹ ያሉት የምርምር ማዕከሎች ለሚያካሂዷቸው ብሔራዊ የምርምር ፕሮግራሞች የሚያስፈልጋቸውን ወጪ የሚችለው ይኸው ድርጅት ሲሆን፣ የተባሉት ክልላዊ የምርምር ማዕከሎች የበጀታቸውን አብዛኛውን ድርሻ የሚያገኙት ከየክልሎቻቸው መስተዳድሮች ነው።

ቁሳዊ ኃብት ከላይ በንኡስ ክፍል 3.2.1 እንደተጠቆመው፣ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት፣ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚያንቀሳቅሳቸው 13 የምርምር ማዕከላትና የምርምር ቤተ ሙከራዎች አሉት። በተጨማሪም ሌሎች ስድስት የምርምር ማዕከላት በመቋቋም ላይ ናቸው። ነባርነት ካላቸው ማዕከላት አንዳንዶቹ (ለምሳሌ፣ የባኮ፣ የሆለታ

እና የወረር የምርምር ማዕከላት) ቀደም ሲል የግብርና ምርምር ተቋም በመባል ይታወቅ የነበረው ተቋም ራሱ ከመቋቋሙ በፊት ጀምሮ የነበሩ ናቸው። ነገር ግን፣ እነዚህ ነባር የሆኑትና ከትርብ ጊዜ ወዲህ የተቋቋሙትም የምርምር ማዕከላት በተለያዩ ወቅቶች ተለይድሰ የተደረገላቸው ሲሆን፣ አስፈላጊ የሆኑት የምርምር መሣሪያዎችና ሌሎችም ቁሳቁሶች ከመንግሥትና ከውጭ ድርጅቶች በተለገሠ ገንዘብ ተገዝተውላቸዋል። ምንም እንኳን ሊሻሻሉ የሚችሉና የሚገባቸው ነገሮች ቢኖሩም፣ እነዚህ ማዕከሎች አስተማማኝ ሊባል በሚችል ጥሩ ሁኔታ ላይ የሚገኙ ናቸው።

- የሰው ኃይል፣ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት ቀጥሮ የሚያሠራው የሰው ኃይል ንበረት በሦስት ይመደባል፣ የምርምር ባለሙያዎች፣ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪዎች እና የአስተዳደር ሠራተኞች። እ.አ.አ. በ2005 ዓ.ም. ድርጅቱ የነበሩት ሠራተኞች ጠቅላላ ቁጥር 2914 ሲሆን፣ የምርምር ባለሙያዎች 591፣ የቴክኒክ ድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች 1119፣ የአስዳደር ሠራተኞች 1204 ነበሩ። ከምርምር ባለሙያዎቹ ውስጥ 98ቱ የዶክትሬት፣ 214ቱ የኤም.ኤ/የኤም.ኤስ.ሲ፣ 9ኙ የከብት ሕክምና ዶክተርነት፣ 270ው የቢ.ኤ እና የቢ.ኤስ.ሲ. ዲግሪ ያላቸው ነበሩ።

በክልል ደረጃ ያሉት የምርምር ማዕከላት ያላቸውን የሰው ኃይል ይዞታና መጠን አስመልክቶ ያለው መረጃ የተሟላ አይደለም። ሆኖም ግን፣ አሁን በእጄ የገባው መረጃ እንደሚያመለክተው ከሆነ፣ ቢያንስ አንዳንዶቹ ተቋሞች ያሉዋቸው ሠራተኞች ብዛት ጠቀም ያለ ነው። ለምሳሌ፣ የአማራ ክልል 187፤ የኦሮሚያ ክልል 167፤ የደቡብ ክልል 68፤ የትግራይ ክልል 53 ሠራተኞች አሉዋቸው።

በግብርና የምርምር ተግባር የተሰማሩ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ያላቸውን የሰው ኃይል መጠን መረጃ ማግኘቱ ቀላል አልነበረም። ይሁን እንጂ፣ በነዚህ ተቋማት ያሉት የምርምር ባለሙያዎች በብዛትም በጥራትም ከፍ ባለ ደረጃ ሊገኙ የሚችሉ መሆኑን መገመት ይቻላል። ወዲያወም ደግሞ፣ የነዚህ ባለሙያዎች ተቀዳሚ የሥራ ኃላፊነት ማስተማር፣ በዚህም ምክንያት ምርምር ማከያሄድ ከጠቅላላ ሥራቸው በጣም አነስተኛውን ድርሻ የሚይዝ መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለዚህም፣ የነዚህ ባለሙያዎች ቁጥር፣ ከሙሉ ጊዜ የምርምር ተግባር ስምሪት አንጻር ሲታይ በጣም ጥቂት ነው።

- የገንዘብ ኃብት፤ በየክልሉና በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ያሉ የምርምር ተቋማት ለምርምር የተመደበላቸውን በጀት ማወቁ በሌላው ዘርፍ ያለውን መረጃ ከማግኘቱም የበለጠ ከባድ ነው። ይሁን እንጂ የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት ላለፉት ስድስት ዓመታት ተመድቦለት የነበረውን በጀት በሚመለከት የተሟላ መረጃ አለን። የድርጅቱን በጀት የገቢተኛ-ከፍተኛ መጠን ስናሰላ፣ እ.አ.አ. በ2000/01 ዓ.ም. ተመድቦለት ከነበረው 167.8 ሚሊዮን ብር፣ በ2001/02 ዓ.ም. ተመድቦለት እስከነበረው 260.6 ሚሊዮን ብር ድረስ ደርሶ እንደነበር እንመለከታለን። ይህንን የገንዘብ መጠን በአማካይ ደረጃ ስናሰላው፣ ድርጅቱ ላለፉት ስድስት ዓመታት በየዓመቱ ይመደብለት የነበረው ገንዘብ 230.1 ሚሊዮን ነበር ማለት ነው (ሰንጠረዥን ይመልከቱ)።

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ድርጅት በጀት በሁለት ጎራ ተከፍሎ የሚመደብ ነው፤ ማለትም፣ «ካፒታል» እና ‹መደበኛ ወጪ መደበኛ ወጪ ሥራ ማስኬጃና የደሞዝ ወጪን የሚያዝ ነው። ለካፒታል በጀት በአማካይ በዓመት 186.7 ሚሊዮን የተመደበ ሲሆን፣ ይህ

ከመሆኑም ዓመታዊ በጀት 81.1 በመቶ ያህሉን ይይዛል። ቀሪው 18.9 በመቶ የመደበኛ ወጪው ድርሻ ነው። ከመደበኛ ወጭው ውስጥ 65 በመቶ የሚሆነው ለደሞዝ ሲውል፣ ለሥራ ማንቀሳቀሻ የሚውለውን ይይዛል። ከዚህም ሌላ፣ ከሰንጠረዡ እንደሚታለው የ«ካፒታል» በጀቱ አማካይ አኃዝ፣ የ«መደበኛ ወጪውን» በጀት አማካይ መጠን በ4 እጥፍ ያህል፣ የ«ደሞዝ» አማካይ መጠን ደግሞ፣ «የሥራ ማንቀሳቀሻ» በጀቱን አማካይ መጠን ወደ 2 እጥፍ በሚጠጋ መጠን ይበልጣል። የ«ካፒታል» በጀቱ መጠን ከፍ ያለበት ምክንያት፣ በአንድ በኩል ስድስት አዳዲስ የምርምር ማዕከሎች ያህል ነው (ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ)። በሰንጠረዡ ላይ ከተዘረዘሩት ማዕከላት ውስጥ አንዳንዶቹ እንደገና እንዲታደሱና እንዲጠናከሩ የተደረጉ መሆናቸው ነው።

ከ2001 እስከ 2006 ለኢግምድ የተመደበለት በጀት (በሺህ ብር ሲሰላ)

ዓመት	ካፒታል	ቋሚ ወጪ			ጠቅላላ ድምር
		ሥራ ማንቀሳቀሻ	ደሞዝ	ድምር	
2000/01	135,340.8	11,010,7	21,450.9	32,461.6	167,802.4
2001/02	223,341.9	13,000.0	24,306.3	37,306.3	260,648.2
2002/03	167,479.7	15,451.0	32,163.8	47,614.8	215,094.5
2003/04	250,759.0	15,451.0	32,163.8	47,614.8	298,373.8
2004/05	178,349.5	13,019,7	32,307.4	45,327.1	223,676.7
2005/06	165,050.7	16,931.7	33,203.7	50,135.4	215,186.1
አማካይ	**186,721.0**	**14,140.0**	**29,266.0**	**43,410.0**	**230,130.3**

ምንጭ፤ የኢ.ት. የግብርና ምርምር ድርጅት የመረጃ ሰነድ (ያልታተመ)።

በኢትዮጵያ ውስጥ ለምርምር የሚያስፈልገው ገንዘብ ምንጩ፣ ወትሮም ይሁን አሁንም፣ ከመንግሥት ግምጃ ቤት የሚመደብ፣ ከገንዘብ ተቋማት የሚገኝ ብድር እና ከተለያዩ ምንጮች የሚለገስ እርዳታ ነው። የተለያዩት ምንጮች ለምርምር በጀቱ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ መጠን ሲሰላ፣ 41.41 በመቶው ከመንግሥት፣ 58.45 በመቶው ደግሞ ከብድር የሚገኝ ነው (ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ)። በሰንጠረዡ ላይ ከተዘረዘሩት አኃዞች ማየት እንዲሚቻለው፣ በእርዳታ መልክ የሚገኘው ገንዘብ እጅግ ዝቅ ያለ ነው። በብድር የሚገኘውም ገንዘብ የሕዝብ ገንዘብ ነው ብሎ ሊገመት የሚችል ነው፤ ምክንያቱም፣ ይህንን ብድር፣ ቢያንስ በመርህ ደረጃ፣ የኢትዮጵያ ሕዝብ በሆነ ወቅት ወደፊት መክፈሉ አይቀርም ተብሎ ስለሚታሰብ ነው።

ምንጭ	ብር	መቶኛ ስሌት
የመንግሥት ግምጃ ቤት	95,302,127	41.41
ብድር	134,500,063	58.45
እርዳታ	92,585	0.14
ድምር	**229,894,775**	**100.00**

ምንጭ፤ የኢግምድ መረጃ (ያልታተመ)

5. የግብርና ምርምር ውጤቶች/ እስከዛሬ የተከናወኑ ተግባሮች

ቀደም ሲል እንደተጠቀሰው፣ የግብርና ምርምር ዋና ግብ፣ በግብርናው ዘርፍ ምርታማነትን ለማሻሻል አዳዲስ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን፣ ዘዴዎችንና ሥልቶችን መፍጠርና ማስተዋወቅ ነው። እነዚህ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች፣ ዘዴዎችና ሥልቶች፣ በተገቢው የጊዜ ገደብ ውስጥና በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ ከዋሉ፣ የግብርናውን ዘርፍ ምርት በማሳደግ ለሀገራቱ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ዕድገት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ አስተዋጽኦ እንዲያበረክት ማድረግ ይቻላል። የሀገራቱ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ደረጃ ተሻሽሎ ማለት ደግሞ፣ የበለጠ የሥራ ዕድል በመክፈትና ለሠራተኛውም የተሻለ የደሞዝና የተሻለ የጤና ደረጃ በማረጋገጥ፣ ሌሎችንም ማኅበራዊ ጉዳዮች በማሟላት ድህነትን ቀንሶ የምግብ ዋስትናንም እውን ማድረግ ተቻለ ማለት ነው።

ለጊዜው ግን፣ የግብርናው ዘርፍ ለሀገራቱ ብሔራዊ ኢኮኖሚ ከሚያደርገው አስተዋጽኦ ጋር የተያያዙትን ጉዳዮች ተወት አድርገን፣ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት ያህል ሲከሄድ የቆየው የግብርና ምርምር ያስገኛቸው ውጤቶችና ያከናወናቸው ተግባሮች ላይ እናተኩር። ሁኔታውን በጽሞና ስንመለከተው፣ የግብርና ምርምሩን ዘርፍ በሚመለከት የሚስበሰቡ መረጃዎች በየጊዜው የሚለዋወጡ ናቸው። ይህን ችግር ደግሞ የሚያባብሰው፣ በኢትዮጵያ ብሔራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓት ውስጥ የተካተቱት የተለያዩ የምርምር ተቋማት ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎች የሌሏቸው መሆኑ ነው። በዚህም የተነሣ፣ በእጄ የገቡትን መረጃዎች መነሻ በማድረግ የተገኙትን ውጤቶችና የተከናወኑትን ተግባሮች ጠቅለል አድርጌ ለማቅረብ እሞክራለሁ። እዚህም ላይ መሠረት የማደርገው ከኢግምድ የተገኙ የቅርብ ጊዜ የመረጃ ሰነዶችን ነው። ይህን ማድረጉ፣ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ተገቢነት አለው። ምክንያቱም፣ አብዛኛው የምርምር ክንውን፣ በተለይ እ.አ.አ. ከ1997 ዓ.ም. ጀምሮ ሲኪያሄድ የቆየው በኢግምድ የበላይ ተቆጣጣሪነት በመሆኑ ነው። ከተጠቀሰው ዓመት ጀምሮ፣ ድርጅቱ ላደረገው ጥረት ምሥጋና ይሁንና፣ ቀደም ሲል በዓለማያ ዩኒቨርሲቲ እና በግብርናና ገጠር ልማት ሚኒስቴር ሥር ይንቀሳቀሱ የነበሩት የምርምር ማዕከሎች/ቤተ ሙከራዎች በኢግምድ ሥር እንዲተዳደሩ መደረጋቸው ዋናው ምክንያት ነው። ስለሆነም፣ ድርጅቱ በቅርቡ ያወጣው ያልታተመ የመረጃ ሰነድ እንደሚያመለክተው፣ የሀገራቱ ብሔራዊ የምርምር ሥርዓት ያስገኛቸው የምርምር ውጤች የሚከተሉት ናቸው፤

- በእህል ሰብል ምርምር ረገድ፣ በ29 የተለያዩ የእህል ዝርያዎች ላይ 400 ያህል አዳዲስና የተሻሻሉ ዘሮች ወጥተው በተለያዩ የሀገራቱ ክፍሎች ላለ በግብርና የሚተዳደሩ ማኅበረሰቦች ታድለዋል። የታደሉት የተሻሻሉ ዘሮች እንደስንዴ፣ በቆሎ እና ጤፍ ያሉትን ጥራጥሬዎች፤ እንደድንች ያለ የሥራሥር ምግቦችና የዘይት እህሎችን፣ እንዲሁም የሀገራቱ ዋነኛ የውጭ ምንዛሪ ገቢ ምንጭ የሆነውን ቡናን ያካትታሉ።
- በተለይ ደረቅ ዐፈር ለሚበዛባቸው ቆላማ ሥፍራዎች ይጠቅማሉ ተብለው የታለመባቸው 17 ዓይነት የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ተለይተው በመታወቃቸው ለተባሉት አካባቢዎች በሥራ ላይ እንዲውሉ ሐሳብ ቀርቧል።
- የዐፈርንና የውኃን አያያዝ በሚመለከት 18 የሚሆኑ የቴክኖሎጂ ቅንብሮች (ፓኬጅ) ተቀርጸው ተሰራጭተዋል።

ለከብት እርባታ ይጠቅማሉ ተብሎ የታመነባቸው 86 ያህል የቴክኖሎጂ ቅንብሮች በሥራ ላይ እንዲውሉ ሐሳብ ቀርቦባቸዋል። ከነዚህም ውስጥ፣ ለወተትና ለሥጋ የሚሆኑ የተሻሻሉ የከብት ዘሮች፣ ለዕንቁላልና ለሥጋ የሚሆኑ የተሻሻሉ የዶሮ ዘሮች፣ የከብት መኖዎች እና የአቀላለብ ሥልቶች ይገኙባቸዋል።

በደን ልማትና አግሮ-ፎርስትሪ ረገድ የተለያዩ የዕፀዋት ዝርያዎች ከነአያያዝና አጠባበቅ ሥልቶቻቸው ጋር ተጠንተው መጠቀሚያ እንዲሆኑ ሐሳብ ቀርቦባቸዋል።

የእርሻ መሣሪያዎችን በሚመለከት፣ የምርምሩ ዋና ዓላማ፣ የተሻሻሉ ማረሻዎችንና ሌሎች መሣሪያዎችን በመከራ አይቶ በአነስተኛ ደረጃ ለሚያመርቱ ገበሬዎች እንዲስማሙ አድርጎ መሥራት ነበር። በዚህም መሠረት፣ በእንስሳት ጫንቃ የሚሳቡ ማረሻዎች፣ ዘርን በረድፍ የሚዘሩ መሣሪያዎች፣ ማረሚያዎች፣ በቆሎ መፈልፈያዎች ተፈትነው በሥራ ላይ እንዲውሉ ሐሳብ ቀርቦባቸዋል።

በማሳ አያያዝና አጠባበቅ፣ በምርት ኢኮኖሚክስ፣ የቴክኖሎጂ ቅንብሮችን በመፈተን፣ በእርሻ ሥርዓቶች ምርምር፣ በግብርና አካባቢ ባሕርይ ጥናት፣ በእርሻ ማሳ ላይ መሣሪያዎችን፣ ዘሮችን፣ ሥልቶችን በመፈተሽና የግብርና ሙያ ቅኝቶችን በማድረግ፣ ቴክኖሎጂዎችን በመፍጠር፣ አስማምቶ በመቀበል፣ በሚያስከትሉት ውጤት፣ እና በግብርና ውጤቶች ገበያ ረገድ አያሌ ግኝቶችና የዕውቀት ዓይነቶች ተመዝግበዋል።

እዚህ ላይ በቁም ነገር መጤን ያለበት አንድ ጉዳይ አለ። ይኸውም፣ እነዚህ ተሻሽለዋል የተባሉት የቴክኖሎጂ ውጤቶችና የሥራ አያያዝ ሥልቶች ነባር ከሆኑት ከባህላዊዎቹ መሣሪያዎችና ሥልቶች የተሻለ ውጤት የሚያስገኙ ሆነው ተገኝተዋል ወይ? የሚለው ነው። መልሱ እንደየአካባቢው ሁኔታ የሚለያይ መሆኑ ግልጽ ነው። ለምሳሌ፣ ከእህል ማምረት ጋር የተያያዙ ቴክኖሎጂዎች ለተጠቃሚዎች ሲሰራጩ ለሥራው የሚመቹ ሁኔታዎችን ከቁም ነገር በማስገባት ነው፤ ሁኔታዎቹም፣ የዝናምን መጠንና የሚዘንብባቸውን ወቅቶችና ፍጥነት፣ እህሉ ደርሶ ለምርት የሚበቃበትን የጊዜ መጠን፣ የዐፈሩንና የመሬቱን ጠባይ፤-ለም ነው ወይስ አይደለም የሚለውን--እነዚህንና የመሳሰሉትን ያካትታሉ። በእንስሳት እርባታም ሙሉ እንደዚሁ የተለዩ ሁኔታዎች ይኖራሉ፤ ለምሳሌ፣ የከብት በሽታና ልዩ ልዩ ተህዋስያን መስፋፋት ወይም ማነስ፣ የመኖ መኖር አለመኖር፣ ካለም የመኖው ጥራት፣ የከብትና የጣአቶች አያያዝና እንክብካቤ፣ ወዘተ. ከቁጥር ይገባሉ። ስለዚህ፣ እንደአንድ ዋና ጉዳይ መታየት ያለበት፣ ልዩ በሆኑ ጥቂት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር የሚፈጠሩት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች እጥቅም ላይ መዋል ያለባቸው ይበጃሉ ለተባሉበት ደረጃና ይበጃሉ ለተባሉበት አካባቢ ብቻ መሆኑ ነው። ክፋቱ ግን በሀገራችን ውስጥ በተባለው መንገድና ሁኔታ መጠቀሙ አልፎ አልፎ የሚታይ ብቻ ነው፤ ስለሆነም ስለቴክኖሎጂዎቹ ዓቅም ወይም ብቃት ደካማነት ሆታና አቤቱታ ተደጋግሞ ይሰማል።

የቴክኖሎጂ ልማት መሐራዎች የሚኪያሄዱት በደንብ በተቀናበሩ የመከራ ጣቢያዎችና ሙያውም ከፍተኛ ሥልጠና ባላቸው ሰዎች ነው። ይሁን እንጂ እነዚህ ቴክኖሎጂዎች ወይ ሁለመለት እውነተኛ ሥፍራና ሁኔታ ወይም ደግሞ እሱን በሚመስል፣ ሥራዬ ብሎ ከቀናበረ ሁኔታ ሳይፈተኑና አስተማማኝነታቸው ሳይረጋገጥ፣ የባለሙያዎቹንም ይሁንታ ሳያገኙ ለተጠቃሚዎች መሰራጨት የለባቸውም። ይህን ማድረጉ ደግሞ የሰውና የቆሳቁስ፣ ምንዘብም ኃይል፣ እንዲሁም ጊዜ ይጠይቃል። በምርምር ተግባር የተሰማሩ ባለሙያዎችም፣ ብዙ ችግርና ልምድ፣ እነዚህን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ከሚሞከሩባቸው የመከራ ጣቢያዎች ጭ ወስዶ ከገበሬዎችና ከከብት አርቢዎች ጋር በቀጥታ ተራክቦ በማድረግ ውጤቶቹን

ለመፈተሽና አስተማማኝነታቸውን ለማረጋገጥ ተጨማሪ ጥረት ማስፈለጉን ተምረዋል። ይህ የመፈተሽና አስተማማኝነትን የማረጋገጡ ሥራ በግብርና መስክ የሚደረግ ሙከራ ይባላል።

ብዙዎቻችሁ ሕገ-ብን ያሳተፈ ትዕይንተ ሙከራ የኤክስቴንሽንና የሥልጠና ዘዴ (Participatory Demonstration Extension and Training System (PADETS)) ስለሚባለውና ከ1990 አጋማሽ ጀምሮ በክልል መስተዳድሮች ደረጃ ሲዘረጋ ስለነበረው ፕሮግራም ሳትሰሙ የቀራችሁ አይመስለኝም። ይህ ፕሮግራም ሳስካዋ ግሎባል 2000 (Saskawa Global 2000) በሚባለው ፕሮግራም ግንባር ቀደምነት የሚመራ፣ ጋናንና ታንዛኒያን ጨምሮ በአያሌ የአፍሪካ ሀገሮች ጠቃሚ ሆኖ የተገኘ ነው። እነዚህ በሳስካዋ ግሎባል 2000 የተጀመሩና በሙከራ ደረጃ ሲሞከሩ የቆዩት ክንውኖች በመንግሥት ደረጃ ተይዘው፣ እ.አ.አ. በ2005 ዓ.ም. ከ4 ሚሊዮን በላይ ለሆኑ ገበሬዎች ተዳርሰዋል። እነዚህ ትዕይንተ መከራዎች ገበሬዎቹ በሚኖሩባቸው አካባቢዎች በተሞከሩበት ጊዜ የተገኘው ውጤት እንደሚያመለክተው፣ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በተገቢው ሁኔታ በተግባር ላይ ማዋሉ፣ የተመረጠ የእህል ዘሮች ቀደም ሲል ገበሬዎቹ ይጠቀሙባቸው ከነበሩት የምርት መሠረታዎች ይልቅ የሚገኘውን ምርት መጠን እስከሦስት እጥፍ ድረስ ከፍ እንዳደረገው ታውቋል (ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ)። ለምሳሌ፣ እ.አ.አ. ከ1996 እስከ 2001 ዓ.ም. በነበረው የስድስት ዓመታት ጊዜ ውስጥ፣ የተሻሻሉ የበቆሎና የስንዴ ዘሮች በአንድ ሄክታር፣ እንደቅደም ተከተላቸው 47 እና 28 ኩንታል ምርት ሲሰጡ፣ በልማዳዊው የአስተራረስ ዘዴ ግን እነዚሁ የእህል ዓይነቶች የሰጡት ምርት፣ እንደቅደም ተከተላቸው በአንድ ሄክታር 16 እና 11 ኩንታል ብቻ ነበር።

የተሻሻሉ የእርሻ ቴክኖሎጂዎች ከነባሩ የገበሬ ዘዴ ጋር ሲነጻጸሩ የሰጡት ምርት

(ምርት በኩንታል/በሄክታር)

ዓመተ ምሕረት	በቆሎ		ስንዴ	
	የተሻሻለው	የገበሬው	የተሻሻለው	የገበሬው
1995/96	36.8	11.8	29.0	9.3
1996/97	51.7	17.6	25.9	10.6
1997/98	42.0	16.5	35.0	10.4
1998/99	51.8	15.5	24.6	10.8
1999/00	57.6	17.6	29.9	12.2
2001/02	40.5	16.5	25.5	12.0
አማካይ	46.7	15.9	28.3	10.9

ምንጭ፤ SG2000

በእንስሳት እርባታም ረገድ እንደእህሉ ሁሉ በጣም የማያረካ ውጤት ተገኝቷል። ለምሳሌ፣ ከደብረ ዘይት የግብርና ምርምር ማዕከል የተገኙ ዘገባዎች እንደሚያመለክቱት፣ የተሻሻሉ የከብት ዘሮች ባጋቡበት የ300 ቀናት ጊዜ ውስጥ ከ2000 ሊትር በላይ ወተት ሊታለቡ ችለዋል። በአንጻሩ የአገር ዝርያ የሆኑት፣ የማታለቡበት (የማያግቡበት) ጊዜም አጭር ሆኖ ለታለቡ የቻሉት ወተት መጠን ከ200 እስከ 300 ሊትሮ ብቻ ሆኖ ተገኝቷል። ይኼው የደብረ ዘይቱ የምርምር ማዕከል፣ ከፍተኛ የዕንቁላልም ሆነ የሥጋ ምርት ሊሰጡ የሚችሉ የዶሮ ዘሮች ያዳቀለ ሲሆን፣ በነባሩ ሥልት ከተራቡት ዶሮዎች የተሻለ ውጤት አስገኝቷል።

የተሻሻለ ቴክኖሎጂ አጠቃቀም እና ለዕድገት ያበረከቱት አስተዋጽኦ አጠቃላይ አስተያየት

ሉ

ምም እንኳን ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ውጤቶች የሚያመረቁ ናቸው ሊባሉ የሚችሉ ሀገራዊ ለምርምሩ ተግባር ከተደረገው ወጪ አንጻር ሲታዩ የሚያዋጡ ሆነው ተገኝተዋል ሚል ጥያቄ መነሣቱ አይቀርም። በዚህ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለና አጠቃላይ ጥናት ተ በተለይ አሁን ባለንበት ደረጃ እንዲህ ያለው አጆንታዊ መደምደሚያ ላይ መድረስ አይደለም። ለግብርና ምርምር የሚወጣ ማንኛውንም ወጪ በንግድ መንፈስ ግብርናን ለማሳደግ እንደዋለ የመዋዕለ ንዋይ አድርጌ እቆጥረዋለሁ። እርግጥ፣ ማንኛውም እንዲህ ላለ ተግባር የሚያፈስሰው ገንዘብ ምርታማ (የሚያዋጣ) መሆን አስቀድሞ ማወቅ መፈለጉ የታወቀ ነው። ስለዚህም፣ የሚፈጠሩ ማናቸውም ውጤቶች፣ በተገቢው መንገድ እና በትክክለኛው ወቅት እጥቅም ላይ ውለው ፍተኛ ውጤት የሚያስገኙ መሆን አለመሆናቸውን ለማየት እንዲቻል የትርፍና ሁኔታ በቅርብ የመከታተል ነገር ይኖራል ብዬ አስባለሁ። ይሁን እንጂ፣ ትዮጵያ ውስጥ በሚደረገው የምርምር ጥረት ላይ ገንዘባቸውን የሚያፈስሱ የመንግስትና ግሳታዊ ያልሆኑ የምርምር ተቋማት በዚህ ረገድ ያላቸው ሐሳብ የተለየ ነው። ለነእሱ፣ ምርምር ተግባሩ ለሕዝብ አገልግሎት የሚሰጥ እንጂ በቴክኖሎጂ ምርምር ላይ ገንዘብ ኩሰስ ትርፍን ከፍ ለማድረግ ሲባል የሚደረግ ነገር ሆኖ አይታያቸውም።

የውጭ ቴክኖሎጂን ከሀገር በቀል ሁኔታ ጋር ማዋደድ

ሀ

ግብርና ምርምር ተግባር የሚገኙ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ዘለቄታዊ ለውጥ ማምጣት ሚችሉት፣ ቴክኖሎጂዎቹ የታሰቡላቸው ተጠቃሚዎች ላሉበት ሁኔታ እንዲስማሙ ሆነው ተቀረቡና ሥራ ላይ ከዋሉ ነው። ስለዚህም፣ በቴክኖሎጂ ምርምር የተገኙ ውጤቶችን ገራዊ ወይም አካባቢያዊ ከሆኑ ሁኔታዎች ጋር አስተካክሎ ወይም አዋዶ መጠቀሚያ ደረግ ከምርምር ጥረቱ ጠቀሜታ ለማግኘት አንዱና ዋነኛው መንገድ ነው። ነገር ግን፣ ከዚህ የተገኘው የተወሰነ መረጃ እንደሚያመለክተው፣ አብዛኛዎቹ የቴክኖሎጂ ውጤቶች፣ መራት ሥልቶችና የቅኝት ግኝቶች ለሀገርም ሆነ ለአካባቢ ሁኔታ እንዲስማሙ ሆነው ቃቷረቱም ወይም ከሁኔታዎቹ ጋር አልተዋደዱም። ለምሳሌ፣ እስከዛሬ በኢትዮጵያ ከፈራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓት ጥረት ተሻሽለው ለመጠቀሚያ ይሆኑ ዘንድ ይሁንታ ጉት 300 ያህል የእህል ዘሮች ውስጥ በኢትዮጵያ የእርሻ ሰብል ተቋም «የተፈተኑ» የእህል ሮች ተብለው ፈቃድ ማግኘት የቻሉት 56ቱ ብቻ ናቸው። ማዕከላዊ የስታቲስቲክስ ሥልጣን መሥሪያ ቤት እ.አ.አ. በ2000/01 የሰብል ዓመት ለናሙና ያህል ባደረገው የእርሻ ራ ቅኝት መሠረት፣ የተሻሻሉ ዘሮች፣ ኬሚካል ማዳበሪያዎች እና ጸረ ተባዮች አጠቃቀም፣ ከዘራው ጠቅላላ መሬት ውስጥ እንደቅደምተከተላቸው 3 በመቶ፣ 39 በመቶ እና 8 በመቶ ርሻ ያዘዋል። ይኼው የመረጃ ምንጭ እንደሚያመለክተው፣ ሀገሪቱ ካላት ጠቅላላ የከብት ሮት የተሻሻሉት የወተት ከብቶችና በጎች የያዙት ድርሻ 1 በመቶ ብቻ ነው።

ኢትዮጵያን ጨምሮ በብዙ የአፍሪካ ክፍሎች የእህል ዘሮችን በማዳቀል/በማዋደድና በሥራ ላይ በማዋል ረገድ የተደረጉ ጥናቶች አሉ። በኢትዮጵያ የተደረጉት ጥናቶች ውጤት ተጠቃለለ ሲሆን፣ አዲስ ቴክኖሎጂዎችን ከሀገር ሁኔታዎች ጋር እያዋደዱ የመጠቀሙ

መጠን እንደየሁኔታው፣ አንዱ ጋ በጣም ዝቅ፣ ሌላው ጋ ደግሞ በጣም ከፍ የሚልበት አጋጣሚ እንዳለ ታውቋል፤ የዝቅታው እና የከፍታው ሁኔታ የሚወሰነው ደግሞ ለተጠቃሚዎቹ በሚቀርብላቸው የቴክኖሎጂ ውጤት ባሕርይ፣ ተጠቃሚዎቹ ራሳቸው ባሉበትና በሚኖሩበት ሁኔታና ደረጃ እና ለየማኅበረሰቡ በሚቀርብለት ማበረታቻና በቅርቡ ባለው የመሠረተ ልማት መዋቅር ሁኔታ ሆኖ ተገኝቷል። ለምሳሌ፣ በዚህ ረገድ፣ እ.አ.አ. በ1989 ዓ.ም. በባኮ አካባቢ የተካሄደ፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂን ተቀብሎ ሥራ ላይ ስለማዋል የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው፣ ለቅኝቱ ከተመረጡት ገበሬዎች ውስጥ፣ 67 በመቶ ያህል የሚሆኑት የተሻሻለ የበቆሎ ዘር፣ 64 በመቶ የሚሆኑት ደግሞ ዘሩን በረድፍ መዝራታቸው፤ 60 በመቶ የሚሆኑ ደግሞ በኬሚካል ማዳበሪያ መጠቀማቸው ታውቋል። በተመሳሳይ በሲዳማ አካባቢዎች እነዚሁኑ የበቆሎ ዘሮች አጠቃቀምን በሚመለከት በ1991 ዓ.ም. የተደረገ ጥናት እንደሚያመለክተው፣ በተሻሻሉት ዘሮች የተጠቀሙት ገበሬዎች ቁጥር ዝቅተኛ ሲሆን፣ አስተማማኝ ዝናም በሌላቸው ቆላማ አካባቢዎች አጠቃቀሙ እጅግ ዝቅ ብሎ ተገኝቷል። በእህል ዝርያዎችና እንደዘርና እንደማዳበሪያ ባሉ ሌሎች ግብኣቶች አጠቃቀምም ላይ የተካሄዱ ሌሎች ጥናቶችም አሉ። የዚህ ሁሉ ቁም ነገር ያለው፣ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ካሉበት ሁኔታ ጋር አዋዶና አቀናጅቶ መጠቀሚያ የማድረጉ ልማድ ወይም ባህል አነስተኛ የእርሻ ይዞታ ባላቸው የኢትዮጵያ ገበሬዎች ዘንድ በጣም ዝቅተኛ መሆኑ ሲሆን፣ ይህም ደግሞ ከቦታ ቦታ እና ከሰብል ዘመን ወደሰብል ዘመን ይለያያል። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን የኢትዮጵያ የእርሻ ሰብል ድርጅት ለሽያጭ የሚያቀርባቸው የተሻሻሉ የእህል ዘሮች ጉዳይ ነው። አንዳንድ ዓመት የተሻሻሉ የእህል ዘሮች ሽያጭ፣ ድርጅቱ በዓመት ከሚያዘጋጀው ጠቅላላ የዘር መጠን 90 በመቶ ሲደርስ፣ አንዳንድ ዓመት ደግሞ ከ30 በመቶ በታች የሚሆንበት ጊዜ አለ።

በዝቅተኛ የልማት ደረጃ ላይ እንዳሉት እንደሌሎቹ ሀገሮች ሁሉ፣ የሀገራችንም ተመክሮ በግልጽ የሚያሳየው በተለይ በዝቅተኛ ደረጃ የሚያመርቱ ገበሬዎችም ሆኑ ከብት አርቢዎች፣ የተለየ ማበረታቻ ወይም መቀስቀሻ ካልተሰጣቸው በስተቀር፣ አዲስ በሚፈጠሩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች ለመጠቀም በጣም የሚያመነቱ ወይም የሚያቅማሙ መሆናቸውን ነው። በዚህ ረገድ፣ አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን በሥራ ላይ ለማዋል ጉጉቱ ያላቸው ሆነው የተገኙት፣ ከሚወጡት የቴክኖሎጂ ውጤቶችና ከአጠቃቀማቸው ጋር የተያያዘ እውነተኛም ይሁን ወይም የግምት ኪሣራ ሊኖር እንደሚችል ለመገመት የሚያስችል ዕውቀትም፣ ካፒታልም ያላቸው በንግድ-ግብርና የተሰማሩት ገበሬዎች ናቸው። ለዚህም ድጋፍ ይሆን ዘንድ፣ ዛሬ በዚህ አዳራሽ ካላችሁት ብዙዎቻችሁ ልታስታውሱ እንደምትችሉት፣ እንደቅደም ተከተላቸው፣ በአርሲ፣ በወላይታ እና በሲዳማ ተቋቁመው የነበሩት፣ እንደጭላሎ የግብርና ልማት ድርጅት (CADU)፣ እንደወላይታ የግብርና ልማት ድርጅት (WADU)፣ የሲዳማ የግብርና ልማት ድርጅት (SORADEP) ያሉትን «የተቀናጀ»ን የገጠር ልማት ፕሮጀክቶች መጥቀስ ይቻላል። እንዲሁም፣ በኋላ መንግሥት የወረሳቸው ትልልቅ የንግድ እርሻ ባለቤቶች አዳዲስ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተቀብሎ መጠቀሚያ በማድረግ ረገድ ትልቅ ጉጉት የነበራቸው ናቸው።

በቅርቡ የዓለማያ ዩኒቨርሲቲ የተቋቋመበት 50ኛ ዓመት ሲከበር በዓሉን ምክንያት በማድረግ የቀረበ ዘገባ፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በሚካሄደው የግብርና ምርምር ረገድ ስለተሳካላቸው አንዳንድ ጥረቶች ያነሣው ጉዳይ ነበር። ዘገባው፣ ለጥረቶቹ መሳካት በምሳሌነት የጠቀሰው የተሻሻሉ የእህልና የእንስሳት ዘሮች ዓይነቶችን ነው። በዘገባው መሠረት፣ የጭላሎው!

የመሳሰሉ እና የሲዳማው የእርሻ ልማት ፕሮጀክቶች፣ በአነስተኛ የእርሻ ይዞታ ደረጃ የግብርና ምርትንና ምርታማነትን ከፍ ለማድረግ በምርምሩ ጥረት በተገኙ ቴክኖሎጂዎች ተሸምለው የተሳካ ውጤት አምጥተዋል። ቁጥራቸው በጣም በተወሰነ የገጠር አካባቢዎች መሥራታቸው በሚኖራቸው አዲስ የተፈጠሩትን የግብርና ቴክኖሎጂዎች መጠቀምን የሚያበረታታ ሥልት (ስትራቴጂ) በሥራ ላይ ማዋላቸው ነው ሊባል ይችላል። የፕሮጀክቶቹ ስያሜ እንደሚያመለክተውም፣ የተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶችን (ግብኣቶችን) በማቀናጀት በተግባር ላይ አውለዋል፤ ለምሳሌም፣ የእህል ዘሮችና ኬሚካል ማዳበሪያዎችን ማፍለቅን፣ ሥልጠናን ጨምሮ ውጤት-ወለድ የሆኑ የቴክኖሎጂ ሥርዓቶችን ማዛመት፣ እንደ መንገድ እና እንደምርት ማዘመኛ (ትራክተር ወዘተ.) ያሉ የመሠረተ ልማት መዋቅሮችን መዘርጋትንና መሥራትን፣ ዋስትና ያላቸውን የገበያ ማዕከሎች መክፈትንና ማካሻ የሚሆኑ የሸቀጥ ዋጋዎችን ማስተዋወቅን በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ነገር ግን፣ የፕሮጀክቶቹ ውጤት የተሳካ ሆኖ ሊዘልቅ የቻለው ፕሮጀክቶቹ በሕይወት እስከቆዩበት ጊዜ ድረስ ብቻ ነው። ፕሮጀክቶቹ በነበሩባቸው አካባቢዎች የፕሮጀክቶቹ ጥረት ቅሪቶች አሁንም ድረስ ያሻራ ያህል የሚታዩ ቢሆንም፣ ጥረቱ የዘመንን ወደፊት መሄድ እየተከተለ አብሮ የሚዘልቅ አልሆነም።

በግል ይዞታ ሥር የነበሩ በርከት ያሉ የንግድ እርሻዎች የግብርና ሥልቶቻቸውን ለማሻሻል፣ ዘመናዊ የእርሻ መኪናዎችንና መሣሪያዎችን፣ እንዲሁም የተሻሻሉ ግብኣቶችን ለመግዛት ገንዘባቸውን አውጥተዋል። በዚያም ልክ በገልህ የሚታይ የተሳካ ውጤት አምጥተዋል። ነገር ግን፣ የደርግ መንግሥት ውጥናቸውን በእንጭጩ አስቀርቶታል። ምንም እንኳን እነዚያ በለእርሻዎች ይጠቀመባቸው የነበሩትን የግብርና ሥልቶች በደርግ ሥር የተቋቋሙት የመንግሥት ተቋማት በጥቅም ላይ ማዋላቸውን የቀጠሉበት ቢሆንም፣ ውጤታቸው የግል በለይዞታዎች ያመጠትን ያህል የተሳካ አልነበረም። የመንግሥት እርሻዎችን ሲያንቀሳቅስ ከነበረው የሰው ኃይል ውስጥ ለአያሌ ዓመታት አንዱ ሆኜ የሠራሁ በመሆኔ፣ የእርሻዎቹ ጥረት ላለመሳካቱ አስተዋጽኦ ያደረጉ ምክንያቶችን መጥቀስ እችላለሁ። ምክንያቶቹን በጥቅሉ ስናያቸው፣ የትግር ምንጭ በጊዜው የነበረው መንግሥት ይከተለው የነበረው የፖለቲካ ፅላማና የሥራ አመራር ሥልት ጥምር ውጤት ነው። አሁን፣ ዛሬ ላይ ሆኜ፣ ነገሩን ወደኋላ መለስ ብዬ ስቃኘው፣ እነዚያን የመንግሥት እርሻዎች መንግሥት ይመለከታቸው የነበረው እንደንግድ ሥራ ማኪያሄጃ (እንደገንዘብ ማፍሪያ) ተቋማት ሳይሆን ለሕዝብ ማኅበራዊ አገልግሎት እንደሚያቀርቡ (የመንግሥት) አካላት ነበር ብዬ መደምደም እችላለሁ።

6.3 የግብርና ምርምር በልማት ረገድ ያመጣቸው ውጤቶች

አሁን ባለንበት ዘመን የተሻሻሉ የቴክኖሎጂ ዓይነቶችና ውጤቶች እያሉለትም እንኳን፣ የኢትዮጵያ የግብርና ዘርፍ ልማት አሁንም ወደኋላ የቀረና ምርታማዊነቱም በጣም የኮሰመነ ነው። የዘርፉን የልማት ደረጃ ዝቅተኛነት በቅጡ መረዳት የሚቻለውም፣ ሀገሪቱ ብዛት ላለው ሕዝቧ ምግብ፣ መጠኑ ከሕዝቧ ቁጥር ለማይተናነሰው የእንስሳት ንብረትም መኖ በበቂ ሁኔታ ማምረት አለመቻሏን ስንመለከት ነው። ከዚህ መሠረታዊ ችግር ሌላ፣ በሀገሪቱ የግብርና-ኢንዱስትሪ ዘርፍ ላሉ ተቋማት የሚያስፈልገውን ጥሬ ዕቃ በማቅረብ፣ ለውጭ ንግድ የሚያስፈልጉ ምርትና ሸቀጦችን መጠንም ሆነ ጥራት ከፍ በማድረግ ረገድ ተጨማሪ ችግር አለባት። ይህን ሁኔታ ይዘን ልናነሣው የሚገባን፣ መነሣትም ያለበት ጥያቄ፣ የሀገሪቱ የግብርና ምርምር ዘርፉ ምርትንና ምርታማነትን በብሔራዊ ደረጃ ከፍ በማድረግ ረገድ ውጤት

አስገኝቷል ወይ? የሚለው ነው። ክፍ ሲል እንደተጠቆመው፣ በተወሰኑ አካባቢዎችና ተለይተው በተመረጡ የልማት ዘርፎች ምርምሩ ምርትንና ምርታማነትን ለማሻሻል የቻለባቸው ውጤቶች ተመዝግበዋል፤ ነገር ግን፣ የተመዘገበው ውጤት ምርትንና ምርታማነትን በብሔራዊ ደረጃ ከፍ በማድረግና በማሻሻል ረገድ ያደረገው አስተዋጽኦ በጣም አነስተኛ ነው።

የኢትዮጵያ ማዕከላዊ የስታቲስቲክስ ባለሥልጣን በ14 ዓመት ክልል ውስጥ (እ.አ.አ. ከ1990/91 እስከ 2003/04 ዓ.ም. ላለው ጊዜ) ያካሄደው ናሙናዊ ጥናት እንደሚያመለክተው፣ አህል የተመረተበት ጠቅላላ የመሬት ስፋት፣ በ1990/91 ዓ.ም. 5.3 ሚሊዮን ሄክታር ከነበረበት በ2000/01 ወደ 9.4 ሚሊዮን ሄክታር ከፍ ብሏል። (ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ።) በዚህ የቦታ መጠን አንጻር የተመረተውን አህል መጠን ስናሰላ ደግሞ፣ በ1990/91 ዓ.ም. የተገኘው የአህል ምርት 73 ሚሊዮን ኩንታል የነበረ ሲሆን፣ በ2003/04 ደግሞ የምርቱ መጠን 117 ሚሊዮን ኩንታል ነበር። በተዘራው መሬት መጠን አኳያ ሆነን የአህል ምርቱን ምጣኔ ስናሰላ ግን፣ ከአንድ ሄክታር መሬት የተገኘው ምርት መጠን፣ ዝቅተኛው 9 ኩንታል፣ ከፍተኛው ደግሞ 14 ኩንታል መሆኑን እናያለን። ከዚህ ሁኔታ በግልጽ የምንረዳው ነገር፣ በአህል ሰብል ረገድ (እንደጥራጥሬ፣ እንደ ሥራ-ሥር ምግቦች፣ እንደዘይት አህሎች ያሉትን የምግብ ሰብሎች ጠቅልለን) ስንመለከተው፣ በብሔራዊ ደረጃ የታየው እድገት መጠን ምክንያት፣ እድገቱም ጎልቶ የሚታይበት፣ የታረሰና የተዘራው መሬት መጠን ከፍ ማለቱ መሆኑን ነው። /በሌላ አነጋገር፣ የምርቱ አጠቃላይ ዕድገት ከፍታ የሚመነጨው ከተዘራው መሬት ብዛት እንጂ በየሄክታሩ ከሚመረተው አህል ብዛት ከፍ ማለት አይደለም። ይህን ይዘን ስንነሣ የምንደርስበትና የማናመልጠውም ድምዳሜ ግልጽ ነው፤ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን ለማፍራት ብዙ ገንዘብ ወጥቶበት የተኪያሄደው የግብርና ምርምር ተግባር በብሔራዊ ደረጃ የሚጠበቀውን ምርታማነት ይህ ነው በሚባል አመርቂ ሁኔታ አላሻሻለውም የሚል ነው። እንዲህ ዓይነቱ መደምደሚያ ሊጎረብጠን የሚችል መሆኑን እረዳለሁ፤ እውነታው ወይም ሀቁ ግን ይኼው ነው። እንዲያውም፣ ከዚህም በባሰ ሁኔታ፣ የተመረተውን የምግብ ሰብል ስናየው፣ ምንም እንኳን መጠነኛ መሻሻልን ያሳየ ቢሆንም፣ ሀገሪቱ ያላት ሕዝብ በአማካይ ደረጃ ከሚያስፈልገው የነፍስ ወከፍ መጠን በእጅጉ ያነሰ መሆኑን እንረዳለን።

የተዘራ መሬት ስፋት፣ የጠቅላላ ምርት እና የምርታማነት መጠን፤ የአሥር ዓመት ክልል

ዓመት	የመሬት ስፋት (በሚሊዮን ሄክታር)	የጠቅላላ ምርት መጠን (በሚሊዮን ኩንታል)	የምርታማነት መጠን (በሄ/ኩንታል)
1990/91	5.3	7.3	14.0
1995/96	7.7	10.2	13.0
1996/97	8.9	10.6	12.0
1997/98	7.5	9.8	13.0
1998/99	8.0	8.6	11.0
1999/00	8.2	9.3	11.0
2000/01	9.4	10.6	11.0
2001/02	7.8	9.9	13.0
2002/03	7.9	7.3	9.0
2003/04	8.5	11.7	14.0

ምንጭ፤ CSA (ለተጠቀሱት ዓመታት ብቻ)

የመደፊት ርእይ

1.

የኢትዮጵያ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ልማት ከግብርናው ዘርፍ ልማት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ መሆኑን መንግሥት አምኖ ተቀብሏል። ይህ አስተያየት፣ በሀገርም ሆነ በዓለምአቀፍ ደረጃ ስለልማት የሚያጠኑ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎችም አስተያየት ሳይሆን አይቀርም። ከኢትዮጵያ ማዕከላዊ የስታቲስቲክስ ባለሥልጣን እና ከሌሎች ምንጮችም (ከተመድ የምግብና የግብርና ድርጅት፣ ከዓለም የምግብ ፕሮግራም እና ከዓለም ባንክም) የተገኙ የብዙ ዓመታት የመረጃ ሰነዶች እንደሚያመለክቱት፣ የሀገሪቱ የግብርና ምርት እና የዘርፉ ምርታማነት ገቢ ያለ ብቻ ሳይሆን የሚዋዥቅም/የማያስተማምንም ጭምር ነው። የመዋዠቁና አስተማማኝ ያለመሆኑ ምክንያት ተፈጥሮም ሰውም በጥምረት ሆነው ከመጠዋቸው ችግሮች ጋር የተያያዘ ነው፤ ባንድ በኩል፣ የአየር ጠባይ ወይም ባሕርይ ተለዋዋጭ መሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ ሰው-በቀል የሆነ ማኅበራዊ ነውጥ። ከቅርብ ዓመታት ወዲህ፣ በግብርናው ዘርፍ ምርታማነት ሳይሆን፣ በግብርና ምርት መጠን ረገድ ጠቀም ያለ መሻሻል የታየ መሆኑ ባይካድም፣ ይህን በግብርና ምርት ረገድ የተገኘውን ውጤት ግን በፍጥነት እያደገ የሚሄደው የሀገሪቱ ሕዝብ ቁጥር መብዛት ጨርሶ ያጣፋዋል/ዋጋ ያሳጣዋል። በዚህም የተነሣ፣ ዛሬ ያለው የነፍስ ወከፍ ምርት መጠን የዛሬ ሃያ ዓመት ከነበረው መጠን በታች መሆኑ ፈጠ ይታያል። ይህንን ሁኔታ በጽሞና ስንመለከተው፣ ከዚያነው ትግል ውስጥ ባለድል ሆነን የምንወጣ አይመስልም። እውነታው ይህ ከሆነ፣ እንግዲያማ፣ የግብርና ምርትንና የዘርፉን ምርታማነት አሁን ካለበት ሁኔታ የተሻለ አድርጎ በማሳደግ ረገድ መጪው ጊዜ ለዚች ሀገርና ለሕዝቧ ምን ይዞለት ይቀርብ ይሆን? ብለን እንጠይቅ።

ምንም እንኳን እስካሁን ባሳለፍነው ጊዜ ሁሉ የነበርንበትን ሁኔታ ስንመለከተው ሰውና አንስሳት ነክአራዊቱ አብረው የሚቦርቁበትን የገነትን ምስል የሚያሳየን ባይሆንም፣ ይህ ሁኔታ ግን ከእግዜር የተላከ ወይም የታዘዘ መርገም ሳይሆን ሰው-ሠራሽ መሆኑን አምናለሁ። እስከሁን ስንሠራው ከቆየነው የተሻለ ለማከናወን የሚያስችለን እምቅ ዓቅም ያለን ነን ብዬም አምናለሁ። ነገር ግን፣ ሁኔታዎችን በወል ያገናዘበና በተጨባጭ ግብ ላይ ያነጣጠረ አቅጣጫን ከተየስን ብቻ ነው ይህ የሚታየው። የኢትዮጵያን የግብርና ዘርፍ ይዞታ ለማሻሻልና ለመለወጥ እስካሁን የተከተልነው አቅጣጫና ሥልት የማያዋጣ አኪያሄድ ሆኖ በመገኘቱ፣ እስካሁን ስናደርገው ከቆየነው የተለየ አንድ ነገር ማድረጉ አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ አኳያ፣ አንዳንድ የደቡብ እስያ ሀገሮች የግብርና ዘርፋቸውን ለማሻሻልና ለመለወጥ የተከተሉትን ፈለግ መጥቀስ ትምህርት የምንቀስምበት ይሆናል። እዚህ ካለነው አብዛኞቻችን፣ እነዚህ ሀገሮች ከነበሩበት ተነሥተው ከፍ ያለ የግብርና ምርትና ምርታማነት ደረጃ ለመቀዳጀት ስላስቻላቸው፣ «አረንጓዴው አብዮት» ስለሚባለው ዕቅድ ሰምተናል ብዬ አስባለሁ። «አረንጓዴው አብዮት» እውን ይሆን ዘንድ የረዱ ሦስት መሠረታዊ ነገሮች ያሉ ይመስለኛል፤ እነሱም፣ አንደኛ፣ የተሻሻሉ የእህል ዘሮችና ዘሮቹን በተገቢው መንገድ ዘርቶ ለማምረት የሚያስችሉ የአጠቃቀም/የአያያዝ ሥርዓቶች መኖር፤ ሁለተኛ፣ በዝቅተኛ ወጪ ሊቀናበርና በተግባር ላይ ሊውል የሚችል የመስኖ ዘዴ መኖር፤ ሦስተኛ እና ከሁሉም በላይ ደግሞ፣ መንግሥታቸው የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖለጂዎችን በሥራ ላይ ለማዋል ያላቸው ፍላጎትና ቁርጠኝነት ነፍስ ማለት ናቸው። ለምሳሌ፣ ከዓለምአቀፍ የግብርና ምርምር ማዕከሎች (በአብዛኛው ደግሞ ከCIMMYT) የተገኙት፣ እንደበቆሎና እንደስንዴ እህሎች ያሉት የተሻሻሉ ዘሮች ወደ ኢትዮጵያ የገቡት ወደህንድም በገቡበት አንድ ወቅት ነው። ህንድ ይህንን አኃዛዊ በመጠቀም፣ የምርምሩ ውጤት እንደደረሳት ወዲያው ፈጥና ተነሥታ

ስትገለግስ፣ እኛ ደግሞ በነበርንበት እንደመስክ ውሀ ረግተን ቀረን። አሁን በዚህ አዳራሽ ያላችሁት ሁሉ ይህን ክስተት በጽሞና አወጥታችሁ አውርዳችሁ የየራሳችሁን «ስም እንድታወጡለት»፣ የየራሳችሁን ምክንያት እንድትፈልጉለት እሻለሁ።

በዚህ የመወያያ ሰነድ ውስጥ እስካሁን በተደጋጋሚ አበክረን ለማየት እንደሞከርነው፣ የግብርና ምርምር፣ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ዕድገትና ልማት፣ በተለይ ደግሞ በግብርናው ዘርፍ፡ ዕድገትና ልማት ላይ ላመጣው ዝቅተኛ ውጤት፣ አለያም ደግሞ ውጤት-አልባነት፣ ዋነኛ ናቸው ነሚባሉት ምክንያቶች አንዱ፣ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተቀብሎና ለሁኔታችን እንዲመቹ አድርጎ በማዋደድ በበቂ ሁኔታ አለመጠቀማችን ነው። ይህን ይዘን ሁኔታውን ስናጠነው፣ ምክንያቱ ራሱ ሌላ ጥያቄን ወልዶ፣ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተቀብሎ በሥራ ላይ የማዋሉ ጥረት ለምን ዝቅ አለ፣ ወይም እስከናካቴውም ለምን የለም? ብለን እንድንጠይቅ ያስገድደናል። ለዚህ ያለን መልስ የሚከተለው ነው። የግብርናውን ዘርፍ፡ የቀለጠፈና ውጤታማ የምርት ዘርፍ፡ እንዲሆን አድርገን ለመለወጥ ነፈለግን፣ ቢያንስ ጠቀሜታቸው ተፈትኖ ውጤታማ በሆኑባቸው ዘርፎች፣ የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተቀብሎ ለሁኔታችን እንዲበጁ አድርጎ የመጠቀሙን ልማድና ባህል ማበረታታቱና በሕገበ፡ ዘንድ እንዲሰርጽ ማድረጉ አስፈላጊ ይሆናል። በዚህ የአስተሳሰብ ፈለግ ወይም አመለካከት መሠረት፣ የግብርና ምርምር ለአንድ ሀገር ብሔራዊ የኢኮኖሚ ልማት የሚያደርገው አስተዋጽኦ በተግባሩም ሆነ በዋጋ ረገድ የሚያዋጣ ሊሆን የሚችለው፣ የምርምሩ ውጤቶች የሆኑት የግብርና ቴክኖሎጂዎች በተቻለ መጠን በአፋጣኝና በሰፊው በሥራ ላይ ሲውሉ ብቻ ነው።

የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በሥራ ላይ በማዋል ረገድ የተደረጉት ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው ጥናቶች እንደሚጠቁመት፣ የተሻሻሉ ቴክኖሎጂዎችን በሥራ ላይ በማዋሉ ሂደት የሚገጥሙ አያሌ ችግሮች አሉ። ፈተም፣ አሁንም ድረስ ለብሔራዊ ኢኮኖሚያችን ሰረሰሩ (ወይም የጀርባ አጥንቱ) ሆኖ በቆየው የግብርና ምርታችን ረገድ የወደፊት ኑሮአችን ዋስትና እንዲኖረው ለማድረግ ከፈለግን፣ እነዚህ አሉ የሚባሉት ዕንቅፋቶች መወገድ አለባቸው። ይህን ባልከበት አንደበት ግን፣ ባለፉት አያሌ ዓመታት በዚህ ረገድ ብዙ የተከናወኑ ነገሮች ያሉ መሆናቸውን መናገርም አለብኝ፤ ነገር ግን ደግሞ፣ በተለይ አሁን ያለንበትንና አላላውስ ያለንን ሁኔታ ስንመለከት፣ በተባለው ረገድ አሁንም ገና ብዙ ሥራ የሚጠበቀን መሆኑንም መገንዘብ ያስፈልጋል። የህልውናው ምክንያት የምርምር አገልግሎት መስጠት የሆነው ዓለምአቀፍ የግብርና ምርምር ተቋም ከተቋቋመ 40 ዓመታት እንዳለፉ፣ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ሥርዓታችንን በማደራጀት፣ የሰው ኃይላችንን በማዳበርና በማጎልበት፣ የምርምር ፕሮግራሞቻችንን በአስፈላጊነት ቅደም ተከተላቸው መሠረት በማዋቀር ረገድ፣ አሁን ካለንበት በተሻለ ደረጃ ላይ መገኘት እንደነበረብን መገንዘብ አለብን። ያሉብንን ችግሮች የማስወገዱ ጉዳይ ይህንን ሁኔታ ከመገንዘብ ይጀምራል ማለት ነው።

የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ሥርዓቶች /አቅም/ ይሻሻላሉ

እስካሁን ባቀረብኳቸው የውይይት ሐሳቦች፣ ለተጠቃሚዎች፣ ማለትም፣ ለገበሬዎች፣ ለከብት አርቢዎች፣ ለግብርና-ኢንዱስትሪዎች፣ ለነጋዴዎች (በተለይ ለውጭ ገበያ ለሚያመርቱት) በዘቲ ልናቀርባቸው የምንችል የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ያሉ መስሎ ታይቶ ሊሆን ይችላል። በአድማጮቼ ዘንድ አቀራራቤ እንዲህ ዓይነቱን ስሜት ፈጥሮ ከሆን፣ ይህ ከወዲሁ መስተካከል አለበት። አሁን እዚህ ያለነው በሙሉ፣ ያሉንና ልንጠቀምባቸው የምንችል የቴክኖሎጂ ውጤቶች የተወሰኑ መሆናቸውን እናውቃለን። በሀገራችን ያሉት ብሔራዊ የግብርና ምርምር ሥርዓቶች/ተቋሞች የሚያተኩሩት፣ የተወሰኑ የግብርና ምርት ሥርዓቶችን/ዘርፎችን (የግብርና አካባቢዎችን) ዒላማ ባደረገ የተወሰኑ የሸቀጥ ዓይነቶች ላይ ነው። ስለዚህም፣ የምርምር ሥርዓቶቻችን ሌሎች መስኮችንም እንዲያካትቱ ሆነው መጠናከር አለባቸው። ለያካትቷቸው ከሚገባቸው መስኮች ውስጥ፤ ቅመማቅመምን፣ የስራስር ምግቦችን ጨምሮ፣ የአትክልትና የፍራፍሬ ምርት ማሳደግን፤ የበለጠ ምርታማ የሆኑ የከብት ዘሮችና አያያዝና የእንክብካቤ ዘዴዎቻቸውን ማዳበርን፤ ዘመናዊ የእርሻ መኪናዎችን ማስተዋወቅን፤ የምርት ማከማቻዎችን ጨምሮ የድኅረ-ምርት ሽቀጦችን አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት፤ የምርት ውጤቶችን መቀመምና ማሸግን፤ የመስኖ ውኃ ልማት ማስፋፋትን፤ እና የሥራ አመራርን፣ የገበያ እና የዋጋ ተመን ፖሊሲ መንደፍን መጥቀስ ይቻላል። የምርምር ተግባራችን በወኃ-አጥ/ቆላማ አከባቢዎች ያሉ የምርት ዘርፎች ላይ ከእስካሁኑ በበለጠና በተጠናከረ መንገድ ማተኮር አለበት፤ በተለይም ከብት እርባታና እርሻን ባቆራኙ የምርት ሥርዓቶች ላይ። ይህን ሁሉ አጠቃለን ስናየው ከወስጡ ተጨምቆ የሚወጣው ዋና ሐሳብ፣ የሁሉንም ተጠቃሚዎች ፍላጎት በማሙዋላት አንጻር ሲታይ፣ የተሻሻሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶቻችን አጠቃላይ ንብረት ብቁ ሆኖ እስኪገኝ ድረስ ገና ብዙ ሥራ ይቀረናል የሚል ነው።

በዚህ ረገድ፣ እነዚህ ገና ያልተሟሉና መሟላት ያለባቸው ፍላጎቶች የኢትዮጵያ የግብርና ምርምር ሥርዓቶች/ተቋሞች በሚያከናውኗቸውና ሊያከናውኑ በሚችሏቸው ነገሮች በኩል ያላቸው አንድምታ ምንድን ነው? በተለይ በሚከተሉት መስኮች ወይም ዘርፎች በኩል፣ ገና ብዙ መሠራት ያለባቸው ነገሮች አሉ፤

- አሁን አገልግሎት በመስጠት ላይ ያሉትን የምርምር ተቋሞች ዓቅም ማጠናከርና እስካሁን በወጉ ተገቢው ትኩረትና አገልግሎት ባልተሰጣቸው በግብርና ምርት ላይ በተመሠረቱ አካባቢዎች አዳዲስ የምርምር ተቋማትን መገንባት፤
- የሰው ኃይላችንን በመጠንም በጥራትም ማሳደግ፤
- የምርምር ዘርፎችንና ፕሮግራሞችን መጠቆምና፣ ተለይተው የታወቁትንም እንደአስፈላጊነታቸው በቅደም ተከተል ለማደራጀት የሚያስችሉ የተሻሉ ሥርዓቶችን/ሥልቶችን መቅረጽ/ማስተዋወቅ፤
- በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉት የግብርና ምርምር ሥርዓቶች/ተቋማት በተሻለ ሊደራጁ የሚችሉበትን ድርጅታዊ መዋቅርና የምርምር ተግባሮቻቸውን በተቀናጀ አኳኋን ለመሥራት የሚያስችላቸውን ዘዴ ወይም ሥልት መፍጠር፣ መዘርጋት፤
- ለምርምር የሚያስፈልገውን የገንዘብና የሌላም ንብረት መጠን ከፍ ማድረግ ብቻ ሳይሆን፣ በሚፈለግበት ጊዜ ለሚፈለግበት ጉዳይ በአፋጣኝ እንዲደርስ አድርጎ ሥርዓቱን ማሻሻል።

❖ የተሻሻሉ የቴክኖሎጂ ውጤቶች አቅርቦት ይሻሻላል

የተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂዎችን የማፍለቅና የመፍጠሩ ጉዳይ፣ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ከሚገባን መጠንና መንገድ ባነሰ ሁኔታ ከመጠቀማችን ጋር ከተያያዙት ችግሮች አንደኛውን ገጽታ ብቻ የያዘ ነው። ሌላ ገጽታው ደግሞ እንዲህ ያሉትን የቴክኖሎጂ ውጤቶች በሚፈለገው መጠንና ዓይነት/ጥራት በወቅቱ የማቅረብ ችግር ነው። በእጃችን ያለው የተሻሻሉ የግብርና ግብኣቶች ላሉት የገበሬ ማኅበረሰቦች ፍላጎቶች ማሟያ የሚሆን ብቃት ጨርሶ የሌለው መሆኑ የሚያጠያይቅ አይደለም። በዚህ ረገድ ያለው ችግር፣ የእህል ዘሮችን ማባዛትንና የመዝሪያ/የመትከያ መሣሪያዎችን፣ የማዳበሪያና የጸረ ተባይ መድኃኒቶችን አቅርቦት፤ የተሻሻሉ የእንስሳት ዘሮችን አቅርቦት፤ የተሻሻሉ የእርሻ መሣሪያዎችንና ቆሳቁሶችን አቅርቦት፣ የተሻሻሉ የንብ ቀፎዎችን አቅርቦት፣ ወዘተ. የሚያካትት ነው።

ባሁኑ ወቅት እነዚህን የቴክኖሎጂ ውጤቶች አባዝቶ/አራብቶ የማቅረቡን ኃላፊነት ይዘው በአብዛኛው የሚንቀሳቀሱት፣ በመንግሥት ሥር ያሉ ድርጅቶች ናቸው። በዚህ መስክ ያለው የግል ዘርፉ ተሳትፎ በእርግጥም እጅግ ውሱን ነው። ለግል ዘርፉ ተሳትፎ ደካማነት የተለያዩ ምክንያቶች ሲኖሩ፣ ከመንግሥት ፖሊሲ የሚመነጩ ዕንቅፋቶች፣ ስለነዚህ ተግባሮች ግንዛቤ/ወይም ለቴክኖሎጂዎቹ ምንም ፍላጎት የሌለ መሆኑ፣ በክህሎትም ሆነ በሀብት/በንብረት ደረጃ ዓቅም አለመኖሩ፣ በተለይ ፍላጎትን በመቀስቀስና ሥጋትን በማስወገድ/ኪሣራን በመከላከል ረገድ ምንም ዓይነት ማበረታቻ አለመኖሩ፣ ወዘተ. በተለይ ሊጠቀሱ የሚችሉ ናቸው። ለትርፍ ሲሉ በግሉ ዘርፍ የሚሰማሩ የንግድ ሰዎችን ቀልብ የሚስብ ተግባር ባለመሆኑ፣ የምርት ግብኣቶችን ማቅረብ በሚያስፈልግባቸው አንዳንድ ሁኔታዎች መንግሥት ኃላፊነቱን ወስዶ መንቀሳቀሱ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ይሁን እንጂ የግብርናውን ዘርፍ እናለማለን ብለን ከተነሳን፣ የግል ዘርፉ በራሱ ተነሣሥቶ ሀብቱን በግብርናው ዘርፍ ልማት ላይ እንዲያውል መንግሥት ጠንክሮ ማበረታታት አለበት። በዚህ ረገድ፣ የግሉን ዘርፍ ለማበረታታት የተወሰዱ አንዳንድ እርምጃዎች መኖራቸውን እገነዘባለሁ፤ ይሁን እንጂ፣ በተባሉት መስኮች እስካሁን የተደረገው ጥረት ከሚገባው በታች መሆኑንም መቀበል ያስፈልጋል። ይህ ሲጨመቅ፣ አሁንም ትኩረት ሊሰጣቸውና ሊወገዱ የሚገባቸው ችግሮችና ዕንቅፋቶች አሉ ማለትን ይሆናል።

❖ የግብርና ምርምር ውጤቶችን የሚጠቀሙ ማኅበረሰቦች ዓቅምና ፍላጎት ይጠነክራል

የግብርና ቴክኖሎጂ የሚጠቀሙ ማኅበረሰቦች የቴክኖሎጂውን ውጤቶች ተቀብለውና የራሳቸው አድርገው የሚጠቀሙበት መጠንና ስፋት ዝቅ ለማለቱ፣ በከፊልም ቢሆን አንድ ምክንያት የሚሆነው፣ የሀገሪቱን የግብርና ውጤት ከሚያመርቱት አብዛኛውን ክፍል የያዙት አራሽና ከብት አርቢ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተግባራቸውን የሚያከናውኑባቸው ይዞታዎች መጠን አነስተኛ ደረጃ ላይ ያለ መሆኑ ነው። ይህ የዓቅም ማነስ ከሚገለጽባቸው ሁኔታዎች፣ በመጠናቸው እጅግ ትንሽ የሆኑና የተበጣጠቁ የመሬት ይዞታዎች፣ እንደበሬና እንደእርሻ መሣሪያዎች ያሉ የግብርና ንብረቶች አለመኖር ወይም ውሱን መሆን፣ አስፈላጊ የሆኑ የግብርና ግብኣቶችን ለመግዛት የሚያስፈልገው ጥሬ ገንዘብ በቂ አለመሆኑ፣ በተለይ በምርት መቃረቢያ ጊዜ በቂ የሰው ኃይል አለመገኘቱ የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ። እነዚህን ችግሮች ደግሞ የሚያባብሳቸው፣ እንደደንና እንደ ግጦሽ መሬት ያሉትን የተፈጥሮ ሀብቶች በደንብና

በወጉ አለመጠቀም፣ በዚህም የተነሣ ንብረቶቹ በመጠንም በጥራትም እየተጎሳቆሉ መሄዳቸው፣ ይህ ደግሞ እንደገና ዞሮ የመሬትንና የሌሎችን የተፈጥሮ ሃብቶች ምርታማነትን የሚቀንስ መሆኑ ነው። እነዚህ ችግሮች ወይም ዕንቅፋቶች ቢያንስ የሚከተሉትን እርምጃዎች በመውሰድ ሊወገዱ ይችላሉ፤

- የተጠቃሚዎቹ የመሬት ይዞታ ዋስትና እና የምርት መጠኑ ከፍ ያለ መሆኑን ለማረጋገጥ እንዲቻል የመሬት ይዞታ ጥያቄዎች መፍትሔ የሚያገኙበትን መንገድ መሻት፤
- መሬትን በተገቢው መንገድ ሥራ ላይ ለማዋል የሚደረገውን ጥረት ለማቀላጠፍ የመሬት አጠቃቀም ሕጎችንና ደንቦችን መንደፍና ተፈጻሚነት እንዲኖራቸው ማድረግ፤
- ለተጠቃሚዎቹ የሚመችና እነሱን የሚያበረታታ የብድር ሥርዓት ዘርግቶ በተግባር ላይ ማዋል፤ ይህ በእርሻና በከብት ርቢ ተጠቃሚ የሆኑትን ማኅበረሰቦች በቀጥታ በገንዘብና በቁሳቁስ እንዲሁም በድጎማ መርዳትንም ይጨምራል። ይህን ማድረጉ ደግሞ በተለይ ተገቢ የሚሆነው፣ የአካባቢ መጎሳቆልን በተቻለ መጠን ዝቅ በማድረግና በየዓመቱ ዋጋቸው እየጨመረ የሚሄዱትን፣ እንደ ኬሚካል ማዳበሪያዎች ያሉትን አስፈላጊ ግብኣቶች እንዲያገኙ በማስቻልም አንጻር ሲታይ ነው። ለምሳሌ፣ ባለፉት ሁለት የምርት ዓመታት የዳፕ እና የዩሪያ ማዳበሪያዎች ዋጋ፣ እንደቅደም ተከተላቸው በኩንታል 320 እና 280 ብር ነበር። ይህ ዋጋ እጅግ ውድ ነው ማለት ሲቻል፣ በዚህ ምክንያት ደግሞ ገበሬዎቹ፣ በተለይ ደግሞ የገዘናም ሁኔታ አስተማማኝ ባልሆነባቸው አካባቢዎችና ሁኔታዎች የሚኖሩት፣ የምርትን መጠን ከፍ በሚያደርጉት በነዚህ ማዳበሪያዎች መጠቀም እንዳይችሉ፣ መጠቀም ከቻሉም በአነስተኛ መጠን ብቻ እንዲጠቀሙባቸው ሆነዋል።
- ቀደም ሲል የነበረውን፣ የእርሻውን ዘርፍ በዘመናዊ መሣሪያ የማደራጀትና የማንቀሳቀስ ዘዴ መልሶ እንዲያንሠራራ ማድረግ፤ ይህን ማድረጉ በተለይ ምርት በሚቃረብበት ጊዜ የሚገጥመውን የሰው ኃይልና የመሣሪያ እጥረት ችግር ለመቀነስ ይረዳል።

❖ በግብርና ምርምር ውጤቶችን የሚጠቀሙ ማኅበረሰቦች ግንዛቤና ስጋትን የመሸከም ዓቅም ይሻሻላል

የችግሩን መጠንና ዓይነት በደንብ መረዳቱ ያዳግተን ይሆናል እንጂ፣ ገበሬዎቹና ከብት አርቢዎቹ ስለተሻሻለ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች መኖርና ስለሚሰጠውም ጥቅም ያላቸው ግንዛቤ በእግጥም ዝቅ ያለ ነው። ገበሬዎቹና ከብት አርቢዎቹ የተሻሻለ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች መኖራቸውንና ጠቃሚ መሆናቸውን እንዲያውቁና እንዲረዱ ማድረግ የሚቻልባቸው የተለያዩ መንገዶች ያሉ ሲሆን፣ ከነዚህም ውስጥ፣ በመስክ የተሰማሩ የልማት ባለሙያዎች ከተጠቃሚዎቹ ጋር በቀጥታ የሚያደርጓቸው ግንኙነቶች፣ ተጠቃሚዎቹ ባለባቸው አካባቢዎች የቴክኖሎጂዎቹን አገልግሎትና ጠቀሚታ፣ አጠቃቀማቸውንም በተግባራዊ መልክ ማሳየትና ተከታታይ ሥልጠና መስጠት፣ በመገናኛ ብዙኃን አማካይነት ትምህርት ማስተላለፍ ይገኙባቸዋል። አሁን ባለንበት ወቅትና ሁኔታ፣ ብዛት ያላቸውን የገበሬዎች ማሠልጠኛ ማዕከሎችን ማቋቋምና የገበሬና የልማት ባለሙያዎችን ምጣኔ (አንድ ባለሙያ-ለስንት ገበሬ ይበቃል የሚለውን) ማሻሻል፣ በግብርና ሙያ የተሰማሩትን

ማኅበረሰቦች በቀጥታና በፊት ለፊት ተገናኝቶ በግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች እንዲጠቀሙ በማግባባት ረገድ፣ ሩቅ አስቦ ሩቅ የሚያሳድር ጠቀሜታ አለው። ከዚህ በላይ በሌላ ሥፍራ እንደተጠቀመው፣ አሁን በሥራ ላይ ያለው የPADETS ፕሮግራም እስካሁን ከአራት ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ የገበሬ ቤተሰቦች የሚጠቀሙበት መሆኑ ተነግሯል። በዚህ ላይ ደግሞ፣ በተጨማሪ፣ ብዙ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የግብርና ሙያ ሥልጠና የሚሰጡ ትምህርት ቤቶችና ኮሌጆች ጥረትም ይጨመርበታል።

ይህም ሁሉ ሆኖ ግን፣ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶችን ተቀብሎ መጠቀሚያ የማድረግ ልማድ ያደገውንም ያህል ቢያድግ፣ የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት በብሔራዊ ደረጃ ለማሳደግ በቂ ሆኖ አልተገኘም። ስለዚህም፣ አሁንም ትኩረት ተሰጥቷቸው መፍትሔ ማግኘት ያለባቸው ችግሮች ያሉ መሆኑን መረዳቱ አንድ ተቀዳሚ ተግባር ነው። ከሁሉ አስቀድሞ፣ እስካሁን በተደረገው ጥረት በግብርና ከሚተዳደሩት ማኅበረሰቦች ውስጥ ተጠቃሚ ሊሆኑ የቻሉት እጅግ ጥቂቶቹ ናቸው። ሁለተኛ፣ የግብርናን ቴክኖሎጂ ጠቀሜታ የተረዱትም እንኳን፣ የቀረበላቸውን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ሙሉ ለሙሉ ተማምነው ለመቀበል እያመነቱ ናቸው። ለምሳሌም ያህል፣ ተገቢው መጠን ነው ተብለው ተሰፍረው ከቀረበላቸው የተሻሻሉ ዘሮች እና/ወይም ኬሚካል ማዳበሪያዎች ውስጥ ተቀብለው በሥራ ላይ የሚያውሉት ግን ተገቢ ነው ከተባለው መጠን በታች የሆነውን ነው። የዚህ ምክንያቱ፣ የተሻሻሉ ግብኣቶችን ለመግዛት የሚያስፈልጋቸው ጥሬ ገንዘብ አለመኖሩ ወይም የዱቤ አገልግሎት መጥፋቱ ሊሆን ይችላል። አንድም፣ በአየር ጠባይ አስተማማኝ አለመሆን ወይም በሌላ ምክንያት ሊደርስባቸው የሚችለውን የሰብል መበላሸት ወይም መጥፋት በመፍራትም ሊሆን ይችላል። ይህን በመጨረሻ ላይ የተነሣውን ችግር አስመልክቶ፣ መንግሥት ለችግሩ ከበፊቱ የበለጠ ትኩረት መስጠት ያለበት ከመሆኑ በላይ፣ አራሾቹ/ ከብት አርቢዎቹ ለሥጋታቸው ዋስትና ማግኘት የሚችሉበትን ዘዴ ፈልጎ ተግባራዊ ማድረግም ያስፈልጋል።

- **የሀገሪቱ ብሔራዊ የመሠረት ልማት መዋቅርና የገበያ ይዞታ አሁን ካለው በበለጠ እንዲለማና እንዲሻሻል ይሆናል**

በግብርናው ዘርፍ የተሰማሩ አምራቾች፣ ምርቶቻቸው ገበያ የሚያገኙ መሆናቸውን ካረጋገጡ እና ገንዘብና ጉልበታቸውን የሚመጥን ትርፍ ማስገባት የሚችሉ መሆናቸውን ካወቁ፣ በተሻሻሉ የግብርና ቴክኖሎጂ ውጤቶች ላይ ገንዘባቸውን ማፍሰስ እንደሚፈልጉ እሙን ነው። አሁን ባለንበት ሁኔታ ግን፣ ለምርቶቻቸው ተመጣጣኝ የሆነ ዋጋ ሊያገኙ የሚችሉባቸው የገበያ አገልግሎቶችን የሚያገኙት በከተሞች፣ ለዚያውም ደግሞ ከሀገሪቱ ሕዝብ በጠቅላላው 16 በመቶ የሚሆነው ብቻ በሚኖርባቸው ነው። ከተሞችን ከገጠሩ ክፍል የሚያገናኘው መዋቅርም ደካማ በመሆኑ፣ አብዛኛዎቹ በዝቅተኛ ደረጃ የሚያመርቱት ገበሬዎች የሚጠቀሙት የቤተሰቦቻቸውን የእለት-ተእለት ፍላጎት ለማሙዋላት ብቻ በሚያስችላቸው፣ ከእጅ-ወደአፍ በሆነው፣ በዚያው በቀድሞው የማምረት ሥልት ነው። የገጠሩ ክፍል ማኅበረሰቦች ከከተማውና እርስበርሳቸውም ተራርቀው እንዲኖሩ ለተገደዱበት ሁኔታ ዋናው ምክንያት የሀገሪቱ የመሠረተ ልማት መዋቅር--ማለትም፣ የመንገድ፣ የመንገሻ እና የገበያን ሁኔታ የሚመለከት የመረጃ /የኢንፎርሜሽን/ ማሰራጫ ዘዴው ደካማ መሆኑ ነው። ምንም እንኳን የመንገድና የመንገሻው መዋቅር በአሁኑ ጊዜ እየተሻሻለ የሄደ ቢሆንም፣ አሁንም ቢሆን፣ ያለበት ሁኔታ የአምራቾቹን ፍላጎት የሚያሙዋላም የሚያረካም አይደለም።

- የምርምር ባለሙያዎች፣ ገበሬዎችና የግብርና ቴክኖሎጂ ተጠቃሚዎች በመካከላቸው ያለውን ግንኙነትና ትብብር እንዲያጠናክሩ ይበረታታሉ

የቀድሞው የእርሻና የሜካኒካል አርትስ ኮሌጅ፣ በአሜሪካው የኦክላሆማ ስቴት ዩኒቨርሲቲ ድጋፍና ትብብር በተቋቋመበት ጊዜ፣ ኃላፊነቱ በግብርናው የዕውቀት መስክ ማስተማር፣ ምርምር ማካሄዴድ እና የኤክስቴንሽን ድጋፍ መስጠት ነበር። የትምህርቱ አወቃቀር ሦስት ማዕዘኖች እንዳሉት ቅርጸ ሽብልቅ ሆኖ፣ እያንዳንዱ ማዕዘን ከላይ የተጠቀሱትን የትምህርት ዘርፎች የሚወክል ነው። ስለዚህም፣ ኮሌጁ በየዘርፉ የሰለጠኑ የሰው ኃይልን ሲያፈልቅ፣ ስልጥነው የወጡት ሰዎች ደግሞ ከሚጠበቁባቸው ተግባራት አንዱ በሆነው የግብርና ቴክኖሎጂዎችን በማፍለቁ ሥራ ይሰማራሉ፤ የነሱ ምርምርና ጥረት ውጤት የሆኑት የቴክኖሎጂ ውጤቶች በተራቸው በግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራም አማካይነት ለተጠቃሚዎች ይሰራጫሉ። ስለዚህም፣ የቀለም ትምህርት፣ ምርምርና የግብርና ኤክስቴንሽን ተግባሮች በሥርዓት የተቀናጁ ዘርፎች ነበሩ ማለት ነው።

ታዲያ ምን ይሆናል፤ ይህ ሦስት ዘርፎችን ያቀናጀ የትምህርትና የሥልጠና ሥልት፣ እ.አ.አ. በ1960ዎቹ ውስጥ ይፈርስና፣ የምርምር ዘርፉ በዲሬክተሮች ቦርድ የበላይነት ይንቀሳቀስ ወደነበረው የቀድሞው የግብርና ምርምር ተቋም እንዲዛወር ሲደረግ፣ የግብርና ኤክስቴንሽን ፕሮግራሙ ደግሞ በቀድሞው የእርሻ ሚኒስቴር ጥላ ሥር እንዲንቀሳቀስ ተደረገ። እነዚህ ሦስቱ ዘርፎች እንዲነጣጠሉ ሆነው የተዋቀሩበት ሁኔታ አሁንም ድረስ ያለ ሲሆን፣ ባሁኑ ጊዜ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ወገኖች ዘንድ ላለው ብዙ አለመግባባትና የመበሳጨትና ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ምክንያት ሆኗል። በነዚህ በሦስቱ ዘርፎች መካከል የተሻለ ቅንጅትና ትብብር እንዲኖር የሚያስችሉ ዘዴዎችና ሥልቶችን ለመዘርጋት የተለያዩ ጥረቶች መደረጋቸው እርግጥ ነው፤ ሆኖም በዚህ ረገድ የተገኘው ውጤት ውስን ነው።

በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲባል፣ አሁን እያደገ ያለው የግብርና ውጤቶች ኢንዱስትሪ ዘርፉ ራሱን የቻለ የኢኮኖሚ ልማት ክልል ሆኖ ከመምጣቱ በላይ፣ ዘርፉ የሚጠቀምባቸው የግብርና ጥሬ ግብኣቶች ከውጭ ከፍተኛ ዋጋ የሚገቡ ናቸው። እነዚህን በአገር ውስጥ በዝቅተኛ ዋጋ ማምረት ይቻላል። በዚህ ረገድ ሊጠቀሱ የሚችሉት፣ የዱቄት ፋብሪካዎች የሚያስፈልጋቸውን (ለዳቦም፣ ለፓስታም የሚሆነውን) ስንዴ፣ በሀገሪቱ ብቸኛ የሆነው የቪኖ ፋብሪካ የሚያስፈልገውን ዘቢብ፣ ከውጭ እያመጡ ነው የሚንቀሳቀሱት። እንዲሁም፣ በሀገሪቱ ብቸኛ የሆነው የቢራ ብቅል ፋብሪካ የሚያስፈልገውን ገብስ፣ እስከቅርብ ጊዜ ያስመጣ የነበረው ከውጭ ነው። በምርምር አገልግሎት ተቋማት፣ በአምራች ገበሬዎች እና በግብርና-ኢንዱስትሪዎች መካከል እስካሁን ሲታይ ከነበረው የጠነከረ ቅንጅት መፍጠር ቢቻል፣ እነዚህ ሁሉ የግብርና ጥሬ ምርቶች፣ የሀገሪቱን ፍላጎት ለማሟላት በሚቻልበት መጠንና ጥራት እዚሁ ሀገሪቱ ውስጥ ሊመረቱ የሚችሉ ነበሩ። በሌላ በኩል ግን፣ ደግነቱ፣ አሁን አሁን፣ የሚመለከታቸው ወገኖች ችግሩን እየተገነዘቡ በመምጣታቸው፣ በተጠቀሱት ሦስት ዘርፎች መካከል፣ በተወሰነም ደረጃ ብቻ እንኳን ቢሆን፣ መተባበርና መደጋገፍ፣ እንዲፈጠር የማድረግ ፍላጎቱ አላቸው። አንዳንዶች የምርምር አገልግሎት ተቋማት የሥራ መሪዎችና ባለሙያዎች ምሥጋናው አይጓደልባቸውና፣ ሦስቱ ዘርፎች ለፍሬ የሚበቃ ትብብር እንዲፈጥሩ በማድረግ ረገድ ብሩህ ተስፋ ፈጥረዋል። ይህ ሊበረታታ የሚገባ ሁኔታ

ነው። መንግሥትም፣ ይህንኑ ተመልክቶ፣ በዚህ አቅጣጫ የሚደረገውን ጥረት በፖሊሲና በፋይናንስ ማናቃቂያ ሊያግዝ ይገባዋል።

የኢንዱስትሪ ምርምር እና ልማት በኢትዮጵያ

አሥራት ቡልቡላ*

1. መግቢያ

ስለ ኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት በምንነጋገርበት ወቅት በመጀመሪያ ኢንዱስትሪ በሚለው ላይ አንድ አጠቃይ መግባቢያ ሃሳብ ያስፈልጋል። በተለምዶ ጠበብ ባለ መልኩ ኢንዱስትሪ ሲባል የማኑፋክቸሪንግ (በፋብሪካ ተግባር) ዘርፉን ቢሆንም ሌሎች በሠፊው ትርጉም ውስጥ ሊካተቱ የሚችሉትን በተዘዋዋሪም ቢሆን መመልከት የግድ ይላል።[1] እነዚህ ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ውጭ ያሉት በምርት ተገልጋይነት ወይም ግብአት አቅራቢነት ከማኑፋክቸሪንግ ዘርፉ ጋር ከፍተኛ ቁርኝት አላቸው። ወሳኝ ሚናም ይጫወታሉ። በመሆኑም የኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት በሚዳሰስበት ወቅት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን ብቻ ሳይሆን ኢንዱስትሪ የሚለውን ሰፋ ያለ አተረጓጎም በመያዝ ነው።

ምርምር አዲስ ዕውነታ/Fact/ ወይም ኢንፎርሜሽን ለማግኘት ጥንቃቄ የተሞላበት ጥናት ወይም ፍተሻ ማድረግ ነው። "ምርምር የሳይንሳዊ አካሄድ ባህል" ነው። ችግርን /ፕሮብሌምን/ ለማወቅ ስልት ማበጀት፣ ማጥናት፣ ለችግሩ ማስወገጃ ወይም መቀነሻ የተለዩ አማራጮችን መዳሰስ፤ በዋጋ፣ በጊዜ እና በአቅም ሊፈቱ የሚችሉትን በመምረጥ የተግባራዊነት ስልት መንደፍ፣ በተነደፈው ስልት መሠረት እየተገበሩ፣ እየተሻሻሉ የመሄድ ባህልን ማዳበር ማለት ነው። የኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት የሚታየው በዚህ አኳያ አግባብነት አለው።

አቀራረቡ የኢንዱስትሪውን ዘርፍ በአጠቃላይ ይመለከታል ቢባልም፣ በማዕከልነት የማኑፋክቸሪንግ ዘርፉን በማቀፍ ነው።

ጽሁፉን ፈር ለማስያዝ በቅድሚያ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ሁኔታ በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል ለማሳየት እሞክራለሁ። ቀጥሎም አጠቃላይ የኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት በ2020 ልትደርስበት ያለበትን ሁኔታ በመዳሰስ አገራችን በኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት በ2020 ልትደርስበት የምትችልበትን ሁኔታ ለማመላከት እሞክራለሁ። በ2020 እይታ ላይ አጠቃላይ ታሳቢዎችን

---

* እኔ አሥራት ቡልቡላ በሳይንስና ቴክኖሎጂ ኮሚሽን በኮሚሽነርነትና በምክትል ኮሚሽነርነት እንዲሁም በብሔራዊ ኬሚካል ኮርፖሬሽን በሥራ አስኪያጅነት አገልግለዋል። በዓለም አቀፍ ተቋማት ውስጥም በአባልነት የሠሩ ሲሆን በUN Social and Technology Commission በኮሬዝዳትነት አገልግለዋል። በአሁኑ ወቅት በሚድሮክ ኢትዮጵያ በአማካሪነት በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

[1] የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ልማት ስትራቴጂ 1994 ዓ.ም

እና ርዕያችንን እውን ለማድረግ ሊተገበሩ የሚገባቸው ወሳኝ ተግባራትን ለመጥቀስ እሞክራለሁ።

ፅሁፉ በሦስት ዋና ዋና ክፍሎች እንዲዘጋጅ ተደርጓል፤
1ኛ/ በመግቢያነት የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ሁኔታ በኢትዮጵያ
2ኛ/ የኢንዱትሪ ምርምርና ልማት ገፅታ
3ኛ/ በኢንዱስትሪ ምርምር እና ልማት የ2020 ርዕይ

2. የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ሁኔታ በኢትዮጵያ

- የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር በሚቀጥሉት 20 ዓመታት አሁን ካለበት 80 ሚሊዮን አካባቢ ወደ 140 ሚሊዮን ይደርሳል ተብሎ ይገመታል።
- በየዓመታቱ ከ2 ሚሊዮን ያላነሱ አዳዲስ ኢትዮጵያውያን ሰዎች ይፈጠራሉ፤ ይህ አሁን ያለውን የሥራ አጥ ቁጥር ዜሮ ብናደርገው እንኳ ወደ 2 ሚሊዮን የሚጠጋ በየዓመቱ ሥራ ፈላጊ ሊሆን ነው!
- ከዓለም ሕዝብ ግማሽ ያህሉ (3 ቢሊዮን) የቀን ገቢው ከአሜሪካን 2 ዶላር በታች ሊሆን ከዚሁ ውስጥ 1.2 ቢሊዮኑ ከ1 ዶላር በታች ነው። የኢትዮጵያ ደግሞ ከአሜሪካን 30 ሳንቲም (1/3 ዶላር) በታች ነው።[2]
- በማናቸውም መመዘኛ በኢንዱስትሪ በበለጸጉ ሀገሮች እና በ3ኛው ዓለም መሀል ያለው ልዩነት በየጊዜው እየሰፋ እንጂ እየጠበበ የመጣበት ሁኔታ አለመኖር[3] የብዙ ሀገሮች /በተለይም 3ኛው ዓለም/ ህልውና በበለፀጉ ሀገሮች ተፅዕኖ ሥር የወደቀ ነው። እንግዲህ እነኚህንና መሰል አስደንጋጭ አሀዞች እና ዕውነታዎች ባሉበት ዓለም ነው የኛንም ሁኔታ እንድናይ የምንገደደው፤
- በኢትዮጵያ የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ሁኔታ ሊወሳ የሚችለው እ.ኤ.አ. ከ1935-41 የኢጣሊያን ወረራ በኋላ ነው በባል ከእውነት አይርቅም። ከዚያ በፊት የነበረው በቤተሰብ ደረጃ፣ በተናጠል የሚደረግ፣ ከጎጆ ኢንዱትሪ ያነሰ፣ የባህላዊ ቁሳቁስ አቀራረብ ብቻ ነበር፤ ለምሳሌ ያህልም፤ ማረሻ፣ ጦር፣ የስለት መሣሪያዎች፣ ሸማ፣ ቁርበት፣ አንቀልባ፣ ብራና ቀለም፣ የሽክላ መገልገያዎች እና የመሳሰሉት ናቸው። ከኢጣሊያን ወረራ በኋላ የኢንዱስትሪው ዘርፍ ኤክስፖርት መር እና ትላልቅ ኢንዱስትሪዎች እንዲመሠረቱ ባለመ አትጣጫ የተነደፈ ነበር።[4] በ1950ዎቹ የተካሄደው የኢንዱትሪ ልማት መንግሥት የውጭ ኢንቬስትመንትን በማበረታት፣ በተለይም በውጭ ባለሀብቶች ይዞታ ሥር የነበሩ የኢንዱስትሪ ተቋማት እንዲገነቡና የውጭ ኢንቨስትመንትን ለመሳብ በተወሰዱ ማራኪ እርምጃዎች ነበር። ከልዩ ልዩ

[2] የፍጹም ድህነት መገለጫው የነፍስ ወከፍ የቀን ገቢ ከአንድ የአሜሪካን ዶላር በታች ነው።
[3] Industrial Development Report 2002/2003, UNIDO
[4] Sustainable Industrial Development and Competitiveness, Ministry of Trade and Industry of Ethiopia and UNIDOI, Vienna, 2004..

ማበረታቻዎች ውስጥ ለምሳሌ ያህል ከ5-10 ዓመት የታክስ ዕፎይታ ጊዜ፣ የግብዓቶች ቀረጥ አነስተኛ መሆን እና በጣም አስተማማኝና ዝቅተኛ የወለድ ተመን የባንክ ብድር አገልግሎት ከብዙዎቹ ውስጥ ጥቂቶች ናቸው።

- በ1960ዎቹ በተባበሩት መንግሥታት የልማት 10 ዓመታት /1960-1969/ ዕቅድ መሠረት የኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት አቅጣጫ ከውጭ የሚገቡ ዕቃዎችን በሀገር ውስጥ በማምረት የውጭ ምንዛሪ ማዳን ላይ ያተኮረ እንዲሆን የተቀየሰ ነበር። በመንግስትም ሆነ በግል ዘርፉ የተሰማሩ ተዋንያን ትኩረታቸው በቀላል የፍጆታ ዕቃዎች ማምረት ላይ እና በመጠነ-ም ለሌሎች በግብዓትነት የሚያገለግሉት ላይ ነበር። ምንም እንኳ ጥቂቶች ኢንዱስትሪዎች በመጠነ-ም ቢሆን የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ በገለገሉም፣ የግብዓታቸው አብዛኛው ክፍል ይሸፈን የነበረው ከውጭ በሚገቡ ጥሬ ዕቃዎች ላይ ነበር። የማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪው ልማት እያደገ መጥቶ የሀገር ውስጥ አጠቃላይ ምርትን(GDP) 14 በመቶ እስከ መሸፈን ደርሶ ነበር። ሆኖም ይህ ዕድገት በ1970ዎቹ መጨረሻ አካባቢ ኢንዱስትሪዎች ከ40-70 በመቶ የሚሆነውን ጉልበታቸው እንዳይጠቀሙ ተገደዱ።
- በ1980ዎቹ በወዳጅ መንግሥታት ብድርና ድጋፍ የአዳዲስ ማምረቻዎች ግንባታ እየተካሄደ ቆይቶ በ1990ዎቹ የመንግሥት ለውጥ ከተከሰተ በኋላ የዕዙ ኢኮኖሚ በነጻ ገበያ ተተካ የሀገሪቱም የልማት ስትራቴጂ ግብርና መር የኢንዱስትሪ ልማት ሆነ[5]።

3. የኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ሁኔታ

የኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት የሚኖረው የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ በሚኖርበት፣ የምርምሩ ጥልቀትም ሆነ ዕድገት የሚወሰነው በኢንዱስትሪው ክፍለ ኢኮኖሚ የዕድገት ደረጃ ነው። በመሆኑም በኢትዮጵያ የኢንዱስትሪ ልማት መሆን ከነበረበት ጋር ሲነፃፀር በጣም በጣም ዝቅተኛ ነው፤ የኢንዱትሪ ምርምርና ልማቱም ዕውነታ ነፀብራቅ ነው።

ቀደም ሲል የኢንዱስትሪ አካሄድ አቅጣጫዎች በተመለከተነው መሠረት የምርምር ዘርፉን ከዚሁ አኳያ ማጤን የግድ ይላል። በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘርፉ የተደረገው የኢንዱስትሪ ምርምር እንቅስቃሴ የተጀመረው በኩባንያ ደረጃ በብሔራዊ ኬሚካል ኮርፖሬሽን ቢሆንም በኢንዱስትሪ አቀፍ ደረጃ በተጠናከረ መልኩ እንዲንቀሳቀስ የተደረገው ከ1987 ዓ.ም. ወዲህ ነው[6]። በአወቃቀርም ረገድ ከኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ዋና መስሪያ ቤት ጀምሮ በየኮረፖሬሽኖቹ እና በሥራቸው በሚገኙ ማምረቻ ፍብረካዎች ጭምር እንዲሆን የተዘረጋ ነበር። በዚህ ወቅት ነበር በኢንዱስትሪውና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መካከል ለምርምሩ ዘርፍ አስኳል የተጣለው።

[5] Sustainable Industrial Development and Competitiveness, MOTI and UNIDO, 2004.
[6] Bekele Bayissa Industrial Innovation Competitiveness in Ethiopia 2003.

ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸውን ዘርፎች በምንቃኝበትም ጊዜ የግብርና ምርምር ዘርፉ አነስተኛ ግን የማይናቅ አስተዋፅዖ አድርጓል። ለጨርቃጨርቅ ኢንዱስትሪ በጥጥ ዝርያ ላይ፣ ለምግብ ፍብሪካዎች የስንዴ ዝርያዎች (ለፓስታ፣ ለዳቦ፣ የቢራ፣ ገብስ፣) የመሳሰሉትን አቅርቧል። በተረፈ የምርምር እንቅስቃሴ ለኢንዱስትሪው ያደረገው አስተዋፅኦ በአመዛኙ እንደሌለ ቢቆጠር መልካም ነው።

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሰለጠነ የሰው ኃይል ከማቅረባቸው በተጨማሪ ተመራቂዎች የሚያቀርቧቸው የመመረቂያ ጽሑፎች ያደረጉት የዕውቀት እርከን ጭማሪ መኖሩ ቢታወቅም ለኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ምርምር ያደረጉት አስተዋጽኦ በተጨባጭ የሚታይ አይደለም። ምናልባት ሲጠነሰሱም፣ ሲደራጁም ይህ አልተጠበቀባቸውም። የኢንዱትሪ ችግር ለመፍታት ምንም ዓይነት ሙከራዎች አልተደረጉም ማለት ግን አይደለም።

በማዕድን ኢንዱስትሪ ዘርፍ የማዕድ ፍለጋና ውጤት ለቁልፍ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች መቋቋም ዓይነተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል። የማዕድን ኢንዱስትሪ ምርምር ተቋም ባይኖርም፣ የጂኦሎጂ ሰርቬይ ኢንስቲትዩት በጠቆማቸውና ባገኛቸው የማዕድን ጥሬ ዕቃዎች ላይ በመመርኮዝ፣ የጠርሙስና ብርጭቆ ፋብሪካዎች፣ የዕምነበረድ ማዘጋጃ ድርጅቶች፣ የኖራ፣ የጀሶ፣ የሲራሚክ፣ የአልሙኒየም ሰልፌት፣ ኮስቲክ ሶዳ እና የፀረ ተባይ ማዘጋጃ ፍብሪካዎች ተቋቁመዋል።

በጤና ኢንዱስትሪው ዘርፍም ቢሆን የተደረገው ምርምር በሥነ-ምግብ ላይ ሆኖ ለህፃናት የአልሚ ምግብ ዝግጅት ሙከራ ተደርጓል። በዚሁ መሠረት የፋፋ የምግብ ፋብሪካ፣ አዮዲን አዘል ጨው ማምረቻ ተቋቁሟል። ይህ እንደሠርቶ ማሣያ የሚቆጠር ብቻ ነው። ለመድኃኒት ማምረቻ ፍብሪካ የሚረዳ፣ ለሌሎች ለጤና ዘርፉ የሚያገለግሉ የምርምር ውጤቶችና ጥናቶች እንዲያበረክቱ ታስቦ የተቋቋሙት የፓስተር ኢንስቲትዩት፣ የሥነ ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት፣ የባህል መድኃኒት ምርምር መምሪያ (በአሁኑ ወቅት ተዋህደው የኢትዮጵያ የጤናና የሥነ-ምግብ ምርምር ኢንስቲትዩት ተብለዋል) በመጠኑም ቢሆን እየተንቀሳቀሱ ነው። ለመድኃኒት ማምረቻዎች ያደረጉት አስተዋፅኦ ከጥራት መፈተሽና ማረጋገጥ ውጭ በጣም ውሱን ነው።

የኢነርጂ ምርምር እንዲያደርግ የተዋቀረ ማዕከል ቢኖርም ከተሠጠው አነስተኛ ትኩረትና ድጋፍ አኳያ አነስተኛ እንቅስቃሴ አድርጓል። ከውጤቶቹም መሀከል "ላቀች" ምድጃ ናት።

በኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፍ ከምርት ጥራት ፍተሻ (የአፈር፣ የብሎኬት ወዘተ...) በስተቀር ምርምር የሚያደርግ የተሰየመ ተቋም እንኳ የለም። በውሀው፣ በትራንስፖርት፣ በመገናኛ ኢንዱስትሪ ዘርፉም የምርምርና ልማት ተግባራትን ለማከናወን የተሰየሙ /የተዋቀሩ/ ተቋማት የሉም።

እነዚህ ክፍተቶች በመጠኑም ቢሆን ለመቅረፍ ታስቦ ሀገር አቀፍ የሣይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲ[7] ተቀርጾ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው።

የኢትዮጵያ ሣይንስ ቴክኖሎጂ ኮሚሽን ፖሊሲውን ተግባራዊ ከሚያደርግባቸው ስልቶች አንዱ የትብብር መስክ መዘርጋት ነው። ከውጭ በሚያደርገው የትብብር መስክ (በተለይም በስውዲናዊው ሲዳ/ሳሬክ) አማካይነት በኢትዮጵያ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ውስጥ የምርምር አቅም የሚገነባበትን ሁኔታ ባለፉት 25 ዓመታት ውስጥ መሠረት ለመጣል የተደረገው ሃያት ተጠቃሽ ነው።

በተባበሩት መንግስታት ሥር ከሚገኘው የዓለም አቀፍ የአቶሚክ ኢነርጂ ድርጅት (IAEA) በሚደረግ ትብብር ለአግሮ ኢንዱስትሪ ግብዓት በሚረዱ ቴክኖሎጂዎች በሰዎች ጤና መስክ፣ በጂኦተርማልና በውሃ ልማት ሥራዎች (IH) የተወሰኑ የምርምርና ልማት ሥራዎች እየተከናወኑ ነው። እነኚህ ቴክኖሎጂዎች ለማኑፋክቸሪንግ እና ተዛማች ኢንዱስትሪዎች ቀጥተኛ ግብዓት የሚሆኑበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

ሀገር አቀፍ የኢትዮጵያ ሣይንስና ቴክኖሎጂ ፖሊሲና ስትራቴጂም ነድፎ ለተለያዩ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ድጋፍ በማሰባሰብ ትርጉም ያለው ለውጥ ለማምጣት ጥረት እያደረገ ነው። በተለይም የድኅረ ምረቃ ፕሮግራሞችን በምርምር ሥራዎች በማስደገፍ እንዲሁም የሙያ ማኅበራትን ሣይንሳዊ መጽሔቶቻቸውን በመደገፍ የማይናቅ አስተዋጽኦ እያደረገ ነው። በድኅረ ምረቃ ፕሮግራሞች የተካሄዱ የምርምር ውጤቶች ለመመረቂያ ማሟያ የተዘጋጁ ሥራዎች ቢሆኑም በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ለኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ አስተዋጽኦ የሚያደርጉ ናቸው።

በሳይንስ መስክ የኢትዮጵያን የዕጽዋት ሀብት በማሣወቅ (ለኢንዱስትሪ ጠቀሜታ የሚውሉትን ለመለየት በመነሻ ለንድነት)፣ የኬሚካል ይዘታዎችንና ጠቀሜታቸውን በመዘርዘር (ናቹራል ፕሮዳክትስ ኬሚስትሪ)፣ በሶላር ኢነርጂ፣ በውሃ ምርምር፣ በእንስሳትና በአዝርዕት ላይ ምርምር በማድረግ በህክምናው ዘርፍ የምርምር አቅም በማጎልበት ቢ.አር.ቲ.ፒ) ለኢንዱስትሪው ዘርፍ አሁን ላሉትም ሆነ ወደፊት ለሚገነቡት አገልግሎት እንዲሰጡ መድረግ ጠቃሚ ነው። በነዚህ ዙሪያ ባለፉት 25 ዓመታት ውስጥ ወደ ብር 800 ሚሊዮን ያህል ወጪ ተደርጓል።[8] ይህ ገንዘብ በኢንዱስትሪ በበለጸጉ ሀገሮች ዓይን ሲታይ የአንድ አነስተኛ ኩባንያ የአንድ ዓመት ምርምር ልማት የሚያወጣውን ወጪ በአማካይ ከዓመት ገቢያቸው ከ5-10 በመቶ የሚሆነውን ይይዛል። አንድ አነስተኛ ኩባንያ የዓመት ገቢው እስከ አንድ ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር ሊደርስ

[7] National Science and Technology Policy
[8] ከሲዳ ሳሬክ እና ከ IAEA የተገኙትን በመደመር የተሰላ ነው።

ይችላል። ይህ የሚሰጠን ግንዛቤ በዚህ ኩባንያ ለምርምር ልማት በየዓመቱ የሚወጣው ከ450-900 ሚሊዮን ብር ይሆናል ማለት ነው።

እንግዲህ ይህን ያለንበትን ዕውነታ ይዘን ነው የ2020 ርዕይ ምን የመስላል የሚለውን የምናስተናግደው።

4. በኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት የ2020 ርዕይ

ለውይይታች እንዲረዳን አስቀድሜ የኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ሊዳስሳቸው ይገባል፣ ለዚህም በቂ አቅምና ጊዜ ይኖራል በሚል የተወሰዱ ታሳቢዎችን አቀርባለሁ።

ለማናቸውም ዕድገት ዋናው ቁልፍ የተማረ የሰው ኃይል ማፍራት በመሆኑ የትምህርት ዘርፉን ሁልጊዜም ለየትኛውም ዘርፍ ቁልፍነቱ መጠቀስም መታየትም አለበት። በዚህ መሠረት የትምህርቱ ዘርፍ ኢንዱስትሪው ምርምር በሚፈልገው መጠንና ጥራት የሰው ኃይል ያቀርባል በሚል ታሳቢ ወስጃለሁ።

ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ዘላቂ ዕድገት ለመምጣት የሚከተሉት ጉዳዮች/ተግባራት ትኩረት እንዲያገኙና እንዲፈጸሙ ይደረጋል። የምርምር ተግባራቸውን በዘርፋቸው በባለቤትነት እየመሩ ያሉ ተቋማት ይጠናከራሉ፤ የሌላቸውም ይቋቋምላቸዋል የሚል ዕምነት ይኖረኛል። መንግሥት በማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ያለው ቀጥታ ተሳትፎ የሚቀንስ፣ ምናልባትም የሚጠፋ ቢሆንም፣ በኢንዱስትሪ ምርምር ተግባር ግን የማይናቅ ቁልፍ ሚና ይጫወታል። አሁን ካለንበት ደረጃ ተነስተን ወደ 2020 መሄድ ያለብን (ለዕውነተኛ ህልውና ቦታ ከሰጠነው) በእመርታዊ ዕድገት ነው። እነኚህ ዕመርታዊ ዕድገቶች ደግሞ እውን ከሚሆኑባቸው መንገዶች አንዱ ለኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ተገቢውን ትኩረት ስንሰጥ ነው።

በተለይ ለተወዳዳሪነት ብቁ በምንሆንባቸው፣ በጨርቃ ጨርቅ፣ በቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ በፖሊ አቀርቦት፣ በእትክልትና ፍራፍሬ ዝግጅት፣ በቅመማ ቅመም ዘይቶች፣ በመድኃኒት አዘል ዕፅዋት ዝግጅት እና በመሳሰሉት ላይ ተገቢውን ትኩረት ይሰጣል የሚል ዕምነት አለ።

ለማምረቻ ኢንዱስትሪ ዕድገት የሌሎች ዘርፎች በምርምር የተደገፉ ልማት ለዕመርታዊው ሰውጥ ወሳኝ ነው። በመሆኑም የእነርሱ በዕይታው መታቀፍ ተገቢ ነው የሚል ፅኑ እምነት አለኝ።

ከላይ የተጠቀሱ መሠረታዎ ተሳቢዎችን ከግምት በማስገባት ከዚህ ቀጥሎ በ2020 ዕውን ይሆናሉ ተብለው የሚጠበቁትን ዋና ዋና የኢንዱስትሪ ምርምር ልማት ውጤቶችን አቀርባለሁ::

በኤነርጂ ዘርፍ፤ በኃይድሮ የኤሌክትሪክ አቅርቦት ሂደት እየቀጠለ ይሄዳል፤ አነስተኛ ጅረቶችና ፏፏቴዎች ለአነስተኛ ተርባይኖች ማንቀሳቀሻነት ይውላሉ፤ በሶላር ኤነርጂ፤ በፎቶ ቮልታይክስ፣ በጂኦተርማል፣ በድንጋይ ከሰል እና በተፈጥሮ ጋዝ/ባዮጋዝ (በመጠኑ) ላይ የተመሠረተ የቴክኖሎጂ ሽግግሮች ይከናወናሉ::

የነዳጅ ዋጋ እያሻቀበ ስለሚመጣ ከኛ የመግዛት አቅም በላይ በከፍተኛ ፍጥነት ስለሚያድግ (በጋምቤላና በኦጋዴን በወሎና አፋር የነዳጅ ድፍድፍ ግኝት ዕውን ቢሆንም) በባዮዲዝል የሚደረገው ምርምር በአግሮ ኢንዱስትሪው የሚካሄደውን ጥናት በፍጥነት እንዲጎለብት ያደርጋል:: የዘይት ማምረቻው ወደ ባዮዲዝል መለወጫው ቴክኖሎጂ በኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ይደገፋል::

በማዕድን ዘርፍ፤ የነዳጅ ዘይት ግኝት በጋምቤላ፣ በኦጋዴን፣ በወሎ እና አፋር እውን ይሆናል:: በአመቺ አካባቢም የነዳጅ ማጣሪያ ይከፈታል፣ የተፈጥሮ ጋዝ ይለማል፣ የድንጋይ ከሰል፣ የፎስፌት፣ የብረትና የኢልማናይት ማዕድናት ልማት ይካሄዳል:: በኢንዱስትሪ ምርምር ላይ ተመስርቶ ፎስፌቱ ለሀገር ውስጥ ማዳበሪያ ማምረቻነት ይውላል፤ የያዩ ቢቂላል ልማት የምዕራብ ኢትዮጵያን ገፅታ ይለውጣል:: በምሥራቅ ኢትዮጵያም መሰል የልማት ገፅታ ለውጥ ይታያል፤ አሁን በመካሄድ ላይ ያሉ የማዕድናት ልማት ሥራዎች በምርምር በተጠናከረ መልኩ ይቀጥላሉ:: የማጥራትና የማዕድናትን ይዘት ከፍ ማድረጊያ ቴክኖሎጂዎች ሽግግር /እንደ ቤኔፊሺየሽን/ በኢንዱስትሪ ምርምር ልማት ይከናወናል::

በኮንስትራክሽን ዘርፍ፤ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች አማራጭ ቴክኖሎጂዎችና ማቴሪያሎች ላይ የምርምር ተግባር በሰፊው ይካሄዳል:: የገጠር መኖሪያ ቤቶች ደረጃ ከፍ የሚልበት የዲዛይን ምርምር ይካሄዳሉ:: የጎጆ አኗኗር ዘመቻ ይካሄድበታል:: የኮንስትራክሽን ዕቃዎች ለምሳሌ፤ የሲሚንቶ፣ የቺፕ ቦርድ፣ የሽክላ፣ ለአነስተኛ ኮንስትራክሽኖች ብረትን በቀርከሃ የመተካት፣ ለሞቃታማና ቆላማ አካባቢዎች ኤር ኮንዲሽኒንግና ሬፍሪጅሬሽን ቴክኖሎጂዎች ሽግግር በስፋት ይካሄዳል:: ለቴክኖሎጂዎች መረጣና ሽግግር የኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት አስተዋፅኦ ጎልቶ ይመጣል::

በዚህ ረገድ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር ተሳትፎ እየጎለበተ የሚሄድበት ሁኔታ እየተመቻቸ ይመጣል:: የምርምር ተግባራቸውም ሰፊ ቦታ ይኖረዋል:: የግብርናውን፣ የማዕድኑን፣ የኮንስትራክሽኑን እና የማኑፋክቸሪንጉን ቁርኝት በአንድ አነስተኛ ምሳሌ ማሳየት ይበቃል:: በቬርሞኒያ የዕፅዋት ዘይት ለቀለም ምርት ሲውል፤ ዕፅዋቱ በግብርና

ምርምር፣ ዘይት ማውጣቱ በኢንዱስትሪ እንዲሁም ሌሎች ተጓደኝ ግብዓቶች በማዕድኑ ዘርፍ ምርምርና ልማት የሚደገፍ ይሆናል።

በግብርና ዘርፍ፤ የግብርናው ምርምር ለማኑፋክቸሪንግ ኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎችን ለማቅረብ የሚደረገው እንቅስቃሴ እንዳለ ሆኖ፣ የኢንዱስትሪ ምርምሩ ዘርፍ ለግብርና በሚሆኑ የቴክኖሎጂ ግብዓቶች ላይ ያተኩራል። የማዳበሪያና የፀረ ተባይ ጉዳይ እንዳለ ሆኖ፤ ለመስኖ ቴክኖሎጂ/ኢሪጌሽን/፣ ለተስማሚ ማረሻዎች፣ ሰብል መውቂያዎች፣ ማጓጓዣዎች የሚሆኑ ተስማሚ ቴክኖሎጂዎችን በመምረጥ፣ በማቅረብ እና በማሻሻል የኢንዱስትሪ ምርምር ሰፊ ድርሻ ይኖረዋል። እንደ ጎማ ዛፍና አይል ፓልም የመሰሉ የኢንዱስትሪ ጥሬ ዕቃ ምንጮች በሰፊው የሚለሙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፤ እነዚህ ከብዙዎቹ በጥቂቱ የሚጠቀሱ ናቸው። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የምርምር አስተዋፅኦ በዚህ ዘርፍም እጅግ ከፍተኛ ይሆናል።

ከላይ የተጠቀሱትን ዓይነት ምሳሌዎች በብዛት ማቅረብ ይቻላል። ሆኖም እነዚህ የተመረጡት ጅምር እንቅስቃሴዎች ስላሏቸውና በኢንዱስትሪው ምርምር ቢታገዙ ለሀገራችን ዕመርታዊ ዕድገት ያመጣሉ ተብሎ ስለታመነ ነው።

ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን የኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ዕውን ለማድረግ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት አጋዥ ተገባራት ሊከናወኑ የሚገባቸው ናቸው።፦

- አጠቃላይ የፖሊሲ ምርምር፤ በተለይም የማምረቻ ኢንዱስትሪ እንዲያድግ፣ የሥራ አጥነት ችግር እንዲፈታ፣ ወዘተ... የተለያዩ የምርምር ሃሣቦች በፖሊሲ ላይ ተዕዕኖ እንዲያደርጉ ማድረግ።
- የኢንቨስትመንት ማነቆዎች የሚወገዱበትን መንገድ በማጥናት እና የሚተገበርበትን ስልት በመንደፍ ተግባራዊ ማድረግ። በዚህም የውጭ ቀጥተኛ ካፒታል ፍሰትን /FDI/ ማሳደግ።
- በኢትዮጵያ የሼር ኩባንያዎች የሚያድጉበት ሁኔታ ካልተመቻቸ የኢንዱስትሪ ዕድገት ይኖራል ብሎ ማሰቡ አስቸጋሪ ነው። የሰው የአብሮ የመሥራት፣ የመተጋገዝ፣ የመጠቃቀም ባህል በምርምር በተደገፈ መልኩ ሊጎለብት ይገባል። ለዚህም የሼር ኩባንያዎች የሚያድጉበት ስልት መቀየስ።
- የፋይናንስ ተቋማት ፕሮጀክት ቀርቦላቸው ፋይናንስ ለማድረግ የሚያዘግሙበት ሁኔታ ተለውጦ እንዲያውም የፕሮጀክቶች ያለህ የሚሉበት ሁኔታ መፍጠር።
- የውጭ ምንዛሪ ለሚያፈሩ እና የውጭ ምንዛሪ ለሚያድኑ የሥራ መስኮች ተጨማሪ ማበረታቻ መስጠት።
- የኢንዱስትሪዎቻችን ተወዳዳሪነት ለማጎልበት ዓለም አቀፍ ደረጃ እንዲኖረው የISO 9000 የHACCP እና የISO 1400 በብዙ ኢንዱስትሪዎች ተግባራዊ ማድረግ።

- የኢትዮጵያ የኤክስፖርት ኢንዱስትሪዎች በጠረፍ፡ አካባቢዎች የሚስፋፉበት ሁኔታ ማመቻቸት፣ ማለት በጂጂጋ፣ ሳዬ፣ ሞያሌ፣ ጋምቤላ፣ ኩምሩክ፣ መተማ፣ ሁመራ።። በተለየ መልኩ የደቡብ ሱዳንን፣ የገበያ ስፋት የቃኘ በጋምቤላ አካባቢ የኢንዱስትሪ ልማት ማስፋፋት።።
- የቻይናን፣ የህንድንና፣ የግብጽን የኢንዱስትሪ እንቅስቃሴ የሚከታተል ልዩ አካል መሰየም፤ በዚህ ዙሪያ ያልውን ጥሩና መጥፎ ጎን በመዳሰስ የኢንዱስትሪ ስትራቴጂ ነድፎ ለመንግሥት ማቅረብና ማስፈጸም።።
- በውጭ የሚኖሩ ትውልድ ኢትዮጵያውያን በሀገራችን የኢንዱስትሪ ምርምርና ልማት ተሳትፎ ከፍ፡ እንዲል ማድረግ።።
- የመንግሥት ተቋማት ለኢንዱስትሪው ዕድገት ዕውነተኛ አጋርነታቸውን እንዲያረጋግጡ ማድረግ፣ ማለትም የማነቆነት ባህል ተወግዶ በእንቅፋት አስወጋጅነት ባህል መተካት።።
- በእኛና በጎረቤቶቻችን ያለው ሰው ሠራሽ ድንበር የሚወገድበትን እና የኮንትሮባድ ቁጥጥር በአደገኛ ቁሶች ዝውውር ላይ ብቻ የሚያተኩርበትን ሁኔታ መፍጠር።። ለዚህም የመንግሥት የገቢ ምንጭ በሀገር ውስጥ በሚደረግ እንቅስቃሴ ዕድገት ላይ እንዲወሰን ማድረግ።። ይህ ያለችንን ላም ብዙ በማለብ ሳይሆን ብዙ ላሞችን በማፍራት እንዲያድግ ማድረግ የሚጠይቅ ነው።።
- ለኢንዱስትሪ ልማት የሚሆን የፋይናስ ምንጭ ከተፋሰሶቻችን ሮያልቲ ለማግኘት የፖሊሲ ምርምር ማድረግ።። የድርድር ስልት መቀየስና መተግበር።።
- የፓተንት እና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ በየኢንዱስትሪ ተቋማት መዋቅር ውስጥ መፍጠር።። በጠቀሜታቸው ላይም ከፍተኛ የአህዝቦት ሥራ ማካሄድ።።

አመስግናለሁ!

ሥርዓታት፣ የፖለቲካ ነፃነት* እና ልማት** በኢትዮጵያ

የራስወርቅ አድማሴ***

ፍሬ-ነገር

ለማንኛውም ህብረተሰብ የሰመረ ሕልውና እና ዕድገት፣ ጠንካራና ሕያው ህብረተሰባዊ ሥርዓታቱ ወሳኝ ናቸው። ዘርፈ-ብዙ የሆኑት ሥርዓታት የሚያበረክቱት ፋይዳዎች ብዛትና አይነትም መተኪያ የሌላቸው የህብረተሰብ አውታሮች ያደርጋቸዋል።

የኢትዮጵያ ህብረተሰብ ካለበት ወሳኝ ደክመቶች አንዱ ዋና ዋና ተግባሮቹን የሚያከናውንባቸው ሥርዓታት በበቂ የሌሉት መሆኑ ነው። ህብረተሰባችን ፈጣን ዕድገትን በማስመዝገብ በአንድ ትውልድ ዕድሜ አሁን ካለበት የድህነት አረንቋ እንዲወጣ ከተፈለገ ደግሞ፣ በየህብረተሰባዊ ዘርፎቹና የኑሮ መስኩቹ ሁሉ ጠቃሚ፣ ሕያው፣ እናም፣ ድርጊት-አጋዥ የሆኑ ሥርዓታትን በብዛት መፍጠር ያሻል።

ጠንካራ ሥርዓታት ዓይነተኛ መልኩ የሆኑበት ህብረተሰብን እውን ለማድረግ የሚቻለው ደግሞ፣ የሕግ የበላይነትና በሕግ ፊት መንግሥትን ጨምሮ የሁሉም ዕኩልነት ሲረጋገጥ፣ እንዲሁም የሕግ አውጭው አካል የተሟላ-ተቀባይነት/አመኔታ ሲኖረውና የፍትሕ አካላት በሙሉ ነፃነት ሲሰሩ ብቻ ነው። እንደ ኢትዮጵያ ባለ በህዝብ ብዛቱና በመሬት ሥፋቱ ግዙፍ፣ በሆነ፣ በአንድ-ወጥነት ሳይሆን በልዩነት ባሸበረቀ፣ ተፈጥሮዊን ጨምሮ በርካታ የተቆላለፉ ችግሮች በተጋረጠበት አገር ደግሞ የህግ የበላይነትንና በሕግ ፊት የሁሉንም ዕኩልነት ለማረጋገጥ የሚቻለው የተሟላ የፖለቲካ ነፃነትን በማስፈን ብቻ ነው።

1. መግቢያ

ይኽ ፅሁፍ የሚያተኩረው በሀገራችን የሥርዓታት ጉዳይ ላይ ሲሆን፤ ዋና ዓላማውም ሥርዓታት ከሶሲዮ-ኢኮኖሚክ ልማትና ከፖለቲካ ነፃነት መሳልበት ጋር ያላቸውን ትስስር

---

* በዚህ ፅሁፍ ውስጥ «የፖለቲካ ነፃነት» የተሰኘውን ቃል-ሃረግ የምንጠቀምበት የአንድን ሰው/ዜጋ ከፖለቲካ ስልጣን ጋር በተየያዘ ዓላማውን የማራመድ፤ ሃሳቡን በነፃ የመግለፅ፤ የመደራጀት የማደረጀትና፤ ለፖለቲካ ስልጣን በምርጫ የመወዳደርና የመምረጥ መብቶች ተጠቃሚ መሆንን ለማመልከት ሲሆን፤ የእነዚህ መብቶች መኖርም ሌሎች ሰዎች ያሏቸውን ተመሳሳይ መብቶች ማክበርን ታሳቢ ያደርጋል።

** በዚህ ፅሁፍ ውስጥ «ልማት» የተሰኘውን ቃል የምንጠቀምበት፤ የኢኮኖማ ዕድገትን፤ ፋይዳዊ የሆነ የንብረት አጠቃቀምንና ዘመናዊነትን የሚያስገኝ ፈጣን የኢኮኖሚና የሶሺያል ለውጥን ለማመልከት ነው።

*** ዶ/ር የራስወርቅ አድማሴ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ሶሲዮሎጂና ሶሻል አድሚኒስትሬሽን ዲፓርትመንት ረዳት ፕሮፌሰር ነው። Fil Kand ዲግሪውን እና ሰፐሊመንተሪ ሰርቲፊኬት በሶሲዮሎጂ ከUppsala ዩኒቨርሲቲ አግኝቷል። ከማህበራዊ ጉዳይ ጋር በተያያዘ በደን የዶክትሬት ዲግሪውን እንዲሁ በሶሲዮሎጂ ከLund ዩኒቨርሲቲ፤ ስዊድን እንዲሁም በልማት፣ በመሬት መከላትና አጠባበቅ፣ በገጠር ልማት፣ እንዲሁም በክተማች ጉዳዮች ላይ ሰፊ የምርምር ሥራዎችን ሰርቷል። ከ1997 እስከ 1999 ድረስ በኢትዮጵያ አካሂዷል፤ እንዲሁም ተመሳሳይ ምርምሮችን በኬንያ። ዶ/ር የራስወርቅ እ.ኤ.አ ከ1997 እስከ 1999 ድረስ የኢትዮጵያ ሶሲዮሎጂስቶች፤ ሶሻል ወርከሮችና ሶሻል አንትሮፖሎጂስቶች ማህበር ፕሬዚዳንት ሆኖ ያገለገለ ሲሆን፤ የማህበራዊ ጥናት መድረክ መስራች፤ እና በአሁኑ ጊዜ የቦርድ አባል በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛል።

1991; Dejene Aredo, 1999) ስሲዬሎጅስቶቹ «የኢክተር-ሲስተም ዳይናሚክስ» ቲዩሪቲሽያኖች (Burns *et al., 1985*) በመሰረቱ የሚጋሩት ትርጉም የኖቤል ሽልማት ሎሬቱ፣ ዳግላስ ኖርዝ (Douglas North) የሰጠውን ትርጉም ነው። ይኸውም፣ የሚከተለው ነው።

ኢንስቲቱዩሽኖች የሰዎችን የእርስበርስ ግንኙነቶችን መልክ የሚያስይዙ እንደ እርሞች፣ ወሎች፣ ልማዶች፣ ሥነ-ምግባሮች የመሳሰሉ ደርዝ-የለሽ ደንቦችንና፤ እንደ ሕገ-መንግሥቶች፣ ሕጐች፣ እና የንብረት መብቶች ያሉትን ባለ-ደርዝ ደንቦች የሚየቅፉ ሰው-ሰራሽ ማዕቀቦች ናቸው (1991: 97)።[1]

የአላን ጆንሰን ብላክዊል የሶሲዬሎጅ መዝገበ-ቃላት (Allan Johnson, The Blackwell Dichtionary of Sociology, 1995) በበኩሉ፣ ለኢንስቲቱዩሽን የሚከተለውን ከፊት ያለ ፍች ይሰጠዋል።

ኢንስቲቱዩሽን ቋሚነት ያለውና በህብረተሰብ ውስጥ ዋና የሆኑ ተግባሮች እንዴት እንደሚከናወኑ የሚያመለክት የመሪ-ሃሳቦች ስብስብ ነው።[2]

አንዳንድ ፀሐፊዎች በበኩላቸው፣ «ኢንስቲቱዩሽን» ህብረተሰባዊ ግንኙነቶችን መልክ የሚያሲዙ ደንቦችን፣ ሕጐችን ወይም ወጐችን የሚያቅፍ ህብረተሰባዊ ጥንቅርን ከማመልከት ይልቅ በእርሱ አማካይነት የሚገኘውንና በቋሚነት መልክ-የያዘዉን የሰዎች ባህርይ (regulated patterns of behavior) የሚያቅፍ ነው በማለት በአፅንኦት ይከራከራሉ (Berry, 1989: Leach et.al. 1999; Peters, 2000)።

በተጨማሪ፣ «ኢንስቲቱዩሽን» የተሰኘው የእንግሊዝኛ ቃል እንደ ትዳር፣ ገበያ፣ ገንዘብ፣ ወይም ትምህርት ያሉትን ሕብረተሰባዊ ግንኙነቶችን መልክ የሚያሲዙ ደንቦችን፣ ሕጐችንና ወጐችን የሚያቅፍ ሕብረተሰባዊ ጥንቅርን ብቻ ሳይሆን፤ ባለ-ደርዝና ደርዝ-የለሽ የሆኑ (ፎርማልና ኢንፎርማል) «ኦርጋናይዜሽንስን» ጭምር ያመለክታል ብለው የሚያምኑና በዚህ ተደራራቢ መልኩ የሚጠቀሙበት ምሁራንም አሉ። በዚህም የተነሳ፣ በአሁኑ ጊዜ፣ «ኢንስቲቱዩሽን» የተሰኘው ቃል ሕጐችን፣ ደንቦችን ወይም ወጐችን የሚያቅፍ ጥንቅርን ከመግለፅ ይልቅ ሰዎችን የሚያቅፈውን «ኦርጋናይዜሽን/ድርጅትን» ወይም የተለያዩ የድርጅት መልኮችን የሚያመለክት እየሆነ መጥቱዋል። በእኛ አስተያየት፣ ይኸን ቃል ለሁለት ተደራራቢ ፅንሰ-ሃሳቦች ማመልከቻነት ማዋሉ ከአስገኘው ጥቅም ይልቅ ገዳቱ ያመዝናል። መንታ የሆነው የቃሉ አጠቃቀም በብዙ ሰዎች ዘንድ «ኢንስቲቱዩሽን» ማለት ይበልጡኑ «ኦርጋናይዜሽን»፣ «ኢንስቲቱዩት» ወይም «ሰትራክቸር» ማለት ሆኖ እንዲወሰድና የአስተሳሰብ ብዥታ እንዲፈጠር ረድቱዋል። የጊዜው ዓቢይ ተግባርም በዚህ ፅንሰ-ሃሳብ ለይ ግልፅነትን ማስገኘት ይመስለናል።

---

[1] Institutions are humanly devised constraints that structure political, economic and social interaction," and consist of internal rules such as taboos customs, traditions and codes of conduct, as well as formal rules including constitutions, laws and property rights.

[2] An institution is an enduring set of ideas about how to accomplish goals generally recognized as important in society.

በዳግላስ ኖርዝ አገላለፅ ኢንስቲቱዩሽን «የግጥሚያው ደንቦች» ጥንቅር ሲሆን «ድርጅት» ደግሞ የግጥሚያው ተሳታፊ የሆኑ ግለ-ሰቦች ስብስብ ነው። (North, 1990: 5) ምንም እንኳን «ኦርጋናይዜሽን/ድርጅት»ም ራሱ በውስጠ-ደንቦች የሚገዛ ቢሆንም፤ ቃሉ በዋናነት የሚያመለክተው ዕንሰ-ሃሳብ፣ በጋራ ተልዕኮዎች የተሳሰሩና ለጋራ ዓላማዎች በአንድነት የቆሙ የግለሰቦችን ስብስብ ነው። ስለዚህም ይሄኛው ዕንሰ-ሃሳብ፤ «ኢንስቲቱዩሽን» የተሰኘው ቃል ከሚያመለክተው ዕንሰ-ሃሳብ ጋር ግንኙነት ቢኖረውም ቅሉ የተለየ ነው።

የአክተር-ሲስተም ቲዮሪም የሚያወሳው እንደ ትዳር፣ ገበያ፣ ገንዘብ፣ ቤተሰብ፣ ትራፊክ፣ ትምህርት የጤና-ጥበቃ ያሉ ኢንስቲቱዩሽኖች ምንም ይኽ ነው የሚባል አንድና ብቸኛ ድርጅታዊ መገለጫ የሌላቸው መሆኑን ነው። እንዲያውም የጋብቻ መዝገብ ቤቶች፣ሱቆች፣ ባንኮች፣ የቤተሰብ-ችሎት፣ የትራፊክ-ፖሊስ ክፍል፣ የትራፊክ-ችሎት እና ትምህርት-ቤቶች ሃኪም-ቤቶችና ላቦራቶሪዎች ወዘተ... የመሰሉ ድርጅቶች የሚፈጠሩትና የሚኖሩት ኢንስቲቱዩሽኖች በምንላቸው የህጐች፣ ደንቦች ወይም ወጐች ጥንቅር በሆኑ፣ ትዳር፣ ገበያ፣ ገንዘብ፣ ቤተሰብ፣ ትራፊክ፣ ትምህርትና፣ ጤና-ጥበቃ ላይ በመመስረት ነው። ትራፊክ፣ የትራፊክ ደንቦችን ያቀፈ ህብረተሰባዊ ሥርዓት ሲሆን፤ የትራፊክ-ፖሊስ፣ የትራፊክ-ችሎትና፣ የመኪና-አነዳድ ትምህርት-ቤቶች ግን ድርጅቶች ናቸው። ገበያ፣ ፕሬስና፣ ትዳር ህብረተሰባዊ ሥርዓታት ሲሆኑ፤ ጅንአድና ሜጋ፣ ሪፖርተርና አዲስ ዘመን እናም የአቶ እከሌና የወይዘሮ እከሊት ትዳር ደግሞ የተወሰኑ የገበያ፣ የፕሬስና፣ የትዳር ድርጅቶች ናቸው - በዚያው ቅደም ተከተል።[3]

ከላይ የቀረቡትን ሃተታዎች መሠረት በማድረግ በዚህ ፅሁፍ ውስጥ ኢንስትቲቱዩሽን የተሰኘውን ቃል የምንረዳው እንደሚከተለው ነው።

ኢንስቲቱዩሽን ማንኛውም ህብረተሰብ ያፈለቃቸውንና የሚጋራቸውን ደርዝ የያዙና ያልያዙ፣ ደንቦችንና ወጐችን ያቀፈና በነሱም የሚገዛ ሕብረተሰባዊ ጥንቅር ሲሆን፤ ከዚህም የሚፈልቀውንና በቋሚነት መልክ የያዘ ባህርይን (የምግባር ዘይቤን) ወይም ልማድን ሊጨምር ይችላል። ሕጐቹ፣ ደንቦቹ ወይም ወጐቹ ማን እንደሚሳተፍ ማን እንደሚገለል፣ ማን፣ ምን፣ መቼ፣ ከማን ጋር፣ እንደሚያከናውን በሰፊው የሚገልፁ ናቸው።[4]

«ኢንስቲቱዩሽን» የተሰኘው የእንግሊዝኛ ቃል፣ «ኢንስቲቱዩት»፣ «ኦርጋናይዜሽን» እና «ስታራክቸር» የመሳለሉትን ዕንሰ-ሃሳቦች ጭምር ለማመልከቻ ተደርጐ በሰፊው በስራ ላይ በመዋሉ የተነሳ የትርጉም መመሰቃቀልና የአስተሳሰብ ብዥታን ማስከተሉን ከላይ አመልክተናል። ባለፉት ሃምሳና ስልሳ ዓመታት ደግሞ፣ ሳይንስ-ነክ የሆኑ የአማርኛ ቃላት አፍላቂዎችና ተጠቃሚዎች በእንግሊዝኛ የሚያስቡ ከመሆናቸው የተነሳ፤ የብዙ አማርኛ

---

[3] አክተር-ሲስተም ዳይናሚክስ ቲዎሪ ይህንን ልዩነት እንደሚከተለው ይገልጸዋል። "A *social institution* is a rule regime which applies to a particular sphere of activity or class of settings and governs the social action and interaction of agents engaged in the sphere. Labour and commodity markets, capitalist enterprises, government agencies, ... A *social organization*—a particular market enterprise, agency or family—is a specific instance of a social institution, a systeme of rules applied in a concrete setting with particular blood and flesh actors engaged" (Burns *et al.*, *1985:263-4)*.

[4] An institution is understood as any social arrangement that is constituted and regulated by formal and informal rules that are socially constructed and shared, specifying to a large extent who may or should participate and who is excluded, and who should do what, when, how, in relation to whom, to which one can add the patterned behaviour it thus engenders (author's translation).

ቃላት አጠቃቀም የእንግሊዝኛውን እየተከተለ ሄዷል። በዚህም የተነሳ፣ ልክ «ኤንስቲቱዩሽን» የተሰኘው የእንግሊዝኛ ቃል «ኢንስቲቱዩት»፣ «ኦርጋናይዜሽን» እና «ስታራክቸር» ከሚሉት ቃላቶች ጋር እየተመሰቃቀለ እንደመጣው ሁሉ፣ ወደ አማርኛ በሚተረጎምበትም ጊዜ፤ «ተቋም»፣ «ድርጅት» እና «መዋቅር» ከተሰኙት የአማርኛ ቃላት ጋር እየተነባበረና እግረመንገዱንም ቀድሞዉኑ በእንግሊዝኛው ቋንቋ የሰፈነውን ብዥታ ወደ አማርኛ ቋንቋ እያዛመተው ሄደ። በመሆኑም «ኢንስቲቱዩሽን» የተሰኘው ቃል ከቆመለት ፅንሰ-ሃሳብ ጋር በጥብቅ የተያያዙና ቀደም ባለው ጊዜ ሃሳብን በትክክል ለመግለጫ በሰፊው ይሰራባቸው የነበሩት «ሥርዓት» «ደንብ» እና «ወግ» የተሰኙት የአማርኛ ውብና ጠቃሚ ቃላት እያደር ከጥቅም ውጭ እየሆኑ መጡ።

የአለቃ ኪዳነወልድ ክፍሌ «መፅሐፈ ሰዋስው ወግሥ፡ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ» (1948 እ.ኢ.አ)፣ «ሥርዓት» የተሰኘውን ቃል እንደሚከተለው ይፈታዋል።

ሥርዓት (ታት)፤ መሥራት፤ መሠራት፤ አሠራር፤ ሥራት፤ ደንብ፤ አገባብ፤ ህግ፤ ትእዛዝ፤ ዓዋጅ፤ ፍርድ፤ ልማድ፤ የሥራ መንገድ።

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል (1993 እ.ኢ.አ) ያወጣው አማርኛ መዝገበ-ቃላት በበኩሉ፣ ስርአትና ደንብ፤ የተሰኙትን ቃላት እንደሚከተለው ይፈታቸዋል።[5]

ስርአት 1. አንድ ነገር የሚሰራበት ወይም የሚከናወንበት ደንብ፣ ህግ።
2. ወግ፣ ባህል።

ደንብ (ደምብ) 1. የተወሰነ ህግ፣ ድንጋጌ፣ ስርአት። 2. ወግ ልማድ።

ከዚህ እንደምናየው እነዚህ ሁለት መዝገበ-ቃላት «ሥርዓት»፣ «ደንብ»፣ «ድርጅት»፣ «ተቋም» እና «መዋቅር» ለተሰኙት የአማርኛ ቃላት ምንም ማብራሪያ የማይጠይቁና የማያሻሙ ትርጉሞች ይሰጧቸዋል። በተጨማሪ፣ ሁለቱም መዝገበ-ቃላት ባንድ በኩል «ሥርዓት»፣ «ደንብ»፣ «ሕግ»፣ «ወግ» እና «ልማድ» የተሰኙት ቃላት በቆሙላቸው ፅንሰ-ሃሳቦች መካከል ያለውን ቁርኝት፤ በሌላ በኩል ደግሞ እነዚህ ቃላት ባንድ በኩል ሆነው፤ «ድርጅት»፣ «መዋቅር» እና «ተቋም» ከሚሉት ቃላት ጋር ያላቸውን ልዩነት በሚገባ ያሳያሉ። ስለዚህ ብዥታውንና መምታታቱን የፈጠረው የአጠቃቀምና የአስተሳሰብ ችልተኛነት እንጅ የቋንቋዉ ጉድለት እንዳልሆነ እንረዳለን። እኛም በማያሻማ መንገድ፣ «ኢንትቲቱዩሽን»ን «ሥርዓት»፣ «ሩልስ»ን ደግሞ «ደንብ» ብለን በመተርጎም እንጠቀምባቸዋለን።

በተጨማሪም «ሥርዓት» የተሰኘውን ቃል በተመለከተ ለአንባቢ አንድ ተጨማሪ ማሳሰቢያ መሰጠት እንወዳለን። ያሁኑ ትውልድ ሥርዓት የተሰኘውን ቃል ብዙውን ጊዜ የሚሰማውና የሚጠቀምበት «ሥነ-ሥርዓት» በተሰኘው ቃል-ሃረግ ውስጥ ውሎ ነው። በዚህ ዓይነት «ሥርዓት» የተሰኘው ቃል «ሥነ-ሥርዓት» ከሚለው ጋር በመጣጋቱ የተነሳ ጭራሹን

---

5 በተጨማሪ ይኸው አዲሱ መዝገበ ቃላት «ድርጅት»፣ «መዋቅር» እና «ተቋም»ን እንደሚከተለው ይፈታቸዋል።
ድርጅት (ስ) 1. የተወሰነ የስራ አይነት የሚካሄድበት ወይም የሚከናወንበት የስራ ተቋም (ፋብሪካ፣ ሆቴል፣ ...)። 2. ዝግጅት። 3. የተወሰነ አላማን ለማራመድ ሰዎች በአባልነት የሚሰበሰቡበት ማዕከል፣ ማህበር ...።
መዋቅር (ስ) 1. ከዋልታ እስከ ታዛ የሚወርድ ዋና ዋና የጣሪያ እንጨት፣ ወራጅ። 2. አንድ ድርጅት የተመሰረተበት ልዩ ልዩ ክፍሎችና ውስጣዊ ግንኙነታቸው፣ አደረጃጀታቸው።
ተቋም(ስ) ልዩ ልዩ መርምርና ጥናት የሚካሄድበት፣ የልዩ ልዩ ሙያዎች ስልጠና የሚሰጥበት ድርጅት።

በኋለኛዉ በመዋጥ «ዲሲፖሊን» «ኦርዶር» እና «ፕሮቶኮል» እንደማለት ተደርጐ ይወሰዳል። ይኸም «ሥርዓት» የተሰኘውን ቃል በተመለከተ ሌላ ተጨማሪ ብዥታን ያስከተለ ይመስለናል።

ሥርዓት ማለት ማንኛውም ህብረተሰብ ያፈለቃቸውና የሚጋራቸው ሕጐችን ደንቦችን ወይም ወጐችን ያቀፈና በነሱም የሚገዛ ሕብረተሰባዊ ጥንቅር እንደሆነና፤ ሕጐቹ፣ ደንቦቹ ወይም ወጐቹ ማን እንደሚሳተፍ፣ ማን እንደሚገለል፤ ማን፣ መቼ፣ ከማን ጋርና፣ እስከ ምን ደረጃ ድረስ፣ ምን እንደሚያከናውን፤ ወዘተ... የሚወሰኑ/የሚያመለክቱ መሆናቸውን አይተናል። ስለዚህ፣ ህብረተሰባዊ ሥርዓታት የምንላቸው፣ እንደ ትዳር፣ ቤተሰብ፣ ሃይማኖት፣ መንግሥት (state)፣ ትምህርት፣ ሕግ (አዎን ራሱ ሕግም)፣ እና የመሳሰሉትን ዋና ዋናዎቹን ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ደረጃና በየህብረተሰባዊ መስኩ ያሉትን ሁሉ ጭምር ነው። ከዚህም የተነሳ ሥርዓታትን በደረጃ መልክ ከፋፍለን መገንዘቡ ሊጠቅም ይችላል።

1ኛ. ህብረተሰብ-አቀፍ ሥርዓታት፡- እነዚህ በህብረተሰቡ በመላ የተንሰራፉና ማንኛውንም የህብረተሰብ አባል የሚመለከቱ አይነት ዋነኛ ሕጐችን፣ ደንቦችንና፣ ወጐችን የሚያቅፉ ናቸው። (ለምሳሌ፣ ትዳር፣ ቤተሰብ፣ ሃይማኖት፣ መንግሥት፣ ሕግ፣ ትምህረት፣ ጤና ጥበቃ፣ እና የመሳሰሉት ሕብረተሰብ-አቀፍ ሥርዓታት ናቸው።)
2ኛ. መስክ-ተኮር ሥርዓታት፡- እነዚህ ልዩ ልዩ የኢኮኖሚ፣ የሶሽያልና ፖለቲካ/አስተዳደር ዘርፎችን የሚመለከቱ ደንቦችን የሚያቅፉ ናቸው። (ለምሳሌ፣ የሆነ የንግድ ወይም የምርት ዘርፍ፣ የሆነ የትራንስፖርት ወይም የመገናኛ ዘርፍ፣ የኢንፎርሜሺን-ቴክኖሎጅ፣ የአካባቢ-ጥበቃ፣ የሆነ የመዝናኛ ዘርፍ ሥርዓት፣ እና የመሳሰሉት መስክ-ተኮር ሥርዓታት ናቸው።)

3. የሥርዓታት ፉይዳዎች

ሥርዓታት፣ ማን፣ ከማን ጋር፣ እንዴት፣ እና በምን መልክ እስከ ምን ደረጃ ድረስ፣ ምንን በተመለከተ፣ ምን እንደሚያደርግ ያመለክታሉ፣ ይወስናሉ፤ በመሆኑም የሰዎችን ባሕርይ መልክ ያሲዛሉ ብለናል። በዚህም የተነሳ የሚከተሉት ዋና ዋና ፉይዳዎች አሏቸው።[6]

አንደኛ፣ ሥርዓታት በሰዎች፣ በቡድኖች፣ በድርጅቶች፣ በመንግሥታዊ አካላት፣ ወዘተ... መካከል የሚኖረውን ግንኙነት በመወሰን ወይም ግልፅ በማድረግ የመረጃ ልውውጥ ወጭን/ድካምን ይቅንሳሉ። ሥራ ያለእክልና በፍጥነት ይከናወን ዘንድ ሁኔታዎችን በማመቻቸት፣ የሚያሠራ ሁኔታ እንዲፈጠርና እንዲቀጥል ይረዳሉ።

ሁለተኛ፣ ሥርዓታት፣ ሰዎችን ምን እርምጃ ቢወሰዱ ወይም ባይወሰዱ ምን ወጤት አንደሚከተል ወይም ሳይከተል አንደሚቀር --በተወሰነ ደረጃም ቢሆን-- በእርግጠኛነት ለመተንበይ ያስችሏቸዋል። ስለዚህም፣ መጭውን ወይም የወደፊቱን ሁኔታ ከወዲሁ ታዋቂ በማድረግ ስጋትን ይቀንሳሉ። በተያያዥም፣ አንዱ ሰው የሌላውን ዕርምጃ አስቀድሞ ይገምት

---

[6] እዚህ ላይ የምንነገረው ያለው ስለ ሥርዓታት አጠቃላይ ጠባይ ነው። በዚህ ክፍል የተዘረዘሩትም የሥርዓት ፉይዳዎች ሥርዓታትን ባጠቃላይ የሚመለከቱ ናቸው እንጂ ይዜን ወይም ያንን የተወሰነ ሥርዓት የሚመለከቱ አይደሉም። ይኸም ማለት አንድ የተወሰነ (specific) ሥርዓት በአንድ የተወሰነ ወቅት ፉይዳ ላይኖረው ወይም እስከነአካቴው በፉይዳዎች ፉንታ ጎጅ ጠባዮቹ ያመዘኑበት ሊሆን ይችላል ማለት ነው።

ዓለምአቀፍ የዘይት ኩባንያዎቻቸውን ጥቅም ላለመጉዳት የሚደረግ ትግል መሆኑ ይታወቃል።

ከላይ ከተነሱት ነጥቦች መረዳት የሚቻለው ትልቅ ቁምነገር ነዳጅ (ኢነርጂ) ትልቅ የፓለቲካ መሳሪያ ጭምር መሆኑና ብርቱ ጥረት አድርጎ የአገር ውስጥን የኢነርጂ ምንጭ ማልማት ከኢኮኖሚያዊና ማሕበራዊ ጠቀሜታው ባሻገር ትልቅ ፓለቲካዊ ጠቀሜታ እንደአለው መገንዘብ ይቻላል።

4 የኢነርጂ ልማትና የተጠቃሚነት ዕድል (Access) በኢትዮጵያ - አሁን ያለው ሁኔታ

የኢትዮጵያን የኢነርጂ ዘርፍ በሁለት ታላላቅ ክፍሎች (ዓይነቶች) - ባሕላዊ (traditional)ና ዘመናዊ - ወይም በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ክፍሎ ማየት ይቻላል። እነሱም፤ ሀ) ባሕላዊ (traditional) ማገዶና የእንስሳት (animate) ኢነርጂ[10] ለ) ነዳጅ ዘይትና ሌሎች የከርሰ ምድር ነዳጆች (fossil fuels) ሐ) የኤሌክትሪክ ኃይል (power) እና መ) ዘመናዊ ታዳሽ የኢነርጂ ምንጮች ናቸው። የመጀመርያው አከፋፈል መደበኛና ድርርቦሽ የሌለው ነው። ይሁን እንጂ ምንጮች ናቸው። የመጀመርያው አከፋፈል መደበኛና ድርርቦሽ የሌለው ነው። ይሁን እንጂ ምንጮች ናቸው። የመጀመርያው አከፋፈል መደበኛና ድርርቦሽ የሌለው ነው። ይሁን እንጂ ይህ አከፋፈል አንዳንድ ዋና ዋና ክፍሎችን የመሸፈን ችግር አለው። ሁለተኛው አከፋፈል ይህ አከፋፈል አንዳንድ ዋና ዋና ክፍሎችን የመሸፈን ችግር አለው። ሁለተኛው አከፋፈል የድርርቦሽ ችግር (ለምሳሌ. የኤሌክትሪክ ኃይልና ዘመናዊ ታዳሽ የኤነርጂ ምንጮች) ያለው ቢሆንም በአገራችን ካለው ሁኔታ ጋር በግልጽ የሚዛመድና የዘርፉን ክፍሎች ለያይቶ ለመመልከት የሚያስችል በመሆኑ ተመራጭነት አለው። ቀጥሎ የቀረበው የዘርፉ ቅኝት ይኸንን አከፋፈል የተከተለ ነው።

4.1 የኢነርጂ ምንጮቻችን የልማት ደረጃ

ሀ) ባሕላዊ ማገዶና የእንስሳት ኤነርጂ

በኢትዮጵያ ዋነኛው ባሕላዊ ማገዶ እንጨት፣ የሰብል ትራፍች (crop residues)፣ ከብት[11] እና የእንጨት ከሰል ናቸው። እነዚህ የኤነርጂ ምንጮች አብዛኛውን የአገራችንን የኤነርጂ ፍላጐት የሚሸፍኑ ከመሆናቸውም በላይ በአገር ውስጥ የሚገኙና በባሕላዊ መንገድ የሚመረቱ ናቸው። ይሁን እንጂ አነስተኛ ድርሻ ካላቸው ከሰብል ትራፍችና ከከብት በቀር ዋነኛው ምንጭ ማለትም እንጨትና ከርሰ የሚመረተው ከሰል በአብዛኛው የሚገኝት ከደን ሀብት በመሆኑና የደን ሀብቱ እየተመናመነ በመሄዱ (ከ40% ወደ 2.8% ወርዷል) [7] ባሕላዊ ማገዶ የሚገኝበት ሁኔታ የልማት ሳይሆን የጥፋት ነው ለማለት ይቻላል። የደን ሀብታችን መመናመን የተፈጥሮ አካባቢ ውድመትን እያስከተለ ያለ ጉዳይ መሆኑ በስፋት

[10] የእንስሳት (animate) ኤነርጂ የሰውንም ይጨምራል።
[11] ከብት። ፋንዲያና የመሳሰሉትን ሁሉ ይጨምራል።

ስድስተኛ፣ ሥርዓታት ህብረተሰባዊ-ካፒታል (ሶሻል-ካፒታል) እንዲዳብር በር ይከፍታሉ። በአንድ ሕብረተሰብ ውስጥ ሰዎች በአንድነት ተቀናጅተው (ቦንድ አድርገው) በመተጋገዝ ውስን የሆኑ ቁሳዊና ሌሎች እንደመተማመን፣ እውቀት፣ ችሎታ፣ ዓይነት ንብረቶችን ለማንቀሳቀስና በጥቅም ላይ ለማዋል የላቸው ችሎታ ሶሻል-ካፒታል ይባላል። ሶሻል-ካፒታል ንብረቶቹ ራሳቸው ሳይሆኑ፣ ንብረቶቹን በተፈለገ ጊዜ አንቀሳቅሶ ለመጠቀም የሰዎቹ ስብስብ ወይም ቡድን ያለው ህብረተሰባዊ አቅም ነው። ስለዚህም ሶሻል-ካፒታል እንደንብረቶቹ በጥቅም ላይ በዋለ መጠን አይፈጅም-አያረጅም፣ አያልቅም። እንዲያውም እያደገ፣ እየጨመረና እየበረታ ይሄዳል እንጂ (Long, 2001: 132-4)። በእንደዚህ፣ በተለይ ኋላ ቀር በሆኑ ሃገራት ልማት ውስጥ እንደ ኢኮኖሚ-ካፒታል እና የሰው-ካፒታል ሁሉ ወሳኝ ሚና ሊጫወት የሚችለውን ይህን ሶሻል-ካፒታል በማስገኘት በኩል ሥርዓታት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። የውስጥ ልማዳዊ ሥርዓታቱን ጠብቆ ያቆየው የጉራጌ ሕዝብ በዚህ የተነሳ የማይናቅ ሶሺያል-ካፒታል ባለቤት በመሆን ለአባላቱና ለሃገር ልማት ከፍተኛ ጥቅም ያስገኘ በት ሂደት የዚህን ክስተት ምንነትና ከሥርዓታት መኖር የሚመነጭ መሆኑን በተጨባጭ ያስረዳል።

ሰባተኛ፣ ሥርዓታት የሚያቅፏቸው ደንቦች ለሰዎች ያሏቸውን ሕጋዊ መብቶችና ያለባቸውን ሕጋዊ ማዕቀቦች ግልፅ አድርገው ስለሚያመለክቷቸው፣ ያለተጨማሪ ድጋፍ የሚያገኙትንና ማግኘት የማይገባቸውን ጠንቅቀው እንዲያውቁ ያደርጓቸዋል። በዚህም የተነሳ መስናና ከጥቅም ፍለጋ ጋር የተያያዘ የፖለቲካ አድርባይነት የሚስፋፋበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ይረዳሉ። በእንደዚህም ለኢኮኖሚ ልማትና ለፖለቲካ ነፃነት ዕውን መሆን ተጨማሪ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ።[8]

ስምንተኛ፣ ሥርዓታት የሚያቅፏቸውን ደንቦችና ወጎች የሥርዓታቱን ይዘት ብቻ ሳይሆን ዳር-ድንበሮቻቸውንም ጭምር በግልፅ ለይተው ስለሚያሳዩ፤ የዴሞክራሲና[7] የፖለቲካ ነፃነት መሠረት የሆነው የሦስቱ የመንግስት አካላት -- የሕግ-አውጭው፣ የሕግ-ተርጓሚውና የአስፈፃሚው -- የሥልጣን መለያየት እንዳይደበዝዝና እንዳይሸረሸር ይረዳሉ።

ዘጠነኛ፣ ሥርዓታት፣ በዴሞክራሲ ፋክክር ውስጥ ተፎካካሪዎች ሊወሰዷቸው የሚችሉት ዕርምጃዎች ለተፎካካሪዎቹ መልካም-ፈቃድ ከተተው ሊመጣ የሚችለውን አደጋ በማስወገድና ፋክክሩ በወግ እንዲካሄድ በማድረግ ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ቀጣይ መሆንና ለሕብረተሰባዊ ሰላም መስፈን ይረዳሉ (ለተጨማሪ ማብራሪያ የግርጌ-ማስታወሻ ቁጥር 13 እና በዘያ ገፅ ለይ የሰፈረውን ይመልከቱ)።

ሥርዓታት፣ ከላይ የተጠቀሱትን ፋይዳዎች ሊያስገኙ የሚችሉት ለይስሙላ የተቀመጡ ባዶ ቀፎዎች ሆነው ሳይሆን በተጨባጭ ህያው ሕብረተሰባዊ ክስተቶች ሆነው ሲገኙ ብቻ ነው። ይህም ማለት፣ የሚከተሉትን ሁኔታዎች የሚያሟሉ መሆን አለባቸው።

በመጀመሪያ ደረጃ፣ ሥርዓታት ማንን-ከማን ሳይለዩ ሁሉንም ሰው፣ ቡድን፣ ድርጅት ወይም መንግሥታዊ የሆነንና ያልሆነን አካል በሙሉ የሥርዓታቱ ደንቦች በሚያዙላቸው መሠረት

---

[7] ባጭሩ ዴሞክራሲ ስንል፣ በነፃ ምርጫ አማካይነት በዜጎች የተመረጡ ባለሥልጣኖች ወደ ፖለቲካ ሥልጣን የሚመጠብትና በዚህም ዓይነት ዜጎች በፖለቲካ ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ውስጥ ተሳትፎ የሚያደርጉበት የፖለቲካ ሥርዓት ማለታችን ነው።

ሳያበላልጡ ማስተናገድ/ማገልገል አለባቸው። እኩል ያስተናግዳሉ ማለት ደግሞ፣ የሥርዓታቱ ደንቦች አበላልጠውም ሆነ አስተካክለው የሚሰጡ፣ እንደዚያው እንደሚደነግጉት ማን-ከማን ሳይለይና ሳይጎድል-ሳይዘል በሁሉም ላይ ተፈጻሚ ይሆናል ማለት ነው እንጂ ሥርዓታት የግድ ለሁሉም አኩል ጥቅም ያስገኛሉ ማለት አይደለም። ለምሳሌ፣ የገባር ሥርዓት የባለጉልቱን ለባለጉልቱ የገባሩን ለገባር ያደርጋል፤ የቄሳርን ለቄሳር የእግዚአብሄርን ለእግዚአብሔር እንዳለው ሁሉ። በሃዲስ አለማየሁ «ፍቅር እስከ መቃብር» ውስጥ እንደምናነበውም፣ የፊታውራሪ መሸሻ ገባሮች ፊታውራሪ ያደረጉትን የንጥቂያ ሙከራ ስኬታማ በሆነ መንገድ ያከሸፉባቸው፣ «ምንም ገዢያችን ቢሆኑ፣ ባያት በቅድመ-አያቶቻችን ከተሰራብን የገባር-ዕዳ ተላልፈው በማን አለብኝነነት ተጨማሪ ግብር አምጡ-ውለዱ ሊሉን አይችሉም» በማለት የሥርዓቱን በሁሉም ላይ መስራትን ተገን አድርገው በመነሳት ነው።

ሁለተኛ፣ የሥርዓታት ምንነታቸው፣ አሠራራቸው፣ ተግባሮቻቸው፣ የሚፈቅዱትና የሚነሱት፣ ወዘተ... ሁሉ በግልፅ በህብረተሰቡ አባላት ዘንድ የታወቀ መሆን አለበት። ለዚህ ጥሩ ብርቅዬ አዎንታዊ ምሳሌ የሃገራችን የፍትህ ሥርዓት ንዑስ አካል የሆነው የመረጃ አስጣጥ ሥርዓት ነው።

ሦስተኛ፣ ሥርዓታት በጥልቀት ታስቦባቸው የሚቆሙ በመሆን አነፃራዊ መረጋጋትና ቀጣይነት ያላቸው መሆን አለባቸው። ማለትም በየጊዜው በለውጥ ስም መያዣ-መጨበጫቸው እስከሚጠፋ ድረስ ከተለዋወጡ ሥርዓት ከመባል ውጭ ይሆናሉ። ለዚህ ጥሩ አሉታዊ ምሳሌ፣ ባለፉት 30 ዓመታት የመኪናዎች ወደ ሃገር ውስጥ አገባብ የተካሄደበት ከመኪናዎቹ ፍጥነት ብዙም ባላነሰ ሲለዋወጥ የሚታየው ሥርዓት ነው --ሥርዓት ከተባለ። አነፃራዊ መረጋጋትና ቀጣይነት ያሻቸዋል ማለት ደግሞ፣ ሥርዓታት ፈፅሞ አይለወጡ ወይም ሁልጊዜ «ያለውን-ሁኔታ» (status-quo) የማስከበሪያ መሣሪያዎች ብቻ ሆነው ያገልግሉ ማለት አይደለም። እንዲያውም ካለው ሥርዓት ተጠቃሚ ያልሆኑ ተዋንያን በሚያካሄዱት የለውጥ ትግል ውስጥ መድረክና ዒላማ በመሆን ሊያገለግሉ ይችላሉ። በታሪክ እንደታየው፣ በ«መሬት ላራሹ»፣ በ«ሰራተኞች በነፃ መደራጀት»፣ በ«ስምንት ሰዓት ሥራ ገደብ»፣ በ«ዎታ ዕኩልነት የሚያረጋግጥ የቤተሰብ ሕግ» እና በመሳሰሉት መፈክሮች ዙሪያ የተካሄዱ ትግሎች ይሽን ያረጋግጣሉ።[8]

አራተኛው የሥርዓታት አስፈላጊ ሁኔታ ቅልጥፍናን እንጅ በይደር ተግባር ማስተጓጎልን የማይፈቅዱ መሆናቸው ነው። የክርክር ፋይሎች ለዓመታት የማይዘጉበትንና በወራት ቀጠሮ ባለጉዳይ የሚንገላታበትን ሁኔታ የሚፈቅደውና «የዘገዬ ፍትህ ከነአካቴው ከተነፈገ ፍትህ ይቆጠራል» የሚለውን አባበል ዕውን የሚያደርገው የአገራችን የፍትህ ሥርዓት ለዚህ አይነተኛ አሉታዊ ምሳሌ ነው።

ሥርዓታት ለህብረተሰብ በሚሰጡት ወሳኝ አገልግሎት የተነሳ አማራጭ የሌላቸው መሆኑ አሌ የማይባል ሃቅ ነው። በመሆኑም ሁሌም፣ የትም፣ በማንኛውም ሁኔታ ቢሆን የመገኘት ዝንባሌ አላቸው -- በሚፈለገው መልክና ደረጃ ባይሆንም። ይሽንን ለማሳዬት የቀን-ተቀን

---

[8] ሥርዓት «ያለውን ሁኔታ» እንዳለ መቀጠል በማይልጉና መለወጡን በሚሹ ተዋንያን መካከል ለሚደረጉ ሽኩቻዎች ጠቃሚ ክፍተቶች ሊኖሯቸው ይችላል። የሚካሄደው ትግልም በደንቦቹ አተረጓጎም ወይም አተገባበር ላይ ወይንም እስከነጭራሹ በደንቦቹ ጠቅላላ መለወጥ ላይ ሊሆን ይችላል። አንዳንዴ ደግሞ፣ አንዳንድ የገመድ ጉተታው አላቀጣ ያላቸው ተዋናያን ትግላቸውን እስከነጭራሹ ወደ ሌላ የትግል መድረክና ለመውሰድ ይገደዳሉ። ይህም በሥርዓቱ ላይ ማመፅን ሳይቀር ይጨምራል።

ህይወታችን መልክ የሚይዝበት «ትዳር/ጋብቻ» የምንለውን ሥርዓት ማንሳት በበቃ ነበር። ትዳር፣ ለአቅመ-አዳም የደረሱ የተቃራኒ ፆታ አባላት ህብረተሰባዊ ዕውቅና ያለውን የግብረ-ሥጋ ግንኙነት የሚመሰርቱበት፣ የወላጅና የተወላጅ ግንኙነት ህብረተሰባዊ ማረጋገጫ የሚያገኝበት፣ ልጆችም ህብረተሰባዊ ወይም ሕጋዊ ጥበቃ አግኝተው በእንክብካቤ የሚያድጉበት፣ እናም «ቤተሰብ» የምንለው ሌላው ተዛማጅ ሥርዓት የሚመሰረትበት ሥርዓት በመሆኑ መተኪያ አልተገኘለትም። በዓይነት ይለያዩ እንጅ ሁሉም የዓለማችን ህበረተሰቦች፣ አንድም ሳይቀር፣ የትዳርና የቤተሰብ ሥርዓታት አሏቸው።

የሥርዓታትን ዩኒቨርሳል መሆን ይበልጥ ለማሳዬት ስንል፣ እስቲ እጅግ ፅንፋዊ (extereme) የሆኑ ሁኔታዎችን እንደ ምሳሌ እናንሳ። አብዮት አጠቃላይ የለውጥ ሂደት ነው። የምንነካነበውም በፊቱ የተደቀኑ የቀድሞ ሁኔታዎችና ሥርዓታት ጠራርጐ እንደሚያስወግድ ሞገድ ነው። ይሁንና፣ አንድ አብዮት ይኸንን ሲያደርግም ቢሆን የራሱን ደንቦች ወጮች እያፈለቀና የራሱ የሆኑ ሥርዓታትን በእንቡጡም ቢሆን እየፈጠረ ነው እንጅ ግራና ቀኙን ባዶ እያደረገ አይደለም ። እነዚህም ሥርዓታቱ አብዮታዊ ሥነ-ምግባር አብዮታዊ ፍትሕ፣ ወዘተ... በመባል የሚታወቁት ዓይነቶች ናቸው።

ሌላው ሰንፋዊ ምሳሌያችን የማፊያና (Mafia) እሱን የመሳሰሉት ሕገ-ወጥ ሥርዓታት ጉዳይ ነው። አንደኛ፣ የእነዚህ አይነቶቹ የወንጀለኛ ደንቦች የሚፈጠሩትናየሚጠናከሩትሕብረተሰቡ ራሱ ለተግባሮቹ ማከናወኛ የሚበጁ ሥርዓታት ማቆም ተስኖት ክፍተት ሲፈጠር ወይንም ይሆኑኛል ብሎ የፈጠራቸው ሥርዓታቱ ፋይዳ-ቢስ ከመሆናቸው የተነሳ ካለመኖር የሚቆጠሩ ሆነው ሲገኙ ነው። ሁለተኛ፣ እነዚህ ሕገ-ወጥ ቡድኖች፣ ሕገ-ወጥ በሆነ መንገድ የራሳቸውን ውስጣዊ የሥራና የስልጣን ክፍፍልና ይህን የማያስከብሩበት ውስጣዊ ደንብ ብቻ ሳይሆን የሚንቀሳቀሱባቸውንም ማህበረሰቦች የሚየስተዳድሩበትንም ደንብ ያወጣሉ፣ ያስፈፅማሉ። እነዚህ ደንቦችና አፈፃፀማቸው አንፃራዊ ቋሚነትና ታዋቂነት ያላቸውና የግዴታ-ውዴታ የተቸራቸው በመሆናቸው የተነሳ፣ የሰዎችን ድርጊት መልክ ከማስያዝ አንፃር ልክ እንደ ሌሎቹ፣ በሕጋዊነታቸው አንደሚታወቁት ሥርዓታት ያገለግላሉ።

4. ሥርዓታት በኢትዮጵያ:- ቀደምት ሁኔታዎች

የኢትዮጵያን የሥርዓታት ምስረታ፣ ዕድገትና ሁኔታ ለየት ያለ መልክ እንዲኖረው ካደረጉት ምክንያቶች ውስጥ ዋነኛው፣ አገራቱ በቅኝ-ግዛትነት ካለመውደቋ የተነሳ የለሙት አገሮች «ቱስም-አናዛኛዮም» ሆነው በውርስ መልክ ያቆሙላት ሥርዓታት ተጠቃሚ አለመሆኗ ነው። በዚህም የተነሳ ያሏት ሥርዓታት በመሠረቱ አገር-በቀል ሆነው ከፊሉ በትውስት ከፊሉ ደግሞ በሳተላሽ ሂደት እየተጣጣፉ የተገኙ ናቸው። ያሉባቸው ችግሮችም ቢሆኑ ከዚሁ ሂደት የፊለቁ ናቸው።

ቀደም ባሉት የታሪክ ወቅቶች፣ በተለየዩ የኢትዮጵያ መልካምድራዊ ክፍሎችና የባሕል አካባቢዎች ታላላቅ መንግሥታዊና ልማዳዊ፣ ባለ-ደርዝና ደርዝ-የለሽ ሥርዓታት ፈልቀው የየዘመናቸው ሁኔታ የሚጠይቀውን ከፍተኛ ጠቀሜታዎች ሲያበረክቱ እንደኖሩ አይካድም። የንጉሥ፣ የርስት-ግባር-ጉልት፣ የገዳ፣ የያጅካ-ቂጫ፣ የጎርዳና-ሴራ እና፣ የሴራ ሥርዓታት ለዚህ ምሳሌ ሆነው መቅረብ ይችላሉ (Bahru Zewde, 2002; Yacob Arsano, 2002)። ያንጊዜም ቢሆን ታዲያ፣ የሥርዓታት ችግሮች መኖራቸው አልቀረም ነበር። ለምሳሌ ያህል፣ በብዙርና

መርህ (principle of primogeniture) ላይ የተመሰረተ ጠንካራ የዘውድ-ውርስ ሥርዓት በመታጣቱ የተነሳ ንጉሥ በሞተ ቁጥር የዘውድ ተቀናቃኞ በሚፈጥሩት ሁከት አገር ሊታመስ፣ ደም ሊፈስና፣ ንብረት ሊወድም ኖሯል። ሁኔታው ሲጠይቅ የነበረውን ጠንካራ የዘውድ-ውርስ ሥርዓት በመፍጠር ፋንታ የውርስ ጥያቄ ሊያነሱ ይችላሉ ተብለው የሚገመቱትን ብላቴኖች በመሉ፣ በራቸው በዘበኛ በሚጠበቅ አምባሟች ላይ በማገት ይፈጠር የነበረውን ሁከት ለማስወገድ ይደረግ የነበረውም ጥረት ያተረፈው ቁም ነገር ቢኖር፣ የስዎችን መብትና ተሳትፎ በዘላቂነት ለመወሰን ፍቱን የሆነው ማዕቀብ ሥርዓት ወይም ደንብ እንጅ ሃይል ተጠቅሞ ሰዎችን በአነላቸው ማግለል ሊሆን እንደማይችል ማረጋገጡ ነው።

ዘመናዊው የኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ማንሰራራት ከጀመረበት ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ወይንም ከአፄ ቴዎድሮስ መነሳት ወዲህ ያለውን ጊዜ ስንመለከትም፣ ባለፉት 150 ዓመታት ሃገራችንን ወደ ልማትና የዕድገት ጎዳና ለማስገባት የተደረገ ጥረቶችን ከተፈታተኑት ዋነኛ እክሎች መካከል አንዱ የሥርዓታት እጦት እንደነበረ የሚያሳዩ መረጃዎች ማቅረብ ይቻላል።

አፄ ቴዎድሮስ ኢትዮጵያን በእንደገና ለማዋሃድና ዘመናዊ ለማድረግ የወሰዷቸው እርምጃዎችና ያደረጓቸው መከራዎች ባብዛኛው በጅምር እንደቀሩባቸው ተደጋግሞ የተነገረ ጉዳይ ነው። ከእነዚህ መከራዎቻቸውም አንዳንዶቹ በቀጥታ አዳዲስ ሥርዓታትን በማቆም[9] ወይም አስቀድሞ የነበሩትን በማድረስ ላይ ያተኮሩ ነበሩ። በራሳቸው በቴዎድሮስ አባባልም የግዛታቸውን ማብቃትና የህይወታቸውን ፍፃሜ ያመጣው ህዝባቸው «ሥርዓት ግባ» ቢሉት አሻፈረኝ በማለቱና በተቀራኒው ድል-አድራጊዎቹ እንግሊዞች በሥርዓት የሚተዳደሩ በመሆናቸው ነበር። (Gebreheiwot Bykedagn, 1912; Bahru Zewde, 2000ª)

የሃገራችንን የሥርዓታት ደሃ መሆንንና ይኽም ለኋላ-ቀርነቷና ለደካማነቷ ያደረገውን አስተዋፅኦ ቀደም ብለው ከተረዱት ጥቂት ምሁራን መካከል አንጋፋው ተመራማሪና ደራሲ ነጋድራስ ገብረህይወት ባይከዳኝ ይገኙበታል። ገብረህይወት በዚህ ጉዳይ ላይ የነበራቸው ትክክለኛና ግልፅ አስተሳሰብ እንኳን በዚያን ጊዜ (እ.ኤ.አ 1912) በዛሬው ዘመንም ቢሆን ወደር የማይገኝለት ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። የአስተሳሰባቸውም ዋና ፍሬ ነገር «አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ» በተሰኘው ዕሁፋቸው እንደሚከተለው ይነበባል።

አእምሮ የሌለው ሕዝብ ሥራት የለውም። ሥራትም የሌለው ሕዝብ የደለደለ ኃይል የለውም። የኃይል ምንጭ ሥርዓት ነው እንጅ የሠራዊት ብዛት አይደለም። ሥራት ከሌለው ሰፊ መንግሥት ይልቅ በሕግ የምትኖር ትንሽ ከተማ ሞያ ትሠራለች ... መንግሥታችን ይህንን ሽ፲ ዓመት መሉ የታፈረች በምኒልክ ግንባር ነው እንጅ በሥርዓታችን ደልዳላነት አይደለምና። (ገፅ 9)

[9] በአማርኛ ቋንቋ በተፃፉና የቀድሞውን ሁኔታ በሚተርኩ ዕሁፎች በተደጋጋሚ የሚነበብ አንድ አባባል አለ። ይኸውም «አገሌ የተባለው ንጉሥ ወይም መስፍን እንደዚህ ያለውን ሥርዓት አቆመ» የሚል ዓይነት ሲሆን፣ «ስርዓት ማቆም» ተብሎ የሚገለፀው አርምጃ በአዋጅ ደንብን ከመደንገግ የተለዩ ሌላ ነገር እንዳልሆነ እንረዳለን። ይኽም፣ «ሥርዓት የሕጉች፣ የደንቦች ወይም የወጉች ጥንትር ነው» የሚለውን ጭብጥ ሕብረተሰቡ ቀደም ሲል ጀምሮ የሚረዳውና የሚገለገልበት እንደነበር በተጨባጭ ያረጋግጣል።

ይህን ከመፃፋቸው አንድ ገፅ ያህል አስቀድመዉ ደግሞ በዚሁ ፅሁፍ የሚከተለውን አስፍረዋል፡፡

> ... ነገር ግን የጤና (የጠና) መሠረት የሌለው ቤት ብዙ ዕድሜ ያገኛል ተብሎ እንደማይታመን እንዲሁም መንግሥታችን መሠረት ያለው ሥርዓት እስኪያገኝ ድረስ ኃይሉ ብዙ ዓመታት ያቆያል ተብሎ አይታመንም፡፡ (ገፅ 7)

በነዚህ ሁለት ጥቅሶች ውስጥ ብዙ ፍሬ-ነገሮች ተካተዋል፡፡ እነዚህን ለማብራራት መሞከሩ አላስፈላጊ ድግምግሞሽ ይሆንብናል -- ፀሐፊው ሁሉንም ባማረ ቋንቋ ገልፀውታል፡፡

ነጋድራስ ገብረህይወት የነበረውን የሥርዓት ጉድለት ከማተት አልፈው ለጊዜው የበጃሉ ያሏቸውን አስር የሥርዓት ማሻሻያ ሃሳቦችን ጠቁመዋል፡፡ እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፡፡ (1) የመንግሥትንና የንጉሥን ሀብት በሥርዓት መለየት (2) ሕዝብ ለመንግሥት የሚከፍለውን ግብር እንደየ ሀብቱ መጠን በቁጥር ማሳወቅ (3) በአይነት የሚከፈልን ግብር አስቀርቶ በብር ብቻ በሚከፈል ግብር መተካት (4) ለአማርኛ ቋንቋ የሰዋሰው ሥርዓት ማበጀትና ትምህርት ቤቶችን መክፈት (5) ከአውሮፖ ሥርዓት ጋር የሚስማማ ፍትሐነገሥት ማውጣት (6) የጦር ትምህረት ቤት ማቋቋምና ሥርዓት ያለው ሠራዊት ማቆም (7) ለመላው ኢትዮጵያ የሚሆን የገንዘብ ሥርዓት በቶሎ መፍጠር (8) በመላ አገሪቱ የሚሰራ የንግድና የቀረጥ ሥርዓት ማውጣት (9) ተዘዋዋሪ የአገር አስተዳደር ተቆጣጣሪዎች በመሾም ሕዝቡ ባንድ መንግሥት ውስጥ መሆኑን ማስረፅ፣ እና (10) የሃይማኖት አርነት ማወጅ፡፡

በዛሬው ጊዜ ላይ ቆመን እነዚህን የማሻሻያ ሃሳቦች ወደኋላ ዞረን ለምንመለከት የአሁን ዘመን ሰዎች፣ እነዚህ የገብረህይወት መፍትሄዎች ገራ-ገር መስለው ሊታዩን ይችላሉ፡፡ በጊዜያቸው ግን እንደ ፅንፈኛ አስተሳሰብ ውጤት የሚገመቱ እንደነበሩ አንዘንጋ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ፣ ነጋድራስ ገብረህይወት የሥርዓታት ግንባታ ጥሪያቸውን ለማስማት የፈለጉት ለማዕከላዊው መንግሥት መሆኑ በራሱ አንድ የታሪክ መዕራፍ እልባት ነው፡፡ ከዳግማዊ ምኒልክ ዘመን የመጨረሻ ዓመታት ጀምሮ ኢትዮጵያ በጠንካራ የተማከለ መንግሥት ሥር ገባች፡፡ በመሆኑም ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ማዕከላዊው መንግሥት የሥርዓት ብቸኛ ሕጋዊ (ሌጂቲሜት) ምንጭ ሆነ፡፡ አካባቢያዊና ልማዳዊ ሥርዓቶች በአብዛኛው ጠፉ፣ ደበዘዙ፣ ወይም ማዕከላዊው መንግሥት በሚፈጥራቸው ሥርዓታት ስር ዋሉ፡፡ ማዕከላዊው መንግሥት አስፈላጊ ሆኖ እስካላገኘው፣ እስካልታየው፣ ወይም እስካልተቻለው ድረስ ሁኔታው ወይም የሕዝብ ጥቅም የጠየቀው ሥርዓት ስለማይፈጠር፣ በደበዘዙት ልማዳዊ ሥርዓቶችና ባልተሟላው የማዕከላዊው መንግሥት የሥርዓት ግንባታ ያልተሸፈነ ክፍተት መፈጠር ያዘ፡፡

ነጋድራስ ገብረህይወት «አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያን» ፅፈው ብዙም ሳይቆይ፣ እንደፈሩት ሁሉ፣ ቀና የዘውድ-ውርስ ሥርዓት መፍጠር ተሰኗት የኖረችው ኢትዮጵያ እንደገና በሥልጣን ሽግግር ሳቢያ ሦስት ዓመት በላይ በፈጀና የርስበርስ ጦርነትን ባስከተለ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ገባች፡፡ ከዚያም በኋላ ቢሆን በማዕከላዊው መንግሥት የሥልጣን ድልድል ሳቢያና፣ የየአካባቢውን ገዥዎች የማዕከላዊው መንግሥት ፍፁም የበታች ለማድረግ በተካሄደው የፖለቲካና የጦር ትግል የተነሳ የተረጋጋ ሁኔታ በመታጣቱ፣ ነጋድራስ ገብረህይወት ያነሷቸው የማሻሻያ ሃሳቦች በአብዛኛው መተግበር የጀመሩት ራስ ተፈሪ/አፄ ኃይለሥላሴ የሥልጣን የበላይነታቸውን ካረጋገጡበት እ.ኤ.አ. ከ1925 አካባቢ ጀምሮ ነበር፡፡

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. ከ1925 ጀምሮ የኢጣልያን ወረራን ለመመከት ዘመቻ እስከተጠራበት እስከ 1935 ድረስ ባሉት አስር ዓመታት ውስጥ ከሥርዓታት ግንባታ አንፃር ከዚያን በፊት ያልታዩ እርምጃ አስመዘገበች። በአይነትም ሆነ በስፋት ከነጋድራስ ገብረሀይወት ራዕይ አልፎ የሄደ ስኬታማ መከራ ተደረገ።

ኩጣልያን ወራሪዎች መባረር በኋላም ቢሆን በእንደገና የተቋቋመው ንጉሠ-ነገሥታዊ መንግሥት የሥርዓታት ግንባታ ስራውን ከበፊቱ በተሻለ ፍጥነት ቀጠለበት። ከነዚህ አንዳንዶቹን እንደ ምሳሌ ያህል ብንጠቅስ፡- አዲስ የገንዘብ፣ የባንክና የቀረጥ ሥርዓት በሥራ ላይ አዋለ። በፊት በአዋጅ ደረጃ ብቻ የቀረውን የገባር-ጉልት/ማደሪያ ሥርዓትን በመሬት የገንዘብ ግብር ስርዓት ተካው። ዘመናዊ የቢሮክራሲ ስርዓትን ዘረጋ። ዘመናዊ የወንጀልና፣ የፍትሐብሄርና፣ የንግድ ሕጐችንና ሥነ-ሥርዓቶቻቸውን በመደንገግና፣ ፍርድ ቤቶችንና የአቃቤ-ሕግ መሥሪያ ቤቶችን በየደረጃው በማዋቀር በመላ አገሪቱ የሚሰራ ዘመናዊ የፍትሕ ሥርዓትን ፈጠረ። ምንም እነኳን ያፈጠጡ ጉድለቶች የነበሩበት ቢሆንም በአገሪቱ ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ በዜጐቿ የተመረጡ ተወካዬች ጭምር የሚመክሩበት ሕግ-አውጭ አካል በተሻሻለ ሕገ-መንግሥት መሠረት ተቋቋመ። የምሳሌው ዝርዝር ረዥም ስለሚሆን፣ በዚሁ እናብቃው።

ታዲያ፣ ከነፃነት መመለስ እስከ 1966 አብዮት ድረስ ያለው ጊዜ ከሥርዓታት ግንባታ አንፃር ከፍተኛ እርምጃዎች የተወሰዱበት ወቅት መሆኑ አጠያያቂ ባይሆንም፣ ሁሉም መከራዎች ሙሉ በሙሉ ስኬታማ ነበሩ፣ ወይንም ፍትሃዊ ነበሩ ማለት አይደለም። ለምሳሌ ያህል፣ የገባር-ጉልት/ማደሪያ ሥርዓትን የተካው የመሬት የገንዘብ ግብር ሥርዓት አርሶ አደሩን ከአይነትና ከጉልበት ግብርና የጉልተኛ እንግልት ነፃ ያወጣ እርምጃ ብቻ ሳይሆን አርሶ-አደሩን ለተነቃይ-ጭሰኝነት ያዳረገ፣ የቀድሞውን ባለጉልት እና ባለ ማደሪያ ደግሞ ወደ ከተማ-ነዋሪ ባለመሬትነት ያሸጋገረ ለውጥ ስለነበር፣ ውሎ አድሮ «የመሬት ላራሹ»ን መፈክር በመውለድ የገጠር መሬትን የመንግሥት ያደረገውን አዋጅ አስከተለ።

ቀናና ቀልጣፋ የፍትሕ ሥርዓት ለመፍጠር የተወሰዱት ዕርምጃዎችም ቢሆኑ፣ ምንም ከብዙ መመዘኛዎች አንፃር ስኬታማ የነበሩ ቢሆንም፣ ለመጀመሪያ ጊዜ መንግሥታዊ አካላትንና ባለሥልጣኖችን በሕግ ፊት ተጠያቂ እስከ ማድረግ ደረጃ ቢደረስም እንኳን፣ እንደ ማንኛውም ሥርዓት ሁሉ የፍትሕ ሥርዓቱ ከተፈጠረበትና ከሚሰራበት የፖለቲካ ሥርዓትና አካባቢ ነፃ ሊሆን ባለመቻል በነበረው አቶክራቲክ አገዛዝ መሸበቡ አልቀረም። የሕግ አውጭውም አካል እጣ-ፋንታ ከዚህ የተለዬ አልሆንም።

ከ1966ቱ የአብዬት ፍንዳታ ተከትሎ የተመሰረተው የደርግ አገዛዝ ከሥርዓታት ግንባታ አንፃር አገሪቱን የኋልዮሽ አስኬዳት። ከዚያን በፊት ተገንብተው የነበሩትን ስርዓታት ማፈራረሱ፣ ደርጉ ከተቀበለው አብዬታዊ አጀንዳ አኳያ አስፈላጊ እንደነበረ የማይካድ ቢሆንም፣ ይህ ሁኔታ ባፈረሳቸው ስርዓታት ቦታ ሌሎችን ሳይተካ ለመቅረቱ በቂ ምክንያት አይደለም። ያም አለ ይኽ፣ ስር-ነቀል ለውጥ፣ የእርስ-በርስ ጦርነት፣ የውጭ መረራን መመከትና፣ የራሱን ፈላጭ-ቆራጭ አገዛዝን ማጠናከር አይነተኛ ተግባሮቹ የነበሩት ደርግ ያፈራረሳቸውን ሥርዓታት በአዲሶች አልተካም። በዚያ ፈንታ አንዳንዴ ከዬት እንደፈለቁ ባማይታወቁ፣ በተበጣጠሱና እርስ-በርስ በሚጋጩና ደግሞም ብዙም ሳይቆዩ ለሌሎች መሰሎቻቸው ቦታቸውን በሚለቁ አዋጆች፣ መመሪያዎችና ቀላጤዎች አገር ለመግዛት ደፋ

ቀና እያለ አገራቱን የሥርዓት አና አደረጋት። መዋቅር መንደፍ እንደዋና ሥራ ተወሰደ። አንዱን በጭንጋፍ የተወለደን መዋቅር በሌላ መዋቅር መተካት እንደ ትልቅ ሥራ ተያዘ።

ደርግ ከዚህ ውጭ ያደርግ ዘንድ ራሱ ፈላጭ-ቆራጭ ተፈጥሮው አይፈቅድለትም ነበር፤ የሥርዓታት መኖርና ሕያው መሆን ከማንም ይበልጥ የፈላጭ-ቆራጮችን፣ የጠረኞችንና የናሩ ሃብታሞችን ሥልጣንና የፈለጉትን እርምጃ የመውሰድ ችሎታ ይገድባልና። የራሱ የደርግ ህልውናና ሥልጣን በደርጉ ሊቀመንበር ፍፁም የሆነ የበላይነት ስር የተመሰረተ ስለነበር፤ የሊቀመንበሩ ፍላጐት፣ ውሳኔና የተነፈሱት ቃል ጭምር ሕግ ሆኖ ነበር። የዚህ ዓይነቱ ያልተገራ የአንድ ግለሰብ የበላይነት በሰፈነበት፣ ሁሉም ነገር አብዮቱና ጦርነቱ በሚጠይቁት ስር በዋለበትና፣ ይኸን አካሄድ መቃወምም እስከ ሞት የሚደርስ ቅጣት በሚያስከትልበት ሁኔታ ውስጥ ሥርዓታትን መገንባቱ ቀርቶ ስለእነርሱ ማሰብም አለመቻሉ አያስገርምም።

በዚህ ዓይነት፣ በደርግ ዘመን ተፈጥረው በሕልውና የቀጠሉት ጥቂት ሥርዓታት በመሉ፤ አንድም ከፅንሳቸው ጀምሮ አለዚያም ውለው-አድረው ለደርግ ቁጥጥርና፣ ብሎም የበላይነት መሣሪያ ሆነው ደርጉን የሚያገለግሉ ነበሩ። ከነዚህም ውስጥ ዋናዎቹ የገጠር የገበሬ ማኅበርና የከተማ ቀበሌ አስተዳደር ሥርዓታት ሲሆኑ፣ በተጨማሪም እንደ እርሻ-ሰብል የግዴታ-ግኝር ሥርዓት እና ሥረዓታዊ መልክ እየያዙ በመምጣት ላይ የነበሩት የጉልበት፣ የአይነትና የገንዘብ ቋሚ የመዋጮ ስብሰባዎች ሊጠቀሱ ይችላሉ።

ደርግ ከወደቀና ኢሕአዴግ አገራቱን ከተቆጣጠረ ወዲህ የሥርዓታት ምስረታ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን መካሄድ ጀመረ። በአንዳራዊ ደረጃ አገራችን ወደ ሥርዓት ጉዳና አመራች። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የሚነሱት ጥያቄዎች፣ የተመሰረቱትና በመመስረት ላይ ያሉት ሥርዓታት በቂ ናቸው ወይ? አሁንስ የሥርዓት ያለህ ብለው በመጮህ ላይ ያሉ ክፍተቶች የሉም ወይ? ያሉትስ ሥርዓታት፤ ሥርዓታት ሊያሰኟቸው የሚችሉትን መለኪያዎች ያሟላሉ ወይ? የሥርዓታት የመጨረሻ ዋስትና ሰጭዎች የሆኑት የፍትሕ ስርዓታት ራሳቸው በተሟላ፣ በተቀላጠፈ፣ በተስተካከለ እና ነፃ በሆነ መንገድ ተግባሮቻቸውን እየተወጡ ናቸው ወይ? የሕግ የበላይነት፣ በሕግ ፊት የሁሉም እኩልነት፣ የመንግሥት አካላትና ባለሥልጣናት ተጠያቂነት እውን ሆኗል ወይ? ወዘተ... የሚሉትና የመሳሰሉት ናቸው።

ያም አለ ይኸ፣ ከላይ ከቀረበው ትረካ በዋነኛነት የምንረዳው ባለፈው ድፍን ምዕተ-ዓመት ህብረተሰባችን ምንም ያህል ቢራመድና በነገበረህይወት ባይከዳኝ ዘመን የነበረው አስከፊ የሥርዓት መታጣት ሁኔታ የፈለገውን ያህል ቢቀረፍም፤ የሥርዓታት ጥያቄ ከቀድሞ ባላነሰ ደረጃ ከፊታችን ተጋርጦ መገኘቱን ነው። በሌላ አባባል፤ ያለንበት ሁኔታ የሚያሳየን የሥርዓታት ግንባታ ህብረተሰብ እስካለ ድረስ የሱን የዕድገት ጉዞ እግር-በእግር እየተከተለ መቀጠል ያለበት የማያቋርጥ ሂደት እንጅ ላንዱና-ለሁልጊዜው ተጠናቋልና ከእንግዲህ እፎይው የሚባልበት ተግባር አለመሆኑን ነው።

5. አንዳንድ የጊዜው የኢትዮጵያ ሥርዓታት ችግሮችና የመፍትሄ ሃሳቦች

በዚህ የዕሁፍ ክፍል ውስጥ አንዳንድ የጎላ የሥርዓት ችግር ያላባቸውን የህብረተሰባችንን ክፍሎች ወይም ዘርፎች ጉዳዮች እንደ ምሳሌ አንስተን እናያለን። ሁሉንም ለዚህ ችግር የተጋለጡትን ጉዳይ ማንሳት ካለን ቦታና ጊዜ አንፃር የሚሞከር ስላልሆነ እንደ ምሳሌ

የምንዳስሳቸው ለያዝነዉ ስራ አመቺ ይሆናሉ ያልናቸውን ብቻ ሲሆን እነሱም የሚከተሉት ናቸው፡- 1. የመ.ያ ደረጃ-ምደባና የሥራ-ፈቃድ፣ 2. የምርት-ጥራት ቁጥጥርና ደረጃ-ምደባ፣ 3. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ 4. የቤተ-መዝገብና ቤተ-መዛሕፍት ጉዳይ፣ 5. የትራፊክ ጉዳይ፣ 6. የመሬት-ሥራት፣ 7. የቢሮክራሲው ጉዳይ፣ እና 8. የዜና-ማሰራጫ አውታሮችና ፕሬስ።

በአገራችን በቅርቡ ከታዩት አበረታች ክስተቶች አንዱ የመንግሥትና የግል የመ.ያ ትምህርት ቤቶች መበራከት ነው። ያለባቸው ችግር እንደተጠበቀ ሆኖ የነዚህ አይነት ትምህርት ቤቶች በብዛት መቋቋም ለወደፊቱ የእጅ ባለመ.ያዎች ለራሣቸው፣ ለአሠሪዎች፣ ለተገልጋዩ የህብረተሰብ ክፍል እና ለመንግስት ጭምር «ፖቴንሻል» ጠቀሜታ እንደሚኖረው አያጠራጥርም። ሆኖም ይኸ «ፖቴንሻል» ወደ ተጨባጭ ጠቀሜታ መለወጥ አለበት። መ.ያተኞችን ማፍራት ማለት መ.ያተኞችን አሠልጥኖ መልቀቅ ብቻ ሲሆን አይችልም። አሠሪዎች ያለስጋትና ያለ ውጣውረድ የሚፈልጉትን አይነት መ.ያ በሚፈልጉት ደረጃ የተካነ ሠራተኛ በቶሎ ለማግኘት የሚያስችላቸው፣ ባለመ.ያ ሠራተኞችን ደግሞ ካለእንግልትና ከኢ-ባለመ.ያዎች ፉክክር በተከበረ ቅጥር የሚገባቸውንና ደረጃቸው የሚፈቅድላቸውን የሥራ እድል እንደየተራቸው እንዲያገኙ የሚፈቅድላቸው፣ የእጅ-ባለመ.ያ ማህበራት እንደያብቡና የመንግስትም የገቢ መሠረት እንዲሠፋ ሁኔታ የሚያመቻች፣ የመ.ያ ደረጃ-ምደባ፣ እውቅናና የስራ-ፈቃድ ሥርዓት መፈጠር አለበት። የሥርዓቱም አተገባበር በዋነኛነት በባለመ.ያ ማህበራቱ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ሆኖ ለእነሱ ተጨበጭ ስልጣንና ሚና የሚያጎናፅፍ መሆን ይኖርበታል። እርግጥ እይታችን በጊዜያዊ ጥቅም ላይ ካተኮረ፣ ለአሠሪዎችም ሆነ ለባለመ.ያዎች ወይም ለተጠቃሚዎች የእንደዚህ ያለው ሥርዓት መፈጠር አላስፈላጊ ተጨማሪ ሸክም ሆኖ ሊታየን ይችላል። ግን ከግዜ በኋላ ሁሉም የልውውጡ ተሣታፊዎችና ህብረተሰቡ ባጠቃላይ ከሥርዓቱ ከሚገኘው የንብረትና የጊዜ ወጭ-ቅነሣ ከፍተኛ ተጠቃሚ መሆናቸውን ይረዱታል።

ሌላም አንድ ተያያዥ ጉዳይ እናንሳ። በከተሞቻችን አነስተኛና «አልባሌ መሣይ» የቤት ቁሣቁስና የግንባታ ግብአቶችን የሚሠሩ የማምረቻ-ታዘዎች በብዛት መታየት ጀምረዋል። እነዚህ አነስተኛ የማምረቻ ድርጅቶች የምርታቸውን ጥራትና አሠራራቸውንም እንደያሻሻሉና እንዲያሳድጉ ከተፈለገ የነሱም ሆነ ከውጭ የሚገቡትን ጨምሮ በፋብሪካ ደረጃ የሚመረቱ የመሰል ምርቶች ደረጃቸው ተለያይቶየሚመደብበትና እንደየደረጃቸው ጥራታቸው ቁጥጥር የሚደረግበት ሥርዓት መፈጠር አለበት። በሥርዓቱ አማካይነት ማለፊያው የምርት ውጤት ከረጋ-ሠራሹ ተለይቶ ለገብያተኛው መቅረብ አለበት እንጅ፤ ራሱ ገብያተኛው እየወጣና-እየወረደ፣ እያነሳና-እየጣለ፣ በዋጋ ላይ እየተደራደረ ፍዳውን በማየትና ለተጨማሪ ወጭ በመዳረግ መሸመት የለበትም። የምንለው ዓይነት ሥርዓት አለ የሚባል ከሆነ አድማሱ ሰፍቶና ሀያው ሆኖ በስራ ላይ መዋል አለበት። ምርቶቹ በአይነትና በመጠን ተለይተው የሚታወቁበት አስተማማኝ የደረጃ-ምደባ ሥርዓት ሳይፈጥርና የተስተካከለ ቁጥጥር በሥራ ላይ ሳያውል ወደ ልማትና የኢንዱስትሪ ህብረተሰብነት ያደገ አገር የለም። የኛም አማራጭ ከዚህ ውጭ ሊሆን አይችልም።

አስቲ ደግሞ ከሁላችንም ከንፈር የማይታጣውንና እንደነሕንድ ለኛም አገር የልማት በር ይሆነናል ብለን የምንመኘውን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅን ነገር እናንሳ። ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅን በአገራችን ለማስረፅ ሥልጠናና የአቅም ግንባታ እንደዋና ግብአት ተወስደዋል። ሆኖም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅን በስፋት በሥራ ላይ ለመዋልና ሕብረተሰባችንን የርሱ

ተጠቃሚ ለማድረግ እነዚህ ሁለቱ ግብአቶች እጅግ አስፈላጊ ሆነው ሳለ፣ በቂ ግን አይደሉም (Daniel Admassie, 2000: 36)::

የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ኢኖቬሽን እንደማንኛውም የቴክኖሎጅ ኢኖቬሽን የራሱ የሆነ ሥርዓት መኖርንና ስር መስደድን ይጠይቃል:: የቴክኖሎጅው ፕሮቶኮሎችና ሳታንዳርዶች እንዲሰርፁ፤ እንዲሁም ኢንፎርሜሽን በጋርዬሽ መጠቀምን ከፍ ለማድረግ ማን፣ ምን ኢንፎርሜሽን፣ በምን ሁኔታ ማስቀመጥ፣ ማስራጨትና በተጠየቀ ጊዜ ማቅረብ እንዳለበት የሚያስገድዱና፤ ማን በምን ሁኔታ፣ እንዴት፣ ወዘተ... የኢንፎርሜሽን ተጠቃሚ መሆን እንደሚችል መብት የሚሰጡ ደንቦችን ያቀፈ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ ሥርዓት ያስፈልጋል:: ይኽ ሥርዓት፣ የአእምሮ ሥራ ንብረትን፣ የዳታ ሚስጥርነትንና ፕራይቬሲን፣ የኮምፒዩተር አላግባብ አጠቃቀምን፣ ኤሌክትሮኒክ የባንክ አሰራርን፣ የሶፍትዌር ጥበቃንና የመሳሰሉትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎችን ስለሚያቅፍ «የሚያሰራ ሆኔታ» ይፈጥራል (Daniel Admassie, 2000: 36):: የዚህ ዓይነት ሥርዓት እስከሌለ ድረስ፣ አዳዲስና ብዛት ያላቸው ኮምፒዩተሮች ሥልጠናቻውን ካጠናቀቁ ሰራተኞች ፊት ስለተደረደሩ ብቻ የሚፈይዱት ነገር የለም:: እርግጥ እዚህና እዚያ፤ በአንዳንድ ታታሪ የሥራ-መሪዎች ጥረት ኮምፒዩተሮች ለታቀደላቸው ሥራ ይውሉ ይሆናል:: ልናሰምርበት የምንፈልገው ፍሬ-ነገር ግን፣ እንደ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጅ መስረፅ ያሉ ዋና ዋና የሕብረተሰቡ ጉዳዬች ለግለሰቦች በጐ-ፈቃድ መተውና በዚያ ላይ ብቻ መንጠልጠል የለባቸውም የሚለውን ነው::

ወደ ረቀቀውና ወደ መጠቀው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ከማንጋጠጣችን በፊት ደግሞ፣ የአገራችንን የወረቀት መዛግብትና የመረጃ አያያዝ እንቃኝ ዘንድ የሁኔታው አሳዛኝነት ያስገድደናል:: ኢትዮጵያ ረዥም የመንግሥት፣ የፊደልና የሥነ-ፅሁፍ ታሪክ ካላቸው አገሮች መካከል ተቆጣሪ ሆና ሳለች፣ እስከ ዛሬ ድረስ ብሄራዊ ቤተ-መዝገብ (አርካይቭ) የሌላት መሆኑ፤ ለጉዳዩ ትኩረት በሰጡ ምሁራን ዘንድ እንደ ትንገርት የሚታይ ሆኗል (Bahru Zewde, 2000ᵇ: 98):: የቤተ መንግሥቱ፣ የፍርድ ቤቶች፣ የአገር አስተዳደር፣ የመሬት ይዞታ፣ ወዘተ... ታሪካዊና አገራዊ መረጃዎች በቅጡ ባለመያዛቸው የትምህርት ተበትነዋል፣ ለጉዳት ተዳርገዋል፣ ወይም እስከነጭራሹ ጠፍተዋል::

ቤተ-መዛሕፍቱም አሉ ከመባሉ በስተቀር ያሉበትን ሆኔታ በተመለከተ ብዙም አወንታዊ ገፅታ አይታይባቸውም:: የመረጃ/ፅሁፍ አሰባሰባቸው፣ አያያዛቸውና፣ ለተጠቃሚ የሚሰጡት አገልግሎት በሙሉ በችግሮች የተሞሉ ናቸው:: እንደ መዛሕፍትና ፅሁፎች እጥረት፣ የማስቀመጫና የማንበቢያ ቦታ አለመኖርና የመሳሰሉ ቁሳዊ ችግሮች በተጨማሪ ለደንቡ የተገዛ አሠራር ማጣት አስሮ ይዟቸዋል (Yeraswork Admassie, 2000:78-92)::

ብሄራዊ ቤተ-መዝገብ በሕግ መቋቋምና ሕግን ተንተርሶ መስራት እንዳለበት ሁሉ፣ ቤተ-መዛሕፍትም የሚመሩበት የመረጃ አያያዝን፣ ልውውጥንና አጠቃቀምን የሚወስኑ ደንቦችን ያሰባሰበ ሥርዓት ያስፈልጋቸዋል:: የዚህ ሁኔታ መሟላትም የማንበብ፣ የመፃፍ፣ የመመራመር፣ ባጠቃላይ የዕውቀት ክምችት ሂደትንና ብሎም የአገር ልማትን ያግዛል:: እዚህ ላይ፣ ለምሳሌ ያህል፣ ከሃያና ከሠላሳ ዓመታት በፊት ቀናና መላ ሃገራቱን የሚያዳርስ የቤተ-መዛሕፍት አገልግሎት ሥርዓት በመዘርጋት ሕዝብዋን የከፍተኛ ፈጠራ-ችሎታ ባለቤት አድርጋ አሁን በያመቱ ከፓተንት-መብት ክፍያ ከፍተኛ የውጭ-ምንዛሪ የምታገኘውን የስሎቬኒያን ጉዳይ መስታወስ እንሻለን::

ባለፉት አሰርተ-ዓመታት በሃገራችን ከታዩት ጉልህ የመሰረተ-ልማት ክንውኖች አንዱ ባጠቃላይ የአውራ ጐዳናዎች ሥራ፣ በተለይ ደግሞ የጠጠር አውራጐዳናዎችን በአስፋልት የሕይወትና የንብረት ኪሳራን በማስከተል ላይ ያለው የትራፊክ አደጋ ቁጥር መጨመር ግን፣ ሃገሪቱ በመሪነት የያዘችውን የተሽከርካሪ አደጋ ተጋላጭነት ደረጃዋን እያጠናከረው መጥቷል። እንደ ዓለም የጤና ድርጅት (WHO) ከሆነ፣ በአመት በመኪና አደጋ የሚሞትን ሰው ቁጥር በተመለከተ (ካለው የተሽከርካሪ ብዛት አንፃር ሲሰላ)፣ ኢትዮጵያ ከዓለም ከፍተኛ ውን ቦታ ይዛለች (SafeCarGuide.com, Inc., 2003-2004)። ብዙዎቹ አስደንጋጭ የሆኑ አደጋዎችም የሚደርሱት በከፍተኛ የገንዘብ ወጭ በአዲስ በመልበስና በመቃናት ለአመች የተሽከርካሪ ዝውውር በተሰናዱት አውራ ጐዳናዎች ላይ እንደሆነ ይነገራል። በአዲስ አበባ ከተማም ቀለበት-መንገድን ጨምሮ የተሰሩት ሰፋፊ መንገዶች «የአደጋ ቀለበቶች» ከመሆን አልዳኑም።

ከዚህ የምንረዳው፣ ፈጣን የተሽከርካሪ ዝውውርን የሚጋብዙ ጐዳናዎችንና ቀለበት-መንገዶችን እውነተኛ የፈጣን ዝውውር መሣሪያዎች ለማድረግ ከተፈለገ፣ ጥረቱ ጐዳናዎቹን ከመስራቱ አልፎ በመሄድ ቀሪውን ጉዳይ መሸፈን እንደአለበት ነው። የተመሰቃቀሉትን የመንጃ-ፈቃድ አሰጣጥ፣ የተሽከርካሪዎች ምርመራ፣ የትራፊክ ምልክቶች አቅርቦት የሚያስተካክል የትራፊክ ሥርዓት ያስፈልጋል። የትራፊክ ሥርዓታችን፣ ከተሞችን በሚያገናኙት ጐዳናዎች ላይ ጭምር እንዲሰራ መደረግም አለበት። እንደ ተጨባጭ ምሳሌም፣ ጐዳናዎቹ በትራፊክ-ፓትሮል ቁጥጥር አማካይነት ሥርዓት መያዝ አለባቸው። በከተት የሚሰቡ ተሽከርካሪዎችም ከሞተር ተሽከርካሪ ጐዳናዎች ውጭ መሆን ይኖርባቸዋል። ወዘተ... ። ይህን ማድረግ ተስኖን በሺህ ሚሊዬን የሚቆጠር ሃብት አፍስሰን ያሰራናቸው መንገዶች ሊቀንስ ለሚችል ኪሳራና በአደጋዎች ሳቢያ ለሚፈጠር የዝውውር እክል የሚዳርገን ከሆነ ግን፣ መንገዶቹን ለመስራት የተነሳንበት ልማትን የማስገኘት ዓላማ በራሱ ከሽፏል ማለት ነው።

በኢትዮጵያ ያለው የሥራዓታት ዕጦት ጉዳይ ሲነሳ፣ ከሠሉም ልቶ የሚታየው የብዙ የሌሎች ችግሮች እናት የሆነው የንብረት መብቶች ጉድለት ጉዳይ፣ በተለይም መሬትን የሚመለከተው የንብረት መብቶች ችግር ነው። ስለዚህ ይህን በአጭሩም ቢሆን እንመልከት ዘንድ ሁኔታው የግድ ይላል።

የኢትዮጵያ አብዮት መሬትን በግል ንብረትነት ለአርሶ-አደሩ ከማከፋፈል ይልቅ፣ መሬትን በመንግስት ቁጥጥር ሥር «የሕዝብ» አድርጎ አርሶ-አደሩ በሚገለገልበት መሬት ላይ የሚኖረውን መብት በተጠቃሚነት መብት ብቻ ገደበው። ይህንም አማራጭ ለመውሰድ አንድ ዋነኛ ምክንያት ነበረው። ዋነኛ ምክንያቱ አብዮቱ ከተከሰተው የሶሺያሊስት ርእዮተዓለም ጋር በተያያዘ፣ የመንግስትና የወል እርሻን መሠረት ያደረገ የገጠር ልማት ለማስገኘት የመሬት በመንግስት እጅ መሆን አማራጭ የሌለው ነው የሚል ሲሆን፣ ከዚህ ጋር አብሮ የሚመጣው የመንግስት የቁጥጥር አቅም መጠናከርም ቢሆን በጊዜው በሥልጣን ላይ የነበረውን ደርግ ሳያማልለው እንዳልቀረ መገመት ይቻላል።

ደርግን የተካው መንግሥት፣ ቀስበቀስ «የገበያ ሥርዓት» ብሎ የሚጠራውን የካፒታሊስት ሥርዓት እንደሚከተል በማስታወቅ፣ የበፊቱን የዕገዳ ወይንም የሶሺያሊስት ኢኮኖሚ

ፖሊሲዎችን ተራ በተራ እየቀለበሰና፣ መዋቅሮቹንም እያፈራረሰ ሄደ። ከአንድ ጉልህ ሥርዓት በስተቀር -- ከመሬት በመንግስት እጅ ከመሆን በስተቀር -- ማለት ነው ።

የኢሕአዴግ መንግሥት ከደርግ የወረሰውን የመሬት ፖሊሲ ለምን እንዲቀጥል እንደሚፈልግ የሚሰጠው ምክንያት ገበሬው ሙሉ የባለቤትነት መብት ካገኘ ካለበት አስከፊ ችግር የተነሳ መሬቱን በሺያጭ አሳልፎ መስጠቱ ስለማይቀር፣ ከመሬቱና ከቀየው ተፈናቅሎ ለአስከፊ ችግር ይጋለጣል የሚል ነው። የዚህ አቋም ተኾዎች በበኩላቸው፣ በርካታ የመከራከሪያ ነጥቦችን በማንሳት ይኽ ላለው የመሬት ፖሊሲ በቂ ምክንያት አለመሆኑን ለማስረዳት ይሞክራሉ። የኢትዮጵያ ገበሬ በረሀብ የሚያልቅበት ሁኔታ ውስጥ እያለ እንኪን ማንም ሳያስገድደው በሬዎቹን በመሸጥ ችግር መፍታትን እንደ ዋና አማራጭ ያለመውሰድ ዝንባሌውን ያነሳሉ። በተጨማሪም፣ «ውስጥ-ለውስጥ» መሬት እየተሸጠ እያለ፣ ይህን አማራጭ ገበሬው በሰፊው አለመከተሉን፤ እንደ ተቃራኒ ማስረጃ ያቀርባሉ። አንዳንዶች ደግሞ የአርሶ-አደሩ ይዞታ ተቆርሶና ተቆራርሶ ትርጉም ያለው የምርት ሥራ ከሚከናወንበት መጠን በታች በመውረዱ የተነሳ «መንግስት መሬትን በቁጥጥሩ አድርጎ ለተጠቃሚው አርሶ-አደር ያዳርሳል» የሚለው ሕገ-መንግሥታዊ ከለላ የተበጀለት ፖሊሲ ትርጉመ-ቢስ እየሆነ መምጣቱን ያመለክታሉ። አንዳንድ የክልል መንግስታትም፣ በክልላቸው አዲስ የመሬት ድልድል ሊካሄድ የሚችልበት ሁኔታ እንደሌለና እንደማይደረግም በማወጅ ለዚህ ግንዛቤ ማረጋገጫ እየቸሩት መሆኑን ይጠቅሳሉ (Zikre-Hig, 2000)። እንደሚሉት፣ መንግሥት ራሱ አንዳንዴ በተግባር፣ ሌላ ጊዜ ደግሞ በቃል፣ የመሬት ፖሊሲውን ችግር እየተገነዘበው የመጣ ይመስላል።

የመሬት-ሥሪት፣ ሰዎች መሬትን በተመለከተ ያላቸውን መሬትን የመያዝ፣ በመሬት የመጠቀምና፣ መሬትን የማስተላለፍ መብቶችን የሚያቅፍ የመብቶች ጥቅል ነው። በመሆኑም የመሬት-ሥሪት ማለት መሬትን የሚመለከቱ የንብረት መብቶች ሥርዓት ነው ማለት ይቻላል። የንብረት መብቶች የሚመለከቱት ደግሞ በአንድ ነገር (ቁስ ወይም የአዕምሮ-ሥራ ውጤት) እና ባለንብረቱ በሆነው ሰው መካከል ያለ ግንኙነትን ሳይሆን፣ ያንን ነገር በተመለከተ በባለንብረቱና በሌሎች ሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት ነው። ስለዚህም፣ የንብረት መብቶች ሥርዓት መኖር ማለት፤ አንድ ባለመብት፣ የንብረት መብቶቹ ማረፊያ የሆነው ነገር ይጠበቅለት ዘንድ እራሱ ዘብ መቆም ሳያስፈልገው በእሱ ፋንታ ሕብረተሰቡ ከሌሎች ሊቀናቀኑት ከሚሹ ተከላክሎ ያስከብርለት ዘንድ የመጠየቅና መከላከያ የማግኘት ሙሉ መብት መኖር ማለት ነው (Bromley, 1991: 15)። በዚህ ዓይነት፣ የመሬት-ሥሪትም መሬትን በተመለከተ በሰዎች መካከል የሚኖረን ግንኙነትና ሕብረተሰቡም ሰዎችን በመሬት ላይ ያላቸውን መብት በተመለከተ የሚሰጣቸውን ሕብረተሰባዊ እውቅናና ድጋፍ ግልፅ የሚያደርግ ዋነኛ ሥርዓት ነው (Burns et.al., 1985: 274; Yeraswork, 2000 (1995): 12-16)።

የመሬት-ሥሪት ከላይ የጠቃቀስናቸው ጠባዮች ያሉት ዋነኛ ሕብረተሰባዊ ሥርዓት እንደመሆኑ መጠን፣ ቀደም ብለን ከዘረዘርናቸው የሥርዓታት ፋይዳዎች ውስጥ ከአንዱ (ከዘጠነኛው) በስተቀር ሁሉንም ለሕብረተሰብ ያበረክታል። እንደዚሁም፣ አንድ የመሬት-ሥሪት በስም ሳይሆን በገቢር እንደ ሥርዓት ይኖር ዘንድ፣ አሁንም አስቀድመን የዘረዘርናቸውን የሥርዓታት አስፈላጊ ሁኔታዎች ማሟላት ይኖርበታል። ከዚህ አንፃር ሲታይ አሁን የሚሰራበት የመሬት ፖሊሲ ከመሬት-ሥሪት ተርታ የማይገባ መሆኑ ግልፅ ነው።

በአሁኑ ጊዜ የሚሰራበት የመሬት ፖሊሲ ለበርካታ የሃገሪቱ ችግሮች ምንጭ መሆኑ በተደጋጋሚ ተመስቷል። የደኖችን ህልውና ከሚፈታተኑት ዋነኛው ችግር አንዱ እንደሆነ፣ አርሶ-አደሩን ለአፈር ጥበቃና ለመሬት ለምነት መጠበቅ በቀጣይነት ቁብ የሌለው ተገልጋይ በማያሳድር ማሳ ላይ ተንጠልጥለውና በእርዳታ እህል እየተደጎሙ የሚገኙበትን «የረሀብ ማሳዎች» እንዳስከተለ፣ የአርሶ-አደሩን መብት እንዳኮሰሰና አርሶ-አደሩን የመንግስት ጭሰኛ ቢጤ እንዳደረገው፣ የመሬት ድልድልን ለፖለቲካ ቂም መቅረፊያና ለፖለቲካ ድርጎ መስጫ በመሣሪያነት እንዲውል በር እንደከፈተ በብዙ ጥናቶች ተመልክቷል (Melaku Bekele, 2003; Yeraswork Admassie, 2000 (1995); Tekie Alemu, 2000; Atakilte Beyene, 2003; Dessalegn Rahmato, 1997; Hoben, 2001; Teketel Abebe, 1998; Yigremew Adal,2000; Ege, 1997; Teferi Abate,2000; Tena Shitarek etal. al., 2001)።

ምንም እንኳን በሀገራችን ያለውን የንብረት መብቶች ሥርዓት ችግር ለማሳየት ትኩረት የሰጠነው በገጠር መሬት ጉዳይ ላይ ቢሆንም፣ የከተማ መሬትንና የተወረሱ ቤቶችን በሚመለከት ከዚህ ብዙም ያላነሰ ችግር እንደተፈጠረ ለመጥቀስ እንፈልጋለን። መንግስት ቤት ስርተው ለማያከራዩ ባለሀብቶች መሬት በሊዝ በማያቀርብበት በአሁኑ ጊዜ፣ ቀደም ሲል ለከራይ ተሰርተው የተወረሱ ቤቶችን አልመልስም ብሎ መጭጭ የማለቱን ፍትሐዊነት ጉዳይ እንዳለ እንገለልና፤ የመንግስት ቦታና ቤት ችረና ነፋጊ ሆኖ መቀጠል፤ መንግሥት በፖለቲካ ኃይሉ ላይ ቁልፍ የኢኮኖሚ ኃይል ደርቦ በመያዝ የዜጎች የተሟላ የፖለቲካ ነፃነት እንዳይሰምር ማድረጉን ልብ እንበል። ይኸ ሁኔታ፣ ልክ እንደገጠሩ የመሬት ድልድል ሁሉ ፖለቲካና ኢኮኖሚን በማሳከር በንግዱም ሆነ በፖለቲካው ማኅበረሰብ ውስጥ ነፃ ፉክክር የሚካሄድበት «የተስተካከለ ሜዳ» እንዳይኖር አድርጓል። በዚህ የተነሳም ለኢኮኖሚ ዕድገትም ሆነ ለፖለቲካ ነፃነት መሳልበት የይበጅ አካባቢን ፈጥሯል።

የገጠርም ሆነ የከተማ መሬት ለሕብረተሰቡ የኢኮኖሚ ልማትና የፖለቲካ ነፃነት መስመር በሚበጅ የመሬት-ሥራቶች አማካኝነት መያዝ፣ በጥቅም ላይ መዋልና መተላለፍ አለበት። ሆኖም፤ እዚህ ላይ፣ መኖር ስለሚገባቸው የመሬት-ሥራቶች በነጠላ ሳይሆን በብዙ እየተናገርን እንደሆነ ልብ እንበል። መቼም-መች ቢሆን፣ በመላ ኢትዮጵያ አንድና አንድ ብቻ የመሬት-ሥራት ኖሮ አያውቅም። የ1967 የመሬት አዋጅም ቢሆን በአንድ በከተማ ልዩነቶችን ለማስተናገድ ሞክሯል፤ በተጨማሪም የመሬት ድልድል የማድረጉና በገጠር የማይኖር ሰው የገጠር መሬት ይዞታ እንዳይኖረው የማገዱ ጉዳይ ባንዳንድ የውስጥ ችግሮቻቸውን በራሳቸው የመፍታት ልማዳዊ አሠራራቸውን እርግፍ አድርገው ባልተው እንደ አንዳንድ የጉራጌ ክፍሎች ሳይተገበር ቀርቷል (Yeraswork Admassie and Fantu Guta, 2003)። ስለዚህ በአንድ በኩል በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉትን መልካምድራዊ ባህላዊና ታሪካዊ ልዩነቶች፤ በሌላ በኩል ደግሞ መላ አገሪቱን የሚያስተሳስሯትን መሰል የእድገት አቅጣጫና የጋራ የወደፊት እድል፤ ሁሉንም፤ መሠረት ያደረገና ለተለያዩ አካባቢዎችና ሁኔታዎች የሚበጁ የመሬት-ሥራቶችን አዘጋጅቶ፤ ፈትሾና መርጦ ማወጅና በስራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል። በዜጎች የኢኮኖሚና የፖለቲካ ነፃነትና እኩልነት ዕኑ መሰረት ላይ ሆና በልማት ጎዳና የምትራመድ ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ከተፈለገ በአዲስ መንፈስና ተነሳሽነት የሚበጁ የመሬት-ሥራቶች ከመፍጠር ወጭ ሌላ መፍትሄ ለማሰብ ያስቸግራል።

እዚህ ላይ ደግሞ ስለመንግስታዊ መስተዳደር ወይም ቢሮክራሲ. ቢያንስ አንዳንድ ነገሮችን ማንሳት እንገደዳለን። በመጀመሪያ ደረጃ የቱ-የቱ የመንግሥት የሥራ ገበታዎች በፖለቲካ ተሿሚዎች እንደሚያዙና የቱ-የቱ ደግሞ ለተቀጣሪ ባለሙያዎች ወይም ሲቪል አገልጋዮች ክፍት እንደሚሆኑ የሚወሰንና ይኸንንም በተግባር ያረጋገጠ ተልጣሩ የቢሮክራሲ. ሥርዓት መገንባት አለበት። የዚህ ዓይነቱ የቢሮክራሲ. ሥርዓት ዕውን መሆን «መልካም አስተዳደር» የሚባለውን በተሟላ መልኩ ለማስገኘት ይረዳል። ምክንያቱም፤ አንደኛ፣ ሥራውን የማይመጥኑ ሰዎች በሆነ የሥራ ገበታ ላይ ተገኝተው ለሥራ ሂደት እንቅፋት እንዳይፈጥሩ ያደርጋል። ሁለተኛ፣ እንደዚያ ያሉትን ሰዎች ወደሚመጥኑት ብቻ ሳይሆን ይበልጥ ውጤታማ ወደሚሆኑበት የሥራ መስክ በመሰደድ ሥራና ሠራተኛን ያገናኛል። ሦስተኛ፤ ቢሮክራሲው፣ በተፈጥሮው ተለዋዋጭና ወገናዊ ከሆነው ፖለቲካ ውጭ ሆኖ ተጣይነት ባለው መንገድ እንዲሠራ ያደርጋል። አራተኛ፣ በተያያዥ ደግሞ የፖለቲካ አቋምና የፖለቲካ ወገናዊነት የግድ «የእንጀራ ጉዳይ» እንዳይሆኑ በማድረግ የዜጎች የፖለቲካ ነፃነት የሚረጋገጥበትን ሁኔታ ይፈጥራል።

የመጨረሻ መጨረሻ ደግሞ፣ ከሁሉም ሌሎች ህብረተሰባዊ ሥርዓታት ጋር በጥብቅ የሚገናኘውንና ለሌሎቹ ጤናማ ህልውና ድጋፍ-ሰጭ የሆነውን የዜና-ማሰራጫ አውታሮችና የፕሬሱን ጉዳይ እንመልከት። ባለፉት አስራ-አምስት ዓመታት የኢትዮጵያ ነፃ/የግል ፕሬስ ካለመኖር ወደ መኖር መጥቷል -- ህልውናው የቱንም ያክል አስቸጋሪ ቢሆንና ነፃነቱም የተገደበ ቢሆንም። ነፃ/የግል ሬዲዮና ቴሌቪዥን ደግሞ እስከነጭራሱ የሉም። የግል ሬዲዮ ጣቢያ መኖርን ይፈቅዳል የተባለውም አዋጅ በግሉ ዘርፍ የሚሰጠው ቦታ እጅግ ጠባብ እንደሚሆንና በግሉ ዘርፍ ላይ ሃላፊነትን የሚደረድረውን ያህል መብቱን እንደማያውቅለት ይነገራል። ይኸ ለአገራቱ የሶሺዮ-ኢኮኖሚክ ልማትም ሆነ ለዴሞክራሲ ሥርዓት ምስረታ የሚበጅ አይደለም። ነፃ የዜና-ማሰራጫ አውታሮችና ፕሬስ ለፍትህ፣ ለዜጎች መብትና ለዴሞክራሲ. ዘብ በመሆናቸው የዚህ ዘርፍ ሥርዓታት መጠናከር ትልቅ ስትራቴጅክ ፋይዳ አለው።

የኢትዮጵያ ነፃ/የግል ፕሬስ ልክ እንደ ኢትዮጵያ መንግሥት ደካማ ጎኖች አነዳለት ግልፅ ነው። መንግሥት ደካማ ጎኖች አለትና፣ ስለዚህ መንግሥት አይኑር እንዳማንልና የመንግሥት አውታሮች በሥርዓታት እንዲገዙ ብቻ እንደምንመኝ ሁሉ፣ በተደላደለ ሥርዓት አማካይነት የሚሰሩና ሙሉ-በሙሉ በነፃነትና በኃላፊነት ስሜት የሚንቀሳቀሱ የዜና-ማሰራጫ አውታሮችና ፕሬስ እንዲኖሩና እንዲያብቡ፤ ብለውም ቀደም ብለን የጠቀስናቸውን የዙሪ ሚናቸውን በስፋትና በጥልቀት እንዲያከናውኑ እንፈልጋለን። ለዚህም፣ በሚያፍን አዋጅ ፋንታ መብትና-ኃላፊነትን ጎን-ለጎን የሚያጎናፅፋቸው የዜና-ማሰራጫ አውታሮችና የፕሬስ ሥርዓት ያሻቸዋል።

በዚህ ክፍል ውስጥ ያነሳናቸውን እናጠቃልል። ቀደም ብለን በዚህ ዕለፍ ክፍል አራት ውስጥ የጠቀስናቸውን የሥርዓታት ፋይዳዎችና በዚህ በያዝነው ክፍል ውስጥ እንደ ምሳሌ የተነሱትን ጥቂት የህብረተሰባችንን የሥርዓታት ችግርና መፍትሄዎች በአንድነት ስንመለከት፣ ሁኔታው ከፈጠረብን ችግር ጎን ለጎን፣ በየህብረተሰባዊ ዘርፉና የሥራ መስኩ ሁሉ የሚከፍትልንም የመፍትሄ እርምጃዎች ዕድል እንዳለ በግልፅ ያሳዬናል። ይህም ግንዛቤ አዳዲስ ሥርዓታትን በማቆምም ሆነ ያሉትን በማስተካከልና ነፍስ እንዲዘሩ በማድረግ ትርጉም ያላቸው የለውጥ ዕርምጃዎች በመውሰድ ላይ እንድናተኩር ይረዳናል።

የአንድ አገር የመልማት ወይም ያለመልማት ዕድል የሚወሰነው በባሕሉ ነው፣ የሚለው ያረጀና ከአውሮፓውያን የተወረሰ ኣስተሳሰብ ሰሀተተኛነት በዓለም-ኣቀፍ ደረጃ ከተጋለጠ ውሎ-አድሯል (Zakaria, 2004:51-55):: የኢትዮጵያ ምሁራን ግን፣ ከዚህ ከውጭ-ሃገር ተተፍቶ ከመጣ የ«በሕል-ወሳኝነት» (cultural determinism) ኣስተሳሰብ[10] ጋር ለረዥም ጊዜ ስንዳራ በመቆየታችን የተነሳ፤ ከኛ ኣልፎ በሕበረተሰባችን በሰፊው ተነሰራፍቷል:: በመሆኑም፣ ባሁኑ ጊዜ፣ «ኃላ-ቀር ባሕላችን ተጠራጣሪ አደረገን፤ ሥራን እንድንንቅ፣ እንድንጠየፍ ገፋፋን፤ ተባብረን አንዳንሰራ አደረገን፤ ቀጠሮ ላለማክበር ዳረገን፤ ለዲሞክራሲ ጋሬጣ ሆነብን፣ ለድህነታችን የማይመጥን ኩራት ኣከናነበን፣ ወዘተ...» አያሉ መራቀቅ፤ የኣዋቂነትና የዘመናዊነት ምልክት ተደርጎ ከሚታይበት ደረጃ ላይ ደርሰናል::

ይበልጥ የሚያሳዝነው ደግሞ የ«ባሕላችንን ችግሮች» በማስወገዱ ላይ ከግራና-ቀኝ የሚቀርበው ኣሰልች መፍትሄ-ተብዬው ሃሳብ ነው:: ከሊቁ እስከ ደቀቁ፣ ከቃለ-መጠይቅ ሰጭው እስከ ሪፖረት ዘጋቢው፣ ከጥናት-መድረክ ከፋቹ እስከ ዓውደ-ጥናት ደምዳሚው ያለው ሁሉ፣ ለሆነና-ላልሆነው እንደማሳረጊያ የሚያቀርበው መፍትሔ «ያስተያየትና የባህርይ ለውጥ ማምጣት!» የተባለውን ሁሉን-ፈዋሽ መሣይ ባዶ ጩኸት ነው:: ይኸ ምሁራዊ-መሣይ ግን «ምክንያትን» እና «ውጤትን» በሚያምታታ የዙሪያ-ጥምጥም ኣስተሳሰብ (circular reasoning) ላይ የተመሰረተ ኣነጋገር፤ «ለውጥ እናስገኝ ዘንድ ምን ብናደርግ ይሻለናል?» የሚለውን መሰረታዊ ጥያቄ «ለውጥማ ለማምጣት መድሃኒቱ ለውጥ ማምጣቱ ነው!» ብሎ በመመለስ የዋሁን ኣድማጭ "ኣፍ-አሰይዞ" ያማልል እነደሆነ እንጅ ከዚያ ኣልፎ ልማትን ከማስገኘት ኣንፃር ስንዝር ኣያራምድም:: ስለዚህ፣ የ«ባሕል ችግራችንን» በተመለከተ ድፍን የሆኑ እሮሮዎችን ዝንተ-ዓለም መደጋገሙንና የማይዘገን ጉም ማሳደዱን ትተን፤ እነዚህን «ባሕል» በተሰኘ "ሚኒ-በስ" ስያሜ ሥር ጨፍልቀን በማስገባት የጋራ ሙሾ የምናወርድላቸውን የተለያዩ የባህርይ ዘይቤዎችን ለመቀየርና መልክ ለማስያዝ በሚረዱን በሥርዓታት ጉዳይ ላይ ብናተኩር ይበልጥ ውጤታማ የሆኑ ተግባራትን ማከናወን ሳንችል ኣንቀርም::

6. ማጠቃለያ:- የሥርዓታት የልማትና የፖለቲካ ነፃነት ትስስርና፣ በዛሬ ላይ የተመሰረተ የ2020 ራዕያችን

የሥርዓታት ችግር ከዘመናዊ ኢትዮጵያ አመሰራረት ጋር ተያይዞ የኖረ፣ ያለና፣ በአፋጣኝ መወገድ ያለበት እንደሆነ ባለፉት ገፆች ተመልክቷል:: ይኽን ችግር ማስወገድ ማለት ደግሞ

---

10 በምዕራባዊው የትምህርት-ገበታ የታነፀው ትውልድ ይኽን ዓይነቱን ግንዛቤ የቀሰመው ቀደም ሲል ከኣውሮፓዊ ሚሲዮናውያን ዘግይቶ ደግሞ እንደ ታዋቂው ዶናልድ ሌቪን ካሉ ምዕራባዊ የሶሻል ሳይንስ ምሁራን ሲሆን፣ በተለይ የሌቪን ኣስተሳሰብ ያሳደረው ተፅዕኖ በኛ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን በታዋቂ ምሁራን ዘንድ ጭምር ከመስፋፋቱ የተነሳ፣ ታዋቂው የፖለቲካ-ሣይንቲስት ሮበርት ዳል ሳይቀር ሌቪንን በመጥቀስ እንደሚከተለው ያለውን በኣጋደለ ስሜት ላይ የተመሰረተ ትንታኔን ሲያስተጋባ ይስተዋላል::

... the extreme distrust prevailing among the Ethiopians helps explain "the lack of organizations for the ariticulation and aggregation of interests in Ethiopia" (Dahl, 1978: 151).

ይኸው ትውልድ አሜን ብሎ ከተቀበላቸው ተዛማጅ ድምዳሜዎች አንዱ የሆነውን «ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ኃላ-ቀርነት ምክንያቱ የተዋህዶ-ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ነው» የሚለውን የቺክ ንድፈ-ሃሳብ በተመለከተ ደግሞ፣ በእንዴትና ለምን በ19ኛው ምዕተ-ዓመት ወደ አገሪቱ በገቡ ኣውሮፓዊ ሚሲዮናውያን እንደተጠነሰሰ፣ እንደተዛመተና ሥር ለመስደድ እንደበቃ የታሪክ ምሁሩ ዴቪድ ቻፕል (Chapple, 1986: 25-39) በማያዳግም ሁኔታ ኣሳይቷል -- ስማ ከተገኘ::

ለልማት አመች ሁኔታን መፈጠር ማለት መሆኑም በበቂ የታዩ ይመስለናል። መጨመር ያለበት ነገር ካለ፣ ይኸን የሥርዓታት ችግር ለመፍታት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎችና የነዚህ የወደፊት ዕጣ-ፋንታ ጉዳይ ነው።

ሕያውና ፋይዳ ያላቸው ሥርዓታት የግድ ሁሉን በእኩል የሚየስተናግዱ፣ የማፈቅዱትና የሚነሱትንም በግልፅ የሚያሳውቁና፣ አንዣራዊ መረጋጋት ያላቸው መሆን እንዳለባቸው ቀደሞ ብለን አሳይተናል። እንደዚህ ያሉ ሥርዓታትም በህብረተሰባችን በበቂ እንደሌሉና፣ ሃገራችን በልማት ጉዳና እንደትራመድና የዜጎቿም የፖለቲካ ነፃነት ዕውን እንዲሆን ከተፈለገ፣ በየህብረተሰባዊ መስኩና በየስራው ዘርፍ ሁሉ የማበጁ ሥርዓታት መቆም እንዳለባቸው በቂ ግንዛቤ የተገኘ ይመስለናል።

በተጨማሪ፣ በዚህ ዕሁፍ የተከተቱት ጭብጦች አንደማያሳዩት፣ ሁሉን በእኩል የማየስተናግዱ ግልፅነትና፣ አንዣራዊ መረጋጋት ያላቸው ሥርዓታት ዕውን መሆን የሚችሉት የፍትህ የበላይነት ሰፍኖ ሁሉም በሕግ ፊት እኩል ሆኖ ሲገኝ ብቻ ነው። ይኸ ሳይሆን ቀርቶ፣ በማንኛውም ዘመናዊ ሕብረተሰብ ዘንድ የሥርዓታት ሁሉ መሠረት የሆነት የህግ ሥርዓታት (legal institutions) የፖለቲካው ሥርዓት የበታችና ጥገኛ ሆነው ከቀጠሉና፣ ከሕግ በላይ ሆነው የሚንቀሳቀሱ መንግሥታዊ አካላትና ባለሥልጣናት በመኖር ከቀጠሉ፣ ወደፊት የሚፈጠሩትም ሆኑ አሁን ያሉት ሥርዓታት ከላይ የተቀመጡትን መመዘኛዎች ሊያሚሉ ስለማይችሉ፣ በስም እንጅ በገቢር አይኖሩም ማለት ነው።

አንድ ጤናማና ታዳጊ የገበያ ኢኮኖሚ ከየትኛውም የኢኮኖሚ ሲስተም በበለጠ የሕግ ሥርዓታትን መኖርና በነሱ ላይ መመሰረትን ይጠይቃል። የሚፈጠሩት ሥርዓታት ተቀባይነት የሰመረ ይሆን ዘንድ የዚህ ዋና አስፈፃሚ የሆነው የመንግሥት አስፈፃሚ ክፍል (executive branch) ከንግድ ሥራ ውጭ ሆኖና የማህል-ቤት ሚና ይዞ፣ ሕግ-አወጭውና ሕግ-ተርጓሚ አካላት ተገቢ ሚናቸውን ይጫወቱ ዘንድ ሁኔታዎችን ከማመቻቸት አልፎ ጣልቃ ሳይገባባቸው የአስፈፃሚ ተግባሮቹን ብቻ ማከናወን አለበት።

በተጨማሪ፣ ሥርዓታት በመሰረቱ የደንቦች ሰብስብ እንደመሆናቸው እነዚህን ደንቦች የሚደነግገው ሕግ-አወጭው አካል የተሟላ ሕጋዊነትና ተቀባይነት ያለው (ሌጅቲሚት) መሆኑ ወሳኝነት አለው። ስለዚህ የሕብረተሰቡን ዋናዋና ሥርዓታት በደንጋጌ ማቆም የሚኖርበት የሕዝቡ ተወካዬች የተሰባሰቡበት ምክር-ቤት ወይንም ይኸ ምክር-ቤት ሕገ-መንግሥታዊ አስራርን ተከትሎ ውክልና የሰጣቸው አካለት ብቻ መሆን አለባቸው።

የልማትንና የዴሞክራሲን ግንኙነት በተመለከተ አንዳንድ በፀጥታ መታለፍ የሌለባቸው ጥያቄዎች አሉ። እነሱም፣ በተለያዩ ጊዜና የአለም ክፍሎች እንደነ ሲንጋፖር፣ ደቡብ ኮሪያና ታይዋን ያሉ ሃገሮች በሕዝብ በተመረጡ የሕዝብ ተወካዬች ምክር-ቤቶችና መሪዎች አማካይነት ሳይሆን እንዲያውም ብሩህና በጐ አመለካከት ባላቸው ግን «ፈላጭ-ቆራጭ» በሆኑ አገዛዞች አማካይነት አይደለም ወይ ብርቱና መልካም ሥርዓታት ገንበተው ወደ ልማት የመሩት? ከዚያስ በኋላ አይደለም ወይ የፖለቲካ ነፃነትንና ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን ለመቀዳጀት የበቁት? የሚሉት ጥያቄዎች ናቸው (Zakaria, 2004: 55-58)። ሆኖም፣ ምንም እንኳን ይኸ ከላይ የተጠቀሰው ሁኔታ በታሪክና በዕንሰ-ሃሳብ ደረጃ ዕውንነት ቢኖረውም፣ ይኸ እንደ ኢትዮጵያ ላለ፣ በሕዝብ ብዛቱና በመሬት ሥፋቱ ግዙፍ ለሆነ፣ በአንድ-ወጥነት ሳይሆን በተለያዩ ባሕርያቱ ለታወቀ፣ ለበርካታ የተቆላለፉ ተፈጥሯዊና ሕብረተሰባዊ ችግሮች

ለተጋለጠ አገር ተጨባጭ አማራጭ አይደለም። የኢትዮጵያን የሶሺዮ-ኢኮኖሚክና የፖለቲካ ችግሮች ለመፍታት ሰፊ ሕጋዊነትና ተቀባይነት ያለው (ሌጅቲሜት የሆነ) የፖለቲካ ሥርዓትና ሰፊ ሕጋዊነትና ተቀባይነት ያላቸው መፍትሄዎች ያሻሉ። እነዚህን ደግሞ ከተሟላ ዴሞክራቲክ አስተዳደር ውጭ ማግኘት የማይታሰብ ይመስለናል።

ዴሞክራሲ በበኩሉ ለፖለቲካ ሥልጣን የሚፎካከሩ ኃይሎችን ግጥሚያ የሚመለከት በመሆኑ፣ ፉክክሩ ከልክ አልፎ ራሱን የዴሞክራሲ አስተዳደሩን አደጋ ላይ እንዳይጥለው ያስፈልጋል። ታዲያ በዲሞክራሲያዊ ፉክክር ውስጥ ተፎካካሪዎቹ ሊወስዷቸው የሚችሉት እርምጃዎች ፍፁም ክፍት ሆነው ለተፎካካሪዎቹ መልካም-ፈቃድ ብቻ ከተተው (አካሄዱ voluntaristic ከሆነ) ለዴሞክራሲ አይበጅም። በተቃራኒው፣ የተፎካካሪዎቹ የውሳኔ ምርጫዎችና እርምጃዎች በሥርዓታት በመታቀብ ወግ በተከተለ (normative በሆነ) መንገድ የሚመሩ ከሆነ ደግሞ ዴሞክራሲ የበለጠ የመስመር ዕድል ይኖረዋል። በዚህ ዓይነት የሥርዓታት መኖር መልሶ ለዴሞክራሲ መገኘት ከፍተኛ አስተዋፅኦ ያደርጋል ማለት ነው (VonDoep and Villalón, 2005: 15-16)::[11]

ዴሞክራሲን በተመለከተ አሁንም መታየት ያለበት አንድ ተጨማሪ ቁም ነገር አለ። ዴሞክራሲ ወይንም የህዝብ-አገዛዝ የተረጋገጠበትን አስተዳደር ዕውን ለማድረግ መሟላት ካለባቸው በርከት ያሉ ሁኔታዎች ውስጥ አንዱ እውነተኛ አገርነት-መንግሥትነት (stateness) ሲሆን፣ ይኽም ባንድ በኩል ይገዛል በተባለው «ሕዝብ» ማንነት ላይ ግልፅ መሆንን የሚመለከት ሲሆን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የመንግሥትን በበቂ የተደራጀ መሆንን ይመለከታል። በሌላ አባባል፣ ዴሞክራሲ የሃገር-መንግሥትን (የstateን) በብቁ የሥርዓታት አውታር ላይ መመስረት ይጠይቃል። አንድ ሃገር-መንግሥት (state) ቀጣይነት ያለው ዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ባለቤት ይሆን ዘንድ የግድ የሥርዓታት ባለቤትም መሆን ያሻዋል ማለት ነው።

እንደ ማላዊ ያሉ የአፍሪካ ሃገሮች ፈላጭ-ቆራጭ አገዛዝን አሽቀንጥረው በመጣል ከትክክለኛ ምርጫ በተገኙ ዴሞክራሲያዊ መንግሥታት መተዳደር ከጀመሩ ውለው አድረዋል። ሆኖም፣ እንደተጠበቀው ልማትና ብልፅግናን በመቀዳጀት ፋንታ ኢኮኖሚያቸው እያደር በማሽቆልቆሉ ሕዝባቸው ለከፋ ረሃብና የኑሮ ችግር ተጋልጧል። (Hammer, 2005) ይኽ አነጋጋሪ ሁኔታ የሚያሳዩንም ዴሞክራሲ ያስፈላጊነቱን ያህል፣ ልማትን ለማስገኘት ግን ብቻውን በቂ አለመሆኑን ነው።

ከላይ የተነበበው ሲጠቃለል፣ ዴሞክራሲ የግድና ሁልጊዜ ልማትን ያስከትላል የሚል ድምዳሜ ላይ አያደርስም። ለማስየት የተፈለገው፣ ዴሞክራሲ ለእድገት ብቻውን በቂ ቅድመ-ሁኔታ ባይሆንም ቅሉ፣ ሃገራችን ባለችበት ሁኔታ ግን አስፈላጊ መሆኑን ነው።

---

[11] በተጨማሪ፣ እነዚሁ ፀሃፊዎች Mozffar ከተባለ ሌላ የፖለቲካ ሣይንስ ምሁር የወሰዱትን የማከተለውን ጠቃሚ ጥቅስ አስፍረዋል።
To produce democracy is to craft institutions. To craft institutions is to design rules that, in the first instance, authorize the restrained exercise of power in public life by both the governors and the governed. And to the extent these rules also encourage accommodation, compromise, and tolerance of diverse opinions, protracted functioning democracies produce rather than reflect a civic "political" culture... in which emancipatory projects might evolve (quoted in VonDoep and Villalón: 2005: 10).

በሌላ በኩል፣ ዴሞክራሲን ወይም የህዝብ የበላይነት የተረጋገጠበት የፖለቲካ ሥርዓትን ዕውን ለማድረግ መሟላት ካለባቸው በርከት ያሉ ቅድመ-ሁኔታዎች መካከል አንዱ፣ ራሱ ልማትና ቢያንስ መለስተኛ የተመቻቸ የኑሮ ደረጃ (ወይም የህዝቡ ኑሮ ከድህነት ወለል በላይ መገኘት) መሆኑን አንዳንድ ምሁራን ይጠቁማሉ (VonDoep and Villalón, 2005: 4)። ይኸ የሚያመለክተን በልማትና በዴሞክራሲ መካከል ያለው ምክንያታዊ ግንኙት (causal realtionship) በሁለቱም አቅጣጫ የሚሄድ፣ ማለትም ዲያሌክቲካዊ መሆኑን ነው።

ከዚህ ሁሉ የምንረዳው ደግሞ፣ በሥርዓታትና በልማት፣ በሥርዓታትና በፖለቲካ ነፃነት/ዴሞክራሲ፣ እንደገና ደግሞ በልማትና በፖለቲካ ነፃነት/ዴሞክራሲ መካከል ባለሁለት አቅጣጫ የሶስትዮሽ ምክንያታዊ ግንኙነቶች ስላሉ፣ ቁርኝቶቹ ውስብስብ መሆናቸውን ነው። በተጨማሪ፣ በዚህ የሶስትዮሽ የምክንያታዊ ግንኙነቶች የግንዛቤ-ቅያስ (conceptual framework) ውስጥ እጅግ ወሳኝ የሆነው የግለሰብና የድርጅት ሚናም በውስጠ-ታዋቂነት መካተቱን ልብ እንበል።[12]

ከሶሻል ሳይንስ ዓላማዎች አንዱ፣ የዛሬውን ሁኔታ አጥንቶ የሁኔታውን የሂደት አቅጣጫ በመገንዘብ፣ እጅግ በተቆጠበ ደረጃ ስለነገው አንዳንድ የወደፊት ግምቶች ወይም ትንቢቶች መሰንዘር ነው። ትንቢቶቹ በጥንቃቄ መቀመጥ አለባቸው ሲባል ደግሞ፣ የህብረተሰብ እርምጃ ሁልጊዜ ወደፊትና በተስተካከለ ፍጥነት የሚሄድ ሳይሆን፣ ወደፊትና ወደኋላ እናም የያዝ-ለቀቅ አካሄድ የበዛበት መሆኑ ታሳቢ መሆን አለበት ማለት ነው።

ዛሬ፣ በ1998 የገና በዓል ዋዜማ ላይ ሆነን ኢትዮጵያ ከአንድ ትውልድ በኋላ በሥርዓታት ግንባታ፣ በልማትና በፖለቲካ ነፃነት/ዴሞክራሲ አንፃር ልትገኝ የምትችልበትን ሁኔታና ልታስመዘግብ የምትችለውን ዕርምጃ ልናልም ስንሞክር (የፖለቲካ አቋማችን የፈለገውን ቢሆንም) ራዕያችን የጨገገ እንደሚሆን መቀበል ይኖርብናል። ሆኖም፣ የህብረተሰብ እርምጃን

---

[12] በህብረተሰባዊ ከዋኝና-መዋቅር (agency-structure) መካከል ያለው ግንኙነት በርካታ ሶሲዮሎጂስቶች በሰፊው ያተቱበት እና የተከራከሩበት ጉዳይ ነው። አመለካከቶታቸውም በሁለት ዋና ነጥቦች ላይ ይለያያል። የመጀመሪያው የልዩነት ነጥብ፣ ከዋኝ (agency) አንድን ነገር የሚያከናወነው ሆን ብሎና አስቦ በመነሳት ነው ወይ? የሚለውን ጥየቄ የሚመለከት ነው። በዚህ ላይ፤ አንዳንዶቹ ተዬሪተሺያኖች የከዋኙን ሙሉ «ዕርምጃውን ሆን ብሎና በነፃ መርጦ የመውሰድ» ችሎታ ሲቀበሉ፤ ሌሎቹ ደግሞ ይህን ችሎታ አጥብበው ያዩታል፤ አሁንም ሌሎች እጅግ ያቃልሉታል (Ritzer, 2000: 413-4)።
ሁለተኛው የልዩነት ነጥብ ከዋኝ (agency) ግለሰብ ተዋናይ ነው ወይስ ብዙ ግለሰቦችን የሚያቅፈው ሰብሰብ (collectivity)? ለሚለው ጥያቄ የሚሰጠውን መልስ የሚመለከት ነው። አንተኒ ጊድንስንና በርዲዩን የመሳሰሉት ከዋኝን እንደ ግለሰብ ተዋናይ በቻ አድርገው ወደ መውሰዱ ሲያዘነብሉ፤ አንደ «አክሽናሊስት-ሶሲዮሎጅስቱ»፤ ተራን ያሉት ደግሞ ከዋኝን በማያሻማ መንገድ እንደ ድርጅት ብቻ አድርገው ይቀበሉታል። «የአክተር-ሲስተም ዳይናሚክስ» ተዬሪተሺያኖቹ እነ ተም በርንስ በበኩላቸው ሁለቱም፣ ማለትም ግለሰብ ተዋናይና የግለሰቦች ሰብሰብ (individual or collectivity) ከዋኝ ሊሆኑ እንደሚችሉ በማረጋገጥ መሃል-ቤት አቋም ይዘዋል (Ritzer, 2000: 413-4)።
በበኩላችን፤ ይህን በመጨረሻ የተጠቀሰውን አቋም በመጋራት ግለሰብና ሰብሰብ ህብረተሰባዊ ተዋናዬች፣ ሁለቱም፤ የከዋኝ ሚና እንደሚጫወቱ አድርገን እንረዳለን። በተያያዥም ከዋኝ የሆነ ግለሰብ ወይም ሰብሰብ ተዋናይ ዕርምጃውን ሆን-ብሎና በነፃ መርጦ የመውሰድ ችሎታ እንዳለውና በህብረተሰባዊ መዋቅር የታሰረ እንዳልሆነ ስንቀበል፤ በተቃራኒው፤ ከዋኙ ዕርምጃዎቹን የሚመርጠውና የሚወስደው በባዶ አካባቢ ሳይሆን ሥርዓታትን ጨምሮ፤ በተወሰነ/በተሰጠ ተፈጥሯዊ-ቁሳዊ-ህብረተሰባዊ ሁኔታ ውስጥ እንደሆነ አድርገን እንረዳለን። በዚህ ዓይነት፤ ድርጅቶች የምንላቸውም የግለሰብ ተዋናያን የተደራጁ ሰብስቦች አንድ ዓይነት ዕርምጃቸውን ሆን-ብለውና በነፃ አማርጠው መውሰድ የሚችሉ ከዋኖች ናቸው። በመሆናቸውም ከሥርዓታት፤ ከፖለቲካ ነፃነት/ዴሞክራሲና ከልማት ጋር ያላቸውን ግንኙነት የምንረዳው በሶስቱም ረድኅ አዳዲስ ቅድጅቶችንና የማሻሻያ ለውጦችን ለማምጣት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወቱ ከዋኖች አድርገን ነው። ስለዚህ፤ በራሱ በዚህ ባነሳነው «ሥርዓታት-የፖለቲካ ነፃነት/ዴሞክራሲ-ልማት» የሶስትዮሽ ቁርኝት ውስጥ ግለሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች በከዋኝነት ተንሰራፍተው የሚገኙ በመሆኑ፤ ግንዛቤው የግለሰብና የድርጅት ሚናን አያንኳስስም። (ልክ ስለ ደም-ዝውውር ሲነገር ደምን እንደ አንዱ የገዝውውሩ አካል እንደሆኑት እንደ ልብ፤ የደም-ሥሮችና ሳንባ አለመውሰዱ የደምን ሚና መርሳት እንዳለመሆኑ ማለት ነው።

አባጣ-ጐርባጣነት አገናዝበን ከተገኘን ደግሞ የዛሬው የፖለቲካ ደመና በፍጥነት ሊገልጥና ብሩህ የዴሞክራሲና የልማት ዘመን በቅርቡ ወይም በቅርብ-ሩቁ ሊከሰት የሚችልበት የተስፋ ክፍተት መኖሩን እንረዳለን። ይኸን ታሳቢ በማድረግ፣ ከአንድ ትውልድ በኋላ፤ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ፣ የሥርዓታት ብዛትና ጥንካሬ አይነተኛ መልኩ የሆነ፤ የሕግ-የበላይነት፣ የፖለቲካ ነፃነትና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት እና፤ ፈጠን ልማት የሚያስመዘግብ ይሆን ዘንድ ተስፋ እናደርጋለን። ይህንንም ተስፋ ዕውን ለማድረግ በሥርዓታት ምስረታና ለዚህ አሰፈላጊ በሆኑት ጉዳዬች ላይ ማትኮር ዋና ቁምነገር መሆኑን በእንደገና በአፅንኦት እናሳስባለን።

እግረመንገዳችንንም፣ በሶሻል ሳይንስ እና በተዛማጅ የዕውቀት ዘርፎች የተሰማሩ ምሁራንም በዚህ ረገድ ሰፋፊ ኢንተር-ዲሲፕነሪ ጥናቶች በማካሄድ ጠቃሚ ጭብጦችን ማስገኘትና አማራጭ የድርጊት ጉዳናዎችን ማመልከት እንደሚጠበቅባቸው መጠቆም እንፈልጋለን። ለተለያዩ የሶሻል ሳይንስ ምሁራንም፣ ሥርዓታትን እንደ ህብረተሰባዊ የደንቦች ጥንቅር መገንዘቡ ራሱ የሚግባቡበት የጋራ ቋንቋ (common grammar) ስለሚያስገኝላቸው፣ በሥርዓታት ላይ ያተኮሩ ኢንተር-ዲሲፕሊነሪ ሥራዎቻቸው ይሰምሩ ዘንድ ይረዳቸዋል።

ከዚህ በተረፈ፣ የንግዱም ማኅበረሰብ ሆነ የተለያዩ የሲቪል ማኅበረሰቡ አካላት፣ ለሥርዓታት ግንባታና መስተካከል መታገል ማለት ለመብታቸው መጠበቅና መጐልበት ዘላቂ መሠረት መስጠት መሆኑን በመረዳት፣ ትኩረታቸውን ወደዚህ ተግባር ጭምር ማዞር እንዳለባቸው ሊገነዘቡ ይገባል። በዚህ ተግባር ላይ ማተኮሩ፤ የሲቪል ማህበረሰቡን የማሳወቅ፣ የማነቃቃትና፣ የአቡካቶ (advocacy) ሥራዎች ይበልጥ ውጤታማ በማድረግ የመደራጀቱን ተግባር የሚያግዝ እንጅ የድርጅትን ሥራ የሚጫረት እንዳልሆነ በመረዳት በሙሉ-ልብ መንቀሳቀስ አለባቸው።

እናሳርግ። የተሟላ ሥርዓት መኖር ለልማትና ለዴሞክራሲ መከሰት በቂ ላይሆን ይችላል፣ ግን እጅግ አስፈላጊ ነው። መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላትን ጨምሮ የሚመለከተው የህብረተሰብ ክፍልና አባል በሙሉ ከተዋደቀበት ደግሞ ሊከናወን የሚችል ነው። የሚያስፈልጉት፣ በጎ-ፈቃድ፣ ቁርጠኛነትና ታታሪነት ናቸው።

ዋቢ ጹሑፎች

Atakilte Beyene. 2003. *Soil conservation, Land Use and Property Rights in Northern Ethiopia: understanding environmental change in smallholder farming systems.* Doctoral Thesis. University of Agricultural Sciences. *Acta Universitatis Agriculturae Sueciae. Agraria 395.* Uppsala.

Bahru Zewde. 2000ª. "The Problems of Institutionalization in Modern Ethiopia: A Historical Perspective." In Alemu Mekonnen and Dejene Aredo, eds., *Institutions, Resources and Development in Ethiopia, Proceedings of the Ninth Annual Conference on the Ethiopian Economy,* PP. 87-112. Ethiopian Economic Association and Department of Economics, Addis Ababa University. Addis Ababa.

Bahru Zewde. 2000ᵇ. "Archives and Historical Research." In Zenebework Tadesse (ed). *Development and Public Access to Information in Ethiopia, Proceedings of the Symposium of the Forum for Social Studies Addis Ababa, 25 March 1999.* Forum for Social Studies. Addis Ababa.

Bahru Zewde. 2002. "Systems of Local Governance among the Gurage: the *Yajoka Qicha* and the *Gordana Sera*". In Bahru Zewde and Siegfried Pausewang (eds), Ethiopia: the Challenge of Democracy from Below. Nordiska Afrikainstitutet and Forum for Social Studies. Uppsala and Addis Ababa.

Berry, Sarah. 1989. Social Institutions and Access to Resources, *Africa* 59: 41-55.

Bromley, D. W. 1991: *Environment and Economy: Property Rights & Public Policy,* Blackwell, Oxford & Cambridge.

Burns, Tom. R., and Helena Flam. 1987: *The Shaping of Social Organization,* Sage Publications, London.

Burns, Tom. R., T. Baumgartner and P. DeVille. 1985: *Man, Decisions, Society: the Theory of Actor-System Dynamics for Social Scientists,* Studies in Cybernetics: 10, Gordon Breach, New York.

Chappel, David. 1986."Protestant Missionary Attitudes in Ethiopia: Gobat, Isenberg and Krapf". *Proceedings of the Third Annual Seminar of the Department of History.* Addis Ababa University. Addis Ababa.

Daniel Admassie. 2000. "Information Technology: Usage and Access." In Zenebework Tadesse (ed). *Development and Public Access to Information in Ethiopia, Proceedings of the Symposium of the Forum for Social Studies Addis Ababa, 25 March 1999.* Forum for Social Studies. Addis Ababa.

Dahl, Robert A. 1978.*Polyacrchy: Participation and Oppositon.* Fifth printing. Yale University Press. New Haven and London.

Dejene Aredo. 2000. "A Conceptual Framework: The New Institutional Economics." In Alemu Mekonnen and Dejene Aredo, eds., *Institutions, Resources and Development in Ethiopia. Proceedings of the Ninth Annual Conference on the Ethiopian Economy,* PP. 87-112. Ethiopian Economic Association and Department of Economics, Addis Ababa University. Addis Ababa.

Dessalegn Rahmato. 1997. Manufacturing Poverty: Rural Policy and Micro-Agriculture. Institute of Development Research, Addis Ababa University. Addis Ababa

Ege, Svein. 1997. The Promised Land: The Amhara Land Redistribution of 1997. Working Papers on Ethiopian Development, No. 12. Trondheim: Norwegian University of Science and Technology. Center for Environment and Development.

Gebrè-Hèywot Baykedagne. 1993 (1912). (አጤ ምኒልክና ኢትዮጵያ) *L'Empereur Menelik & L'Ethiopie*. Maison Des Etudes Ethiopiennes. Institut National Des Langues et Civilizations Orientales. Addis-Abeba/Paris

Hammer, Joshua. 2005. "Freedom is not Enough: Malawi got free elections and a free press more than a decade ago, but food crises have only grown worse." Newsweek International. Vol.CXLVI, No. 20. November 14, 2005

Hoben, Allan. 2001. Ethiopian Land Tenure Revisited: Continuity, Change, and Contradictions. Paper presented at the Institute of Development Research's Conference on Land Issues. April 6-7, 2001. Addis Ababa

Johnson, Allan. 1995. *The Blackwell Dictionary of Sociology: A User's Guide to Sociological Language*. Blackwell Publishers. Cambridge Massachusetts and Oxford

Leach Melissa., R. Mearns & I. Scoones. 1999: Environmental Entitlements: Dynamics and Institutions in Community-Based Natural Resource Management, *World Development* 27: 225-247

Long, Norman. 2001. *Development Sociology: Actor Perspectives*. Rutledge. London and New York.

Melaku Bekele. 2003. *Forest Property Rights, the Role of the State and Institutional Exigency: The Ethiopian Experience*. Doctoral Thesis. University of Agricultural Sciences. *Acta Universitatis Agriculturae Sueciae. Agraria 409*. Uppsala

North, Douglas C. 1991: "Institutions, Journal of Economic Perspectives", *Journal of Economic Perspectives*, 5 (1), 97-112.

North, Douglas C. 1990: *Institutions, Institutional Change and Economic Performance*. Cambridge University Press, Cambridge.

Peters, Pauline E. 2000: "Grounding Governance: Power and Meaning in Natural Resource Management", Keynote address to the International Symposium on Contested Resources: Challenges to Governance of Natural Resource in Southern Africa, University of the Western Cape, October 2000.

Ritzer, George. 2000. *Modern Sociological Theory*, Fifth Edition. McGraw-Hill Higher Education. Boston, New York, London, New Delhi, etc.

SafeCarGuide.com, Inc. 2003-2004. *International Injury & Fatality Statistics*. (http://www.safecarguide.com/exp/statistics/statistics.htm)

Teferi Abate. 2000. *Government Intervention and Socioeconomic Change in a Northeast Ethiopian Community: An Anthropological Study*. Ph.D. Dissertation, Boston University.

Tekie Alemu. 2000. Insecure Land Tenure Regimes and Soil Conservation. Paper number 21, presented at a Symposium for Reviewing Ethiopia's Socioeconomic Performance 1991-1999. Addis Ababa.

Teketel Abebe. 1998. *'Tenants of the State'*. Lund Dissertations in Sociology 24, Department of Sociology. Lund University, Lund

Tenna Shitarek, Sintaheu Manaye and Berihun Abebe. 2001. Strengthening User-Rights over Local Resources in Wollo, Ethiopia. Issue paper no. 103, International Institute for Environment and Development. London

VonDoepp, Peter, and Leonardo A. Villalón. 2005. "Elites, Institutions, and the Varied Trajectories of Africa's Third Wave Democracies" In Villalón, Leonardo A., and Peter VonDoepp (eds), *The Fate of Africa's Democratic Experiments: Elites and Institutions*. Indiana University Press. Bloomington and Indianapolis.

Yacob Arsano. 2002. "*Seera* a Traditional Institution of Kambata ". In Bahru Zewde and Siegfried Pausewang (eds), Ethiopia: the Challenge of Democracy from Below. Nordiska Afrikainstitutet, Uppsala and Forum for Social Studies, Addis Ababa.

Yeraswork Admassie. 2000 (1995). *Twenty Years to Nowhere: Property Rights, Land Management and Conservation in Ethiopia*. Red Sea Press. New Jersey.

Yeraswork Admassie. 2000. "Social Science Research and Access to Information." In Zenebework Tadesse (ed). *Development and Public Access to Information in Ethiopia, Proceedings of the Symposium of the Forum for Social Studies Addis Ababa, 25 March 1999.* Forum for Social Studies. Addis Ababa.

Yeraswork Admassie and Fantu Guta. 2003. "Spatial Population Balance and Rural Viability in Ethiopia." Module 6, Roles of Agriculture (ROA) Project, FAO and Ethiopian Economic Association. Addis Ababa.

Yigremew Adal. 1997. "Rural land holdings readjustment in West Gojam, Amhara region." Paper presented at the Workshop on Access to Land and Resource Management in Ethiopia, organized by the Land Tenure Project of Addis Ababa University, Nov. 28-29, 1997. Addis Ababa.

Zakaria, Fareed. 2004. *The Future of Freedom: Illiberal Democracy at Home and Abroad.* Horton & company. New York and London

Zikre Hig of the council of the Amhara National State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia. 5th Year No.46. Proclamation No. 46/2000: Proclamation Issued to Determine the Administration and Use of the Rural Land in the Amhara National Region. August 5, 2000. Bahir Dar.

ኪዳነወልድ ክፍሌ:: 1948 (እ.ኢ.አ):: መፅሐፈ ሰዋስው ወግሥ፤ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ:: በደስታ ደክለወልድ የታተመ:: አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት:: አዲስ አበባ::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል:: 1993 (እ.ኢ.አ):: አማርኛ መዝገበ ቃላት:: አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ:: አዲስ አበባ::

በዶ/ር የራስወርቅ አድማሴ ጽሑፍ ላይ የተሰጠ አስተያየት

ያዕቆብ አርሳኖ*

የጽሑፉ አቅራቢ "ሥርዓታት፣ የፖለቲካ ነፃነትና ልማት በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ የሥርዓታትን ምንነትን፣ የሥርዓታትን ፋይዳ፣ ሥርዓታት በኢትዮጵያ ቀደምት ሁኔታዎችንና ሥርዓታት በኢትዮጵያ አንዳንድ ጊዜያዊ ችግሮችና መፍትሔዎቻቸውን በመተንተን አቅርበዋል::

ለማንኛውም ሀብረተሰብ የሰመረ ሕልውናና ዕድገት ጠንካራና ሕያው ሥርዓታት ወሳኝ መሆናቸውን፣ ዘርፈብዙ የሆኑት ሥርዓታት ለኅብረተሰቡ ያላቸው ፋይዳ መተኪያ የሌለው መሆኑን፣ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ዋና ዋና ተግባራትን ለማከናወን ሥርዓታት በበቂ የሌሉት መሆኑን፣ ፈጣን ዕድገት ለማምጣትና ከድህነት አረንቋ ለመውጣት ሕያው፣ ጠቃሚ፣ እና ድርጊት አጋዥ የሆኑ ሥርዓታትን መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን፣ ሥርዓታት ለኅብረተሰብ ፋይዳ የሚኖራቸው የሕግ በላይነት ሲረጋገጥና መንግሥትን ጨምሮ ሁሉም በሕግ ፊት እኩል ሲሆን ብቻ መሆኑንና ለዚህም የተሟላ የፖለቲካ ነፃነትን ማስፈን እንደሚያስፈልግ የሚያስመዘግቡ ፍሬ ሀሳቦች በጽሑፉ ቀርበዋል::

የጽሑፉ ዓላማ ሥርዓታት ከሶስዮ-ኢኮኖሚ ልማት ጋር ያላቸውን ትስስር ማሳየትና ያላቸውን ፋይዳ ማመልከት መሆኑ ተገልጿል:: ጽሑፉ የሚያተኩረውም በኢትዮጵያ የሥርዓታት ጉዳይ ላይ መሆኑ ተመልክቷል::

አቅራቢው "አከተር ሲስተም ዳይናሚክስ ቲዎሪ" ተማሪና አቀንቃኝ መሆናቸው፣ ከኢንስቲቱሺናል ኢኮኖሚክስ ጸሐፊዎችና መሰል አቋም ካላቸው የፖለቲካ ሳይንስና የታሪክ ተመራማሪዎች ሀሳብ ጋር የሚጋሩ መሆኑን አሥምረውበታል::

በጽሑፉ መነሻ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ዋና ዋና ተግባሮቹን የሚያከናውንባቸው ሥርዓታት በበቂ የሌሉት መሆኑን ጸሐፊው አስገንዝበዋል:: በሳቸው እምነት፣ የኢትዮጵያ የልማት ችግር መያዣ መጨበጫ ከጣው "ኋላ ቀር" ባሕል ምክንያት ነው ከሚለው ብሾፓ ጋር ሳይሆን፣ በተጨባጭ ከሚታይና ሊወገድ ከሚችል ክስተት ጋር ነው:: በዚህ የተነሣ የደራሲው አይታ አዎንታዊ ነው:: ተስፋ መቁረጥን ሳይሆን ለድርጊት ተነሳሽነትን ይጋብዛል::

---

* ዶ/ር ያዕቆብ አርሳኖ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት ክፍል ረዳት ፕሮፌሰር ሲሆኑ በማስተማርና በምርምር ሥራ ላይ ይገኛሉ:: ዶ/ር ያዕቆብ ካሳተሟቸው መጻሕፍት ውስጥ Traditional Institutions of Kembata የሚል ከUppsala ዩኒቨርሲቲና ከማህበራዊ ጥናት መድረክ ጋር አሳትመዋል:: አሁን ደግሞ National Hydro Politics Nile and Ethiopia የሚል በማሳተም ላይ ይገኛሉ::

የሥርዓታትን ምንነት በተመለከተ ቀደምት ሥነ ጽሑፎችንና በመስኩ አንቱ የተሰኙ ሊቃውንትን ዋቢ በመጥቀስ የሥርዓታትን ትርጉም ደራሲው አብራርተዋል። ሥርዓታት የሰዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት መልክ የሚያስይዙ መሆናቸው ገልጸዋል። በተጨማሪም እንደ እርሞች፣ ወጎች፣ ልማዶች፣ ሥነ ምግባሮች የመሳሰሉ ሥርዓታት "ደርገ የለሾች"፣ እንደ ደንቦች፣ ሕገ-መንግሥቶች፣ ሕጎች፣ የንብረት መብቶች ያሉት "ደርገ ያላቸው" በማለት አብራርተዋል።

ሥርዓታት የመሪ ሀሳቦች ጥንቅር መሆናቸው ተሠምሮበታል። ስለሆነም ሥርዓታት ከድርጅት የተለዩ መሆናቸውን ጸሐፊው በጥልቀት አብራርተዋል። ሥርዓታትን በደረጃ መልክ በመለየት ጎብረተሰብ አቀፍ ሥርዓታትና መስክ ተኮር ሥርዓታት በማለት ለይተው አብራርተዋል።

የሥርዓታት ፋይዳን በማስመልከት ጸሐፊው ሶሻል ካፒታል እንዲዳበር የማድረግ ፋይዳን ጨምሮ 8 ዓይነት የሥርዓታት ፋይዳዎችን አቅርበዋል። ሥርዓታት ለጎብረተሰቡ በሚሰጡት ወሳኝ አገልግሎት የተነሳ አማራጭ የሌላቸው ጠቀሜታ እንዳላቸውም አብራርተዋል።

በቀደምት ሁኔታዎች አንባር ሲጫን ሥርዓታት በኢትዮጵያ አገር በቀል መሆናቸው ችግሮቻቸውም ከዚሁ ሁኔታ ጋር የተያያዙ እንደሆኑ በጸሐፊው ተብራርቷል። በተለያዩ የኢትዮጵያ አካባቢዎች ታላላቅ መንግሥታዊና ልማዳዊ ባለ ደርገና ደርገ የለሽ ሥርዓታት ፈልቀው የየዘመናቸው ሁኔታ በሚጠይቀው መንገድ ሲሰራባቸው መቆየቱን ደራሲው አስገንዝበው፤ የንጉሥ፣ የርስት፣ የገባር፣ የጉልት፣ የገዳና የኢጀካ ሥርዓታትን በምሳሌነት ተጠቅሰዋል። ካለፉት 150 ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ ማዕከላዊ መንግሥት ማንሰራራቱን በማውሳት ሀገሪቱ ግን የሥርዓታት እጦት እንዳልተለያት ጸሐፊው የዚያን ዘመን ምሁራንን ዋቢ በመጥቀስ አብራርተዋል።

ከኢጣሊያን ወረራ ጥቂት ዓመታት ቀደም ብሎና ጠላት ከተሸነፈ በኋላ በኢትዮጵያ መንግሥታዊ ሥርዓታት በስፋት መዘርጋታቸውን አውስተዋል። የተዘረጉት ሥርዓታት ለሀገሪቱና ለሕዝቧ ፍትህን ያሰፈኑ እንዳልነበሩና በአውቶክራሲው አገዛዝ ከመሸበብ እንዳላመለጡ አውስተዋል።

የ1966ቱ አብዮት ቀደም ሲል የተገነቡትን ሥርዓታት እንደአፈራረሰው፣ ከሥርዓታት አንባር አገሪቱ የኋልዮሽ መሄዷን፣ መዋቅር መዘረጋት፣ ወዲያውም በሌላ መዋቅር መተካት ዋና የደርግ መንግሥት ተግባር መሆኑንና ሀገሪቱም የሥርዓት አና ሆና እንደነበረች ጸሐፊው አብራርተዋል።

የደርግ መንግሥት ተወግዶ የኢህአዴግ መንግሥት ሥልጣን ከጨበጠ ወዲህ የሥርዓታት ምሥረታ መካሄድ መጀመራቸውንና በአንጻራዊ ደረጃ አገራችን ወደ ሥርዓታት ጎዳና ማምራቷን ጸሐፊው ተንትነዋል። ነገር ግን ሥርዓታቱ ገና ያልተሟሉና በብዙ ጥያቄ ውስጥ ያሉ መሆናቸውን አስገንዝበዋል።

የሥርዓታትን ጊዜያዊ ችግሮች በኢትዮጵያ አስመልክተው ደራሲው እንደሚከተለው አብራርተዋል፡፡

1. የመ.ያ ትምህርት የመስፋፋቱን ያህል ከልማት ተግባር ጋር ቀጥተኛ የቅንጅት ሥርዓት አልተበጀም፡፡ የግል ተነሳሽነትና የፈጠራ ችሎታ ከፍ እያለ ቢመጣም የጥራት ዕድገቱና ወደ ፋብሪካ ደረጃ የማሳደጉ ሥርዓት ገና ነው፡፡
2. የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ የልማት መሣሪያ የመሆኑን ያህል በተገቢው መጠን የመስፋፋቱና ጥቅም ላይ የመዋሉ ሥርዓት ለግለሰቦች በጎ ፈቃድ የተተወ ይመስላል፡፡ እስከ ዛሬ ድረስ የብሔራዊ ቤተመዝገብ ሥርዓት በአገሪቱ ውስጥ አልተበጀም፡፡
3. በገጠርም በከተማም መንገዶች እየተስፋፉና ደረጃቸው እየተሻሻለ ቢሄድም በትራፊክ ሥርዓት ደካማነት የተነሳ ብዙ ሕይወትና ንብረት ይወድማሉ፡፡
4. በኢትዮጵያ የንብረት መብቶች ሥርዓት ጉድለት ከሁሉም ቁንጮ የሆነ የሥርዓት እጦት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የመሬት ፖሊሲ ችግር የመሬት መበጣጠቅን አስከትሏል፡፡ ይህም የድህነት መባባስን አስከትሏል፡፡ የተወረሱ የግል ቤቶች ለሕጋዊ ባለቤቶች አልተመለሱም፡፡ አዲስ የግል ቤቶች እንዲሰሩ ግን መሬት በሊዝ እየተሰጠ ነው፡፡

የመንግሥት ቢሮክራሲ ሥርዓት ችግርን አስመልክተው ደራሲው ሲያብራሩ፣ የሥራ ምደባና የሹመት ሥርዓት የተደበላለቁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ነፃ ሬዲዮና ነፃ ቴሌቭዥን ፈጽሞ የሹመት ሥርዓት የተደበላለቁ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡ ነፃ ሬዲዮና ነፃ ቴሌቭዥን ፈጽሞ አለመፈቀድና የነፃ ዜና አገልግሎት አውታሮች አለመኖር የነፃ ፕሬስ ሥርዓት የአለመኖር ማረጋገጫ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ጸሐፊው ጽሑፋቸውን ሲያጠቃልሉ በኢትዮጵያ ሕያውና ሩይዳ ያላቸው ሥርዓታት እጦት መኖሩን፣ ሁሉን በእኩል የሚያስተናግዱ፣ ግልጽነትና አንፃራዊ መረጋጋት ያላቸው ሥርዓታት እውን የሚሆኑት በፍትህ የበላይነት መሆኑን፣ የሀገሪቱ የንግድ ሥርዓት ከሕግ አስፈጻሚው አካል ሽሚያ ነፃ መሆን እንዳለበት፣ በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አግባብ የፖለቲካ ፉክክር በተፎካካሪዎች መልካም ፈቃድ የሚወሰን መሆኑ ቀርቶ አስቀድሞ በተበጀ ሥርዓት መታቀብ እንደሚኖርበት መክረዋል፡፡ በጸሐፊው አስተያየት ደሞክራሲ ሁል ጊዜ ልማትን ያቀዳጃል ለማለት ባይቻልም ለኢትዮጵያ ዓይነቱ ሁኔታ ዳሞክራሲ አስፈላጊ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ በጸሐፊው የምርምር ግኝት አንፃር ሥርዓታት፣ ዲሞክራሲና ልማት በሶስትዮሽ ተስተጋብረው ሲያበቁ ለሶስዮ-ኢኮኖሚ ዕድገት ትልቅ ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ አብራርተዋል፡፡

ጸሐፊው ስለ ሥርዓታት ያቀረቡት ትንታኔ በጥሩ መረጃና የአቀራረብ ዘዴ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ ትምህርታዊነትና የሥርዐት ችሎታ ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡

ከርዕያ 2020 የመድረክ ውይይት አልፎ ለሰፊው አንባቢ፣ ለማንበራዊና ለፖለቲካ ምርምር ጭብጥ የሚሰጥ ሥራ መሆኑን ማጤን ይቻላል፡፡ ጸሐፊው በምሁራዊ ችሎታ ላቀረቡት ጽሑፍ፣ ከፍ ያለ አክብሮት ይገባቸዋል፡፡ ደፋር አቀራረባቸውም ለሌሎች ተመራማሪዎች አርአያነት አለው፡፡

በሌላ በኩል "የፖለቲካ ነፃነትና ልማት" ተብሎ በነፊል ርዕስነት በተመለከቱ ጉዳዩች ላይ ጸሐፊው ብዙ ትኩረት አልሰጡበትም። በርግጥ ይኸኛው ነፊል ርዕስ ለብቻው በአሁኑ ጸሐፊው ወይም በሌላ ጸሐፊ አማካይነት ራሱን ችሎ መቅረብ ያለበት እንጂ በሰፊው ተተንትኖ ከቀረበው "ሥርዓታት" ጋር ተዳብሎ ባይቀርብ ይመረጥ ነበር።

በአጠቃላይ ጸሐፊው የሥርዓታትን ጽንሰ-ሃሳብና ፋይዳቸው ላይ ሰፊ ትንተና በማቅረብ የኢትዮጵያ የቅድመ-ሥርዓታት ሁኔታ እንዲሁም የተወሰኑ ዘርፎችን በመምረጥ በአሁኑ ወቅት ስለገጠመን የሥርዓታት ችግሮችና መፍትሄዎች ላይ ሰፊ ማብራሪያ ሰጥተውናል። በመጨረሻም፤ ሁላችንም ልንጋራው የሚገባንን ርዕያቸውን አካፍለውናል። ርዕያቸው "ከአንድ ትውልድ በኋላ፤ የኢትዮጵያ ህብረተሰብ፣ የሥርዓታት ብዛትና ጥንካሬ አይነተኛ መልኩ የሆነ፤ የሕግ-የበላይነት፣ የፖለቲካ ነፃነትና መልካም አስተዳደር የሰፈነበት እና፤ ፈጣን ልማት የሚስመዘግብ ይሆን ዘንድ ተስፋ እናደርጋለን። ይህንንም ተስፋ ዕውን ለማድረግ በሥርዓታት ምስረታና ለዚህ አሰፈላጊ በሆኑት ጉዳዬች ላይ ማትኮር ዋና ቁምነገር መሆኑን በእንደገና በአፅንኦት እናሳስባለን"።

ለዚህ ትምህርታዊና በበቂ መረጃ በማስደገፍ ላቀረቡልን ጽሑፍ በድጋሚ ዶ/ር የራስወርቅ አድማሴን ላመሰግን እወዳለሁ።

አመሰግናለሁ!

መንግሥት፣ ኢንፎርሜሽን እና ሕዝብ

ዓቢይ ፎርድ*

ትርጉም፤ በዮናስ አድማሱ

መንደርደሪያ

በወግ የተዋቀረ ዲሞክራሲያዊ የሆነ ብሔራዊ መንግሥትን ፈጥሮ በዘላቂነት ለማቆየት ከሚያስፈልጉትና የሀገሪቱን አንድነት ጠብቀው ለማቆየት ከሚረዱት ሥርዓቶች ውስጥ አንዱ የሆነው የመገናኛ ብዙኃን ተቋም ሕጋዊነቱ የጸደቀለትና በሕዝቡ ዘንድ ተቀባይነትን ያገኘ መሆን አለበት። የተለያዩ ቋንቋዎች፣ ባህሎች፣ የመገናኛ መንገዶች የተለያዩ ብሔረሰቦችን ውስጣዊ አንድነት ለማስጠበቅ የሚበጁ ተቋማት ሆነው በሚያገለግሉበት፣ ብዛት ያላቸው ብሔር-ብሔረሰቦች ባሉበት በአንድ በፌዴሬሽን በተዋቀረ ብሔራዊ መንግሥት ውስጥ አንድ ማዕከላዊ የሆነ መንግሥታዊ የኢንፎርሜሽን ሥርዓትን አቁሞ ሕጋዊነትንም፣ ሕዝባዊ ፈቃድንም እንዲያገኝ ለማድረግ ከተፈለገ፤ ለዚሁ ዓላማ የሚያገለግል ራሱን የቻለ ፖሊሲ መንደፍ ያስፈልጋል። እንዲህ ያለው ፖሊሲ ደግሞ፣ ለዎች በተፈጥሮአቸውና በማኅበራዊ አቋማቸው ከሚያከናውኗቸው መሠረታዊ ተግባራት አንዱ የሆነውን ኢንፎርሜሽንን የመሰብሰብ፣ የማከማቸት፣ የተከማቸውን ባስፈለገ ጊዜና መጠን የመመልከት፣ የመተርጎምና የማብራራት፣ እንዲሁም የማሰራጨት፣ በዚህ ዘዴና ሁኔታ የተገኘውን ኢንፎርሜሽንም አጣጥሞ ለጠቀሜታ የማዋልን አስፈላጊነት በትዕግሥት ተረድቶና ተገንዝቦ ተግባራዊ ለማድረግ ዝግጁነቱን ያሳየ መሆን አለበት። ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ተግባራት ሕዝቦችን፣ ኅብረተሰቦችን፣ ባህሎችንና ሀገሮችን እርስ በርስ የሚያገናኘው መረብ የሚዋቀርባቸውና ሕይወትም የሚዘራባቸው ክንውኖች ናቸው። ነገሩን ከዚህ አንጻር ስንመለከተው፣ እውነትም የሰው ልጆች በሙሉ በተቀዳሚ የኢንፎርሜሽን ተገዢ የሆኑ፣ በዚህም ባሕርያቸው፣ «ሚቶቻቸውን» (አፈ ታሪኮቻቸውን)፣ የአኗኗር ዘዴና ሥልቶቻቸውን፣ ደንቦቻቸውንና ትውፊቶቻቸውን ከአንድ ትውልድ ወደሌላ ትውልድ፣ ወይም ከአንድ የባህል ቀየ (ወይም ጎራ) ወደሌላ የባህል ቀየ (ወይም ጎራ) የሚያስተላልፉባቸውን የተለያዩ የመገናኛ ሥልቶች ፈጥረው ያዳበሩ ፍጡራን ናቸው ማለት ይቻላል። ሰዎች እንዲህ ባለ አኳኋን ለአንድነታቸው መጠየቂያም ሆነ ዋስትና አድርገው የሚጠቀሙበትና ለሕይወታቸው መሠረታዊነት ያለው ግንኙነት የመፍጠር ባሕርይ ከሌላቸው የፍጥረት ዝርያዎች፣ በምድራችን ያሉትን ሕዝቦች በብሔር/ብሔረሰብ፣ በቋንቋ ወይም በሌሎች መሥፈርቶች እየለየን በተለያዩ ኅብረተሰቦች ከፍለን ልንመድባቸው አንችልም ነበር። ስለዚህም፣ የአንድ ኅብረተሰብ ውሁድነት መጠን ኅብረተሰቡ ካለው አጠቃላይ የግንኙነት ሥርዓትና ሥልት ቅልጥፍና ጋር በቀጥታ የተቆራኘ

---

* ፕሮፌሰር አቢይ ፎርድ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ በጆርናሊዝምና ኮሚዩኒኬሽን ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ዲንና የፐሮጀክቱ መሪ ናቸው። ከዚያ በፊት በዋሽንግተን ዲሲ በሚገኘው ሀዋርድ ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የኮሙዩኒኬሽን ትቤት ሙሉ ፕሮፌሰር ነበሩ። ከዚህም በኋላ በኮሎምቢያ ዩኒቨርሲቲና በሌሎች በተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች፣ በአፍሪካ በተለያዩ ቦታዎች በፊልም የቴክኒክ ላይ ጉዳዮች ምክትል ዳይሬክተር ሆነው አገልግለዋል። በተጨማሪም የወርልድ ስፔስ ሬዲዮ አማካሪና በ1994 ዓ.ም ደግሞ የቀድሞ የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ጂሚ ካርተር ኤክስፐርት ሆነው ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሀገ-መንግስት የሚዲያውን ረቂቅ በማዘጋጀት ተሳትፈዋል።

ነው። እንዲህ ያለው ቅልጥፍና ደግሞ ተጨባጭ ሊሆን የሚችለው አንድ ማኅበራዊ ቡድን ወይም ወገን፣ ዘለቂታ ባለው የጊዜና የሥፍራ ክበብ ውስጥ ከሌላ ማኅበራዊ ቡድን ወይም ወገን ጋር ተራክቦ ሲያደርግ ቆይቶ የተለየ የብሔር/ብሔረሰብ ስያሜና መለዮ ካለው ቡድን ጋር ተረጋግቶና ተደላድሎ፣ በዚያም ውስጥ ዘልቆ መኖር ሲችል ነው። የተለያዩ ብሔር/ብሔረሰቦች በወል በሚኖሩበት ብሔራዊ መንግሥት ውስጥ ደግሞ የዲሞክራሲያዊ አስተዳደር መርሆዎችን ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት በሚደረግበት ጊዜ፣ እያንዳንዱ ብሔር/ብሔረሰብ የየራሱን ህልውናና መለዮ (ወይም ማንነት) ለማረጋገጥ የራሱን ጥረት ሲያደርግ በተለያዩ ፍላጎቶችና ጥቅሞች የተነሣ በተለያዩት ወገኖች መካከል ግጭት መፈጠሩ አይቀርም። ስለዚህም እንዲህ ያሉትን የፍላጎትና የጥቅም ልዩነቶች በወገ አቀራርቦ ሊፈጠሩ የሚችሉ ሥጋቶችን በማለሳለስ ውህድናን ለመፍጠር ጥረት ማድረገ ብዙ ብሔር/ብሔረሰቦች ያሉባትን ሀገር (ብሔራዊ መንግሥት) የሚመራ ማንኛውም መንግሥት ካለበት ፈተናዎች አንዱ ነው።

የግንኙነት (የመገናኛ) ሥርዓቱ ያሉበት እንከኖች

ከአንድ ከተወሰነ ክበብ አልፎ ሁሉንም የሚያዳርስ መሠረታዊና አስፈላጊ የሆነ የኢንፎርሜሽን ሥርዓትን በአንድ ሀገር ለሚኖሩ ዜጎች በሙሉ አግባብነት ባላቸው ፖሊሲዎች መሠረት በባለቤትነት ይዞ በተገቢው መንገድ መምራትንና ማስተዳደር መቻል የአንድ መንግሥት አማናዊነትከሚታወቅባቸው መሠረታዊ ባሕርዮች አንዱ ነው። ይልቁንም የዚያ መንግሥት መንግሥትነት የሚታወቅበት መለዮ ነው ማለት ይቻላል። እስከዛሬ ድረስ በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ሁሉም ሰዎች በጋራ ስለሚያስተሳስራቸው የወደፊት ህልውናቸው በኢንፎርሜሽንና በዕውቀት ላይ የተመሰረቱ ውሳኔዎችን ለማድረግ እንዲችሉ ሆኖ፣ ሁሉንም ዓይነት ኢንፎርሜሽን፣ ለሁሉም የሀገሪቱ ዜጎች በማንኛውም ጊዜ እንዲያገኙ ለማድረግ የሚያስችሉና የተሳካላቸውም በታሪክ የታወቁ የግንኙነት ሥርዓት አርኣያዎች (ሞዴሎች) ኖረውም አያውቁም፤ አሁንም የሉም። ስለዚህም፣ ልዒቃን የሚባሉት ወገኖች ከላይ ሆነው የሚቆጣጠሩበት፣ ደቂቃን (ወይም ብዙኃን) የሚባሉት ወገኖች ደግሞ ከታች ሁነው የሚተዳደሩበት፣ ከወደአናቱ ጠባብ ሆኖ ወደግርጌው እየሰፋ የሚሄድ (የፒራሚድ ቅርጽ ያለው) የመንግሥት አወቃቀር መቅረት አለበት የምንለውም ሆነ ልናስወግደውም የምንሞክረው አይደለም። እንዲህ ያለው መንግሥታዊ ውቅር በአንድ ግለሰብ ፈላጭ ቆራጭነት በሚገዛበት ሁኔታ የኢንፎርሜሽን ሥርጭትን የመምራቱና የማስተዳደሩ ጉዳይ ይህን ያህልም ያልተወሳሰበ፣ ቀላል ቀመርን ተከትሎ የሚሄድ ነው። እንዲህ ባለው የመንግሥት ሥርዓት ኢንፎርሜሽን የሚተላለፍበት አቅጣጫ አንድ ወገን ብቻ የሚንገ፣ ስለዚህም በባሕርዩ የግልጽነት ጥያቄ ጨርሶ የማይነሳበት ነው። በሌላ በኩል ግን፣ ይኸው የመንግሥት አወቃቀር በዲሞክራሲያዊ መንገድ በሚመራበት መንግሥት ውስጥ የኢንፎሜሽን ስርጭቱና የሚጓዝበትም ሥልት በእጅጉ ውስብስብ ነው። ባንድ በኩል ሥርዓቱ በግልጽነት መርህ የሚንቀሳቀስ ሲሆን፣ ወዲያውም ደግሞ ኢንፎርሜሽኑ የሚሰራጭበትና የሚንቀሳቀስበት አቅጣጫ ከአናት ወደታች ብቻ ሳይሆን ከታች ወደአናትም ጭምር ነው፤ በሌላ አባባል፣ የመዋቅሩ አቋም ይዘቀዘቃል ማለት ነው። የሕዝብ፣ ለሕዝብ በሕዝብ (ሕዝብ ያቆመው፣ ለሕዝብ የሚሠራ፣ በሕዝብ የሚመራ) የሚለው የመንግሥት ጽንሰ ሐሳብ ከእንዲህ ዓይነቱ መርህና አወቃቀር የመነጨ ነው።

የመንግሥት ፖሊሲ (ኢንፎርሜሽን)

አንድ ኅብረተሰብን በደንብ ለመምራትና ለማስተዳደር የምንጠቀምባቸው ሥነ ሥርዓቶች፣ ቢያንስ እንደሚታመነው፣ የሕዝቡን ፍላጎቶችና ጥያቄዎች ለማሟላት ሲባል፣ ኅብረተሰቡን የሚያስተዳድረው መንግሥታዊ አካል መስተካከል፣ መቻቻል፣ መቀነስ፣ መስፋት፣ ወይም ደግሞ እነዚህን የመሰሉ ለውጦች ያስፈልጓቸዋል ብሎ የሚያምናቸውን ተፈራራቂና ተጻራሪ የሆኑ ጽንሰ ሐሳቦች፣ ሁኔታዎችና ነገሮች የግድ በውስጣቸው ያካተቱ ናቸው። በዚህ ረገድ፣ ለምሳሌ ያህል፣ እንደመንግሥት ፖሊሲ ያሉት እነዚህ ሥርዓቶች በዓላማቸው ለበጎ ተብለው፣ በግብራቸው ደግሞ በጎደለው ይሞላሉ፣ የተዛባውን ያስተካክላሉ ተብለው የሚቀረጹ ሲሆኑ፣ እጅጉን ወስብስብ በሆነ ማኅበራዊ ዐውድ ውስጥ ተለይተው የታወቁ እንከኖችንና ሳንኮችን ለማስወገድ እንደ ደንብ ተወስነው በተግባር ላይ እንዲውሉ የሚደረጉ ናቸው። እንዲህ ያሉት ሥነ ሥርዓቶች ግን፣ የታሰበላቸው ዓላማ ምንም ይሁን ምን፣ በባሕርያቸው ያለባቸው አንድ ችግር በአንድ በተወሰነ ወቅትና ሁኔታ ለሚፈጠር ችግር እዚያው በዚያው አጣዳፊ መፍትሔ ለመስጠት ያህል የታቀዱ መሆናቸው ነው። በሌላ አባባል፣ እነዚህ መፍትሔዎች፣ በየጊዜው ያለማቋረጥ በሚለዋወጡ የሰዎች ፍላጎቶችና ተፈጥሮአዊ በሆነ የመወዛገብና ሥርዓት-አልባ የመሆን ዝንባሌ ግፊት ያለማቋረጥ በሚንቀሳቀስ ኅብረተሰብ ላይ ሁሉንም እኩልና በአንድ ዓይነት መንገድ በሚያደላድል ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቁጥጥር ሥር ለማዋል የሚደረጉ ሰብኣዊ ጥረቶች መከሰቻዎች ናቸው። እንዲህ ያለው ውዝግብና ሥርዓት-አልባነትን «የመናፈቅ» አዝማሚያ ባለበት ኅብረተሰብ ውስጥ ሥርዓትን መሠረት አድርጎ ለማስፈን ደግሞ፣ ለሁሉም የጋራና አማካይ በሆነ የቦታ ክልል እና ማኅበራዊ-ፖለቲካዊ ሥርዓት ውስጥ የሚኪያሄዱ ማናቸውንም ሰብኣዊ ክንውኖች መልክና ሥርዓት ለማሲያዝ ሲባል፣ ሁሉም ኅብረተሰቦች፣ መልኩ እንደየሁኔታው ቢለያይም፣ አንድ ዓይነት የቁጥጥር ዘዴና ሥልት ያስፈልጋቸዋል። ያለሱም ሊኖሩ የማይችሉበት መመኪያቸው ነው ማለት ነው። ይህን መሠረተ ሐሳብ ይዘን ስንነሣ፣ መንግሥታት የሚያወጧቸው ፖሊሲዎች፣ ባንድ በኩል፣ ሰዎች በገዛ እጃቸው በራሳቸው ላይ ሊያደርሱ ከሚችሉት ጥፋትና ጉዳት ለመጠበቅ፣ በሌላ በኩል ደግሞ በዓይነቱና በጥራቱ ከፍ ወዳለ የኑሮ ደረጃ ለመድረስ የሚያስችሉ የአስተዳደር መሣሪያዎች መሆናቸውን እንገነዘባለን። መንግሥት የሚያወጣው ማንኛውም ፖሊሲ በባሕርዩ በአጠቃላይ በሕዝቡ ላይ በመሉ፣ ከዚህም ጋር ተያይዞ፣ በተፈጥሮው ነፃ ነው ተብሎ በሚታመነው ማንኛውም ግለሰብ ግላዊ ድርጊት ላይ፣ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ፣ ተጽእኖ የሚኖራቸውን የመታቀብና የግዴታ (የኃላፊነት) ሐሳቦችን በውስጡ ጸንሶ የያዘ ነው። ስለዚህም፣ ማንኛቸውም አስተዳደራዊ ፖሊሲዎች፣ ሰው-ሠራሽ የሆኑ ጊዜያዊ የግዴታ መሣሪያዎች ሲሆኑ፣ ተግባራቸውም፣ የሰዎችን ተፈጥሮ የሚወስኑትንና የሚያንቀሳ ቅሱትን ተፈጥሮአዊና ሳያቋርጡ የሚጓዙ ነፃ ግፊቶች መገደብና (ተገቢ ነው ተብሎ የሚታመነውን) አቅጣጫ ማሲያዝ ነው።

አንዱ፣ ችግር ይሆንብኛል፣ ይቀናቀነኛል ብሎ ለሚያስበው አንድ ኃይል ምላሽ ወይም መመከቻ ይሆነኛል ብሎ በሚፈጥረው ሌላ ኃይል መካከል፣ ማለትም በሁለት ተጣራሪ ወይም ተቀናቃኝ ኃይሎች መካከል፣ የሚፈጠረው ግጭት፣ ብዙውን ጊዜ ሌላ ሦስተኛ ችግርን ይወልዳል። እንደገናም ደግሞ፣ በዚህ ዓይነት አዚያሄድ የሚፈጠረው እያንዳንዱ ችግር ሌላ መፍትሔን ይሻል፤ ሁኔታው እንዲህ እያለ ይቀጥላል። ይህን አፍታተን ስናየው፣ የመንግሥት ፖሊሲዎች፣ ባንድ በኩል ለተፈጠሩ ችግሮች መፍትሔ የመሆናቸውን ያህል፣

በሌላ በኩል ደግሞ የትግር ምንጭም ይሆናሉ። ሁለት ተዛራሪ ወይም ተቀናቃኝ ኃይሎች ሲጋጩ በመካከላቸው በሚነሣው ፍትጊያና ፍጭት ሁለቱም ይዳከማሉ፤ ዓቅማቸውም ይበላል። ይህ ደግሞ በተራው፤ ማኅበራዊ ሥርዓቱ አንዲዳከም፤ መፍትሔ ሳይፈለግለት ወይም ሳይገኝለት ከቀረ ደግሞ፤ መላው ሥርዓት ይናጋና ቅጥ የሌለው ትርምስና ሥርዓት አልባነት ውስጥ እንዲዘፈቅ ያደርጋል። እንዲህ ያለውን አገልግሎት አስቀድሞ ለመከላከል ሲባል ታዲያ፤ የመንግሥት ፖሊሲዎች፤ በየጊዜው፤ ሲዳከሙ እንዲጠናከሩ፤ ግብና ዓላማቸውን ሲስቱ እንዲስተካከሉ ወይም የትኩረት አቅጣጫቸውን እንዲለውጡ፤ ጊዜ ያለፈባቸው፤ ያፈጁ ሲሆኑ ደግሞ ጨርሰው ተነቅለው በሌላ እንዲተኩ ይደረጋል። ይስተካከሉም አቅጣጫቸውም ይለወጥ፤ ወይም ጨርሰው በሌላ ይተኩ፤ በማናቸውም ሁኔታ የሚፈጠረውና ተግባራዊ የሚሆነው ማኝኛውም አዲስ ፖሊሲ ደግሞ በተራው፤ መፍትሔ የሚሻ አዲስ ችግርን ይዞ ነው የሚመጣው። የነገሩን መላ በዚህ አንጻር ስንመለከተው፤ የመንግሥት ፖሊሲዎች ሁሉ በቆመበትና ባለበት ሁኔታ፤ ወዲህ ተግባራቸውን ሲወጡ፤ ወዲህ ደግሞ ያንኑ ተግባር ለመወጣት አቅሙ የሌላቸው ስንክሉሎች ይሆናሉ ተብሎ ሊተረጎም ይችላል።

ይህም ሁሉ ሆኖ ግን፤ ኅብረተሰቦች ባሉበት እንደቆሙ ወይም እንደረገ እንዳይቀሩ፤ አለያም ደግሞ ከነበሩበትም አቆልቁለው ጨርሶ እንዳይበላሽ ለማድረግ፤ በዚህም ኅብረተሰቦቹ ያለማቋረጥ እየተለወጡ እየታደሱ የሚሄዱ መሆናቸውን ለማረጋገጥ እንዲቻል በውስጡ፤ በባሕርዩ ባለው ተቃርኖአዊ ቁርኝት (ዳያሌክቲካዊ ግንኙነት) ምክንያት ዋናውን አንቀሳቃሽ ግፊት የሚያፈልቀው ሰው-ሠራሽ በሆነው (ሰብአዊ ቁጥጥር) ኃይል እና ተፈጥሮአዊ በሆነው (ተፈጥሮአዊ ነባነት) ኃይል መካከል የሚደረገው የማያቋርጥ ግጭት ራሱ ነው። ይህንን ዕንቆቅልሽ መሰል ክስተት በደንብ የሚገልጽልን ዘይቤ፤ የመራመድ ሂደትን ቻይናውያን የሚገልጹበት ተነጻጻሪ ዘይቤ ነው። እነሱ እንደሚሉት፤ መራመድ (ወይም እርምጃ) ወደምንጓዝበት አቅጣጫ ሰውነታችንን ስናንቀሳቅስ እንደመውደቅ አድርገን ዘንበል ማለታችንን፤ ወዲያውም ደግሞ እንዳዘነበልን እንዳንደፋ ደግሞ ሌላውን (ወደኋላ የቀረውን) እግራችንን ፈጥነን ወደፊት በማራመድ፤ ይህን ባናደርግ መደፋት የማይቀርልን ነው ማለት ነው። የሁለቱን እግሮች እንቅስቃሴ በማፈራረቅ እየደጋገምን የምንወስደው ይህ እርምጃ ወደተፈለገው አቅጣጫ የምናደርገውን ጉዞ ለማጠናቀቅ ይረዳናል። ይህም ሆኖ ግን፤ ሂደቱ፤ የሚራመደውን ሰው ለመደናቀፍ፤ አልፎ አልፎም ጨርሶ ለመውደቅ አደጋ የሚያጋልጠው መሆኑን መርሣት የለብንም።

የፖሊሲ ምርምርና ትንተና

በማንኛቸውም ዓይነት የአስተዳደር ሥርዓት ውስጥ የሚገኘው ፖሊሲ በባሕርዩ ውስብስብና ሁለገብ በመሆኑ፤ ይህንን ባሕርዩን መርምረን የምንረዳባቸው መሣሪያዎችና ዘዴዎች ያስፈልገናል። እነዚህ መሣሪያዎችና ዘዴዎች ደግሞ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ማኅበራዊ ተዋንያን፤ ማለትም ማኅበሩን በሚያስተዳድሩና በሚመሩት ወገኖችና በሚተዳደረው ሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት ውስብስብነት የሚመጥኑ መሆን አለባቸው። እዚህ በምንነጋገርበት ሁኔታ፤ የፖሊሲ ትንተና ወይም ምርምር ስንል፤ ጠቅለል ባለ አነጋገር፤ የሚከተሉትን ዓይነት ጥያቄዎች ለመመለስ በሚቻልበት ረገድ ላሉ ችግሮች መፍትሔ ለመፈለግ የምንጠቀምባቸውን ሥልቶች (ቴክኒኮች) በሥራ ላይ ማዋል ማለት ነው። ጥያቄዎቹ የሚከተሉትን ጉዳዮች ይመለከታሉ፤ (1) በኅብረተሰብ ውስጥ ከሚነሱ ችግሮች አንጻር

መንግሥት በይፋ አሳውቆ የተነሣባቸውን ዓላማዎች፤ (2) እነዚህን ዓላማዎች ከግብ ለማድረስ መንግሥት የሚወስዳቸውን (ወይም ከመውሰድ የሚቆጠብባቸውን) እርምጃዎች። ከነዚህ ጋር ተቆራኝቶ በሦስተኝነት ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ ደግሞ፣ የመንግሥት ባለሥልጣናት እንወስዳቸዋለን ብለው ያለሙባቸውን እርምጃዎች የእርምጃዎቹ ተቀባይ ወይም ተጠቃሚ ይሆናል ተብሎ የተተኮረበት ኅብረተሰብ እርምጃዎቹን የሚቀበልበትን ወይም አልፈልግም የሚልበትን መጠን የምንለካበትን ሁኔታ የሚመለከት ነው።

የኢንፎርሜሽን እና የግንኙነት ዐምዶች

የመንግሥትን ፖሊሲ መርምሮ ለመረዳት አስፈላጊና ወሳኝ የሚሆነው አንድ ጉዳይ፣ እንደ ኢንፎርሜሽን፣ ዕውቀት፣ ኃይል (ሥልጣን) እና ግንኙነት የሚባሉትን ጽንሰ ሐሳቦች ምንነት በውል መገንዘብና መረዳት ሲሆን፣ ዋናው ትኩረታችን ግን መጨረሻው ጽንሰ ሐሳብ ላይ ያረፈ መሆን ይኖርበታል። ከዚህ ባለነሰ ደረጃ ደግሞ ልንረዳቸው የሚገባን ጽንሰ ሐሳቦች፣ (የሕዝብ) ፍላጎቶች/ ችግሮች/፣ ዋስትና /ጸጥታ/፣ አቅርቦትና ፍላጎት፣ የጋራ ደኅንነት፣ አንድ ዓላማን ማራመድ (ለዓላማ መሟገት)፣ የጋራ ስምምነት፣ ስትራቴጂ፣ ሕዝብ-ተኮር፣ ልሂቅ-ተኮር፣ ወዘተ... የመሳሰሉት ናቸው። ይህ ደግሞ በተራው፣ አንድን ነገር በሌላ ነገር በምንተረጉምባቸው በድምፅ ወይም በሌሎች ረቂቅ ትእምርቶች (ምልክቶች) አማካይነት በመጠቀም ከተወሰኑ ማኅበራዊና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ጋር ራሳችንን አዋድደን ወይም አስማምተን ለመኖር የምንችልበትን ዘዴ ይፈጥርልናል። እነዚህ ረቂቅ ትርጉም አዘል ሐሳቦች እንደነሱው ረቂቅ የሆኑ አንድምታዎች ይጸንሱና በልማድ የምንቀስማቸውንና የምንማራቸውን፣ እንደ «ጥሩና መጥፎ»፣ እንደ «ውበትና አስቀያሚነት»፣ እንደ «ጨዋና ያልታረቀ»፣ እንደ «ክርስቲያንና እንደአረማዊ»፣ ወዘተ... ያሉትን አመለካከቶች ይወልዱና ያወርሱናል። እንዲህ ባለ አኳኋን የምንማራቸው ዕሴቶች ይዳብሩ፣ ይደንድኑና ውለው አድረው መንግሥት በሚያወጣቸው ፖሊሲዎች ላይ እንደየሁኔታው አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተጽእኖ የሚኖራቸው መርሖዎች እና/ወይም ደንብ-አከል ልማዶች ይሆናሉ። ለዚህ መረጃ ይሆነን ዘንድ፣ ለምሳሌ ያህል፤ ቀደም ሲል በዩናይትድ ስቴትስና በደቡብ አፍሪካ ይሠራባቸው የነበሩትን የዘር ልዩነት ፖሊሲዎች እናስታውስ፤ እንዲሁም፣ የክርስትና እምነት ተከታዮችና የእስልምና እምነት ተከታዮች በሆኑ ኅብረተሰቦችም ዘንድ፣ እንደቅደም ተከተላቸው፣ ወንድና ሴት በአንድ-ለአንድ ደንብ በባልና ሚስትነት እንዲኖሩ የሚያዘውን ሥርዓትና አንድ ወንድ ከአንዲት ሴት በላይ እንዲያገባ የሚፈቅደውን ሥርዓትም እንዲሁ እናጢ ናቸው። እንዲህ እያለ ይቀጥላል።

አንዲህ ያሉት ዕሴቶች አንዴ እንደማኅበረሰቡ የጋራ እምነት ወይም ልማድ ሆነው ከተዋቀሩ በኋላ፣ የሰው ልጅ በያለበት የሚኖርበትን ኅብረተሰብ አንድ ላይ አያይዞና አዋህዶ የሚያቆይባቸውን ውስብስብ የሆኑ ማኅበራዊ ዘዴዎችንና ሥልቶችን ይቀይሳል፣ ያንባል። ወዲያውም ደግሞ ከዚህ ጎን ለጎን፣ እንዲህ ያለው የሰዎች ማኅበር ከላይ በተጠቀሰው ዓይነት ማኅበራዊ ውቅር ተመሥርቶ የተገነባውን ሥርዓት በመጠቀም፣ ሊኖር ከተገደደበትና ለኑሮውም በተቀዳሚ አስፈላጊ የሆኑትን የምግብና የመጠለያ ፍላጎቶቹን ለማሟላት የሚያስችሉትን ንብረቶች ቃርሞ ይሁን አፍርቶ ከሚያገኝበት የተፈጥሮ አካባቢ ጋር ለሕይወቱ የሚበጀውን ምርታማ ግንኙነት ይፈጥራል። ይህንን ተግባሩን በሆነ ደረጃና መጠን የተሳካ ለማድረግ ደግሞ፣ የሚኖርበትን ኅብረተሰብ የሚያስተሳስረውንውስብስብየግን ኙነት መረብ የሚያንቀሳቅሰውንና በሕይወት የሚያቆየውን፣ የተለያዩ መልኮችና ደረጃዎች ያሉትን

ኢንፎርሜሽንን ማምረት፣ የተመረተውን ፈልጎ ማግኘት፣ የተገኘውን ማከበት ወይም ማከማቸት፣ ያከማቸውን መልሶ አንደየፍላጎቱ ማውጣት፣ ያወጣውን ላለበት ሁኔታና የኑሮ ዓይነት እንዲመች አድርጎ ማረቅ፣ መለወጥ፣ ማሻሻል፣ ይህንን ደግሞ ማሰራጨት፣ ከዚያም እንዲህ ሆኖ በተዘጋጀው ራሱን መጥቀም አለበት።

ነገሩን በዚህ ረገድ ስንመለከተው፣ የአንድ ኅብረተሰብ ውሁድ ሆኖ መቆየት ኅብረተሰቡ በአጠቃላይ በእጁ ባለው የግንኙነት ሥርዓትና ዘዴ ቅልጥፍና መጠን የሚወሰንና በሱም ላይ የተመሠረተ መሆኑን እንረዳለን። ይህንን፣ ለጊዜው «የስንቅና ትጥቅ» ችግር የመፍታት ጉዳይ ብለን ልንጠራው በምንችለው የሰዎች ግዳጅ የተነሣ፣ ማንኛውም ኅብረተሰብ ቢሆን፣ በእጁ የሚገኘውን የኢንፎርሜሽን ንብረት በወጉ ይዞ መጠቀሚያ ለማድረግ የሚቻልበትን አመራር ከሚሰጠውና፣ ከላይ እንደተገለጸው እንደ «ፒራሚድ» ቅርጽ፣ ልሂቃኑ ከላይ፣ ብዙኃኑ ከታች ሆነው ከተዋቀሩበት፣ በታሪክም እንዳየነው ለዚሁ ጉዳይ ሲባል አስፈላጊነቱ ምትክ ከሌለው፣ መንግሥት ከሚባለው አካል ነፃ ሊሆን አይችልም። እንዲህ ያለው መንግሥት ተግባርና ኃላፊነት ኢንፎርሜሽን በኅብረተሰቡ ውስጥ በወጉ ተሰብስቦ፣ ተከማችቶ፣ በደንብ ተዋቅሮ ለሕዝቡ መጠቀሚያ የሚውልበትን ሁኔታ መንገድ ማመቻቸት፣ ለአኪያሄዱም አመራር መስጠት ነውና። እንዲህ ባለው ሁኔታ ታዲያ፣ ኅብረተሰቡ በፈጠራቸው የተለያዩ ማኅበራዊ ሥርዓቶችና ደንቦች ምክንያት፣ ለኅብረተሰቡ ኑሮና ሕይወት አስፈላጊ የሆነውን ኢንፎሜሽን አመንጭቶ፣ አስፋፍቶና አዳብሮ ለማሰራጨት ከማንም የበለጠ የመግባት የመውጣት ሥልጣን ያላቸው የልሂቃኑ ቡድን አባላት፣ ያሉባቸው ኅብረተሰቦች የሚጓዙባቸውን አቅጣጫዎችና የሚመሩባቸውን ቅኝቶች፣ እንዲሁም የሚያከናውኗቸውን ተግባሮችና ሙያዎች መልክ ለማሲያዝ ወሳኝ የሆኑ ሚናዎችን ሊጫወቱ የሚችሉም፣ የሚጫወቱም ናቸው። ይልቁንም ደግሞ፣ በሁሉም ማለት ባንችል፣ በአብዛኛዎቹ ኅብረተሰቦች ውስጥ፣ የመንግሥት ፖሊሲን በመንደፍ ረገድ፣ ከታች ወደላይ ከሚያገዘው ይልቅ ከላይ ወደታች እንዲወርድ የሚያደርገውን የእርከን አቅጣጫ ወደመከተሉ የሚያዘነብለውን የኅብረተሰቦችን አዝማሚያ የሚመግበው እንዲህ ያለው የመረ-ተመረ መንግሥታዊ አወቃቀር ነው።

ከዚህም ወሰብሰብ ባለ ሁኔታ፣ እንዲህ ዓይነቱ የመንግሥታዊ ሥርዓት አወቃቀር፣ እጅጉን የላቀና የረቀቀ የኢንፎርሜሽን ሥርዓት ባለባቸውና እጅግ በልጽገዋል በሚባሉት ሀገሮችም ሲሠራና ሲሠራበትም እናያለን። እንዲህ ባሉት ሀገሮች፣ የኢንፎርሜሽን ሥርዓቱ፣ የሀገራቱ ዜጎች መንግሥቶቻቸው ምን ምን ፖሊሲዎችን እንደሚያወጡ ለማወቅ ያስችላቸዋል፤ የወጡትን ፖሊሲዎች ሁሉ ምንነትና አኪያሄዳቸውን በደንብ ይረዱታል ማለት ባይሆንም። እዚህ ላይ በወጉ ሊጤን የሚገባው አንድ ቁም ነገር፣ መንግሥት የሚያወጣውን ፖሊሲ ምንነት «ማወቅ» እና የወጣውን ፖሊሲ ምንነት «መረዳት»፣ ሁለቱ ለየቅል መሆናቸው ነው። «ማወቅ» የሚለውን ጽንሰ ሐሳብ ስንጫን፣ ለምሳሌ ያህል፤ በዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ፣ አንድ ሰው ጋዜጦችን በማንበብ፣ ቴሌቪዥን በማየት ወይም ሬዲዮ በማዳመጥ ስለሚወጡት የተለያዩ ፖሊሲዎች ሊያውቅ ይችላል ማለት ነው። በዚህ ረገድ፣ ያሉት የመገናኛ ብዙኃን አውታሮች የፖሊሲዎቹን ይዘቶችና ዋና ዋና ቁም ነገሮች ለይተው በማቅረብ አንባቢውንም ሆነ ተመልካቹን ወይም አድማጩን ይረዳሉ። «መረዳት» የሚለውን ሐሳብ ስንጫን ግን ሁኔታው የተለየ መሆኑን እናያለን። ልዩነቱ ያለው፣ ፖሊሲዎቹን ለማውጣት ምክንያት የሆኑትን ጉዳዮች፣ ዓላማቸውን፣ እንዲሁም ፖሊሲዎቹ የዜጎቹን ኑሮና ሕይወት በምን ዓይነት መንገድ እንደሚነኩ አስተንትኖ መረዳት መቻል ወይም አለመቻል ላይ ነው። ፖሊሲዎችን ከነውስጠ ውስጣቸው በዝርዝር ጠልቆ መረዳት እንዲቻል፣

ፖሊሲዎቹን ተገቢና አስፈላጊም በሆኑት መሣሪያዎችና ዘዴዎች በደንብ መመርመርንና ማስተንተንን ያስፈልጋል። መንግሥታት የሚያወጧቸውን ፖሊሲዎች በዝርዝር አስተንትኖ ለመረዳት ብዙ ሰዎች ወይ ጊዜው የላቸውም፣ አለዚያም ችሎታውና ብቃቱ አይኖራቸውም። ወይም ከሁለቱም ያጡ ናቸው።

የዚህ አንድምታ የሚከተለው ነው። ቀልጣፋና ብቁ ሆኖ መንቀሳቀስ ለሚፈልግ መንግሥት ፖሊሲዎችን መርምሮና አስተንትኖ በመረዳት ማስረዳት የሚችሉ፣ በተገቢው ሥልጠና የተቃኙ፣ ይልቁንም የታሸ የፖሊሲ ምርምር ባለሙያዎች ያስፈልጉታል። እነዚህ ባለሙያዎች በዚህ ረገድ የሚያከናውኑት ተግባር በመሪ አካላቱ (ማለትም በመንግሥታት) እና በሚመሩዋቸው ሕዝቦች መካከል ሊኖር ለሚገባው ውይይትና መግባባት መሠረት ይሆናል። እነዚህ ባለሙያዎች፣ ውስብስብ የሆኑት የመንግሥት ፖሊሲዎች ሲታለሙም ሆነ ሲነደፉ መሠረት ያደረጓቸውን ምክንያቶች ዜጎች ሊረዱ የሚችሉባቸውን ሁኔታዎች በማቀላጠፍ፣ ይቅር ቢሉት ሊወገድ የማይችለውንና ሁለ-ገብ በሆነው፣ የ«ፒራሚድ»ን ቅርጽ ይዞ በተዋቀረው መንግሥታዊ ሥርዓትና ለዲሞክራሲ ሥልት ሥሱ በሆነውና ከታች ወደላይ የሚያልመውን «የተገለበጠ ፒራሚድ» አወቃቀር በሚናፍቀው ሐሳብ መካከል እንደድልድይ ሆነው ሁለቱን በማቻቻል ቅራኔውን የሚያረግቡና መግባባትን የሚፈጥሩ አማካይ አካላት ወይም ድልድይ ሆነው ያገለግላሉ። እንዲህ ላለው ዲሞክራሲያዊ ተራክቦ ደግሞ ዓይነተኛ የሆኑት መድረኮች፣ ሰፊና ጥልቅ ክርክር ማኪያሄድ የሚበረታታባቸውና ተቃራኒ ሐሳቦች በዲሞክራሲያዊ ድምፅ ብልጫ የሚፈቱባቸው፣ እንደ ፓርለማ (የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት)፣ እንደመማክርት ጠቅላላ ጉባኤ (ኮንግረስ) ያሉትና ሌሎችም እነሱን የመሳሰሉት ሸንጎዎች ናቸው።

ስለ 2020ዋ ኢትዮጵያ ያለኝ ርእይ

በ2020 ዓመተ ምሕረት ኢትዮጵያ ምን ልትሆን ወይም ልትመስል እንደምትችል ያለኝን ርእይ በጽሞና ልመለከትና ልቆዝምበት ስነሣ፣ ሁኔታውን ብሩህ አድርጎ የሚያሳየኝን መንገድ መርጫለሁ። አሁን ያሉትን የተለያዩ ሁኔታዎች አጣምሬ ስመለከታቸው፣ ኢትዮጵያ አሁን ያለችባቸውን ማኅበራዊ-ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ-ፖለቲካዊ ሁኔታዎች በደንብ ለማሻሻል አቅሙም ተስፋውም አላት ብዬ አምናለሁ። ሀገሪቱ ወደማስበው ሁኔታ ለመድረስ የምትጓዝበት መንገድ አልጋ-ባልጋ ሳይሆን አስቸጋሪና አቀበት ሙሉ የሆነ መንገድ መሆኑ ለማንኛችንም ግልጽ ነው። ይህን አቀበት ግን ልትወጣው ትችላለች፤ ደግሞም ትወጣዋለች ብዬ አስባለሁ። ይህን ማድረግ ትችል ዘንድ ግን አሁን የተተበተበችበትን፣ በፍርኃት፣ ባለመቻቻል እና በመደናበር ቃና የተቃኘ ቋንቋና የአመለካከት ሥልት በጣጥሳ መጣል አለባት። አሁን በጎብረተሰባችን የተንሰራፋውና የገነነው የተስፋ መቁረጥ ዘይቤ ወይም አዝማሚያ ሥፍራውን፣ የዲሞክራሲ ግዳጆች የግድ ከፊታችን የሚጋርዱብንን ፈተና ምንነት አጣጥሞ በመረዳት ለተበረዘ በራስ የመተማመንና ዓቅምና ሥልጣን የሚያቀዳጅ ዘይቤ ወይም አመለካከት እንዲለቅ መደረግ አለበት። ሀገሪቱ ከፊቷ ተጋርጦ የሚጠብቃትን ዐቀበት መውጣት እንድትችል ለማድረግ ደግሞ የዲሞክራሲ ሥርዓትን ምንነትና አኪያሄድ በወጉ መረዳቱ ሩቅ አስበን ሩቅ እንድናድር ለማድረግ ብዙ ይረዳናል። እንደዚች ያለች የሚያኮራ ታሪክና የሚያኮራ ሕዝብ ያላት ኩሩ ሀገር ቁም ነገርን ከለዛ አጣምራ የያዘች ሆና እንድትገኝ ለማንኛችንም ግልጽ ነው። ይህን አቀበት ግን ልትወጣው ትችላለች፤ ደግሞም ትወጣዋለች ብዬ አስባለሁ። ይህን ማድረግ ትችል ዘንድ ግን አሁን የተተበተበችበትን፣ በፍርኃት፣ ከተፈለገ ደግሞ፣ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ከፊታችን የተጋረጠውን አቀበት መውጣት የምንችል፣ የምንወጣውም መሆናችንን አምነን መቀበል አለብን። እንደኔ እንደኔ ከሆነ፣

እንችላለን ብዬ አምናለሁ። ወዲያውም ግን ጉዞው የመስክ፣ የሜዳ ሽርሽር እንደማይሆንም አውቃለሁ። ኢትዮጵያውያን ጨርሰው ሊወጡ ከማይችሉበት አረንቋ ወይም ረግረግ ውስጥ ተዘፍቀዋል የሚለው ተስፋ የሸሸው የጨለምተኝነት አመለካከት ያቅረኛል። ራሳቸውን ከነበሩበት የድህነትና የመከራ ፍዳ በተሳካ ሁኔታ ፈልቅቀው ለማውጣት የቻሉ ብዙ ሀገሮች በዓለማችን ዙሪያ ያሉባቸውን ሁኔታዎች በምሳሌነት መጥቀስ ይቻላል። ታዲያ ኢትዮጵያ ይህን ማድረግ የማትችልበት ምክንያት ምንድን ነው? የምጽአት (የዓለም-አበቃለት) እና የጽልመት ሽቃዮች ልንላቸው የምንችላቸው ወገኖች፣ የኢትዮጵያን ምንነትና የወደፊት ዕጣ ፈንታ ለኢትዮጵያውያን ቀርቶ ለቀረውም ዓለም ሊነግሩ፣ ሊበይኑ፣ ሊወስኑ በተነሱበት ሁኔታና መንገድ አይለው እንዲገኙ መፍቀድ የለብንም። በእንግሊዝኛ የሚገኝ አንድ ዘይቤ የራሴ ላድርግና፣ እኔ የኢትዮጵያን ሁኔታ ስመለከተው፣ የያዘችው ጽዋ «ግማሽ ሙሉ እንጂ ግማሽ ባዶ» ሆኖ አይታየኝም።

እናም በ2020 ዓመተ ምሕረት፣ ኢትዮጵያ ከፊቷ በተጋረጠባት አቀበት የምታደርገውን ጉዞ አብዛኛውን አገባዳ፣ ባለችበት አካባቢ ሰላምና መረጋጋት እንዲሰፍን፣ ልማት እንዲስፋፋና እንዲዳብር በማድረግ ረገድ አዎንታዊ ሚና የምትጫወት ሀገር ትሆናለች።

አንድ ሰው ምንም ነገር መሥራት አይቻልም የሚል ዕምነት በውስጡ ካሳደረ፣ የራሱን አለመቻል በኩራት ለመጠየቅ በዓለም ላይ አለ የሚባሉ ምቹ ምክንያቶችን ፍለጋ ሲዞር ይኖራል። በአንጻሩ ደግሞ፣ አንድ ሰው፣ ማንኛውንም ነገር አልሞ እውን ማድረግ ይቻላል ብሎ ካመነ፣ ሕልሙን እውን ለማድረግ የሚያስችሉትን ማጠየቂያዎች እንዲሁ በኩራትና በመተማመን ይጠቀምባቸዋል። ነገሩ የምርጫ ጉዳይ ነው። በበኩሌ፣ በ2020 ዓመተ ምሕረት፣ ለዚያን ጊዜ የታለመላትን ግቦች ኢትዮጵያ በአብዛኛው እውን ታደርጋቸዋለች ብዬ አምናለሁ።

ሚዲያ እና ልማት በኢትዮጵያ*

ዘካርያስ ቀነዓ*

መግቢያ

"ሚዲያና ልማት በኢትዮጵያ" የተሰኘው ርዕስ ሠፊ ርዕስ ነው። በእንዲህ ዓይነቱ በጊዜ በተገደበ መድረክ ይህን ርዕስ ፍትሐዊ በሆነ መልኩ መዳሰስ ይቻላል ብሎ ማሰብ አጉል ይሆናል። በዚሁ ስሜት በዚህ ጽሁፍ ስለሚዲያ፣ ስለልማት፣ ስለሁለቱ ትስስር፣ በኢትዮጵያ ስላለው ኘሬስና እርሱን ስለሚገዛው ሕግ ጥቂት ሀሳቦች ለመፈንጠቅ ተሞክሯል። በማጠቃለያነትም ፀሐፊው መነሳት አለባቸው ያልኳቸውን ጥቂት አስተያየቶች ሰንዝሬአለሁ።

የሚዲያ ትርጓሜ

ሚዲያ የሚለው ቃል የእንግሊዝኛ ቃል ነው። ቃሉ እንግሊዝኛ ቢሆንም የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማሕበር በዚህ ርዕስ ላይ ወረቀት አዘጋጅቼ እንዳቀርብ በቃል ሲጠይቀኝና በተከታይም በጽሑፍ ሲያሳውቀኝ አሁን አሁን ለቃሉ በአማርኛ "ብዙሃን መገናኛ" የሚል መጠሪያ እንደተሰጠው አውቆ ነገር ግን ሚዲያ የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል እንደሚሻል መርጠ ይህ ፍሑፍ የሚዘጋጅበትን ርዕስ "ሚዲያና ልማት በኢትዮጵያ" በማለት ቀርጸታል።

"ሚዲያ" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ብዙ ቁጥርን የሚያመለክት ሲሆን የዚህ ቃል ነጠላ "ሚዲየም" የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል ነው። በነጠላውም ወሰድነው በብዙ ትርጉመ፣ ቃሉ በእግሊዝኛ "communication" በአማርኛም ግንኙነት ወይም አሁን "መገናኛ" በመባል እየታወቀ ከመጣው ቃል ጋር የተሳሰረ፣ የተቆራኘ ሆኖ ይገኛል። ስለዚህም ርዕሱ በሌላ አነጋገር ሲቀመጥ communication and development ወይም Development and communication ወይም Development communication ወይም communicating for development ተደርጉ ሊወሰድ ይችላል። እንግዲህ ለግንኙነቶች፣ ለመገናኛ፣ በነጠላ ሚደየም ሊኖር ቢችልም "ሚዲያ" የሚለው ቃል ግን በብዙ ቁጥር እንደመቀመጡና እንደ ጅምላነቱ ሁሉንም የመገናኛ አውታሮች የሚያጠቃልል ሆኖ ሊወሰድ ይችላል።

---

* ዘካርያስ ቀነዓ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሕግ ፋኩልቲ ረዳት ፕሮፌሰር ናቸው። ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሕግ የባችለር ዲግር አግኝተው ሳይመረቁ በፊት ለአንድ አመት፣ ከተመረቁ በኋላ ደግሞ ለ2 ዓመታት ያህል በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ከመስራታቸው ውጭ ረዥም ዘመን በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በሕግ ፋኩልቲ በመምህርነት ለ17 ዓመታት በማገልገል ላይ ይገኛሉ።

ደፍለር እና ዴኒስ የሚባሉ ፀሐፍት ሚዲያን በነጠላ (medium) በሚል ትርጉሙን እንደሚከተለው ያስቀምጡታል።

Medium (plural media) Any subject or device used for communicating a message by moving physical information over distance or preserving it though time. The medium links the sender to the receiver. A medium may be as simple as a carved stone or as complex as a satelitte linked television system. (Defleur & Dennis, 1994: 634)

ይህ በግርድፉ ሲተረጉም ሚዲያ ማለት መረጃን በማንቀሳቀስ መልዕክትን በርቀት የሚያስተላልፍ ወይም የሚያቆይ ማንኛውም ዕቃ ወይም መሣሪያ ነው። ሚዲያው/ መገናኛው/ ላኪውን ከተቀባዩ ያገናኛል፤ ሚዲያው በጣም ተራና ቀላል ከሆነው ከጥርብ ድንጋይ አንስቶ ውስብስብ እስከሆነው ከሳተላይት ጋር እስከሚገናኝ የቴሌቪዥን ሲስተም ሊደርስ ይችላል።

ካዛን የሚባል ሌላ ፀሐፊ ደግሞ በበኩሉ በብዙ በማስቀመጥ mass mediaን እንደሚከተለው ይተረጉመዋል።

"This term refers to technologically based media of communication whose messages are transmitted publicly by a private or a public organization to a large, heterogeneous and anonymous audience.... & (Fayad E. Kazan 1993:15)

ይህ ወደ አማርኛ ሲመለስ እንደሚከተለው ሊቀመጥ ይችላል።

መገናኛ ብዙሃን ወይም ብዙሃን መገናኛ የተሰኘው ሐረግ የሚያመለክተው ቴክኖሎጂያዊ መሠረት ኖሮት መልዕክቶች በይፋ የሚተላለፉበት የግል ወይም የሕዝብ ተቋም ነው።

ሌሎች የጋራ ፀሐፍት ሚዲያን በቀላል ትርጓሜ ሲገልጹት እንዲህ ብለውታል።

"The means employed in mass communication...."

ይህ ወደ አማርኛ ሲመለስ "ሚዲያ ማለት ሕዝብን ለመገናኘት የሚያገለግል ዘዴ ማለት ነው" ብሎ ሊወሰድ ይችላል።

የሚዲያ ዓይነቶችና ክፍፍሎች

ሚዲያ ሲባል ዓይነቱ ብዙ ነው። የተለያዩ ክፍፍሎችም አሉት። በጣም የታወቁት የሚዲያ ክፍፍሎች ሁለት ሲሆኑ እነርሱም Print media (የህትመት ሚዲያ) እና Broadcast media (የስርጭት ሚዲያ) በመባል የሚታወቁት ናቸው። የሕትመት ሚዲያን በተመለከተ ጃንዳ፤

ቤሪ እና ጐልድማን በጋራ በጸፉት The Challenge of Democracy በተሰኘው መጽሐፋቸው እንዲህ ይገልጹታል፡-

Print media communicate information through the publication of words, and pictures on paper. Prime examples of print media are daily newspaper and popular magazines. Because books seldom have a large circulation relative to the general population, they are not typically classified as a mass medium.

ይህ ወደ አማርኛ ሲመለስ፡-
የሕትመት ሚዲያ መረጃዎችን የሚያሠራጨው ታላትን እና ሥዕሎችን በወረቀት ላይ በማተም ነው፡፡ የሕትመት ሚዲያ ዋነኛ ምሣሌዎች ሬዲዮ እና ቴሌቭዥን ናቸው፡፡

የሚል መልዕክት ሲኖረው በሌላ በኩል broadcast mediaን እንደሚከተለው ይገልፁታል፡፡

Broadcast media communicate information electronically through sound and images. Prime, examples of broadcast media are radio and television.

ይህ ወደ አማርኛ ሲመለስ እንደሚከተለው ይነበባል፡-
ብሮድካስት ሚዲያ መረጃዎችን የሚያስተላልፉት በኤሌክትሮኒክስ አማካይነት ሆኖ በሥዕሎችና በምስሎች በመጠቀም ነው፡፡ ዋኖቹ ብሮድካስት ሚዲያዎች ቴሌቭዥንና ሬዲዮ ናቸው፡፡

በጣም የታወቁት የሚዲያ ዓይነቶች ወይም ክፍፍሎች ከዚህ በላይ የተመለከቱት ሁለቱ ይሁኑ እንጂ ዛሬ ዓይነታቸው በርክቷል፡፡ ከላይ ከተገለፁት ከሁለቱ ውጪ የሆኑ ነገር ግን እንደ መገናኛ ዘዴዎች ሊወሰዱ የሚችሉ አሉ፡፡ ለምሣሌ፤ ስልክ፣ ፋክስ፣ ኮምፒውተሮች በኮምፒውተር በኩል የመረጃ መረብ ተዘርግቶለት በዓለም ዙሪያ የሚያገናኝ internet በመባል የሚታወቀው የመረጃ መረብ ወዘተ፤ አልፎ ተርፎም ዛሬ ሙዚቃ፤ ፊልም ወይም ሲኒማ በቪዲዮ ካሴት፤ በዲቪዲ፣ በሲዲ ወዘተ... የሚሠራጩ ሁሉ የመገናኛ ዘዴዎች ናቸው፡፡ ሆኖም ስልክም ሆነ ፋክስ እንደዚሁም ኢንተርኔት የመገናኛ ዘዴዎች ቢሆኑም እንደ ብዙሀን መገናኛ ግን ተደርገው የሚወሰዱ አይደሉም፡፡ እነዚህኞቹ የመገናኛ ዘዴዎች እንደ ቡድን መገናኛ ዘዴዎች (group media) የሚወሰዱ ናቸው፡፡ የክፍፍልን ነገር ካነሣን ሚዲያዎች የሀገር ውስጥ እና የውጭ እንዲሁም Regional and local ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ ከመገናኛ ብዙሃን አኳያ ባለቤትነትም እንደ አንዱ የክፍፍል ዘርፍ ሊወሰድ ይችላል፡፡ በብዙ አገሮች የሕትመት ሚዲያም ሆነ የብሮድካስት ሚዲያዎች ባለቤትነት በግልና በመንግሥት የተያዙ ሲሆኑ እንደሚስተዋለው ከሆነ የሕትመት ሚዲያዎች በአብዛኛው በግል ባለቤትነት ሲያዙ የብሮድካስት ሚዲያዎች ደግሞ በመንግሥት ባለቤትነት የመያዝ ሁኔታ ይታያል፡፡ እንደ ባለቤትነቱ ዓይነትም የሚሰራጩት መረጃዎች ይለያያሉ፡፡ መረጃዎቹ በግል ወይም በመንግሥት ሚዲያ ከመሠራጨታቸው የተነሣ በተደራሾች ላይ የሚፈጥሩት ጫናና

ተዕዕኖም በዚያው ልክ ይለያያሉ። ለነገሩ በግል ባለቤትነት የሚያዙት ሚዲያዎች እና በመንግሥት ባለቤትነት የሚያዙት ሚዲያዎች በዓላማም ጭምር ይለያያሉ።

የልማት ትርጓሜ

ልማት በታሪክ የተለያየ ትርጉም እየተሰጠው የመጣ ቃል ነው። ዛሬም ቢሆን በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው የልማት ትርጓሜ አለ ብሎ ማለት ያስቸግራል። ካዛን ልማትን እንደሚከተለው ያስቀምጠዋል፡-

Development is a planned, organized, future-oriented, ecologically sound dynamic and sustainable process aimed at actualizing the human potential and the material capacities of society efficiently so that people will be able to achieve high standard of quality of life, have control over themselves, over their destiny and over their social political and material environment (Kazan, 1993:14)

ይህ ወደ አማርኛው ሲመለስ እንደሚከተለው ሊቀመጥ ይችላል።

ልማት ሰዎች በሕብረተሰብ ውስጥ የተሻለ የኑሮ ደረጃ እንዲኖራቸው፤ የራሳቸውና የዕጣ ፈንታቸው ተቆጣጣሪዎች እንዲሆኑ፣ በማሕበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ እና ማቴሪያላዊ ከባቢያቸው ላይ የበላይነት እንዲኖራቸው የሚያደርግ እምቅ ችሎታቸውን እውን የሚያደርጉበት የታቀደ፣ የተደራጀ የወደፊትን ታሳቢ የሚያደርግ ታዳጊ/ ተለዋዋጭና ቋሚ ሂደት ነው።

በሌላም በኩል በምዕራቡ ዓለም ተቀባይነት ያገኘው የልማት ትርጓሜና ዕይታ በርካታ ገጽታዎች ያሉት መሆኑን ይኸው ካዛን የተሰኘው ፀሐፊ ሲያስቀምጠው እንዲህ ብሏል፡-

The western paradigm of development contained several essential elements and premises. These were

1. that, to achieve economic development, societies must develop a free enterprise and free trade system;
2. that societies aimed at development must also feature a free press and free flow of information;
3. that people in these societies should possess those values and attitudes that reflect the western middle class life style, which can be realized by individual efforts; and
4. that development mainly refered to economic productivity and growth and to the accumulation of consumer goods. (Kazan, 1993:48)

የዚህ የአማርኛ ምልስ እንደሚከተለው ሊቀመጥ ይችላል።

የምዕራቡ ዓለም የልማት ዕይታ በርካታ ዋና ዋና ሐሳቦችንና መንደርደሪያዎችን የያዘ ነው። እነርሱም፣-

1. ኢኮኖሚያዊ ዕድገት ላይ ለመድረስ ሕብረተሰቦች ነፃ ተቋማትና ነፃ የንግድ ሥርዓት ማዳበር እንዳለባቸው፡

2. ዕድገትን የሚያልሙ ወይም ግብ የሚያደርጉት ሕብረተሰቦች ነፃ ኘሬስና ነፃ የመረጃ ፍሰት ሊኖራቸው እንደሚገባ፣
3. የእነኚህ ሕብረተሰቦች ሕዝቦች በግል ጥረት ሊደረስባቸው የሚችሉና የምዕራቡን የመካከለኛ ደረጃ መደብተኞች የአኗኗር ዘይቤ እሴትንና አመለካከትን የማንፀባረቅ ችሎታ ያላቸው መሆን እንዳለባቸው፤ እና
4. ልማት ሲባል በዋናነት የሚያመለክተው ኢኮኖሚያዊ ምርታማነትን፤ ዕድገትን እና ለሸማቾች የሚሆኑ ሸቀጦችን ማከማቸት መሆኑን ነው።

ከላይ ከተጠቀሰውና ከታወቀው የምዕራቡ ዓለም የልማት ዕይታና ትርጓሜ ወጣ ባለ መልኩ የተሰያዩ ፀሐፍት ለልማት የሚከተለውን ትርጓሜዎች ሰጥተዋል። ለምሣሌ Inayatullah የተሰኘ ፀሐፊ የሚከተለውን አስቀምጧል።

Change toward patterns of society that allows a society a greater control over its environment and over its own political destiny and that enables its individuals to gain increased control over themselves.

ይህ የእናያቱላህ ትርጓሜ ወደ አማርኛ ሲመለስ፤

ሕብረተሰብ አካባቢውንና የራሱን የፖለቲካ ዕጣ ፈንታ እንዲቆጣጠርና እንዲወስን የሚያደርግና ግለሰቦች ራሳቸውን እንዲቆጣጠሩ የተሻለ ብቃት እንዲኖራቸው የሚያደርግ የለውጥ ዓይነት ነው። የሚል መልዕክት ይሰጣል።

ሮጀርስ የተሰኘ ሌላ ፀሐፊ በበኩሉ ለልማት የሚከተለውን ትርጓሜ ሰጥቷል፡-

A widely participatory process of social change and material advancement including greater equality, freedom and other valid qualities for the majority of the people through their gaining greater control over their environment (Moemeka 1994:10)

ልማት ብዙሃን የተሻለ አካባቢያቸውን የመቆጣጠር ብቃት እንዲኖራቸው የሚያደርግ አሳታፊና የተሻለ እኩልነትን፣ ነፃነትንና ሌሎች ዋጋ ያላቸው እሴቶችን ጨምሮ ማቴሪያላዊ መሻሻል የሚያስገኝ ማሕበራዊ ሂደት ነው።

በጀርመን የተገናኘ አንድ የዓለም አቀፍ የብሮድካስት ኢንስቲቲዩት የሥራ ኮሚቴ (A working committee of the Int'l Broadcast Institute) ለልማት የሚከተለውን ቀላል ትርጓሜ ሰጥቶታል።

The improvement of the well being of the individual and the betterment of the quality his/her life.

ልማት ማለት ያንድ ግለሰብ ደህንነትና የኑሮው ደረጃ መሻሻል ማለት ነው።

አንድሩ ሞሜካ የተሰኘ ፀሐፊ በበኩሉ ልማትን እንደሚከተለው ገልጾታል፡-

Therefore. though seen from different perspectives, development means one basic thing in all perspectives and to all people a change for the better in the human cultural, socioeconomic, and political conditions of the individual and consequently of the society. (Moemeka, 1994: 11)

የምዕራቡን የልማት ዕይታና ትርጓሜን ሲያጣጥል ይኸው አንድሩ ሞሜካ የተሰኘው ፀሐፊ እንደሚከተለው አስቀምጧል፡፡

Development is not really a matter of technology or of gross national product, more importantly it is a matter of increased knowledge and skills, growth of new conscience, expansion of the human mind, the uplifting of the human spirit and the fusion of human confidence (Ibid)

ልማት ማለት የቴክኖሎጂ ወይም ጅምላ የሀገር ምርት ጉዳይ ብቻ አይደለም ይልቁንስ የተሻለ ዕውቀትና ክሂሎት፣ የአዲስ ንቃተ ሕሊና እድገት፣ የሰው አዕምሮ ስፋት፤ የሰው ሞራል የማንሣት እና በራስ መተማመንን የማስገኘት ጉዳይ ነው፡፡

የሚዲያና የልማት ትስስር

ሚዲያና ልማት ወይም ልማትና ሚዲያ ሁለት የተለያዩ የማይገናኙ በያሉበት የራሳቸው ሚናና ገጽታ ያላቸው ሊመስሉ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን በሁለቱ መካከል ትስስር ወይም ቁርኝነት መኖሩ ብዙም የሚያከራክር አይደለም፡፡ ሚዲያ የግንኙነት ዘዴ ወይም የመገናኛ ዘዴ እንደመሆኑ መጠን በመገናኛ ዘዴዎች አማካኝነት በሰዎች በዜጐች ባሕል/ ኑሮ ሕይወት ውስጥ ለውጥ ወይም ዕድገት ማምጣት ይቻላል፡፡ ዜጐችን ወደተሻለ ደረጃ፣ ከፍ ወዳለ ደረጃ ማሳደግ ደግሞ ልማት ነው፡፡ ስለዚህም ነው በሚዲያ ላይ ከፍተኛ መራኮትን የምናየው፡፡ በብዙ ሀገሮች ሚዲያዎች በተለይም የብሮድካስት /ሚዲያዎች በመንግሥት ቁጥጥር ስር እንዲሆኑ የሚፈለገው በነርሱ አማካይነት ከፍተኛ ለውጥና ውጤት ማምጣት ይቻላል ተብሎ ስለሚታመን ነው፡፡ በሕትመት ሚዲያዎች (print media) ም ቢሆን ለተለያየ ዘዴ፣ ጠበቅ ያለና የማያፈናፍን ሕግ በማውጣት ሳንሱር በማድረግ ቅጣቶችን በማብዛት በግል ባለቤትነት ስም የሕትመት ሚዲያዎች በመንግሥት ደጋፊዎች እንዲያዙ በማድረግና ሥራውን በመቆጣጠር የመንግሥት ሥልጣን የያዙት ያላሰለሰ ጥረትና ትግል የሚያደርጉት፡፡ በተለይም ነፃ ኘሬስ የሕዝብ ነፃነት መገለጫ በመሆኑና በመንግሥታት ላይ ሳንሱር በመሆኑ መንግሥታት በቀላሉ የሚያዩት ነገር አይደለም፡፡

ነፃ ኘሬስ ወይም የሕትመት ሚዲያ የሁለትዮሽ ማለትም የሕዝቦችና የመንግሥታት የጋራ መነጋገሪያ መድረኮች ናቸው፡፡ በዚህ ሂደትም በበርካታ ሀገራዊ፣ ማሕበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ወዘተ ጉዳዮች ላይ ሃሳብ ለሃሣብ የሚለዋወጡበት ነው፡፡ የብሮድካስት ሚዲያዎች ባብዛኛዎቹ ሀገሮች በመንግሥታት የመያዝ ሁኔታ ቢስተዋልም እንደ ሕትመት ሚዲያ

እነኚኖቹም በአንድ አቅጣጫ ብቻ የመረጃዎች መፍሰሻ ቧንቧዎች ሳይሆኑ በሁለት አቅጣጫና የመረጃዎችን ፍሰት የሚያስተናግዱ እንዲሆኑ ይጠበቃል።

ሚዲያ በሕዝብ ወይም በተደራሾች አስተያየትና አመላካከት ላይ ለውጥና ተጽዕኖ የማምጣቱን ያህል በያንዳንዱ ተደራሽ ማንነት፣ ስብዕና፡ አኗኗር፣ አመጋገብ፣ አለባበስ፣ ጤና፣ ሕይወት ወዘተ ላይ ጫናን ይፈጥራል፤ ሚዲያ በመልካም እና ለመልካም ይለውጣል ያሻሽላል፤ እንደመረጃው ዓይነትም ለበጐ/ ለመልካም፤ በመልካም ያልሆኑ አሉታዊ ተጽዕኖዎችን ያመጣል።

የሚከተሉት ሁለት ፓራግራፎች ስለሚዲያ የተሰጡ መጥፎና በጐ አስተያየቶችን ያንፀባርቃሉ።

The effects of the media may be bad, claim some critics. They warn us that mass communication may be doing things to us that we really do not want. Some say that media content makes us more violent, weakens our moral character, controls our beliefs, attitudes and opinions, leads us to buy things we do not need, and heavily influences many of the decisions that we think make independently (Difleur and Dennis 1994:20)

ይህ ወደ አማርኛ ሲመለስ እንደሚከተለው ሊቀመጥ ይችላል፡-

አንዳንድ ሀያስያን የሚዲያ ውጤት ወይም ተፅዕኖ መጥፎ ሊሆን ይችላል ይላሉ። እነኚህ ወገኖች የሕዝብ መገናኛ ዘዴዎች በኛ ላይ የማንፈልጋቸውን ነገሮች እያደረገብን እንደሆነ ያስጠነቅቃሉ። እንዳንዶቹ ሃያሲያን ሚዲያዎች ወደኛ የሚያደርሷቸው መረጃዎች ይዘት እኛን የበለጠ ዱለኞች፣ የሞራል እሴቶቻችንን የሚያዳክሙ፣ እምነቶቻችንን፣ አስተያየቶቻችንንና አመለካከቶቻችንን የሚቆጣጠሩ እና ሳንወድ የማንፈልጋቸውን ነገሮች እንድንገዛ የሚያደርጉን እኛ በገዛ ራሳችንና በነፃነት የወሰንናቸው በሚመስለን ውሳኔዎቻችን ላይ ከባድ ተጽዕኖ የሚያደርጉ ናቸው ይላሉ።

የሚዲያን በጐ ተፅዕኖ በተመለከተ ደግሞ የሚከተለውን እንይ፡-

Other analysts claim the media are forces for good in society. They say that the media enrich our lives and bring us all closer together, provide us with satisfying and stress- relieving entertainment, and make us more aware of important public issues and problems. These analysts maintain that the media help us understand social problems, enlighten us politically, improve our aesthetic tastes for good music and theater, and aid in rooting out corruption or incompetent government officials. (Ibid.)

የዚህ የአማርኛ ትርጉም እንደሚከተለው ነው።

ሌሎች ተንታኞች ደግሞ ሚዲያዎች በሕብረተሰቡ ውስጥ ለመልካም የሆኑ ሃይላት ናቸው ይላሉ። እነኚኞቹ ሚዲያዎች ሕይወታችንን ያዳብራሉ፤ ሁላችንን ያቀራርቡናል፤ ሕይወት ከሚፈጥርብን ጫና የሚያላቅቁ አርኪ መዝናኛዎችን ያቀርቡልናል፤ ስለ ዋና ዋና የሕዝብ ጉዳዮችና ችግሮች እንድናውቅ ያደርጉናል ይላሉ። በእነኚኞቹ ተንታኞች አቋም ሚዲያዎች ማሕበራዊ ችግሮችን እንድንረዳ፤ የፖለቲካ ዕውቀትና ግንዛቤ እንድናገኝ ጥሩ ሙዚቃና ቲያትርን የመለየት ችሎታ እንዲኖረን እና ሙስናን ለመዋጋትና ብቃት የሌላቸውን የመንግሥት ባለሥልጣናትን ለማስወገድ ይረዱናል። ይላሉ።

ዛሬ ዛሬ ብዙ ፀሐፍት ሚዲያዎች ልማትን፣ ዕድገትን፣ በራስ የሚተማመን ስብዕናን፤ ነፃነትን፣ የተሻለ ሕይወትን ለማምጣት መዋል አለባቸው የሚል አቋም ያንፀባርቃሉ። ይህንኑ ተከትሎ ይመስላል የዛሬው የመወያያ ርዕስ "ሚዲያ እና ልማት" የተባለው። ዛሬ በርካታ ፀሐፍት "mass communication must be for development" የሕዝብ መገናኛ አውታሮች ለልማት በሚል መርህ ዙሪያ ብዙ ይላሉ ይዘክራሉ። ሌሎችም Development Communication በሚል መርህ ብዙ ጽሑፎችን ለንባብ አብቅተዋል፣ እያበቁም ናቸው። "የሚዲያ ለልማት" አቀንቃኞች የሐሳቦች ልውውጥና የመረጃዎች ፍሰቶች ለልማት ሂደቶችና ዓላማዎች ይዋሉ የሚሉ ሲሆን፤ ሚዲያዎች ለልማት ይዋሉ ሲባልም በ human aspect of development በሰው ኃይል ዕድገትና ልማት ላይ አትኩሮት ይደረግ የሚሉ ናቸው። አንድሩ ሞሜክ ሮዛሪዮ ብሬይድ በ1979 ዓ.ም የጻፈውን በመጥቀስ እንዲህ ይላል፡-

In a very broad sense, development is the art and science of human communication applied to the speedy transformation of a country (economic growth, modernization, industrialization etc) and the mass of its people (self-actualization, fulfillment of human potential, greater social justice etc.) Through the identification and utilization of appropriate expertise in the development process that will assist in increasing participation of the intended beneficiaries at the grassroots level (Moemeka, 1994: 12-13)

የዚህ የአማርኛ ትርጉም፡-

በጣም ጠቅለል ባለ መልኩ ልማት በአንድ ሀገር ፈጣን ለውጥ ለማምጣት /ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን፣ ዘመናዊነትን ኢንዱስትሪያዊ ዕድገትን ወዘተ. እና ያብዛኛውን ሕዝብ / ራስን የማስቻል ችሎታን ዓውቆ የማውጣት፤ የላቀ ማሕበራዊ ፍትሕ ወዘተ በልማቱ ሂደት የተጠቃሚነቱን ተሳትፎ በገበቅተኛ ደረጃ ሊረዱና ሊጨምሩ የሚችሉ ኤክስፐርቶች በመጠቀም የሚረዳ የመገናኛ የመድረሻ ሳይንስ ወይም ጥበብ ነው የሚል ነው።

ናይሬያ የሚባለው ሌላ ሀሐፊ የሚዲያንና የልማትን ትስስር እንዳጭላ ሞሜካ እንደሚከተለው ገልጾታል፡-

Mass media could play a valuable role in development by bringing about the appropriate exposure to change and by slowing change down when it was likely to have a negative impact.

መገናኛ ብዙሃን ለተገቢ ለውጥ የመጋለጥ ሁኔታ እንዲኖር በማድረግና የለውጥ ፍጥነት አሉታዊ ውጤት ሲኖረው ደግሞ ዝግ እንዲል በማድረግ በልማት ረገድ ጠቀሜታ ያለው ሚና ሊጫወት ይችላል።

ሌሎችም እንደ ሌርነር፣ ፖይ፣ ሮጀርስ ሽራውም የመሳሰሉት የሚዲያ ላይ ፀሐፍት የልማትንና የሚዲያን ትስስር ወይም ሚዲያ ልማትን ለማምጣት ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ማስረገጣቸውን ካዛን እንደሚከተለው ይገልፃል።

Directly or indirectly endorsed, a model of development in which urban political elite, often advised by international agencies or western governments determined the goals of society and set about manipulating the masses towards these goals. The very models of broadcasting imported from the west confirmed the notion of heavily concentrated media systems physically and structurally located close to the centers of political and military power, employing technologies equipped only for one way conmunication. (Kazan, 1994: 49)

ከተሜ የፖለቲካ ምሁራን ባብዛኛው በአለም አቀፍ የሚዲያ ተቋማት ወይም በምዕራብ መንግሥታት አማካይነት በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የሚቀበሉት የልማት ሞዴል የሕብረተሰብን ግቦች የሚወስን እና ሕብረተሰቡንም እነዚያ ግቦች ላይ ለመድረስ የሚያንቀሳቅስ ነው። ከምዕራብ የተወሰዱ የብሮድካስት ሚዲያ ሞዴሎች የሚዲያዎቹን በፖለቲካ እና በወታደራዊ ማዕከሎች ዙሪያ መከማቸት እና የቴክኖሎጂያቸውን በአንድ አቅጣጫ ግንኙነት መሠራትን ያመለክታሉ።

የልማትንና የማዲያን ትስስር ሲያሰምር አንድሩ ሞሜካ በበኩሉ የሚከተለውን ጽፏል፦

In broad terms, the ultimate objectives of national develop- ment (urban and rural) are economic growth, equitable distribution of facilities and of benefits, national cohesion, and human development. These are also, in broad terms, the ultimate objectives of development communication, even though because of the importance attached to intelligent understanding of development issues develop- ment communication gives the pride of place to human development. (Moemeka, 1994)

ባጠቃላይ አገላለጽ በገጠርም ይሁን በከተማ የብሔራዊ ልማት ግቦች የኢኮኖሚ ዕድገት፣ ፍትሐዊ የአገልግሎቶችና የጥቅማ ጥቅሞች ስርጭት አገራዊ አንድነት እና የለው ኃይል ልማትን ማምጣት ነው። የልማት ጥያቄዎችንና ጉዳዮችን በጥልቀት ከመረዳት የተነሣ የመገናኛ ብዙሃን ለልማት ለሰው ኃይል ልማት ቀዳሚ ቦታ ከሚሰጥ በስተቀር የሚዲያ ወይም የብዙሃን መገናኛ ዘዴዎች ለልማት መዋል ዓላማዎችም እኚሁ ለልማት የተጻፉት ዓላማዎች ናቸው።

አንግዲህ ትልቅ የሕዝብ መድረሻ፣ ትልቅ የመረጃ መፍሰሻ የሆነው ሚዲያ የልማት አጀንዳ ማስፈፀሚያ ሊሆን እንደሚችል ብዙም የሚያጠራጥር ጉዳይ አይደለም።

ሚዲያ በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ከቀድሞው ንጉሥ ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ ዘመን ጀምሮ ሁለቱ ዋና ዋና የሚዲያ ዓይነቶች ማለትም ብሮድካስት ሚዲያ እና የሕትመት ሚዲያ (print media) በሥራ ላይ ነበሩ። አሁንም አሉ። ብሮድካስት ሚዲያን በተመለከተ የኢትዮጵያ ቴሌቪዢንና የኢትዮጵያ ሬዲዮ በቀድሞ ንጉሥ መልካም ፈቃድና ለውጥ ፈላጊነት እንዲጀመሩ ተደርገው ይኸው እስከዛሬ ድረስ ምንም የጐላ ተፎካካሪ ሳይመጣባቸው ላለፉት ብዙ ዓሥርተ ዓመታት ቆይተዋል። የብሮድካስት ሚዲያ ዛሬም በኢትዮጵያ ውስጥ በመንግሥትና አሁን የመንግሥት ሥልጣን በያዘው የፖለቲካ ፓርቲ ባለቤትነትና ቁጥጥር ሥር ናቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ እስካሁን የነበረውና አሁንም ያለው የብሮድካስት ሚዲያ ሁኔታ የመንግሥትን ሞኖፖሊ የሚያመለክት ነው። በቅርብ ጊዜ የብሮድካስት ሚዲያን በከፊልም ቢሆን privatize አድርጐ regulate ለማድረግ ሕጐች ቢወጡም እስከዛሬ፣ እኔ እስከማውቀው፣ የግል ብሮድካስት ሚዲያ በኢትዮጵያ ውስጥ አልተጀመረም፤ ምናልባት ለሞኑን በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን መመልከቻ መስኮት የብሉ ናይል ቲቪ የሚል ተመልክቼአለሁ። ይህ የግል ይሁን የመንግሥት ይሁን ለኔ ብዙም ግልጽ አይደለም።

ብሮድካስት ሚዲያ privatize ቢደረግም እንኳ ትርጉም ያለው ተጽዕኖ ማምጣት እስኪችል ድረስ ጊዜ ይወስዳል። ደግሞም የግል ብሮድካስት ሚዲያ ቢኖርም በአድማጮች ወይም በተመልካቾች ፍላጐት ላይ የሚያተኩር እንደሚሆን ካሁኑ ግንዛቤ መውሰዱ መልካም ነው።

በኢትዮጵያ ውስጥ የመንግሥት ብሮድካስት ሚዲያዎች ባብዛኛው ባንድ መስመር የመረጃ ፍሰት ላይ የሚያተኩሩ ናቸው ቢባል ስሕተት አይመስለኝም። በኢትዮጵያ ውስጥ የመንግሥት ብሮድካስት ሚዲያዎች ሕዝብ አሳታፊ ናቸው ለማለትም ያስቸግራል። በተለይ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሕዝብና የመንግሥት የጋራ መድረክ ነው ለማለት የሚቻል አይመስለኝም። የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ምናልባት አሳታፊና ሕዝባዊ ነው ለማለት የሚያስደፍር ሁኔታ ቢኖር በምርጫ ጊዜ ለተለያዩ የፖለቲካ ድርጅቶች እና ግለሰቦች የሚሰጠው ትንሽ የአየር ጊዜ ነው። በዚህም አሳታፊነቱ ላይ ጥያቄ ሊነሳበት ይችላል።

በኋላ ላይ የምለው ቢኖረኝም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን እንደ ብሮድካስት ሚዲያነቱ ቆም በሎ ራሱን መፈተሽ ያለበት ጊዜ የደረሰ ይመስለኛል። ለመሆኑ ሕዝብ የምናስተላልፋቸውን ኘሮግራሞች ይከታተላል ወይንስ አይከታተልም? ተጽዕኖ እያመጣን ነው ወይንስ እንዴት ነው? ዛሬ አማራጭ የቴሌቪዥን ጣቢያዎችና መስመሮች በሽ በሆነበት ጊዜ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሥርጭት በደረሰባቸው ቦታዎች ላይ ኘሮግራሞቻችን ተቀባይነት አላቸው? ወይንስ የላቸውም? ብሎ መረጃ ለመሰብሰብ መሞከር መልካም ይመስለኛል። ከዚህም ሌላ ሕዝብ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ከሚተላለፉት ኘሮግራሞች የትኞቹን ነው ወዶ የሚከታተለው? ሌሎቹን ለምን አይከታተልም ብሎ ጠይቆ ምክንያቶቹን ለማወቅ መሞከር ጊዜው የግድ የሚል ይመስለኛል።

የሬዲዮ ሥርጭትን በተመለከተ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የተከፈቱት ሬዲዮ ፋናና፣ ኤፍ ኤም አዲስ 97.1 ሥርጭታቸው በሚደርስባቸው ቦታዎች የተሻለ አድማጭ ያላቸው ይመስላል። ምርምር ባላደርግባቸውም በኔ ግምት ሬዲዮ ፋናና ኤፍ ኤም አዲስ 97.1 ከኢትዮጵያ ሬዲዮ ይልቅ የተሻለ ሕዝብን የሚያሳትፉ ይመስለኛል። አሳታፊ በሆኑ መጠን ደግሞ ተወዳጅነታቸውና ተደማጭ ነታቸው ይጨምራል።

ዛሬ በሳተላይት ዲሽች አማካይነት የውጭ ብሮድካስት ሚዲያዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በተለይም በከተሞች አካባቢ ትልቅ ሚና ኖሯቸዋል። የዛሬ ሁለት ሦስት ዓመት ገደማ ለተወሰነ ጊዜ ይተላለፍ የነበረው ቲቪ አፍሪካ የተሰኘው የቴሌቪዥን ፕሮግራም ምን ያህሉን የቴሌቪዥን ተመልካች ተቆጣጥሮ እንደነበር በተለይም ለስንቱ ወጣት ሱስ ሆኖ እንደበር የቅርብ ጊዜ ትዝታችን ነው። ከዋኖቹ የብሮድካስት ሚዲያ ወጣ ስንል electronic media ፖኤሌክትሮኒክ ሚዲያን እናገኛለን። እናም እነዚህ የኤሌክትሪክ ሚዲያዎች ወይም ዓለም አቀፍ የኮምፒውተር የመረጃ መረቦች የብዙዎችን ጊዜና አትኩሮት ተቆጣጥረውት እናገኛለን። በነኚህ መረቦች ጥሩ ጥሩ መረጃዎች የመገኘታቸውን ያህል ብዙ ርካሽና የጨቅላዎችንና የወጣቶችን ሥነ አዕምሮ የሚያበላሹ መረጃዎች ይተላለፋሉ። በነኚህ መረቦች ይህ ነው የማይባል የመረጃ ወረራና ጦርነት ተከፍቷል። ሀገራችንም ከእነኚህ የአለም አቀፍ መረቦች የመረጃ ወረራና ጦርነት ውጪ አይደለችም። ለጊዜው ሁሉም ቤት ባይንኳኳም ነገና ተነገወዲያ ግን አይቀርም። ዛሬ የመረጃ ወረራው መገለጫ ዓይነቱ ብዙ ነው። ከአለም አቀፍ መረቦች ባልተናነሰ ሁኔታ ዛሬ የሙዚቃ ባሕል ወረራ፣ ልዩ ልዩ ፊልሞች ወይም ሲኒማ በቪዲዮ በዲቪዲ እና በሲዲ የሚሠራጩ ሁሉ በጐም ይሁን አሉታዊ፣ ትልቅ ተጽዕኖ የሚያመጡ ሌሎች ሚዲያዎች ናቸው።

ወደ ሀገራችን print media መለስ ስንል በዋናነት የምናገኘው ኘሬስን ነው። በኘሬስ ውስጥ በዋናነት የሚጠቃለሉት ደግሞ ዕለታዊ ጋዜጦች፣ ሳምንታዊ ጋዜጦች እና መጽሔቶች ናቸው። በኢትዮጵያ ውስጥ ከ1983 ዓ.ም ወዲህ የግል ጋዜጦችና መጽሔቶች በአበረታች ቁጥር መውጣት ይዘዋል። ይህ መልካም ሲሆን ከእነኚህ የግል print media ጋር ተቆራኝቶ ያለው የኘሬስ ነፃነት ጉዳይ አብሮ ካልታየ በኢትዮጵያ የሕትመት ሚዲያ ጉዳይ ታየ ለማለት አይቻልምና ትንሽ በዚያ ላይ እናተኩራለን።

በዓለም ዙሪያ ሠፍኖ ካለው አሠራር እንደምናየው የኘሬስ ነፃነት የሚከበረውም ሆነ የሚገደበው በሕግጋተ መንግስት፣ በልዩ የኘሬስ ሕጐች እና በወንጀለኛ መቅጫ ሕጐች ነው።

ወደ ሀገራችን ወደ ኢትዮጵያ ስንመጣ በመጀመሪያ ከታሪክ አኳያ ስንመለከት ለመጀመሪያ ጊዜ በወጣው የሀገሪቱ ሕገ መንግሥት ማለትም የ1923ቱ ሕገ መንግሥት ውስጥ የግል አኗኗርን አስመልክቶ የሚከተለው ሠፍሮ ነበር።

<u>አንቀጽ 26</u> ሕግ ከሚፈቅድበት ጊዜ በቀር የኢትዮጵያ ተወላጅ የሚጻጻፈውን ወረቀት ማንም ሰው ቢሆን በግሉ ሊመረምርበት አይችልም ከ1923ቱ ሕገ መንግሥት ቀጥሎ በ1948

የወጣው እና ከተሻሻለው የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ሕገ መንግሥትካ የሚባለው ወጣ። በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ በአንቀጽ 41 እና 42 ሥር የሚከተለው ሠፍሮ ነበር።
አንቀጽ 41 በመላው ንጉሠ ነገሥት ወስጥ በሕግ መሠረት የንግግርና የጋዜጣ ነፃነት የተፈቀደ ነው።

አንቀጽ 42 ለሀገር ፀጥታ አሰፈላጊ የሆነ ድንገተኛ ነገር የታወጀበት ጊዜ ካልሆነ በቀር በጽሕፈት መላላክ ግንኙነት ላይ የመቆጣጠር ሥራ አይደረግም።

ከ1948ቱ ሕገ መንግሥት ቀጥሎ የኘሬስ ነፃነትንና ገደብን አስመልክቶ በዋናነት የሚጠቀሰው ሕግ 1949ኙ የቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሲሆን በዚያ ሕግ ወስጥ በበርካታ ቁጥሮች ሥር የኘሬስ ነፃነትን የሚመለከቱ ክልካይ እና የቅጣት ድንጋጌዎች ሠፍረው ነበር። የ1949ኙ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በ1997 ዓ.ም በአዲስ የወንጀላኛ መቅጫ ሕግ ተተክቷል።

ወደ ቅርብ ጊዜ ታሪካችን መለስ ስንል የምናገኘው በ1983 ዓ.ም. የወጣውን የሽግግር ጊዜ ቻርተር እና እርሱ ከወጣ ከሁለት ዓመታት በኋላ የወጣውን የ1985ቱን የኘሬስ ነፃነት አዋጅ ነው። በነገራችን ላይ አዋጅ ቁጥር 34/1985 ዓ.ም. ተብሎ የወጣው የኘሬስ ነፃነት አዋጅ አሁንም ሥራ ላይ ነው። እንደምናውቀው ይህን አዋጅ ለማሻሻል በ1995 ዓ.ም. ረቂቆች ቀርበው ውይይት ሲደረግባቸው ነበር። ሆኖም እስካሁን የኘሬስ ነፃነት አዋጅ ቁጥር 34/1985 በሌላ ሕግ አልተተካምና ይህ አዋጅ ገና ወደ ታሪክነት ደረጃ አልተሸጋገረም።

ምንም እንኳን በ1983 ዓ.ም. የወጣው የሽግግር ጊዜ ቻርተር በ1987 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሕገ መንግሥት ቢተካም ይኸው ላለፉት 11 ዓመታት ያህል ሕገ መንግሥቱን ተከትሎ የወጣ ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ጋር የሚጣጣም የኘሬስ ሕግ አልወጣም።

የኘሬስ ነፃነት በሕግ ዕውቅና የማግኘት ሁኔታ በተሻለ መልክ በሀገራችን መታየት የጀመረው በ1983 ዓ.ም. በወጣው ከሽግግር ጊዜ ቻርተር ጀምሮ ነው ቢባል ስሕተት አይመስለኝም። ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች መርሆዎች እመራለሁ ብላ በወቅቱ ማለትም ለሽግግሩ ጊዜ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ በነበረው ቻርተር በክፍል አንድ አንቀጽ አንድ ሥር የሚከተለውን አሥፍራ ነበር።

የተባበሩት መንግሥታት ጠቅላላ ጉባዔ እ.ኤ.አ. በዲሴምበር 10 ቀን 1948 ዓ.ም. የፀደቀውንና የታወጀውን ቁጥር 217 ሠ(ሀህሀ) ውሳኔ መሠረት በማድረግ የግለሰብ መብቶች ያለአንዳች ገደብ በሙሉ ተከብረዋል። በተለይም እያንዳንዱ ግለሰብ፡-

ሀ/ የእምነት ሀሳብን የመግለጽ፣ የመደራጀት በሠላም የመሰብሰብና የመቃወም ነፃነት አለው።
ለ/ የሌሎችን ሕጋዊ መብቶች እስካልተጋፋ ድረስ በማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ወስጥ ያለአንዳች ገደብ የመሳተፍና የፖለቲካ ፓርቲዎችን የማደራጀት መብት አለው።

ኢትዮጵያ በሽግግር ጊዜ ቻርተር ወስጥ ተከብረዋል በማለት ባሠፈረችውና እንደ አውሮፓ አቆጣጠር በ1948 ዓ.ም. በወጣው የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ በአንቀጽ 19 ሥር የሚከተለው ሠፈር ይገኛል፡-

ማንኛውም ሰው ሐሳቡን በነፃነት የመያዝ እና የመግለጽ መብት አለው፡፡ ይህ መብት ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳብን በነፃነት የመያዝን እና በማንኛውም መገናኛ ዘዴ መረጃዎችንና ሐሳብን የመፈለግ፣ የመቀበል እና የማስተላለፍ፣ በድንበር ያልተገደበ መብትን ያካትታል፡፡

ሀገራችን በሽግግር ጊዜ ቻርተር ውስጥ የግለሰብ ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶችን አስመልክቶ በ1948ቱ የሰብዓዊ መብቶች መግለጫ ውስጥ የተካተቱትን መርሆዎች ከተቀበለች በኋላ ለመጀመሪያ ጊዜ የኘሬስ ነፃነትን የሚመለከት፣ ልዩ ሕግ ማለትም አዋጅ ቁጥር 34/1985ን አውጥታለች፡፡ ከላይ ለማመልከት እንደተሞከረው በዓለም ዙሪያ ካሉት አሠራሮች ስንነሳ የኘሬስ ነፃነት የሚጠበቀው በሕግጋት መንግሥት እና በልዩ የኘሬስ ነፃነት ሕጐች ነው፡፡ ሕግጋተ መንግሥት መሠረታዊ የሆኑ መብቶችንና ነፃነቶችን ያያዘ ሠነዶች እንደመሆናቸውና ገዘርዘር ጉዳዮች በሕግጋት መንግሥት ውስጥ በተመለከቱት መርሆዎች ጥላ ሥር በገዘርገዘር ሕግ ስለሚገለጹ በሕገ መንግሥት ውስጥ የሠፈሩትንና ዕውቅና የተሰጣቸውን ነፃነቶችና መብቶች ሳይጥስ በሕግጋት መንግሥቱ የታሰቡትን ገደቦችንም አካቶ ዝርዝር ሕግ ማውጣቱ አስፈላጊ ነው፡፡ ከኘሬስ ነፃነት አኳያ በቻ ሳይሆን ከሌሎችም በሕግጋተ መንግሥት ወስጥ ከሚካተቱት የተለያዩ ጉዳዮች አኳያ ዝርገዘር ሕግ ማውጣት የግድ አስፈላጊና ለነገ የማይባል ጉዳይ ነው፡፡

ወደ ኘሬስ ነፃነት አዋጅ ቁጥር 34/1985 ስንመለስ በመቅድሙ ወስጥ በግልጽ እንደሠፈረው አዋጁን ማውጣት ያስፈለገው፡-

- ሀሳብን በነፃ የመግለጽ መብት በኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር የተረጋገጠ ስለሆነ፣
- ሀሳብን በነፃ የመግለጽ መብት በተሟላ መልኩ ተግባራዊ ሊሆን የሚችለው ነፃ የሆነና የተጠናከረ ኘሬስ ሲኖር፣ ሲገለበትና ሲስፋፋ በመሆኑ፣
- ነፃ ኘሬስ ዜጐች ሃሳባቸውን በነፃ የሚገልፀበት መድረክ ከመሆኑም በላይ የግለሰብና የሕዝቦች መብት እንዲከበርና ዲሞክራሲያዊ ባህል እንዲዳብር በማድረግ እንዲሁም ዜጐች የተለያዩ አንገብጋቢ ጉዳዩች ላይ ሚዛናዊ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በመንግሥት አመራርና አሠራር ላይ ሃሳብ እንዲያቀርቡ ለማስቻል ጉልህ ሚና የሚጫወት ስለሆነ፣
- ኘሬስ ይህንኑ ተግባሩን ሊያከናውን የሚችለው የቅድሚያ ምርመራ ሴንሴርሺኘ እና ሌላም ተመሳሳይ ገደብ ሳይደረግበት በነፃና በሃላፊነት ስሜት ሊንቀሳቀስ የሚችልበት ምቹ ሁኔታ ሲፈጠርለት ስለሆነ፣
- በዚህም መሠረት ስለኘሬስ ነፃነት መብትና ግዴታ የሚደረግ ሕግ ማውጣት አስፈላጊ ስለሆነ፤ነው አዋጁ የታወጀው ይላል፡፡ ወደ ውስጥ ሲገባ በአንቀጽ 3 ላይ ኘሬስ ነፃ መሆኑን ለመደንገግ፣

1. በኢትዮጵያ ውስጥ የኘሬስ ነፃነት ዕውቅና አግኝቷል፤ ተረጋግጧል፡፡
2. የቅድሚያ ምርመራና ማናቸውም ሌላ ተመሳሳይ ገደብ በዚህ አዋጅ ተከልክሏል ይላል፡፡

I/ የኘሬስ ዓላማዎች የሚል ርዕስ በተሰጠው የአዋጁ አንቀጽ ላይም፣
ኘሬስ ለመሠረታዊ ነፃነት፣ ለሠላም፣ ለዲሞክራሲ፣ ለፍትሕ፣ ለእኩልነት፣ ለማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት መፋጠን የቆመ ነው፡፡

2/ በዚህም መሠረት ኘሬስ፣
- ዜና ይሰበስባል፣ ያሠራጫል፤
- በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ያቀርባል፤
- በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ ትችት ያደርጋል፤
- በሌሎች ዘዴዎች በመጠቀም የሕዝብን አስተያየት በመቅረጽ ተግባር ይሳተፋል፤
- ዓላማውን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራት ያከናውናል ይላል።

የኘሬስ መብቶች

የኘሬስ አዋጅ በክፍል ሶስት በአንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ /1/ /2/ እና 4/ሀ/ ሥር የኘሬስን መረጃ የማግኘትና የማሠራጨትን መብት አስመልክቶ፣
1. ማናቸውም የኘሬስ ተቋምና ወኪል በሌሎች ሕጐች የተሰጣቸው መብቶች እንደተጠበቁ ሆነው ከማናቸውም መንግሥታዊ የዜናና የመረጃ ምንጭ ዜናና መረጃ የመጠየቅ፣ የማግኘትና የመመዝገብ መብት አላቸው፣
2. ማንኛውም የኘሬስ ተቋምና ወኪል ያገኛቸውን ዜና መረጃና ሌሎች የኘሬስ ውጤቶች የማሠራጨት መብት አላቸው

በማለት ሲደነግግ የኘሬስ መረጃ የመጠየቅ፣ የማግኘት፣ የመመዝገብና የማሠራጨት መብት ግን ያለገደብ የተሰጠ አይደለም፤ እናም አዋጁ በዚሁ በአንቀጽ 8/3/ ሥር የኘሬስ መረጃ የመጠየቅ፣ የማግኘት፣ የመመዝገብና የማሠራጨት መብት ከሚከተሉት 5 ሁኔታዎች አኳያ የማይሠራ መሆኑን በልዩነት ደንግጓል።

ሀ/ በተወካዮች ምክር ቤት ምስጢር ነው ተብሎ የተወሰነ መረጃ፣
ለ/ በሌሎች ሕጐች ምስጢር በሆነ መረጃ፣
ሐ/ ፍርድ ቤቱ በሌላ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር በፍርድ ቤት በዝግ ችሎት የታየን ጉዳይ በሚመለከት መረጃ፣
መ/ በፍርድ ቤት ተይዞ በመታየት ላይ ያለን ጉዳይ በሚመለከት መረጃ፣
ሠ/ አስቀድሞ ካልተፈቀደ በስተቀር ወንጀል የተፈፀመበትን ግለሰብ የሚመለከት የግል መረጃ።

ሌላው በአንቀጽ 8/4//ሀ/ ሥር በመብትነት የተገለፀው የዜና ምንጭን ያለመግለጽ ሲሆን ይህም ቢሆን በልዩነት ሊገደብ የሚችልበት ወይም የማይሠራበት ሁኔታ በአንቀጽ 8/4/ /ሰ/ ሥር እንደሚከተለው ተደንግጓል፣

ፍርድ ቤት በመንግሥት ፀጥታ ወይም በቻርተሩ መሠረት በተቋቋመው የመንግሥት አስተዳደር ወይም በአገር መከላከያ ኃይል ላይ የተፈጸመ ወንጀልን በሚመለከት ግልጽና የቅርብ ጊዜ አደጋ የሚያስከትል ሲሆን ወይም በከባድ ወንጀል ክስ ላይ አማራጭ የሌለውና ወሳኝ የሆነ የመረጃ ምንጭ ሲሆን የኘሬሱ አሳታሚ ወይም አዘጋጅ የመረጃ ምንጩን እንዲገልጽ ሊያዘው ይችላል።

የኘሬስ ግዴታዎች እና ኃላፊነቶች

በ1985 ዓ.ም. የወጣው የኘሬስ አዋጅ መብቶችን ብቻ አንሳጽፎ አላቆመም። በኘሬስ ላይ ግዴታዎችን እና ሃላፊነቶችንም ጥሏል። ከዚህ አኳያ የአዋጁ አንቀጽ 10 የኘሬስ መብቶችን ይዘት ሕጋዊነት ስለመጠበቅ በሚል ርዕስ የሚከተሉትን ግዴታዎች አስፍሯል።

1. ማናቸውም ኘሬስ የሚያወጣው ወይም የሚያሠራጨው የኘሬስ ውጤት በሕግ የሚያስጠይቅ ይዘት የሌለው መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፤
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም ኘሬስ የሚያወጣው ወይም የሚያሠራጨው ኘሬስ ውጤት፡-

ሀ/ በመንግሥት ፀጥታ ወይም በቻርተሩ መሠረት በተቋቋመው የመንግሥት አስተዳደር ወይም በአገር መከላከያ ኃይል ላይ ከሚፈፀም ወንጀል፤

ለ/ በግለሰብ፤ በብሔር/ብሔረሰብ በሕዝብ እና ድርጅት ላይ ከሚፈፀም የስም ማጥፋትና በሀሰት የመወንጀል ድርጊት፤

ሐ/ ብሔረሰብን ከብሔረሰብ ከሚያጋጭ ወይም በሕዝቦች መካከል የእርስ በእርስ ግጭት እንዲፈጠር ከሚፈፀም የማነሳሳት ወንጀል፤

መ/ ለጦርነት ከሚደረግ ቅስቀሳ፤ነፃ መሆኑን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት።

በዚህ በአንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ላይ ለተጻፉት ግዴታዎች መፈፀም አዋጁ ሃላፊነትን በአንቀጽ 10 በንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት አከፋፍሏል። እናም በአዋጁ ኃላፊነትን ማከፋፈል አካሄድ በአንቀጽ 10 በንዑስ አንቀጽ 2 ከ /ሀ - መ/ ከተዘረዘሩት ግዴታዎች አንዱን የጣሰው በየጊዜው እየታተመ የሚወጣ ጋዜጣ ወይም ማጋዚን ወይም መጽሔት የጣሰው የኘሬስ ውጤት በየጊዜው እየታተመ የሚወጣ ጋዜጣ ወይም ማጋዚን ወይም መጽሔት ካልሆነ አሳታሚው፤ ግዴታውን የጣሰው የኘሬስ ውጤት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የሚሠራጭ ከሆነ ደግሞ ጉዳዩ የሚመለከተው ጋዜጠኛና ኘሮግራም አዘጋጅ ተጠያቂ እንደሚሆኑ ሃላፊነትን አከፋፍሏል።

በአንቀጽ 10 በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 ሥር የተጻፉትን ግዴታዎች የተላለፈ የኘሬስ ውጤት አዘጋጅ ጋዜጠኛ፣ ኘሮግራም አዘጋጅ ወይም አሳታሚ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት በወንጀል ተጠያቂ ሆኖ መቀጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ተጠያቂ የሆነው ሰው ከአንድ ዓመት በማያንስ ከ10 ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከብር 10,000 በማያንስ ከብር 50,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ወይም በሁለቱም እንደሚቀጣ በአዋጁ አንቀጽ 20 /1/ ሥር ተደንግጓል።

የአዋጁ የቅጣት አንቀጽ ማለትም አንቀጽ 20 በንዑስ አንቀጽ /2/ ሥር በኘሬስ ሥራ ላይ የተሠማራውንና ያልተመዘገበውን ወይም የኘሬስ ሥራ ፈቃድ ያላወጣውን የኘሬስ ባለቤት፤ አሳታሚ ወይም ዋና አዘጋጅ እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም እስከ 10,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል በማለት ሲደነግግ፤ በዚሁ በአንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ /3/ ደግሞ ከአንቀጽ 10 - 14 የተጻፉት ግዴታዎች ሳይፈፀሙ ቢቀሩ የኘሬስ ባለቤት፤ አሳታሚ ወይም ዋና አዘጋጅ ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እሥራት ወይም ከብር 5,000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ወይም በሁለቱም እንደሚቀጣ ይደነግጋል። አንቀጽ 20 /4/ በመጨረሻም የጅምላ ድንጋጌን ያስቀምጣል፤ እናም በዚህ በአንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ /1/ /2/

እና /3/ ከተመለከተው ውጪ ይህን አዋጅ የጣሰ ወይም እንዳይፈፀም ያሰናከለ ሰው በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል ይላል። ይህ ንዑስ አንቀጽ ከአዋጁ አንቀጽ 19 ጋር አብሮ ሊነሳይ ይችላል። አዋጁ በአንቀጽ 19 ላይ ከኘሬስ ጋር የመተባበር ግዴታ በሚል ርዕስ የመንግሥት ባለሥልጣናት ካለባቸው የተጠያቂነት መርህ የተነሳ እና ከሕገ-መንግስት ሥራ የማወቅ መብት የተነሳ ከኘሬስ ጋር የመተባበር ግዴታ እንዳለባቸው ይደነግጋል። እናም ቀደም ሲል አይተነው እንዳልኖነው በአዋጁ አንቀጽ 8 ኘሬስ መረጃን የመጠየቅ፣ የማግኘት፣ የመመገብና የማሠራጨት መብት ስላለው ይህ መብት ተግባራዊ ይሆን ዘንድ የአዋጁን አንቀጽ 19 መደንገግ ያስፈለገ ይመስላል። እናም ከሕግ አግባብ ውጪ መረጃን በመከልከል አዋጁን የጣሰ ወይም ባጠቃላይ አዋጁ እንዳይፈፀም ያሰናከለ ማንም ሰው አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌ መሠረት እንዲቀጣ አንቀጽ 20 /4/ ይደነግጋል።

ቀደም ሲል ለማየት እንደሞከርነው የኘሬስ አዋጁ በአንቀጽ 20 /1/ ላይ የጸፈው ቅጣት ተፈፃሚነት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ተፈጻሚ የማይሆኑትን ቅጣቶች ላይነካ ነው። ይህ ድርብ ድርብርብ ቅጣት ለምች በኘሬስ ሥራ ላይ እንዳይሠማሩ የሚያስፈራራ የተሰማሩትም ቢሆኑ ሥራውን እንዲያቆሙ የሚያደርግ ወይም ቅጣቶቹን ፈርተው አላስፈላጊ የሞንታቂ ሳንሱር በራሳቸው ላይ እንዲያደርጉ የሚያደርግ ነው።

የኘሬስ አዋጁ በቅጣት መልክ ባስቀመጣቸው የአንቀጽ 20 ድንጋጌምች ላይ አተኩርን እንጂ የአዋጁ አንቀጽ 14 በኘሬስ አማካይነት ለሚደርስ ጉዳት የፍትሐብሔር ተጠያቂነትም ሊኖር እንደሚችል ይደነግጋል። ስለዚህም አንድ የኘሬስ ውጤት አዋጁን በመጣስ ምክንያት አንድ ጋዜጠኛ፣ አዘጋጅ ወይም አሳታሚ ተጠያቂ ሊሆን የሚቀጣው በሶስት ፊት ይሆናል። አንደኛ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት፣ ሁለተኛ በኘሬስ አዋጁ የቅጣት ድንጋጌምች መሠረት ሶስተኛ ደግሞ በፍትሐብሔር ሕግ እና ወይም በንግድ ሕግ መሠረት ካሣ በመክፈል እንዲሁም እንደሁኔታው በራሱ ወጪና ኪሣራ የእርምት መግለጫ ወዘተ.. በማውጣት ይሆናል። እንዲያውም በአዋጁ አንቀጽ 16 /1/ መሠረት አንድ የኘሬስ ወጤት እንዳይሠራጭ ወይም እንዳስፈላጊነቱ እንዲወረስና በተመሰነ ጊዜ ውስጥ እንዲታጠል በፍ/ቤት ሲወሰን ቅጣቱ በአራት ፊት ሊሆን ይችላል።

የአዋጁ አንቀጽ 14 ድንጋጌ ተቀጪዎቹን ወይም በሃላፊነት የሚጠየቁትን ወገኖች ከማብዛት አኳያ በአንቀጽ በንዑስ አንቀጽ /2/ /ሀ/ እና /ለ/ ሥር ከጋዜጠኛው፣ ከአዘጋጁ ወይም ከአሳታሚው ሌላ በኘሬስ አማካይነት ለሚፈፀም የወንጀል ድርጊትና ወይም ለሚደርስ የፍትሐብሔር ጉዳት የኘሬስ ድርጅቱ በተደራቢነት ተጠያቂ ይሆናል ይላል። ይህ ድንጋጌ ተፈፃሚ የሚሆነው በወንጀልም ሆነ በፍትሐብሔር በኘሬስ አማካይነት ተጠያቂነት ሲኖር ሲሆን በተለይም በወንጀል ተጠያቂነት ሲኖር ወንጀሉን ከፈፀመው ጋዜጠኛ፣ አዘጋጅ ወይም አሳታሚ ውጪ የኘሬስ ድርጅቱን በተደራቢነት ተጠያቂ ማድረግ የሚገርም አካሄድ ሲሆን በመጀመሪያ ደረጃ በሕግ የሰውነት መብት የተሰጣቸው ድርጅቶች በወንጀል የሚጠየቁት በሕግ በግልጽ በተደነገጉት ጥቂት ሁኔታምች ሲሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ አንድ ሰው በወንጀል የሚጠየቀው እውቆ ወይም በቸልተኝነት ሕግ አታድርግ ያለውን ሲያደርግ ወይም በሕግ ማድረግ የሚገባውን ሳያደርግ ሲቀር ወይም እንደሁኔታው በሃላብ፣ በድርጊት ከአንድ የወንጀል ተግባር ጋር ሲተባበር ወይም ተካፋይ ሲሆን ነው። በሌላ አነጋገር አንድ ሰው በወንጀል የሚቀጣው ሕግ የደነገገውን ተላልፎ ሲገኝና ጥፋተኝነቱም በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ነው። ይህ ሳይኖር አንድን የኘሬስ ድርጅት በተደራቢነት በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ ያልተለመደ አካሄድ ነው።

አዋጁ በአንቀጽ 14 /2/ /ለ/ ሥር ያስቀመጠው የጉዳት ካሣ ድንጋጌ ቀላል አይደለም። በተለይም በተደራቢነት በወንጀል ተጠያቂ ነው፤ ጥፋተኛ ነው የተባለው የኘሬስ ድርጅት ለንግድ የተቋቋመ ከሆነ በተጐጂው ከሳሽ ላይ የደረሰውን ጉዳት ክብደትና መጠን እግምት ውስጥ በማስገባት በንግድ ሕግ መሠረት ድርጅቱ ያስመዘገበውን ካፒታል አጥፍ ሊደርስ ይችላል የተባለው ሰዎች በኘሬስ ሥራ ላይ እንዳይሠማሩየማድረግ፣ የተሠማሩትም ከሥረው ሥራውን እንዲያቆሙ የሚያደርግ እጅግ ከባድ ውጤት ያለው ይሆናል።

የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌዎች

ከኘሬስ ጋር በተያያዘ በ1997 ዓ.ም. በወጣው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ውስጥ በርካታ ድንጋጌዎች አሉ። የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ጠቅላላ ክፍል ውስጥ ማለትም ከቁ 1-237 ካሉት ድንጋጌዎች ውስጥ ቁ 32 እና ተከታታዮቹ በተለይም ከኘሬስ ጋር በተያያዘ እነማን በወንጀል ተጠያቂ ሊሆኑ እንደሚችሉ ከቁ. 42-47 ያሉት ድንጋጌዎች አግባብነት ሲኖራቸው የሕጉ ልዩ ክፍል ወደሚባለው ማለትም ከቁ. 238 - 733 ባሉትም ውስጥ እንደዚሁ በተለያየ መልክ ኘሬስን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች አሉ።

በመጨረሻም የወ.መ.ሕግ 3ኛው ክፍል ማለትም ከቁ. 734 - 865 ካሉትና የደንብ መተላለፍ ድንጋጌዎችን ወይም የደንብ ተላላፊ መቅጫ ሕግን ከሚባለው ክፍል ውስጥም ለኘሬስ አግባብነት ያላቸው ድንጋጌዎች አሉ።

በአጠቃላይ አነጋገር አዲሱ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ወይም የወንጀል ሕግ ከኘሬስ ነፃነት አኳያ ጠበቅ ያሉ ድንጋጌዎችን ይዞ ወጥቷል።

ሀገራችን ከሠብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች አኳያ በሽግግር ጊዜ ማለትም በ1983 ዓ.ም. እና የ1985ቱን የኘሬስ አዋጅ ስታወጣ ከነበረችበት ብዙ አበረታች ምዕራፎችን ወደፊት ሄዳ ነበር። የኘሬስ ነፃነትን ጨምሮ ሠብዓዊ መብቶችና ሕገ መንግሥታዊ ነፃነቶች በሀገራችን በሚገባ ለመከበራቸው ገና ብዙ ቢቀረንም፤ ቢያንስ ቢያንስ ግን የተለያዩ ዓለም አቀፍ የሠብአዊ መብቶች ማስከበሪያ ድንጋጌዎችን ተቀብላ በማጽደቅ እና የራሷ የሕግ ሥርዓት አካል በማድረግ ረገድ ሀገራችን ብዙ ርቀት ሄዳለች ቢባል ስሕተት አይመስለኝም። በዚህም ረገድ ኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነትን፣ ዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ፣ የሰሻልና የባሕል መብቶች ስምምነትን፣ ዓለም አቀፍ የሕፃናት መብቶች ስምምነትን፣ የአፍሪካን ሠብአዊና የሕዝብ መብቶችን ቻርተር ተቀብላ የራሷ ማድረጓ እንደ ቀላል እርምጃ የሚታይ አይደለም። ዳሩ ችግራችን ሕግ ሣይሆን ሀገሩን ተግባራዊ ማድረጉ ላይ ነው።

ከእነኚህ ኢትዮጵያ ተቀብላ የራሷ ካደረገቻቸው የሠብዓዊ መብቶች ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች ውስጥ ዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት በሚባለው ሰነድ በአንቀጽ 19 ሥር የሚከተለው ሠፍሮ ይገኛል፦

1. ማንም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለጽ ነፃነት ይኖረዋል፤
2. ማንኛውም ሰው ያለ ማንም ጣልቃገብነት ሀሳቡን የመግለጽ ነፃነት ይኖረዋል፤ ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ ገደብ ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት በሥነ ጥበብ መልክ ወይም ባለቤቱ በሚመርጠው በማንኛውም

የማሠራጫ ዘዴ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሐሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሠራጨት ነፃነትን ያካትታል።

3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 2 ሥር በተመለከቱት ነፃነቶች መገልገል ልዩ ግዴታዎችና ሃላፊነቶችን ያስከትላል። በመሆኑም በነፃነቶቹ ላይ የተወሰኑ ገደቦች ሊደረጉ ይችላሉ፤ ገደቦቹም በሕግ የተመለከቱትና

ሀ/ የሌሎችን መብቶችና መልካም ሥም ለመጠበቅ

ለ/ የሀገር ደህንነትና የሕዝብን ሠላምና ፀጥታ ወይም ለሕገ-ወጥ ጤና ወይም ለመልካም ሥነ ምግባር አስፈላጊ የሆኑት ብቻ መሆን ይኖርባቸዋል።

የ1985 የኘሬስ ሕግ ከወጣ ከሁለት ዓመታት በኋላ በወጣው የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በአንቀጽ 29 ላይ የኘሬስ ነፃነትን አካቶ ስለአመለካከት እና ሀሳብን በነፃ ስለመግለጽ መብት ተደንግጓል። በአንቀጽ 29 ሥር የሚከተለው ሠፍሯል።

አንቀጽ 29 የአመለካከት እና ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል።
2. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው። ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ፡ ወይም በሕትመት በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሳብ የመሰብሰብየመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል።
3. የኘሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙሃን እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል። የኘሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል።

ሀ/ የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣

ለ/ የሕዝብንጥቅምየሚመለከት መረጃ የማግኘት ዕድልን።

4. ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሀሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ኘሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል።
5. በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩአስተያየቶችንለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል።
6. እነዚህ መብቶች ገደብ በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ሕጎች ብቻ ይሆናል። የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ገደቦች በነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ። የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በሕግ የሚከለከሉ ይሆናሉ።
7. ማንኛውም ዜጋ ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦችን ጥሶ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል።

አንዱም የ1985ቱ የኘሬስ ሕግ ከወጣ በኋላ ሀገራችን ሕግ በማውጣት ረገድ ብዙ ርቀት ሄዳለች የሚያሠኘው ይኸው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 29 ሥር ሠፍሮ የሚታየው ነው። የኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 29 ቃል በቃል ከዓለም አቀፍ የሲቪልና የፖለቲካ መብቶች ስምምነት የተወሰደ መሆኑ ቀረብ ብሎ ሁለቱን ለሚያይ ሰው ግልጽ ነው።

ከ1985 ዓ.ም. ጀምሮ እስከዛሬ ድረስ በሥራ ላይ ያለው የኘሬስ ሕግ ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 29 እና ኢትዮጵያ ተቀብላ የራሷ ካደረገቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች ሠነዶች ደረጃና መስፈርት አኳያ ሲታይ ቶሎ መቀየር የነበረበት ሠነድ ነው። ሆኖም ይኸው ሕገ መንግሥት ከወጣበት ከ1987 ዓ.ም. ጀምሮ ይኸው ለ11 ዓመታት ያህል ያው ሕግ ተፈፃሚ ሆኖ ቀጥሏል። በ1995 ዓ.ም. የኘሬስ ሕጉን ለማሻሻል እንቅስቃሴ ተጀምሮ ነበር ሆኖም ከዚያን ወዲህ ደግሞ ወሬውም የለም። ምናልባት ውስጥ ውስጡን ሕጉ እየተዘጋጀ ሊሆን ይችላል። በ1995 ዓ.ም. ካንዱም ሁለቱ ለውይይት ቀርበው የነበሩት ረቂቆች ግን ከሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 29 እና ኢትዮጵያ ተቀብላ የራሷ ካደረገቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብቶች ሠነዶች አኳያ በደንብ የተፈተሹ ነበሩ ለማለት ያስቸግራል። በመሆኑም ቢያንስ በሕግ ረገድ ደህና ከተራመድን በኋላ ወደኋላ እንዳንመለስ አዋጅ ቁጥር 34/1985ን የሚተካው አዋጅ እውነተኛ ዲሞክራቲክ የኘሬስ አዋጅ እንዲሆን ሁሉም የበኩሉን ጥረት ማድረግ ተገቢ ይሆናል። በመጨረሻው የኘሬስ ዓዋጅ ላይ በእጅጉ ሊታሰብባቸው ከሚገባቸው ነጥቦች ጥቂቶቹን ቀጥለን እንነካካቸዋለን፦

1. ለኘሬስ ሥራ ፈቃድ ወይም ላይሰንስ መጠየቅ ኘሬስን ነፃ ማውጣት ሳይሆን በሠንሠለት አሥሮ ጨለማ ውስጥ ማስቀመጥ ነው። የኘሬስ ነፃነት በጅምላ አነጋገር ሲቀመጥ ከቅድመ ምርመራ (Censorship) እና ከሥራ ፈቃድ (Licensing) ኘሬስን ነፃ ማውጣት ማለት ነው። ዲሞክራቲክ ስርዓት ባላቸው ብዙ ሀገሮች የኘሬስ ነፃነት Licensingን አስቀርቷል። እንግዲህ ቅድመ ምርመራን አስቀርቶ ለኘሬስ የሥራ ፈቃድ ማውጣት መጠየቅ ለኘሬስ መሰረታዊ ነፃነትን ሳይሆን ግማሽ ነፃነትን ማጐናፀፍ ስለሆነ ለኘሬስ ሥራ ፈቃድ (Licensing) እንዲቀር መታገል እጅግ ወሳኝ ይሆናል።
2. የዐቃቤ ሕግም ሆነ የማስታወቂያ ሚኒስቴር በኘሬስ ሥራ ፈቃድ መከልከል፣ ማገድ፣ መሠረገዘና የኘሬስን ውጤት ማገድ ወዘተ ላይ መሠማራት እጅግ ሊታሰብበት የሚገባው ጉዳይ ነው። ነፃ ኘሬስ ይኖረን ዘንድ የእነኚህ የአስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች ሚና በእጅጉ ሊፈተሽ ይገባል።
3. ስለመረጃ ነፃነት፣ መረጃን ስለመስጠት ግዴታ እና ስለሚስጥራዊ ሠነዶች ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል። ኢትዮጵያ በጥንቃቄና በደንብ የተፈተሸ የሚስጢር ሠነዶችን ሕግ ሳታወጣ በፊት የኘሬስ ሕጉን አሻሽላ ብታወጣ ምናልባት ውሃ ቅዳ ውሃ መልስ እንዳይሆንባት መጠንቀቅ ተገቢ ነው። መረጃ ስለማግኘት ነፃነትና መረጃን ስለመስጠት ግዴታም እንደዚሁ በጥብቅ ማሰብ ተገቢ ነው።
4. ስለቅጣቶች እንደዚሁ ሊታሰብበት ይገባል፣ በኘሬስ ሕግ ውስጥ የተቀመጡትና በወንጀለኛ መቅጫ እና በፍትሐብሔር ሕጉ የተቀመጡት ድርብርብ ቅጣቶች የኘሬስ ነፃነትን ከማጐናፀፍ ይልቅ የሚያደበዝዙት እንዳይሆኑ መጠንቀቅ ያሻል።

ሀገራችን ኢትዮጵያ በዲሞክራቲክ ጐዳና መጓዝን መርጣለች ከተባለ አሥራ አንድ ዓመታት ሆነን። አንድን ሥርዐት ዲሞክራቲክ ከሚያሰኙት መመዘኛዎች ውስጥ በዚያ ሥርዓት ውስጥ ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ እና መረጃን የማግኘት ነፃነት መኖሩ እንደመሆኑ መጠን የ1985ቱን የኘሬስ ሕግ ተክቶ የሚወጣው ሕግ የዲሞክራቲክ ሥርዓት የኘሬስ ሕግ እንዲሆን ጥረት ማድረግ አሰፈላጊ ነው።

የሚወጣው የኘሬስ ሕግ ከዓለም አቀፍ የሠብአዊ መብቶችና ነፃነቶች ሠነዶች፣ መስፈርቶች አኳያ ታይቶና ተፈትሾ ተጣጥሞ መውጣት ይኖርበታል። የሚወጣው የኘሬስ ሕግ በቃል እንደተገለፀው ዲሞክራቲክ ሥርዓት ለመገንባት የበኩሉን አስተዋጽኦ የሚያደርግ ሊሆን ይገባል።

ከዚህ በላይ ካስቀመጥኳቸውና ትኩረት ይገባቸዋል ካልኳቸው ነጥቦች ዙሪያ ብዙም ሳልወጣ፣

- በኘሬስ ሥራ ላይ ለመሠማራት ፈቃድ /ላይሰንስ/ መጠየቅ በኘሬስ ነፃነት ላይ ከቅድመ-ምርመራ የማይተናነስ ውጤት ይኖረዋል። በመሠረቱ የኘሬስን ሥራ ለመሥራት ላይሰንስ የሚጠይቅ የኘሬስ ሕግ ዲሞክራቲክ ሕግ ነው ከመባል ይልቅ አምባገነን የኘሬስ ሕግ ወደመሆን ያዘነብላልና የላይሰንስ ነገር መቅረት አለበት።
- በኘሬስ ነፃነት ላይ የሚጣሉት ገደቦች በነፃነት ምክንያት ስድነትና የሌሎችን መብቶችና ነፃነቶችን መርገጥ እንዳይኖር ለመከላከል የሚያስችሉ እና የሰዎችን መልካም ስምና ዝናን ለመጠበቅ አስፈላጊ የሆኑቱ እንደዚሁም የሀገር ደህንነትና የሕዝብን ሠላምና ፀጥታ ወይም ለሕዝብ ጤና ወይም ለመልካም ሥነ ምግባር አስፈላጊ የሆኑት ብቻ መሆን ይኖርባቸዋል። ከነኚህ ውጪ የሆኑ ገደቦች የኘሬስ ሕግን ከዲሞክራቲክ ሕግነት ጐራ አውጥተው ወደ አምባገነን ሕግነት ጐራ ስለሚያስገቡት ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።
- አስፈፃሚ መሥሪያ ቤቶች የሆኑት ዐቃቤ ሕግና የማስታወቂያ ሚኒስቴር በተቻለ መጠን ሕገ-መንግሥታዊ ዕውቅና ባገኘው የኘሬስ ነፃነት ላይ ሻካራ እጃቸውን እንዳይጭኑ ካልተከላከልን እና ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ፈቃድ የመከልከል፣ ፈቃድ የማገድ፣ ፈቃድ የመሠረዝ ሥልጣን፤ ለዐቃቤ ሕግ የሕትመት ወይም የሥርጭት ዕገዳ ሥልጣን ወዘተ.. ከሰጠን የሚወጣው የኘሬስ ሕግ ዲሞክራቲክ ሕግ ከመሆን ይልቅ ወደአምባገነን ሕግነት ይሄድብናልና መጠንቀቅ ተገቢ ይሆናል።
- በመጨረሻም ልዩ ልዩ እና ድርብ ድርብርብ ቅጣቶችን ያካተተ የኘሬስ ሕግ አስበርጋጊ ከመሆኑም በላይ ጋዜጠኞች ቅጣቶችን ፈርተው በራሳቸው ላይ ሳንሱር እንዲጥሉ የሚያደርግ ነው የሚሆነው። ሳንሱር ደግሞ ቀጥተኛና በእጅ አዙር የሚጣል ሊሆን ስለሚችል ከነፃነት ይልቅ ቅጣትና ሃላፊነት ተኮር የሆነ የኘሬስ ሕግ አውጥተን ሕጋችን ዲሞክራቲክ ሥርዓትን ሊያስገነባን ይችላል ማለት ከማስመሰል ያለፈ ስለማይሆንና የሚወጣውንም ሕግ ዲሞክራቲክ ሕግ ከመሆን ይልቅ አምባገነን ሕግ ስለሚያደርግብን እንጠንቀቅ።

ሚዲያና ልማት በኢትዮጵያ

የእስካሁኑን የሚዲያ ታሪካችንን ስንቃኘው ሚዲያን ለልማት እንዲውል ስለማድረጋችን አጠያያቂ እንደሆነ በበኩሌ ምንም አልጠራጠርም። በኔ ግምት የእስካሁኑ የሚዲያ አጠቃቀማችንና ታሪካችን ኘሮፖጋንዳዊና ፖለቲካዊ እንደነበርና አሁንም ትኩረቱ በዚያው ላይ እንደሆነ ይሰማኛል። ለነገሩ ሚዲያን ለልማት ለማዋል ወይም ሚዲያዎች ልማታዊ ይሆኑ ዘንድ የሰከነ የፖለቲካ ሥርዓትን ይሻል፣ የሠከነ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓትን ይሻል፤ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈንን ይሻል። በሀገራችን በኢትዮጵያ እነኚህ ተሟልተዋል ያሰኝ ዘንድ ገና ብዙ የሚቀረን ይመስለኛል። በሀገራችን በየጊዜው ፖለቲካዊ ለውጦች ቢደረጉም የሰከነ ሕገ መንግሥታዊም ሆነ ፖለቲካዊ ወይም ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ኖሮናል ለማለት አያስደፍርም።

ሚዲያዎቻችን የሚታዩት በዚሁ ባልሰከነው ሥርዓታችን ውስጥ ነው። ከ1983 ዓ.ም ወዲህ የታየው የኘሬስ ነፃነትና ብቅ ብቅ ብለው ጭል ጭል ያሉትና እያሉ ያሉት የኘሬስ መጤዎች የሚታዩትና የሚገመገሙት በዚሁ ባልሠከነው የፖለቲካና የሕገ መንግሥት ሥርዓት ውስጥ

ነው። በመንግሥት ቁጥጥርና ባለቤትነት ሥር በሞኖፖል የተያዘውን ብሮድካስት ሚዲያን ትቶን ኘሬስንና ውጤቶቹን ስንመለከት ባለፉት 15 ዓመታት ትኩረታቸው ልማት ላይ ነበር ለማለት የሚያስቸግር ይመስለኛል። ከላይ ጠቅም እንዳደረግሁት ትኩረታቸው በፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ፣ በእንካ ስላንቲያ ላይ ነበር፤ አሁንም ያው ነው። በተለይም ባለፈው ግንቦት ከተካሄደው ምርጫ በፊት ጀምሮ፣ የምርጫ ጊዜውን አካቶ ከምርጫ በኋላም በተፈጠሩት የተለያዩ ልዩነቶች እና አለመግባባቶች ዙሪያ በመንግሥት እና በግል ኘሬስ መካከል ከፍተኛ መናቆር ተፈጥሮ ይኸው እስከ እሥራትና ክስ ድረስ ደረሰ። እንግዲህ መንግሥት በባለቤትነትና በሞኖፖል በያዘው የብሮድካስት ሚዲያ እና የርሱ በሆነት የኘሬስ ውጤታቸው ልማት ነክ የሆኑትን መረጃዎች፣ ትምህርቶች እና ዕውቀት ለሕብረተሰቡ ሊያደርስ ሲሞክር ነበር ካልተባለ በስተቀር ሚዲያዎቻችን ልማት ተኮር ናቸው ለማለት ያስቸግር ይመስለኛል። ከዚህም በኋላ ከኘሬስ ነፃነት አኳያ አካሄዳችን ብዙም ግልጽ አይደለም ምን ዓይነት የኘሬስ ሕግ ሊወጣ እንዳለም ብዙም ግልጽ አይደለም።

ቀደም ሲል ለመጠቆም እንደተሞከረው አንድን የዲሞክራቲክ ሥርዓት ለመገንባት እጅግ አስፈላጊ ከሆኑት ነገሮች ነፃ ኘሬስ አንዱ ነው። ነፃ ኘሬስ የሀሳቦች ነፃ የገበያ ቦታ ነው፤ ነፃ ኘሬስ ሕዝብና መንግሥት ሀሳብ ለሀሳብ የሚለዋወጡበት የጋራ መድረክ ነው። ነፃ ኘሬስ አፈ-ሕዝብ ነው፤ አፈ-መንግሥትም ነው። የኘሬስ ነፃነት በዋናነት የሚያጠነጥነው ሳንሱርንና ፈቃድን ለማጥፋት ቢሆንም ነፃ ኘሬስ ነፃነቱ በመንግሥት ላይ የጣለው ሳንሱር ነው። ነፃ ኘሬስ መንግሥት አካሄዱን እንዲያስተካክል፣ ራሱን እንዲያይ፣ ራሱን እንዲገመግም የሚረዳው ሆኖ የሚመራውን ሕዝብ የልብ ትርታ የሚያዳምጥበትም ነው። በመሆኑም ሚዲያዎች ልማትን ያግዙ ዘንድ እውነተኛ የኘሬስ ነፃነት እንዲሰፍን ማድረግ ወሳኝ ነው።

በኘሬስ ነፃነት ላይ የሚጣሉት ገደቦች አስፈላጊነታቸው አሌ የማይባሉ፤ በዓለም ዙሪያ ተቀባይነት ያላቸው፤ በጥንቃቄ የተፈተሹ መሆን ይኖርባቸዋል። ከሁሉም በላይ በኘሬስ ነፃነት ላይ የሚጣሉት ገደቦች ነፃነቱን የሚያመክኑ እንዳይሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ሊደረግ ይገባል።

ብሮድካስት ሚዲያ ለግል ባለሀብቶች የተከፈተ የኢንቨስትመንት መስክ እንዲሆን ካልተደረገ በዚያ በኩል ሙሉ በሙል ልማትን ማገዙ አጠራጣሪ ነው።

በመንግሥት የተያዙ ሚዲያዎች ለሕዝብ ተሳትፎ በራቸውን የከፈቱ መሆን አለባቸው አሳታፊነታቸው ልማትን የሚያግዝ ይሆናልና።

ማጠቃለያ/መደምደሚያ

- በኢትዮጵያ ውስጥ የሠከነ የፖለቲካ የሕገ መንግሥትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት እንዲሰፍን ምን መደረግ አለበት? የሚለው ጥያቄ ሀፊ ውይይት የሚሻ ጉዳይ

ይመስለኛል። ከሌላው ትግር ሁሉ አፍያ ብለን ወደ ልማት ማተኮር እንችል ዘንድ ምን መደረግ አለበት? በሚለው ጥያቄ ዙሪያ ሁሉም ሊወያይ፣ ሐሳብ ሊያመነጭ ይገባል።

- የፖለቲካ፣ የሕገ መንግሥትና ዲሞክራሲያዊ ሥርዓታችን ሳይሸነን በልማት ሥራዎች ላይ ማተኮር ያስቸግር ይመስለኛል። ከልማት በፊት ሕገ መንግሥታዊ ሠላም፣ ዲሞክራሲያዊ ሠላምና ፖለቲካዊ ሠላም ያስፈልገናል።
- የሠከነ ሥርዓት ሲኖረን ያን ጊዜ ሚዲያዎቻችንን ከልማት ዕቅዶቻችንና አጀንዳዎቻችን ጋር አቀናጅተን፣ አዋህደን፣ አስማምተን፣ ጥረቶች ወደዚያ እንዲያተኩሩ ማድረግ ይቻላል።
- መተባበል፣ መቻቻል፣ እኩልነት፣ መከባበርና አንድነት ሲኖር ያን ጊዜ ሚዲያዎቻችን ለልማት እንዲውሉ ማድረግ ይቀላል።
- አለመተባበል፣ መናናቅ፣ አለመቻቻል፣ ሲኖር የሚዲያ የትኩረት አቅጣጫ በዚህ ምክንያት የሚፈጠረውን ችግር ወደ ማርገብ፣ አሳት ወደማጥፋት ይሆናልና።
- ከመናቆር ፖለቲካ፣ ከዘላለም ኘሮፖጋንዳ ስንላቀቅ ያኔ ሚዲያዎቻችን ትኩረታቸው ወደ ልማታዊ ሥራዎችና ተግባራት ይሆናል፣
- ጋዜጠኞቻችን በሙያዊ ሥነ ምግባር የታነፁ፣ ሕግ የሚያከብሩ፣ ሚዛናዊና እውነተኛ መረጃ ለሕዝብ የሚያቀርቡ፣ ለእውነት የቆሙ በሐቅ የሚሠሩ መሆን ይጠበቅባቸዋል። በዚህ ረገድ እስካሁን ተቋቁመው በስራ ላይ ያሉትም ሆነ ወደፊት የሚቋቋሙት የሚዲያ ማሰልጠኛ ተቋማት ክፍተኛ አስተዋጽኦ ስለሚኖራቸው ለዚህ ራሳቸውን ብቁ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

በመጨረሻም የእስካሁን የሚዲያዎቻችን ታሪክ፣ አጠቃቀማችን፣ የአመጠት ውጤቶች መፈተሸና መገምገም ያለባቸው ይመስለኛል። "ሚዲያ" የተሰኘው መሣሪያ ወደፊት እንደት ለልማት ሊውል እንደሚገባ ሰፊ ጥናት ሊደረግበት የሚገባ ይመስለኛል። በዚህ ጽሁፍና በዚህ ጽሁፍ ላይ ውይይት በሚያደርገው መድረክ መነሻነት ቀጣይ ጥናቶች ተካሂደው ሚዲያዎቻችን ልማትን የሚያግዙ እንዲሆኑ መደረጉ ሁላችንም የምንስማማበት ሀሳብ ይመስለኛል።

ርዕይ

የዛሬ 22 ዓመት እንደኢትዮጵያ አቆጣጠር በ20/20 ዓመተ ምህረት ለአገሬ ለኢትዮጵያ የምመኘው፦

ዲሞክራሲና ሰላም የሰፈነባት፣ እውነተኛ የኘሬስ ነፃነት የተከበረባት፣ የሕግ የበላይነትና ፍትህ የሰፈነባት፣ ሕዝቦቿ በነፃነት፣ በእኩልነት፣ በወንድማማችነትና በአንድነት የሚኖሩባት ከድህነትና ከልመና የተላቀቀች ሀገር ሆና ማየትን ነው።

ከተሞች ለሀገር ልማት በኢትዮጵያ

አበበ ዘለዐለ*

1. መግቢያ

የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበር "Vision 2020 Ethiopia" በሚል የውይይት መድረክ ከፍቶ ሀሣቦችእንዲፈልቁ፣እንዲንሸራሸሩ፣ የሀገሪቱ የወደፊት አቅጣጫ ላይ መሠረት የሚጥል ሥራ በማከናወን ላይ መሆኑ የሚመሰገን ተግባር ነው።

እኔም ለዚህ አቅጣጫ ቅየሳ ለውይይት መነሻ የሚሆን ሀሳብ እንድወረውር እድሉ ስለተሰጠኝ ከልብ አመሰግናለሁ። የተሰጠኝ ርዕስ 'ከተሞች ለሀገር ልማት በኢትዮጵያ' ሰፊ ሀሳብና በማደግ ላይ ያለ በመሆኑ ሁሉን ለመንካት አልሞክርም። የመረጥኩት መንገድ በተቻለ መጠን በመጀመሪያ የአህጉራችንን ከተሞች ከማየታችንና የት ለመድረስ እንዴት እንሂድ የሚለውን ከማየታችን በፊት አጠቃላይ የከተሞች አመሠራረት፣ ለሀገር ዕድገት ያላቸው ሚና እና ስለከተሞች ያሉ ንድፈ ሀሳቦችን ነካ ነካ አደርጋለሁ። ከዚያ ወደኛ ሀገር ሁኔታ በመመለስ የከተሞቻችን አመሠራረት፣ እድገታቸው፣ አሁን ያላቸው ገጽታና ሚና እና ያለባቸው ፈተናና በጐ ሁኔታዎችን ከዳሰስን በኋላ ከተሞቻችን በሀገሪቱ ልማት ምን ሚና ይዘው እንዴት አድገው ማየት እንደማልም፣ በመቀጠል ይህንን ህልም እውን ለማድረግ እንዴት ብንጓዝ እንደሚሻል ሀሣቤን አቀርባለሁ።

2. የከተሞች ውልደትና ሚናቸው

ከተማ ህዝቦች በጥግግት የሚኖሩበት፤ ህዝቡ አብዛኛው ሥራውና ገቢው ከግብርና ውጭ የሆነ፤ የተሻለ መሠረተ ልማት ያለበት፤ የመኖሪያ መሥሪያ ቦታ ብሎ መተርጐም ይቻላል። በተለያዩ ምሁራን በተለያያ አገላላጽ ለከተማ ትርጉም ተሰጥቷል እንዴትም ብለን ተረጐምነው ዋና መለያው የሚሆነው ከተሞች የአገልግሎት ማዕከልነታቸው፣ የህዝብ መኖሪያ፣ የሥራ ተቋማት ጥግግትና በቅርበት ያለበት፣ የተሻለ ኑሮ ሁኔታ ያለበት፣ ዘመናዊ አኗኗር የሚታይበት /modern way of life, better quality of life/ ማለት ይቻላል።

---

* አቶ አበበ ዘለዐለ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በማኔጅመንት፣ ቀጥሎም ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በከተማ ሥራ አመራር (Urban Management) ከኔዘርላንድ አግኝተዋል። አቶ አበበ ለ16 ዓመት በተለያዩ የኃላፊነት ሥራዎች ላይ ያገለገሉ ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ የአዲስ አበባ ከተማ አውቶብስ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ፣ የአዲስ አበባ ከተማ ልማት ቢሮ ኃላፊ እና የመሬት አስተዳደር ባለሥልጣን ሥራ አስኪያጅ ሆነው አገልግለዋል። በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በመምህርነት፣ በምክትል ዲንነትና በስልጠናዎች አስባባሪነት በመስራት ላይ ይገኛሉ። አቶ አበበ በበርካታ ጥናቶች ውስጥ በኮሚቴ አባልነትና መሪነት ሰርተዋል።

ከተሞች አመሰራረታቸውና እድገታቸው በአብዛኛው በስደት በሚመጡ ተቋማት፣ ህዝቦችና ካፒታል እንደሆነ የተረጋገጠ ነው። ከተሞች ከጥንት ጀምሮ የአስተዳደር ማዕከሎች፣ የባህል ማዕከሎች፣ የአገልግሎት ማዕከሎች እና የዕድገት ምሰሶዎች በመሆን የሚታወቁ ቢሆንም በዋናነት አሁን ላለንበት ዘመን ሥልጣኔ መሠረት የኢንዱስትሪው አብዮት ሲሆን ለዛሬዎቹ የከተሞች አፈጣጠርና ሚናም ከዚያው ጋር የተቆራኘ ነው። ከተሞች በዚህ ዘመን በማህበረሰብ መቀየር /መሻሻል/ /social transformation/ ማዕከልነት የሚታዩ ናቸው።

የሀገሮች የዕድገት ደረጃ /development level/ እና የከተሜነት ደረጃ /level of urbanization/ ቀጥተኛ ተዛምዶ አላቸው። አንዳንዴም የሀገር ዕድገትን በከተሞች የዕድገት ደረጃ መለካት ይችላል የሚሉ ባለሙያዎች አሉ።

አሁን ያለንበት ዘመን አለም ወደ ከተማነት ከዚያም አልፎ ከተሞች ወደ ተሳሰረ አንድ መንደርነት እየተራመዱ እንደሆነ በበርካታ ጥናታዊ ዕሁፎች ቀርበዋል።[41]

ይህን የሀገሮች የልማትና የከተማነት ደረጃ ተዛምዶና ዓለም ወደ ከተማነት በፍጥነት እየተቀየረች እንዳለች ለመገንዘብ የሚከተለውን ሠንጠረዥ ማየት ይቻላል።

ሠንጠረዥ 1.1፤ የከተማ ህዝብ ብዛት መቶኛ ድርሻ

	የከተማ ህዝብ ከጠቅላላ %		
	1980	2000	2020
የዓለም	59	47	57
አፍሪካ	27	38	49
ኢሮፕ	69	75	80
ሰሜን አሜሪካ	74	77	82
ማዕከላዊ አሜሪካ	60	67	73
ደቡብ አሜሪካ	68	80	85
ኤዥያ	27	38	50
በማደግ ላይ ያሉ ሀገሮች	29	41	52
የበለፀጉ ሀገሮች	71	76	81

ምንጭ:- Urban future 21 (2000) P.4

የከተሞችን ሚና የጐላ መሆኑን የሚያሳየው ሌላው ጉዳይ ካላቸው ህዝብ ብዛትና ከያዙት ቆዳ ስፋት በላይ ለሀገራዊ ምርት ያላቸው አስተዋጽኦ የጐላ መሆን ነው። በለሙት ሀገሮች ሀገራዊ ምርት የከተሞች ድርሻቸው እስከ 85% ሲሆን ባልለሙት ሀገሮች 50% ይደርሳል። ለመንግሥት ገቢ ያላቸው ድርሻም እጅግ ከፍተኛ እንደሆነ ይገመታል።[42]

[41] Urban future 21 (2000) P.5
[42] NUPI (2002)

ከተሞች የማህበረሰብ ለውጥ /social transformation/ እና የውጤታማ ሥራዎች ዘርፍ ለውጥ ማዕከል ናቸው። ከተሞች የኢንዱስትሪው አብዮት ማዕከል ሆነው ማገልገላቸው የሚታወቅ ሲሆን፣ አሁንም የአገልግሎትና የመረጃ ዘመን ለውጥ ማዕከል ሆነው በማገልገል ላይ ናቸው።

ከተሞች ለህዝቦች የተሻለ ኑሮ እንደሚቸሩ ይታወቃል። ለዚህ ማረጋገጫው የማህበራዊ አገልግሎቶች መዳረስ፣ ለህዝቡ ህይወት ዘመን መርዘም፣ የተማረው ህዝብ ብዛት፤ የህፃናት ሞት ዝቅተኛነት በሁሉም ሀገሮች ከገጠር በከተማ የተሻለ እንደሆነ መረጃዎች ያረጋግጣሉ።

ይህ ሚናቸው እንዳለ ሆኖ የከተሞች እድገት ለአስተዳደር ፈተና የሚፈጥር ከመሆኑ አንፃር እንደችግር የታዩበት ዘመን ነበር። ከተሞች የገጠር ጥገኛ እንደሆኑ፤ የማህበራዊ ችግር መፍለቂያ፤ ለመንግሥት ጠንቅና ሳይፈለጉ የሚያድጉ አደጋዎች እንደሆኑ ተደርገው ይታዩ ነበር። በሌላ በኩል ከተሞች የመሰረተ ልማት ዝርጋታ፤ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት፤ ከማህበራዊ ትስስር መላላት ጋር በተያያዘ የወንጀል መበራከት፣ የትራፊክ መጨናነቅ፣ የአካባቢ መበከል፣ የመሀል ከተማ እርጅናና በፕላን ለመምራት አስቸጋሪ መሆን ፈተናዎችን አልፈዋል አሁንም እየተጋፈጡ ናቸው።

የከተሞችን ሁኔታ /dynamism/ ለመረዳት እና በሥርዓት ለመምራት በከተሞች ላይ የተለያዩ ምርምሮች ተከናውነው ንድፈ ሃሳቦች (theories) ቀርበዋል። ጐላ ጐላ ያሉትን ለመጥቀስ፡-

ክርስቶየለር የተባለ ተመራማሪ ከተሞች በውስጣቸው ሲያራጁ ውድ ዋጋ ያላቸው ሸቀጦች ማዕከላዊነትን እንደሚይዙ፤ በተዋረድ ዋጋቸው የቀነሱት በንዑስ ማዕከላዊነት እየወረዱ እንደሚያራጁ የጀርመን ከተሞችን በማጥናት ሲያረጋግጥ፤ ከከተማ ከተማ ያለው ርቀትና ለእያንዳንዱ ከተማና ማዕከል የሚያገለግለውን ህዝብ ብዛት ለማመልከት ሞክሯል።

የቫንተሁኔን ሀሣብ በመያዝ በርገስ የሚባል ተመራማሪ እንዳመለከተው ደግሞ ከተሞች ዋና የንግድ ቀጠናዎችን በማዕከላዊነት አደራጅተው የሚሰፉት ሌሎች ግልጋሎቶች ማዕከሉን በመክበብና በጥቅጥቅታ /concentric/ ወይንም እንደክንፍ፡ በመዘርጋት እንደሚሆን ይጠቅሳል፡ ከከተሞች ማዕከል ጀምሮ የሽግግር ዞን ወዘተ... እያለ እያንዳንዳቸው የሚኖራቸውን የሥራ ክፍፍል ባህሪ ለማሳየት ሞክሯል።

ሌሎች የከተሞችን መጠንና ደረጃ ለመረዳት ጥናት ያካሄዱ በርካታ ተመራማሪዎች ሲኖሩ ጀርጅ ኪንግላይ ዚፕ /1941/ የከተሞችን ደረጃና የህዝብ ብዛት ተዛምዶ በቀመር እንደሚከተለው አስቀምጠታል።

$$\frac{\text{በሀገሪቱ የትልቁ ከተማ ህዝብ ብዛት}}{\text{የ "ሀ" ከተማ ደረጃ}} = \text{የ "ሀ" ከተማ ህዝብ ብዛት}$$

የሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል። የ"ሀ" ከተማ ማለት ደረጃዉን ለማወቅ የተፈለገው ከተማ ማለት ነዉ።

ይህንን መሠረት በማድረግ ዋልተር /1956/ ባደረገው የዳሰሳ ጥናት የከተሞች ዕድገት ሚዛን ያልጠበቀ እንደሆነ፣ አንድ ግዙፍ ከተማ በጣም ከሌሎች የወጣ /primate city/ ከሆነ ሌሎቹ እንዲሁ ሚዛን ሳይጠብቁ እንደሚያድጉ፤ የሁለተኛ፣ የሦስተኛ እና የአራተኛ ደረጃ ከተማ ህዝብ ብዛት ድምር ከአንደኛ ደረጃ ከተማው ሲካፈልና በመቶኛ ሲቀመጥ የትልቁ ከተማ ግዝፈት መለኪያ /primate city index/ እንደሆነ በቀጣይም ትልቁ ከተማ ከሌሎች የተለየ እንደሚሆን አመልክቷል።

ሊንስኪ /1969/ ይህንን ንድፈ ሃሣብ ተቀብሎ ክስተቱ በዋናነት የሚታየው በድሃ ሀገሮች፣ በውጭ ገበያ በማመራ፣ በግብርና በሚተዳደሩ፣ ከፍተኛ የህዝብ ዕድገት ባለባቸውና በቀኝ ግዛት በነበሩ ሀገሮች እንደሆነ ይጠቁማል።

ሌሎች ተመራማሪዎች ደግሞ ትክክለኛ የከተማ መጠን /optimal city size/ እንዳለ በግራፍ አስደግፈው አቅርበዋል። ህዝቡ ሲያንስ የአገልግሎት ወጭ እንደሚበዛ፤ በተዘረጋው መሠረተ ልማት ህዝብ በጨመረ ቁጥር ነጠላ ውጭ እንደሚቀንስ ነገር ግን ከተወሰነ ደረጃ በኋላ ይህ ሁኔታ መቀጠሉ ቀርቶ ወጭው እንደሚንር ህዝቡ ተጠቃሚነት ደግሞ የህዝቡ ቁጥር ሲያንስ እንደሚጨምር ሁለቱ ክስተቶች በግራፍ ላይ የሚገናኙበት ቦታ ትክክለኛ የከተማ ደረጃ እንደሚሆን ያሳያል።

ስለ ከተማ ዕድገትም እንዲሁ በጥናት የተረጋገጡ ንድፈ ሃሣቦች አሉ። ለምሣሌ (Hayot 1936) North (1956) & Tiebort (1962) የከተሞች እድገት ምጣኔ ወደውጭ በሚልኩት የምርት ምጣኔ ይወሰናል ይላሉ። ከተሞች ማደግ የሚችሉት በከተማው ተመርቶ ወደውጭ የሚላከው ወደከተማው ከሚገባው በዋጋ የበለጠ እንደሆነ ነው ሲሉ። Keynesion urban growth model የኤክስፖርት ቤዝ ቲዮሪን መሠረት አድርጐ የከተሞችን የገቢ ምጣኔ ከውጭ ሽያጭ እና ከሥራ ፈጠራ አዛምዶ ለማሣየት ሞክሯል። በሌላ በኩል supply model of urban growth የከተሞች እድገት ላለው ይጨምርለታል (circular and accumulative causation) እንደሚባለው እንደሆነ ያመለክታሉ።የነዚህ ሁሉ ጥናታዊ ሥራዎች ፋይዳ ከተሞችን በመረዳት /ለተሻለ ሀገራዊ ጠቀሜታና ለከተሞች እድገት/ መሠረት ለመጣል እንዴት መመራት አለባቸው በሚለው ዙሪያም በርካታ ሀሣቦች ለማግኘት ነው። በመቀጠል ወደ ሀገራችን ሁኔታ እገባለሁ።

3. ከተሞች በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ከተሞች ከአክሱም ዘመነ መንግሥት ጀምሮ የአስተዳደር፣ የንግድና አገልግሎት ማዕከልነት የተደራጁበት ሁኔታ እንደነበር መረጃዎች ያሳያሉ። ነገር ግን ዘመናዊ ከተማ በአስተዳደር፣ በመሠረተ ልማትና ከሌሎች ሁኔታዎች ጋር ተያይዞ ሲታይ የተጀመረው ከዘመናዊ መንግሥት ምሥረታ ጋር በ19ኛው ክፍለ ዘመን እንደሆነ ለማየት ይቻላል።

ዘመናዊ ሁኔታን የመቀጠሉ ሃደት በ19ኛው ክፍለ ዘመን ይሁን እንጂ ብዙዎች ከተሞች አመሠራረታቸው የቀደመ ነው። በዋናነት ከተሞቹ አመሠራረታቸው በወታደራዊ ካምፕነት፣ በፖለቲካና አስተዳደር ማዕከላት/ ይህም ሲሆን ለጥበቃ ምቹነት እየታየ የተመሠረቱ እንደሆነ፣ በኢኮኖሚያዊ ክስተት የተመሠረቱት በቅርብ የመጡት በምድር ባቡር መዘርጋት ጋር የተያያዙትና አሁን በትልልቅ ከተሞች አካባቢ የሚታዩት ብቻ ናቸው።

አመሠራረታቸው ከላይ የተገለፀው መልክ ቢኖረውም እድገታቸው ግን እንደማንኛውም የአለም ከተሞች በኢኮኖሚ መስህብነታቸው ህዝቦችና የኢኮኖሚ ተቋማት በዓላጉታቸው የሚስፍሩባቸው ሆነው ነው።

የከተሜነት ደረጃ እጅግ ዝቅተኛ መሆን የሀገሪቱ የእድገት ደረጃ ዝቅተኛነት መገለጫ ተደርጎ ሊታይ የሚችል ነው። የከተሞቹ መስፋፋት ከኢኮኖሚ ዕድገት ምጣኔ ጋር በማይጣጣም ሁኔታ እጅግ የፈጠነና ሌሎች ፈጣን የከተማ እድገት አላቸው ከሚባሉት ጐራ ያለ ነው። የከተሞቻችን ደረጃና ዕድገት ምጣኔ በሚከተለው ሰንጠረዥ ማየት ይቻላል።

ሠንጠረዥ 1.2 የከተማ ህዝብ ድርሻ በመቶኛና የእድገት ምጣኔ

ዓመተ ምህረት	የከተማ ህዝብ ድርሻ %	የከተማ ህዝብ ዕድገት %	የአጠቃላይ ህዝብ ዕድገት %
1975	9.5		
		4.54	2.48
2000	14.92		
		5.53	1.98
2025	29.89		

ምንጭ:- UNCHS, 1996

ከተሞች ያላቸው የህዝብ ድርሻ ከ16% ያልዘለለ አነስተኛ ይሁን እንጂ በሀገሪቱ ደረጃ ከሚገኘው ሀገራዊ ምርት አስተዋጽኦዋቸው ከ40 በመቶ እንደማያንስ፣ ለመንግሥት ገቢ ምንጭነትም ከዚህ የበለጠ ድርሻ እንዳላቸው ይገመታል።[43]

[43] NUPI (2002)

ከተሞች የማህበረሰብ ትራንስ ፎርሜሽን ሚና እየተጫወቱ ነው። ያላቸው ፖለቲካዊ ሚናም የጎላ ነው።

ከተሞቻችን የራሳቸው ልዩ የሚያደርጋቸው በርካታ ባህሪያት አላቸው። እነርሱም፤

- ለወታደራዊ ጠቀሜታ ሲባል በተራራ ላይ መሠራታቸው ለውበታቸው ማማር እና የአየር ንብረታቸው ለኑሮ ተስማሚነት መሆን በጎ ጎን አለው።
- የከተሞች አሰፋፈር በቅኝ ግዛት ከፋፍለህ ግዛ አለመቃኘቱ፣ በኋላም ነባ ገበያ በፈለገው እንዲመራቸው ባለመደረጉ የህዝቡ አሰፋፈር ስብጥሩን የጠበቀ፣ በዘርና በገቢ ልዩነት ያልተከፋፈለ፣ በባህላዊ ተቋማቱ ዕድር፣ ማህበር፣ እቁብ ምክንያት ማህበራዊ ግንኙነቱ የጠበቀ፣ ህዝቡ አማኝና ተቻችሎ የመኖር ባህልን ያዳበረ መሆኑ በማንኛውም መመዘኛ በሰላማዊነታቸው የሚወደሱ፣ በአንፃራዊነት የከተሞች ስጋት የሆነው ለላማዊ ኑሮ መናጋትና የወንጀል መበርከት የማይታይባቸው መሆናቸው ለመኖሪያነት፣ ለኢንቨስትመንትና ለጉብኝት ተመራጭ ያደርጋቸዋል።
- የከተሞቻችን ዕድገት እንደ ቀደምት የበለጸጉ ሀገሮች ሃያት መጀመሪያ የምርት ኢንዱስትሪ ማዕከል ከዚያም የአገልግሎትና መረጃ ማዕከል ሆነው እያደጉ ሳይሆን በአለማቀፋዊ ለውጥ (globalization) ግፊት ከምርት ኢንዱስትሪ ቀድመው ወደ አገልግሎት ዘርፍ፡ ሚዛን እንዳዘነበሉ መረጃዎች ያመለክታሉ።

ከተሞቻችን ምርቶቻቸው ከግብርናው ያላቸው ቁርኝት የላላ ቢሆንም ባሉበት ሁኔታም ለገጠሩ ህዝብ የአስተዳደር፣ የአገልግሎትና የንግድ ማዕከልነት ሚና እየተወጡ እንዳለ ይታወቃል።

ከተሞቻችን እንደበለፀጉት ሀገሮች የከተማ ማስፋፋት ከኢንዱስትሪው አብዮት ጋር፣ ከኢኮኖሚ ዕድገት፣ ከምርትና ምርታማነት ማደግ ጋር ተቆራኝተው ያልተራመዱ በመሆናቸው በሌሎች ታዳጊ ሀገር ከተሞች እንደሚታየው ኢኮኖሚው በአብዛኛው መደበኛ ያልሆነ /Informal/ ዘርፍ የበዛበት፣ በጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት እንቅስቃሴ የተመሠረተ ነው። ይህ መደበኛ ያልሆነው የሥራ ዘርፍ ፈርጀ ብዙ ነው። የሥራ መስክና የገቢ ምንጭ፣ የመኖሪያ ቦታና ቤት ማግኛው ሰፊ መንገድ እሱ ነው።

ከተሞቹ እንደማንኛውም ከተማ እየሰፉ ሲሄዱ የመሀል ክፍላቸው እያረጀ ይሄዳል። በሌሎች አገር ከተሞች እርጅናው ሲከሰት የኢኮኖሚ መስህብነታቸው ካለ በገበያ ኃይል የመሀል ክፍሉ እራሱን ያድሣል። በእኛ አገር ያረጁ መሀል ከተሞች እንዳያታደሱ የሚያደርገው የመንግሥት የከራይ ተመን ጣሪ፣ የፕላን ክልከላ እና የባለሀብቶች ተስፈኛነት ብቻ ነው። በእኛ ሀገር ሁኔታ የመሀል ከተማ እድሣት በገበያ ኃይል እንዳያመራ ቤቶች የግል አለመሆን በተለይ የተወረሱ የቀበሌ ቤቶች መበራከት ሰፊ ችግር ሆኗል። የመሀል ከተማው ልማት ያለመንግሥት ጣልቃ ገብነት እየተመራ አይደለም፣ ፍጥነቱ የተጓተተ ነው። መሀላቸው

የኢኮኖሚ መስህብነት አንዳለ ሆኖ እያደገ አይደለም። በተነፃራሪ ዳራቸው እየተለወጠና እየተለጠጠ ይታያል።

በጐ ጐናቸው አንዳለ ሆኖ የእድገት ስርጭታቸው ሚዛን ያልጠበቀ በሌሎች ታዳጊ ሀገሮች የታየው /low of primate city/ ሂደት የሚንፀባረቅበት ሁኔታ ይታያል። በአህዝ ለመደገፍ የሚከተለውን ሠንጠረዥ ማየት በቂ ነው።

ሠንጠረዥ 1.3 ከተሞች በህዝብ ብዛት

የከተማ ስፋት በህዝብ ብዛት ምጣኔ	1984				1994			
	ብዛት	%	የህዝብ ብዛት	የህዝብ ብዛት %	ብዛት	%	የህዝብ ብዛት	የህዝብ ብዛት %
<2000					389	42	452855	6
2000-4999	182	58.3	559149	14.1	295	32	948127	12.8
5000-9999	71	22.7	489663	12.2	127	14	884684	11.9
10000-19999	36	11.5	491017	12.4	61	6.7	834431	11.3
2000-49999	12	3.9	351929	8.9	39	4	1059183	14.3
50000-99999	10	3.2	657018	16.6	8	.8	716053	9.7
100000-499999	-				3	.3	404942	5.5
500000-999999	-							
<1000000	1			35.7	1		2084568	28.2
ድምር	312						7384893	

ምንጭ:- CSA 1991, 1999

4. የኢትዮጵያ ከተሞች በጐ ሁኔታዎችና ፈተናዎች

ከዚህ በላይ ለማየት በተሞከረው መሠረት፣ የከተሞች በጎ ጎኖች የሚከተሉት ናቸው።-

- የከተሞቹ አየር ንብረት ለኑሮ ተስማሚ መሆኑ፣
- ሌሎች ሁኔታዎች ከተፈቱ፣ ሰላማቸውና ደህንነታቸው የተረጋጋ ከሆነ ኢንቨስትመንትን የሚስብ እድል ያላቸው መሆኑ፣
- ሌሎች የኢንቨስትመንት ማነቆ ሁኔታቸው ከተፈታ ሊሰራ የሚችል ርካሽ የለው ጉልበት መገኛ መሆናቸው፣
- በቤት ግንባታ ለሚሠማራ ባለሀብት ሰፊ የፍላጐት ክፍተት መኖሩ፣
- ከተሞቻችን አሁን ያሉበት ደረጃም ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ ያልወጣ ገና በማደግ ላይ ያሉ የአስተዳደር አስቸጋሪነታቸው ገና ትልቅ ፈተና ውስጥ ያልወደቀ መሆኑ ተስፋን የሚያመለክትመሆኑና የመሳሰሉት ናቸው።

በሌላ በኩል ለከተሞች ማደግና ብሎም ለሀገር ያላቸው ሚና መገልበት ፈተና የሚሆኑት ደግሞ የሚከተሉት ናቸው።

- ያላቸው የመሠረተ ልማት በዝቅተኛ ደረጃ መገኘት፣
- የዕድገት ፍጥነታቸው ከኢኮኖሚው ፍጥነትና ሃደት በራቀ ሁኔታ በገጠር ገፊ ሁኔዎች መመራትና ከቁጥጥር ውጭ ሊወጣ የሚችልበት ስጋት፣
- የመሀል ከተማ እርጅናና ወደ ጐን መስፋት፣
- ከላይ ለኢንቨስትመንት መስህብ በዕድልነት የታየው የስራ አጥና የቤት እጥረት ሳይፈታ በቆየ ቁጥር ለበርካታ ማህበራዊ ጠንቆችና አደጋዎች የሚያጋልጥ መሆኑ፣
- የመዘጋጃ ቤቶች የገንዘብና የማስፈፀም አቅም አናሳነት፣
- ከተሞች ዕድገት መሠረት ነባ የሀብትና የሰው ዝውውር /ከቦታ ቦታ ተዘዋውሮ መሥራትና መከተም/ መነሻው ኢኮኖሚያዊ መስህብና የተሻለ ኑሮ ፍላጐት የመሆኑን ያህል የዕድገት ዋልታ፣ የምርታማነት ለውጥ ማፋጠኛ መሆናቸውን የሚያደናቅፍ ገቸ አመለካከቶች መኖራቸው፣
- የማህበራዊ ትስስር መላላት፣ ህገወጥነት፣ የአካባቢ ብክለት ተጠቃሽ ፈተናዎች ናቸው።

5. የኢትዮጵያ ከተሞች ከአንድ ትውልድ በኋላ

በ2020 ከተሞች በአገልግሎት ተዋረድ ተደራጅተው፣ የገጠር መንደሮች የዘመናዊ ከተማ ኑሮ የሚሰጡ፣ ከፍተኞቹ ከተሞች ደረጃቸውን የጠበቀ አገልግሎት የሚያቀርቡ፣ የመኖሪያ ቤትና የስራ አየነት ችግር አጀንዳ መሆኑ ጊዜው አልፎበት፣ ሁሉም ከተሞች በያንስ በመንገድ መረብና የህዝብ ትራንስፖርት ተገናኝተው፣ ህዝቦች በዘመናዊነት፣ በደስታ የሚኖሩባቸው የሞቁ፣ የደመቁ የስራና የመኖርያ ስፍራዎች ሆነው የማየት ራዕይ አለኝ።

ባለው የመረጃ ግመታ በ2020 በሀገራችን የከተማ ኑሮው ድርሻ ከ20% እንደማይዘል ያሳያል በእኔ ምኞትና እምነት ከዚህ የበለጠ መሆን አለበት ይቻላልም እላለሁ።

ይህንን ራዕይ እውን ለማድረግ መከተል ያለብን አቅጣጫዎች አንድ በአንድ ለማስቀመጥ እሞክራለሁ።

5.1 የአከታተም ሥርዓታችንና አመራራችን ስርጭቱ የተበተነ ግን ትስስር ያለው /defused and decentralized but integrated urbanization/ እንዲሆን ማድረግ።

አሁን ባሉት ከተሞች የገጠሩን ህዝብ ስቦ በማስፈር የሚፈጠር ከተማ ለልማት የተመሳሰበና ለአስተዳደር የከበደ ይሆናል። የከተማ ልማቱ ልቅ ከተተወና በራሱ ከተራመደ ከላይ በንድፈሃሳብ ያየነው low of primate city መሰረት መቀጠሉ አይቀርም። ይህ እንዳይከሰት በገጠር ከተሞች እንዲመሠረቱ ማለትም የገጠር አገልግሎት ማዕከላት ት/ቤት፣ ጤና

አስተዳደር፣ ውሀ፣ መብራት ወ.ዘ.ተ... በአንድ ማዕከል በማደራጀት ህዝቡ በነሱ ዙሪያ በሃያት የሚሰባሰብበት፣ በነዚህ ማዕከላት የመሠረተ ልማት መረብ መዘርጋት አስፈላጊ ነው። ከበላይ ከተሞች ጋር በአግባቡ የተገናኘ የመንገድና፣ የትራንስፖርት መረብ መዘርጋት ያስፈልጋል።

ለዚህ ስርዓት ትግበራ ከተሞች የአገልግሎት ተዋረድ ወጥቶላቸው መደራጀት አለባቸው። መሠረታዊ የሆኑ ግልጋሎቶች በነዚህ የገጠር መንደሮች ካልቀረቡ ለተሻለ ኑሮ ፍለጋ ወደ ትልልቅ ከተሞች ያለው ፍልሰት ሊገታ አይችልም። ፍልሰት የከተሞች ዕድገት ምንጭ እንደሆነና ተፈላጊነትም እንዳለው የሚታመን ሆኖ አደጋው የፍልሰት መጠን ከተሞች ካላቸው የማስተናገድ አቅም በላይ መሆን፣ የአቅም ችግር ሳይገጥም የሚፈልሱት በከተሞች የተሻለ ምርታማ /productive/ እና የተሻለ ኑሮ እንደሚኖሩ አምነውና አማርጠው የሚፈልሱ ቢሆን በእርግጠኝነት ከነበሩበት ሁኔታ የተሻለ ሥራ የሚሰሩና ኑሮን የሚያሻሽሉ ስለሆነ ለከተማ ዕድገት የሚበጅ ይሆናል። ካልሆነ ግን አማራጭ በማጣት በገጠርና አነስተኛ ከተማ መኖር ስላልቻሉ ተገፍተው በሚሰደዱ ከተሞሉ ለከተሞቹ ዕድገት ከማምጣት ይልቅ በዋናነት ወደ ማቆርቆዝና ወደ ውድቀት የሚገፋ ይሆናል።

መሠረታዊ አገልግሎቶች በታችኛው እርከን ተሟልተው መካከለኛና ከፍተኛ አገልግሎት ፍላጐት ለማሟላት የኑሮ ሁኔታቸው ተቀይሮ በስደት ወደላይኛው እርከን ቢገቡ ስጋት ሳይሆን ተፈላጊ ነው። ሌሎች ግን መድረሻ አጥተው ዝቅተኛውን እርከን ለመልቀቅ የሚገደዱትን ባሉበት ማቆየት የሚቻለው በሚዘረጋ ትራንስፖርትና የግንኙነት መረብ እና መሠረታዊ አገልግሎቶች መኖር ውጤታማነትና ደህንነቱ የተጠበቀ /efficient & safe/ መሆን ላይ ነው።

ስለሆነም ይህንን ስርጭቱ የተበተነ ግን የተሳሰረ አከታተም ለማረጋገጥ የቱ ከተማ በምን አገልግሎት ደረጃ ማደግ እንዳለበት ተለይቶ ሊታወቅ፣ አጋዥ የሆኑ የግንኙነት መረብ፣ የመሠረተ ልማት ዝርጋታና የመሬት አቅርቦት በዚሁ አግባብ ሊረጋገጥ ይገባል። ለምሣሌ የገጠር መንደሮች እስከ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ይሰጥባቸው ከተባለ በትምህርት መስኩ ቀጥሎ ያለው እርከን በቀጣዩ የከተማ ደረጃ መደራጀት አለበት። ይህ ሁለተኛ ደረጃ ከተማ ሲመረጥ ሁሉም የመጀመሪያ ደረጃ ከተሞች ሊደርሱበት የሚችል አማካይ ቦታ ሆኖ ግንኙነታቸውን አጋዥ ትራንስፖርትና መገናኛ መረብ መዘርጋት አለበት።

የዚህ አፈፃፀም ከተሞች ለአስተዳደር አስቸጋሪ ሳይሆኑ ማደግ የሚችሉ ሲሆን፤ የህዝቦች ማህበራዊ ትስስር ሳይቆራረጥ፣ ተበራርዞ ቅርጹን ሳያጣ፣ ጥሩ የአካባቢ ሁኔታ ባለበት፤ ከብክለትና ትፍጭግ (pollution & congestion) የነፃ የከተማ ልማት ማረጋገጥ ጠቀሜታ አለው። በዚህ ሥርዓት ምሥረታ ሃደት አሁን ያሉትም ሆነ ቀጣዮቹ ትልልቆቹ ከተሞች ከመስፋት ወደጥራት ትኩረት የሚያደርጉበት ሁኔታ መታየት አለበት።

ይህ መርህ በቻይና ጥሩ ውጤት ያስገኘ፣ ገጠሩ በትንሽ የሰው ጉልበት በማሽን የማረሰ እርሻ የማያውይበት ሳይሆን ገበሬው ከእርሻው ሳይርቅ የከተማ ኑሮ የሚያገኝበት፣ ዳር እስከ ዳር ሀገሪቱ ደምቃ የምትጓገዝበት ሁኔታ ይፈጠራል። አለዚያ እንደ ግብጽ የተወሰነ ቦታዎች ከተሞች ብቻ ሆነው ህዝቡ በነሱ ተከማችቶ ሀገሪቱ ምድረ በዳ የሆነችበት አካሄድ ለኛ ሀገር አይጠቅምም። ልማትም አያፈጥንም። የዚህ አመራር ከበድ የሚለው በከተሞች አመራረጥ ሚና መለየትና የግንኙነት መረብ ዝርጋታ ስራው ብቻ ይሆናል። እዚህ ላይ ከፖሊሲ መንደፍ ጀምሮ ለትግበራው መረባረብ ያሻል።

5.2 የሰመረ የገጠርና ከተማ ትስስር ማስፈን

ከላይ የተገለፀው በርካታ አነስተኛ ከተሞች መፍጠር ማስተሳሰር በራሱ ሊሳካ የሚችለውና ውጤት የሚያመጣውም ከገጠር ጋር ያላቸው ትስስር ጥብቅ ሆኖ ሲመራ ነው። ከተሞቹ የግብርናውን ምርት በግብአትነት ተቀብለው ወደ ኢንዱስትሪ ምርትነት የሚቀይሩ፣ ለግብርናው ምርት ግብአት አቅራቢና የsocial and sectoral transformation ማዕከል ሆነው ጠንክረው ሲወጡ ነው።

የገጠሩ ምርትም ለከተሞች ፋብሪካ ግብዓት ትኩረት የሰጠ፣ ነዋሪዎቹን በምራት የሚገፋ ሳይሆን ምርታማ ሆኖ መመራት አለበት። እዚህ ላይ የገጠር መሬት ስራት ዋስትና ያለው መሆን እና ምርታማነትን የሚጨምር አድርጐ መሄድ ያስፈልጋል። ህገመንግሥታዊ የመሬት ባለቤትነት ወሰን እንዳለ ሆኖ ለባለይዞታ የሚሰጠው ዋስትና እና ጥበቃ ከሰርተፊኬት ያለፈ በህጋዊ ማዕቀፍ ደረጃ መረጋገጥ ያለበት ነው። የሀገራዊ ምዝገባ ስርዓት (National legal cadastre) ያስፈልጋል።

ግብርናው ለኢንዱስትሪና ለውጭ ገበያ ምርት ለማምረት ወጥነት ያለው ምርት እንዲያመርት ሰፋፊ እርሻ ቢሆንና በማሽን ቢታረስ ጥሩ ነው። በተቻለበት ቦታ ሁሉ ጠቀሜታው እየተመዘነ መተግበር አለበት። በጠባብ ይዞታ ጉልበትን በስፋት መጠቀሙንና ወጥ ምርጥ ምርት አመራረት ላይ ያለውን ግጭት ለማስታረቅ ባለይዞታዎች ተደራጅተው እርሻቸውን የሚያቀላቅሉበት ወይንም ባሉበት ሁኔታ ወጥነት የሚያስገኝ የተጠናከረ የግብአትና የቴክኒክ ድጋፍ እገዛ ማድረግ ወሳኝ ነው።

የመሬቱን ምርታማነት ከማሳደግ አንፃር በሰው ጉልበት መጠቀምም በስፋት እስከተገ፣ ድረስ ይቻላል። አንዳንዴም የተሻለም እንደሆነ እንደቻይና ባሉ ሀገሮች ታይቷል። ለመሬቱ ምርታማነት ግን አሁን ሀገራችን ባለችበት ሁኔታ ወሳኝ ሚና ያለው የውሃ ጉዳይ ሆኗል። ዝናብ ጠብቆ የሚዋኽርቅ ምርታማነት ላይ መሠረት ተደርጐ ኢንዱስትሪ ሊቋቋም አይችልም። ኢንዱስትሪ አስተማማኝ ግብአት ይጠይቃል። ከምንም በላይ የማህበረሰብና አከናዋኒያዊ ሽግግር ልናመጣ ከሆነ ግብርናው ከዝናብ ጥበቃ መላቀቅ አለበት።

5.3 የከተሞች ፕላን ሥራ እድገታቸውን አጋዥና አፋጣኝ እንዲሆን ማድረግ

እንደነበረውና እንዳለው ሁኔታ ከተሞቻችን ያለፕላን የሚመሩበት፣ ፕላን ተሰራ ሲባልም ዓላማው መቆጣጠር የሆነበት፣ ተለዋዋጭነትን የማይመልስ፣ የከተማ ባለድርሻዎች በባለቤትነት ያልተሳተፉበትና ያልያዙት፣ በባለሙያ ቢሮ ውስጥ የተነደፈ ከሆነ ከወረቀት አያልፍም። ከዚህ ካለፈም ዓላማው ለማደናቀፍና ለራስ ጥቅም ማራመጃ ለባለሙያዎች ብቻ የሚያገለግል ከመሆን አይዘልም።

ዘመናዊ ፕላኒንግ አሰራር መከተል ይገባናል። ይህ ሲባል ደግሞ በየጊዜው ዛሬ ይህ መጣ ሲባል የነበረውን ጥለን በአፈጻጸም የራሣችን ሳናሳድግ አዲስ ፍለጋ መዞርና ማወጅ የትም አያደርስም። «እስትራቴጂክ ፕላኒንግ» አሰራርና አተገባበር ተብሎ ብዙ ተደክሞ የራሳችን ልናደርገው የሚችል ሞዴል እየወጣ ባለበት፣ በአዲስ አበባና አዳማ የተሞከረ በሂደት ማሳደግ ሲገባ በይዙቱ ብዙም ያልታየ ግን አዲስ ስም የወጣለት አዲስ ነው ስለተባለ ብቻ IDP (Integrated Development Planning) ካልሆነ የሚል ሌላ መከራ ተጀምሯል። በእኔ እምነት አዲስ ሃሣብ ምን የሚጠቅም እውን አዲስ ነገር አለው ብሎ የጀመርነውን መንገድ ለማበልፀግ ማዋል ጠቀሜታው የጐላ ነው። የስትራቴጂክ ፕላን ሥራ በተግባር መጀመሩ ማለት በዚህ ሂደት ያለፉ ባለሙያዎች አሉ ማለት ነው። በህዝቡ ተዋውቋል፣ በዚህ ላይ መገንባት እንጂ መናድ ወይም እንደገና ሌላ አዲስ መከራ ማድረግ ብዙ የሚበጅ አይሆንም።

ፕላኖቻችን የከተሞቻችን ልዩ ባህሪ ማለትም የኗሪውና የተቋማት አሰራርና ስብጥር (mixity) መጠበቅ አለባቸው። ፕላኖች ለሁሉም ከተሞች የሚያስፈልገ የልማት መሥሪያዎች ከመሆናቸው አንፃር ሁሉም ሊኖራቸው ይገባል። ይህ ሊሳካ የሚችለው ባለው ተቋማዊ አደረጃጀት አንድ FUPI(Federal Urban Planning Institute) ብቻ ሊሆን አይችልም። አዲስ የተረቀቀው የፕላን ህግ ይህንን ሃሣብ አንፀባርቋል። ህጉ የክልላዊ ተቋማት መኖርን፣ የግል ተቋማት ተሳትፎና የመዘጋጃ ቤቶችን ባለቤትነት ያሳያል። ጅምሩ ጥሩ ሆኖ ወደተግባር ለመቀየር ክልላዊ ተቋማት አፈጣጠርና የግል ዘርፍ ማሳደግ ሥራ ፕሮግራም ሊቀረፅለትና ሊተገበር ይገባል።

5.4 ከተሞችን ጥሩ የሥራ፣ መኖሪያና የመዝናኛ ቦታ ማድረግ

ይህ ሁኔታ ዘርፈ ብዙ ጥረት ይጠይቃል። የኗሪዎች የሥራ ዕድልና ገቢ የሚያድግበት፣ የመኖሪያ ሁኔታ ማመቻቸት ሲባል ከመኖሪያ ቤት ግንባታ ጀምሮ ለመኖር የሚያስፈልጉ መሠረታዊ አገልግሎት ውሃ፣ መብራት አብረው የሚሄዱ ጤና፣ ትምህርት ወዘተ ማሟላትን ይጠይቃል። መዝናኛ ሥፍራዎችም ለጐብኝ ብቻ ሣይሆን ለኑሮ አስፈላጊ ናቸው።

ለሥራ ፈጠራና ገቢ ማሻሻል የኢንዱስትሪ ልማት ወሳኝ ነው። ለዚህ ዘርፍ አጋዥ የሆኑት የመሠረተ ልማት ዝርጋታና የቦታ አቅርቦት ትኩረት ይሻል።

በሌላ በኩል የኢኮኖሚ መሠረታችን አነስተኛ ተቋማት ከመሆኑ አንፃር ከዚህ ዘርፍ ለመለወጥ የሚችሉትንና /transformed/ ከግብርናው የተሳለሩትን ለይቶ ልዩ ድጋፍ መስጠት ያስፈልጋል። እንደ /business incubator እና BDSS (Business Development Support Service) ያሉ ተቋማዊ ድጋፍ ማደራጀት ያሻል።

በመኖሪያ ቤትና መሠረታዊ ማህበራዊ ተቋማት ግንባታ የመንግሥት ትኩረቱ የግል ዘርፍ፣ ማህበራትና ህዝቡ በራሱ ሊሰራ የሚችልበትን ሁኔታ (enabling environment) መፍጠር ላይ መሆን አለበት። መንግስት በቀጥታ ግንባታ ውስጥ መግባት የግድ ካልሆነ አይመረጥም። በሰፊ ምርት ወጭ ቅነሳና በሳይት ማኔጅመንት የሚኖረውን ጠቀሜታ እንዲሁም ለወጭ ቁጠባ የማቴሪያልና የአሰራር ዘዴ ጥናት ማካሄድ የሚኖረውን እድል ለማግኘት መንግሥት ያደራጃቸውን አሁን በቤት ምርትና አስተዳደር ሥራ የተሰማሩ ተቋማት የዚህ ድጋፍ ባለቤት እንዲሆኑ መቃኘትና መቀየር አለባቸው።

የመንግሥት ግንባታ በማኔጅመንት ውጤታማ አለመሆን /inefficiency/፣ በጥራት ቁጥጥር ደካማነት፣ የተጠቃሚውን ፍላጐት ከመመለስ ወደ ወጥ ምርት የማዘንበል፤ ለሙስናና አድሎ የተጋለጠ ከመሆን አንፃር ተደጋፊ አይደለም። መንግሥት ቤት የሚሰራበትን ገንዘብ በባንክ ውስጥ ሆኖ ለግልና ማህበር ቤት ሰሪዎች በብድር ቢቀርብ የተሻለ ይሆናል። ከተቻለ ለዚህ ሥራ /vencher capital/ መፈለግ አለበት። ህዝቡን ለዚህ ሥራ ለማሳተፍና የገንዘብ እጥረትን ለማቃለል እንደ እንግሊዝ አይነቱ /building society/ አይነት አዳዲስ ዘዴ መፍጠርና የቁጠባ ባህል የሚያድግበት ወጭ ቆጣቢ ግንባታና የቤት አስተዳደር የሚታይበት ሁኔታ መፈጠር አለበት።

ለኢንዱስትሪ ልማቱም ሆነ ለመኖሪያ ቤት ሥራ ወሳኝ ከሆኑት ግብአቶች አንዱ መሬት ስለሆነ እዚህ ላይ እሱን ማንሳት አስፈላጊ ነው። መሬት በሊዝ ስርት መቀጠል ተደጋፊ ነው የሚል ዕምነት አለ። ለዚህም የሊዝ ስሪት፤

- ለሚፈለግና ለጠቃሚ መስክ ትኩረት ሰጥቶ ማስተናገድ፣
- ከብክነትን በፕላን ለመምራት፣
- ለተደጋገፈ ድጐማ አሰራር /cross subsidization/ ለመተባበርና፣
- ለመሰረተ ልማት ዝርጋታ ገቢ ለማግኘት የሚያስችል ነው።

ሆኖም የአሰራር ማሻሻያዎች ማድረግ ግን አስፈላጊ ነው።

በእኔ እይታ ማሻሻያ የሚያሻቸው፡-

- የይዞታ ዋስትና ከማረጋገጥ አንፃር የሊዝ ዘመን ሲያልቅ ውሉ ሊታደስ የሚችልበትና የማይቻልበት ሁኔታ ግልጽ ድንጋጌ፣
- የሊዝ ግዴታውን ባልተወጣ ላይ የባንክ ዋስትና መያዣውን መብትና የመዘጋጃ ቤቶች መብት ግጭትን የሚያስታርቅ የህግ ማሻሻያ፤
- እንዲሁም ሊዝ ከነባር የኪራይ ስሪት ጋር ያለውን ልዩነት በአግባቡ የሚያሳይ የህግ ማዕቀፍና የግንዛቤ ማሳደጊያ ሥራ ያስፈልጋል።
- ከዚህ በተጨማሪ አልሚና ገንቢውን ከማያለማና ከማይገነባው መለየት የሚያስችል የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት ያሻል። አሁን እንዳለው ከእውነታ ውጭ የሆነ ፍላጐትና የአቅርቦት ውሱንነት ላልተረጋጋ የመሬት ገበያና ለዋጋ ንረት በር ይከፍታል። ይህም ከስቱት በግልጽ እየታየ ያለ ጉዳይ ነው።

5.5 ለከተሞች ልማት የሚበጅ የአመለካከት ለውጥ ማምጣት

እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ከተሞች ገጠር ሲለውጥ ይለወጣሉ በሚል ቅኝት ትኩረት አልነበራቸውም። የራሳቸው ፖሊሲም አልነበረም። አሁን መሻሻል አለ፤ ፖሊሲ ተነድፏል፤ ግን በስፋት ሊተኙና ውይይት ሊደረግበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ከላይ ስለከተሞች አደረጃጀት የተቀመጠው ሃሣብ በፖሊሲው መካተት ያለበት ነው። ከዚያ ውጭ አሁንም ፈተና የሆነው ጉዳይ የከተማ እድገት የሀብትና የገልበት ዝውውር ነፃነትን ይጠይቃል። ከተሞች በኢኮኖሚ ሁኔታ የተሳቡ ኃይሎች ክምችት መሆናቸው አይቀሬ ነው። ይህንን እየተፈታተነ ያለው ጉዳይ ማንነትን መጠበቅ በሚል ለካፒታል ቀለም ለመስጠት መሞከርና ዝውውርን የመገደብ ዝንባሌ፣ መያን ለባለመያው ከማለት ውጭ እንዲሁ ለመገደብ ሲሞከር ታይቷል። ለከተሞች አስተዳደራቸውን ነፃነት ይነር ተብሎ የማደራጀት ስራ ሲከናወንም ይህ አመለካከት ብልጭ ድርግም የሚል ስጋት ሲፈጥር ተስተውሏል።

ከተሞችን ለማሳደግና ልማት ለማረጋገጥ ብሔራዊ ማንነትን ማጥፋት የግድ አያስፈልግም። በተዘዋዋሪ ማንነትን መጠበቅ ልማትን አይገታም፣ ልማትን በማስቀረት ማንነትን መጠበቅ ይቻላል ወይ ለሚለውም ከመብት አንፃርም ሆነ ከተጨባጭ ሁኔታው አይቻልም። ችግሩ በዚህ ዙሪያ የሚሸከረከር ነው። ለልማት ሲባል ማንነትን መጭፍለቅ ያስፈልጋል፣ በሚልና ማንነትን ያጠፋል በሚል ስጋት በማንነት ጥበቃ ሰበብ ለካፒታልና ለመያ ቀለም በመስጠት መገደብና ልማት ማጓተት ከፖለቲካ መብትም ሆነ ከጠቀሜታ አንፃር አደጋ ነው።

ዛሬ ግሎባላይዜሽን በሁሉም በር በደረሰበት ጊዜ በር ልዝጋ ማለት እንኳን በአንድ ሀገር ውስጥ ባለ ዝውውር ከሀገር ውጭም አይቻልም፤ አይጠቅምም። ማንነትን መጨፍለቅም ከፍላጐት ውጭ አይቻልምም/አይጠቅምም፣ ግጭቱ ታርቆና ተፈቶ ከሄደ ብቻ ነው በሂደት ሁለቱ ፍላጐቶች መደጋገፍና ምናልባትም መዋዋጥ የሚችሉት። ማንነትን አጥር አበጅቶ መከላከል አይቻልም፤ አይበጅምም። የሚቻለው ማንነት የሚጠብቀው የግልም ሆነ የማህበረሰብ የውስጥ እምነት ሲሆን ብቻ ነው። በየትም ቦታ ሆኖ ማንነቱን መጠበቅ የፈለገ

ይችላል። ያልፈለገ ካለበት ማህበረሰብ የወጣ ማንነት በግልም ሆነ በጋራ ሊይዝ ይችላል። ስለዚህ ሁሉም ነገር በሰከነ አግባብ በህዝብ ፍላጐትና እምነት መመራት አለበት። የህንዱን አለባበስና አኗኗር የትም ሆነው ሲጠብቁት፤ በአረቡ አለም በመንግሥት ህግም ሆነ በማህበረሰቡ ካለው ስርዓት የወጣ የምዕራባዊ አኗኗር የማመርጡ /የሚኖሩ አሉ።

ማንነትን መሠረት ያደረገ አደረጃጀት መሠረቱ በሀገሮች ይጀምራል። አንድ የማያደርግ አንድ ነገር ሳይኖር አንድ ላይ አይኖሩም። በሀገር ውስጥም በትልቁ የሀገር ማንነት ሥር ሌሎች ሊጠበቁ ይገባል የተባሉ የህዝብ አመኔታ ያገኙ /ፍላጐት የሆኑ/ የግልም ሆነ የማህበረሰብ ማንነት ጥያቄዎች በዲሞክራሲያዊ መንገድ መልስ ማግኘት አለባቸው። ከዚህ ስንነሳ በኛ ሀገር ውስጥ ማንነትን መሠረት ያደረገ አከላለል መኖሩ በራሱ ጉዳት ሆኖ ሊቀርብ አይችልም። ልዩነቱን መጠበቅ የሚቻለው ህዝቡ ከፈለገው ነው። ልማቱን ልዩነቱ ተጠብቆ ማረጋገጥ ከተቻለ አንድ እሴት ነው። ልዩነት የእድገት ውድድር መሠረት ሊሆን ይችላል። አደጋ የሚሆነው ሀገሮች ዛሬ ልማትን ማረጋገጥ ለህልውናቸውም ሆነ ለህዝባቸው ኑሮ አስፈላጊ በመሆኑ ከየትም ሀገር ካፒታልና ሙያ ለመሳብ ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ ከሌላ ሰፈር የመጣ በአፍንጫችን ይውጣ ሲባል ነው።

ሀገሮች የውጭ ባለሀብትና ባለሙያ ወደሀገራቸው ሲመጣ መቀበል ብቻ ሣይሆን ጨርሶ እዚያው መሠረት እንዲጥል ልጆቻቸው በቋንቋቸውና በመጡበት ሀገር ደረጃ ማስተማር ከፈለገ የሚያስተምሩበት ሁኔታ በማመቻቸት፣ በቋንቋቸው ግልጋሎት የሚያገኙበት ሁሉም ነገር በተቻለ መጠን ቀደም ቀርቦ እየጠበቁ ባለበት ዓለም በአንድ ሀገር ውስጥ ይህንን መተግበር እንደስጋት ሲታይና ሲያቅት አስቸጋሪ ይሆናል። ማንነቱ ያታወቅ ለማል ተጨፍለቅ አይጠቅምም ማለትም በር ልዝጋ ለሚለው አስተሳሰብ መጠንከር መሠረት የሚጥል፣ ለከተሞቻችን ብሎም ለአህጉራችን እድገት እንቅፋት የሚሆን ነው። ሁሉም መስተካከል ያለበት አመለካከት ነው።

5.6 ለከተሞች ያልተማከለ አደረጃጀትና አመራር

የከተማ ልማት በስርዓት ካልተመራ ልቅ ከተተወ ወደ ውድቀት ሊከት የሚችል ሂደት አለው። ከተማ ማህበራዊ ትስስርን ያላላል። የሥራ አጥነትና የገቢ ማጣት የኑሮ ሁኔታ ልዩነት ከቀጠለ ህዝቦች ተቀራርበው ያሉበት ሁኔታን ሊያናጉ የሚችሉ፣ የወንጀልና የሥርዓት ማፍረስ አደጋ ምንጭ ሊሆኑ ይችላሉ። ከተሞች ከገጠር የከፋው መከማቻዎች እና የኑሮ ምሬት የተመላባቸው ከሆኑ የፖለቲካና አስተዳደር መስጫ ማዕከል ከመሆናቸው አንፃር ይህንን ሚናቸውን በአግባቡ ሊወጡ አይችሉም። ለሀገር ውድቀትም ሊመሩ ይችላሉ። ለሁሉም ተገቢው ትኩረት ያሻል።

ለከተሞች አደረጃጀታቸው የተጀመረው የአስተዳደር ነፃነት መስጠት /autonomy/ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። የማዘጋጃ ቤቶች ገቢ የሚያድግበት ሁኔታ መታየት ያለበትና የማይታለፍ ጉዳይ ነው።

የማዘጋጃ ቤቶችን ሁለት ገጽታ የተረዳ አደረጃጀት ያሻል። መዘጋጃ ቤቶች የተወሳሰቡ ቴክኒካል ሥራ ያላቸው፤ በአዋጭነት መስመር የሚራመድ የንግድ ተቋም ባህሪ ያላቸው /corporate entity/ እና የፖለቲካ መብትና ጥያቄ ያላቸው ህዝቦች የሚኖሩባቸው (Political entity) ናቸው። አደረጃጀቱ እንደየሀገሮቹ የፖለቲካ እይታ ሚዛኑ ቢለያይም ይህ መርህ የተጠባበቀ ነው።

ይህ መርህ በሀገራችን ከተሞች ስፋትና የህዝብ አሰፋፈር ስብጥር ተቃኝቶ መተግበር አለበት። በአነስተኛ ከተሞች ፖለቲካው በምክር ቤት ደረጃ ተወስኖ ሥራው በባለሙያዎች መመራት ሲኖርበት በተዋረዱ ከከፍተኛዎች እንደ ሚሰጣቸው የፖለቲካ ሥልጣን መጠን በአፈፃፀም መዋቅሩ ውስጥ የሚኖራቸው ደረጃ መወሰን አለበት። አሁን በተወሰኑ ከተሞች የተፈጠረው አደረጃጀት መነሻ ታሳቢው የባለሙያ ሥራን ለባለሙያ ለመስጠት የሚል ቢሆንም የተሰጠው የህግ ማዕቀፍና አደረጃጀት መነሻውን የሚደግፍ አልሆነም። የሙያ ስራው የመገ ፋትና ወደጐን የመታየት፣ ነፃነት ያለው ሥራ አስኪያጅ የተባለው አካል ድርሻ በእንግሊዝ ያለው (town clerk) ሚና ያላለፈ እንዲያውም የተገለለና ለውጤት የማያበቃ አደረጃጀት ሆኗል። ስለሆነም በጥናት ተደግፎ መቀየርና መሻሻል አለበት።

5.7 ከተሞች እራሳቸውን እንዲያድሱና ወደጐን አካሄዳቸውን እንዲያስተካክሉ የሚያስችል ማዕቀፍ መከተል፦

ከተሞቻችን የመሀል ክፍላቸው ሣይቀየር ወደጐን የሚሰፋበት የተሻለ ግንባታ ወደውጭ የሚወጣበት አካሄድ መቀየር አለበት። ይህ መቀየር የሚችለው ገበያው በራሱ ኃይል የሚንገዘበት ስልት ሲቀየስ ነው። ስለሆነም የመንግሥት ቤቶች ባለቤትነት በፍጥነት ወደ ግል መዞር ይገባዋል። በዚህ ላይ አንድ ግቢ ያሉ ቤቶች በአንድ ባለቤት ሥር እንዲሆኑ ማስቻል ለልማቱ ቦታ ማሰባሰብን በማቅለል ልማቱ እንዲፋጠን አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

በሌላ በኩል አሁን ያለው የቪላ መኖሪያ ቤት ሥራ እና ግቢ ክለላ አካሄድ ለመስፋፋት የሚዳርግ ቦታ የማይቆጥብ እና ሊቀጥል የማይችል ስለሆነ የብሎክ ልማት የሚመጣበት አካሄድ መከተል ይገባል።

5.8 ከተሞችን ህጋዊ ስርአት የሰፈነባቸዉ ማድረግ

ሕጋዊ ስርአት በሌለበት ከተማ ልማት ማረጋገጥ አይቻልም። በከተሞቻችን ያለዉ ህገወጥነት ፈርጀ ብዙ ነዉ። መነሻዉ የህጋዊ ገበያዉ የተለያዩ ህብረተሰብ ክፍሎችን

ካለመመለስና ህግ ያማስከበር ብቃት ማነስ እንዲሁም የግንባቤና የህግ ማእቀፍ ክፍተት ናቸዉ። ስለሆነም ህጋዊ ስርአት ለማስፈን፤

- ህጋዊ ገበያዉ በአግባቡ እንዲሰራና የተለያዩ ፍላጎቶችን የሚመለስ እንዲሆን ማስቻል
- አሁን በህገወጥነት የሚፈረጀዉን ዘርፍ ማጥፋት አይቻልም። በቻል እንኳን ጉዳቱም የከፋ ይሆናል። ስለሆነም ህጋዊ ማእቀፉን በማስፋትና የግንባቤ ማስጨበጫ ስራዎችን በመስ ራት ወደ ህጋዊ አሰራር ማስገባትና መደገፍ
- ህግን የማስፈጸም ብቃትን ማሳደግን ይጠይቃል።

6. ማጠቃለያ

ከከተሞች ሚናና ባህሪ ተነስተን፣ የሀገራችን ከተሞች ሁኔታ ዳሰን፣ ራዕይ አስቀምጠን በማስፈፀሚያ እስትራቴጂ ለመደገፍ ሞክረናል። የኛ ከተሞች ወበታቸውና ስላማዊነታቸው በበጉ ጉን ሲታይ ከአቅማቸው በላይ የሆነ የህዝብ ፍልሰትና ብዛት ከአቅማቸው በላይ መሆንና የተዛባ አመለካከት ፈተናቸው መሆኑን አይተናል። ራዕያችን በ2020 ከተሞች በአገልግሎት ተዋረድ ተደራጅተዉ፤ የገጠር መንደሮች የዘመናዊ ከተማ ነሮ የሚሰጡ፤ ከፍተኞቹ፤ ከተሞች ደረጃቸዉን የጠበቀ አገልግሎት የሚያቀርቡ፤ የመኖሪያ ቤትና የስራ አጥነት ችግር አጅንዳ መሆኑ ገዜዉ አልፎበት፤ ሁሉም ከተሞች በያንስ በመንገድ መረብና የህዝብ ትራንስፖርት ተገናኝተዉ፤ ህዝቦች በዘመናዊነት፤ በደስታ የሚኖሩባቸዉ የሞቱ፤ የደመቁ የስራና የመኖሪያ ስፍራዎች ሆነዉ ማየት እንደሆነ አስቀምጠናል።

ይህን ራዕይ ለማሳካት ከተሞች፤

- ስርጭታቸው የተበታተነና ትስስር ያላው እንዲሆን ማድረግ፤
- ከገጠሩ ጋር ያላቸዉ መስተጋብር የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ፤
- በዘመናዊ ፕላን መምራት፤
- ለኢሪዎቻቸው ምቹ የሥራ፣ የመኖሪያና የመዝናኛ ሥፍራ እንዲሆኑ ማድረግ፤
- ለከተሞች ዕድገት ጤናማ አመለካከት መገንባት፤
- ያልተማከለ መልካም አስተዳደር ማስፈን፤
- አራሳቸዉን እንዲያድሱና ወደ ጎን የሚያደርገትን መስፋፋት ለማስተካከል የሚያስችል ማእቀፍ መከተል፤
- በመጨረሻም ህጋዊ ስርአት የሰፈነባቸዉ እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊ እንደሆነ አይተናል።

ይህ የእኔ እይታ ነው። በውይይቱ በሚቀርቡ የተለያዩ ሃሳቦችና ትችቶች ዳብሮ የጋራ ይበቃኝ።

በድጋሚ የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሙያዎች ማህበርንና ታዳሚዎችን ክለብ አመሰግናለሁ።

ከተሞች ለሀገር ልማት በኢትዮጵያ ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

አበበ ከበደ*

1. መንደርደሪያ

በቅድሚያ "ከተሞች ለሀገር ልማት በኢትዮጵያ፡ በ2020" በሚል ርዕስ ዙሪያ በአቶ አበበ ዘልዑል አማካኝነት በተሰናዳው ርዕስ አዘል ፅሁፍ ላይ አስተያየት እንድሰጥ እድሉን በማግኘቴ መድረኩን ላዘጋጀው የኢትዮጵያ የኢኮኖሚክስ ባለሞያዎች ማህበር የጠለቀ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ርዕሱ እጅግ አዲስና ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ትኩረት እያገኘ የመጣ ጉዳይ ነው። እንደሚታወቀው ምንም እንኳን ከተሞች ከሰው ልጅ የረዥም ዘመን የሥልጣኔ ታሪክ ሂደት ጋር ተቆራኝተው የዘለቁ ሕዋዊ ክስተቶች (spatial phenomena) ቢሆኑም ተገቢውን ወቅታዊ ግንዛቤ አግኝተው የመነጋገሪያ እና የምርምር አጀንዳ ወደ መሆን ደረጃ የተሸጋገሩት እ.ኤ.አ ከተገባደደው የሃያኛው ምዕተ ዓመት አጋማሽ ጀምሮ ነው። በተለይም የከተሞች እድገት በሚዛናዊና ተመጣጣኝ ልማት እስካልታጀበ ድረስ - የሚያመራው ሥራ አጥነትን ወደ ማስፋፋት ነው፤ የሚለው የእድገት ንድፈ ሃሳብ (growth theory) አለመስራትና የገጠርና የከተማ ልማት (rural and urban development) በመባል በአማራጭነት በተግባር ላይ ሲውሉ የቆዩ የእድገት ሞዴሎች የተጠበቀውን ያህል ውጤታማ እንዳልሆኑ ሲታወቅ እንዲሁም ሕዝቦችም የሥራ እድል ይሰጣሉ ብለው ወደሚያምኑባቸው ከተሞች መሰደዳቸውን እንዳልገቱ ከተረጋገጠ ወዲህ ነው። (ዩአንዲፒ፡ 1996፡ i)

በዚህ ረገድ ለትኩረት ማግኘቱ ጉልህ አስተዋጽዖ እንዳደረገ የሚታመንባቸው ምክንያቶች በርካታ እንደሆኑ ባይካድም አብይ ድርሻውን ይዞ የሚገኘው ክስተት ግን እ.ኤ.አ. ከ1970 ወዲህ እየተስፋፋ የመጣው የኢኮኖሚክ ግሎባላይዜሽን ነው።

ክስተቱ በይዘቱ ከተማ - ጠቀስ (urban – oriented) እና ግል ሴክተር መር (private sector led) በመሆኑ የተነሣ የዚሁ ክስተት ግንባር ቀደም ተጠቃሚዎች ሆነው የተገኙት ከተማ በመባል የሚታወቁት ሰብአዊ ሠፈራዎች (Human Settlements) ናቸው።

ባሁኑ ወቅት ለዚህ ሥርዓት መስፋፋትና ዓለማችንን በፍጥነት እያዳረሰ መምጣት ከፍተኛ ውን ሚና እየተጫወተ ካለው የኢንፎርሜሽንና የኮሚዩኒኬሽን የቴክኖሎጂ አብዮት ጋር በተያያዘ ምክንያት የከተሞች እድገትም ሆነ ልማት ከተሞችን በአካል ከሚገኙበት ገጠርማ

---

* አቶ አበበ ከበደ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በማኔጅመንት ቀጥሎም post graduate diploma በPolicy and Development እና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በኢኮኖሚክስ ዲቨሎፕመንት ከእንግሊዝ አግኝተዋል። አቶ አበበ ለበርካታ ዓመታት በዕቅድ ዝግጅት ላይ የሰሩ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር የፖሊሲ ጥናት መምሪያ ኃላፊ ናቸው።

አካባቢ፣ አስተዳደር ክልልና ሀገር ይልቅ በንግድና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ከተሳሰሯቸው የሌሎች ሀገሮች ከተሞች ጋር የሚቆራኙበትን ሁኔታ በመፍጠር ላይ ይገኛሉ። ይህንኑ አዲስ ክስተት በማጤን ይመስላል ባሁኑ ጊዜ እንደ ጆን ፍሪድማን የመሳሰሉ የዘርፉ ቀደምት ተመራማሪዎች የከተሞችን ኤኮኖሚ ያዊና ማህበራዊ ግንኙነቶችን (economic and social relations) እንደ ድንበር የለሽ (boundary less) ክስተት ከመመልከት አልፈው የትኛውም ሀገር ቢሆን ይህንኑ ሁኔታ መልሶ ወደ ሀገራዊ ይዘቱ ለማምጣትና ክስተቱን ውስጣዊ ለማድረግ የሚያስችል በውል የሚታወቅ ስልት እንደሌለው (ጆን ፍሪድማን፡ 2005፡ xv) ያለምንም ማንገራገር (without any reservation) አስተያየታቸውን እየሰነዘሩ ያሉት።

እንግዲህ የአቶ አበበ ዘልዐልን ጽሁፍ ባጭሩ ለመቃኘትና አስተያየት ለመስጠት የምሞክረው ይህንኑ ዓለም አቀፋዊ ክስተትና ምሁራዊ ግኝት እንደመንደርደሪያ በመንተራስ ነው።

2. የከተሞች አለም አቀፋዊ የእድገት ሂደትን (Global Urbanization Process) በተመለከተ

ፅሁፉ የከተሞችን ዓለም አቀፋዊ የእድገት ሂደት በተለያዩ የታሪክ ምዕራፎች ያለፈና ባሁኑ ወቅት በአገልግሎትና የመረጃ ዘመን ላይ ስለመገኙ፡ የሰነዘረው አስተያየት በወቅቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ ከሚንሸራሸረው ንድፈ ሃሳብ (ሮቢንሰን፡ 2004፡ 5) ጋር ያለምንም መዛነፍ የሚጣጣም ነው።

ከዚሁ ጋር ተያይዞም ይኸው ዘመን ለከተሞች መልካም እድል የመክፈቱን ያህል በርካታ ችግሮችን እየደቀነ መሆኑን ማመላከቱም ሊላው በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ከተካሄዱ እና መካሄድ ላይ ከሚገኙ የምርምር ሥራዎች ጋር የሚጣጣም አመለካከት ነው።

ከዚህም አልፎ ከተሞችን እንደ ኤኮኖሚያዊ ጥገኛ ስፍራዎች አድርጐ የመመልከቱ አዝማሚያ እ.ኤ.አ. እስከ 1970ዎቹ ድረስ በስፋት የሚንሸራሸር አስተሳሰብ መሆኑን አስመልክቶ ያነሳው ነጥብም ትክክለኛና እስከ ቅርብ ዓመታት ድረስ ሀገሮች እንደ ዋነኛው የሕዋዊ የልማት ስትራቴጂ (Spatial Development Strategy) ጽንሰ ሃሳባዊ ማዕቀፍ (Conceptual Framework) (ዩኤንዲፒ፡ 1991፡ 8) ሲገለገሉበት የቆየ አመለካከት ነው። በመሆኑም ይህንኑ አመለካከት እንደ ጽሁፉ አንድ አካል አድርጐ ለማቅረብ መሞከሩ ተገቢ ነው።

3. የኢትዮጵያ ከተሞችን የእድገት ሁኔታና ማህበራዊና ፊዚካላዊ ገፅታ (Social & Physical Landscapes) በተመለከተ

በዚህ ንዑስ ርዕስ ሥር ፅሁፉ የኢትዮጵያ ከተሞችን እድገት ከሞላ ጐደል ከሌሎች ዓለም አቀፍ የከተሞች ታሪካዊ እድገት ሂደት ጋር በሚመሳሰልበት መልኩ ለማሳየት መጣሩ ከዚህ ቀደም ይህን ጉዳይ በማስመልከት በስፋት ሲንሸራሸር የቆየውን ማለትም የኢትዮጵያን ከተሞች የአከታተም ሂደት ከአለም አቀፉ ልምዱ ጨርሶ እንደተለየ ሂደት አድርጐ የመሣሉ አገባብ ወይንም ልማዳዊ አስተያየት (conventional view) መሠረት የለሽነት በውል ያመላከተ አስተሳሰብ ነው። እንደ ፅሁፉ አመለካከት ከተሞቻችን አሁን ካሉበት የእድገት ደረጃ የደረሱት የአለም አቀፍ ሂደቱንና የአብዛኞቹ የታዳጊ ሀገሮች ከተሞችን የእድገት ፈለግ በተከተለ ሁኔታ

ነው። በኔ አመለካከት ይህ እይታ አዲስና በጠለቀ ምርምር ሊዳብር የሚገባው አቀራረብ መስሎ ታይቶኛል።

ይሁን እንጂ ከላይ ከተንፀባረቀው ነጥብ በመቀጠል በተንሸራሸረው ሌላ ነጥብ ላይ ግን ከአቶ አበበ ዘልዑል አመለካከት የምለይባቸውን ነጥቦች ለማሳየት እፈልጋለሁ።

እንደ አቶ አበበ አመለካከት የኢትዮጵያን ከተሞች ልዩ የሚያደርጋቸው ገጽታ ከተሞቹ ለወታደራዊ ጠቀሜታ ሲባሉ የተቆረቆሩ መሆናቸው ነው።

በእርግጥ ይህ ሁኔታ እንደ ጐንደር፣ አንኮበር፣ አዲስ አበባን ወ.ዘ.ተ. የመሳሰሉትን ከተሞች ሊመለከት የሚችል ክስተት ሊሆን ይችላል። ይህ ማለት ግን ሁሉም የኢትዮጵያ ከተሞች ለዚሁ ዓላማ ሲባል የተቆረቆሩ ናቸው ብሎ ለመደምደም የሚያስችል አይመስለኝም። እንደ እኔ አመለካከት ለብዙ የኢትዮጵያ ከተሞች መቆርቆርና ማደግ፦

- አንድም ለአስተዳደርና ለግብይት ማዕከልነት አመቺ መሆናቸው፣
- አለያም ለሕብረተሰብ ጤና ተስማሚነታቸው፣
- ወይንም ከውበት አንፃር ማራኪ አቀማመጥ ላይ መገኘታቸው
- አለበለዚያም የሦስቱ ወይም የሁለቱ ቅልቅል የሚፈጥሯቸው ሁኔታዎች

የበለጠውን ድርሻ የሚያቅፉ ይመስሉኛል። ለዚህም አባባሉ አቶ አበበ በፅሁፋቸው ላይ የባቡር መስመርን ተከትለው የተቆረቆሩትን ከተሞች እንደ አንድ አብነት ለመጥቀስ መጣራቸው እንደ አንድ ጭብጥ ማስረጃ ሊወሰድ ይችላል።

ሌላው ሊብራራና ሙያዊ ስምምነት ላይ ሊደረስበት የሚገባው አስተያየት የኢትዮጵያ ከተሞች የአሰፋፈር ሁኔታን የዳሰሰው ነጥብ ነው። በዚህ ላይ የአቶ አበበ አመለካከት በተለያየ አጋጣሚ ከተሞችን በሚመለከቱ የምርምር ፅሁፎች፣ የውይይት መድረኮች፣... ወ.ዘ.ተ. አማካኝነት ከሚንሸራሸሩት ሃሳቦች ጋር ፍፁም ተመሳሳይና በእጅጉን የሚጣጣም ነው። እንደ እኔ አመለካከት የከተሞች ውቅር (urban structure) ከተሞቹ በሚገኙበት ሀገር ታሪክ፣ የመሬት አቀማመጥ (topography) የተፈጥሮ ሀብት፣ እና አየር ፀባይ የሚወሰን መሆኑን ተንተርሶ የሚንፀባረቅ በመሆኑ አባባሉ እውነታነት ያለው ቢመስልም ለሁኔታው በዚህ መልክ መከሰት አስተዋፅዖ የሚያደርጉትን ወሳኝ ፋክተሮች - ማለትም ኢኮኖሚያዊ ምክንያቶችን - በመጠቆም ረገድ ግን የሚፈለገውን ያህል ርቀት ተጉዟል ለማለት አልደፍርም።

ሌላው ለከተሞቻችን አሁን ባሉበት ገፅታ ላይ መገኘት ከፍተኛውን አስተዋፅዖ ያደረገው ሀገሪቱ ለቅኝ ግዛትነት አለመዳረጓ ነው የሚለው አስተያየት በቂና ሁኔታውን በአጥጋቢ መልኩ የሚገልፅ ነው ብሎ ለመቀበል በጣም አስቸጋሪ ነው። በእርግጥ አመለካከቱ በአፍሪቃ፣ በእስያና በላቲን አሜሪካ ከሚታዩ አቻ ከተሞች አንፃር ሲመዘን የተጠቀሰው ምክንያት ሚዛን የሚደፋ ነጥብ ለመሆኑ እምብዛም የሚያከራክር ላይመስል ይችል ይሆናል። በተለይም የቅኝ ግዛትነት ታሪክ ትቷቸው ያለፋቸው ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፊዚካላዊ ውጤቶች ሲታዩ በሰነዱ የተንፀባረቀው ሀሳብ ከእውነታው እምብዛም የራቀ እንዳልሆነ በቀላሉ ለመገንዘብ ይቻላል። በመሆኑም የኢትዮጵያ ከተሞች ከዚህ የውጭ ጣልቃ ገብነት ነፃ በሆነ ሁኔታ ለማደግ በመቻላቸው በፅሁፉ ላይ እንደተመለከተው፦

- የአስፋፊር ስብጥራቸው በዘርና በገቢ ልዩነት ያልተከፋፈለ፣ ባህላዊ እሴቶች ለረዥም ዘመናት ሳይታወክ የቀጠሉባቸው፣ በሌሎች ከተሞች ከሚታዩት ማህበራዊ ችግሮች (ማለትም የወንጀል መበራከት፣ የሠላም መጥፋት...ወ.ዘ.ተ) የፀዱ መሆናቸው፣

ለመኖሪያነት፣ ለኢንቨስትመንት፣ ለጉብኝት ተመራጭ እንዲሆኑ አድርጓቸዋል። ይህ ማለት ግን ይህንኑ ሁኔታ በቀጣይነት ይዘው ለመራመድ ይችላሉ ማለት አይመስለኝም። አሁን ከምናየው የአከታተምም ሂደት አንፃር ባንድም ሆነ በሌላ መልኩ የተባለውን ማህበራዊ ሠላም ይዘው ለመቀጠላቸው ተጨባጭ ዋስትና የለም። በተለይም የኢኮኖሚክ ፖሊሲው አቅጣጫ የነዳ ገበያ የኢኮኖሚ መርህን ተከትሎ የሚራመድ እስከሆነ ድረስ የከተሞች ገጽታና ይዘት በኢኮኖሚም ሆነ በመሠረተ ልማት የመለያየቱ ሁኔታ አይቀሬ ነው። (ፊንስቲንና ካምፐቤል፡ 2002፡ 1)

በሌላ አገላለፅ የኢኮኖሚ እድገት ከሚያስከትላቸው አላስፈላጊ አሉታዊ ውጤቶች አንዱ በከተማ ነዋሪዎች መካከል የሚከሰቱ የማህበራዊና የፊዚካል ልዩነቶች ናቸው። ይህ ሁኔታ ቀደም ሲል በለሙም አሁንም በመልማት ላይ በሚገኙ ሀገሮች በስፋት የሚታይ ሕዋዊ እውነታ (spatial reality) ነው። ከላይ በመግቢያዬ ላይ የጠቀስኩት የኢኮኖሚክ ግሎባላይዜሽንም ይህንኑ ልዩነት ከማጥበብ ይልቅ ይበልጥ የሚያሰፋው ስለመሆኑ በለመዱ ሀገሮች የሚታዩ ዘመናዊ የአከታተም ሂደቶች በተጨባጭ እያመላከቱት ያለ ክስተት ነው። በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ በአሜሪካ ታላላቅ ከተሞች ለሀብታሞች ሲባል የተከለሉ ልዩ የመኖሪያ አካባቢዎች (Exclusive Residential Zones) (ፊንስቲንና ካምፐቤል፡ 2002፡ 1) ብዛት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በመምጣት ላይ ከመሆኑም ባሻገር ለእነኝህ አካባቢዎች ልማትና ኤኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፊዚካላዊ የመሠረተ ልማት አውታሮችና አገልግሎቶች የተደረገ ወጪዎች ከከተማ ነክ ገቢዎች ተቀናሽ ይሆኑ ዘንድ የሚስተጋበ ድምጾች ወደሚደመጡበት ደረጃ እየተደረሰ ነው። (ጋልብሬዝ፡ 1992) ይህ አዝማሚያ ወደ ታዳጊ ሀገሮች በመገለቱ የተነሳም የነዋሪዎች የድህንነት ጥበቃ ወጪዎች ከሚገመተው በላይ እያናሩ በመሄድ ላይ ናቸው። (ባኦቺ፡ 2003፡6)

ከዚህ አኳያ የኢትዮጵያ ከተሞች ከላይ ከተመለከተው ከፋፋይ ፊለግ ራሳቸውን መሉ በመሉ ተከላክለው በርዕሱ ላይ በተጠቀሰው የጊዜ አድማስ ውስጥ ማለትም እ.ኤ.አ በ2020 በጽሑፍ ወደ ሠፈረው ራዕይ ሊያመሩ ይችላሉ ብሎ ለመደምደም አዳጋች ነው። ከማዳገትም አልፎ አለማችን ከግሎባላይዜሽን አሉታዊ ተጽእኖ ጨርሶ ባልተላቀቀችበትና ሀገሮችና ዜጎቻቸው ከሂደቱ ፍትሐዊ ተጠቃሚዎች መሆናቸው ባልተረጋገጠበት ሁኔታ ይኸው ራዕይ ያለምንም እንከን እውን ይሆናል ብሎ ለማሳመን ብዙም የሚቻል አይመስለኝም። ይህም ብቻም አይደለም። ይኸውም የተቃረነ እውነታ እንዴት ሊለወጥ እንደሚችልም የተጠቆመ ነገር የለም። ታዲያ ይህንኑ የአቀራረብ ክፍተት በማጤን ይመስለኛል አቶ አበበ ወደ ዋናው ርዕሰ ጉዳዩ ማለትም የከተሞችን ልማት ከግሎባላይዜሽን አንፃር ለመመልከትና ራዕያቸው እውን የሚሆንበትን መንገድ ከማመላከት ይልቅ በቴክኒካዊና አስተዳደራዊ ስትራቴጂዎች አማካኝነት ወደ ራዕያቸው ግብ መጓዝን የመረጡት።

በእኔ አመለካከት ቴክኒካዊም ሆነ አስተዳደራዊ ስትራቴጂዎች ከጊዜና ከስፍራ (time and place) ውጭ ሊታሰቡ የሚችሉ የራዕይ ግብ ማስፈፀሚያ መሣሪያዎች አይደሉም። ውጤታማነታቸውንም ሆነ ስኬታማነታቸው የሚረጋገጠው ለተነደፉለት ዓላማ የሚውሉበት

ጊዜና ሥፍራ በሚገባ ሊመቻችላቸው ብቻ እንደሆነ እስካሁን ድረስ የተመዘገቡ ተሞክሮዎች በግልፅ የሚያሳዩት ጉዳይ ነው።

ስለሆነም በፅሁፉ የተካተቱት ስልቶችን ከግሎባላይዜሽን አንፃር ውጤታማነታቸውን እንደገና በጥልቀት ለመፈተሽና ለመመርመር ቢሞክር ከስትራቴጂዎቹ ውስጥ የሚዘልቁትና የማይዘልቁትን ለመለየትና በሂደትም አዳዲስ ከተገኙም ለማካተት አመቺ ሁኔታዎችን ለመፍጠር ይቻላል የሚል የፀና እምነት አለኝ።

ለማጠቃለል እንደሚታወቀውና በበርካታ ጥናቶች አማካኝነት በውል እንደተረጋገጠው ጭብጥ ሁኔታዎች (Contexts) የፖሊሲ አቅጣጫዎችንና የማስፈፀሚያ ስትራቴጂዎችን ውጤታማነት በሦስት ዓይነት መንገድ ይወስናሉ ተብሎ ይታመናል። እነርሱም፦

- አንደኛው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የሚፈልቁባቸውን ታሪካዊ ሁኔታዎች በመመርኮዝ የእድገትም ሆነ የልማት ቅደም ተከተሎችን ለማስቀመጥ ማስቻል፣
- ሁለተኛው በፖሊሲ አጀንዳዎች ዙሪያ የሕዝቦች ባህላዊና ርዕዮተ አለማዊ ዝግጅት መኖሩን ማረጋገጥ እንዲሁም
- ሦስተኛውና የመጨረሻው ደግሞ የሚወጠኑትን የፖሊሲ አርምጃዎች የመተግበር እድል ማመላከት ናቸው። (ፊንስቴን እና ካምፕቤል፡ 2002፡ 3)

ስለሆነም በፅሁፉ የተንፀባረቀው የአቶ አበበ ራዕይ በተጨባጭ ወደታለመለት ግብ ሊያመራ የሚችለው በቅድሚያ ከላይ የተዘረዘሩት አንኳር ነጥቦችን ግምት ውስጥ በማስገባት ለራዕዩ ስኬታማነት የተነደፉትን ስትራቴጂዎች ማለትም፦

- የአከታተም ሥርዓታችንንና አመራራችንን ለማስተናገድ ለከተሞች የአገልግሎት ተዋረድ እንዲወጣላቸው ማድረግ፣
- የሰመረ የገጠርና የከተማ ትስስርን ማስፈን፣
- የከተማ ፕላን ሥራ እድገትን አጋዥ እንዲሆን ማድረግ፣
- ከተሞችን ጥሩ የሥራ የመኖሪያና የመዝናኛ ቦታ ማድረግን ለዚህም ልማቱን ኢንዱስትሪ መር ለማድረግ መጣር፣ በውል ለመፈተሽና ውጤታማነታቸውን ለማረጋገጥ ሲቻል ነው።

እንደሚታወቀውና በታሪክ ሂደት እንደተረጋገጠው እነኝህ ስትራቴጂዎች ብሔረ መንግሥታት (Nation– States) በተጠናከረ ሁኔታ የራሳቸውን የውስጥ ጉዳይ በራሳቸው በሚወስኑበት ጊዜ በሥራ ላይ ውለው መልካም ፍሬ ያስመዘገቡ ቢሆንም አሁን ከሚታየው የኢኮኖሚክ ግሎባላይዜሽን የጨዋታ ሕጐች አንፃር ምን ያህል ፍሬያማ ሊሆኑ እንደሚችሉ ጽሁፉ የሚገባውን ያህል ርቀት በመጓዝ አላመላከተም።

ያም ሆኖ ግን ለከተሞች ልማት ወቅታዊነት ትኩረት ሰጥቶ በራዕይ መልክ እንዲቀረጽና በሕብረተሰብ ዘንድ እንዲሰርጽ ለማድረግ መጣሩ ይበል የሚያሰኝ ጅማሮ ነው። ወደፊትም ከዚህ ርዕሰ ጉዳይ ጋር በተያያዙ ልዩ ልዩ ርዕሶች ላይ ተመሳሳይ መድረክ እንደሚዘጋጅ ከፍተኛ ተስፋ አለኝ።

በጽሞና ስላዳመጣችሁኝ አመሰግናለሁ !!

ከተሞች ለሀገር ልማት በኢትዮጵያ ጽሑፍ ላይ የቀረበ አስተያየት

ይመር መሐመድ*

በቅድሚያ ከተሞች በሀገር ልማት ላይ ሰለሚኖራቸው ሚና በሙያ ማህበራት ደረጃ መነጋገሪያ አጀንዳነት መነሳቱ በራሱ ትልቅ ጅምር በመሆኑ ደስተኛ ነኝ። ወደ ጥናቱ በማተኮር አጠቃላይና በተወሰኑ ክፍሎች ላይ ያነጣጠሩ አስተያየቶችን እንደሚከተለው ለማቅረብ እሞክራለሁ።

አጠቃላይ አስተያየት

- የከተማ ትርጓሜ፣ መመዘኛዎችና አዊ ልምድ ከኢትዮጵያ የከተማ ትርጓሚ ጋር አነጻጽሮ በማቅረብ ቢጀመር፣ የተሻለ ይሆን ነበር ።
- የከተሞች ውልደት/አፈጣጠርና እድገት ከመሠረታዊ ምክንያቶች/ ኃይሎች ጋር አዛምዶ መቅረብ ነበረበት፣
- የጥናቱ ዘዴ ያለመገለፀና በጠንካራ መረጃ ላይ ያልተመሠረተ መሆኑ፣ እንደ ጉድለት ይታየኛል
- ከከተማ ልማት ጋር የተዛመዱ ንድፈ ሃሳቦችን ቢያንስ ከጥናቱ ይዘት ጋር የተዛመደ ባህሪያቸውን (መነሻ እሳቤዎችን፣ ድምዳሜዎችና ደካማ ጐኖቻቸውን) ማሳየት ያለመቻልና ከኢትዮጵያ የአከታተም ሥርዓት አንፃር ምን ትርጉም እንደሚኖራቸው ማሳየት ነበረበት።
- የኢትዮጵያ ከተሞችን ሁኔታ ስንመለከት ባህሪያቸውን፣ ጂኦግራፊዊ ሥርጭታቸውንና ተዋረዳዊ አወቃቀራቸውን እንዲሁም ለመስፋፋታቸው መሠረታዊ የሆኑ ምክንያቶችን አይገልጽም። ይህን ማወቁ የሀገራዊ አከታተም ሥርዓት ሂደት እንዴት እየተጓዙ እንዳለ በመረዳት መልካሙን አጠናክሮ ድክመቱን ማስወገድ የሚቻልበትን መንገድ መቀየስ ያስችላልና ነው።

የኢትዮጵያ የአከታተም ሂደት በስፋት መካሄድ የጀመረው ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ በ20ኛው ክፍለ ዘመን ሲሆን ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች፤

- የኢጣሊያ ወረራ
- የመንገዶች ከአዲስ አበባ በአምስቱም በሮች ወደተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች መዘርጋት
- የኢትዮ ጅቡቲ ባቡር ሃዲድ መዘርጋት
- የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ አገልግለቶች በከተሞች መደራጀት

---

* አቶ ይመር መሐመድ የመጀመሪያና ሁለተኛ ዲግሪያቸውን በጂኦግራፊ አግኝተዋል። አቶ ይመር የ20 ዓመት የሥራ ልምድ ያላቸው ሲሆን፣ ለ11 ዓመታት ያህል በብሔራዊ ከተሞች ፕላን ኢንስቲትዩት በተለያዩ የኃላፊነት ቦታዎች አገልግለዋል። በአሁኑ ወቅት በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ ውስጥ በመምርህነትና በዲንነት እየሰሩ ይገኛሉ። አቶ ይመር በዘርፉ ጥናቶች ቢተለይ በመንገድ ልማት ዙሪያ ባሉት ላይ ተሳትፈዋል።

- የገጠር ከተማ ህዝብ ፍሰት
- የመንግስት አስተዳደራዊ አወቃቀር በየጊዜው መለዋወጥና አዳዲስ የአስተዳደር ማዕከላት መፈጠር
- ንግድ፣ ሃይማኖት፣ ወታደራዊ እንቅስቃሴ፣ ወዘተ... ናቸው

እነኝህ ሁኔታዎች ሁሉንም የሀገሪቱን ክፍል በእኩል ደረጃ ባለማዳረሳቸው የአከታተም ሥርጭቱም ሚዛናዊነት የጎደለው ሆኖ እናገኘዋን። ተዋረዳዊ አወቃቀራቸው ሚዛናዊ ከአለመሆኑም በላይ ተግባራዊ ሚናቸውም በተዋረድ የተደራጀ አይደለም። ይህም ሀገራዊ የአከታተም ሥርዓቱ በኘላን የሚመራ የአለመሆኑ ውጤት ነው። ጥናቱ የከተሞችን ሚና በሚገባ ያመለከተ ቢሆንም በመረጃ በማስደገፍ ይበልጥ ጠንካራ ማድረግ አልቻለም። ለምሳሌ ከሀገሪቱ ጠቅላላ የትምህርት፣ የጤና፣ የባህል፣ የመሠረተ ልማት፣ ኢኮኖሚና ሌሎች ማህበራዊ አገልግሎት ተቋማት ውስጥ ምን ያህሉ በከተሞች እንደሚገኙ ነገር ግን የከተማውንም ሆኖ የገጠሩን ነዋሪ እያገለገለ እንዳለ ማሳየት ይቻል ነበር።

በዝርዝር ጉዳዮች ላይ የተሰጠ አስተያየት

በጥናቱ የከተሞች ማዕከላዊ ክፍል በግል ሳይሆን በቀበሌ ቤቶች በብዛት መያዝ ለዚህ የከተማ ክፍል እንደገና የማልማት ሥራ እንቅፋት ሆኖ ተጠቅሷል። በእኔ አስተያየት እንደመልካም አጋጣሚ እንጂ እንደ ማነቆ አይታየኝም። ምክንያቱም የቤት ካሣ ክፍያ፣ አስገድዶ የማስሸጥ ወይም እንደገና የአካባቢውን ደረጃ ጠብቀህ ሥራ የሚል ክርክር አያስነሳም፣ ቤቱም መሬቱም የመንግሥት ነው ከባለሀብቱ በማገኘው ገንዘብ ነዋሪዎቹን ማቋቋም ወይም መሬቱን በማሸጋሸግ ነዋሪዎችን እዚያው ማስፈር ይቻላል።

ከከተሞቻችን በጎ ሁኔታዎች ውስጥ ያልተካተተና መጠቀስ ያለበት የሚመስለኝ፤

- ከሌሎች ሀገሮች ጋር ሲነፃፀር ሠፊ የመሬት ሀብት መኖርና
- የከርሰ ምድርም ሆነ የገፀ ምድር ውኃ በአብዛኛዎቹ አካባቢ መገኘት ነው

የከተሞችን ሚና ለማጐልበት እንደፈተና ከተጠቀሰት መካከል በህዝብ ዝውውርና ስብጥር ላይ ገቾ አመለካከቶች ተብለው የተጠቀሰው በእኔ አስተያየት ታሪካዊ መሠረት የሌለው ጊዜያዊ ክስተት በመሆኑና አንዳውም ከተሞቻችን የተለያየ ቋንቋ ባህልና ሀይማኖት ያላቸው ሰዎች ተባብረውና ተስማምተው የሚኖሩባቸው አካባቢዎች በመሆናቸው ዘላቂ ችግር ሆኖ አያታየኝም።

ሌላው ፈተና የማዘጋጃ ቤቶች የማስፈፀም አቅም ማነስ ብሎ ማንሳት መሠረታዊ የሆነውን የከተሞች ችግር አያገልፀውም። ይልቁንም የመወሰን፣ የማቀድና የመፈፀም ሥልጣንና አቅም ያለው የከተማ አመራር አለመኖር ቢባል የተሻለ ይገልፀዋል ብዬ አስባለሁ ።

የተቀመጠውን ራእይ እውን ለማድረግ መከተል ስለአለብን አቅጣጫዎች

በተራ ቁጥር 5.2 ሥር የገጠርና ከተማን ትሥሥር ለማጠናከር የገጠር ምርታማነትን ማሳደግ፣ አስፈላጊነቱ ተጠቅሷል። ነገር ግን አሁን ባለው የተበጣጠሰ የእርሻ መሬት ይዞታና

አዳዲስ የሚፈጠሩ ቤተሰቦች መሬት በማያገኙበት ሁኔታ ኢንዱስትሪን የሚመግብ ምርት ለማምረት የሚቻል አይሆንም። ስለዚህ ሠፋፊ እርሻዎችን የማልማት ጉዳይ ትልት ቦታ ሊሰጠው ይገባል ።

የገጠርና ከተማን የልማት ተደጋጋፊነት ለማጠናከር ያልተጠቀሰውና ወሳኝ ሚና ያለው የሚመስለኝ የገጠር ልማት ስትራቴጂን አግባብ ባለው የከተማ ልማት ስትራቴጅ መደገፍ ነው። ሁለቱ ስትራቴጅዎች አማራጮች ሳይሆኑ የማይነጣጠሉና ተደጋጋፊዎች ናቸው። በዚህ ረገድ ከተሞቻችን ያለምንም ሀገራዊ የከተማ ልማት ስትራቴጅ እየተንዘፈ ስለሆነ ከገጠር ልማት ስትራቴጅ ጋር የሚናበብና የሚደጋገፍ የአከታተም ሥርዓትና ልማት ስትራቴጅ ያስፈልጋል።

የከተሞች እድገት በኘላን መምራት አስመለክቶ ጽሁፍ በጥቅልም ቢሆን ያስቀመጣቸውን ሃሳቦች በመሉ እጋራለሁ። ነገር ግን የኘላን ዓይነቶች/ደረጃዎች ለሁሉም ከተሞች አንድ ወጥ መሆን እንደሌለባቸውና ከኘላን ዓይነት አልፎ አንድ አይነት ማንዋል እየተዘጋጀ በመሆኑ ይህ ተገቢ አለመሆኑን በተገለፀው ሃሳብ ላይ መጨመር እፈልጋለሁ።

ከተሞችን ጥሩ የሥራ፣ የመኖሪያና የመዝናኛ ቦታ ማድረግ በሚለው ሥር ጥናቱ መሬትን አስመልክቶ በሊዝ ሥሪት የመቀጠልን ተደጋጋፊነት ጠቅሷል። እዚህ ላይ እያንዳንዱ ከተማ በሊዝ ወይም ከሊዝ ውጪ ስለመሆኑ መወሰን ያለበት በከተማው አስተዳደርና በነዋሪው መሆን ይኖርበታል የሚል እምነት አለኝ። የኢንቨስትመንት ስበት በቀጥታ ከመሬት ጋር የተገናኘ በመሆኑና በከተሞች መካከል ውድድር በመኖሩ የሚያዋጣውን መወሰን ያለበት ከተማው መሆን አለበት። በተጨማሪም በመሬት ማልማት ሥራ ውስጥ የግሉ ዘርፍ ቢሳተፍ ልማቱን ያፋጥናል።

በተራ ቁጥር 5.6 ያልተማከለ አደረጃጀትና አመራር ሥር ጠቃሚ ነጥቦች ተነስተዋል። ነገር ግን በእኔ እምነት ትልቅ ትኩረት የሚሻው ያልተማከለ አደረጃጀት ብቻ ሳይሆን ብቃት ያለው፣ ሥልጣን ያለው፣ ልማት ተኮር፣ በባለመብያ የሚመራ በሚመራው ከተማ ሀብት ላይ ማዘዝ፣ ማቀድና መፈፀም የሚችል አመራር መፍጠር ነው።

የእኔ ራዕይ

ከተሞቻችን እርስ በእርሳቸውና ከገጠሩ አካባቢ ጋር ጠንካራ የልማት ቁርኝት ያላቸው፣ ፈጣን የኢኮኖሚና ማህበራዊ ልማት የሚታይባቸው መልካም አስተዳደር የሰፈነባቸው ለነዋሪዎቻቸው ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ ሆነው ማየት ነው።

CoE 2020

































ISBN 978-99944-54-00-6

Printed by Rehobot Printers